@OLDBOOKSPDF



@OLDBOOKSPDF

ነገም ሴላ ቀን ነው

"ከዛሬ ሙዱ ሃያ ዓመት ገደማ በፊት በዩናይትድ ስቴትስ (አሜሪካ) ሁለት ዓይነት የአኗኗር ዘዴዎች ነበሩ ። የሰሜኑ ክፍል የአኗኗር ዘዴ ከተማዎችን የማሳደግና የነገውን በኢንዱስትሪ የበለፀገ አገር መፍጠር ሲሆን ፣የደቡቡ ክፍል የአኗኗር ዘዴ ደግሞ በጥጥ እምራች ባሪያዎች ጉልበት የሚለማ እርሻና የትላንቱን ውብ ሕይወት እያሰላሰሉና እየናፈቁ መኖር ነው ።

ለሰሜኑ ክፍል በባሪያ ጉልበት መኖር አስፈላጊ አልነበረም ። ለደቡቡ ግን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ መሠረቱ ይሽው ነበር ።

በ1860 የተመረጠው ፕሬዚደንት አብርሃም ሊንከን ለመመረጥ የበቃው አንድ አገር በግማሽ ነፃነትና በግማሽ ባርነት ሥር መኖር የለባትም የሚለውን መሠረተ ጉዳይ ይዞ ነበር ።ይህንን ሐሳብ የሚቃወሙ አሥራ አንድ ኩሩና አሻፈረኝ ባይ ሀገሮች ፣የሐሳቡ እናት የሆነው ማኅበር አባል አንሆንም በማለት ተገንጥለው የአሜሪካ ኮንፌደሬሽ መንግሥት በመባል የሚታወቅ ማኅበር አቋቋሙ ።

ሰሜኑን ከሚቃወሙት የጋራ ሀብት ሀገሮች ማህል ጆርጂያ ትገኝበታለች ።የዚህ መጽሐፍ ታሪክ የሚጀምረውም የዚህችን ሀገር ልጅ የደስታ ሕይወትና ቆራጥ ጀግንነት በሚያሳየው ፡ይመጣል ብለው በጉጉትኝነት በሚጠብቁት ጦርነት ላይ ተመስርቶ ነው ።" እግረመንገዱንም ፤

ከጦርነቱ በፊት ፡ በጦርነቱ ውስጥና ከጦርነቱም በኋላ ሲድህ ቢንቆዋቱቅ ያዘገመ ሲነሳ ሲወድቅ የከረመ ፣ክልጅነት እስከ ፅውቱት አሣር አበሳውን ያየ ዓለም ሲሳቡንም የገበየ ፣በተስፋ የፉፉ በቾልተኝነት ያንቀላፋ ፣ በናፍቆት የሰነበተ በተስፋ መቁረጥ የነከተ ፣ በቅናት የተነከሰ በልባዊ ፈታድ የተካሰ ከሁሉም በላይ ግን "ፍ፡ል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ" ሆኖበት ባለመግባባት የተለከፈና ብዙ የልጅ ልጆች ወልዶ የሳመ ፍቅር ይታይበታል ።

@OLDBOOKSPDF

ሬት በትለር፣ አስካርሌት አዋራን ፈቀደ ።

አስካርሌት ኦሃራ አሽሌይ ዊክስን አፈቀረች ።

አሽሌይ ዊክስ ደግሞ ሜላኒ ሐሚልተንን አገባ ።የአራት ሰዎች የፍቅር ሕይወት "ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ" ሆነ ።

በጦርነቱ ንፋስ ምክንያት ብዙ ቤት ፈረሰ ፡ብዙ ደም ፈሰሰ ፡ በአገር ላይ አስከፊ ውድቀት ደረሰ ።በፍቅርም አውሎ ንፋስ ሰበብ የስንቱ አንጀት ተላወሰ ፡ የስንቱ ሐሞት ፈሰሰ ፡ የስንቱ ልብ ድን በሩ ተጣሰ ክብሩ ተገሰሰ ።

በአሥራ ስምንተኛው ክፍለ ዘመን በተደረገው ጦርነት ሳቢያ ጥፋት የደረሰባቸውን አገሮች እንደገና ከትቢያ ለማንሳት መሞከሩ አልቀረም ። ቅዝምዝሙን ሰዶ አንድ ጊዜ የሳተ አፍቃሪም ሌላ ጊዜ መወርወሩ አይቀርም -ነገም ሌላ ቀን ነው !

— ተርጓሚው —

@OLDBOOKSPDF

ክፍል አንድ

ምዕራፍ 1

እስካርሌት ኦሃራ ውብ አልነበረችም ።የመንደሩ ሰው ግን እን ደመንትዮቹ የታርሌተን ወንዶች ልጆች ይም ግባትዋ ሲስበው ቆንጆ ናት ይላታል ። የፊረንሳይ መሳፍንት ዘር የሆነችው እናቷ ስስላሳ ተፈ ጥሮና ፣የአየርላንዳዊው አባቷ ግትር ባህሪ ፣ፊትዋ ላይ በግልጽ ይነበ ባል ።ያም ሆኖ መልኩዋ ማራኪ ነው ።ከአገሯ ሸል ያለች ከወደ ግንጭሷ ማዕዘናማ ናት ። ዓይኖቹዋ እንደኩል የጠሩ ናቸው ።ቅንድ ቦቿ ከጫፍና ከጫፍ ወደላይ ቀልበስ ያሉ ሲሆኑ ውብ አይኖቹዋን በተጠንቀቅ ቆመው አጥረዋል ። ከቅንድቦቿ በላይ ጥቅጥቅ ያሉት ጥቁቁር ሽፋሽፍቶቿ ከጫራና ከሐኝ ወደላይ ከፍ እያሉ በመሄዳቸው ፣ በዚያ በደበብ ሴቶች እጅግ በሚደነቀው የግንባሯ ቆዳ ቀለም ላይ ዘመም ያለ አግዳሚ መስመር ሠርተዋል ። የእስካርሌት የቆዳ ቀለም ጠየናቂነቱም በላይ በባርኔጣዋ ስለሚጠበቅ ፡በጓንቲዋ ስለሚከለልና በስስ የፊት ሻሽ ስለሚያበቅ የጀርጂያው ጠራራ ፀሐይ አያርፍበ ትም ።

ሚያዝያ ወር 1861 ነው ።

ታራ ውስጥ በጣም ትልቅ ከሚባለው የአባቷ የጥጥ እርሻ አጠ ገብ ከባልንጀሮቿ ከስተዋርት ታርሌተንና ከብሬንት ታርሌተን ጋር ቀዝቃዛና ጥላ ቦታ ተቀምጣ ሳያት እጅግ ትማርካለች ፣ ታንሆልላለች። አዲሱ ባለ አረንጓዴ አበባ ስስ ቀሚሷ አሥራ ሁለት ያርድ አርቡን እንደማዕበል እያተራመሰ ዳሌዋ ላይ ቡጭ ይላል ። ይሄ ቀሚስ በቅርቡ አባቷ ከአትላንታ ከመጣላት ባለጠጣነቱ ተረክዝ ነጠላ ጫማ ጋር መልክ በመልክ ተጣጥሟል ። ከሶስቱ መንደሮች በቅጥነቱ ተወዳዳሪ ያላገኘው ባለ አሥራ ሰባት ኢንች ኸቦ አይሞላ ወገቧ ላይ፤ ይሄ ስፈት ከመልክ የተዋጣ እንከን የለሽ ቀሚስ ልክክ ይልና ወደ ደረቷ ሲል ጠሰት አድርጉ እየያዘ—የአስራ ስድስት ዓመት ልጅ ጡት የበሰለ ፍሬ ይሄውላችሁ —እዩት ፡ ብሎት ይላል ። ምንም እንኳ ያ ትህትት ቀሚሷ በጥሞና ቢወርድ ፡ ምንም እንኳ ኩሩ ፀጉሯ በስነ

@OLDBOOKSPDF

ስርዓት ቸስብስቦ ቢቋጠርና እነዚያ ለስላሳ አጀቹዋም በጨዋ ደንብ አጭኖቹዋ ላይ ቢያርፉ ማንኑቱዋን ማን በምንም ዓይነት ሊደብቁ ላት አልቻሉም ። እነዚያ የሚያማምሩ ዓይኖቹዋ አሳባቂዎች ናቸዋ ። በዚያ በጥንቃቄ በተያዘ የደስ ደስ ባለው ሬቲ ላይ ወዲህ ዘወር ፡ ወዲያ ከብለል ፡ ወዲያ ቀና ወዲህ ደፋ እያሉ ፈቃደ መ·ሉነቱዋንና የሕ ይወት ለስቲን እያጋለጡ በአለባበሷ ልትቸፍነው የምትሞክረውን ባህ ሪዋን ይፋ ያወጡባታል ። ኩራ ጠባይን ከእናቷ ፡ ኮስታራ ሥነምግባ ርን ከሞግዚቷ ከማሚ ወርሳለች ። ዓይኖቹዋ ግን የገዛ ራሱዋ ናቸው ።

ከግራና ከቀኙዋ መንትዮቹ ወንዶች ባልንጀሮቹዋ በባለጌዋ መነ ዕሮቻቸው ፀሐይዋን አማድም እያዩ ተዝናንተው ወንበሮቻቸው ላይ ተንጋለዋል ። ረዣዥሞም ጡንቻማ እግሮቻቸውንም ጉልበታቸው ድረስ በሚደርስ ቦት ጫማ አሽገው ያለሀሳብ አጣምረው ዘርግተው ይዝና ናሉ ። ኢሥራ ዘጠኝ ዓመታቸው ነው ። ስድስት ፊት ከሁለት እንች ቁመት አላቸው ። ረዣዥም አጥንት ፡ፊርጠም ፊርጠም ያለ ጡንቻ ፡ ፀሐይ የመታው ዓይነት ፊት ፡ የቀይ ቡናማ ፀጉር ፡ የደስ ደስ ያላቸው ዓይኖችና ትዕቢት የሞላው ልብ አላቸው ። ተመሳሳይ የሆነ ሰማያዊ ኮትና ወደቢጫ ያሚወስደው ቦላሌ አድርገዋል ። እነዚህ መንትዮች በጣም ይመሳሰላሉ ። እንዱን ካንዱ መለየት በጣም ያዳግታል ። እነ ሱን ለመለየት መሞከር ሁለት ተመሳሳይ መጠን ያላቸውን የጥጥ ድውሮች ለመለየት እንደመሞከር ነው ።

የከሰዓት በኋላዋ ፀሐይ አማድም ሜዳው ላይ ትፈስሳለች ። ከለም ለም አረንጓዴው የደጁ መልክ ጋር ሲታይ ጥቅጥቅ ያለው ባለጎጭ አበባ ዝቅ የፀሐይዋን ብሩህ ፀዳል ወስዶ የፍኳት ግርማ ሞገስን ተላ ብሷል ። የመንትዮቹ ልጆች ፈረሶች መንገዱ ዳር ታስረው ይግጣሉ። እንደጌቶቻቸው ፀጉር ቀያይና ትላልቅ ፈረሶች ናቸው ። ከፈረሶቹ እግር እግር ሥር እየተጫጫሁ የሚጣሉ ፡ ምን ጊዜም ስቱዋርትና ብሬንት በሄዱበት የሚሄዱ አዳኝ ውሾች አሉ ። ከነሱ ራቅ ብሎ እንደን ጉሥ ተኩሶ የተቀመጠው ጥቁርና ነጭ ጋሪ ገመቾች ውሻ በአፉ የእግር ጥፍሮቹን እየታከከ በትዕግሥት ልጆቹን ወደ እራት እስኪ ሄዱ ይጠብቃል ።

በአጣጭቹ ውሾች ፡ በፈረሶቹና በመንትዮቹ ልጆች ማህል ከቋሚ ወዳጅነት በላይ በጣም የጠለቀ ግንኙነት ፡ በጣም የቀረበ ዝምድና አለ ። ሁሉም ጨነጭች ናቸው- ያለሀሳብ የሚፈነጩ ። ሁሉም የፀዱ ናቸው—ግርማ ሞገስ ያላቸውና መንፈሰ መ·ሉ ። ልጆቹም እንደ ሚጋልቧቸው ፈረሶች አትንኩኝ ባይ ናቸው ። ሆኖም በደንብ ለሚ ይዛቸውና በደንብ ለቀርባቸው ለቻለ ከማር የጣፈጠ ፀባይ አላቸው።

@OLDBOOKSPDF

እስካርሴት ፡ ብሬንትና ስቱዋርት ምንም እንኳ ለእርሻ ቦታ ዘና ያለ ሕይወት የተፈጠሩ ቢሆኑና ከልጅነታቸው ጀምሮ ሲፈነጩበት ቢያድጉም ፤ ችልተኛም ለስላሳም አልሆኑም ። በየጫካው ደጋ ቀላ ሲል እንዳይገ ገጠሬ ታይለኛ ፡ ንቁና ከመጽሐፍ ውስጥ ስለሚ ገኝ ዕውቀት ምንም ደንታ የሌላቸው ናቸው ። በሰሜን ጆርጂያ የም ትገኘውን ከሲይትን የተባለችውን መንደር ኑሮ ከነአውግስታ ፡ ከነቻርልስተንና ከነሳቫና ኑሮ ጋር ሰናወዳድረው ገና ጥሬ ገና ለጋ ነው ቢባልም ፤ አዲስ የማያጣ መንፈስ ይታይበታል ። በጣም የተደላደሉትና ቁየት ያሉት የደቡብ ክፍል ነዋሪዎች የላይኛውን ጆርጂያ ነዋሪዎች የዝቅዝቅ ያዩዋቸዋል ። ይንቋቸዋል ። እዚህ ሰሜን ጆርጂያ ውስጥ ግን ፡ አንድ ሰው ፤ የተከበረ ሰው ለመሆን የሚያስ ፈልጉትን ዋናዋና ነገሮች እስካሚላ ድረስ ፤ አለመማሩ የሚያሳፍር ነገር አይደለም ። በነሱ እምነት ደህና ጥጥ ማምረት ፡ ጥሩ ፈረስ ጋላ ቢና አንጣጣሪ አዳኝ መሆን ፤ ጥሩ ደናሽ መሆንና ሴትን በወጉ ማጫወት እንዲሁም እንደገ-በዝ ተገቢውን የመጠጥ ዋንጫ መጨበጥ የቻለ ሰው ፡ የጨዋ ልጅ የሚገባውን መልካም ተግባር ፈጽሟል ።

መንትየቹ እንደዚህ ባለው የጨዋ ልጅ ተግባራት ማንም የማይ ደርስባቸው ናቸው ። ሌላው የተካኑበት ነገር ደግሞ በመጽሐፍ ቹሩን ሥር ያለ እንዳችም ነገር ለመረዳትና ለመማር አለመቻላቸው ነው ። ቤተሰባቸው የሚሞትው ፈረስ ፡ የሚያሳድረው ባሪያና እንደልቡ የሚ ዘራው ገንዘብ ያለው ባለጠጋ ነው ፤ በመንደሩ የሚተካከለው የለም። ልጆቹ ግን ትረቤታቸው ካለ ከመጨረሻው ድህ ቤተሰብ ልጅ እን ኳን ያነስ የሰዋሰው እውቀት ያላቸው ናቸው ።

ስቱዋርትና ብሬንት ዛሬ ከሰዓት በኋላ ትምህርታቸውን ጥለው እዚህ ታራ መኖሪያ ውስጥ የሚቦዝኑበት ምክንያትም ይሄው ነው። ከዚህ ቀደም ከሶስት የጆርጂያ ዩኒቨርሲቲዎች ተባረዋል ። ዛሬ ደግሞ ለአራተኛ ጊዜ ተባረው ነው የመጡት ። ታላላቅ ወንድሞቻቸው ቶምና ቦይድም ፤ ታናናሽ ወንድሞቻችን ከተባረሩበት ት/ቤት እንማርም ብለው ፡ ጥለው ወጥተዋል ። ስቱዋርትና ብሬንት ከትምህርት ቤት መባረ ራቸውን እንደጨዋታ ነው ያዩት ። አስካርሌትም ብትሆን የፌይትቪል ሴቶች አካዳሚ ትምህርቷን ከአንድ ዓመት በፊት ካቋረጠች ወዲህ፤ በፈታድናነት እንዲት መጽሐፍ እንኳ ገልጣ አንብባ የማታውቅ በመ ሆኗ የባልንጀሮቿን መባረር እንደ ቀልድ ነው ያየችው ።

"እናንተኮ ከት/ቤት መባረር ደንታችሁ አይደለም ። ቶምም ቢሆን ያው ነው ። "አለች ። "ቦይድ ግን እንዴት እሺ አለ! እሱ እንኳን የትምህርት ነገር አይሆንለትም ነበር ። እነአጅሬ ከቨርጂኒያ ዩኒቨርሲቲ፣

@OLDBOOKSPDF

ከዚያ ከአላባማ ፡ ቀጥሎ ደግሞ ከደቡብ ካሮላይና ያስወጣችሁት ሲያንስ እሁን ደግሞ ከጀርጂያው ዩኒቨርሲቲ አስተዋችሁት ። በዚህ ዓይነት መጨረሱንም እንጃ ።”

“አይ ፡ አሱስ ፌይትቪል በዳኛው ፓርላሚ ቢሮ ቁጭ ብሎ ሕግ ማንበቡን መቀጠል ይችላል ።” አለና መለሰ ብሬንት ፡ ብዙ ሳይጨነቅ ። “ለዛውም ይሄን ያህል የሚያስጨንቅ ጉዳይ አይደለም። ትምህርት ብንቀጥል እንኳ ዓመቱ ሲያልቅ ዩኒቨርስቲው መዘጋቱ አይቀርም ነበር”

“ለምን ?”

“ጦርነቱ! ጦርነቱ ነዋ ፡ ጦርነቱ እንደሆን በማንኛውም ቀን መጀመሩ አይቀርም ። መቼም ጦርነት እየተካሄደ እኛ ኮሌጅ ቁጭ ብለን እንማራለን ማለት ዘበት ነው ። አይመስልሽም ?”

“ኤጭ ፡ ጦርነት የሚባል ነገር አይኖርም ባክህ ።” አለች እስካርሌት ለልትት ብላ ። “ወሬ ነው ። አሽሊይ ዊከስና አባቱ ፡ ለአባቴ ሲነግሩት-ያውም ባለፈው ሳምንት-ዋሺንግተን ያሉት የኛ ኮሚሽነሮች በኮንፌደሬሲው ጉዳይ ከሚስተር ሊንከን ጋር . . እ . . ስምምነት ላይ ይደርሳሉ ብለዋል ። ብቻ ያም ሆነ ይህ ያንኪዎች እኛን ጦርነት መግጠሚያ ልብ የላቸውም ፡ ይፈሩናል ። ምንም ዓይነት ጦርነት አይኖርም ። እኔ ደግሞ የዚህ የጦርነት ወሬ እንደአንድ ነገር ነው ያንገሸገሸኝ እወቂ!”

“ጦርነት አይኖርም!?” መንትዮቹ አንድ ትልቅ ጥቅም የተወሰደባቸው ይመስል እሪ ብለው ጮኹ ።

“ለምን የኔ ቆንጆ ፡ ጦርነትማ አሳምሮ ይኖራል” አለ ስቱዋርት ። “አየሽ እኛን ይፍሩን እንጂ ከአትላንታ ወዲያ ጂኔራል ቦሬ ጋርድ ከፎርት ስምተር እንዳይሆን አድርገው ደቁሰ ካስወጣቸው በኋላ ወይ እንደገና ፊት ለፊት ቆመው መጋተር አሊያም በመላው ዓለም ፊት ፊሪ እየተባሉ መኖር ሲኖርባቸው ነው ። እንዴ ፡ ኮንፌደሬሲው እኮ . . ”

እስካርሌት ትእግስት የማጣትና የመሰልቸት ምልክት ይታይ ባታል ።

“ከእንግዲህ ወዲያ ጦርነት የሚል ቃል ካፋችሁ ሲወጣ ብሰማ በቀጥታ ቤቱ ገብቼ በሬን አቆልፋለሁ ። በሕይወቴ እንደዚህ ‘ጦርነት እንደሚል ቃልና “መገንጠል” እንደሚባል ነገር ልቤን ያደከመው ምንም የለም ። ያ አባባ ፡ ነጋ ጦርነት ነው ፡ ጠላ ጦርነት

@OLDBOOKSPDF

ነው ፣ ለዎ ሳ ጦርነት ለእራት ጦርነት ክለ ጦርነት ወሬም የለው ። አባባን ሊመይቁ የሚመጡት ለዎች በሙሉ ካለ ፎርት ሰምተርና ካለ ሐገሮች ነሳነት ፣ እንዲሁም ካለ ኤብ ሊንከን ወሬ አያው ቁም ። ጨቪ ፈቪ እስኪለኝ ድረስ ይደጋግሙታል ። ወጣቶች ሁሉ ስለዚህና ስለጥንቱ ሠራዊታቸው ይለፈልፋሉ ። በዚህ ፀደይ በተደገሰ በማንኛውም የዳንስ ምሽት ፓርቲ አንድ ደህና ቀልድ ፣ የረባ ሚወታ ሳንሰማ እንቅልፋችን እንደመጣ እንበተናለን ። ምነው ብትሉ ይሄ የጦርነት ዝብንብ ወሬ ሰላለ ። መቼም ጀርጂያ ከጣና በኋላ ብትገነጠል በጣም ደስ ደለኛል ። አለበለዚያ የጣና ፓርቲዎቻችን በሙሉ መበላሸታቸው ነው ። ወጣም ወረደም ከእንግዲህ "ጦር ነት" ካሳችሁ ቤቴ መሣባቱ ነው ። "

የምሯን ነው ። ምክንያቱም አስካርሌት ፣ ራሷ መነጋገሪያ አር ዕስት ያልሆነችበት ማናቸውም ሙይይት አይጥማትም ። በሚራሽ በትእግሥት አታዳምጠውም ። ብቻ ስትናገር ፈገግ ብላለች ። ፈገግ ስትል ደግሞ አውቃ የጉንጯን ስርጉድ ወደ ውስጥ ጉድጉድ ፣ ቅንድቦቿን እንደቢራቢሮ ክንፍ በፍጥነት አርግብ - አርግብ ፣ ክፍት ከድን እያደረገች ነው ። ልጆቹ ልከ እሷ እንዳጠመደቻቸው ሠረዟ ውስጥ ገቡ ፣ በሁኔታዋ ፍንድቅድቅ ብለው ፣ ስላሰለቿት ይቅርታ ይጠ ይቋት ጀመር ። ለሷ በመቆርቆራቸው ሰጉዳዩ ስሚት ማጣቷን ከም ንም አልቆጠሩትም ። አርግዛ በጉዳዩ አስበውበታል ። ለንገሩ ሠር ነት የወንዶች ጉዳይ እንጂ የሴቶች አይደለም ። ስለዚህም አሁን የምታሳየውን አዝማሚያ ሴት በመሆንዋ ምክንያት እንደሆን ነገር ቆጠሩት ። እንደምንም ብላ ከአሰልቺው ርዕስ ካራቀቻቸው በኋላ ወደነሱው የቅርብ ጉዳይ መለሰቻቸው ።

"እንደገና ከት/ቤት ስለመባረራችሁ እናታችሁ ምን አሉ ለመሆኑ ?" የዛሬ ሶስት ወር ከቨርጂኒያ ዩኒቨርሲቲ ተመልሰው ሲመጡ የእናታቸው ሁኔታ ታያቸውና ተረበሹ ።

"መቼም" አለ ስቱዋርት "እስካሁን እንኳ ምንም ለማለት ዕድል አላገኘችም ። ቶምና እኛ ዛሬ በሌሊት እሷ ላትነሳ ተነስተን ወጣን ። ቶም አሁን ፎንቱን ቤተሰብ ዘንድ ያመሻል ። እኛ ደግሞ ወደዚህ መጣን ። "

"ትላንት ማታስ ወደቤት ስትገቡ ምንም አላሏችሁ ?"

"ማታማ በለስ ቀንቶን ነበር ። ልክ እኛ ስንገባልሽ እማማ ባለፈው ወር ከከንተኪ ያገኘችው የፈረስ ግልገል መምጣቱ ኖሮ

@OLDBOOKSPDF

አገር ይራኮታል ። ፈረሱ ፈረስ እንዳይመስልሽ—አብድ የሚያክል ፈረስ ነው ። አስካርሴት ፤ ለአባትሽ ነግረሽ መጥተው ማየት አለባ ቸው ። ገና ካሁኑኑ ወደዚህ ሲመጣ መጣት ነገር ነው ረግጦ ረግጦ የለቀቀው ። ሊያመጡት ወደ ጅንስበሮ የሌዱትን የማማን ባሪያዎች እንኳ ሁለቱን ደጠቸዋል ። ደሞ ልክ እኛ እግራችን በራሱን ሲረግጥ፡ ጋጣውን አፈራርሶልሽ እንጀሪ የተባለውን የማማን የዱሮ ፈረስ ረግጦ ኖሮ ግቢ—ነፍስ ውጪ—ነፍስ ይባላል ። እማማ ፡ ስኳር በክረጢት ይዛ ታከመዋለች ። ታባብለዋለች ። ባሪያዎቹ ተደናግጠው ይገቡበት ጠፍቷቸዋል ። ከፈሰቹማ በየጣራው አማዳሚ እንጨት ላይ ተንጠልጥሰው በፍርሀት ያስተውላሉ ። እማማ ከፈረሱ ጋር እንደሰው ቅነጋገራለች ። እሱም ከእጅዋ እየተቀበለ ይቅማል ። መቼም የፈረስ ነገር ከተነሳ እንደእማማ የሚሆን ማንም የለም ። ግና ስታየን ብቻ 'እናንተ አራታችሁ ደግሞ ምን ትሠሩ መጣችሁ ? ሠቼም የናንተ ነገር በግብጽ ላይ ከወረደው ቁጣ ይከፋል !' ወዲያው ፈረሱ ማን ኮራፋትና ማስጎር ሲጀምር 'በሉ ባይኔ እንዳላያችሁ ! ጥፉ ከፈቴ! አታዩምን ውዱ ትልቁ ፈረስ ተናዶ ሲቅበጠበጥ አይታያችሁም ? ቆይ ጠዋት እንነናኝ ብቻ! አራታችሁም ጠብቁ!' ከዛ ጉበኑን ተኛን። ዛሬ ጠዋት ኮሽታ ሳናሰማ ከመንታድ በፊት ሹለክ ብለን ወጣን። ያ ቦይድ እሷን ማግባባት ስለሚችልበት እዚያው ተውነው እልሻ ለሁ ።"

"ታዲያ ቦይድን ይመቱት ይሆን?" አስካርሴት ፤ እንደተቀ ረው የመንደሩ ሰው ወይዘሮ ታርሴተን ነፍስ ያወቁ ወንዶች ልጅ ጅን እንደሀገን ልጅ የመቅጣቷንና ሲያስፈልግም በፈረሷ አለንጋ የመግረፏን ነገር ፡ ልትለምደው ያልቻለችው ነገር ነው ።

ወይዘሮ ቢትሪስ ታርሴተን በጣም ጉበዝና ታታሪ ሠራተኛ ናት ። ሠፌ የጥጥ እርሻ ፡ በመቶ የሚቆጠሩ ኔግሮ ባሮችና የስም ንት ልጆች ቤተሰብ አስተዳዳሪ ከመሆኗም በላይ በማዛቱ ውስጥ በጣም ትልቁ የፈረስ ማርቢያ ጣቢያ የሷ ነው ። ተናዳጅ በመሆ ንዋ የአራቱ ወንዶች ልጆቿ ነገር ወዲያው ቁጣ ያደርጋታል ። አንድ ፈረስ ወይም ባሪያ በአለንጋ እንዳይመታ ቋሚ ትእዛዝ ሰጥ ታለች ። ነገር ግን ራሷ ልጆቿን በአለንጋ ስትቆነድዳቸው የሚያማ ቸው አይመስላትም ።

"አይ ቦይድማ ንክች አታደርገውም ። ብዙ ጊዜ ቦይድን አት ነካውም ። ምክንያቱም አንድም የበኩር ልጅ በመሆኑ አንድም ደሞ በሽተኛና ቁጫጫ ስለሆነ ታዝንለታለች ።" አለ ስቱዋርት በስድስት ፌት ከሁለት ኢንች ቁመቱ እየተኩራራ ። "ነገሩን እንዲያስረዳት እቤት ትተነው የመጣነውም ለዚህ ነው ። እረ በፈጣሪ እማማ ግን

@OLDBOOKSPDF

ከእንግዲህ እኛን እንደሌጅ መግረፍ ፣ ማቁም ይኖርብታል! እኛ የእ ሥራ በጠኝ ዓመት ፣ ቁም ያማም የሚያ አንድ ዓመት ጉረምሶች ሃን እሷ ግን እንደስድስት ዓመት ልጅ ነው የምታየን ። ”

“እሴ እምለው ፣ እናታችሁ ነፃ በዊክሰ ቤተሰብ መደ ተዘጋጀው የመስክ ጣብሃ በእዲሱ ሬሬሰ ይሆን የሚሄዱት ?”

“እሷማ ትፈልግ ነበር ፣ አባባ ግን የሰም አይሆንም ሬሬሱ ሞኝ ደኛ ነው ብሏታል ። ብቻ እሱም ባይለ ሴኖቹም በሄ አይሏትም። እሁኑ ቢያንስ በወይወትሽ አንድ ጊዜ ሣሬ እንኳን በልጪዋ ሰት ጠግ በሠረገላ እንዳማረብሽ መሐይ አለብሽ ብለዋታል ። ”

“ነገ እንደማይዘንብ ተስፋ አደርጋለው መቹም ።” አለች እስ ካርሴት ። “አንድ ሰምንት ሙሉ ሳያቋርጥ በየቀኑ ነዘነዘን ፡ መቹም ደጅ የተደገሰ የመስክ ጣብሃ ፣ በገናብ ምክንያት የቤት ውስጥ ሽር ሽር ዓይነት ሲሆን እንደሚያስጠላኝ ምንም ነገር አያስጠላኝ ። ”

“ኦ ፣ ንግግ ልክ እንደሰኔ ቀን ሞቃት ነው አሚሆነው ። አት ወራጠሪ ብራ ነው አሚመስለው?” አለ ስቱዋርት ። “ያቺን የማታ ፀሐይ ተመልከቻት ። አየገለው ቅሪቷን ። እንደዚህ ያለ ልብ የሚሰርቅ ቀይ ቀለም አይቼም አላውቅ ። የማታውን ፀሐይ አጠላለቅ በማየት እኔ የነገውን አየር ሁኔታ ሰመኖገር ይቻላል ።”

ሁሉም ወዴቀዩ እድማስ ሳመመልከት አዲስ የታሪበውን ፤ ለኝ ይን የሚታከተመሩና ፈረሰ የሚያደክመውን የጂራልድ አሚራን ትኩስ የጥዋ እርሻ ተሻግረው በሳይናቸው ንሞዱ ። ፀሐይዋ ከፍ ሊንት ወንዝ ማዶ ካሉት ተራሮች ጀርባ ቀይ ማምጫዋን ለብሳ ተጠቅልላ ልትተኛ ነው ። የሚያዘያው የቀን ሙቀትም ቀስ በቀስ እየለዘዘ ፀጥር አያሸች አንደምታስተኛ ሞገዚት ለብ ባለ እቅፉ ውስጥ ሕየደባበሰ አስጠቡት ማባበል ጀምሯል ።

የዚህ ዓመት በደይ ወበታማ ዝናቡን ይዞ ቸኩሎ መጥቷል ። ሐምሬዊ አበቦች ጠብታ ኹቶዋቸውን መሳስነስ ጀምረዋል ። የይማ ውድ ሣርች ደብዛዛውን የወንዝ ጸርቻና ባሻገር ያተኮለኮሉትን ተራ ሮች ፤ የጎጭ አበባ ቀሏቸውን አናክተው እየበተኑባቸው ነው ። እርሻ እየተግባደደ ነው ። በደም የተንከረው የበሀይዋ ግርማ ሞገስም በአ ዲሱ ተልም ውስጥ ደንግል ገላው የተጣሠሠውን የጅርጀያ ትኩስ የሸክላ አፈር ይብሱን ደማት ቀይ ረጭቶበታል ። የተራበው ንርጥብ መሬት ይረቱን ገልብሠ የጥ ዘር ይጠባበቃል ። የልቡን የገለጠው አዲስ የታረሰ አፈር ፣ በላዩ ሐምሬዊ ተለም ያለው አሸዋ ይታያ በታል ። ማራና ቀኖን ደማም ተልሙን ተክትሎ ጸር ጸሩን ባለው

@OLDBOOKSPDF

ጥላ ውስጥ ቢጫ ድብልቅ ቀይ ቀለም ይጐላበታል ። በእርሻው ቦታ የተሠራው ቢትም ኑሯ የሸክላ ልብሱን ለብሶ በእርሻው ማሀል ሲታይ—ከፍተኛ መናወጽና መናጋት የደረሰበት ፣ ሽቅብና ቁልቁል ሲነሳና ሲወደቅ ሐምራዊ አረፋ የሚደፍቅ ፡ ሞገዳማ ቀይ ባህር ላይ የቆመ ደሴት ይመስላል ። እዚህ ፣ እንደሚዳማው ማዕከላዊ ጀርጂያ ቢጫ የሸክላ አፈር እርሻዎች ወይም እንደበለፀገው የዳር አገር ጥቁር መሬት እርሻ ፣ ረግጭምና ቀጥ ቀጥ ያሉ ትልሞች የሉም። በሰሜን ጀርጂያ ጠመዝማዛ ጋራዎች ፣ ግርጌያቸው ወጸለው ወንዝ ሰም አፈራቸው እየተሸረሸረ እንዳይጣ ፣ በሚሊዮን በሚቆጠሩ አጫ ጭር ጥምዝ የእርከን እርሻ በጄ በመጠቀም መከላከል የተለመደ ነው ።

ይሄ ከዓለም አንደኛ የጥጥ እርሻ ቦታ ከዘናብ በኋላ ደም የመ ሰለ ቀይ አፈር ፣ ቀይ መሬት ነው ። በደረቀና ዝናብ በሌለ ጊዜ ደግሞ የሸክላ አፈር ጸጥታ መሬት ነው። ደስ ደስ የሚሉ ነጫጭ ቤቶች ያሉበት ፣ በሰላም የሚኖሩ የማይለሟሙ ማሳሞች የተንጣ ለሉበትና እየቀንቀረፈፉ እንደ ቀንድ አውጣ የሚሰቡ ወንዞች የሚ ጀዱበት ድንቅ ቦታ ነው ። በአንባሩ ግን የተገላቢሠሽ የሆነ ወላይ ያሉቸው ነገሮችም የሚታዩበት ነው -እጅግ በጣም ብሩህ የሆነች ፀሐይና እጅግ ድቅድቅ ያለ ጥቁር ጥላ ። የተጠረገው ሜሳና በጥጥ የተሞሳው እርሻ ሞቃቱዋን ፣ ዝምተኛዋንና የደስ ደስ ያሳትን ፀሐይ በፈገግታ ተሞብሎ ያጫውታታል ። የእርሻው ዳርቻ ላይ ግን እልም ያለው የተሰያት ጠራራ ፀሐይ እያለ እንኳ አሻፈረኝ ብሎ በም ሥጢራዊው ግልበቱ ጥሞጥቅ እንዳለ ቆሞ እርሻውን ለጥቁር ጥላና ለቅዝቃዜ የሚዳርግ ፍጹም ድንግል ጫካ ይታያል ። የጥድ ፡ የአር ዘሊባኖስ ፡ የቀረፎ ፡ የዝግባ ፡ የጥቁር እንጨት ዘር ማንዘር እጅግ ተጠጋግቶ አጥር ሠርቶ ጥቁር ጥላውን እጥጡ ላይ ጥሏል ። የክክ ዛፎቹማ እየተወዛወዙ በዜማ ማስጠንቀቂያ ይሰጣሉ፡- "ተጠንቀቁ! ተጠንቀቁ! ክአለታት አንድ ቀን በእጃችን ነበራችሁ ። መልሰን ልን ወስዳችሁ እንችላለን ።" ይሳሉ ።

እድጅ ጥላው ሥር ቁጭ ያሉት ሶስቱ ባልንጀራሞች እየቀ ረበ የሚመጣ የፈረሰ ኮቴ ድምጽ ፣ የልጓም ሰንሰለቶች ቅጭልጭል ድምጽና የኔግሮዎች ሰላሳ ሐሳብ የለሽ ሳቅ ሰሙ ። ጥቦ ለቀማ ውለው የሚመጡ ኔግሮዎችና በቅሎዎች መግባታቸው ነው ። ከወደ ቤት የእስካርሌት እናት የወይዘሮ ኤለን አሃራ ፤ ለስላሳ ድምጽ በእርጋታ እየተንሳፈፈ መጣ- ቁልፍ የምታስቀምጥበትን ትንሽ ቅር ጫት የያዘችውን ትንሽ ባሪያ ስትጣራ ነው ። በጣም ቀጭን ታና ያለው የልጅቱ ድምጽ "አሺ እመቤቴ" ሲል ከተሰማ በኋላ ኤለን

@OLDBOOKSPDF

ከጥጥ ለቅማ ለተመለሱት ሠራተኞች ኩርማን ምግብ ወደምታድ ልበት የጭስ ማድቤት አቅጣጫ እየተራኮቱ የሚሄዱ በርካታ ኩቴ ዎች ድምጽ ተከተለ ። የግህኖችና የማንኪያዎች ገጭ—ክውም መሰ ማቱ አልቀረም ። ይህ የመጨረሻው ድምጽ ፣ የታራ የምግብ ቤት ኃላፊ የሆነው - ሥርክ የተባለው የቤት አገልጋይ- ለራት የሚሆን የምግብ ሳህን ጠረጴዛ ላይ ሲደረድር ነው ።

ይሄ የእራት ድምጽ ጊዜው መምሸቱንና ወደ ቤት መንገድ መጀመር እንዳለባቸው መንትዮቹን አስገንዝቧቸዋል ። ሆኖም የእና ታቸውን ዐይን የማየቱን ነገር በጣም ስለጠሉት ፣ እዚያው ታራ ደጃፍ መናፈሻ ላይ እየተዝናኑ ድንገት እስክርሌት አራት ትጋብ ዘቸው እንደሆነ መጠበቁን የተሻለ ዘዴ አድርገው ተቀመጡ ።

"ስሚ እስክርሌት ፣ የነገው ነገር" አለ ብሬንት ። "መቼም እኛ ራቅ ቦታ ስለነበርን ስለማብሣውም ሆነ ስለጸንሱ ባናውቅም ፣ ነገ ማታ ብዙ ጸንስ እንደምታስደንሽን ተስፋ አለኝ ። ለብዙ ሰው ቃል ገብተሻል እንዴ?"

"ታዲያስ ! እናንተ ሁሉ ወደ ቤት ትመለሳላችሁ ብዬ በምን አውቃለሁ ? ጠንቋይ አልቀልብ ። ገና ለገና ሁለታችሁ ትመጣላችሁ ብዬ የማድግዳ ጌጥ ሆኜ አልገኮር"

"ሆሆይ፤ አንቺው ነሽ የማድግዳ ጌጥ ? አዳሚ መረባረቡ ቀርቶ አንቺ ቆመሽ ልትቀሪ?" ልጆቹ ከት ብለው ሳቁ ። "የውልሽ የኔ ማርሽት! የመጀመሪያውን የመከፈቻ ቫልስ ዘፈን ከእኔ ጋር ትደ ንሻለሽ ። ከስቱዋርት ጋር የመዝጊያውን ። የማይቀረው ደሞ ፣ ራት ከኛ ጋር ትበያለሽ ። ባለፈው ግብግ ላይ እንዳደረግነው ዝቅተኛው የደረጃው መውጫ ላይ እንቀመጥና ማሚ ጂንሲን ጠርተን እንደ ገና ኮከባችንን ቁጠሪልን እንላታለን"

"ኧኔ የማሚ ጂንሲን ኮከብ ቆጠራ አልወደውም ። ትዝ ይላች ኋል ባለፈው ያሰችኝ 'ሐር ጥቁር ፀጉርና ረጅም የከንፈር ጺም ያለው ባል ታገቢያለሽ' —እኔ በጭራሽ ጥቁር ፀጉር ያለው ወንድ ያስጠላኛል ።"

"እንቺ ቀይ ፀጉር ያላቸው ወንዶች ናቸው የሚጥሙሽ—አይ ይል የኔ ማርሽት ? አለ ብሬንት እንደማሽሚጠጥ አድርጎ ፣" በይ አሁን ቫልሱንና ራቱን ቃል ግቢልን"

"ቃል ከገባሽልን ደግሞ አንድ ምስጢር እንነግርሻለን"

"ምንን የምን ምስጢር ?" አለች እንደልጅ ያለው የማወቅ ጉጉቷ ተቀሰቀሰ ፣ በጣም ችኩል ብላ ።

@OLDBOOKSPDF

"ስቱዋርት ፣ ትሳንት አትላንታ ውስጥ የስማኑን እንዳይሆን ብቻ እሱ ከሆነ እወቅ ፣ እንዳንናገር ቃል ገብተናል"

"መቼም ወይዘሮ ፒቲ ናቸው የነገሩን"

"ወይዘሮ ማን ?"

"እንዴ በደንብ ታውቂያቸዋለሽ ፣ እኒያ የቻርለስና የሚላኒ ሐሚ ልተን አክስት አትላንታ ውስጥ የሚኖሩት — የአሽሌይ ዊክስም አክ ስት ናቸው ፣ ወይዘሮ ፒቲ ፓት ሐሚልተንን እንዴት ታጨያቸዋ ለሽ ?"

"እረ አውቃቸዋለሁ—አውቃቸዋለሁ ። በዕድሜዋም እንደሳቸው ያለ ልጋጋም ሴት አይቼ አላውቅም "

"እዎ አሳቸው ናቸው ። ትሳንት አትላንታ ወደዚህ የሚያመጣ ንን ባቡር ስንጠብቅልሽ ፣ ሠረገላቸው በቤንዚን ማደያው ጋ ሲያ ልፍ አይተውን ኖሮ ቀጥ አድርገው አስቆመና መምተው ሰላም አሉን ። ወዲያው ጨዋታ ቀጠሉ ። የጨዋታ ጨዋታ ፣ ነገ የዊክስ ቤተሰቦች የሚያዘጋጁት ግብዣ የቀሰበት ድግስ ነው ፣ ፍጥምጥም ነውኮ አይሉልሽም"

"አዘአሱንማ አሳምሬ አውቀዋለሁ" አለች እስካርሌት ፣ የምታ ውቀውን ወሬ ሴላ መስሏት በማጓጠጓ እየከፋት ።

"ያ ነፈገ የሳቸው አህት ልጅ ቻርሊ ሐሚልተንና ሐኒ ዊክስ ናቸው የሚፈጣጠሙት ። ከዓመታት በፊት አገር አውርቶ የጨረሰው የጠነዛ ወሬ ነው ። ምንም እንኳ ወንድየው ወደኋላ እያለ ገሸሽ ለማለት ቢፈልግ እንድ ቀን እንደሚፈጣጠሙ ማንም ጅል የማይ ስተው ነገር ነበር ። "

"ነፈገ ነው ብለሽ ነው?" አለና ጠየታት ብሬንት ። "ምነው ባለፈው የገና በዓል ካንቺው ዘሪያ ሲያንጎበጉብ አልነበር እንዴ?"

"እሱን እኔ ልረዳው አልችልም ። ለምን መደድከኝ ይባላል እንዴ?" አለች እስካርሌት ፣ በግዴለሽነት ትከሻዋን ከፍ ዝቅ አድ ርጋ ። "እንደሚመስለኝ ማን የሆነ ገንዘት ሞዛዛ ነው"

"በዚያ ላይ ደሞ ጥጥምጥሙም ቢሆን የሱ አይደለም ።" አለ ስቱዋርት ፣ የማታውቀውን ነገር ለመናገር በመቻሉ አሸናፊነት አየ ተሰማው ። "ቀለበት የሚታሠረው በአሽሌይና በሚላኒ (የቻርለስ አህት) ማህል ነው!!"

@OLDBOOKSPDF

የአስካርሌት ራት አልተለወጠም ። ከንፈሯ ግን ፥ ያለማስጠንቀቂያ ቦቅስ እንደቀመሰና በመጀመሪያዋ ደቂቃ አመዱ ቡን ብሎ ምን እንደተፈጸመ እንኳ ያላወቀ ሰው ከንፈር ይመስል ፥ አሸቦ መሰለ ። ራቱዋ ካለመለወጡም የተነሳ ያ ነገር ማግኘዘብ የማይችለው ስቱዋርት በመሬው የተገረመችና በጣም የጓጓች መስሎት ወሬውን ቀጠለ።

"ወይዘሮ ፒቲ እንደሚሉት በወይዘሪት ሜሊ ጤና ማጣት ምክንያት ቀለበቱ እስከሚቀጥለው ዓመት አይነገርም ተብሎ ነበር ። ነገር ግን የመርነቱ ወሬ በጣም በመበርከቱና ክፉኛ በማስጋቱ የሁለቱም ቤተሰቦች ጋብቻው መፋጠኑ ይበጃል አሉ ። ስለዚህ እንግዲህ ነገ ማታ በራቱ ግብዣ ላይ በይፋ ሊነገር ነው ። በይ እንግዲህ አስካርሌት እኛ ሚስጥሩን ነግረንሻል ፥ አንቺ ደግሞ ራት አብረሽን እንደምትበይ ቃል ግቢልን ። "

"እንዴ በደንብ አንጂ" አለች አስካርሌት ከመቅጽበት ።

"ቫልሶቹንም በሙሉ?"

"በሙሉ"

"በጣም ግሩም ልጅ ነሽ ። እርግጠኛ ነኝ ሌሎች ወንዶች ዕብድ ሆነው ፀጉራቸውን ይነጫሉ ። "

"ለምን ኮረንቲ አይጨብጡም" አለ ብሬንት "እኛ ሁለታችን እንደጥጥርጥራቸው እናደርጋቸዋለን ። አየሽ አስካርሌት አንቺ እንግዲህ ጠዋት ግብዣው ቦታ ስንገናኝ አብረሽን ትቀመጫለሽ"

"ምን?"

ስቱዋርት ጥያቄውን ደገመላት ።

"እንዴታ ፥ በደንብ ነዋ"

መንትዮቹ እርስ በእርስ በደስታ አይን ይተያዩ እንጂ መገረማቸው አልቀረም ። ምንም እንኳ አስካርሌት ከብዙ ወንዶች አስቀድማ ሁለታ የምትወልላቸው ቢሆንም እንዲህ አይነቱን የእሽታ መልስ ግን በእንዲህ ያለ ፍጥነት ሰጥታቸው አታውቅም ። ለወትሮው ብዙ ጊዜ እንዲለምኗትና እንዲለማመጡዋት ታደርግና የበለጠ በለመኑዋት ቁጥር እሺም እምቢም ሳትል ልባቸውን የበለጠ ታንጠለጥል ነበር ። ያኮረፉ ከመሰላት ሳቅ ሳቅ ትላለች ። የተናደዱም እንደሁ በእንስታዊ ጥበቡዋ ታቀዝቅዛቸዋለች ። ዛሬ ግን ሙሉ ነገን የነሱ ልትሆን ያለአንዳች ማንገራገር ቃል ገባችላቸው ። እንግዲህ ነገ ግብዣው ላይ ከጐንዋ ሊቀመጡ ነው ። ሁሉንም የቫልስ ዳንሶች ልታስ

@OLDBOOKSPDF

ደንሳቸው ነው። (በፈጥቹ በሙሉ የቫልስ ዳንሶች እንዲሆኑ ማድረጉን ደግሞ ያውቁበታል) በዛ ላይ ራት የሚበሉትም ከሷው ጋር ነው። ልባቸው ሮቢ ረገጠ። እንዲህ ያለ ዕድል የሚገጥማቸው ከሆነማ ከዩኒቨርሲቲ መባረር ገንት መግባት አይደል እንዴ!

ባገኙት ድል በጣም ተበረታቱና ወፈያቸው ሁሉ ስለግብግቡ በታ፡ ስለዳንሱ፡ ስለአሸሼይ ዊክስና ስለሜላኒ ሐሚልተን ሆነ። አንደኛው ሲያቋርጥ አንደኛው ጣልቃ እየገባ ቀልዱን ያሸጉዶት ደዋል። ሁሉም ይስቃሉ። በጨዋታ እያጣፈጠም እግረ መንገዱን የአራት ግብግቡን ነገር ይጠቁማል። አስካርሌት መናገሯን እንዳቆመች ሰመረዳት ጥቂት ጊዜ ወስዶባቸዋል። የጨዋታቸው አየር ጠባይ ግን ጠጣም ወረደም እየተቀየረ ሄድዋል። እንዴት እንዳለወጡት እንጀ የከሰዓት በኋላውም መቀት ቀስ በቀስ ተሰውሯል። አስካርሌት ለሚጠይቋት ጥያቄ ሁሉ ትክክለኛ መልስ ትመልስ እንጂ ለነሱ ወሬ የሰጠችው ትኩረት በጣም ጥቂት ነው። በመጨረሻ አንድ የተዛባና የተለወጠ ነገር አንዳለ ልብ ሲሉ፡ በትክክል ምን እንደሆነ ባያውቁትም ሚራ እንደተጋቡ ወደቅድሙ መንፈሷ ሲመ ልሷት ታግሉ ታግሉና ሰዓታቸውን እየተመለከቱ ያለፈቃዳቸው ብድግ ብድግ አሉ።

ሀሐይዋ በአዳዲሶቹ የአርቫ ሚሰዎች ላይ በጣም ዘለግ ብላ ታበራለች። ረገቦቹ የጫነ ዛፎችም በወንዙ ዳር ዳር ተገጥግ ጠው በገፀ ጽልመታቸው አጥልተዋል። የጭስ ማውጫው ቱሎ ቱሎ ወደ ሚዳው መተንፈስ ጀምሯል። ሚጨቶች፡ ዝዬዎችና ተርከኒ ዎች ሚዳው ውስጥ ሲዘሉና ሲሮጡ ቆይተው ከሚዳው እየተ ሰናበቱ ነው። ስቱዋርት ጮክ ብሎ "ጂምስ" አለና ተጣራ። አንድ የአነሱት ያህል ዕድሜ ያለው ጥቁር ልጅ፡ ቤቱን ዞሮ ፈረሶቹ በረ ሻው ወደታሠሩበት ቦታ መጣ። ጂምስ የልጆቹ የግል ጠባቂ በመ ሆኑ የሄዱበት ይሄዳል። የልጅነት አብሮ አደጋቸው ስለሆነ በአሥ ረኛው የልደት በዓላቸው ጊዜ ለመንትዮቹ የግል ስጦታ ተብሎ የቀረበ ነው። ልክ እሱ ከኾ ሲል የታርሌተን አጻኝ ውሾች ቀዩን አፈር አያ ራጎ ተነሱና ጌቶቻቸው የሚሄዱበትን ሰዓት በተስፋ ይጠባበቁ ጀመር። ልጆቹ እጅ ነሱ—ተጨባበጡና፡ ነገ የሚከሶች ድግስ ላይ በጠዋት መጥተው እንደሚጠብቁት ለአስካርሌት ነግረዋት ወዲያውኑ ቁልቁል ሸመጠጡ። ጂምስ ይከተላቸዋል። እየሁሩ ባርሜጣቸውን እያውለበ ለቡላት የአርዘሊባኖስ ሠልፈኛ የሰራውን ጐዳና በግልቢያ ዘለቁት። ከታራ ዐይን የሚነልለውን የአፈር መንገድ ዞር እንዳሉ፡ ብሬንት ልጓሙን ስቦ እንደ የዶግውድ ዛፍ ሥር አረፍ አለ። ስቱዋርትም አቆመ። ጂምስ ከነሱ ጥቂት አርምጃ ቀረት ብሏል። ፈረሶቹም ጠን

@OLDBOOKSPDF

ከራው ልጓም የጠበቀባቸው ቢሆንም ቀጫጭኑን የፀደይ ሣር ለመ ንጨት አጐነበሱ ። ታጋሾቹ አዳኝ ውሾችም እንደገና በለስላሳው ቀይ አፈር ላይ ሰሽ አሉና ተና ብሰው በደብዛዛው ምሽት ውስጥ በክብ እየተሽከረከረ ወደሚወጣው ጭስና ወደ ጭስ ማውጫው በናፍቆት ያስተውሉ ጀመር ። የበሬንት ሰፈና አስተዋይ ፊት ግራ መጋባትም ንዴትና እልህም ይታይበታል ።

"እኔ እምለው ፡" አለ ። "እራት የምትጋብዘን አይመስልም ነበር እንዴ?"

"እኔ መሰለኝ ነበር"አለ ስቲዋርት ። "እንዲያውም ካሁን አሁን ካሷ ወጣ እያልኩኝ ስጠባበቅ ነበር ። ለምን ይመስልሃል ያልጋበ ዘችን ?"

"ለምንም ። ለረኃቦም ጊዜ ስላሳየችንና ከብዙ ጊዜ በኋላ ወደ ቤት መምጣታችን ስለሆነ እንዳታውየን ብላም ይሆናል ። ሌላ ጊዜ ግና ብዙ የምንግራት ነገርም አለ"

"በበኩሉ ግና ስንመጣ በጣም ደስ ያላት መስላ ታይታኝ ነበር"

"እሪም ያሰብኩት እንደሱ ነበር"

"ካዛኮ በማግሽ ሰዓት ሙሰጥ ተለዋውጣ ቅዝቅዝ ከማለትዋ የተነሳ ራሷን ያመማት መስሎኝ ነበር ። "

"እሪም ልብ ብዬው ነበር ፣ ግን ምን እንደዛ እንዳደረጋት አል ገባኝም ። "

"እንጂ ። የሚያበሳጫት ነገርም አላየሁም ። "

ለትንሽ ደቂቃም አሰበ ።

"ምንም ሊመጣልኝ አልቻለም ። ደሞምኮ አስክርሌት ስትናደድ በደንብ ነው የሚያስታውቅባት ። ግንም ያነባታል ። እንደ ሌሎች ሴቶች ፣ ይሄን ልደብቅ ፣ ይሄን ልናገር አትልም ።" አለ ብሬንት ።

"እኔ እምወድላት ሀሳይዋ ደግ አሰ ነው ። ቀዝቀዝ ያለች መስላ ነገር ባሠደ አምቃና በንዴት እሳት ጉርሳ ከቦታ ቦታ ስትዞር አት ሙልም- እቅጩን ትነግርሃለች ። ያም ሆነ ይህ ግን እኛው እራ ሳችን ከተናገርነው ነገር ማህል አንድ ዝም ያሰኛት ወይም ሀሳብ ላይ የጣላት ነገር አለ ። እርግጠኛ ነኝ ፣ የኛ መምጣት በጣም አስ ደስቷታል ፣ እራትም ልትጋብዘን ሀሳብ ነበራት ። "

"ከትምህርት ቤት ስለተባረርን አይመስልህም?"

@OLDBOOKSPDF

"እረ የሰማያቱ ያለህ! ምነው እንደጅል ያናግርሃል ጃል? ስለሱማ ገና ስናወራላት አይደል እንዴ ልጂ እስኪፈርስ የሳቀችው። ደሞኮ እስካርሌት ኦሃራ እኛ ከመጽሐፍ ስለሚገኝ ዕውቀት ካለን ዕምነት የበለጠ የሌላት ልጅ ናት።" ብሬንት ወደፈረስ ጠባቂው ፌሮ ዞሮ አዚያው አፈረሱ ኮርቻ ላይ እንዳለ ተጣራ፡-

"ጂምስ!"

"አቢት ጌታዬ"

"ከእስካርሌት ጋር ያወራነውን ሰምተህ የለ?"

"ምነው ጌታ ብሬንት፣ አሁን ማ ይመት እሌ ነጮችን የም ሰልል ሰው ነኝ?"

"የግዚሀር ያለህ፣ መሰለል? አናንተ ባሪያዎች እኮ በየአካባቢው የሚሠራ የሚነገረው ሁሉ አንድ አይቀራችሁም። አንተ ውሸታም፣ ምነው በመኖፈሻው ዳርዳር ስትል በዓይኔ በብረቱ አሳየሁህና ነው፣ በል አሁን እውነቱን ንገረኝ። ለመሆኑ ስንጨዋወት ከነበረው ነገር ውስጥ ወይዘሪት እስካርሌትን የሚያናድድ ወይም የሚያስከፉ ነገር ነበረበት እንዴ?"

ጂምስ ስለተጠየቀና ስለተወተወተ አቦልቆ እያየ የሰማውን ሁሉ አልሰማሁም እያለ ማስመሰሉን ትቶ ሽሩባፍቶቹን ሰብሰብ አድርጎ እቅጩን ለመናገር ወሰነ።

"የሰም ጌቶቼ፣ ማንኛችሁም ከተናገራችሁት ውስጥ እሷን የሚያበሳጭ ነገር የተናገራችሁ አልመሰለኝም። የእናንተ መምጣት በጣም ያስደሰታትና ስላጣቻችሁም እጅግ የናፈቀቻችሁ መሆኑን እንደ ወፍ ፈንድቃ ስትነግራችሁ ነበር። ሁኔታዋ ከዚያ ወዲያ ነው የተለዋወጠው። በተለይ ስለ ጌታ አሽሌይና ስለ እሜቴ ሜሊ ሐሚልተን ጋብቻ ስታወሩማ ለየላት። ከዚያ በኋላ ጨዋታዋ እየቀነሰ ሄደና በላይዋ ላይ አሞራ ሲያልፍ ተሸማቃ ፀጥ እንደምትል ድምቢጥ ወፍ ቀስ በቀስ እርጭ አለች።"

መንትየቹ እርስ በእርስ ተያዩና ራሳቸውን ነቀነቁ። ነገሩ ግን አልገባቸውም። "ጂምስ ያለው ትክክል ነው። ምክንያቱ ግን ግልጽ አልሆነልኝም።" አለ ስቱዋርት።

"በእግዚሀር! አሁን አሽሌይ ለዚ ከባልንጀራ በቀር ምኗ ነውና ነው። መቼም ከሱ ፍቅር ይዟታል አይባልም። ሆኖም ሁኔታዋ በፍቅር እንደጠፈችለት ያህል ነው።" ብሬንት በነገሩ በመስማማት ራሱን ነቀነቀ።

@OLDBOOKSPDF

"ሚሄ ምናልባት አሽሌይ ነገ ቀለበት ማሠሩን ለአገር ሁሉ ሲነግር ለሷ በሳልንግራት በሽታ ይሆን እንዴ መቼም ከዳሮ ጀምሮ የቅርብ ዓይኗዋ ነውና ፣ መጀመሪያ ሊንግረኝ ይገባል ብላ ሊሆን ይችላል ትላለህ ? ሴቶችኮ እንዲህ ያለውን ነገር ቶሎ የማወቅ ኃላት አላቸው ።"

"መቼም፣ ምናልባት ። እውነት ነገ መሆኑን አልነገራት እንደ ሆነስ ? ይሞኮ ነገሩ በድብቅ እንዲሆንና ድንገት ለለው እንደ ዱብ አለ ብንገር ተዓምር ለመፍጠር የታሰበ በመሆኑ ለሷ ብቻ በግል የሚነገርበት ምክንያት አይታየኝም ። ወዲያውም ፣ ማንም ቢሆን የራ ሱን የቀለበት ሶኝ ሥርዓት የግል ሚስጥሩ የማድረግ መብት አለው ። እያደለም እንኤለ እሽል ራሳችን ብንሆን የሜሲ አክስት ባያነግሩን ኖሮ ከየት አባታችን እንሰማው ኖሯል ። ብቻ አሽሌይ ሚላኒን እንደሚያገባ እስክርሌት አስቀድማ ታውቃለች ማለት ነው። ደም እኛም ብንሆን ለብዙ ዓመት የምናውቀው ጉዳይ ነው ። የዊክ ስና የሐሚልቶን ቤተሰቦችኮ ከጥንትም ሲመርድ ሲዋረድ በመ ጣው ዘሀሳቸው መሠረት የአነስትማችኮ ልጅች ሲጋቡ ነው የኖ ሩት ። እንዴ፡ ቤተሰብ ከሌላኛው የዘመዶቹ ቤተሰብ የአክስቱን ልጅ ማግባቱ ያለ ነገር ነው ። በለዚህ አሽሌይ ዊክሰም ሚላኒን አንድ ቀን ሊያገባት እንደሚችል የሚያጠራጥር ጉዳይ አይሆንም ። ለም ባሉ ዘረ ዊክስ የወይዘሪት ሜሊን ወንድም ቻርለስን እንደምታገ ቡው ማለትኮ ነው ።"

"በቃ ይሽው ነው ። ይሄነን አርዕስት እንተወው ። ያም ሆነ ይህ ግን እራት በላልጋበዘችን ቅር ብሎሻል ። መቼም ዜት ሄጂ እማማ ከትምህርት ቤት ስለመባረራችን አንስታ ስትጨቀጭቀኝ ሠስማት አልፈለግም ። ይሄ የመጀመሪያችን ይመስል እሷ እንዳ ጲስ ትጮህብናለች ።"

"እይ ምናልባት ቦይድ አስካሁን አረጋግቶና አለስልሶልን ይሆናል ። ያ ደታታ ጥጥረት እንዴት ያለ ምላስኛ እንደሆነ ታው ቃለህ ። ቱማ ያለችውን ሴትዮ እንዴት አድርጉ ቀዝቃዛ ሠህ ሙስጥ እንደሚከታት አይተሃል መቼም ።"

"ልክ ነው ። አያደርገውምስ አይባልም ። ግን ቦይድ ብዙ ጊዜ ይሬጅበታል ። አንድ ነገር ተረድታ ወዲም ግራ ተጋብታ 'በቃ ተመው ይልሽ ለሕግ ትምህርትህ አትም እንዳያንስህ ቃላትህን ቆጥብ' እስክ ትለው ድረስ ስንት ሙሪያ ጥምጥም መንገድ መጂድ ይኖርበታል ። ምናለ በለኝ ነሰ ጋር ቁጭ ብሎ ለማውራት ጊዜ አያተኝም ። ምክ ንያቱም እማማ የዚያ ያዜሱ ፈረስ ነገር እንደእብድ አድርጓታል።

@OLDBOOKSPDF

ለራት ቋሚ ብለ ተረጋግታ ከየይድ ጋር እስክታወራ ድረስ ነገሩ አይሳክም ። ራት እስክሚያልቅ እንደገና የንዴት ኃይሏን ታጠራቅ ምና ደሞ ሁራ ከረዩ ትላለች ። ከዛ እንግዲሁ የዩኒቨርሲቲው ምን ስለር ፣ እንቺንና እኔን እንደዛ አንተና አንቺ ብሎ አሞርዶ ከሰደ ቢን በኋላ የኛ ነሊጅ ሙስጥ መቀመጥ የማይሞክር ነገር ንው እደለ ፣ ቦይድ እስኪያስረዳቲ ድረስ አራት ሰዓት ይሆናል ። በምንስ ለሩ ድፍረት ተሜዛ ልምን አትሚድለውም ነበርን ወይኔ ታርሴተን እያለች የምትደንፋበት ደረጃ እሰኪያዶርሳት ድረስ ደግሞ አሁስ ለሊት ይሆናል ። የለምየለም ። እስክእክስ ለሊት ድረስ ወደ ቤት መሄድ የለብንም ። "

መግትዋቹ እርስ በእርሱ በመከፋት ሳይን ተያዩ ። የመጨረሻ ፈርጣማና ተራጋጭ አመለሟ ፈረስ እያስፈራሞሙም ። ትከሰና ሣድያ ቁብችውም እይደለም ። ዝምፈቤት ጋር ጠብ ስሜት አጀሰጣ ቹውም ። የዚች የነስተይ ወጣጅ እናታችው ስድብና ዛቻ እንዲሁም በፈረስ አለንጋ መጋረፍ ሣኒ እንደ ጦር የሚያስፈራቸው ነገር ነው ።

"እንግዲያው" አለ ብራንት "ወደ ዊክስ ይተስብ እንሂድ ። ኤሽሌይና ሌሎቹ ሕዝባረዱች ብመሄዳችን ጭጽስቱው እራት ይጋብ ዙናል ። "

ስቱዋርት ትንሽ ቅር የመሰኘት ሁኔታ ይታይበታል ።

"እይ ፣ እዚያስ ባንሄድ ይሻላል ። እንሱ ለራሳቸው በነገው ድግስ ዝግጅት ተጠምደው ነጭሳቸውን አያወሩም ። በዛ ሳቃ . . . "

"አ ፣ እሱን ረስቼዋለሁ ባክህ" አለ ብራንት በጭሬያ ። "የለም በቃ መደዛ እንሄድም " ፈረሳቸውን ኮልኩለው በዝምታ ለጥቂት ጊዜ ተጓዙ ። በስቱዋርት ጉንጮች ላይ የመደናገጥ ቅላት ይታያል ። ስቱዋርት እስከለፈው በጋ ድረስ ኢንዲያ ዊክስን ሲያሳድድና ሲያ ጫውት ፣ ልቧን ሲበላ ከርሟል ። ይሄን ደግሞ የሷም የሱም ቤተሰቦች ፣ የሰፈሩም ሰው በጠቅላላ የሚያውቀውና ይሁን ያለው ነገር ነው ። ኢንዲያ ዊክስ ረጋ ያለች ልጅ ስለሆነች ስቱዋርትን ቀዝቀዝ ታደርገው ይሆናል ብለሎ ስለሚታመን የመንደሩ ሰው የሁለቱን ወዳጅነት ፈቅዶታል ። ጉጉትና ተስፋ ማድረግም በየሰዉ ልብ ውስጥ ቤቱን ሠርቱ ነበር ። ስቱዋርትም ቢሆን ምንም እይ ንዶለው ። ደህና አዎ ይሆናታል ። ብራንት ግን በነገሩ አልረካም ። ብራንት ኢንዲያ ዊክስን በመጠኑ ይወዳታል ። ግን በጣም ግልጽና ለማዳ በመሆኑዋ በጭቅር ሊወድቅላት ባለመቻሉ ከወንድሙ ከስ ቱዋርት ጋር ፉክክር ገጥሞ እሷን ለመከተል አልፈለገም ። መንት

@OLDBOOKSPDF

ዮቹ ወንድማማቾች በሕይወታቸው በሴት ጉዳይ የተለያየ ፍላጎት ሲያድርባቸው ይህ የመጀመሪያ ጊዜ መሆኑ ነው። ብሬንት ይቺን ምንም ልትስበው የማትችል ልጅ ወንድሙ መውደዱን በጣም ተቃ ውሞታል። አይሆንም ፣ አትሆንህም ባይ ሆኗል።

በዚህ ማህል ባለፈው በጋ ጆንስቦሮ ውስጥ በዋርካዎች በተከ በበው መናፈሻ ቦታ ላይ የፖለቲካ ስብሰባ ተደርጎ በነበረበት ወቅት ሁለቱም እስካርሌት ኦሃራ ላይ አይናቸውን ጣሉ። ካወቋት ብዙ ጊዜያቸው ነው። እንዲያውም አፈር ሲፈጩና ዕቃ ዕቃ ሲጫወቱ የኖሩ የልጅነት ሕብረ አደገኞች ናቸው። በዛ ላይ ልክ እንደነሱ ፈረስ መጋለብ የምትችል፣ ልክ እንደነሱ ዛፍ ላይ መውጣት የሚ ሆንላት ወንዳወንድ በመሆኗም በደንብ የሚያውቋት ባልንጀራቸው ናት። አሁን ግን ያቺ የሚያውቋት ብጥሌዋ እስካርሌት ኦሃራ አድጋ ትክለ ሰውነቷ ሐውለት ሠሪ ተጠንቅቆ የቀረፀው መስሎ ሽንጥ ዳሌዋ የሩቅ የቅርቡን የሚማራ ሆኖ፣ እጮጠጮጤዋ ሊፈነዳ ይመስል ጡት መያዣዋን ሊበጥስ ደርሶ፣ ሲያዩዋት በአለም ላይ አንደሷ የደም ግባት፣ እንደሷ ማራኪ የለም አሰኝቻቸው።

እነዚያ አንዱኩል የጠሩ ዓይኖቹዋ ሲደንሱ ለመጀመሪያ ጊዜ አስተዋሉ። ጥቂት ፈገግ ስትል ጉንጯ ላይ የሚጫወቱት የወበት ስርጉዶቿን ጥልቀት ገና አሁን ልብ አሉ። የእጆቿንና የእግሮቿን ተመጥኖ ማነስና የወገቧን ቅጥነት በጥሞና የተገነዘቡት ገና በቅ ርቡ ነው። እነሱ ስለሱዋ የሚሰሙዋት አስተያየት ቀልጣፋ ፈገግ ታዋን እንድትመጣባቸው ሲያስገድዳት፣ የሷ ፈገግታ ደማሞ በፊ ንታው ስለነሱ ያላትን እድናቆት ስለሚመሰክር ፍንድቅድቅ ብለው ነፍሳቸው ጮቤ ትረግጣለች።

በመንትዮቹ የሕይወት ታሪክ ውስጥ ያ ቀን የማይረሳ ቀን ነበር። ስለሆነም ይህንን ጉዳይ ባነሱት ቁጥር፣ እስከዛሬ የእስካር ሌትን ሙንጅና እንዴት እንዳልተገነዘቡ ይገርማቸዋል። እስካርሌት ልብ ብለው እንዲያስተውሏት ስሚታቸውን የቀሰቀሰችበትን ምክ ንያት እስከዛሬም አላወቁት። እስካርሌት ማንም ወንድ ከሷ በስ ተቀር ሌላ ሴት ሊያፈቅር አይችልም የሚል የራሷን ሕግ ደን ግጋለች። ስለዚህም በዚያ የፖለቲካ ስብሰባ ላይ ኢንዲያ ዊክስንና ስቱዋርትን አብረው ስታያቸው ለዚያ አጸኝና መንትፌ ተፈጥሮዋ እጅግ ከባድ ጥቃት ተሰማው። ስቱዋርትን ከኢንዲያ ነጥቃ የራሷ ማድረግ ብቻ የቀናተኛ ተፈጥሮዋን ጥማት የማያረካላት መስሎ ስለታያት የወጣመድ መረቧን ብሬንትም ላይ መዘርጋት እንዳለባት አምና እሱም ላይ ዘረጋችበት። የወጣዱ ጥንካሬ ሁለቱንም ከመ ሠረታቸው አናጋቸው።

@OLDBOOKSPDF

እንዲህ አድርጋ ጉድ ሠርታቸው መንትየቹ ወንድማማቾች በፍቅር ወደቁላት ። ብሬንት በማግሽ ልብ ሲያሳስቃቸውና በጂ ለያገባቸው በመጠኑ ሲያሯሩጣቸው የነበራት ሳቭጆይ ያሉት ልጃ ገረዶች - ኢንዲያ ዊክስና ሌቲ ሙንሮም- ከፍቅር መዝገብ ተፋፉ። ከሁለቱ ወንዶች አንደኛውን እስካርሌት መርጣ ብትይዝ ቀሪው ምን እንደሚያደርግና መሸነፉ የሚያሰከትልበትንም ስሜት እነዚህ ወንድ ማማቾች አስበውትም ተጠያይቀውብትም አያውቁም ። ድልድዮን ስንደርስ እናቋርጠዋለን የሚሉ ዓይነት ናቸው ። ሰጊዘው በመሀከላ ቸው ምንም መቀናናት ስለሌለ ለአንድ ሴት በፍቅር መውደቃቸው ደስስ ብሏቸዋል ። በሆነው ሁሉ ረክተዋል ። ይሄ ሁኔታቸው የጉ ረቤቱን ሰው ሁሉ አሰየው አሰኝቷል ። እናታቸውን ግን አናዷታል። እናታቸው አስካርሌትን አትወዳትም ።

"ያቺ ጨላጣ አስስት አንጻችሁን ይዛ ብታርፍ ዋጋችሁን ታገኙ ነበር ።" ብላቸዋለች ። "ወይ ምናልባት ሁለታችሁንም እሺ ብላ ወደ አ'ታ ትሄዱ ነበር ። ያውም እነዚያ ሞርሞኖች ከተቀበሏችሁ ነው። በጣም ያጠራጥረኛል ። እኔ የምጨነቀው እንዲህ ብላችሁ ብላችሁ አንድ ቀን በዚች ሁለት ሠልክ ፣ ዓይን አውጣና ኩሳሳ ፍጥረት ምክ ንያት ተቀናንታችሁ እንዳትጋደሉ ነው ። አረ ተጋድላችሁ ባረፋ ችሁ ፤ ግልግል ነበር ።"

ከዚያ ስብሰባ ቀን ጀምሮ በቱዋርት የኢንዲያ አጠባቡ መኖር ያስጨንቀዋል ። ኢንዲያ የሱን በድንገት መለወጥ አውቃበት ያሳየ ችው ምንም ምልክት የለም ። በቃልም ሆነ በመልክ አንዳችም ለውጥ አልታየባትም ፤ በጣም ጨዋ ልጅ ናት ። እሱ ግን የገዛ ሕሊ ናው እየቆጠቆጠው ምኞት አይሰማውም ። እሷ ከገኑ ካለች ቆን ቅንቅ ይለዋል ። ደርሶ ይቅበጠበጣል ። ኢንዲያ እንድታፈቅረው እንዳ ደረጋት ፣ አሁንም ቢሆን እንደምታፈቅረው ያውቃል ። በልቡ ግን የጨዋ ሰው ሥራ እንዳልሠራ ይታወቀዋል ። ታዲያ እኮ አሁንም ቢሆን በጣም ይወዳታል ። እርጋታዋንና የጨዋ ልጅ አስተዳደጓን መጽሐፍ ማንበብ መውደዷንና ይህ ቀረው የማይባሰውን ወርቅ ፀባይዋን ሁሉ ያከብረዋል ። ምን ያደርጋል ታዲያ ፣ ሁል ጊዜ እንድ ዓይነት ፣ አሰልቺና የማይጥም ሁኔታዋ ከእስካርሌት ጉልሀና እንደ አየር ጠባይ ተለዋዋጭ ፣ በቅልጥፍና የሚተጣጠፍ ጨዋታና ደም ግባት ጋር ሲወዳደር ፈተና ይመድቃል ። ከኢንዲያ ጋር የቆመ ሰው የት እንዳለ በደንብ ይታወቀዋል ፣ አካባቢውን አሁንም አሁንም የመመልከቻ ጊዜ አለው ። ከእስካርሌት ጋር ያለ ሰው ግን የት ይኑር የት ሳይ ታወቀው አልም ጥፍት እስኪል ድረስ ይመሰጣል ። ይሄ ታዲያ እን ድን ወንድ አይረታውም ፣ አያንሆልለውም ፣ ግራ አያጋባውምን አይ

@OLDBOOKSPDF

ጥለውም ያም ሆኖ ግን ደስ የሚል ነገር ነው ። ቢረቱም ቢወ ድቁም ነብስን የሚያስደስት ነገር ውስጡ አለ ።

"በል እንግዲያው እነ ካድ ካልቨርት ቤት እንሂድና አራታችንን አንብላ ። ካትሊን ከቻርልስተን መምጣቷን እስካርሌት ነግራናለች። ምናልባትም ስለፎርት ሰምተር ያልሰማነው አዲስ ወሬ ይዛ መጥታ ይሆናል ። "

"እሄሄ ካትሊን ናት ስለፎርት ሰምተር የምትነግረን ። እሷ ለራሷ ፎርት ሰምተር መወረሩን እንኳ የምታውቀው እኛ ያን ኪዎቹን ድርሻቸውን ካጠፋናቸውና ካስወጣናቸው በኋላ ነው ። እሷን ወንድሜ ፡ ስለ ሄደችባቸው የጸንስ ፓርቲዎችና ፡ ስላወጣ ቻቸውና ስላፈቀረቻቸው ወንዶች አውሬ በሳት ። "

"ምን ችገረህ ስትዘባርቅም መለማት አንድ ጨዋታ ነው ። ያዝናናል ። እግረ መንገዳችንንም እማማ እስክትተኛ ድረስ መደበቂያ ይሆነናል ። "

"መቼም ካትሊንን እንኳ እወዳታለሁ ። ተጨዋች ናት ። ስለካሮ ሬትና ስለቀሩት የቻርልስተን ሰዎች መስማትም አፈልጋለሁ ። ከዚያች ያንክ እንጀራ እናቷ ጋር ግን ራት አስከሚበላበት ሰዓት ድረስ ቁጭ ከማለት ግሀነም መግባት ይሻላል ። "

"ምነው ስቱዋርት ይሄን ያህል አትጨክንባት ። እስከዚህ ክፉ አይደለችምክ"

"መጨከን አይደለምክ ታሳዝነኛለች ፡ ማዘኔ ነው ። ከሚያሳዝኑኝ ሰዎች ጋር መሆን ግን አልፈልግም ። ሁል ጊዜ አንተ እንዳይጨ ንቅህና ቤቷን ቤቱ ብለህ እንድትቀመጥ ከልክ በላይ ወዴህ ወዲያ ስትል ሰላምህን ታሳጣህለች ። ደሞክ የደቡቡን ሰዎች ያልሰለ ጠኑ ፡ ጥሬ ባላገሮች አደርጋ ነው የምትገምተው ። ለማማ ለራሷ እንኳ ነግራታለች - አፍ አውጥታ ። ደቡባውያንን ትፈራለች ። እኛ አጠ ገቧ ካለን ነፍሷ ተመንጭቃ ልትበር ትደርሳለች - በፍርሃት ። ምን እንደምትመስለኝ ታውቃለህ- እወንበር ላይ የተቀመጠች ዶሮ ፡ ወንበር ላይ የተቀመጠች ዶሮ አይኖቹዋን በስጋት እያቁለጨለጨች አንድ ሰው በተንቀሳቀሰ ቁጥር ከአሁን አሁን ያዘኝ አነቀኝ እያለች ለመጮህ እንዳኮበኮበች ትውላለች ። የዚች ያንኪም ይኸው ነው አመሷ ። "

"ግን አትጥረድባት ።መቼም ልጅዋን ካድን እግሩን በጥይት መት ተህባታል ሴላው ቢቀር"

@OLDBOOKSPDF

"አይ ያኔ እንኳ የጨዋታ ነበር እንጂ ክሙራት ተነስቼ አል መታውም ።" አለ ስቴዋርት ። "ደሞም ካድ ራሱ ያከፋት እንዳ ልሆነ ገብቶታል ። ከትሊንም ሆነች ፌርርድ ወይም አቶ ክልቨርት በጭራሽ ቅሬታ አልተሰማውም ። ያቺ ያንኪ እንጀራ እናቱ ብቻ ናት የባጡን የቆጡን እየቀባጠረች ጠብ ያለሽ በዳቦ ስትል የከ ረመችው ።እኔንማ ገና ከጫካ የወጣሁ የዱር አውሬ አድርጋ ነው የምታየኝ ።እነዚህ የደቡብ ጥሬዎች እያሉ የሠለጠነ ሰው እንዴት በሰላም ይቀመጣል ትላለች ።"

"ሙቼም አይፈረድባትም ።ያንኪ ናት ።ያንኪ ደግሞ ለበለሙ አብ ወልዱ እንኳ ዐባይ የሚባል ያለተፈጠረበት ጋጠ ወጥ ነው ። ወጣም ወረደ ልጄን ተኩሰህ መትተኸዋል — አይደም እንጀራ እናቱ ናት ።"

"ለምን ጀሀነም አትግባም! እሷን የምትለድበበት ምንም ምክን ያት የለም ። አለቂ ባንተ በራስህ እየው ።ያን ጊዜ ቀኒ ፎንቱን እን ተን እማርህ ላይ በሽጉጥ የመታህ ጊዜ እማማ ምን አለች ።ከብራኳ የወጣሀ ልጅዋ ነህ ፣ ግን ቀኒን ሰደበችው ፣ አልሰደበችውም ።ይልቁንም ዶክተር ፎንቴንን ተሳሎ አስጠርታ ቁስሉ እንዲታሽግለህ ካደረገች በኋላ ፣ ቀኒን ሙንፈሱን የረበሸው ምን እንደሆነ ዶክተሩ እንዲጠይ ቀውና እንዲያፈጋጋው ነግረችሰት ። ይሄ አጉል የግጥሚያ ጨዋታ ከጨዋዎቹ ጉረቤቱ ሊያራርቃቸው መሆኑን ተናገረች ።ታስታውሳ ለህ ይሄ የሷ አድራጎት ቀኒን ህሊናውን ነክቶ ሊያሳበደው እንደደ ረሰ?"

ሁለቱም ልጆች ልባቸው አለክፈርበ እየጮሁ ሳቁ ።

"እማማ እኮ መጫወቻ ማለት ናት—ምስኪን ።" አለ ቭሬንት ለእናቱ ያለውን ፍቅር በሚገልጽ ታና ። "የፈለክውን ነገር እንድታደ ርግልህ ጠይቃት ፣ አንዳችም ሰው ፊት የሚያሳጣህ ጣጣ ውስጥ ሳትገባ ትፈጽምልህለች ።"

"አሱስ ልክ ነህ ነገር ግን ዛሬ ማታ አባባና እህቶቻችን ፊት የውርደት ማቅ ማከናነቢን አትተውም ።" አለ ስቱዋርት ከልቡ ተመ ስጦ ። "ይኸውልህ ብሬንት ፤ይሄ ማለት እኮ ከእንግዲህ ወደአውሮፓ አንሄድም ማለት ነው ።ሁለተኛ ከኮሌጅ ተባርረን ብንወጣ ታሳቱ ሽርሽር እያልን አውሮፓን የምናስስበት ፕሮግራም ሁሉ አፈር ድሜ ጋጠ ማለት ነው ።"

"ኤጭ ጀሀነም ይግባ ግድ አለን እንዴ እኛ ነአውሮፓ ውስጥ ምን የሚታይ ነገር አለና ነው ?እርግጠኛ ነኝ እነዚያ አውሮፓውያን እዚህ ጆርጂያ ውስጥ የሌለ አንድም ነገር አያቀርቡልንም ። ፈረሶቻ

@OLDBOOKSPDF

ቸው እንደኛ ፈረሶች አይሮጡ ፥ ሴቶቻቸውም እንደኛ ሴቶች ቆንጆ አይደሉ ።ለምኑ ነው ?ደሞ ካባባ ውስኪ የሚወዳደር ምርጥ ራይ ውስኪ እንደሌላቸው እመራረዳለሁ ።"

"ያሳቸው የመልክዐ ምድር ወጥትና ሙዚቃ ሌላ ነው" አለ አሽሌይ ዊክስ ሲናገር ።አሽሌይ አውሮፓ ነጥሱ ናት ።ሁልጊዜ ስሰፈ ነው ወሬው ።"

"እሱ እንኳ መቼም የዊክስ ዘር ስለሆነ ነው ።የዊክስ ዘሮች ስለ ሙዚቃ ፣ ስለ መጽሐፍና የመልክዓ ምድር ወጥት ያላቸውን ፍቅር ታውቀዋለህ ።እማማ አያታቸው ከቨርጂኒያ ስለመጣ ነው ብላ ነበር። የቨርጂኒያ ሰዎች ለእንዲህ ያሉ ነገሮች ትልቅ ዋጋ ይሰጣሉ ትል ነበር ።"

"እንደፈለጉ ባክህ እራሳቸው ይገናኑበት ።በበኩሴ የምጋል በው ጥሩ ፈረስ ፥ የምጠጣው መጠጥ ፥የማጫውታት ሱንጆ ሴትና የማ ሸጥባት አስቀያሚ ሴት ቤጠኝ የኑሮን አውሮፓ እንዐርፀስ ይስደ ዱት...ጉዞው ቁሪ አልቀረ ጉዳዮችን ነው እንዴ?አሁን አውሮፓ ሆነን ቢሆንና ቦርኑቱ ቢመጣ ምን እንደሚከተል ይታይሀል ? ቶሎ ወደ ቤታችን ስመመለስ እንችልም ነበር ። በበኩሴ አውሮፓ ክምሄድ ወደጦርነት ብሄድ ይሻለኛል ።"

"እኔም እሱ ነው ምርጫዬ ። ለምን የፈለገው ቀን አይሆንም ። እ ብሬንት ይልቅ ራት የት ልንበላ እንደምንችል አሁን መጣልኝ ። በል ቀጥ ብለን ወደ አቪል ዋይንደር መኖሪያ ቤት በረግረጉ መሬት አዙርጠን እንሂድና ኤራታችንም ወደቤት መምጣታችንንና ለወታደ ርነት ልምምድ ዝግጁ መሆናችንን እንንገረው?"

"ብራቮ! ብራቮ! አይ እንተ ዘዴ መቼም እምላስህ ጫጭ ሳይ ነው ያለው ።"አለ ብሬንት በሀሳቡ በጣም ስሄቱ ተነክቶ እየጮኸ ። "ስለ ሠራዊቱም አዲስ ወሬ ካለ እንሰማለን ። በዛውም የዩኒፎርሙ ቀለም ምን ዓይነት እንዲሆን እንደተወሰነ ይነግረናል ።"

"መቼም የዘጭሽን ቀይ ቀለም ከመረጠ እኔ ብሞት ከሥራ ዊቱ ጋር አልዘምትም ። ያንን ቀይ ሱሪ ስለብስ ሴት የሆንክ ነው የሚመስለኝ ።የሴቶች ኩርሲ እኮ ነው የሚመስለው?"

"እንግዲህ ወደ ዋይንደር ቤት ለመሄድ ወስናችሁ ማለት ነው? እህ ለመሄድ ከሆነ ያሰባችሁት ደህና ራት አታገኙም።" አለ ጂምስ። "ምግብ አብሳይዋ ሞታባቸው ሌላም አልተጠሩ ።እንዲት ልዩስኩስ ያለች ባንሩ የተናቀች ሠራተኛ ናት ለጊዜው ያለቻቸው ። "እግሮዎቹ ሁሉ ጉድ እያሉ ነው የነገሩኝ ።"

@OLDBOOKSPDF

"እሪ የእግዚር ያለህ! ምነው ሴላ ደህና ባርያ ቢገዙ?"

"እንዴ ምን ሆናችሁብኝ ፤ ደግሞ በየት አገር ነው እንደነሱ ያሉ የማይረቡ ደህ ነጮች ባሪያ የሚገዙት ? በዕድሜያቸው ከአራት በላይ ኬግሮ ኑሮዋቸው አያውቅም ።"

ጂምስ ድምጽ ውስጥ ጥላቻ እንዳለበት ያስታውቃል ። የታርሌተን ቤተሰብ ከሙቶ በላይ የሚያዛቸው ባሪያዎች ያለው ባለፀጋ ቤተሰብ በመሆኑ ጂምስ በጌቶቹ ሀብት እየተመካ እንደሌሎች የሀብታም ባሪያዎች ሁሉ ጥቂት ባሪያዎች ያፏቸውን ገበሬዎች ቁልቁል ያያል ይንቃል — ያንቦጥጣል ።

"እንተ እቤል ዋይንደርን ነው የማይረባ ነጭ የምትሰውን ሁሉ ተኛ እንዲህ ያለ ቃል ከአፍህ ሲወጣ ብሰማ የውስጥ ቆሻሀን ነው ወደላይ የምገለብጠው ። እርግጥ ደህ ሊሆን ይችላል ፤ የማይረባ ርካሽ የሚባል ሰው ግን አይደለም ።በበኩሌ አንድ ሰው ጥቁርም ይሁን ነጭ ስለሱ ከፉ ሲናገር ብሰማ ድራሹን ሳላጠፋው እንቅልፍ አይወስደኝም ። በሰፈራ እኩ ከሱ የተሻለ ሰው አይገኝም ። ያ ባይሆንማ ኖሮ ሠራዊቱ የመቶ አለቃ አድርጎ ይመርጠው ነበር ?"

"እሱን እንኳን እንጂ" ብሎ መለሰ ጂምስ በጌታው ማስፈራሪያ ምንም ሳይረበሽ ። "መኮንኖችን ከሀብታሞች ማህል እንጂ ከርካሽ ድሆች እንደማይመርጡ በደንብ አውቃለሁ"

"እሱ እርካሽ ደህ አይደለም እኮ ነው የምልህ አንተ ! አሁን ግን ይመት እሱን መሳይ ሰው እንደስላቱራ ቤተሰብ ከሉት ርካሽ ነጮች ልታወዳድር ነው ፤ አቤል ሀብታም አይደለም ። እነስተኛ ገበሬ ነው እንጂ ባለሰፊ እርሻ ገበሬ አይደለም ። እና ሠራዊቱ ውስጥ ያሉት ወጣቶች እሱን የመቶ አለቃ አድርገው በመምረጣቸው ማንም ባሪያ ተነስቶ ስለሱ አጉል ነገር መናገር የለበትም ። ሠራዊቱ የሚሠራውን ያውቃል ።"

የፊረሰኛ ሠር የሚባለው ሠራዊት የተሟቋመው ጆርጂያ ከሕብረቱ አገሮች ተገንጥላ ከወጣችበት ቀን ጀምሮ ነው ። ከሰስት ወር በፊት መሆኑ ነው ። ከዚያ ጊዜ ወዲህ ምልምል ወታደሮች የጦርነት ያለህ እያሉ ሲያፋጨ ከርመዋል ። የሠራዊቱ ስም ነገር ግና አልተነሳም ። ሆኖም አሰተያየት እንዲሰጥበት የሚያስፈልግ ሆኖ አይደለም ። ልክ ማንም ሰው በዩኔፎርሙ ስፌትና ቁልም ላይ አስተያየት እንዳለው ሁሉ በዚህም ላይ አስተያየት ይኖራል ። "የክላይተን የጹር ነብሮች ፣" "እሳት በላው ሠር" ፣ "የሰሜን ጆርጂያ (ሐሣር) ፊረሰኞች" ፣ "ዙቁ ቮች" ፣ "የአገር ውስጥ ጠመንጅኞች (ምንም እንኳን ሠራዊቱ የሚታ

@OLDBOOKSPDF

ጠቃሙ ሽጥ ፡ ጕራዴና ተወርዋሪ ሰንጢ ቢሆን) ፡ "የክላይትን ማራጫ ለባሾች" ፡ "ደም የጠማው ሙበረቅ" ፡ "የራጥና ሬዲዎች" ፡ የሚሉ ሰሞች ተሸጕድጕደው ነበር ። የስም ማውጣቱ ነገር እስኪገባደድ ድረስ ግን ማንም ሰው ጠራን ሠራዊቱ እያለ ይጠራዋል ። ሆኖም ስም ከመ ጣለት በኋላ እንኳ "ሠራዊቱ" መባሉ አልቀረም ።

መክንኖች የሚመረጡት በሠራዊቱ አባላት ነው ። ምክንያቱም የመንደሩ ሰው እንዳይመርጥ የመርነት ልምድ የለውም ። ትንሽም ልምድ ያላቸው ቢኖሩ በሚክሲኮውና በሴሚኖሉ መርነት ላይ የነበሩ አባት መረጭች ናቸው ። ሠራዊቱ ደግሞ አባት መረጭቹን ወይ ካልወደዳቸው ወይ ካሳመናቸው ወይ በግል ካልቀረባቸው በቀር መረ ይሁኑ ብሎ በጭራሽ በጀ አይልም ። ኤራቱን የታርሴተን ቤተሰብ ወንዶች ልጆችና ሶስቱን የርንቴን ቤተሰብ ወንዶች ልጆች መቼም የማይመለከቸው ሰው የለም ። ሆኖም እንዳይመረጡ ፪ ቆሎ ጓተው እሳት ውስጥ የሚገቡና ማምለጥና ማጭበርበርን እንደተራ የሚቆጥሩ በመሆናቸው ሰው ሁሉ አዝኖ ተዋቸው ። ፎንቴኖችማ ጭራሽ ደርሶ ቱማ የማለትና ሚደለው ደምስሰው ለማለት የመቸኮል ጠባይ ስላላቸው ለምልመሳው ብቁ አልሆኑም ። አሽሌይ ዊክስ ከሰ ፊሩ ምርጥ የራረስ ጋሳቪ በመሆኑና ቅዝቃዛ አእምሮው ሥነ ሥርዓትን ለማስከበር አመቺ ነው ተብሎ ታምኖበት በሻምበልነት ተመ ረጠ ። ሬይሞርድ ካልሽርት ደግሞ ሁሉ ሰው የሚወደው በመሆኑ በምክትል መቶ አለቅነት ተመረጠ ። አንስተኛ ገበሬውና የአሣ አጥማጅ ልጅ የሆነው አቤል ዋይንደር ሰሙስ መቶ አልቅና ተመረጠ።

አቤል ጮሌ ነው ። አልተማረም ። ግዙፍ ነው ። ልበ ሩህሩህና ከሴሎች ልጆች በእድሜው ጠና ያለ ሲሆን ሴቶች ያሉበት ቦታ ጠባዩን በማሳመር የሚተካከለው የለም ። በሠራዊቱ ውስጥ ደጅ ጥና ትና ጭራ እየቆሉ መሽም በመጠኑ አለ ። ብዙ አባቶቻቸውና አያቶ ቻቸው ከተራ ገበሬነት ሀብታም የሆኑት በዚህ መንገድ ነበር ። አቤል በሠራዊቱ ውስጥ ካሉት ሁሉ ክር በጥስ የሆነ አነጣጣሪ ተኳሽ ነው። ከየትና የት ቆሞ የሽኮኮ ዓይን ነጥሎ ያወጣል እየተባለ ይነገርለ ታል ።በዛ ላይ ከቤት ውጭ ያለን ኑሮ በደንብ ተለማምዷል ። በዝ ናብ ጊዜ የእሳት መሞቂያ ሥፍራ ማዘጋጀት ፡ እንስሳትን ማሰማራ ትና ውሀ ያለበትን ቦታ ፈልጎ ማግኘት ይሆንለታል ። ሠራዊቱ ለእን ዲህ ያለው ችሎታ ዋጋ ስለሚሰጥና እሱንም ስለሚወደው መክንን ጂህ ያለው ችሎታ ዋጋ ስለሚሰጥና እሱንም ስለሚወደው መክንን አደረገው ። እሱም ቢሆን ያለአንዳች ጉራና እዩኝ እዩኝ ፤ ከልቡ ለማ ገልገል ሙያውን አክብሮና ግዴታዉ ብሎ ተያይዞታል ። ይህ ሁሉ ሆኖ ግን የሰፈ አርሻ ባለይዞታዎች ሚስቶች ባሪያዎች ከደህና ቤተሰብ ባለመወለዱ መናቃቸውን አልተዉም ። ምንም እንኳ ከነሱም ማህል

@OLDBOOKSPDF

ለወግ ማዕረግ የበቁና ከነጮች ጉዶቻቸው አኩል የሚቆሙ አኩዮ ቻቸው ቢኖሩ ነጣሩን በአምንታ አልተቀበሉትም ።

በሙጅመሪያ ወደ ሠራዊቱ ለመግባት የሚመለመል ሰው ዘር ወገኑ ታይዩ ነበር ። የባለ ሰፊ እርሻ ሌጆች የሆኑ ፈለጥርነቱ የሚያስ ፈልገውን ፈረስ ፣መግሪያ ፣ቁሳቁስ ፣ዩኒፎርምና የግል አሽከር ሊዮቅ ርቡ የሚችሉ ነበሩ የሚመረጡት ።ነገር ግን ገና አንገቷን ቁና በማ ድረግ ላይ ባለችው በድንግሏ የክላይቱን መንደር ሐብታም ባለሰፊ —እርሻ ገበፈዎች ቁጥር በጣም ትንሽ ነው ። በተጨማሪም ጠንካራ ሰራዊት ለመመሥረትና በቂ ብዛትም እንዲኖረው ከድሀው ገበሬም፡ ከአፃኑም ፣ ከአሣ አጥማጁም ፣ ከቅጥቃጩም ፣ አልፎ ተርፎም ከደሀ ነጮችም መመልመል አስፈላጊ ሆነ ።

እንዚህ የጎለጮቹም ምስኪን ወጣቶች እንደሐብታም ጐረቤቶ ቻቸው መርነት ከመጣ ያንኪምቱን አፈር ማስጋጥ አለብን የሚል ብርቱ ፍላጐት ነበራቸው ።ደሩ ግን ያቺ ክፉ የገንዘብ ጥያቄ ማንቆ ሆነችባቸው ። ፈረስ ያሳቸው ትናንሽ ገበሬዎች ቁጥራቸው በጣም ውሱን ነው ።አብዛኛውን ጊዜ ብየአርሻው ቦታቸው የሚጠቀሙባቸው ከአ ራት በማይበልጡ በቅሎዎች ነው ። ለሠራዊቱ ለመመልመል ብቃት አላችሁ ቢባሉ እንኳን ከአሰት እንጀራ ማብሰያ ኮርፈው ወደመር ሚዳ የሚላኩ በቅሎዎች አይኖሯቸውም ። ደሀዎቹ ነጮች እንኳን አንድ በቅሎም ቢኖራቸው ራሳቸውን ከና አድርገው የሚያዩ ናቸው ። የየ ጢሻው አዳኞችና አሳ አጥማጆች ደግሞ ፈረስም ሆነ በቅሎ የላቸ ውም ። ሙሉ በሙሉ ከመሬታቸውና ከረግረጉ መሬት የሚገኘውን ነገር ዕቃ በዕቃ ወይም ዐይነት በዐይነት በመለወጥ ዘዴ እየተጠቀሙ የሚኖሩ ናቸው ። በዚህ አኗኗራቸው ደግሞ ገንዘብ እንደብርት የሚ ታይ ነገር ነው ። ጥሬ ብር በዓመት አምስት እንኳ ከቆጠሩ በጣም ትልቅ ገንዘብ ነው ። ፈረስና ዩኒፎርም ከነሱ ህልም ውጪ ናቸው ። ይህም ሆኖ ሀብታሞቹ በባለዐግነታቸው እንደሚኮሩ ሁሉ እነሱም በድህነታቸው የሚኮሩ ናቸውና ከሀብታም ጐረቤቶቻቸው እጅ እም ስት ሳንቲም እንኳን በምዕዋት መልክ ቢሞቱ አይቀበሉም ። ስለዚህ አንድም የሁሉንም ሰው በጦርነቱ ውስጥ የመሳተፍ ፍላጐት ለማር ካት ፣አንድም የሠራዊቱን ጥንካሬ ለመጠበቅ ሲባል ባለሰፊ እርሻ ዎቹ የመንደሩ ሀብታሞች ማለትም የአስካርሌት አባት ፣ጆን ዊክስ ፣ በከ ሙንሮ ፣ ጂም ታርሌተን ፣ ቬማ ካልቨርት ፣ (አንገስ ማኪንቶሽ ብቻ ሲቀር) ሠራዊቱን ለመርጃና የፈረስና የሰው ቁጥር ለመጨመሪያ የሚረዳ ገንዘብ አጥተው ሰጡ ። መላ ተበለ የተመረጠው ሌሳው መንገድ ደግሞ እያንዳንዱ ሀብታም የራሱንና የሌሎቹንም ሰዎች ልጆች ራሳቸውን ችለው ወደሠራዊቱ እንዲቀላቀሉ ማድረግ ነበር።

@OLDBOOKSPDF

በአፈጻጸም ላይ ግን አነሰ አነሰ ያለ የሀብት ድረጅ ያላቸው ልጆች ከብሬ ተንካ ሳይሉ ፊረስና ዩኒፎርም እንዲቀበሉ ማድረግ ነበር ።

ሠራዊቱ ለጦር ልምምድና ጦርነቱ ቶሎ እንዲጀመር ለመፀለይ በግምት ሁለት ጊዜ ጆንስቦሮ ላይ ይገናኛል ። የፊረስ ብዛት ከታ ባለ መስተካከሉ ምክንያት አሁንም ሙሉ ዝግጅት ለማድረግ አልተቻለም። የራሳቸው ፊረስ ያላቸው ያላቸው ግን ከየቤታቸው ግድግዳ እየነቀሉ ያመጡትን የጥንት ጦርነቶች ቅርስ የሆኑ ጐራዴዎች እያወናጨፉ ፤ ጀግና ፊረሰኛ ማድረግ አለበት ብለው ያመኑትን ልምምድ ለማድረግ ከዋናው ሜዳ ጀርባ እየጋለቡ ፣አቧራውን እያጨሱ ጩኸታቸውን ያስነኩታል ።ፊረሰ የሌላቸው የሌላቸው ደግሞ በሁላርድ መጋዘን ፊት ለፊት ተሰምጠው ፤ የሚጋልቡትን ጓደኞቻቸውን እያዩ ቅንባሠ ያሻክሉ ፤ የጥንት ጀብድ ታሪኮችን ይተርካሉ ።አለበለዚያም የተኩስ ውድድር ይጀምራሉ ። ማናቸውንም ተኩስ ማስተማር አስፈላጊ አይደለም ። አብዛኛዎቹ የደቡብ ነዋሪዎች ሲወለዱ ጀምሮ ጠመንጃ ከእጃቸው ሳይለይ ነው የሚያድጉት ።የአደን ሕይወትም ከአስተዳደጋቸው ጋር የተሳሰረ በመሆኑ ብዙዎቹ አንጣጣሪ ቅልጥም ሰባሪ ናቸው ።

ከየባለእርሻዎቹ ቤትና ከየረግረጉ ቦታ መጋዘኖች ሰየጦር መሪው የሚሰጠው የጦር መሣሪያ ዓይነት እጅግጉድ ይፈላል ። ጥንት አሴጂ ኢሶች በተባረሩ ጊዜ የንበሩ ረጃጅም ያውሬ ማደኛ ሪሾች ፣ጀርጂያ ገና ወጣት ሳለች ንዋሪ የንበሩት ሕንዶች ይይዙት የንበረው ባፉ ጐራሽ ናስማስር ጠመንጃ ፣ በሚከሲኮውና በሴሚኖል ጦርነቶች ላይ በ1812 ያገለገሉ የፊረስ ሽጉጦች ፣ ብርማ እጀታ ያላቸው የተኩስ መሳለሚያ ሽጉጦች ፣ ባለረጅም ካርታ ዴሪንጀር የኪስ ሽጉጦች ፣ ባለ ሁለት አፈሙዝ የአደን ጠመንጃዎችና የሚያማምሩ ባለአብረቅራቂ የእንጨት ሰደፍ ፣ የአንግሊዝ ጠመንጃዎች ይሸጐዳጐዳሉ ።

ልምምዶቹ ሲያበቁ የጆንስቦሮ አዳራሽ ቦታ ይጠበቃል ።ያንኪዎች እስከመጡበት ጊዜ ድረስ ከልምምድ በኋላ የሚፈጠረውን እምባዳሮ መኩንኖቹ በእለት ሁኔታ ለመመገብ እስኪታክታቸው ድረስ ታቸግረውበት ነበር ።ከእነዚህ አምባዳሮዎች በአንደኛው ውስጥ ነበር ስተዋርት ታርሉተን ካደ ካልቨርትን ፣ ዶሲ ፎንቴን ደሞ ብፈንትን በተኩስ ያቆሰሉት ። ሠራዊቱ በሚደራጅበት ጊዜ መንትዮቹ ወንድማማቾች ከቨርጂኒያ ዩኒቨርሲቲ ገና ተባረረው የመጡበት ጊዜ ስለነበር በጉጉትና በስሜት ተቀላለው ነበር ። የዛሬ ሁለት ወር እርስ በእርስ ተታኩሰው ከተቋሰሉ በኋላ ግን እናታቸው ወደ መንግሥት ዩኒቨርሲቲ እንዲገቡ አደረገቻቸው ።ከዚያ ንቅንቅ እንዳይሉ አስጠንቅቃ

@OLDBOOKSPDF

ቸዋለች ።እዚያ በነበሩ ጊዜ በልምምድ ላይ ያለውን ደስታና ጨዋታ አጥተውት ነበር ። በነሱ ግምት ከጓደኞቻቸው ጋር ጥይት እየተኩሱና እየጮሁ ፈረስ እስከጋለቡ ድረስ ትምህርት ጊዜ መጥፎ ነገር ነው።

"በል አቪ ንጠር ገጠሩን እየሰነጠቅን አቢል ቤት እንሂድ" ብሎ ብሬንት ሐሳብ አቀረበ ። "በጂራልድ አሃራ መኖሪያ ግርጌ ባለው ወንዝ ጥሩ ጥጉን ይዘን በፎንቱን የግመሽ መሬት በኩል ቶሎ እንደርሳለን።"

"የምንበላው ግን አናገኝም ፣ ያው ድንችና ቅጠላ ቅጠል ብቻ ነው" አለና ከርከር ጀመረ ጂምስ ።

"እንተማ ምናምኒት አታገኝም" አለ ስቱዋርት ኮስተር ብሎ "ምክንያቱም እንተ እማማ ጋ ሄደህ ለአራት እንደማንመጣ መንገር ስላለብህ ነው።"

"እንዴ ምን በወጣኝና!" ጂምስ ጨኸቱን አቀለጠው ። "በሞራሽ አላደርገውም! እሜቴ መጀመሪያ ቢመቱኝ ከናንተ የተሻለ ምን አገኛና ነው የምሄደውን በመጀመሪያ ነገር እናንተ ሁላችሁ በድጋሚ ቢትባረሩ ለምን ዝም ብዬ እንዳየሁ ይጠይቁኛል ። ሁለተኛ ደግሞ ዛሬ ማታ ሁላችሁም ተገቢ ቅጣታችሁን እንዳታገኙ ለምን ጥያችሁ እንደ ሄድኩ እጠየቃለሁ ። በመጨረሻም የሰኔ ጉንዳን እንዳየች ዳክዬ ቱማ ብለው ሲዘልሉብኝ ስዘሀ ሁሉ ጠቡ እኔ መሆኔን እረዳለሁ ። ስለዚህም ወደ ዋይንደር ቤት ይዛችሁኝ የማትሔዱ ከሆነ ፣ እዚሁ ጫካ ውስጥ ቁጭ ብዬ አድራለሁ ፣ ወይ የማታ ተረኛ ተቆጣጣሪዎች ያገኙኝ ይሆናል ። ቢሆንም እሜቴ ተበሳጭተው ከሚያገኙኝ ተቆጣጣሪዎቹ ቢይዙኝ ይሻለኛል ።"

መንትዮቹ ግራ በመጋባትና በመናደድ ወደ ቁርጠኛው ባሪያ ልጅ ተመለከቱ ። "መቼም ተቆጣጣሪዎቹ እንዲይዙት ማድረጉ እንኳ ጅልነት ነው ።እንደዛ ከሆነ ደግሞ እማማ ለሳምንታት የምታወራው ነገር አገኙች በለኝ ።አቤት ፡መቼም ባሪያ ሲባል አዳ ነው ።አስቸጋሪ ፡ አንዳንዴ የእነዚያ የባሪያ ነፃ አውጪ አቦሊሽኒስቶች ሐሳብ ትክክል ነው እላለሁ ።"

"ለማንኛውም እኛ ልንጋፈጠው የማንፈልገውን ነገር ጂምስ ይጋ ፈጥ ማለት ትክክል አይደለም ።ይዘነው መሔድ አለብን ።እና አንተ ጋጠ ወጥ ጅል ባሪያ ለንዚያ ለዋይንደር ባሪያዎች እኛ ዶሮ ጥብ ስና አላማ ስንበላ እነሱ ግን ከጥቸልና ከባሕር አዛ በስተቀር የ ሚ በሉት እንደሌላቸው ታውራላቸውና ነግሬሃለሁ! ኋላ ለእማማ ነው የምነግርልህ ።ወደ ጦርነቱም በታ ከኛ ጋር ይዘንህ እንሄድም ።"

@OLDBOOKSPDF

"እኔ ነኝ የማወራው? ለነዚያ ርካሽ ኤግሮዎች ነው እኔ የምናገረው! የለም የኔ ጌታ የተሻለ ፀባይ ነው ያለኝ እሚቴ ቢትሪስ እናንተን ቀጥተው እንዳሳደጓችሁ ሁሉ እኔን ቀጥተው የለ እንዴ?

"እሱስ ሶስታችንምን ቢሆን በደንብ አልቀጣችንም" አለ እስቱዋርት በልና መንገድ እንቀጥል።"

ትልቁን ቀይ ፈረሱን ከወደ ኋላው መታ መታ አድርጎ እጫማው ላይ ባለው መከራከሪያ ተጣ ተጣ በማድረግ ባለ ሽቦውን አጥር በቀላሉ አሻግሮ እጀራልድ አንፃራ እርሻ ውስጥ ወዳሉት ለስላሳ ሜዳዎች ዘለቀ። የብሬንት ፈረስ ተከተለው። ከዚያም የጂምስ። ጂምስ የኮርቻውን ጫፍና የፈረሱን ጋማ ይዟል። ጂምስ በፈረስ አጥር መዝለል አይወድም። ሆኖም ከጌቶቹ ጋር እኩል ለመጓዝ ሲል ብቻ ከዚህ ከፍ ያለውንም ዘልሏል።

ቀዩን ፈረፈር ተከትለው፣ ቁልቁል በኮረብማታው ወርደው፣ እወንዙ ግርጌ ሲደርሱ ጨለማው ላይን መያዝ ጀመረ። ይሄኔ ብሬንት ጮክ አለና :—

"ስቱዋርት፤ እስካርሌት እራት የምትጋብዘን አልመሰለህም ነበር እንዴ?" ብሎ ጠየቀ።

"እኔማ እስካሁንም ድረስ እንደሱ ነው የሚመስለኝ" ብሎ መለሰ እስቱዋርት በጩኸት "ግን ለምን ገመትክ...."

@OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ 2

እስካርሌት ፡ መንትዮቹ ልጆች ታራ ውስጥ እደጎጥዋ ላይ ጥለ ዋት ከሄዱ በኋላና የመጨረሻው የፈረስ ኮቴ ድምጽ ከሞተ ወዲህ ፣ በሕልም ፡ በሰመመን እንደሚንገዘ ሰው እየተሳበች ወደ መቅመጫዋ ተመለሰች ።ፊትዋ በሕመም ምክንያት ጣር እንደያዘው ሁሉ ድርቅ ርቅ ፡ ግትርትር ብሏል ። አፍዋም ቢሆን ፡ መንትዮቹ ምስጢሯን እንዳያውቁባት የውሸት ፊገግታ ለማሳየት ስትሰጥጠው ከመቆየትዋ የተነሳ እንደወትሮው አይደለም ። በደካም ስሜት ዛል እንዳለች ተቀመጠችና በአንዱ እግሩዋ መሬቱን ትቆረቁር ጀመር ። ከስቃይዋ የተነሳ ልባ ያለልክ አብጦ ደረትዋን ፈጥርቆ ሊወጣ ደርሷል ። እንግዳ በሆነ የልብ ትርታ እመር እመር ይላል ። እጆችዋ ቅዝቅዝ ብለው በረዶ ሆነዋል ። አንዳች የመከራ ጫና ከፉኛ ይደቁሳታል ። ፊትዋ ላይ ሕመምና ግራ መጋባት ይነበባል ። የፊለገውን ነገር እንደልቡ የሚያግኝ ቀብራራ ልጅ ለመጀመሪያ ጊዜ የኑሮን አስከፊ ገጽታ ሲያይ እንደሚሆነው ያለ ግራ መጋባት ስፈነባት ።

ወይ ጉድ — አቨሌይ ፡ ሚላኒ ሐሚልተንን ሲያገባ ነው እኮ!

በፍፁም እውነት ሊሆን አይችልም ። መንትዮቹ ተሳስተው መሆን አለበት ፡ እንደተለመደው ሲቀልዱባት ነው እንጂ የሦራቸውን አይደለም ።አሽሌይ እሷን ሲያፈቅር በጭራሽ አይችልም ።አይችልም — አይችልም ።እረ ማንም አይችልም ።ደሞ ከዛች ኮሳሳ ፍጥረት ከሚላኒ ጋር ማን ፍቅር ይይዘዋል ። እስካርሌት የሚላኒን ቀጫጫ ሰውነትና ከሞላ ጐደል የቤት ልጅ መልክ የሚሰጣትን ግልጽ የልብ ቅርጽ ያለው ፊቷን በጥላቻ አስታወሰች ። አሽሌይ ደግሞ በወራት ሊሚቆጠር ጊዜ አይታት አያውቅም ። አምና በአሥራ ሁለቱ ዋርካዎችውስጥ ደግሶት ከነበረው ፓርቲ ወዲህ ወደ አትላንታ ከሁለት ጊዜ በላይ አልሄደም ። የለም — የለም ፡ አሽሌይ በጭራሽ ከሚላኒ ጋር ፍቅር ሊይዘው አይችልም ። ምክንያቱም ... አይ በዚህ ጉዳይስ አትሳሳትም!! ምክንያቱም እሱ ከእራስዋ ጋር ፍቅር የያዘው ስለሆነ ነው!! እራሷን እስክርሌትን ነበር የሚያፈቅረው!! እረ በደንብ አድርጋ የምታውቀው ነገር ነው!!

ማሚ የአዳራሹን ወለል ድው ድው እስኪል ድረስ እየረገጠችና እየነቀነቀች ስትመጣ እስካርሌት ሰማችና በእግርዋ መሬቱን መቆር

@OLDBOOKSPDF

ቀራዋን ታብ አድርታ ፊትዋን አበባ አሰለ ቡኻድሪግ ታሰትክነለ ግሎ ። አንድ መጥር ነገር እንዳጠማት ማሚ አንዳትጠረጥር ሚድ ሬማ የሚዲ ነው ። ማሚ የእሃራን ቤተሰብ በሙሉ በነፍሱም ሀበታም የሬስዋ ኤኖርታ የምትቆጥርና የኡሃሪዎችን ሚስጥር እንደራስዋ ሚስ ጥር የምታይ ናት ። ስለዚህ ከፅ, የተሸሸገ ቅኑጣት ታሀል ሚስዮር እንኳን ደም እንዳጠማው አዳኝ መሸ ያትበጠብጣታል ። የማሚ የማ ወቅ ጥላት ቸሉ ከልረክ ጉዳዩን ባንድ አፍታ ኤለን ጀሮ እንደምታ ደርስው አስክርሌት አላምራ ታውታለች ። እንዲህ ከሆነ ደማሞ አስክርሌት ሀብን ነገር ለእናቷ ጥርዋርጥ አድርታ መንገር ወይም እንድ ፃሚያጣጣ ውሸት መፍጠር ይሞርባታል ።

ማሚ ክንዛሁዋ ስውነቷ ድንገት ከአለፍጥ ብቅ አለች ። ነገን ንጆቹንና እንደገሠሩ አደን ሸረኛ የሆኑትን ዓይሃቹሞን ታነቋቋጨሚ ቸቀለች ። እንደዘለቄታት የሚዘረቀርቀው ሥቱር ፊቷ ለቱባ አፍሪካዊ ኑቷ ምስክር ነው ። ኔስክመጨረሻዋ የደም ጠብታ ድረስ ለአሃራ ቤተሰብ ዘታማኝነት የምታሳግል ። ከአለን አሃራ ኡናት ቤት ስትወ ርድ ስትዋረድ የመጣች የአለች ምጣዚት የነበረች ናት ። አለን በለስቱ ሰዓት ልጀጢ ዓመል ብሰሩ ስትሯርጣም ሆነ በቢትአሽከሮቹ ስትበ ሳው መጽደኛና ንሽ መዘገ የሥትሠናት ማሚ ናት ። ማሚ ጥቱር ትሠን እንጂ ነጠያጭና ኩራትዋ ከፔታጣና ከአመለትዋ ቢበልጥ እዛጂ አደንስም ። ያደነቸው በአለን አሃራ ኡናት መኝታ ቤት ውስዋ ነው ። የአለን እናት መይዘር ሰላማ ሮቢንጅ ራታ ደቡ ። ሰለኳስ ኦጥ ንጫና መልክ መልክም የፈረንሳይ ተወላጅ ሴት ሲሆኑ ትንሽ ጥሩት ከየ አሽከሮቻቸውንም ሆነ ልጆቻቸውን ያለምሀረት መትጣት ልማዳ ቸው ነው ። አለን ለታጣባ ከሲቨና ወደ ዩጋው አገር በትመጣ ማሚም አብረ መጣቸ ። ማሚ የወይደቻውን ሁሉ ጸባዩን ማረቅ ትጠዳለች ። አሁን የአስክርሌት ምጣዚት ናት ። አስክርሌትን ስትወዳት ነፍሷ ትመ ጣለች ። ይሞም ትኑረታታሷች ። ስለዚህ ጸባዩዋን የማረቁና ሞበረ ንብነ ትን የማስተማሩ ነገር የዕለት የሰርክ ተግባርዋ ነው ።

"ልጆቹ ሄጹ እንዴ! ለምን እራት አልጋበዝሽዋቸውም አስክርሌነ ጀ እስ እት ሁለት ተጨማሪ ብበታ እንዴያዘጋጅ ስፓርክ ነግሬው ነበር። ምነው መልክም ጸበይሽ ። እንግዳ ተቀባይነትሽ ሁሉ ምን በላው?"

"አዘክሽ ስለጦርነቱ እያወሩ በጣም አታክተውኝ ስለነበር ደግሞ እራት ከጋበዝኳቸው ከአባባ ጋር ይግቡና ስሙ ሊንከን ማውራት ከጀመሩ እልሃን ያስጨርሰውልኛል ብዬ ነው!"

"እውነስ ያንቺ ጸባይ ከባሪያዎቹ ምንም የማይሻል ሆነ ። እኔና እማማ ኤለን አንቺን ለማለተሚር የሰፋነው ሁሉ ከንቱ ቀረ ሠደም

@OLDBOOKSPDF

በዚህ በቅዱሳን ያንተ ልብስነት ሳትያዝብኝ ነው የተላመጥሽውን ስራሉ ብርዱ ሙጣጣ ያሳቅሩል! ስመሣኑ አትክሻሽ ላይ ምንም ሳትያዝቢ በማታ ብርድ ውስጥ መቀመጥ ጉንፋት እንደሚያስይዝሽ ስንት ጊዜ ልንገርሽ! በይ እሁን ቶሎ ወደ ቤት ግቢ አለኳርሴት ።"

አስካሌት በቁጣና በማዲለሽነት ፊትዋን ከማሚ ዘወር አድርጋ ማሚ ለሰ አንተ ልብሱ ስታሰላስል የፊትን ሠለዋወጥ ስላላስ ተሞለች ተመስጌን አለች ።

"የለም እኔ እህሀሁ ቁጭ ብዬ የአሐደሞን አጠላለት ውበት ማየት አፈልጋለሁ ። በጣም ወብ እኮ ነው ። ሩጪና አንተት ልብሱን አንጪ ልኝ አንቺ ። አባክሽ ማሚ አባባ እስኪመጣ እዚሁ ልሁን ።"

"እሪ ደምጽሽም ጉንፋን እንደያዘው ሰው ግርንኒል" አሰች ማሚ ብጥርጣሬ ። "አይ አልያዘኝም እሰብ ።" አለች አስኳርሴት ተዕማሰቷን አጥታ ። "ይልቅ ሂጂ አንተት ልብሴን ፈልጊልኝ ።"

ማሚ ዝርግድ —ዝርግድ ንያለች ወደ አዳራሹ ሄደች ።እርቁ ላይ መዳለችው ሃረድ ሪሙክ ብላ በትጣሬ አስኳርሴት ትሰማታለች ።

"አንቺ ሮባ የአስኳርሴትን አንተት ልብስ ወዴህ ጎጅ ።" ወዲያው ደሞ ሮሙክ ብላ "የማትረባ እግር አንድ ሣጎ እንኳ ተሚኤሎላት ያሏትን ፈጽማ አታውቅም ። እሪ ራሴ ፎት ወጥቼ መፈለግ ሊኖርብኝ ነው።"

አስካሌት ደረጀው ደጃ — ደዝ ሲል ስተሰማ ቀስ አለኝተ ብድግ አለች ። ማሚ በትመለስ መቼም ደንኑ የአስካሌትን የአንማዳ መቀበል ማብረታበትን ማጣት እየጠበሰች ዴስክሩዋን መቀጠል አይቀርም ። አስካርሴት ደሞ እንደዚህ ልባ ሙስሰና ቅስሚ ተሰብሮ ባለችበት ጊዜ በእንደዚህ ያለ ጥቃትን ጎዳይ ማማ ስትቀባጥር ለመስማት ፈጽሞ ትፅግስት አይኖራትም። ይህ የልባ ሕመም ትንሽ ቀለል እስኪላት ድረስ የት ቦታ መደበት እንደሚሻል ቆማ ስታመነታ አንድ ሐሳብ ደንገት ብልጭ ብሎ የተሰሩ ጨረር ፊንጠቀባት። አቧኗ የአሽከርየውን የፓርክን ሚስት ዴልሰ, የምታትባል አዲስ ሠራተኛ ፣ ጎንዘቦን ከቡልሎ ሲገሣ ዛሬ ከሰዓት በሁሞላ አሥራ ሁለቱ ዋርካምች መደሚባለው የሚከሶች እርሻ ቦታ ሄዷል ። ዴልሰ, በአሥራ ሁለቱ ዋርካምች ውስዋ ዋና ሞግዚትና አዋላጅ የንበረች ናት ። ፓርክ ክስድስት ወራት በፊት ያጣትን ዴልሰን እንዲገዛለት ጊታውን ሌት ተቀን ይጨቀጭቀው፡ያሠቱ ተው ነበር ። ግዙዋ እንዲያመጣለትና አብረው እርሻ ውስዋ እንዲኖሩ ብሎ ነው ። ዛሬ ከሰዓት ጂራልድ እንደወትሮው እንቢ ማለቱን ትቶ ዴል ሰን ሊገዛ ሄዷል ።

@OLDBOOKSPDF

መቼም አስከረሌት ያለ ጥርጥር ይሄ የሰማችው የሚዘገንን ታሪክ እውነት መሆኑን አባቷ እንደሚያረጋግጥሌት ተማምናለች ። ዛሬ ከሰዓት የሰማው ነገር ባይኖር እንኳ ምናልባት በሚከሰች ቤተሰብ አካባቢ ያለውን ሽርጉድና መሰስ ቀሰስ ያይ ይሆናል ።ከአራት በፊት ሰብ ቃው አማኙቹ ካናገርኩት ምናልባት እውነቱን ያስረዳኝ ይሆናል ። ከነዚያ መንታ ሌጆች አስቀያሚ ተሌዮች ውስጥ አንዱ መሆኑን አረ ጋግጣለሁ ።

የጀራልድ መምጫ ሰዓት ደርሰዋል ። ለብቻው እንድታገኘው ከፈለገች ደግሞ ዋናው ኤሙራ ጐጻና ከመጋቢው መንገድ የሚገናኝበት ቦታ ድረስ መሄድ ይኖርባታል ። ቀስ ብላ ኮሽ ስታደርግ የበረንዳውን ደረጃ ወርዳ ሄደች ። ማሚ በሯቱ መሰኩት እንዳታያት አልር አልፎ በትክሻዋ አሻገራ በጥንቃቄ ወደ ሁዋላ ታያለች ።ከማርገበገቡትና እንደ በረዶ ነጭ ከሆኑት የመሰኩት መጋረጃዎች ማህል አየልቶ የሚ ያይ ትልት ጥቁር ፊት እንደሌለ ካረጋገጠች በሁዋላ ልቧን ምልታና ባለ አረንጓዴ አበባ ቀሚሰዋን ወደ ላይ ሰብሰብ አድርጋ ይዛ ፣ እነ ዚያ ባለ ጌዮ ጥብጣብ ማሰሪያ ጎጠላ ጫማዎቿ ሊሸከሚትና ሊያስሮጧት በሚችሉት መጠን ቸልቸል ወደ ኤሙራ ጐጻናው በረረች ።

በኮረኮንቹ መንገድ ግራና ቀኝ የቆሙት የአረቢ — ሊባኖስ ዛፎች ከወደ ጭንቅላታቸው ቅርንጫፎቻቸውን ከማስተሳሰራቸው የተነሳ መን ገዱን በተራራ ማህል የተሬሰራሰና ደብዘዝ ያለ ረዥም ዋሻ አስመ ስለውታል ። በነዚህ ዛፎች እቅፍ ውስጥ ስትገባ ማንም ከወደቤቱ አቅጣጫ ሊያያት እንደማይችል ስላረጋገጠች ሩጫዋን ቀነስ ፡ትንፋ ሽዋን ለቀቅ አድርጋ በዝግታ መራመድ ጀመረች ። ልብሰችዋ ጥብቅ አድርገው የያዝዋት በመሆናቸው ትንፋሽዋ ቁርጥ ቁርጥ እስኪል ድረስ ማግ አፍኖዋት የመሮጥዋ ነገር የማይሆን ሆነ ። ቢሆንም በተቻ ላት ሁሉ ፈጠን ብላ መራመድዋን ቀጥላለች ። ስለዚህም ወዲያውኑ ኮረኮንቹን መንገድ ጨርሳ እዋናው መንገድ ገባች ። አሁንም ቢሆን በቤትዋና በአዕ ማህል ጥቅጥቅ ያሉ ዛፎች እስከሚከልሉዋት ድረስ መጠምዘጥውን ዞራ ተራመደች ።

በመጨረሻም ቁና ቁና እየተንፈሰችና ራትዋ ፍም እስኪመስል ድረስ ቀልቶ አንድ የሣር ገማጅ ጉቶ ላይ ተቀምጣ አባቷን መጠበ ቅዋን ቀጠለች ። ከወትሮው በጣም ዘግይቷል ። እርሷ ግን መዘግየቱን ወዳዋለች ። ዘግይቶ የሚመጣ ከሆነ ፡ትንፋሽዋን ዋጥ አድርጋና ረጋ ብላ ፡የልብዋን እንዳያውቅባትና እንዳይጠረጥርም የተመለቃቀለ ፊት ዋን በመጣ በመጣ አባብሳ ፡ ተዘጋጅታ ትጠብቀዋለች ። ካሁን አሁን የፈረሱን ኮቴ ለመስማት ጎትታ ትጠብቀዋለች ። በተለመደው ይህ

@OLDBOOKSPDF

ነው በማይባል ፍጥነቱ በኮረብታው በኩል ሲመጣ ለማየት በጉጉት ታስተውላለች ። ደቂቃዎች አለፉ ፤ ጂራልድ ግን አልመጣም ። ቁልቁል ወደ መንገዱ አትኩራ ታያለች ። ያ የልብዋ በሽታም ጸጥም አነረሸ ባት ።

"ሠላ በፍፁም እውነት ሊሆን አይችልም!" አለች በሃሳቧ ። "ሥነው ቸሎ መጥቶ ቢገላግለኝ?"

በጠዋቱ ዝናብ ምክንያት እስካአሁን ድም የመሰለውን ጠመዝ ማዛ መንገድ በሚያይ ተከትላለች ። ይህ መንገድ በኮረብታው ላይ ቁል ቁል ወርዶ ወደ ሥርፋፋው የፍሊንት መንዝ እንደሚዘ ኣት ፤ ከዚያም ጥልፍልፍ ባሉት ደረጃጃዎቹ በታዎች ሥር ሥር ሽክ ብ መደሚቀጥ ለው ኮረብታ ወጥ አሽሉይ ወደሚኖርበት "የአሥራ ሁለቱ ሥርኳዎች" መንደር እንደሚያደርስ ፤ በሥሥብዋ ሳለችው ። ለሷ የዚህ መንገድ አካሄድ መዴትም ወደ ኋላትም ባደሠን ወደ አሽሉይ ሰፈር ብቻ ነው ። አዎ ያ መንገድ የሚያደርስ የሚመስላት መደብያ ጊንጀግሪነ ቤታ መቅደስ ለኮረብታው ዘሙድና ጉልላት ሠዋ ወደ ቆመ ባለ ነጭ አምድ ሙሀ ቤት ነው ።

"ወይኔ አሸሉይ! ወይኔ አሸሉይ!" አለች በሃሳቧ ። ራቧ እንደ አንድ ነገር ፈሥኖ ይመታል ።

መንትያዎቹ የታርሴሥን ሊጅች ከጎኗሥት ሥምሥምታ ወሬ ወዴህ ቁልቁለ ሕለናሥን ሲጫናት የነበረው ጹብ እጸና አስጨናቂ ነገር ቀስ በቀስ ከሕሊናዥ ተንፋሥኮና ሁለት ዓመት ሙሉ ጨምሮዶ ይዟት ለነበረው ትኩሳት ቦታውን ለቀቀ ።

ኢያደገች ስትሄድ አሽሉይ ይሆን ያህል ግራኪ እንዴሉሆነ ይሰ ማት የነበረው ስሜት ሁሉ አሁን እንግዳ ነገር መስሎ ታያት ። በሰ ጅነትዥ መደሉዥ ሲመላለስ ነበር ። ሆኖም እስከዚህም ጉዳዩ ብላ አት መለከተውም ነበር ። ያኔ የሣፊ ሁለት ዓመት ወደ አውሮፓ የሚያደ ርገውን ታላቁን የሽርሽር ጉዞ ፈጽሞ ሲመለስ እበቷ ድረስ መጥቶ ከጠየቃት መዴህ ማን ታፊቅረዋለች ። በታ ። ታሪኩ ያሽው ብቻ ነው ።

እፊት ለፊት በረንዳ ላይ ቆማ ነበር ። አጅፊ ደግሞ ግፈጫ መሉ ልብሱን ለብሶ ባለጌጥ ሽሚዙንና እንከን የለሽ የሚያደርገውን ሰፊ ክራቫቱን ገዥ አደርጉ ፤ በረጅሙ ጐዳና ላይ ሽቅብ እየጋለበ ይመ ጣል ። የልብስ አለባበሱን ዝርዝር ሁኔታ ፤ ኖተወለመለ ቦት ጫማውን ማማር ፣ እከራባቱ ላይ በስርዓ የተያያዘውን የማሪኩን ኘንሥ ሚዴላ የራስ ምስል ፣ አሲን ሲያደ ያመለቀውን ሰፊውን የታናማ ባርኔጣ ሁሉ ንም አንድ በአንድ አሁን ድረስ ታስታውሳለች ። ከፊቷቸ ዴብ ብሎ

@OLDBOOKSPDF

ልጓሙን ከርቻው ላይ ጣል አድርጎ ቆሞ ያስተውላት ነበር ። ቀዘዘ ያለት ማሬጫ ዓይኖቹ ፈገግ ብለው በሰፈው ተከፍተዋል ። ብሩሁዋ ጸሐይ ሥማ ጸጉሩ ላይ ስትፈስ ከብር የተሠራ ባርሚጣ ያደረገ አስመ ስላዋለች ። ነዚያም፡—"አስካርሴት አደግሽ'ኮ!" አሳትና ደረጀውን ላይ ጨነት ወጥቶ እጅዋን ሳመ ። አቤት! ድምፁ! ልክ ለመጀመሪያ ጊዜ እን ያሰማችው ሁሉ ስትሰማው ልሂ እንዴት እንደጋለበ በጭራሽ አትረ ሳውም ። እንደሙዚቃ የሚፈስ ፡ ቃናውን እየጠበቀ የሚወርድ ፡ ዝማ ፡ ዘለግ ያለ ድምጽ ።

በዚያችው ትጽበት ልቢ ፈቀደው ። እንደው ያለመላ ዝም ብላ ፈለገችው ። ትመገበው ምግብ እንደምትፈልግ ሁሉ ፈለገችው ። ትጋ ለበው ፈረስ እንደምትፈልገው ሁሉ ፈለገችው ። ትተኛበት ለስላሳ አልጋ እንደምትፈልግ ሁሉ ፈለገችው ።

ለሁለት ዓመታት ያህል በየዶንሱ ግብግ ፡ በየአጣ ማርበያው ፡ በየሽርሽር ቦታው ፡ በየመገናኛ ሥፍራው ይዟት ይዞር ነበር ። እርግጥ የታሴትን መንትያ ወንድማማች ወይም ካድ ካልቨርት የሚያህ ሯትን ያህል አይደለም ። ጠጣም ወረድ ግን በሳምንት አንድ ጊዜ ታራ መጥቶ ሳይጠይቃት የቀረበት ጊዜ የለም ።

በፍቅር ተጨዋውተው ፡ በፍቅር ዓይን ተያይተው እንኳን አያ ውቁም ። አስካርሴት አጠገባቸው ስትቀመጥ ሌሎች ወንዶች ዓይን ውስጥ የምታየውና የምታውቀው ብሩህና ሞታት ብርሃንም ቢሆን እሱ ማሬጫ ዓይኖች ውስጥ የለም ። ያም በሆን ግን...ያም ሆኖ እን ደሚያፈቅራት ታውቃለች ። በዚህስ በምንም ዓይነት አትሳሳትም ። እሷን የማፍቀሩን ነገር ላንድ አፍታም አትጠረጥር ። ያፈቅረኛል የምትልበትን ሁነኛ ማስረጃ ወይም ምክንያት አትርቢ ብትባል ምንም የላትም ። ነገር ግን እንደሚያፈቅራት ከተጨባጩ ምክንያት ይልት ቀልቧ ይነግራታል ። ከልምድ ያገኘችው እውቀት እሱ እንደ ሚያፈቅራት አሳምሮ አሳምኗታል ። አብዛኛውን ጊዜ ዓይኖቹ ከበድ ሳይሉና ድካም ሳይጫናቸው ወይም ሩቅ አገር ሳይሰደዱ በጉጉትና በሐዘን ሲመለከታት ለሷ አስተያየቱ እንቆቅልሽ ሲሆንባት እሱን ደግሞ ታስገርመዋለች ። እንደሚያፈቅራትማ በደንብ ታውቃለች ። ታዲያ ለምንአልነገራትም ለምን እንደሆነ ሊገባት አልቻለም ። ዳሩ ስለሱ የማታውቀው ነገር ሙቼ ይሄ ብቻ ሆነና! ስለሱ የማታውቀው በጣም ብዙ ነገር አለች ።

ሁልጊዜ ሲመጣ ያጫውታታል ፡ ያዝናናታል ፡ ነገር ግን ነገረ ሥራው ሁሉ ከሰው የተገለለና ሩቅ ነው ። ምን እንደሚያስብ የሚያ ውቅ ግንም ሰው የለም ። አስካርሴትማ ወንዶቹ የሚያስቡትን በማወ

@OLDBOOKSPDF

ቅና በመገመት ረገድ የመጨረሻዋ ደካማ ናት ማንም ሰው ያሰበ ውን ነገር ነና እንዳሰበው በሚናገርበት በዚህ አካባቢ ያአቸሴ እንደዚሀ ቁጥብ መሆን በጣም የሚያናድድ ነገር ነው። በተለመዱት የመንደሩ ወንዶች ተግባራት ሚለትም አደን ሣጅን ፡ ቁማር መጫ ወት ፡ መጽንስና የፖለቲካ ውይይት አንፃር አሽሴ ያው እንደሌለው ወንድ ነው። በፈረሰ ግልቢያና ጉማሰ ደሞ የሚደርስበት ተወዳዳሪ የለውም። ታዲዩ በነዚህ የወንድ ልጅ ተግባራት አንፃር ዘሰሉቹ የሚለየው ፡ እሱ እነዚህን ነገሮች እንደ ሕይወቱ ሣጭና እንደኑሮው ዓላማ እልማየቱ ነው። ለመጽሐፍት ማንበብ ባዕው ፍቅር ፡ ለሙዚቃ ባለው ፍላጎትና ማጥም ለመጻፍ ባለው ልዩ ዝንባሌ ብቸኛ ነው። በዚህ ረገድ የራሱ ዓለም አለው።

እንዲህ ያማረ ሐር አጥር ሕያለው ከጨዋታና ከመጥጀጅ በቃ ምን ያርቀዋል ? ብቸኛ የሚያደርገው ምንድን ነውን እሰ በሕይወቷ ልትመሰቻው የማትችለውት ማን ተወዳጅ የሠነተን ነገሮች ስለአ ውሮፓ ፡ ስለመጽሐፍት ፡ ስለሙዚቃና ስለማጥም ታነቷት ልታ ብድ እስክትደርስ ድረስ የሚያወራላት ምን ይሁን ብሎ ነው ? ሁሉ ማታ ማታ እስክርሌት ከሱ ጋር ራት ሲራቱ በረንዳ ላይ ጨለ ምለም ባለው ብርሃን ሙስጥ ተቀምጣ ትጽጀና ተስፋብታው ወደ መኝታዋ ለትሄድ መንፈሷ ይረበሻል። ሰላም ታጣለች ፡ ደሏንዋ ላይ ሆና የማታነሳ የማትጨለው ሃሳብ የለም። በቢሀ ዓይነት ለጠዙ ሰዓታት ዘሃሳብ ስትሞሸት ፡ በትጨነት ትጽጀና ግሥለም ዩሚቀጥ ለው ስንጎኝ እንደሚያፈቅረኝ መናገሩ አይተርም በሚለው ማሪን ጊያ ሃሳቧ ተጠቅልላ ትተቸለች ። ያ ያሰበችው የሚተሳከው ጊዜ ይመጣል ፡ አሱም ይሄዳል። ሲሳም ይመጣል ፡ ተመልሶ ይሄዳል። ያ የሠራ አካላቷን የሚያሳሳት ትክሳት ከቸን ጠያ ቀን ማለቱ ከቱ ጨመረና መጠኑ እየበዛ ከመሄዱ በስተቀር አንዳችም ነገር ጠፋ አላለላትም።

ታፈቅረሞለች ። ትፈልገሞለች ። ነገር ግን ምኑም አይጣፍም። ማንኑቱን መረጸት አልቻለችም ። በታሪ አኖት ላይ እንደሚነፍሰው ንፋስና በሙሪያዋ እንደሚጠመጠመው ወንዝ በጣም ቁጥኑኛ ግልጽ ሆና ቀርባለች ። አሰ እንደሆነች ፡ ጭጭ ያልሆነና ውስብስብ ያለ ነገር በሞራሽ አይጣችም ። እሰከምጽእት ብታስበውም አያንለጽ ላትም ። ሁልጊዜ እንዴሁ ናት ። ደሽው አዞን ታዲዩ በሕይወት ለመጀመሪያ ጊዜ ሙሉ የማያጨበጭ ፡ የተወሳሰበ ተሪጭር ያለው ሰው ገጠማት ።

አሽሴይ ትርፍ ጊዜዎቹን በመሥራት ሳይሆን ቁሜ ቁለመ በማሰብ ከሚያሳልፉ ሰዎች ሐረግ ላይ ያለ ሰው ነው። ከሠራኋ

@OLDBOOKSPDF

ከሚታዩ ከሚዳሰሰው ዓለም ጋር ቅንጣት ታህል ግንኙነት የሌላቸውን ባለሕዛረ ተስፎ ሕልሞችን ሲያባዝት ይውላል። ሲያጠነጥን ያድራል። አራቱ ውስጥ ባለው በውበት ከጀርጂያ በሚበልጥ ዓለም ውስጥ ሲዞር ሲሽከረከር ቆይቶ ሲመለስ ፣ ወደ ሚጠላው ቦታ በመመለሱ ይከፋዋል። ሰዎችን ያያል ፣ መጀ አይወዳቸውም ወይም አይጠሏቸውም። ንደን ትኩር ብሎ ያስተውላዋል። ግን ሊያዘንቡትም ወይም አይደሰትባትም። ዓለምንና በዚም ውስጥ አሱ ያለውን ቦታ ተተብለ፣ በምንቸገረኝ ትከሻውን ከፍ ዝቅ ያረግና ወደ መዚቋውና ወደ መጽሐፉ ይመለሳል—መደተሻለው ዓለው።

አእምሮው ለያ አእምሮ አንግዳና ባዳ መሆኑን አየወቀ ለምን ምርኩዙው አንዳደረጋት አስከርሌት አታውትም። የሱ አስከዛሬ ምሥጢር መሆን ልክ ቁልፍም መወርወሪያ መክፈቻም እንደሌለው የተዘጋ በር የማወቅ ጉጉቷን አሳሰባት። ስለሱ ስመረዳት ያልቻለችው ነገር ሁሉ የበለጠ አንድታቀረው አደረጋት። ያ አንግዳ የሆነ ቁጥብ ጨዋታና መጣባቱ። በቅለበለው ቁጥር የራሷ ልታደርገው የመፈለግ ቁርጠኝነቷን አበረታቱት።

በጣም ወጣት መሆንዋና ትምጥል አሰተዳደጓ ሽንፈት የሚባል ነገር እንደሌለ አድርጋ እንድታምን ስለሚገፋፋት አንድ ቀን ማፍቀሩን ይገልጽልሻል የሚለውን እምነቷን ፈጽሞ አንዳትጠራጠር አድርንታል። አሁን ደግሞ ይህረምሽ ብሎ ይሄ አስፈሪ ወፌ እንደ ብራ መብረቅ ደንገት ጹብ አለ — ኤሽሌይ ሚላኒን ሊያገባ ?! በቅራሽ አውነት ሊሆን አይችልም !

ምንጩ ባለፈው ሳምንት አይደለ እንዴ ወደ አመሻሹ ላይ ከፈይርሂል አየጋለቡ መደቤት ሲመጡ—"አስከርሌት ፥ አንድ በጣም አስፈላጊ ነገር ልነግርሽ አፈልጋለሁ። ነገር ግን እንዴት እንደም ንግርሽ እንጃ" ብሏት ኖበረው።

በመሽከርመም መልክ ዓይኖቿን ወደመሬት ደፍታ ያ ተናፋቂው ቀን መጣ መሰለኝ ፥ ያ አስደሳች የምሥራቹ ቀን መጣ ! ብላ አሰበ ልቧ እንዳንድ ነገር ይመታ ጀመር። ከዚያም ቀጠል አድርገ- "ግን ይቅር አሁን ባልነግርሽ ይሻላል ! ወደ ቤት በጣም ትታር በሶል ብዙ ጊዜ እያኖረንም። መይዜ አስከርሌት እንዴት ያለሁት ፈሪ ነኝ ዘሞቱ ! "አለና ፈረሱን ኮልኩሎ ሽቅብ ወደ ታራ ይዟት ሸመጠጠ።

አስካርሌት እግንድ ጎማጅ ላይ ቁጭ ብላ ያላትን ነገሮች እንድ በአንድ ታሰላስል ጀመች። እንደዛ በሀሴት የሞላትን ንግግሩን እንደ

@OLDBOOKSPDF

ገና ማጨን ፡ እንደገና መመርመር ያዘች ። ወዲያው ድንገት ሃሳቧ ሁሉ አንድ አደገኛ ትርጓሜ ይዞ አፈጠጠባት ። ክፉና ደብቅ ትር ጉም ይዞ መጣባት ። ምናልባት የዚህን የፍጥምጥሙን ወሬ ፡ ከሚ ላኒ ጋር ቀለበት ሊያስር መሆኑን ሊነግራት አስቦ እንደሆነስ !!

ው፤ ምነው አባቷ ወደቤት በመጣባት ፤ ይሄን ያንጠለጠላትን ነገር ፡ ይሄን ቀልቧን ያቆሰላትን ነገር ከእንግዲህ ለአንዲት ደቂቃም ቢሆን ታግሳ ለመጠበቅ አትችልም ። ቁልቁል ፡ አሁንም አሁንም ቁል ቁል ወደ መንገዱ ትመለከታለች ። ሆኖም ምንም የሚያስደስታት ነገር አልተገኘም ።

አሁን እንግዲህ ጸሐይዋ ከአድማሷ ግርጌ እየወረደች ወደምሽት ቤቷ እየሄደች ነው ። ቀይ ፍም የተረጨበት የዓለም ዳርቻ ቀስ በቀስ ቢታውን እየለቀቀ ወደ ሐምራዊነት ተለወጠ ። ሰማያዊው ሰማይም ወደ አረንጓዴ ሰማያዊ ተቀየረ ። አካባቢው ላይ የተ ጫነው ምድራዊ ያልሆነ ዝምታ በገጠሩ የምሽት ብርሃን ታጅቦ እስክርሌትን እየዋጣት ነው ። ጥላ የዘሃበት ደብዛዛ ምሽት ቀስ በቀስ እየዳኸ የባላገሩን መንደር እትራ ሙስጥ ሲያስገባ መንቀሳቀስ ጀም ሯል ። ቀያዮቹ የአርሻ ትልምችና የተሸረሸረው ቀይ መንገድ ተለ ምራዊውን ደም ለበስ ቀለማቸውን ትተው ግልጥጥ ያለ ቡናማ መሬት ሆኑ ። መንገዱን አሸርጠ ሲከድ በሚታየው የግጠሽ ሜዳ ላይ ፈረሶች ፡ በትለሞችና ላሞች ተጠሳልፎ በተሠራው የሽቦ አጥር ላይ አንገታቸውን ብቅ ብቅ አድርገው በእርጋታ ቆመዋል ። ወደ የጋጣቸው ተንደተው እራታቸውን ለማግኘት ይጠባበቃሉ ። የግ ጠሹን መንገድ አጥረው በሰልፍ የቆሙትን ጉቶዎች ጥቁር ጥላ እንሰላቱ የወደዱት አይመስሉም ። የሰውን ልጅ ጓደኝነት እንደረ ለጉ ሁሉ ጀሮዋቸውን እያርገበገቡ ወደ እስክርሌት ያያሉ ። እንግዳ በሆነው የምሽቱ ፈዛዛ ብርሃን ውስጥ እኒያ ቀን በጸሐይ ሲታዩ ብሩህ አረንጓዴ የነበሩ ረዣዥም የኮክ ዛፎች አሁን ከጥቁር ሰማ ያዊው የሰማይ ግድግዳ ፊት ለፊት ጥቅጥቅ ያለ ግዙፍ ጫካ ሰርተው ዝግተኛውን ወንዝ እግራቸው ሥር ደብቀዋል ። ከወንዙ ባሻገር ከሚታየው ጋራ አናት የሚከሰት ቤት ረዣዥምና ነጫጭ የጭስ ማውጫዎች ይታያሉ ። ዙሪያቸውን ከበው የቆሙት የዋርክ ዛፎች የሠሩት ጥቅጥቅ ጨለማ ቤቱን ስለሚከልለው ቤት የመኖሩ ምልክት አልፎ አልፎ ጭል ጭል የሚለው የፋኖስ ብርሃን ብቻ ነው ። የጸደይ ወር እርጥብ ሽታና አዲስ የታረሰው መሬት ትኩስ መዓዛ እንዲሁም ከምድር ማጎጸን ወደ አየር የበቀለው ማንኛውም አረንጓዴ ሕይወት ለጋ ተፈጥሮ እስክርሌትን እሽሩሩ ይላታል ።

@OLDBOOKSPDF

የምትጠልቅ ጀንበር ውበት ፡ የጸደይ ወር ቁንጅናና የአዲሶቹ አረንጓዴ ዕጽዋት ልምላሜ ሰእስክርሌት ምንም ታምር አይፈጥሩ ባትም ። የተፈጥሮ ውበት ፡ ከምትጠጣው ውሃና ከምትተነፍሰው አየር የተለየ ስሜት አይሰጣትም ። እሷ ፡ ውበትን ከሴቶች መልክ ፡ ከፈረስ አቋም ፡ ከሐር ቀሚሶች ቀለምና ከመሳሰሉት ተጨባጭ ነገሮች ላይ በቀር ሌላ ቦታ አግኝቶለሁ ብላ ከልቧ አስባ አታውቅም ። ያም ሆኖ በእንክብካቤ በተያዘች የታሪ ጋሻ መሬቶች ላይ በለዛዙ የሚወርደው ከፈል ብርሃን የተረበሸ አእምሮዋን ያረጋጋላታል ። ይህን መሬት እነደምታፈቅረው ሳታውቅ እንኳ ታፈቅረዋለች ። በጸሎት ጊዜ ከፋጥስ ሥር የምታየውን የአናቷን ፊት እንደምታፈ ቅር ሁሉ ይህንንም መሬት ከልቧ ታፈቅረዋለች ።

በዝግታ እየተጭመዘመዘ በሚሄደው መንገድ ላይ ጂራልድ ዝርም አላለ ፡ ምልክቱም የለ ። አሰጉ ለመጠበቅ ብዙ ከቆየች ደግሞ አለጥርጥር ማሚ ሰፍለጋ ትመጣባታለች ። ከመጣችም እየገፈ ታተረች ወደ ቤት ታስገባታለች ። ደግነቱ አይኑዋን እያጨናቆረች እየጨለመ ወደሚሔደው መንገድ ትክ ብላ ስታይ ከወደፊጠቹ ጋራ ግርጌ ከከነም ከከነም የሚል የፈረስ ኮቴ ሩቅ ድምጽ ሰማች ። ፈረሶቹና ላሞቹም በፍርሃት ሲበታተኑ አየች ። እንግዲህ እንደተለ መደው ጂራልድ አሃራ በከፍተኛ ፍጥነት እየጋለበ በገጠሩ ቤቶች ውስጥ ውስጡን እያቆራረጠ ወደቤቱ መምጣቱ ነው ማለት ነው።

ወፍራሙን የባቱን ጠንቻ ወጥሮና ቀጥ አድርጎ ገትሮ ፡ እየ ጋለበ ከኮረብታው አናት ብቅ አለ ። በጣም አጭር ሰው በመሆኑ ከሩቅ ሲታይ ትልቅ ፈረስ ላይ የተቀመጠ ትንሽ ልጅ ይመስላል። ፈረሱን በአለንጋው እየገረፈ እየጮኸ መጭ ሲለው ያ ነጭ ሽበቱ ጸጉሩ ወደኋላው ይቆማል ።

አስካርሌት መንፈስዋ ሁሉ እንደፈረሱ ቢጋልብባትም ፡ ጂራ ልድ በጣም የሚያነቅ ፈረስ ጋላቢ በመሆኑ በኩራትና በፍትር ዓይን መመልከቷ አልቀረም ።

"እኔኮ ገና ትንሽ ሲጠጣ ለምን አጥር መዝለል እንደሚያ ሰኘው ይገርመኛል" ብላ አሰበች ። "ባለፈው ዓመት እዚሁ ቦታ ከፈረሱ ወድቆ ጉልበቱን ከተሰበረ ወዲህ ደህና ትምህርት አግኝ ቷል ብዬ ነበር ። ደሞ'ኮ ሁለተኛ አጥር ላይዘል ለእግማ ቃል ገብቶ ነበር ።"

አስካርሌት አባቷን እንደአባት ሳይሆን እንደአሀዶቿና እንደ የዕድሜ ጓደኛ አድርጋ ነው የምታየው ። ጂራልድ አጥር እየዘለለ

@OLDBOOKSPDF

ምስጢሩን ከሚስቱ በመደበቁ እንደልጅ ኩራት ይሰማዋል ። እፀም አንሳንያ ከማሚ እየተደበቀች የምትሠራው ተንኮል እንዲሁ ያስደስታታል ። ስለዚህ አባትና ልጅ እንደጓደኛ የመተያየት ፡ እንደ ባልንጀራ ምስጢር የመካፈል አንድነት ፈጥረዋል ። ከመቀመጫዋ ተነስታ ታስተዙለው ጀመር ። ያ ትልቅ ፈረስ ያለ የሌለ ጋዜጣን እጠራችም ያንን አጥፍ አመር ብሎ ሲዘል ያልምንም ችግር እንደ ምትዘር ሠፍ ይመስላል ። ኒራልድ አለንታውን አየር ሳየር እያወ ኘፈፈ ፍንድቅድት ብሎ በክፍተኛ ድምጽ እየጮኸ ሂድ ይለዋል ። የተጠቀለለ ነጭ ጨራ ወደኋላ ተበቦ ከንፋስ ጋር ይጫወታል ። እሰካርሴት በዛፎቹ መሀል መጥፋዋን ልብ ሳይል ልጓሙን ሳብ ረብብ አድርጎ የፈረሱን አንገት ሠታ ሠታ እያደረገ አበጀህ አለው ።

"በመንደሩ አንዳንት ያለ አንበሳ የለም ። እረ ባጉራም አይገኝ አለው ለፈረስ በኩራት ። ምንም ጊንኳ ሠላሳ ዘጠኝ ዓመት እሚ ሬክ ውስጥ የኖረ በንም የአየርላንዳዊነቱ የቋንቋ ኃና ድምፁ ውስጥ ያደላል ። ጽጉሩን ጥሎ ጥሎ በእጁ ሳግ ሳግ አደረገ ፡ የሸ ሚዙን ኮሌታና አንዱ ትከሻ ወደ ግራ ጆሮው የተመሳቀለ ክራፃ ነት አስተካከለ ። ያኔ በችኮላ ኮለባበሱን ማሰተካከሉ ልምን እንደሆነ እሰካርሴት ገብቷታል ። ሚስቱ ራት ሲጥም ንሥቢት ሊጠይቅ ሄዶ የሚመለስና በሥነ ሥርዓት ፈረሱን ሲንዳ የቆየ ፊዉ ባል ለመ ምሰል ነው ። ለፅም ቢሆን እሙነትኛ አላማዋን ሳታሳውቀው ጥያ ቄዋን ለመጀመር አመቺ ሁኔታ መፈጠሩ ታውቂታል ።

ከት ብላ ሳቀች ። ልክ እንዳሰበችውና እንደፈለጎችው ጀራ ልድ በድንገተኛው ድምጽ ግራ ተጋባ ። ወዲያው ግን እንደሆነች አወቀ ። እንደግፊርም አንደተከላካይነትም ያለ ስሜት አጠጣር ፊቱ ሳይ ታየ ። ጉልበቱ ድርትርት ስላለበት ከፈረሱ በችግር መረደና ልጓሙን ክንፉ ላይ ሳል አድርጎ ወደኋ መጣ ።

"እሺ እሚቱ" አለ ጉንጩን ቆንጠጥ አድርጎ ። "እኔኑ መሰ ለሱን ሥራዩ ብለሽ ይዘሽዋል ማለት ነው ። ደሞ እህትሽ ሱዌለን ባለፈው ሳምንት እንዳደረግችው ሂደሽ ለእናትሽ ልትነግሪ ነው?"

በዚያ ጉርሻና ድምጹ ውስጥ የንደሉት ኃና ይኑር እንጂ አንድ የማባበል ስሜትም አለበት ። እሰካርሴት ምላሷን በጥርሶቿ ማህል እንደያዘች የተመሳቀለውን ከፈባቱን በታ ቡታ ቅመልከለታችሁ ፈቱን ወደፊት በማም ባስጠነው ቁጥር የቦርቦን ውሰኪ ሽታ ከሚ ንታ መዓዛ ጋር ተደባልቆ አንድ ጊዜ አወጻት ። ከዚህ ሽታ ጋር የቅንባሠ ፡ በዘይት የታሸ ቆዳና የፈረሶች ጠረን አብሮ ሸታታል ። ይህን ጠረን አሰካርሴት ሁል ጊዜ ካባቷ ጋር ታዛም ደዋለች ። ከለዚ

@OLDBOOKSPDF

ሀም በጣም ስለተዋጣትና ቀልዷም ስለወደደው ሌሎች ወንዶች ላይ እንኳ ብታማኘው ሳይታወቃት ደስታ ይሰማታል ።

"ምነው አባባ እኔ እንደ ሰዊስን ቱሪናሩ መሰልከህ እንዴ?" አለችና ምስጢር ጠባቂነቷን አረጋግጣ አሰባበሱ መስተካከሉን ለማ የት ራቅ ብላ በኩራት ተመለከተችው ።

ጀራልድ ከአምስት ፊት ምንም ያህል የማይበልጥ ቁመት ያለው ሰው ነው ። ከወደሆዱ በርከት ፡ ከወደ አንገቱ ደንደን ከግለቱ የተ ነሳ ቁጭ ብሎ ሲታይ ለማያውቀው እንግዳ ሰው በጣም ግዙፍ ይመስላል ። ከወገቡ በላይ ያለውን አጭርና ነዶ ያለውን ሰውነቱን የተሸከመት ጠማርና ጡንቻማ እግሮቹ ፡ ውድ በሆነ ቆዳ በተሠራ ፀጉ ጫማ እድገጃው ድረስ ተሸፍነው ፡ አንደጉረኛ ልጅ አግር ይንፈራጠጣሉ ። ብዙ ትናንሽ ሰዎች ስለራሳቸው ከምር የሚያስ ቡት ነገር ብጣም አስንራሚና አስቂኝ ነው ። ጸሩ ግን ሁሉም ባገሩ ይከበራል ። ግራር በሌለበት እንዚራ አድባር ይሆናል ። በዶሮ አርባታ ሽቦም ውስጥ አውራ ዶሮ ንጉሥ ይባላል ። ጀራልድም እን ደዛው ነው ።

መቼም በሠፈሩ ሚንም ቢሆን ጀራልድን የማይረባ ከራራ ደውይ ሊለው አይደፍርም ። የስልሳ ዓመት ሽማግሌ ነው ። ገብስማ ጸጉሩ ልምጭጭ ብሎ የተጠቀለለ ነው ። መሰሪ ፊቱ ምንም የመጨ ማደድ መልክ አይታይበትም ።

ዓይኖቹ ፡ ከአእምሮው ጥቂቱን ክፍል እንኳ ለሚንቀት አንዳል ገበረና ጭንቅላቱንም በቁማር ጨዋታ ላይ ካርታ ለመሳብ በስተቀር ተጠቅሞበት እንደማያውቅ ሃሳብ የለሽ ወጣት ፡ ያለጭንቅ ይዝናናሉ ።

የነጠረ የአየርላንድ ተወላጅ መልክ አለው ። የሱን መሳይ አየር ላንዳዊ መልክ ጥሎት በመጣው ትውልድ አገሩ ውስጥ በየአቅጣ ጫው ይገኛል ። ክብ ፡ ደመ ሙሉ ፡ ግራጭ አፍንጫ ፡ ሰፊ አፍና ግርማ ያለው ነው ።

ጀራልድ ቁጠኛ ፡ በየትንሹ ነገር ግንፍል የሚል ይሁን እንጂ ልቡ ገር ነው ፡ ሩህሩህ ነው ። ድመት ሚያው ስትልም ሆነ ሕጻን ሲያለቅስ ይባባል ። አሽከር ምን ጥፋት ቢያጠፋ በቁጣ ሲቸግቀቅ ማየት አይወድም ። ይህን ሩህሩህነቱን ሰው ሲያውቅበት ግን በጣም ይናደዳል ። ይህን ያወቀበት ሰው ጠላቱ ነው ። እሱ ምንም ከልቡ ባይሆን እየሰኸና እያምባረቀ በቁጣ ትእዛዝ ሲሰጥ ፡ ሰው ደንግጦ ሲርበተበት የማየት ደስታ ይገብዘዋል ። እንደዚህ ሲጮህባቸው አሚን ብለው ሲተበሉ ፡ ሲሽቆጠቆጡ ይረካል ። ጸሩ አልገባውም እንጂ

@OLDBOOKSPDF

በቤተሰቡ ውስጥ እንደ ሚስቱ እንደ ኤለን ተደማጭነት ያለው አንድም ሰው የለም። በለስላሳ ድምጽዋ ተስቦ ብላ ስትናገር ሁሉም ይታዘዝላታል። ይህ በጥፊም አልገባውም። ይህንን እንዲያውቅ ደግሞ ከኤለን ጅምሮ እስከ መጨረሻው ዝቅተኛ ሰሌ ድረስ ያሉት ሰዎች የሚናገረውን ሁሉ እንደሀግ የተቀበሉ በማስመሰል ይሸነግሉታል።

እስካርሌት በዚህ ጸባዩና ጩኸቱ የምታደንቀው ከሌሎቹ ሰዎች ሁሉ ያነሰ ነው። ከልጆቹ ሁሉ ትልቋ ልጁ እሷ ናት። ሶስት ወንድ ልጆች ወልዶ ተብሮአል። ከእንግዲህ ሌሎች ልጆች እንደማይወልድ ስለታወቀውም እሷን ልክ እንደ ወንድ ልጁ ነው የሚያያት። ይህ ነገር ደግሞ እሷን በጣም ያስደስታታል። ከታናናሽ እህቶቿ ይልቅ ባባቷ የወጣች አስቂ ናት። ምክንያቱም ያቺ ስትወለድ ካሮሊን ኢሪን ትባል የነበረችውና እሱን ካሪን የምትባለው የመጨረሻ ታናሽ፣ ልስልስ ያለችና ባለብዙ ሕልም፣ ባለብዙ ምኞት፣ ስትሆን፣ የክርስትና ስሙዋ ሱዛን አሊናር የሚባለው ሱዌለንም ደግሞ ፤ በወብትዋና በጨዋ ሴት ጸባይዋ የምትኮራ በመሆኑዋ፣ አባታቸውን አይመስሉትም።

ከዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ እስካርሌትና አባትዋ ድብቅ የጋራ ስምምነት አላቸው። ለምሳሌ የማግሽ ማይል ርቀት ያለውን መንገድ በእግሩዋ ከመሄድ ይልቅ በእጀራጭ አጥር ስትዘል ቢያያት ወይም ከጥቅረኛዋ ጋር እደጃፉ ላይ ስትጫወት ብታመሽ በግሉ ይገስጻትና ይቆጣት እንደሆን ነው እንጂ ለኤለን ወይም ለማሚ አይነግርባትም። እስካርሌትም ብትሆን ለሚስቱ ከማለ ከተገዙት በውዋላ አጥር ሲዘል ብታገኘው፣ ወይም ሁልጊዜ ከመንደር ሃሚት እንደምትሰማው እሱ በካርታ ጨዋታ ላይ ያጠፋውን ገንዘብና የደረሰበትን ኪሳራ ልክ ብታውቅ፣ ሱዌለን እንደምታደርገው ዓይን አውጥታና ነገር አሳምር ብላ በገበታ ጊዜ አታወራበትም። እስካርሌትና አባቷ እንዲህ ያለው ነገር ኤለን ጅሮ ከደረሰ እጥዳት ላይ እንደሚጥላት እርስ በርሳቸው ተማምነው የውሸን ነገር ያነሳ ውሸ ይሁን ተባብለዋል። ኤለንን የሚጎዳ ማንኛውንም ነገር ለማድረግ የሚገፋፋቸው ደግሞ ምንም ነገር አይኖርም።

እስካርሌት አባቷን ድንግዝግዝ ብሎ እየጠፋ ባለው ብርሃን ውስጥ ተመለከተች። ለምን እንደሆነ ባታውቅም ከአባቷ ጎን መሆንዋ ምኞትን ሰጥቶዋታል። እንድ ሕያው፣ ተጨባጭና ሻከር ያለ በሱ ላይ የምታየውና የምትፈልገው ነገር አለ። ብቻ ነገርን አብዝ ልጥሎ በማየት አንባር ከሰው ሁሉ በታች በመሆንዋ ነው እንጂ፣ ይህን ፀባይ የወደደችው የጣ ራስዋን ፀባይ ስለሚመስል ነው።

@OLDBOOKSPDF

እናቷ ኤለንና ሞግዚትዋ ማሚ ይሆን ወንጸ ወንድ በባይሞን ለማ ስማል ያላደረጉት ነገር አልነበረም ። ምን ያደርጋል በሞራሽ አልፀ ነሉቸውም ።

"አሁን በደምብ አማረብህ" አለች ። "በኔ ግምት አራስህ ጮኽህ ዛላላወቅህ በስተቀር ማንም ዘያህን ሊያውቅብህ አይችልም ። በበ ኩሌ ግን አምና ጉልበትህን ከተሰበርክ በሁዋላ ያንኑ አጥር ልዝ ለል ማለት . . . "

"ሆሆይ! ደሞ ብዬ ብዬ የገዛ ሴት ልጄ ይህንን ዝለል ይሆንን እትዝለል ስትለኝ ዝም ብዬ ሳዳምጣ" አለ ጮክ ብሎ ፥ ለሁለተኛ ጊዜ ጉንጯን ቆንጠጥ አድርጎ ፥ "እንግቱ የራሴ ነው ። ብሰበረው ባልሰብረው ምን ቁርጥ አረጋችሁ ። እረ ደሞ የሆነሰ ሆነና ያን ገት ልብስሽን ሳትለብሽ እዩጅ ምን ትሰሪያለሽ?"

ደስ ከማይለው ውይይት ለመላላገል ሲል በተሰመያዉ ዘያው ወሬ መለወጡ መሆኑ ስለገባት ከንዴን በከንጂ አጥፍ አደረገቸና፦

"አንተን ስለብቅ ንበር ። ይሄን ያህል ታመሻለህ ብዬ አልገ መትኩም ። ዲልሲን መጣት አለመጣትህን ስጣወቅ በጣም ጎት ቻለሁ ። "

"መጣትስ ገዝቻታለሁ ፥ ዋጋዋ ግን ድራሽን ነው ያጠፋው— እሷንና ልጅዋን ፕሪሲንም ጭምር ነው የገዛችው ። ጆን ዊክሰጣ እንደውም በነፃ ካልወሰዱኳቸው ብሎኝ ነበር ። እኔ ጂራልድ ኦሃራ ግን ንግድ ሌላ ወዳጅነት ሌላ ብዬ አሻፈረኝ አልኩት ። ንክች አላ ያርገውም አልኩ ። ለሁለቱ ሶስት ሺህ ሰጠሁት ። "

"እረ የሰማያቱ ያለህ አባባ ሶስት ሺህ አኮ ብዙ ነው፤ ደሞም ፒሪሲን መጣት አልነበረብህም!!"

"ወየው ጉድ! የገዛ ልጆቻችን ዳኝነት እንስጣችሁ የማለቡት ዘመን ደረሰና ብለን ብለን!" ብሎ ጮሽ ጂራልድ በግልፍተኝ ነት "ፕሪሲ ጥሩ ትንሽ ልጅ ናት ። ስለዚህ . . . "

"አውቃታለሁኝ ሞላጫና የማትረባ ፍጥረት ናት ።" አስካርሌት ቀስስ ብላ በጠባይ ገባችው ። በጨዋቱ እምብዛም አልተጨነቀ ችም ። "ደሞ እሷን የገዛህበት ዋናው ምክንያት ዲልሲ እፅንም ግዛ ስላለችህ ነው ። "

ጂራልድ አንድ የለጋስነት ሥራ በፈቃዱ በሰራ ቁጥር ፥ ሲታ ወቅበት እንደሚሆነው ሁሉ ግራ ተጋባ ። አስካርሌትም ይህንኑ እፊቱ ላይ ስላየችበት ክት ክት ብላ ሳቀች ።

@OLDBOOKSPDF

"ታዲያ ብገዛ ምርጫ፣ ሁለቱ ከጠልጅዋ የምታስብና የምታስላስል ከሆነ ዲልሲን ገዙት ማምጣቱ ምን ጥቅም ይኖረዋል? ብቻ ለማንኛውም ከእንግዲህ ወዲያ ማንም ባሪያ በዚህ መንደር ሚስት እንዲያገባ አልፈቅድም። በጣም ውድ እኮ ነው። በይ ነይ እንግዲህ የኔ ልጅ ገብተን እራት እንብላ"።

አሁን ጥላው ሁሉ ከብድ እያለ ሄዷል። የመጨረሻዋ የብር ሃን ነጠብጣብ ከሰማይ በመስናቢቷ፣ አካባቢው ሁሉ አረንጓዴ መልኩን ተገፈፈ። የፀደይን መቀትም ለዘዝ ያለ ቅዝቃዜ ቦታውን ተክቶታል። አስካርሴት እንዴት አድርጋ ጂራልድ ሳያውቅና ሳይ ጠረጥር ስለ አሽሌይ እንደምታነሳበት ቸግሯት ተጣቶራለች። ይሄ ደማም በጣም ችግር ነው። ምክንያቱም መሰሪነት የሚባል ነገር በቂራሽ በአስካርሴት ደም ውስጥ አልተፈጠረም። ጂራልድ ደሞ ልክ እሷ የልቡን እንደምታውቅበት ሁሉ እሱም ደክማ የማታለያ ሽፋኖችዋን በተሳሉ ይገልጥባታል። የልቧን ገልጦ ያይባታል። አልፎም በዘዴ ያውጣጣታል።

"የአቦራ ሀሉቱ ዋርካዎች" ሰምች እንዴት ናቸወ?"

"እንደተለመደው ናቸው። ካድ ዝልቨርትም እዚያው ነበር። ስለዲልሲ ተንጋግሬ እንደጨረስኩ ሁላችንም እሮቱ ሠዓት ሳይ ተቀምጠን መጠጥ ቀርቦ እንጫወት ነበር። ካድ ግና ከአትላንታ መምጣቱ ስለነበር የሚያወሩት ሁሉ ስለመርከት መሆኑ ብስጭት አድርጎት..."

አስካርሴት ዙና ዙና ተነፈሰች። ምክንያቱም ጂራልድ አንዴ ስለመርከትና ስለመጓጓዘል ማውራት ከጀመረ ማቆምያ አይኖረውም። ደሞ ወደ ሌላ ልትጠመዝዘው ሞከረች።

"ስለ ነገው ድግስ ምንም አላወሩ?"

"እምን ያወሩ ይመስለኛል። ያቺ ወይዘሪት ማናት...ማነው ስሟ...ያቺ ቆንጅዬ ትንሽ ልጅ፣ ያቺ እንኳ አምና እዚህ መጥታ የነበረች የአሽሌይ የአክስት ልጅ። ታውቂያለሽ።...እምን —አዎን አሁን መጣልኝ ወይዘሪት ሜሳኒ ሐሚልተን ነው ስሟ—እሷና የሷ ወንድም ቻርለስ ከአትላንታ ቀደም ብለው መጥተዋል። እና.."

"አሃ መጥታለቻ?"

"መጥታለች።እንዴት ያለች ጥሩ ልጅ እኮ ናት። አቤት ፀባይ-ፀባይ ማለት የሷ ነው። ስለራሷ እንዲት ቃል እንኳ ከአፍዋ አትወጣም።

@OLDBOOKSPDF

በይ የኔ ልጅ ፤ነይ አሁን መደሁሞላ አትበይ ፥ እናትሽ ይሄኔ በአግር በፈረስ ትፈልገናለች ።"

እስካርሌት ገና ወሬውን ስትሰማ ወሽመጥዋ ተበጠሰ ። እሷማ ከቅስፉ ተጸራሪ የሆነ ተስፋ ይዛ ፥ ሚላኒ ሐሚልተን እዚያው አመሮ ይቃ ቤቱ አትላንታ ውስጥ ትተራለች ብላ ፤ትመኝ ነበር። የዚህ ሳያ ንስ ደግሞ ፀባየ ሸጋና አንገትዋን የደፋች ጨዋ ልጅ መሆን ዋን የዛ አባትዋ ሲነግራት የመጣ ይምጣ ብላ የልቧን ለመናገር ተነሳሳች ።

"አሽሌይስ እዛ ነበር?"

"ነበረ" ጇራልድ የልጁን ክንድ ከክንዱ ላይ ገፍትሮና ወደሷ ዞሮ ትክ ብሎ ዐይን በይኗን ያያት ጀመር ። "አስከአሁን አምሽተሽ ስትጠብቂኝ የነበረው ለዚህ ከሆነ ፥ ዙሪያ ጥምጥም ሳትሂጅና ዳርዳር ሳትይ ብትጠይቂኝ ይሻል አልነበረም?"

እስካርሌት ምን እንደምትል ጠፋት ።ስትበሳጭ ፊትዋ መቅላቱ ተሰማት ።

"በይ ተናገሪያ ።"

አሁንም ምንም አልተናገረች ። ምነው አባቷንም እንደሌላው ስው በጅዋ ነቅንቃ አፍሀን ዝጋ ማለት በቻለች እንዴት ጥሩ ነበር ።

"አሽሌይማ እዚያው ነበር ። እንዲያውም አሁኑ እንደ ጠየቁኝ ሁሉ እሱም ስለአንቺ ደህንነት በትህትና ጠይቆኝ ነበር ። ደሞ በምንምዓ ይነት ነገ ከግብግቡ ቦታ መቅረት እንደሌለብሽ ነገሩኝ ።እኔም ምንም እንደማያስቀርሽ አረጋገጥኩላቸው።" አለ በመሰሪነት ።"ለመሆኑ የኔ ልጅ ይሄ ባንቺና በአሽሌይ መሀል ያለው ነገር ምንድነው ?"

"ምንም የለም" አለች ባጭሩ ክንዱን በሃይል እየገሠተች ። "እሺ እንግባ አባባ"

"አ ፥ አሁን ደግሞ አንቺ ሠንሽ እንግባ ባይዋ" አለ ነገሩ ጉብ ቅት። "ሆኖም ዛሬ እዚሁ ቆሜ አድራለሁ እንጂ ይሄን ነገር በደንብ ሳልረዳ እቤቱ አልገባም ። አሁን ሳስበው ስሞኑን ሁኔታሽ የተለዋወጠው ለካ ለዚህ ነው ።ካንቺ ጋር ጉዳይ ጀምሮ ነበር እንዴ ?ላግባሽ ብሎ ጠይቆሽ ነበር እንዴ ?"

"አይ" አለች ባጭሩ ።

"እሪ እሱም አያረገው" አለ ጇራልድ ። በንዴት ዛጣን አለች። ጇራልድ ግን በጁ ገፍትሮ ዝም አሰኛት ።

@OLDBOOKSPDF

"ሰብስብ በይ እሜቴ ዛሬ ከሰዓት ነው ከራሱ ከጅን ዊክስ አፍ እርግጠኛውን የሰማሁት ፡ አሽሌይ ወይዘሪት ሜላኒን ሊያገባ ነው ። ነገ ለሕዝብ ይገለጸል"

የእስካርሌት እጅ ከክንዱ ላይ ዘፍ ብሎ ወደቀ ። የተባለው ሁሉ እውነት ነው ማለት ነው!

አንዴት ሕመም ልክ እንደመርዘኛ እውሬ ጥርስ እልብዋ ላይ ተተከለ ። ከዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ ፡ አንድም በሀዘን የሚመልከትዋት አንድም የገዛ ልጇ ለገባችበት ችግር መፍትሄ በማጣቱ በብስጭት የሚያስተውሏት ፡ የዓይኖቹ ሁኔታ በጣም ተሰማት ። እስካርሌትን ያፈ ቅራታል ። ነገር ግን የዕን ከልጅነት የመጣ ችግር ወደ እሱ በማሸጋገሯ ቅር ተሰኝቷል ። ኤለን ብትሆን የዚህን ሁሉ መልስ ታውቅ ነበር። እስካርሌት ችግሩዋን ወደፊ መውሰድ ነበረባት ።

"እራስሽን በአደባባይ ስታጋልጪ ፡ ነበናሽን ገልጠሽ የኛንም ገበና ስታሳዪ ነበር ማለት ነዋ ነ?" አለና አምባረቀባት ፡ እንደተለመደው በስሜት ግንፍል ብሎ "ማንንም የመንደሩን መጣት መማረክ እየቻልሽ ፡ የማይወድሽን ሰው አፍቅረሽ ስትከተይ ነበር ማለት ነው ?"

ንደቅና የተዋረደ ክብሩዋ ስሜት ሕመሙዋን በከፊል ፈወሰላት ።

"እኔ በጭራሽ አልተከተልኩትም ። ብቻ እንደው ነገሩ ግርም ብሎኛል ።" "አንቺ ቀጣፊ ! ደሞ ትዋሽኛለሽ ?" አለና ጇራልድ ፡ በቅሬታ የተንዳ ፊትዋን ትኩር ብሎ አይቶ ርህራሄ በተሞላ አንደበት እንዲህ አላት፡— "በጣም አዘናለሁ የኔ ልጅ ፡ ብቻ ለማንኛውም አንቺ ገና ልጅ ነሽ ። ደሞ እኮ ብዙ ሌሎች ወዳጆች አሉልሽ "።

"እማማ አንተን ስታገባ አሥራ አምስት አመታ ነበር ።እኔ ግን አሥራ ስድስት ዓመቴ ነው ።" አለች እስካርሌት ፡ በጣም በተዳከመ ድምፅ ።

"የእናትሽማ ለየት ይላል" አለ ጇራልድ "እሷ እንዳንቺ ሰል ጣላ አልነበረችም ። ብቻ አሁን ነይ ወዲህ ልጇ ፡እይሆሽ ዘና በይ። ቅር አትሰኚ ። በሚመጣው ሳምንት ወደ ቻርልስተን ይዣሽ እሄድና አክስትሽን አውላሊን ትጠይቂያለሽ ። እዚያ ስለፎርት ስምተር አንዳንድ ነገር ሲያወሩ ስትሰሚ የአሽሌይን ነገር ባንድ ግምንት ውስጥ ጨርሰሽ ትረሺዋለሽ ።"

"ወይኔ! ሕፃን ናት ብሎ ነው ማለት ነው የሚዛምተው" አለች በልቧ ፡ ለዘንና ንደት ህቅ እንቅ አያስኛት ። "አንዲት አሻንጉ

@OLDBOOKSPDF

ሊት ቢገሃልኝ ቁስሌ የሚሸር መስሎታል እኮ ።" "እሁንእንግዲህ አጭሽን ባትነቀንቂብኝ ጥሩ ነው"ጂራልድ አስጠነቀቃት ።"ልብ ቢኖርሽ ኖሮ ወዶ እሰቱዋርት ታርሌተንን ወይም ብሬንት ታርሌተንን ባባባሽ ነበር ። አስቢበት እስቲ የኔ ልጅ ። ከመንትዮቹ አንደኛውን አግቢ ።የኛና የነሱ አርሻም በጋራ እንዲለማ እናደርጋለን ።እኔና ኗም ታርሌተን አንድ ጥሩ ቤት እንሰራልሻለን ።ይኸውም ሁለቱ አርሻዎች የሚገናኙበት ቦታ ላይ ነው ።እና.."

"እኔን እንዶ ሕፃን ልጅ ማየትህን አቁም በቃ!" ብላ ጮኸች አስካርሌት ። "ወደ ቻርልስተን መሄድም ሆነ ፣ቤት እንዲኖረኝወይም መንትዮቹን ለማግባት በሙራሽ ፍላጐት የለኝም ።እኔ የምፈልገው.." ብላ ነጣጣርዋን አቆመች ።ግን በጊዜው አደለም ።

የጂራልድ ድምፅ ያለ ወትሮው ዝግ አለ ።በጣም ቀስፅ ብሎ ከመናገሩ የተነሳ እያንዳንዱን ቃል ለልፎ ለልፎ ብቻ ከሚጠቀም በት የሚሰብ መጋዘን የሚያወጣ ይመስላል ።

"እንቺ የምትፈልጊው አሽሊይን ብቻ ነው ።እሱን ደግሞ በሙራሽ አታገኘውም ። አሱ ሳግባሽ ቢል እንኳ እኔ ከጆን ሚክስ ጋር ሳለኝ ወዳጅነት ሰል ብቻ ቅር እያለኝ እሺ እል ይሆናል ።" ግራ የተጋባ መልኩዋን በማየትም "እኔ ልጂ ደስ እንዲሳት እፈልጋለሁ ፣ እንቺ ግን ከሱ ጋር ደስተኛ አትሆኚም ።"

"የለም! እኔ በጣም ደስተኛ እሠናለሁ!"

"እሱስ በሙራሽ ደስተኛ አትሆኚም የኔ ልጅ ። ደስታ የሚገኘው የሚመሳሰሉ ሰዎች ሲጋቡ ብቻ ነው ። "

አስካርሌት አንድ ጩኸ-ጩኸ የሚል ሽረኛ ስሜት ተሰማት። "ምነው ይኸው አንተ ደስ ብሎህ ትኖር የለምን አንተና እማማ አትመሳሰሉም ። "ብላ ፤ በመሀል ለዚህ ድፍረቱ በቦክስ ጆሮግንዱን ቢለኝስ በሚል ሲጋት አቁረጠች ።

"የኛ ሰዎችና የዊክስ ዘሮች አንድ አይደሉም" አለ በቀስታ፤ የሚናገራቸውን ቃላት እየፈለገ "የዊክሶች ጠላይ ከማናቸውም ጐረ ቤታችን አይነጥምም ። እንዲያውም እንደነሱ ያለ ቤተሰብ በሕይ ወቱ አይቼ አላውቅም ። በጣም ልዩ ሰዎች ናቸው ። ስለዚህም የነሣ አከለቶቻቸውን ልጆች በማሳበት ፣ ይህንኑ ከሰው የማይጥም ልዩ ባህሪ ለራሳቸው ይዘው መኖር ይሻሉ ።"

"ለምን አባባ አሽሌይ እኮ እንደነሱ . . . "

"ስብስብ በይ እሜቴ! እኔ አሱን ተቃውሜ ምንም የተናገ

@OLDBOOKSPDF

ርኩት ነገር የለም ። ምክንያቱም በበኩሴ አሰን ስለማልጠላው ነው። ጠላያቸው ከሰው አይገጥምም ስል ደግሞ እብዶች ናቸው ማለቴ አይደለም ።

"ኤሱ እንደ ካልቨርቶች ባለ በሴለው ገንዘብ ፈረስ አገኝ ብሎ ቁማር የሚጫወት ወይም እንደ ታርሴተኖቹ ሰክሮ በየቆሻሻው ላይ የሚወድቅ ፤ ኤልያም እንደ ፎንቴኖች ደርሶ ሚንፍል ብሎ እንደ ዋዛ ሰው የሚገድል ሰው አይደለም ። እንዲህ ዓይነቱ ለየት ያለ በባይ እንኳ በቀላሉ ሊታወቅ ይችላል ። ግን ይኸው እግዚሀር ምስክሬ ነው ፤ ጀራልድ እሃራም ራሱ እንዲህ ዓይነቶቹ ፀባዮች አሉት ! አንቺ ሚስቱ ብትሆኝ አሽሌይ ሌላ ሴት ፍለጋ ይሄዳል ወይም ይደበድብሽ ነበር ማለቴም አይደለም ። እርግጥ እንዲህ ሲያደርግ ብታይው ላንቺ ደስታሽ ነበር ። ምክንያቱም ነፃ ይሳሳል ። የሱ ግን ነገረ ሥራው ሁሉ ልዩ ነው ። በጭራሽ እመሉ ሊገባሽ አይችልም ።

"እኔ እወደዋለሁ ፤ ነገር ግን የሚናገረውን ነገር ጭራና ቀን ዱን ለመያዝ አልችልም ። በይ አሁን የኔ ልጅ አንድ ነገር ንገሪኝ ፤ እንደው ውነቱን ንገሪኝ እስቲ—ይሄ እሱ ሌት ተቀን ተደፍቶ የሚውልበትና ስለመጽሐፍ ፣ ስለግጥም ፣ ስለሙዚቃና ስለዘይት ቅብ ስዕል የሚያነበንበው ሁሉ ይገባሻል ?"

"ወይኔ አባብዬ!" ብላ ትእግስቷን ጨርሳ ጮኸች እስካር ሌት "እኔ ባገባው ይሄን ሁሉ አስተወው ነበር እኮ !"

"አሆሆሆ ! እሱማ ትኾያለሽ ። አንቺ ፣ ምን ይሳንሻል !" አለ ጀራልድ ፤ እንደቀልድ እየተፈታተናትና ትክ ብሎ እያስተዋላት ። "እንግዲያው ልንገርሽ ፣ አንቺ—እንኳን ስለአሽሌይ ይቅርና ስለማ ንኛውም ወንድ ቅንጣት ነገር አታውቂም ። ማንም ሴት ባሏን ቅንጣት ያህል እንኳ አመሉን አስትታ ልትለወጥ አትችልም ። ይህንን ልብ ብለሽ አስታውሺ ፤ ይጠቅምሻል ። እናም ዊከሶችን ስለ መለወጥሽ ነገር . . . እሪ በፈጠረሽ የኔ ልጅ! ቤተሰባቸው በሙሉ እንደዛው ነው ። ሁልጊዜም እንዲሁ ነበሩ ። ምናልባትም ወደፊት በዚሁ ይቀጥሉ ይሆናል ። እውነቱን ነው የምነግርሽ በጣም ልዩ ሆነው የተፈጠሩ ሰዎች ናቸው ። ወደኒውዮርክ ፣ ወደ ቦስተን ሄደው የዘይት ቅብ ስዕልና የኦፔራ ቲያትር እንደሚያዩ አትመለከቺም እንዴ ። ለያንኪዎች ገንዘብ እየከፈለ በጀርመንኛና በፈረንሳይኛ የተዛፉ መጻሕፍት ሲያስመጣ እንኳን አታዩም እንዴ! ታዲያ እዚያ ቁጭ ብለው እግዚሀር በሚያውቀው ምን እንደሚያልሙ እንኳን እንጂ ፤ ብቻ ቁጭ ብለው ሲያነቡ ይውላሉ ። ይልቅስ ይሄን ጉተው እንደማንም ጨዋ ሰው እደን ቢሄዱና ክርታ ቢጫወቱ ሳይሻላቸው ቀርቶ ነው ።"

@OLDBOOKSPDF

"እንዴ ፣ በሙንጅራ እንደአሽሌይ ፈረስ ግልቢያ እሚችል ማን አለና ነው?" አሰች እስክርሌት አሽሌይ ሲታሪት ተብሎ ሊሰደብ ንድድ ብሉዋት ። "ማንም እንደሱ የሚችል የለ—ምናልባት አባቱ ቢደርስበት ነው ። ከርታ ጨዋታሳ ቢሆን ምነው ባሰረዉ ሳምንት አይደል እንዴ ጀንስቦሮ ውስጥ ሁለት ሙቶ ነበር የቡንደሀ—እራ ስህን ! ።"

"እነዚያ የካልቨርት ልጆች ሹክ ብለውሻል ማለት ነው" አሰ ጄራልድ ፣ ንግሩን ለወጥ አድርገው ። "ሕንጂ የገንዘቡን ልክ ልታውቂ አትችይም ነበር ። አሽሌይ ክምርጥ ጋላቢ ጋር መጋለብ ፣ ከምርጥ ቁማርተኛ ጋር ካርታ መጫወት በደምብ ይችላል ። ከእንደኔ ያለው ምርጥ ሰው ጋር ማስት ነው፤ ዘባ ላይ ልጠማ ካለ ደማም የታርሌተን ልጆች ጥምብዝ ብለው ጠረጴዛ ሥር እስክሚወድቁ ድረስ ምንም ሳጅሰነር ለመሉዋት አንደሚችልም አልክድም ። የማያ ደርገው ፣ የማይሥራው ነገር የለም ። ነገር ግን ይሄን ሁሉ ነገር የሚያሄርገው ከልቡ አደለም ። ስለዚህ ነው ነገሩ ሁሉ ከሰው ጋር አይጣጥምም ያልኩሽ ።"

እስክርሌት ሙሉ አሰች ን ጉዘሚ ተሰበረ ። ለዚህ ለመጨረሻው ሃሳብ ምንም መክላከያ ኡታሉትም ልልምሰችም ። ምክንያቱም ጄራ ልድ የተናገረው እትመህን ስለሆነ ነው ። አሽሌይ ፣ ግሩም አድርጎ የሚ ሠራው ሥራ መቂጥ ሁሉ ሊቦን አያሄርም ። ሰው ሁሉ ያስደስተ ኛል ፣ ያረካኛል የሚለው ሰው በሞቱ አይሰጠውም ።

ጄራልድ ዝምታዋን በደንብ ስላጠኑው ክንዲን በኋኗ መታ መታ አደረገና "አሁንስ አስክርሌት ፣ እውነቱ ታየሽ አይደል ? ! ታዲያ እንደአሽሌይ ያለው ባል ምን ባል ይሆንሻል ! ዊከሶች ሲባሉ የተምታታባቸው ፣ ግራ የገባቸው ሰዎች ናቸው" ። ከዚያ ደሞ በመ ለማመሞ መልክ "ከጥቂት ጊዜ በፊት ስለ ታርሌተኞች ስናገር እነሱን ገሸሽ ለማድረግ የሞከርኩ እንጸይመስልሽ ፣ የኔ ልጅ ። እነሱም ግሩም ልጆች ናቸው ። ግን አይንሽን የጣልሽበት ካድ ካልቨርትም ከሆን ጥሩ ነው ፣ እኔ እስማማለሁ ። ምንም እንኳ ሽማ ግሌው አባታቸው ያዊነ ያንክ ቢያገባ ፣ ካልቨርቶች ጥሩ ሰዎች ናቸው ። እኔ ስሞትም እንኳ . . . የኔ እመቤት አጸምጪነ ታራን ላንቺና ለካድ ትቼ ነው የማልፈውና . . . "

"እኔ ካደን በጨውም አልተምስው" ብላ ፊሸኝት እስክር ሌት በንደት ። "ንሱን ወዴኔ መግፋትህን ተወት ብታደርግና በጣም ደስ ይለኛል ። ታራንም ሆነ ማንኛውንም ያረጀ ሰፊ እርሻ አልፈ ልግም ። ሰፊ እርሻ ምን ይረባል የፈለከው . . . "

@OLDBOOKSPDF

ልትል የፈለገችው "የፈለከውን ሰው ካላገኘህ" ነበር። ጂራልድ ከኤለን ቀጥሎ በዓለም ላይ እጅግ የሚያፈቅረውን ነገር ለሰጠታ ሲያቅርብላት አይቸኝም ስትል ሲሰማ ደሙ ፈላና ገነፈለ።

"ወየው ጉድ !ደሞ እንቺ ሆንሽ—እንቺ እስካርሌት አማራ፤ ውድ መሬቴን ታራን—ምን ትረባለች የምትይኝ ?"

እስካርሌት በችኮነት እራስዋን በእምንታ ነቀነቀች። ልብዋ እጅግ ምርር ከማለቱ የተነሳ አባቷ ይናደዳል እይናደድም ብላ እንኳ ሳታ ስብ እንደው አፍዋ እንዳመጣላት ነው የምትናገረው።

"በዓለም ላይ ከማንኛውም ነገር ጋር እኩል ሊሆን የሚችል ነገር መሬት ብቻ ነው።" አለ ጮክ ብሎ፤ አጫጭርና ወፋፍራም ክንዶቹን በንዴት እያወራጨ። "ምክንያቱም በዚህ ዓለም ላይ የሚያልት የሚያረጅ የሚያፈጅ አሱ ብቻ በመሆኑ ነው። ይህን በጭራሽ እንዳትረሺ የኔ ልጅ። ሊለፉለት፤ ሊሰሩለት፤ ሊሞጉለት፤ ሊሞቱለት የሚገባ አሱ ብቻ ነው።"

"ውይ ምነው አባባ" አለች በመከፋት "ልክ እንደአየርላንዳዊ ሰው ነው የምታወራው!"

"ታዲያስ አማፍርበት ይመስልሻል እንዴ መቼ አፍሬበት አውቅና ነውኒ የለም፤ እንደውም እጅግ አኮራበታለሁ። ደሞም እሜቴ! አንቺም ማማሽ ቤትሽ አየርላንዳዊ እንደሆነ አትርሺ ! ለማንም የአየርላንዳዊነት ጠብታ ደም ላለው ሰው መሬት እናቱ ናት። በዚህስ ባንቺ ነው የማፍረው በአሮጌው ዓለም ካለው ከሚገ መንደር በስ ተቀር እጅግ ውብ የሆነውን ቦታ ነው የሰጠሁሽ፤ በይ ምን ትሆኜ እንግዲህ ! አንቺ አነፍናፊ !" ።

ጂራልድ በእስካርሌት ላይ ያየው የሀዘን ስሜት እስኪገታው ድረስ ጮክ እያለ መናገሩን ቀጥሎ ነበር።

"ማን ገና ልጅ ነሽ ። የመሬት ፍቅር ገና ወደፊት ይይዝ ሻል። አየርላንዳዊ ከሆንሽ ይሄ ነገር በጭራሽ አይቀርልሽም። ገና ልጅ ነሽና አሳብሽን ሁሉ ወዳጅ መረጣ ላይ ጥለሽዋል። እያደግሽ ስትሄጂ ሁሉንም እያደር ትረጂዋለሽ... በይ አሁን ሀሳብሽን አንዱ ላይ አሳርፊና ወይ ካደን ወይ መንትዮቹን አልያም ከኢባን ሙንሮ ልጆች አንዱን ምረጭ። ከዚያ በሁዋላ ምን ዓይነት ውለታ እንደ ዋልክልሽ ትገነዘቢያለሽ!"

"ውይ ምነው አባባ !" ጂራልድ ውይይቱ እየሰለቸው ሄደ ። ችግሩ አሁንም ከሱ ጫንቃ የወረደ ባለመሆኑም በጣም ተበሳጨ

@OLDBOOKSPDF

ታራና የመንደሩ ልጆች ከተሰጠዋት በሁዋላ እስካርሌት መከፋትን ሲያይም በጣም አዘነ ። እሱማ በጣም ውድ የሚላቸውን ከሀታምች ሲያቀርብላት አጨብጭባና እልል ብላ ፡ ሰማ የምትቀ በለው ነበር የመሰለው ።

"እንግዲህ እሜቴ ስምዖንን አትዘርጊብኝ ። እንዳንቺ የሚያ ስብ ፡ ጨዋና የደበብ ሰው እንዲሁም ኩሩ የሆነ ባል ካገኘሽ ግንን አባባሽ ማን ይሄን ያህል ሊያሰበብም ። የሴት ልጅ ጥቅር የሚመ ጣው ካጣች በሁዋላ ነው ።"

"ውይ ምነው አባባ ፡ ይሄ ነበ የዴርና ጊዜው ያለፈበት አስተሳሰብ ነው ፤ ።" "የዴሮው ይሁን እንጂ ጥሩ አባባል ነው ። ብዙ አሜሪካውያን እንደአሸከረ ፡ እንደያንኒ ያፈተጉትን ለማግባት ያሯሯጣሉ ! ጥሩ ትዳር የሚሆነው ግን ለሴቶች ጠላቻቸው ሲመ ርጠላቸው ነው ። ምክንያቱም እንዳንቺ ያለች ገልቱ ልጅ ጨዋውን ከዴርየው ሰመሰየት አትችልምና ነው ። አሁን ሚክስችን ተመልከ ቻቸው ። ለዚህ ሁሉ ትውልድ ሰድሚ እንዴከበሩና እንዲኮሩ ፡ ጥንካ ሬንም እንዲያገኙ ያደረጋቸው ምን ይመስልሻል ? የሚመስሱዋቸ ውንና በተሰበቻቸው እንዲያገቡ የመረጠላቸውን ፡ የአከሱዮቻቸ ውን ልጆች ስለሚያገቡ ነው ። "

"ወይኔ" አለች እስካርሌት በጨኸት ፡ የጂራልድ ቃላት ያን የማይቀር እውነት ዳግም ሲያረጋግጡላት ። ጂራልድ ያቀረቀረ እራ ስዋን ትክ ብሎ እያየ ባንድ እግሩ የማዱን መሬት ይቆረቁራል ።

"ማልቀስሽ እንዳይሆን ብዮ" አለና በእጁ አገጭዋን ቀና አድ ርን ፊትዋን ለማየት እየሞከረ ጠየቃት ። የገዛ ፊቱም ምስቅልቅል ብሏል ።

"አይደለም" አለችና በምሬት ጮሣ ተናገረች ፡ እራስዋን ወደ ኋላ ምንጭቅ አድርጋ ።

"እሱ እንኳን ውሽትሽን ነው ። ሆኖም በመዋሸትሽ እኮራብሻ ለሁ ። ኩራት ስላለሽ ታስደስችኛለሽ የኔ ልጅ ። ነገም እግብግው ላይ ኩራት እንዲሰማሽ እፈልጋለሁ ። ከጉዳይ ለማይጽፍሽ ወንድ ብለሽ ልብሽን ሰቅለሽ እንደነበር አንስተው የመንደሩ ሰዎች ሲሳለቁብሽ ማየት በፍፁም አልሻም ።"

"እንዴ ከጉዳይ ጽፎኝ ፡ ወዶኝ ነበር እንጂ" አለች እስካርሌት ባሳቧ ፡ ዘዘን ልቧን እያቆሰላት ። "እንዴ አሳምሮ ነው እንጂ የመ ደኝ! ይህን በደንብ አውቃለሁ ። አፍ አውጥቼ መናገር እችላለሁ ።

@OLDBOOKSPDF

እንደውም ትንሽ ጊዜ አግኝቼማ ቢሆን ፡ ወይኔ ዊክሶች የአክስቶቻቸውን ልጆች ብቻ ነው ማግባት ያለባቸው ባይባል ኖሮ አስፕው ነበር ።"

ጄራልድ ከንዲን ያዝ አድርጎ ከክንዱ ጋር አጣላለፈው ።

"በይ አሁን ወደራት እንግባ ። ደሞ የተጎጋርነው ሁሉ በህልታችን መሀል ይቅር ። በዚህ ነገር እናትሽን አላስጨንቃትም ፡ አንቺም አደራሽን ። በይ አፍንጫሽን ተናፈጪ ፡ ጭሽ የኔ ልጅ።"

እስክርሌት አፍንጫዋን በተቀደደ መሀረብዋ አፀዳችና ከንድ አክንድ ተያይዘው ፈረሱ ከኋላ ፀቅጣት እየተከተሉአቸው በሞሰማው ውስጥ ሽቅብ መንገድ ጀመሩ ። እቢቱ አለነብ ሲደርሱ ፡ በያረሻው ደብዛዛ ብርሃን ውስጥ እናቷን ኤየችና አሃደገና ስማውራት ቃጥ ቱዋት ነበር ። እናቷ የወጉር ሽፋንዋን ፡ የእንገት ልብስዋንና የእጅ ዙራብዋን አድርጋለች ። ከሁዋላዋ ማሚ ቆማለች ። የማማ ፊት መብረቅ ያዘለ ጥቁር ደመና መስልዋል ። በእጅዋ ኤሰን አሃራ ባሪያ ዎቹን ስታከም የምትይዘውን የመድኃኒትና የሩሻ መያዣ ጥቁር በርሳ ይዛለች ። የማሚ ከንፈር በጣም ትልቅ ነው ። እንደ ሙዳ ሥጋ ተንጠልጥሏል ። ስትናደድማ የታችኛውን ሰምበጭዋን ከመደበኛ ርዝመቱ ሁለት እጅ አበረዝማ መዘርጋት ትችላለች ። አሁንም በረጅሙ ዘርግተዋለች ። ያለፈቃድዋ በተሠራ ሥራ ምክንያት የተና ደደች መሆንዋን እስክርሌት አውቃለች ።

"ጄራልድ" አለች ኤሰን ፡ ሁለቱ ተያይዘው ሲመጡ ስታይ ። ኤሰን ካገባች ኣሥራ ሰባት ዓመት ቢሆናትና የስድስት ልጆች እናት ብትሆንም በጣም ወጣ አጥባቂና ጥንቁቅ ናት ። "ጄራልድ ፡ አስላትሪዎች ቤት ሸሽታ ገብቶዋል ። የኤሚ ልጅም ጎና እንደተመለደ ስለሞተ መጠመቅ ያስፈልገዋል ። እዚያ ከማሚ ጋር ሂጂ የምረዳው ነገር እንዳለ እረዳለሁ ።"

ድምጽዋ ጄራልድን ፈቃድ የመጠየቅ ዓይነት ቃና አለው ። እርግጥ ጥያቄው እንዲያው ለወጉ የቀረበ ይሁን እንጂ ጄራልድን በጣም ያረካዋል ።

"ኧረ የፈጣሪ ያለህ" ብሎ ጮኸና "እንዚያ የማይረቡ ነጮች ደሞ ለምንድነው በእራት ሰዓት የሚጠሩሽ ያውም እትላንታ ውስጥ ስለጦርነት የሚወራውን ልነግርሽ ባሰብኩበት ሰዓት! ሂጂ ወይዘሮ ኤላን ። መቼም ችግር መኖሩን ሰምተሽ እርዳታ ከላይሪ ግሽ እንቅልፍም አይወስድሽ !!"

@OLDBOOKSPDF

"አምን ፡ እሜቴ የሚረዱትን ኔግሮም ሆነ የማይረባ ነጭ ማታ ማታ ሳይረዱ ያደሩ እንደሆነ በጭራሽ እንቅልፍ አይኖራቸውም። ለምን፧ ራሳቸው መታከም እየቻሉ እኮ ነው የሚያስቸግሩዋቸው።" አለች ማሚ በማልጎምጎም ፡ እድጅ ወደ ቆመው ጋሪ ሰመሄድ ደረ ሽውን እየወረደች።

"ወደ ገበታው ሄደሽ እኔ መቀመጫ ላይ ተቀመጪ ፡ የኔ እመ ቤት" አለች ኤለን ፡ በለሰለሰ እጅዋ የእስካርሌትን ጉንጭ ትም ትም አድርጋ።

እስካርሌት ምንም እንኳ እንባዋን አምታ የያዘች ቢሆንም ምን ጊዜም የማይቀዘቅዘው የእናትዋ ተአምራዊ ሰላምታና ከሚንሿሿው ሐር ቀሚስዋ የሚመጣው የለመጂ ሽታ የመሰለ መዓዛ ሕዋሷን ነዘራት። እስካርሌት የኤለን አሃራ ነገር አይሆንላትም። እንድ ልብ ዋን የሚሰርቃት ስሜት ይሰማታል። ከሷ ጋር መኖር ልዩ ተአምር ነው። ልዩ ደስ ደስ ፡ ልዩ እንክብካቤ ነው።

ጂራልድ ባለቤቱን ደግፎ ጋሪው ላይ አወጣና ነጂውን ተጠ ንቅቆ እንዲነዳ ነገረው። ጋሪ ነጂው ቶቢ ፡ የጂራልድን ሬረሶች ለሃያ ዓመት ተንከባክቦ የያዘ ሰው በመሆኑ የጣዛ ሥራውን እንዴት እንደ ሚሠራ በመነገሩ ሰምበጪን ጣለ። ማሚን ከጐኑ አስቀምጦ አብ ረው ሲሄዱ ላያቸው ያከረፉ አፍረካውያንን ስዕል ቁልጭ አድርጎ ማየት ይቻላል።

"ስንዚህ የማይረቡ አስላተራዎች እኔ ባልረዳቸውና እየከፈሉ ቢታከሙ ኖሮ" አለ ጂራልድ ፡ "እነዚያን የረግራጋ ቦታ ጋሻ መሬ ቶች በቀላል ዋጋ ይሸጡልኝና አክባቢውን ጥለው ይሄዱ ነበር እኮ። መንደሬውም ደህና ይግላገል ነበር።" ከዚያ እንደተለመደው መቀለድ አሰኝውና "ነይ የኔ ልጅ ፡ እንግባና ዴልሲን ከመግዛት ራንታ እንተን ለጆን ዊክስ ሸጨህ መጣሁ ብዬ ለፖርክ ልንገረው" አለ።

የፈረሱን ልጓም አጠገቡ ለቆመ ትንሽ ኔግሮ ሰጠና ደረጃውን ዠመዛገት ጀመረ። የእስካርሌት የልብ ቁስል ዱሮ ረስቶ እሱ አሁን የሚታየው በአሽከሩ መቀለዱ ብቻ ነው። እስካርሌትም ከሱ ሁዋላ ሁዋላ እየተከተለች ፡ እግሯን የግድ እያነሳች ደረጃውን ትወ ጣለች። ወዲያውም የእሷና የአሽሌይ መጋባት ከጂራልድና ከኤለን ሮቢላንድ አሃራ ጋብቻ የባሰ ልዩ ነገር እንደማይሆን አሰበች። ልክ እንደሁልጊዜው ግልፍተኛውና ሃሳብ የለሹ አባቷ እንደ እናቷ ያለችውን ወርቅ ሴት እንዴት ሊያገባ እንደቻለ ግርም አላት። ምክ ንያቱም እንደሷ እናትና አባት በትውልድ ፡ በአስተዳደግና በአስተሳ ሰብ ብለለት እጅግ የሚለያዩ ባልና ሚስት በጭራሽ ስለማይገኙ ነው።

@OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ ፭

ኤለን አሃራ ሠላሳ ሁለት ዓመቷ ነው። በጊዜዋ በነበረው የዕድሜ ድልድል የመሀከለኛ ዕድሜ ወይዘሮ የምትባል ሴት ናት። ስድስት ልጆች ወልዳ ሦስቱ ሞተውባታል። አሞሩን ድንክዬ ባሏን በደንብ አድርጋ በቁመት የምትበልጥ ረጅም ሴት ብትሆንም ያንን ፣ ዳሌዋን ኮራ አድርጎ የሚያሳይ ቡፌ ቀሚሷን አድርጋ ረጋ ባለ ግርማ ሞገስ ስትንቀሳቀስ አካሄዷ ቁመቷን ያስረሳል። በነፊል በጥ ቁር ስስ ቀሚስ ከተሸፈነው ሳንቃ ደረቷ ፣ እንደመቃ እየተመዘዘ የወጣው ብርሌ እንገቷ ፣ ጥቁር ብርሃን በፈሰሰበት ሠማ ፀጉሯ ከብ ዱት ምክንያት ጥቂት ወደ ኋላ ጋለል ያለ ይመስላል። ደማቅ ጥቁር አይኖችዋና ለነሱ ከፈጣ የሆነው ቅንድቧ ከፈረንሳዊ እናቷ የተወረሱ ሲሆኑ በ1791 የፈረንሳይ አብዮት ወደ ሐይቲ የተሰደዱት አያቶቿ ከመሠረት ያበቀሉት መልክ ነው። ስንዴዎ አፍንጫዋንና ከወደ ጉንጭዋ ለስለስ እያለ የሚሔደውን ማዕዘናማ ግንጭላን የናፖሊዮን ወታደር ከነበረው አባቷ ወርሳለች። አብሪት የሌለበትን የፊቷን ኩራት ፣ የደስ ይሏንና ቅልድ አልባ ገጽታዋን ግን የወረሰ ችው ከኑሮና ከሕይወት መሆን አለበት።

ዓይኖችዋ የሚያበሩ ቢሆን ኖሮ ፣ ፊትዋ የፈገግታ ሙቀት ቢኖ ረው ኖሮ ወይም ደሞ አቢተሰቧና አሽከሮቿ ጀሮ ውስጥ በዝግታ የሚደርሰው የድምጽዋ ቅኝት ቶሎ ቶሎ የሚወጣ ቢሆን ኖሮ ሰው ባያት ቅጽበት ዓይን የምትገባ ቆንጆ ሴት በሆነች ነበር። ስትናገር የድምጽዋ ቃና ለስለስ ያለ ፣ የዳር አገር ጅርጂያውያን ዓይ ነት ነው። አናባቢዎቹን ፊደላት እንደውሀ ታፈሳቸዋለች። ተናባቢ ዎቹን ሆሄያት ደግሞ እንደልብ የመነበቡን እድል እየረገጠች ትለ ማሳቸዋለች። የፈረንሳይኛ ቃና ግን በጭራሽ አይሰማባትም። ይሄ ድምጿ አሽከር ላይ በቁጣ ሲጮህ ተሰምቶ አይታወቅም። ልጅን ሲገስጽም ሆነ ሲያስፈራራም ተሰምቶ አይታወቅም። ያም ሆኖ ግን በጨቨትና በቡራ ከረዩ የተሞላው የባሏ ድምጽ እንደ ዋዛ ሰሚ ሲያጣ ፣ ይህ የሷ ድምጽ ድፍን ታራ የሚታዘዘው ፣ ድፍን ታራ እሺ እመቤቴ የሚለው ነው።

እስካርሌት ስለእናቷ ባላት አስተያየት አንጻር ከሆነ ኤለን ከዱሮ እስከአሁን ምንም የተለወጠችው ነገር የለም። በማወደስም

@OLDBOOKSPDF

ሆነ በመውቀስ አንጀር ድምጿ ሰሰላሳና ጣፋጭ ነው። አልፎ አልፎ ጀራልድ ከሚፈጥረው የቤት ወጪ ውጣ ውረድ በስተቀር እመ ኗም ቢሆን ቀናና የማያሥረበሽ ነው። መንፈሷ የረጋ ፡ ለችግርና ለክፉ ጊዜም የማትናወጽና የማታሳነበድ ሴት ናት። ይህም በሶስቱ ወን ዶች ልጅነቷ ሞት ጊዜም የተረጋገጠ ነው። እስካርሌት ፡ እናቷ የተለመጠችበት መንበር መደገፊያ ወገቧን ሲነካ አይታ አታውቅም። ከናቷውም ወይ በምጣብ ጊዜ ፡ ወይ የታመመችን በምታስታምም በት ወቅት አለያም የእርሻውን ቦታ ሂሳብ በምትሠራበት ሰዓት ካልሆነ በስተቀር ቢያንስ የሰፈት ሥራ በእጅዋ ይዛ ካልሆነ ቁጭ ማለት አያሠንላትም። የሥራ ሰው ናት። ሥራው ብዙ ማጊያጊያዋ የሚፈልግና ሰፊ ካልሆነ በስተቀር የሰው ዕርዳታ አትሻም። በሌላ ጊዜ ከሆነ ግን የጀራልድን የተቀደደ ሸሚዝ ፡ የሴቶቹን ልጆች ቀሚስ ወይም የባሪያዎቹ ልብሶች ከመስፋት አትቦዝንም። እስ ካርሌት ፡ የእናቷን እጅ ፡ ለስፌት ከምትጠቀምበት የጣት መከላ ከያና ከመርቅ የተሠራ የመርፌ መያዣ ፡ ተለያይቶ አይታው አታ ውቅም። የሀዲጊዜ ሥራዋ ብዙስላሽ ክር መልቀም አለያም የስ ፌት ዕቃ ማስተመጫ የሆነውን ትንሽ የእንጨት ሳጥን ተሸክማ ከክፍል ክፍል ኤለንን መከተል የሆነው ትንሽ ኔግሮ ልጅ ፡ በሌ ለችበት ሰዓት ከሆነም ፡ ኤለን የምጣብ ቤቱን የምጣብ አሠራር ፡ ጽዳቱን ፡ አለበለዚያም ለጅምላ ሽያጭ የሚዘጋጀውን የእርሻ ቦታ የሥራ ልብስ አመራረት ስመቆጣጠር ስትጣደፍ ታያታለች።

እናቷ ስትበሳጭ በጭራሽ አይታት አታውቅም። ቀንም ይሁን ማታ በራሷም ሆነ በሰው ምክንያት ከረጋው ፀባዩዋ የሚያርቃት ምንም ነገር አይተኛም። ኤለን ወደ ግብጣ ለመሄድ ወይም እንግዳ ለመቀበል አለያም ችሎት ለመዋል ወደ ጅንሰቦሮ ልትጓጓስ ልብ ሷን ስትለብስ የሚስማማትን ለመምረጥ ሁለት ሰዓት ይፈጅባ ታል ፡ ያውም የሁለት ሠራተኞችና የማሚ ዕርዳታ ተጨምሮበት። ለድንገተኛ ነገር ድረሽ ተብላ ስትጠራ ግን ልብስ ስትለብስ ያሳት ፍጥነት ተዓምር የሚሰኝ ነው።

እስካርሌት የመኝታ ክፍሏ የእናቷን እልፍኝ አቋርጦ ስለሆነ ሷት ገና ጮህ ሲቀድ የሚመጡትን በጥቁሩ የእንጨት ወለል ላይ በፍጥነት የሚራመዱ ጥቋቁር ባዶ እግሮችንና የእናቷን በር የመንኳኳት ድምጽ እንዲሁም ወይ ስለህመም ወይ ስለመሞሊድ ወይ ስለመሞት በሹክሹክታ የሚያወሩ የተደናገጡ ኔግሮዎች ድምጽ ከልጅነቷ ጀምሮ ስትሰማ ኖራለች። ልጅ ሳለች ወደ እናቷ መኝታ ቤት በር እየዳኸች ተሯደና በተዳዳ ወደውስጥ ትመለከት ነበር። ኤለን የመድሀኒት ሳጥኗን በብብቷ ሥር ይዛ ፡ ፀጉሯን በወገ ልጋ ፡

@OLDBOOKSPDF

የደረት ቁልፎቿ እንደተከፈቱ ፤ ጂራልድ ከሚያንኮራፋበት ጨለማ ክፍል ወጥታ ቀና ተደርጎ ወደተያዘው ብሩህ የሻማ ብርሃን ስት ሄድ ታያታለች ።

እስካርሌት እናቷ ከእልፍኝ ወዶታች ለመሄድ በእግር ጣቷ ያለኮሽታ እየተራመደች ስትወርድ ፍርጥም ብላ ነገር ግን በሐዘን ስሜት ስታንሾካሽክ መስማት በአንቀልባ እንደመታዘል ያህል ምቾት ይሰጣት የነበረ የማትረሳው ነገር ነው ። "እሽሽሽ እንደዚህ ጮክ ብላችሁ አይደለም ፤ ጂራልድን እንዳትቀሰቅሱት ። እስከዚህ ድረስ የሚገል በሽታ እንኳን አልያዛቸውም ።"

አም ፤ ተመልሰው እየጸሁ ወደአልጋ ሄዱ ፤ በጀርባ ተንጋሎ ፤ ኤለን ራት ብላ መሄዷን ሚወቅና ሁሉ ነገር በትክክል መያዙን እርግ ጠኛ መሆን ፤ በጣም ማሩም ነገር ነበር ።

በየጠዋቱ ያ ሁሉ የማታው ማዋለድና የሚሞት ሰው ማየት ከለፈ በኋላ ሽማግሌው ዶ/ር ፎንቴንና ልጅየው ዶ/ር ፎንቴን ተፈ ልገው የጠፉ እንደሆነ የሚረዳት ስታጣ ጥቁር ዓይኖችዋ በጭ ንቀት ክብድ እንዳሉ እንደተለመደው ወደ ቁርስ ገበታው ትመጣና ትቀመጣለች ። ይሄ ሁሉ ሲሆን ግን ድምጿም ሆነ ሁኔታዋ በው ስጡዋ ያረገዘችውን ጭንቀትና ምጥ አያጋልጥባትም ። አካባቢዋን ተቆጣጥራ በአእምሮዋ ይዛ በረታ እንትስቃሴዋ ውስጥ እንደበረት የጠነከረ ልቧ ለመላው ቤተሰብ ባለውለታ ነው ። ለጂራልድና ለሴ ቶቹ ልጆች ጭምር ። ጂራልድ ግን ይህን ከሚያምን ቢሞት ይሻለ ዋል ።

አንዳንድ ጊዜ እስካርሌት ረገጢም እናቷን ደህና እደሪ ብላ ተሰ ናብታ ለመተኛት ጉንጮችዋን ልትስም በእግር ጣቶቿ ስትንጠራራ የኤለንን አፍ ስታስተውል የሳይኛው ክንፈሯ ስስና በጣም ጠባብ፡ ዓለም በቀላሉ የሚገዳው ዓይነት ሆኖ ታገኘውና ለመሆኑ ለመሳቅ ወደ ላይ ቀልበስ ብሎ ወይም በረጅም የማታ ወሬ ለሴት ጓደ ኞችዋ ምስጢር ብጤ ትንሾካሾክ በት ይሆን ብላ ተገረመች ። የለም ይሄ በጭራሽ ሊሆን አይችልም ፤ እማማ ሁልጊዜም አንድ ዓይነት ሴት ናት—የጥንካሬ ምሰሶ ፡ የጥበብ ምንጭና ለማኛውም ጥያቄ መልስ ለመስጠት ዕውቀቱን የታደለች ።

እስካርሌት ግን ተሳስታለች ። ምክንያቱም የሳቫናዋ ኤለን ሮቢ ላንድ በዛ ቆንጆ የዳር አገር ከተማ ውስጥ እንደማንኛውም የአሰራ አምስት ዓመት ኮረዳ ስታለች ፡ ተጫውታለች ። ለረዥም የማታ ሰዓ ታትም ከጓደኞቿ ጋር የልብ ምስጢሯን አውግታለች ። ከአንድ ምስ

@OLDBOOKSPDF

ጠር በስተቀር። ያ ዓመት በሃያ ስምንት ዓመት ዕድሜ የሚበልጣት ጀራልድ አሃራ ሕይወቷ ውስጥ ዘው ብሎ የገባበት ዓመት ነበር። ያ ዓመት ወጣትነትና ባለጥቁር አይኑ ያከሰቷ ልጅ ፊሊፕ ሮቢ ላንድ ከሕይወቷ ውስጥ የወጡበትም ዓመት ነበር። ምክንያቱም ፊሊፕ በዚያ በእንግዳ አመሉና በሚዋጉ ዓይኖቹ ገላምጦ ሳቫ ናን ሳንዴም ሰሀሰም ሲሰናበት በኤለን ልብ ውስጥ አየጋለ ይፍም የነበረውን አንዳች መሳት ከራሱ ጋር ይዞባት በመሄዱና እሷን ላገባት ዶጋን እማር የአየርላንድ ተወላጅ የልሷን ቀፎ ብቻ ትቶ ላት በመኩበለሉ ነው።

ያም ሆኖ ግን በጭራሽ በሚይታመን ዕድሉ እሷን ማግኘ ቱን እንደሰማይ መና ሰሚቆጥረው ጀራልድ በጣም በቂው ነበረች። ስለዚህም ምንም ይተደላት ምን እሱ የሚያጣው ነገር አልነበረም። በጣም ጮሌ ሰው በመሆኑ እንደሱ ያለ በዘርም ሆነ በሀብት እዚህ ግባ ተብሎ ስሙ የማይጠራ አየርላንዳዊ በዚያ አገር አለ የሚባለ ውን ሀብታምና ኩሩ ቤተሰብ ልጅ በድል አድራጊነት እጁ ማግ ባቱ እንደልዩ ተአምር መሆኑን አሳምሮ አውቋል። ጀራልድ ራሱን ሰው ያረገ፡ ራሱን የፈጠረ ሰው እኮ ነው።

ጀራልድ ከአየርላንድ ወደ አሜሪካ የመጣው በሀያ አንድ ዓመቱ ነው። እንደማናቸውም ከናቱም ይሁን ሳይከፋው ሊያገኝ ወይ ሊያጣ እንደሚመጣ አየርላንዳዊ እየተጣደፈ የለበሰውን ልብስ ብቻ ይዞ፡ ከመሣፈሪያው በላይ ሀብት ሽልንግ ብቻ ቋጥሮ፡ ከሚያጠ ፋው ጥሩት የበለጠ ዋስትና ብሎ ባመነው ጭንቅላቱ ላይ ዋጋ ውን ለጥፎ ነው ጀራልድ መደዚህ የመጣው። ከዚህኛው ክፍለ ገሀነም ለእንግሊዝ መንግሥትም ሆነ፤ ለራሱ ለሠይጣን እንኳ ሊሸጥ የሚችል የፕሮቴስታንት ሃይማኖት ዶጋፊ የሆነ አንድም አሬንጅ ግን የለም። ሆኖም ግንም የእንግሊዝ ባላባት ምስለኔ የሆነ ሰው ይባረር አይባረር ይመት ወይስ አይመት የሚለውን አወዛጋቢ መግት መንግሥት የሚወስንበት ከሆነ ጀራልድ አሃራ ጭራውን ሽጉብ አጉን ለቆ በመጣበት አግሩ መመለስ ሊኖርበት ነው። እርግጥ ጀራልድ እንዲህ ያለውን አሬንጅማን እንዲህ ያለውን የፕሮቴስ ታንት ሃይማኖት ዶጋፊ "ተልካሻ" እያለ አፍ አውጥቶ ይሳደባል። በመሳደቡ ደግሞ ማንም ምስለኔ "ቦይን ወተር" የተባለውን ጦር ነት ትዝታውን እያላበነ መልስ ሊሰጠኝ አይገባም ባይ ነው።

"የቦይን ጦርነት" ከመቶ ዓመት በፊት የተካሄደ ጦርነት ነው። በዚህ ጦርነት ስቱዋርት የተባለ ልዑል ኮብልሏል። የአሃራ ዘሮችና ጐረቤቶቻቸው ተስፋቸውን፡ ሕልማቸውን፡ መሬታቸውንና ሀብታ

@OLDBOOKSPDF

ቸውን ልዑሉ ሲኮበልል የተነሳው የአፄ ጳውሎ ጭካኔ ይጠባቸው የጀመው ነና ችላንት ይመስላቸዋል። የአራጋጁ ዊሊያም የተባለው መሪ በል ሁሉ እግር ተተካ። ዊሊያምና የተጠሉ ሠራዊቱቹ ከነበርቱካናማ ጥምጥማቸው የልዑል ስዙዋርት ደጋፊ ናቸው የነበሉትን አየርላን ዲዊዎች በሙሉ እያሳደዱ ቆራርጠው ሊጥሉ ተነሱ።

በዚህና በሌላም ምክንያት የጂራልድ ቤተሰብ የክፉ ውጤት ሊያስከትል የሚችል ትልት ጠብ ባይመስላቸውም መጨረሻው ግን በጣም ሙጥሮ ሆነ። ለዘመናት እነዚህ የኦሃራ ቤተሰቦች ከእንግሊዝ መንግሥት ጋር ሳይጣሙ ቆዩ። መንግሥትን የሚያረር ተግባር ይፈጽማሉ ተብለው ይጠረጠራሉ። ስለሆነም በዚህ ሰበብ በጉህ ቅጻጅና በጠዋት ማህል አየርላንድን ን ለቅቆ እግሬ አውጭኝ ማለት ተጀመረ። ጂራልድ የመጀመሪያው የኦሃራ ዘር አልነበረም። እምብ ዛም የማያስታውሳቸው ሁለቱ ታላላቅ ወንድሞቹ ጀምስና እንድ ሬው እንግዳ በሆነ የማታ ሰዓት ሲመጡ ሰንብተው ለብዙ ሳምንታት ሲጠፉ እናታቸውን ከፍተኛ የጭንቀት ማጥ ይዟት ነበር። በሰባቢ የኦሃራ ደሳሳ ቤት ውስጥ የጠመንጃ ክምችት ተቀብሮ ከተገኘ በኋላ ነው ወደ አሜሪካ የሄዱት። አሁን በጣም የቅናቸው የሳቫና ኑጋጄዎች ሆነዋል። እናታቸው በየጊዜው "ብቻ የት እንዳሉ እግ ዚሀር ነው የሚያውቀው" እያለች የሁለቱ የበኩር ልጆቿ ነገር በተነሳ ቁጥር ትንሰፈሰፋለች። ስለዚህ ወጣቱ ጂራልድ ወደንሱ ተሳበ።

ከቤት ሲወጣ እናቱ በችኮላ ስማውና የካቶሊክ ምርቃቷን በጆሮው ሹክ ብላ መርቃው ሲሆን አባቱም "ማን እንደሆንክ አስ ታውስ፡ የማንንም ምንም ነገር አትንሳ" ብሎ የመለያያ ማስጠን ቀቂያውን ሰጠው። አምስቱ ረሳሆም ወንድሞቹም እያደነቁት ነገር ግን በዕድሜም በሰውነትም የቤተሰቡ የመጨረሻ ትንሽ ልጅ በመሆኑ በታላቅነት ስሜት ፈገግ እያሉ ተሰናበቱት።

አምስቱ ወንድሞቹና አባታቸው ከስድስት ጫማ በላይ ቁመ ታቸውን ይዘው እንደቆሙ ትንሹ ጂራልድ በሃያ አንድ ዓመቱ አምስት ጫማ ከአራት ተኩል እንች ብቻ ቁመት ይዞ እግዜር በጥበቡ ሊሰጠው የቻለው ቁመት ይህን ብቻ መሆኑን እምኖ ተቀ ምጧል። ጂራልድ ቁመቱ በማጠሩ የሚፀፀት ሰው አይደለም። የፊ ለገውንም ነገር ለማግኘት አጭር ቁመቱ እንትፋት ሆኖት አያው ቅም። እንዲያውም ጂራልድን ጂራልድ ያረገው እጥር ምጥን ማለቱ ነው። ምክንያቱም በጣሙ ብዙ ሰዎች ማህል የሚኖሩ ትናንሽ ሰዎች ጠንካሮች መሆን አለባቸው የሚለውን ትምህርት በጊዜ ስለተረዳ ነው። እናም ጂራልድ ጠንካራ ነበር።

@OLDBOOKSPDF

ረዣዥሞቹ ወንድሞቹ ኮስታራና ረጋ ያሉ ሲሆኑ ያ ለዘለዓለም የተንኮታኮተው የቤተሰባቸው በገና ተሞልቶ የነበረ ባህል በአእምሮአቸው ውስጥ በጥላቻ በተመረዘ ትውስታ እየተጉላላ በመራር ቁልድ መልክ ይወጣል። ይናገሩታል። ጂራልድም ግዙፍና ጉንጭማ ቢሆን ኖሮ እንደሌሎቹ የአሃራ ዘሮች በምስጢር ቁስ ብሎ ጨለማ ለበሶ መንግሥትን ከሚቃወሙት አመጸኞች ጋር ይቀላቀል ነበር። ጂራልድ ግን እናቱ በፍቅር እንደምትገልጸው "ክፍት እፍና ደደብ ሞንቅላት" ነው። ቶሎ ቶማ ይላል። ለጠብ ለቡጢ ይጣደፋል። የትከሻው አጥንት በአይን አስከሚታይ ድረስ ገጧል። በረገጎቹ የአሃራ ዘሮች ግሀል ልቡን ሞልቶ ሲንራደድ በተርኪኒኮች መካከል ያለች የምትጠራራ የወፍ ጫጩት ይመስላል። እነሱም ይወዱታል። እየኮረኮሙ ያስጨሁታል። ትንሽ ወንድም በቆመበት ቦታ በማያቆይ ግሩፍ ጭበጣቸው እንደመዶሻ እየመቱ ድንፋታውንና እንዶአንበሳ መጮሁን እየሰሙ ይገናኙሉ።

ጂራልድ ወደ አሜሪካ ይዞት የመጣው ቅንጣት ታህል እንኳ ትምህርት ቢኖር አሱንም እንኳ ሳያውቅ ነው። ቢነገረውም ጉዳዩ አይደለም። እናቱ ማንበብና ጥሩ አድርገው መፃፍ አስተምራዋለች ፊደላትን በምልክት ማስቀመጥና በቁጥር ማንም አይደርስበትም። የመጽሐፍ ዓለም ዕውቅቱ እዚያው ሳይ ያበቃል። የሚያውቀው ላቲን ቢኖር የቁርባን ፀልት ነው። የሚያውቀው ታሪክ ደግሞ አየር ላንድ የሰራችውን በርካታ ስህተት ብቻ ነው። የመዝሙር ግጥሞች በስተቀር ግጥም የሚባል አያውቅም። ሙዚቃም ቢሆን ለዓመታት ሲወርድ ሲዋረድ ከመጣው ከአየርላንድ መዝሙር በስተቀር የሚያውቀው ነገር የለም። ከሱ ይበልጥ ዕውቀት የዘለቃቸውን፣ ከሱ ይበልጥ የመጽሐፍ ትምህርት ያላቸውን ሁሉ ያከበራል፣ ያደንቃል። የራሱ ዕውቀት ማነስ፣ የራሱ አለመማር ግን አይሰማውም። ከእንግዲህስ አሁን በገባባት አዲስ አገር፣ ማንም ቆርቆሮ ራስ ደንቆሮ ብር በብር በሆነባት አዲስ አገር፣ መማር ምን ይጠቅመዋል? ማንም ሰው ጠንካራ ከሆነና ሥራን ካልፈራ ትልቅ ሰው በሚባልበት አገር እውን ዕውቀት ምን ይረባዋል?

ላቫና ያለውን መጋዘናቸውን ሊያላዩት የወሰዱት ጀምስና እንድሪውም ቢሆኑ አለመማሩ ምንም አልዐበታቸውም፤ ጥሩ እጅ ጽሕፈት፣ ትክክለኛ የቁጥር ስሌት ችሎታውና ክርክር ሲከራከር ያለው ጭሌነት ለሰጡት የሚገባውን ከብር እንዲያገኙጽፉት አያረጋቸው። የሰነ ጽሁፍ እውቅትና የመዘጋ አድናቆት አለኝ ብሏቸው ቢሆን ኖሮ ገና ዱሮ አይንህን ላፈር ብለው የጉሪጥ ባዩት ነበር። በምዕተ አመቱ መጀመሪያ ላይ አሜሪካ ለአየርላንድ ዜጎች የአብ

@OLDBOOKSPDF

ርሃም የጣራ ቤት ንበረት ። ደማ ነፀረች ። ጅምስና አንድረው ዕቅም ችን በተሸፈኑ መኪናዎቸው ሥነው ከሳቪና ወደ ጅርጅያ የደሴት ዝተማምች እየወሰዱ ዛፊ ባለመጋዘን ሆነዋል ። ጂራልድም ልብሱ ቸው ከበረ ። ደቡብን ወደደው ። አናም በራሱ አስተሳሰብ ወዲያ ውኑ ደቡባዊ ሆኗል ። ስለደቡብና ስለደቡቡ ሕዝብ በሙራሽ ሲረ ጻው የማይችል በጣም ብዙ ንባር አለ ። ብቻ በሱ ዝር ተፈጥሮና ቸን ልቡና ራሱ እንደሚጠፋውና እንደሚሰማማው ሕድርን ልማድና ወኑን ፣ ባህልና አኗኗሩን ለመደው ። ቋሚርና ፈረስ ግልቢያ ሞቅ ያለ ፖለቲካና የፍልሚያ ድንበች ፣ የሀገሮች ነፃነትና ሉሉንም ደን ኪዎች መራጣም ፣ የላሪያ ስፎዓትና የሞጥ ኝጉሥ ፣ ለርካሽና ዝቅ ተኛ ነጮች ጥላቻን ማሳየትና ሴቶችን ከልቡ በላይ ማቹከርመምና ማጫወት የሱ ሆኑ ። ሬሳው ቀርቶ ትንባሠ ማኝከንም ጭምር ተማረ ። ለሙብኒ የሚሆን ሙንቅሳት ጭሰን መሄድ እላሸውም ። ከራሱ ጋር የተፈጠረ የራሱ ቋንቋሰት ኖለው ።

ዞሮ ዞሮ ጂራልድ ግን ያው ጂራሬድ ሆኖ ቀረ ። የአኗኗሩ ሁኔ ታና ሃሳቡ ቸብዉለ ። የራሱን ብሀርያት ግን ሲለሙጣቸው ቢኾል እንኳን አይለሙጣቸውም ። ሙቤታሞቹን ባልፍገኒና ባለጥጥ ሰፌ አርሻ ባለቤቶች ፣ ከአረንጓዴው ጣጣታቸው በቅልበ ፈረሶቻቸው ሆነው ፣ የሚያማምሩት ሚሰኔቻቸው ስረነሳ አየተንቀቀሰቸውና የላሪ ያዎቻቸው ኃሪ ጨዎቹቸው፣ ዘዴ ሊቸና ሲጋልቡ አያየ በጣም ያደ ዓቃቸዋል ። ጽሩ ምን ያረጋል ጂራሉድ ኑንዶነሱ ማማር ፣ እጅነሱ መልክ መልክም መሆን አለቻለም ። የነሱ ሰነቁና የተሻገበረዘሪ ድምጽ ደስ እያለው ወዲጂሮው ይገባል ። የቡ ጉልድፍ ጨበት ግን ከምላቡ እሮቀላቱመ ይቀራል ። ሰለታሚ ዋና ዋና ጉዳዮችን ሲፈ ጽሙ ያለቸውን ያቁም ነገረኝነት ግርማ በጣም ወዶታል ። ክርታ ሲፍወቱ ቤት ንብረት ፣ የእርሻ ፀታ ወይም ባፊያ እያሉያቹ መሆኑ ሲከስሩ ኪማራቸውን ያለምንም ጭንቅ በጥሩ ቀልድ ኦጅበው ሲሰ ርዙ እንዲሁም ሳንቲሞችን በትናንሽ ልጅች አስበው እስኪበታተኑ ድረስ ያሳቸውን የቴማር ስነ ስርዓት በጣም አደንቆታል ። ችግሩ ጂራልድ ደህነትን ደህና አድርጎ ስለሚያውቅ ንንብቡን ሲከስር በፊ ገማታ ወይም የደስደስ ብለው ግርማ ሞገስ ሲቀበል አልቻለም ። እነዚህ የጀርጂያ ዳርቻ ልጋር ሰዎች ደስ የሚሉ ግጣዎች ናቸው ስለሰላሳ ድምጻቸው ፣ ሱሉ የመናደጃቸው ፣ እንዲሁም ወዝ ያለው ተለዋዋጭነታቸው ጂራልድን ከልቡ እንዲገቡ አድርገውታል ። ሆኖም ወጣቱ የእየርለንድ ዜጋም ቢሆን እረፍት የለሽ ፣ ሕይወት የተሞላና ንቁ ተፈጥሮ አለው ። እንግዳ ሆኖ የመጣው ንፋስ ፣ አርፐበትና ጨፃ አዘለ ከሚነፍስበት ፣ ጭጋግ የተከናነቡ ረግረግ ቦታዎች የመባ ትኩ ሳት ከማይፈጥሩበት ልጋር ሲሆን ያገሩ አየር ጠባይ ከነዚህ ከፊል

@OLDBOOKSPDF

ትሮቢካዊ ፡ ወባማና ወይስ ደዌ ሰናይ ነሽ ያለው አገር ነዋሪ ሰዎች ይለየዋል ። ከነሱ ጠቃሚ ጠቃሚውን ተማረ ። ፡ የማይረባውን ተወ ። ደው ዋነኛና ጠቃሚ ነገር ነው ። ለካርታ የሚሆን ቀልጣፋ ተፈ ጥሮ አለው ። ሌላው ደግሞ መጠጥ ነው ። እነዚህ የመረጣቸው ነገሮች ከሦስቱ ዋና ዋና ንብረቶቹ ሁሉ እጅግ ዋጋ የሚሰጣቸውን ሁለት ነገሮች አግኖጽፈውታል ። እነዚህም ወንድ አሽከሩና የእርሻ በቃው ናቸው ። ሦስተኛው ባለቤቱ ናት ። እሷን የሰጠው ምስጢራዊው የእ ግዚዘር ቸርነት ነው ።

ፖርክ የተባለው የቤት አሽከር የነግ ልጥልጥ የመሰለ ጥቁር ሲሆን በሥራው ይህ ይቀረዋል የማይባል ኩሩ ሰው ነው ። ጂራልድ በጥራ እንጂ በኒውእርሊያንስ መጠጥ ከማይተካከለውና ከቅዱስ ስም ያን ደሴት ከመጣው ባለሰፈ እርሻ ሀብታም ጋር አንድ ለሊት ሙሉ ቁማር ተጫውቶ አሸንፎ ነው ፖርክን ይዞ በድል አድራጊ ነት ቤቱ የገባው ።የፖርክ የፅሮ ጌታ እንኳ የፖርክን ዋጋ እጥፍ አድርጐ ከፍሎ መልሶ ሊወስደው ፈልጐ ነበር ።ነገር ግን ጂራልድ ንክች አላደረገውም አለ ። ምክንያቱም አንድም የመጀመሪያ ባሪያው "ባገሩ ምርጥ የሚባል የቤት አሽከር" በመሆኑ ፤ አንድም ከጥንት ጀምሮ ሲመኝ የነበረው የባሪያ አሳዳሪ የመሆን ሕልም ስለነበረ ውና የልቡ ስለሞላ ነው ።ሌላው ሕልሙ ባለሰፊ እርሻ ባለፀጋ መሆን ነበር ።

ጂራልድ አንደወንድሞቹ እንደ ጂምስና አንደ አንድሪው ቀኑን ሙሉ በዋጋ ክርክር ላይ ማሳለፍና ፣ ለሊቱን ሙሉ ደግሞ በሻማ ብር ሃን ሂሳብ ሲደምሩ ሲቀንሱ ማደር በጭራሽ አያዋጣም ብሎ ወስ ኗል ።ወንድሞቹ አይፈልጉ እንጂ እሱ በንግድ አብሯቸው ከሚሠራ ቸው ሰዎች ጋር ጥሩ ዓይነት ወዳጅነት ስለሚሻ ያ ደግሞ "ከንግድ" ጋር የማይሄድ በመሆኑ ባለሰፊ እርሻ መሆን ይሻላል ባይ ሆኗል ። ከዕለታት አንድ ቀን የራሱ ወገኖች ሀብት ንብረት የነበረ መሬት ላይ ጭሰኛ ሆኖ በቆየ ሀብታም የመሆን አየርላንዳዊ ጥማት ተነሳስቶ ከጸር ዳር አረንጓዴ በአረንጓዴ የተጥለቀለቀ የተንጣለለ ጋሻ መሬት ኖሮት የማ የት ፍላጐቱ የትና የት ነው ።በሌላ በምንም በማይለውጠውና በጣም ግትር በሆነው ዓለማው መሠረት የሚኖርበት ቤት ፣ የሚያርስበት መሬት ፣ የሚያሳድረው ባሪያና የሚጋልበው ፈረስ እንዲኖረው ይፈ ልጋል ። ከዚያ ይኖርበት ከነበረ አገር ይልቅ ይሄኛው በእንግድነት የመጣበት አገር ይሻለዋል ። ምንም እንኳን ያመረተውን የሚበላ በት ግብርና ድንገተኛ የሆነው የመወረስ አደጋ ሁለቱ ዋና ዋና ስጋ ቶች ቢኖሩም ንብረቱ እንዲኖረው ያለውን ፍላጐት አላሸነፉበ

@OLDBOOKSPDF

ችም ። ዳሩ ግን ይህን ዓላማ ማለምና በተግባር መተርጉም ሁለት የተለያዩ ነገሮች መሆናቸውን ጊዜ እያለፈ ሲሄድ እየተረዳ መጣ ። የልቡ እንዳይሞላና ተስፋ ያደረገውን እንዳያገኝ ከአገር ጫፍ እስከ አገር ጫፍ ርስተ ጉልቱን ተክሎ የተቀመጠው የጀርሚያ መሳፍንት የማያስቀምሰው ሆነ ።

ውሎ አድሮ የዕድል እጅና የቁማር እጅ ተጨባበጡና ታራ ብሎ የሰየመው ሰፊ እርሻ መሬት ባለቤት አደረጉት ። እግረ መንገዱንም ወደደጋማዋ ክሳባቢ አንዲሸጋገር ገፋፍተው ሰሜን ጀርሚያ ውስጥ አስከተሙት ።

በፀደይ ወር አንድ ማታ ሳቫና ባለ አንድ ሀንባ ውስጥ ተቀምጠ ሳለ ባጋጣሚ ከጐኑ የንበረ እንግዳ ሰው ሲያወራ የጂራልድን ጆሮ ሳበው ። የሳቫና ተወላጅ የሆነው ያ እንግዳ ከአሥራ አራት ዓመት በኋላ ወደ ቆላው አገር ከርሞ መምጣቱ ነው ። ጂራልድ ወደ አሜሪካ ከመምጣቱ ከአንድ ዓመት በፊት የነበሩት ሀንዶች ፣ ሰዋተውት የሄዱትን ማዕከላዊ ጀርጂያን ፣ መንግሥት በቶምቦላ ለመስጠት አስቦ ባወጸደረበት ጊዜ ከሸንሩት ባለ ዕድሎች ማህል ይህ እንግዳ አንዱ ነበር ። እዚያ ሄዶም እርሻውን ጀመረ ። አሁን ግን መሬቱ ላይ ያለውም ቤቱ በለተቃጠለ "ያን የተረገመ ቦታ" ሸጠ ለመግላገልና እፎይ ለማለት ይፈልጋል ። የቦታ ነገር ልቡን ሰቅ ሎት የከረመው ጂራልድ ይሄኔ ቀልጠፍ ብሎ ሰውየውን ይተዋ ወቃል ። ሰሜናዊ ጀርጂያ ከጊዜ ጊዜ ከካሮላይናና ከቨርጂንያ በሚ መጡ አዲስ ሰዎች እየተጥለቀለቀ መሆኑን እንግዳው ሲናገር የጂ ራልድ ቦታ የመግዛት ጉጉት ሰሚይ ያረሰ ። ጂራልድ ሳቫና ውስጥ ለረጅም ጊዜ ሲኖር ስለዳር አገሩ ሁኔታ አጥብቆ በተረዳው መሠረት ከጀርጂያ በስተቀር አገሩ ሁሉ በጫካ የተሞላ ነው ። ከየጫካው ደግሞ እየዘለለ የሚወጣ አንዳንድ ጨብራራ ህንድ ብቅ ይላል ። ለአሳራ ወንድሞቹ ንግድ ሲል ያልሠረበት ቦታ የለም ። ከሳቫና ወንዝ መዶ ማይል እርቀት ላይ የሚገኘውን አውንስቃን ገመበኝቷል። ከዚያች ከተማ በስተምዕራብ ሲል የሚገኙትን ትናንሽ አሮጌ ከተ ማዎች በሙሉ ውስጥ ውስጡን ዘልቆ አይቷቸዋል ። ያ አክባቢ ልክ እንደዳር አገሩ የተደላደለ መሆኑን ያውቃል ። ነገር ግን እንደእንግ ዳው አገላለጽ የሱ እርሻ ቦታ ከሁለት መቶ ሀምሳ ማይል የበለጠ ከሳቫና ወደደቡብና ወደሰሜን ገባ ያለ ነው ። ከቻታ ሁቺ ወንዝም ምንም ያህል አይርቅም ። ከዚያ ዥረት ወደሰሜን ሲል መሬቱ እሁ ንም ቢሆን በቹረከ ጐሣ ሰዎች የተያዘ መሆኑን ጂራልድ ያው ቃል ። ስለዚህ ያ እንግዳ ሰውዬ ሕንዶች እንደሚረብሹትና ከተ ሞቹ እንዴት እያደጉ እንደሆነ እንዲሁም እርሻዎቹ በዚያች ድን

@OLDBOOKSPDF

ግል ከተማ እንዴት እየለመ እንደ ሄዱ ሲናገር በጣም እየተገረመ ያዳምጠዋል ። ወሬያቸውን እያወሩ አንድ ሰዓት ያህል ካለፉ በኋላና ሁኔታው ተዝቀዝ ሲል የቡሩህ ዓይኖቹን የሞህኑት በሚያምሳ የሙሉ አስተያየት ካርታ ብንጫወትስ የሚል ሀሳብ አመጣ ። ለሊቱ እየገፋ ሲሄድ የመጠፀም ዙር ቁጥር እየበረከተ መጣ ።ብማህል ሴሎቹ ሁሉ ባዶ እጃቸውን ቀርጠው ተመልካች የሆኑበትና ጂራልድና እንግዳው ሰውዬ ብቻ የቁማሩን ጨዋታ የተያያዙበት ሰዓት መጣ ። እንግዳው ሰውዬ ገንዘቡን ፈጠርሶ የእርሻ ቦታውን የሚያስይዝበት ደረጃ ደረሰ ።ጂራልድ ገንዘቡን ሁሉ ስበስበና በላዩ ላይ ቦርሳውን ጫነበት ።ያ ፀርሳ የያዘው ገንዘብ የአሃራ ወንድ ማማዎች ድርጅት ገንዘብ ቢሆን እንኳ የጂራልድ ሕሊና ነፃ ጠዋት ከቁርሳን በፊት ምሉ ይሸጥር እንደሆነ ነው እንጂ ለዛሬ የራሱ አድርጉ ይዘታል ።የሚፈልገውን ነገር ያውቃል ።ጂራልድ የፈለገውን ለማግኘት የሚጠቀምበት መንገድ ከመንገዶች ሁሉ በጣም ቀጥተኛውን ነው ።በዚህ ላይ በሕይወቱ ወሳኝ በሆነው ዕጣ ክክቡ ላይ ያለውም እምነት ይሸለው ነው ።ብጥሱቱበዘው ገንዘብ ላይ የጫነው ቦርሳ ከያዘው ገንዘብ በላይ ተጭኖታል ብያወጣ ነገን ይውጠኝ ይሆን ብሎ በጭራሽ አስቦም አያውቅ ።

"አንተ እንድምትረታኝ የሚያጠያይቅ ነገር አይደለም ።በዚያ ቦታ ላይ ከእንግዲህ ምንም ታክስ የሚባል ባለመክፈሉ በጣም ደስ ብሎኛል ።" አለ መሬቱን አበይዘ የሚሄዉተው እንግዳ ሰውዬ ቅስምና ብዕር እንዲሰጠት እየጠየቀ ። "ቢቱ ባለፈው ዓመት ተታጥሎ መሬቱ ጸጥ እየዋጠው ነበር ።ያም ሆነ ይህ መሬቱ ያንተው ነው ።"

"አየህ ፖርክ ፣ በልጅነትህ የአየርላንዱን ውስኪ (ፖቲን) በጡመ እያጠጡ ከእናትህ ጡት ለይተው ካሳሳድጉህ በስተቀር ውስኪን ከካርታ ጋር አትደባልቅ" አለ ጂራልድ የዚያኑ ዕለት ማታ ወደ አልጋ ሲጠጣ ፖርክ እየደገፈው ሳለ ።ያም የቤት አሽከር ስአዲሱ ጌታው ያለውን አድናቆት ለመግለጽ በማያውቀው የአየርላንዳዊያን የአንጋገር ዘዴ ፣ ከሁለቱ በስተቀር ሲገባ በማይችል የቋንቋ ዲቃላ ተጠቅሞ የንሽ አበጀህ መልሱን ሰጠ ።

ጭቃማው የፍሊንት ወንዝ ፣በዋርካና የወይን ሐረግ በተጠመጠመ ጠባቸው የኬክ ዛፍ ማድማጃዎች ማዕል ድምፁን አጥፍቶ እየገሰገሰ በለስላሳ ክንዱ የጂራልድን መሬት በሁለት በኩል አቅፎታል ።በተቃጠለው ቤት ትቢያ መሀል ባለው ከይላ ላይ ለቆመው ለጂራ

@OLDBOOKSPDF

ልድ ፣ ይሄ ረጅሙ የአረንጓዴ ዛፍ ማድማዳ ፣ ለድንበር መከለያ ራሱ የተከለው አጥር መስሎ ታየውና ልቡ በደስታ ማዕበል ተጥለቀለቀ ። ረመጥ በወረሰው የተቃጠለው ቤት ጥቁር መሠረት ድንጋይ ላይ ቆሞ ወደ ዋናው ጉዳና የሚገናኘውን መንገድ በሰልፍ ቆመው ወዳጅቡት ዛፎች ቁልቁል ተመለከተና ከምስጋና ፀሎት በላይ የሆነ የደስታ ስሜት አፍኖት የስስትና የጉጉት መሀላ ማለ -በልቡ ። ከእንግዲህ እነዚህ ጥላቸውን ያጠሉ በመስመር የተከለኩሉ ዛፎች የሱ ናቸው ። ከእንግዲህ ይህ ደስስ የሚል አረንጓዴ ሜዳ የሱ ነው ። ከእንግዲህ የነጫጭ ትክብ አበቦች ማረፊያ የሆነውና እወገብ ድረስ የሚሸፍን አረም ግርጌውን ያጥለቀለቀው የማሣኖሊያ ዛፍ የሱ ነው ። ያልተስተካከለው ጥሻ ሜዳ ከነቀጫጭን የኮክ ዛፍ ችግኙ ቀይ አፈር ገላውን በረጅም አድማስ ላይ ሂ አድርጎ ተኝ ቷል ። ያህ ሜዳ የጂራልድ አሣራ ንብረት ሊሆን የቻለው አንድም የማይወናበድ አየርሳንጻዊ ጭንቅላት ስላለው ፣ አንድም ያለ የሌለ ውን ነገር በካርታ የማስያዝ ከባድ ድፍረት ስላለው ነው ።

ጂራልድ ዓይኖቹን ጨፍኖ አሰበ ። በፀጥታ በተዋጠው ያልታ ረሰ ጋሻ መሬት ማህል አቧርጠ ወደቤቱ የመጣ መስሎ ተሰማው ። በእዚህ በእግሩ በረገጠው መሬት ላይ አንድ ወቱት የመሰለ ነጭ ሕንፃ ይበቅላል ። መንገዱን የሚያሳርጥ አዲስ የአጥር ሀዲድ ይዘ ረጋል ። ይህ አጥር ወፋጥራም ከብቶቸንና ትላልቅ ሰንጋ ፈረሶችን ከበ ይቆማል ። በኮረብታው ጻር ጻር እየተጠቀለለ ወርዶ ወደለሙ የወንዙ ግርጌ አፈር የሚዘልቀው ቀይ መሬት ለአይን በሚታክት የጥጥ ተክል ተሞልቶ የፀሐይ ብርሃን ሲያርፍበት እልፍ አእላፍ የዳክዬ ጉጆዎች አስኪመስል ድረስ ነጭ ብርሃን ይተፋል ። እነሆ የአሣራዎች አዳኛ ንብረት እንደገና ይከማቻል ። ጂራልድ ያለች ውን ትንሽ የቁማር ገንዘብ ቋጥሮ ፣ ሌላ ሥራ ከማይዋጥላቸው ወንድሞቹ ጥቂት ገንዘብ ተበድሮና በቦታው ካርታ ከባንክ ብድር ወስዶ በመጨመር የመጀመሪያዎቹን የጥጥ እርሻ ሠራተኞች ጉል በት ገዝቶ ፣ የታራ ነጭ ሕንፃ እንጉቱን ብቅ አድርጎ በኩራት እስ ኪታይ ድረስ መሬቱ ላይ ባለው የምስለኔው ባለአራት ክፍል ቤት ብቻውን በወንደላጤ መልክ ሲኖር ወደታራ መጣ ።

ማሳውን አስመንጥሮ ጥጥ ተክለበት ። ከጅምስና ከስቱዋርት ተጨማሪ ገንዘብ ተበድሮ ብዙ ባሪያዎች ገዛ ። የአሣራ ዘሮች የገሳ መተሳሰርና ፍቅር በጣም ከፍተኛ ነው ። በከብረትም ሆነ በክስረት ጊዜ እጅ ለእጅ ይያያዛሉ ፣ ይደጋገፋሉ ። ይህ ከሌላ ከምንም ዓይነት የቤተሰብ መዋደድ የመነጨ ሳይሆን ፣ ያለፈው ከፋ ዘመን፣ አንድ ቤተሰብ ራሱን ለማኖር በዓለም ፊት አንድ የማይበገር ግንባር

@OLDBOOKSPDF

መፍጠር እንዳለበት በሳስተማራቸው ነው። ጂራልድ የሚፈልገውን ያህል ገንዘብ አበደሩት፤ በቅጣዮቹ ዓመታት ከነወለዱ ተመለሰላቸው። ከመሬቱ ኩታ ገጠም የሆነውን መሬት ሁሉ ጂራልድ በየጊዜው በገዛ ቁጥር እርሻው በጣም እየሰፋ፣ በወርዱም በቁመቱም እየተልጠጠ ሄደ። ያ ሀልም የነበረውም የነጭ ህንፃ መኖሪያ ፎቅ ቀስ በቀስ እውን ሆነ።

ሕንፃው በባሪያ ጉልበት የታነፀ ነው። ቀስ እያለ እያዘገመ አየር ላይ ሲሄድ ቆይቶ አሁን ወደወንዙ እየተዳፋ ለሚያቅለቀለቀው ግና በአዲስነቱ ዘመናትን ያሳለፈ በመምሰሉ የጂራልድን ደስታ እጥፍ ድርብ አድርጎታል። አሮጊቶቹ የዋርካ ዛፎች በእግርና በእጁ ቸው ሥር ስንትና ስንት ሕንዶችን አሳልፈዋል። ዛሬ በወፍራም ግድግዳቸው ቤቱን በጣም እየታከኩ አቅፈው ሽቅብ ወደ ሰማይ ይዘልቁና በቅርንጫፎቻቸው እንደጃንጥላ እያጠሉ የቤቱን ጣራ ከፀሐይ ይጠብቃሉ። የጣቢውም ግቢ አረሙ ተንቅሎ አዳዲስ ሰር ተተክለውበት አረንጓዴ ምንጣፍ ከጥር እጥር የተዘረጋበት መስ ሏል። ጂራልድ የጣቢውን ሙበት በመንከባከብ ረገድ እጅግ ጠንቃቃ ነው። የባሪያዎቹ መኖሪያ የሆኑት ነጫጭ ቤቶች መደዳ ድረስ የማሕደውን መንገድ በሰልፍ የሚያጅቡት የአርዘሊባኖስ ዛፎች፣ አካባቢውን በጣም የረጋና የጥሩላደለ ከማድረጋቸው የተነሳ ለታራ ዘለዓለማዊነትን ያጐናጽፉታል። ጂራልድ ከሩቅ ዋናውን አውራ መታጠፊያ ዞር እየታለበ ብቅ ሲል ያንን ከአረንጓዴ ቅርንጫፎች መሀል አንጣጥን እንደ ሰጦን አስግጎ የወጣውን የገዛ ቤቱን ጣራ ያይና እያንጓጓ አይታው አዲስ እንደሆነ ሁሉ ልቡ በኩራት ከአፍ እስከገደፉ ይሞላል።

ይሄ ትንሽ ፍጥረት፣ ይሄ ግትር ድንክዬ፣ ይሄ ቁጡ ጉረኛና ጫጊ ጂራልድ የሚባል ሰው ይሄን ሁሉ ውብ ነገር፣ ይሄን ሁሉ ድንቅ ነገር ሠራ። ገነባ። ሕልሙን እውን አደረገ።

ጂራልድ ከሱ እርሻ በስተጣራ በኩል ኩታ ገጠም መሬት ካላ ቸው ከማኪንቶሽ ቤተሰብና በስተቀኝ ረግረጉን አፈር ይዞ በወ ንዙና በጀን ዊክስ እርሻ ቦታ ማሀል የማትረባ ሶስት ጋሻ መሬት ይዘው ከሚካለሉት ከስላተሪ ቤተሰብ በስተቀር ከጉረቤቶቹ ሁሉ በጣም ይስማማል፤ ይዋደዳል።

የማኪንቶሽ ቤተሰብ በትውልዳቸው የእስኮትላንድና አየር ላንድ ቅልቅልና አሬንጅሜን ሲሆኑ፣ በካቶሊክ ቀን መቁጠሪያ ላይ ያሉትን መላእክት ባህሪ ሁሉ እንኳ አላቸው ቢባል በጂ

@OLDBOOKSPDF

ራልድ ዓይን ከትውልድ ትውልድ ሲረግማቸው የሚኖር ዘሮች ናቸው። በርግጥ ጆርጂያ ውስጥ ለሰባ ዓመታት ኖረዋል። ከዚያ በፊት ደግሞ በካሮላይና የአንድ ትውልድ ዕድሜ ኖረዋል። ሆኖም በአሜሪካ ምድር ለመጀመሪያ ጊዜ እግሩን ያሳረፈው ቤተሰብ ከእልስተር የመጣ መሆኑ ብቻ ለጂራልድ በቂው ነው። በጣም ዝግ፥ ምስጢር በሆዳቸው እንዳመቁ የሚኖሩና እነሱ ያሉት ብቻ ልክ ነው ብለው የሚያምኑ ከቸር ቤተሰብ ናቸው። ከማንም አይገጥሙም። ያገር እድር አደውቃቸው፥ ቡና አይጣጡ፥ ሰው ቢሞት አይቀበሩ ብቻቸውን አፈንግጠው የሚኖሩ ናቸው። የሚጋቡትም ቢሆን ከካሮላይና ዘመዶቻቸው ጋር ነው። ደሞ ጂራልድ ብቻ አልነበረም የሚጠላቸው። የሩቅ የቅርብ ጐረቤት አይናችሁን ላፈር ብሏቸዋል። የባሪያ ነፃ አውጪ የሆኑት የአቦሊሽኒስቶች ደጋፊ ናቸው የሚለው ጭምጭምታ ወሬ እንኳ የማኪንቶሽን ቤተሰብ ተወዳጅ ሊያደርገው አልቻለም። ሽማግሌው የቤቱ አባወራ አንገስ ማኪንቶሽ አንድ ባሪያ እንኳ ነፃ አልቀቀም። እንዲያውም ሕብረተሰቡ በምንም ዓይነት ይቅርታ የማያደርግለትን ጥፋት ፈጽሟል። ወደስዚያና የሸንኮራ አገዳ እርሻዎች ለሚሄዱ ባሪያ ነጋዴዎች የራሱን ኔግሮዎች አሳልፎ ሸጧል ይባላል። ሐሜታው እስከአሁንም ድረስ አለ።

"እምነ፥ እርግጥ ነው የአቦሊሽኒስት ቡድን አባል ነው" አለ ጂራልድ ለጆን ዊክስ ሲያስረዳ። "ነገር ግን ማንም የፕሮቴስታንት ሀይማኖት ደጋፊ የሆነ አፈንጅማን የስኮትላንድ ተወላጅነቱን የሚጋፋ ማናቸውም አዟም ሚናቸውም ዕምነት ከመጣህበት አቋሙን ገፍቶ ጥሎ ስኮትላንዳዊነቱ ሲጠናበት ታገኘዋለህ።"

የስላተሪዎችም አንጸባራቂ ጐዳይ ነው። እነሱ ደግሞ ደሀ ነጮች በመሆናቸው አፈንጋጩና ግትሩ አንገስ ማኪንቶሽ የሚያገኘውን ያህል እንኳ የአንገት በላይ ክብር ከጎረቤት አላገኙም። የቤተሰቡ አባወራ የሆነው ሽማግሌው ቶም ስላተሪ ምንም እንኳን ጂራልድና ጆንዊክስ በተደጋጋሚ አስፈላጊውን መሬት አንስጥህና ከድህነት ተላቀቅ ቢሉት ያሉትን ጥቂት ጋሻ መሬቶች ይዞ አይጨምር፥ አያድግ ዕድሜ አለመኑን እየተነጫነጨ በድህነት ተቆራምዶ ይኖራል። ሚስቱ አንድ ከሰውነት የወጣች ቀሰስተኛ ቆርጫጃ ፀጉር ናት። ጥንቸል ጥንቸል የመሳሰሉ ኮስማና ልጆች ወልዳለች፥ በየዓመቱ መሬልፊኗን ስለማታቋርጥ የነዚሁ የጐስቋላ ጥንቸሎች ቁጥር በዓመት በዓመት ይጨምራል። ቶም ስላተሪ ምንም ባሪያ የለውም። እሱና ትላልቅ ወንዶች ልጆቹ አንዴ መጥተው በሆነ ጥሞ ለቁማ እርሻውን ይዘውታል። ሚስትየውና ትናንሽ ልጆቿ የጓሮ አትክልት ብለው የሚጠሩትን ቦታ ይንከባከባሉ። ሆኖም ለምን

@OLDBOOKSPDF

እንዴሁ እንጀ ጥሙም ደህና ይሀ አያውቅም ፡ አትክልቱም በወይ ዘር ስላተሪ ጭሚ የልጅ ማዘል ሥራ ምክንያት ከማቲምጅ አፍ የሚተርፍ ነገር አጥርቶ አያውቅም ።

ቱም ስላተሪ በየጉረቤቱ ደጃፍ እየዘረ ዮጥጥ ዘር ወይም የአ ሳማ ሥጋ ሲለምን ማየት የተለመደ ነገር ነው ። ስላተሪ ባለችው የመጥይ አትም ሀሉ ጉረቤቶቸን ይጠላል ። ምክንያቱም ከጨዋ ታቸው ባሻገር አሽሙራሾው ፡ ከዮርሳቸው ፈገግታ ጀርባ የሆዳ ቸው ንክሻ ለሰሚታየው ነው ። በተለይ "ለኔማር የሚያዝኑ ሀብ ታም ሰዎችና" ሲጠምድ እንዴሕንድ ነገር ነው ። በመንደሩ ሙሰጥ የቤት ሠራተኞች የሆኑ ኔባሮምች ዝትጥና ኑሯችን ይነታሉ ። ዘኑ ሯቸው የሚበሉት ፡ የሚለብሱት ጥሬቸው ያለበታት መቀመጣቸው በቅናት ሲያቃጥለው ሠስጥ ውስጡን እንደሚሰድቡት ማስቡ ደግሞ የጉን ውታት ይሆንበታል ። ከቡ የመክራ ኑሮ ጋር ሲነፃ ፀሩ ጠግበው መብላታቸው ፡ ደህና ይሀና ልብስ መልበሳቸው ፡ ሲታመሙ ደራሽ ፡ ሲያረጁ ጣሪ ሚግኝታቸው ግልጽ ነገር ነው ። በጊዮታቸው መልክም ሥም ይኮራሉ ። ከወሎም በላይ ደግሞ እሱ በሰው ሀሉ ሲናቅ እነቡ ከጀሀና ዘር ሰዎች ጋር መሆናቸው በጣም ያኮራቸዋል ።

ቱም ስላተሪ የእርሻ ቦታውን በመንደሩ ለሚኖሩ ለማናቸውም ባለሰፊ እርሻ ሀብታምች ከሞጋሙ በሰስት እጥፍ አትርፎ መሸጥ ይችል ነበር ። እነዚያ ሀብታሞች ብራቸውን ፡ ከማነበረሰቡ ሜይን ፡ ጉድፍ ለማውጣት እንደተጠቀሙበት ኢያርገው ይቅጥሩት ነበር ። እሱ ግን በዓመት ጥቂት ጀነያ ጥጠንና የጉረቤቱንም ምጽዋት በቂዩ ነው አለ ።

ከቀረው የመንደሩ ሕዝብ ጋር ጂራልድ ጥሩ ግንኙነት አለው ። ይህ አሜሪ ሰው በቀልቅ ፊረስ ላይ ተቀምጠ ገና ብት ሲል የዊ ከስ ፡ የክልቨርት ፡ የቃርሉቱን እና የርንቲን ቤተሰቦች ፈገግ ይላሉ ። ከዚያም በስኳር ላይ የተጨመረ ቦርቦን ውስኪና ማጣፈጫ ቅመም የተጨመረበትን ረጅም ብርጭቆ ሰምልክት ያሳዩታል ። ጂራልድ የሚወደድ ሰው ነበር ። ሕማኖት ልጆች ፡ ኔግሮምችና ውሾች ገና ሲያዩት የሚገባቸውን የሩሀሩህ ልቡን ፡ የዝነጂና አዛኝ ጀሮውን እንዲሁም ክፍት የክለ ደብተሩን ከሚጮኸው ድምፁ በስተጀርባ ብቅ ማለት የንረቤቱ ሰው የተረዳው በተስተመጨረሻ ነው ። የሰን ወደመንደሩ መድረስ የሚያመለክቱ በርካታ ነገሮች አሉ ። የሚጮኸ አዳኝ ውሾችና ሮጠው ፊረሱን ለመያዝና የለመዱትን ስድባቸውን ከሱ እየተቀበሉ ለመጮህ የሚጣሉ ጥቂቁር ትናንሽ

@OLDBOOKSPDF

ልጆች ይታያሉ ። እሱ ለአባቶቻቸው የያንኪ ፖለቲከኞችን ባደ
ነት ሲያስረዳ ልጆቻቸው ገለበቱ ላይ ተቀምጠው በኋላ እንዲያ
ፈናጥጣቸው ወይም እንዲያስጋልባቸው ይሰምኑታል ። የሱ ጓደኞች
ሴት ልጆች እንደባልንጀራቸው እየቆጠሩት ስለጥቅር ጉዳይ ምስጢ
ራቸውን ያካፍሉታል ። የጐረቤቱ ወጣቶችም ቢሆኑ አባቶቻቸው
ሳያውቁ ላጠፉት ጥፋት የሚያማክሩት ጄራልድን ነው ።

"አንተ ድንጋይ ራስ የሆንክ ልጅ አንድ ወር ሙሉ ይህንን
እጅህ ላይ አቆየኸው!" ብሎ ይጮሀል ። "እረ የሰማያቱ ያለህ! ይህን
ከማድረግህ በፊት ምናለባት ገንዘቡን እኔን አስቀድመህ ብትጠ
ይቀኝ"

እንደልቡ የተሰማውን ነገር ልድቱ የሚድረቱ ነገር በጣም ከመ
ለመዱ የተነሳ ማንንም አያስቀይምም ። ወጣቱ እንደማፈር እንደመ
ሸኮርመም ይታጣውና፡ "አይ ጌታዬ እንዳልረብሽህ ብዬ ነው ።
አባቴ ደግሞ . . . "

"አባትህማ ግሩም ሰው ነው ። እሱ የማይከድ ነገር ነው ።
ብቻ ኮሰታራ ነው ። በል እኔን ይሄን ያዝና ሂድ ። ስለዚህ ጉዳይ
ሁለተኛ እንዳልሰማ"

የባለሰፊ አርሻዎቹ ሚስቶች የሱን ነገር ለመቀበል የመጨ
ረሻዎቹ ናቸው ። ያቺ ጄራልድ "ገም የማለት ተሰጥኦ ያላትና
ታላቅ ሴት" የሚሉት ወይዘሮ ዊከስ አንድ ቀን ምሽት የጄራልድ
ፈረስ ቁልቁል ሲጋልብ ከሰማች በኋላ ለባሏ እንዲህ ብላ ነገረችው ።
"ምላሱ የባለጌ ነው ነገር ግን ፈጣሞ ሰው ነው" ጄራልድ እንደተ
ለመደው መጣ ማለት ነው ። መጀመሪያ ጐረቤቶቹ የጐሪጥ ያዩት እንደ
ነበርና እንደማያምኑትም አያውቅ ስለነበር አካባቢውን ሁሉ አውቆ
ለመጨረስ አሥር ዓመት እንደፈጀበት አልገባውም ። ገና ታራን እግሩ
ሲረግጥ የታራ ሰው የሆነ ይመስለው ነበር ።

ጄራልድ አርባ ሶስት ዓመት ሲሆነው ሰውነቱ ደንዳና ፡ ፊቱ
ያመለመለ ነበር ። ምንም እንኳ ኑሮው የተደላደለ ቢሆን ፡ ምንም እን
ኳን ታራን ከልቡ ቢወዳት ፡ ምንም እንኳን የመንደሩ ሰዎች ልባቸ
ውንም በራቸውንም የከፈቱለት ቢሆን አንድ ነገር ከማሰብ ሊገታው
አልቻለም ። ሚስት ያስፈልገዋል ።

ታራ ፡ የቤት እመቤት ፡ የቤት እመቤት፣ እያለች ትጮሀለች ።
የሚዳ ሠራተኛ የነበረው ወፍራሙ ምግብ አብሳይ ከሚዳ ኔቪሶት
ወደ ማይቤት በእድገት የመጣ በመሆኑ ምግብ በሰዓቱ አይደርስ
ለትም ። የቤት ሠራተኛ ተብላ የተቀጠረችው ገረድም እንደዚሁ

@OLDBOOKSPDF

ጥሮ ሰሎሚ የነበረች ስትሆን እንድ ቀን ንፁሕ ልብስ ለብሳ ከለ ማወሷም በላይ የቤቱ ዕቃ በሙሉ አፀራ ባፀራ ሆኖ እንግዳ ሲመጣ ማሳቀቁ ይብሳል። በዚቱ ያለው የሰለጠነ የቤት ሠራተኛ ፖርክ ሲሆን ሌሎቹን ሠራተኞች በሙሉ የሚቆጣጠር እሱ ነው። ደሩ ግን እሱም ቢሆን ብዙ ዓመት ቆይቶ የጂራልድን እንደ እድሉ ያደር ሄደነት የአኗኗር ዘይቤ ሲመለከት እያደር ማደለሽ እየሆነ ሄዷል። እርግጥ እንደቤት ውስጥ አስተናጋጅነቱ የጂራልድን መኝታ በደንብ ያነጥፋል። እንደ ቤት ሠራተኛነቱም ምግቡን ወግና ልማዱ ሰይጎደል ያቀርባል። ከዚህ ውጭ ግን ሁሉንም ነገር እንደፍጥርጥሩ ማለት ጀምሯል።

ኤማርሃቹ በማይሳሳተው አፍሪካዊ ተፈጥሮአቸው ጂራልድ የሚፈጥሀ እንጂ የማይናነስ ውሻ መሆኑን ደርሰውበታል። ስለዚህ ምንም ሕሊናዊ ዳኝነት ሳያነሱ አይን ያወጣ ጥቅም ያወስዱበታል። እንደአገሩ ልማድ ከሆነ ባሪያዎች ለደቡቡ ክፍል ይሸጣሉ፣ በአ ለንታ ጆርባቸው አስኪለጥ ይገረፋሉ። እዚህ ታራ ውስጥ ከጂራልድ ቤት ግን አንድም ባሪያ ተሸጦ እያወቅም። አለንታም ቢሆን በሠ ራተኛ ጀርባ ላይ ያረፈው አንዲት ቀን ብቻ ነው። እሱም ጂራልድ ቁጥጋ ሙሉ አደን የሞላበት ፈረስ ሳይታጠብና ሳይመ ገብ በመቅረቱ ነበር። የጂራልድ አብተሞይ ጓይኖች የጉረቤቶቹ ቤቶች እንዴት በሥነ ሥርዓት እንደሚያዙ ተመለከቱ። እነዚያ ሰለሳላ ፀጉር ያላቸው ባለሰፉ ቡሩ ቀማስ ሚስቶቻቸው እንዴት አሽከሮቻቸውን ሰጥ ለጥ አድርገው እንደሚገዙ አስተዋለ። እነዚህ ሴቶች ጉሀ ሲቀድ ጀምረው ማታ ሙሾቅት ድረስ እንዴ ማደቤት፣ እንዴ የልጅ መጣዙቶች ጋ፣ ሌላ ጊዜ ልብስ ስፌቱን፣ ደሞ ልብስ አጠባው ቦታ ሲሉ ያለእረፍት ከመቆጣጠር ሥራ ጋር ታስረው እንደ ሚውሉ ምንም አያውቅም ነበር። እሱ የዚህን ሁሉ ልፋት መል ካም ሠጠሩን ብቻ ስለሚያይ በጣም ይደነቃል።

የሚስት አስፈላጊነት በጣም ጎልቶ የታየው አንድ ቀን ወደ ኸሎት ለመሔድ ሲለባበስ ነው። ሠራተኛዋ እንዳይሆን አድርጋ አጨማዳ ተከሳ ያዘጋጀቸውን ሸሚዝ ፖርክ ይዞ ሲመጣ፣ እንኳን ጂራልድ የመጨረሻ ገቅተኛው ሎሌው የማይለበሰው ዓይነት ሆነ። "ጌታዬ ጂራልድ" አለ ፖርክ፣ ጂራልድ መናደዱን እያየ በታማኝነት እንደበት። "እርሶ ሚስት ያስፈልግዎታል። በርከታ ኤማርሃች ያሏት የቤት አመቤት ታስፈልግዎታለች።" "ጂራልድ ፖርክን ስለድፍረቱ እና ለለአፍ አልፈቱ ይቅጣ ይገስጸው እንጂ አውነቱን እንደ ነገረው በልቡ ታውቆታል። ሚስት ይፈልጋል። ልጆችም መውለድ አለበት። ይህን አሁን ካላደረገው ደግሞ ከአሁን ወዲያ በጣም ይረፍዳል።

@OLDBOOKSPDF

አይሆንም ። ግን ሚስት ከየት ይመጣል ። መጭም ጐረቤቱ አቶ ካልሸርት እንዳደረገውና ያቺን መከኗን የቤት እመቤት ያንኪ ሚስት ብሎ እንዳስቀመጠው ጉትጉ አያገባም ። እሱ የሚፈልጋት ሚስት ዘሯ ዘር ማንዘሯ ጨዋና የተከበረ መሆን አለባት ። እንደወይዘሮ ዊክስ ያለች ከሩ ፡ ማርማ ሞገስ ያላት ቤት ንብረቷን በወጉ የም ታስተዳድር ሴት ወይዘሮ ናት አቃራ የምትበጃት ።

ዳሩ ግን በዚህ መንደር ሰምች ዘንድ ትዳር በመያዝ ረገድ ለጂራልድ ሁለት ዋና ዋና ችግሮች አሉበት ። የመጀመሪያው ሴት ዳር የምትሆን ምራቷን የቁለች ልጅገረድ አለመኖሯ ነው ። ሁለ ተኛው ደግሞ ምንም እንኳን ጂራልድ በዚህ መንደር ለአሥር ዓመት ያህል የኖረ ሰው ቢሆንም "ሳገሩ ባዳ ሰሰው እንግዳ" የሆነ የውጭ አገር ዜጋ ነው ። ስለእሱ ቤተሰብና ስለትውልዱ የሚ ያውቅ ማንም ሰው የለም ። ምንም እንኳ የድጋማው ጆርጂያ ሰምች እንደዳር አገሩ መሳፍንት አልደፈርም ባይነትና ግትርነት እጅግ ባያጠቃቸው ፡ ማንም ቤቱ ሰብ ስለአያት ቅድመአያቱ ምንም ለማይ ታወቅ ወንድ ፡ ሴት ልጁን አይሰጥም ፡ አይድርም ።

እንዚህ የመንደሩ ሰምች ምንም ያህል አብረውት አደን ቢውሉ ምንም ያህል አብረው ቢጠጡና የፖለቲካ ውይይትም አብረውት ቢወያዩ እንዲሁም ከለባቸው ቢወዱት ሴት ልጃቸውን ግን አማ ብለው የሚለጡ በጭራሽ እንደሌለ ጂራልድ ይታወቅዋል ። በዛ ላይ እሱ ልጁን ለጂራልድ እንሆራ አልድርም አለ ፡ እገሌ ሴት ልጁን ለጂራልድ እንሆራ እንደማይሰዋ ጥናገረ የሚል ሐሜታ በተ በሳበት በተጠማበት ቦታ ሁሉ እንዲወራ አይፈለግም ። ጂራልድ በም ንም ነገር ከጐረቤቶቹ እንዲያንስ አይፈልግም ። ባገሩ ሰው ባህል መሠረት ማንም ሴት ልጁን የሚድርለት ሰው በደቡብ ማዛት ከዐያ ሁለት ዓመት በላይ የኖረ ፡ መሬቱ ያለውና ብዙ ባሪያዎች የሚያዝ እንዲሁም ጊዜው የሚፈቅደው የጨዋ ልጅ ሥነ ምግባር ያለው መሆን አለበት ።

"ጄንልኝ ፈረሴን ። ወደ ሳቫና እንሒዳለን ።" አለው ለፖርክ "ደሞ አንድ ጊዜ እንኳ "እምነት" ዝባዝንኬ እያልክ ስታወራ አሰ ማህና መልሺ ነው የምሸጥህ ። እኔ ማለት ያለብኝን ነገር እንድት ናገር አልፈልግም ።"

ጀምስና አንድሪው በዚህ ጉዳይ ላይ ምክር ሊሰጡት ይችላሉ ፡ ደሞም ከነሱ የጥንት ወዳጅት ሴት ልጅት ማህል ጥሩ ሚስት ሊያገኝ ይችላል ። ለጥሩ ባልነትም ተቀባይነት ያገኛል ። ጀምስና አን ድሪው ግን ታሪኩን በትእግሥት ካዳመጡ በኋላ ይሄን ያህልም

@OLDBOOKSPDF

አሳደፋፈራትም ። እነሱ ገና ወደ አሜሪካ ሲመጡ ሲሉ ያገቡ በመሆ ናቸው ሳቫና ውስጥ ምንም ያፈሩት ዘመድ የለም ። የጥንት ወዳ ጆቻቸውም ሴት ልጆች ቀደም ብለው ያገቡና የራሳቸውን ልጆች የሚያሳድጉ ናቸው ።

"እንተክ ሀብታም አይደለህም ። ደሞም በጣም ትልቅ ቤተሰብ የለህም ።" አለ ጀምስ ።

"ገንዘብ አማኝኾለሁ ። ቤተሰብም ቢሆን ወደፊት ትልቅ ቤተ ሰብ አፈራለሁ ። ደሞ ማንነም ወፍ ዘራሽ ሴት አላገባም"

"እ በጣም ክፍ ክፍ ያረክ መሰለኝ አራስሆን" አለ አንድሪው በደረቱ ። ያም ሆኖ ስጂራልድ ብዙ መልካም ነገር አድርገውለታል ። ጀምስና አንድሪው ሽማግሌ ሰዎች ናቸው ። ሳቫና ውስጥም በሀሰት እግራቸው ሲመቆም ችለዋል ። ብዙ ጓደኞችም አሉዋቸው ። ለአንድ ወር ያህል በየጓደኞቻቸው ቤት እያኮሩት አረት ላይ ተጣጉ ፡ ዳንስ ላይ ታዩ ፡ ሽርሽርም ሄዱ ።

"አይኔን የጣልኩባት አንዲት ሴት ብቻ ናት" አለ ጂራልድ በመጨረሻ ። "እኔ ታራን ሳልረግዋ በፊት የተወለደች ። "

"ማናት ይቺ እይገሀን የጣልክባት ?"

"ወይዘሪት ኤለን ሮቢላንድ" አለ ጂራልድ ። ሲናገር ትንሽ አፈር እንደማለት ብሎ ። እንዚያ የኤለን ሮቢላንድ ገርመም እድር ገው የሚያዩ ጥቂቱር ሳይኖች ትዝ ሲሉትና ምን ያህል ልቡን እንዳ ጠፉት አስታውሶ አሁን "አይኔን የጣልኩባት" ማለቱ አሳፍሮታል ። የአሥራ አምስት ዓመት ልጃገረድ ሳይ ሲታይ በጣም እንግዳ የሆነ ብዙ ፀባይ ቢታይባትም እሱን ግን ደም ግባቷ አሸንፎታል ። በዛ ላይ አንድ ፀጉት የሚዘራ የሚመስል የተስፋ መቁረጥ ስሜት ፊቷ ላይ ስለሚያንጎበጎብ ልቡን ነካው ። ይህ ስሜት በዓለም ላይ ከማንም ሰው ጋር ሲቀመጥ አድርጎት የማያውቀውን በጣም ጨዋ ሆኖ እንዲቀመጥ አድርጎታል ።

"እንዴ!አባቷ አትሆንም እንዴ ፡ ልጅህን !"

"እኔ ገና የመጀመሪያዬ እኮ ነው ፡" አለና ጮኽ ጂራልድ በነ ገሩ ተናዶ ። ጀምስ ቀስ ብሎ በእርጋታ መናገር ጀመረ ።

"ጂሪ" አለ ጂራልድን አቆላምጦ "ጂሪ በሳቫና ምድር አንተ ፍላጎቱ ይኑርህ እንጂ አማርጠህ ለማግባት ትችላለህ ። ይቺ ግን አባቷ እንደምታውቀው የሮቢላንድ ዘር ናቸው ። ዘር ነገዳቸውን እስ

@OLDBOOKSPDF

ከትውልድ መጀመሪያ የሚቆጥሩ ። ፈረንሳዮችኮ ከራታቸው እፍን ጫቸው ድረስ ነው ። እናቷም - እግዚሀር ነፍሷን ይማረው- በጣም ታላቅ ሴት ነበረች"

"እኔ ግዴለኝም ባክህ ስለሱ" አለ ጂራልድ ቸግ ብሎ ። "በዛ ላይ እናቷ ሞታለች ። ሽማግሌው አባቷ ሮቢላንድም ይወዱኛል ። "

"እንደማንም ሰውነትህ ሊወዱህ ይችላሉ ።አማች ሁኑኝ ስትል ግን የሚወዱህ አይመስለኝም ።""ለማንኛውም ልጅቷ እራሷ አታገባም" አለ አንድሪው ማህል ጥልቅ ብሎ ።"ሰራሷ አንድ ዓመት መሉ ከዛ ከድኩላው ያክስቷ ልጅ ከፈሊፕ ሮቢላንድ ጋር ጥፍ ያለ ፍቅር ይዟት ቤተሰብ በመሉ እንድትተወው ነጋ ጠባ ሲወተውታት አሻፈረኝ ያለች ናት ።"

"እሱማ ከወር በፊት ወደ ሉዚያና ሄዷል"አለ ጂራልድ ።

"እንዴት አወቅህ ?"

"እውቃለሁ" አለና መለስ ጂራልድ ።ይሀን በጣም ጠቃሚ ወሬ ፖርክ እንዳመጣሰት ለመሸሸግ ሳይጨነቅ ። ፖርክ እንዳመጣው ወሬ ቤተሰብ በጣም በአስቸኳይ ፊሊፕን ስለፈለገው ወደ ምዕራብ ሄዷል ።"ደሞምኮ አሷም ብትሆን ይህን ያህል እስክማትረሳው ድረስ ያፈቀረችው አይመስለኝም ።አሥራ አምስት አመትኮ ጥቅርን በደ ንብ ለማወቅ ግና ሰጋ ፅድሚ ነው ። "

"ላንተ ከሚድሯት መቼም ለዚያ ለድኩላው ያክስቷ ልጅ ቢለ ጧት ይመርጣሉ ።"

እንዲህ በመግት ተከርሞ የፒየር ሮቢላንድ ልጅ ድንኩን የአየ ርላንድ ተወላጅ ከደጋው አገር ልታገባ መሆኑ ሲነገር ጅምስና አን ድሪው በጣም ገረማቸው ። ድፍን ሳቫና በየቤቱ በሩን ዘግቶ አማ ። አንሸካሸከ ። ተቸ ።ወደምዕራብ የሄደው ፊሊፕ ሮቢላንድ ምን ይው ጠው ይሆን እየተባለ መጨረሻው ተናፈቀ ። ሹክሹክታውና ሐሜ ታው ግን ምንም ምላሽ አላገኘም ። ከሮቢላንድ ሀር ሁሉ እንክን የለሽ የምትባለው ውቧ ኤለን ይሀን ጨክታም ግምባ ፊት ቁመቱ ጀሮዋጋ እንኳ የማይደርስ ድንክ እንዴት ልታገባ እንደቻለች ለድ ፍን አገር ምስጢር ሆኗል ።

ጂራልድ እራሱም ቢሆን እንዴት ሊሆን እንደቻለ በጭራሽ አያውቅም ።እሱ የሚያውቀው ነገር ቢኖር አንድ ተዓምር መፈጠ ሩን ብቻ ነው ።ያቺ በጣም ቀይ ፡ነገር ግን በጣም ረጋ ያለች ኤለን

@OLDBOOKSPDF

ጥሳሱን አጅጥን እነጥጅ ሳያ ጣል አድርጎ "እሺ ጂራልድ አገባለሁ" ስትለው በሕይወቱ አመጀመሪያ ጊዜ በማም ጨካ በማም ሚምት ሆኖ ወጥ አለ ።

የርዘለንድ ዘሮች በጠቅላላ መልሱን በዘራል ያመቱት እንጂ ነጥሩ ሁሉ የዘራ መብረት ሆኖባቸው አመጓቸው ሁን ብሏል ። ታሪ ክን በሙሉ የሚያውቁት አለንና ምጣኒታ ሚሚ ብቻ ናቸው ።አለን በመጨረሻ ምሬት እንደሚያስቅስ ጉንሽ ልጅ ሽሊቱን ሙሉ ስት ሰት ብላ ስታለስበስ አደራ ጠጥት ነው በተሳዩ ሳያ መስና የተነሳ ችው ።ግሳዩ እንደዘህ ነው ።ማማ የኤለን ስም ያስበት አንድ የተጠ ቀለለ ጉበር አምጥታ ነበር ። የአጅ ሥራራ እንግዛ ነው ። ከጂው አረባ ያንቴ የተሳበ ነው ያሰለ ።በራቃ አንጅ ጽሕፈት ቤዴሊፕ ሮዘለንድ የጥፃራ ኦራት ያብዝዘምጭ ከአንድ በጀመአርሳይንስ ዛስ የተጣፈ አሥር ያብዛቪ ጋር አምጥታ እያሳተሰቸ ጥቅሉን አደረጊ ሕስተምጣ ሰት ነበር ።ሞቱስ ያብዝዘ አንድ በጥ ቢት ሙሳው በተነሳ አምጣነር ሰፀብ የሞተመን የዘጸጅሞን የፈሲን ሮዘለንድን ሞት መርዶ ያዘለ ነበር ።" እነሱ ናቸው ። እነሱ ናቸው ተጠያቂ ። አባስና ፓውሊን እንዲሁም እማማ ኦላሊ ናቸው የጣቃት ። እነሱ ናቸው ያስዘዴት ። የተረዛመ ናቸው ።በጣም ነጠ የጠመድኳቸው ።ሠልቶኛ ዓይናቸውን አላያም ።ብታ እሄዳለሁ ።አነር ጥቹ ሕዘበልሳለሁ ።ሁለተኛ እንዳሴያቸው ድራሼ ያጠፉል ።ምሄንን ከተማ ወይም ጥቅረኛዬን የሚያስታውስ ሻነ ማንንም ሰው የማሳጀብት በታ ንለጀሳለሁ"

ማሚ ከኤለን ጋር አብራ ስታሰቅስ ፡አብራ ስታነብ ከሞላ ጉደል ለሊቱን ካሳለፉት በኋላ በመጨረሻ ፡"የለም የኔ መርት እንደሁስ ማድ ረግ አትችያም"

"አደርገዋለሁ ። እሱት በማም ያማ ፡ በማም ፋብሩህ ልጅ ነበር ። አደር ገዋለሁ ። ካልሠን ግን መጀ ቻርልስተን ሄጀ ባዳም እገባለሁ ።"

ያህ የጓያም ጨማበት ጥለጉት ነው በመጨረሻ የሸማግሌው ንና ቅስማቸው ተሰብሮ የተመመጨውን ያባጀን የጢኖር ሮበለንድን ልብ ያሸነፈው ። ምንም እንኳ የነዩሲስ ዕምንት ተዛታይ ቢሆኑ ሠሳ ኔያቸው መልፈት የማይል ግትርና አፈንጋጭ ካዘን ናቸው ። ስለሆነም ገዳም ጎብታ ከምትመኑበስ ይልቅ ጂራልድ አ ሃራን ብታማባ ይሻ ላል ብለው አመኑ ። ምንም በሆንኑ የቤተሰብ ማጣቱ ነገር ነው እንጂ ከሱ ጋር በግል ምንም አያንት ጥላቻ የላቸውም ።በዘህ ዓያነት ኤለን በሮበለንድ ስም መጠራታ ተርጮ በሳኋ ዘሮች የቤተሰብ ስም በአ ገራ ልትጠራ ፡ ሳሽናን ይማማ ሳታይ ፈቃን አሠራ ጀርባዋን ሰጥታ ፡

@OLDBOOKSPDF

ማማንና ሃያ የቤት ኔግሮዎችን አስከትላ መህከለኛ ዕድሜ ካለው ባሏ ከጂራልድ አሳራ ጋር ወደ ታራ ሄደች ። ታራ ገባች ።

በዓመታቸው የመጀመሪያዋን ልጃቸውን ወለዱ ። ስሟንም በጂራልድ እናት ስም ስየሚት ። ኪቲ እስካርሌት ተባለች ። ጂራልድ ወንድ ልጅ ይፈልግ ስለነበር ቅር ቢሰኝም በትንሿ ባለሐር ፀጉር ሴት ልጁ ተደስቶ ለታራ ባሪያዎቹ በሙሉ ራም ለመጋበዝና ራሱም የደስ ደሰኝ ጥምብዝ ብሎ ስመስከር ወደኋላ አላለም ።

ምንም እንኳ ኤለን ቸኩላ ወስና አሱን ማግባትዋ የሚዐዕታት ቢሆን ማንም የሚያውቅባት የለም ።ጂራልድማ እንኳን ሊያውቅ አይኗን ባያት ቁጥር በኩራት ተነሳፍቶ ሊፈነዳ ይደርሳል ።ያቺን ጨዋ የባሀር ዳርቻ ከተማ ሳቫናንና ከሱዋጋር የተያያዘውን ትዝታ ወደኋላዋ ጥላ ወደታራ መንደር ከደረሰች ጊዜ ወዲህ ሰሜን ጆርጂያ የኤለን ቤት ሆናለች ።

የአባቷን ቤት ስዘለዓለም ጥላ ሙዋታለች ። የአባቷ ቤት ቆንጆ ቤት ነው ። የግድግዳው መክመሮች መት መታቸውን ጠብቀውና ለስለስ ብለው እንደሴት ቅርፀ ሰውነት የተስተካከሉ ናቸው ። ቤቱ ሙሉ ቅዝፈያ ሳይ ያሰ መርከብ ይመስላል ።ጠመዝማዛ እንደአም ባር የሚለሰልሱ መደዳዎቻች ያጌዋቸው ደረጃዎች በኩራት ከመ ሬት ወደ ላይ ብድግ ከሚሉት በፈረንሳይ ቅኝ ገዥዎች ቤት አሠ ራር ዘዴ ከተሠሩት ሐምራዊ ግድግዳዎች ጋር ይዋሀዳሉ ። ደብዘዝ ያለ ብዙ ብር የፈሰሰበት ሥርማ ምንስ ያለው ነገር ግን ካገር የተነ ጠለ — ከመንደር የራቀ ቤት ነው ።

ኤለን ያንን ባለግርማ ሞገስ መኖሪያ ቤት ብቻ ሳይሆን ከጀር ባው ያለውን ስልጣኔ ሙምር ጥላ መጥታ አሁን የተቀመጠችበት ቦታ አንድ ከፍለ ዓለም አቋርጣ የመጣች ያህል እንግዳና የተለየ አለም ነው ።

ይሄ ሰሜን ጆርጂያ በጣም ጠንካራና ብርቱ ሰዎች የያዙት ክር ካሳ ቦታ ነው ።ሽቅብ ወደ ኮረብታው ሲል ሰማያዊ ጠርዝ ካላቸው ተራሮች ግርጌ ጥቂቱር ድንጋይ አፍጦ በላያቸው ላይ የሚታይ ቀያይ ኮረብታማ መሬቶች ዙሪያ ገባውን ይታዩዋታል ። በባሀር ዳርቻ ያደ ገች በመሆንዋ አሁን የምታየው ሁሉ ገና ጥሬና ድንግል መስሎ ታያት ። እሷ የለመደችው ፀጥታ የዋጣቸውን የደሴት ጫካዎችን ውበት ነው ። እሷ የለመደችው በግራጫ የባሀር ዕፅዋትና በአረንጓዴ ሐረግ የተተበተበውን ዛፎች ውበት ነው ። እሷ የለመደችው ኂ ብሎ የተኛ ውን ያ ነጭ የባሀር ዳር አሸዋ ቡቲምር ዛፍ እንደታጀበ በክፈል

@OLDBOOKSPDF

ትሮፒካዊ የፀሀይ ሙቅት ሥር አምሮ ሲታይ የሚሰጠውን ውበት ነው ። ያሄ አሁን ያለችበት ቦታ የክረምቱን ቁርና የበጋውን ታጠሰ ሲያፈራርቅ የቆየ ነው ። በሰምቹ ውስጥም አንዳች ጥንካሬና ጉልበት ይነበብባቸዋል ። ትሁትና ሩህሩህ ፡ ተጫዋችና ሲጋስ ፡ እንዲሁም በመልካም ሥነ ምግባር የታነፁ ናቸው ። ነገር ግን ንፃይለ ኛነት ፡ የጉልማሳነት ችኩላና ዶሎ የመቆጣት ባህሪ አላቸው ። ጥሳቸው የመጣችው የባህር ዳርቻ ሰዎች ማናቸውንም ጉዳያቸውን ፍልሚያና መርኃ-ቸውንም ሲምር ምንም ሳያጨነቁ ሊፈጽሙ እንደሚችሉ በግልፅ የሚኮሩ ናቸው ። እነዚህ የሰሜን ጅርጂያ ሰዎች ግን አመፀኞች ናቸው ። ጉዳያቸውን ሁሉ በንይል የማስፈጸም ዓመል አለባቸው ። በዳርቻው አገር ሕይወት በሰላል ። ጭምር:ል ። እዚህ ሕይወት ገና ሲጋ ፡ ገና ልጅ ገና በበሰት የተጦላና አዲስ ነው ።

ኤለን ሳቫና የምታውቃቸው ሰዎች ሁሉ ካንድ መንገ እንደተ ጨሰሩ ሁሉ ባንድ ፋብሪካ እንደተመረቱ ሁሉ ባህላቸውና አመለ ካከታቸው በጣም የተመሳሰለ ነው ። እዚህ ግን የተለያዩ ሰዎች ተከ ማችተው ይኖራሉ ። ሰሜን ጅርጂያ ውስጥ የሰፈሩት ሰዎች ከተለ ያየ ቦታ የመጡ ናቸው ። ከሌሎቹ የጅርጂያ ከተሞች ፡ ከካርለይና ከቨርጂንያ ፡ ከአውሮፓና ከሰሜን መጥተው የከተሙ ናቸው ። አንዳ ንዶቹ እንደጂራልድ አዱኛ ሊያፈሩ የመጡ እንግዳና የውጭ አገር ሰዎች ናቸው ። አንዳንዶቹ ደግሞ እንደ ኤለን ያሉ ከደሀና ቤተሰብ ተመልደው በትውልድ መንደራቸው ያለው ሕይወት ሰል ችቷቸውና አስጠልቷቸው የሚሳሳሙትም ዓይነት አልሆን ብሏቸው ወደራቅ አገር ተሰደው መጠለያና መኖሪያ ያበጁ ናቸው ። አብዛ ኞቹ ግን እንዲሁ ያለ ምክንያት ከጥንት አባቶቻቸው ሲወርድ ሲዋ ረድ በመጣና ከሕይወታቸው በተሞሃደ ከቦታ ቦታ የመዘዋወር አረፍት የለሽ ደማቸው ስበብ የመጡ ናቸው ።

እነዚህ የተለያየ የአስተዳደግ መሠረት ያላቸውና ከተለያየ ቦታ መጥተው አንድ ላይ የተከማቹ ሰዎች ፡ የመንደሩን አኗኗር እጅግ የተመሰቃቀለ ስላደረጉት ለኤለን እንግዳ ነገር ሆነባት ። ሕይወትን ቅይጥና ሕብረ ቀለም የፈሰሰበት ስላደረጉትም ከቶ ልትለምደው አልተቻላትም ። ያም ሆኖ ግን እንደው በደመ ነፍስ ፡ እንደው በተ ፈጥሮአዊ ቀልብ የዳርቻው አገር ሰዎች የትም ቢሄዱ እንዴት መኖር እንዳለባቸው አውቃለች ። የሰሜን ጅርጂያ ሰዎች ምን ምን እንደሚሠሩ ምንም የሚነገር ነገር አልነበረም ።

የማንኛውንም አካባቢ ጉዳይ አፋጥኖ መፈጸም የደበብ የብል ጽግና ማዕበል ማንቀሳቀሻ ኃይል ነበር ። ዓለም በሙሉ የጥጥ ያለህ

@OLDBOOKSPDF

ይላል። ይሄ የአዲሱ መሬት ድንግል ገላ ደግሞ ገና ያልተነካ፣ ገና ያልተበላ መሙላድ ያልጀመረ ሽለ ሙቅ ማህፀን ነው። ቪ. ያፈራል ፣ ኦልፍ ያዘረዝራል። የመንደሩ ሕይወት፣ የአካባቢው አስት ንፋስ ፣ የሕዝቡ የልብ ትርታ ደም መስሜና ደም መቀበያ በር፣ ጥቃ ነው። ጥቃ ተከላና ጥቃ ለቀማ የቀዩ አፈር ሕይወት መሽከርከሪያዎች ናቸው። ጥምዝ በታሪሱት ትልሞች ጉያ ሐብት ይበቅላል፣ አዳኝ ይለማል። ከዚሁ ጋር አብሮ አብሪትም ይበቅላል፣ አብሪትም ይለማል። አብሪት ከአረንጓዴው ቁጥቋጦ ሳይ ይረገዘና ነጭ በነጭ በሚጥለቀለቀው የጥጥ ጋሻ መሬት ላይ ተወልዶ ይንሰራፋል። በእንደኛው የጥጥ ትውልድ ባለጸጋ የሚሆኑ ከሆነ በሁለተኛው እንዴት ይበለጽጉ እንዲት ይቀጅሩ ይሆን!

ይሄ በነገ ላይ ያለ እርግጠኝነት ፣ ይሄ በነገ ላይ የተጣለ እምነት ስዚህ አካባቢ ሕይወት ጉጉትና ታይለኛ ጥሳትን ወለደለት። ስለዚህ የመንደሩ ሕዝብ ሰአለን የማይገባት ተሰፋ ፣ ስአለን የማ ገባት በኑሮው መርከቱና መደሰት ይታይበታል። እንዲገናኙና እን ዲጫወቱ የሚያደርጋቸውን ያህል ግንዛቤና ባሪያ አላቸው። ስለዚህ ይዝናናሉ፣ ይጫወታሉ። ለዓሣ እርባታ ፣ ለእደን ወይም ለፈረስ ግልቢያ ካሉዋቸው ምንም አጣዳፊ ሥራ ቢሆን ለመተው ወደኋላ አይሉም ። ያስግብዛና ያለፀንስም የሚያጨፍ ሰምንት የላቸውም ።

አለን እንኮኑት ለመሆን በጭራሽ አልቻለችም። አሰን ልቧ እዛው ሳቫና ቀርቷል። አብዛኛውን እሷኑቷን ፣ አብዛኛውን ማንነ ቷን ሳቫና ትታ መጥታለች። ያም ሆኖ ግን ታከብራቸዋለች። አልፎ አልፎም ስውን በሚመስለው ላይሆን በሆነው የመዳኘትና ዋጋ የመሰጠት ባህሪ ስላላቸው እንዲሁም ግልጽና ቀጥተኛ ስለሆነ ታደንቃቸዋለች።

በመንደሩ ፣ ሁሉ ሰው የሚወዳት ፣ ሁሉ ሰው የሚያፈቅራት ውድ ጐረቤት ሆነች። ዜቷን አከባሪና ደግ የቤት እመቤት፣ መል ካም እናትና ወርቅ ሚስትም ሆነች። ያኔ ለቤተክርስቲያን ታው ለው የነበረውን ልባዊነትና ራስን አለመውደድ አሁን ለልጅዋ፣ ለቤት ንብረቷና ከሳቫናና ከጉዞታዋ አላቆ እዚህ ላመጣት ሰው ሰዋችው ይህን ሁሉ ነገር ስታደርግ ደግሞ እንዳችም ጥያቄ አትጠይቅም።

እስካርሌት አንድ ዓመት ሞልቷት በማሚ ማምትም ሚንኛውም ሴት ሕፃን ሊኖራት የሚገባውን የጤናና የጉልበት መብቷን ስት ጐናጸፍ፣ ስሚ ሱዛን ኤሊኖር የተባለችውና በዘልማድ ማን ሱዌለን ብለው የሚጠሯት ሴት ልጅ ተወለደች። ወዲያው እቧን ተከትላ የቤተሰቡ የሰም ባህረ መዝገብ ጸሚት ላይ ካሮሊን አይሪን ተጣለ

@OLDBOOKSPDF

የተመዘገበችው ካሪን ተወለደች። ከዚያ በኋላ ሶስት ወንዶች ልጆች ተወለደው ሶስቱም በእግር ቆሞ መሄድ ሳይጀምሩ ሞቱ። ከቤቱ መቶ ያርድ ርቀት ላይ ከአናታቸው ከተጠላለፉት የአርዘሊባኖስ ዛፎች ግርጌ ከሶስት ድንጋዮች ሥር ተቀበሩ። በየድንጋዮቹም ላይ "ጎንሽ ጀራልድ እዚሬ" ተብሎ ተቀረጸባቸው።

ኤለን፣ ታራ ከመጣችበት ቀን ጀምሮ ትልቅ ለውጥ ታይቷል። ምንም እንኳ የአሥራ አምስት ዓመት ልጅ ብትሆን አንድ ትልቅ እርሻ የሚያስፈልገውን ኃላፊነት የሚሸከም የቤት እመቤት ትከሻ ነበራት። ሴት ልጅ ከትዳር በፊት ቁንጅና፣ ጨዋነት፣ እንደማር የመጣፈጥ፣ የመማረክና የመጊያጊያ ተግባሩዋ ይገላል። ከትዳር በኋላ ግን ነጭም ይሁን ጥቁር፣ መኖም ይሁን ከዚያ በላይ ቤተሰብ የሚስተዳደር ችሎታና ሙያ እንዲኖራት ተደርጋ መሠልጠን አለባት።

ኤለን ማንም የጨዋ ልጅ ሊኖረው በሚገባው መሠረት ይህን ዝግጅት አሟልታ ለትዳር ተመኝታ ያደገች ናት። በዚያ ላይ የመጨረሻዋን ያነገና ተርፋሉ ጌዚ፣ ቀልጣፋና ፈጣን የማድረግ ኃይል ያላት ማሚ ከጐንዋ አለችላት። በሀሀ ዓይነት የጀራልድን ቤት ሥነ ሥርዓት አስያዘችው፣ ከብርን አሳናፀፈችው። መጣ ማረግ አሳያችው። አግረ መንገዱንም የታራ መንደር ከዚህ ቀደም አይታ ሰምታ የማታውቀውን ዓይነት ድምቀትና ቁንጅና ሰጠቻት። ሕንፃው ያለምንም መሐንዲሳዊ ጥሰን ባመችና በተሟላ ሰዓት ትርፍ ቤት እየተጨመረበት ቅጡን አጥቶ የተሠራ ቢሆንም ኤለን ከትርጽ ያጣውን በግርማ ሞገስና በለዛ እንዲሟላ አድርጋ አሳመረችው። የማናቸውም የጀርጂያ ባለሰፊ እርሻ መኖሪያ ቤት የአርዘ ሊባኖስ ዛፎች ከልተተከሱበት ተሟልቶ አይገኝም። የጀራልድንም ቤት እስከ ዋናው መንገድ ድረስ ተሰልፈው ያሳመሩት እነሁ ዛፎች ሲሆኑ ከሌሎቹ ዛፎች ለጋ አረንጓዴ ቀለም ጋር ሲነፃፀር አካባቢውን ጥላማ ያደረገ ተፈጥሯቸው ልዩ ስሜት ይፈጥራል። ከነጩ የሸክላ ግድግዳ ጋር ሲተያዩ የሚያንፀባርቁት የወይን ሐረጎች በረንዳው ላይ እየዳሁ ከበሩ ጐን ከበቀሉት ከባለጥቅል ሐምራዊ ቅጠል ተክሎች ጋር ይቀላቀላሉ። በነጭ አበባ የተሸሞነሞኑት ዛፎች ደግሞ የግቢውን ሜዳ አጥለቅልቀው የበቱን የተዛቡ ቅርፆች ሸፍነዋል።

በበጋው የፀደይ ጊዜ የሚጐርፈው የቢርሙዳ ሣር በመባል የሚታወቀው የግቢው ሣር የፈላ አረንጓዴ ልብሱን ለብሶ የተበጠረ ከምከም መስሎ ሲበቅል ከበቱ ንፎ እንዲጫወቱ የተፈቀደላቸው ዶሮዎች፣ ተርኪኒዎችና ዝዬዎችን ሳይቀር እየሳበ ሲንሰንሰበት ይው

@OLDBOOKSPDF

ላሉ ። የሚያማምሩ አበቦችና ከመሬት ሳይነሱ ለውበታችን ስገዱ የሚሉ እጽዋት በእንቡጥ ገላቸው የተርከፈፈችን አንጋፋ መሪዎች ዋል ። ከቤቱ ጋር የተያያዘና ከበት ወደደጅ ሲወጡ ወይም ከደጅ ወደቤት ሲገቡ ዐሐይ ወይም ዝናብ የሚከላከል ጣራው የተለየ ፣ ሣድማዳ የሌለው ወደግቢው አትክልት የሚዘልቅ ረጅም በረንዳ አለ ። ከዚህ አጠገብ የአትክልቶቹ ጠባቂ ጥቁር ልጅ ሁልጊዜም ይቆማል ። ቡቱቶ ፎጣ በአጁ የያዘ አንድ ትንሽ ጥቁር አግሮ ታራ ደረጃዎች ላይ ቁጭ ብሎ መታየቱ ከታራ ተለይቶ የማይታይ የሁልጊዜ ስዕል ነው ። ሆኖም ሁልጊዜ ይከሩዋል ። ምክንያቱም በፎጣው እያራገበ ዶሮዎቹን እሽ ከማለት በስተቀር በጁ እንኳ እንዲነካቸው ስለማይፈቀድለት ነው ።

ኤለን ታራ ውስጥ እግሩ ሰሚረግጥ ወንድ ባሪያ ከምትሰጣቸው በደርዘን የሚቆጠሩ ሥራዎ ኃላፊነቶች ውስጥ የመጀመሪያ ይሄ ዶሮ ጥበቃ ነው ። በዚህ ሁኔታ አሥር ዓመት ሲሞላቸው ወደ ትልቁ አባባ ሂደው የእርሻ ሥራ ይማራሉ ። ወይ ወደ አቶ አምስ ሄደው የኩርኩርና የአናቢነት ሥራ ይሰለጥናሉ ወይም ደሞ ወደሳም ሐሳፊው ወደፊሊፒ አሰበለዚያም የበቅሎ ኃላፊ መሆነው ልጅ ወደ ኩፊ ይላካሉ ። ስንዚህ ሁሉ ሥራዎች ብቁ ካልሆኑ ግን ወደ ጥጥ እርሻ ተልከው ጥጥ ሲቃሚ ይደረጋሉ ። በኔግሮዎቹ እምነት ወደዚህ ሥራ መሳክ ትልቅ ውርደትና በሕብረተሰቡም ዘንድ ተቀባይነት ማጣት ማለት ነው ።

የኤለን ኑሮ ቀላል አልነበረም ። አስደሳችም አልነበረም ። እርግጥ ኑሮ ቀላል ይሆንልኛል ብላ ጠብቃም አታውቅ ። አስደሳች ካልሆነም የሴቷ ስህተት ፣ የሴቷ ሰንፍና ነው ተብሎ ነው የሚታመነው ። ይሄ የምትኖርበት ዓለም የወንዱ የበላይነት የሚከበርበት የወንዶች ዓለም ነው ብለው ከሚያምኑት ሰዎች ጋር ተሰልፋ ተቀብላዋለች ። የንብረቱ ባለቤት ወንድየው ነው ። የምታስተዳድረው ሴትዮዋ ናት ። የማስተዳደሩን ፣ የአዛዥ ናዛዥነቱን ምስጋናና ስም የሚቀበለው ግን ወንዱ ነው ። ለዚህም ሲታ ብልህነቱን ፣ ቀልጣፋነቱንና አስተሳሰቡን እያደነቀች ትኖራለች ። ወንድየው በትንሽ በትልቁ እንደብራት ይጠይቃል ። ሲታ ግን በምሷ ሰዓት እንኳ ጮሀ እንዳትረብሸው ድምጿን ለማፈን ትጣጣራለች ። ወጎ ዶች ሲናገሩ እንደልባቸው ፣ ሲሰክሩ ጥምብዝ አስኪሉ ነው ። ሴቶቹ ደግሞ ስድቡን ችለው ፣ ለቴቡቱን ከምንም ሳይቆጥሩ ኃይለ ቃል ሳይ ናገሩ እያስተናገዱ ያስተኟቸዋል ። ወንዶች ባለጌዎችና ልቅ አሮች ሴቶቹ ግን ሁልጊዜ ራሀሩህ ፣ ደግ ጨዋና ይቅር ባዮች ናቸው ።

@OLDBOOKSPDF

ኤሰን ለማናቸውም ትልቅ ሴት በሚደረግ እንክብካቤ በጨዋ ደንብ ነው ያደጎችው ። ይህም መልኳና ደም ግባቷ ሳይቀንስ እን ዴት የኑሮን ጫና ለመሸከም እንደምትችል አሰተምሯታል ። ስለዚህም ሶስት ልጆቿ በእሷ እንዲወጡላት ትጥራለች ። በሁለቱ ትናንሽ ሴት ልጆቿ በኩል ይሄ ጥረቷ ተሳክቶላታል ። ሰዊሰን የተባለችው ሁለ ተኛዋ ልጅዋ ቆንጆ ለመሆን በጣም ትጓጓ ስለነበር የእናቷን ትእ ዛዝ ሰጥ ሰጥ ብላ ተቀብላለች ። ካሪን የተባለችውም የመጨረሻ ትንሿ ልጅ ዓይናፋር በመሆንዋ ወደመሬዋት ትሄዳለች ። እስካር ሴት ግን ቁርጥ ባላቷ በጂራልድ ወጥታ ከሴትነቱ ይልቅ ወንዳወ ንድ ፀባይዋ እያመዘነባት ተቸግራለች ። አመሷም ሆነ ጨዋታዋ ከዊክስ ልጆች ወይም ከአሁዮቿ ጋር አይገጥምም ። የምትጫ ወተውም ሆነ የምታወራው ከአግሮዎች ልጆች እና ከጐረቤት ከሚ መጡ ልጆች ጋር ነው ። እንደልጅ ዛፍ ሳይ ትወጣለች ፡ እንደ ልጅ ድንጋይ ትወረውራለች ። ነገሬ ሥራዋ ሁሉ እንደሠራ ልጆችና አር ሻው በታ እንዳሉት የኔም ልጅች ነው ። ማሚ እስካርሌት እንደ ሴት ልጅ ሁሟ እያለች ያልተቋጣችበት ጊዜ የለም ። ብቻ እናት የዋ ኤለን በመታገስና አርቆ እያስተዋለች ነገሩን ችላዋለች ። ልጆች በልጅነታቸው ፅጉ ፅጉም ሆነ ሰርግ ሰርግ እየተጫወቱ የወደ ፊት ፍቅረኞቸውን እንደሚመርጡና ሴት ልጅም የመጀመሪያ ቁማ ባሩዋ ማግባት ነው ብላ ስለምታምን ዝም ትላለች ። ልጅዋ ገና ብዙ ዕድሜ የምትኖር ስለሆነች ወንዶችን የመሣሪኪያ ዘዴዎችን የመማሪያ ጊዜ እንዳላት ይሰማታል ።

ማሚና ኤለን ስለዘህ ጉዳይ ትኩረት መስጠት የጀመሩት አስካ ርሌት እደግ ስትል ነው ። እስካርሌት ይህን ወንዶችን የመማረ ክን ጥበብ ተክናዋለች ። ከእናቷም ሆነ ከሞግዚቷ ጥቂት ነው የጨ መረችበት ። የቀለም ትምህርት ግን እስከዘሀም ናት ። ብዙ አስተ ማሪ ተቀጠረላት ፈትቢል አጠባለው ምርጥ የሴቶች ት/ቤት ውስጥም እንድትገባ ተደረገ ፡ ምን ያደርጋል ቀለም አይዘልታትም ። እንደው እንደነገሩ ሬደል ቅጠረች ይባላል እንጂ አልተሞላላትም ። ለጸንስ ካሷት ግን እንዘርት ናት—ባሳሩ እንደሷ እሚውረገረግ የለም ። ፈገግ ብላ ጉንጯን ስርጉድ ማረግ ማንም አይደርስባት ። እንዴ እር ግብ እማሩዋን እያፈራረቀች ሰዘር ሰነ በማለት ጸሴዋን ከቀሚሷ ጋር እያሞናደለች መዲህ ዘንከት ወዲያ ዠርገድ እያለች ሰው ማለ ሙምጀት ታውቅበታለች ። ቀልጠፍጠፍ ያለች ናት ቀና ብላ ወንዶ ችን ታይና እንጸፈረች ሁሉ ሽፋሽፍቷን እርግብግብ አድርጋ አይኖ ጀን ድፍት ማድረግ ይሆንላታል ። ከዚህ ሁሉ በላይ ግን ምን እንዳሰበችና እንደፈለገች ወንዶች እንዳያውቁባት እንደ ሕፃን

@OLDBOOKSPDF

ልጅ ፊት ባማረ በተጥበ ፊቷ ውስጥ ስሚቷን የመሸሸግን ጥበብ ከሃነቱን ተቆጣጥላለች - ምላሙ ናት ።

ኤለን ለስለስ አርጋና አጣፍጣ እየነገረቻት ፡ ማሚ ደሞ እየደ ጋገመች ሀሳይዋን እየሳገቻት ፡ እስክርሌት ጥሩ ሚስት እንድትሆን ፡ መልካም ሚስት የባል ዘውድ እንድትሆን ፡ የሚያስችላትን ፀባይ ሁሉ ሊያስጨብጧት ይዋራሉ ።

"እየሽ ኩራ ጨመት ማለት አለብሽ ፤ ሴት ልጅ እንዲህ ስት ሆን ነው ደኅ ።" ትሳለች ኤለን "ድግሞም ከነሱ በላይ ማወቅ ሽን ብታውቂም ወንዶች ሲያወሩ ማህል ጥልቅ ብለሽ አውቃለሁ እንዳትይ የኔ እመቤት ። ወንዶች ዓይን አውጣና ፊት ለፊት የሆነች ሴት አይወዱም ። "

ከዚያ ደሞ ማሚ በሰበርባራ ንግግርዋ ማጠናከሪያ ታክል በታለች ። ማሚ ንግግሯ አምብዛም ቁና አይደለም ። " አፍ አው ጥተው አቪ ወይም አምቢ እሚሉ ሴቶች ባል አያገኙም እኮ ፤ " ፈገግ ብላም "ወጣት ሴቶች አንገታቸውን ደፍተው 'አም ምናል ባት ይሆናል' 'አንተ እንጸልከ ይሁን' ማለት አለባቸው" አለች ።

በተቻላቸው ሁሉ ኩራ ሴት ማድረግ የሚገባትን እየተፈራ ረቁ አስረዱዋት ። እስክርሌት ግን እንደው በአኳኋኗ ባለባበስዋና በመልኩዋ ብቻ ኩራ መሆን ነው የተያዘላት ። ይህ ኩራ መሆን ከው ስጥዋ የሚያመነጨው ጥበብ ምን እንደሆነ አልገባትም ። ለምን ማወቅ እንዳለባትም ደሞ አይታያትም ። አምራ ተኳክላ መቅረብ ይበቃታል። ሌላ ምን ያስፈልጋል ። ሴት ልጅን ተወዳጅ የሚያደርጋት አቀራ ረብዋ ነው ። ከፍትፍቱ ፈቱ ነው እኮ ጉዳዩ ። እስክርሌት ደግሞ እም ትፈልገው የስው መውደድን ነው ። ጄራልድ እራሱ እንኳ በአም ስቱም ከተሞች የሚያክሳት የሚወዳደራት እንደሌለ በመጥቀስ ለለሷ ቹንጅና ሁልጊዜ ይናገራል ።

ደግሞም እውነት አለው ። እሷም እራሷ ብትሆን ከሎረሌት ቀርቶ ከሳቫናና ከአትላንታ ድረስ ላማባሽ እያለ የማይጠይቅ ደጅ ጠኚ እንደሌለ አሳምራ ታውቃለች ።

እድሜ ለማሚና ለኤለን በአስራ ስድስት አመቷ ቆንጆ ደማ ምና ያያት የሚደነግጥላት ሽጋ ልጅ ሆናለች ። ብቻ በፈታድዋ አፃ ሪና ግትር ናት ። ያልከላት ካልሆነ ብላ ድርቅ ትላለች ። ቱሎ ኩርፍ ቶሎ ግንፍል ማለት ካባቷ የወረሰችው ፀባይ ነው ።

ከእናቷ የወረሰችው ነገር ቢኖር ግን በትንሹም ቢሆን ራስ ወዳድ አለመሆንንና ሁሉን መቻልን ነው ። ትንሽ ትንሽም ማቁ

@OLDBOOKSPDF

በርበር ይሠንሳታል ። አለን እንዲህ ያለ አባይነት ልጅዋ እንዳለባት አታውቅም ። ታታልሎኛለች ብላ አትጠራጠርም ። አስካርሌት እናቷ ፊት ተበሃ መሠንዋን አታሳያም ። ጨዋ ረጋ ያለች ጥሩ ልጅ ሆና ትተርባለች ። አልበልዚማ የእናቷን ግልምጫም አትችለው ። እንዴ ነልመጥ ስታረጋት ከፈር ነው የምትደባልቃት ።

ማሚ ግን በደንብ አውቃታለች ። ውልፊት አታስደርጋትም ። ዋና ልታሠበረብር ሲሉጣት ትደነብሰች ። ማሚ ከአለን ይልቅ ፀይ ነዋ እንደ ጠር ያመጋል ። ስለዚህ አስካርሌት ማሚን ለደኸም ጊዜ አታሳት አታውቅም ።

እነዚህ መከራዎች ለአስካርሌት በላይ አመልና ውበት ተቆርቁ ረውና አዝነው አልነበረም ፣ የአገሩ ልማድ የደቡብ ሕዝብ ባህል ስለሠጉ ነው ። ያህ ስደቡብ ሴቶች ታሳት ኩራት ነው ። እን ደውም ሂፊልድ በአሷ ላይ የሚያሳየው ግትርና ጨካኝ አመል ነው እንዲቆረቁራቸው ያረጋቸው ። እናንም እንዳንዴ ይሄ ብልሹ ፀባይዋ ባል ከማግኘቷ በፊት ነው እንዳያረጋት በማሰብ ለእሱ ሊነግሩት ይታጣቸዋል ። አስካርሌት አሽሊያን ማግባት እሱን ብቻ ማግባት ነው የምትፈልገው ። የሠንሾውን ሆኖ ወንዶችን የሚስብ መንገድ ሁሉ ታጠቅማ ፣ መከሚጨው ከስፈለገ ተከማጫ ፣ ሙርዶት እንኳ ካስ ፈለገ ተዋርዳ ፣ አይስማሙጡ ተለማምጣም ቢሆን አሽሌይን ማግ ባት ነው የምትፈልገው ። ወንዶች ምን እንዲህ እንደሚያሥርጋቸው አይገባትም ። ብቻ መሣረኪያው መንገድ ይሄው መሆኑን ታውቃ ለች ። ለምን እንዲህ ሲሆን እንደቻለ ምክንያቱን ለማወቅ ፈቃዷ አይደለም ። ለራሷ ፣ እንኳን የሰዎች ጭንቅላት እንዴት እንደሚሠራ ቀርቶ የራሷም ጭንቅላት ነገረ ሥራ አይገባትም ። እሷ የምታው ቀው ይሄ ይሁን ስትል ወንዶችም ይሄ ይሁን እንደሚሉና እን ዳሻት እንደምትሠሯቸው ብቻ ነው ። ልክ እንደ ሂሳብ ስሌት ሕግ አንዴ የተነደፈ ነው ። እሷ ደግሞ ከትምህርቷ ሁሉ በመጠኑም ቢሆን የሚሆናት ሂሳብ ስለነበር አላስቸገራትም ።

ስለ ወንዶች ጭንቅላት የምታውቀው ነገር ቢኖር ስለ ሴቶች ጭንቅላት የምታውቀው ያህ ከዚያ በላም ያነስ ነው ። ምክንያ ቱም ሴቶችን አስከዚህም አትጠጣቸውም ። እስከዛሬ የሴት ጓደኛ ጥሯት አያውቅም ። ስለሴላት ደግሞ ደንታ አይሰጣትም ። ለእሷ ሴቶች ሲባሉ እሠቱም ጭምር ወንዶችን የሚሻሙዋት ባላንጣዎችዋ ናቸው ። ከእናቷ በስተቀር ሁሉንም ሴቶች የምታያቸው በዚህ ዓይን ነው ።

እናቷ አለን አ'ሃራ ልዩ ናት ። አስካርሌት ትድስት ሰማያዊት ብላ—ከሰው ጥሪት ሁሉ የተለየች አድርጋ ነው የምታያት ። ልጅ

@OLDBOOKSPDF

ሆና በእናቷና በድንግል ማርያም መሀከል ልዩነቱ አይታያትም ነበር። አድጋ ትልቅ ከሆነች ወዲያ እንኳን ይሀን ሀሳቧን አልለወጠችም። ለእሷ ኤለን ማሶት ልዩ እንክብካቤ የምታደርግ ምቹ ሰማያዊ ገነት ወይም ብቸኛና ምርጥ እናት ማለት ናት። እሷ የትክክለኛ ፍርድ፣ የዕውነትና ከልብ የመነጨ ጥቅር ማጎደር ናት። ታላቅ እናት! ድንቅ ሴት!

እስካርሌት እናቷን ለመምሰል፣ በእናቷ ለመወጣት ትሻለች። ዳሩ ግን በጣም ችግር ነው። ዛሬ ጊዜ ቆንጆ፣ ትክክለኛ፣ የሰው መውደድ ያለውና፣ ራስ ወዳድ ያልሆነ ሰው፣ አብዛኛውን ጊዜ ጣፋጩንና አስደሳቹን የሕይወትን ክፍል አያገኝም። የሚፈልገውን ቆንጆ፣ የወደደውን ጥቅረኛም ያጣል። ይሀን መሳዩን የሚያስደስት ዓለም ለማጣት ደግሞ ሕይወት እጅጉን አጭር ትሆናለች። አንድ ቀን አሽሌይን ከጣች ወዲያ ትልቅ ሆና ስታረጅና ጊዜ ሲኖራት እንደ እናቷ መሆን ትችል እንደሆን ነው እንጂ አሁን በጭራሽ አትችልም። አስከዛ ድረስ ግን.....

@OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ ፭

የዚያን እለት ማታ እራት ሲበላ አስካርሴት እናቷ ባስመኖሯ በእናቷ ቦታ የቤቱ አዛዥ ናዛዥ የመሆን ሰሜት አእምሮዋ ውስጥ ገባ። ሆኖም የአሽልያና የሚላኒ መታበት ጉብያ እንደታሳት መርዶ ተሰድኗት ሀሳቧም ተልፏም በዚሁ ነገር ላይ አትኩሯል። ተስፋ በቆረጠ መንፈስ የእናቷን ከሰላተሪምት ቤት መመለስ ትጠብቅ ጀመር። እዎ፣ ያለ እናቷ አይሆንላትም። ያለሷ ብቸኝነት የዋጣትና ሰማይ የተደፋባት ይመስላታል። እነዚህ ስላተሪምትና ዕድሜ- አስማቸውን የማያለት በሽታቸው እናቷን ኤለንን ከዚቷ አውጥቶ የመውሰድ መብት ማነው የሰጣቸው፣ ያውም አስካርሴት እንዲህ እንደእህል ውሃ በምትፈልጋት ሰዓት!!

በእራቱ ሰዓት ጊዜ ሁሉ የጂራልድ ጨክት ጅሮዋን ሲበጥ ሰው ትንሽ እስኪቀረው ድረስ ሲያንባርቅባት ቆይቷል። ትእማሥታ ተሟጠጠ ሊያልቅ ምንም አልቀረም። ማምሻውን ምን እይነት መርዶ እንደነገራት እረስቶ የእሱን ትኩስ ዜና— የፎርት ሰምተርን ወሬ ጠረጴዛውን አልፎ አልፎ በጠሜ እየደበደበና እጅቹን በአየር እያ ወናጨፈ በማጠናከር ያወራል። አብዛኛውን ጊዜ በምግብ ሰዓት ጂራልድ እሱ ብቻ በሚሰማበት ሁኔታ ንግግር ማድረግ የሚወድ ቢሆንም እስካርሌት ደግሞ በራሷ ሀሳብ ውስጥ ትሰጥምና አትሰ ማውም። ዛሬ ግን ድምፁ እጅግ ከፍ ከማለቱ የተነሳ፤ የተቻ ላትን ያህል ላለመስማት ብትሞክርና፣ የሱን ጨክት — የኤለንን መመለስ በሚያበስረው የሠረገላ ጉማ ድምጽ —ለመተካት ብት ጣጣር አልሆነላትም።

እርግጥ እንዲህ ልቧን ወየሮ የያዘውን የሀሳብ ጫና ፍርጥ አድርጋ ለኤለን አትነግራትም። ምክንያቱም ኤለን፤ ልጅዋ ከሌላ ሴት ጋር ቀለበት ያሠረ ሰው ማፍቀሯን ብትሰማ፤ በጣም ስለምታዝንና ክፉኛ ስለምትደነግጥ ነው። ያም ሆነ ይህ፤ በሕይወቷ ለመጀመሪያ ጊዜ ያጋጠማትን መሪርና አሳዛኝ ትርኢት ለመሸከም የእናቷን ድጋፍ፣ የእናቷን አይዞሽ ባይ አንደበት ትሻለች። ምንጊዜም ኤለን ጐኗ ካለች ምኞት ይሰማታል። ኤለን ጐኗ ካለች የማይታረም፣ ኤለን ጐኗ ካለች የማይሻሻል ምንም ነገር የለምና እሷ ስትኖር ምኞት ይሰማታል።

@OLDBOOKSPDF

በጐጳጳው የሚሄድ የሠረገላ ጉማ ድምጽ ሰማችና በድንገት ከወንበሯ ብድግ ብላ ተነሳች ። ሃጥም የጮማው ድምጽ ከቤቱ ጓሮ መሄዱን ስታይ ተመልሳ ዘፍ ብላ ተቀመጠች ። አለን አይደሉችም ማለት ነው ። አለን ብትሆን ኖሮ ሠረገላው በፊት ሰፊቱ በር በኩል ይቀም ነበር ። ወዲያው የኔጮሮዎች ድምጽ ከውስጣው የጓሮ ሚዳ እንደተምጉምታ ተሰማ ። ሱዮስ በጣም ቀጭንና የበኮስኪያን ታጭል የመሰለ ሳቅ ተከተለ ። እስክርሴት በመስኮቱ አሻግራ ወደ ውጪ ብትመለከት ፖርከን እየቾው ።

ከጥቂት ጊዜ በፊት እንደወጣ ነው ። አሁን በሹፌ ከፖጄን የተ ሠራ ኾባ መሰል ነገር አቅጣጥሎ ይዚል ። በውጋጋኑ ፣ ከሰረገላው ላይ የሚወርዱት ሰዎች በደንብ ተሰይተው አይታወቁም ። ሳቁና ውካ ታው ከዚያ ከወሰማው አየር ጋር እየተመሰ ወደ ቤት ይገባል ። ደስተኛ ቢጉኛ ፣ ሀሳብና ጭንቅ የሌለበት ሳቅና ሁኳታ ። ለማናቸ ውም ጀሮ ሰስሳሳ የሚባል ነው ። በመዚው ታና ማምት ቢታይ ግን በጣም ሲጢጥ የሚል ቀጭን ድምጽ ነው ። ከዚያም የእግር ኮቴ ደረጀውን ሲወጣ ። ወደ ቤቱ በሚያመራው ኮሪደር አድርጎ ፣ ከም ግብ ቤቱ ፊት ለፊት ከሰው ኦዶራቭ ሲቆም ይሰማል ። ለትንሽ ጊዜ ተንሸካሸከሁና ፖርከ ገባ ። የተሰመጀው ጨጭጋጋ ኩራት የሞላው መልኩ ከፊቱ ላይ በንኖ ጠፍቷል ። ዓይኑን እያጉረጠረጠ ጥርሱን እያፍለቀለቀ ነው የሚታየው ። "ሄታዪ" አለ ቁና ቁና እየተነፈሰ አዲስ ሙሽራ ሚስት የማግኘቱ ደስታ ፊቱን እያበራው ። "አዲስ ሠራትኛ መጥታለኛ ። "

"አዲስ ሴት ሠራተኛ፣ እኔ አዲስ ሠራትኛ አልገባሁም" አለ ጂራልድ እንደጨጣ የታጣው በመምሰል ።

"እንዲ ገዝተዋል እንጂ ጌታዬ፣ ገዝትዋል እንጂ ! ከአርሶ ጋር ለመነጋገር እደጅ እየጠበቀች ነው ። "ብሎ መለሰ ፖርከ ፣ በማ ጉንድቅድቅ የማለትና በስሜት የተሞላ የእጅ ማወናጨፍ እየታየ በት ።

"እሺ አንግዲያው ትጣባ መሽሬሞ" አለ ጂራልድ ። ፖርከ ከመቅጽበት በርሮ ከዊከስ የእርሻ ቦታ ወደ ታራ የመጣች ሚስቱን ለማስገባት ሄደ ። የታራ ቤተሰብአባል ልትሆን ነው ማለት ነው ። የተባለችው ሴት ገባች ። እሷን ተከትላ የአሥራ ሁለት ዓመት ልጅዋ ፣ በጣም ሰፊ ቀሚስ ከመልበሷ የተነሳ እውስጡ የጠፋ በቀች መስላ ፣ እናቷ እግር ሥር ድክ ድክ እያለች ገባች ።

ዴልሲ ረዥምና ቀጥ ያለች ሎጋ ናት ። ፊጋማ የመዳብ ቀለም ያለው ፊቷ ላይ ምንም የሚነበብ መስመር ባለመኖሩ ከሰላሳ እስከ

@OLDBOOKSPDF

ስልሳ ባለው ዕድሜ ክልል ውስጥ ናት ከማለት በቀር ይሄን ያህል ዕድሜ አሳት ብሎ ለመናገር ያስቸግራል ። ከኔግሮነትዋ ይልቅ የሕ ንድ ክልሰ ደሙዋ የበለጠ ጐልቶ ይታይባታል ። የቆዳዋ ቀይነት ፣ የግንባሯ መረዝም ፣ የግንጭኗና የጉንጭ አጥንቶቿ መፍጠዋ ፣ ከወደ ጫፍ ደፍጠጥ ብሎ ከወደማህሉ ወጣ ገባ ያለው አፍንጫዋ ከመ ፍራሞቹ የኔግሮ ክንፈሮቿ ጋር ሲታዩ ፣ ሁለም የሁለት ዘር ቅይጥ፣ የሁለት ገመጣ ቅልትል ልመሆኗ ምስክር ናቸው ። በራሷ የምትሥማ መንና ስትራመድም በኩራት ነው ። በኩራት ከማሚም ትበልጣለች ። የግሚ ኩራት ከኩሮፍ ክልማድ የተገኘ ሲሆን የዚችዋ ግን ከደ መዋ ጋር አብሮ ያለ ፣ አብሯት የተፈጠረ ኩራት ነው ።

ንግግሯም ቢሆን እንደአብዛኛዎቹ ኔግሮዎች የተወሳገደ ሳይሆን ቃላት እየመረጠች በጥንቃቄ የምትናገር ናት ።

"እንደምን አመሻችሁ እመቤቶቹ ። ጌታዬ ስለረበሽኳችሁ ይቅ ርታ ። የመጣሁት እኔንም ልጄንም ስለገዙን ክልብ ለማመስገን ነው ። ብዙ ጊዜ እኔን ብቻ እንጂ ትንሿን ልጄን ፕሪሲን ጨም ረው አይገዙንም ። እርስዎ ግን እሷ እንዳላገኘና እንዳላስብ ብለው ሁለታችንንም ስለገዙን በጣም አመሰግናለሁ ። ይህን ውለታዎትን የማልረሳ መሆኔን እንዲያዩም ሥራዬን በሚገባኖ የምችለውን ያህል በመሥራት አረጋግጥልዎታለሁ ።

"እህም . . እህም . . "አለና ጉሮሮውን አጠራ ። ደግ ሲሠራ እን ጂህ በግልጽ መታየት ስለማይወድ ተደናግጧል ። ዳልስ. ወደ አስካ ርሴት ሦር ብሳ የዓይኖቿን ዳርና ዳር ጨምደድ ጨምደድ አድርጋ ፈገግ ለማለት ሙሞክሯን አሳየች ። "እትዬ አስካርሌት ጌታዬ ፫ራ ልድ እኔን እንዲገዙ ደጋመሽ መጠየቅሽን ፓርክ ነገረኝ ። ስለዚህ ልጄን ፕሪሲን ያንቺ የብቻሽ ገረድ ፣ የብቻሽ ሠራተኛ እንድትሆ ንልሽ ሰጥቼሻለሁ ። "

ወደ ኋላዋ ዘወር ብላ ትንሿን ልጅ አንደርድራ ወደ ፊት አመ ጣቻት ። በጥጣ ትንሽ ጥጦረት ናት ። የወፍ እግር የምታህል ቀጫጭ እግር ነው ያላት ። ከራሷ ሳይ በጥንቃቄ ተጠምጥሞ ቁልቁል ወደ እግሯ የወረደው ሻሽ የተንሠረገገ የወፍ ጭራ መስሏል ። በጣም ጠንቃቃና ያዩትን የማይስቱ የሚመስሉ ዓይኖችና ሆነ ተብሎ አስቀ ያሚ እንዲሆን ያበላሹት የሚመስል አመሰካከት ከፊቷ ላይ ይነ በባል ።

"አመሰግናለሁ ዲልሲ" አለች አስካርሌት ። ሆኖም ስለዚህ ጉዳይ ማማ የምትናገረው ነገር ያለ ይመስለኛል ። ከተወለድክ ጀምሮ ሞግዚቱ እሷ ስለሆነች እንዲህ ያለው ነገር ይመለከታታል ። "

@OLDBOOKSPDF

"ማማ እያረጅች ነው።" አለች ዲልሲ ፣ ማሚን ሊያስቆጣ በሚችል ዝግተኝነት። "እርማጥ ማሚ በጣም ጥሩ ሞግዚት ናት። ነገር ግን አንቺ ወጣት በመሆንሽ ትኩስ ሞግዚት ያስፈልግሻል። የኔዋ ፕሪሲ ሰው/ት እንዲያ አንድ ዓመት በሞግዚትነት ያገለገለች ስለሆነች በጣም ጥሩ ሞግዚት ትሆንሻለች። ፕልፍ መጥለፍም ሆነ ወጥ መስራት ልክ እንደትልልቆቹ ታውቅላጥሩለች።"

ፕሪሲ በእናቷ አድናቆት ተግሳጥ እንደኩራት ተሰማትና ወደ እስክርቤቱ ፈገግ አለች። እስክርቤቱም ሰፈገግታው ምላሽ መስጠት ነበረባትና ፈገግ አለችላት።

"ምን ሳይነት አንድ ፍሬና ተልጣሩ ልጅ ናት።" አለችና በሦዱ ፣ ቆይታ ሮክ በሚለት ፣ "አመሰግናለሁ ዲልሲ ፣ እማማ ወደ ቤት ስትመለስ እሚበጀውን እንመክርሐለን።"

"እግዚአብሔር ይስጥልኝ እመቤቴ ፣ ደህና እደሪ።" አለችና ዲልሲ ፊቷን አዙራ ከትንሿ ልጅዋ ጋር ሄደች። ፖርክ በጥሞና አካሄዷን እያስተዋለ ከለቡ ፈንደሻል። ግቢው ከፍ ብሎ ጀራልድ የተለመደ ንግግሩን ሲጀምር በራሱ በጣም በጥሏቱ የረካ ሲሆን በአደማጮቹ ግን እንዲት ቅንጣት አልተደሰተም። ስለ ወርንቱ በቅርብ መምጣትና ደቡብሽ ላይ ያንኪዎቹ የሚፈጽሙት ዘለፋ እስከመጪ በትእግስት እንደሚጠበቅ የሚሰጠው ዲስኩር—"እም— ልክ ነህ አባባ" እና "የለም አባባ—" የሚሉትን መልሶች በጣም በጥቂቱ ነው የፈጠረው። ካሬን ከትልቁ አምፖል ሥር ካለው በርጩማ ላይ ተቀምጣ ፣ እናቷሪዋ በመሞቱ ምክንያት የለበሰችውን ጥቁር የሀዘን ልብስ አውልቃ ጥላ ፣ በሀሳቧ እራሷን በአዲስ የሙሽራ ልብስ ውስጥ እያየች በደስታ ማዕበል ተውጣ ዕንባዋ ዱብ ዱብ እስኪሚል ድረስ በፍቅር ትጥስህት ውስጥ እንደምትዋኝ ልጃገረድ ሆናለች። ሱዌለን ደግሞ "የተከፋ ያረጋ" እያለች በምትጠራው ያረጀ ላይ እጆቿን አጣፍታና አስሜቷ ውስጥ እየዋኘች ፣ በነገው ግብሯ ሥነሥርዓት ወቅት እስቱዋርት ታርሌትንን ከእሁቷ መንጭታ አላታ፣ እስክርቤት የሌላትን ፣ ወንድ የመማረክ ችሎታ እሷ እንዳላት ለማሳየት በጣም ቸኩላለች። እስክርቤት በበኩሏ ስለ አሽሌይ ጭንቅ ላቷ ውስጥ የተፈጠረውን ሀዘት ታስታምማለች።

ለመሆኑ ፣ እሷ እንዲህ ወሽመጦን የሚቆርጥ ነገር አጋጥሟት በምትጨነቅበት ሰዓት አባቷ ስለ ፎርት ስምተር ማለቂያ የሌለው መሬ የሚያወራባት ለምንድነው፣ እንደተለመደው ፣ ሰው ራሱን በጣም ስለሚወድ የሷን ሥቃይ ከመጨፍም አለመቁጠሩ ፣ ዓለምም እንደወትሮዋ መሆኗን መቀጠሏንና ስለሷ ልብ መቁሰል ቁብ እንደሌላት በለጋ አእምሮዋ አስባ ተበሳጨች።

@OLDBOOKSPDF

ሚንትላቷ ውስጡ ውሽንፍሙ አውሎ ነፋስ (ሳይክሎን) የገባ ያህል ተንጫጫባት። ያም ሆኖ ፡ ያ የተመገበበት ከፍል ምንም ሰውጥ ሳይታይበት እንደወትሮው በፀጥታና በሰላም መቀመጡ የሚገርም ነው።

ከጣዱ የማሆጋኒ ጠረጴዛና የኰኔ ከመዲሞዎች ፡ ሰፊው ከብር የተሰራው ጌጥ ፡ በሚያብረቀርቀው መልል ላይ አዚህም አዚያም እንደ ፈርዮ ጣል ጣል ያለ ትንጠብ ጣቦች ፡ ሁሉም የወትሮ ቦታቸውን ይዘው ተቀምጠዋል — ምንም ነገር እንዳልሆነ ምንም ነገር እንዳል ተፈፀመ ሁሉ። ምኽት የሚሰጥና ደስ የሚል ከፍል ነው። በጨናግው ቀን ቤተሰቡ ሁሉ ከእራት በኋላ በዚህ ከፍል ውስጥ ዝግ ብሎ የሚጫወተውን ጨዋታ በጣም ትወደዋለች። ዛሬ ግን በጎደኛ ስማየት እንኳ ጠልታዋለች። እንደጠም ያሳዝን ፈዝዝት ፈርታ ነው እንጂ ሹልክ ብላ ወጥታ ፡ በፈለጣው አዳራሽ አደርጋ ቁል ቁል ወደ ትንሿ የኤለን ቤሮ ገብታ ፡ አርጊው ሶፋ ላይ ሆና ስቅ ስቅ ብላ ባለቀሰች እንደ ሔዘኑ በመጣላት ነበር።

ከቤቱ ሁሉ እስክርሌት በጣም የምትወደው ከፍል ያ ነው። ኤለን በየጠዋቱ ከራት ሰራት ቁጭ ብላ የአርሻዋን ሂሳብ የምትቆጣጠርበትና የበላይ ጠባቂውን የጆናስ ሚልከርሰንን ሪፖርት የምታጻምጥበት ከፍል ነው። ጀፈልድ በተወሳዋገዩ ወንበር ላይ ተቀምጠ ፡ ዕቶቹ ልጅት ደግሞ ባለሳ ሰመሠገ በጣም ያረጀና ሲቀ መጡባቸው ሲጠጠጠጥ በሚሉት የሶሩ በርጨሜግዎች ላይ ተኮፍሰው ፡ ኤለን የሂሳብ መዝገቡ ላይ ስትጽፍ ሰላም ሥራ እንዳ ይሰሩ በስንፍና ተጕልተው ያዩዋታል። እስክርሌት እዚያ ክፍል ሂዳ ከኤለን ጋር መቀመጥ እንዴት ፈለጋለች። ሚንትላቷን እናቷ ሚን ላይ ጋበል አድርጋ ማልቀስ እንዴት አሰኝቷታል። መቸጉድ ዛሬ እማማ ከነጭራሹ ቤት አትመጣም ማለት ነው እንዴ?

ከጥቂት ጊዜ በኋላ በጠጠራማው ጕዳና ላይ የጕማ ድምጽ ተሰማ። ወዲያው የኤለን ለበላላ ድምጽ የሠረገላውን ነጂ ድምጽ እያሸነፈ. ኤቤቱ ውስጥ በለቀ። ሽንቁጢ ሱብ ረገብ እያለና ፊቷ የድካም መልክና የሐዘን ስሚት ወርሮት ፡ በጥንት ወደ ክፍሉ ስትገባ ፡ እዚያ ያለው ሕዝብ በሙሉ በመረም አሰተዋሳት። የለሚ ሽታ ያለው ሽቶዋ ከቀሚሷ እጥፋት ውስጥ እየተፈለቀቀ የሚወጣ እየመሰለ ቤቱን አወደው። እስክርሌት ይህን መዓዛ ባሸተተች ቁጥር በእእምሮዋ ውስጥ ኤለን ትቀረፅበታለች። ማሚ የታችኛው ከንፈ ሯን ወደ ውጪ ዘርግታ ፡ ሽፍሽፍቶቿን ወደታች ሰብሰብ አድር ጋና የቆሰ ቦርሳዋን በእጅዋ እንጠልጥላ በጥቂት እርምጃዎች ርቀት እመቤቷን ትከተላለች። ማሚ ሰብቻዋ ቃጭተመትመግለች። የምትና

@OLDBOOKSPDF

ገረው ነገር እንዲሰማ ሳይሆን በሚሆነው ሁሉ እንዳልተስማማችና ቅሬታ እንዳላት ለመግለጽ ያህል ብቻ በጥንቃቄ ታጉተመትማለች ።

“ስለዘገየሁ በጣም ይቅርታ አድርጉልኝ ” አለች ኤሰን ፣ የእንግት ልብሷን ከበድ ከበድ ካሉት ትከሻዎቿ አውልቃ ለእስካርሌት እየሰጠች ። አለፍ ስትልም የእስካርሌትን ጉንጮች በእጇዋ ትም ትም አደረገችላት ።

ጂራልድ የሷን መምጣት ሲያይ በተአምር ፉቱ የፈካ ይመስል ባንዳፍታ ፈገግ አለ ።

“ሕጻኒ ተጠመቀች?” አለና ጠየቃት ።

“አዎ ፣ ግን ሞታች ። ምስኪን ነገር ።” አሰኘ ። “እንዲያውም ኤሚም እንዳትሞት ቦግቦበሁ ። ብቻ እሷስ ትተርፋለች ።”

ሴዮቹ ሁሉ በመገረምና ጥያቄ በተሞላ መልክ ወደሷ ዞር አሉ። ጂራልድ እንደፈለሰፉ እንደሚመራመር ዓይነት ተመስጠ ራሱን ነቀነቀ ።

“ወቼም ፤ ስልጅነቷ እንኳ ያለጥርጥር መሞቱ ይሻላታል ፤ ያ ምስኪን አባቷ ግን . . . ”

“መሽቷል ። አሁን ወሎት ብናደርስ ይሻላል ።” አለች ኤሰን በቀስታ አቋርጣው ። ኤሰን ስትናገር ቀስ ከማለቷ የተነሳ እስካርሌት እናቷን በደንብ ባታውቃት ኖሮ ባልሰማቻትም ነበር ።

የኤሚ ስላተሬን ልጅ አባቱ ማን እንደሆነ ለማወቅ ብትጥል እስካርሌት እንዴት ደስ ባላት ነበር ። ሆኖም ይህን ዓይነቱን ወሬ ከእናቷ አሰማለሁ ማለት ከንቱ ድካም ነው ። እስካርሌት የምት ጠረጥረው ጆናስ ዊልከርሰንን ነው ። ምክንያቱም ብዙ ጊዜ አመሻሹ ላይ ከኤሚ ጋር አብረው ሲሄዱ ስላየቻቸው ነው ። ጆናስ ያንኪ ነው ። ወንደላጤም ነው ። የአርሻ የበላይ ጠባቂ ሆኖ የመሥራቱ ነገር ከመንደሩ ሕዝብ ሕይወት ጋር እንዳይገናኝ ላንዴም ለሁሌም አግዶታል ። አጥሮታል ። በመሆኑም ከሱ ጋር የጋብቻ ዝምድና መፍጠር የሚፈልግ አንድም ቢተሰብ የለም ። ከስላተሪዎችና እነሱን ከመሳሰሉ ርካሾች በስተቀር ። ሆኖም ከስላተሪ ቢተሰብ በትምህርት በጣም የላቀ በመሆኑ ፤ ከኤሚ ጋር ብዙ ጊዜ በምሽት ቢነሸራሸርም ሊያገባት እንደማይፈልግ ግልጽ ነው ።

እስካርሌት የማወቅ ጥላቻዋ በጣም ስለጠና ቱና ቱና ተነሬ ስች ። ሁልጊዜ እናቷ በምታውቀው ሁኔታ አንድ ነገር ሲፈጸም

@OLDBOOKSPDF

እስክርሉት ደግሞ ምንም ነገር እንዳልተፈጸመ ሁሉ እንድም የምታ ውቀው ነገር አይኖርም ። ኤለን ፡ እራሷ እንደምትፈልገው ያልተሳካ ጉዳይ ሲገጥማት ፡ እንዳላየ ፡ እንዳልሰማ ማለፍ ልማዷ ነው ። እስክ ርሌትም ይህንን ዘዴ እንድትማርላት ብዙ ጥራለች ። ሆኖም የተሳ ክላት አይመስልም ።

ኤለን መቁጠሪያዋን ከምታዋርበት ከመዳይዋ (ከማስቀመጪ ያው) ውስጥ ለማምጣት ስትሄድ ፡ ማሚ ፍርጥም ብላ መናገር ጀመረች ።

"እሚቴ ፡ ምንም ዓይነት ፀሎት ከማድረስዎ በፊት ራት መብ ላት አለብዎ ። "

"እመለሳለሁ ። ማሚ ። ምንም አልራበኝም ።"

"የለም እኔው ራሴ ነኝ የማዘጋጅልዎ ። በደንብ ይበላሉ አይ ዞም ። " አለች ማሚ በኩራት ኮስተር ብላ ፡ ቁልቁል በአዳራሹ ወደ ማድቤት እየሄደች ። "ፖርክ" አለች በጨኸት እየተጣራች ። "እሳቱን አቀጣጥይው በሳት ሠራተኛዋን ። እሚቴ መጥተዋል ። " በክብደቷ ድም ድም የሚለው ወለል ድምፅ ሲቀንስ ለብቻዋ የምታጉተመትመው ነገር ሁሉ እየጮሳ መጥቶ እያንጓንፉ ቃል ምጣብ ቤት አተሰበሰበው ቤተሰብ ጆሮ ጥልት ይጣል ።

"ለንዚህ ልክስክስ ነፍሶች ምንም ጠላታ ሠሥራት አያስፈል ግም ብዬ ደጋግሚ ተናግሬያለሁ ። ጠላታ አማይከብጻቸው የመጨረሻ ሀፍረተ ቢሶች ናቸው ። እናም እሚቴ ኤለን እንዚህን በእግሮዎች የሚጠበቁ ነፍሶች ፡ ከእግሮዎች ጋር እጅና ዓንት የሆኑ ነፍሶች አድ ናለሁ ብለው ስውነታቸውን ጨረሱ ። እኔ ዳሮውነም ብያለሁ . . . "

ከዛራ በቀር ሌላ ምንም በሌለው መሳላስፈያ ኮሪደር ውስጥ ስታልፍ ድምፄ እየከሰስና እየሞሳ ሄደ ። ማሚ ባስቤቶቿ ነገሯን እንዲረዱላት የምታደርግበት ዘዴና ዘየጎዳዩ ሳይ የሚሰማትን ሀሳብ የምትገልጽበት መሳ አሳት ። አንድ ጥቁር ፡ ሰራሱ የሚያጉተመትመው ውን ነገር ሥራዬ ብሎ ማዳመጥ ስጨዋ ነው ክብሩን የሚያጎድፍ ጉዳይ መሆኑን ታውቃለች ። ይህንን ክብር ለመጠበቅ ሲል በሚቀ ጥለው ክፍል ሆኖ ብትሙህ ፡ ብታንባርቅ እንኳ ቸል ሲሏት እንደ ሚገባም አሳምሯ ታውቃለች ። ይህ ግምቷ አንድም ቀን መሬት ጠብ ብሎ አያውቅም ። ከብዙ ነገር አድኗታል እሷ ያሳሰበቻት ነገር ከውሷ ዝንፍ ብላ አታውቅም ።

ፖርክ ፡ ማሀን ፡ ማንኪያና ያፍ መጥርጊያ ወረቀት ይዞ ወደ ክፍሉ ገባ ። ከሱ ኋላ ኋላ ጃክ የሚባል ትንሽ ጥቁር ልጅ ይከተላል ።

@OLDBOOKSPDF

ጃክ ባንድ እጁ በቾኮላ ናይለን ጃኬቱን እየቆለፈ ፣ በሌላኛው እጁ ርዝመቱ ከራሱ ቁመት የሚበልጥ ፣ ጭራው ከሰሰ ጋዜጣ ወረቀት ተተልትሎ የተሰራና የቀርከሀ እጀታው ከሱ ቁመት ከፍ ያለ የዝምብ ማባረሪያ ይዟል ። የአሥር ዓመት ልጅ ነው ። ኤለን ከወፍ ላባ የተሠራ እንዴት ያለ የዝምብ ማባረሪያ ነበራት ። ሆኖም ልዩ ዝግጅት ባለ ቀን ነው እንጂ ለሌላ ቀን ስለማትጠቀምበትና ፓርክ ፡ ኩኪና ማሚ- የጢኮክ ላባ የመጥፎ ዕድል ምልክት ነው- ብለው ሴት ተቀን ስለጨቀጨቋት ከናካቴው የዝንብ መከላከያ ቀርቷል ።

ኤለን ፡ ጀራልድ ገተት ባደረገላት መቅመጫ ላይ ገና ቁጭ ከማለቷ አራት የተሲያዩ ድምጾች ከየአቅጣጫው ወረዱባት ።

"እማማ ፡ ያዲሱ ቀሚሴ ሄጥ በጣም ላልቷል ። ነገ ማታ በ"አሥራ ሁለቱ ዋርካዎች" የሚጠጉ ቦታ የምለብሰው እሱን ስለሆነ ቶሎ አጥበቀሽ ስፊልኝ ። "

"እማማ ፡ የእስካርሴት ቀሚስ ከኔ ያምራል ። እኔ ወይንጠጅ ቀሚስ አይስማማኝም ። እሷ ግን ወይንጠጅም ያምርባታል ። እሷ ወይን ጠጁን ትልበስና እኔ የኗን አረንጓዴ ልልበስ ። "

"እማማ ፡ እኔ አሁን አሥራ ሰስት ዓመቴ ነው ። ትልቅ ልጅ ነኝ ። ነገ ማታ እማብጥው ቦታ ብሄድ ምን አለበት . . . "

"ዝም አትሉም እናንተ ልጆች ፡ ዛሬ ነማሬያችኋለሁ ኋላ ወይዘሮ ኤለን የማታምኝው ነገር!!ካድ ክልቨርት ዛሬ ጠዋት እት ላንታ ነበረልሽ ፡ እናም ሁላችሁም ወጥ ብላችሁ አደሙሽ ብሎ እንዲህ አለ 'በተገናኛችሁ ቁጥር ያልጠርነት ፡ ያለ ሚሊቪያ ማሰልጠን ፡ ያለ ሠራዊት ማቋቋም ወሬም የላችሁ እንዴ! እዚያ ቻርልስተንም ከእንግዲህ ምንም ዓይነት የያንኪ ስድብና ዘለፋ በትእግሥት ማዳመጥ እንደማይቻል ንበር ሲወራ የነበረው ። ' "

ኤለን የየአቅጣጫው መከባ ግራ እያጋባት በደከመ ፈገግታ ፈካ ብላ እንደማንኛውም ጨዋ ሚስት በመጀመሪያ ልባሷ መልስ ለመስጠት ወደሱ ዘወር አለች ።

"የቻርልስተን ኩሩ ሕዝብ የሚያስበው ያንን ከሆነ ፡ እኛም ሳንውል ሳናድር የነሱን አቋም መያዝ አለብን" አለች ።

በኤለን አስተሳሰብና ዕምነት ከሳቫና በስተቀር ፡ የዚያ ከፍለ ዓለም ኩሩ ደም ባብዛኛው የሚኖረው በዚያች የባህር ወደብ በሆነች ትንሽ ከተማ ነው ። የቻርልስተናውያንም ዕምነት ይሄው ነው ።

@OLDBOOKSPDF

ቀጥላ ለካሪን መልሰ ሰጠች ። "የለም ካሪን እንቺ በሚቀጥለው ዓመት ትሄጃለሽ ። ያኔ የትላልት ሰዎች የግብጥ ልብስ ለብሰሽ ስትሄጂ እንዴት ዓይነት ቆንጆ ልጅ ትሆንልኝ መሰለሽ የኔ ሽጋ፣ ቅር አይበልሽ የኔ ቆንጆ ። ወደሽርሽርና ወዲ ግብጥ ቦታ የሚከደው እኮ አሥራ አራት ዓመት ሲሞላ ነው ።

"የቀሚስ ካፖርትሽን አምጪ እስካርሌት ፣ ከፀሎት በኋላ ጌሙን አስተካክልልሻለሁ ። "

"ሱዌለን ፤ ነገርሽ አላማረኝም የኔ ሽጋ ። እስካርሌት አረንጓዴው እንደሚያምርባት ሁሉ ያንቺም ወይን ጠጅ ቆንጆ ሆኖ ከመልክሽ ጋር ይሄዳል ። ደሞ ለነገ ማታ የኒን የአንገት ሐብል ታጠልቂበታለሽ ። ምኑ ነው የከፋሽ ። "

ሱዌለን ከእናቷ ጀርባ ሆና በድል አድራጊነት እስካርሌትን ታንጓጥጣለች ። እስካርሌት የእናቷን የአንገት ሀብል ልትለምን ስትዘጋጅ ሱዌለን ቀድማ የዕድሉ ባለቤት በመሆኗ ኮራች ። ሆኖም እስካርሌት ለማብሸቅ ያህል ሱዌለን ላይ ምላሷን አወጣችባት ። ሱዌለን በጨቅጫቃነቷና በሁሉን ለኔ ባይነቷ በጣም እንጂት የምታደብን ልጅ ናት ። እንዳወም እንዳንዴ ኤለን ባትገላግላቸው ኖሮ እስካርሌት በቦክስ ጀሮ ማንዴን ልትሰት መታጣቷ አልቀረም ።

"አሁን ፣ አቶ ጄራልድ ፣ ከልቨርት በለቻርልስተና ፍሙያን የተና ገረውን በደንብ ንገረኝ ። "

እስካርሌት ፣ ኤለን ስለመርነትና ስለፖለቲካ ምንም ግድ የሌላት መሆኗንና እንዲህ ያለው ነገርም የወንዶች ጉዳይ እንጂ ሴቶችን ሊጨንቃቸው የማይገባ ነገር ነው ብላ እንደምታምን ታውቃለች ። ሆኖም ለባሏ ደስታ በጣም የምትቀረቅር ሴት በመሆኗ ብቻ ጄራልድ የሚያስደስተውን ወሬ ሊያወራ በጥሞና ታዳምጠዋለች ።

ጄራልድ የመርነቱን ወሬ ሲጎትትን ማሚ እመቤቷ ፊት ወር ቅማ መልክ ያለው ብስኩት ፣ የጾሮ ጥበስ ፣ ቅቤው የሚንጠፈጠፍ ትኩስ ቢጫ ያም በሣህን በሣህን አድርጋ አቀረበች ። ማሚ ያንን ትንሽ ልጅ ቆንጠጥ ስታደርገው የያዘውን የዝንብ ማባረሪያ በኤለን ዙሪያ ያርገበግበው ጀመር ።

ማሚ ከጠረጴዛው ጀርባ ቆማ በሹክ እየሞላ ካሣህን ወደአፍ የሚሄደውን ምግብ ትክ ብላ ስታስተውል ፣ በራሷ ኃይል የኤለንን ጉሮሮ የምታሳልፈውና ትንሽ እንኳ አልገባ ብሎ ቢያንገራግር ልኩን ልታሳየው የተዘጋጀች ትመስላለች ። ኤለን ደስ እያላት በደንብ በላች።

@OLDBOOKSPDF

እስክርሴት ግን አኖቷ ከመደክሚ የኑነሳ የምትበላው ምን እንደ ሆነ እንኳ ለይቃ ለማየት እንዳልቻለች ገብድታል። የማሚ የማይ በጣር ፈት እንድትበላ እንዳደረጋት አውቃለች።

ጀራልድ ፣ ባረያዎችን ነጻ እናወጣለን እያሉ እያውሩ ሆኖም ቀጩ ድንበሩ እንኳ ስለማይሰፋቸው ያንኪዎች ሸፍጥና ሌብነት አልተያየት መሰጠት ሲቀጥል በማህል ኤሲን ተነሳች ።

"በሎት ልናደርስ ነው!" ብሎ ያለፈውን መየቀ ።

"አም ። መሽቷል እኮ ፣ አራት ሰዓት ስትል የጠረጴዛው ሰዓ ትም አራት ለማለልክት ደወለ ። ክረን ቀደም ብላ መተኛት ነበረ ባት ። "ፖርክ ፣ እባክህ ሩፍሱን አቁበኝ ፣ የፀሎት መጽሐፌን ደሞ ማሚ ስጪኝ ።"

በማሚ ጉልህ (ቫክራ) ቡክቡክታ እየቀነጻ ጀክ የዘንብ ማለረ ፊያለውን እንድ ጣማ ጥሎ ማዘኖቹን ማነሳሳት ያዘ ። ማሚ ካሮኒው ከመጪኖ ወለም የኤለንን የተቀሰደደ የፀሎት መጽሐፍ ትፊል ጋለኝ ። ፖርክ በእግር ጣጥቡ በጥንቃቄ እየረገጠ ሄዶ የመንሠለቱን ቀለበት ይዘ በዝግታ ገፍቶ ከፈጸርገው ጠረጴዛው በብርሃን ፍክት ተጥለቀለቀ ። የብርሃኑ ጥላም ትርኢት ላይ አለፈ ። ኤለን ሞሚፈን እስተኬሳ ወጂ መፊት ገቡ ብላ ተንበረከከች ። የተከፈተውን የፀ ሎት መጽሐፍ ወለቡ ላይ በርግታ እጆቿን በጓዮ ጨብጣ ጭና ለፀ ለት ተዘጋጀች ። ጀራልድም እንኑ ተንበረከከ ። እስክፒሴት እና ሴዌለን በጠረጴዛው ፈት ቢፈት የተለመደ በታቸውን ይዘዋል ። ክንለበታቸው በታች ያለውን የቀሚሳቸውን ክፍል እጥፈዋል— የሚቆረቁረው ወለል ላይ ቢጥሙ ህመም እንዳይለማቸው ያደረ ጉት ነው ። በዚህ ፅድሜዋ ለውጎድ እምብዛም ያለደገው ትንሿ ካረን በጠረጴዛው ላይ እንደልብ መንበርከክ ባለመቻሏ እወንበሩ ላይ ተንበርክካ ፊቷን ወደ መጽሓፈያው በማድረግ ትጸልያለች ።

ይህንን ዓይነቱን ፈት አዙሮ መለወይ ትወደዋለች ። ምክን ቱም እንዳንዴ እንቅልፍ ቢመስጓት እንኳ እናቷ እንዳታያት ስለሚ ረዳት ነው ።

የቤቱ አሽከሮችም በየፀክሳቸው በየበሩ ሥር ፀሎት ለማድረስ ለመንበርከክ ተሯሯጡ ። ማሚ ስትንበረከክ ድምጿ እንደማንራት ያህል ይሰማል ። ፖርክ እንደሸምበቆ ቀጥ ብሏል ። ገረዶቹ ሮዘና ቲና ሸማ ቀሚሳቸው ወለሉ ላይ ግራና ቀኝ እስከሚፈስ ድረስ በኩራት ተንበርክከዋል ። ኩኪም ከነጭ ሻሂ ሥር ቢጫ መስለሰች በፀሎት ጊዜ ሁሌ እንቅልፍ የሚያሸንፈው ጆክም ሲያንቀላፉ ማሚ

@OLDBOOKSPDF

እንዳትቆነጥጠው ከሷ በማም ርቆ ተንበርክኳል ። ከነሙት ጌቱቻ ቸው ጋር መፀለይ ከየዕለቱ ታላቅ ከንውኖች አንዱ በመሆኑ ባለ ጥቂቱ ብሌን ዓይናቻቸው በተስፋ በርተዋል ። እርግጥ ከጥንት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው ፣ የሩቅ ምሥራቅ መልክ ያለው የፀሎት ሥነ- ስርዓትና እጅግ በሚስቡና በሚያማምሩ ቃላት የተዋበው የስብከት ሐረግ እምብዛም ባይገባቸውም ለልባቸው የሚሰጣቸው እርካታ አለ ። "እግዚአብሄር በረከትህን ስጠን ፡" "እምላክ ሆይ ምህ ረትህን ሰጠን ።" ሲሉ ሰውነታቸውን ወደ አንድ ወገን ዘመም እያ ደረጉ ነው ።

ኤሰን ዓይኖቿን ጨፍና ፣ ድምጿን አንዴ ከፍ አንዴ ዝቅ ፣ አንዴ ለስለስ አንዴ ወጥ እርጭ እያደረገች ትፀልያለች ። ቤታን ፣ ቤተሰቧንና ኔግሮ አሸከሮቿን እግዚአብሄር እንዲባርክላትና ደስተኛ እንዲያደርግላት ስትማፀን የተቀሩት በሙሉ ሞንቅላታቸውን በዚያ በቢጫው መብራት ውስጥ ጐንበስ አድርገው እሚን ይላሉ ። ታራ ውስጥ ላሉ ሁሉ ላባቷ ፣ ለእናቷ ፣ ለእህቶቿ ፣ ለምቱ ቦስት ልጅ ችዋ እንዲሁም "በዓለም ለሚሰቃዩ ነብሳት ሁሉ" ፀሎት ካደረሰ ችላቸው በኋላ ነው መቋጠሪያዋን በረገሯቸው ጣቶቿ እያሸሸች መቋጠር ጀመረች ። በዝግታ እየተመመ እንደሚመጣ ንፋስ ክነጭና ከጥቁር ጉሮሮዎች የሚወጣው ድምፅም፡ "እመቤታችን ማርያም ሆይ ፣ አንቺ የሞንቅ አማላኟን ፣ ስእሁንም ለዘለዓለምም ስለሀጢ ያታችን አማልጂን ።" ይላል ።

እስካርሌት ፣ ምንም እንኳ ልቧ የቆሰለበትና ፣ ልውጣ ልውጣ ሲል ያፈነችው እንባ ሀሞም ቢሰማት ሁልጊዜ በዚህ የፀሎት ሰዓት እንደሚሆነው ሁሉ ፀጥታና ሰላም መንፈሷን አቅፎታል ። የቀኑ መከፋቷና የነገውም ፍርሃቷ ከከፊል ሰዓት ሂዶ ጥሰቱን ተክቶላታል ። እርግጥ ይህን ስሜት ያመጣላት ልቧን ወደ እግዚአብሔር መመ ሰሏ አይደለም ። ምክንያቱም ሰሏ ሐይማኖት በእፍ ከመነባር የማ ያልፍ የአንባት በላይ ጉዳይ ነው ።

ይልቁንም ወደ ጌታ ዘፋን ፣ ወደ መላእክትና ቅዱሳን በራፍ የዘረውን የእናቷን የረጋ ፊት ስታይና የምታፈቅራቸውን ሁሉ እን ዲባርክ ስትፀልይ ስትሰማ ነው መንፈሷ የተረጋጋው ። ኤሰን ወደ መንግሥተ ሰማይ በታማዘንች ቁጥር እስክርሌት መንግሥተ ሰማይ ያለጥርጥር ይሰማታል ብላ ታምናለች ።

ኤለን ስትጨርስ ፣ በፀሎት ሰዓት መቁጠሪያውን ፈልጎ ማግ ኘት የማይሆንለት ጂራልድ በጣቱ መቁጠር ጀምሯል ። የሱ ድምፅ ከፍ ሲል ስትሰማ እስክርሌት ባንድ ጊዜ ሀሳቧ ብትን አለባት ።

@OLDBOOKSPDF

ሁልጊዜ በፀሎት መጨረሻ ሕሊናዋን መመርመር ፣ በዕለቱ የሠራቻቸውን ጥፋቶች አጢና እግዚአብሔር ይቅር እንዲላትና ብርታቱን እንዲሰጣት መዐልይ እንዳለበት እናቷ ያስተማረቻት ቢሆንም ፣ አሁን እሷ የልቧን ማሰላሰል ብቻ ነው የታያት ።

እናቷ እንዳታያት ፊቷን በታጠፉ እጆቿ አቅፍ ውስጥ ደፍታ ወደ አሽሊይ መሪር ጉዳይ ሀሳቧን አሰማራች ። እስካርሌትን ከልቡ እያፈቀረ ሳለ እንዴት ሚላኒን ለማግባት ያቅዳል ? አሷ እንዴት እንደምታፈቅረው አያወቀ እንዴት ሆነ ብሎ ቅስሟን ለመስበር ይነሳሳል?

ከመቅጽበት ሰማያት ሰንጥቆ እንደተወነጨፈ ተወርዋሪ ኮከብ አንድ ሐሳብ በአእምሮዋ ተፈነጠቀ ።

"አየ ፣ አሽሊይ እኮ እንደማፈቅረው አያውቅም !!" በዚህ ድንገት ደራሽ ሐሳብ ድንጋጤ ገባት ። ቁና ቁና ተነፈሰች ። አዕምሮዋ ለረኽሮምና ትንሩሽ አልላ ለሆነ ጊዜ ሽባ የሆነ ያህል ፀጥ ዝም ብሎ ቆይቶ ወዲያው ሽምጥ ግልቢያውን ወደ ፊት ቀጠለ ።

"እውነት እንዴት ያውቃል ፣ ሁልጊዜ ሲያገኘኝ አንገቷን የደፋች ጭምት ሴት ሆኜ ነው እሚያየኝ ። እማልደፈርና አትን ከኝ ባይ ሆኜ ሲያገኘኝ እንደው እንደማንም ወዳጅ እንኺ ከዚያ ከፍ አድርጌ እንደማላየው አድርጎ ሊገምት ይችላል ። አዎ ፣ ለዚህ ነው በፍፁም የልቡን ነግሮኝ የማያውቀው ፣ ልክ ነው ፣ ቢያፈቅረኝ ኑስፋ ቢስ አፍቃሪ የሚሆን መስሎት ነው ። ለዚህ ነው ሁልጊዜ ሁኔታው . . . . . "

አእምሮዋ በከፍተኛ ፍጥነት ወደጥንቶቹ ቀናት ገሰገሰ ። እነ ዚያ ግራጫ ዓይኖቹ ለወሰጣዊ ስሜቱ መጋረጃ ሆነው በሰፊው ይከፈቱና እርቃናቸውን ሲቀሩ እንግዳ በሆነ ስሜት ተሞልተው ሲያስተውሏት ይዛቸዋለች ።
ከቱውንም በውስጣቸው ስቃይንና ኑስፋ መቁረጥን እንዳዘሉ ትገ ይላታል ።

"ተስፋም የለኝ ብሎ ቅስሙ የተሰበረው ወይ ከብሬንት ወይ ከስቱዋርት አሊያም ከካድ ጋር ፍቅር የያዘኝ መስሎት ይሆናል ። ምናልባትም እኔን የማያገኝ ከሆነ ፣ ሚላኒን አግብቶ ቢተሰቡን ማስ ደሰት የተሻለ አማራጭ ነው ብሎ ገምቶ ይሆናል ። ሆኖም እኔ እንደማፈቅረው አውቆ ቢሆን ኖሮ ግን . . "

ያ ቶሎ ግንፍል ጥንድት የሚለው መንፈሷ ከቅስም መሰበር አዘቅት ወጥቶ ፣ ሽቅብ ወደ ተሳከረ ደስታ ተመነጠቀ ፣ ተስፈንጠረ

@OLDBOOKSPDF

ለአሽሌይ ቸል ማለትና ለእንግዳ ፀባዩ ምክንያት አገኘችለት—የቧን የጥቅር ስሜት ባለማወቁ ነው ይሄው ነው። ብኩንቲ ፍላጎቷን ለማገዝ በጥንት እየሮጠ ያሰበችውን እንድታምን አደረጋት ፣ እምነቷ ደግሞ በፈንታው የገመተችው ነገር ሁሉ እርግጠኛና ዕውን የሆነ ነገር መሆኑን ማስተማመኛ ሰጣት። እንደምታፈቅረው አውቆ ቢሆን ኖሮ ወደፊ ይጣደፍ ነበር። አሁን ማድረግ ያለባት . . .

"ወይኔ !" አለች በከንፈ ሀሳቢ ፣ የተከደኑ ቅንድቦቿን በጣቶቿ የመቆፈር ያህል እያሸች ። "ይህን ነገር እስከዛሬ አለማሰቤ ምን ጅል ነኝ ባካችሁ ! አሁን እንደምንም እንዲያውቅ ማድረግ አለብኝ። እኔ እንደማፈቅረው ካወቀ በጭራሽ እሷን እያገባም እንዴት ብሎ?"

ቀና ስትል ጀራልድ እንደጨረሰና የእናቷ አይኖች እሷ ላይ እንዳረፉ ተገንዘበች። በጥንት የዐሎት መነባንቧን ጀመረችና መቅጠሪያዋን ስታነሳቸለች ፣ ድንጋጤ በወጠረው ስሜት የምታወጣው ጉልህ ድምፅ ፣ ማሚ አይኖችዋን ገልጣ ወደሷ እንድታነጣጥር አስገደዳት። ፀሎቷን እንደጨረሰች ፣ ሰዌለንና ካሪን ግን ገና በዐሎት መጀመራቸው ስለሆነ እእምሮዋ አዲስ ወደ ተወሰደው ሐሳብ እሁንም ተወረወረ . . . . . ።

አሁንም እኮ ገና ነው ! አልረፈደም ! ሰው እንደሆን ማውራት ልማዱ ነው። ባለጉዳዩ ከሰዉኖዋ ሴት ጋር ቀለበት እያሰረ እነሱ ገና ስለሁለቱኖዋ ያወራሉ። የአሽሌይ ቀለበት ማሰር ደማሞ ገና እስካሁን በይፋ አልተገለጸም" ። ለነ ነው በታ ፣ ገና ብዙ ጊዜ አለ !

በአሽሌይና በሜላኒ መካከል ያለው ግንኙነት ፣ እንደው ቃል ከዳን ብቻ ከሆነና ጥሩር ከሰለ ኋት ሥል ከዳነን ሕፍርሶ እስካርሴትን ማግባት ይችል የለም እንዴ ! ያስ ጥርጥር ያደርገዋል።

እስካርሌት እንደምታፈቅረው ካወቀ በቀጥታ ያገባታል። አንድ መንገድ ፈልጋ ይሆኑ እንዲያወቅ ማድረግ አለባት። ደሞ እንድ ዘዴ አታጣምከባ እንግዲህ . . .

እስካርሌት ከነጎደችበት የደስታ ጉዳና ድንጓት ተመንጥቃ ስትወጣ ፣ ለነ የማሳረጊያ ፀሎቷን አልጨረሰችም። እናቷ ይች ልጅ ተበላሸች በሚል ዓይን ታስተውላት ኖሮ ገሊመጠቻት። እስካርሌት ፀሎቷን እንዳገባደደች ዓይኗን ገልጣ በጥያኔት አካባቢውን ማተረች። የተንበረከኩትን ፍጡራን ፣ ጭነዝ ያለውን ለስላሳ የሩሲ ብርሃን ፣ አማሮቃቹ ወዲህ ወዲያ ሲሉ የሚያጠሉትን ጉልህ

@OLDBOOKSPDF

ሞላ ተመለከተች ። ከአንድ ሰዓት በፊት ላይኔ ስትጠላቸው የነበሩት የተስመዱ የቤት ቃሎች በዚችው ቅጽበት ውስጥ የሷን ስሜት ቀልም መረሱና ያ ቤት እንደገና የሚወዷድ ፣ ፍንጀ ማረፊያ ቤታ ሆኖ ታያት ። ይኸን ቅድበትም ሆነ ይህንን ትርኢት አሰክዕድሚ ልኳም አትረሳቸውም!

"ታማኟ ድንግል ማርያም" አለች እናቷ ። መልክ ማርያምን ማንበብ ሲጀምሩ ፣ አስክርሌትም በታላቅነት "ለኛም ፀልይልን" ብላ መሰለች ። ኤለን የጌታ እየሱስን እናት ታሪክ በልሰላሳ ድምጿ ዝማ ብላ ሙተረክ ጀመረች ።

አስክርሌት እንዲህ ያለው ለነሥርዓት በተዳረገ ቁጥር ፣ ከለጅ ንቷ ጀምሮ ከድንግል ማርያም ጉልት እናቷን ኤሰንን የምታደንቅ በት ነበረ ። ሁልጊዜም ለዘለት ዓይኗን ስትጨፍን የኤለን ወደ ሰማይ ያንጋጠጠ ፊት እንጂ የተባረከችው ድንግል ማርያም ፊት በሚራሽ ታይታት አያውቅም ። "ለታመመ ጤንነት" ፣ "የጥበቧ መጣኛ በዛ" "የሐጢያተኞች መጠጊያ" ፣ "ሚስጥራዊዋ ጽጌረዳ" እነዚህ ቃሎች ሁሉ የኤለን ተማባራትና ምልክቶች ስለሆኑ እጅግ በጣም ጠብ ታሉች ነበሩ ። በዘፈው ማታ የፀሎት ሥነ ሥርዓት ላይ ማን የራሷ መንፈስ ሞንቀት ላይ ስለነበር ልስልስ ባለ ድምጽ በለሆ ላስ የሚነግሩት ታሳትና በሹክሹክታ የሚስጡት መልሶች የምታ ጠቀውን ውበት ሁሉ ዘልቀው ስለአገኘቸው ክለመደችው ሁሉ የተለየ ሆንባት ። እናም ክሲኦዊ ሮጥታ በቅጥታ አሽሌይ እቅፍ ውስጥ ልትወድት ትችል ዘንድ ስእማሮጅ መንገድ ስለተከፈተላቸው እማዚአብሔርን ክልብ አመሰገነች ።

"አሜን" ሲባል ሁሉም እንደመጽከም ብሏቸው ሰውነታቸው ዓጉሉ ተነሱ ። ማሚ በቲናና በሮዛ ድጋፍ ተነሳች ። ሃርክ አንድ ረጅም ጫፍ መሰል ነገር በማሽው እሳት ለክሰ ይዞ ፣ ወደ አዳራሹ ሄደ ። ከጠመዝማዛው ደረጀ ፊት ለፊት ምግብ በት ውስጥ ሲገለ ገሉበት ያልቻለ የብፈ ዕቃ በሰፈው ጠፍጣፋ አናቱ ላይ በርክታ ማሾዎችና ፣ ዘየሽማ ማስቀመጫው ላይ የተደረደሩ ሻማዎች ተሰል ፈዋል ።

ሃርክ አንድ ማሾፍ ሶስት ሻማዎች ለኮሰና—ለንጉሥ ና ለንግ ሥት መኝታ ቤት አገልጋይነት የተመደበ የመጀመሪያ ባለሚል በሚ ጥረው ዘቀ መንግሥታዊ የክብርና የጦማ ሞገስ አሳሄድ ዓይነት ብርሃኑን ከራሱ በላይ ከፍ አድርጎ ይዞ ፣ ሰውን ሁሉ እየመራ ደረ ጀውን መውጣት ጀመረ ። ኤለን የጂራልድን ክንድ ይዛ ትከተለ

@OLDBOOKSPDF

ዋለች ። ቀጥለውም ሴቶቹ ልጆች በሱፈው ላይ ከተደረደረላቸው ሻማ የየራስ የየራሳቸውን ይዘው ይከተላሉ ።

እስካርሌት ወደ ክፍሏ ገባች ። ሻማዋን በረኽው መሳቢያዋ ላይ አኖረችና ከቁምሳጥኗ ውስጥ ለዳንስ የሚሆናትን - ትንሽ በመ ርፈ መያያዝ የሚያስፈልገውን ቀሚስ መፈለግ ጀመረች ። አክንዲ ላይ ቀሚሱን ጣል አድርጋ ቱስ ባለ እርምጃ አዳራሹን አቋርጣ ሄደች ። የናትና አባቷ መኝታ ቤት በር ገርበብ እንዳለ ነው ። በሩን ከማንኳኳቷ በፊት ዝግ ይበል እንጂ ፈርጠም ያለ ታና ያለው የኤለን ድምጽ ጆሮዋን ያዘው ።

"ጂራልድ ፣ ያን ጆናስ ዊልከርሰን የሚባል ሰው ከሥራ ማበ ረር አለብህ" ጂራልድ እንደታፈነ ሁሉ አምባረቀና ፈነዳ፦

"እና ሴላ ታማኝና ዓይን በዓይን የሚያጭበረብረኝ ምስለኔ ከየት አባቱ ላመጣልሽ ነው?"

"ነገ ጠዋት መባረር አለበት ። ቢግ ሳምም ቢሆን ይሀና ፎር ማን ነው ። ሴላ ምስለኔ አስከታገኝ ድረስ እሱ ሥራውን በኃላፊ ነት ሊመራልህ ይችላል ።"

""""አሃ "አለ የጂራልድ ድምጽ " አሁን ገባኝ ነገሩ! ትልቁ ሰው ጆናስ በአባትነት . . . "

"መባረር አለበት ብያለሁ ፣ መባረር አለበት ።"

"ለካ የኤሚ ስላተሪ ልጅ አባት እሱ ነው ማለት ነው " ብላ አሰበች እስካርሌት ።

"ዱሮስ ከያንኪ ምን ይጠበቃል? ከዛች ልክስክስ ነጭ ልጃገ ረድስ ምን ይጠበቃል ?"

የጂራልድ ጩኸት ጋብ ብሎ ሲሞትና ለትንሽ ጊዜ እረፍት ሲገኝ እስካርሌት በሩን አንኳኩታ ገባችና ቀሚሱን ለእናቷ ሰጠች ።

እስካርሌት ፣ ልብሷን አወላልቃ ሻማውን ካጠፋች በኋላ ገና ጋደም ስትል የነገው ዕቅዷ አንድ በአንድ ፍንትው ብሎ ታያት ። ካባቷ ከጂ ራልድ የወረሰችው አንድ ወጥና ግትር ፣ ርቱዕ አዕምሮዋ ለሚወልደው ዓላማዋ መሳካት ፣ ዓይኖቿ ሁሉ እግቡዋ ላይ ይተክላሉ ። የምታስበውና የምትከተለውም ወደዚያ ግብ የሚያደርሳትን በጣም ቀናውንና አጭ ሩን መንገድ ስለሚሆን ዕቅዷ ቀላልና ግልጽ ይሆንላታል ። እንግ ዲህ እቅዷን እንደሚከተለው ደረደረች ፦

@OLDBOOKSPDF

በመጀመሪያ አባቷ ጂራልድ እንዳዘዛት ኮስታራና ኩሩ ልጅ ገረድ ሆና ትቀርባለች ። "እሥራ ሁለቱ ዋርነምኝ" መንደር ልክ ስትደርስ በጣም ተጫዋችና ደስተኛ ትሆንና ትሰታለች ። ንብቧን በደስታ ትሞላለች ። እንግዲህ ይህን ያየ ማንም ሰው በአሽሊይና በሚላኒ መጋባት ምክንያት እንዳችም ቅሬታና በደል የተሰማት መሆኑን ቅንጣት ታህል አይጠረጥርም ። እዛ ካለ ከማንም ወንድ ጋር ትሳሳቃለች ፤ ትላፋለች ።ይሄኔ አሽሌይ ውስጡን በቅናት ብግን ይላል ። ክዱሮው በበለጠም እሷን የማግኘት ፍላጐቱ ያይላል ። ሊሞት እንደ ሐሙስ በቀረውና ያረጀ አውራ ዶሮ ከሚመስለው የሱዊለን መዳጅ ጀምራ እስከ አይናፋሩና ቡበው የሚላኒ ወንድም ቻርለስ ሐሚልተን ድረስ ፣ ማንንም ለትዳር ያመቻል የምትለውን ሁሉ ሳት ንቅና ቁልቁል ሳታይ ማጫወቱን ትያያዘዋለች ። ወንዶቹ እንግዲህ በቅፎ ዙሪያ እንደሚርመሰመሱ ንቦች በዙሪያዋ ይራኮታሉ ። እጅብ እጅብ ያረጓታል ።ያለጥርጥር አሽሌይ ይሄን ሲያይ ሜላኒን ጥሎ በመምጣት ከሷ አድናቂዎችና አጀቢዎች አንዱ እንዲሆን ይገደዳል። ከዚያ እንደምንም ብሎ ከሱ ጋር ብቻዋን ልትነጋገር የምትችልበት አንድ አጋጣሚ ትፈጥርና ከእጇቡ ራቅ አርጋ ነጥላ ትወስደዋለች። ይህ ዘዴና መላዋ እንደሚሰራ በጽኑ ተስፋ አደረገች ።ምክንያቱም እቅዱ ካልሠራ በጣም አዳጋች ይሆንባታልና ነው ።ሆኖም አሽሌይ እንዳሰበች ይሳደረባ እንደሆነ ማለትም ቀድሞ ካሳናገራት የመጀመሪያዋን እርምጃ ራሷ በመውሰድ ሂዳ ልታናግረው ቆርጣ ደመደመች ።

በመጨረሻ ብቻችውን ሲቀሩ ፣ አሽሌይ እንዚያን እሷን ነበው፣ ጉምሸተውና ቂምጠው ሁሪያዋ ያሰፈሰፉ የነበሩትን ወንዶች ሁሉ ያየበትን ስዕል ልታሙሰ እንደገና እንዳዲስ የተወዳጅነቷን ነገር ሲያብሰለስል ፣ እንደገና እንዳዲስ ስሜቱን መገበር ሲጀምርና ቁሞት፣ ሐዘንና ተስፋ መቁረጥ ሲመነው ታያት ።ይሄኔ እሷ ፣ ምንም እንኳ ዓለም በሙሉ እሷን ፈላጊ ፣ የእለም ወንድ በሙሉ የሷ ጥቅር ባለ ሚል ለመሆን ተፍጨርጭራ ቢሆን ፣ እሷ ግን ካለሱ የምትመርጠው ወንድ እንደሌለ በመንገር ፤ ታስደስተዋለች ።ይህን ደግሞ ከልብ በመ ነጨ ትሀትና እጅግ ባማረ ፣ በጣፈጠ አኳኋን ስታረጋግጥለት ከሱ ሮው ሺ ግዜ በልጣ ፣ሺ ግዜ ልቃ ትታየዋለች ። እርግጥ ይህን ስታደ ርግ እንደው ቅብጥብጥ ብላ እግምት ውስጥ በሚከት ሁኔታ ሳይሆን በጨዋ ሴት ወግ ነው ። ሌላው ቀርቶ አፈቅርሃለሁ ብላ እንኳ አፍ አውጥታ አትነግረውም—በጭራሽ አታደርገውም ። ብቻ ያም ሆነ ይህ ዝርዝሩን ለሱ የማቅረቡ ጉዳይ ይሄን-ያህልም የሚረብሻት ነገር አይደለም ። ከዚህ ቀደም ተመሳሳይ ችግር ገጥሟት በሚገባ ተወጥ ዋለች ። አሁንም አያቅታትም ።

@OLDBOOKSPDF

አሊጋዊ ላይ እንደተንጋለለች ፣ የጨረቃ ብርማ ብርሃን እንደሸፈናት አሳይዋ ላይ እየፈሰሰ ትርዒቱን አንድ በአንድ ታየዋለች ።ምን ያህል እንደምታፈቅረው ሲገነዘብ ፣ ምን ያህል እንደምትወደው ሲረዳ አፉቱ ላይ የሚነበበው የመደነቅና በደስታ የመጥለቅለቅ ስሜት ግና ከሁኑ ታየች ። ሚስቱ እንድትሆን ሲጠይቃት የሚጠቀምባቸው ቃላት አራሳቸው ግና ከሁኑ ተሰሚት ።

እንደዚህ ሳይነት ጥያቄ ሲያቀርብለት እንግዲህ ነው እንደሚ ታውቀው ከሌላ ሴት ጋር ቅሰበት ካሰረ ወንድ ጋር መጋባት የማይ ታሰብ ነገር መሆኑን አሰረድታ እምቢታዋን ትገልጸለች ።እሱ ደግሞ ዲጋግሞ ያለምናታል ። ትግደረደራለች፣ ቢሆንም በእምቢታዋ ትፀናለች ። በጣም ይለምኗታል ፣ ጠንከር ይግጠናታል ። በመጨረሻ ከብዙ መግ ደርደርና እምቢታ በኋላ እጁ ትሰጣለች ። ከዚያ የዚያኑ አለት ከሰ ዓት በኋላ ወሄ ጀንበሮ ጠፍተው ይሄዳሉ ።ከሀ.....

መቸ ጉድ ! ነገ ማታ በዚህ ሰዓት እኮ መይዘር አሽሉይ ሚክስ ትሆን ይሆናል! ተንበታ አልጋዋ ላይ ቁጭ ብላ ፣ ጉልበቶቿን በራሷ እየታከከች ለረኅምና ለሚያሰት የደስታ ጊዜ መይዘር አሽሉይ ሚክስ ሆና ቆየች—የአሽሉይ ሙሽራ ! ወዲያው አንዲት ቅዝቃዛ እንደቀ ሰት ሹል የሆነች ሐሳብ አእምሮዋን ጠቀ አደረገቻት፦ ይሄ ሁሉ ነገር እሷ እንዳሰበችው ባይሳካስ ፣ አሽሉይ እንጥፋ ብሎ ባይለም ናትስ ! ምን ሊመጣት ነጠላ ይሆን እርኩስ ጠላቧ መዲያ ከእኔ ምርጥ ነፍትራ ጣለችው ።

"ያንንስ አውን አላሰብሽውም" አሰች ጥርጥም ብላ ።

"አሁን ካሰብኩት እንጐሉን ያዘረዋል ፣ ያናድደኛል ። እሱ ካፈቀረኝ - ነገሮቹ ሁሉ እኔ እንደፈለኩት የማይሳኩበት ምንም ምክ ንያት የለም ። እንደሚያፈቅረኝ ደግሞ አሳምሬ አውቃለሁ!!"

ከአጣሏ ቀና አሰች ። ከዚያ በጥቁር ሽፋል የተከፈፉና የታ ጀበ ሙባ አይኖችዋም ከፊፈረቃዋ ብርማ ብርሃን ጋር አብረው አንበሣረቱ ። እኛ ኢሰን ፣ መፈለግና የፈለጉትን ማግኘት የተለያዩ ነገሮች መሆናቸውን በሚራሽ ነገራት አታውቅም ። የሷ ሕይወት ደግሞ ፣ ጉዞዋና ግልቢያዋ ሁሉ ሽቅብ ወደጅራቱ እንጂ ቁልቁል ከጅራቱ ጋር እንዳልሆነ አላስተማራትም ። በብራማው ብርሃን ጥላ መስጥ ተንጋለለችና በደፍረትና በዮንክሬ ተሞልታ ሕይወቷ በደ ስታ ከመጥለቅለቅ የተነሳ የማይሳክ ነገር የለም ብላ በምታ ምን የአሥሬ ሰደስት ዓመት ልጅ አእምሮ የተነደፈ ዕቅዷን ዘር ግታ ፣ ቆንጆ ሎሚስና ጠብ መልክ ዕድሉን ድል ማድረጊያ ዋና መሣሪያዎች ናቸው ብላ ደመደመች ።

@OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ 5

ከጠዋቱ አራት ሰዓት ነው። ቀኑ ሞቃት። ወሩ ሚያዝያ። ለሚያዚያ ወር በጣም ሙቀታማ ነው ሊባልት ይቻላል። በሰፋፊዎቹ መስኮቶች ዘልቆ፣ በሰሚያዊዎቹ የመስኮት መጋረጃዎች ውስጥ አልፎ የሚገባው ወርቃማው የፀሐይ ጨረር በቤቱ ውስጥ እየፈሰሰ የእስካርሌትን ክፍል በብርሃን ሚዕበል አጥለቅልቆታል። የክሬም ቀለም የተቀቡት ግርግዳዎች በዚያው ሚዕበል ውስጥ ሰጥመው ያበራሉ። ከማሆጋኒ እንጨት የተሠሩት የቤት ዕቃዎች ውስጣዊ ቀለማቸውን እያወጡ እንደወይን ዓይነት ቅላት ለብሰዋል። አልፎ አልፎ ደብዘዝ ደበዘዝ ከሚሉ ንጠብጣብ ዕቃዎች በስተቀር ድፍን ወለሉ እንደመስታወት ያንፀባርቃል።

በጋ እየሳቀ መምጣቱ ነው። የመጀመሪያው የጆርጂያ በጋ። የፀደዩ ነፋሻ እየር፣ ጠንካራው ሙቀት ዘራፍ ከማለቱ በፊት ቦታውን ያለፈቃዱ ለበጋው መልቀቁ ነው። ለብ፣ ለስለስ ያለ ሙቀት ቤቱን እየሞላው ነው። አበቦች ንጥር መዓዛቸውን ከዚህ ሙቀት ጋር አጅበው ልከዋል። አዲስ ያቆጠቆጡ ዛፎችና አዲስ ግልብጥ የሆነው ቀይ አፈር ትኩስ ሽታም አብሮ ወደ እስካርሌት ክፍል እየተመመ ይገባል። እስካርሌት በመስኮቱ አሻግራ ጠጠር የተነጠፈበትን አውራ ጎዳና፣ ከማራና ቀኝ ያጀቡትን ባለረዣዥም ቅጠል ቢጫ የፀደይ አበቦች ታያለች። በዚያው መንገድ ጉን እንደ ቡፌ ቀጫስ ኮፈፍ ብሉው ዙሪያ ገባውን ያለበሱ ሌሎች በተለያዩ ቀለም ያሌጡ አበቦች ተነጥፈው ይታዩዋታል። ጨዋታ አዘውታሪዎቹ ወፎችም በተለመደው የማረፊያ ዛፍ ፍለጋ ከንፈያቸው፣ ከፊሎቹ በማራጭ ዜማ፣ ከፊሎቹ ጆሮ በሚሰቀጥጥ በቀጭንና ጮርናና ድብልቅ ድምጽ እያዜሙ፣ በመስኮቷ ስር ባሉት ዛፎች ላይ ያንጎብባሉ። እስካርሌት ይህን የተፈጥሮ ድንቅ ቅኝት፣ ከቅጠሎች፣ ከአበቦችና ከወፎች መዐዛና መዓዛ ጋር ያለዐሳብ የመመገብ ሙሉ ነፃነት የየንጋት ፀጋዋ ነው። ማንም የማይነጥቃት፣ ማንም የማይሻማት በመስኮት የሚመጣ ስጦታ! በመስኮት የሚገባ ፀጋ! ለመትረፉ እንዲህ ያለ የተዋበ ጠዋት ሁልጊዜም እስካርሌትን ወደ መስኮቱ ይጠራታል። የመስኮቱን ደፍ በታጠፉ ክንዶቿ ደገፍ ትልና የታሪን መንደር ሽታና ድምጽ በደስታ ትኮመኩማለች። ዛሬ ግን ለንጋት ፀሐይም

@OLDBOOKSPDF

ሆነ ዙሪያውን ጥርት ብሎ ታራ ላይ ለተደፋው ሰማያዊ ሰማይ መበት ፥ ከቱ ምንም ዓይን ያላትም ። አፈረ ከተድቅነው አማዳሪ ሀሳብ ባሻገር ፥ ማታ ከወጠነችው ዓላማ ባሻገር ፥ ምንም ነገር ልታይ አይቻላትም ።

"ለእግዚሀር ምሥጋና ይግባው ዛሬ ብራ ሊውል ነው ፥ አይ ዘንብም ።" አለች በልቧ አልጋው ላይ ካለው የካርቶን ሳጥን ውስጥ ውሃ አረንጓዴ ቀለም ያለውና እንደጅረት የሚፈስ ሀር የተንጣለለ በት የማብገር ቀሚስ ፥ ከነባለፈርጥ መቀነትና ወርቁ ዘቦ ጌጡ ተጣ ጥሮ ተቀምጧል ። ወደ "አሥራ ሁለቱ ዋርከምኞች" መንደር ተወስዶ ዳንሱ እስከሚጀመርበት ሰዓት ድረስ በሥነሥርዓት በሚቀመጥበት ሁኔታ የተዘጋጀ ቀሚስ ነው ። ሆኖም እስካርሌት ገና ሰታየው ተደ ናገጠች ። ወጥኗ የተሳከላት እንደሆነ ያንን ቀሚስ ዛሬ ማታ አት ሰብስውም ። ምክንያቱም በእቅዷ መሠረት ዳንሱ ከመጀመሩ በፊት እዩና አሽሌይ ወደጆንስቦሮ ሊጋቡ መሄዳቸው ነው ። ዋናው አሰቸ ጋሪ ጥያቄ ወደ ግብጥው በታ ምን ዓይነት ቀሚስ ለብሳ ትሂድ-ነው ።

ምን ቀሚስ ብትለብስ ነው ውበት ደምግባቷን ከውስጧ ፈን ቅሎ አውጥቶ ፥ ማራኪ ገጽታዋ አሽሌይ በምንም ዓይነት እንዳይተ ዋት የሚያደርጋት፣ ከጠዋቱ ሁለት ሰዓት ጀምራ ይኸው እስከረፋዱ ድረስ አንዱን ስታጎላ አንዱን ስትጥል ቆየች ። አሁን ባለ ጊዜ የመስዋ ሱሪምኞች ፥ ከላይ የሚለበስ ናይሰን ቀሚስ ፥ በለስት ደረጃ እየተደራረበ የሚወርድ የጊጥ ረዴፍ ያንቆጠቆጣቸው ሦስት በሱሪ የሚለበሱ ቀሚሶች ደግ ፥ ተበሳጭታ እንደቆመች ነች ። በልዩ ልዩ ቀለም የተሞቡ የተለያዩ ልብሶችና የተንዘረፈፉ ጥብጣቦቻቸው በወ ለሉ ፥ በአልጋውና በየወንበሮች ላይ እንደጉድ ዙሪያዋን ተከመሩ ።

ርዙን ቀሚስ ከነሐምራዊ ኤላባቹ ብትለብሰው ቆንጆ ነበር ። ነገር ግን ባለፈው በጋ ከሚላኒ ጋር የ"አሥራ ሁለቱን ዋርከምኞች" መን ደር ሰመጫወትና ስትሄድ ስለለበሰችው አሁን ደግሞ ብትለብሰው ያለጥርጥር ሚላኒ ታስታውሰዋለች ። ደሞ ለክፋቷ ታወራው ይሆ ናል ። ጥቂቱ ባለበራ ኑሉታና እንጥጉው በነገሥታት ወርቀ ዘቦ ጥልፍ ያጌጠው ቀሚስ የነሟ ቆጸዋን ቀለም ከጭት አድርጎ ያወጣው ነበር ፥ ነገር ግን ትንሽ ጠና ያለች ያስመስላታል ። አስካር ሶት ራቷ ላይ መፈጠሟደና የአገጯ ጠንከሮን ጠየሮ መታየት ለማ ረጋገጥ እንደፈለጎች ሁሉ ወደ መስተዋቱ ዞራ የአሥራ ስድስት ዓመት ልጃገረድ መልኳን እየች ። ከሚላኒ ለጋ ስግላጋ ወብ ገጽታ አንጻር ፥ ጠቁም ጥቂት እንኳ ጠና ብሎ መታየት የሚይሞክር ነገር ነው ። ባለጌውና ባለመረብ ጥልፉንም ቀሚስ ሞክራው ነበር ፥ ግን

@OLDBOOKSPDF

ከሷ ቅርጽ የሚጣጣም አልሆነላትም ። ከሷ ይልቅ ከኻሪን ተመሣሣኝ ቅርጽና ቀበጥባጣ መልክ ጋር አሳምሮ ይሄዳል ።

የተማሪ ልብስ ነው እሚመስለው ። እሪ ተማሪ ያስመስላታል !! በሚ ላኒ የኮራ ትክለ ሰውነት ፊት ተማሪ መስሎ መቆም መቼም አይ ሞከርም ። አረንጓዴውና ቡፍ የሚል ቀሚሷ ፣ በየእጥፋቱ ላይ ካለው አረንጓዴ ባለዘርፍ ጥብጣብ ጋር በጣም ያምራል ። እሷም በጣም የም ትወደው ቀሚስ ነው ። ዓይኖቿን ጠቅር አድርጎ ጥቁር አልማዝ ያስመስላቸዋል ። ችግሩ ይሄ ቀሚስ ደሞ ወዶ ጠቦቱዋ አካባቢ ቅባት ነገር ነክቶት አንድ ክብ ነጥብ ምልክት ፈጥሯል ። አርግጥ የደረት ጌጧን እዚህ ምልክት ላይ በማያያዝ ልትሸፍነው ትችላለች ። ግን ምን ያረጋል የሚላኒ ዓይን የመርፌ ቀዳዳ አንኳ ከርቀት የሚ ለይ ነው ። በተረፈ እንግዲህ የቀሩት ቀሚሶች የተለያየ ቀለም ያላ ቸው የጥጥ ቀሚሶች ሲሆኑ ፣ እነዚህ ደግሞ ለማብሣው ስነሥርዓት እምብዛም የሚሆኑ ዓይነት አይደሉም ። ትላንት ሰብሳው የነበረው ከሰስ ጥጥ የተሠራው አረንጓዴ ሽንሽን ቀሚሷም ከነዚህ ጋር ተቀ ምጧል ። ከሰዓት በኋላ የሚለበስ ቀሚስ ነው ። በቀጭኑ ብትን እያለ ፏ ብሎ የሚታይ ኮኤታ ያለውና ሰዳንስ እንደሚሆን ዓይነት እጥር ብሎ የተሰራ እንጥጉ አለው ። ወጣም ጠረደ ምንም ማድረግ አይ ቻልም — ይሄንኑ መልበስ ነው እሚሻለው ። በቃ ። ደሞኮ እንጂ ፣ ክንዱም ሆነ ደረቷ ግልጽ ቢሆን የሚያሳፍር ሰውነት ያላት አይ ደለችም ። በጠዋት ግልጥልጥ ማለት ደንብ አይሁን እንጂ ለነሳዋ ጥራትም ሆነ ምጥንነት እንኳን እንከን አይወጣለትም ።

ይህንኑ ለማረጋገጥ እመስተዋቱ ፊት ቆማ እየተሽከረከረች ትክለ ሰውነቷን ከየአቅጣጫው ሚትራ ሰታበታ ምንም የማይወጣ ላት ባለ ሽጋ ቅርጽ መሆኗን አመነች ። እንጂ አጭር ይሁን እንጂ ክብ ነው ። ከንዶቿ ለስላሳና ትምቡክ እንዲሁም ጥርት ያለ ተለም ያላቸው ናቸው ። እጉጠጉጠዉ ጡቶቿ ከደረቷ ወጣ ብሰው በተጠ ንቀቅ ሾለው የቆሙ አስጎምጂ ነገሮች ናቸው ። የአሥራ ስድስት ዓመት ልጃገረዶች እንደሚያደርጉት ሁሉ የጡቶቿን ቅርጽ ሰማ ውጣትና ቀጥ አድርጋ ለማቆምም ሆነ የደረሰና ዓይን የሚገባ ሙሉ ጡት ለማስመሰል ጨርቅ ብጨ ጭስጉሳ ማሳበጥ አላስፈለ ጋትም ። የኤለንን ምጥን እጅጥና በልኩ የተሠሩ እግሮች በመውረዷ በጣም ደስ አላት ። የኤለንን ቁመትም እንደዚሁ መርሳ ቢሆን እን ዴት በወደደች ፣ ብቻ ያሁኑ የራሷ ቁመትም ቢሆን የምትወደው ዓይነት ነው ።

ረኾም ቀሚሷን ከወደ እግሯ ከፍ አድርጋ ከሙስጥ በለበስ ችው ሱሪ ላይ የባቶቿን ቅርጽ እያየች—እግርን ገልጦ የሚያሳይ

@OLDBOOKSPDF

ልብስ ለመልበስ አለመቻሉ አሳዘናት ። በጣም ቁንጅ የአግር ቅርጽ አላት ። እራሳቸው የፈይትቪል አካዳሚ ሴኞች ያመኑላት ጉዳይ ነው ። የወገቧ ቅጥነት ነባርማ እንኳን በፈይትቪል ፣ በጅንስቦሮ ወይም በሌሎች ሶስት መንደሮችም እንደፃ ክንብ አውራ እሚለካከ ወንብ ሲሥሩ ቢውሉ አይገኝም ። ስለወገቧ ስታስብ ወዲያው ዋናው ቁም ነገር ትዝ አላት ። አረንጓዴው ቸንቸን ቀሚስ የወገቡ ልክ አሥራ ሰባት አንች ነው ። ማሚ ያሰፋችላት ቀሚስ ደግሞ ባለ አሥራ ስምንት አንች ነው ። ማሚ ልታስተካክልላት ይገባል ። በሩን ብርግድ አድርጋ ከፈተች ። የማማ ኪዛድ አደምጄ ከአምድር ቤት ይሰማታል ። ማሚ ስትጠግት እንደምትናደድና እንደምትጮህ አየወቀች ፍክ ብላ "ማሚ" ብላ ተጣራች ። ኤሰን ዕቃ ቤት ሆና ሰዕለቱ ፡ የሚያስፈለጋውን ምግብ እየመረጠች ለዜኪ እያሰጠች በመሆኗ ማሚ ምንም የሚረብሽ ድምጽ እንዲሰማ አትሻም ።

"እንዳንድ ሰዎች ክንፍ አውጥቼ የምበር ይመስላቸዋል እንዴ! እኔ ስንት ቦታ ልሁንህ" እያለች እያጉረመረመች ማሚ ያረጀውን በጥድፊያ መውጣት ጀመረች ። ቁና ቁና እየተንፈሰች ገባችና - ወር ነትን ሲጠብቅ ቆይቶ ሲያርስለት ለመዋጋት ዝግጁነቱን እንዳረ ጋገጠ ሰው ዓይነት- ሆና ቆመች ። በሁለቱ ጥሩቱር ኢጆቿ ግና ጭሱ የሚታይ ትከስ ምግብ ያለበት ትሪ ይዛለች ። በቅቤ የተለቀለቁ ሁለት ትላልቅ ያም ፡ በነሪም የራሱ ኪኩችና በቅባት ውስጥ የሚዋኝ የአሳማ ሥጋ ፡ ብሉኝ ብሉኝ ይላሉ ። ማሚ የተሸነመችውን ጭነት ስታይ እስካርሌት ብሰጭቲ ሁሉ እየቀነሰ ሄደና ቀስ በቀስ ወደ ሀዘንና ድንጋጤ ተለወጠ ። አፏ ልብስ ስታማርጥ ለካ ዋናውን የማሚን የግብግ ሕማ ዘንጣታዋለች፡- በማሚ የሞግዚትነት ሥነ ሥርዓት መሠረት ማንኛዋም የአሃራ ቤተሰብ አባል የሆነች ልጅ ግብግ ከተጠራች ፡ ወደግብግው ከመሄድዋ በፊት ጥብስቅ አድርጋ በልታ ፡ ሆዷን ሞልታ ስታበቃ እግብግው ቦታ የሚቀርብላ ትን ምግብ ቀመስ ቀመስ አድርጋ መተው አለባት አንጂ ፡ እቤቱ የሚላሰ የሚቀመስ እንደሌለው የተራበ ሰው ፡ እጅ አንዳነሳ አየጮረሱ ግምት ላይ መውደቅ ፡ በጥበት የተከለከለ ብልግና ነው ።

"ምንም ጥቅም የለውም ፡ እንዳመላሽው መልሰሽ ውሰጂልኝ"

ማሚ ግን ትሪውን አጠረጴዛው ላይ አስቀመጠችና በሁለት እጆቿ ወገቧን ይዛ ኮስተርተር ብላ ፡

"እረ ጎሺቱ ማሚ! ምነው እሚቱ — አላበሳሽውም እንዴ? ባለፈው ጊዜ ግብግ ስትሄጂ እንደሆነው ይሆናል ብለሽ በጭራሽ አትጠርጥሪ ፡ እያንዳንዷን ቁራሽ ልትም አድርጌ ነው አማስበላሽ"

@OLDBOOKSPDF

"እኔ በጭራሽ አላደርገውም ። ይልቅ ነይና ወገቤን ጥብቅ አድርገሽ እሰሪልኝ ። ረጅዷል እኮ ። ሠረገላው በፊት ለፊቱ በር ሲመጣ ድምፁን ሰምቸዋለሁ ። "

"ስሚ እስካርሌትዬ ፤ ይልቅ ትንሽ ቅመሺ ፡ ጥሩ ልጅ ሁኚ እንጂ ፣ ካሪንና ሱዌለን እንኳን እስኪጠግቡ ድረስ ነው የበሉት"

"ይብሏ ፤ አማሞች!" አለች እስካርሌት በጥላቻ ። "ከጥንቸል የተሻለ የመንፈስ ጥንካሬ የላቸውም ፤ ከርሳቸው ከጐደለ የደቂቃ ትእግሥት የላቸውም !! እኔ ግን አላደርገውም! እህል የሚባል ባይኔ አላይም ። አንድ ጊዜ ወደካልቨርት ቤተሰብ ግብዣ ስሄድ አንድ ትሪ ሙሉ ምግብ አስጨርሰኝ ፤ ከሳሻና ድረስ ያመጡትን ጣት የሚያስቆርጥም አይስክሬም አንድ ማንኪያ እንኳን መብላት እንዳቃተኝ የረሳሁ አይምሰልሽ ። ዛሬ ግን ምንም ሳልቀምስ ሄጄ እዛ እንደልቤ መብላት አፈልጋለሁ ። "

የእስካርሌት ግትርና ድፍረት የተሞላበት እምቢታ ማሚን በጣም አናደዳት ። አንዲት ጨዋ ልጃገረድ ማድረግ ይገባታል ብላ ማሚ የምታምነውና አሁን እስካርሌት የምትናገረው ነገር ሰማይና ምድር ሆነ ። ምንም በማህል አስታራቂ ሀሳብ የለም ። ሱዌለንና ካሪን፣ ማሚ ገና ስትቆጣቸው ብርክ ይይዛቸዋል ። ወዲያው በአክብሮት እሺ እሺ ይሏታል ። እስካርሌት ግን ባህሪዋ ወንዳ ወንድ ስለሆነ በቁጣም ሆነ በልመና ሥነ ሥርዓት ሰማስያዝ አስቸጋሪ ነው ። ከባድ ትግል ያስፈልጋል ። እንዲህ ጥሬ ሣራ ጠባይዋን ከገራቻት በኋላ ግን ለማንም ነጭ አእምሮ ሲገባ የማይችል ውጤት ስለሚታይ አስገራሚ ነገር ይሆናል ።

"ሰው በዚህ ቤተሰብ ላይ የሚያወራው ሁሉ ላንቺ ግድ ባይሰጥሽ ለእኔ በጣም ትልቅ ነገር ነው እናቴ ። " አለች እየተቆጨች ። "እዛ ግብግቡ ላይ ማንም እየተኑሳ ምን ያለች አሳዳጊ የበደላት ናት ሲልሽ በትእግስት ቆሚ የማያምጥ አይምሰልሽ ። የታረመች የተቀጣች ልጅ ፤ ቀስ እያለች እንደወጡ ትንሽ ትንሽ መጉረስ እንዳለባት ደጋግሜ ነግሬሻለሁ ። ይሄ እጅ እንደሞላና ጉንጭ እንደቻለ መጮሰጮስ የጨዋ ልጅ ወግ ማረግ አይደለም ። ከነተረቱ እንኳን 'የሴት ምራቋ ደንዳና ነው' ሲባል አልሰማሽምን እግብገቡ ቦታ ሂደሽ የምትሰገበገቢ ከሆነ እኔ ደግሞ ሞቻለሁ ብትሔጂ ! አትሄጂትም! "

"እማማ ጨዋ ሴት ናት ፤ ግን በደንብ ትበላለች" አለች እስካርሌት ተታውሞዋን ለመግለጽ ።

@OLDBOOKSPDF

"እንቺም ስታገቢ በደምብ ትብያለሽ" አለች ማሚ ። "እሚቴ ሌለንም ባንቺ ዕድሚ ሳሉ እውጪ ሰው ግብግ ላይ በጭራሽ አይበሉም ነበር ፤ አከሰቶችሽ ፖሊንና አውሳሊም እንደዚያው ነበሩ ። አሁን ሁሉም አግብተዋል ። ወጣት ሴቶች ሆዳም ሲሆኑ ፤ አብዛኛውን ጊዜ ባል አያገኙም ። "

"እኔ በጭራሽ አላምንም ። ባለፈው ጊዜ ግብግ ሂጂ ፤ ምንም ሳልበላ ነበርና የሄድኩት ጥብስቅ አድርጌ ሰበሳ ፤ አሽሌይ ዊክስ አይቶ ደሀና አድርገው የሚበሉ ሴቶች በጣም ደሰ ይሉኛል ሲል ነበር"

ማሚ በጣም አዝና አራሷን ነቀነቀች ።

"አይ እስካርሌት ፤ ወንዶች በልባቸው የሚያስቡትና ባፋቸው የሚናገሩት እኮ በጣም የተለያየ ነገር ነው ። አሽሌይ ደግሞ ላንቺ የቅጸር ወሬ ሲያወራልሽ ሰምቼም አላውቅ ። " እስካርሌት እንገሸገሻት ፤ ባይኗ መጣችባት ። ፍርጥም ብላ በቁጣ ልትናገር ጀመረችና ስሜቷን ተቆጣጠረች ። አማሚ እጅ ውስጥ እስካለች ድረስ ዋጋ የለውም ። ማሚም እስካርሌት ፊት ላይ የሚያንጥበበውን የመከፋት ስሜት ልብ አሰኙና ከዘር ማንዘሯ ሲወርድ ሲዋረድ በመጣላት መላ የመቀያየር ዘዴ ፤ ትሪውን ብድግ አድርጋ ቁናቁና እየተንፈሰች ወደ በሩ ራመድ ራመድ አለችና ፦—

"እሪ እሺ እናቴ ። እኔ" ግንም ሴት ጨዋ ሴት መሆኗን ለመለየት የሚትበላውን ዓይነት ምግብ ማወቅ ብቻ በቂ ነው ' ብዬ ለኩኪ ስንግራት ነበር ። 'እኔ በሕይወቴ ከወ/ት ሜሊ ሐሚልተን ያነሰ የምትበላ ሴት አይቼ አላውቅም ። ወ/ት ሜሊን መቼ ያየሁዋት መሰለሽ .... ባለፈው አሽሌይን ልትጠይቅ .... ማለት ኢንዲያን ልትጠይቅ ሂዳ ነው ። "

እስካርሌት በጥርጣሬ ዓይን ታያት ጀመረች ። ማሚ ሰሬ ፊት ላይ የሚታየው ግን— እስካርሌትና ሜላኒ ሐሚልተን የተለያዩ ሴቶች መሆናቸውን አበክሮ የሚያስረዳ— የዋህነትና አዘኔታ ብቻ ነው ።

"እሱን ትሪ ቁጭ አድርጊና ነይ ወጣቤን አጥብቀሽ አሰሪልኝ" አለች እስካርሌት ብስጭትጭት ብላ ። "በኋላ ይልቅ ትንሽ ለመብላት አሞክራለሁ ። አሁን ከበላሁ ወገብ ሽንትጥ እስኪል አጥብቂ ለማሰር ያስቸግረኛል ። "ማሚ ድል በመምታቷ ተደስታ ትሪውን ቁጭ አደረገች ።

"ምንድነው ዛሬ የምትለብሺው የኔ እምቦሳ"

@OLDBOOKSPDF

"ያንን" አለች እስካርሌት ባለአረንጓዴ አበባውን ሸንሸን ቀሚስ እያሳየች ። ማሚ ወዲያው አነሳችና ፡

"እረ በጭራሽ አይሆንም ። ይሄ ለጠዋት የሚሆን ቀሚስ አይደለም ። የጠዋት ፀሐይ ደረት ደረትሽን ብሎ ባንዴ አመድሽን ነው አሚያወጣው ። ለራሱ አንገት የለው ፡ ኮሌታ የለው ደረት ግልጥጥ አድርጎ የሚያሰጣ ቀሚስ ። እረ ንሺቲ ማሚ! ምኑው ምን መጣ ብሽ እናቲ ። በጋ ተክረምት ቅቤና ወተት ባፍ ባፍንጫሽ ሰግተሽ ከርሜ ባለፈው ሳቫና ጸርቻው ሳይ ለፀሐይ ተሰጥተሽ እንደሆንሺው መሆን መቼም አይሞክርም ። ኋላ ለእናትሽ ነው እምነግርልሽ ።"

"ለብሼ እስክጨርስ ድረስ ለእማማ አንዲት ቃል ብትተነፍሺ፣ አንዲት ጉርሻም አልቀምስልሽ እወቂ" አለች እስካርሌት ቅዝቅዝ ብላ ። "እማማ እንደሆነች አንድ ቀሚስ ለብሼ አይታኝ ልቀይር ያልኳት እንደሆን ፡ ጊዜ የሰም እያለች እሺ አትልኝም ።"

ማሚ በረኸሰው ተንፈሰችና የሚሻለውን መላመት ያዘች ። እስካርሌት እንደሕፃን ልጅ አንዴ ይሁን ያለችው ነገር ካልሆነላት ቅኑን ሙሉ አኩርፋ ፡ ተኳፍታ የምትውል ናት ። ስለዚህ ይሄንኑ ይሁን ያለችውን ከስጓት የሚለበስ ቀሚስ ለጠዋቷ ግብግ ትልበስ ውና ትረፍ እንጂ በጭራሽ በጂ አትልም ። ማሚ ይሀንኑ ሀሳብ አፀናች ።

"በይ እሺ ፡ ጨርቋን ጥበቅ አድርገሽ ያዢና ቁጪኝ" ብላ አዘዘች ማሚ ። እስካርሌት እንደታዘዘችው አደረገች ። ባንድ እጅዋ ጨርቋን ጥበቅ አድርጋ ይዛ ባንድ እጅዋ የአልጋውን የራስጌ ብረት ይዛ ቆመች ። ማሚ በደንብ ጉተተችላት ። እስክትንቀጠቀጥ ድረስ አጥብቃ ሳበችው ።

ያ ወትሮውንም ጠባቡ ችቦ አይሞላ ወገቧ ሸንቅጥ ብሎ ወደ ሆዷ ገባ ። እስካርሌት አይን ላይ የኩራትና የደስታ ብርሃን እንደ ከዋክብት ፈነጣጠቀባት ።

ማሚ፦" አሁን ያንችን የእምቦሳዬን ወገብ የሚያህል ቀጭን ወገብ በድፍን አገር ይገኛል? በጭራሽ አይገኝም ።" አለች በእርግጠኝነት ። "ይገርማል ፡ የሱዌለንን ወገብ እንደዚህ ላርገው ብል እኮ ፣ ገና ከሃያ ኢንች ሰብስብ ሳደርገው ፤ እረ ሞትኩኝ ትላለች?"

"ውይ !" አለች እስካርሌት ። "ስትናገር በችግር ነው ።" እኔ በሕይወቴ እንዲት ቀን እንኳ ፡ ገለሎ መውደቅ ቀርቶ ደክሞኝ እንኳን አላውቅም ።"

@OLDBOOKSPDF

"እሱማ አሁን ወንብሽን ስታጠብቂ ቢያምሽ ይሄን ያህል አይጎዳም።" አለች ማሚ በምክር መልክ። "አንቺ አንዳንዱ ነው የም ታበሽቂኝ ምን ላስጠነቅቅሽ እንደ ነበረ ታውቂያለሽ- ይሄንን በአ ባብ ፥ በአይጥና በጉንጮር መያንጣሽን ተይ። እቤት እንኳ ቢሆን ግዴለም ፥ ከሌላ ሰው ጋር ስትሄጂ ግን በሚራሽ መጥፎና አስጥሪ ንገር ነው። ይሄን ደግሞ ብዙ ጊዜ ነግሬሽ.."

"ውይ ማሚ ስሞትልሽ ዋሉ በይ! አሳዮሬውን ባለ አገኘለው ዛራ ታያለሽ። ሳልሙሀ ፥ ሳልደንግዮ እንዴት አድርጌ ባል እንደ ማግኝ ታያለሽ። ው... ፥እንዴት ጥበቅ አድርጉኛል ይሄ ኩርሲ! ቀሚ ሱን አልብሺኝ።"

ማሚ ያንን አረንጓዴ ሽንሽን ቀሚስ ፥ ቡፍ ብለው ያልጸሳ ጻሉ የሰዉት ፀሳንቲም ላይ ደርባ አለበሰቻት። ከኋላ ማጅራቷን ግልጦ ገቡ ብሎ የሚቆልጭ ዓይነት ስለሆነ ፥ መርፌ ቁልፍ መሳይ መቆለፊያውን አጠላለፋ ቆለፈችላት።

"ታዲያ ፀሐይ ላይ ከሆንሽ በሚራሽ ያንገት ልብስ እንዳይለ ይሽ። ደግሞ ወብቆሽ እያለሽ ባርሜጣሽን እንዳታወልቂ" ትእዛዝ ሰጠቻት። "ኖ አለበለዚያ እንደ ወ/ሮ ሰላተሪ ከሰል መስለሽ ነው የምትመጪ ጥቁ ቆይ እሱን ማሩን ብዬ። ታዲያ በጥድ ፊያ እንዳትጎርሺ። እልብሽ ላይ ይቆምና ደሞ ላስመልሰው ትያ ለሽ።"

እስካርሌት ትእዛዙን አክብራ በሶን ሥርዓት እትሪው ፊት ለፊት ተቀመጠች። አንዷን ገርሻ እንኳ መደሆኗ ማስገባት ትቻል አትቻል እርግጠኛ አይደለችም። ደሞ በልታ ከጠገበች በኋላ ለመ ተንፈስ እንኳ የማትችል መሆኗን አውቃለች። ማሚ ፎጣውን ከተሰ ካለበት አውርዳ እስካርሌት አንገት ላይ አሥራ ቁልቁል በደረቷ ላይ ዘረጋችላት። እስካርሌት ሳንድዊቹን መብላት ጀመረች። ሳን ድዊች በጣም ትወዳለች። የማዲን ዋጠችው።

"አፍ ምንው ባጣሁና ባረጥኩ" አለች በምሬት ፥ ሳንድዊቹ ላይ ከባድ ጥቃት እያደረሰች። "እንደው ዕድሜ ልኬን ያለጥላትቱ አርቲፊሻል መሆን ትክት አለኝ። ግና ጥቁብ እስክል መብላት እየቻልኩ የወጥን ያህል እንኳ ሆድ የሌለኝ ማስመሰሉ ሰለቸኝ። መርጥ እየቻልኩ- ለሰው ይምሰል ብዬ እርምጃዬን እየቆጠርኩ መሄድ ፥ ግና ስንትና ስንት ጊዜ ፈጣን ዳንስ መጫወት እየቻልኩ በየፓርቲው ላይ አንድ ለስለሳ ዳንስ- ዋልስ ብቻ ተጫውቼ "ምት ኩኝ ልቢ ፈሰሰች" እያልኩ ለመወደድ ብዬ መሞሸት በጣም ነው የደከመኝ። ደሞ እሚገርመኝ ምንም እንደማታመዛዝን ገልቱ ሴት

@OLDBOOKSPDF

የኔን ማማሽ ያህል እንኳ ጭንቅላት የሌላቸውን ግብዝና ጅል ወንዶች " እንዴት ያለህ አስተዋይና ጉሩም ሰው ነህ!" እያልኩ የማሳምንበትን ፣ በሞራሽ ህሊናዬ የማይፈቅደውን ነገር ማዳለሴ ነው ። ወንዶቹ እንዲህ ሲያሞካሿቸው በጣም ትልቅ የሆኑ እየመሰላቸው የባጥ የቆጡን ይቀባጥራሉ — ጅሎች ናቸው!... ሌላ ጉርሻ መጨመር አልቻልኩም"

"እንዲት ትኩሰ ኪክ ሞክሪ በሞቴ" አሰቻት ማሚ በመግፀን ።

"እኔ እምለው ማሚ ስምንድነው ሴቶቹ ገና ለገና ባል እና ገኖለን ብለው እንደዚህ ግብዝ የሚሆኑት ?"

"እየሽ አስካርሴት ፣ እኔ እንደሚመለሰኝ ወንዶቹ ምን እንደ ሚፈልጉ አያውቁም ። የፈለጉ የሚመስላቸውን ነው ጌንጂ በእርግጥ የሚፈልጉትን አያውቁትም ። ስለዚህም የሚፈልጉ የሚመስላቸውን ነገር እንዲያገኙ ባደረግሻቸው ቁጥር ከብዙ ጣጣ ትገላገያለሽ ። በከንቱ እንዳታረጂም ይረዳሻል ። ታዲያ ወንዶቹ እንደወጉ የምትበላ አንዲት ዓይጥ መሳይ ምንም አንሳል የሌላት ልጅ ካገኙ የሚፈልጉት እሷን ይመስላቸዋል ። አብሳኛው ወጌ በጭንቅላት የምትበልጠውን ሴት ለማግባት ፈታጆኛ አይደለም ።"

"እንደዛ ከሆነ ታዲያ ከተጋቡ በኋላ ሴትዮዋ በጭንቅላት ክሱ የምትልቅ መሆኑን ሲያውቅ አይገረምም ?"

"ካገቧቸው በኋላማ ረፈደ ፣ በቃ ። በዛ ላይ ሚስቶቻቸው ካደረጉዋቸው በኋላ እያንዳንዳቸው ለሚስታቸው አስተዋይነትና ለት ዳሯ አሳቢነት ያመራሉ ። "

"እኔ ግን የልቤንና የምፈልገውን ነገር የምናገርበት ቀን ይመጣል ። ያኔ ማንም ያሸውን ቢለኝ ደንታ አይሰጠኝም ።

"እሱን እንኳ ተይው ። " አሰኝ ማሚ ቆጣ ብላ ። "እኔ ነብሴ ቆማ አታረጊውም ። በይ እስ ከዚኩ ሞክሪ ። በሽርባው መረቅ ማማ ማማ አርጊው የኔ ቆንጆ ። "

"እኔ ግን ያንኪ ሴቶች እንዲህ ያደርጉ አይመስለኝም ። ባለ ፈው ዓመት ማሬቆጋ ውስጥ አያለን መዓት ሴቶች አይቻለሁ ። ታዲያ በሞራሽ አሁን እንቺ እንደምትይው ሲሸጃሉ አያቼም አላ ውቅ ። እንደውም ወንዶች ፊት ይኩሩና የበሰሉ ሴቶች መሆናቸውን ያሳዩ ነበር ። "

ማሚ በኃይል አስነጠሰች ።

@OLDBOOKSPDF

"አሃ፣ የያንኪ ሴቶች! አምን ፣ እነሱማ በእርግጥ አፋቸው ያመ ጣላቸውን እንደልባቸው ይናገራሉ ። ሆኖም ግናቸውም ቢሆኑ አግ ቡን ፣ የባል ያለህ' እያሉ ሲናገሩ ሳራቶጋ ውስጥ በጭራሽ አልሰ ማሁም ። "

"እንዴ፣ ታዲያ የያንኪ ሴቶች ቆመው ይቅሩልሽ እንዴ ! እነ ሱም እኮ ግግባት አለባቸው ።" አሰች እስካርሌት በክርክር መልክ ።

"እንዲሁ በዓርባ ቀን ዕድል አያድጉ መቼስ ። ግግባትና የልጅ እናት መሆን ይገባቸዋል ። ብዙ ባለትዳሮች አሉኮ ። "

"እረ ንቪቴ ግሚ ። እነሱን የሚያገቧቸው - ለገንዘባቸው ሲሉ እኮ ነው— ነው እምልሽ ። "አለች ግሚ ፍርጥም ብላ ።

እስካርሌት ኪኳን መረቁ ውስጥ ነክራ ወዳፏ ከተተችው ። ግን ያውቃል ። ግሚ ከምትናገረው ውስጥ በጥቂቱ ዕውነት ሳይ ኖር አይቀርም ። ዕውነት አላት ። ምክንያቱም ኤለን እናቷም በተለ ያየ ጊዜ በሚያምር ቃናና በተመረጡ ቃላት ይሆንኑ ዕውነት ደጋ ግማ ነግራታለች ። በርግጥም ደም የሴቶች ጓደኞቿ እናቶች ልጆ ቻቸው ወንድ እንዴት እንደሚጠኑ ፣ እንዴት እንዴት እንደሚግ ደረደሩና እንደምትታደን ጥንቸልም እንዴት ዓይናቸውን ማቁለጭ ለጭ እንዳለባቸው በቅጡ ለማስተማር ይሞራሉ ። እንዲህ ያለውን አስተዳደግ ለልጅ ለማሳየት ፣ አርሞና ኮትኩቶ ለወግ ማረግ ለማ ብቃት መቼም ትልቅ ብስለትና ልምድ ያስፈልጋል ። ከባድ ነገር ነው ። ምናልባት እሷ ድርቅ ያሰች በመሆኗ ሊሆን ይችላል ያል ገባት ።

አንዳንዴ በዚህ ጉዳይ ሳይ ከአሽሌይ ጋር ትከራከርና የልባን ትጎግረው ነበር ። ምናልባትም ይሄ ችኮነቷና ስለሽርሽርና ስለግል ቢያ ያላት እጅግ ጥጥ ያለ የደስታ ስሜት ሳይሆን አይቀርም አሽ ሌይን ወደ ደካማዋና ሁሉን አሽዋ ሚላኒ አንዲሄድ ያስገደደው ። ወይ ዘዴዋን ትቀይርና በሌላ መላ ልታጠምደው ትሞክር ይሆን! አይ እንዲህ በተጠና የሴት ወጥመድ ውስጥ የሚወድቅ ከሆነማ አሽሌይን እንደ ዱሮው ላትወደው ነው ። ግንም ወንድ" ሞትከኝ እንዴት ውብ ነህ የኔ ማር ወለላ ነህ ነው ልልህ" ለምትል ግልፍ ጥና ደካማ ሴት ከተሸነፈ ሁለተኛ ዓይኑን ማየት አትሻም ። የሚገ ርመው ግን ወንዶቹ ሁሉ የዚህ ፈሊጥና መጭበርበር ተገዢዎች የዚህ የሽንገላ ልማድ አፍቃሪዎች ሆነው መገኘታቸው ነው ።

ቆይ እሺ ፣ ባለፈው ጊዜ አሽሌይ ላይ የተጠቀመችበት ዘዴ ስህ ተት ከሆነ . . . ዳሩ ምን ያረጋል አሰፈ ። ተበላሸ ። አሁን ማቀድ ያለ

@OLDBOOKSPDF

ባት አዲስ ዘዴ ነው ። ትክክለኛውን ዘዴ በጣም ትፈልገዋለች ። እጅግ በጣም ፈትዳዋለች ። እሱን ለማግኘት ያላት ጊዜ ግን ጥቂት ሰዓት ብቻ ነው ። ጥቂትና ሙድ ሰዓት ። የራባትን አሽሌይ አግኝታ ለመጥገብ ዕድል የፈቀደላት ጥቂት ሰዓት ብቻ ። ምን ብታደርግ ይሻላታል ። እሱን በጅሞ ለማግባት የሚያዋጣው ዘዴ ሙትት ፍስስ ማለት ከሆነ ሙትት ፍስስ ትልለታለች ። መሸንገልና ማስመሰል ፣ መግልፈጥና ማስክኳት ፣ ደደብና ደንቆሮ መሆን እንዲሁም ‘መያድ ኩህ አበድኩልህ’ ማለት የሚያዋጣ ከሆነም ከካትሊን ካልቨርት የባሰች ሞኝ እንግስ ደንቆሮ ሆና ትቀርብለታለች ። ድፍረት የተሞላና ዓይን ያወጣ አቀራረብ ካስፈለገም እንደመላ ቅጡ ትሆን ለታለች ። ብቻ በእቅሚም ፣ ከእቅሚ በላይም ባለ ዘዴ ሁሉ አሽሌይን የራሷ ለማድረግ የሚበጃትን መላ ሁሉ ያሙጭኝ ትላለች ። በለስ የሚቀናት ቀን ይህ የዛሬው ብቻ መሆን አለበት ። ዛሬ ይገኛል ወይም ለዘለዓለም ያመልጣል ! በቃ!

የሰው መሄጃ መንገድ ይገርማል ። የሚገራት ጠፍቶ ነው እንጂ እስካርሌት እሃራ እኮ ያላንዳች ማስመሰል ፣ ያላንዳች ወንድን የመሳቢያ ሽፋን ፣ ውበና ብሉኝ ብሉኝ የምትል ልጅ ነበረች ። ዳሩ ማን ይንገራት ። እርግዋ ቢነግሯት በጣም ትደሰታለች ። ግን አታምንም ። ይሄ እሷ የምትኖርበትም የሥልጣኔ ዓለም አያምንም ። ምክንያቱም- መቼም ሆነ መቼ ፣ ጥንትም ይሁን ዛሬ ፣ የሴት ልጅ የተፈጥሮ ውበት ብቻ ከሁሉም በልጠና ራሱን ችሎ የቁንጅና አርማ ይሆናል ብሎ የሚያምን ዓለም ስላልሆነ ነው ። ያልተነካካ ፣ ያልተቀባባ ፣ አጅ አጅ ያሳለ ፣ ንፁሕና የተፈጥሮ ንጥር ውበት መች የሚዋዋለት ዓለም ነውና !

ሠረገላው የቀዩን አፈር መንገድ ያዙ ቁልቁል ወደ ዊክሶች እርሻ መንደር እስካርሌትን እያከተራተሩት ነው ። የአናቷና የማሚ አብረዋት አለመምጣት እስካርሌትን ሐሴናሞን የሚቅበጠበጥ የተሰረቀ ደስታ እንዲሰማት አደርጓታል ። እንደራሷ ከምትወዳት እናቷና እንዲልጅዋ ከምታያት ሞገዚጂ ተሸሽጎ ፣ ራሱን መውቀሱን በማይተው ሐሴና ጨርቅ ተጠቅልሎ የተሰረቀ የግሷ ደስታ! ከእንግዲህ በመላ የነደፈችውን ፕላን የሚያታውስ ፣ በዝግታ ከፍ ዝቅ እያለ የሚቆጣት ትንሽብም ሆነ በኩርፊያ የሚዘረጋ ጥቁር ክንፉ እግብግው በታ አያጋጥማትም ። በርግዋ ያቺ መጠ አሀጂ ሱዊለን ነገ ሜራና ቀንድ ጨምራ ትዘገዘክላታለች ። ነገር ግን እስካርሌት ያሰበችው ይመላላት እንጂ ፣ በሷ ወሬ ከሚመጣው ቁጣ ይልቅ አሽሌይን የማግባቷ ነገር ግራ ያጋባቸውና ሚዛኑ ወደሷ አሸናፊነት ያጋድላል ። አቤት ዕድሏ ዛሬ! እንኳንም ኤለን ተጎፍታ አለች እንድትቀር ተደረገችላት ።

@OLDBOOKSPDF

ጂራልድ ራሱን በጠዮት በብራንዲ አጋግሎ ፥ ገና ሳይነጋ ጆናስ ዊልክርሰንን ከሥራ አባርሮታል ። ኤለን ሰውየው ከመሄዱ በፊት የጥቂ እርሻቸውን ሂሳብ ሙል ለማስያዝና ለማስላት ብላ ነው ግብግቡን ትታ ታራ የቀረችው ። እስክርሌት በጠባቂ ጽ/ቤት ውስዋ እናቷን ደህና ሁኚ ብላ የተሰናበተችት ፥ ኤለን በወረቀት በተሞላ ዶሴ ፊት ለፊት እንደተቀመጠች ነው ። ጆናስ ዊልክርሰን ባርሚጣውን በጁ ይዞ ከጀርባዋ ቆሚል ። እንዲህ ባለ ወግ በሌለውና ውርደት በተሞላ ሁኔታ ከመንደሩ ሀብታሞች ሁሉ እጅግ ከናጠጠው ሀብታም ቤት ፥ ከምስለኔነት በመባረሩ ፊቱ ገርጥቷል ። በገረጣ መልኩ ውስዋ ሊደበቀው የፈለገው ቆሽት መድበንና ጥላቻ ደህና አር ገው ካዩት ፏ ብሎ ይነበብበታል ። ይሄ ሁሉ የደረሰበት ደግሞ በት ንሽ ጥፋት ነው ። አሚ ስላተሪ ከሚንም ልጅ ልትደትል እንደም ትችልና ከሱ መውለዷ በጣም ትልቅ ጥፋት እንዳልሆነ ሰጇራልድ ለማስረዳት ደጋግሞ ሞክሮ ነበር ። ይህ ልመናው የጂራልድን ልብ አራርቶለት ነበር ። ኤለን ግን ፍንክች ያላ ቢላዋ ልጅ አለች ። ጆናስ የደቡብ ተወላጆችን በሙሉ ይጠላቸዋል ። ተዘቅዝቅ ብለው እየተለላለሱ ሊያግባቡት መሞክራቸውን ስለሚያውቅና በሆሳቸው ግን የሱን በነሱ ላይ በምስለኔነት መሾም መቃወማቸውን ስለ ሚገባው እጅግ በጣም ተከፍቷል ። በደቡቦች ላይ የሚጠላው ባህሪ ዋና ወኪል ፥ እንደጣአትም የምትመለክ ቤት አለን አየራ በመ ሆኗ ፥ ከምንም በላይ እሷን ዓይትሽን ሳፈር ይላል ። የሷ ነገር ያን ገሸግሸዋል ።

ማሚ የጥጡ እርሻ ሐላፊ እንደመሆኗ ኤለንን ለመርዳት እዛው ቀርታለች ። የሴቶቹን የዳንስ ቀሚስ እጭኗ ላይ ይዛ ከሹፌሩ ከዮቢ ጐን ተቀምጣ የምትሄደው ዲልሲ ናት ። ጂራልድ በብራንዲ እንደ ጋለ በእደን ፈረሱ ላይ በኩራት ገብ ብሎ ከሠረገላው ጐን ጐን ይጋ ልባል ። ዊልክርሰንን በሥራው ዐያፍ ሥራ እንዲህ በዮሎ እንዴባረር በማድረጉ እጅግ በጣም ጥንድትድት ብሏል ። በቦታው ኤለንን ተክ ኖ ሐላፊነቱንም ለፀ.ው ሰዮቶ እርይ ማለቱን እንጂ እሷ ከግብግቡ በመቅረቷና ሴቶች ጓደኞቿን ለማየት የነበራትን ጉጉት መሚኑን ከገ.ጸይም አልጣፈው። ለሱ የታየው ደስ የሚል የወደዱትን መሆኑና እርሻዎቹ ሁሉ የተሞቡ መሆናቸው፡ ወፎቹም መዘመራቸው ነው ። ከዕድሜው በጣም አንሶ እንደገና ጐልማሳ የሆነ መሰለው ። በጣም ፍንጥዝጥዝ ከማለ ቱም የተነሳ ስለማንም ማሰብ ተስኖታል ። "ፔጣ ኢን ኤ ሎው ባክድ ካር" የተሰኘውን የአየርላንዳውያን መዝሙር አንጻንዴ በፎክታ ይዘም ረዋል ።ወይም ደሞ የሮበርት ኢሚትን አሳዛኝ ቅላጼ — "ሺ ኢዝ ፋር ፍሮም ዘላንድ ዌር ሽር ያንግ ሔሮ ስሊፕስ — (" ወጣቱ

@OLDBOOKSPDF

ጅማናዋ ከተሻበት ምድር እጅግ በጣም ርቃ ፣ ውሷ ትኖራለች እንደ ከከብ ደምቃ ") የሚለውን ዜማ ይዶጋግማል ።

ቀኑን ሙሉ ስለያንኪዎችና ስለመርኑቱ ሲያወራ እንደዋለ እያስ ታወሰ በጣም ተደስቷል ። ከወገብ በታች ቡፍ ብለው የሚታዩ ደማቅ ቀሚሶች የለበሱ ቆንጆ ቆንጆ ሴት ልጆቹን ከባለጌው ግንጥላ ሥር ሲያይ ደግሞ ከፍተኛ ኩራት ተሰምቶታል ። ኮርቷል ። ተኩፍሏል ። ትላንትና ከእስካርሌት ጋር ስለተነጋገረው ነገር ቅንጣት ታህል አያስታውስም ። ሁሉም ሙልጭ ብሎ ከጭንቅላቱ ጠፍቷል ። ረስቶ ታል ። አሁን የሚያስበውና የሚያስተውሰው ነገር ቢኖር ይህ ቀረሽ የማትባል ቆንጆ ልጅ መሆኗንና የሷ አባት መሆኑ ታላቅ ዋጋና ክብር እንደሚያስጠው ብቻ ነው ። እና ዛሬ እነዚያ የሚያሣምሩ ደንቅ አይ ኖጅ እንደ አየርላንድ ተራራዎች ማራኪ መሆናቸውን እያየ ፈገግ አለ ። ያሄ በመጨረሻ ያስፈገገው ሀሳብ ስለራሱ ምርጥ ሰውነት እን ዲያስብ አደረገው ።ምክንያቱም ከዚያ አረንጓዴ ተራራ ጋር የሚታ ወሰውና ከትውልድ ሐገሩ ጋር የሚያስተሳስረው አንድ ቅላጼው ያማረ የደወል ዜማ ጆሮዎቹ ላይ ያንኮሮላልና ነው ። ይህንን ዜማ ከቅኝቱ እስኪወጣ ድረስ እየጮኸ ሰሴት ልጆቹ እያሰማ የትላንት ደስ ታውን ያጋራቸው ጀመር፡— "ዘ ዌሪንግአፍ ዘ ግሪን" — ("ምድር አረንጓዴ ሲለብስ").....የሚለውን መዝሙር ዘመረላቸው ።

እስካርሌት ፣ እናቶች ስሚቀብጥ ባለጌ ልጅ ባሳቸው የፍቅርና የጥላቻ ዓይን እያየችው ወደ አመሻሹ ላይ ጥምብዝ ብሎ እንደሚሰክር ታመቀች ።እና ማታ ሲመሰስ እንደተመለደው "አበሥራ ሁሉቱ ዋርካ ዎች" መናፈሻና በታራ መካከል ያለውን ማንኛውንም አጥር ሰመ ዝለል እንደሚሞክር ታስባት ። መቼም እንደወትሮው የሰማይ እም ላክ የልቡን ቀኖንት አይቶ ከልጠበቀውና የፈረሰ አስተዋይነት ካል ተጨመረበት ወድቆ እንክትክቱ ከመውጣት እንደማይድን ታውቃ ለችና በለስ እንዲቀናው ተመኘችለት ።ድልድዮን ሁሉ ቁልቁል በን ቀት እያየ ፣ የሞላ ወንዝ ሁሉ ፈረሱን እያስሞኝ እያጋረጠ ይጋልብና እየጮኸ ወደ ቤት መሞቱ በልቡ ቢሮው ሰፋ ላይ ፓርክ ተሸነሞ ያስተኛዋል ። እንዲህ ያለ ግብግ ባለ ቀን ሁሉ ፓርክ ፋናስ ይዞ ከዳራሹ ፊት በር ላይ ቆሞ መጠበቁን ልማድ አድርጉታል ። ትላንት የገራው የዛሬ አሽከር !

በነጋታው አዲሱን ግራጫ ሱፍ ልብሱን ሆነ ብሎ ያበላሸዋል ። ጠዋት ለመግል ለመሣዙት እንዲመችውና ፈረሱ እንዴት ድልድይ ላይ በጭለማ እንደጣለው በረሸመ በመተረክ ፡ ኤለንን ለማሳመን ሲል ነው ። ግልጥጥ ያለ ውሸት ። ማንንም ሊያታልልበት የማይችል

@OLDBOOKSPDF

የጅል ውሸት ። ደግነቱ ሁሉም የቤተሰቡ አባላት በዚህ ውሸት የተታለሉ በመምሰል ብልጥ የሆነ እንዲመስለው ያደርጉታል ። በደስታ ራሱን ይገብዛል ።

አባባ እኮ ታላፊነት የማይሰማው ፣ ግዴለሽ ፣ ራሱን በጣም የሚወድ ግን ግሩም አባት ነው ፣ ብላ አሰበች እስክርሌት ፣ ለሱ ያላት ፍቅር ሙስጢን እያሞቃት ። ዛሬ ጠዋት በጣም ከመደሰቷና በስሜት ከመጥለቅለቋ የተነሳ ዓለምንም እሱንም እመውደዷ ማህደር አግብታቸዋለች ። ዛሬ በጣም ቆንጆ መሆንዋን አውቃዋለች ። ስለዚህ ገና ጀንበር ዘቅዝቅ ሳትል እሸሌይን በጅዋ ታገባዋለች ። ፀሐይዋ ሰብ ያለ ሙቀትዋን ታፈስ ባታስች ። ዝንኛው የጀርጅያ ፀደይ እንሆ አሬቷ ከነማርማ ሞገሱ ፪ ብሎ ተዘርግቶ ፍንትው ብሎ ይታያታል ። በመንገዱ ሳርቻ ላይ ያሉት እንጀይ ዘርች ሰስላሳ ፣ ለምለም አረንጓዴ ቅጠሎቻቸውን አንዣርገዋል በሸረሞቱ ዝናብ የተሰነጠቀውን ቀይ ጉድባ ሸፍነው ፣ ከአይን ደብቀ ውታል ። ቀፎን አፈር ሳናቆ የመጣውና ራቁት ደረቱን ግልጦ የቆመው ጥቁር የባልጭት ድንጋይ ፀደይ የፈለፈሳቸውን የቹሮኪ ሮዝ አበቦች ፍንጥጥጥቅ ቀሚስ ለብሶ ፣ ከማርጌው በወይን ጠጅ አበቦች ጥለት ተንቆጥቁጧል ። ከወንዙ በላይ ጫካ ለብሰው የቆሙት ጋራዎች የደጣውድን ነጫጭ አበቦች እንደአንጥት ልብስ ጠምጥመው ሲያ ቡ ፣ አረንጓዴወን ዛፍ ከሁንም በረዶ አልለቅም ብሎ የመጥኛ ያለው ይመስላል ። አበባ አንዳቸን የሚያፈሱት የክራብ ዛፎች ደግሞ ዕንቡጠቻቸውን እያረሰሱ ። እስክ ዛሬ ያፈኗቸውን ነጭ ኮት በጉልበት እያወለቁ ፣ ጥልቅ ሐምራዊ ሽሚዛቸውን የሚያስ መርቁ ይመስላሉ ። ከነዚህ ዛፎች ሥር እየሰረቀኙ የሶቅጣጣው ፀሐይ አልፎ አልፎ እየፈነጣጠቀኙ በምታሳያቸው ቸምበቆዎች አቅራቢያ ያሉት የጫካ አበቦች ዙሪያውን ተሸምቸሙመው በቁይ ፣ በብርቱካንና በሮዝ ጎብረ ቀለም የተሠራ የአበባ ምንጣፍ የተንጠፈበት ሜዳ አስ መስለውታል ። እዚሁ ውስጥ በስሱ የሚንፍስ ጣዕመ መጫዝ የተጫነ አየር ከባለ ሽቶው ቁጥቋጦ እየተሳበ ይመጣል ። ያ ቁጥቋጦ በተንፈሰ ቁጥርም ሽቱው ዓለምን እያወደ ለሚጠጣ መጠጡን ፣ ለሚበላ መብ ሉን እየባረከ የሰውን ልጅ ፍላጎት ያለመልማል ።

"የዚህን ቀን መጠት አስክምት አልረሳውም" አሉች እስክርሌት በልቧ ። "ማን ያመኖል ሙፍልዳት ይህ ቀን እኩ የሙርጌ ቀን ይሆን ይሆናል ?"

ልቧ ውስጥ ጥያቄ እየተርበተበተ ፣ አፏና አሸሌይ በዚህ በአ በቦች ፈርጥ ባጌጠና አረንጓዴ ልምላሜን እንደፀጉር ባጐፈረቹ ውበት ውስጥ ወይ ባሬወት ክስዓት በኋላ ፣ ወይም ዛሬ ማታ በጨረቃ ፣ በፍጥነት እየተንዱ ወዶ ጀንበሮ ሲጋልቡ ታሰባት ። በዛ ላይ እንድ ቁስ

@OLDBOOKSPDF

ይይዛሉ ። ያው መቼም ጸጋም ሥርጉ በቂስ በተክሊሉ መፈጸም እን ዳለበት ግልፅ ነው ። እሱን ከእትላኑታ እንመስዳለን ። ብቻ ያ እንኳ የኤሰንና የጂራልድ ጭንት ነው ። እሷ ምን አገባት ። ደንግት እንድ ክፉ ሐሳብ ትገ አላት ። ልጅዋ ከሰው ባል ጋር መኮብለሏን ሰትሰማ ኤለን ልቧ ቀጥ ነው የሚለው ። ፊቷ በጥላ ሞት ድንዛዜ ነጭ ኖራ መልበሱ ከሁኑ ታያት ። ብቻ ኤለን የሷን ክፍተኛ ደስታ ስታይ ይቅ ርታ እንደምታደርግላት ታውቃለች ። ጂራልድም መጮሁና አገር ይያዘልኝ ማለቱ ፡ የስደብ መጎት ማውረዱም አይቀርም ። ደግነቱ ዞሮ ዞሮ ምንም እንኳ ትላንት አሽሌይን ማግባቷን እንደማይፈልግ ቢንግራት ፡ በሱ ቤተሰብና በዊክሰኞ ቤተሰብ ማሀል የጋብቻ ዝም ድና መፈጠሩን ሲሰማ ደስ ይሰኛ ንዴቱን ይተዋል ።

"ለዛውም ያ ነጣባው በኋላ የሚያስጨንቀኝ ጉዳይ ነው ።" አለች በልቧ ፡ የሙንቅትን ጉዳይ ከእንቦጳ ገጥታ እያስወጣች ። መቼም በዚች ሉብ ያለ ሙሉት በሚፈጸምባት ቤሐይ ፡ በዚህ ውብ የፀደይ ሰዓት ፡ የ"አስራ ሁለቱ ዋርኳሾች" መኖሪያ ቦታ ጭስ ማውጫዎች አንጣት በወንዙ መሻገሪያ ተራሮች አፍት ብቅ ማለት በጀመረበት ቀን ፡ ዝም ብሎ ደስታን ከሙጉንፊስ ሉላ ፡ በጥ ብሎ ደስታን በደም ሥር ከማ ፀዋወር ሌላ ፡ ምን ለማስብ ይቻላል !

"ዕድሜ ዘለዓለሜን እዚህ ቦታ እኖራለሁ ፡ የዚህ ዓይነት ሀምሳ ፀደዮች ወይም ከዚያ በላይ ማየት አለብኝ ። ለልጆቼና ለልጅ ልጆቼ እንዴት ያለ አስደናቂ ዘደይ እንደነበረ ፡ ከእንግዲህ ከዚህ ያማረ ፀደይ በዕድሜያቸው እንደማያዩ እነግራቸዋለሁ ።" በዚህኛው የመጨረሻው ሀሳቧ እጅግ ከመደሰትዋ የተነሳ ላታስበው እግሩ ከሚጋልበው ጂራ ልድ ጋር "ምድር እንዴዴ ሲለብስ"ን መዘመር ጀመረች ። ጂራልድ ለት ብብሯ ያለውን አድናቆት በጣም በመጮህ አረጋገጠላት ።

"ባሬ ጠጥት ሰምን እንዲህ ደስ እንዳለሽ አልገባኝም" ። አለች ሱዌለን ። ተናዳለች ።

ከእስካርሌት ይልቅ የዳንሱ አረንጓዴ ልብስ እሷ ብትለብሰው ከባለ ቤታ በላይ እንደሚያምርባት እያሰበች መልበስ ባለመቻሏ በሽቃለች ። እቺ እስካርሌት ለምንድነው ልብሶቹንና የፀጉር ጌጧን ለሰው ማሞስ የምትሰስተው ? አንዳንዴ እንኳ እንዴት እሺ አይባልም ? እናቷስ ለም ንድነው አረንጓዴ ለሱዌለን የሚሆን ቀለም አይደለም እያለች ለሷ እምታግዘው ? "የአሽሌይ ቀለበት ዛሬ ማታ በደፋ እንደሚገለፅ እን ቺም እኔም እናውቃለን ። አባባ ራሱ ነው ዛሬ ጠዋት የተናገረው ። ታዲያኮ አንቺና አሽሌይ ለብዙ ወራት የቅርብ ወዳጅች ነበራችሁ ።"

@OLDBOOKSPDF

"እንቺ ያን ብቻ ነው የምታውቂው" አለች አስካርሌት ፤ አልበ ሽኩም ለማለት ምላሷን እያወጣችባት ። አቤት ነገ ጠዋት ይሄኔ ሱዊ ለን እንዴት ይገርማት ! !

"ተይ እንጂ ሱዚ ያ እንዳልሆነ ልብሽ ያውቀዋል !" አለች ካሪን በመታወም ፤ በመደንገጥም ። "አስካርሌት ብሬንትን እንደምትፈልግ የታወቀ ነው ።"

አስካርሌት በፊጣኝ የተሞሉ ፤ እንደኩል የጠሩ አይኖቿን ወደታናሽ እህቷ መረመረቻቸው ።እንዴት ሰው እንደዚህ እንደሚወዳት አስባ ገረማት ። የካሪን የአሥራ ሶስት ዓመት ልብ ለብሬንት ታርሌተን ፍስስ ቅልጥ እንደሚል ድፍን ቤተሰቡ ያውቃል ። ብሬንት ደሞ ስለ ካሪን የሚያወቀው ነገር ቢኖር የአስካርሌት ታናሽ እህት መሆ ነኗ ብቻ ነው ። ኤለን በለሊት ጊዜ ካሪን ዕንባ አሙጥታ አስክታሰቅሰ ድረስ ብሬንትን እያነሱ ያበሽቋታል ።

"የኔ እመቤት ፤ እኔ ስለብሬንት ይችን ታህል ግድ አይሰጠኝም ።" አለች አስካርሌት በለታስነኗ ደስታ እየተሰማት ።

"እሱም ስለኔ ደንታ አይሰጠውም ።ይልቁንስ እንቺ አስክታድ ጊለት ነው እሚጠብቀው !"

የካሪንን ክብ ፊት ሐምራዊ ቀለም ወረሰው ። ደስታና ጥርጣሬ እፊቷ ላይ ትግል ገመሙ ።

"እውነትሽን ነው አስካርሌት ?"

"አስካርሌት ፤ አስቲ ምን መሆንሽ ነው ? እማማ ፤ ካሪን ስለፍቅ ረኛ ለማሰብ ገና ልጅ ናት" እያሰኝ አየገረሽን ፤ ያንቺ እጭንቅላቷ ውስጥ እንዲህ ያለ ሀሳብ ማስገባት ምን ይባላል ?"

"እንግዲህ እንዳሻችሁ ሰፍልፉ ። አስቲ እኔ ይችን ታህል ይሰ ማኝ እንደሆን ታያላችሁ ። "አለች አስካርሌት መልስ በመስጠት ።" እናንተ ካሪንን የምታከላክሉት ከእንድ ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በቁንጅና አጥፋችሁ እንደምትሄድ ስለገባችሁ ነው ።"

"እንቺ ልጅ እንግዲህ ምላስሽን ሰብሰቢ ጓላ ። አለዚያ ዋ ! አቶ ምስሻለሁ ።" የቁጣ ማስጠንቀቂያ ሰጣት ጄራልድ ።

"አስቲ አንዴ ዝም በሉ ! ምንድነው ይሄ እምሰማው ? የሰረገላ ድምፅ አይደለም እንዴ? ወይ ታርሌተኖች ወይ ሮንቱኖች መሆን አለባቸው ።"

@OLDBOOKSPDF

የመንገዱ መጓናኛ አጠገብ እየደረሱና ከጫካው አቀበት ቁል ቁል እየበረሩ ሲሄዱ ፥ ከወደ ሚሞሳና ፌርሒል የፈረስ ኩቴና የሠረገላ ድምፅ በጣም ግልፅ እየሆነ መጣ ። ከዛፎቹ ጀርባም የሴቶች ፍንዳታና ሳቂታ ድምፅ ገኖ ይሰማ ጀመር ። ጂራልድ ከሁሉም ፊት ፊት እየጋለበ ቆየና ቶቢ ሠረገላውን አራትያው መንገድ ላይ እንዲያቆም አዘዘው ።

"የታርሌተን ቤተሰብ ሴቶች ናቸው ።" አለና አሳወቀ ። በጣም በደስታ በተሞላ ድምፅ ሥላ ብሎ ። መቼም ከመንደሩ ሲቶች ሁሉ ከአለን ቀጥሎ በጣም አድርጐ የሚወድደው ባለ ቀይ ፀጉሯን ታርሌተንን ነው ። ፊት ለፊት ከልጓሙ ትይዩ የምትታየው ደሞ እሷ ራሷ ናት ። መቼም ፈረስን ቀጥ ሰጥ አድርጐ ለመምራት የተፈጠረ እጅ እሷ ዘንድ ነው ያለው ! ሳይን ቅለል ያለ ፥ እንደእርጥብ ቆዳ ጠን ካራና ሲስሙት ውለው ቢያድሩ የማይጠገብ ቁንጅና ያለው እጅ!" ከናንተ ውስጥ እንደዚህ የተሞበ እጅ ያላት ሴት አለመኖርዋ በጣም ያሳዝናል" አለ ቀጠለና ። በፍቅር ዓይን ያያቸዋል ፥ ግን ጉድለታቸውን የመናገር ድፍረቱ አልተለየውም ።

"ካሪን ስራሷ ቸምታታና ቡቡ ናት ። ሱዌለንም ብትሆን የእጅዋ ልስላሴ የአንጀራ ጠርዝ የሚቀድደው ነው ። ኤንቺም ብትሆኚ የማትረቢና . . . "

"ያምሆነ ይህ ፡እኔ እንደሆን እንደርካሽ ሴቶች የተጣልኩ አይደለሁም"አለች እስካርሌት በሃም ፍላት ።" ደሞ ወ/ሮ ታርሌተን አራሳቸው እንኳ አደን ሲሄዱ በመከረ የሚያልሙ ሴት ናቸው ።

"ታዲያኮ ከተኮሰች እንደወንድ ማሀል አጓዳ የምትለያይ ናት ። መርበትበት የለ ፥ ደክሞኝ የለ ። በሉ ዝም በሉ ያቻት እራሷም መጥታለች ።"

የታርሌተን ቤተሰቦች ደማቅ ደማቅ ልብሶቻቸውን ለብሰውና ጂራልድ እንደገመተውም ታርሌተንን እንደታቦት ሠረገላው ሠግነት ውስጥ አስቀምጠው ሲመጡ ፥ ጂራልድ እርካቡ ላይ ቆሞ ፥ ከፈረሱ ብድግ ብሎና ባርሚላውን ክፍ አድርጐ እጅ ነሳ ። ወ/ሮ ታርሌተን አራቱን ልጆቿን በግብግ ቀሚሶቻቸው እንደተንቆጠቆጡ ከነሞዛ ታቸው ይዛ ፥ ሠረገላውን በሳጥን በሳጥን መልክ በተሠሩ ካርቶኖች አጅባ ብቅ ስትል ፥ የሠረገላው ሹፌር መኰሚያ ቦታ እንዳጣ በግልፅ ይታይ ነበር ። በዚህ ላይ ሞገደኛዋ ቢትሪስ ታርሌተን ሁለት እጆቿ በጠና እስኪሉ ድረስ ማንም ገና ያለ ሰው — ጥቁርም ሆነ ነጭ ልጓሙን እንዲነካ የምትፈቅድ ሴት አይደለችም ። ቢትሪስ ምንም እን

@OLDBOOKSPDF

ኳን ቀጫጫና ለቋሳ ብትሆንና ፣ ፀጉሯ እንኳ ሳይቀር የስስ ፊቷን ቀለምና ባህሪ የወረሰ ቢመስል ፣ ፍፁም ጤነኛና ጉልበተኛነት የሚለማት ሴት ናት — የስምንት ልጆች እናት ያውም ሁሉም እንደኗ ቀይና ህይወት የሞላቸው ናቸው ። የመንደሩ ሰው — እንዲህ በተሳካ ሁኔታ ልጆቿን ለማሳደግ የቻለችው ፣ ለፈረሰው የምትሰጠውን ፍቅር ያህል እንኳ ስለማትሰጣቸውና ወዲያውም በጠንካራ ዲሲፕሊን አንጻ ስለምትይዛቸው ነው ይላል ። "መቆጣት መቅጣት ያስፈልጋል ፣ ግን ቅስማቸው እስኪሰበር ድረስ መሆን የለበትም" ትላለች ወ/ሮ ታርሌተን ። ልጆች የማሳደጊያ መመሪያዋ ይኸው ብቻ ነው ።

ፈረስ በጣም ትወዳለች ። ወሬዋ ሳይቀር ስለፈረስ ነው ። ፈረሶች በጣም ይገቧታል ። ከማንኛውም የመንደሩ ነዋሪ የተሻለ ልትንከባከባቸው ፣ ልትገራቸውና ልታለምዳቸው ይቻላታል ። የፈረስ ግልገሎች ደጅዋ የሚራኮቱትን ያህል ስምንቱ ልጆቿ እንኳ በዚያ በኮረብታ ላይ በተንጣለለ ቤቷ ውስጥ አይሯሯጡም ። በእርሻ ቦታዋ ውስጥ ስትዘዋወርም ወንዶችና ሴቶች ልጆችዋ ፣ የፈረስ ግልገሎቿና አዳኝ ውሻዎችዋ ትልቅ እጅብ ሠርተው ይከተሏታል ። ፈረሶቿን — በተለይም ቀይ በቅሎዋን ኔሊን እንደሰው ማስተዋያ አዕምሮ ያላቸው እንሰሳት አድርጋ ታያቸዋለች ። የቤት ውስጥ ሥራ በጣም በዝቶ ጊዜ ያሳጣት እንደሆን ፤ አንድ ትንሽ ባሪያ ጠርታ የስኳር እርቦዋ ላይ እህል አድርጋ ፣ "በል ለኔሊ በእፍኝህ እየዘገንክ አብላት ፣ ሰሥራ ጉዳይ ወጥቻለሁ ቶሎ እመለሳለሁ ፤ በላት ።" ትለዋለች ።

በጣም የተለየ አጋጣሚ ካልሆነባት በስተቀር የግልቢያ ልብሷን ሁልጊዜ ትለብሳለች ። ግልቢያ ቢኖርባትም ባይኖርባትም መጋለቢ አይቀርም ብላ ስለምታምን ልትወጣ ስትነሳ የፈረስ ግልቢያ ልብሷን ትለብሳለች ።

የገናብ ቀንም ይሁን ብራ ቀን ሁልጊዜ ጠዋት ጠዋት ኔሊ ኮርቻ ተጭና ከቤቱ ፊት ለፊት ወደላይ ወደታች እየተዘዋወረች የእመቤቷን የወ/ሮ ታርሌተንን ከቤት ሥራ ተለይታ መምጣት ትጠባበቃለች ። ሆኖም የፈይር ሐል የእርሻ ቦታ ሥራ እንዲህ ውልፊት የማያስደርግና ለመገናኘት ጊዜ የሚሰጥ ባለመሆኑ ፣ ኔሊ ኮርቻዋን እንደተጫነች ፣ በመጣምሪ እንዳቆመች ትዕግሥት ባጣ ጥበቃ ወዲህ ወዲያ ስትንቀሳቀስ ፣ ወ/ሮ ታርሌተን ደግሞ የግልቢያ ሠሪዋን እክንዱ ላይ እንዳንጠለጠለችና አዲስ የግልቢያ ቦት ጫማዋን በጅዋ እንደያዘች ያለእረፍት ትራወጣለች ።

ባሬ ግን ፣ ከጠባብ ሥሪዋ በላይ ጥቁሩን የሐር ቀሚስ ለብሳና በግራ ዓይኗ በኩል ዘመም ያለ ኋባ መሰል ጌጥ ያለውን ጥቁር

@OLDBOOKSPDF

ባርሜጣዋን አድርጋ ልክ እንደወትሮዋ ለአደን የወጣች ትመስ ላለች ።

ጂራልዶን ስታይ አለንጋዋን አውናጭፋ እንደናንክ በሚቀጣው እንቅሥቃሴ አሠሯቸውን የሚያራክቱትን ፈረሶች አቁመቻቸው ። ሰረገላው ላይ በስትዳላ የተሞሙጠት ሴቶች ልጆች ከተቀመጠበት ዘልጣ ብለው እንግታቸውን ብቅ አድርገው በደመቀ ሁኔታ ሞቅ ያለ ሰላምታ አቀረቡ ። ሰላው ወገን በደንገተኛነት እየተደናገጠ አመ ላሙን መለሰ ። እንደውም ዝር ሉም ለሚያስተውል ሰው እንዚህ ታር ሰተኞች ለዓመት ሁለት ጣሙት ከፈሃራዎች የተለዩና እንጂ ግን ሁለት ቀናቸው አይመስልም ። ብዙ ታርሰሁኖች በጣም ጥሩ ቢሁ ስብ ናቸው ። ከረበቶቻቸውን ይወዳሉ ። በተለይም ለአሃራ በተበበ ሴት ልጅች ያላቸው ፍቅር እጅግ የጠለቀ ነው ። ከረንና ስዊስንን ሰ.መ.ቻቸው መዙም እንደሁድ ነው ። ኔዘም ይሁን ያ ፣ ከመንደራ ሰው ሁሉ ከዘያች ከቅል ራስ ከሰጉሊን ከልቨርት በሰተቀር አሰከርሴትን የሚወድ ማነም የለም ሠ

በዘን በዘን የመነደሩ በዙ ማብሞና ሽርሽር ማዘንጀት ይመ ጸል ። በ,ንስ ከሕሙንት ሕንዶ, በአማኒ ይዘ,ንሽል ። እነዘያ ወጉ ቀያጅ የታርሰትን ቤተሰብ ሐጅች ረንጠዚያና ፈሽታ አጅግ ከመው ደሰችው ያቀነሳ እየሠንጭን ፈሽታ ሲዝናንበት ከዘህ በፊት ሴሳ ፈሽታ አይተው የሚያጠኩም አይመስሉም ።

ታዲያ ዛሬም እንዲህ ሰአራት አንድ ጠባብ ሠረገላ ክፍል ውስጥ ተጣብቀው ተቸግረዉበት ፣ ቀሚሳቸው እስኪ,ጨማደድና ባለጽጌረጻ ጌጡ የሠለኖ መሰባሰያ ባርሜጣቸው ጌደስበርስ ቡቲጋሬት ቂጥር ዙሪ ያውን ያንዘረዘሩን ጥቁር ሀር ጥብጣብ አንዱ ካንዱ እስኪጠሰለፍ ድረስ ፤ እየተጓተሙ መጥተዋል ። ከባርኔጣዎቻቸው በታች የቀይ ወጉር ዓይነት ተደርድሯል ። የሐሩቲ ሽር ቀይ ወጉር ። የነሚላ አንጀሪ ቀይ ወጉር ። የራዳ የመሳጠ ቀይ ወጉር ። የትንሿ ቤትሰ ካሮት መሳይ ቀይ ራስ ። ሁሉም የጭዱ ዝርያዎቹን እንደጉረር ሰብስው ተቀምጠዋል ።

"መልካም የቅንጅ ከምችት አዘጅተሻል አሚቱ" አለ ጂራልድ ፍርጥም ብሎ ፣ ፈረሱን በሠረገላው ጉን ሳይ እያሽረ ። "ሦኖም እንደእና ታችው ለመሠን ገና ብዙ መንገድ ይተራቹዋል ።"

ወ/ሮ ታርሴሁን ወደ በና የሚያደሉ ቀያይ ዓይናቸውን ዘወር ወር እያደረጉትና የታችኞው ከንፈሯን እየመጠጠች ነጀንን ሚታነነ የሞላው አድናቂነን ከሽፎጭ ቀላቅላ አቀረበችው ።

"አንቺ እማማ እንባይህ ይዘን ሽመጥሽን ተይ ፤ አለባ ለአባባ ነው የምንሳረው ። አዩ አባባ ጂራልድ ፣ አሳ, እኮ እንደርሶ ያለ ቀንጅ ወንድ አጠባቢ ነዩች ፣ በሞራሽ አታስቀምሰንም ።"

@OLDBOOKSPDF

በዚህ ድንገተኛ ተረብ እሰክርሌትም እንደሌለቹ ሳቀች ። ብቻ እንደተለመደው ደሃ የታርሌተን ልጅች ከእናታቸው ጋር በደንብ ለመጫወት ያላቸው ነጻነት ቅናቷን ቀስቀሰና የሳቋን ዐታ ወሰደባት ። እነሱ ልጇ ከእናታቸው ጋር ሲጫወቱ ልክ እንደእኩያቸው ነው ። ከአስራ ስድስት ዓመት አንድ ቀንም የዘለሳት አትመስላቸውም ። ሰእ ስካርሌት ፡ እናቷን እንዲህ ያለ ነገር ለመናገር ማሰብ መቼም እንደ ትልት ሐጢያት ያዋርዳል ። እንደእርኩሰት ይታሰባል ። የነሱ ግን እንድ ደስ የሚል ነገር አለው ። ቢሰድቧትም ቢተጅትም ውስጥ ውስጡን የሚያደንቋት ፡ አብረው የሚያስከብሯት በሄ አላቸው ። የመ/ሮ ታርሌ ተን ዓይነት እናት ቢኖረኝ ብላ ታርሌተንን ከኤለን አሰበልጣ ልታ ያት ሞከረች ፡ ብቻ እንዲህ ያለው ልፊያና ቧልት እንኳ ከእናት ጋር አይታሰብም ። ይህን ነገር ባታድርገው እንኳ ማሰቡ በኤለን ፊት እንዴት ያለ አሳፋሪ ተግባር መሆኑን ልቧ ያውቀዋል ። በነዚህ የታደሉ የታርሌተን ሴቶች ሠረገላ ውስጥ እንዲህ ያለ መሳቀቅና ማፈር የለም ። እንደተለመደው ከጐረቤት እከዮቹ በማሳቂ ግራ እሚያጋባ መናደድ ትሮሮዋን እንቃት ።

የሷ ጭቅላት እንኳ ፈጣን ይሁን እንጂ ለመተንተኛ የተሠራ ጭቅላት አይደለም ። ብቻ የታርሌተንን ልጅች በማማሽ ቀልብ ስታ ጤናቸው እንደፈረሰ ግልጋሎቹ ጋጠወጥ ነና እንደ ጥንቸል በርጋጊ ሆነው ያደጉ በመሆናቸው እንድ ወጥ የሆነ ምን ግዴነት ታደላቸዋለች ። በእናታቸውም በአባታቸውም የሰሚን ጅርጂያ ተወላጆች ናቸው ። የለ ሚን ጅርጅያ ዘር ማለት ደማሞ ክዋናሞቹ አበው በእንድ ትውልድ ብቻ የሚርቅ ዝርያ ነው ። ከአራሳቸውም ሆነ ከለአካባቢያቸው ኡርማ ጠኞች ናቸው ። ልክ እንደሚከሰት ቢተ ሰብ ወዴት ወዴት እን ደሚሄዱ አስቀድሞ ተልባቸው ይጎሬቸዋል ። ታዲያ ከአሃራዎች ፡ በማም በተለያዩ መንገዶች ይራራሉ ። እንደ አስክርሌት የዳር አገሩ መሳፍንትና የአየርላንድ ገበሬዎች ዘር ቅልቅል ዝርያ የለባቸ ውም ። እንደሷ በማም ቁጡ ደም በደረታቸው ውስጥ አይፈላባቸውም ። እንደሷ ባለ ለስላሳ እንደበት ቅምጥል መሳፍንትና የድሆቹ መሠሪ አየርላንዳዊያን ቅይጥ ውጠትም አይደሉም ። አስክርሌት እናቷን እን ደልላት ብታከብርና ወዷያውም ደማሞ በጐሯን አየመሳጨረችና ከሷ እየተኩራከረች ብትጫወት ደስ ይላታል ። አርግጠኛው ችግሯ ግን ተጠቃላ ከሁለት አንዱን የመሆንና ያለመሆን ጉዳይ ነው በመን ዶች ፊት የተከበረችና አስተዳደጓ ጨዋ የሆነች መምሰል ሲያምራት በሌላው ውስጣዊ ስሜት ግዴን ደማሞ ለጉንሽ ጊዜ ከተሳሙች ልቧን ሁሉ ከናትፍት የምታደርግ ፡ ዓይናውጣና ደፋር ሴት መሆን ሲከ ጅላት ፤ የመጀመሪያውና የጎለሸው ስሜቷ ይጋጨባታል ።

@OLDBOOKSPDF

"ወ/ሮ አሰን ዛሬ ጠዋት ወዴት ሄዳ ነው?" ብላ ወ/ሮ ታርሴ ጎን ጠየቀች ።

"ያንን የመፈታችንን ምስለኔ ከሥራ ለማስወጣትና ሂሳቡን መተሳሰብ አለብኝ ብላ ነው የቀረችው ። ለመሆኑ ያንቺስ ባለቤት ፣ ወንዶቹ ልጆችሽስ የታሉ ?"

"እ ግና ዱሮ ወደ "አሥራ ሁለቱ ዋርክሾፕ" መናፈሻ ሄደዋል ። የተደባለቀውን መጠጥ መጠን ቀምሶ ለመለካትና አግረመንገዳቸውን ናሙናውን ሊያዩ ነው ። በኔ ግምት ግን እስክ ነገ ጠዋት ባይነክት ጥሩ ነው ባይ ነኝ ። እንደውም ሄጂ ጆን ዊክስን ማሳደሪያ ቦታ ባይኖረው እንኳ ሉሊቱን እዚሁ እንዲያሳድራቸው እነግረዋለሁ ። ወደ ጋጣው ግድም ያሳድራቸው ። አምስት ሰው እንኳ በበኩሉ የሚበላ ይመስለኛ ። ሶስት ግን . ."

ጀራልድ በጥድፊያ ርዕሱን ለመለወጥ ሲል ወሬዋ ውስጥ ጣልቃ ገባ ። የገባ ልጅቱ ኋላ ኋላው እየተከተሉት ካለፈው ክረምት በዊክሶች ግብዣ እንዴት ጥምብርብር ብሎ እንደተመለሰ አስታው ሰው ወሬውን መከታተላቸውን ተገንዝቧል ።

ስለዚህ አቋረጠና ሌላ ጠራ ጀመረ ።

"ወ/ሮ ታርሌተን ባሬ ምነው ፈረስ ግልቢያውን ተውሽው ? እሺን ይዘሽ እየጋለብሽ ካለመጣሽ በጭራሽ አንቺ አትመስይኝም ። በሦ ሜር ኢሊያድ ውስጥ የተላከውን መልክተኛ ስቴንተርን ነው የምት መስይኝ ።"

"መልክተኛ ? ! እሷን ነው መልክተኛ የምትለኝ ? ደሞ ስቴንተር እኮ ጋጋኖ አፍ የእድር ሰፋፊ መሳይ መልክተኛ ነው ። ባይሆን ከወ ንብ በታች ፈረስ ከወጥብ በላይ ሰው የሆነችውን ሴንተርን ብትል ያምርብሃል ። "ብላ አምባረቀችበት ።

"ስቴንተርም አልኩሽ ስንተር ያው ነው" አለ ጀራልድ መላ ሳት ያደነታም ሳይሰጠው ፣

"ያንቺ ድምፅና የጋጋኖ ድምፅ እኩ አንድ ነው ።በተለይማ አሳኝ ውሾችሽን እያነዳሽ ስትጮሂ ቁርጥ አሱን ነው ."

"ይሄው ልሻ አማ ፣ እሷ የነገርኩሽ ነገር ።" አልች ሐቲ ።" ቀበሮ ከሆሽ ልክ እንደጋጋኖ ነው የምታንባርቂው አላልኩሽም ?"

በማሰል ወ/ሮ ታርሌተን ጣልቃ ገባችና ! "ያም ቢሆን መቼም ግሚ ጅሮ ግንድሽን ውሃ ስታስነካሽ የምትጮሂውን ያህል አልጮህ

@OLDBOOKSPDF

ሞሞጂጣ ! ያውም ገና አሥራ ስድስት ዓመትሽ ! ለምን ዛሬ አትጋል
ቢም ስላልከው ግን እሊ በጠዋት ግልገሏን ታጠባ ስለነበር እንዳላስ
ቸግራት ብዬ ነው ።"

"ይገርማል ! እስካሁን ታጠባለቻ ?" አለ ጂራልድ ። የእየርላንድ
ዜጐች ለፈረስ ያላቸው ሩህሩህ ስሜት ዓይኖቹ ውስጥ ቦግ ብሎ
ሲበራ ይታያል ። እስካርሌት ደግሞ የሷን እናትና ወ/ሮ ታርሌተንን
እያወዳደረች በጣም ደነገጠች ። ኤለን በቅሎዎች ግልገሎቻቸውን
ወይም ላሞች ጥጆቻቸውን ያጠባሉ ብላ በጭራሽ አታምንም ። እሪ
ሌላው ቀርቶ ዶሮዎችም እንቁላል ይጥላሉ እንጂ አትልም ። እንዲህ ያለ
ነገር ለማሰብ በጭራሽ ጊዜውም ደንታውም ኖሯ የላትም ። ወ/ሮ
ታርሌተን እንዲህ ያለ ቸልታ በጭራሽ የለባትም ።

"እንድ ኮሳሳ ግልገል አይደለች ?"

"የለም ቆንጆ ትንሽ የፈረስ ግልገል ነው ። የእግሯ ርዝመት
ሁለት ያርድ ነው ። ጋልበህ መጥተህ ማየት አለብህ አቶ ጂራልድ
እውነተኛው የታርሌተን ቤተሰብ ፈረስ እሱ ነው ። የወገኑ ዘጣ
ነት ራሱ ልክ እንደሔቲ ፀጉር ነው ።"

"እሪ ሁለመናው እንደሔቲ ነው" አለች ካሚላ ወዲያው ሔቲ
ቅስ ብላ ውስጥ ለውስጥ ድብን አድርጋ ብትቆነጥጣት አሪ ብላ
ቀሚሷ ሁሉ ትርምስምሱ እስኪወጣ ድረስ ዘለለች ። "ግልገሎቿ
ሁሉ ንብሳቸውን እየተመገቡ ነው ዛሬ ።" አለች ወ/ሮ ታርሌተን ።
"የእሽሌይንና የዚያችን የአትላንታሞን የእስስቱን ልጅ ፍጥምጥም
ከለማንበት ሰዓት ጀምረው በእግራቸው መሬቱን እየጫሩ "መሄድ
መሄድ አለኝ" ሲሉ ነበር ያረፈዱት ። ግን ነበረ ስሚ እቱ ! እምን
አምን ሚላኒ ! እግዚሃር ይባርክት ! ውነጅዬ ትንሽ ልጅ እኮ ናት ።
ብቻ ይሽው እግዚሃር ምስክሬ ነው ! ስሚም ሆነ መልኳ አሁን እን
ዴም ትዝ አይለኝም ። ያ የኛ ወጥ ቤት የዊከሶኞን ገረድ ያገባል ።
ታዲያ ፍጥምጥሙ ዛሬ ማታ ሰየሰው እንደሚነገር ትላንት ማታ
አውርዶልን ነበር ። እኛ ጠዋቱኑ ሰማነው ። እንደው ቤቶቹ ልጆቿ
በሙሉ እንዳንድ ነገር በወሬው ተጥራመሱ ። እኔ ደሞ ለምን እንደሁ
እንጃ ከቁጠር አልቆጠርኩት ። ነገሩ እንደሁ አገር ያወቀው ጠሀይ
የሞቀው ጉዳይ ነው ። ድንገት ማክን ካሉት የበርር ቤተሰብ ያክስቱቹ
ልጆች መሃል አንዷን ካሳገባ በቀር እሷት እንደሚያገባ ማንም ያው
ቃል ። ያውኳ ሐኒ ዊክስ የሚላኒን ወንድም ቻርለስን እንደምታገባ
ማለት ነው ። እኔምለው አቶ ጂራልድ ፡ እንዚህ የዊክስ ቤተሰቦች
ከቤተሠዎቻቸው በሩጪ ሲላ እንዳያገቡ የሚያግድ ህግ አላቸው ማለት
ነው ? ምክንያቱም አየህ መቼም . . . ?"

@OLDBOOKSPDF

አስካርሌት የቀረውን እንዱንም አልሰማች ። ድንገት የኮን ፀሐይ ከመቅደበት በፊመና እንዶተሸፈነችና የአለምን ቀለማት ሁሉ ገፋ ወስዳ ጥላ — ጨለማ ውስጥ የከተተችው ያህል ፤ የአስካርሌት ብርሃን ጨለመ ። ለምለም አረንጓዴ ቅጠሎች ከል ለበሱ ። ጠወ ላለጉ ። የደማ ውድ ቁጭለ ጠቋቆረ ። በአካባቢው የፈነዱ አበ ቦች ቀለም ጠብትን የተራቆተ ቡቱቱ ጫርቅ መሰለ ። የአስካርሌት እጅ የሠረገላውን መቀመጫ እጀታ ይቆረቁራል ። የያዘችው ግንቁ ላም ይንቀጠቀጣል ። የአሽሌይን መፈጣጠም መስማቷስ ይሁን እሺ ፤ እንዱት የመንዱሩ ሰው ሁሉ እሱኑ እያነሳ ያውራው ደሞ ! ብጅ መዲያው ያ የተነሳችበት ዓላማና ጠንካራ ልቧ ይሆን ብስጭታን ረዙና ጸሐማው የሸፈናት ፀሐይ እየሳቀች ብቅ አለች ። የደበዘዙ ያካ ባቢው ጥሪታት አዲስ እንደበቀሉ ፡ አዲስ እንዳበቡና እንዳፈሩ ሁሉ እንገታቸውን ቀና አድርገው ቆሙ ።

አሽሌይ እንደሚወዳት እንደሆነ የታወቀ ነው ። አርግጠኛ ናት ። ጥቂ ምጥመ ቀርቷል ተብሎ ሲነገር ወ/ሮ ታርሌተን ከሙ ብላ ስትገረም ታያትና ፊገግ አለች ። አሽሌይና አፅ. በጠፍ ጨረታ ጠፍተው ሲሄ ዱማ አቤት የሚኖረው ግራ መጋባት ፡ አቤት የሚኖረው መገረም! ያሳወቁ አለቁ እሱ ! ሙሉ አድሮ መቼም ጉረቤት ሁሉ ፡ ይቺ አስካር ሌት ምን ጉድ የጉድ መጨረሻ ናት ፡ ስለሜላኒ ፊቷ ሲመራ የቂንና የአሽሌይን ሴራ እያወጣች ዝም ማለቷ ሲል ታስባትና ጉንፉን ስር ጉድ ሰርጉድ አድርጋ ስራሷ ፈገግ አለች ። በተለይማ ይቺ ሐሬ እናቷን እንዲህ በጥሞናና በተመስጠ ስታዳምጥ ቆይታ ነገሩ ሌላ መሆኑን ስታውቅ እንዴት አጪዋ ጹብ ይል ! እንዴት እንቁቅልሽ ይሆንባት !

"እቱ ጂራልድ ፡ አንተ ያሻህን በል" አለች ወ/ሮ ታርሌተን ። "በበኩሴ ግን ይሄ ያህስት ልጅ ካክስት ልጅ መጋባት ጅልነት ነው የሚመስለኝ ። አሁን አሽሌይ የሐሚልተንን ልጅ ያግባ በሞቱ ? ሐኒ እንኳ ያንን ጭጥግ ጭምት ቻርልስን ማግባቷ መቼስ . . . . . "

"አይ እማማ ፡ ሐኒ ቻርሊን ካሳገባች እኮ በቃ አለቀላት እንድ ሰው መያዝ አትችልም ከዛ ወዲያ" አሰች ራንዳ ። ጨካኝ ናት ። ዝነኛ በመሆኗ ደግሞ በራሷ መኩራራት ይነበብባታል ። "ስራሷ ክሱ ሌላ ወንድ አታት ፤ የመጀመሪያዋም የመጨረሻዋም እሱው ነው ። ለዛ ውም ሲኮራባት አይጣል ነው ። በደንብ አይዛትም ። መፈጣጠም ብቻ ምን ራይዳ አለው ። አስካርሌት አራስሽስ ባለፈው ዣና እንዴት ይከ ተልሽ እንደነበር ትዝ አይልሽም እንዴ . . ?"

"እንግዲህ በሰው ነገር ዋልቅ ዋልቅ አትበይ እሚቴ ፣ የርጐ ዝንብ ! እኮ ሰነን !" አለች እናቷ በቁጣ አቋርጣት ።" የአክስት ልጅ አይደለም

@OLDBOOKSPDF

የአክስት ልጅ ልጅ መጋባቱ ያስጠላል ። ዝምድናውን ያላላዋል ። ያረክሰዋል ። ሰው እኮ እንደፈረሰ አይደለም ።አንድን በትሙ ከገባ ወንድማማቹ ወይም ፈረሷን ካባቷ ማዳቀልና ጥሩ ዘር ማግኘት እኮ ምንም አይደለም ። ፈረሶች ናቸዋ ! በሰው ግን ጨርሶ የተለየ ነው ፣ ብልግና ነው — ስድነት ። በዘር ፡ብሥጋ — ዝምድና መቀስድ ፡ምናልባት አንድ ምርጥ ዘር ማውጣት ይቻል ይሆናል ።ደህና ሀሞት ግን ማግኘት ዘበት ነው ። አንተ . . . ”

“ አያያይ ! በዚህስ በጅንብ ነው የምታወሽ ፣ ይሆን አልተበልም ። ለመሆኑ ከሚክሶች የተሻለ ቤተሰብ ፣ ከነሱ የተሻለ ዘር በድፍን አገር ዞረሽ ታገኛለሽ ? ደሞ ገና ክአያት ከቅድመ አያት ጀምሮ ጋብቻ ሲሆኑ ፣ እርስ በርስ ሲጋቡ የቆሩ ናቸው ። ምኑ ነው አሁን እንዳዲስ የሚያናግርሽ ? ”

“ቢሆንም አሁን ዘመን ሲሽረው የሚገባው ጊዜ ደርሰናል ። እር ግጥ እንደ አሽሌይ ያለው መልክ መልኩም ሽጋ ሲይሆን ፡መቼስ ሁሉም . . ብቻ አሱም ቢሆን . . አሁን እንጣን ሁለት ዘር አሰዳቢ ለድ ልጃገረዶች ከሚክስ ትቆጥራቸዋለህ ፣ ውንጅሎች ናቸው ግን ምን ያደርጋል ስዶች ሆኑ ! ደሞ ወ/ሮ ሚሲሲን ተመልከት ፡እነዙ ብትሳት ኑሩሽ የሚመስጓት ሰናና ናት ።የልብ ጥንክሬ ፡ድፍረት የሚነበል ነገር ግን ደግ ሙስጥ አይደለም ፣ ጥሩሮ ሳይ እንኳ የለም ። የራሱ የምትለው ምናምኒት ሐሳብ የሌሳት ቡቡ ናት ። “ እሺ እማማ ፣ ተይ እማማዬ ይቅር ፣ ምነው ቤቱር እማማዬ” በቃ ። ስለ ቃል በድፍረት ከፏ እሚ ወጣ ሴት አያደለችም ። ምን ማለቱ እንደሆነ አሁን ገባህ ? ያ ቤት ሰብ ልክ እንደኔምዝ ተያይ ሀገር ልጆች ወይም እንዳንተዋ አስከር ሴት አዲስና ታይለሽ እንዲሁም ጥራት ያለው ይም ይለፈልገዋል ። የምለው አልገባ ብሎህ እንዳገጠፉሩ ፡ነፌ እምለው የዊክስ ዘሮች ከራሳቸው ልማድ ፡ ከራሳቸው ባህል አንጻር ጥፋ ሰዎች ናቸው ። አንም እንደምወዳቸው ታውቃለህ ።ግን እውነቱን እንነጋገርና እርስ በርስ በመጋባት ያንኑ ዝርያ እንደ ፋብሪካ መራቢያፈላቸው ትክክል ነው ? የተጠረገ ፡ የተወለወለ መንገድ ከገጉ የዊክስን ዘሮች የሚያሀላቸው የለም ። ኮረኮንች ፣ አባጣ ጉሪጓጣና ጭቃማ መንገድ ላይ ግን አይችሉም ፡ ልብ ይገሳቸዋል ፡ ሐሞት ያንሳቸዋል ። ወደፊት ድፍረት ይዘራሉ እንዳንል ደግሞ በደማቸው ውስጥ የለምና እርስ በርስ እየተጋቡ ደንኑ ወደ ቢስ ሞራል እንዳባሙ ይኖራሉ ። ስለዚህ ከቃ ጊዜ ቢመጣ ለመቋቋም አይችሉም ማለቴ ነው ። የደህና ጊዜ ትልቅ ሰዎች ናቸው ። እስቲ አሁን ለኔ በየትኛውም ወቅት ሲጋልብ የሚችል ፈረስ ስጠኝ ፣ በዝናብና በጠራራ ፀሐይ ፣ በጭቃና ባፀራ እንደልቤ እየን ዳሁ አሳይሃለሁ ! እንሱ በንድ ይሄ የለም ። እዚህ ካለው ህዝብ የተ

@OLDBOOKSPDF

ልዩ የሆኑት በዚሁ በእርስ በርስ መጋባታቸው ምክንያት ነው ። ሁሉ ጊዜ ፒያኖ ላይ ማቅርቀር ፣ አሊያም መጽሐፍ ውስጥ ሞንቅላታቸውን መቅበር ነው ሥራቸው ። እርግጠኛ ነኝ አሽሌይ አደን ሂድ ከሚሉት መጽሐፍ አንብብ ቢሉት ይሻለዋል ! ! አዎ ፣ ከልቤ የማምነው ነው የምነግርህ አቶ ጂራልድ ! እሱቲ አጥንታቸውን እንኳ ተመልከተው ፣ በጣም ስስ ነው ። ምግዚት የሚሆናቸው እመቤትና ጌታ ይፈልጋሉ ። ለጥንካሬ . . . ”

“አሃሃህ” አለ ጂራልድ ፣ ድንገት ይህን እንዲህ የጣመውን ርዕስ ኤለን ብትሰማ ምን ያህል የተጋነነ ይሆንባት ነበር ብሎ አሰበ ። በእርግጥም ደግሞ ልጆቿ እንዲህ ያለው ውይይት ሲካሄድ ይሰሙ ነበር ቢሏት ልቧ ፈሰሳ ትወድቃለች ። ሆኖም ይቺ ወ/ሮ ታር ሱቱን ምንጊዜም ቢሆን ሰራቂ የሚጥማትን አርዕስት ካገኘች ለሴላ ሰው ጉዳይ ጆሮዋ ድፍን ነው ። እሷ ያሰሙም ይሁን የፈረስ ፣ ለጅ ማሳደግ ዋና ጉዳይዋ ነው ።

“እኔ የምናገረውን የማውቅ ሴት ነኝ ። የራሴ እህስት ልጆች እርስ በርስ ተጋብተው ሲያበቁ እንዴሁ ያበጠ እንቁራሪት መሰለው ቁጭ ብለዋል ። ታዲያ እንደለመዱት ቢተሰቦቼ አሬንም ያክስቴን ልጅ እንዳገባ ሲጠይቁኝ አራስ ነበር ሆንኩባቸው ። የለም እማማ ፣ ልጆቼንና የልጅ ልጆቼ ሁሉ የፈረስ በሽታ ይይዛቸዋል አልኳት ። እማማ ይሄን የፈረስ በሽታ ሳንሳ ስተሰማማ ታንቄ እሞታለሁ አለች ። ብቻ እግዚር ይስጣት እያቴ ፣ የኔን ንቅንቅ አሰማለት አየችና ደነፈችኝ ። ስለፈረስ ማርባት ብዙ ስለምታውቅ ትከክል መሆኔን አረጋገጠች እንዲያውም ከአቶ ታርሌተን ጋር እንድኮበልል ረዳችኝ ።እና ልጆቼን ተመልከት ! በጣም ትላልቅ ጤናማ ልጆች ናቸው ። ቦይድ አምስት ፈት ከአሥር ኢንች ቁመት ከመሆኑ በስተቀር ለመሀላ እንኳን አንድ በሽተኛና ክስማና ልጅ አታገኝም ።አሁን የዊክስ ዘሮች...” ጂራልድ የካሪንን የመደናገጥ መልክና የሱዌለንን ጉጉ ፊት ሲያይ ፣ ምና ልባትኮ ሁለቱ ልጆች እናታቸውን እሱ እንዴት ይገከባከባት እንደ ነበር ይጠይቋታል ብሎ በመስጋት ፣ “እመቤቱ እንቺን ላቋርጥሽ አይ ደለም ።” በማለት አቋረጣት ፣ ፈጠን ብሎ ። ሴቶች ሊያስቡ የሚገባቸውን ነገር ሳይቀር ልብ ለማለት በመቻሉ በጣም ደስ አለው ።

ሐቲ ታርሌተን እግዚር ይሳጣት ፣ ከስጋቱ ገላገለችው ።

“እሬ በማርያም እማማ ፣ እንሂድ እንጂ ልቀቂን !” ጮኸች ትዕግስቷን ሱርስ አድርጋ ። “ይሄ ጠራራ ፀሐይ ፊቱን ሞሽለቀኝ ፣ እንዲያውም ግና ካሁኑ እንገቱ ላይ ችፍ የሚል ነገር ወጥቶብኛል ።”

@OLDBOOKSPDF

"ቆይ እመቤት ፤ እንድ ደቂቃ ታገሺ" አለ ጂራልድ ። "ለሠራ ዊታችን እሸጥሳችኋለሁ ያልሺውን ፈረሶች ነገር ምን አደረገሽ ገመር ነቱ ከዚች ካሁኗ ሰዓት ጀምሮ በማናቸውም ደቂቃ ሊጀመር ይች ላል ።ልጅቱ ይሄን ጉዳይ ቶሎ ለመጨረስ ይፈልጋሉ ። የክሴይተን መንደር ሠራዊት ስለሆነ የክሴይተን መንደር ፈረሶች ያስፈልጉናል ። እንቺ ግን መቼም ያ ግትርነትሽ አልለቅ ብሎሻል ፤ ደህና ደህና ፈረሶ ችሽን አልሸጥ ብለሽ ስንት ደጅ አስጠናሽን ።"

"ምናልባት እኮ ጦርነት ከናካቴው ላይኖር ይችላል" አለች ታር ሴተን ቆጣ ብላ አሁን አዕምሮዋ ከዊከሶች እንግዳ የጋብቻ ልማድ ሙሉ በሙሉ ተላቋል ።

"እንዴ ለምን እሜቴ ? እንዶሱ ለማለትማ አትችይም..."

"እማማ" አለች ሔቲ እንደገና አቋርጣ "እንቺና ጋሼ ጂራልድ እዚህ የምታወሩትን ነገር በ"አሥራ ሁለቱ ዋርካዎች" መነጋገር አት ችሉም እንዴ ?"

"ልክ ነሽ ሔቲ" አለ ጂራልድ ። "እንግዲህ ከአንዲት ደቂቃ በላይ አላቆያችሁም ፤ ወደ አሥራ ሁለቱ ዋርካዎች አሁኑኑ እንደርሳ ለን ።እዚያ ያለ ማንም ሰው ሽማግሌ ላይል ወጣት ስለፈረሶች ነገር ማወቅ ይፈልጋል ። አቤት ! እንደዚች እንደናንተ እናት ያለች ስለፈረ ሶቹ ነብሷ ሊወጣ የሚደርስ ቆንጆ ሴት በጭራሽ አጋጥማኝ አታው ቅም ።እኔምለው ወ/ሮ ታርሴተን ፤ የሀገር ፍቅርሽን ፣ጀግንነትሽን ሁሉ ምን በላውን ኮንፌዴሬሲው ምንም ትርጉም ፤ ምንም ስሜት አይሰጥ ሽም ማለት ነው ?"

"እማማ ፤" ትንሿ ቤትሲ አሰቀሰች "ይሄውልሽ እንግዲህ እቺ ራንዳ ልብሴ ላይ እየተቀመጠች ቀሚሴን ታጨማድድብኛለች ።"

"አይ ዝም በይ ፤ ራንዳን ወደዛ ግሬያትና አርፈሽ ቁጭ በይ ። ስማኝ አጭ ጂራልድ ፤" እንደገና መናገር ጀመረች ። ዓይኖቹዋ ከበታ ቸው ሠመጠት ጀምረዋል ። "ኮንፌዴሬሲው ላይ ጥላቻ ያለኝ አታስ መስሰኝ ! ! ላንተ የሚሰማህን ያህል ፣ አንተ የምትወደውን ያህል ፤ ለኔም ይሰማኛል ! እኔም አወደዋለሁ ። እኔ እኮ አራት ወንዶች ልጆ ቼን ለኮንፌዴሬሲው አላማ የሰጠሁ ነኝ ። አንተ ምንም አልላከም ያም ሆነ ይህ ልጆቼ እራሳቸውን ለመጠበቅ ይችላሉ ። ፈረሶቼ ግን አይችሉም ። ማን እንደሚጋልብባቸው ባውቅ እኮ በነጻ ብሰጣቸው ግዴ ለኝም ። የጨዋ ልጅ የፈረሰ አስተዳደግ ይጣዋል ።

ለሱ ከሆነ ላንዲት ደቂቃ አላመነታም ነበር ።

@OLDBOOKSPDF

ነገር ግን የማንም አንጨት ፈላጭና መጫኛ ነኳሽ ከሚመጣባቸው ቀድሚ ብሞት ይሻለኛል ! የለም ጌታዬ ፡ በየጦሩ ሜዳ ደሀና ሰው ወጣ ባቸው አልመጣባቸው ፡ ተንከባከቧቸው አልተንከባከቧቸው እያልኩ እንትልፈን ማጣት አልፈልግም ። ስመሆኑ ስታስበው የማንም ጅላንፎ ውድ ፈረሶቹን አረፋ እያሰደፉ አንድያውን ቅስማቸውን ሰብሮ እነ ጸለቃቸው የምፈቅድ ይመስልሃል ? ሰምን እዚሁ አንተቲን አልሳ ጥም ! የለም የኔን ፈረሶች መፈለግህን በማም አደንቃለሁ ፡ ግን ወደ አትላንታ ሄጻችሁ አሮጌ ጦጣ ፈረሶችን ሰብስባችሁ ገዝቃችሁ ለንዚያ ለተራ ቱርታ ገበሬም ብትሰጧቸው ይሻል ይመስለኛል ። ልዮነቱ አይገባችውም ።”

“እማማ ፡ ምነው ባክሽ መንገድ ብንሮምር ?” ብላ ጠየቀች ካሚለ እስካሁን ይሬሱቀጭቱ ከነበሩት እሁኖቹ ሁብረ ዜማ ውስጥ ቀቀ ላቅላ ።“እውን ማን ያጠፉት በመጨረሻ ውድ ፈረሶችሽን መስጠት ሽን ልብሽ ሳያውቅ ቀርቶ ነው ፡ እሰምረሽ ትሰጪያቸዋለሽ ። አባ ባና ልጅሽ ኮንፌዴሬሲው ፈረስ በማም እንደሚያስፈልገው እየጠ ቀሱ ሲያስረዱሽ አያልኮስሽ ትቷ ጨያቸዋለሽ ።”

ወሮ ታርሉቦን ክሰተ ብላ ነገሩን ላለመቀበል ራሷን ነቀነ ቀች ።

“እንዲህ ያለ ነገር በሞራሽ አሳይርግም ።” አለች ፈረሶቹን በቀስታ ዣረፍ እያደረገች ። ሠረገላው በጭንት ተንቀሳቅሰ ።

“በማም ሚሩም ሲት ፍት” አለ ጀራልድ ባርኔጣውን አድርት ራሱ ሰረገላ ላይ ቦታውን እየያዘ ።“ሂድ እንሂድ ቶቢ ፡ አስቲ እንደም ንም ኤፕለስልሳትና ፈረሶቹን እንድትሰጠን እናደርጋታለን ። አሷም እኮ እውነት አላት ። ጨዋ ሰው ካልሆነ የፈረስ አያያዝ አያውቅበትም ። የሱ ቦታ ከእግረኛው ወገ ጋር ነው ። ማን የሚያሳዝነው የሠራዊቱን ቁጥር ሊያሟሉ የሚችሉ የባለሰፈ እርሻ ልጆች ነበጨዋ ልጆች በበቂ አይገኙም ። ምን ይመስልሻል ቆንጂት ?”

“አባባ እባክህ ወይ ከኋላችን ሁን ወይ ከፊታችን ቅደም ፡ በአ ሷራ አጥንህ ነደልክን እኮ” አለች እስካርሌት ፤ ምንም ዓይኑት ወይ ይት ለማድረግ ፈቃደኛ ባለመሆን ። ከሀሳቧ የሚነጥል ነገር ሆ’ባታል ። እሷ ለራሷ ሀሳቧንና የፊታን ቁንጅና በወግ በወጉ አስተነከሰ “አሥራ ውለቱ ዋርክሥችን” መኖፈሻ ከመድረሷ በፊት ማራኪ ሆኖ መቅረቧን ለማረጋገጥ ትፈልጋለች ። ጀራልድ በታማኝነት ፈረሱን ኮል ኩሎ ፡ ከታርሌቶን በተሰቦች ሠረገላ ኋላ ድርሶ ያንኑ የፈረስ ጭትጭቁን እስኪሰማ ድረስ ነመጭ ሲል የቱዩ እሷራ ጉም አፈነው ።

@OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ 6

ሠረገላው ወንዙን ተሻግሮ ጸጥቱን ተያያዘው ። ግና የ"አሥራ ሁለቱ ዋርካዎች" አካባቢ በዓይን የሚታይበት ቦታ ሳትደርስ እስካርሌት ከረጃጅሞቹ ዛፎች በላይ እየተትመለመለ የሚተነውን ጪስ ተመለከተች ። በሚነዱ ፍልጦች የሚጠበስ የአሣማና የበሬ ሥጋ ከሩቁ ይሸታል ።

ለድግሱ የተቆፈሩት ጉድጓዶች ከትላንት ማታ ጀምረው እየጨሱባቸው ነው ። አሁን እንግዲህ ከበላያቸው ሥጋ እየተጠበሰና መረቁ በየክሰሉ ማህል እየተንጠፈጠፈ ትርክክ ያለ የፍም ጓል ጉድጓዱን ይሞላዋል ።

እስካርሌት አሁን ከሩቅ የምታሸተው ግሩም መዓዛ ፤ ከትልቁ ቤት ደጃፍ ያሉት ዋርካዎች የሚተነፍሱት ጣፋጭ ሽታ መሆኑን አውቃለች ።ጆን ዊክስ ድግስ ሁልጊዜ የሚደግሰው ሠፈ ጥላ ቦታ በሚገኝበት ወደ ሮዝ አበባው የአትክልት ቦታ ከሚያወርደው ተዳፋት ላይ ነው ። ይሄ ቦታ የካልቨርት ቤተ ሰዎች ከሚደግሱበትም ቦታ በተሻለ ሁኔታ የሚያስደስት ነው ። ወ/ሮ ካልቨርት የድግስ ምግብ ስለማትወድና ከድግሱ በኋላ የምግብ ሽታ እዜት ውስጥ ይቀራል ስለምትል ፤ ሩብ ማይል ርቀት ላይ ባለ መጠለያ በሌለው ሜዳ ላይ እንግዶቿን ታፈሳቸዋለች ።ጆን ዊክስ ግን በድጉን አገር በድግስ አዘገጃጀትና በአንግዳ አቀባበል በጣም የታወቀ ነው ።

ረዣዥሞቹ የቨርጭር ግብግ ጠረጴዛዎች በጣም በውድ ዋጋ በሚገዛው የዊክሶች ልዩ ጨርቅ ተሸፍነው ጥላው ውስጥ ይደረደሩና መደገፊያ የሌላቸው አግዳሚ ወንበሮች አብረው ይኮለኮላሉ ። ባለመደገፊያ ወንበሮችና በርጫጫዎችም ቢሆኑ አግዳሚውን ለማይወዱ ሰዎች እዛም እዛም ተበታትነው ተቀምጠዋል ። እንግዶቹን ጭሱ እንዳይረብሻቸው ተብሎ የሥጋ መጥበሻው ጉድጓድ ራቅ ተደርጐ የተዘጋጀ ነው ።ከትልቁ ጐላ የድግሱ ወጥ ሽታ ከርቀትም ያውዳል ። ቢያንስ አንድ ደርዘን ባሪያዎች ትሪ ትሪያቸውን ይዘው ወደላይ ወደ ታች እንዲሉ ማድረግ የአቶ ጆን ዊክስ የዘወትር ልምድ ነው ። ከዶሮ ቤቱም ጀርባ ሌላ የድግስ ቦታ አለ ። እዚያ የሚመገቡት የእንግዶች የቤት አገልጋዮች ፤ ፈረስ ያገኙ ፤ የሠረገላ ሹፌሮች እንዲሁም ሌት

@OLDBOOKSPDF

አገልጋዮች ሲሆኑ ፣ ለሥራ ተከፋይ ያም እና በተለይ ለእግሮ
ዎች በጣም ተወዳጅ የሆነው ጨዋራ ይቀርብላቸዋል ። ወቅቱ ከሆ
ነም ሀብ ሀብ ይጨምርላቸዋል ።

እስካሌት የትኩስ አማማ ሽታ ወደአፍንጫዋ ሲገባ አጥጫ
ዋን በእድናቅት ሽብሽብ አድርጋ አጣጣመችውና ሲጠበስ የምግብ
ፍላጐቷን በሚገባ እንደሚቀሰቅሰው ተስፋ አደረገች ። መቼም ሆዷ
እስኪነፋ በመብላቷና ለቅጥነቱ ብላ ወገቧን በጣም ሽምቅቅ እድርጋ
ያሰረችው በመሆኑ ካሁን አሁን አመመኝ እያለች በስጋት ነው የምት
ራመደው ።

በዋጋብ ለመታመም ቀርቶ አማሳት እንኳን ፤ እንዲህ ሀዘብ በተሰባ
ሰበበት ወይ ለሽማግሌዎች ወይ ለአሮጊቶች የተለመደ ይሆን እንደ
ሆን ነው እንጂ ፤ እንደሷ ላሉው መቼም ነውር ነገር ነው ።

ዳንቱን ጨርሰው አፋፍ ብቅ ሲሉ ነጩ የሚከሰች ቤት የተዋጣ
ቅርፀኑን አዋህዶ ረዥም ምሰሶዎችን በተጠንቀቅ እንዳሰለፈ ፤ ስፋፊ
በረንዳዎቹን እንዳሳመረ ፤ ጠጪሳሩ ጣራውን እንዳንጣለለና በውበቷ
እርግጠኛ በመሆን ለጋሥነቷና ባለሞገስነቷ እንደሚያረካት ውብ
ሴት — አምሮ ቅጥ ብሎ ቆሟል ። አስካርሌት ይሄን የአሥራ ሁለቱ
ዋርካዎች መናፈሻ ከታራ አብልጣ ታፈቅረዋለች ። ምክንያቱም ይሄ
ቤት የጂራልድ ቤት የሰለውን ገነታዊ ቁንጅናና ታላቅ ክብርን የተ
ጐናጸፈ በመሆኑ ነው ።

ሰፊው መጠምዘግ መንገድ በሠረገሎች ፤ ኮርቻ በተጫኑ ፈረሶ
ችና ሞቅ ያለ ሰላምታ በሚለዋወጡ ዓይኖሞችና ዘመዳሞች ተሞል
ቷል ። ሣቅን ብለው የሚያገጡ አማሮዎች ፤ እንደተለመደው ግብግ
በመኖሩ ፍንጥዝ ብለው የፈረሶቹን ልጓም ለማውለቅና ኮርቻ ለማውረድ
ወደዶሮ ቤቱ ጀርባ እየገሠቱ ይወስዳሉ ። የጥቁርና የነጭ ሀጻ
ናት መዓት እንደጉድ ይሯሯጣሉ ፤ አዲስ የበቀለውን የሣር ሜዳ እን
ደልብ እየፈነጩበት ሰኞ ማክሰኞና ንክክቶሽ እየተጫወቱ ምን
ያህል እንደሚበሉ እያወሩ ጉራቸውን ይነዛሉ ። ከፊት ለፊቱ
በረንዳ አስክበሉ የኋለኛው ጥግ ድረስ በረጅሙ የተንጣለለው
አዳራሽ ሰው በሰው ሆኗል ። የእሣራ ቤተሰብ ሠረገላ ወደፊት ሰፊቱ
ደረጃ ሲቃረብ አስካርሌት ፤ ከፈረስ ፀጉርና ከሻማ ጨርቅ የተሰራ
እንደቢራቢሮ የደመቀ ትላልቅ ቀሚስ የለበሱ ልጃገረዶች ፣ ወይዛ
ዝኛ ፎቅ በሚመስደው ደረጃ ላይ እንዳቸው እንዳቸው ወገብ ላይ እጃ
ቸውን አድርገው ሽቅብ ሲወጡ ፤ ቁልቁል ሲወርዱ ፤ የደረጃዎቹን
መደገፊያዎች ለማየት ቆም ዘመም ሲሉና እታች ካለው አዳራሽ ውስጥ
ያሉትን ወንዶች ሲጠሩ ፣ ሲስቁና ሲያስካኩ ተመለከተች ።

@OLDBOOKSPDF

በተከፈቱት የፈረንሳይ መስኮቶች ውስጥ አልፍኝ የተቀመጡት አሮጊቶች ይታዩኛታል ። የጥቁር ሐር ቀሚሳቸውን ለብሰው በማራገቢያው ለራሳቸው እያራገቡ ስለልጅት ስለበሽታና ማ ማንን ለምን እንደገባ ይጫወታሉ ። የዊክስ ቤተሰብ ዋነኛ የቤት ሠራተኛው ቱም ፤ በአዳራሹ ውስጥ ተፍ ተፍ እያለ ክብር በተሠራ ማቅረቢያ ትሪ ረዣዥም ብርጭቆዎችን ቡናማና ማራጫ ቦላሉ በምርጥ ሽሚዝ ሰለበሱት ወጣቶች ሲያቀርብ አጅ እየነሳና ፈገግታ እየመገበ ነው ።

ፀሐይ ያረፈበት የፊት ለፊቱ በረንዳ በእንግዳ ጢም ብዛል ። አምን ፤ የከተማው ሰው በሙሉ ንቅሳ አዘሀ መሞቷል ማለት ነው ፤ ብላ አሰበች አስከርሌት ። አራቱ የታርሌተን ወንዶች ልጆችና አባታቸው ረዥሙን ምስል ተደግፈዋል ።

መንትዮቹ ወንደማማቾች ስቱዋርትና ብሬንት እንደተለመደው ሳይ ነጣጠሉ ጉን ለጉን ናቸው ።ቦይድና ቶም ከእባታቸው ከጀምስ ታርሌተን ጋር ሆነዋል ። አቶ ካልቨርት ከዚያች አሥራ አምስት ዓመት ጀርጀያ ውስጥ ኖራ የዘሀ አገር ሰው መምሰል ካቃታት ያንኪ ሚስቱ ጉን ሽጉጥ ብሏል ።እሱ ለሷ ያለውን እዘአታ አያየ ማን ሰው ለሷ ትውትና ደግ ይሆንላታል ። የካልቨርት ልጆች እናት በመሆን ከሴላ ዘር ያደባለቀችውን የመጀመሪያ ዘሯን ለሀጉት ግን ማንም አይረሳላ ትም ። ሀለቱ የካልቨርት ወንዶች ለጆች ፊሮድና ካድ ከጠይሟ እህታቸው ከክትሊን ጋር እዘያው ቆመው ጅ ርንቱንና እሙሻውን ሰለ መንሮን ያጫውቷቸዋል ። አሌክስና ቶም ርንቱን ደግሞ ለዲ ሚቲ መንሮ በጀሮዋ የሆነ ነገር እደንሽክሽኩ በሳት ይገድሏታል ። ከዚህ አሥር ማይል ከሚርቀው ሉቨጀጅ ደረስ የመጡ አሉ ። ከዚይ ትቪልና ከጀንስቦሮም እንደዚሁ የመጡ አሉ ። ቤላው ቦርቶ ኬኤትላ ግታና ከማከን ድረስ እንኳ የመጡ ጥቂት ሰምኛ አሉ ።ቤቱ ዘሰው ብዛት ሊፈነዳ ደርሷል ። የንግሩ ፡ የሳቁ ፡የውኪታውና የሴቱ ጩኸት ሳያቋርጥ እንደማዕበል ከፍና ዝቅ እያለ ይሰማል ።

በረሸሙ በረንዳ ደረጀ ላይ ዋናው ብለደማስ ባለ በጎማ ፀጉሩ ጆን ዊክስ ቁጥ ብሎ ቆሟል ። ያን እንደጀርጅያ የቢጋ ፀሐይ የሚሞቀው ፣ ምን ግዘም የማይቀዘቅዝ የደስ ደሱንና ሣሩም አቀባበሉን እንግዶቹ ላይ ይፈነጥቃል ። ከጐኑ ሐኒ ዊክስ ቆማለች ። ሐኒ የተባለች ው ካባቷ ጀምራ እስከመጨረሻው የአርሻ ቦታ ሠራተኛ ድረስ ሐኒ እያለች ማቆላመጥ ስለምትወድ ነው ። የሚመጡትን እንግዶች ስትቀበል አንዷም ፈገግታ ሳይለያትና እየሳቀች ነው ።

የሐኒ ለስው ሁሉ ማራኪ ሆኜ ልታይ ልታይ ማለት ከአባቷ ረጋና ሰብሰብ ያለ አቄቋም አንጸር ሲታይ ቀቃራኒነቱ ይገለል ። ምናልባትኮ

@OLDBOOKSPDF

ወ/ሮ ታርሌተን ስለሐኒ የተናገረችው አንድ ተንኮል ሳይኖረው አይቀ ርም ብላ አሰበች እስካርሌት ። መቼም ያለ ጥርጥር የዊክስ ቤተሰብ ዘሮች በጣም ይመሳሰላሉ ።ጆን ዊክስና በአሽሌይ ላይ ሲታይ ችም ችም ያለውና ወርቃማው ሽፋል ፣ በሐኒና በኢንዲያ ላይ ቀለም የለ ሽና የተበታተነ ነው ። ሐኒ ልዩ ከሆነው አስተያየቷ ጋር ስትታይ ዋንቸል ትመስላለች ።

ኢንዲያ የትም አልታየችም ። በእርግጥ ግን ለአሽከሮቹ የመጨ ረሻ ትዕዛዝ ሰጥታ ለመገላገል ስትል ይሄኔ ማድቤት እንደሆነች ለእ ስካርሌት ታውቂታል ። "ምስኪን ኢንዲያ" አለች እስካርሌት በልቧ "እናቷ ከሞተች ወዲህ በቤት ጣጣ ተይዛ ከስቱዋርት ታርሌተን በቀር ፍቅረኛ እንዳትይዝ ሆናለች ። መቼም እሱ ከሷ ይልቅ እኔን በጣም ቆንጆ ሆኜ ቢያገኘኝ በምንም ዓይነት የኔ ስህተት ሊሆን አይ ችልም ።"

ጆን ዊክስ እስካርሌትን እንደተለመደው ሊቀበላት ደረጃዎቹን ወርዶ እጇን ዘረጋ ። እስካርሌት ከሰረገላው እየወረደች ሳለች ሱዌ ለን ስታሽሟጥጣት እየቻትና ከተሰበሰበው ሰው ማህል ፍራንክ ኬኔዲ እንዳለ ገባት ።

"ከዚያ ካረጀ አውራ ዶሮ የተሻለ ፍቅረኛ መያዝ አልችልምና ነው እኔ !" አለች ልቧን በጥላቻ ሞልታ ። መሬት ስትረግጥ እግረመ ረመንገዷን ጆን ዊክስን በማመስገን ፈገግ አለች ።

ፍራንክ ኬኔዲ እየተጣደፈ ሱዌለንን ከሠረገላው ሊቀበል መጣ ። ስዌለን በኩራትና በመንቀባረር መልክ ወረደች ።እስካርሌት ይህን ስታይ በያት በያት እሰኝቷት ነበር ። ፍራንክ ኬኔዲ ከመንደሩ ሰው ሁሉ የበለጠ መሬት ያለውና እንደመሬቱ ሰፊ የሆነ ሩሀሩህ ልብ ያለው ሆኖ ሳለ ፣ የአርባ አመት ሽማግሌ ፣ ቅብጥብጥ ፣ ዝንጅብል የመ ሰለ ጢም ያለውና ነገረ ሥራው ሁሉ የጃጀች አሮጊት አይነት ስለ ሆነ ፣ ሀብታምነቱ ቦታ ያጣል ። ሆኖም እስካርሌት ፣ እቅዷን አስታውሳ ፣ ጥላቻዋን ሁሉ ዋጥ አድርጋ ወተት ፈገግታዋን እንዴ ስትመግበው ሽማግሌው በቱሙ ሊመድቅ ምንም አልቀረው ።ለሱዌለን የዘረጋውን እጇን አዚያው ትቶ በመደናገጥ ለእስካርሌት ሰላምታ ሰጣት — እኖ ገለፈጠ ።

እስካርሌት ከጆን ዊክስ ጋር ሰላምታ እየተለዋወጠች እንኳ ዓይኗ አላረፈም ። ከተሰበሰበው ህዝብ ማህል በዓይኗ አሽሌይን ታስ ሳለች ። እሱ ግን በረንዳው ላይ የለም ። ከደርዘን የሚበልጡ ድምጾች ሰላምታ አቀረቡላት ። ስቱዋርትና ብሬት ወደቧ እየመጡ ነው ።

@OLDBOOKSPDF

የሙንሮ ሴቶች ልጆች ስለቀሚሷ ያላቸውን አድናቆት ሊገልፀላት አንዳንድ ነገር እየተጋፉ ነው ። ወዲያውኑ አስካርሌት የዚያ ሁሉ ድምፅ ማዕከል ሆነች ። ያም ያም ሮክ እያለ ሲናገር ድምፁን ከአዳራሹ ከሚመጣው ድምፅ በላይ ለማውጣት የሚሞክር ይመስላል ። ግን እሽሌይ የታለ ? የት ደረሰ ? ሚላኒና ቻርለስስ ? በታቻላት የምትፈል ነውን ላለማሳወቅ እየሞከረች ቁልቁል ወደ አዳራሹ አየልቃ ከበው የሚስቁትን ሰዎች ተመለከተች ።

እያወካችና እየሳቀች የቢቱን ውስጥና አካባቢውን ሁሉ ስት ቃኝ አይኑዋ አንድ እንግዳ ሰው ላይ አረፈ ።ብቻውን አዳራሹ ውስጥ ቆሞ ቅዝቅዝ ባለ አስቸጋሪ አስተያየት ትኩር ብሎ ያያታል ።እንግዳህ አንድ ወንድ ለመሣረክ መቻሏን አረጋገጠች ። ስለዚህ አንድ እን ስታዊ የድል አድራጊነት ደስታ ተሰማት ።ቀሚስዋ ደረቷን ግልጥጥ አድርጉ የማሰየቱ ነገር ደግሞ ድንጋጤ ላይ ጣላት ።በነዚህ በሁለት ስሜቶች ተሳከረች ። ያ እንግዳ ሰው ጠና ያለ ይመስላል — ቢያንስ ቢያ ንስ የሰላሳ አምስ ዓመት ።ረዥምና ፈርጠም ጠም ያለ ትክለ ሰው ነት አለው ። አስካርሌት በህይወቷ እንደዚህ ያለ በጡንቻ የተገነባ ሰፊ ትከሻ ያለው ሰው አይታ እንደማታውቅ ታስባት ።

ለእንድ ሙሉ ሰው ሰሚባል ወንድ ፣ ይሄ እጅም ይበዛበታል መቼም ። ዓይኑዋ ከዓይኑ ጋር ሲጋጭ ፈገግ ብሎ ባጭሩ ከተከረከመው የከንፈር ጢሙ በታች ያሉትን ወተት የመሰሉ ጥርሶቹን ፍል ቅልቅ አደረገላት ። የፊቱ ቆዳ ጠየም ያለና እንደባህር ወንበዴ ጨፍገግ የሚል ነው ።ዓይኖቹም ቢሆኑ ፣ ትንሽ ፓልባ ለመዝረፍ ወይም ልጃገረድ ለመድፈር እንደተዘጋጀ የባህር ወንበዴ ጥቁቁርና የሚያስፈሩ ናቸው ።ፊቱ ላይ ግዴለሽነት ይንፀባረቅበታል ።ፈገግ ሲልላ ትም ቢሆን ከንፈሮቹ ላይ የአሽሙርና የሽርጉዳ ቀልድ ይታይበታል። ስለዚህም አስካርሌት ትንፋሽዋን ዋጥ አደረገች ።ይሄ መቼም ለወት ሮው እንደስድብ የምትቆጥረው አስተያየት ነበር ።አሁን ግን የመሰ ደብ ስሜት ስላልተሰማት ተናደደች ።ማን እንደሆነ ለማወቅ አልቻለ ችም ።ሆኖም የትልቅ ዘር ደም ፊቱ ላይ ለመኖሩ ጥርጥር የለውም ። ይህ ደም ፣ ከሙሉዎቹ ቀያይ ከናፍሮቹ በላይ ባለው የጭልፊት ኩምቢ በመሰለው አፍንጫው ላይ ገላ ባለው ግንባሩና እሩቅ እሩቅ በሚያዩ ዓይኖቹ ውስጥ ታትሟል ።ለፈገግታው ምላሽ የሚሆን ፈገ ግታ ሳትሰጠው ፊትዋን ወደ ሌላ ዘወር አደረገች ።ወዲያው አንድ ሰው "ሬትነ ሬት በትለር ! ና ወዲህ ! ጆርጅያ ውስጥ አለች የምትባለ ዋን ልበ ሙሉ ሴት ና ላስተዋውቅህ !" ሲለው ዘወር አለ ።

ሬት በትለር ? ይሄ ስም የሚታወቅ ስም ነው ።እንደውም ባንድ

@OLDBOOKSPDF

ስም በሚያጐድና፡ ተግባር የሚታወቅ ሳይሆን እይቀርም ። ሆኖም ልብ ዋን አሽሌይ ላይ የጣለች በመሆንዋ ይህን ሐሳብ ተወችው ።

"ወደ ርቅ ሄጂ በጉሬን ማበጠር አሰብኮ" አለች በአጀባት የወ ዳጅ ሠራዊት ማህል ኮቦሎው ሰብኽቸው ሊያደርጓት ይጣጣሩ ለነበ ሴት ጋር ስትሄዱ አያችሁና ሞ ።"

እስቱዋርትም ቢሆን አፏ ከሌላ ወንድ ጋር ልጫወት ብትል በጀ እንደማይሳት ገብቷታል ። ሲጠጣ ነው ያረፈደው ። እፊት ላይ አንድ ጠብ ያለሽ ዘዳዐ የሚል የትዕዚት መልክ ስለሚነበብ እስከ ዛሬ ካገኘችው ልምድ እንደምታወቀው ይህ መልክ ችግር የመጣ ጠር ጻር ጻሩ መሆኑን ተረድታለች ። አጸራሽ ውስጥ እንደገባች እማረ መንገዷን ያተኘኽቸውን ጓደኞቿንና ፀጉርዋን ምንጭርጭር አድርጋና ማንባርዋ ላይ ላብ ጉፉ ጭፍ ብልቱት ከወደጓሮ የምትመጣዋን ኢን ዲያን ሰላም ለማለት ሙም አለች ። ምስኪን ኢንዲያ ! የተመነጫጨረ በጉርና ሽፋሽፍት እንዲሁም ዙሪ አጥሮ ይዘ መታየት እኮ ደግ አይ ደለም ። በተለይ ዕድሜ ግና ሃያን ሳያልፍና ገበያው ሳይቀዘቅዝ እንዲህ መሆን ጥሩ አለነበረም ።

እንደውም እስቱዋርትን ሰለንጠቅጥት ቅር መሰኘትዋንም እንጂ ። ሰውማ ኑበለዋ እስኪመጣ ትወደዋለች ነው ኤሚሊው ። ግን እነዚህ የዊክስ በሮች ምን እንደሚያስቡ ማን ያውቃል ፣ ኑሬቸው ሁሉ ግራ የሚያጋባ ነው ።

በጉዲዩ የተቀየመች ቢሆን እንኳ ቅያሜዋን ልቧ ውስጥ ቀብራ አንዳችም ቅር የመሰኘት ምልክት ሳይታይባት ፣ እስካርሌትን እንደ ወትሮው በመጠኑ ፊት በማድረግና በትህትና በማጫወት ይዛታለች ።

እስካርሌት ደስስ እያላት አነጋግራት ስታበቃ ወደ ርቅ መውጣቷን ቀጠለች ። እየወጣች ሳለች ከሠዋላዋ አንድ ፈራ ተባ ያለ ድምፅ ስሟን ሲጠራ ሰማች ። ዘወር ብትል ዓይን አፋሩን ቻርለስ ሐሚልተንን አየ ችው ። በነጨ ግንባሩ ላይ ለስላሳና ቡናማ ፀጉር ተጠቅልሎ የሚታይ መልከ መልክም ልጅ ነው ። ዓይኖቹ እንደለማዳ ሰልጣ ውሻ ጥርት ያሉ ደማቅ ቡናማና እርግት ያሉ ናቸው ። ስስ አረንጓዴ ቀለም ያለው ሱሪውን ከባለሸንሸን ሸሚዙ ጋር ገጭ አድርጐ ሽክ ብሏል ። ገናዠር ስትልበት ጉንጩ ቀላ ። ምክንያቱም አሴዶች ፊት ዓይኑ አፋርና ሽቀ ጥቁዋ በመሆኑ ነው ።እንደ አብዛኞቹ ዓይን አፋር ወንዶች ሁሉ እንደ እስካርሌት ያሉ ግልፅ ፣ ተጨዋችና ጭንት የሰሽ ሴቶችን ያደንቃል ። አፏ እንኳን ከዚህ ቀደም ከአንተት በላይ ፈጣታ ባሻገር አሳይ

@OLDBOOKSPDF

ታው አታውቅም ።ስለዚህ አሁን ሙሉ ፈገግታዋን መግባ ሰላምታ ስታቀርብለትና ሁለት እጅጉን ወደሱ ስትዘረጋ ውላ ሆነና አረፈ ። ትንሩሽ አጠረው ።

"ውይ ቻርለስ ሐሚልተን ፡ የዋንቱ የጠዋቱ ሽጋ ! ነብስ ነገር ! መቼም ከአትላንታ ድረስ ይዜን ሁሉ መንገድ አጭርጠህ የመጣኸው የኔኑ ልብ ለመብላት መሆኑን ምንም ጥርጥር የለኝም !"

ቻርለስ በጣም ከመደንገጡ የተነሳ ትናንሽ ያመ ሞታት እጅጉዋን በእጁ አንደያዘ የሚደንሱ ዓይኖችዋን እያየ እየተንተባተበ ሊናገር ምንም አልቀረው ። አሁን እሷ የምታናግረው ዓይነት አንጋገር ሴቶች ለሌላ ወንዶች የሚያደርጉት ጭውውት እንጂ በሳሙራሽ ለሱ የሚሆን አይደለም ። ለምን እንደሆነ አያወቅ እንጂ ሴቶች ሁሉ እንደ ታናሽ ወንድማቸው እያዩ ደግ ይሆኑለታል ። እሱን ማሸነርመምና ለመዳጅነት መከጀልን ግን በጭራሽ አይታጠም ። ሴቶች ልጆች ከሌሎች ከሱ በቁንጅናም ሆነ በአለማዊ ሀብት ከሚያንሱ ወንዶች ጋር እንደሚያዴርጉት ሁሉ ከሱም ጋር እንዲሁም ከሱም ጋር የፍቅር ጨዋታ እንዲጫወቱ ሁልጊዜ ሲመኝ ነበር ። ሆኖም አልፎ አልፎ ይሽው ፅድል ሲያጋጥመው ደግሞ ይተነፍስበት ጀል ፡ይጠራው ነገር ቅጡ ይጠፋውና ይደናገጣል ። ይርበተበታል ። ጭራሹን በድንና ጄዳ ይሆናል ። ከዚያ ማታ አለጋው ላይ ይጋደምና ቀን ያመለጠውን ፅድል ሁሉ እያሰላሰለ መይዴ ይህን ብል ሞሮ መይዴ ያን ባደርግ ጥሮ እያለ ይቆጫል ። ጸሩ ምን ያደርጋል ሴቶቹ እንዴ ካዩትና ከሞከሩት በኋላ ያን ፅድል ለሁለተኛ ጊዜ የሚሰጡት በጣም በጥቂቱ ነው ።

ሌላው ቀርቶ ምንም እንኳ አፍ አውጥቶ ባያነጋግራት በልቡ ፡ በሚመጣው የበልግ ወር ሲያገባት ያሰባትን ሐኒን እንኳ ከልክ ባለፈ የዋህነትና ይሉኝታ ታጥሮ ቃል ሕያናግራትም ። እንዳንዴ የሐሩ ጨዋታና ማባባት ሁሉ ምንም እንደማይረባው ያስባል ምክንያቱም ሴወንድ ያላት ፍላጐት በጣም ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሳ ማንም እንደሱ ቢቆርባት ግዘዷና መከንፏ አይቀርም የሚል ዙርጠኝነት የሴለበት ፅምነት ስላለው ነው ። ቻርለስ እሷን የማግባትም ፡ስ ፋው የጨለጠ ነው ። ምክንያቱም ሲያነብ የሚጠላቸው ውድ መጽሐፎቹ የሚነግሩትን ስስፍታሪ ሲሰጠው ይገባል የሚለውን ፍቅር እሷ በሜራሽ ስለማትቀስቅስበት ነው ። እሱ ሁልጊዜ የሚመኘው እንዴት አክሳቲ ሁሉ እሳት የሚተራና ልቧ በተንኮል የተሞላ ሰንጀ ሴት እንድታፈቅረው ነው ።

እዚህ ደሞ እሳቷ እስካርሌት ኦሃራ ገደልከኝ ፡ ልቤን ሰተልከኝ ትለዋልች !

@OLDBOOKSPDF

አንድ ነገር ለመናገር ያስባል ነገር ግን ምንም አፍ የለውም። ቃል ለሙንፈስ አልተቻለውም። ሆኖም እሷ ሳታቋርጥ ጨዋታ ስለ ምታመጣ የሱ መናገር ባለማስፈለጉ በልቡ መረቃት። መቼም ፣ግሩም እንዳይለው ከግሩም በላይ የሆነ ዕውነት ነው ነገሩ።

"በል አሁን ፡ ተመልሼ እስክመጣ እዚችው ቦታ ትጠብቀኛለህ። የግብግቦውን ምግብ አብረን ነው የምንበላው። ደሞ ሌሎች ሴቶች ልትከተል ትሄድና ዋ! እኔ እቀናለሁ። ነገርከህ።" እነዚህ ቃላት ከነዚያ በግራና ቡቅኝ ስርጉድ ስርጉድ በሚሉ የውበት ጉድጓዶች ከተከበቡ ቀይ ከንፈሮች የወጡ ናቸው። በዛ ላይ እነዚያ በህይወት የተሞሉ ሽፋሽፍቶች ከበታቻቸው የሚያበሩትን ኩልል ያሉ ዓይኖች ያጫውታሉ።

"አላደርገውም" አሰ በመጨረሻ የሞት ሞቱን ተንፍሶ። አራጁን እንደሚጠብቅ በግ አድርጋ ታየኛለች የሚል ነገር እንኳን በእውኑ በህልሙም የለ።

በያዘችው የተጣጠፈ ማራገቢያ እንዴ ከንዴ ላይ በቀላሉ መት ታው ወደ ፎቅ ለመውጣት ፈቷን ስታዞር ፡ ዓይኗ አሁንም ከቻርለስ ጥቂት ርቆ በቆመው ሬት በትለር ላይ አረፈ። ያለጥርጥር የተንጋገ ሩትን በሙሉ እያምፀለ። ምክንያቱም እንዴ ደቦል ድመት ቆሞ የተ ንኮል ፈገግታ እያሳያት መሆኑን አስተውላለች። እንደገና በዓይኖቹ ከእ ማር ጥፍሯ እስከራስ ጠጉሯ ዳሰሳት። እንዲህ ያለው አስተያየት በሞ ራሽ አጋጥሟት የማያውቅ ዓይነት ነው።

"እሪ የሰማያቱ ያለህ!" አለች እስካርሌት ለራሷ በንዴት ፡ የጀራ ልድን የህልኒዚ መሀላ ተጠቅማ። "እርቃኔን ምን እንደምመስል እንደሚያውቅ ሰው ነው እኮ አስተያየቱ" ብላ ጭንቅላቷን ወደ ላይ አቅንታ ወደፎቅ ለመሄድ ደረጀውን ጀመረች።

እስካርሌት ፎጣና ብርድልብስ እሚቀመጥበት መኝታ ቤት ስትገባ ካትሊን ካልቨርት መስተዋት ፊት ለፊት ቆማ ትጌያጊያጣለች። ከን ፈሮቿንም እየነከሰች ቀይ ለማድረግ አበሳዋን ታያለች። ልክ የጉን ጮቿን ዓይነት አበቦች በጉሯ ላይ ሰክታለች። እነዚያ ደስ የሚሉ ዓይኖቿ በስሜት ተሞልተው ይደንሳሉ።

"ካትሊን" አለች እስካርሌት ፡ ቀሚሷን ሽቅብ እየጐተተች!

"ማንነው ያ ታች ቤት ያየሁት በትለር የተባለ ሰው?"

"አታቲውም እንዴ የኔ እመቤት?" ብላ በሹክሹክታ ጠየቀች፣ ዲልሲና የዊከስ ቤተሰብ ልጅች ሞግዚት ቱሜ ብለው ሰው ወደሚያ

@OLDBOOKSPDF

መብት ከፍል በጥርጣሬ አያየች ። "አቶ ጆን ዊክስ ፥ ፈት በትለር እዚህ በመምጣቱ ምን እንደተሰማው እንኳ ። እርግጥ አሱ ከኬዲ ጋር ለጥጥ ንግድ ጉዳይ ቀጠሮ ስለነበረው ኬኔዲ ወዲህ ይሁት መጣ ። ዝም ብሎ ጥሎት እንዳይጠፋ ቸግሮት ነው አብሮት እንዲመጣ ያደረገው"

"ምንድነው ሰውዬው ችግሩ ?"

"የኔ ቆንጆ ፥ ማንም በጂ ብሎ የማይቀበለው ሰው እኮ ነው !"

"እውነትሽን ነው !"

"ስነግርሽ ። ማንም ከሰው አይቆጥረው "

አስካርሌት ይሄንን የሰማችውን ነገር በፀጥታ ታጣጥም ጀመር ። ምክንያቱም ከእንደዚህ ያለ አገር አልቀበል ካለው ሰው ጋር ባንድ ጣራ ሥር ተቀምጣ ስለማታውቅ ነው ። በጣም ስሜት የሚነካ ነገር ነው ።

"ምን አድርገው ይሆን ?"

"አሄሄ! አስካርሌት ፥ በቅራሽ መጥፎ የባለጌ ሰው ሥራ ነው የሠራውስ ።ስሙ ፈት በትለር ይባላል ፥ የቻርልስተን ተወላጅ ነው— ከዚያ ነው የመጣው ። እዚያ ያሉ ዘመዶቹ በጣም ጣሩም የተባሉ ሰዎች ናቸው ። ነገር ግን ከሱ ጋር ንግግር እንኳን የላቸውም ።ካሮ ፈት ናት ባለፈው በጋ ያጫወተችኝ ። ለነገሩ ከሱ ጋር ምንም ዝም ድና የላትም ፥ ግን ስለሱ ልቅም አድርጋ ታውቃለች ። እረ ማንም ያቃል ። ታዲያ ይሄው ልሽ ከቂስት ፖይንት ይባረራል ። እኔማዲህ ይታ ይሽ ! ካሮ እንኳን አንዳታውቀው የተደበቀ አዘያፊ ነገር ሠርቶ ነው ። በዛ ላይ ያቺ አላገባም ያሳት ልጅገረድ ታሪክም አለ ።"

"ባክሽ ንገሪኝ !"

"የኔ እመቤት ምንም ነገር አታውቂም ማለት ነዋ ? ካሮ ባለ ፈው በጋ ነገረችኝ ። እናቷ አሁን ታሪኩን ማወጅን ቢሰሙ እታነታ ለሁ ነው እምትለው ። ነገሩእንደዚህ ነው ። ይሄ በትለር የሚባል ሰው አንዲን ቻርልስተናዊት ሴት ይይዝና በጋሪ ሽርሽር ይወስዳታል ። ማን እንደሆነች እስካሁን አላወኩም ፥ ጥርጣሬ ግን አለኝ ። መቼም ብታው ቀው ኖሮ እሺ ብላ አትሄድለትም ነበር ። አሊያም ሰው ሳታስከትል አትወጣም ነበር ። የኔ እመቤት ፥ ከሞላ ጐደል ሴሊቱን ሙሉ አቆይ ቷት በመጨረሻ ወደቤት — በአግሯ ። እህስ ቢሉት ፈረሱ በጥሶ ጋሪውን ጥሎ ስለጠፋ ጫካ ውስጥ ብቻችንን ቀረን ።መቼም ምን እን ደሆነ መገመት . . . ."

@OLDBOOKSPDF

"ጓደ መጣሁት አይሆንልኝም ። ንገሪኝ ባክሽ" አለች እስክርሌት ፡ የመጨረሻውን ክፉ ነገር ለመስማት ጓጉታ ።

"በሚቀጥለው ቀን አግባት ቢባል አሻፈረኝ ንክች አላደርጋ ታትም ፣"

"አዩ" አለች እስክርሌት ተስፋዋ ሁሉ ሞቶ ።

"ምን ይልልሻል ፡ ልጅቷን ምንም ስላላረኳት የማገባበት ምክን ያት አይታየኝም ። ወንድሚ እፋለመሞለሁ ፡ የእህቱን ስም አጥፍቷል አለ ። ዘንለር ሆዬ የማንንም ደንቆሮ ጅል ከማገባ ሞቱን አመርጣለሁ አለ ። ፍልሚያ ገጠሙ ። ሬት በትለር የልጅቷን ወንድም በፍልሚ ያው ላይ ገደለው ። በትለር ቻርልስተንን ለቆ መውጣት ነበረበት ። ወጣ ። አሁን ማንም ሰው አልቀበልህ አለው ። "ካትሊን በድል አድራጊነት መንፈስና በጊዜ ጨረሰች ። ምክንያቱም ዲልሲ ጽዳት ሥራዋን ለመሥራት ተመልሳ በመምጣቷ ነው ።

"ልጅ ወለደች እንዴ ታዲያ ?" አለች እስክርሌት በሹክሹክታ ወደ ካትሊን ጆሮ ተጠግታ ።

ካትሊን ራሷን በንዴል ነቀነቀች "ያው እኮ ነው ግን ፡ እንዴ አበ ሳሽድታል ።" መልሳ ተናገረችት ።

እንዲያው አሽሉይ እንን እንዲህ ባደረገችና ባየሁት አለች እስክ ርሌት በልባ ። መቼም እሷን አሳብባም ብሎ አይከራከም ። ያም ሆኖ ግን ሬት በትለር ያቺን ጅል ልጃገረድ አሳብባም በማለቱ እሱን የማ ከበር ስሜት ተሰማት ።

እስካርሌት ከቤቱ ፡ ዙሮ ካለ አንድ ቅልቅ ዋርካ ጥላ ሥር ከፍ ያለ ጉቶ ላይ ተቀምጣለች ። የቀሚሷ ዘርፍ በአካባቢዋና በባለሁ ለት አንች አረንጓዴ የሞርኮ ሞድ ጌጣጌጥ ጫማዋ ላይ ቡፍ ብሎ ወር ዷል ። በጅዋ አንዲት ሣህን አልኮሆም ። ሰባቱ አፍቃሪዎች በዙሪያዋ አሉ ። ግብዣው ሞቅ የሚልበት ለዓት ላይ ነው ። ሳቅና ጨዋታው ደር ቷል ። የብር ማንኪያዎች ከሳህኖች ጋር ሲጋ ጨ ይሰማል ። ጣፋጩ መጣው ከበድ ያለው የሥጋ ጥበስ ከሩት አፍንጫ ይወጋል ። አንዳ ንዴ ኃይለኛው ንፋስ ከወደ ጉድጓዱ የሚያመጣው ሞስ የተሰበሰበ ውን ሰው ድንገት አፍን ሲያደርገው ሲቱ በጫጫታ ሲቀበለው ወንዱ ደግሞ በማራገቢያ ለማባረር ቢጋይል ሲሰንገር ወላጋውና ድብልቅ ልቱ በጣም ይበረታል ።

አብዛኞቹ ወጣት ቤዶች ረዣዥምቹ አግዳሚዎች ላይ ከወንድ ጓደኞቻቸው ጋር ተቀምጠዋል ።

@OLDBOOKSPDF

አስካርሴት ግን የተቻለውን ያህል ወንድሞ በሁሪያዋ ለመሰብሰብ ባላት አላማ መሠረት ፡ አንዲት ሴት ሁለት ጐን ብቻ ስላላት ወንድ ጐኔ ላስተምሮ ካለች ሁለት ብቻ ለማስተናገድ እንደምትችል በመገመት ፈንጠር ብላ ለብቻዋ መቀመጡን መርጣለች ። ከየዛፉ ሥር የሚያማምር ጥቁቁር ቸኮለስ የለበሱና ሳካባቢው ድምቀት የሚሰጡ ደስተኛ ባልና ሚስት ይታያሉ ። ባለቻቸው የሞቱባቸው ሴቶችም ፅድሚ ሳይሰዩ ከንይናሞቹ ከመዳጅ ፈላጊዎቹና ከሳቂታዎቹ ልጃገረዶች ተለይተው ፡ ለብቻቸው ተስብሰበዋል ። የመጉት ሚስት የሆኑ ሴቶች ሴሳ አያገቡም — ይሂ በደቡቡ ውስዋ የተለመደ ነው ። በዕድሚያቸው ትል ትንት ምንም ሳይሰማቸው የልባቸውን ከሚጫወቱት ከአሮጊቷ ፎን ቲን ጀምሮ ፡ በመጀመሪያ እረግዝና አስከምትሰቃየው የአሥራ ሰባት ዓመቷ አሊስ ሙንሮ ድረስ ስለወሊድና ስለማህጸን ጉዳይ ሲወያዩና አንዳንድ ዋና ዋና መመሪያዎችን ሲለዋወጡ ማየት በጣም ደስ ይላል ።

አስካርሴት በጥላቻ ዓይን አያዮቻቸው በልፀ አንድ ላይ እጅብ ያሉ ወፋፍራም ቱሪዎች ይመስላል አለች ። ያገቡ ሴቶች ምንም ጨዋታ አያውቁም ባይ ናት ። እፀ አሽሌይን ብታገባ ወዲያውኑ በየ ዛፉ ሥርና በየእልፍኙ ውስዋ ከሚሰበሰቡት ያገቡ ሴቶች ጋር እንደ ምትቀላቀልና ጥቁር ሐር ለብሳ ጨዋታ የለሽና ቀልድ አልባ ንግግር እንደምታደርግ አልታሰባትም ። እንደማንኛዋም ልጃገረድ አዕምሮዋ መጥቆ እስከፍላጐቷ ማርከያ ድረስ ብቻ ነው የሚመስጻት— አይጥ ብታልም ዋሬዋን ።በዛ ላይ አሁን መቼም ከፍላጐቷ ውጪ የሆነ ማናቸውም ጨዋታ ፡ግናቸውም ውይይት ውስጥ መግባት ደስ አይ ላትም ።

ዓይኖቿን ወደጠበታዋ ደፋችና አንድ የተገመጠች ብስኩት ይዛ በሷሰ የምጣብ ፍላጐቷ የሚዳን ትታግላለች ።መቼም ማሚ እንዲህ ስትሆን ብታያት እሰየው ላሚ ወለደች ነው የምትለው ።ምንም እንኳ የአፍታሪ መዓት በሁሪያዋ ቢያንጣጥብ በህይወቷ እንደዚህ እንዳውኑ ከፍታት፡ እንደዚህ እንደአሁኑ ቅስሚ ተጋሳክሶ አታውትም። አሽሌ ይን በሚመለከት ትላንት ማታ የንደፈችው ፕላን ለምን እንደሆነ በማታውቀው ምክንያት ከሽፎባታል ።ሴሎች በደርሆን የሚቆጠሩ ወንዶችን ለመሳብ ችላለች ። አሽሌይን ግን አልቻለችም ።ስለዚህም የትላንትና ከሰዓት በኋላ ፍርሻቷ ሁሉ ተመልሶ ጭንቅላቷን ወጥሮ ዋታል ።ልቧ በፍጥነት ይመታ ይመታና ደማም እርጭ ብሎ ድም ፀን ያጠፋል ። ጉንፈቷ እንደፍም ይቀሰና ደሞ መልሰው አመዱን ይነስንስባቸዋል ።

@OLDBOOKSPDF

አሽሌይ በሷ ዙሪያ ከከበቡት ወንዶች ማህል አንዱን ለመሆን ጥረትም አላደረገ ።እንዲያውም ከመጣች ጀምሮ ለብቻዋ አላገኛት ውም ። እረ እንዲያውም ከሰላምታ በቀር ቃል እንኳን አልተለዋወ ጡም ። በጓሮው ያትክልት ቦታ ስትመጣ እሳው ድረስ መጥቶ አግኝ ቷት ነበር ፤ ነገር ግን ያቺ በስንት መከራ ተንጠራርታ አትከሻው ጋ የምትደርሰው ሚላኒ ከንዲን ከከንዱ እንዳጣመረች ተጣብቃበታ ለች ።አስክርሌት በየት በኩል ታነጋግረው ።

ሚላኒ በጣም ቀጫጫ ናት ።ሰማላጋና ቢነኩት ጥርምስ የሚል ሰውነት ነው ያላት ።ሲያዩዋት በእናቱ ሰፊ ቀሚስ ውስጥ የተደበቀ ህጻን ትመስላለች ።በዛ ላይ አፋርታሞቹና ደንጋጣዎቹ ትላልት ዙናማ ዓይኖችዋ ሲጨመሩ የባሰውን ስስ ያደርጓታል ።ሐር ጥቅል በጉሯ እንደጥቁር ደመና ተከምሮ አንዲት የሐር ቅርንጫፍ እንዳትወጣ ተደርገ በመረቡ ውስጥ ታቅፏል ።ይሄ ጥቁር ነዶ ወደ ሚንቧሯ ላይ ረሸቦምና ሠሬ በታ የተከማቸ በመሆኑ የልብ ቅርፅ ፈጥን ያሳላ ዋል ። የጉንጯ አጥንት በጣም ሰፊ ፤ አገጯ በጣም ሹል የሆነ በጣም የሚወደድ ጨዋ ፊት ይሁን እንጂ ግልፅ ያለ ጠጣፋ ፊት ነው ። እሷ ደግሞ ይህን ግልጥነቱን የምትሸፍንበት አንዳችም የሴት ጥበብ የሌላት ናት ።እሷ እንደመፊት ቅልል የምትል ነፋንደሚር ጣፋጭና አንደምንጭ ውሃ ጥርት ያለች መስታወት ናት ።ፊቷ ብርሃን እንደሚያሳልፍ ሁሉ ውስጡዋን የሚያሳይ ይመስላል ።ብቻ በጣም ግልፅ ያለችም ትሁን ደቃቃ ፣ጣርማ ሞገስ ያለው አረማመዷ ቢጣም የሚያስነብራትና ከአ ሥራ ሰባት ዓመት ዕድሜ በላይ አድርገ የሚያሳያት ነው ።

ግራጫው ሱፍ መሰል ቀሚሷ ከቀይ መቀነቷ ጋር በዘርፋ ዘርፉ የተሸፈነው ሰውነቷን ገና እንዶልጅ ሰውነት ያልጠና ያስመሰለዋል። ቀይ ወራጅ ዘርፍ ያለው ቢጫ ባርሚጣዋም ከፊም መልክ ያለውን ቆዳዋን የበለጠ ያፈካዋል ።ከበድ ከበድ ያሉት የጆሮ ጉትቻዎቿ ከነረዣዥም የወርቅ ጠርዛቸው ፣ በጥንቃቄና በጥራት ከታሠረው የፀጉሯ መረብ ሥር ጀምረው ይንጠለጠሉና ቡናማ ቅጠሎች የሚንፀባርቁበት ከከ ረምት ጫካ ውስጥ የሚታይ የረጋና በጥቂት ውሃ ከመሰለው ዓይኗ አጠገብ ይጫወታሉ ።

በጭምት መውደዷ እንደታጀበች ፈገግ ብላ ነው ለአስክርሌት የእንኳን ደህና መጣሽ ሰላምታ የሰጠቻት ።እግረ መንገዷንም አረን ጓዴ ቀሚሷ እንዴት እንደሚያምር አድንቃ ነግራታለች ።አስክርሌት ግን ከአሽሌይ ጋር ለብቻዋ ለማውራት የነበራት ጉላጉት በጣም ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሳ በአግባቡ እንኳ ለሰላምታዋ አፀፋ አልመለሰ ችላትም ።ከዚያን ሰዓት ጀምሮ አሽሌይ ከእንግዶች ሁሉ ፈንጠር

@OLDBOOKSPDF

ብሎ ሚላኒ ሥር ባሰችው በርጨጣ ላይ ተተምጦ የዝግታ ወፈውን እያወራ ያንን እስክርሌት የምትወደውን የቅስታ ፈጣታውን ፈገግ ሲል ቆይቷል ።ንግሩን ሁሉ ያከፋው ደግሞ እሱ በቀስታ ፈገግ ባለ ቁጥር ሚላኒ ዓይኖች ውስጥ የሚፈጠረው አንድ የደስታ ብልጭታ ፤ እስክርሌትን ሚላኒ ውብ ናትኩ እስከማለት እንድትደርስ ማድረጉ ነው ።

ሚላኒ አሽሌይን ስታየው ደግሞ በዚያ በግልፅ ፊቷ ላይ የሚታየው ብርሃን በውስጧ አንድ የሚንቀለቀል እሳት እንዳለ ከመናገሩ የተነሳ ፤ ያፈቀረ ልብ ሰው ፊት ላይ የሚነበብ ከሆነ አሁን ሚላኒ ሐሚልተን ላይ የሚታየው እጅግ አስተማማኝ ማስረጃ ነው ያሰኛል ።

እስክርሌት ሁለቱን ላለማየት በጣም ሞከራ ነበር ፤ነገር ግን አልሆነላትም ።የትም የትም ስታይ ቶይታ ማረፊያዋ እንሱ ሆኑ ። ባየቻቸው ቁጥር ደግሞ በዙሪያዋ ከሚያንጎበጎቡት የወንድ ወዳጅቿ ጋር የምታነጻጽርውን ጨዋታ ፡ልፊያ ፡ሣቅ ንግግር በጣም አጉልታ ፤ እሰው ፊት የማይባለውን ነገር ሁሉ በድፍረት እየጮኸች እየተና ገረች ፣ የጀሮ ጉትቻዎቿ ከልኩ በላይ እንዲደንሱ ሞንቅሳቲን እያነታ ነቀችና እየተምነቀነቀች እንትስታሴሞን በመሉ ከቅድመ በአጥፍ ትጨምር ጀመር ።የባጡን የቆጡን ትቀባጥራለች ፡የትኛውም ወንድ ከልቡ እንደማይጫወት ፡ሞንኛውም ወንድ ሌትን አስኪያገኝ ብቻ አበድኩ ሞትኩ እንደሚል ፡ማንኛው ወንድ ምንም ቢላት ከእንግሊህ እንደማታምን — ጮክ እያለች ትናገራለች ።በንግግሯ መሀልም እንደ ማጣፈጫ የምትጠቀምበትንና ወንዶቹም ወደው የሚስቁበትን "ድራዲ ንዳንዳን" የሚል ፈሊጥ ጣልታ ታስገባለች ።ይሄ ሁሉ ሆኖ ግን አንዱንም ነገር አሽሌይ ልብ ያለ አይመስልም ።እሱ ከሚላኒ ላይ ዓይኑን አልነቀለም ። ቀና እያለ ዓይን አይኗን ያያል ።አሷም ቁልቁል እሱን ብቻ ትመለከታለች ።ከዓይኖቿ ውስጥ የሚፈነጠቀው ጨረር የሱ መሆኑን የሚያረጋግጥ የባለይዞታነት መብትን ያዘለ ዓይነት ነው ።

ስለዚህ እስክርሌት ቅስሚ ተንክቷል ።ተጐሳቁላለች ። መቼም ከውጪ ለሚያይ ሰው ማንም እንደሷ ገበያው የሞቀላት ልጃገረድ ምንም የሚያጐሳቁላት ነገር እንደማይኖር ይረዳል ።ያለጥርጥር በዚያ ጉብኝ በታ ከሷ የባሰ ቆንጆ ፡ከሷ የበለጠ ማራኪ የለም — የወንድ ዓይን ሁሉ ማረፊያ እሷው ናት ።ወንዶቹ ላይ የፈጠረችባቸው መተራ መስ ሴቶቹ ላይ ከፈጠረችው በቅናት እንጀት መቁሰል ጋራ ተደ ምሮ በሌላ ጊዜ ቢሆን ኖሮ ነብሷን ባስደሰታት ነበር ።

ቻርለስ ሐሚልተንን እንደማይነታነት አድርጋ በዓይኗ እየሳበች ከአጠገቧ ተከላው ከሷ በቀኝ በኩል ተጣትሮ ፡የታርሌተን መንትያ

@OLDBOOKSPDF

ወንድማማቾች እንኳ ሲጎዳኙ ያለምንም ጠመልት ሞኒል ፍባንድ አጅ የሷን የንሩስ ማራገቢያ ይዟል ።ብሌላኛው እጁ ካመጣው አንዲት ነገር ያልተመለሰትን የማብጥ ሳሀን ይዟል ።ካሁን አሁን ዓይኑን ጣለ ብኝ ስትል ።ዘግትርነት ከቅድም እስካሁን ዞር እንኳን አልልም ያላት ምስኪኗ ሐኒ ።ምሬቷ በዝቶ በእንባ ልትገነፍል ምንም አልቀራት ። ጭምቱና ዓይናፋሩ ካድ ደግሞ ክእስክርሌት በጣራ በኩል በኩራት ቆሞ አየያጋገመ ቀሚሷን በመግሙት እንድታስታውሰው አየገሙገሙ ቀና እያለ በታመቀ ሞላቻና ቅናት በሚጨሱ ዓይኖቹ ስቱዋርትን ያስተውላል ።በሱና በመንትዮቹ መሀል የጠበ ክብሪት ከተጫረ ጥሂት ቆይቷል ።ሽማግሌው ፍራንክ ኪኔዲ ድሪያ አንጻማሪው አውራ ዶር ከንሩን አውርዶ ፣ ከዋርክው ጥሳ ወደምግብ ጠረጴዛ እየተጣ ደፊ እየሄደ ፣ ለዚህ ሥራ የተመደበ ብደርሀን የሚቆጠሩ አሳላፊ እሽ ከሮች የሌሉ ያመስል ቆንጆ ቆንጆ ምግብ እያነሳ በመመላለስ የእስክ ርሌትን ዓይን ለማግኘት ደጅ ይጠናል ።በዚህ ምክንያት እፈጭው ሱዌለን አትርፋ ፣ እብዋ ብሰ ንዴቷና ኢልኳ ሴት ልጅ ልትሸፍነው ከምትችለው በላይ ሆኖባት እስክርሌትን በማለምጫ አፈር ድሜ ታስገባታለች ።ትንሿ ካሪን ድግሞ ምንም እንኳ እስክርሌት ጠዋት አይዞሽ አታጪውም እያሰኘ ያበረታታቻት ቢሆን ፣ብራንት የወጉሯን መቋጠሪያ ጥብጣብ ነክ አድርጉ ""ታዲያስ ሲስ!"" ከማለት ያለፈ ጨዋታ እንኳ ላያጫውታት ልቡን ሁሉ ለእስክርሌት በመገበሩ ፣ ለቅሶ ለቅሶ ብሏታል ። ለወትሮው በጣም ሩህሩህ ሆኖ ባሳበየለሽነት ተገዘናንቱ ትልቅ ሴት የሆነች እስኪመስላት ድረስ ያጫውታት ፣ያሽ ኮረምማት ነበርና ካሪን ወጉሯን ከፍ አድርጋ ተሠርታ ፣ቀሚሷን ዝቅ አድርጋ አስፍታ እንደፅውኑትኛ አፍታሪ ክንኑ የምትቀመጥበት ቀን ከዛሬ ነገ ይመጣል እያለች ስትናፍቅ ከርማለች ።አሁን ታዴያ ጭራሽ ለእስክርሌት የወደቀ ይመስላል ።የሙንሮ ቤተሰብ ሴቶች ልጆችም በፎንቱን ቤተሰብ ወንዶች ልጆች ከድተዋቸው መሄድ ቅፌታቸውን ለመሸፈን ችለው ነበር ።ነገር ግን ቶኒና አሌክስ በእስክርሌት ዙሪያ ባለው የጥሎ ግለፍ ውድድር የወንዶች ተሰበት ማሀል ተደባልቀው በሷ ልብ ውስጥ ቦታ ለማግኘት ሰልፍ ንብተው ሲቁለጨለጩ ማየት አና ዴቸዋል ።

የእስክርሌትን ሥራ ፣የእስክርሌትን ብልግና በመቃወም ቅንድባ ቸውን ከፍ እያደረጉ ሌሉቲ ታርሌተን የሽሙጥ ቲሌግራም ያስተላል ፉስ ።እስክርሌት ""ፍጥነት"" ከሚለው ቃል በቀር ሌላ የእንትስታሴ ሀግ የላትም ።ሶስቱ ወጣት ሴቶች በአንድነት ባለጌዋ የፀሐይ መከላ ከያ ባርኔጣቸውን እንሰተው በበቂ — መብላታቸውን ገልፀው ፣ ምስ ጋና ያቀርባሉ ።ግሩታቸው ባሉት ወንዶች ክንድ ላይ ጣታቸውን ጣል

@OLDBOOKSPDF

እያደረጉ ወደሮዙ የአትክልት ቦታ ወደበደይ ውበት እንዲሁም የበጋ ውን ቤት ማማር የሚያዩ ለመምሰል ይጣጣራሉ ።ይሄ በዘይ ከዋናው ትርዒት ማሬማፊማ መቼም እንኳን ወንድ ዓይኑን ለጣለባት ለሴላም ሴት ቢሆን የሚጠፋ ጥበብ አይደለም ።

እስካርሴት ፣ የደም ግባቷ ምርኮኞች የሆኑ ሶስት ወንዶች በሷ ቆቹ ላይ ሁሉ ከልጅነት ጀምሮ የሚታይ ተመሳሳይ ምልክት መፈ ለግ ያስፈልጋል እያሉ ወዲህ ወዲያ ሲያዩ እያየች ከት ብላ በግሳ ድምፅ ሳቀችና ይህን ሁኔታ ያስተውል እንደሁ ለማረጋገጥ ሰረቅ አድርጋ ወደ አሸሴይ ተመለከተች ። እሱ ወይ ፍንክች ያባ ቢላዋ ልጅ ።አጅሬ የሚሳኒን መቀነት ጫፍ በጣቶቹ እያፍተለተለ በመጫ ወት ወደላይ ፈገግ ይልላታል ።

መቼም እስካርሴት የዚችን የሚላኒን ነጭ ቆዳ ደሟ እስኪወርድ ድረስ በጥፍሯ ብትቧጥጠው ፣ አሲያም በጥርሷ ብትነሰገላት ፈታዴ ነበር ።

ዓይኗን ከሚላኒ ነቀል አድርጋ ወደሌላ አትጣጫ ዘወር ስታደርግ ከዘገቡ ነጠል ብሎ ቆሞ ከጆን ዊክስ ጋር የሚያወራው ሬት በት ሶር ሲያያት ዓይን ለዓይን ተጋጠሙ ።ቀደም ብሎ ጀምሮ ሲያስተውላት ቆይቶ ኖሮ ነና ስታየው ሳቂ ።እስካርሴት ከተሰበሰበው ህዝብ ሁሉ ፣ ከላቅ ከፍንደቃዋ ጀርባ ምን የተደበቀ ጥላቸት እንዳለት የሚያውቅ ፣ ይሄ ሰው ብቻ እንደሆነና በማጠቁም አንቺ ጉድኛ በሚል የሽርደዳ ስሜት የሚገረም መስሎ ታያት ።እሱንም በጥርሷ ብትዘለገለውና በጥ ፍሯ ብትቧጥጠው ደስታዋ ነበር ።

"ብቻ በዚህ ግብግ ቦታ እስክከሰዓት በኋላ ልቆይ እንጂ'አለች በልቧ''ለማታው ዝግጅት ሴቶቹ ሁሉ ትንሽ ስመተኛት ወደ ፎቅ ሲወጡ ፣እኔ ምድር ቤት እቀርና ከአሸሴይ ጋር ለማውራት ዕድል አገኛለሁ ።መቼም እንዴት ተወዳጅ ሆኜ እንዶ ዋልክ አሳምሮ ተገን ዝቧል ።''ደሞ በሌላ ተስፋ ልቧን እሹራሩ እያለች ታባብለ ጀመር። "ደሞኮ እውነቱን ነው ።ሚላኒን ማጫወት ይገባዋል ።ሌላው ቢቀር የአክስቱ ልጅ ናት ።ተወዳጅም አይደለች ።እሱ ጐኗ ካልሆነና አይሆሽ ካላላት እንዲሁ የግድግዳ ጌጥ ሆና መቅረቷ ነው ።''

በዚህ አዲስ ሀሳብ አዲስ ድፍረት ወለደች ።አዲስ ተስፋ አለመ ለመች ።ስለዚህም የጀመረችውን ወንዶችን የመሳብ ዘመቻ በእጥፍ አጠናክራ ቀጠለችና ኢላማዋን ቻርለስ ላይ አነጣጠረች ። እነዚያ ቡናማ ዓይኖቹን በጉጉት እሷ ላይ ጥሏቸዋል ።ለቻርለስ በጣም ግሩም ቀን ነው — የህልም ቀን ።ያላንዳች ጉልበትና ድካም በእስካር

@OLDBOOKSPDF

ሌት ፍትር ተነድፋ ወይዘሮ ፀደይ ዳኛቸው ከሐኒ ጋር የነበራ
ውን ግንኙነትና ሐኒን ራሷን ጨፍጋጋና ድንግጡግዝ ያለ የገ
ጋታ አየር ውስጥ ገፍቶ እንዲከታቸው አድርጐታል ።

አሁን እንግዲህ ሐኒ ቀሚን ጆሮ እሚሰነጥቅ ድምጽ ያላት
ድንቢጥ ወፍ ሆና ስትታየው እስካርሌት ደግሞ የምታምር የመ
ስቀል ወፍ ሆናለታለች ። ትላፋዋለች ፣ ታሽኮረምመዋለች በማራ
ኪው ዓይኗ ታጫውትዋለች ። ጥያቄ ትጠይቀውና ራሷ እየመለሰች
አንድ ቃል ሳይናገር ሁሉንም የሚያውቅ አስተዋይ ሰው ነኝ ብሎ
እንዲገምት ታደርገዋለች ። ሴሎቹ ወንዶች ነገሯ ሁሉ እንቆቅልሽ
ሆኖባቸዋል ። ቻርለስ እጅግ ዓይናፋር ከመሆኑ የተነሳ ሁለት ተ
ታታይ ታላት እንኳ ገጣጥሞ ስሚት እንዲሰጡ ማድረግ የማይች
በመሆኑ እነደዚህ ግልጽ ባለ ወኔታ ወደሱ ሚዘንበሏ አናዴቸዋል
ከውስጣቸው ሊገነፍል የደረሰው ንዴታቸውን ለመሸፈን ሲሉ ጨዋ
ነታቸውን ከፉኛ ወጥረውታል ። ሁሉ ሰው እርስ በርሱ ሲባላ ደር
ሷል ። በአሽሌይ ላይ ያነጣጠረችው አስካሁን አልቀናትም እንጂ
በሌሎቹ ወንዶች ላይ ያነጣጠረችው ኢላማውን መትቷል ። አስካ
ርሌት የመጨረሻው የአሳማ ጥብስና ዶሮ ከተበላ በኋላ ኢንዲያ
ተንስታ ወደ ቤት እንግባ ብላ ሌቶቹን ለመኝታ ትጋብዛለች የሚል
ተስፋ ነበራት ። ከቀኑ ስምንት ሰዓት ነው ። የከሰዓትዋ ፀሐይ አናት
ላይ ታርፋለች ። መሞቅ ነው ። ሆኖም ኢንዲያ ሶስት ቀን መሉ
ግብግቡን ስታዘጋጅ ደፋ ቀና ስትል ስለከረመች የዛፉን ጥላ ወዳ
ዋለች ። ከአንድ ከፈይትቪል ከመጣ ደንቆሮ ሽማግሌ ጋር ቁጭ
ብላ ትነታረካለች ።

ሰው እንቅልፍ እንቅልፍ የሚለትና የመደበት ሁኔታ ይታይ
በታል ። ኔግሮዎች ምግብ ተቀምጠበት የነበረውን ጠረጴዛ ያፀዳሉ—
ወዲህ ወዲያ ይላሉ ። ውካታውና ሳቁ ቀስ በቀስ እየሟሸሸ በየቡ
ድኑ ቀለበት ውስጥ ፀጥታ እጁን እያስገባ መጥቷል ። ሁሉም የጠ
ዋቱ ግብግ ሥነ ሥርዓት ማለቁን የምታበስረውን አስተናጋጅ እየ
ጠበቁ ነው ። ማራገቢያዎች በቀስታ እየተንቀሳቀሱ ነው ። አያሌ
ሰዎች በጥጋብና በወበቁ ምክንያት ምኞት አጥተው ይንቆራጠጣሉ ።
ግብግቡ ስላበቃ ሞታቷ ፀሐይ ለብ እስክትል ድረስ አረፍ አረፍ
ብለው የእንቅልፍ መቅሰሳቸውን ለማግኘት ይፈልጋሉ ።

በዚህ በጠዋቱ ግብግና በማታው ዳንስ መካከል ያለውን የእ
ረፍት ጊዜ በሰላምና በፀጥታ ማሳለፍ በአብዛኛው ሰው ዘንድ የተ
ለመደ ነው ። ወጣት ወጣቶቹ ግን ገና ጉልበታቸው ያልደከመ ፣
ሮጠው ያልጠገቡ በመሆናቸው አሁንም ከመቅበጥበጥ አልቦዘኑም ።

@OLDBOOKSPDF

ነገሩ በድን መደሌላው እየተዚዚሩ በለስላሳ ድምጻቸው በቀስታ አያወሩ ፡ ይዝናናሉ ። እንደፈረስ ግልገል ያመ ትኩስ ናቸው ከቁ ንጅና ጋር ንጽለኛነት ይነበብባቸዋል ። የእኩለ ቀን በሐይ ድካሙን ሁሉ በተበበሰበው ሰው ላይ አመርቃበታለች ። ሆኖም በድካሙ ውስጥ የመሸገ ታምቆ ሲፈነዳና ከዛድ እሳት ሊያቀጣጥል የሚ ችል የሰሚት ከምኞትም አለ ።

ሲትና ወንድ በጣም በሚያምር ሁኔታ ተጣምረዋል ። ትንሽ አመፀኛነት በደስ ደሳቸው ውስጥ አለ ። ትንሽ የልማዳነት ባህሪም አ ።

ሠ በሐይዋ እያበረታች በሄደችና ጊዜውም ቀስ በቀስ ባለፈ ሲር እስክርሊትና ሴሎችም ሰዎች ወደ ኢንዲያ አተኩረው ያያሉ። ግማር ሁሉ ወደ መሞቱ እቅራቢያ ነው ። እፀዋታው መቃብር ውስጥ ይንፃት ተነስቶ እንዳረገ ሁሉ የጂራልድ ድምጽ ጋል ባለ ቃና ኢሙህ ተሰማ ። ከሚበገርው ጠረጴዛዎች ጥቂት ራቅ ብሎ ክጆን ዊክስ ጋር በጣም ምቹ ያለ ክርክር ይዟል ።

ፕ "እረ በመድኃኒአለም፣ ሰውዬ! ያንኪዎቹን ከፎርት ስምተር ካባረርናቸው ወዲያ ፡ ደሞ የያሚን በሰላም መጽፊያር አመጣህብኝ! ሰላም! ደቡብ ክህብረቱ የተገነጠለው በጎበፈቱ ደግነትና ርህራሄ ሳይሆን በጉልበቱ መሆኑን ማለየት አለበት ። በሚያደርገው ነገርም አንዳችም ሰድብ ሲሰደብ እንደማይገባው እሁንም በፈርጣማ ክንዱ ማረጋገጥ ይኖርበታል ። "

"ወይዜ እምላክ!" አለች እስክርሌት በልቧ ። "ይኸው ጀመረ እንግዲህ በቃ አሁን እንግዲህ ሌሊቱን ሙሉ ቁጭ አድርጉ ሲያጨቃጭቁን ሊያድር ነው።"

በአንድ አፍታ አየሩ ላይ ሲያንጣባብብ የነበረው እንቅልፍና መያበት ድራሹ ጠፉና በየታው ምት ያለ የንግግርና የክርክር አውሎ ንፋስ ተነሳ ። ወንድ ወንዶች ከየአግዳሚውና ከየወንበሩ ፡ እጆቻ ቸውን ለ ቡጢ እንደሚያዘጋጁ ሁሉ ጨብጠው እየተነሱ አንዱ ካንዱ የበለጠ ለመደመጥ ጮክ እያለ እየተናገረ ባንድ ጊዜ አካባ ቢውን ድብልቅልቁን አወጡት ። ጆን ዊከስ ሲቶቹ እንዳይሰላቹብኝ ስለማናቸውም ፖለቲካም ሆነ ስለአስፈሰፈው ጦርነት እንዳታነሱ ብሎ በለመነው መሠረት ከጠዋቱ ጀምሮ ምንም ቃል ሳይተነፈስ ቆይቶ ነበር ። አሁን ታዴያ ገና ጂራልድ "ፎርት ስምተር" የሚ ለውን ቃል ሲናገር ሲሰማ ሰው ሁሉ ድካሙም ሆነ የእረፍት እን ቅልፍ ተረሳውና አካሉም ቀልቡም እነርሱና ላይ ሆነ ።

@OLDBOOKSPDF

"እንደ*ታ፣ እንዋጋለን እንጂ! ።" ሌቦች ያንኪዎች፣ . . . "በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ድባቅ እንመታቸዋለን ። . . ." "ምን ጊዜም የማይረሱት ትምህርት እንሰጣቸዋለን ! . . ." " በስላም መደራደር ነመቼ በሰላም በጂ ይሉና ? . . ."""የለም የለም ። "

"ሊንከን ኮሚሽነሮቻችንን እንዴት አድርጎ እንደሰደባቸው አታዩም እንዴ ? "ታዲያስ ሰምተርን ነጻ አወጣለሁ እያለ እየማለ፣ እየተገዘተ ስንት ሰምንት ሙሉ አጉላላቸው ! . . ." "ጦርነት ፈሊ ገሞል ጦርነት እስኪያንገሸግሻቸው ድረስ ከንዳችንን እናሳያቸዋለን!" ከሁሉም ድምጾች በላይ የጀራልድ ንልቶ ተሰማ ። እስካርሌት ልትሰማ የቻለችው ግን- "ጎረ በግዚሃር ! የሀገሮች ነግነት ነው!" የሚለውን ደግመው ደጋግመው ሲሙሁ ነው ። ጀራልድ በጣም ይሰ ብሎታል ፣ ልጂ ግን ክፍቷታል ።

መንጠለ ፡ ጦርነት . . . መንጠለ ፡ ጦርነት . . . ። እነዚህ ቃላት ሰረኸቦም ጊዜ ሲደጋገሙ እንደቆሳ ብስል የማይድን የመሰልቸት በሽታ ተክሰውባት ቆይተዋል ። ሀሬ ግን ታሎቹ የሚጠሩበት ድምጽ ራሱ አሰጠሳት ። ምክንያቱም ይህ ድምጽ ማለት የክርክሩ መጋ ጋል ማለት ነው ። ይህ ድምጽ ማለት እነሱ ከርክራቸውን ሰረ ጅም ጊዜ በቅጠሉ መጠን እሷ እሽሌይን ለብቻው ለማንጋገር ታመ ቻቸው የነበረውን ዕድል ማጣት ማለት ነው ። ደሞክ ጦርነት እን ደማይኖር ሁሉም ልባቸው ያወቀዋል ። እንደው ለመናገር ሱስ፣ እንደው ለእንደበት ወግ ሰመናገር ያህል ብቻ ተናግረው መልሰው ራሳቸውን ማጸመጥ ስለሚጠዱ ነው ።

ቻርለስ ሐሚልተን ከሴሎቹ ወንዶች ጋር ተንስቶ አልሄደም። ስለዚህም ብቻውን ከእስካርሌት ጋር የመቆየት ዕድል በማግኘቱ ወደሷ ጠጋ ዘመም ብሎ አዲስ የተወለደው ፍቅር ብርታትን ሰጥ ቶታልና በሹክሹክታ ያናግራት ጀመር ።

"እስካርሌት በበኩሌ . . . በበኩሌ . . . የምንዋጋ ከሆነ ወደ ደቡብ ካሮላይና ሂጂ እዚያ ያለው ሠራዊት ሙስጥ ገብቼ ለመገ መት ገና ዱሮ ወስኛለሁ ። ዋድ ሐምፕተን ፈረሰኛ ሠራዊት እየመ ለመለ ነው አሉ ። ያለጥርጥር ከሱ ጋር መሄድ እፈልጋለሁ ። በጣም ደንቅ ሰው ነው— ደሞም ያባቴ ጥሩ ጓደኛ ነበር ። "

እስካርሌት "ታዲያ ምን ይጠበስ፣ ሶስት ጊዜ ላጨብጭብለት እንዴ ስለጅግንነቱ!" አለች በልቧ ። ቻርለስ የልቡን ምሥጢር ለች ርብ መጻፏ ሚካሬሉ ነው ። ምን መመለስ እንደሚገባት ባለማወቋ ዝም ብላ ታየዋለች ። በእንዲህ ያለው ጉዳይ ውስጥ ሴቶች መግባት

@OLDBOOKSPDF

ይፈልጋሉ ብለው ለምን ወንዶቹ እንደሚጀምሉ ሁልጊዜ ይገርማታል። እሱ ግን ዝምታዋን እንደመቀበል ወስደውና በችኮላና በድፍረት ቀጠሉ።

"ብሄድ፣ እኔ ብሄድ ትር ይልሻል እንዴ እስካርሌት?"

"ትራሴ ውስጥ አንተቲን ቀብሬ ስንሰቀሰቅ ነው የምከርመው" አለች እስካርሌት ከንፈት በላይ፣ እሱ ግን የምር አድርጎ ስለመሰደዉ ፊቱ በደስታ ቀላ። እጅዋን በቀሚሷ እጥፋት ውስጥ ብትደብቀውም እሱ በድፍረቱ ተደስቶ ሹራሽ እጅዋን ከሃቀሚሱ ሞምቅ አደረገው። በዝምታ ሁሉን ነገር መቀበሏ በጣም አስደስቶታል።

"ትፀልይልኛለሽ ታዲያ"?

"ምን ያለው ጅል ነው በሞቲ- የቂል ቆንሲል! "አለች እስካርሌት በልፂ። ምርር ብላ። ድንገት ከዚህ ወሬ የሚገላግላት ነገር ባገኝ ብላ አካባቢዋን ቃኘች።

"ታዲያስ እንዳልኩሽ ታደርግልኛለሽ?"

"እንዴታ ቻርለስ! ቢያንስ በየማታው ሶስት ጊዜ መቁጠሪያዬን ይገር እፀልይልሃለሁ።"

ቻርለስ አካባቢውን እንዴ ዘወር ብሎ አየ። ትንፋሹን ዋጥ ሐሞቱን ከስትር አደረገና አያት። ምናልባት ብቻቸውን ሊሆኑ የሚችሉበት ሌላ አጋጣሚ አይኖር ይሆናል። አጋጣሚው እንኳ ቢሰጠው፣ እንዲህ ያለውን ከሰማይ የወረደ እድል ለመጠቀም ድፍረቱ እንደዛሬው ላይኖረው ይችላል።

"እስካርሌት፣ አንድ ነገር ልነግርሽ አፈልጋለሁ። እኔ— እ'ኔኮ አፈቅርሻለሁ።"

"እ?" አለች እስካርሌት፣ በሚከራከሩት ሰዎች አሻግራ አውንም ሚላኒ እግር ሥር ቁጭ ብሎ ወደሚያወራው አሽሌይ እየተመለከተች።

"እውነቲን ነው!" አለ ቻርለስ በሹክሹክታ። ወጣት ሴቶች እንዲህ ያለ ነገር ሲነገራቸው ወይ ይስቃሉ ወይ ይጮሃሉ አሊያም ልባቸው ፈስሳ ይወድቃሉ ብሎ ይገምታል። እሷ ምንም የሆነች ችው ነገር የለም። "አፈቅርሻለሁ! አንቺ በዓለም ላይ ካሉት..." በሕይወቱ ለመጀመሪያ ጊዜ አፋን ፈቶ በሴት ፊት ለመናገር ድፍረቱን አሳኝቷል። "በዓለም ላይ ካሉት ሴቶች ሁሉ እጅግ የተዋብሽ፣ በጣም ደግና ልዩ ጣዕም ያለሽ የማር እሸት ነሽ። ሁሉ

@OLDBOOKSPDF

ነገርሽ ተወዳጅ ነው...ስለዚህም ከልቤ አፈቅርሻለሁ። እንደኔ ሌላ ወንድ ትወጂልሽ ብዬ ተስፋ ባላደርግም የኔ እመቤት ፤ ፈታድሽ ሆኖ ትንሽ ብታደፋፍሪኝ እንድታፈቅሪኝ ስሚድረግ በዓለም ላይ ያለ ማንኛውንም ነገር ላደርግልሽ ፍጹም ዝግጁ ነኝ። እኔ ወደ ፊት . . . ”

ቻርለስ በሚሀል አቋረጠ። የውስጥ ስሜቱን ለእስካርሌት ገልፁ ለማሳየት ምንም ዓይነት ሌላ መንገድ አላገኘም። ስለዚህ ሌላውን ሁሉ ዝብዝብ ትቶ። “ሳግባሽ አፈልጋለሁ” አላት።

እስካርሌት “ሚግባት ”የሚለውን ቃል ስትሰማ ግና ፤ ከሄደ ችበት የህሳብ ገዳና ተመለሰችና እንዳንድ ነገር አንቀጠቀጣት። እሷ ትዳሮን ከእሽሌይ ጋር በስተኮር እስባው ስለማታውቅ ፤ ምንም ልትሸሽገው የሚትችለው የብስጭት ስሜት ፊቷ ላይ እየታየባት ቻርለስን ትኩር ብላ ተመለከችችው። ለራሷ ሚንቀት ሊያሳብዳት በደረሰበት በአሁኑ ሰዓት ፤ ምናለ ይሄ ዝግ መሳይ ጅላንሬ አጉል ጣልቃ ገብቶ ባያስቸግራት ፤ የሚነጠጉትትን ዙናማ ዓይኖች ትኩር ብላ አየቻቸው— ምንም ዓይነት የአይናፋር ልጅ የመጀመሪያ ፍቅር ውበት አላገኘችባቸውም። ምንም ዓይነት ፤ ህልም እውን የሆነበት ትር ኢት የለባቸውም። እንደ እሳት የሚምዘገዘግ የደስታና የልስላሴ ስሜትም ሲንቀለቀልበት አታይም። እስካርሌት ፤ ብዙ ሳግባሽ የሚል ወንድ አጋጥሟታል። እንዴያውም ከቻርለስ ሐሚልተን ሺ ግዜ የሚበልጡ ወንዶች ጠይቀዋታል። እንደቻርለስ ሐሚልተን በሰው ግብግ ላይ ያውም መንፈሷ ሁሉ በሌላ ጉዳይ በተወጠረበት ጊዜ ሳይሆን ፤ ሥነሥርዓት ባለው የጨዋ ወግ የሚጠይቁ የተከበሩ ወንዶች ታውቃለች። አሁን የምታየው የሃያ ሁለት ዓመት ልጅ ፤ እንደ ቀይ ስር የቀላ ደደብ ፍጥረት ነው። ምን ዓይነት ደደብ እንደሚመስል በነገረችው እንዴት በወደደች ነበር። ነገር ግን ሌለን ያስተማረቻት የጨዋነት ታላት ለዚህ ዓይነቱ ድንገተኛ አደጋ ምላሽ በመሆናቸው ፤ በፍጥነት ወደ አፏ ሲመጡላት ፤ ዓይኖቿን ደፋ አድርጋ ፤ የረዥም ጊዜ ልማድ በኃይል እየገፋት እንዲህ ስትል አጉተመተመች “ቻርለስ ፤ ሚስትህ እንድሆን መፈለግህን እንድሰማ የሰጠሽኝ የክብር እድል በጭራሽ ያልጠረጠርኩትና ድንገተኛ ነገር በመሆኑ ለጊዜው ምንም መልስ ለመስጠት በጣም ያዳግተኛል። ”

ይሄን ዓይነቱ ዘዴ መቼም የወንድን ከንቱነት እያለሰለሰ ከፍ ላጐት ገመዱ ላይ ግን እንዳይወርድ ማድረጊያ ምርጥ መላ ነው። ቻርለስም እንዲህ ያለው ንግግር እንግዳ እንደሆነና እሱ የመጀመሪያው ጽዋ ቀማሽ እንደሆነ ሁሉ ከመቀመጫው ብድግአለ።

@OLDBOOKSPDF

"እስከምጽዓት ድረስ እጠብቃለሁ፤ አንቺ እርግጠኛ ሆነሽ እፊ ልግሀለሁ ካላልሽኝ በስተቀር አልፈልግሽም። እባክሽ አስካርሌት በተስፋ እንድቀመጥ ብቻ ተስፋ ስጪኝ!"

"እ" አለች አስካርሌት። የሙሌ ዓይኖቿ በጦርነቱ ወሬ ውስጥ የማይሳተፈውንና አሁንም ሚላኒን ፈገግታ የሚመግበውን አሽሌ ይን ይመለከታሉ። ይሄ እድሞን ጨቡጦ ድርቅ ያለው ጅል ወሬውን አቁሞ ትንሽ ሩታ ብታሳኝ ምናልባት ምን እንደሚያወሩ ይሰማት ይሆናል።

ምን እንደሚያወሩ ደሞ መስማት አለባት። ይቺ ሚላኒ ምን ብታወራለት ነው እንዲህ በትኩት ዓይኖቹ የሚያበሩት!

የሚያወሩትን ለመስማት እየተፍጨረጨረች ሳለች የቻርለስ ንግግር ጣልቃ ገባና ያጻመጠችውን አደበዘዘባት።

"ውይ ዝም በል በናትህ! አሽሽ!" አለች ዝም እንዲል እጁን እየቆነጠጠችና ወደሱ ሰታይ።

በነገሩ ግራ የተጋባው ቻርለስ ማመናጨቅ ራቱን አቁላው። ጥቂት ቆይቶ ግን ዓይኗ እዘቱ ሳይ እንደተተከሰ ሲያይ ፈገግ አለ። አስካርሌት የሱን ንግግር ሌላ ሰው እንዳይሰማ ፈርታለች። በእንዲህ ያለው ጊዜ በተፈጥሮዋ ተናዳጅና አፋር ታም ናት። ጭንቀትም ይሰማታል። ስለዚህ ድምፁ እንዳይሰማ ሰግታለች። ቻርለስ ማንንም ሴት በሕይወቱ አስደንግጦ ስለማያውቅ ወንድነት ተሰማው። ድንጋጤዋ በጣም የሚያሳክር ነበር። ራሱን በማይለቨና በምን አገባኝ መልክ አመቻችቶ በጥንቃቄ የአስካርሌትን ቁንጥጫ ምላሽ በመስጠት ፤ አይሆንም ብሎ የተታወሙችውን ነገር ቶሎ የመረዳትና የመቀበል የሠለጠነ ችሎታ ያለው ዓለማዊ ወንድ መሆኑን ሲያረጋግጥላት ሞከረ።

እሷ ለራሷ እንኳን መልኩን ማየት ቁንጥጫውንም ሳትሰማ የሚላኒ ወብ ለዛ የሆነውን ጣፋጭ ድምጽ ጥርት ባለ ሁኔታ ማጻ መጪን ቀጥላለች፡-"የአቶ ታኬሬን ሥራዎች በሚመለከት አሁን ባልከው አልስማማም። ሽረኛ ሰው ነው መሠሪ። የሰው ጥፋት በቀር ደግ ነገር አይታየውም። እንደ ዲከንስ ጨዋ አይደለም።"

አሁን ይሄ ለወንድ ልጅ የሚነገር ነገር ነው በእግዚሃር አለች አስካርሌት በልቧ። በእፎይታ ሳቋን ልትለቀው ምንም አልቀራት። ሚላኒ አዋቂ የቀለም ሰው ሆና ቀርባለች። መቼም አዋቂን ሴት፤ ወንዶች ምን እንደሚሉ ግልጽ ነው። ወንድ ለአንድ ነገር ፍላ ጎት ኖሮት እንዲቆይና ፍላጐቱንም ለመንከባከብ እንዲቻል መጠ

@OLDBOOKSPDF

ቀም ያስብን ዘያ ስለራሱ ማሙራት ሲሆን ፣ ቀስ በቀስ የወሬውን እቅጣጫ ወደራስ ጉዳይ መቀየስና በዚያው አንዲቀጥል ማድረግ ደግሞ የሴት ልዩ ጥበብ ሊሆን ይገባዋል ። ሚሳኔ—"እንዴት ያለህ ግሩም ሰው ነህ! " ወይም " እንዴት ልታስበው ቻልክ እባክህ ይሄዬ የኔ አሮጌ ሜንቅሳት ቢሆን ኖር ገና ለማሰብ ስሞክር ፈንዲቱ ያርፍ ነበር!" ብትል ኖሮ ፣ አስካርሌት እንድትጠነትታት ጥሩ ማሳ ስቢያ ይሆናት ነበር ። ይቺ ማን ወንድ እማሯ ሥር አስቀምጣ በማም ምርር ያለ ቁም ነገር ከማውራቷ የተንሳ ቤቱ ክርስቲያን ውስጥ ያለች ትመስላለች ። አስካርሌት የወደፊት ሂስቱዎ ብሩህ ሆኖ ታያትና ከመደሰቷ ፣ የተሳሳ ወደ ሻርለስ ስትዞር ፣ ጨረር የሚፈነጥቁ ደማቅ ዓይኖችዋንና ክንፁህ የደስታ ስሜት የመላጨ ፈገግታ የሞላው ፊቷን አሳየችው ። ይህ የዊትር ገጽታዋ ያስከረው ቻርለስ ማሬ ገቢያዋን አንስቶ ሲያራግብላት ፣ እጁን በኃይል ከማወናጨፉ የተ ነሳ ወጉሯን በታትኖ ምስትልትሉን አወጣው ።

"አሽሌይ ፣ እንተኑ በዚህ ጉዳይ ሳይ ምንም አስተያየት አልሰ ጠህም" አለችም ታርሌተን ፣ ከሚከራከሩት ሰዎች ለየት ብሎ መጥቶ ። አሽሌይ ይቅርታ ጠይቆ ተነሳ ። አስካርሌት በመርቃማው በጣሩና በከንፈር ሂሙ ሳይ የምታበራውን ቡሕይ ኖ በማይለሽነት ሲቆም እንኳ ያለውን ማርማ —ምንስ ስታይ ፣ - እንደሱ ቆንጆና እንደሱ የተዋበ ማንም የለምኮ— አሰኛ በለቧ ። ሽማግሌዎቹ ሰዎች እንኳን እሱን በጥሞና ለማጸመጣ ቆመዋል ።

"ምን ሆናችሁ ጉበዝ ፣ ጅርጂያ የምትዋጋ ከሆነማ አብሬያት እዘምታለሁ ። ካለበለዚያማ ምን ልፈጥር ሠራዊቱ ውስጥ ግባሁት" አለ ። እንዚያ ማራጫ ዓይኖቹ ከአፎታችው በጣም ወጡና ፈዘዝ ቀዘዝ ማለታቸው ቀርቶ ከዚህ ቀደም አስካርሌት አይታ ባቸው በማታውቀው ሁኔታ ቦሳ—ጥንክር ብለው ታዩ ። "ሆኖም ልክ እንደ አባቶቻቸው ያንኪዎቹ በሰላም እንደሚሸጉንና ምንም ጦርነት እንደማያኖር . . . " እጁን በሉላው እጁ ይዞ ፈገግ ሲል ከርንቱንና ከታርሌተን ልጆች አካባቢ የሚሁም ድምጽ መጣ ። " አዎን ፣ አዎን ። መሰደባችንንና መዋሸታችንን አሳምሬ እውቃለሁ ። ነገር ግን እኛ በያንኪዎቹ ቦታ ብንሆንና እነሱ ከሀብረቱ እንደኛ ተገንጥለው የሚወጡ ቢሆን የኛ አቋም ምን ይሆን ነበር? ሥርሀቢ ያው ነው ። እሱም ብንሆን እንወያውም ነበር ። "ሩ "አዱ! ደሞ ተመልሶ ያንኑ ጀመረ" አለች አስካርሌት በልቧ ። "በሌላ ሰው ጉዳይ ሁልጊዜ እጁን ያስገባል ። "ለሱ ክርክር ማለት እንድና እንድ ብቻ አቋም የሚወስድበት ነው ። እንዳንድ ጊዜ አሽሌይን መረዳት በጭራሽ አይቻልም ።

@OLDBOOKSPDF

"እስቲ በማም ቱማ ሳንልና ሳንቆጣ ነገሩን እንየው ። አንደ ዚያ ካየረግን ምንም ጦርነት አንዳይኖር ማድረግ እንችላለን ። በዓ ለም ላይ ያለው አብዛኛው መከራና ሥቃይ በጦርነት ምክንያት የተ ፈጠረ ነው ። እናም ጦርነቱ ሲያልቅ ጦርነቱ ለምን ተካሄደ የሚ ለውን የሚያውቅ ነው አይኖርም ። "

እስከርሊት አበንሽሽ ። አሸሌይ በድፍረት ረገድ እምብዛም ጎጥቶ አማይገሩ ሰው ሙሦኑ ዕድለኛ ነው ። አለበለዚያ ችግር ይፈ ጠር ነበር ። ይህን እ ሰበች ሳለች በአሸሌይ ላይ እንደማዕበል የሚተራመስ የድምፅ ጭጋድ ተንሳበት ። የቁጣ እሳት ተጫረበት ።

ከዘሩ ጭሳ ያረፈው የሬይተኪሉ ጽንቀሮ ሽማግሌ እንዲያን ይመቀሙኝ ጀመር ።

"ስለምንድነው ከርከሱ ምንድነው የሚሉት?"

"ጦርነት ከጦርነት ነው ጊሚሉት ሥለለች ኢንዲያ አጅዋን እጆ ርው ላይ ከልላ ። "ያንኪዎቹን መውጋት እንፈልጋለን ነው የሚሉት!

"ጦርነት ከጦርነት ነው ያልሽኝ ?" ብሎ ሮኸ ። ከዘራውን ለማንሳት አጅን ሰደ እየፈለገ ። ወዲያው ፣ ከዚህ ቀደም ለዓመ ታት አሸይቶት በማያውቀው ጉልበት ጥንጥር ብሎ ከወንበሩ ተነሳ ። "ስለጦርነት አኔ እንግራችኋለሁ ። እኔ እዛ ነበርኩ" ። አቶ ማክሬ ያገሩ ሰዎች እንደሚነግሩት ያለ የጦርነት ወሬ የሚያወራበት ዕድል አብዛኛውን ጊዜ አያገኝም ።

ከዘራውን እያወዛወዘ እየጮኸ በፍጥነት ወደ ተሰበሰበው ሕዝብ ሄደ ። የሚጮኽውን ድምጽ ሁሉ ስለማይሰማ ወዲያውኑ አካባቢ ውን ለመቆጣጠር ቻለ ።

"አናንት የእሳት አራኖች ፣ እኔን አድምጡኝ ። እናንተ ለመ ዋጋት አትፈልጉም ። እኔ ተዋግቻለሁና ስለጦርነት አውቃለሁ ። በሲሚኖሉ ጦርነት ውስጥ ተዋግቻለሁ ። በሚክሲኮው ጦርነትም ለመዋ ጋት በመሄዴ ጅልነቱን አረጋግጫለሁ ። ሁላችሁም ጦርነት ማለት ምን እንደሆነ አታውቁም ።

ለእናንተ ጦርነት ልጃገሪዶች አበባ እየበተኑባችሁ በጥሩ ፈረስ እየጋለቡ መሸኘትና ጀግና ሆኖ ወደ ቤት መመለስ ይመስ ላችኋል ። ግን በጭራሽ አይደለም ። የለም ጊዮቭ ጦርነት ወደ ረሀብ አገር መሄድ ነው ። ጦርነት ወደ ተሰቦ አገር መሄድ ነው ። ጦርነት ቀዝቃዛ ውሃ ውስጥ ያለልብስ እያደሩ የብርድ በሽታ መሸ መት ነው ። ተስቦና ብርድ በሽታም ካልሆነ የሆድ ሀመሙ አይቀር

@OLDBOOKSPDF

ላችሁም ። ወርነት ሆድን ምን እንደሚያደርገው ሄዶ ያየ ያቅዋል- የተቅማጡ ፣ የ . . . ”

ሴቶቹ በንዴት ጥም መስሉ ። ልክ እንዶትልቋ እማማ ፎንቴን አቶ ማከፊም የክፉ ዘመን አስታዋሽ ነው ። እሱ ሆድ ውስጥ ወር ነት ያኖረው ደዌ ሰው ሁሉ ሊረሳው የሚፈልገው ክፉ ትዝታ ነው።

“ሂጂና አያትሽን አምጪው ” አለች ከሽማግሌዎቹ ልጆች ማህል አንዷ ፡ አጠገቧ ላለች ወጣት ልጃገረድ ። “እኔ በበኩሌ” አለች ቀጠል አድርጋ በሁሪያዋ ስሚገኙት የሙት ሚስቶች በሙ ከሹክታ ። “ከቀን ወደ ቀን እየባሰበት ስመሄዱ ምስክር ነኝ ። ዛሬ ጠዋት የተናገረውን እንኳ ብንሰራችሁ የማታምኑት ነገር ነው ። ያቺን የአሥራ ስድስት ዓመታን ሜሪን “አሁን እንግዲህ ሆኔ ሴት—ወይዘሮ . . . ” አሳሳት መሰላችሁ ። አቶ ማክሬንን ከተሰበ ሰበው ሕዝብ ማህል እውጥታ አንዴትመጥ ስማድረግ ስትሄድ ጨኸቱ ሁሉ ቀንሶ ወደ ሹክሹክታ ቀለወጠ ።

ከዚያ ባፍ ሥር ተሰበሰበው ከሚያሸክቡት ሴቶችና በተመለመ ከሚወያዩት ወንዶች ሁሉ ለየት ብሎ ዝም ያለ የሚመስል አንድ ወንድ ሰው አለ ። የኤስካርሴት ኤይኖች ባፍ ተደግፎና እጆቹን እሱሪው ኪስ ውስጥ ከቶ ከቆመው ፊት በትለር ከሚባል ሰው ላይ አረፉ ። ጆን ዊክስ ካጠገቡ ከዚዶ ጆምሮ ብቻውን ቆሟል ። ውይይቱ እየ ተጋጋለ ሲሄድ ሁሉ እንዳችም ሀሳብ እልሰነዘረም ። ባጭሩ ከተሳ ጨው ጢሙ በታች ያሉት ቀያይ ከንፈሮቹ ወደ ታች ቀልበስ ብለ ዋል ። በጥቁቁር ዓይኖቹ ውስጥ ያለው ከመገረም የመጣ የጥላቻ ነፀ ብራቅ ከሩቅ ይታያል ።የሚያዳምጠው ውይይት የሕፃናት ጨዋታ እንደሆነ ሁሉ ጥላቻው እጅግ ጉልቶ ይታይበታል ።ምንም የማይ ጥም ፈገግታ ነው ያለው ፤ አሰች እስካርሌት በሀሳብዋ ።እስቱዋርት ታርሌተን ቀይ ፀጉሩን አንጨፍርሮና ዓይኖቹን እያቁለጨለጨ “እንዴ! ባንድ ወር ጊዜ ውስጥ ድራሻቸውን ነው የምናጠፋው! ምን ጊዜም ቢሆን ከገልቱ ጀሌ ሠራዊት ይልቅ ጨዋና ጀግና ሕዝብ የተሻለ ይዋጋል ።በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ያውም ኳንድ ጦርነት በላይ ...”ብሎ በድጋሚ እስኪናገር ድረስ ፊት በትለር ዝም ብሎ ሲያዳምጥ ቆይቶ ነበር ።በመጨረሻ “ግበዝ” አለ ።ድምጹ ተመስጦ ያለበትና የቻርልስተን ተወላጅነቱን በግልጽ የሚያሳውቅ ነው ። የሚ ናገረው አዚያው ባፍ ሥር እንደቆመና እጆን ከኪሱ ሳያወጣ ነው ።

“እንዲት ቃል እንድናገር ትፈቅዱልኛላችሁ?”

በዓይኖቹ ውስጥ ጥላቻ እንደሚነበብ ሁሉ ባጠቃላይ ሁኔታው ላይም ጥላቻ ይታያል ።በማሾፍ የታጀበና እንዳንዴም የሚዋጥ ጥላቻ።

@OLDBOOKSPDF

ሰምቹ ሁሉ ወደሱ ሮር ሀር አሉና ሁለግዜ ለእንግዳ ሰው እንደ ሚያደርጉት በትህትና ሊያጸምጠት ፀጥ አሉ ።

"ለመሆኑ ከናንተ ማህል ከማዘን ዴክሰን መስመር ብሱተደ በብ የመድኩ ፋብሪካ አሰመኖሩን አስቦ የሚያውቅ አለ ? ወይም ደግሞ የደበብ መግሪያ ግምጃ ቤት በጣም ጥቂት መሆኑን የተገነ ዘበ አለ ? የሱፍ ፋብሪካ ፡ወይም የጥጥ ፋብሪካ ወይም የቆዳ ፋብሪካ ምቹስ ቢሆኑ ? ለመሆኑ አንድም የመር መርከብ እንዲሌለንና የያን ኪምች ሠራዊት ሳምንት ባልሞላ ግዜ ውስዮ ወደባችንን ደምስሶ ጥፐ አንኳ ወደውጭ እንዳንልክ እንደሚያደርገን አታውቁም ?ማን መቼም አርግጠኛ ነኝ ይህን ነገር አስቱድማችሁ አስባችሁበታል ?"

"ወዴዬ የኛን ልጅች የማይረቡ ሙርንጭሌች ናቸው እኮ ነው እሚለሙ!" ብላ አሰበች እስክርሌት ፣ የፈላው ደምዋ ወደጉንጭዋ እየወጣ ።

እርግጥ ጎንዲሀ ያለውን ሀሳብ ያበበች እስዋ ብቻ አልነበረችም ። ብዙዎቹ ልጅች እና ሳቲ ሚንሺኳሽክ ጀምረዋል ። ጅንዊክስ አንዳ ንዴ ማደፍ — ማደፍ እያለ አተናጋሪው ጉን እየደረሰ ይመለሳል ። ይህ ሰው የሱ እንግዳ መሆኑን ለማሳወቅ የሚሞክር ፡እዚያ ለተገኙ ትም ሴቶች ደማሳየት የሚጥር ይመስላል ።

"የእኛ የአብዛኞቹ ደቡባውያን ችግር" አለና ቀጠለ ፌት በት ለር ፡"ብዙ አለመጓዛችን ወይም ከጉዟችን ምንም ትምህርት አለማ ትረፋችን ነው ።እርግጥ እናንተ ሁላችሁ ብዙ የተጓዛችሁ ፡ብዙ ያያ ችሁ ናችሁ ።ግን ያያችሁት ምንድን ነው ፣እውሮፓን ፣ ኒዎርክን ፣ ፊላ ደልፊያን ።እርግጥ ሴት ሴቶቹ ደግሞ ወደ ሣራቶጋ ሄደው ይሆናል (ሴቶች ወደ ተሰበሰቡበት ዘወር ብሎ በትንሹ እጅ ነግ) ሆቴሎችን መ፡ዚየሞቹን ፣ የጎንስ ቦታዎችንና የቁማር ቤቶችን አይታችኋል ። ወደ የቢታችሁ ተመልሳችሁም ከደቡብ አገራችሁ የሚበልጥ ሀገር የለም ብላችሁ አምናችሁ ይሆናል ።በበኩሌ የትውልድ አገሬ ቻርል ስተን ነው ። ሆኖም ያለፉትን ጥቂት አመታት ያሳለፍኩት ሰሜን ውስጥ ነው ።"ወተት የመሰሉ ጥርሶቹን በማሾፍ መልክ ፍልቅልቅ አደረገ ፤

እዚያ የተሰበሰበው ሁሉ ቻልስተን ውስጥ ለመኖር ያልቻለበትን ምክንያት ያውቃል ብሎ እንደገመተ ሁሉ ፈገግ ብሎ ።ሰው አወቀ አላወቀ ግን ደንታው አይደለም ።"እንናተ ሁላችሁ ያላያችሁዋቸውን ብዙ ነገሮች እኔ አይቻለሁ ።ጥቂት ምግብና ትንሽ ብር ከሰጡዋ ቸው ፡ሽንጣቸውን ገትረው ለያንኪዎች ለመዋጋት ፈቃደኛ የሆኑ አያሌ ስደተኞችን ፣ ፋብሪካዎቻቸውን ፡የጠመንጃ መሥሪያ መጋዘኖ

@OLDBOOKSPDF

ምቾውን ፣ የመርከብ መሣሪያዎቻቸውን ፣ የብረትና የከሰል ማዕድን ኑድግዶቻቸውን ፣ ብቻ በጠቅላላው እኛ የሌለንን ነገሮች ሁሉ አይቻለሁ ።አይቻለሁ ፤ እኛ ያለን ነገሮች ጥቂ ፣ ቢሪያዎችና ድንቁርና ብቻ ናቸው ።ስለዚህ በእንድ መር ጊዜ ውስጥ ድርሻችንን ሊያጠፉን ይች ላሉ ።”

ለትንሽ የውጥረት ቅፅበት ውጭ ሆነ ።ሬትበትለር ከዚሉ ምን የመስለ ነጭ መሃረብ አውጥቶ ኮሊታውን ጠረግ ጠረግ አድርጉ አጸዳ ።ወዲያው አንድ የትርምርምታ ድምፅ ከተሰበሰበው ሕዝብ መሀል አስተጋባ ።ለመጀመሪያ ግዜ ቀፎው የሁንካ ንብ ሀምምም የሚል ድምፅ ሲያሰማ እንደማያሳስት ሁሉ ይህ ያሁኑም ድምፅ ከዜፍ ሥር የመጣ ለመሆኑ እያጠራጥርም ።አስከርሬት ፣ ምንም እንኳ በንዴት ጭንቅላቱ ሳንባ ቢመስል አፍ በሀቁኛ ልብናዋ ውስጥ ያለ ነገር ይህ ሰው የተናገረው በሙሉ እውነት መሆኑን ነግሮዋታል ። እውነትም ቀምንገር እንደተናገረ ገብቶዋታል ።ልክ ንው ።እስቲ በድ ፍን አገር ውስጥ አንድ እንኳ ፋብሪካ መኖ አይታ ታውቃለች ። የጀ ማየት ጸጉርና እይሁን የሚል በውስ የት አግኝታ ታውቅና ነው። ያም ሆኖ ፣ ምንም ሁናቴው እውነት ቢሆን ፣ እንዴህ በይፉ ባደባ ባይ መናገሩ የጨዋ ሰው ምባር አይደለም ። ያውም ሰው ሁሉ ጸከታን በሚገዘይበት ሁብጥ ሳይ ።

እስቴፍርት ታርሌሳን ንፉሽፉሾቹን አኮሚትሮ ከብሪንት ጋር ሌት ለሊት መጥተው አሳሩ ሥር ፉሙ ።እርግጥ መኝም የታርሌተን ልጆች ምንም በነሱ እጅግ የተበሳጩ ቢሆኑ በሰላማዊ የግብግ በታ ጠብ አጭረው የማይበጠበጡ አስተዳደግ ውዋዎች ናቸው ። ሌት ሴሳቹ ግን በግብግ በታ የሚነሳ ጠበኛ እምባጻር የሚያዩት አልር አልር ዘመሆኑ በነሱ የመጣት ጸበታ ተሰምቷቸዋል ። እንደውም እብዘኛ ወሳ ጊዜ ለለጠብ የሚሰሙት ከሉስትኛው አፍ ነው ።

“ጌታው”አለ አስቴዋርት ኮክተር ብሎ“ምን ማለትህ ነው ?” ሬት በትህትና ግን በማኾፍ መልክ እየው“እሬማ ያልኩት”አለና መመለስ ጀመረ ። “እንድ ግዜ ናፖሊዎን እንደተናገረው — መቼም ስለ ናፖሊዎን ስምታችሁ ይሆናል ።እና እሱ እንዳለው ።እግዚሃር የሚረዳ ጸው ጠንካራውን ሠራዊት ነው!”ወደ ጀንዊክስም ዞር አለና እንደ ቀልድ ባለና ይምሰል በሌለበት አንጋገር “የመጽሐፍት ቤትህን ልታ ሳየኝ ቃል ነብትህልኝ ነበር እኮ ።እሁን ብታሳየኝ መልካም ፈቃድህ ይሆን ይሆን ? ዛሬ ከሰዓት በሁዋላ ወደ ጀንሶበሮ ሳልሄድ አልቀርም ብዬ እሰጋለሁ ።ትንሽ ሥራ አለኝብኝ ።”

እንዲ ሽክርክር አለና ሁሪያውን የተሰበሰበውን ሰው ተመልከቶ ፣ ተረከዝና ተረከዙን አጋጨና እንደምርጥ የጥንስ ባለሙያ ንን

@OLDBOOKSPDF

በስ ብሎ አጅ ነሳ ።እንደሱ ያለ ጠንካራና ግዙፍ ሰው እጅ ሲነሳ ለዩ ግርማ ሞገስ አለው ።ነገር ግን ልክ እራቱ ላይ ድንገት በጥፊ ተመትቶ ምንም ማድ ያልሰጠው ሰው ይመስላል ።ከዚያ ጥቁር እራሱን ከፍ አድርጎ አየር ላይ እያሳየ ከጀንዊከስ ጋር ሚዳውን አጽር ጠው መንገድ ጀመሩ ።ከሁዋላው እየተወው የሄደው ያ የተንኮል ግቡ ፣ ጠረጴዛውን ከበው ወደ ተቀመጡት በምኞ ጀሮ ጥልቅ ይሰል ።

ግራ የሚያጋባ ዝምታ ሰፍኖ ቆየ ያ ጉምጉምታ እንደገና ተጀመረ ። ኢንዲያ ድክም ኒያሳት እግሩ ሥር ነሲው መቀመጫዋ ተነሳችና ወደተበሳጨው ንስቱዋርት ቃርሴተን ሄደች ። የምትናገ ረውን እስክርሴት አትጠግም ሆናም ቀና ብላ የከፋው ፊቱን ስታይ የሳይኖችዋ ሁኔታ እስክርሴት ሀሊና ውስዋ አንድ ሰሴት ፈጥሮ ዋል ። ሚላኒ እቨሴደን ስታይ እፈቷ ላይ ያታይ የነበረው ዓይነት ሁኔታ ነው ። ይህንን ለብ ያሳለው ንስቱዋርት ብቻ ነው ። እሃ ፣ ስካ ኢንዲያ ታፈቅረዋለች ። ያኔ ከአንድ ዓመት በፊት እስክርሴት ከስቱዋርት ጋር በማሳው ስትጨዋወትና ስትሳፋ ባትታይ ኖሮ ይሄኔ ኢንዲያን አግብቱ ይቀመጥ እንደንበር ላንድ አፍታ ውል አሳት ። ሆኖም ሌሎች ሲዮች ወዳጅነታቸው ወደ አሷ አንዳይመጡ በደምብ አጥበቀው መያዝ ከለቻሉ ይሄ ፍሷ ጥፋት አንዳይደለ በማሰብ ሀሊናዋን የቆጠቆጣት ነገር ጠፍሳት ።

በመጨረሻ እስቱዋርት ዝት ብሎ የማዱን በሚመስል ፈገግታ ፈገግ ብሎ በእምነታ ሞንቅሳቱን ነተነቀ ። ምናልባት ኢንዲያ የም ትገላገሙው ፈት በትለርን ተከትሎ ሄዶ ችግር እንዳይፈጥር ሲሆን ይችላል ። አንድ የትህትናን ወግ የተከተለ ድምጽ ከየዛፉ ሥር ተሰማና እንግዶቹ ሁሉ ብደግ — ብድግ አሉ ።

ከጠረጴዛ ልብሱ በሳይም የጸበ የኬክ ፍርፋሪዎችን አራገፉ ። ያገቡ— ያገቡት ሴቶች ሞገዚቶቻቸውንና ልጆቻቸውን እየጠሩ ተሰባስበው ለመሄድ ተዘጋጁ ።ልጅ እማሮቹ ኮረዶች ደግሞ እርቅ ወዳሉት መኝታ ቤቶች ሄደው በሚስጥር ለመንሾካሾክና የከሰዓት በሁዋላ አጭር እን ቅልፋቸውን ለመተኛት እያወሩና እየሳቁ ወደ ቤቱ አመሩ ።

ከመ/ሮ ቃርሴተን በስተቀር ሴቶቹ በሙሉ የጓሮውን መናፈሻ ፣ ዋርክሞቹንና የዛፎቹን ጥላ መቀመጫዎች ለወንዶቹ ትተው ሄዱ ።

መ/ሮ ቃርሴተንን ያስቀሯት ፣ ጂራልድ ፣ ካልቨርትና ሌሎች ለሠራ ዊቱ ለሚያስፈልገት ፈረሶች ጉዳይ ከሷ መልስ የሚጠብቁ ሰዎች ናቸው ።

አሽሌይ ፣ እስክርሴትና ቻርለስ ወደ ተቀመጡበት ቦታ ሄደ ። እራቱ ላይ በሀሳብ የመመሰጥና የመደንቅ ፈገግታ ይታይበታል ።

@OLDBOOKSPDF

"እርኩስ ሠይጣን ነው ይሄ ሰውነ አይደለ ሥአለ ወደበትለር እያየ ።"እንዚያን ቦርጂያዎቹን ይመስላል ።"

እስካርሌት በመንደሩዋም ሆነ በእትላንታ ወይም በሳቫና እን ዲህ ያለ የቤተሰብ ስም ሰምታ እንደሆን ለማስታወስ ሞከረች ።ነገር ግን ትዝ አልል አላት ።

"አሳውታቸውም ። ይዛመዳቸዋል እሱ ኧኔማ ናቸው እንሱ ሥ

የቻርለስ ፊት ልውጥውጥ አለ ።ሐፍረትና ውርደት ባንድ ወገን፣ ፍቅር በሌላ ወገን ሆነው እላዩ ላይ ይሟገቱበታል ።ብቻ ትንሽቆይቶ ሲት ልጅ ማራኪ ፣ ጨዋና ቆንጆ ከሆነች ደም ማባትዋን የሚያካትትላት ዕውቀት ባይኖራትም በቂዋ መሆኑን በመገንዘቡ ፍቅሩ አሸናፊ ሆነና እንዲህ ብሎ መለሰላት ።

"ቦርጂያዎች ግሊያኖች ናቸው ።

"ሙይ!"አለች እስካርሌት በነገሩ ጣዕም በማጣት ።"የውጪ— አገር ዜጐች ናቸዋ ። "በጣም ሙብ የሆነ ፈገግታዋን ለአሽሌይ ለመ ሙገብ ወደሱ ዘወር አለች ።እሱ ግን ባንድ በማይታወቅ ምክንያት ወደሱዋ አይመለከትም ።ቻርለስን ነው የሚመለከተው ። እፊቱ ላይ ነገሩን የመረዳትና የሐዘን መልክ ይታይበታል ።

እስካርሌት እወለሉ ላይ እንደቆመች ቀረች ።በደረጃው መደገ ፊያ ሥር አሾልታ በጥንቃቄ ወደ አዳራሹ ውስጥ ትመለከታለች ። ባዶ ነው ።እፎት ላይ ክሉት መኝታ ቤቶች በኩል እንዴ ከፍ እንዴ ዝቅ የሚል ድምፅ ይሰማል ።

ዝማ ያለ የሹክሹክታ ድምፅ ። አልፎ አልፎ ከት ብለው እየሳቁ "እው ነትሽን ነው ነኣትይኝም !"ታዲያ ምን አለሽ?"ይባባላሉ ። ሴቶቹ ሁሉ፣ ቀሚሶቻቸውን አውልቀው የውስጥ ልብሶቻቸውን ላላ — ላላ አድር ገውና ፀጉራቸውን ወደሁዋላ በረሻሙ ለቅቀው በስድስቱ ሰፋፊ መኝታ ቤቶች ውስጥ ባሉት አልጋዎችና መቀመጫዎች ላይ ሀና ብለው እረፍት እየወሰዱ ናቸው ። የከሰዓት በሁዋላ አጭር እንቅልፍ ያገሩ ልማድ ነው ። ይህ ልማድ በተለይ ጠዋት ማለዳ ጀምረው ማታ በዳንስ እስከሚያበቁ ድረስ የፌሽታ ድግስ ሆነው ለሚውሉ የቀን ግብግዎች ፣ እጅግ አስፈላጊ ሆኑዋል ። ለአንድ ለግማሽ ሰዓት ያህል ኮረዶች ሁሉ ያጋጠማቸውን ሲያወጉ ፣ ሲንቻቹና ሲስቁ ይቆዩና አሽከሮች መጥተው የመሰኩት ግርዶሾቹን አውርደው ይዘጉላቸዋል ። ከዚያም በዚያ በሞቃቱ ደብዛዛ ብርሃን ውስጥ የሚዝናኑት ሴቶች ወሬና ቻቻታ ቀስ በቀስ ወደሹክሹክታ ፤ ቆይቶም አልፎ አልፎ ብቻ በትንፋሽ ወደ ሚጣስ የዝምታ ክልል ይሸጋገራሉ ።

@OLDBOOKSPDF

እስክርስቶስ ወደ አዳራሹ ከመግባቷ በፊት፡ ሜላኒ፡ ከሐሻና ከሔቲ ታርሴተን ጋር አልጋው ላይ መተኛትዋን ፤ እርግጠኛ ስለነበረች ቁል ቁል ደረጃውን መውረድ ጀመረች ። በምድር ቤቱ መስኮት አሻግራ ስትመለከት በዛፉ ጥላ ሥር የተቀመጡት ወንዶች በረኛዥም ብር ጭቆ መጠጥ ጐንጨት እያሉ ተቀምጠው ይጫወታሉ ። እስኪመሽ ድረስ እዚው እንደሚያረፍዱ ታውቃለች ። የተሰበሰቡትን ሁሉ በአይ ኑዋ በመቃኖት እንድ በእንድ አሰተዋለች ። አሽሌይ ግን እመሐ ላቸው የለም ። ከዚያ ዝምብላ ስታዳምጥ ድምፁን ሰማች ። ልክ እንደተመኘችው አሽሌይ ፊት ለፊት ካለው ሚዳ ላይ ሆኖ ግና እናቶችና ልጆችን እየተሰናበተ ነው ። ልቧን እጥሮሮዋ ውስጥ ቀር ቅራ ፈጠን ብላ ደረጃውን ወረደች ። አሁን አቶ ዊክስን ብታገኘው ምን ልትል ነውን ሲሰሙ ሴቶች ሁሉ መልክም እንቅልፋቸውን ሲለጥጡ አሰቡ ከዚህ ብቻዋን ለመዘዋወርዋ ምን ምክንያት ልትሰጥ ነው ? እይ መቼም ይሄንን መቻል አስባት ።

የመጨረሻው የደረጃ እርከን ላይ ስትደርስ እምዛብ ቤቱ ውስጥ አሽከሮች በከቦዋቸው (በሀላፊያቸው) ትእዛዝ ቤቱን ለዳንስ ለማዘጋጀትና ጠረጴዛዎቹንና ወንበሮቹን ለማንሳት ወዲህ ወዲያ ሲሉ ሰማች ። አዳራሹን ማሀል ለመሀል አሳርጠው ሲሄዱ ፊት ለፊት ተከፍቶ የሚታየው የመጽሐፍት ቤቱ በር ነው ። ድምጽ ሳታሰማ ሰተት ብላ ገባች ። እዚህ ተቀምጣ አሽሌይ እንግዶቹን ተሰናብቶ እስኪመጣ ጠብቃ ለመገረመው ነው ።

የመስኮቱ መጋረጃዎች ብርሃኑን ስለጋረዱት መጽሐፍት ቤቱ ግማሹ ብርሃን ግማሹ ጨለማ ሆኗል ። ይህ ረዣዥም ግድግዳዎች ያሉትና ከዳር እዳር በመጻሕፍት የታጨቀ የመጽሐፍት ቤት ከፋኖ ተጫጫናትና ከሩት ። አሁን ልትሞክር ያሰበችውን ነገር ለማከናወን የምትመርጠው ቦታ ይህ አልነበረም ። ብዙ መጽሐፍት የሚያነቡ ሰዎች እንደሚያስጠሉዋት ሁሉ ባንድ ቦታ የተደረደሩ መጽሐፍትም ያስጠሏታል ። ይህም ሁሉንም ሰዎች ያጠቃልላል ። አሽሌይን ግን አይጨምርም ። ትላልቆቹ የቤቱ ቁሳቁሶች ሁሉ በደብዛዛው ብርሃን ውስጥ ገዝፈው አፈጠጡባት ። ከፍ—ከፍ ያሉ መደርደሪያ ዎችና በጣም ዝቅ ያሉ የመቀመጫ መደቦች እንዲሁም ሰፋፊ የእጅ መደገፊያዎች ያሏቸው ለረዣዥም የዊክስ ቤተሰብ ወንዶች የተሰሩ ወንበሮች ፤ በለስላሳ ጨርቅ የተሸፈኑ ለሴቶች የሚሆኑ በርጨማዎች አሉ ። በረዥሙ ከፍል ውስጥ ከእሳት ማንደጃው ፊት ለፊት በቁመቱ የተዘረጋውና አሽሌይ በጣም የሚወደው ሰፊ ሶፋ ከፍ ያለውን የጀርባ መደገፊያውን ሲያሳይ እንድ የተኛ ግዙፍ እንስሳ ይመስላል ።

@OLDBOOKSPDF

በሩን ሳመል ታህል ብቻ ገርበብ አድርጋ በማታ ያለልክ እየ መታ የሚጋልበውን ልብዋን ለማረጋጋት ትጥር ጀመር። ትላንት ማታ አሽሉይን አናግረዋለሁ ያለችውን ነገር ለማስታወስ ብት ሞክርም ምናምኚት ነገር ትዝ አልል አላት። ለመሆኑ አንድ ነገር አስባ አውን ተረስቷት ነውን ወይስ አሽሉይ ራሱ አንዲያናግራት መስና ነበር የተወችው? ምንም ለማስታወስ አልቻለችም። ወዲያው አንድ ድንገተኛ የጭርሐት ቅዝቃዜ በላይዋ ላይ ሰፈነባት። ይሄ የፊራ ልብዋ ጆሮዋ ላይ ድው—ድው እያለ ባያስችግራት እኮ ምን አንደምትሰገር ማሰብ ትችል ነበር። ሆኖም የመጨረሻውን ሰው ሲሰናበትና በፊት ለፊት ወደ አዳራሹ ሲመጣ ሰማችና የልብ ትር ታዋ ሙራሽ እንደ አታሞ ይደለቅ ጀመር።

ለማሰብ የቻልችው አንድ ነገር ቢኖር እሱን ማጥቀሯን ብቻ ነው። ስለሱ የምታውቀውን ማንኛውንም ነገር ታፈቅራልች በኩራት ቀና ከሚለው ከወርቃማ ራሱ ጀምራ፣ ቀጠን ረዘም እያሉ እስከ ሚወርዱ በት ጫማዎቹ ድረስ ታፈቅረዋለች። ያንን ሳቁን ግራ ሲያጋባት እንኳ ሳይቀር ታፈቅረዋለች። መሳቅው እስኪጠፋት ድረስ የሚያደናግጣትን ሀሞታውን ጭምር ታፈቅረዋለች። ምኑው ወደሷ መጥቶ ክንዱን ከአንዱ አፍለልፎ ይዟት በሄደና ሀሳቧን ለመግ ለጽ የምትደነጋመውን ኪኳ፣ ባስቀረላት። መቼም እሷን ማጥቀር አለበት— "ምናልባት ብበልጅ" ዓይኖቹን ጭምት አድርጋ ጨፈ ነችና ለራሷ ማጉተምተም ጀመረች፡- "እመቤቴ ድንግል ማሪያም ሆይ፣ ክብር ምሥጋና ላንቺ ይገባሻል..."

"ምንው እስክርሌት!" አለ የአሽሉይ ድምጽ ጆሮዋ ላይ ከሚ ጮህባት የሕዝቡ ጉርምርምታ ዘልቆ መጥቶ። እሷ ግራ ተጋባች። እሱ ከዳራሹ ቆሞ በክፈል ገርበብ ባለው በር ውስጥ አሾልቆ ያያ ታል። ፊቱ ላይ ጉጉት፣ ማሾፍና አስፃሪነ እንቆቅልሽ ተደባልቆ ይንበብበታል።

"ከማን ነው የተደበቅሽው?—ክቻርልስ ነው ክታርሌተን ወንድማማችች።"

አንዴ ምራቋን ዋጥ አደረገች። አሃ፣ ለካ ወንዶቹ በሙሪያዋ እንደንብ ሲያንጎራጉሩ ልብ ብሎ ኖሯል! እሷ ምን ያህል እንደተ ረበሸች ቅንጣት ታህል ሳያስተውል የሚያበሩ ዓይኖቹን ከፍቶ ፊት ለፊት ቆሞ ሲያዩት እንዴት ያምራል፣ እንዴት ልብ ይሰር ታል! ታል መናገር ስላታታት ገም ብላ እጅዋን ዘርግታ ወደክፍሉ አስገባችው። ወደክፍሉ ሲገባ ነገሩ እንቆቅልሽ ቢሆንበትም ወዶ ታል። መጨነቅና ክብድ የማለት ስሜት ይታይባታል። ከዚህ ቀደም

@OLDBOOKSPDF

በጭራሽ አይቆጣት የማያቀው የዓይን መቅሳት ዛሬ ይታይባታል። ሌላው ቀርቶ በያብዛዛው ብርሃን ውስጥ እንኳ የድንጋጤዋን ብዛት የሚያሳየው የጉንጮቿ ሳንባ መምሰል ራሱ በጣም እንግዳ ነገር ነው። ከመቅጽበት በሩን ከኋላው ዘግቶ እጅጉን አፈፍ አደረገው።

"ምንድን ነው እሱ?" አለ ሹክሹክታ አክል በሆነ ድምጽ።

እሷ ገና እጅጉን በእጁ ሲነካው ያርድ ያንቀጥቅጥ ይዟታል። ልክ እንዳስመሸው፣ ልክ እንዳቀደችው፣ ልክ እንደተመኘችው እነሆ አሁን ሊፈጸም ነው። ጭራና ቀንዳቸውን የማትይዛቸው አንድ ሺህ ሙሉ የሰሸ ሀሳቦች መጡላት። ግን አንዳቸውንም ጨብጣ ቅርጽና መልክ ሰጥታ አንዴት ታል እንኳ ጠብ ልትልላት አልቻለችም። እንዲሁ ሠራ—አከሳቷ እየራደ፣ ከአግር — ጥፍሯ እስከራስ ጠጉሯ እየተንቀጠቀጠች ሽቅብ ፊት ራቱን ሚየት ብቻ ሆነ። እሱ ምነው አይናገር?

"ምንድን ነው ነገሩ?" ብሎ ደግሞ ጠየቃት" የምትነግሪኝ ሚስጥር አለሽ እንዴ?"

በድንገት አንደበቷን ፈታችው—ቃላትም አንደጉድ መጡላት። በዚሁ ፣ ቃላት በመጡበት ድንገትኖ ፍጥነት እየበረሩ የኤለንም የትምህርት ዓመታት ሁሉ ገደል ገቡ። በቦታውም ቀጥተኛው የጂራልድ እየርሳንዳቸ ደም፣ በሴት ልጅ አፍ ውስጥ ቃላት እየሆነ ይፈስ ጀመር።

"አምን—ምሥጢር ነው። አፈቅርሃለሁ።"

ለጥቂት ጊዜ ሁለቱም በጣም በጥ—አርጭ ከማለታቸው የተነሳ እንኳን ቃል ፣ እስትንፋሰም ያላቸው አይመስሉም። ወዲያው ደስታና ኩራት በሰውነታ ቢሰራጭ መንቀጥቀጧ ሁሉ ቀረ። ለም ንድነው ከዚህ ቀደም ይህን ነገር ያላደረገችው? ከሌሎቹ ከተማሪ ቻቸው የሴት ሥነ—ምግባሮች ሁሉ በቀላል ሁኔታ ተወጣችው። ዓይኖቿ ዓይናቹን ይፈልጉ ጀመር።

በዓይኖቹ ውስጥ አንዳች የመከፋት ውጥረት ይንቀለቀላል። የሆነውን ሁሉ አለማመንም ይነዳል። ሌላም ነገር አለ—ምን ይሆን? አምን ፣ አንድ ጊዜ ጂራልድ አይኖች ውስጥ አይታዋለች ፣ ትንሹ አዳኝ ውሻው አደን ሂዶ የገዛ እግሩን ሰብሮ የመጣ እለት እስከመግደል በደረሰበት ጊዜ ዓይኑ ላይ ተስለው የነበረው ስሜት ነው አሁን አሽሌይ ዓይኖች ላይ የምታየው። እስቲ አሁን ስለሱ ምን አሳስባት በእግ ዚሃርን በጣም ርካሽ ሐሳብ አኮ ነው ስሱ። አሽሌይስ እንዲህ ግራ

@OLDBOOKSPDF

የተጋባ መልክ ይዞ የመቅረቡ ሳያንስ ቃልም የማይተነፍሰው ምን ልሁን ብሎ ነው? ወዲያው ሁኔታውን ሁሉ አሸንፎ የሚሸፍን መላ ያገኘ ይመስል በቆራጥነት ፈገግ ብሎ ።

"ቅኑን ሙሉ የሰበሰብሽው ፣ የወንዱ ሁሉ ልብ አልበቃ ብሎሽ ነው?" አለ ፣ በዚያው በጥቱ አባብሎ አዛይ ድምፁ እሹሩሩ እያላት ። "ሙሉ በሙሉ በሞኖፖል ለመያዝ ፡ ያገሩን ሁሉ ወንድ መቶ በመቶ የራስሽ ለማድረግ ፈልገሽ ነው? መቼም የኔ ልብ እንኳ ከዱሮ ውም የራስሽ ነበር—ጥርስሽን ነቅለሽ ያደግሽበት ነው ። "

አንድ የተሳሳተ ነገር አለ—አረ ብዙ የተሳሳተ ነገር አለ! ይሄ እፀ ያቀደችው መንገድ አይደለም ። ጭንቅላቷ ውስጥ እንደአብድ ጨርቃቸውን ጥለው ከሚተራመሱት ሀሳቦች ውስጥ አንደኛው ፣ ቅርጽና ሰውነት እያበጀ ደምና ሥጋ እየተዋሃደው ሕያው ሀሳብ እየሆነ መጣ ። እንዴት እንደሁ እንጃ ፡ ሰምን እንደሆነም እንጃ አሽሌይ እሷ እንደምትቃለደው ፡ እንደምትሳፋው ዓይነት ነው የሚያስበው ። ነገሩ የተለየ መሆኑን ግን ያውቀዋል ። በተለየ መልኩ ይረዳዋል ። ይሄን እሷም አሳምራ ታውቃለች ።

"አሽሌይ — አሽሌይ— ስሞትልህ ንገረኝ — ልትነግረኝ ይገባል— አሁን ጨዋታና መሽኮርመሙ ይቅር በቃ ! እውነት ልብህ እኔጋ ነው? እውን ልብህን ሰጥተኸኛል? ወይ የኔ ጌታ ፣ እኔኮ አፈቅ..."

በእጁ አፏን ይዞ በፍጥነት ዝም አሰኛት ። ሽፋን ያደረገውን ዘዴውን ትቶ ወደራሱ ፡ ወደማንነቱ ተመለሰ ።

"እስካርሌት እንዲህ ያለ ነገር — መናገር የለብሽም !! አይገባም !ደሞም ክምርሽ አይደለም ። አየሽ ውለሽ አድረሽ ስለመናገርሽ ራስሽን ትጠያለሽ ፣ ስለማዳመጤ ደግሞ እኔን ትጠይኛለሽ!!"

ጭንቅላቷን ምንጭቅ አድርጋ ራሷን አሸሸች ። አንድ ፈጣንና የሚያቃጥል የስሜት ንፍጥ በላይዋ ላይ እየጋለበ ነው ።

"በጭራሽ ፤ አስከመጨረሻያውም አንቱን መጥላት አይሆንልኝም ። እውነቱን ነው የነገርኩህ —እኔ አፈቅርሀለሁ ። ደሞ ልትጠላኸኝና ልትንከባከበኝ እንደሚገባህ አውቃለሁኝ ምክንያቱም . ." አቋረጠች ። ከዚህ ቀደም ፤ እንደዚህ እሱ ፊት ውስጥ እንደም ታየው ያለ ጭንትና ሰቆቃ ፤ በማንም ፊት ውስጥ አይታ አታውቅም ።

"አሽሌይ ፤ ትጠነቀቅልኛለህ ፤ ትንከባከበኛለህ? አይደል የኔ ጌታ?"

"አምን"አለ ቅዝቅዝ ብሎ ። "እጠነቀቅልሻለሁ ። "

@OLDBOOKSPDF

ከንጭራሹ እጠላሻለሁ ፤ ታስጠይኛለሽ ቢላት ኖሮ እንኳ እን ዲህ እንዳሁኑ አትፈራም ነበር ። እንዲህ እንዳሁኑ እጅጌውን ጭም ድድ አድርጋ ይዛና የሙጭኝ ብላ ያላንዳች ቃል ያላንዳች ድምጽ በፍርሃት አትዋጥም ነበር ።

"እስካርሴት" አለ "ከዚህ ወጥተን አሁን የተነጋገርናቸውንም ነገሮች እንዳልተነጋገርንባቸው አድርገን ጨርሰን ልንረሳቸው አይ ቻለን ይሆን?"

"በጭራሽ" አለች በሹክሹክታ "እኔ አልችልም ። ምን ማለትህ ነው?— ልታገባኝ አትፈልግም ማለት ነው እንዴ?"

"እኔማ ሚላኒን ላገባ ነው" ብሎ መለሰላት ። እንዴት እንደሆን ሳታውቀው ፤ እፅ ዝት ባለው ባለ ፀጉር ወንበር ላይ ፤ እሱ ደግሞ እግሯ ሥር በርጨማ ላይ ቁጭ ብሎ እጅና እጅዋን ማጥም አድርጎ ይዞ አገኛችው ። ምንም ትርጉም የሌላቸው ፤ ምንም ስሜት የማይ ሰጡ ነገሮችን ይናገራል ። ከሞቲት ጊዜ በፊት ወደ አእምሮዋ ገብቶ የነበረው ነገር ሁሉ ሙልጭ ብሎ ታጥቦ ከሜንቅላቷ ወጥቶ ፤ ባዶ ሆናለች— አና ። አሁን እሱ የሚናገራቸውም ቃላት በመስታወት ላይ እንደሚፈስ ዝናብ አእምሮዋ ላይ ምንም ስሜት ሳይፈጥሩ ይወ ርዳሉ ። አንድ አባት ላኮረፈ ልጁ ወይም ሳዘነ ልጁ እንደሚናገረው ያሉ—ፈጣን ፣ ለስላሳና ባዘኔታ የተሞሉ ቃላት ቢሆኑም የማይሰሙ ጀሮዎች ላይ እያረፉ በከንቱ ይባክናሉ ።

የሚላኒን ሰም ሲጠራ ልብ ገዛችና የሚያበሩ ግራጫ ዓይኖ ቿን ተመለከተች ። በውስጣቸው ያንን ሁልጊዜ ስታየው ግራ የሚያ ጋባትን የሩቅነት መንፈስና ራስን የመጥላት ስሜት አነበበች ።

"አባቱ የጥምጥሙን ሥነ ርሥዓት ዛሬ ለሕዝቡ ሊገልፀው ነው ። በቅርቡ ልንጋባ ነው ። ልነግርሽ ይገባ ነበር ፤ ነገር ግን ታው ቂያለሽ ብዬ ስለገመትኩ ሳልነግርሽ ቀረሁ ። ደሞ ማንም ለብዙ ዓመታት ሲያወራው የቆየ ጉዳይ በመሆኑ የማያውቀው የለም ብዬ ገመትኩ ። በጣም ብዙ ወዳጆች አሉሽ ብዬ — አላሰብኩም ነበር ። እኔ እንዲያውም እስቲዋርት . . . . "

ሕይወት ፣ ስሚትና አካባቢን መረዳት እንደገና ወደ አእምሮዋ መግባት ፣ እንደገና ቦታ ቦታቸውን መያዝ ጀመሩ ።

"ግንኮ እጠነቀቅልሻለሁ ብለኸኝ ነበር"

ሞቃት እጅቹ ጨመቅ አድርገው እጅጅን ጉዲቸው ።

@OLDBOOKSPDF

"ውዴት ፤ አንቺን የሚጎዳሽን ንግግር እንድናገር ሚድረግ አለ ብሽ እንዴ ?" በገምታ ንግግሩን እንዲቀጥል ገፋፋችው ።

"እንዴት አድርጌ እነዚህን ነገሮች እንድታያቸው ላድርግሽ ፤ የኔ ቆንጆ ? አንቺ እኮ በጣም ወጣት ፣ በጣም ለጋና ሀሳብ— የለሽ በመሆንሽ ትዳር ምን እንደሆነ አታውቂም ። "

"እኔ እማውቀው አንተን ማፍቀሬን ነው"

"ተጋቢዎቹ የኔና ያንቺን ያህል ልዩነት ካላቸው የተሳካ ትዳር ለመመሥረት ፍቅር ብቻውን በቂ አይደለም ። እስካርሌት የሰው ሁሉ ነገሩ ያስፈልግሻል ፤ ሰውነቱ ፣ ልቡ ፣ ነብሱና ሐሳቡ ሁሉ ያንቺ መሆን አለባቸው ። እነዚህን ሁሉ በጅሽ ካላገባሻቸው ፣ እነዚህን ሁሉ የራስሽ ካላደረግሻቸው በጣም ትጎሳቆያለሽ ። በጣም ትጎጃለሽ ፣ ትሰቃያለሽ ። እኔ ደግሞ እነዚህን ሁሉ ልስጥሽ አልቻልኩም ። እኔን በሙሉ ፣ ራሴት በሙሉ ለማንም ሰው ልሰጥ አልችልም ። እኔም ብሆን ያንቺን እኩሮ ሁሉ ፣ ያንቺን ነብስ በሙሉ ለኔ እንድት ሰጪኝ አልፈልግም ። ያ ከሆነ በጣም ትጐጃለሽ — ትሰቃያለሽ ። ስትጐጂና ስትሰቃይ ደግሞ እኔን ምርር ብለሽ ትጠይኛለሽ፡-ምን ያህል በምሬት ልትጠይኝ እንደምትችይ ይታየኛል! የማነባቸው መጽሐፍትና የማፈቅረው ሙዚቃ ሰጥቂት ጊዜም ቢሆን እኔን ካንቺ ነጥለው ፣ እኔን ካንቺ ነጥቀው ስለሚወስዱብሽ በጣም ትጠያቸዋለሽ ። እናም እኔ . . . ምናልባትም እኔ . . . "

"ታፈቅራታለህ"

"እሷኮ ልክ እንደኔ ናት ፤ የደሚ ቅናሽ የአካሉ ክፋይ ናት ። እርስ በርሳችን እንግባባለን ። ስለሆነም እንመሳሰላለን ። እስካርሌት! እስካርሌት! ጋብቻ የተቀደሰ እንዲሆን ፣ ትዳር ሰላም የሰፈነበት እንዲሆን የሚጋቡት ሰዎች የሚመሳሰሉ መሆን አለባቸው የሚለውን ቁም ነገር እንዲገባሽ ለማድረግ አልችልም ማለት ነው?"

ይህን ከዚህ ቀደም አንድ ሌላ ሰው ነግሯታል" የሚመሳሰሉ ሰዎች ካልተጋቡ ምንም ደስታ አይኖርም ። "ግን ነበር ያለው!ይሄን አባባል ከሰማች በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዓመታት ያለፉ መስላት ። ያም ሆኖ ግን በእርግጥ ምን ማለት እንደሆን ገና አልገባትም ።

"ግን እኮ እጠነቀቅልሻለሁ ብለኸኝ ነበር"

"ያን ማለት አይገባኝም ነበር"

ከሞንትላቲ አንዱ አካባቢ ቀስ በቀስ የምትቀጣጠል እሳት

@OLDBOOKSPDF

ተያያዘችና የቱጣ ነበልባል አከላ ጭንቅላቷ ውስጥ ያለውን ነገር ሁሉ ባንድ አፍታ እያቃጠለች ረመጡን ብቻ አስቀረችው።

"መቼም ባለጌ በመሆኔ ስለተናገርኩት..." ፊት ባንዴ ነሞሆነ።

"ሚሻኒን እንደማገባ እያወኩኝ መናገሬ ብልግና ነው። ባንቺ ላይ ጥፋት ሠርቻለሁ። በሚለኒ ላይ ደግሞ የባሰ ጥፋት ፈጽሜ ያለሁ። እንደማይገባሽ ሳውቅ መናገር አልነበረብኝም። ላንቺ ከመ ጠንቀቅ አንዴት ወደ ኋላ ማለት ይቻለኛል? — እኔ የሌለኝ የህይወት ጉጉት፣ እኔ ውስጥ የሌለ የሕይወት በለት አንቺ ውስጥ አለ አይደለም እንዴ፣ እኔ የሰለኝ በህልበት በእመና ማፍቀር፣ እኔ ውስጥ የሌለ በጎይል በችግል የማፍቀር ችሎታ ያለሽ አይደለሽም እንዴ፣ አንቺ ጌት እንደ እሳት፣ እንደንፋስ እንዶሌሎች ማሙጭ ነገሮች ሁሉ ተጨለባው ፍጥረት ነሽ እኔ ግን..."

ስለ ሚሻኒ አሰበችና በድንገት እንዚያን ፈጋ ያሉ፣ ዐጥቶኛ ቢጥማ ዓይኖችዋንና ሩቅ ሩቅ የማየታቸውን ነገር፣ በዋቁር አልቦ ውስጥ ያሉትን በጣም ዝማ ያሉ ትናንሽ እጆቿንና የከሩ ዝምታ ኘነቷን ነገር አሰላሰለችው። ወዲያው ጉዴትና ቁጣዋ እንዴ እሳተ ገሞራ ፈነዳ። ይሄ ቁጣዋ ደንን አባቷን ጀራሲድን ግደል—ግደል ያለኘው የነበረ ቁጣ ነው። ይሄ ቁጣዋ አየርላንዳዊ አያት—ቅድም አያቶቿን እያስገነፈለ ኋላ በሕይወታቸው ጭምር ዋጋ የከፈለበትን ሰህተት ያስፈፅማቸው የነበረ ቁጣ ነው። ዓለም የሰነዘረችውን ጹላ ሁሉ በኢኮብ ትእግሥት የመሸከምን ምኤናቷን ወገኖች — የርቢላን ጾችን — ሊመርድ ሲዋረድ የመጣ ጨካት ሁሉ እፈር ድሜ አስ ግጣዋለች።

"ለምን አትናገረውም ታዲያ፣ አንተ ፈሪ—ቡከን ነኢን ማግ ባት ፈርተህ ነው፣ ከዚያች "እምን" ኔና "አይደለም" ከማለት በቃር አፏን ሰመክፈት ከማትችልና አይጥ የመሳሰሉ ማቲዎች ለመፈል ፈል ብቻ ባል ከምታገባ ለጭላ ጅል ጥሎረት ጋር ለመኖር ብለህ እኔን ማግባት ፈራህ። እኮ ለምንድነው..."

"ስለ ሚሻኒ እንዲህ ያለውን ነገር መናገር የለብሽም!"

"'ይሀን አታድርጊ' የምትለኝ ባሪያህ አይደለሁም እኔ! ይሀን አትበይ፣ ይሀን አታድርጊ የምትለኝ አንተ ማን ነህና ነው? አንተ በከነነ ሰድ ባለጌ! አንተ... ታገባኛለህ ብዬ እንዳምን ካደረግኸኝ በኋላ..."

"ባክሽ በግክክል ፍረጂ" ድምጹ የልመና ቃናን ያዘለ ነው። "እስቲ እንደው በሞቱ ፍረጂኝ፣ በሕይወቱ አንዴስ እንኳን..."

@OLDBOOKSPDF

የሚናገረው ዕውነት መሆኑን ብታውቅም እንኳ በትክክል ፍርድ ለመስጠት ግን ፈቃደኛ አልሆንችም። እስከዛሬ አብረው ሲቆዩ ለእንዲት ቀን እንኳ ከጓደኝነት ድንበር አለፍ ብሎ፥ አንዲት ቀን እንኳ ከባልንጀርነት አጥር ዘሎ ብሎ ሴላ ቅጥር ግቢ ሳይገባ የቆየ የመሆኑን ነገር ስታስብ፥ አዲስ ቋጣ እንደገና እቅጠቀጠበት— ከተደፈረ ክብርና ከእንስታዊ ክንቱነት የተወለደ ቁጣ! እስከዛሬ ሰት ከቀለው ከረመች—እሱ ግን አሁን ምኗንም የራሱ ሳያደርግ ነው። ከሷ ይልቅ በጥርሃት የተሸማቀቀ አመዳም ፊት ያላትን ለቋሳ ጅል ሚላኗን መረጠ። አይ፥ የዚህ የዚህ ምንው የኤሰንና የማሚን ምክር ተቀብላ እንኳን ማፍቀሯን መውደዷን እንኳን ሳትገልጽለት እርሱ ቁም ባለች ኖሮ። በዚህ የሐፍረት ማጥ ውስጥ ከመጨቅየት መቼም የማይሻል ነገር የለም።

እጆቿን እንደጨበጠች ብዙማ አለች። አሱም ከበላይዋ እንደ ምስሶ እያዘላ ቀስላ። ራቁ ላይ የተኙደፈው ድምጽ አልባ የሲቃይ ስዕል፥ ተጨባበጩ ዓለም ሠክራና ሰቆቃ በሆንበት ሰዓት የማዴን እንዲቀበለው የተገደደን ሰው፥ ከቃይ ይመስላል።

"እስከሕይወቱ ፍጻሜ ድረስ የምጠላው ሰው ቢኖር አንተ ነህ። አንች ቡነን ብለኒ፥ አንች ዝሙቱ አተላ—. . አንች ትቢያ የወ ዳቂ መጨረሻ. . "ምን ነበር ልትለው የምትፈልገው ቃልን የባሰ ሙጥር ስድብ ለማሰብ አልቻለችም።

"እለክርሰት—ኣባክሽ. . . "

ለማኝ እጆቹን በረጋሳት። እሷ ግን ባሰ በሴሰ ኃይሏ ተንጠ ራርቃ በጥፊ መረገጥበት። ዩጥ ላለው ክፍል ውስጥ የጥፊው ጭብጥ እንዳበንጋ ግርፊያ ድምጽ አሰተጋባ። ከመቅጽበት ያ ቁጣዋና ንዴቷ ሁሉ ተግፈፈለትና ልቧ ብቻውን ቀረ—እና ቤት።

በደከመ ነጭ ራቁ ላይ እጅዋ የተወው አሻራ፥ ሰምበሩ ጉልቶ ቀልቶ ይታያል። እሱ ምንም አላለ። ያንን አትም የለሽ እጅዋን ያዝ አድርጎ ወደ ከንፈሮቹ አስጠጋና ሳመው። እንደገና ለመናገር እየ ታጣት፥ ግን ዓና ታል ሳይወጣት በፊት በራን በጥሞና ዝማ አድ ርጎ ከኋላው ዘግቶባት ጥሏት ሄደ።

ድንግት ቁሙ አሰች፥ የንዴቷ ኃይል፥ ጉልቤቷን አለሞ ታል፥ አድክሞታል። እሱ ሄዷል። በጥፊ ፍም የመሰለው ራቁ ትውስታ ግን እስከ አለተ ሞቷ ድረስ ዕፀቱ ልቧን እንዳደማው ይኖራል።

በስስ ኮቲው የሚለማው እርምጃው ቁልቁል በረሻሮ፡፡ አዳራሽ ውስጥ እየራቀ፥ እየደከመና እየሞተ ሲሄድ፥ እሷ የሠራችው ሥራ

@OLDBOOKSPDF

ሁሉ መጥቶ መላ ሰውነቷ ላይ ተጫነ ። ከእንግዲህ ለዘለዓለም እጣ ችው ሚሰት ነው ። ካሁን ወዲያ ባያት ቁጥር እንዴት ተንጠራርታ አካላቷ ሁሉ አንድ እጅ እስከሚሆን ድረስ ኃይሏን አጠራቅማ ፣ ፍቅሩን ስለነሳት ፣ እንደተወረወረችበት እያስታወሰ ከልቡ ነቅሎ ይጥላታል ። እስከዛሬ ጠልቶ የማያቅበትን ልቡን ሙሉ ጉልበቱን ተጠቅሞ ይጠላበታል ።

"እንደሐኒ ዊክስ ዓይናውጣ ባለጌ ሆንኩኝ" አለች በልባ እንደ ድንገት እያሰበች ። እናም ሰው ሁሉ ሐኒ ዊክስን ማልጥጥ ያለች ዓይን አውጣ በመሆኗ እንዴት እንደሚጠላት ራሷም እስካርሴት ከሰው ሁሉ በላይ በዚሁ ፀባይዋ እንዴት ዓይንሽን ለአፈር እንዳ ለቻትና የጥላቻ ሰቅ ትስቅባት እንደነበር ፣ ሁሉንም አስታወሰች። የሐኒን ማልብ ብልግና ፣ በየሄደችበት እንዴት እንደምትመናቀር ፣ እወንዶች ከንድ ላይ እየተንጠለጠለች ምን ዓይነት ሴት አሳፋሪ ንግግር ትናገር እንደነበር አሰላሰለችና ይሄ ሃሳብ አዲስ የንዴት ፍም ላይ ወዘታት ። በራሷ ተናደደች ። በአሽሊይ ተናደደች ። በዓለም ተናደደች ። እራሷን የጠላች ለለሠ ነ ፣ በእሥራ ስድስት ዓመት ልጅ ነረድ የቀመሰቻቀለና በውርደት የጭለለ ፍቅር የብስጭት ማፊት ስበብ ሁሉንም ጠመደች ። ሁሉንም ጠላች ። እንዲት ቅንጣት ታህል የመውደድ ስሜት ቀንበጥ ብቻ ፍቅሯ ጠለጥ ተቀላቅላ ነበር ። አብዛኛውን ጊዜ የሷ ፍቅር ይገነባ የነበረው ከከንቱነትና ከራሷ ደም ግባት ላይ ከመመከት ግብዝ ተፈጥሮ ነበር ። አሁን እንግዲህ ሁሉንም እጥታ ባዶዋን ቀርታለች ። ሁሉን ነገር በማጣቷ ከተሰ ማት ስሜት ይልቅ ደማም ፊሲን ሕዝብ ፊት አጋለጥኩ የሚለው ጥርሃት የበለጠ ሚዛን ይደፋል ። እንደሐኒ ማልብ ሆና ኑሯል እንዴ? ሰው ሁሉ ይስቅባት ነበር እንዴ? ይሄ ሀሳብ ሰውነቷን ይንጣት ፣ ያንቀጠቅጣት ጀመር ።

እጆቿ ገኗ ባለች ትንሽ ጠረጴዛ ላይ አረፉ ። አንዲት ትንሽ ሮዝ የአበባ ማስቀመጫ ሁለት እግር አትክልቶች እንደቆ ሙባት ጠረጴዛዋ ላይ ተቀምጣለች ። የእስካርሴት ጣቶች ይዳ ስሷታል ። ቢቱ የፀጥታ በረዶ በመሥራቱ የተነሳ እስካርሴትን ጨሂ ጨሂ የሚል ሰማት ተሰማት ። አንድ ነገር ማድረግ አለባት ፣ አለ በለዚያ ማበዷ ነው ። ያቺን ያበባ ማስቀመጫ አንሳችና ወደ እሳት ማንደጃው ቦታ ወረወረቻት ። የረሻሙን ሶፋ ጀርባ እግዚሃር አወ ጣው ። ማስቀመጫዋ ከእምነበረድ ከተሠራው የቤቱ ማድማዳ ጌጥ ጋር ጥቂት ግጭት ብትፈጥር ባንድ ጊዜ ብትንትኗ ወጣ ።

"ይሄም" አለ አንድ ድምጽ ከረሻሙ ሶፋ ሥር "ይሄም በጣም በዛ" ።

@OLDBOOKSPDF

እስካርሴት እንደዚህ ድምጽ የሚያስደነግጥና የሚያስፈራ ነገር በፍፁም ገጥሟት አያውቅም ። እንድ ቃል አርሳ የምታወጣበት ጠብታ ምራቅ እስከምታጣ ድረስ አፏ ክሽኽ ብሎ ደረቀ ። የወንበሩን ጀርባ ጭምድድ አድርጋ በጅዋ እንደያዘች ጉልበቶቿ ሊከዷት እየዳዳቸው ፤ እንደሎጥ ሚስት ተገትራ ሳለች ሬት በትሰር ተኽዶበት ከነበረው ከሰፋው ሥር ብድግ ብሎ ከልኩ በጣም የተጋነነ ትህትናን ያዘለ የእጅ መንሳት ሰላምታ ሰጣት ።

"መቼም ይሄን አሁን እኔ የሰማሁትን ጉድ እየሰሙ ከቀን እንቅልፍ መረበሽ በጣም መጥፎ ነገር ነው ። ግን ሕይወቴን እደጋ ላይ የሚጥል ሙከራ ለምን ይደረግብኛል?" የአውነት ሥጋና ደም የለበሰ ሰው ነው ። ጣረ ሞት አይደለም ። መሳአክት ይጠብቋት እንጂ የተባለውን ሁሉ ከሰማማ ጉድ ፈላ ያለ የሴሳትን ጉልበት ክብርን መጠበቅ ላይ በማረባረብ ፤

"ጌታው ፤ እዚህ መኖርህን ማሳወቅ ነበረብህ"

"እርግጥ?" ነጫጮቹ ጥርሶቹ ብልጭ አሉ ። ደፋሮቹና ጥቁቁ ሮቹ ዓይኖቹ ሳቁባት ። "አፋኞህበት ድረስ መጥተሽ ችግር የፈጠርሽው እንቺ ራስሽ ነሽ ። ኬፊሲን እንድጠብቅ በመገደዴ እዚሁ መቆየት ነበረብኝ ። ታዲያ እገር የጠላው ሰው ነኝ በሚለው ስሜቴ ምክንያት ጓሮ መስኩ ላይ ሰመተኞት እንደማይፈቀድልኝ በመገመት ማንም በማይረብሸኝና ሊቀበለኝ የማይሻው ህብረተሰብ የማይደርስበት ቦታ መርጨ ተኛሁ ። ዳሩ ምን ያደርጋል!" ትከሻውን ከፍ ዝቅ አደረገና ለስለስ ያለ ሳቅ ሳቀ ።

እስካርሴት ምኑው ከምናገራቸው ሞቼ ባረፍኩት ያለኑዋትን ቃላት ፤ የዚህ ፤ እገር የጠላው ስድ ሰውዬ መስማት ደህና የቀዘቀዘ ብስጭቷን እንደገና ቀሰቀሰባት ።

"የሌሊት ወፍ . . " አለችና ጀመረች ፤ አንጀቷ እርር ድብን ብሎ ።

"የሌሊት ወፍኮ አብዛኛውን ጊዜ የምታዳምጠው በጣም የሚያዝናናና ግሩም ትምህርት የሚሆን ነገር ነው" አለ በሽሙጥ ። "እን ደሌሊት ወፍ ጣራ ጥግ በመታከክ ካለኝ የረኽርም ጊዜ ልምድ አንጻር ፤ እኔ . . . "

"ጌታው ፤ በፍፁም ጨዋ ወንድ አይደለህም!"

"ጥሩ አስተውለሻል ፤ እመቤት" እየተዝናና መለሰላት ። "ሆኖም አንቺም ብትሆኚ ጨዋ ሴት አይደለሽም" በጣም የምታስገርም ሴት ሆና ያገኛት ይመስላል ። አሁንም ለስለስ ያለች ሳቅ ሳቀ ። " ምክ

@OLDBOOKSPDF

ነያቱም ይሂን እኔ ዛሬ ሲነገር የሰማሁትን ዓይነት ነገር ተናግራ፤ ማንም ብትሆን ጨዋ ሴት ልትባል አትችልም ። ያም ሆኖ ሌቶች ፣ ቆንጆ ናቸው የሚባሉ ደመ ግቡ ሴቶች እንኳ የሚስቡኝ በጣም በጥቂቱ ነው ። ምን እንደሚያስቡ አውቃለሁኝ ። ነገር ግን ያሰቡትን ለመናገር ድፍረቱ ወይም የአስተዳደግ ጉድለቱ ያንሳቸዋል ። ያም ቢሆን ከጊዜ በኋላ ይሰለቻል ። አንቺ ግን ውድ ወ/ት አስካርሌት፤ በጣም ድንቅ መንፈስ ፣ በጣም ክቡር መንፈስ ያለሽ ግሩም ሴት በመሆንሽ ባርኔጣዬን ከፍ አድርጌ እጅ እነሳሻለሁ ። እንዳንቺ ያለች ኃይለኛና ሞገደኛ ሴት እንደ አቶ አሽሌይ ዊክስ ያለ ሸጋ ሰው ምኑ እንደሚጥማት ሊገባኝ አልቻለም ። መቼም እንዳንቺ ያለች— እንዴት ብሎ ነበር የገለፀሽ— በሕይወት ስስት የተሞላሽ ግን መንፈስ ደካማና የከፋሽ ሴት . . . ለማግኘት በመቻሉ በሁለት እግሩ ተንበርክኮ እግዚአብሔርን ማመስገን ነበረበት ። ”

“አንተ እግሩ ጥፍር ታ እንኳን አትደርስም!” በንዴት ብግን ብሳ ጮኽሽ ።

“እንዴ ፣ አንቺ እኮ እስከ አሁኑ ምትሽ የምትጠይው ሰው እንደሚሆን መናገርሽን አትርሺ!” ሶፋው ውስጥ ስምጥ ብሎ ተቀመጠና ፣ መሳቅ ሲጀምር ሰማችው ።

መማደል ብትችል ኖሮ አሁኑኑ ብትገለው ፈቃዷ ነበር ። በማድያው ፋንታ በምትችለው አቅም ሁሉ ኮራ ብላ ከክፍሉ ወጣችና በፉን ወደኋላዋ በኃይል ወርውራ አስጨሃ ዘጋችው ።

ደረጀውን በጣም በፍጥነት ከመውጣቷ የተነሳ ፎቁን ጨርሳ ላይኛው ወለል ላይ ስትደርስ ልቧ ፈስሳ የምትወድቅ መስሏት ነበር ። የመውጫውን መደገፊያ እንቅ አድርጋ ይዛ ቆመች ። ልቧ ባንድ ወገን ንዴት ፣ ባንድ ወገን የስድብ ውርደት ፣ በሌላ ወገን ከብዙ መራ ወጥ የመጣ ድካም ከመሸከሙ የተነሳ በመዶሻ የሚቀጠቀጥ ይመስል ሲመሃ ፤ እንደኛውን ደረቷን ፈጥርቆ ጥሶ ፈንድቶ የሚወጣ ይመስላል ። ደህና አድርጋ ለመተንፈስ ትፈልጋለች ። ነገር ግን የሚያሚ መቀነት በየት በኩል —ጥስቅ አድርጎ ይሄታል ። አሁን እዚህ ልቧ ፍስስ ብላ ወለሉ ላይ ተዘርራ ቢያገኙዋት ምን ይሉ ይሆን ? አ ፤ ምን የሚያስቡት ነገር አለ? ሁሉን ነገር ነው የሚያስቡት—አሽሌ ይንና ያንን በትለር የሚባል ሸቃባ ሰውዬ ፤ እንዲሁም በትናት ያረ ሩትን ልጃገረዶች በሙሉ፣ በሕይወቷ ለመጀመሪያ ጊዜ ፤ እንደ ሌሎቹ ሴቶች የሚሸነፉት እሞሉ ጨው ይገር በመጣሁ አሰኛት።

@OLDBOOKSPDF

ነገር ግን የኩምጣቤ፥ የጨው ወዘተ... ማስቀመጫው እንኳ ዕቃ የላትም ። እንደሁልጊዜው የሰውነት መደንዘዝ፥ የመደበትና እንቅልፍ እንቅልፍ የማለት አመል ስለሌለባት ኩራት ተሰማት ። ካሁን ወዲያማ ልቧ እስክትፈስ ድረስ የሚያደክም ምንም ነገር አታደርግም ! !

ቀስ በቀስ የህመም ስሜትዋ እየጠፋላት ሄደ ። በደቂቃ ውስጥ እየተሻላት ትሄዳለች ። ኢንዲያ ከተኛችበት ቀጥሎ ወዳለው መልበሻ ክፍል ቀስ ብላ ትገባና ልብሷን አወላልቃ እዚያ ከተኙት ሴቶች ጋር ትተኛለች ። ልቧን ካለረጋጋችውና ፊቷንም በቅጡ በቅጡ ካላደረጉው ያበደች ሴት እንደምትመስል ታውቃታል ። ከተኙት ሴቶች እንደኛዋ ነቅታ ከየቻት አንድ የተበላሸ ነገር መኖሩን፥ አንድ የሆ ነችው ነገር እንዳለ ያውቁባታል ። መቼም ማንም ይሁን ማን ዛሬ የደረሰባትን ነገር በጭራሽ ማወቅ የለበትም ።

ወደ ሜዳው በሚያሳየው ሰፊ መስኮት አሻግራ ስትመለከት በየዛፉ ጥላ ሥርና በየበረንዳው ሳይ ባሉት ወንበሮች ሰምቼ አሁ ንም ተቀምጠዋል ። እነዴት ያስቀናሉ! ምነው ወንድ በሆነች ኖሮ! ይሄ ዛሬ ያየችው ዓይነት ሥቃይ በጭራሽ አይደርስባትም ነበር! እዚያው እንደቆመች እይኢ ቅልጥና ድንዝዝ ብላ ስታስተውል፥ አንድ በጣም ፈጣን የሆነ የፈረሶች ኩይ ድምጽ ሰማች ። እቧራው ቦነነ ። ሬግሮዎቹን የሚጫራ አንድ የተረበሸ ድምጽም ተሰማ ። አንድ ሰው እየጋለበ አረንጓዴውን ሜዳ አቋርጠ ደክሚቸው ወደ ቀቀመጡት ሰምች ሄደ ።

የረፈደበት እንግዳ ነው ። ነገር ግን የኢንዲያ ኩራትና መመኪያ በሆነው አረንጓዴ ሜዳ ላይ ለምን እንደዚህ እንደሚጋልብ እንጃ! ማን እንደሆነ ሊታወቅው አልቻለችም ። ሆኖም ከኮርቻው ወርዶ የጆን ዊክስን ክንደ ጡበጦ ሲያወራ ሰውነቱ በሙሉ መረበሽና መቅበጥበጥ ይታይበታል ። ሰው ሁሉ ረዣዥሮም ብርጭቆውንና ማራ ገቢያውን በየጠረጴዛው ላይና በየተቀመጠበት ግር ላይ እየጣለ መጥቶ ሰውየውን ባንድ ጊዜ ከበበው ። ምንም እንኳ እሷ ከለች በት ሩቅ ቢሆን የሰምቹን ጉርምርምታና ጥያቄ፥ ውትወታና የመጮ ትሳት ስሜት እንዲሁም በአየሩ ላይ የሚተመውን የውጥረት መን ፈስ ታነባለች ። ወዲያው ግራ ከተጋባው ሕዝብ ድምጽ ሁሉ በላይ ድምፁን ከፍ አድርጎ እስቱዋርት ታርሌተን "አ.ሁ.. ሁይ!" ብሎ ጮኸ ። ድምፁ ልክ እደን ጫካ ውስጥ የሚጮኸውን ዓይነት ነው ከዚያም ለመጀመሪያ ጊዜ ሳታውቀው የአመፁን ጩኸት ሰማች።

አራቱ የታርሌተን ቤተሰብ ልጆች የፎንቴን ልጆች እየተ ከተሏቸው ከሰው ተነጥለው በፍጥነት ወደ ፈረሶቹ አቅጣጫ ሲሄዱ

@OLDBOOKSPDF

ተመለከተች ። "ጂምስ! ጂምስ! ፈረሶቹን ጫናቸው!" እያሉ ጮሁ አግረ መንገዳቸውን ።

"ያንድ ሰው ቤት ተቃጥሏል ማለት ነው" አለች እስካርሌት በልቧ ። ብቻ እሳት ኖረም አልኖረ አሁን እሷ ማድረግ ያለባት ሳይታወቅባት መኝታ ቤት ገብታ ድምጿን አጥፍታ መተኛት ነው።

አሁን ልቡዋ ረጋ ብሎላታል ። በእግር ጣቷ ቀስ እያለች እየረገጠች ሽቅብ ወደ ዐጥፋው አዳራሽ ለመግባት ደረጃውን ወጣች።

ቤቱ ማታ በሙዚቃና በሻማ ብርሃን ድብልቅልቁ እስኪወጣ ድረስ ፤ ልክ እንደሌቶቹ ልጆች እንደተኛ ሁሉ የሚያስደንግጥ እር ጭታ ወሮታል ። በጥንቃቄ የመልበሻ ክፍሉን በር ያለአንዳች ክሽታ ከፈተችና ሹልክ ብላ ገባች ። እጅዋን ወደኋላዋ አድርጋ አሁንም የበሩን እጀታ እንደያዘች ናት ። በወዲያኛው በኩል ወደመኝታ ቤት በሚያስገባው በር ክፍተት የሐረ ዊክለ የሹክሹክታ ድምጽ መጥቶ ጆሮዋ ጥልቅ አለ ።

"እንደሚመስለኝ ማንም ቀልጣፋ ልጃገረድ ማድረግ የሚገባትን ሁሉ ዛሬ እስካርሌት ፈጽማለች"

እስካርሌት ልቧን የተሰመደ ግልቢያውን ሲጀምር ተሰማትና በእጅዋ ጨመቅ አድርጋ ያዘችው ። ሳታውቀው ደረቷን በጣም ከመጫኗ የተነሳ ልቧን መጋለቡን የምታስቆመው ይመስላል ። "የሌሊት ወፎች ብዙ ጊዜ ዋና ዋና ትምህርት የሚሰጡ ነገሮች ችን ይሰማሉ" የሚል አባባል ትውስ አላት ። ተመልሳ ትውጣ ይሆን እንዴ! ወይስ መኖሯን ታሳውቅና ድንጋጤ በድንጋጤ ታድርጋ ቸው ? የሚቀጥለው ድምጽ ግን እንቅስቃሴዋን እንድታቋርጥ አደ ረጋት ። የሚላትን ድምጽ ስትሰማ የደነገጠችው ድንጋጤ የጅብ መንጋ ቢከባት እንኳ የሚሰማትን ድንጋጤ በእጥፍ ድርብ የሚ በልጥ ነበር ።

"ውይ ሐኒ እንደዚህ ጨካኝ አትሁኝ ። እሷኮ ዱሮም ተጫዋችና ግልጽ ልጅ ናት ። እኔ በበኩሌ እዚያ ከነበሩት ሁሉ በጣም ማራኪ ሆና ያገኘኋት እሷን ብቻ ነው ። "

"ውይ ጉዴ!" አለች እስካርሌት በልቧ ፤ በጥፍሯ ጡቷን ጫን ብላ እየወጋች ። "ይቺ አይጥ የመሰለች ፍጥረት ለኔ ትከራከር ደሞ!"

መቼም ሐሜተኛዋ ሐኒ ራሷ መሸከም ከምትችለው በላይ ነው ። እስካርሌት ራስ ወዳድነትን በሚመለከት ከራሷ አስበልጣ

@OLDBOOKSPDF

ለሌሎች የምታስብ አንድ ሴት የምታውቀው እናቷን ኤለንን ብቻ ነው። ሚሳኒ አሽሌይን በእጅዋ ማግባቷን ስላረጋገጠች መሆን አለበት እንዲህ ያለች ቅዱስ ክርስቲያን የሆነችው። እስካርሌት፥ ሚሳኒ ባንድ ወገን ጦርነት እያካሄደች ባሸናፊነት የምትወጣበት፥ ባንድ ወገን ደግሞ ስለደግ ሥራዋ የምትመሰገንበት ዘዴ መፍጠሯ ነው— ብላ አሰበች። እስካርሌት ይህንን ዘዴ በተደጋጋሚ ሌሎች ሴቶችን ለወንዶች ስታማ ብዙ ጊዜ ተጠቅማበታለች። ታዲያ ብዙ ግብዝ ወንዶች ደግና ራስ ወዳድ ያልሆነችዋ ሴት ናት ብለው እንዲ ያምኑ አድርጋቸዋለች።

"አይ ሜሊዬ" አለች ሐኒ ድምፁዋን ኮምጠጥና ከፍ አድርጋ፥ "ታውረሻል ማለት ነው።"

"ባክሽ ቀስ በይ ሐኒ" አሰች ሳሲ መንሮ በቀስታ። "ቤት ያለው ሰው ሁሉ ይሰማችኋል እኮ!"

ሐኒ ድምጽዋን ትቀንሰ እንጅ ወሬዋን ቀጥላለች።

"መቼም ለመያዝ የቻለችውን ወንድ በሙሉ ነጥቃ ሰመውሰድ ስትራወጥ ባይንሽ በብረቱ አይተሻል። ሴላው ቀርቶ የገዛ አህቷን ወዳጅ ሽማግሌውን ኬኔዲን ሰማሽኮርመም ስትጥር ተመልክተሻል። እንደሷ ያለ አይምሬ ሴት መቼም፥ በጭራሽ አይቼ አላውቅም! ጨሳጣ— ጨሳጣ እኮ ናት፣ ደሞ ምርለስንም ልታጠምድ መረቧን ስትጥል ነበር እኮ።" ሐኒ የልቧን በልቧ ይዛ የፌዝ ሳቅ ሳቀች። "ደሞ እንደምታውቂው —ምርለስና እኔ....."

"እውነትሽን ነው?" አሱና ብዙ ድምጾች በሹክሹክታ ጠየቋት፥

"ብቻ ለማንም እንዳትነግሩ እናንተ— ግና መንገድ ላይ ነኝ፥ አላጠናቀቅኩትም!"

ሁሉም እየሳቁ ሳሉ አንዷ ሐኒን ቆንጠጥ ስታደርጋት አልጋው ሲጢጢጥ እያለ ተንቋቋ። ሜሳን፥ ሐኒ ወንድሟን ብታገባ እንዴት ደስ እንደሚላት በቀስታ ተናገረች።

"በበኩሉ እንደ እስካርሌት ያለች ቀበጥባጣ እህቴ እንድትሆን በጭራሽ አልፈልግም።" አለ የሐኒ ታርሌተን ድምጽ። "ለሷ ግን ከእስቱዋርት ጋር ብትጋባ ይሻላታል። ብሬንት እሷ ከጉዳይ እን ደማትጽፈው ይናገራል፥ ግን ራሱ ጠፍ ብሎ ሊያብድ ደርሷል"

"እንደው ምን አለች በሉኝ" አለች ሐኒ አንድ ምሥጢር በመናገሯ ትልቅነት እየተሰማት። "እሷ ጉዳዬ ብላ ልቧ እስኪጠፉ የምትወደው አንድ ሰው አለ — እሱም አሽሌይ ነው!"

@OLDBOOKSPDF

ሐሚታውና ሹክሹክታው እየተጋጋለ ጥያቄውና ማልቃ መግ
ባቱ እየተፋፋመ ሲሄድ አስካርሌት በስጋትና በሐፍረት ልቧ ልት
ቆም ደረሰች ። ሐኒ ወንዶችን በሚመለከት የጅል አስተሳሰብ
ነው ያላት ። ደደብ ናት ። በሴቶች ጉዳይ ማን— ምንም አስካርሌት
ብትንቃት— እነደው በደመ ነፍስ የምታውቀው መዓት ነገር
አለ ። እዚያ መሣሀፍት ቤት ውስጥ ከአሽሌይና ከራት በትለር ጋር
ያጋጠማት የክብር መቁሰልና ውርደት ራሱ ይህንኑ የሚመ
ለከም ማለረሽ ነው ። ወንዶች —ባለጌው ሬት በትለር እንኳ ቢሆን፣
የሰሙትን ምሥጢር ሲደብቁ ይችላሉ ። እንደሐኒ ዊክስ ያለችው
መንታ ምላስ ላይ ያረፈ ወሬ ግን ገና አሥራ ሁለት ሰዓት ሳይሞነ
ሳቸሩ በሙሉ ይሰረሰል ። ጂራልድማ ገና ትለንትናውኑ በሬት ልጂ
ላይ የመንደሩ ሰው ሲሰቅባት ማየት አልፈለማም ብሎዋት ነበር ።
አሁን ታዴዎ እንዴት ይስቋት ይሆን፣ የሚያጣብቅ ላብ ከብብቷ
ወርዶ በጉድኗ ሰደ ተዓጠፈጠረ ።

የሚሳኔ ድምጽ ከሁሉም ጉሉ ብሎ ተቃወሞውን አሰማ ።

"ሐኒ ፣ ያልሆነ ነገር አትናገሪ ። በጣም ሞኝነት ነው ።"

"ነው እንጂ ሚለ ። አንቺ ሁለጊዜ ምንም ደግ ነገር ልባቸው
ውስጥ የሌለን ሰዎች ደግ ነገር ውስጣቸው የምትፈልጊ ሰው ሆነሽ
ነው እንጂ ነገሩን ትጅርቪበት ነበር ። መሆኑ ደግሞ ደስ ብሎኛል ።
እንኳን ሆነ ። እሷም ዋጋዋን ታገኛለች ። እስካርሌት እሃራ እኮ
ፅድጣ ዓለሟን የሌሎች ሴቶችን ፍቅረኞች በማላደድ ችግር በትፈ
ጥር የምትኖር ናት ። ራስሽ በደምብ እንደሞታወቂው እስቱዋርትን
ከኢንዲያ ነጥቃ ለታበቃ ቦር በል አለችው ። ዛሬ ደግሞ ያው አቶ
ኬኔዲን ፣ አሽሌይንና ቻርለስን ለትነጥቅ ሰትሞክር . . ."

"ቤቲ ሙሄድ አለብኝም አለች እስካርሌት ባላቧ ። "ቤቴ
ሙሄድ አለብኝ ቢቃ!"

ምንው ባንድ በሆነ አለማት ወይም ብዓምር ከዚህ አንስቶ
ታሪ ላይ ቀጭ ምዚያዴርማና ዋስትናዋን የሚያረጋግጥ አንድ ነገር
ብኖኛት ። ምንው ከኤለን ጉን ለመቅመጥ በቻለች ። ዝም ብላ ዓይኗን
ለማየትም ቢሆን ምንው ከኤለን ጉን ለመቀመጥ በቻለች ። የቀ
ሚሰን ሜጭ ይህ ለመጠለል እንደትችል ፣ ጭኗ ላይ ተጅማሩ የደረ
ረሰባትን ታሪክ ሁሉ ዘርግሳላት አዘይ እንደትል ፣ ዕድል በዋራት
እንደሩት በተገላገለች ። ከእንግዲህ አንዲት ቃል የመስማያ ግዜ ያህል
እንኳ ብትቆይ ተንደርድራ የሐኒን ጨብራራ ዘቦር ጉሙት አው
ጥታ እንደጨራተለት ፣ ሚለኒ ሐሚልተንንም የደማትሽ ዋጋ ደሟ ነው

@OLDBOOKSPDF

ብላ እንደምትሩፋባት የታወቀ ነገር ነው። ዳሩ ዛሬ ምን ያልሆነችው ርካሽ ነገር አለ—ዋናው ችግሯም ይሄው ነው።

ቀሚሷ ድምጽ እንዳያሰማባት በጀርባ ሜን ብላ ደግፋ ቹክክ ብላ ደፈጣ ላይ እንዳለ አውራ በዋንታቂ እየተራመደች ወደ ኋላ ሄደች። ቤቷ ። የሚታያት ቤቷ ብቻ ነው። ቁልቁል አዳራሹን እቋርጣ ፣ የተዘጉትን በሮችና ዝምታ የቋጣቸውን ክፍሎች አልፋ በት ጣደፍ ሁሉ ወደ ቤቱ እሄዳለሁ የሚለውን ሀሳቧን አጠንክራለች።

ፊት ለፊቱ በረንዳ ላይ ሰትዶርስ እንድ አዲስ ሐሳብ አዕምሮ ዋን ያዛትና ቆመች — ለካ ቤት መሄድ ኦትችልም ከዚህ ጠፍቶ መሄድ የሚሞከር ነገር አይደለም፤ የሷቶቹን ሽሙጥ ፣ራሷን ሐፍረ ትና ቅስም ስብራት ሁሉ ችላ በረትታ መቀመጥ አለባት።ወደ ቤት ሮጦ መሄድ ለበለጠ ሐሜት በር መክፈት ፣ለባላንጣዎቿ የበለጠ ትጥቅ መስጠት ይሆናል።

አጠገቧ ያለውን ምሰሶ በተጨበጠ እጅዋ ሚን አድርጋ ተደግፋ — ምነው እንደሳምሶን ጠንካራና ኃይለኛ በሆንኩ ፣ ጠቅላላ "አሥራ ሁለቱን ዋርካዎች"ና በውስጡ ያለውን እያንዳንዱን ሰው ድራሹን አጠፋው ነበር — አለች ።ታሳያቸው ነበር ።እንዴት አድርጋ እንደም ታሳያቸው አታውቅም ፣ ቢሆንም ከማድረግ ወደ ኋላ አትልም ነበር። እሷ ላይ ካደረሰባት ጉዳት በእጥፍ ድርብ የሚበልጥ ከፍተኛ ጥቃት ታደርስባቸው ነበር ።ዋ ንዶ!

ባውኒ ደቂቃ አሽሌይን ራሱን ረስታዋለች ።ባውኒ ደቂቃ ለሷ አሽሌይ ማለት ፣ ያ ሎጋው ለግላጋው የምታፈቅረው ሽጋ ልጅ ሳይ ሆን ፤ ከዊከስ ቤተሰብ ውስጥ ያለ ማንም ተራ ሰው ነው ።ባውኒደቂቃ ለሷ አሽሌይ ማለት ፤በ"አሥራ ሁለቱ ዋርካዎች" ካሉት የመንደሩ ሰዎች አንዱ — እንዲያውም ማንም ሰው ማለት ነው ።ሁሉንም እን ዳንድ ነገር ነው የጠመደቻቸው ።ስለሚስቁባት ፣ስለሚያሾፉባትና ስለ ሚያሟት ካንጀቷ ጠልታቸዋለች ።

"በቃ ወደ ቤት አልሄድም"አለች በልቧ ።"እዚሁ ቆይቼ ወሽ መጣቸውን ነው የምበጥሰው ።ቆሽታቸው ድብን ይበል ።ለእናቴም ቢሆን አንድም ነገር አልነግራትም ። ኧረ ለማንም ቢሆን ምንም ነገር አልተነፍስም ።"እንደገና ወደዚያው ቤት ልትገባ ፣ እንደ ገና ደረጃዎ ቹን ልትወጣና እንደገናም ሌላ መኝታ ቤት ልትገባ ልቧን ደንደን ሐሞቷን ኮስተር ፣ ትጥቋን ጠበቅ አድርጋ ፊቷን መለሰች ።

እየተመለሰች ሳለች ከረሻሙ አዳራሽ ጥግ ቻርለስ ቢመጣ አየ ችው ።እሱም አያትና በጥድፊያ ወደሷ መጣ ። ፀጉሩ ተመሰቃቅሏል ፣ ፊቱም ከመረበሽ ብዛት ሣምባ መስሏል ።

@OLDBOOKSPDF

"ምን እንደተፈጠመ ሰማሽ"ግና አጠገቧ ሳይደርስ በጩኽት ጠየቃት ።"ሰምተሻል ፣ ፖል ዊልሰን ነው ከጆንስቦሮ ድረስ ወሬ ውን ይዞ የመጣው!"በጣም እየቀረባት ሲመጣ ወሬውን አቋረጠ። እሷ ትኩር ብላ ከመመልከት በቀር ቃል አትመልስለትም ።

"ሊንከን በበኃ ፈቃድ የሚመለመሉ ወታደሮችን እየሰበሰበ ነው አሉ — ሰባ አምስት ሺህ ወታደሮች!"

ደሞ የዚህ የሊንከን ወሬ መጣባት! እንደው ወንዶች ሲባሉ ዋናውን የሚከነክን ጉዳይ ትተው አርቲ ቡርቲ ነገር ማውራት ነው እንዴ ሥራቸው?ይሄ እዚህ ፊቷ የተገተረ ጅላንፎ ደሞ ሊንከን በዚህ ገባ ፣ በዚህ ወጣ እያለ እየዘላበደ ፣ እሷ እንዲህ ልቧ በቆሰለ በት ፣ መልኳም ስሚ ዘንዶፈበት ሰዓት ስለሊንከን እንድትጨነቅ ይፈልጋል ።

ቻርለስ ትኩር ብሎ አያት ። ፊቷ አመድ መስሏል ።ጠባብ ፀይ ኖቿ ብቻ እንደ እንቁ ያበራሉ ።ማንም ሴት ፊት ሳይ እንዲህ ያለ የሚንቀለቀል የሲያ እሳት ።ማንም በይኖች ውስጥም እንዲህ ያለ እንደ ሮኾት የሚረጭ ወላፈን አይቶ አያውቅም ።

"እኔኮ ገልቱ ነኝ" አለ ። "በጥምና ልነግርሽ ይገባ ነበር ።ሴት ልጅ እንዴት ስለ እንደሆነች ዝንባሎዋ ።ስላስቀየምኩሽ ይቅርታ አርጊልኝ ።ስሜትሽን በጣም ጐዳሁሽ ፣ውሸ በብርጭቆ ሳምጣልሽ ?"

"አይ — አያስፈልገኝም" አሰኙና አቅል የለሽ ፈገግታ ሰጠኾው ። ከንዴን ያዘና "ነይ እዚያ ኤማዳሚ ሳይ እንቀመጥ"አሳት ።

ራሷን በመነቅነቅ መስማማቷን ገለፀች ።በጥንቃቄ እጅዋን ይዞ ደረጃውን አወረዳትና በሳሩ ማህል አድርጦ በፊት ለፊት በኩል ካሉት ዋርካዎች ሁሉ በጣም ትልቁ ዋርካ ሥር ወዳለው የብረት አግዳሚ ወንበር ሄዱ ።ሴቶች እንዴት ስስና ተሰባሪ ነገሮች ናቸው ጃል ፣ ግና ጦርነትና ጭካኔ ስሙ ስለተነሳ ብቻ ነብስና ሥጋቸው ይላቀቃል ፣ ብሎ አሰበ ። ይሄ ሐሳብ ወንድነቱን አጉልቶ አሳየውና ወንበሩ ላይ ሲያስቀምጣት ከድሮው በእጥፍ ኮርቶ በጨዋነት ተቀመጠ ።በጣም ተለዋውጣለች ።ያም ሆኖ አመድ በነፋበት ፊቷ ውስጥ የሚያየው ቁንጅናዋ ልቡን ሊያስጋልበው ጀምሯል ።ምናልባት የሱ ወደ ጦር ሜዳ መሄድ አስከፍቷት ይሆን እንዴ ?የለም ፣ ይሄ ይሆናል ማለ ትስ የለበጣ ይመስላል ።ታዲያ ምንድነው እንዲህ በእንግዳ አስተያ የት እንድታየው ያደረጋት ?እጅጉስ መሀረቧን ሲይዙ ምን እንዲህ ያንቀጠቅጣቸዋል ፣ ሻኧ ሳይቀር ይርገበገብ የለ እንዴ ?እንዲህ ያለ መርገብገብ ያጋጠመው ስለጭቅር ባነበባቸው መጽሐፍት ውስጥ ነው

@OLDBOOKSPDF

— ወንዶችን አታሎ በፍትር ለመያዝ የሴቶች ዓይኖች ሲቅበዘበዙ የሚታይባቸው ዓይነት እርግብግብታ ።

ቻርለስ ሶስት ጊዜ ለመናገር ጉሮሮውን ከጣራ በኋላ ሶስት ጊዜም የፈለገውን መናገር ሳይሳካለት ቀረ ።ወይዋዜዋ እንደሚዋጉ ሁሉ በጣም ትክ ብሎው ስለሚያዩት ቀና ብሎ በሙሉ ዐይኑ ሊያያት አልቻለም ።ስለዚህ መሬት መሬት ያያል ።

እስካርሌት አንድ አዲስ ዕድና ሐሳብ በአእምሮዋ አያብላላች በችኮላ የሚከተለውን አሰበች፡—"ብዙ ብር አለው ።ወላጆችና ዘመዶች ስለሌሉት ከአማች ጭቅጭቅ እድናለሁ ።ከዚህ ከወሬኛ ሀገብርቅ አትላንታ መኖሩም በጣም ጥሩ ነው ።ስለዚህ አሁኑኑ ባገባው— ያ አሽሊይ ኩም ይላል ።እስካሁን ከሱ ጋር ያደረግሁትም ሁሉ ፤ እንደው ለጨዋታና ለመዝናኛ እንደሆነና በትፈፀመውም ነገር ምንም እንዳልተሰማኝ በደምብ ይገባዋል ።ያቺን ሐረንም መሽመጧን እቆርጣታለሁ ። ከቻርለስ ወዲያም ምንም ዓይነት ወዳጅ ስለማታገኝ ያገር መሳቂያ መሳለቂያ ትሆናለች ። ሚላኒም ብትሆን ቻርለስ ወንድሟ በመሆኑ ፣ከልፀደም ስለምትወደው አንጀቷ ድብን ይላል ።ስቱዋርትና ብሬንትም ቢሆኑ በቅናት መታበሳቸው አይቀርም....'' ።ስቱዋርትና ብሬንትን እንኳ ለምን ልትጨቃቸው እንዳሰበች አታውቅም ።ክሮክክ አሠቃቀቷው በስተቀር እንስ ምንም ክፉ ነገር አልፈፀመባትም ። "ታዲያ አይ ቻርለስን ካገባሁ በኋላ የራሴ ቤት ኖሮኝ ፣ ጥሩ ጥሩ ልብሶች ሰብሼና ምርጥ ሠረገላ ላይ ተቀምጬ ወደዚህ ተመልሼ ልገበያቸው ስመጣ ሁሉም ቅስማቸው እንክትክት ይላል ።ያኔ እንዳቸውም አፋቸውን ሊከፍቱብኝ ፣ እንዳቸውም ሊስ ቁብኝ በፍፁም አይችሉም —በፍፁም!''

"በእርግጥ ፣ውጊያው መካሄዱ አይቀርም ማለት ነው''አለ ቻርለስ ፣ ከብዙ ያልተሳኩ ሙከራዎች በኋላ ።"ግን አይዞሽ አትፍሪ እስከርሌት ፣ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ድምጥማጣቸውን አጥፍተን ጠርጎ ኩን እንጨርሳለን! አሪ እያሉ ጭራቸውን ቁልፈው ባይፈረጥጡ ምን አለ በደኅ! ሠራዊቱ ጀንስቦሮ ላይ መግኖንት ስለሚኖርበት ፣ የዚፈው ምቹት የሰንስ ድግስ ያሸን ያህል የሚቀቅ አይመስለኝም ።የታርሌተን መኑትያ ወንድማማችትም ወሬውን ለመናገር ሄደዋል ። መቼም ሴዮቹ እንደኤት እንደሚያዝኑ ይታየኛል ።''

"ወይዬ ጉዴ '' አለች እስካርሌት ፣ የተሻለ ነገር አየጠበቀች ግን ከዚህ በኋላ ምንም ወሬ ሳትፈልግ ።

ቀስ በቀስ ራሷን እየገዛች ፣ ቀስ በቀስ እየቀዘቀዘችና እንም

@OLDBOOKSPDF

ሮሞንም እየሰበሰበች መጣች። በመላ ስሚቷ ላይ ጨዛና ጭጋግ እን ጸረፈበት ሁሉ መንፈሷ ተረጋጋና ዘና አለች። እንደገና ሕይወት መዝ ራት ፡ እንደገና መንቀሳቀስ አሰኛት። ይሆን የደስደስ ያለው ሽማዬ ልጅ ብታገባው ምናለበትና እንደማንም እንደምታውቀው ወንድ ጥሩ ልጅ ነው። ድሆስ ለምንስ ቢሆን ሣድ አሳት አንዴ አሏ ። በጭ ራሽ። ከአንግዲህ ለምን ዘጠና ዓመት አትኖርም ፣ ሁለተኛ ለምንም ነገር አትጨነቅም።

"እኔ እምልሽ ፡ ከሞድ ሐምኑተን የደቡብ ካሮላይና ሽሊቃ ወር ጋር ልሂድ ፡ መደስ ከአትላንታ ኬላ ጠባቂዎች ጋር ልሰለፍ ፡ መወ ስን አትኖኖል እኮ ?"

"ጠቸ ጉድ! " አለች አንደገና ። በይኖቻቸው መንጎድ ላይ ተግናኙ ። እታላየቹ የወደን ሽፋልጅ እንደተስመደው ጉድ ሠሩት —ቦና ደፋ አለና አንድያውን አነሠልለው ጣሉት ።

"ገስክርስት ፡ ተጠበቂኖልሽ መቹም ያንኪዎቹን ድራሻቸ ውን አጥፍተን እስክንመለስ ከጠበቅሽኝ ግኑት እንደገባሁ አቆጥረ ሞለሁ!" ለጥያቂው መልስ የምትሣንራቸውን ታሳት በመጠበቅ ላይ ሳለ ፡ ከንፈሮቿ ከፍርና ዝር ወደላይ መልስ ቸልበስ ብለው ስፊ ገማታ ማነጣበጣቸውንና ማበሳምጀታቸውን ፡ እንዲሁም እጉን ጮጂ ላይ ያጠለትን ነሳ ፡ ለመጀመሪያ ጊዜ አስተዋለና ፡ —እነ ዚህን መሰም ምን ማለት እንደሆነ አስዘ— ደህና አድርጎ ምራ ቹን ሞጠ። እጅሞ በላብ እንደራሰ ንጅ ውስዋ ይላወሳል።

"አይ ፡ ለመጠበቅስ አልፈልግም" አለችና ዐይኖቿዋን ከደነች።

አጅዋን በሞብልው ውስዋ እንደያዘ አፉን ክፍቶ ቁረ። በማንባ ሪ አየች።ውና— ምን ያለው እንቁራሪት ነው በሞቱ— ብላ አሰበች። በተደጋጋሚ አፉን ይከፍታል ፡ ደሞ መልሶ ታል ሳይጠጣው ይዘጋ ሞል። ፊቱ ቀሳ።

"ለመሆኑ ታሪቅሪኖስሽ?"

ምንም ሳይናገር ዝም ብሎ ያያት ጀመር። አንድ አዲስ የድንጋጤና የመሽበር መንፈስ ተጭጮታል። ምናልባት ወንድ ልጅ ሲት እንዴህ ያስ ጥያቂ መጠየት አይገባውም ይሆናል። ሲት ልጅም ለእንዴህ ያለው ጥያቂ መልስ መስጠቷ የጨዋ ደምብ አይሆን ይሆናል። ቻርለስ ከዚህ ቀደም የዚህ ዓይነት ነገር አጋጥሞት ስለ ማያውቅና ልምዱ ስለሌለው አውን ምን ማድረግ እንደሚገባው ጠፍቶታል። ዘገሽ ዘገሽ አለው። ሊዘናንላትና ሊስማትም ከጅሎት ነበር።

@OLDBOOKSPDF

ሚዳ ሚዳውን እየሮጠ ፡ ላገኘው ሰው ሁሉ— ጥቁርም ሆነ ነጭ— እንዳፈቀረችው ሊነግርም ፈለገ ። እንደው የሚያደርገው ቅጡ ጠፍ ቶታል ። ብቻ ደግነቱ እጅዋ እጁ ውስጥ መኖሩ ። እጅዋን በኃይል ጭምቅ ከማድረጉም የተነሳ ቀለበቷ ቆዳዋን ዘልቆ ሥጋዋ ውስጥ ሊገባ ምንም አልቀረው ።

"በቅርቡ ታገቢኝ የለ ፡ እስካርሌት ?"

"ህእ" አለች ፡ በጣቶቹ የቀሚሷን እጥፋት እየነካካች ።

"እንደውም የኛን ሠርግና የሜላ . . . ."

"አይ!" አለች በችኮላ ፡ ዐይኖቿን እንዳንድ ነገር አጉረጥርጣ ። ቻርለስ ሁለተኛ ስሙት እንደሠራ ታወቀው ። እርግጥ ነው ፡ ሴት ልጅ የገዛ ራሷ የሆነ ሠርግ ትፈልጋለች እንጂ ወግ ማረግን እንደ ጸበ ቁርሳ መከፈል አትሻም ። እነዚህን እየደጋገመ የሚሠራቸውን ስህተቶች እያየች እንዳላየች ማለፏ መቼም ደግነቷን ነው የሚያሳይ ። አዩ ፡ ምነው ጊዜው ጨለምለም ያለ በሆነና ጭለማው ድጉረት ሰጥቶት እጅጅን እየሳመ ለማለት የሚፈልገውን ሁሉ እንድ ሳያስቀር በዘረገፈላት !

"ታዲያ ላባትሽ መቼ ነሽማሴ ልላክ?"

"ቶሎ ብትልክ ይሻላል" አለች ፡ ቶሎ መልስ ከሰጠች እየተ ጫነ ጣቷን ሊቆርጥ የያረሰውን ጨመታውን እሷ ተው ከማለቷ በፊት ያቋርጣል ብላ ተሰፋ አርጋ ።

ከተቀመጠበት ተስፈንጥሮ ተነሳ ። ለጥቂት ደቂቃ ፡ ክብር ካል ገታው በስተቀር ማሩን ሁሉ እየረጋገጠ ጥሎዋት የሚሮጥ መስ ሏት ነበር ። ንፁሕና የዋህ ልቡን ዐይኖቹ ላይ አንጠልጥሎ ፍንድቅ ድቅ ብሎ ዐይን ዐይኗን ያያታል ። መቼም በሀይወቷ ፡ ማንም ወንድ እንደዚህ ያለ የሌለ የማየት ኃይሉን እላይዋ ላይ ሲጨርስ አይታ አታውቅም ። ወደፊትም ሊያጋጥማት አይችልም ። ያም ሆኖ ራሷን ከሱ አርቃ ዝም ብላ ስታስተውለው ጥፋ ይመስላታል ።

"አሁኑኑ ሄጄ አባትሽን እፈልጋቸዋለሁ" አለ ፡ በፊቱ ሙሉ እየሳቀ ። "ይቅርታ አድርጊልኝ ውዲት— በጭራሽ ልታገስ አል ችልም ። "ስሷ ያለው የመውደድ ስሜት እየጠነከረ በመምጣቱ አንዴ የነገራትን ነገር ደግሞ ይነግራታል ።

"እሺ ። "አለች ። " በቃ እዚሁ እጠብቅሀለሁ ። ስጣም ቅዝቅዝ ያለና ነፋሻ ነው"

@OLDBOOKSPDF

ሚዳውን አቋርጦ በቤቱ ጆርባ ሲዞር ለዐይን ተሰወረ ። ከንፋስ ጋር ከሚጫወተው ዋርካ ሥር ብቻዋን ቁጭ ብላ ቀረች ። ከፈረ ሶቹ ማሠሪያ ቦታ በርካታ ሰዎች በፈረስ በፈረስ ሆነው እየተመሙ ነው ኤግሮ ለሊሌዎቻቸውም ከኋላ በፍጥነት እየጋለቡ ይከተሏቸ ዋል ። የሙንሮ ቤተሰብ ልጆች ባርኔጣቸውን እያውለበለቡ አለፉ ። ፎንቴኖችና ካልቨርቶችም እዋናው ጐዳና ገብተው እየጮሁ ይጋ ልባሉ ። አራቱ የታርሌተን ልጆች የግቢውን ሚዳ እያቋረጡ በአ ጠባቢ ሲያልፉ ብሬንት፡-"እማማ ፈረሶቹን ትሰጠናለች አኮ !አሂሂ!" አለና አምባረቀ ። ሣሩ ሁሉ ደፉ ቀና አለ ። ሁሉም ሄዱ ። እሷ እንደ ገና ብቻዋን ቀረች ።

ያ ነጭ ህንፃ ረዣዥም ምሰሶዎቹን አሰልፎ ከሷ እንዶተ ኳረፈ ሁሉ ራቅ ብሎ ቆሚል ። ከእንግዲህ የሷ ግንዘብ አይሆንም። አሽሌይ ሙሽራው እድርጓት ወደዚህ ከሷ ጋር የመምጣቱ ነገር አከትሚል ። ወይኔ አሽሌይ! ወይኔ አሽሌይ! እግዚሃር ይይልሃ ! ምን አደረግኩኝ ? ምን አጠፋሁኝ? በውስጧ ፣ ከተደራረበው የቆሰለ ክብሯና የቀዘቀዘ ሐሞቷ ካብ ሥር ፣ የሚፍለቀለቅ ስሜት አለ ። አንድ ግና ሊጋ ፣ ግና ወጣት— ከከንቱነቷም ሆነ ሁሉን ለኔ ከሚል ስግብግብነቷ በላይ የሆነ— ትኩስ ስሜት እየተወለደ ነው ። አሽሌይን ታፈቅረዋለች ። እንደምታፈቅረው ደሞ ታውቃ ለች ። ይህንን ፍቅሩን ፣ ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት ቻርለስ በኮረኮ ንቹ መንገድ ቦሮ ካዩኗ ሲጠፉ ፣ አስታወሰችው ። እንደዚች እንዳ ሁኋ ቅጽበት ግድ ኖሯት ፣ እንደዚች እንዳሁኋ ቅጽበት ሥራዬ ብላ አስባበት ፣ እንደዚች እንዳሁኋ ቅጽበት ያ ፍቅር በጽኑ ውል ብኋት በጭራሽ አታውቅም ።

@OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ 7

እስካርሌት በሁለት ሳምንቶች ውስጥ ሚስት ሆነች ። ከዚያ በቀጠሉት ሁለት ወራት ውስጥ ደግሞ የሙት ሚስት ሆነች ። በእርግጥ ምንም ሳታስብበትና በጥድፊያ ባለትዳር ብትሆንም ወዲያው ከዚህ ከትዳር ለንሰሰት እፎይ ብላ ሰመጣሳገል ቻለች ። ዳሩ ግን እንዚያን ከትዳር በፊት የነበሩ የመዝናናትና እንደልብ የመጨፈር የምንግዴ ሕይወት መብትና ነፃነቷን ፣ መልሳ ለማግኘት አልቻለችም ። ከሰርጓ ማግስት ቀጥሎ በነበሩት ወራት የባሏ መሞት ሐዘን ተከተለባት ። በልቧ እፎይ አለች እንጂ በሌላ ወገን የከፋት ነገር ተፈጥሯል — የልጅ እናት መሆን ታክለባታል ። ባንድ ጀምበር ሚስት ፣ በሌላ ጀምበር የሙት ሚስት ፡ ደም በሌላ ጀምበር እናት ።

ዓመታት ካለፉ በኋላ እስካርሌት የእነዚያን የ1861 የሚያዝያ ቀናት ከንዝርዝር ውስጥ አመሻሻቸው ለማስታወስ በጭራሽ አትችልም ። ጊዜና ከንሠኖቹ ሁሉ እንደሀልም ፡ እንደቅዠት እየተደራረቡ ያለአንዳች እውንነት ወይም ተጨባጭ ምክንያት ብዥ እንዳለ ፊልም አለፈዋል ። መቼም አስከትሞት ድረስ እንዚያ ቀናት በትዝታዋ መዝገብ ውስጥ ባዶ ገጽ ሆነው ይቀራሉ ። በተለይ ቻርለስ ለጋ ብቻ ሲጠይቃት አቪ ባለችበት ቀንና በሠርጋቸው ቀን ማህል ያለው ትውስታ ጭራሽ ጭልምልም ያለ ነው ። ሁለት ሳምንት ፡ መቼም በሰላሙ ጊዜ አንኳን ጋብቻ ፍጥምጥም የማይደረግበት ጊዜ ነው ። ከፍጥምጥም ወዲያ ደግሞ የአንድ ዓመት ወይም ቢያንስ ቢያንስ የስድስት ወር ሞቅ ያሉ ቀናት ተጠብቆ ነበር ጋብቻ የሚፈጸመው ። ዳሩ ግን ደቡቡ በአሳት በተያያዘበት ጊዜ በመሆኑ ድርጊቶቹ ሁሉ ንፋስ ተሸክሟቸው እንደሚነጉድ ሁሉ በከፍተኛ ፍጥነት ስለ ሚበሩ የጥንቶቹ ቀናት የእርጋታ ጉዞ ውበት ፡ ለዛው መጥፎ ብሎ ጠፍቷል ። ያኔ ፡ ኤለን እጆቿን አጣጥፋ የረጋ ወተት ቅቤ ይወጣዋል እያለች እስካርሌትን በመምከር ፡ ደግማ ደጋግማ ነገሯን ሁሉ እንድታስበበት ሞክራ ነበር ። ሆኖም እስካርሌት የእናቷን ልመና ሁሉ ጆሮ ዳባ ልበስ ብላ ሚዳ አፈሰሰችው ። ማግባቱን አንባች ። ያውም በአንድ አፍታ—በሁለት ሳምንት ውስጥ ።

አሽሌይ ከሠራዊቱ ጋር በተጠራ ጊዜ ለመሄድ እንዲያመቻው የሠርጉን ቀን ከበጋው መጀመሪያ ወደ ግንቦት መግቢያ ሲያዛውረው

@OLDBOOKSPDF

እስክርሌት የሠርጓን ቀን ከሱ ሠርግ በፊት አደረገችው ። ኤለን እምቢ ብላ ነበር ። ነገር ግን ከዋድ ሐምፕተን ሻለቃ ጦር ጋር ወደ ደቡብ ካሮላይና ለመሄድ ቻርለስ በጣም በመጣደፉ ፡ ባዲስ ፍቅሩም ግፊት በመወትወቱ ፡ ፒሬልድም ሁለቱን ወጣቶች በመደገፉ ፤ የተባለው ሠርግ እሷ በፈለገችው ቀን ለመሰረግ በቃ ። ፒሬልድ ፡ አንድም በጦር ኑቱ ትኩሳት ምክንያት ፤ አንድም እስክርሌት ጥሩ አቻ ፡ መልካም አኩያ ለመምረጥ በመቻሏ ፡ ሁደለቅ የሠርጉን መፋጠን ይሁን አለ ። ለዛውስ ጦርነቱ መጣሁ መጣሁ እያለ በሚፎክርበት ሰዓት በሁለት ፍቅረኞች ማህል ጣልቃ ገብቶ — አርጉ አታርጉ የሚለው ፤ እሱ ማን ነውና ነው ? ኤለን ለሱት የደቡብ ሴቶች አንደሚያደርጉት ሁሉ ተሟግታ ተሟግታ በመጨረሻው እጅዋን ሰጠች ። ያ በእርጋታና በትርፍ ጊዜ የመ ዝናኛት ወጣ የተምለው ዓለሚቸው ፤ ግርግር በበዛበት ዝባዝንኬ ሕይወት በመተካቱ ፤ ልመናቸው ፡ በሎታቸውና ምክራቸው ሁሉ ከንቱ ቀርቶ ፤ እንደ ንፍፍ እየጠራረገ ከሚወስዳቸው ጠንካራ ንፋስ ጋር አብረው እንዲነፍሱ ተገደዱ ።

ደቡቡ በጉጉትና በመረጋት ስሜት ተሳክሯል ። መቼም ጦርነቱን በአንድ ወጊያ ክፍተሚ እንደሚያደርሱት ማንም ያወቃል ። በዚህ ምክንያት ኤያንዳንዱ ወጣት በጥድፊያ ሰጦርነቱ ይመዘገባል ። ስለ ዚህም በጥድፊያ ለፍቅረኛው ቀለበት ያስራል ። ቀለበት ያሰረው ደግሞ በእጭር ጊዜ ሠርጉን ይደግሳል ። እንዲህ በቶሎ አቀለጣጥፎ ጋብቻ ወን ውል እያለያዘ ወደ ቨርጂኒያ ሂዶ ያንኪዎችን ድባቅ ለመምታት ልቡ ተነሳስቷል ። በደርዘን የሚቆጠሩ ከጦርነቱ በፊት የሚፈጸሙ የጋብቻ ሥነ ሥርዓቶች ስላሉ ሰው ሁሉ ለመለያየ ለቅሶና ለሐዘን ምንም ጊዜ የለውም ።ሴት ሴቶቹ የኒፎርም ይሰፋሉ ፡ ካልሲዎች ይጠ ልፋሉ ፤ የሚጠቀለሉ ፋሻዎችን ያዘጋጃሉ ። ወንድ ወንዱ የሰልፍ ልም ምጹንና ተኩሱን ጭያዳብታል ። ከአትላንታ በስተሰሜን ወደምትገ ኘው ወደ ቨርጂኒያ የሚሄዱ በሠራዊት የተሞሉ ባቡሮች በጀንስቦሮ አያቋረጡ እንደጉድ ይግተለተሳሉ ። ለሚለቪያው የኒፎርም ለማዘጋ ጀት በተመረጡ ሕዝባዊ ክብንያዎች የተሰፋትን ፤ ደማቅ ቀይ ፣ ውህ ሰማያዊና አረንጓዴ የኒፎርሞች የለበሱ የተለያዩ ክፍሎች በደ ስታ ይታዎማሉ ። አንጸባራቂ ትናንሽ ቡድኖች ደማሞ እዚት የተሰፉ ባርሚጣዎችን እደርገዋለ ። ሴቶቹ ክናካቤው የኒፎርም ያልለበሱም አሉባቸው ። ሁሉም ቢሆኑ በማማሽ ሥልጠናና በማማሽ ትጥቅ የሚ ዓዙ ናቸው ። ነገር ግን በስጂት ተሞልተው ሊፈነዱ ከመድረሳቸው የተነሳ አየሮጡ ወደ ሽርሽር የሚሄዱ ይመስላሉ ። እነዚህን ዘማቾች የሚመለከቱት ገና በዝግጅት ላይ ያሉት ወጣቶች ልምምዱን እንባ ደው ሽርጂኒያ ከመድረሳቸው በፊት ጠርነቱ አልቆ ጉድ እንዳይሆኑ

@OLDBOOKSPDF

ሰማተዋል ። በዚህም ምክንያት ሠራዊቱን ቅሎ የማዘመት ተግባር በጣም በጥድፊያ እየተሠራ ነው ።

በዚህ የወርኃት ዝግጅት ጥድፊያ ማህል የአስካርሌት ሠርግ ድግስ ደግሞ እየተጧጧፈ ነው ። በዚህም ተብሎ በዚያ አሷ ራሷ እንኳ መቼ ተገባያደ ብላ ባላሰበችበት ሰዓት የኤለንን የመ·ሽራ ልብስ ከነ ሽዋሉ ሰብሳ ፡ የአባቷን ከንድ ይዛ ፡ የታራን ደረሽ በከፍተኛ አጀብ ወርዳ በአንግዶች ጢም ብሎ ወደተሞላው አዳራሽ ገባች ። ሁሉ ነገር ካለፈ በኋላ እንደሀልም ሙል ሙል የሚለት — ማድግዳው ላይ የተሰ ቀሉት በመቶ የሚቆጠሩ የሚንቦገቦጉ ሻማዎች ፡ የእናቷ በጥቅር የተ ሞላ ፊትና በመጠኑ ደንገጥ ያለ አኳሃን ፡ እንዲሁም ጋብቻዋ የአብር ሃም የሣራ እንደሆን ስትነግልይላት በዝማታ ይንቀሳቀሱ የንበሩ ከንፈሮቿ ፡ ጂራልድ በቤራንዳና በኩራት ፈቱ በላብ ቸፍ ብሎ ፡ ሴት ልጁ ገንዘ ብም ፡ መልኳም ስምም ፡ ደህና ዘርም ያገባች መሆኗ ሲያስፈነድቀው ፡ አሽሌይ ደግሞ ከደረጃዎቹ ግርጌ ከንዱን ከሚሰኔ ከንድ ጋር እንዳ ቆሳሰፈ ቆሞ ፡ የሚታየው ትርዒት ነው ። በአሽሌይ ፊት ላይ የሚነበበ ውን ሁኔታ ስታይ የሚዘነጋው ሀሳብ መጣባት — "ይሄ እውን ሲሆን አይችልም ። ሲሆን አይችልም ። ቅዠት ነው ። ሕልም ነው ። አሁን ባላ ስበው ይሻላል እንጂ በዚህ ሁሉ ሰው ፊት ጨቧቱን እሰቀዋለሁ ። አሁን በጭራሽ ለማሰብ አልችልም ። ሌላ ጊዜ ፡ ልቋቋመው በምችል ጊዜ አስ ብበታለሁ ። ሌላ ጊዜ ፡ ፀጉሯን ለማየት በማልችልበት ጊዜ አስብበ ታለሁ ።"

ፈገግ ባሉትና በተሰተሰቡት እንግዶች ማህል ማለፉም ቢሆን ሕልም የመሰለ ነገር ነው ። የቻርለስ ሣምባ የመሰለ ፊትና የሚንቀ ጠቀጥ ድምጽ ፡ የሷም ቀዝቃዛና ግራ የተጋባ መልክ ይታያታል ። በመጨረሻ እንኳን ደስ ያለሽ የመባሏ ፡ የመሳሚ ፡ የጥበስ ግብግቦውና ጸንሱ ሁሉ እንደሕልም ያለፈ ነገር ነበር ። አሽሌይ ጉንጯን ሲስማት የተሰማት ስሜት ፡ የሚላት "አሁን በእርግጥ እውነተኛ እህትማማችች ሆንን" የሚል ለስላሳ ድምጽ—ይሄ ሁሉ እውን ያልሆነ ቅዠት ነበር ። የቻርለስን አክስት ወይዘሮ ፒቲፓት ሐሚልተንን ከመቀመጫ ቸው ያስነሳቸው የስሜት ማንፋሰት እንኳን ሳይቀር ፡ የስመመን መነ ፈስ እንደዋጠው ባዶ ሕልም ነው የሚታያት ።

ሊነጋጋ ሲል ጸንሱም ግብግቦውም ሲገባደድ ፡ ታራንና የምስሌ ውን ቤት እጨናንቀውት የንበሩት ከአትላንታ የመጡት እንግዶች ፡ በየአልጋው ፡ በየሶፋውና በየምንጣፉ ላይ ሲተኙ ፡ የጐረቤቶቹም ሰዎች ሁሉ በሚቀጥለው ቀን በ"አሥራ ሁለቱ ሞርካዎች" መናፈሻ ቦታ ለሚደረገው ሠርግ ለመዘጋጀት ወደየቤታቸው ሲሄዱና አካባ

@OLDBOOKSPDF

ቢው ሁሉ እርጭ ሲል ፥ ያ ሁሉ እንደሕልም እንደ ቅዠት የታየ ነገር ከገሀዱ ዓለም ጋር ተጋፈጠና እንደመኪና መስታወት እንክትክቱ ወጥቶ ዱቄት ሆነ ። ገሀዱ ዓለም ፥ ፊቱ በደስታ ጥም የመሰለውን የቻርለስን ዘመልበሻ ከፍታ መውጣት አላያት ። ገሀዱ ዓለም አንገቷ ድረስ አንሰላውን ስላ የሚይዙም መልኳን ስታሳየው እንኳ ከምንም ሳይቆጥራት በደስታ የሚፈነድቀውን ቻርለስን አላያት ።

አስካርሌት ባልና ሚስት በአንድ አልጋ ውስጥ እንደሚያድሩ በደንብ ታውቃለች ። ነገር ግን እስከዚህም ከጓደኛ ፅሩ አስባበት አታውቅም ። ከእናቷና ከአባቷ አንጻር ስታየው ነገሩ ትክክል ነው ። በራሷ ላይ ደርሶ ስታየው ግን በጭራሽ አልዋጥ አላት ።አሁን ሰመጀመሪያ ጊዜ ከዛ ክ"አሥራ ሁለቱ ዋርካዎች" ግብግ በኋላ በራሷ ላይ ምን ዓይነት መዘዝ እንዳመጣች ተገነዘበች ። ለራሷ በችኮላ የሚይዞን ውሳኔ በመወሰኗ የህይት ምጥ በሚያሰቃያትና አሽሌይን ለዘለዓለም የማጣቷ ነገር እንደ እግር እሳት በሚለበልባት ሰዓት ፥ የዚህ ልታግባው ፈጽሞ እቅድ ያልነበራት ልጅ አብሯት እንድ አልጋ ውስጥ ማደር ፥ በጭራሽ ልትሸከመው ከምትችለው በላይ ሆኖባታል ። እሱ እያመነታ ወደ አልጋው ሲጠጋ በኮረነን ድምጽዋ እንሾካሾከችለት ።

"እንዲኽ ብለህ ብትጠጋኝ እፊ ብፎ ነው የምጮኸው ፥ ላንቃዬ እስከሚሰነጠቅ እጉሮ እደባልቀዋለሁ፥ በል ከጣዜ ጥፋ ፥ ጫፌን ትነካኝና ወየልህ !"

ቻርለስ ሐሚልተን በዚህ ዓይነት የሠርጉ ፅለት ማታ በመኝታ ቤቱ ጥግ ባለ ፥ ባለመደገፊያ መንበር ላይ ጉልበቱን ታቅፎ አደረ ። ይሂን ያህልም አልከፋውም ። ምክንያቱም የመሸራይቱን ትህትናና ልስላሰ ለስተረዳው ወይም የተረዳው ለለመሰለው ነው ። ፍራቻዋ ሁሉ ሚሙቱ እስኪጠፋና እሱን ለመቀበል ዝግጁ እስከትሆን ድረስ ለመጠበቅ ፈቃደኛ ሆነ ። ብቻ ... ብቻ እየተገላበጠ ፥ ለመመቻቸት እየ ሞከረ በጣም በቅርቡ ወደ ጦርነት እንደሚሄድ አሰበና እንዴ በሀ ይል ተነፈሰ ።

የአስካርሌት ሠርግ እንደሕልም እንደቅዠት እንዳለፈ ሁሉ የአ ሽሌይ ደግሞ ክፅ በባሰ የሕልም ጭጋግ ውስጥ እንደተሸፈነ አለፈ ። አስካርሌት በ"አሥራ ሁለቱ ዋርካዎች" መናፈሻ አልፍኝ ፥ ውሀ አረንጓ ዴውን "የሠርግ ማግስት ተሚፅን" እንደለበሰች ከትላንት ማታ ጀምሮ እየበሩ ባሉት በሙቶ በሚቆጠሩ ሻማዎች ማህል ቆማ ፥ የሜ ላኔ ሐሚልተን ትንሽ ፊት የወበትን ፀዳል ስቶንናፀፍ ተመለከተች ። ወ/ት ሜላኒ ሐሚልተን ወ/ሮ ሜላኒ ዊከስ በምትሆንባት በዚ ህች ቅፅበት ፊቷ ላይ የሚበራው ቁንጅና እጅግ አስደንጋጭ ነው ።

@OLDBOOKSPDF

እንግዲህ እሽሉይ ለእንዲም ለሁለም መሂዱ ነው ። ከሞብጧ ተፈል ቅቆ ወጥቶ ማምለጡ ነው ። የፅው እሽሉይ ። እዩ ምኑን የፅው ሆነው አሁንማ የሰው እሽሉይ ሆኗል ። ሰመሆኑ የሰ ሆኖ ያውቃል እንጂ ፣ አስካርሌት በሞንትሳቲ ውስጥ መጓት ንገሮች እየተርመሰመሰ የም ታስብ የምታለመውን ሁሉ አሳጧት ። ሞንትሳቲም ስማሰብ ከሚኝ ለው በላይ ሃሳብ ስለበዛበት ደክመው ። ተረባበሸ ። እሽሉይ አፈቅር ሻለሁ ሲሳት አልነበረም እንጂ ፣ ታዲያ ምን ሰያያችው ፣ ይሄን ለማለ ታወስ ብትችል በጣም ጥሩ ነበር ። ቻርለስን በሚማቲ የመንደሩን ሰዎች ሐሜተኛ ምላስ እንዴታጠፍ ኢድርጋ ፣ አፋትሙን አስዘግታ ነበር ። ዳሩ ያ አሁን ለፅ ምን ረባት ፣ በዚያን ጊዜ በጣም ትልቅ ጉዳይ ነበር ። አሁን ግን ከቸሞር የሚጣፍ ነገር አይደለም ። ያም ቢሆን ለፅ ትልቁና አስፈላጊው ጉዳዩ እሽሉይ ብቻ ነበር ። አሁን እሱም አመለጣት ። እሷም ብትሆን አስሚናገር ብቻ ሳይሆን በጣም ከምት ጠላው ሰው ጋር ተጋብታ አርፋለች ።

አቤት ! የሆነው ነገር ሁሉ እንዴት ይፀፅታል በሉ ! ባደረጉት ነገር ተበሳጭው ፀጉራቸውን ለለሚነጫ ሰዎች ሰምታለች ። ነገር ግን እንደው እንደወሬ ተቀብላ እንደወሬ የተወችው ነገር ነበር ። ዛሬ ግን በእርግጥ ምን ማለት እንደሆነ ገባት ። ከቻርለስ ለመጣላገል ባሳት ኃይ ለኛ ፍለጋትና በደህና ወደታራ ተመልሳ እንጻሳገባች ልጇንረድ ተዝ ናንታና ነፃ ሆና ለመኖር ባሳት ጥኑ ምኞት ኣእምሮዋ እንደተወ ጠረ ፣ የሆነውን ሁሉ ስታስባው ለተሠራው ሥራ ተወታፀ እፀ ራፅ እንደሆነች ታወታት ። ኤለን ተይ ብላ ልታስቆማት ሞክራ ነበር ፣ እሷ ግን በጀ አላለችም ።

በዘህ ሁኔታ አሽሉይ ሠርግ ላይ ማታውን ሙሉ ሬሕፈረች ። ሌሊ ቱን ሙሉ ያነሰች ። ለፅ በሐዘን እንደቆሰለ ማንም ሰው እንጻያውቅ ባት እየሳቀች ፣ የሆነ ያልሆነውን እየዘባረቀች ፣ እማረ መግንዲንም እፅን ያስተኛ ሙሽራ አድርጎው በሚያቅጥት ግብዝ ሰዎች ደደብነት እየ ተገረመች ፣ የምትዝናና መስላ አደረች ። የቅለሚን ስብራትና የልቧን መቁሰል ያየ አንድ ሰው የለም ። ለማየት ብልጣብልቹው እማዜር የተ መሰጣን ይሁን አለች ።

አስካርሌት በሁለተኛው ቀን ማታ ማሚ ለብፅን አመላለቃላት ከጄያች በኋላ መኝታዋ ላይ እንዳለች ፣ ቻርለስ ከሁለተኛውንም ማታ መንበር ላይ ተቀምጠው ላድሮ ነው እንጂ እያለ ግራ ገብቶት ከመል በቸ ክፍል ሲወጣ ፣ ድንገት ፈንዳችና ለቅሶዋን ለቋቀችው ። ቻርለስ አልጋ ላይ ወጥቶ እስከሚያባብላት ድረስ ተንሰቀሰቀች ። ታሷ ሳይመጣ ፣ ወሰጧን አየነጀጀች ፣ ሰውነቷን እያንቀጠቀጠች ፣ እንባዋ እስኪያ

@OLDBOOKSPDF

ልቅ ድረስ እልቅሳ ስታበቃ ፥ እደረቱ ላይ ተደፍታ በቀስታ ትንሰቀሰቅ ጀመር ።

ጦርነቱ ባይኖር ኖሮ ፥ ሁለቱ መኳንንት ለሽርሽር ወደ ሳራቶጋ ወይም ዋይት ሰልፈር ከመሄዳቸው በፊት ፥ ለነሱ ክብር ሲባል በሰማቸው በሚዘጋጁ ግብዣዎችና ዳንሰኞች ለመዝናናት ፥ በመንደሩ ሁሉ እየተዘዋወሩ ደስታቸውን ያሳመልሙ ፥ ሐሴትን ይገበዩ ነበር ። ጦርነቱ ባይኖር ኖሮ ፥ እስካርሌት የሶስተኛ ቀን ፥ የአራተኛ ቀንና የአምስተኛ ቀን የሠርግ ልብሷን ለብሳ ፥ ለክብሯ ሲባል በፎንቴን ፥ በክላቨርትና በታርሌተን ቤተሰብ በሚዘጋጀው የዳንስ ግብዣ ላይ ትገኝ ነበር ። አሁን ግን የዳንስ ግብዣም ሆነ የሠርግ ማግስት ሽርሽር የለም ። ሠርጋቸው ባለፈ በሁለተኛው ሳምንቱ ቻርለስ ከአሜኤል ዋድ ሐምፕተን ሻለቃ ጦር ተቀላቅሎ ወደ ጦር ሜዳ ሄደ ። እሱ በሄደ በሁለት ሳምንቱ ደግሞ አሽሌይና ሥራዊቱ ሄዱ ። መንደሩ እና ቀረ — ወንድ ልጆቹን ተራ ቆጥ ።

ቻርለስ ከሄደ በኋላ በነበሩት ሁለት ሳምንቶች ውስጥ እስካርሌት አንድም ቀን አሽሌይን ብቻውን አይታው አታውቅም ። ሌላው ቀርቶ በመጨረሻው መሪር የመለያያ ቀን እንኳን ፥ መደበቋቻ የሚሄደው ባቡር ላይ ለመሳፈር ታራ ቆም ብሎ በተሰናበት ጊዜ ፥ ለብቻዋ ልታናግረው አልቻሉችም ። ሜላኒ የወጉር ጌጧን አድርጋና ሻሏን ትከሻዋ ላይ አጣፍታ በአዲስ መሸራ ክብርና ወግ ማረግ እንደደመቀች ከንዱ ላይ ተንጠልጥላበታለች ። አሽሌይን ወደ ጦር ሜዳ ለመሸኘት ጥቁር ከነጭ ላይል ድፍን ታራ ነቅሎ ወጥቷል ።

ሜላኒ "አሽሌይ ፥ እስካርሌትን ላማት እንጂ ፥ አሁን እኮ እህትማማች ሆነናል" አለች ። አሽሌይም ፥ የፊቱ ደም እንደተመጠጠ ሁሉ ግር ጥት እንዳለና በውጥረት እንደተያዘ ሁሉ ጭንቅ እያለው ፥ በቀዝቃዛ ከንፈር የእስካርሌትን ጉንጭ ዳሰስ አደረገው ። እስካርሌት ይህን ድር ጊት በሜላኒ ማሳሰቢያ እንደተፈጸመ አድርጋ ስላሰበች ፥ ከመሳሙ ቅንጣት ደስታ አላገኘችም ። ይልቅስ ልቧ ድንዝዝ ብሎ እንደበደን ነው የቆመችው ። ሜላኒ ለመሰናበቻ እስካርሌትን እቅፍ አደረገቻትና ፦

"እትላንታ መዋቀሽ እኔንና አክስቱን ፒቲፓትን ትጠይቂን የለ ? የኔ ቆንጆ ፥ እዚያ እንድትመለሺ በጣም እንፈልጋለን ። የቻርሊን ሚስት በጣም እንድንሳሀባት እንፈልጋለን ። እሺ የኔ እናት ?"

አምስት ሳምንቶች አለፉ ። በነዚህ አምስት ሳምንቶች ውስጥ በር ከት ያሉ የቻርለስ ደብዳቤዎች ደረሷት ። ቻርለስ ከደቡብ ካሮላይና በጻፈላት ደብዳቤዎች ውስጥ ለሷ ያለውን ፍቅር ፥ ወደፊት ጦርነቱ

@OLDBOOKSPDF

ሲያልቅ ምን ማድረግ እንደሚፈልግ ፡ ለሷ ሲል ጀግና ስመሆኑና በጀ
ብድ የተሞላ ታሪክ እንዴኖረው ከፍተኛ ምኞት እንዳለውና የመር
አዛዡ ዋድ ሐምፕተን ላይ ያለውን ታላቅ እምነት ይገልጽላታል ።
በሰባተኛው ሳምንት ከራሱ ከአሎኤል ሐምፕተን ቴሌግራም ደረ
ሳት ። አብሮም እንድ በታላቅ ትህትና የተጻፈ የመርዶና የማስተዛዘኛ
ደብዳቤ መጣላት ። ቻርለስ ሞተ ። ኩስኔሉ ፡ ቻርለስ ከመሞቱ በፊት
ለደውልላት ፈልጎ ነበር ። ነገር ግን ቻርለስ ቤተሰቡ እንዳይጨነቅና
እንዳያረበሽ በማሰብ ከዛፊ ነገ በሽታው ይለቀኛል ፡ ከዛፊ ነገ
ቀለል ይልልኛል በማለት እንዳይደውል አደረገው ። ይሄ ያልታደለ
ልጅ የሷን ልብ በጥቂር የረታ መስሎት መታለሉ ብቻ ሳይሆን ፡
በመር ሚዳም ከብርና ገናን እንዲሁም ለመ ጥርነትን አግኝቶሁ ብሎ
ተስፋ በማድረጉ ጭምር ተታሏል ። እንኳን ከብርና ገናን ሊገ-ና
በጭ ፡ እንኳን ለመጥር ጀግና ሊሆን ፡ የምኪዎቹን ዓይን እንኳ ሳያይ ፡
በደቡብ ካሮላይናው የመር ሠፈሩ ውስጥ እንዳለ በኩሩኝ የጀመረው
የብርድ በሽታ በጣም ባጭር ጊዜ ውስጥ ሕማድር ጥጪው ።

መቼም ሳይደግስ አይጣላም ፡ በጥቂት ጊዜ ውስጥ የቻርለስ ወንድ
ኋጅ ተወለደ ።በእነሩ ልማድ መሠረት በመር ሚዳ የሞተ ሰው ልጅ
በመሩ አዛዥ ስም ስለሚጠራ የቻርለስ ልጅ ዋድ ሐምፕተን ሐሚልተን
ተባለ ። እሰካርሴት አርኮብ መሆኗን ያወቀች እለት በተስፋ መቁረጥ
ስቅስቅ ብላ አልቅሳ ፡ ምነው ሞቼ ባረፍኩት ብላ ነበር ። ሆኖም ማሚ
ሴዎች የበለጠም ችግር ይደርስባቸዋል ፡ እያለች እያዕናናቻት ብዙም
ሳትቆገር ሁሉንም ችላ ዘጠኙን መር በሆዷ ተሸከማ ወለደች ። ምንም
እንኳ ሰው ባያውቅባትም ሰልጁ ያሳት ፍቅር በጣም ትንሽ ነው ።
ከቻርለስ ልጅ እንዲኖራትም ሆነ ያረገዘችው ልጅ እንዲወለድ ፈቃዷ
አልነበረም ። ስለሆነም ከተወለደ በኋላ የራሷ አልመስል አላት ። ያብ
ራኳ ክፋይ የሥጋ የደሟ ቅጂ መሆኑ በጭራሽ አልዋጥልሽ አላት ።

ከአራስ ቤት በአጭር ጊዜ ውስጥ ተገላግላ ሰውነቷ ደህና ይሁን
እንጂ አዕምሮዋ ግን ተመሰቃቅሎባታል ። መንፈሷን ለማደስና እሷን
ለማረጋጋት ያልተደረገ ነገር የለም ። እሷ ግን ያው ናት ። ኤለን ነጋ
ጠባ እየመጣች ትመክራታለች ። ለሷ መጨነቋን እየነገረች እይዘሽ
ትላታለች ። አባቷ ጄራልድም ከተለመደው በእጥፍ ድርብ እየማለ
እየተገዘተ መደራት የተሻለ ሕይወት እንደሚኖራት ያሰረዳታል ። ከጆ
ንስቦሮም ስፍር ቁጥር የሌለው የማይረባ ስጦታ ይዘላት ይመጣል ።
ሽማግሌው ዶክተር ፎንቲን ሳይቀር የሰጣት የሚጠጣ መድሃኒት እን
ዴት የአዕምሮ ሰላም አልሰጣትም ብሎ ነገሩ እንቆቅልሽ ሆኖበታል ።
"እንዲህ እየደጋገመ የሚያማትና የሚረብሻት የቅስም ስብራት ነው ፡
አንድ ልቧን ያቆሰለው ነገር ይኖራል" ብሎ ለኤለን ነግሯት ነበር ።

@OLDBOOKSPDF

እስካርሴት ለመናገር ብትፈልግ ኖሮ ግን የሷ ችግር እንሱ ከሚሉት በጣም የተለየና እጅግ የተወሳሰበ መሆኑን ታስረዳቸው ነበር ። የሷ ሕመም ሕይወትን መስልቸት መሆኑን እልነገረቻቸውም ። የሷ ችግር እናት ለመሆን በሞራሽ አለመፈለግ መሆኑን አላስረዳቻቸውም ። ከሁሉም በላይ ደግሞ የሷ ዋነኛው በሽታ በእሽሌይ አለመኖር ምክንያት የተፈጠረባት ፣ ዓይኑን የማየት ረሀብ ፣ እሱን የማግኘት ጠኔ መሆኑን አልገለጸችላቸውም ።

ሕይወትን የመሰልቸት ነገር በጣም አሳሳቢና በሞራሽ ሊቆም ያለተቻለ ነገር ነው ። ጦርነቱ ወንዱን ሁሉ ይዞት ከሄደ በኋላ በመን ደሩ መዝናናት የሚባል ነገር ቀርቷል ።ኑሮ ጋዝ ጋዝ ብሏል ። ደስ ደስ የሚሉት ወጣቶች በሙሉ ፣ ነፍስ ነፍስ ያሳቸው ሥጫዎች ወጣ ቶች በሙሉ ፣ በጦርነቱ ባቡር ተገዝዋል — አራቱ የታርሌተን ቤተሰብ ልጆች ፣ ሁለቱ የካልቨርት ቤተሰብ ልጆች ፣ የሙንሮ ቤተሰብ ልጆችና ከጆንሰቦሮ ፣ ከፈይትቪልና ከሳቨጆይ የመጡት ቆንጆ ቆንጆ ወን ዶች ሁሉ አንድ ሳይቀሩ የጦርነቱ ንፋስ ወስዷቸዋል ። ሽማግሌ ሽማ ግሌዎቹ ፣ አክሰ ስንኩሎቹና ሴት ሴቶቹ ብቻ ቀሩ ። እንሱም ቢሆኑ ስፈት ሲሰፉ ፣ ጥልፍ ሲጠልፉ ፣ ጥጥና በቆሎ ሲተክሉ ፤ ለሠራዊቱ አሳማ ፣ በግ ፣ ከብት ሲያረቡ የሚኖሩ ደጀኖች ናቸው ። ለንፋሱማ የኮሚ ሳሪያቱን ሠራዊት ከሚመራውና በየወሩ ራሽን ለማምጣት ከሚመላ ለሰው ፣ በእድሜው ገፋ ከረገመ ከሱዊለን ወጻጅ ከፍራንክ ኬኔዲ በስ ተቀር ፣ አንድም ዓይን የሚሞላ ወንድ አይታይም ። አኮሚሳሪያቱ ው ስጥ ያሉትም ወንዶች ቢሆኑ አስከዚህ የሚጥም የለባቸውም ። ፍራን ክ ሲት ላጫወት እያቸ የሚለፋደደው ዓይነት ጨዋታ ደግሞ ፤ በትህ ትና ማናገሩንም እሰክትተው ድረስ የሚያበሳጫት ነገር ነው ። እዚ ያው ከሱዊለን ጋር ይሞሳፈጥ !

አኮሚሳሪያቱ ሠራዊት ውስጥ ያሉት ወንዶች የሚጥሟት አይነት ቢሆኑ እንኳን የሷን ሁኔታ እምብዛም የሚያሻሽሉላት አይሆንም ። የሙት ሚስት ናትና ልቧ ከሟቹ ጋር መቃብር ወርዷል ። እሷ እንኳ ባታምንበት ማንኛውም ሰው የልቧን መቃብር መውረድ ስለሚያምን በዚያው መሠ ረት በባይዋን ማሳመር ይኖርባታል ። ይኼ መቼስ በጣም የሚያናድዳት ነገር ነው ። ምክንያቱም በበኩሏ ስለቻርለስ ትዝ የሚላት ፤ እሺ እገ ባሀለሁ ያለችው ለትእፊቱ ላይ ያየችው የሚሞት በማ የመሰለ ጅላጅል መልክ ብቻ ነው ። እሱም ቢሆን ከእእምሮዋ መዝገብ እየተፋቀ ነው ። ያም ሆኖ ግን የመጓት ሚስት ናትና ፀባዩዋን ማሳመር አሌ የማትለው የማይቀር ጉዳይ ነው ። ከእንግዲህ ያላገቡ ልጃገረዶችን ደስታና ነፃነት ስትገመግም መኖሯ ነው ። ለፅ የተፈቀደላት ከሰው ፣ ከአገር ተንቀሳ የሐዘን ማቅ ለብሳ መቀመጥ ነው ። አሰን ይሄን ከነገረቻት ቆይታለች ።

@OLDBOOKSPDF

እስካርሌት ከፍራንክ ጋር ከመጣ መቶ አለቃ ጋር ግቢው ውስጥ ባለው አትክልት ቦታ ሆና ስትስቅና ስታስካካ ፥ ስትሳፋና ስትንተት ሳለች ፥ ድንገት ኤለን አገኘቻትና በጣም በመከፋት የሙት ሚስት እንዴት መሆን እንዳለባት መግለጫ ሰጠቻት ። የሙት ሚስት በቀ ሳሉ እሰው አፍ እንደምትገባና ለሀሜት ምቹ መሆኗን ከ እስከ ብላ አስረዳቻት ። የሙት ሚስት ፀባይ ከአዋላጅ የበለጠ በጥንቃቄ የተ ሞላ መሆን አለበት ።

"መቼም እግዚሀር በሚያውቀው እንደ አዋላጅ ከሆነች ሕይወ ቷን በሙሉ ስትጨነቅ የምትኖር ሳቅ ፈገግታን የማታውቅ ሆና ትቅር ማለት ነውና ፥ የሙት ሚስትም ከሟች ባሏ ጋር መቀበር አለ ባት ማለት ምን አማርኛ ነው ?" አለች እስካርሌት በልቧ ፥ የአናቷን ለስላሳ ድምጽ በታባቸሮነት እያዳመጠች ።

የሙት ሚስት ለምልክት እንኳ እንዲት ጠብታ ደማቅ ቀለም የሌለበት ጥቁር ልብስ መልበስ አለባት ። አበባ የለ ፥ የመቀነት ጥብጣብ የለ ፥ ሐበልና ጉትቻ ወይም ማኖቸውም ጌጣጌጥ የለ ፥ ብቻ ከሚቹ ፀጉር ከተሠራ ኖሐበል ኀመድ በስተቀር ምንም ዓይነት ጌጥ በላይዋ ላይ መታየት የለበትም ። የፀጉር ወለባዋን ጭምር ሸፍና የም ታስርበትም ጥቁር ቫሽ ፥ ወደታች እስከ እግር ጥፍሯ ድረስ መውረድ ያለበት ሲሆን ፥ ወደትከሻዋ ከፍ ተደርጎ ሊያዋር የሚችለው ከሶስት ዓመት ሐዘን በኋላ ነው ። ፈክ ብላ መሳትም ሆነ ድምጿን ከፍ አድ ርጋ መናገር በጭራሽ አይፈቀድላትም ። ፈገግ ስትል እንኳ ሐዘኗን በማያስረሳ ሁኔታ መሆን አለበት ። ከሁሉም በላይ አሰቃቂውና አስፈ ሪው ሕግ ደግሞ በምንም ዓይነት ወንዶችን ቀና ብሎ ማየትና ፍላጎ ትን ማሳየት ፈጽሞ የተከለከለ መሆኑ ነው ። ወንዱ ለሷ ፍላጎት ቢያ ድርበትና ስሜቱን ቢገልጽላት ፥ ሚች ባሏን በመጥቀስ ምን ያህል የተ ከበረች ሴት መሆኗን በጨዋ ደንብ አስረድታ ልታቀዘቅዘው ይገ ባል ። አሃ ፥ አንዳንድ የሙት ሚስቶች እኮ አርጅተው ሊሞቱ አንድ ሀሙስ ሲቀራቸው ሁለተኛ ባል ያገባሉ ። የጐረቤቱን ምላስና ዓይን ግን እንዴት እንደሚችሉት እግዚሀር ይወቅ ፥ አለች አስካርሌት በልቧ ። እንዲህ የሚያደርጉ መቼም ሰፊ አርሻና በደርዘን የሚቆጠሩ ልጆች ያላቸው ተስፋ የቆረጡ አሮጊቶች መሆን አለባቸው ።

ማማባት ሠጥፎ ነው ። አማቡኩ የሙት ሚስት መሆን ግን የሞት ሞት ነው ! ቻርለስ ልጅ ስለወለደላትና ትንሹን ዋድ ሐምፕተንን ስለተካላት ትልቅ ደስታ ሲሰማት እንደሚገባ የሚነግሯት ሰዎች ምን ደነቦች ናቸው ! እሁን አብራው ልትኖር የምትችል ፥ እሱን የማሳ ደግን ፀጋ የተጐናፀፈችለት ልጅ መኖሩ ትልቅ ነገር ነው የሚሉ ምን

@OLDBOOKSPDF

ዓይነት ደደቦች ናቸው ! ሁሉ ሰው እንዲህ ያለ የጭቅር ማቧተሻ ከየት ይገኛል እያለ ያዳንቃል ። እሷም መቼም እፍ አውሃ ደንቆሮዎች ናችሁ አትላቸው ነገር — አፉን ይዛ ቁጭ ትላለች ። አልገባቸውም እንጂ በሕልሟም በወሯም የማታስበው ነገር ቢኖር ይሄ አውን እነሱ እጹብ ድንቅ የሚሉትን ነገር ነው ። ለዋይ ያሳት ፍቅር በጣም ትንሽ ነው ። እንዳንዴማ ከነአካቴው ልጅዋ መሆኑንም ማሰብ ያቅታታል ።

በየንጋቱ ከእንቅልፏ ስትነሳ ለጥቂት ጊዜ የዱሮውን የጥንቷን የጠዋቷን አስካርሴት አግራ ትሆናለች ። ወዘይዋም እንደወትሮዋ ከእስካርሴት መስኮት ሙሉ ባሉት የማግኖሊያ ዛፎች ላይ ታበራለች ። ወፎችም እንደወትሮዋቸው ይዘምራሉ ። የተለመደው ጣፋጭ የአባማ ጥበስም ቡታው እየተሰረተ ወደአፍንጫዬ ይጣላል ። እሷም እንደጥንቷ ግዴለሽ ፡ እንደድሮዋ ሐሳብ የለሽ ወጣት ሆናለች ። ወዲያው የፈራና የደነገጠ ሕሣን ሰቅሶ ሰማች ። ይሄ ድምጽ አስካርሴት ላይ የሚፈጥር ባት አንድ ሀሳብ አለ፡—"እዚህ ቤት ሕሣን ባይኖር ኖሮ ምን ነበረ በት !" ትንሽ ቆይታ የራሷ ልጅ መሆኑን አስታወሰች ። መቼም በጣም የሚያስደነግጥ ነገር ነው ።

አሽሌይ! ዉ. . . ! ከሁሉም በላይ ደግሞ አሽሌይ ። በሕይወቷ ለመ ጀመሪያ ጊዜ ታራን ጠላቻት ። ከጦራራው ግርጌ ወጸለው ወንዝ እየተ ጠማዘዘ የሚሄደውን ረጅም ቀይ መንገድ ለመጀመሪያ ጊዜ ጠላ ችው ። ለምሰም እረንጓዴ የጥጥ ተክል የበቅለባቸውን ቀይ እርሻዎች ለመጀመሪያ ጊዜ ጠላቻቸው ። እያንዳንዱ ሜዳ ፡ እያንዳንዱ ዛፍና ቁጥ ቋጠ ፡ እያንዳንዱ የከብትና የእሣር መንገድ ሁሉ የሚያስታውሳት አሽ ሌይን ነው ። እሱ የሌላ ሴት ባል ሆኗል ። ለዛውም ወደ ጦርነት ሄዷል ። ነገር ግን ምስሉ አውንም በነዚያ መንገዶች ወደአመሻሹ ላይ እየመጣ መንፈሷን ያስጨንቃታል ። በነዚያ ግራጫ ዓይኖቹ ፈገግ እያለ በበረን ዳው ጥላ ላይ ሆኖ ያያታል ። ለአንዲት ቅፅበት ሳታስብ የማታልፈው ከወደ "አሥራ ሁለቱ ዋርካዎች" የሚመጣ የፈረስ ኮቴ በዚያ የወንዝ ዳር መንገድ ላይ ይታየታል ፡ ይሰማታል ። አሽሌይ !

አስካርሴት የ"አሥራ ሁለቱን ዋርካዎች" መናፈሻ ቦታ አንድ ጊዜ ትወደው ነበር ። አውን ግን በጣም ጠላችው ። ትጥላው እንጂ ልቧ ወደ ዚያ መሄዱ አልቀረም ። ጆን ዊክስና ሌሎቹ ሴቶች ስለ አሽሌይ ሲያወ ሩና ከቨርጂኒያ የላከውን ደብዳቤ ሲያነቡ ይሰማታል ። እሷን ይገዳ ታል ። ሆኖም እንድታዳምጣቸው ትገደዳለች ። ግትሯንና ሞገዛዋን ኢን ዲያን አትወዳትም ። ጅሏን ሐረንም እንደዚያው ትጠላታለች ። እነሱም ከራዋ ይጠሏታል ። ያም ሆኖ ከነሱ ተንኖላ ለመኖር አልቻለችም ። ታዲያ ሁል ጊዜ ወደ "አሥራ ሁለቱ ዋርካዎች" መናፈሻ ሄዳ ቤቷ ስት

@OLDBOOKSPDF

መለስ አልጋዋ ላይ እንዴ ከተጋደመች ሰአራት ስትጠራ ሁሉ አልፈ
ልግም ብላ ትተኛለች ።

አለንና ማሚን ከሁሉም ነገር በላይ ያስጨነቃቸው ይሄ ምግብ አልበላም ማለቷ ነው ። ማሚ ፣ አሰክርሴት ዛሬ የሙት ሚስት ናት ፣ ደሰ እንዳሳት መብላት አለባት ፣ እያለች በጣም ጣፋጭና የሚያስገ መኝ ምግብ ታቀርብላታለች ። እሷ ግን ምንም ዓይነት የምግብ ፍላ ጐት የላትም ። ዶክተር ሮንቴን እንዳንዴ ቅለማቸው የተስበረና ተስፋ የቆረጡ ሴቶች በጣም ይጐዱና አስክ ሞትም የሚደርሱበት ጊዜ አለ ብሎ ለአለን ሲነግራት አለን በድንጋጤ ፊቷ ኖራ መሰለ ። ይሄን ዓይነት ስጋት በራሷም ልብ ውስጥ የነበረ በመሆኑ አመደ ቡን አለ ።

"ዶክተር እንደው ምንም ለማድረግ አይቻልም ማለት ነው ?"
"አካባቢ መለወጥና ሌላ ቦታ ፣ ሌላ ትርጓት ፣ ሌላ መንገድ ማየት መቻል ብቻ ነው መፍትሔው" አለ ዶክተሩ ከብሽተኛዋ ለመ ገላገል ሲል ።

አስክርሴት ያለፍላጐቷ ልጅዋን ይዛ መጀመሪያ ያባቷን ወገኖች አሣራዎችንና የአናቷን ወገኖች ሮቢላንዶችን ልትጠይቅ ወደ ላቫና ሄደች ። ቀጥሎም የኤለንን እህቶች አክስቶቿን እማማ አላሊንና ፓሊ ንን ልትጠይቅ ወደ ቻርልስተን ሄደች ። ሆኖም ኤለን ከጠበቀችው ጊዜ ቀድማ ከአንድ ወር በፊት ሰምን እንደተመለሰች እንኳ ሳትና ገር ወደ ታራ ተመለሰች ። ሳቫና በጣም ጥሩ ጊዜ አሳልፉ ነበር ። ነገር ግን አጐቶቿ ጀምስና አንድሪው እንዲሁም የአጐት ሚስቶች በጣም ያረጁ በመሆናቸው ለአስክርሴት ምንም ሰሚት የማይሰጣ ትን የዴሮ ትዝታቸውን ማውራት ብቻ ነው ሥራቸው ። አልጣሚ ትም ። ሮቢላንዶችም ዘንድ ያው ነው ። ቻርልስተንማ በጣም አስቀያሚ ነበር ብላ አሰበች — በልቧ ።

አክሰቷ ፖሊንና ከሳቸው ትንሽ አርጀት የሚሉት በዕድሜ ምክ ንያት አልፎ አልፎ ነገር የሚሰቱትና በመጠኑ ተጫዋች የሆኑት ባለቤ ታቸው የሚኖሩት በወንዙ ዳርቻ ባለ በአንድ የእርሻ ቦታ ነው ። የነሱ እርሻ ከከተማው በጣም የራቀ በመሆኑ ከታራ የባሰ ብቸኝ ነት የሚሰማበት ቦታ ነው ። በጣም ቅርብ የሚባለው ጐረቤታቸው ከነሱ ሃያ ማይል ርቆ ነው የሚኖረው ። ያውም በጥድና በዋርካ ጥቅ ጥቅ ያለ ረግረግና ጭልም ያለ ጫካ አቋርጠ ተሄዶ ነው ። አስክር ሴት እንዚያን እንደሸበት ያሉ አፅሞት በላያቸው የለበሱ የዋርክ ዛፎች ስታይ ጂራልድ ይነግራት የነበሩ የአየርላንድ ጣረ ሞቶችና መናፍ ስት በግራጫ ጭጋግ ውስጥ የሚሮጡባቸው ታሪኮች ይመጡባታል ። ምንም የምትሠራው ሥራ የላትም ። ያው ቀን ቀን ጥልፍ ይጠልፋሉ

@OLDBOOKSPDF

ማታ ማታ ደግሞ ከሁልወር ሳይቀን ጽሑፎች ውስጥ አንዱን እጮት ኬሪ ያነብላታል ።

አማማ አላሊ በአንድ ትልቅ የአትክልት ቦታ ውስጥ በሚገኝ ቪላ ቤት የሚኖሩ ሲሆን ምንም የሚያስደስት ጨዋታ የላቸውም ።አስካ ርሌት በጣም ሰፊና የተጠቀለለ ምንጣፍ የሚመስሉ ቀያይ ኮረብታ ዎች ባሉበት አገር ያደገች በመሆኗ ይህ ጠባብ አካባቢ አስር ቤት መሰላት ። ከአማማ ፖሊን ቤት ይልቅ እዚህ የተሻለ ማዘበራዊ አኗ ኗር አለ ። አስካርሌት ግን ሰምቼን አልወደደቻቸውም ። ሁልጊዜ ካለባ ህልና ካለቢተሰብ ጉዳይ ወፈም የላቸው ። ኤለን የሮቢላንድ ዘር ታላቅ ሆኖ ሳለ በደም በአጥንቱ ዝቅ ያለውን መጤ የአየርላንድ ተወላጅ ማግ ባቷን በመገረም ይናገራሉ ። ስለዚህም በአባቷ በኩል የማን ልጅ እን ደሆነች በልባቸው እያሰቡ እንደሚያመሠግት ይገባታል ። አክስቷ አማማ አላሊም ከጀርባዋ በሷ ማንነት ሰምቹ እንዳያገኙ ማፅናናታቸው ይሰ ማታል ። ይሄ በጣም አናዷታል ። አሷ እንደሆነች ካባቷ በስተቀር ስለ ቤተሰብ ጉብ የላትም። ከሮሌው አየርላንዳዊ ሚንቅላቱ በስተቀር ምንም ወዳጅ ሳይኖረው ፣ ይሄን ሁሉ ሀብት ፣ ይሄን ሁሉ ባሪያ ፣ ይሄን ሁሉ እርሻና ሰፊ ቦታ ለቤተሰብ ይወየ ብርቅ ሰው በመሆኑ ቅኮራበታለች ።

ሌላው እንዚህ ቻርልስተኖዊያን የሚኩራሩብት ነገር ደግሞ የፎ ርት ሰምተር ጉዳይ ነው ፤ ኧረ የሰማያቱ ያለህ ! ለመሆኑ እነሱ የመጀ መሪያዋን ዋይት ተክሰው ጦርነቱን ሳይቀሰትሱ ኖሮ ሌላ የነሱ ቢጤ ጅል መተኩሱ እንደማይቀር አያውቁም እንዴ ፤በዛ ላይ እስካር ሌት የደጋማውን ጀርሚያ ፈጣንና ታይለኛ እንዲሁም ፊደላትን ረገጥ አድርጌ የመናገር ስልት ለምዳ እዚህ ቆላማው ጀርሚያ ውስጥ ያለው ዝማና ዝቅ ያለውና ፊደላትን ሳይረግጡ የመናገር ስልት አልዋጥ ልሽ ብሏታል ። ከእንግዴህ እንደዚህ ያለ የእንጋገር ስልት ብትሰማ እሪ ብላ ትጮሀለች ። በጣም ከመናደዷ የተነሳ እንዲያውም እንድ ጊዜ አክስቷ እስኪበሳጩ ድረስ በማሾፍ እንደጀራልድ ስትናገር ነበር ። ከዚህ ሁሉ በኋላ ወደ ታራ ተመለሰች ። ምናባቱ ፣ በቻርልስተና ዊያን የአነጋገር ስልት ከምትቆስል እዚያው ታራ ገብታ በእሽሌይ ትዝታ ብትቆስል ይሻላታል ።

ኤለን ኮንፌደሬሲውን ለመርዳት የታራን ምሮት በእጥፉ ለማሳደግ ሌት ተቀን እየሰራች ሳለች ትልቋ ልጅዋ አስካርሌት ከስት ብላ እጥ ንቷ ወጥቶ ገርጥታና ምላሷ ሾሎ ከቻርልስተን በመመለሷ በጣም ደነገጠች ። የችሰም ስብራትን ነገር እራሷም ስለምታውቀው የአስካር ሌትን ሞንቀት ለማታለል ፣ እያንኮራፋ ከሚተኛው ከጀራልድ ጉን ተጋ ድማ በየማታው ስታስብ ፣ ስታወጣና ስታወርድ ነበር ። የቻርለስ አክ

@OLDBOOKSPDF

ስት ወይዘሮ ፒቲፓት ፡ እስካርሌት አትላንታ መጥታ ረዘም ላለ ጊዜ እንድትቀመጥ በተደጋጋሚ ደብዳቤ እየፃፉ ይጨቀጭቁ ነበር ። አሁን ኤለን ለመጀመሪያ ጊዜ ይሄንን ጉዳይ ከልቧ አሰበችበት ።

ወይዘሮ ፒቲፓትና ሜላኒ ለብቻቸው አንድ ትልቅ ቤት ውስጥ ይኖራሉ ። የቢሉሳባቸውን ሁኔታ በደብዳቤያቸው ሲጽፉ "ቻርሊዬ በመሄዱ ምክንያት አሁን በቤቱ ማንም ወንድ የለም ። እርግጥ ወንድሚ ሔንሪ አለ ። ነገር ግን ሁልጊዜ ከእኛ ጋር አይኖርም ። መቼም ስለሔንሪ እስካርሌት ሳትንግርሽ አልቀረችም ። ስለሱ ብዙ ነገር በወረቀት ላይ ማተት የጨዋ ተግባር አይደለምና ትቼዋለሁ ። እስካርሌት ወደእኛ ብትመጣ እኔና ሜሊ በጣም ደስተኞች እንሆናለን ። ከሁለት ይልቅ ሶስት ብቸኛ ሴቶች የተሻሉ ናቸው ። በዚያ ላይ እስካርሌት እንደሚለኔ ሆስፒታል ውስጥ ያሉትን ጀግኖች ልጆቻችንን ብትረዳ ምናልባት ለሀዘኗም መጽናኛ ይሆናት ይሆናል ።... ደሞም እኔና ሜሊ አዲስ የተወለደውን ሕፃን ለማየት በጣም ቸኩለናል..."

እንግዲህ እስካርሌት ሻንጣና የሀዘን ልብሷ ተዘጋጅላትና ዋድ ሐምፕተንንና ሞግዚቱን ፕሪሲን ይዛ ፡ የማሚንና የኤለንን ምክር በጭንቅላቷ ፡ ጄራልድ የሰጣትን በኮንፌዴሬሲው የተመነዘረ ብር በቦርሳዋ አድርጋ ወደ አትላንታ ተጓዘች ።ወደአትላንታ መሄዷን እንኳ ከልብ የምትፈልገው ነገር አልነበረም ።ወይዘሮ ፒቲፓትን የምታያቸው ከአሮጊቶች ሁሉ በጣም ገልቱ አድርጋ በመሆኑና ከአሽሌይ ሚስት ጋር በአንድ ጣራ ሥር መኖር ደግሞ በጣም አስቀያሚ ነገር በመሆኑ ጉዳዩ የማይሆን ነው ። ነገር ግን ያንን መንደር ከነክፉ ትዝታው ፡ ከነአሰቃቂ ትውስታው የሚያስረሳትን ማናቸውንም ዓይነት ለውጥ ትፈልግ ስለነበር ወደ አትላንታ መሄድን አሜን ብላ ተቀበለች ።

@OLDBOOKSPDF

ክፍል ሠላሳ

ምዕራፍ ፰

በ1862 ግንቦት ወር ማለዳው ላይ አስካርሌትን የያዘው ባቡር ወደ ሰሜን እየገሰገሰ ነው ። አስካርሌት ፣ መቼም ቻርልስተንና ሳቫና እንዳሰለቿት ሁሉ አትላንታ እንደማትሰለቻት እርግጠኛ ናት ።ምንም እንኳ ወይዘሮ ፒቲፓትንና ሜላኒን ብትጠላቸው ፣ ከጦርነቱ በፊት ከረምት ላይ የጐበኘቻት አትላንታ አሁን ምን ያህል ተሰውጣ እንደ ቁየቻት የማየት ጉጉት አሸንፏታል ።

ከማንኛውም ከተማ ይልቅ አትላንታን ትወዳታለች ። ጂራልድ "አትላንታና አንቺ እደሚያችሁ አንድ ነው"እያለ ይንገራት ስለነ በር ፣ለአትላንታ ያላት ፍቅር ለብቻ ነው ።አርግጥ እያደገች ስትሄድ ጂራልድ ስለአትላንታ የነገራት በመጠኑ የተጋነነ ነገር ሆኖ አግኝታ ዋለች ።ጂራልድ አንዳንድ ታሪክ ሲያወራ ለታሪኩ ማጣፈጫ ትንሽ ቅመም ያስፈልገዋል ብሎ ሲያምን አጣፍሞ ማቅረብ ልማዱ ነው ። ያም ሆነ ይህ አትላንታ ከሷ ዕድሜ በዘጠኝ ዓመት ትበልጣለች ። ይህም ቢሆን ከሌሎች ከተሞች ጋር በትወዳደር አሁንም ገና በጣም ወጣት ከተማ ናት ።ቻርልስተንና ሳቫና የዕድሜ ባለፀጐች ናቸው ። ሳቫና ሁለተኛ ምዕተ ዓመቱን ይዟል ። ቻርልስተን ደግሞ ሶስተኛውን ይዟል ። በሷ ወጣት ዓይን እነዚህ ከተሞች ፣ ፊታቸውን በማራገቢያ እያናፈሱ ፀሐይ የሚሞቁ የጃጁ አሮጊቶች ይመስሏታል ። አትላንታ ግን አብሮ አደግ እኩያዋና የሷው የትውልድ ባልንጀራ ናት ። እንደሷው በወጣት ግልፍተኝነት የተሞላች ፣ እንደሷው ማትርና እኔ ያልኩት ይሁን ባይ ከተማ ናት ።

ጂራልድ የነገራት ታሪክ የተመሠረተው እሷና አትላንታ ስም የወጣላቸው በአንድ ዓመት ውስጥ እመሆኑ ላይ ነው ። አስካርሌት ከመወለዷ በፊት በነበሩት ዘጠኝ ዓመታት ውስጥ የከተማይቱ ስም መጀመሪያ ተርሚነስ በኋላ ደግሞ ማርታስቪል ይባል ነበር ።አስካርሌት ስትወለድ ከተማይቱም አትላንታ የሚባል አዲስ ስም ወጣላት ።

ጂራልድ በመጀመሪያ ወደሰሜን ጆርጂያ ሲመጣ አትላንታ የም ትባል ከተማ ከነአካቴውም አልነበረች ። ይቺን ከተማ የሚመስል

@OLDBOOKSPDF

ትንሽ መንደር እንኳ አይታይም ነበር ። ጥሬ ጫካና ድንግል መሬት ብቻ ነበር ዙሪያ ገባውን ያጥለቀለቀው ።ከዚያ በተከተለው ዓመት በ1836 ግን በመንግሥት ትዕዛዝ በቅርቡ የቼረኪ ጉጣ በያዘው ግዛት ውስጥ ወደ ሰሜን ምዕራብ የሚሄድ የባቡር ሐዲድ ተዘረጋ። የሐዲዱ መድረሻ በግልፅና በማያሻማ ታወቀ ። ተንሲና ምዕራቡ አገር ነው ።መነሻው ግን እስከዚህም አልታወቀም ። ጆርጂያ ውስጥ በትክክል ከየት ቦታ እንደሚነሳ ሳይወሰን ለአንድ ዓመት ቆየ ። ከዓመት በኋላ አንድ መሀንዲስ በቀዩ የሸክላ አፈር ላይ የክልል እንጨቱን ተክሎ የባቡሩን መስመር የደቡብ ክልል የጥንቷን ተርሚነስ የዛሬዋን አትላንታ አደረገው ።

እሰሜን ጆርጂያ ውስጥ አንድም የባቡር ሐዲድ አልነበረም ። ሌላም ቦታ ቢሆን ያሉት በጣም ጥቂቶች ናቸው ።ጂራልድ ሌለንን ከማጣቱ በፊት በነበሩት ዓመቶች ውስጥ ግን ከታራ በስተሰሜን ሃያ አምስት ማይል ርቀት ላይ ያለው ትንሹ የሠፈራ መንደር ቀስ በቀስ ወደ ትልቅ መንደር አደገና አውራ ጐዳናዎቹን ወደሰሜን ማስረዘምጀመረ ። የባቡር ሐዲድ ዘመን የጀመረው እንግዲህ ከዚህ ጀምሮ ነው ።ከአሮጌው ከተማ ከአውነሰታ ተንስቶ በአትላንታ አቋርጦ ወደ ተንሲ ከሚወስደው አዲስ መንገድ ጋር የሚገናኝ ሁለተኛ የባቡር መስመርም ወደ ምዕራብ ተዘረጋ ።ከሌላው የጥንት ከተማ ከሳቫና ተንስቶ የጆርጅያን ልብ ማሀል ለማሀል ሰንጥቆ በመጀመሪያ ወደማክን ከዚያም ወደ ሰሜን በጂራልድ የጥንት መንደር አቋርጦ ከሌሎቹ ከሁለቱ መንገዶች ጋር አትላንታ ላይ የሚገናኝ ሶስተኛ የባቡር መንገድም ተዘረጋ ። ቃዲያውም ሳቫናን ባለ ትልቅ አውራጐዳና አደረጋት ። የሁሉም መገናኛ ከሆነችው ከወጣቲ አትላንታ አምባርት የሚነሳና በደቡብ ምዕራብ በኩል ወደ ሞንትጐመሪና ሞባይል የሚሄድ አራተኛ የባቡር ሐዲድ ተዘረጋ ።

ከባቡር ሐዲድ ጋር የተወለደችው አትላንታ የባቡር ሐዲዶቹ ባደጉ ቁጥር አያደገች ሄደች ።የአራቱ የባቡር መንገዶች ሥራ ሲጠና ቀቅ አትላንታ ከደቡቡ ፣ ከምዕራቡ ፣ ከሰር አገሩ ። በአውነሰታ በኩል ደግሞ ከሰሜኑና ከምስራቁ ጋር ትገናኝ ጀመር ። የሰሜንና የደቡብ ፣ የምስራቅና የምዕራብ መተላለፊያ መንገዶች ሁሉ መገናኛ አትላንታ በመሆኗ ትንሿ መንደር በመናኸሪያነቷ የሞቱ ህይወት አገኘች ። ማደግ መመንደግ ጀመረች ።

ከእስካርሌት የአሥራ ሰባት ዓመት ዕድሜ ትንሽ ከፍ ባለ ጊዜ ውስጥ ፣ አትላንታ ከአንድ የባቡር ሀዲድ ከልል ችካል ተነስታ በሸ ሀና በአሥር ሺ የሚቆጠሩ ችካሎች የቆመባት ፣ አገሮች በመሉ ዓይ

@OLDBOOKSPDF

ናቸውን የጣሉባት የሞቀች የደመቀች ፡ድል ያለች ከተማ ሆነች ። የቆዩትና የጥንቶቹ በአዝጋሚ እርምጃ የሚጓዙ ከተሞች ይቺን አዲስ ከተማ ጫጩት እንደፈሰፈሰች ዶሮ በቅናት ኩፍ ብለው ያዩዋታል ። ይቺ ቦታ ከሌሎቹ የጀርጂያ ከተሞች የምትለየው በምንድነው ? እን ዲህ በፍጥነት ያደገችውስ ለምንድነው ? ደሞኮ ይኼ ነው የሚባል ስሟን የሚያስጠራ ነገር የላትም ይላሉ በልባቸው ። ያው የባቡር ሀዲዶችና ጥቂት የኮልበት ሠራተኛ ሰዎች ብቻ ናቸው ያሏት ።

በከተማይቱ የሠፈሩት ሰዎች በተከታታይ ተርሚነስን ፡ ማርታስ ቪልንና አትላንታን ያዩ ሲሆኑ ሁሉም ጠንካራ ፡ሁሉም ሠራተኛ ሰዎች ናቸው ።የባቡር ሐዲዶችን እምብርቷ ላይ ወደምታስተላስረው ወደዚች ከተማ በጣም ሩቅ ከሆኑ አገሮችና ከጀርጅያ ጥንታዊ ከተ ሞች ድረስ የሚመጡ በርካታ አረፍት የለሽና ኃይለኛ ሰዎች አሉ ። በጉጉትና በከፍተኛ ፍላጐት ተሞልተው የመጡ ናቸው ።መጋዘኖቻ ቸውን በነዳጅ ማከማቻው ጣቢያ ዙሪያ በሚገናኙት አምስቱ ቀያይ የጭቃ መንገዶች አትራቢያ ይሠራሉ ። ቤታቸውን በዋይት ሆልና በዋሽ ንግተን መንገድ አካባቢ እንዲሁም የጠፍር ነጠላ ጫማ ያረጉ ቁጥር የለሽ የሀንድ ትውልዶች በአማር እየሄዱ ባቀኑት ፒችትሪ ትሬይል በሚባለው ከፍ ያለ ቦታ ዳር ዳር ሠርተዋል ።በዚያ ቦታ ይኮራሉ ። በዚያ ቦታ ዕድገት ይኮራሉ ።ያንን ቦታ ለማሳደግ የነሱን ጥረት በመ ፈለግ ይኮራሉ ። አሮጌዎቹ ከተሞች አትላንታን ያሻቸውን ይበሏት ። አትላንታ ደንታዋ አይደለም ።

የሳቫና የአውጉስታና የማከን ከተሞች አትላንታን የጠሉበት ሰበብ ለእስካርሌት ዳግም አትላንታን መወዳጀ ፡አትላንታን ማቀፊያ ምክንያት ሆናታል ።ልክ እንደሷ ይቺ የአትላንታ ከተማ የተገነባ ችው ጀርጂያ ውስጥ ባለ አዲስና አሮጌ ቅይጥ ባህል ነው ።በራሱ ፈቃድ የተፈጠረውና ከኃይለኛው አዲስ ልማድ ጋር ፍልሚያ የገጠ መው አሮገው ልማድም ቢሆን በሁለተኛ ደረጃ የሚመረጥ እንጂ የሚናቅ አይደለም ።ሴላው ቢቀር መቼም ከራሷ ጋር ከተወለደች ወይም ቢያንስ ከራሷ ጋር ስም ከወጣላት ከተማ ጋር እንደ እህትማ ማቾች የመተያየት ነገምድና የመፍጠርና የግንኙነት ስሜትን ማዳበር ያለ ነው ።

የትላንትናው ማታ በዝናብ ብስብስ የሚያደርግ ኃይለኛ ምሽት ነበር ።እስካርሌት አትላንታ ስትገባ ግን ሞቃቷ ፀሐይ ፣ በቀይ ጭቃ ላይ የሞሉትን ወንዞች እየከበቡ የሚጠማዘሉትን እርጥብ መንገዶች ለማድረቅ በቆራጥነት ትታገል ነበር ።በነዳጅ ማከማቻው አካባቢ ያለውን ባዶ ቦታ በተከታታይ እንደሸማኔ መወርወሪያ የሚመላለ

@OLDBOOKSPDF

ሱት ተሽከርካሪዎች ይሞሉታል ።መኪናዎችና ሌሎች ተሽከርካሪ ዎች ሲገቡና ሲወጡ ያን መንገድ ትርምስምሱን ያወጡታል ። በጭ ራሽ የሚይቆሙ የጦር መኪናዎችና አምቡላንሶች ከባቡር የሚወርዱ ቁስለኞችን ሲቀበሉ ፣ አስፈላጊ ቁሳቁሶችን ሲጭኑና ሲያወርዱ ፣ ጭቃ ውንና ግራ መጋባቱን የባሰ ያበዙታል ።

ጋጽከሁማው ሲገቡና ሲወጡ ያለ ትርምስ የሹፌሮቹ ዛቻና መሀላ ፣ የበቅሎዎች መራኮትና በረሸሙ የሚረጨው የጭቃ መዓት ሰጉድ ነው ።

አስካርሌት ከባቡር መውረጃው የመጨረሻ ደረጃ ላይ ቆማለች ። ጥቁር የሀዘን ቀሚሷን ለብሳ ከሞላ ጐደል ተረክዟ ድረስ የወረደ የቁር ሹሯን ደርባ ሁይ ሆንጆ ልጅነቷን እያሳየች አካባቢውን ትጣ ኮራለች ። ነጠላ ጫማዎቿን ጭቃ እንዳይነካባት በመውረድና ባለ መውረድ መሀል እያመነታች እንደድር ከተተበተበት ጋሪዎች ፣ መረ ኃላዎችና መኪናዎች ግህል ወ/ሮ ፒቲፓትን በዓይኑዋ ትፈልጋ ለች ። እኒያ ሰምባ ፊት ድቡልቡል አሮጊት ዘራቸውም የለ ። አስካርሌት ጉጉ ዓይኖችዋን እዚህም እዚያም ስትወረውር አንድ ያረጀ ኤግሮ ፣ ቆርጫጫ ፀጉሩን እንደሽንብራ በራሱ ላይ ዘርቶ በኩራት እየተጐማለለ ባርሜጣውን በእጁ ይዞ በጭቃው ግህል ወደሷ መጣ ።

“ወይዘሮ አስካርሌት እንቺ ነሽ፣ ፒተር እላላለሁ ።የእሜቴ ፒቲ ፓት የሠረገላ ሹፌር ነኝ ።እዚህ ጭቃ ውስጥ እንዳትወድቂ ።” አለ እንደትዕዛዝ ባለ መኮሳተር ።አስካርሌት ቀሚስዋን በእጅዋ ሰብስባ ይዛ ልትዘል ስትዘጋጅ ።“እንቺም እንደ እሜቴ ፒቲ እግርሽን እንደ ልጅ ውሃ ሲነካሽ ትወጀለሽ እንዴ ። እረ ቆይ ልሸከምሽ ።”

ምንም እንኳ ቀጭንና በዕድሜው የጎላም ቢሆን አስካርሌትን ያለችግር አንከበከባት ።በባቡሩ ወለል ላይ ፕሪሲ ህጻን ታቅፋ እያ ትና ቆም ብሎ “እንዚያ ያንቺ ልጅና ሞግዚቱ ናቸው እንዴ ።የዎር ለስን ልጅ ለመያዝ በጣም ታንሳልኾ!ህ! ብዎ ስለሱ ወደፊት እንነጋ ገራለን ።እንቺ ልጅ ፣በይ ተከተይኝ ።ልጁን እንዳትጥይው ደግሞ ጠን ቀቅ በይ ።”

አስካርሌት ወደሰረገላው በፒተር እቅፍ ተይዛ መሄዱን ያለፈ ቃዱ ተቀበለች ። በዛ ላይ እጐት ፒተር ፕሪሲንና እሷን ሲተች ሁሉ ዝም ብላ ተቀበለችው ።ፕሪሲ ደምበር ጉተር እያለችና ቁና ቁና እየቮ ነፈሰች ጭቃውን ጨቅ ጨቅ እያደረገች ተከትላቸው በጭቃው ግህል ሲሄዱ ፣ ቻርለስ ስለእጐት ፒተር የተናገረው አስካርሌትን ትዝ አሳት

@OLDBOOKSPDF

ጫባቱ ጋር ያኖ በሁሉም የሚከሲኮ ዘመቻዎች ተካፍሏል ። አሳቱ ሲቆስል ቁስሉን አክሞለታል —እንዲያውም ህይወቱን ያዳነው እሱ ነበር ።እባችና አጥታችን በልጅነታችን ስለሞቱ እኔንና ሜላኒን ታቅርና እንኮኮ ብሎ ያሳደገን እሱ ነው ። አክስታችን ፒቲፓት ከወንድሟ ከአጐት ሐንሪ ጋር ትንሽ መታታር የፈጠረችውም ያን ሰሞን ስለነበር እኛ ዘንድ መጥታ ፣ እኛን እየተንከባከበች ማሳደግ ጀመረች ። ምንም ረዳት የሰላትና እንደቆንጆ ምስኪን ልጅ የምታሳዝነ ነብስ ናት ። እናም አጐት ፒተር ያዘንላት ነበር ። ህይወቷን ለማዳን ምን ማድረግ እንደምትችል አታውቅም ። ስለዚህም ፒተር ምን ማድረግ እንደሚገባት አስቦ ሰጪ ይወስንላት ነበር ። አስራ አምስት ዓመት ሲሞላኝ የኪስ ገንዘቤ ከፍ እንዲል የወሰነልኝ እሱ ነው ። አጐት ሐንሪ ከዩኒቨርሲቲ ዴግሪህን መውሰድ አለብህ ሲል እሱ ግን ለከፍተኛ ትምህርት ወደ ሐርቫርድ መሄድ አለብህ ብሎ ሽንጡን ገትሮ የተከራከረ ነበር ። ሚስ በደንብ አድጋለች ብሎ ሲያምን ፀጉሯን እንድትሠራና ወደጸንስ ፓርቲም እንድትሄድ የወሰነም እሱ ነው ። ለወይዘሮ ፒቲ ብርጅ ነው እትሙጫ — ባሬ ውርጭ ነው ሻልሽን አድርጊ ..የሚሉትም እሱው ነበር ። . . በህይወቱ ካሞከሯቸው ጥቂቶች ሁሉ በጣም ማሩም በውኃ ለቤተሰቡ የሚያልፍ እሱ ብቻ ነው ። የሱ ዋና ችግር ሰዓታችንንም እንዲራቡ ልጆች በሥጋም በነብስም የራሱ አድርጐ ማየቱ ነው ። ጆሞ በደንብ ያቅፃል ።"

ፒተር ሠሪጣሰው ሳይ ወጥቶ አለንጋውን ሲይዝ ቻርለስ ያለው ነገር ተረጋገጠ ።

"እማቱ ፒቲ አንቺን ለመተበል ባለመምጣታቸው ከፍቷቸዋል ። አንቺ የማትረዚያቸው መስፈቻቸው ሰማተዋል ። እኔ ግን እሳቸውና ወ/ሮ ሚሲ አዲሱን ቀሚሳቸውን ጭታ በጭታ ከሚያደርጉ ሳንቺ የቀሩ በትን ምክንያት ባስረዳ ይሻላል ብዬ እኔው ብቻዬን መጣሁ ። ወ/ሮ አስኳርሰት ፣ ልጇን ተቀብለሽ አንቺ ብትይዥው ይሻላል ።እላ ደቺ ሰቋሳ ባሪያ ትጥለዋለች ።"

አስኳርሰት ወደ ጥሪሲ አየችና በኃይል ተነፈሰች ። ፕሪሲ ብቁ ናት የምትባል ምግዚት አይደለችም ። አጭር ጥብቆ የምትለብስ ቀጫጫ ባሪያ የነበረችና በትርቡ ወደ ሻርዴ ቀሚስ ዕድገት ያገኘች መሆኗ ራሱ ስንት ያጨቃጨቀ ጉዳይ ነበር ።ግና ብዙ ሳትኖር ፣ ግና የታራን ህይወት በመርዱም በቁመቱም ሳታይ ፡ይህን የዕድገት ደረጃ ያገኘችው የኾግር ጊዜ በመሆኑ ነው ።ሶድሚ ለመርነቱ ከሚሰሪያቱ ከታራ የሚፈለጉት ነገር በመብዛቱ ምክንያት ኤለን ማሚንም ሆነ

@OLDBOOKSPDF

ጴልሲን—ኧረ ሮሣ ወዲያም ይሉኛል ዓይኖቿ ሕሳልፉ አልሰጥም በማለቷ ፕሪሲ ያለተቀናቃኝ የእስካርሌትን ልጅ አቅፋ ፡ እስካርሌትን አጅባ ወደ አትላንታ እንድትሄድ በመወሰኑ እግረ መንገዱን አዲሱን ቃሚስ የመልበስን ክብር ተጐናፀፈች ። ፕሪሲ ከ"አስራ ሁለቱ ዋርክዎኝ" ወይም ከታራ የአንድ ማይል ርቀት ያህል እንኳ ርቃ ሄዳ አታውቅም ። ስለዚህም በባቡር መጓዟም ሆነ ወደ ሞግዚትነት ዕድገት ማግኘቷ ትንሽና ጥቁር የራስ ቅሏ ውስዋ ላለው አንጐሏ ከምትችለው በላይ ሆኖበታል ። ከጆንስቦሮ እስከ አትላንታ ያለውን የሃያ ማይል ርቀት ስትጓዝ በጣም ፍንደቅደቅና እርብሽ ከማለቷ የተነሳ እስካርሌት መንገዱን ሁሉ ልጅዋን እንድትይዝ ተገዳ ነበር ።አሁን ከቶማ ከደረሱ በኋላ ደም ትላልቅ ፎቆችንና በርካታ ሰዎችን ስታይ የፕሪሲ መደናበር የትና ደረሰ ። አንዴ ወደ ግራ አንዴ ወደቀኝ ስትዞር ስትቆለመም ፡ አንዴ ወደ ፎቅ አንዴ ወደ ምድር ቤት ስታንጋጥጥና አንገቷን ስትሰብር፡በማታ ስትጠዛም ፡ ስትሽከረከር ህሳቡንም አብራ ቀልብ ስታሳጣው አንገቱን ልትቀጨው በመድረሷ ምስኪኑ ልጅ ምርር ብሎ አለቀሰ ።

እስካርሌት የማሚን መሳጭር የአየንት ከንዶች በጣም ናፈቀቻቸው ። ማሚ ህሣንን ማባበል አያስፈልጋትም ። ማሚ ህሣንን ማዘል ፡ እንኩት ማለት አያሻትም ። ዝም ብላ እጅጅን እላዩ ላይ ጫን ማድረግ ብቻ በቂዋ ነው ። ያኔ ህሣኑ ፀጥ ፡ እርጭ ብሎ ይገኛል ። ዳሩ ምን ያደጋል ማሚ ያለችው ታራ ነው ። እስካርሌት ምን እንደምታደርግ ግራ ገብቷታል ። ተንሸን ዋድን ከፕሪሲ መቀበሏ ምንም ዋጋ የለውም ። እፕሪሲ እጅ ሳለ እንደሚያለቅሰው ሁሉ እሷም እጅ ሲገባ እሪታውን ያስነካዋል ።በዛ ላይ የፀጉር ጌጥ ጥበጣቢን ሞምድድ አድርጐ መያዙና ቀሚሷን ማበስበሱ አይቀርም ። ስለዚህ አንተ ፒተር ልጁን ተቀብላ እንድትይዝ ያቀረበላትን ሀሳብ እንዳልሰማ ዝም አለች ።

"ምንልባት ወደፊት ስለህጻናት በደምብ አውቃለሁ" አለች በሀሳቧ ፡ ብስጭት ብላ ። ሠረገላው በዚያ ነዳጅ ጣቢያውን በከበበው ሬሳ ረጣ መንገድ ሲገሰግስ "ኤጭ ከህጻናት ጋር መጨማለቁን መቼም የምለምደው አይመስለኝም ።" አለች አሁንም በልቧ ፡ የሞድ ፊት በለቅሶ ላምባ ሲመስል አይታ "እኪስሽ ውስጥ ያለውን ደረቅ ጡጦ ስጪው ፕሪሲ ። ዝም የሚልበት ዘዴ ፈልጊ እንጂ ። እንደራበው አውቂያለሁ ።ነገር ግን አሁን ምንም ላደርግለት አልችልም ።"

ፕሪሲ ጠዋት በማማ የተሰጣትን ደረቅ ጡጦ ስትሰጠው ህጻኑ ጋብ አለ ። እስካርሌት ዝምታ ሲሰፍንና አዳዲስ ነገሮችን ማየት ስትጀምር መንፈሷ መነሳሳቱን ፡ የዝግታ ስምምማውን ጀመረ ። አንተ ፒተር

@OLDBOOKSPDF

በመሐረሻ ከጅታው መንገድ ወጥቶ ቁልቁል በጥሻትሪ ጐዳና ሠረ ገላውን ሲያበረው ለወራት ተሰምቷት የማያውቀው የአዲስ ነገር መፈለግ ስሜት ፡ በውስዋ መላወስ ፡ በውስዋ መዘዋወር ጀመረ ። ይቺ ከተማ እንደኔት አድጋለች በሉ ! ባለፈው መጥታ ካየቻት እኮ ገና አንድ ዓመት መሠኑ ነው ። ታዲያ በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ አትላንታ ይሄን ያህል የተለወጠችው ፡ ይሄን ያህል ያደገች የፋፋችው ምን በልታ ምን አማኝታ ነው! ሊታመን ፡ሊሆን የማይችል ነገር ነው ።

ባለፈው ዓመት እስካርሴት በራሷ ጣርና ሰቆቃ ውስጥ ተዘፍቃ ስለነበር ስለጦርነት የሚወራው ወሬ ሁሉ ስልችት ብሏት ወጊያው ከተጀመረበት ሰዓት ጀምሮ አትሰንታ በዕድገት መመንጠቋን ለማ የት ምንም ዓይን አሌነበራትም ። አንዚያው በሰላም ጊዜ ከተማይ ቱን የንግድ መናኸሪያ ያደረጓት የባቡር መስመሮች በጦርነት ጊዜ ደግሞ እጅግ ቁልፍ የጦር አምባ አድርገዋታል ። ከጦርነቱ የወጊያ መስመር ርቀው ከተማይቱና የባቡር መስመሮቿ ሁለቱን የኮንፌዴሬ ሲውን ሠራዊቶች ማለትም የቨርጂኒያውንና የትንሲውን ሠራዊቶች ከምዕራቡ ሠራዊት ጋር የሚያገናኙ ደም ሥር ሆነዋል ። እናም አትሳ ንታ ወደ ደቡብ — በጣም ወደ ውስጥ ድረስ ብማገናኘት ፡ የጦር መሣሪ ያና ሉላም ቁሳቁስ ለማመላለስ ትረዳለች ። አሁን እንግዲህ አትላንታ ጦርነቱ ሲሚፈልገው ሁሉ ምላሽ የምትሰጥ ዋና ማከፋፈያ ሆነች ። የቁስለኞች ማዘሚያ ደሀና ሆስፒታል አላት ።ሰዩቡት እንደ ጠቅላይ ግምጃ ቤት የሚያገለግልና ጦርሜዳ ላለው ሠራዊት ተፈላጊውን ቁሳ ቁስ ሊያከፋፍል የሚችል የምግብና የጦር መሣሪያ መጋዘንም አላት ።

እስካርሴት በጣም የምታስታውሳትን ትንሿን ከተማ ዙሪያ ገባ ዋን ተመለከተች ። ያቺ ትንሽ ከተማ በቦታውም የለች ። አሁን የም ታያት ከተማ ፡ ድንገት ባንድ ጀምበር አድጎ በጣም ታታሪና ግዙፍ ሠራተኛ ሆኖ እንዳደረ ህጻን መሰለቻት ።

አትላንታ ለኮንፌዴሬሲው የደም ሥር እንደሆነች በማወቋ ኮርታ ፡ እንደ ንብ ቀፎ በሠራተኞቿ ህምህምታ ታጅባለች ።ንቦች ልጆቿ ሌት ተቀን እየታተሩ የአርሻዋን ከተማ ወደ ኢንዱስትሪ ከተማ ሊለውጧት ይሯሯጣሉ ። ከጦርነቱ በፊት ሁሉም ደቡባውያን የሚኮሩባቸው ከሚሪላንድ በስተደቡብ የሚገኙት ጥቂት የጥጥ ፋብ ሪካዎች ፡አነስተኛ የሱፍ ፋብሪካዎች ፡ የመሣሪያ ግምጃ ቤቶችና የምርት መሣሪያ ሱቆች ነበሩ ። ደቡቡ ትላልቅ የሀገር መሪዎችና ወታ ደሮች ፡የአርሻ አጥቂዎችና ዶክተሮች ፡ጠበቆችና ገጣሚዎች ያፈራል ። መሀንዲሶችንና መካኒኮችን ግን አፍርቶም አያውቅ ።እንዲህ እንዲህ ያለውን ያንኪዎች ይጨነቁበት ይል ነበር ። አሁን ግን የኮንፌዴሬሲው

@OLDBOOKSPDF

ወደቦች በያንኪ የጦር ጀልባዎች ስለተዋለቀለቱ ከአውሮፓ የሚገ
ቡት የኮንትሮባንድ ዕቃዎች ጥቂት ብቻ በመሆናቸው ደቡቡ የጦት
ሞቱን የራሱን የጦር መሣሪያ ፋብሪካ ማቋቋም እንዳለበት አውቆ
ሙከራውን ቀጥሏል ። ስሜኑ ዓለምን በሙሉ መሣሪያና ወታደር አር
ዱኝ ማለት ይችላል ።ስሜኑ እንደልቡ በሚያፈስሰው ብር ኃይል በዚ
የሚቀጠሩ የአየርላንድና የጀርመን ወታደሮችን በጣፍ ያጣበል ።
ደቡቡ ግን ከአብራኩ ካወጣቸው ልጆቹና በራሱ ጥሬ ዕቃ ከሚሠ
ራው መሣሪያ በቀር አለኝታዉ የሚለው ምንጭ የለውም ።

አትላንታ ውስጥ ያሉት ለጦር መሣሪያ የሚሆኑ ዕቃዎችን የሚ
ያመርቱት ፋብሪካዎች እጅግ አመርቂ ያልሆኑ ሥራዎችን ይሠራሉ ።
ሥራዎቹ አመርቂ የማይሆኑበት ምክንያት በጣም ጥቂት ጥሬ ዕቃ
ብቻ ስለሚገኝና የአያንጳንጳ የማምረቻ ማሽን ሞዴል በኮንትሮባ
ንድ ኮጋዴዎች በኩል ከአንግሊዝ አገር ድረስ ተጎድፎ የሚመጣ በመ
ሆኑ ነው ። ዛሬ አትላንታ ውስጥ ስኩኮላይቱ እንግዳ ለህዝቡ ባዳ
የሆኑ በርካታ ፊኖች ይታያሉ ። የአገራቱ ተወላጆች ለመትሮው
አንድ ፀጉረልውጥ ሰው ቀርቶ የምዕራቡ ክፍለ — ዓለም ዓይነት የአ
ኑጋገር ሰልት ከለሙ ጀርዋቸውን ጥበረው እንግዳው ሰው ላይ ይጠ
ቋቋሙ ነበር ። አሁን ግን የኮንትሮባንዱን ሥራ እየሠሩ ያመሣሪያ
ፋብሪካ ለማቋቋም የሚረዳ ዕቃ የሚያመጡትን አውሮፓውያን ዞር
ብለውም አያዩዋቸው ። እነዚህ ባለሙያ ሰዎች ባይኖሩ ኖሮ ኮንፌዴ
ሬሲው ሽጉጦችንና ጠመንጃዎችን ፡እንዲሁም መድፍና ባሩድ ለመ
ሥራት ፈፅሞ ባልቻለም ነበር ።

ሥራው ቀን ከሌት እየተሰራ የተመረተው የጦር መሣሪያ በባ
ቡር ሐዲዶች ደም ሥር ውስጥ ወደሠሰቱ የጦር ግንባሮች ሲነፋና ሲጋዝ
የኩተማይቱ ልብ በኃይል እየመታ መሆኑ ያስታውቃል ። በየ
ትኛውም ሰዓት ባቡሮች እንደአንበሳ እያገሱ ይገባሉ ፣ ይወጣሉ ።
ከአዲሶቹ ፋብሪካዎች እንደጉድ እየተትጐለጐለ የሚወጣው ጭስ በነ
ጮቹ ቤቶች ላይ እንደገናብ ካፊያ ይፈስባቸዋል ። ይወርድባቸዋል ።
ማታ ማታ ሰው ሁሉ ከጉሮ በኋላ እንኳ የፋብሪካው ሆድ ዕቃ ፍም
እንደጐረሰ ፡ መዶሻዎች ግው ግው እንዳሉ ያድራሉ ። ከአንድ ዓመት
በፊት ባዶ ቦታ በነበሩት ሜዳዎች ላይ ዛሬ የልንም ሠንሠለት ኮር
ቻዎችና ፋብሪካዎች የሚሠሩ የጐጆ ኢንዱስትሪዎች ተተክለውባቸ
ዋል ። የክባድና የቀላል ጦር መሣሪያ ፋብሪካዎች ጠመንጃና መድፍ
ያመርታሉ ። መጻመጫና ማቅለጫ ፋብሪካዎች ሽቦዎችንና በያንኪ
ዎች የተሰባበሩ መኪናዎች መጠገኛ ዕቃዎችን ያመርታሉ ። የእርከብ
የኮርቻ ዕቃ ፡ የገመዶች ፡ የድንኳኖች ፡ የቁልፎች የሽጉጦችና የጐራዴ
ዎች ማምረቻ የሚሆኑ የተሰያዩ እንዱስትሪዎች ይንቀሳቀሳሉ ። የማ

@OLDBOOKSPDF

ቃለ ጫ አንዱስትሪዎቹ ገና ካሁኑ የብረት እጥረት እየገጠማቸው ነው ። ምክንያቱም በኮንትሮባንድ የሚገባው ብረት በጣም በማነሱ አሲያም ከናካቴው በመጥፋቱ ነው ። አሳባማ ውስጥ ያሉት የማዕድን ጉድጓዶች የሚዕድን ሠራተኞቹ ወደጦርማንባር ሲሄዱ ቦዝነው ይውላሉ ።

|በአትላንታ ሚዳምች ውስጥ የብረትና የሽቦ አጥሮች ፡ ከብረት እየተከፈሉ የሚሰሩ የቢጋ ቤቶች ፡ የብረት መዝጊያዎችም ሆኑ የብረት ሐውልቶች ዛሬ እይታየም ። የብረት ዘር ተጠራርጎ በመጸመጫ ፋብሪካዎች ሆድ ገብቷል ።

በፒችትሪ ጐዳናና በአቅራቢያው ባሉት መንገዶች ዳርቻ ሁሉ የተለያየ ክፍለ ጦር ጠቅላይ ጽ/ቤቶች አሉ ። እያንዳንዱ ጽ/ቤት የደምብ ልብስ በለበሱ ወታደሮች ተጥለቅልቋል ። በኮሚሳሪያቱ ሰዎች ተሞልቷል ። በሲግናል ወታደሮች ፡ በፖስታ አገልግሎት ሠራተኞች ፡ በባቡር ሠራተኞችና በሚሊተሪ ፖሊስ አዛዦች ተጣቧል ። ከከተማዋ ውጭ ፈረሶችና በቅሎዎች የሚጫኑ የሚራገፉበት ቦታ አለ ። በአውራ መንገዶቹ ዳር ዳር ደማሞ ሆስፒታሎች አሉ ። አጐት ፒተር ስለ እነዚህ ሆስፒታሎች ለእስካርሌት ሲነግራት ፡ የጠቅላላ ህክምና ሆስፒታሎቹን ፡ የተላላፊ በሽታ ሆስፒታሎቹንና የአካለ ስንኩላን ሆስፒታሎቹን በጣም ከፍተኛ ቁጥር ስትሰማ ፡ እስካርሌት አትላንታ ቁስለኛ በቁስለኛ ሆናለች ማለት ነው ፡ አሉች በልቧ ። በየቀኑ ደማሞ ባቡሩ ከፋይቭ ፖይንት የበለጠ ቁስለኛ ፡ የበለጠ በሽተኛ ያመጣል ።

ያች የጥንቷ የጠዋቷ ከተማ ቀረች ። አሁን በፍጥነት እያደገች ያለችው አዲሲ ከተማ ናት ። አዲሲ ከተማ በጭራሽ ታከተኝ ደከመኝ የማይል ጉልበት ይፈስበታል ። የዚህ የተጣደፈ ህይወት ሁኔታ ፡ ገና ከገጠሩ ያረፈና የረጋ አየር ወጥቶ የመጣችውን እስካርሌትን ትንፋሽ አሳጠራት ። ያም ሆኖ ወዳዋለች ። አየሩ እንድ ስሜቷን የሚቀሰቅስ ኃይል ሰጥቷታል ። የከተማይቱ በየጊዜው የሚጨምረው የልብ ትርታ ከሷ የልብትርታ እኩል እንደሚንዘፈፍ ሆኖ ተሰማት ።

የከተማዋን ዋና አውራ ጐዳና ይዘው ሲጓዙና የጭቃ ጉድጓዶችን እያለፉ ሲሄዱ እያንዳንዱን አዲስ ህንጻና አዲስ ፊት በልቧ እየመዘገበች ናት ። የእግር መንገዱ የየማዕረጉንና የአገልግሎት ፈርጁን ዩኒፎርም በለበሱ ሰዎች ጢም ብሎ ሞልቷል ። ጠባቡም መንገድ በተሽከርካሪ ተጣቧል ።ሠረገላዎች ፡ጋሪዎች ፡ አምቡላንሶች ፡መንገድ የሚያቋርጡ በትልሞች ላይ የሚርከሩ ሹፌሮች ያሳቸው ሸራ የለበሱ የወታደር መኪናዎች ይታያሉ ። ግራጫ ለባሽ መልዕክተኞች ትዕዛዞችንና የቱሌግራም መልዕክቶችን ይዘው ከዚህም ከዚያ ጠቅላይ

@OLDBOOKSPDF

ጦር ሠፈር ወደዛኛው ጦር ሠፈር ይበርራሉ ። አካለ ስንኩላን ደግሞ አብዛኛውን ጊዜ በግራ ወይም በቀኝ ያገፍ ከምታደርግ ሴት ጋር ክራንች ይዘው ብቅ ሲሉ ይታያሉ ።ምልምል ወታደሮቹ ሙሉ ወታደሮች እየሆኑ ከሚመጡበት ማሰልጠኛ ሠፈር ግድም መለከት ይነፋል ፤ ከበሮ ይደለቃል ።

እጮት ፒተር ጥቂት ያንኪዎች በክንፈዴራሲዎ ወታደሮች ጠመንጃ ተደግፍባቸው ወደ እሥር ቤት ሲሄዱ አይቶ ሰማያዊ ዩኒፎርም ወደለበሱት ያንኪዎች በአለንጋው ሲያሳያት የመጀመሪያዋ ጊዜ በመሆኑ እስካርሌት ልቧ እጉሮሮዋ ላይ ተሰነቀረችባት ።

"ዎው!" አለች እስካርሌት በልቧ ።ክዳንሱ ግብግ ወዲህ እውነተኛ ደስታ ያገኘችበት ቀን ቢኖር ይሄ ነው ። "በቃ ይሄንን ቦታ ልወደው ነው፤ ህይወት እስትንፋስ አለው !መንፈስ ያንቃቃል ! !"

ከተማይቱ እስካርሌት ከተገነዘበችው የበሰጠ ህይወት ያላት ናት ። በደርዘን የሚቆጠሩ አዳዲስ ቡና ቤቶች ተከፍተዋል ።ጦር ሠራዊቱን የሚያሳድጉ ሴትኛ አዳሪዎች ከተማዋ ውስጥ ይርመሰመሳሉ። ባለቀይ መብራት የሴት ቤቶች ቁስ የሚያስቱ ቆንጆ ቆንጆ ሴቶች እደጃፋቸው አቁመው ግቡ ግቡ ይላሉ ።እያንዳንዱ ሆቴል ፤ማደሪያ ቤትና የግል መኖሪያ ሰው በስው ሆኗል ። ሰዉ ፤ የቆሰለ ዘመዱን ለመጠየቅና ለማስታመም እንዲችል ወደትልቁ የአትላንታ ሆስፒታል ቀረብ ብሎ ለመቅመጥ ሲል እንዚህን ቤቶች አጣቧል ።በየግምንቱ ፓርቲ ይደገስባቸው ፣ዳንስ ይጨነስባቸውና ባዛር ይዘጋጅባቸው የነበሩ ቦታዎች ናቸው ።በጦርነት ምክንያት የተፈጠሩት ሠርጐች ቁጥር ሥፍር የላቸውም ነበር ። ሙሽሮቹ ብርማና ወርቅማ ልብስ ለብሰው ሽርሽር ይሄዳሉ ።ኮራዴ ከኮራዴ ተጠሳልፎ ፣የደስ ደሱ ተበልቶ ተጠጥቶ ቫምፓኛ ተረጭቶ ፣ የመሸኛ መለኪያ ከመለኪያ ተገጫጭቶ ይኼድባቸው ነበር ። በየማታው በጥቁር ዝፎች የሚሸፈኑት የተኙ መንገዶች በሚደንሱ እግሮች ድምጽ ይቀሰቀሳሉ ። ከየአልፍኙ የሚመጣው የፒያኖ ድምጽም በእንግዳ ወታደሮች ቅኝት ይሟሽና "ዘ በግለስ ሳንግ ትሩስ" እና "ዮር ሌተር ኪም በት ኪም ሌት" የሚሉ በማም የሚያሳዝኑ ፣ አንድ ዘለላ እንባ ወጥቶት የማያውቀውን ዓይን እንኳ እንባ በእንባ የሚያደረጉ ፣ ዜማዎች ይሰሙበታል ።

ስምጥ ስምጥ በሚያደርገው ጭቃ ውስጥ አቋርጠው ቁልቁል በአውራ ጐዳናው ሲሽቆለቆሉ እስካርሌት ፤ እጮት ፒተርን መዓት ጥያቄ ጠየቀችው ።ፒተርም አሁንም አሁንም በአለንጋው እየጠነቆለ እያሳያት ፣በእውቀቱ እየኮራ መልስ ይሰጣታል ።

@OLDBOOKSPDF

"ያ የመሣሪያ ወንጀል በቅ ነው። ዳኞች እመቤት ጠመንጃና ሌላ የጦር መሣሪያ ያስቀምጡብታል ።የለም እመቤት እሱስ መጋዘን አይደለም ።የኮንትሮባንድ ዕቃዎች ሥራ ቢሮ ነው ። ወ/ሮ እስካርሌት የኮንትሮባንድ ዕቃዎችን ሥራ ቢሮ አታውቂም ? በቻርልስተንና በዊልሚንግተን በኩል የኮንፌዴሬሲውን ጥጥ ይወስዱና በምትኩ ከውጪ ዕቃ ፣ባሩድና ጠመንጃ ያስገቡልናል ። ምን ዓይነት የውጪ ዜጐች እንደሆኑ እንኳ አላሳይሽም ። እሜቴ ፒቲ እንደሚሉት እንግሊዞች ናቸው — የሚናገሩት ግን እንድም አይሰማ ።እዎን እመቤት በጣም ኃይለኛ ጭስ ነው ፣ ጥላሸቱ የአሜቴን ከሀር የተሠራ የመስኮት መጋረጃ አጠፋው ። ከዚያ ከማቅለጫ ቤትና ከመጻመጫው ነው የሚመጣው ። ማታ ማታ የሚፈጥሩት ድምጽ ደሞ አይጣልብሽ! ማንም ለመተኛት አይችልም። የለም እመቤት በደምብ እንድታይ እኔ አቆምልሻለሁ ። ለእሜቴ ፒቲፓት በቀጥታ ይገርሽ እንደምመስሰ ቃል አልገባም ። ...ወይዘሮ እስካርሌት ፣ ወይዘሮ ሜሪ ዌዘርና ወ/ሮ ኤልሲንግ ሰላም ይሉሻል ።"

እስካርሌት እንዚህ ሁለት አሮጊቶች ከአትላንታ ታራ ድረስ ሰሏ ሠርግ የመጡ እንደንበሩ ዘጣም ግር እያላት ከሰማቸው አስታወሰች ።እንዚህ ሴቶች የወይዘሮ ፒቲ ፓ በጣም የቅርብ ጓደኞች ናቸው ። ከእንድ ቸቀጣ ቸሎጥ ሰቅ ይጀጥ ሠረገላ ውስጥ ቁጭ ብለዋል ። የሰቁ ባለቤትና ሁለት ዐሐፊዎቹ ፣ በኣገር መንገዱ ላይ ቆመው ከዋጥ የተሠሩትን ልብሶች ለማጢው ሰው ያሳያሉ ።ወይዘሮ ሜሪዌዘር ረሻም ናቸው ። ጡታቸውን በጣም ጥብቅ አድርገው ከማሠራቸው የተነሳ እንደመርከብ አጭጫ ቆሟል ። ጉበስማው ዐጉራቸው ባንድ ወገን ጫፍጫፉ በክራት ቡና ተቅብዶዋል ። ሌላውን ዐጉርሻን በሙሉ ቡና ተቅቢው ቢባሉ አሻፈረኝ አሉ ። በጣም ቀይ ክብ ፊት ያላቸው ናቸው ።የጨዋ መሠሪነትና የማዘባ ልማድ ይነበብባቸዋል ።ወይዘሮ ኤልሲንግ ከኖኛዋ ዘድሜ አንስ የሚሉ ቀጭንና ልጅ ሆነው በጣም ቆንጆ እንደነበሩ የሚያስታውቁ ናቸው ።ያም ሆኖ ቀስ በቀስ የጠፉ ቢጋነትና የአዛሸንት መንፈስ እንደነበራቸው ይታይባቸዋል ።

እንዚህ ሁለት ሴቶችና ወ/ሮ ዋይቲንግ የአትላንታ ምሰሶዎች ናቸው ።ሶስቱን የበተስኪያን ክፍሎች ቀጥ አድርገው ይዘዋል ።ባዛሮችን ያዘጋጃሉ ።የስፈት ክበቦች ውስጥ ይሳተፋሉ ።ግብዣዎችንና ሽር ሽሮችን ይመራሉ ።ማ ከማን ጋር ይሂድ ማን ከማን ጋር ይቅር የሚለውን አሳምረው ያውቃሉ ። ማ በጭለማ ተደብቆ እንደሚጠጣ ፣ ማ መቼ ልጅ እንደምትወልድም ጭምር ያውቃሉ ።በጆርጂያ ፣በደቡብ ካሮለይናና በቨርጂያ የሚኖር የማንም ሰው ወሊድ ጉዳይ ውስጥ ያገ

@OLDBOOKSPDF

ባናል ባዮች ፣አዛኝ — ሳቁኮ ኑኖው ከነዚህ ከሶስቱ ከትማዎች በስተቀር በድፍን አገር ቢያዞሯቸው ከተማ አየን አይሉም ። ትልቅ ሰው የሚባል ጨዋ ሰውም ሊበቅል የሚችለው እነዚሁ ሶስት ከተሞች ውስጥ ብቻ ነው ። መልካም ፀባይ የሚባለው ምን ዓይነት ፀባይ እንደሆነ እናውቃለን ይላሉ ።ባዮት ፀባይ ሳይ አስተያየት ሳይሰጡ ደግሞ በጭራሽ እያልፉም ። ያውም ወይዘሮ ሜሪዌዘር ባለ በሴሰ ድም ጸቸው ጮክ ብለው ፣ ወይዘሮ ኤልሲንግ ሊሞት በደረሰ ድምፃቸው ቀስ ብለው ፣ ወይዘሮ ዋይቲንግ ደግሞ ከናካቴው እንዲህ ያለውን ነገር ማውራት እንደማይገባ ስለሚያምኑና ስለሚጠሉም በጣም እየተንሾ ካሾኩ ይናገራሉ ። እነዚህ ሶስት ሴት ወይዘሮዎች እርስ በርሳቸው መጠላላታቸውና አለመተማመናቸው ልክ የሮሚን ነባስታት ዓይነት ነው ። ምናልባትም በጣም የሚቀራረቡት እንዴ እንዴ ስለሚጠሉና ስለማያምኑ ሊሆን ይችላል ።

"በሆስፒታሉ ውስጥ ከኔ ጋር እንድትሆኚ ስፒቲ ነግሬያት ነበር እኮ" አሉ ወይዘሮ ሜሪዌዘር ፈገግ እያሉ ። "ስ፱/ሮ ሚድም ሆነ ለወይዘሮ ዋይቲንግ ቃል እንዳትገቢ ደግሞ!"

"እሳረገውም"አለች እስክርሌት ፣ ወይዘሮ ሜሪዌዘር ስለምን እንደሚያወሩ እንኳ ሳታውቅ ። ያም ሆኖ ግን በደምብ ስለተቅበጧትና ስለ ፈለጓት እንድ ልቢን ጋል የሚያደርግ የደስታ ስሜት ተሰምቷታል ። "በቅርቡ እንደገና እንደማገኛዎት ተስፋ አለኝ ።"

ሠረገላው መንገዱን ቀጠለና በማህል ለእንዲት ቅድብት ቆም አለ። ሁለት ሴቶች በቅርጫት በቅርጫታቸው መጠቅለያ ፋሻ ይዘው ሽቅብ ወደሚያወጣው መንገድ ሲያዘርጡ ፣ እነሱን ለማሳለፍ ነበር የቆመው ። በዚሁ አጋጣሚ እስክርሌት እንድ በጣም ደማቅ ልብስ ለብሶ ከእግር መንገዱ ላይ ቆሞ የሚያያት ሰው ሳይ ዓይንዋ አረፈ ። ሰውየው ቫል ብጤ ሳዩ ጣል እድሮኑ እግር ጥፍሩ ድረስ አውርዶታል ። ከዚያ ዘወር ስትል እንዲት ረኽም ፣ ፊቷ ከሚታመነው በላይ ቀይ የሆነ ሴት አየች ። በህይወቷ ለመጀመሪያ ጊዜ እንዲህ ያለች ሴት ማየቷ ነው ።"በጉሯን እንድ ነገር አድርጋብሽ"አለች በመደነቅ እያየቻት ።

"እግት ፒተር ማናት ያቺ" አለች በሹክሹክታ

"እሷ እንጂ"

"ታውቃታለህ ። እኔ እንኳን አውቃታለሁ ማን ናት ያ"

"ስሟ ቤል ዋትሊንግ ነው" አለ እግት ፒተር የታችኛውን ከን ፈሩን እያስረዘመ ።

@OLDBOOKSPDF

አስካርሌት የሴትየዋን ስም ሲጠራ ከስሚ በፊት "ወ/ት" ወይም "ወ/ሮ"እንዳልጨመረ ልብ ብላለች ።

"ማን ናት ግን?"

"ወ/ሮ አስካርሌት"አለ ፒተር ትክም ብሎ ፡የተደናገጠውን ፈረስ እየገረፈ ።"እሜቴ ፒቲ መኼም ይሄንን የማያጣጥፍ ጉዳይ ውስጥ ጥልቅ ብለሽ ጥያቄ መጠየቅሽን በጭራሽ አይፈልጉትም ። አሁን እዚች ከተማ ውስጥ ጥቂት የማይረቡ ሰዎች ገብተዋል ። በለ ነሱ ማውራት ግን አስፈላጊ አይደለም"

"ኧረ የሰማይቱ ያለህ!" አለች አስካርሌት በልቧ ፡ ገምታዋን እያ ጠናች ። "በጣም መጥፎ ሴት መሆን አለባት ፣"

አስካርሌት ከዚህ ቀደም መጥፎ ሴት አይታ ስለማታውቅ እየተ ገላመጠች ከብዙው ህዝብ ጋር አስክትቀላቀል ድረስ እየጮኸ ።

መጋዘኖቹና አሻዲሶቹ የጦርነት ሀንየምች እሁን በጣም ተራር ቀዋል ፡ በማህሉቸውም ባዶ ቦታ አለ ። ዘመጨረሻ የኃላዬ አከባቢ ወደኋላ እየቀረ የመኖሪያው አከባቢ እየገሰ መጣ ።አስካርሌት ልክ የጥ ጌት ጓደኛ እንዳገኘች ሁሉ እያኘሻንዱን ቤት በጉራ በጉራ ተመለከ ተች።ከየሴይደን ቤት እንደተከበረ ቸሚል ከየቦኔል ቤተሰብ ቤትም ትናንሽ ነጫጭ ምስሎቹንና አሪንጓዴ መጋረጃዎቹን እንደያዘ አለ። ከባለ ቀይ የጆርጂያ ሸክላ አጠጋግቶ የሠራው የማክለር ቤተሰብም የመኖሪያ ቤት ያውና ። አሁን የሠረገላው ፍጥነት እንዲቀንስ ተገደደ። ምክንያቱም ከየበረንዳው ፡ ከየእቅልፉት ይታውና ከየእሣር መንገዱ እንዴነሽ ሲሉ የሚጠሯት ሰምች እየበዙ ስለመጡ ነው ። አንዳንዶቹ ሲመል ታዘል ያምታውታቸው ናቸው ። አንዳንዶቹን ለማስታወስም በችግር ነው ። ከብዛቸውን ግን ከናትቱው አታውቃቸውም ። ወ/ሮ ፒቲ ፓት ያለተርጥር የአስክርሌትን መምጣት በሰፈሩ ነገሩውታል። አሁንም አሁንም ትንሹን ጥድ ከፍ እያደረጉ ማሳየት አስፈልጎል ። ምክንያቱም ሲያዩትና ፎክ ብለው ሲያዎሩት የሚፈልጉት ቤቶች እንደምንም ለባሣሃት ስለሚሸጡ ነው ። ሁሉም እየጮሁ የጥልፍ ክበብ ፡ ስፌት ክበብ አንዴሁም አሠሪዋች ከሚቴ ውስጥ መግባት አስችሽ ይሏታል ።

አንድ በአረንጓዴ የከረቦን አንጨት የተሠራ ቤት አንዳሰፉ አንዲት ትንሽ ጥቁር አሮ ከፊት ለፊቱ ደረጃ ሳይ ቁጭ ብላ "ሄይ፣ መጥታለች" አለችና ጮኸች ። ወዲያው ዶክተር ሚድና ባለቤቱ እንዲሁም ትንሹ ልጃቸው የአስራ አንድ ዓመቱ ፊል ብቅ ብለው ሰላ ምታ አቀረቡላት ። አስካርሌት እንሰውም እሠረግ ላይ እንደነበሩ አስ

@OLDBOOKSPDF

ታወሰች ። ወይዘሮ ሚድ በእንድ ድንጋይ ላይ ቆማ በሠረገላው ተንጠራርታ ሕፃን ለማየት ትሞክራለች ። ዶክተሩ ግን ጭቃውን ከም ንም ሳይቆጥር ውስጡ በሁለት እግሩ ተተክሎ ሠረገላው አጠገብ ቆመ ። በጣም ረዥምና ግዙፍ ሰው ነው ። የእግሮ ጢሙ ግራጫና ሹል ነው ። የለበሰው ልብስ በጣም ከመሳሳቱ የተነሳ በንፋስ ኃይል እላዩ ላይ የተለጠፈበት ይመስላል ። ድፍን አትላንታ የጥንካሬና የጥበብ ሁሉ መሠረት ፣ አድባራችን ፣ ዋርካችን ይሰዋል ። እንደእምነታቸው ጠንካራና የጥበብ ሰው መሆኑ እንግዳ ነገር አይደለም ። ምንም እን ኳን የትንቢት ንግግር ቢያበዛና ትንሽ ጉረኛነት ቢታይበትም ያቺ ከተማ አሰኝ የምትለው ደግና ጨዋ ሰው ነው ።

እስካርሌትን ከጨበጠና ዋይን ሆፉን መታ መታ አድርጎ ካደነቀው በኋላ ፣ ዶክተሩ ፣ ወ/ሮ ሺቲ በገባችለት ቃል መሠረት እስካርሌት ከወይዘሮ ሚድ ጋር በስተቀር ሌላ ሆስፒታል ወይም ፋሻ ጥቅላላ ኮሚቴ መግባት እንደሌለባት አወጀ ።

"ውይ ጌታዬ፣ እስካሁን እኮ ለአንድ ሺህ ሴቶች ይሆናል ቃል የገባሁት !"

"ወ/ሮ ሚሪዌዘር አንደኛዋ እንደሚሆኑ እርግጠኛ ነኝ!" ብላ ጮኸች ወ/ሮ ሚድ በንዴት ። "የማይረቡ ሴትዮ፣ ሙቼም የመጣ ባቡር አንድ አይቀራቸውም — እየሄዱ ሥሩ ይቆማሉ ። !"

"እኔ እሺ ብዬ ቃል የገባሁት ምን እንደሆነ ስላላውኩ ነው" አለች እስካርሌት ከሀተታዋ አምና ። "እነዚህ የሆስፒታል ኮሚቴዎች ምንድናቸው?"

ዶክተሩና ሚስቱ በድንቁርናዋ ደነገጡ ።

"ግን አንቺ ምን ታደርጊ እዛ ንጠር ውስጥ ተቅበረሽ" ወይ ዘሮ ሚድ በእስካርሌት ቦታ ሆና ይቅርታ እንደመጠየቅ አለች ። "በተለያዩ ሆስፒታሎች ለተለያዩ ቁናት የሚያገለግሉ የነርሶች ኮሚ ቴዎች አሉን ። የቆሰሉትን እናክማለን ። ዶክተሮቹንም እንረዳለን ። ፋሻዎች እናዘጋጃለን ። ልብስ እናቀርባለን ፣ ድነው ከሆስፒታል ለመ ውጣት ሲችሉም ወደ ራሳቸን ቤት እንወስዳቸውና በደምብ እን ሚመው ተመልሰው ከሠራዊቱ ጋር ለመቀላቀል እስኪችሉ ድረስ እናቆያቸዋለን ። የእንዳንዶቹን— በጣም የደኸዩትን ደግሞ ሚስቶ ቻቸውንና ቤተሰቦቻቸውን እንንከባከብላቸዋለን ። ዶክተር ሚድ የእኔ ኮሚቴ እሚሠራበት የኢንስቲትዩቱ ሆስፒታል ውስጥ ነው የሚሠራው ። ታዲያ ሰው ሁሉ እንዴት ያለ ግሩም ዶክተር ነው እያለ . . ."

@OLDBOOKSPDF

"በቃ ፣ በቃሽ ፣ ወይዘሮ ሚድ ።" አለ ዶክተሩ በፍቅር ። "ስለኔ በሰው ፊት እያጋነንሽ የባጠን ያቆሙን አትዘባርቂ ። እኔ በጣም ትንሽ ሥራ ነው የምሠራው ። ከሠራዊቱ ጋር አብሬ እንድሄድ ብት ፈቅጂልኝ እንኳ ደህና ነበር ።"

"ብትፈቅጂልኝ!" በንዴት ጮኸች ። "እኔ ነኝ እንዴ እኔ ሆንኩ እንዴ ፈቃጅዋ? ድፍን አገር አይለቅህም ። በጂ አይልም ፣ ታውቃለህ። አየሽ እስካርሌት ፣ ባለፈው ከቨርጂኒያው ሠራዊት ጋር የመር ሜዳ ሀኪም ሆኜ ክልሄድኩ ብሎ የከተማው ሴት በሙሉ የልመና ማመ ልከኝ ጽር ፣ ፊርሞ ፣ እግዚኦ ብሎ አስቀረው ። እርግጥ ነው ደሞ፣ ከተማዋ ያላንተ ምንም አይሆንላትም ። "

"በቃሽ ፣ በቃሽ ባክሽ ወይዘሮ ሚድ" አለ ዶክተሩ ፣ በግልጽ የሙግላውን ፀሐይ እየሞቀ ። "ምናልባት አንድ ልጅ ወደ ግንባር ከላ ከን ለጊዜው ይበቃ ይሆናል ።"

"እኔ ደሞ በሚቀጥለው ሐመት እሄዳለሁ!" ትንሹ ፊል ጮክ ብሎ ተናገረ ፣ ጉጉትና ተስፋ እንደምሳው ። "ታምቡር መቺ እሆ ናለሁ ። ታምቡር መምታት እየተማርኩ ነው እኮ ። ትስሙኛላችሁ፣ ቆይ ሄጂ ታምቡሬን ላምጣ"

"እይ ፣ ተው እሁን እይሆንም" አለች ወይዘሮ ሚድ ወደቢ ጠጋ እያረገችው ። አንድ ድንጣኛ ሙጥሬት እፈድ ላይ ያንጣብብ ባል ። "በሚመጣው ዓመትም እይሆንም ጌታዬ ። ከዓመት በኋላ ባይሆን ትሄዳለህ"

"ምኣዝ፣ እስከዛማ ጦርነቱ ያልቃል!" ሮቬና በንዴት መንጭ ጭት ቢሄድ ሞከረ ። "ቃል ግብተሽልኝ ነበር እኮ ደሞ!"

በልጁ ጭንቅላት ላይ እናትና አባቱ ተያዩ ። እስካርሌትም ውኔ ታቸውን ፋወስከቱች ። ትልቁ ልጃቸው ጴርሲ ሚድ ቨርጂንያ ስለ ዘመቱ የቀራቸውን ትንሹን ፊል እንቅ አድርገው መያዝ አስባቸው።

እገት ፒተር ጉሮሮውን አጸዳ ።

"አሚቱ ፒቲ ቅድም ስወጣ ተናደው ነበር ። አሁን ደግሞ እዚህ ስቆይ በጣም ነው የሚበሳጩት ። ቶሎ ብንሄድ ይሻላል"

"ደህና ሣቲ ። ከሰዓት በኋላ እመጣለሁ" አለች ወ/ሮ ሚድ "ደሞ ወ/ሮ ፒቲን ፣ አንቺ እኔ ኮሚቴ ውስጥ ክልገባሽ የባሰ ብስጭት እንደሚደርባቸው ንገሪልኝ"

ሠረገላው ተንቀሳቀሰና በጭቃው መንገድ ቁልቁል እየተሽቆለ ቆለ ሳለ አስካርሌት ወደ ኋላዋ ዞር ብላ ፈገግ አለች ። በወራት ለሚ

@OLDBOOKSPDF

ቆጠር ጊዜ ያልተለማት የደስታ ስሜት አሁን ተሰማትና ልቧን ሞቅ አደረገላት።አስላንታ ፣ ከነሀዘብ ብዛቷ ከነትርምሷ ፣ ከነጭፈራዋ፣ ከነወጠራት አዳዲስ ስሜት ፣ በጣም አስደሳች ፣ በጣም አዝናኝ ናት። ከቻርልስተኑ ብቸኛ እርሻና የወጥቃውን በረዶ ከሚሰብረው አዞ ይልቅ ይቺ የአትላንታ ኩሶማ በጣም ግሩም ናት ። በጣም ሙቅ ናት ። ከትላልቅ የንሮ አትክልት ማድጣዎች ውስጥ ተደብቆ ከሚ ያልመው ቻርልስተን ይልቅ ወጣቷ አትላንታ ፪ ጊዜ ትሻላለች ። ጭቃማውን ወንዝ በየሳርቻው ከዘረጋውና በቱምር ዛፍ የታጠረ መንገድ ካለው ክላቫና ይልቅ ለጋዋ አትላንታ ፪ ጊዜ ትመረጣ ለች ። አምን ፣ ምንም እንኳ ታሪ ተወዳጅ ብትሆን ፣ አንዳንዴ ፅጌዘ ውም ቢሆን ከታሪ ትሻላለች ።

ይቺ ኩሶማ ከንጭጭማ ጠፋብ መንገዷ አንድ ልብ የሚነክ ነገር አላት ። የሚጠቅለቡ በሚመለሱ ቀያይ ኮረብታዎች ሚህል ሆና አንድ ጥሬ ፣ አንድ ጥና ግርድፍ ግን ጣፋጭ ነገር ውስጧ አለ ።

ይሄ የክሶማይቱ ጥልንት ፣ ይሄ የክሶማይቱ ግርድፍንት ምናል ባት አለግና ሚሚ አርመው ዕትኩሩው ክሳደጥት ከአስክርሌት ወባይ ወጪ አሁንም ያበ ጥሬነትና ግርድፍንት ሊሆን ይችላል ። ወጻያው በደንግጥ ይሄ ነው የኔ ሕይወት አለች ። በፅጥጭኖና በዝ ግታኛ ጥያቄ ክሶማው ውስጥ አይደለም የኔ ሀይወት የሚለመል መው ፣ አለች በልቧ ።

አሁን ቤቱቹ እየቀራራብ ሄዱ ። አሰካርሌት አንገቷን ከሥረገ ላው ብቅ አድርጋ የመይዘር ጊቲ ፓትን ቀይ ሸክላ ቤት አየችው ። ከክሶማው በስተሰሜን ቢል ከሞላ ጐደል የመጨረሻው ቤት ነው ። ከዚህ ዘልቀው ሲጀሩ የሮች ትሪ ቅጸና እየጠበበና በትላ ልቅ ዛፎች ሥር እየተጠግበበ ቀስቀስ ባለው ዝምተኛ ጫኳ ጉያ ንብቱ ይደበቃል ። ከዚያ ወዲያ ሣንም አያየው ። ከእንጨት የተሠራው ንፁህ አጥር ነጭ ቀለም ተቀብቷል ። ይሄ አጥር የሚከበው ለምለም ግቢ በመትቱ በሚበትሉት ቢጫ አበበኙ የፊክ በመሆኑ ቢጫ ከዋክብት የፈሰሱበት ይመስላል ። አፅት ለፊት ደረጃ ላይ ሁለት ጥቁር የለ በስ ሴቶች ቆመዋል ። ክንሰቹው አንዷም ግዙፍ ቀይ ሴትዮ እጅ ጀኑ እሽርጧ መሰዋ ጀንጣ ወተት የመሰሰ ነጫጭ ጥርሶቿን አረፋ የደፈቀች እስኪመስል ድረስ ዴርድራ ፡ በሰፊው ፈገግ ብላ ቆማለች ። በጅቧዋ ወደዘር ጊቲፓት ብትናንሽ እግሮቻቸው ቆመው የሚርበተበቱውን ልባቸውን ለማረጋጋት የፈለጉ ይመስል እጆቻ ውን ጠቀምጠው ሥር ቀብረዋል ። ከጐናቸው ሚላኒ ቆማለች ። አስካርሌት ሚላኒን አየቻት ። በዋላቻዋ ወስጥ አንድ ነገር ተነ

@OLDBOOKSPDF

ዘበች ። በእትላንታ ውስጥ ታዘረጋችው ቢረዥ ሁሉ ወደዚች ትን ሽየና ቀጫጫ ቤት ለመድረስ ነበር ። ያ ሁሉ ስሚቷን እንደጉርፍ እያጠበ ያመጣት ደስታ ወደዚች ጥቁር ለብሳ ወደ ቆመች ፣ ዘማ ጥቅልል ፀጉሯ የቤት እመቤት ልስላሴ ይዞ የልብ— ቅርጽ ያለው መልኳን ወደ ሽፈነውና በፍቅር በተሞላ ፈገግታ በደስታ እንኳን ደህና መጣሽ ወደምትላት ቤት ኖሯል ።

አንድ ደቡባዊ ፣ ሻንጣውን ጠቅልሎ ዘመዶቹን ለመጠየቅ የሃያ ማይል ርቀት ያለው መንገድ ሲሄድ እንዳንዴ የጥያቃው ጊዜ ከአ ንድ ወር አይበልጥም ። አብዛኛውን ጊዜ ግን ከወርም ይረዝማል ። እነዚህ ደቡቦች እንግዳ እንደሚወዱ ሁሉ ዘመድ መጠየቅም ነብ ሳቸው ነው ። ደሞም በልማዳቸው መሠረት ለገና በዓል ሄደው እስከ ሐምሌ ድረስ እንኳን ቢቆዩ ነውር የለበትም ። አዲስ የተጋቡ ሙሽሮች ለማር ጨረቃ ሽርሽራቸው ዘመድ ቤት ሄደው ካረፉ አብዛኛውን ጊዜ ሁለተኛው ልጃቸው እስኪወለድ ድረስ ይቆያሉ ። አልፎ አልፎማ እንዳንድ አክስቶችና አጐቶች እሁድ እሁድ እራት ተጋብዘው ዘመድ ቤት ሄደው በዚያው ለዓመታት ይከርሙና ሞተው ፈላቸው ከዛ ቤት እስኪወጣ ይቆያሉ ። በንዚያ ሰዎች እንግዳ ምንም ችግር አይፈጥርባቸውም ። ምክንያቱም በዚያ በሞቃ ህይወት በተሞላ፣ ሰፊ ማደሪያ ባለበት ፣ የሚጫንው ፈረስ የሚታዘዘው አሽከር ውጪ ማቢውን ባጣበበበት ፣ የሚበላው የሚጠጣው በተትረፈረፈበት አገር ፣ ሁሉም የአብርሃም የሚራ ቤት ነው ። እንግዳ ይወዳሉ ። ህፃን ይሁን ሽማግሌ ፣ ወንድም ይሁን ሴት ዘመድ ጥየቃ መሔዱ የተለመደ ነው ። በማናቸውም ዕድሜና ፆታ ውስጥ ያሉ ባለማር ጨረቃ ሙሽ ሮች ፣ አዲስ የተወለደ ልጃቸውን ለዘመድ ለማሳየት የሚፈልጉ እናቶች ፣ ያገገሙ በሽተኞች ፣ ዘመድ የሞቱባቸው ሀዘነተኞች የሴት ልጅቻቸውን የወዳጅ ምርጫ በምክር ለማስተካከል የሚሹ አባቶች ዘመድ ይጠይቃሉ ። ሩቅ ቅርብ ይጓዛሉ ። ሄኔላት ዘመናቸው ሳይ ያደረሱ ልጓገረዶች ብዘመድ ቀመክረው የሚበጃቸውን ባል መምረ ጣቸው የተለመደ ነውና ፣ የነሱ ወሳጆችም ሞምሮ ዘመድ ይጠ ይቃሉ ። ዘመድ ጠያቂ እንግዶች በነማታ በሚጓዘው የደቡቦች ህይ ወት ሳይ የለውጥ ቅመም ይጨምሩበታል ። በደስታና በእንቅስቃ ሴም ይሞሉታል ። ስለዚህ እንግዶች ሲመጡ ስቀው ፣ አሰየው ብለው ይቀበላሉ ።

እስካርሌትም ወደ እትላንታ ስትመጣ እንግዲህ ለምን ያህል ጊዜ እንደምትቆይ ምንም አታውቅም ። ዘመድ ጥየቃዋ እንደሳቫናና እንደቻርልስተን አሰልቺና ህይወት አልባ ከሆነባት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ወደ ቤቷ ትመለሰለች ። ቆይታዋ ያማረና ደስ የሚል

@OLDBOOKSPDF

ከሆነላት ግን እስከወዲያኛው ትሰነብታለች ። ያም ሆነ ይህ ግን ገና ከመድረሷ ወይዘሮ ጢቲና ሜላኒ እዚሁ መኖር አለብሽ እያሉ ግፊታቸውን ቀጥለዋል ። ያላመጡት ክርክር ፣ ያላቀረቡት መሣት የለም ። ለእሷ ካላቸው ፍቅር የተነሳ አብራቸው እንድትሆን እበክ ረው ተማጠኗት ። ብቻቸውን በመሆናቸውና ያ ትልቅ ቤት ማታ ማታ ሊውጣቸው ስለሚደርስ ፍርሃት አለባቸው ። እሷ በጣም ደፋርና ልበ ሙሉ ስለሆነች ጥንካሬን ትሰጣቸዋለች ። በጣም ተጫዋች በመሆኗም ላዘነ ልባቸው ጥሩ መጽናኛ ትሆናቸዋለች ። አሁን ቻርለስ የሞቱ ስለሆነ የሷና የልጅዋ አጠገባቸው መኖር የሱን ቦታና የሱን እጦት ይተካላቸዋል ።

በዛ ላይ በቻርለስ ኑዛዜ መሠረት የቤቱን ግማሽ ወራሽ እሷ ናት ። በመጨረሻም ባሁኑ ሰዓት ኮንፌዴሬሲው እያንዳንዱን ጥልፍ ጠላፊ እጅ ፡ እያንዳንዱን ስፌት ሰፊ ጣት ፡ እያንዳንዱን ፋሻ ጠቅ ላይ እጅ ይሻል ። የቆሰሉትን የሚያክምና የሚጠግን ኃይልም በጣም ያስፈልገዋል ።

ከመጣሪያ ግምጃ ቤት አጠገብ ባለው አትላንታ ሆቴል ውስጥ አልቤርት ተክራይቱ የሚኖረው ወንደላጤው የቻርለስ አጐት ሐንሪ ሐሚልተን በዚህ ጉዳይ ላይ ኮስተር ብሎ አንጋጫት ነበር። ሐንሪ እጭር ፣ ቁጠኛና ቦርቂም የሆነ ጨዋ ሽማግሌ ነው ። ፊቱ ሳምባ ይመስላል ። ረዥም ብራማ ፀጉር አለው ። ከሴቶች ጋር ሲነጋ ገር በተለይ ጨቅጫቃ ከሆኑበት ብዙ ጊዜ ትግሥት የለውም ። አሁን በዚህ ትእግሥት የለሽነቱ ምክንያት ነው ከእህቱ ከወ/ሮ ፒቲፓት ጋር መለያየት የፈለገው ። ከልጅነታቸው ጀምረው በዚህ በስ ሜት ግንፍልታ ጉዳይ ተቃራኒዎች ናቸው ። በተጨማሪም ወ/ሮ ፒቲ ቻርለስን ሲያሳድጉ "የጀግናውን ልጅ ቡክን አረማሺው!" እያለ ይጨቃጨቅ ስለነበር በፅባይ በጣም ይራራቁ ነበር ። ከአመ ታት በፊት ወይዘሮ ፒቲን ሙልጭ አድርጎ ሰድቧቸው ስለነበር ፡ ስለሱ ሲያወሩ በጣም ተጠንቅቀውና በሹክሹክታ ከመሆኑ የተነሳ እንግዳ ሰው ያንን ታማኝ ሽማግሌ ቢያንስ ነፍሰ ገዳይ ነው ብሎ መገመቱ አይቀርም ። ስድብ ደረጃ ያደረሳቸው ወይዘሮ ፒቲ እሱ በአደራ አስቀምጠት የነበረውን ገንዘብ ለእንድ ለማይረባ የወ ርቅ ማዕድን ሥራ ላውል ብለው በተነሱበት ጊዜ ነበር ። እሱ በጭ ራሽ እሻፈረኝ አላቸው ። እንዲያውም እሳት ገርሶ እሳት ለብሶ ከዶሮ የተሻለ ጭንቅላት የሌለሽ ቆርቆሮ ራስ ነሽ እያለ ሙልጭ አድርጎ ሰደባቸው ። ለመጀመሪያ ጊዜ ከአምስት ደቂቃ በላይ አብሯቸው እን ዲቆይ ያደረገውም ይሄው የስድብ ውርጅቡኝ የማውረድ ፍላጎቱ ነበር ። ከዚያን ጊዜ ወዲህ አጐት ፒተር የቤት ወጪ ገንዘብ እንዲ

@OLDBOOKSPDF

ወስዱ በወር አንድ ጊዜ መጀ ቢሮው ሲወለዳቸው ከሚያናግሩት ያንገት በላይ ንግግር በቀር ከሐንሪ ጋር ቁጭ ብለው ተጨዋውተው አያውቁም ። ሁልጊዜ ለትንሽ ሰዓት እጮት ሐንሪ ቢሮ ደርሰው በመጡ ቁጥር ቀኑን ሙሉ የተለመደ አሞሌ ጨውዋቸውን እያሸተቱ አልጋቸው ላይ ተደፍተው ሲያለቅሱ ይውላሉ ። ሚላኒና ቻርለ. ከአጎታቸው ጋር በጣም ስለሚግባቡ ለማስታረቅ ብዙ ጊዜ ሞክረው ነበር። እላቸው ግን እንደ ሕፃን ልጅ ሌምቧቸውን ዘርግተው አሻፈረኝ አሉ ። ሐንሪ ዕዳቸው ነውና መቻል አለባቸው ። ቻርለስና ሚላኒ ከዚህ ሁኔታ የተረዱት አልፎ አልፎ በዚህ በደባል ኑሯቸው ውስጥ ጭቅጭቅ መኖሩ ደስታ እንደሚሰጣቸው ነው ።

እጮት ሐንሪ እስካርሌትን ገና እንዳገኛት ወደዳት ። ምንም እንኳን ቆሎ ስሜቷ የመነካት ነገር እንደሚያጠቃት ቢያውቅም በመጠኑ ብስለት ያላት መሆኗን አይቶ ወደዳት ። ለፒቲና ለሚላኒ የውርስ ገንዘብ ብቻ ሳይሆን እስካርሌትም ከቻርለስ ለወረሰችው ንብረት ባለአደራ ነው ። እስካርሌት ፣ ቻርለስ የወ/ሮ ፒቲን ቤት ግማሽ ብቻ ሳይሆን የእርሻ መሬትና የከተማ ቦታና ንብረትም ጭምር ስለተናዘዘለት ትልቅ ሴት የመሆኗ ነገር በድንገት ደራሽ የደስታ ጮርቆ አዋለቅልቋታል ። የውርሷ እኩል የሆነው ፣ በማምጃ ቤቱ አካባቢ ካለው መንገድ አጠገብ የተሠራው መጋዘንም ጦርነቱ ከተጀመረ በኋላ ዋጋው በሶስት እጥፍ እድጓል ። እጮት ሐንሪ አንደኛዋን አትላንታ እንድትቀመጥ የጠየቃት ቻርለስ በወርሷ የተ ወላትን ንብረት ዝርዝር በሚተነትንላት ጊዜ ነበር ።

"ሕፃኑ ዋድ ሐምፕተን ሲያድግ ፣ በጣም ሀብታም ወጣት ይሆ ናል ።" አለ ። " አሁን አትላንታ እያደገች በሄደችበት ፍጥነት አንፃር በሃያ ዓመታት ውስጥ የንብረቱ ዋጋ አስር እጥፍ ያድጋል ። ታዲያ ልጁ ንብረቱን እያየ ቢያድግ ወደፊት እንዴት መቆጣጠር እንዳለበት ይረዳል ። . . . እምን ፣ የሚለኒንም የፒቲንም ንብረት እንዴት እንደሚቆጣጠርም ይማራል ። ከእንግዲህ እኔ ምንም ያህል በሕይወት ስለማልቆይ ከሐሚልተን ዘር የሚቀር ወንድ እሱ ብቻ ይሆናል ።"

እጮት ፒተር ፣ እስካርሌት ወደዚህ የመጣችው እንደኛዋን ለመ ኖር ነው ብሎ ተቀብሎታል ። በሱ ዕምነት የቻርለስ ልጅ እሱ እየ ተቆጣጠረ ማሳደግ በማይችልበት አካባቢ ማደጉ አይሞየለትም ። ለዚያ ሁሉ ከርከር እስካርሌት የመለሰችው መልስ ፈገግታ ብቻ ነው። እትላንታን እንዴት እንደምትወዳት ሳታጠናና ከባሏ ዘመዶች ጋር አብራ የመኖሯን አስተማማኝነት ሳታረጋግጥ መልስ ለመስጠት አልፈለገችም ። በዛ ላይ ገና ጀራልድና ኤለንንም ለማሳመን መቻል

@OLDBOOKSPDF

አለባት ። ከዚህ ሁሉ በላይ ግን አውን ታውን የመናፈቋ ነገር አሳ ስቧታል ። ታራን እንዳንድ ነገር ናፍቃታለች ። እነዚያ ቀያይ የእርሻ ማሳዎች ናፍቀዋታል ። ከመሬት እንጉቱን ቀና ያደረገው አረንጓዴ የጥጥ ተክል ናፍቋታል ። ያ የምሽት ጀምበር ጥልቂያ ሰዓት ላይ መንደሯን የሚሜን እርጭቃ ናፍቋታል ። ጂራልድ የዚያ መሬት ፍቅር በደሟ ውስጥ እንዳለ የነገራት ሁሉ አሁን ለመጀመሪያ ጊዜ ትርጉሙ እየገባት መሆኗል ።

ስለዚህ ለምን ያህል ጊዜ እንደምትቆይ ለተጠየቀችው ጥያቄ ቁርጥ ያለ መልስ ከመስጠት ለጊዜው ተቆጥባ ፀጥ ባለው የጢኽ ትሪ ጉዳና ጫፍ ላይ ያለውን የቀይ ሸክላ ቤት ኑሮ በደፈናው ተያይዛዋለች ።

ከቻርለስ ዘመዶች ጋር እየኖረች ፡ ቻርለስ የመጣበትን ቤተ ሰብ ስታይ በእንድ ጀምበር ሚስት ፡ በሌላ ጀምበር የመጉት ሚስት ደሞ በሌላ ጀምበር የልጅ እናት ያደረጋት ሰው አሁን በመጠኑ እየገባት ፡ ግንኙነቱ በትንሹም ቢሆን እየታወቃት መጣ ። ለምን ዓይነ አፋር እንደሆነ ፡ ለምን ግልጥ እንደሆነና ለምን ሀሳቡን ተማባሪዋ ለማድረግ ያቅተው እንደነበር ለማወቅ አሁን ቀላል ሆነ ። ቻርለስ ግንባሩን አስማጠፍን ፡ ልበ ሙሉነትንና ቁጡነትን ከወታደር አባቱ በደም የወረሰ ቢሆንም እንኳን ፡ በሴታ ሴት አስተዳደጉ ምክንያት ጭንቀው ጨጥጥ ብሎ ከደሙ ወጥቷል ። ነገረ—ሥራቸው ሁሉ እንደወጉን ከሆነው ከወ/ሮ ፒቲና ከወንድሞቹ ይልቅ ከሚቀርባት ከሜሰኒ ጋር በጣም የጠበቀ ወዳጅነት ኖሮት ያደገ በመሆኑ ፡ በዓለም ላይ በጣም ለስላሳና ተወዳጅ የሆኑትን ሁለት ሴቶች እንስታዊ ፀባይ ወረሰ ።

ወ/ሮ ፒቲያት የዛሬ ስልሳ ዓመት የጠሳችው የመጀመሪያ ስም ማሪ ጀን ሐሚልተን ነበር ። ነገር ግን ዱሮ አንደ የሸጹ አባታቸው ፡ የልጅነት ቅብጥብጥነታቸውንና የሚወላከፉ ትናንሽ እግሮቻቸውን አይተው እንደ ቅልድ የሰጧቸው የቅጽል ስም እስከዛሬ ዋና ስማቸው ሆኖ ቀርቷል ። ማንም በእውነተኛ ስማቸው አይጠራቸውም ። ከዚያ በተከተሉት ዓመታት የቅጽል ስማቸውን የሚጸረሩ ፡ ከልጅነት ስማቸው ጋር የማይሄዱ ብዙ ፀባዮች አብቅለዋል እናም ከዱሮዋ ከምትበርቅና ድክ ድክ ከምትል ሀዳን አሁን ለሳቸው የተረፉቸው ወፍራሙን ሰውነታቸውን ለመሸከም የማይችሉ ቀጫጭን እግሮቻቸውና ያለ አላማ የመፈንደቅ ፈሊጣቸው ናቸው ። አንድ ጊዜ ያሉት ካልሆነ ድርቅ ብለው ይሟገታሉ ። ፊታቸው ያደረ ሰምባ የመሰለና ብርማ በጉር ያሳቸው ናቸው ። ቀሚሳቸውን በመ

@OLDBOOKSPDF

ቀኑታቸው ጥብቅ እደርሳለሁ በሉኝ ብዙ ጊዜ ለመተንፈስ በመጠኑ ይቸገራሉ ። በትናንሽ ነጠላ ጫማ ውስጥ በግድ ያስገቧቸው ትናንሽ እግሮቻቸው ከአንድ አጥር ማዘ. እስከሚቀጥለው አጥር ማዘ. ድረስ መሄድ ያቅታቸዋል ። በማናቸውም የደስታ አየር የሚታሰል ልብ አላቸው ። ትንሽ ተንኰሰ የሚያደርግ ነገር ከገጠማቸው ግን ያለሀፍረት ሚኩረፉቸውን እያሳዩ ሊሞቱ ይሥርሳሉ ። ልቤ ፈሰሰች እያሉ ሊወድቁ እስኪቃረቡ ድረስ የሚያቃስቱት እጎደው ለስው ይም ሰል መሆኑን የማያወቅ የለም ። ነገር ግን ሰው ሁሉ ስለሚወዳቸው ይሠን አመላቸውን አጋልጡ ወይም ቀጣፊ ብሎ የሚያስቀይማቸው የለም ። ሁሉ ሰው ይጠዳቸዋል ። እንዲሰዋን እያሞላቀቀም አበሳሽቷ ቸዋል ። እንደሱምነገረኛ የሚቀበላቸው አንድም ሰው የለም ። ሃገ ራቸውን የምሩን የሚወለድ አጎት ሐንፈ ብቻ ነው ።

በዓለም ሳይ ከማናቸውም ነገር የቀሸለ የሚወዱት ሐሚታ ነው ። ምግብ እንኳ ከሚወዱት በላይ ሰው ማማት ይወዳሉ ። ስለ ዚህም ከልባቸው ሰመጡት ብለው ሲይሠኝ እንደው ሰአፍ አመ ሳቸው የሌሎችን ጉዳይ እያኔ ሰብዙ ሰዓት ሲያጡ ፣ ቢቸረድዱ ይመሳሉ ። ስሞች ፣ ቀኖች ወይም በታሞች የማስታወስ ችሎታ የሳቸውም ። የአትላንታን ድራማ ቀዋንያን ከሰላ ተዋንያን ጋር ያሞታሉ ታል ። ሆኖም ማንም የሰቸገኝ ነገር ከሞር ወሰዶ የሚሞኝ ስለሌለ ማን ንም እያስቀይመውም ። የሚዘገንን ወይም ስው በሰማው ንጡርነት ያለው ምንም ምንም ዓይነት ሠራ የሚንሣራቸው የለም ። ምንም ስልሳ ዓመት ቢሞላቸውና ቢያረጁ የመሬቷ ሃሰግታ ፍላጎታቸው ግና እሳረጀ ምና ዓይኖቻቸውም እንኳ እሷሃ አሮጌ ልጅ ከሚሥጠር ከልል የማግለል ቤራቸውን እንዳልፍሳቸው ይዋራሉ ።

ሚሳኒ ስክስታቸው ትመስላለች ። እፅ ዓይን እኖርነቱም ፡ በድ ንጋጤ ሬድ መቅላቱም ትዘትናውም ተዋሀዷታል ። በቂ የማስተዋል ችሎታውም አላት ። "ከሞላ ንይል የምቀበለው ነገር ኑው መቼም" አለች እስክርሌት በፎቧ ፡ ከራቷ ጋር እየቀማጥላች ። ሚሳኒ ወሪሞ ፕቲ እንደሆኑት ሁሉ ከአዋቂ ተክለሰው እንዳደገ ምንም እንደማያጨቅ ልጅ ናት ። ነገር ግን ከክፉት ጋር እንዳልተዋወቀ ልጅ ርህራሄ ፡ ፅሙትነ ፡ ፍቅርና ሞኝነት አሰት ። ክፉት ቢያጋጣማትም ፈጽን ታዝ ርበታለች ። ሁልጊዜም ደስ ብቷት የምትኖር ስለሆነ ባከብቢዋ ያለ ሰው ሁሉ ደስ ብሎት እንዲኖር ትሻለች ። ከልሆነም ቢያንስ በራሳቸው እንዲደሰቱ ታደርጋለች ። ይሠን ቀናንቷን ለማርከት ስትል ግንኙም ቢሆን በጎ ንኦነ ማየትና በጣም አድንቆ ማሙራት ባህ

@OLDBOOKSPDF

ሪዋ ነው። የፈለገው ደደብ ሠራተኛ እንኳ ቢሆን እንዲት ጠቢ ታህል መታመንና ደግነት ሳታገኝበት ቀርታ አታውቅም ። የፈለገችው አስቱያሚ ልጃገረድ ለምን አትሆንም ፣ በሷ ቤት ፣ ወይ ግርማ ሞገስ ፣ ወይ የለውነት ቅርጽ አሊያም የጨዋነት ፀባይ የሴላት አንድም አትሟርም ። የመጨረሻውን ጥጋቢለና አሰልቺ ሰው እንኳ በእርግጥ የሆነውን ትታ ሊሆን የሚችለውን መልካም ነገር ማየት ትመርጣለች ።

ከደግ ልቧ ያላንዳች ማስመሰል በቅንነት በምታመሳጫቸው በነዚህ የመሳሕትት ፀባዮቿ ምክንያት ፣ እያንዳንዱ ሰው አጠገቧ መቀመጥ ይወዳል ። ደሞ ትክክል ነው ። ራሱ እንኳ በራሱ ውስጥ አለ ብሎ ያሳሰበ ያላሰመውን ነገር እሷ አግኝታ ከምታደንቅ ቅድስት ሴት ጉን ማን ይርታል ፣ በክተማው የሷን ያህል የሴት ጓደኛ ያለው ማንም የለም ። ከማንም የበለጠ የወንድ ጓደኞችም አሏት ። የወንድ ወዳጆችና አፍቃሪዎቿ በጣም ጥቂት ናቸው ። ምክንያቱም የወንድን ልብ ማጥመዱን እግዚሐለ ወዳድነት ሰለምታየውና ለዚህ ፈቃደኝነቱ ስለሌላት ነው ።

በአካባቢ ያሉትን ሰዎች ኑሮ እንዲቀልላቸው ሚድረግና በራሳቸው እንዲደሰቱም ሚድረግ የጀቡብ ሴቶች በጠቅላላ ከልጅነት እስከ አውቀት የተማሩት ማብረግብኔት ነው ። የደብቡን ህብረተሰብ ደስተኛ የሚያደርገው ይሄ እንከታዊ የማበደሰቹ መላ ነው ።

ወንዶች ደስ ብሏቸው የሚኖሩበት ፣ ባሳንጣ ሳያፈሩ የሚገናኙበትና ድንግል ብቡንነታቸውን ያለተቀናቃኝ በይዞታነት አጽድቀው የሚቀመጡበት አገር ለሴት ልጅ መኖሪያ በጣም አስደሳች መሆኑን ሴቶቹ ያውቃሉ ። ስለዚህም ወንዶቹ በራሳቸው የሚደሰቱ እንዲሆኑ ሴቶቹ ከልደት እስከሞት ይጣጣራሉ ። በዚህ የረኩት ወንዶች ደግሞ በቆራጥነትና በአድናቆት ብድራቸውን ይከፍሏቸዋል ። በእርግጥ ወንዶቹ ለሴቶቹ በዓለም ላይ ከእንድ ነገር በስተቀር ሁሉንም የፈለጉትን ይሰጧቸዋል ። ይሄ እንድ ነገር ያውቃሉ የመባል ክብር ነው ። እስካርሌትም የሚላትን ዓይነት ለዛ እግኝታለች ። ነገር ግን የሷ ለዛ የተፈጥሮ ሳይሆን በጥናትና በጥበብ እንዲሁም በሰለጠነ እንስታዊ ዘዴዋ ያገኘችው ነው ። በሁለቱ ሴቶች ማህል ያለው ልዩነት ፣ ሚላኒ ደግ የምትሆነውና ደግ የምትሠራው ሰዎች እንዲደሰቱ ብላ ሲሆን ፤ እስካርሌት ግን የራሷን ፍላጎትና አላማ እግብ ለማድረስ ብቻ መሆኑ ነው ።

ቻርለስ ከሚወዳቸው ከሁለቱ ሴቶች ምንም የሚያጠነክረው ነገር አላገኘም ። ጭካኔንም ሆነ ተጨባጭ ድርጊትን አልተማረም ።

@OLDBOOKSPDF

የተወለደ፥ ያደገና ነብስ እስኪያውቅ የኖረበት ቤት እንደወፍ ጐጆ የሰለለና በእርግብ ላባ የተደለደለ ነበር። ከታራ ጋር ሲነፃፀር በጣም የረቃ ቅዝቅዝ ያለና እሮጌ የጨዋ ቤት ነው። እስካርሌት እንዳስተዋለችው ከሆኑ ይሄ ቤት የወንድ ጠረን፥ የወንድ ሽታ ያለህ እያለ የሚጮህ ቤት ነው። ይህ ቤት የብራንዲ፥ የትምባሆና የቆዳ ቅባት ከወንድ ጠረን ጋር ተሻሽቶ የሚፈጥረው ተባዕታዊ አየር ይነሰ ዋል። ይህ ቤት የጮርናናና እንዳንዴ የሚሰደብ ድምጽ ረሀብ ይዞ ታል። ይህ ቤት ጠመንጃ ስቀሱብኝ ይሰል። የጮረምሳ ድምጽ እን ዲሻከረው ፥ ኮርቻ እንዲሟን እንዲራገጥበት፥ አጸኃ ውሻ እንዲ ጮኽበት በብርቱ ይለምናል። እስካርሌት ያንን ኤሰን ሆር ባለች ቁጥር የምትሰማውን የሁለቱን ሰዎች የጠብ ድምጽ፡- ወይ የሚሚና የፖርክን የጠብ ጭራ ወይም ደግሞ ያሮዛንና የቲናን አለበሳቢት ምላስ አሊያም እሷ ራሷ ከሱዌሰን ጋር ስትጣላ የምትሳደበውን እን ጀት የሚያቆለል ስድብና የጀራልድን የማስፈራሪያ ቁጣ አሁን በጭራሽ ለታገኛቸው አልቻለችም። ታዲያ ቻርለስ ከእንዲህ ያለው ቤት ወጥቶ ሲታ ሲት ቢሆን ምን ይሃርግል። እዚህ ቤት እኮ ሳቅና ጨዋታ እንገታቸውን አስገብተው እያውቁም። ድምጽ ከጥ ተዶርጎ ተወርቶ አይታወቅም። የሀሳብ ልዩነት ያለው ሰው ሀሳቡን ተሸቆ ጥቅጠ ነው የሚገለጸው። በዛ ባይ ማድቤት ያለው ጥቁር ባሪያ ፈላጭ ቆራጭ ንጉሥ ሆኗል። እስካርሌት መጀሀ ስትመጣ ከማሚ ልጓም አመለጥኩ ብላ ነበር። ሆኖም የቻርለስን ሚስት በጥበቅ እቆጣጠራለሁ የሚለውና የሴት ዓይነት ነገናዛ ጠባይ ያለው አሳት ፒተር ከማሚ የባሰ ጣኑቃ ሆኖባታል። ከደጉ መጀማቡ።

በዚህም ብላ በዚያ አስካርሌት እዚህ ቤት ከመጣች ወዲያ ልብ ገዝታለች። የጥንቷን እራሷን አጥፍታለች። ወዲያውም ምንም ልብ ሳትለው መንፈሷ ወደጨናማ በታው መመለስ፥ ቀልቧ ሁሉ መረጋጋት ችሏል። ዛና አስራ ሰባት ዓመቷ ነው። በጣም የሚደነቅ የአካል ጤንነትና ታይል አላት። የቻርለስ ዘመዶች ደግሞ በተቻ ለው ሁሉ ደስተኛ እንድትሆን ያልተቆጠበ ጥረት ያደርጉላታል። ይህን በሚያደርጉበት ጊዜ ጥቂት የመሳሳት ችግር ቢፈጠር እንኳ የነሱ ጥፋት አይደለም። ምክንያቱም እሷ የአሽሌይ ስም በተጠራ ቁጥር ለሚነሳባት የልብ ህመም ምንም ዓይነት ፈውስ ሊሰጧት አይችሉምና ነው። ሜላኒ ደግሞ በጣም ብዙ ጊዜ የአሽሌይን ስም ትጠራለች ዘ ያም ሆኖ ሜላኒና ወ/ሮ ሚቲ እሷን ለማባበልና ያለ ቃያታል ብለው ከሚያስቡት ሐዘን ለመገላገል ደክመኝ ሳይሉ ይፍ ጨረጨራሉ። እሷን ልጧን እንመለሰሰን ብለው የራሳቸውን ሀዘን ወደጎን ትተው መከራቸውን ያያሉ። ምግቧን እየተሰዋወጡ በደምብ

@OLDBOOKSPDF

እንድትበላ ያደርጋሉ ። የክሰዓት በኋላ እንቅልፏ እንዳይጓደል በተ ቻለ ያስተኳከላሉ ። ሠረገላ እየነዳች አየር እንድትቀበል ያደርጋሉ። እንደልቧ የመሆኗን ነገር ፥ ማናለብኝነቷን ፣ መንፈሰ ሙሉትነቷንና ፈሽቃ ወዳድነቷን ፣ የሰውነቷን ቅርጽ ፥ ትናንሽ እጅ እግሮቿንና ነጠሳ ጀሪዋን በየጊዜው ከማድነቅ አልፈው ተርፈው እያቀፉ እየሳ ሟት እንደሀዘኑ ልጅ እያሻሹት ፍቅራቸውን በመግለጽ አለቅጥ ያሞካ ሿታል ።

እስክርቤቶ መቃቅሯና መሳሙ ምንም ስሚት አይሰጣትም ። መሞላቷን ግን እኔደጠየት በሐይ ልቧን ከፍታ ተቆጣጥሮለች ። መቼም በድፍን ታራ ከሰሏ ይሄን ያህል መለካም ንገር ተናግሮ የሚ ያወቅ ሰው የለም ። እንዲያውም ማሚ ጊዜዋን የምታሠፋው እሷን በመሠውስ ነው ። ትንሹ ዋድም እያበሳጫትም ።ቤተሰቡ በሙሉ ጥሩር ከነጭ ያጫውትዋል ። ትረቤኮ በሙሉ ማሙሽ ማሙሽ ይለዋል ። እን ዲያውም እኔ ልቀፈው እኔ ልቀፈው ጠርነት ነው ። በተለይ ሚሳኒን በማቀፍ የሚቀድማት የለም ። ምርር ብሎ በሚያለቅስበት ሰዓት እንኳ "ወይ የኔ እምበሳ ምነው የኔ ልጅ በሞንክ" ትላለች ሚሳኒ ።

እስክርቤቶ አንዳንዴ ስሜቷን መደበቅ ያቅታታል ። ምክንያቱም ወ/ሮ ፕሮን እሁንም ትዝባህ አሮጌት አድርጋ ስለምታያቸውና ጭቅ ጭቃቸው ስለሚያበሳጫት ነው ። ቀናት እየገፉ በሄዱ ቁጥር በሚሰኒ ላይ ያሉት የቅናት ጥሰቻም እየበረታ ሄደ ። እንጽጅድ ጊዜማ ሚሳኒ ሰለ አሸሔይ ከራት በኮሞሳ ፍቅር እየተናነረች መይም የኤፈውን ፍቁሳቢ እያነበበች ሰለች እስክርቤቶ ድንግት እንደ ሰብድ ብደሚ ብሳ ትመዋለች ።ዋቻ ወሣም ወረኗ በዛ እክባቢ ሊኖር የሚችለውን የመ ጨረሻ ደስተኛ ሀይወት ለማሣየት ችሳች ። ከሳሻናም ሆን ከቮርል ስተን ወይም ከታራ የኮሻሰ እትሳንታ አለደሉም ናት ።

እትሳንታ ሙስሞ በተረጠረው ከሰዋርነት በመጣ ሥራ ምክንያት ስት ቦዝን ወይም ሚጻ ማጸውት ስትባዝን የምታሳልፈው ጊዜ የሳትም ። እንዳንዴ ግን ሻማሞን እጥፍ ራሷን ትራበ ውስጥ ቀብራ— "ወይኔ እሸሔይ ባያገባ ኖሮ በዚያ በሰሽቃ በተሰከፈ ሆስፒታል ውስጥ ባልሠራ ኖሮ፣ ወይኔ ሌሎች ፍቅረኞች ቢኖሩኝ ኖሮ!" ማለቷ አልቀ ረም ።

የነርስነቱን ሥራ መጸያውት ጠላችው ። ጓሩ ምን ያረጋል በወይ ዘሮ ሚደኖ በወዬዘር ሚፈዌዘር ኮሚቴምች ውስጥ ስለምትሠራ ዝማ ያታዋ መሸሽ አልቻለችም ።ይሄ ማለት ደማም ሠኮሯን በፎጣ ጠቅ ልላና ከሳይ አስከታች ድረስ ሽርጧን አድርጎ በዚያ በወበቅ በተሞ ላና በሚከፈሉ ሆስፒታል ውስጥ ስታረተርት መዋል ማለት ነው ።

@OLDBOOKSPDF

እያንዳንዱ በአትላንታ ያለች የሙት ሚስት ወጣትም ትውን እሮጊት እስክርሌትን እጉል ወግ —ማጥበቅ እስኪመስላት ድረስ የነርስ ነቱን ሥራ በጉጉት ታጣድፋለች ።እነሱን እንደጉድ በሚያራሩጣቸው አላማና አገር መውደድ እንደምታምን አድርገው ይገምታሉ ።እሷ ለጦርነቱ ቅንጣት ታህል ፍላጐት እንደሌላት ቢያውቁ መቼም ደንግጠውም አያባሩ ።አቨሌይ በጦርነት ላይ ሊሞት ይችላል ከሚለው ስጋት በለተቀር ጦርነት ብሎ ነገር ምኑም አይጥማት ። ቁስለኛ የማከሙንም የሆስፒታል ሥራ እንዴት እንድምትገላገለው ስለማታውቅ ብቻ ነው እንጂ ለአንዲት ደቂቃ ውስጡ የመቆየት ፍላጐት የላትም ። ደሞ ያለጥርጥር በነርሰነት ሥራ ውስጥ ምንም የሚያዝናና ነገር የለበትም ።ሰሷ ነርስነት ማለት የጣርና የሲቃ ድምጽ ፣የአዕምሮ ሁከት ፣ ሞትና እስቀያሚ ጠረን ማለት ነው ።ሆስፒታሎቹ በእድፍ በነተቡ ፣ እንደጨጐጊት ጺማቸው በሚኮሰኩስ ፣ ቁስል እንደወረሰው አውሬ በሚከረፉ ሰዎች የተሞሉ ናቸው ።የቁስላቸው ማመርቀዝና የመከርፋት የመግማታቸው ብዛት የመጨረሻውን አዛኝ ከርስቲያን እንኳን አጥወልውሎ እሚጥል ነው ። የሆስፒታሉ የቁስል ከርፋት ጉኖ ከበሩ ሳትገባ አፍንጫዎን ሲበጥሰት ይደርሳል ። እጅዋ ላይና ፀጉሯ ላይ የሚቀረው የሚያቅለሸልሽ ሽታ በህሊሟ ሳይቀር ሲያስመልሳት ይታጣዋል ። የህንብና የትንኝ መሳጭ በሰሞቹ ቁስል ላይና በክፍሎቹ ሁሪያ ጢዝ ዝዝ እያለ ቁስላቸውን እየንከሰ ያስሬሣቸዋል ።ያስልቅሳቸዋል ።እስክርሌት ፤ ትንሿ የንስሳትን ቦታ እያከክሽ በሰላሳው አጅዋ ማራባቢያውን ይዛ ትኳዋዋ እስኪንጠል ድረስ ታወዛውዛለች ።መቼም እነዚህ ቁስለኞች ሞተውላት ቢያርፉ እንዴት ደስታዋ ነበር ።

እስክርሌት ለጨዋ ሴት ትልቅ ውርደት ነው ብላ የምትጣጣላቸው ሽታ ፣ቁስል ወይም እርጅና ገላ በሞላበት ቦታ መቀመጥ ለሚለኒ ምንም ስሚት አይሰጣትም ።ብቻ እንዳንዴ ዶክተር ሚድ የበሰበሰ ቁስል ያለበትን ገላ ቅጭር ሲያወጣ ሚዘንባ የቀዱ ጥፍና ዕቃዎቹን ይዛ ስትቆም ፊቷ ንጭ ይሆናል ። እንዳውም እንድ ቀን እንዲህ ያለ ቀዱ ጥፍ ከጭኳደደ በኋላ ጣሳኒ ሆዱ አንሰላ ማስቀመጫው ከፍል በርጣ ላይ ስታስመልስ እስክርሌት አማኝታታለች ። ሆኖም ሜላኒ ቁስለኞቹ ፊት ከሆነች በጣም ቻይ ፣ አዛኝና የደስ ደስ ያላት ሆና ለሰምትታይ በሆስፒታሉ ያሉት ሰዎች መልወክ ምህረት ብለው ይጠሯታል ። እስክርሌትም በዚህ ስም ብትጠራ ትወድ ነበር ።ነገር ግን ይሄ ስም በውስጡ ቅማል የወረሳቸውን የሚድሁ ሰዎች መንካትን ፣ ትንፋሽ እጥሯቸው ህቅ እንት የሚሉ በሽተኞች ትምባሆ አትሩቸው እንደሆን ለማረጋገጥ ጉሮሯቸውን በጣት መጻበስን ፣የተቆረጠ እግር በፋሻ ግሽግን መግል የያዘን

@OLDBOOKSPDF

ቁስል እዞን እያወጡ ቁስሉን ማጠብን ነይጠቅልላል ።የለም ነየለም ይሄ ነርስነት ብሎ ነገር በጭራሽ አይጣጣትም ።

አስካርሌት ምናልባት የሚያገግሙት ወንዶች አብዛኞቹ ከደህና ቤተሰብ የመጡና ቁንጅዎች በመሆናቸው እነሱን የማሳሳትና የማጫወት ሥራ ቢሰጧት እዚህ ቦታ ለብዙ ጊዜ የመቆየት ትዕግሥት ይኖራት ነበር ። ዳሩ ግን የመጣ ሚስትነቷ ይህን እንዳታደርግ ያግዳታል ።የከተማይቱ ወጣት ሴቶች በልጅነት ዓይናቸው አሰቃቂ ነገር ካዩ ድንጋጤው እበሽታ ላይ ይጥላቸዋል ተብሎ ስለሚፈራ የማከምና የመጠን ሥራ አይፈቅድላቸውም ።ስለዚህ የማገገሚያው ክፍል ሀላፊነት ተሰጥቷቸዋል ። የትዳር ሆነ የመጣ ሚስትነት ችግር ስለሌለባቸው የሚያገግሙትን ሰዎች በመግባባት ረገድ ይህና ዕድል አግኝተዋል ።በመሆኑም የመጨረሻዋ አስቂያሚ ልጃገረድ እንኳ ባል የማግኘት ችግር እንደማይገጥማት አስካርሌት ተገንዝባ ሰች ።

በሞት አፋፍ ካሉትና በአስቃቂ ሁኔታ ከቆሰሉት ወንዶች በስተቀር ፣ የአስካርሌት ዓለም የሴቶች ዓለም ነው ። እሷ ደግሞ ከነገሯ ሁሉ ሴቶችን መውደድም ሆነ መጥላት አይሆንላትም ።ከዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ በጣም ይስለቻታል ። ያቺ ሆዋ በሳምንት ሶስት ቀን የሚሰነ ዓደጉኞ በሚመሩዋቸው የስፌት ክበቦችና የፋሽ ጥቅለሳ ኮሚቴ ዎች ውስጥ መሳተፍ አለባት ።ቻርለስን የሚያውቁት ሴቶች በሙሉ ያዝኑላታል ፣ ይንከባከቧታል ።በተለይም በከተማይቱ በጣም የታወቁት የሙሳ እጅግ ሚስቶች ልጅቱ ፋኒ ኤልሲንግና ሜይቤል ሜሪዌዘር በጣም ይራሩላታል ። ሆኖም የሚያዩዋት እንደበታትና እንደጀኗች አሮጊት በመሆኑ ያሰላጫታል ።ወሬያቸውም ስለዳንስና ስለጥቅ ረጮቻቸው በመሆኑ አንድም በደስተኞነታቸው ትቀናለች ፣ አንድም ይሄ የሙት ሚስትነቷ በነጠቃት ነፃነት ትንገበገባለች ። ወቸ ጉድ! አስካርሌት እኮ ከሩኒም ሆነ ከሜይቤል ሶስት እጥፍ የቆነጀች ሽጋ ልጅ ናት!! ሀይወት እንዴት አድሎኛና ጨካኝ ነው በሉ! ልቧ ከሚቹ ጋር መታሰር ገብቷል ብለው የሚያስቡትስ ምን ያሉ ጭቦኞች ቢሆኑ ነው! አላወቁም እንጂ የሷ ልብ እኮ ቨርጂኒያ ውስጥ ከአሽሊይ ጋር ተቀምጧል !

አስካርሌት የሚያስከፏት ነገሮች ቢኖሩም ፣ ምኞቷን የሚያሟሉላት ሳንካዎች ቢያጋጥሟትም አትላንታ አስደስታታለች ። ስለዚህም ማም ንታት በጨመሩ ቁጥር የዘመድ ጥየቃ ጊዜዋም እየተራዘመ ሄደ ።

@OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ 9

የበጋው ጊዜ ተጋምሷል ።እስካርሌት ማለዳ መኝታ ቤቷ እንደ ተቀመጠች በመስኮት ወደ ውጪ ታያለች ። እምብዛም ምኞት አልተሰማትም ።ሠረገላዎችና የጋሪ ተሽከርካሪዎች ሲቆሙን ፡ መታደሮችን ፡ ሞግዚቶችን ጭነው በፒች ትሪ ጐዳና ከከተማው ወጥተው ሲጓዙ ትመለከታለች ። ለሆስፒታሎቹ መርጃ የሚሆን ገንዘብ ለመሰብሰብ ስተዘጋጀው ባዛር ማሳመሪያና የድንኳን ማጊያጊያጫ እንጨት ለመፈለግ መሄዳቸው ነው ። ከየአናታቸው ቅርንጫፎቻቸውን መን ገድ ላይ ያስጐነበሱት ዛፎች ያንን የቀይ አፈር ጐዳና በከፊል ፀሀ ይና በከፊል ጥላ ውስጥ አድርገው የዳማ መጫወቻ ሰሌዳ አስመ ስለውታል ።የፈረሶቹ እግር በተነሳ ቁጥር ትንሽ ትንሽ የአቧራ ጉም ይፈጠራል ። አንዱ ጋሪ ሌላኛውን ይከተላል ። አራት አራት ኮስታራ ኔግሮዎች መጥረቢያ መጥረቢያቸውን ይዘው ከአረንጓዴው ጫካ ዛፍና የወይን ሐረግ ቆርጠው ሲመጡ በየጋሪው ላይ ተኩልክለዋል ። ጋሪዎቹ ከኋላ ዕቃ መጫኛያቸው ላይ ትላልቅ ባለክዳን ቅርጫቶች ፡ ሰዎች ለምሳ ማስቀመጫ የሚገለገሉባቸውን ከዋርካ የቀሡ ቅርጫቶችና በደርዘን የሚቆጠሩ ሁበሀቦችን ከምረዋል ። ሁሉት ጥቁሮች ባንጆና አርሞኒክ አፋቸው ላይ አድርገው “ኢፍ ዩ ዎንት ቱ ሀቭ ኤ ጉድ ታይም ጃይን ዘ ካቫልሪ” የተሰኘውን ዜማ ይጫወታሉ ። ከነሱ ቀጥሎ የ-ተደረደሩት ደስተኛ ልጃገረዶች ባበባ ያጌጡ ቀሚሶቻቸውን ሻሎቻ ቸውንና ባርኔጣዎቻቸውን እንዲሁም የፀሐይ መከላከያዎቻቸውን አድርገው ይዓዛሉ ። አርኒቶቹ ሴቶችም እንዱ ሠረገላ ላይ ያሉ ሰዎች ለሌላቸው ሰዎች የሚነግሯቸውን ቀልዶችና ጨዋታዎች እየሰሙ በረ ገግታ ተቀምጠዋል ። በሞግዚቶችና በጠንካራ ሴቶች ተደግፈው የተቀ መጡም ያገሙ በሽተኞች አብረው አሉ ። ሴቶቹ ያጨዋወቷቸዋል ። ከሠረገላዎቹ ጐን ጐን መኰንኖች በፈረስ በፈረስ ሆነው እንደቀንድ አውጣ እየተሳቡ ይሄዳሉ ። የሠረገላ ጐማዎች ከሸክም ብዛት የሲቃ ድምጻቸውን ያሰማሉ ።የፈረስ መኰልኰያ አርክቦች ቅጭቅጭ ይላሉ ። የፈረሶች መጣምሮች ያበራሉ ። የፀሐይ መከላከያዎቹ ይርገበገባሉ ። ማራገቢያዎች ከንፋሱ ጋር ይጫወታሉ ። ኔግሮዎች ይዘፍናሉ ። ሁሉ ሰው በፒችትሪ ጐዳና በኩል ወጥቶ ሰምለም የዛፍ ቅርንጫፍና ሐረ ጐችን ለመቁረጥ እንዲሁም ሁበሀብ ለማድጣት ወዲያውም ሽርሽር

@OLDBOOKSPDF

ብሎ ሲመጣ መሄዱ ነው ።"ከኔ በስተቀር ድፍን አገር ወደዚያው ይሄዳል" አለች እስካርሌት በሀሳቧ ።

ሁሉም እጃቸውን እያነሱ ለእስካርሌት አውለበለቡላት ።እሷም አፀፋውን በከብር ለመመለስ በትኧላት ሁሉ ሞከረች ።ነገር ግን አልሆነላትም ። ትንሽ ፣ ግን በጣም ሀይለኛ የሕመም ስሜት ከልቧ ጀምሮ ሽቅብ መጥቶ ጉሮሮዋ ላይ ተከማች — ከጥቂት ጊዜ በኋላ እምባ የሚሆን ሀይለኛ የሕመም ስሜት ።እንግዲህ ከሷ በስተቀር እያንጸንጹ ሰው ወደ ሽርሽር ሄደ ። ከሷ በስተቀር እያንጸንጹ ሰው ግቃ ወደ ባዛሩ ይሄዳል ።ከሷ በስተቀር እያንጸባረቁ ሰው በባዛሩ ላይ በሚደረገው ጸንስ ላይ ተካፋይ ይሆናል ።ከሷ ከሜላኒና ከወ/ሮ ፒቲፓት እንዲሁም እንደነሱ ከለታደሉ ሌሎች ሐዘንተኞች በስተቀር በከተማው ያለ ሰው ሁሉ ባዛሩ ላይ ይገኛል ። በድግሱ ይዝናናል ። ሜሊና ወይዘሮ ፒቲፓት እንኳ ቀሩ እልቀሩ ሰሟት አለሰጣቸውም ። ከናካቴው የመሄድ ሀሳጉ ትም አላደረባቸው ። ለእስካርሌት ግን ሩላል ነገር አይደለም ። ለመሄድ በጣም ትፈልጋለች ።

ይህ መቼም ጥሩ ሥራ አይደለም ።ለዚህ ባዛር ዝግጅት ከማንም ከከተማው ካሉት ልጃገረድ የተሻለ እንዲያውም እጥፍ የሠራች እስካርሌት ናት ።ከልቧ በጥታለች ።የሕፃናት ክፍያዎች ጠልፋለች ። ብርድልብሶችንና የእንሳት ርጫዎችን አዘጋጅታለች ።ጌጣጌጦችን ፣ ጣሀኖችንና ፍንጃሎችን ።የጠዎ መሲጫ ኩባያዎችን በቀለም አስው ባለች ።ማሟሸ ደርሀን የሚሆኑ የሶፋ ትራሶችን በክንፈዶፊሲው ባን ጺራ አንቆጥቁጣ ጠልፋለች ።ሼርማን ባንዲራው ላይ ያሉት ኮከቦች ሞላት ተዝንፈዋል ።በፈሎሹ ከሞላ ገደል መደከብነት መሰደ ቸዋል ። አንጻንዶቹ ስድስት አንጻንዶቹ ሰባት ያጨረር መስመር ሰርተዋል። ቢሆንም አጠቃላይ ውጤታቸው ሰምሯል)ትላንትና ለምሳሌ በፊት የዶሮ ቤት ከንበረው አሏራ የጠጣ መሣሪያ መጋዘን ውስጥ ቢጫ ሐምራዊና አረንጓዴ ቫካራ ጨርቆችን ስትዶረድርና ስታጣብቅ ሰው ነቷ እለት እሰኪለ ደክማ ነው ወደቤት የሄደችው ።በሴቶች የሆስፒታል ኮሚቴ ተጠጣሪነት የሚሠራው ይህ ሥራ ቀላል አልነበረም ።ከወ/ሮ ሜሪዌዘር ፣ከወይዘሮ ኤልሲንግ ኒና ከወይዘሮ ዋይቲንግ ሥር ሆኖ ሥራ መሥራት እንደባሪያ መነዳት ነው ።ሴት ልጆቻቸው እንዲሉ ዝነኛ እንድነበሩ የሚለፍፉትን ዲስኩር መስማት አራሱ አንድ አንጉለ የሚያዘር ነገር ነው ።በዛ ላይ ወ/ሮ ፒቲፓትና ኩኪ የሚያራረብ ኪክ ሲጠብሱ አግኟን ብለዋት እጅዋን አቃጥሏት ሁለት ጣቶቿ ውሀ ቋጥረዋል ።

እንደ ሜጀ ባሪያ ።እንደትሪላ ሲያለፉት ከርመው ታሜያ አሁን ፈሽታው ሲጀመር ከብር በሚባል ከንቱ ሽፉን ባዛሩ ላይ

@OLDBOOKSPDF

መጣኽት የለብሽም ማለት ነው ደህና ይሁኑልኝ ቤተሰቦች ፡ የሙት ሚስት በመሆ
ኗና በሚኖሯለው ክፍል የሚያስቅስ ልጅ ስላላት ከአገር ደስታና
ከአገር ፈቨታ የምትነጠል ከሆነ በእውነት ጥሩ ሥራ አልተሠራም።
ምነው የዛሬ ዓመት አይደለም እንዴ ይህን ጥቁር ከል ሳይሆን የሚያ
ምር ቀለም ያለው ቀሚስ ለብሳ ትደንስ የነበረውን ሁለት ሰስት
ዓመት አልሆነው ፡አምና አልነበረም እንዴ ሽክ ብላ ዘንጣ ያለችን
ዱኽ ዓይን ሚሸት ከሶስት የተለያዩ ወንዶች ጋር ትወዳጅ የነበረው ።
ግና አሥራ ሰባት ዓመቷ ነው አሁን ።አሣሮቿ ግና ብዙ ዶንስ ያሳራ
ቹዋል ። ዝንጣ ግና ብዙ መውረግረግ ይቀረዋል ። ዓይኖቿ ግና ብዙ
መስለምለም ብዙ መቁለጭለጭ ብዙ ማንጎት ይቀራቸዋል ። እረ
ምን የጉድ አዋጅ ነው በሉ ነበሯራሽ ጥሩ ሥራ አልተሠራም ።ሕይ
ወት ከጭብጧ ተፈልቅቃ እያመለጠቻት ነው ።ሕይወት ከጅዋ ወጥታ
በሞቃት የዚጋ ጥላ ውስጥ በተዝረጋገው በግራጫ የኒፎርሞችና በሚን
ቃጫቀርጪ እርካቦች እንዲሁም በአበባ በተጌጡ ቀማሶችና በባንጆ
ሙዚቃ በታጀበ መንገድ ላይ ነንደችባት ።ብጣም ውድ ጓደኞቿን
አስማና ጠማና ያዳነቻቸውን ሰምኛ ምንም ዓይነት ፈተማታ
ሳትሰጥና ያለአንዳች የዱስታ በጫት እጅዋን ታውለብልብላቸው እንኚ
የጉንጭን ስርጉዶች ሣን ለመሸሸግ አልሞከችም ። ከባሏ ጋር መታ
ብር ያልገባውን ልቧን እንደገባ ማስመሰል አልሆነላትም ።

እስክርሌት እጅ መንሳቷና ማውሰብሰቧ የኮሮረጠው ሁልጊዜ
ደረጃ ሲወጡ ማለክልክና ቁና ቁና መተንፈስ ልማዳቸው የሆኑት
ወ/ሮ ፒቲፓት ድንግት መጥተው ከመስኩቱ ገሎትው ሲወስዷት
ነው ።

"ምነው የእኔ ውንጅ አብደሽል ልብሽ ? ደሞ ብለሽ ብለሽ እመኝታ
ቤትሽ መስኮት ላይ ቁመሽ ሰውነሮች እጅሽን ታውለበልቢ ጀመር?
ነውር ነው ፡ሐፍረትህ እኔ ሠቼም ሳይሽ አመዷ ቡጎ ነው ያለው ፡
እናትሽ ይህን ብትሰማ ምን ትላለች ?"

"አይ መኝታ ቤቴ መሆኑንኮ እኔስ አያመቁም።"

"እንዴ መጠርጠራቸውስ ቢሆን ፡ያው እኮ ነው ። ነውር ከመሆን
አያስቀረውም ። አየሽ የኔ እመቤት ፡ እንዲህ ያለውን ነገር ከማድረግ
መቆጠብ አለብሽ ። ስው ልጇ ፡ እንኳን እንዲህ ተመችተሽው እንዲያ
ውም እንደያው ነው ፡ ሥጋሽን ነው በሐሜት የሚዘለዝለው ። ምን ጊዜ
እንዲህ ቀበጠች ?ባሏ ሠላት ዓመቱ ሳይወጣ እሷ መኝታ ቤቷ መስ
ኮት ላይ ቂጢጥ ብላ ትገለጥጣለች...ብቻ ተይው ። ያም ሆን ይህ ሌሎ
ቹም ባያውቁ ወ/ሮ ሚሪዌዘር መኝታ ቤትሽ መሆኑን ታውቃለች?"

"እኽህ አሮጊት ድመት መቼም በንዴ ፀንደሩን ይሰቀልቱታል።"

@OLDBOOKSPDF

"ምነው የኔ እመቤት ፣ አረ ስው እንዳይሰማሽ ዝም በይ ፣ዶሊ ሚሪዌዘር እኮ በጣም ወዳጄ ናት ።"

"ቢሆንም ከአሮጊት ድመትነታቸው አይለውጣቸውም ። ..ውይ በሞትኩት.. በቃ በቃ አክስቴ አያልቅሱ በቃ ፡ የመኝታ ቤቴ መስ ኮት መሆኑን እረስቼው ነው ። ይቅርታ ያድርጉልኝ ፣ ሁለተኛ አይለም ደኝም ። እኔ...እኔ..እኔኮ ሲያልፉ ለማየት ብቻ ነው ብት ያልኩት ። አባቴያቸው ለመሄድ ጓጉቼ ነው ።"

"እረ በጉዴ ወጣሁ!"

"አምን መሄድ አፈልግ ነበር።ቤት መቀመጡ ስልችት ብሎኛል።"

"እስካርሌት ፣በፈጠረሽ ሁለተኛ እንዲህ ያለ ነገር ካፍሽ ላይ ወጣ ቃል ግቢልኝ ።ስው እኮ የበና መጠጫ ነው የሚያደርግሽ ። ለምስኪኑ ቻርሊ ተገቢውን አክብሮት አልሰጠሺውም ።"

"ውይ ምነው አክስቴ አያልቅሱ"

"በሞትኩት አልቅሺ አንቺንም አስለቅስኩሽ" አሉ ወይዘሮ ፒቲ ፓት ፣መንሰቅሰቃቸውን ቀንስ እድገርው ከቀሚሳቸው ኪስ መሀ ረብ እየፈለጉ ።

ያ የሕመም ስሜት በመጨረሻ እስካርሌት ጉሮሮ ላይ ደረሰና ተከማቸ ። ጮክ ብሳ አለቀሰች ። ወይዘሮ ፒቲፓት ቻርሊ ትዝ ብሏት ነው ብለው አሰቡ ። እሷ ግን ያለቀሰችው የመጨረሻው የጋሪ ጉማ ድምጽ በመሞቱ መንገደኞቹ ርቀው መሄዳቸውን አስባ ነው ። ሜላኒ ፊቷን ጭንቅት እንዳመሰቃቀለው ፣ በጅዋ የፀጉር ቡሩሽ እንደያዘች የተ ለመደው ንዴህ ጥቁር ሀር ፀጉሯ መሬብ ስለሌለው እፊቷ ላይ እየፈ ሰሰና ማዕበሉን እያተራመሰ ከክፍሉ እየተንደረደረች መጥታ—

"ምንድነው ነገሩ፣ ምን ሆናችሁ?"

"ቻርሊዬ ነው"አሉ ወይዘሮ ፒቲፓት በስቅስቅታቸው ውስጥ ። እስካርሌት በቻርሊ ጉዳይ በማዘኑዋ ደስ ብሏቸዋል ። ጭንቅላታቸ ውን አሜላኒ ደረት ላይ አንጋለሉ ።

"ወይኔ ጉዴ" ፣ አለች ሜላኒ የወንድሟ ስም ሲጠራ ከንፈሯ እየ ተንቀጠቀጠ ።

"እስካርሌትዬ ባክሽ ጠንክር በይ፣ ባክሽ ለመርሳት ሞክሪ፣"

እስካርሌት አልጋዋ ላይ ተዘርራ መንሰቅሰቋን ቀጠለች ። ድም ጿን ከፍ አድርጋ ከንቱ ለባከነው ወጣትነት ተንሰቀሰቀች ። ልትደሰት

@OLDBOOKSPDF

በት ሲገባት ፡ልትገናናበት ሲገባት ለተነፈጓቸው የወጣትነት ነፃነት ተንሰቀሰቀች ።ሁሉን ነገር እያለቀሰ እንደሚያግኝ ህፃን ተንሰቀሰቀች ። አሁን ግን መንሰትሰት እንደማያዋጣ ስለአወቀች በንዴትና በተስፋ መቁረጥ ደጣማ ደጋግማ ተንሰቀሰቀች ።ራሷን ትራሱ ውስጥ ተብራ እግሯን እያንፈራገጠች እዬዬ አለች ።

"ምነው ሞቼ ባረፍኩት ፡"አለ ወ/ሮ ፒቲጋት በሀዘንና በስቅ ስቅታ ።በዚህ የሐዘን ኤግዚቢሽን ፊት ቆመው እንኳ ያ ፡እንኳን አዘ ውት ኀና ሲያስበት የሚወርድ እምባቸው አሁን ቀጥ ብሏል ። ሚሳኒ የወንድሟን ሚስት ለማባበልና ለማጽናናት ወደአልጋው ተጠጋች ።

"የኔ እናት ፡በቃ እታልትሺ ፡ቻርለ. ምን ያህል ይወድሽ እንደ ነበር አስቢና ትጽናኚያለሽ ።የውዱን አፍቃሪሽን ልጅ አስቢና ተጽ ናኚ ።"

እስካርሌት ከወጣትነት የደስታ ከለል የመገለል ሰቃይ ባንድ ወገን ፡ይዟን ስቃይዋን አሰመረዳታቸው በሌላ ወገን ባንድነት ጭጋ ምዶ አንደበቷን አሰራትና ቃል መናገር አቃታት ። አሰመናገሯ ግን በጅቷታል ። ምክንያቱም በስሚት ተግፍቷታ በዚያ ከጂራልድ በመረሰችው ግልጽና ቀጥተኛ አምንቷ አውነቱን ፍርጥ አድርጋ አጠያ ቸውን ዱብ ልታደርገው ትችል ነበር ። ሜላኒ ትክሻዋን መታ መታ እያደረገች ማጽናናቱዋን ስትቀጥል ወ/ሮ ፒቲጋት ደግሞ ግዙፍ ሰውነታቸውን በእግር ጣታቸው ተሸክመው ሄደው የመስኮቱን መጋረጃ ዘጉት ።

እስካርሌት "አትዝጉት እሱን" አለችና ጮኸች ፡በለቅሶ ሳምባ የመሰለውንና ያበጠ ፊቷን ከትራሱ ጥና እያደረገች ።"ይሄን ያህል እኔ ሞቻለሁ እንዴ መጋረጃ ለመዝጋት አትም ያጣሁ የሞታስመስ ሉኝ — ዳሩ ብሞት ይሻል ነበር ። ብቻ አሁን ብቻዬን ተዉኝ ።"

መልሳ ጭንቅላቷን ትራሱ ውስጥ ቀበረችው ። ጥቂት የዙክ ዙክታ ውይይት ከተካሄደ በኋላ አጠገቧ ቆመው የነበሩት ሴቶች ኮሽ ሳያደርጉ በእግር ጣታቸው እየተራመዱ ወጡ ።

ያረጀውን እየወረዱ ሳሉ ሜላኒ ለወ/ሮ ፒቲጋት እንዲህ ስትላ ቸው ሰማች ። "እስቲ ፡እስካርሌት ፊት ስለቻርለ ባታነሺ ጥሩ ይመ ስለኛል ። በጣም ይረብሻታል ። ምስኪን ልጅ ፡ፊቷ እንደዛ ዝብርቅርቅ ያለው እኮ ሳለማልቀስ ስትታገል ነው ። ምንም እንዳትጨነቅ ብናደር ጋት ጥሩ ነው ።"

እስካርሌት የአልጋውን ምንጣፍ አቅሙን በተሰለበ ንዴት መንቅራ ጣለችው ።የከፋ ስድብ ለመሳደብ እየተጣጣረች ነው ።

@OLDBOOKSPDF

"የሰማያቱ ያስህ"አለች ጮክ ብላ ። በመጨረሻ የእርዷታ ስሜት ተሰማት ። ይቺ ሚላኒ ግና በአሰራ ስምንት አመቷ እንዴት ለወንድሟ ህዘን ብላ ክፉ ሰብሳ ከፈሽታ ርቃ አቤት መቀመጥ ይቻ ሳታል ነወይ ጉድ ነሚላኒ እኮ ዕድሜ የሽምጥ እየጋለበ ጥሎን እንደ ሚሄድ አይታያትም ። ።በታውቅም ስሜት አይሰጣትም ።"

"ሣን እኮ የሆነች ለጭላ ፍጥረት ናት ።እንደኔ ዝነኛና ተወዳጅ አይደለችም ። ስለዚህ እኔ የማጣውን እጦት እሷ አታጣም ። በዛ ላይ... እህ እሽሉዬ አለሳት ። እሷ ማንም የልኝም ።"ርሄ ትኩስ ስሜት ትኩስ የሐዘን ጫናውን አሸክማትና ትኩስ የእንባ ዘለላ አፈሰሰች ።

እስካርሌት እመኻታ ቤቷ እንዳለች አስከሰአት ድረስ እንደጨ ፈገጋት ዋለች ።ወዲያው ቬርቬር ጉዳጉቹ ሲመለሱ የሚፈጥሩት ድምጽ አጎታትና በመስኮቱ አሻግራ ስትመለከት ጋሪዎቹ በሚከ ዛፍ ብወይን ሐረግና በትኖንሽ አጽዋት ክምር ተሞልተው አየችና ከፉት ። እያንዳንዱ ሰው በሀሰታ ብሳት የደከመ ይመስላል ።እንደጠ ዋቱ እጃቸውን አውለበለቡላት ።እሷም እየከበዳት አዕፋውን መለ ሰች ።ሕይወት አዙን ጉበፉ አሰቃራው ጉዳይ ሆኗለች ።በእርግጥም ድግሞ በዚህ ሁኔታ መኖር ዋጋ ቢስ ነው ።

እራት ተበልቶ ጋደም በሚባልበት ሰዓት እስካርሌት በጭራሽ ባልጠበቀችው ሁኔታ ወይዘሮ ሚሪዊዘርና ወይዘሮ ኤልሲንግ ሲጠይቋ ቸው መጡ ። እስካርሌት ሚላኒና ወይዘሮ ፒቲፓት በድንጉጭ ጉብኝ ምጽዋው ተደናግጠው የደረት ቁልፉችውን እየቆለፉና ፀጉራቸውን ላማ ላማ እያደረጉ መጀለልጭ ወረዱ ።

"የወይዘሮ በኔል ልጆች እኮ ኩፍኝ ያዛቸው" አሉ ወይዘሮ ሚሪዊዘር ።ወይዘሮ በኔልን ተጠያቂ ናቸው ያሚል ዓይነት አስተያየት እየተነበበባቸው ።

"የማክሰር ሴት ልጆችም ወደ ቬርጂኒያ ቅሎ ድረሱ ተብለው ተጠርተዋል"አሉ ወይዘሮ ኤልሲንግ ሲጮት በቱቃረበ ድምጻቸው ለምንም ነገር ግድ የሌላቸው መሆኑን በሚያሳይ ሁኔታ እየተምነቀ ነቁ ። "ዳሳስ ማክሰር ቆስቷል አሉ ።"

"እንዴት ክፉ መርዶ ይዛችሁ መጣችሁ" አሉ ሴኖቹ "ታዲያ አሁን ምስኪኑ ዳላ..."

"የለም ።እንደው ሥጋ ለሥጋ በትክሻው ውስጥ ነው ጥይቱ ያለፈው ።"አሉ ወ/ሮ ሚሪዊዘር ፊጠን ብለው ። "በዚህ በክፉ ጊዜ ሊደርስ የሚገባው ነገር አልነበረም ። ሴት ልጆቹ ይዘውት ሊመጡ

@OLDBOOKSPDF

ወደሰሜን ሊሄዱ ነው ።ያም ሆነ ይህ አውን እኛ ቶሎ መሄድ አለ ብን ።እዚህ ቁጭ ብለን ስናወራ አናድር መቼስ ።እዛው የመሣሪያ መጋዘን ሄደን የማጊያጊያጡን ሥራ መጨረስ አለብን ። ወ/ሮ ፕቲ አንቺና ወ/ሮ ሚላኒ ለዛሬ ማታ በወይዘሮ ቦኔልና በማክለር ሴት ልጅች ቦታ ተተክታችሁ እንድትሠሩ እንፈልጋችኋለን ።"

"ውይ ዶሊ ዛሬ አንችልማ"

"አልችልም የሚባል ነገር ካጭሽ እንዲወጣ አልሻም ፕቲ"አሉ ወይዘሮ ሜሪዌዘር ጮክ ኮስተር ብለው ። "ባሪያዎቹ የሚበሳና የሚ ጠጣውን ሁሉ ድራሹን እንዳያጠፉት መቆጣጠር አለባችሁ ። የወ/ሮ ቦኔል ሥራ ያ ነበር ። ሚላኒዬ ደግሞ የማክለርን ልጅች ሥራ ተክተሽ ትሠሪያለሽ ።"

"እዬ ፣ ምስኪን ቻርሊዬ ሞቶ ጎና ሙት ዓመቱ ሳይደርስ እኛ ወደዚያ መሄድ የምንችል አይመስለኝም እና..."

"እሱንማ በደንብ አውቃለሁ ። ሐዘኑ ምን ያህል መሪር እንደ ሆነባችሁማ አሳምሬ አውቃለሁ ።ሆኖም ለታላቁ ዓላማችን ስንል የማንከፍለው መስዋዕትነት አይኖርም"ወ/ሮ ኤልሲንግ ቁጣ በሚያ በርደው ለስላሳ ድምፃቸው አጽረጡና ተናገሩ ።

"እርግጥ መሥራቱ እንኳ ደስ ይለናል ።ግን ሴሎች ቆንጆ ቆንጆ ወጣቶችን ብትመድቡ ምን ያስቸግራችኋል ?"

ወይዘሮ ሜሪዌዘር ከሙያ ስንጣሪ የሚወጣ በሚመስል ድምጽ አስነጠሱ።"እዬ አንቺ ደግሞ።ዛሬ ወጣቶቹ ምን እንደነኳቸው እንጃ፣ ምንም ዓይነት ሐላፊነት ብትሰጫቸው የሚሸከሙ አይደሉም። ሴላ ቦታ ላይ ያልተመደቡት ሴሮች በሙሉ ኑ ሥሩ ስትያቸው እንድሺ ሰበብ እየደረደሩ በጀ አለል አሉ ።በነሱ ቤት አታለው ልባቸው ወለቋል ። ማ መሰልኳቸው ፣ እነሱ ከመኩንኖቹ ጋር አሽኩለሌ ለማ ለት የማያመች ሥራ መሥራት አይፈልጉም ፣ አውቄባቸዋለሁ ። ማጋጣ ሁሉ! ከባንኮኒ ጀርባ ቆመው ቀሚሳቸው ስለማይታይላቸው እዚያ እንዳይመደቡ ሥጋት ይዟቸዋል ። ያ የኮንትሮባንድ ዕቃ የሚያመጣ ሰውዬ ማነው ስሙ...ት..."

"ካፒቴን በትለር"አሉና ሞስላቸው ወ/ሮ ኤልሲንግ ።

"አምን ፡ከሠስፒታል ዕቃው ጨመር ፡ከቃሚስና ከጌጣጌጡ ቀነስ አድርገ ቢያመጣ እኮ እንዴት ግልግል ነበር ። ዛሬ አንድ ቀሚስ ፡የሁኝ ሴሎች ሃያ ሰላሳ ቀሚሶች ደሞ ማየት ይኖርብኛል ። ካፒቴን በትለር — እንደዚህ ስም ያንገሸገሸኝ የለም ። አውን እንግዲህ

@OLDBOOKSPDF

ወ/ሮ ፒቲ ለመማት ጊዜ የለኝም ።መምጣት አለብሽ ብያለሁ ፣መም ጣት አለብሽ ። ሁኔታችሁን ማንም የሚረዳው ማንም የሚያውቀው ነገር ነው። ለዛውም እኳላኛው ክፍል ስለምትሆኑ ማንም እያያችሁም።ሚ ሊዬም ፊት ለፊት ሆና ለሰው ዓይን አትጋለጥም ። ምስኪኖቹ የማ ክለር ሴት ልጆች የተመደቡበት ክፍል በታች በኩል ጠርዙ ላይ ካሉት ክፍሎች ውስጥ አንዱ ስለሆነ ማንም ልብ አይላችሁ ።"

"መሄድ ያለብን ይመስለኛል"አለች አስካርሌት ፣ለመሄድ ያላ ትን ጉጉት ደብቃና ፊቷን ግልጽና የሚታመን ለማድረግ እየሞክ ረች ።"ስሆስፒታሉ ማድረግ ካለብን ነገሮች ሁሉ በጣም ትንሹ እኩ ነው ይሄ"

ከመጡት ሴቶች አንዳቸውም እሷን አላነሷትም ነበርና ወደሷ ዞረው አተኩረው ተመለከቷት ። መቼም ምንም ያህል ለአላማው ሟች ቢሆኑ ፣ ምንም ለአላማቸው ብለው ካባር ልማድ ለማፈንገጥ ወደኋላ ባይሉ ፣ና ሐዘኗ ዓመት ያልሞላውን የመሉት ሚስት ነይና ባዛር ላይ ተገኝ አይሉም ፣ አላበዱም ። አስካርሌት የትክታ አስተያየታቸውን እንደልጅ ባለ ንግግር ሰበረችው ።

"እንደሚመስሽ ሁላችንም በመረባረብ ዓላማው የተሳካ እንዲ ሆን መጣጣር አለብን ።እኔም ከሜላኒ ጋር እዚያ ምድብ ላይ ተገኝቼ ማገልገል አለብኝ ።ምክንያቱም ከአንድ ሁለት የተሻለ ይሠራል ። አይመስልሽም ሜላኒ ?"

"መቼም"አለች ሜላኒ ማ በረዳኝ እያለች ።በሐዘን ላይ ያለች ሴት በእንዲህ ያለው ያእደባባይ ስብሰባ ላይ መገኘት ምን ያህል ነውር እንደሆነ ስለምታውቅ የምትመልሰውን አጥታ ተደናገጠች ።

"አስካርሌት ትክክል ናት ፣እውነት አላት"አሉ ወ/ሮ ሜሪዌዘር መልስ ለመስጠት መጸከማቸውን ተገንዝበው ።ተንስተው ሽንሽን ቀሚሳቸውን ዳሌያቸው ላይ አወዛወዙት ።"ሁለታችሁም ፣ሁላችሁም መምጣት አለባችሁ ።በይ ወ/ሮ ፒቲም ያንኑ ሰበብ መደርደርሽን እንደገና እንዳትጀምሪ ። ማሰብ ያለብሽ ሆስፒታላችን ምን ያህል ተጨማሪ አልጋዎች እንደሚያስፈልጉት ፣ምን ያህልስ ተጨማሪ መድ ሀኒቶች እንደሚያስፈልጉት ነው ።ለዛ ደግሞ ምን ያህል ገንዘብ እንደ ሚያሻ አስቢ ።ደሞም ቻርለ ይህን ዓላማችንን ስትረዱ እንዴት እንደ ሚወዳችሁ አስተውሉ ።"

"መቼም"አሉ ወ/ሮ ፒቲፓት እንደተለመደው ጠንከር ያለ ሰው ሲከራከራቸው እንደሚሉት ።"መቼም ሰው ይገባዋል ካላችሁ እሺ"

@OLDBOOKSPDF

የእስካርሌት ልብ "የማይታመን ነገር፣ እውን መሆኑ በጭራሽ የማይታመን ነገር!" እያለ ጮቤ ረገጠ ፡ በሐምራዊና በቢጫ ቀለም በተንቆጠቆጠው ባንኪኒ ውስጥ ስትገባ ። ይሄ ባንኪኒ የማክለር ሴት ልጆች ተመድበውበት የነበረ ነው፣ ወጣም ወረደም በመጨረሻ እፓርቲው ድግስ ላይ ተገኝች ። አንድ ዓመት ሙሉ ከደስታ ተለይታ ከቆየች በኋላ ፡ አንድ ዓመት ሙሉ የሐዘን ክል ለብሳ ከቆየች በኋላ ፡ አንድ ዓመት ሙሉ ድምጿን ከፍ አድርጋ እንዳታወራ ታግዳ ከቆየችና ከምላ ጐደል ልታብድ እስከምትደርስ ድረስ ከሚንፉት የአንድ እመት አሰልቺ ሕይወት በኋላ በአትላንታ ውስጥ እስከዛሬ ከተደገሱት ፓርቲዎች ሁሉ በጣም ከፍተኛው የዳንስ ፓርቲ ላይ እነሆ ተገኘች! እንግዲህ በርካታ ሰዎችን ልታገኝ ፡ ደማቅና ውብ መብራቶችን ልታይ ፡ ድንቅ ሙዚቃን ልትሰማና ዝነኛው ካፒቴን በትለር በኮንትሮባንድ ያስገባቸውን ምርጥ ምርጥ ጌጣጌጦች በዓይኗ በብረቱ ልታይ ነው ።

ከባንኪኒው ጀርባ ባለች አንድ በርጩማ ላይ ተቀምጣ እስከ ዛሬ ከሰዓት በኋላ ድረስ በጣም አስቀያሚ የማሰልጠኛ ቦታ ወደንበረው አዳራሽ ከላይ እስከታች ተመለከተች ።ዛሬ ያገኘውን ውበት እንዲያገኝ ሴቶቹ ያላደረጉት ጥረት የለም ። በጣም አምሯል ። እያንዳንዱ ሻማና የሻማ ማስቀመጫ ከድፍን ስትሳንታ ለዛሬ ማታ ታፍሶ ታስሶ የመጣ መሰላት ። ብርማ ማስቀመጫዎች በደርዘን የሚቆጠሩ ጌጠኛ እጀቻቸውን ዘርግተዋል ። የቻይና ሥራዎች የሆኑት ደግሞ ከወደግርጌያቸው ቅርፃቸውን ሰብስበው ቆመዋል ።በአዳራሹ ቁመት በተደረደሩት የጠመንጃ አፈሙዝ ብራዮች ላይ ከየኅይላቸው ቁመትና ቀለም ያላቸው ሻማዎችን አቅፈው የተኮለኮሉ እያለ የነሐስ ሻማ ማስቀመጫዎች አሉ ። የእንጀሪ ሽታቸው ያውዳል ። ሻማዎቹ በአበባ የተንቆጠቆጠ መሸፈኛ የለበሱ ጠረጴዛዎች ላይ ፡ በሂሳብ መከፈያ ባንኪኒዎች ላይ ፡ የበጋው ኀፍስ ለመንደድ በሚያስችግርበት የመስኮቱ ደፍ ላይ ሳይቀር ተደርድረዋል ።

አዳራሹ መሀከል ከኮርኒሱ በጣ ሦስሰት ተንጠልጥሎ ይወርድ የነበረው ትልቁ አስቀያሚ ፋኖስ ዛሬ በመንትያ በሚወርድ የወይን ሐረግ ተጐንጉኖ በወሐይ ብዛት ሊረግፍ በደረሰ የወይን ቅጠል ተከበ ያ ያረጀው ፋኖስ የጐሮውን እይመስልም ። አዲስ ሆኗል ። ግድግዳዎቹን መጓዝቸው መንፈስን የሚያድስ የአናናስ ዛፍ ትርንጫፎች የከፈቃ ሲንሆ ፡ በአራቱ ማዕዘናት ደግሞ ለሞጊቶችና ለአሮጊቶች መቀመጫ የሚሆን ጐጆ የመሰለ ትርጽ ፈጥረውላቸዋል ። ረገቦቹም የወይን ሐረጐች እንደገመድ ተጐንጉነው በክብና በጥምዝ እየወረዱ ባንኮኒዎቹን አሳምረዋል ። ለመስኮቶቹ ልምላሜን አጐናጽፈዋል ። ሻካራ

@OLDBOOKSPDF

ምቹን የጣንኪ ዘርፍ ጨርቆችም ድምቀት ሰጥተዋቸዋል ። አዳራሹን ሙሉውን ለምለም አረንጓዴ መስክ ያስመሰሉት ሲሆን ፣ በዚህ ጣልቃ ጣልቃ በባንዲራዎቹ ቀይና ሰማያዊ መደቦች ላይ ፏ ብለው የሚያበራት የኮንፈደሬሲው አርማ የሆኑት ኮኮቦች ለቤቱ ግርማ ሞገስ ሆነዋል ።

ለሙዚቀኞች ተብሎ ከፍ ተደረጉ የተሠራው መድረክ በጣም ውብና በጥበብ የታሞላ ነው ። በኮከብ በደመቀው ባንዲራና በአረንጓዴው ጫካ ታውጅ በትክክል ጠርዙ የት እንደሆነ ለማወቅ አይቻልም ። አስካርሌት በሀሳቧ የከተማው ባለ ማስቀመጫ አበቦች አንድ አልቀሩም አሉች ። ሌላው ቀርቶ የወይዘሮ ኤልሲንግ አራቱ የላስቲክ አበቦች እንኳ በአራቱ ማዕዘናት ላይ የክብር ቦታ ተሰጥቷቸዋል ።

ከመድረኩ መዲያ ባለው የአዳራሹ ጥግ በርካታ ሴቶች ይታያሉ ። ግድግዳው ላይ የፕሬዚዳንት ዴቪስና የጆርጂያ የራሷ ሰው የሆነው "ትንሹ አሌክ ስቲፈንስ" የተባለው የኮንፈደሬሲው ምክትል ፕሬዚዳንት ትላልቅ ፎቶግራፎች ተሰቅለዋል ።ከፎቶግራፎቹ በላይ እጅግ በጣም ሰፊ ባንዲራ ይታያል ። ከበታቻቸው ባለው ረጅም ጠረጴዛ ላይ በክብሣዋ አትክልት ቦታዎች ሁሉ ያሉ የአበባ ዓይነቶች ከሠ እስከ ፕ ተከልከሰዋል፡—ቀያይ ቢጫና ነጭ ጽጌረዳዎች ፣ ወይን ጠጅና ቀይ የቦጋምቢል አበቦች ፣ ቢጫና ነጭ የአደይ አበቦች ፣ ነጫጭ የሙሽራ አበቦች ፣የምሽት ንግሥት የሚባሉት የጃዝሚን አበቦች ፣ የመላዕክት ትራምፔት በመባል የሚታወቁት ጥሩምባ የመሳሰሉ ሰማያዊ አበቦች ፣ ብቻ የአበባ ዘር ከነቀለሙ ተሰብስቧል ።በማሀል በማሀል የሙሰዋዕት ማቅረቢያ ስፍራ የሚነድ እሳት ይመስል ሻማዎች እዛም እዛም ይበራሉ ። በእንዲህ ያለው ልዩ ሥነሥርዓት ወቅት እጅግ የሚለያዩት እነዚያ ሁለት ፊቶች ቁልቁል ትርሢቱን ያስተውሉ ።እነዚህ ሁለቱ ፊቶች ፣ አንደኛው ፍርጥም ያሉ ኩሩ ከንፈሮች ቀዝቃዛ ዓይኖችና ጠፍጣፋ ጉንጭ ያሉት የዴቪስ ፊት ነው ።ሌላኛው ጥልቅና እንደእሳት የሚንበለበሉ ጥቁቁር ዓይኖች ያሉበት ያለ ሕመምና በሽታ ሌላ አይቶ የማያውቅና በጨዋታና በእሳት ችግሩን ድል የመታው የስቲፈንስ ፊት ነው—ሕዝብ የሚወዳቸው ሁለት ታላላቅ ሰዎች ፊቶች ።

የባዛሩን ሐላፊነት የተሸከሙት የኮሚቴው አንጋፋ ሴቶች ከእኖ እስከ ገደፋ እንደተጫነ መርከብ ክብድ ብለው ይንጣለላሉ ። የፈረደባቸውን ወጣት ሞግዚቶችና የሚስቁ የሚገለፍጡትን ልጃገረዶች እያጣደፉ እየነዱ ወደየባንኪያቸው ካስማሩ በኋላ ምግብና መጠጥ ወደሚደረደርበት ወደኋላኛው ክፍል በሚወስዱት በሮች ወጥመው ሄዱ ።ወይዘሮ ፒቲፓት ቁና ቁና እየተነፈሱ ኋላኋላ ይከተላሉ ።

@OLDBOOKSPDF

ሙዚቀኞቹ መደበኛ ባልሆነ ወጥ ሁኔታ ቦታቸውን ያዙ ። ጥቂ ቁር ናቸው ። ይስቃሉ ። ወሩፍር ጉንጫቸው ገና ካሁኑ በሞራ እንደ ታሸ ሁሉ በላብ ያብረቀርቅ ጀመር ። ሙዚቃቸውን መቃኘት ሲጀምሩ ስለራሳቸው ዋጋና አስፈላጊነት የተሰማቸው የኩራት ስሜት ይታይ ባቸዋል ።እትላንታ ማርታስቪል ትባል ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ አርኪ ስትራዎችን በባዛር ፡በዳንስ ግብግ ወይም በሠርግ ላይ ሁሉ በሙ ምራት የታወቀው የወይዘሮ ሜሪዌዘር የሠረገላ ሹፌር ሽማግሌው ሴቪ ፡ሰው እንዲያይለት ለጥ ብሎ እጅ ነሣ ። ባዛሩን ከሚያዘጋጁት ሴቶች በተቀር የመጣው ሰው ጥቂት ይሁን እንጂ ፀይን ሁሉ ወደሱ ዞረ ። ቫዮሊን ፡ አኮርዲዮን ባንጆ ፡ የቶም ቶም የሙዚቃ መሣሪያዎች ቀስ በቀስ እፍኞውን ፈተው "ሎሬና" የተሰኘውን ለዳንስ በጣም የማይመች ዝግተኛ ዜማ መጫወት ጀመሩ ። ዋናው ዳንስ የሚመጣው ለባዛር የተዘጋጁት ዕቃዎች በሙሉ ተሸጠው ሲያልቁ ነው ። የለስላ ሳው ዜማ ጣፋጭ ቃና እጀሮዋ ሲደርስ እስክርሴት የልብ ትርታዋ ፈጠን ፈጠን ማለት ጀመረ፡—

ዓመትም መንገዱን ይዞ ፡እያዘገመ ነው...

በረዶው በየሳሩ ላይ ፡ጊዜ ጠብቆ ወረደ ።

የፀሐይም እግር ቁልቁል ፡እሰማያት ግርጌ ሄደ... ሎሬና.. ሎሬና"

አንድ ፡ሁለት ፡ሶስት እንድ ሁለት ፤ስት ምክ በሉ — ሶስት ። እንደገና ሁለት ሶስት ። እንዴት ያለ ውብ ለስላሳ ሙዚቃ ነው ባክ ችሁ ። እጀጀን ጥቂት ዘርጋ አድርጋ ዓይኖቿን ጨፍና ከሙዚቃው አሳ ዛኝ ቅኝት ጋር አብራ ነጐደች ። የሎሬና ጥቅረኛዋን የማጣት አሳ ዛኝ ቅላጼ ከገዛ ራሷ ስሜት ጋር ተቀላቅሎ ጉሮሮዋ ላይ አንዳች ሕመም ፈጠረባት ።

ወዲያው ለስላሳው ሙዚቃ ነፍስ የዘራባቸው ይመስል በጨ ረቃ ብርሃን ፈዘዝ ያለ መልክ ከያዙት የታችኞቹ መንገዶች ፡ የተለ ያዩ ድምጾች ወደአዳራሹ ገቡ ። የፈረስ ኩቴ ድምጽ ፡ የሠረገላ ጐማ ድምጽ ፡ ፈረሰቹን እዚህ እሰር አላስርም የሚሉ ኔግሮዎች የጭቅ ጭቅ ድምጽ ፡እየተመሠ መጣ ። ከደረጃዎቹ ላይ ግራ የመጋባት ድምጽ ይሰማል ። በደስታ የመጥለቅለቅ ድምጽ ፡ ከሚሸኟቸው ወንዶች ጐር ናና ድምጽ ጋር የተቀላቀለ የሴቶች ንግግር ፡ በዚያ ከሰዓት በኋላ ብቻ የተለያዩ ጓደኞሞች ሴቶች ሲገናኙ የሚፈጥሩት ዋካታ አየሩን ባንዴ ሞላው ።

በአንድ አፍታ አዳራሹ ሕይወት አገኘ ። በሴቶች ተጥለቀለቀ ። እንደ ቢራቢሮ የተሸጐረጐረ ቀለም ያለው ቀሚስ የለበሱ ፡ እዳሌ ላይ

@OLDBOOKSPDF

ቡፍ የሚል ቀሚስ ፤ ከወደግርጌው በወርቀዘቦ የተጠለፈ ቀሚስ ፥ በየዓይነቱ ተርመሰመሰ ። ራቁታቸውን የሆኑ ትናንሽ ክብ ትከሻዎች ሙ ። ልስልስ ያሉ ትናንሽ ራቁት ደረታቸውን የሚያሳዩ ቀሚሶች የለበሱ ሴኖች ታዩ ። አክንድ ድረስ በማዴለሽነት የታጠፈ ሻል የለበሱም አሰበት ። ጠቃጠቆ ቀለም የተቀቡ ማራገቢያዎች ፥ ከዳክዬና ከጢክክ ላባ የተሠሩ ከእጅ ጓንቲ ላይ በጥብጣብ የሚንጠለጠሉ ማራገቢያዎች ፥ ይርገበገባሉ ። ወርቃማ ጥቅልል ፀጉር አራሳቸው ላይ የከመሩና ከሚዘናፈለው ፀጉራቸው ጋር የሚደንሱ የወርቅ የጆሮ ጉትቻዎች ያደረጉ ሴኖች በርካታ ናቸው ። በክንትሮባንድ የገቡ ጌጣጌጦችና የሐር ጨርቆች እንዲሁም ጥብጣቦች በየዓይነቱ ይታያሉ ። የለበሷቸውና ያደረጓቸው ሁሉ እንድም ለወዲ ዋጋቸው ፥ እንድም ደንኪዎች ላይ ኩራትና ጥላቻቸውን ሊገልጹባቸው ነው ።

ለኮንፈደሬሲው መሪዎች ሲባል ክድኖን ከተማው ተፈልገው የመጡ ይመስሉ የነበሩት አበቦች ሁሉም እንዳልመጡ አሁን ተረጋገጠ ። አዲስ የመጡት ልኝገረዶች በጣም ትንንሽና ገና በጣም ሙላ የሆኑ አበቦችን ይዘው መጥተዋል ። ከቀይ ጆሯቸው ጀርባ የሰኳቸው ልዩ ሮዝ አበቦች ናቸው ። በተጠቀለለ ፀጉራቸው ዳርዳር የተሰኩ የምሽት ንግሥትና የዓይነት እንቡጥ አበቦች ጭምቸም ጌኖ እጅግ ይማርካል ። በስስ ሻሾች ላይ እንደዋዛ የተሰካኩ አበቦችም አሉ ። እነዚህ ሻሽ ላይ የተሰካኩ አበቦች ምሽቱ ከመገባደዱ በፊት እንደብርቅና ድንቅ ጥንታዊ ዕቃ ለመኩንኖች በስጦታ መልክ ተሰጥተው እዩኒፎርሞች ደረት ኪስ ላይ የሚተከሉ ናቸው ።

በተሰበሰበው ሕዝብ መሀል በርከት ያሉ ዩኒፎርሞች ይታያሉ ። እነዚህን ዩኒፎርሞች ከለበሱት ማህል አለካርሌት የምታውታቸው ብዙ አሉ ። በሆስፒታል አሊጋዎች ላይ የምታውታቸው አሉ ። መንገድ ላይ የምታውታቸው አሉ ። በማሰልጠኛው ስፍራ የምታውታቸውም አሉ ። እነዚህ ዩኒፎርሞች እንደአንድ ነገር ያበራሉ ። የሚያንፀባርቁ ቁልፎቻቸውና በእጅጌና በኮሌታቸው ላይ የሚለጠፉት የተቆላለፉ የወርቅ ፈርመቻቸው የጀግና ምልክት ናቸው ። በቦላሌዎቹ ላይ ያሉት ቀይ ፥ ቢጫና ሰማያዊ መስመሮች የተለያዩ አገልግሎት ከፍሎች መለያ ሲሆኑ ያንን ግራጫ ዩኒፎርም በጣም የተለየና ፍጹም ያደርጉታል ። ኮይና ወርቃማ ሻሾች ወዲህ ወዲያ ይወዛወዛሉ ። የሚያብለጨልጩ ሻምላዎች ከተመለመሉ ቦት ጫማዎች ጋር ይጋጫሉ ። የፈረስ መኮልኮያና መውጫ እርካቦች ይጋጫሉ ይቅጨለጨላሉ ። ይወዛወዛሉ ።

ሰዎቹ ሰላምታ ሲለዋወጡ ፥ እጃቸውን እያውለበለቡ እንዴነህ ፥ እንዴነሽ ሲባባሉ በእድሜ የገፉ አሮጊቶች እጅ ላይ እየተደ-

@OLDBOOKSPDF

ሰላምታ ሲያቀርቡ ስትመለከት እስካርሴት በልቧ እንዴት ቆንጆ ቆንጆ ወንዶች ናቸው፣ አለች። ሁሉም ወጣት ይመስላሉ። ሙሉ በሙሉ ቢጫማ የሆነው የከንፈር ጺማቸውና ድብን ያለ ጥቁር እንዲሁም ቡናማ የአገጭ ጺም አያሳቸው እንኳ በጣም ቆንጆዎች፣ በጣም ግዴ ለሾች፣ ከንጹሕነታቸውን በማንነቃ ያስሩና ፀሐይ ያጠቆረው ቡናማ ፊታቸው ላይ ነጭ ፋቫ የጠመጠሙ ይሁኑ እንጂ ቆንጆዎች ናቸው። እንደንዶቹ ክራንች ይዘዋል። ከሚደግፏቸው ወንዶች እርምጃ እኩል እርምጃቸውን እያዘጋጉከሉ የሚሄዱ ኩሩ ሴቶች አሉ። ከዩኒፎርሞቹ ሁሉ የተለየና አምረን ደምቀን መጥተናል የሚሉትን ሴቶች ዝቅ የሚያደርግ እንደትሮርክ ወፍ ያማረ ዩኒፎርም አለ። የሉዚያና ዙዌቭ ቀለም ያለውና ክላይ ሰማያዊ ቢልቻ የመሰለ ሲሆን ቦላሌው ነጭ መስመር አለበት። የተረከዝ መሸፈኛው ከፊም ቀለም አለው። ጥብቅ ያለች ትንሽ ቀይ ኮኬት ክላይ ተጨምሮበታል። አንድ ጥቁር የሚገለፍጥ ዝንጀር የመሰለ ሰው ያንን የመሰለ ያማረ ዩኒፎርም ለብሶ ማንነቃውን በጁ ይዞ ሰጣቸዋል። የሚይቤል ሚሪዌዘር ፍቅረኛ ሬኔ ፒካርድ ነው። መቼም በእማሩ መሄድ የሚችል የሆስፒታሉ ሰው አንድ አልቀረም። ግልብጥ ብሎ ሠጥቷል። ከጦር ሜዳ ለአረፍት ወይም በሕመም ፈቃድ የመጡ፣ በማክኘና በአትላንታ መካከል ባሉ ባቡር ጣቢያዎች፣ በፖስታ አገልግሎትና በኩሚሳሪያቱ ቅርጫፍ ጽ/ቤት ውስጥ የሚሠራ አንድም ሰው አልቀረም። አቤት አዘጋጃቹ ሴቶች እንዴት ደስ ይሉቸው! መቼም ሆስፒታሉ ዛሬ ማታ የሚያገኘው ገንዘብ እንጂ!

እታች ካለው መንገድ የከበሮ ድምጽ፣ የእግር ኩቴና የሠረገላ ዊሬሮች የእድናቆት ጩኸት ሰሰማ። ኔጋሪት ተንሰመ። መለከት ነፉ። አንድ ወፍራም ድምጽ ጩኸቱ ሁሉ እንዲቆም አዘዘ። በዚያች ቅድስት ከተማ ጠባቂዎች ሚሊሻያዎች ደማቅ ዩኒፎርሞቻቸውን እንደለበሱ ጠባቡን ደረጀ ነቀነቁት። እጅ እየነሱ፣ ሰላምታ እየሰጡና እየተጨባበጡ ሲገቡ ክፍሉን መተንፈሻ አሳጡት። ከከተማ ጠባቂዎች ውስጥ በሰርነት በመቀለዳቸው የሚኮሩ፣ የዛሬ ዓመት በዚህ ጊዜ ጦርነቱ ካላበቃ ወደቨርጂኒያ ለመዝመት ቃል የገቡ ትናንሽ ልጆች ይገኙባቸዋል። ከወጣት ወንዶች ግርማ ሞገስ ጋር እኩል በዩኒፎርም በመሰለፋቸው የሚኮሩ፣ ወጣት በሆንን ኖሮ እያሉ የሚመኙ፣ ነጭ ጢም ያበቀሉ ሽማግሌዎችም አሉባቸው። በሚሊሻያው ውስጥ በመካከለኛ ዕድሜ ላይ የሚገኙ ወንዶች አሉ። ሽማግሌዎችም አሉ። በወታደር ዕድሜ ከልለ የሚገኙ እንደታላቆቻቸው ሆነ እንዳባቶቻቸው ደስታ የማይታይባቸው ሰዎችም አሉ። ሰዉ፣ ገና ካሁኑ እነዚህ ከጄኔራል ሊ ጋር ለምን አልዘመቱም ነበር እያለ መንሾካሾክ ጀምሯል።

@OLDBOOKSPDF

ይሄ ሁሉ ሠራዊት እንዴት አዳራሹ ውስጥ ይገባል ? ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት ሰፊ ይመስል የነበረው አዳራሽ አሁን ባንዳፍታ በሰው ተጠቀጠቀ ። በፀጉር ቅባትና በሽቶ በሻማዎች ሽታ ፣ በአበቦቹ መዓዛና በመጠኑ ከጫማ ጋር ከገባው አቧራ ጋር ያ የጥንቱ የመታ ደር ማሠልጠኛ አዳራሽ ተጨናነቀ ። የሰው ጉርምርምታና ሕምሕምታ ከሞላ ጐደል ምንም ለመስማት እንዳይቻል አድርጐታል ። መደነፃ መጥ አቃተ ። ሽማግሌው የኦርኬስትራ መሪ ሌቪ ፡ "ሎሬና" የሚለውን ዜማ መሀከል ላይ አቋርጦ የበዓሉን ደስታና የጭንጋታ ስሜት ለማ ጀብ የተገፋፉ ይመስል እንድ ጊዜ እጅ ከነሳ በኋላ ኦርኬስትራውን "ቦኒ ብሉ ፍላግ" የተሰኘውን ዝነኛ ዜማ እንዲጫወት ፈቀደለት።

በሙቶ የሚቆጠሩ ድምጾች በአጀብ ተቀበሉት ። የደስታ ጩኸት ይመስል ላንቃቸው እስኪሰንጠቅ ከዳር እዳር ጮኹት ። የከተማ ጠባቂ ዎች ጥሩምባ ነፊ መድረኩ ላይ ወጥቶ ከሙዚቃው ቅኝት ጋር አስ ተካክሎ ገባበት ። የሱ ቅኝት ከሌላው ሕብረ ዜማ ከፍ ብሎ በቀጭኑ ይሰማል ። የጭብጨባ እጆች እንዲንቀሳቀሱ ያደረገው ከልብ የመነ ሰጥ ስሜት የሕዝቡን አንደበት አዝለቆት ፡—

"እሰይ እሰይ ደቡብ ነፃነቱን ጠራ
"ብቸኛ ኮከብ ባዘልው "ቦኒ ብሉ ፍላግ" ጮራ
እሰይ እሰይ እሰይ ደቡብ ነፃነቱን ጠራ !"

ወደ ሁለተኛው ግጥም ሲገቡ ፣ አስካርሌትም ከሌላው ሕዝብ ጋር እየ ዘመረች ሳለች ከጀርባዋ የሜላኒን ግልጽ ፣ ጣፋጭና ቆንጆ ቅላጼ ያለው ድምጽ ሰማች ። እንደመለከቱ በቀጭኑ የሚፈስ ድምጽ ። ዘወር ብላ ብትመለከት ሜላኒ እጆቿን እዶረቷ ላይ አጣምራ ከተጨፈኑ ዓይኖቿ ዳርና ዳር እምባ እየፈለሳት ቆማለች ። ሙዚቃው ሲያበቃ ለአስካርሌት ፈገግታ መገበቻት ። ዓይኖቿን በመሀረብ እየጠራረገች ይቅርታ እንደመጠየቅ ዓይነት፡—

"በጣም ደስስ ብሎኛል" አለች በሹክሹክታ ። "በወታደሮቹ በጣም ኩራት የተሰማኝ ከመሆኑ የተነሳ እንባዬን መቆጣጠር አልቻ ልኩም"

በዓይኖቿ ውስጥ የሚበራው ጥልቅ ብርሃን በጣም ከማንፀባረቁ የተነሳ ትንሿን ግልጽ ሬቲን በውጋጋኑ አጥለቅልቆ እጅግ ውብ አድ ርጓታል ።

ሙዚቃው ሲያበቃ ፍቅረኛ ወደ ፍቅረኛዋ ፣ እናት ወደ ልጅዋ ፣ ሚስትም ወደባሏ ስትዞር እፊታቸው ላይ የሚነበበው ነገር የሁሉም አንድ ዓይነት ነው ። በጨምዳዳም ሆነ በትምቡኪ ጉንጫቸው ላይ የሚወርደው

@OLDBOOKSPDF

የኩራት እንባ ፣ በከንፈሮቻቸው ላይ የሚታየው ፈገግታና በጥልቅ ዓይኖቻቸው ውስጥ የሚንቀለቀለው እሳት ፣ ከቶም አንድ አካል አንድአም ላል ነው ። ያ አንደነበልባል የሚያንበለብል ውስጣዊ ስሜት ምናምኔት የቁንጅና ነጠብጣብ እንኳ የሌለባትን ሴት እቁንጅና አገር ሰይ በጣም ተወዳጅ በጣም ተፈቃሪ ሴት ያደርጋታል ። የደቡብ ሴቶች ወንዶቻቸውን ሲወዱቸው ሰብቻ ነው ። ሲተማመኑባቸው ለብቻ ነው ። ሲያምኗቸውም የመጨረሻዋ የሰውነታቸው እስትንፋስ እስክ ትሚጠዋ ድረስ ነው ። እንደዚህ ያለ ግራጫ ለበስ ጀግና ሠራዊት በእነሱና በያንኪዎች ማህል ብረት መዝጊያውን ሠርቶ ቆሞ እንዴት ተደርጐ ነው ሴቶቹ ጥቃት የሚደርስባቸው? ግና ጠዋት ዓለም ስትፈጠር ፣ ግና ማለዳ የሕይወት ገሀ ሲቀድ ጀምሮ እንደዚህ ያለ ጀግና ሠራዊት ፣ እንደዚህ ያለ ለንፁሉ አይሳሰ ወታደር ፣ እንደ ዚህ ያለ ቆራጥ ሕዝብ ፣ እንደዚህ ያለ ተወዳጅ ጦር ኖሮ ያውቅ ይሆን፣ እንደነሱ ያለ ዓላማ ፣ እንደነሱ ያለ ትክክለኛና ሐቀኛ ዓላማ ከድል በስተቀር ምን ሊያጋጥመው ይችላል ? ወንዶቻቸውን የሚወዱትን ያህል የሚወዱት ዓላማ ፣ እኛቸውንም ልባቸውንም የገበሩለት ቅን ዓላማ ፣ ሴት ተቀን የሚያወሩለት ሴት ተቀን የሚጨነቁ የሚጠበቡለ ትና ሴት ተቀን የሚያለሙለት አላማ ፣ ካስፈለገ እነዚህን ውድ ባለቦቻቸውን ፣ ውድ ልጆቻቸውን የሚሰውለትና ወንዶቹ በጦር ሜዳ ባንዲራቸውን እንደሚይዙ ሁሉ አጠቃቸውን ለመሸከም ዝግጁ የሆኑለት ታላቅ ዓላማ ነው ።

በልባቸው የመሰጣዕትነት ጉርፍና ማዕበል ይተራመሳል ።የኮን ፌዴሬሲው ጉርፍና ማዕበል ይተረማመሳል ። የመጨረሻው ድል እደ ጉሩቸው ላይ ቆሞ በራቸውን እያንኳኳ ነውና የኮንፌዴሬሲው ጉርፍ ግድቡን ጥሶ ሊፈስ ነው ። በቫሲ ውስጥ ስቶንዎል ጃክሰን የተጉ ናዐፈው ድልና በሰባቱ ቀን ጦርነት ፊኞሞንድ አካባቢ ያንኪዎች የቀመሱት የሽንፈት ፅዋ ለዚሁ ሁነኛ ማስረጃ ነው ። እንደ ጄኔራል ሊ እና እንደ ጃክሰን ያሉ የጦር መሪዎች እያሉ ከድል ሌላ ምን ይመጣል ፣ አንድ የመጨረሻ ቅጣት ከተቀጡ ያንኪዎቹ እያለቀሱ ተንበርክከው የሰላም ያለህ ፡ ማለታቸው አይቀርም ። እንበሶቹም የደቡብ ወንዶች እየጋለቡ ወደቤታቸው በመግስገስ ልጆቻቸውን ይስማሉ ፣ ሚስቶቻቸውን ያቅፋሉ ። አንድ ተጨማሪ ድል ። ከዚያ ወዲያ ጦር ነት ያከትማል ።

በእርግጥ ባዶ ወንበሮችና ያባቶቻቸውን ፊት ዳግመኛ የማያዩ ሕፃናት ፊቶች አሉ ። ምልክት ባልተደረገባቸው የቨርጂኒያ መቃብሮች ችና በዘጠናሺህ የተነሲ ተራሮች ማህል የሚወድቁ ቆራጥ አባቶች

@OLDBOOKSPDF

ይኖራሉ ። ታዲያ ለእንደዚያ ያለ ከበር ዓላማ ይሄን የመሰዋዕትነት ዋጋ መክፈል ይበዛበታል እንዴ ? ለሴቶቹ ቀሚስ ፣ ሻይቅጠልና ስኳር ማግኘት ይከብድ ይሆናሉ ። ከታላቁ ዓላማ አንጻር ግን ከቶም ኢምንት ነገር ነው — ጨዋታ ። በዛ ሳይ ሴት ተቀን የሚከንሱት ኮንትሮባንዲስቶች እነዚህን ቁሳቁሶች በያንኪዎች እፍንጫ ሥር አሳልፈው ያመጧቸዋል ። ስለዚህም ዕቃዎችን ማግኘት የሚያከራ ነገር ይሆናል ። ራሱኤል ሲመስና የኮንፌደሬሲው የባህር ሐይል እንዚያን የያንኪ የጦር ጀልባዎች በአስቸኳይ ድባቅ መትቶው የባህር በራችንን ይከፍቱልናል ። የአንግሊዝ የጥጥ መዳመጫ ሩብሪካዎች የደቡብን ጥጥ በማጣታቸው ሥራ የፈቱ ስለሆነ እንግሊዞች ኮንፌደሬሲው ጦርነቱን እንዲያሸንፍ እየረዱ ነው ። ደሞም እንድ የመሳፍንት አገዛዝ ከሌላ የመሳፍንት አገዛዝ ጋር እንደሚረዳዳ ሁሉ የብሪታኒያ መሳፍንትም ኮንፌደሬሲውን ያግዛሉ ። እናም ሁለቱ እንድ ላይ እነዚያን አፍቅሮተ ንዋይ ያሰከራቸው ያንኪዎች መግቢያ መውጫ ያሳጧቸዋል ።

በዚህ ዓይነት እንግዲህ ሴቶቹ ቀሚሳቸውን እየነሰነሱና እያሸካኩ ፣ልባቸው በኩራት ሲፈነዳ ደርሶ መንዶቻቸውን በፍቅር ዓይን ያያሉ ። ከአደጋ አፋፍና ከሞት ሥጣጭ የሚገኝ ፍቅር በሰላሙ ጊዜ ከሚገኘው ከማናቸውም ፍቅር በእጥፍ ድርብ እንደሚበልጥ አሳምረው ያውቃሉ ። ስለዚህም ይሆንን የጠርነት ዋዜማ ፍቅር እንደ ክፉ ቀን እህል ይቸግሉ ።

እስካርሌት በመጀመሪያ የተሰበሰበውን ሕዝብ ስታይ በፓርቲው ላይ በመገኘቷ የተሰማት ደስታ መሰን አልነበረውም ። እየቆየች ስትሄድ ግን በማማሽ ልቡና መንፈሳቸው ሰጣም ክፍ ያለውን ደስተኛ ሰዎች አሰኒና ደስታዋ ሁሉ ቀስ በቀስ በነነ ። እዚያ ያለች እያንዳንዷ ሴት እንደአሳት በሚቃጠል የፈንጠዝያ ስሜት ትንድዳለች ። እሷ ግን ያ ስሚት እውስጧ አይነድም ። እንዲያውም ቅጥ አሳጥቶ መንፈሷን አፍዝዞታል ። እንዴት እንደሆነ በማታውቀው ምክንያት አዳራሹም ቁንጅናውም ደበዘዘባት ። ሴቶቹም የደስ ደሳቸው አልሞጥ አላት ። ስታሳቁ ዓላማ ተብሎ በተከፈለው ሞቅ ያለ መስዋዕትነት የሚያንዐባርቁት ፊቶችም ጭራሽ የግልቱነት መልክኽ መስለው ታዩዋት ። ግብዝ ፊቶች !

በአንዳፍታ ባጥለቀለቃት ራስን የመግዛብ እውቅት ውስጥ እንደሰጠመች አፏን በመገረም ከፍታ ፣ ከነዚህ ሴቶች ጋር ጠንካራ የልብ ኩራታቸውን እንደማትጋራ ተገነዘበች ። ከነዚህ ሴቶች ጋር መስዋዕትነት የመክፈልን ጥላጐት እንደማትጋራ አጤነች ። በጠቅላ

@OLDBOOKSPDF

ላው ለዓላማው ብለው የሚያደርጉትን ነገር በሙሉ እሷ ከልቧ የማ
ታደርግ መሆኗን በሚገባ አሰበች ። በድንጋጤ እንድ ነገር ታሰባት ።
«እረ በጉዴ ጠፋሁ ! የልም ፡ የሰም እንዲህ ያሉትን ነገሮች ማሰብ
የለብኝም ! ስህተት ነው — ሐጢያት ነው» ያም ሆነ ይህ ግን ዓላማ
የሚሉት ነገር ለእሷ ምንም ስሜት የማይሰጣት ነገር መሆኑንና ሌሎ
ቹም ሰዎች ቢሆኑ በዚያ ሙሀዘ ባለ ግትር ዐይናቸው እያዩዋት
ስለአላማው የሚናገሩት ነገር ፈጠርሶ አይዋጥላትም ። የዓላማው ቅዱስ
ነት በፍጹም አይሰማትም ። ጦርነቱም ቢሆን ሰተቀደሰ ዓላማ የሚዋ
ጉት ጦርነት ሳይሆን ሰውን ለክንቱ እልቂት የሚዳርግ ፡ ግንዘብ ያለፍሬ
የሚያስጨርሱና ሊገኝ የሚችለውን ምቾት እንዳይገኝ እንቅፋት የሚ
ፈጥር ነገር ነው ። አታክቺና አስልቺ የሆነውንም የጥልፍ ጠለፋ ፡
የሐሽ ጥቅሰና የጨርቅ መሳጨቱም ዝንቱ ዓለም የማያልቅ ሥራ
ጠኟን ከማሻከርና ጥፍሯን ከማዶልዱም በቀር የሚረባ ነገር አለመ
ሆኑን አሙቃለች ። ደግ ያ ሆስፒታል ፡ አቤት አቤት አቤት ! ሆስፒ
ታል ብሎ ነገር መቼም ነፍሷን የሚያደማ ነገር ነው ። የሚከረፋ
የቆሳ ቁስል ፡ የማያቆም ሣቃሰትና የሞት ጣር ፡ የምትሞት ሴት ደም
የለሽ አስፈሪ ፊት ፡ ያም ሞት ። በጣም ሰልችቷታል ፡ እንገሽግሿታል ።

እስካርሴት ቅዝዝ እንዳለች አካባቢዋን ቃኘች ። እነዚህ አሁን
በልቧ ያስገቧቸውን ሀሳቦች በዙሪያዋ ያሉት ሰዎች ግልጽ ፊት
ላይ የሚያነቡባት መሰሏት ሰግታለች ። ምነው እሷም እንደሌሎች
ሰዎች ያለ ስሜት ቢስማት ምናለበት ፤ እነሱ ዓላማቸውን በቅን
ልቦና ይደግፋሉ ። በመሐል ልብ ሲሰጪለት ያስባሉ ። የሚናገሩና የሚያ
ደርጉትን ሁሉ ከጎጇቻቸው ይፍገራሉ ፡ ክንጇታቸው ያደርጋሉ ።
እናም እሷ በልቧ ምን እንዳለ እንድ ሰው እንኳ ቢጠረጥር . . . የለም
የለም ማንም ማወቅ የለበትም ! በውሸት አያስመሰለች ለዓላማው
ጉጉት እንዳላት በዓላማው እንደምትኰራ ማሳየት ይኖርባታል ። የእ
ንድ የኮንፌዴሬሲው መኰንን የሙት ሚስት መሆኗንና የሱ ዓላማ
ዓላማዋ ፡ የሱ ትግል ተጋድሎዋ መሆኑን ማስመሰል አለባት ። በሱ
ሐዘን ቅስሟ መነካቱን ፡ ልቧ ከሱ ጋር መቃብር መውረዱን በማ
ሳየት ባሏ ለዓላማው ብሎ በመሞቱ ፡ ዓላማውን ሲያራምድ በመው
ደቁ የምትዕናና መሆኗንም ማስገንዘብ አለባት ።

ወይኔ ! ምነው እሷ ከሴቶች ሁሉ የተለየችው ለምንድን ነው ?
እነሱ እንደሚያደርጉት ምንንም ሆነ ማንንም ማፍቀር እሷ በጭራሽ
አትችልም ። ምን ዓይነት ብቸኛ ስሜት ነው ያላት ? ካገር የተነጠለ . .
እሷ ሰራሷ ከዚህ ቀደም በመንፈስም ሆነ በአካል ብቸኛ ሆና አታ
ውቅም ። በመጀመሪያ እነዚህ ሀሳቦቿን ገፍትራ ለመጣል ሞክራነበር ።
ነገር ግን ሰራሷ ታማኝነትን አጠንክሮ ያስተማራት ተፈጥሮዋ እሻ

@OLDBOOKSPDF

ፈረኝ አለ ። ስለዚህ ወደ አዲስ አበባ ስመጣ ሚላኒ ከባንኩ ውስጥ ሆነው እንግዶቹን ሲያስተናግዱ ፣ ሞንቅላቷ ከራሷ ጋር መጣቱን ቀጥሏል ። እንደሁልጊዜው ራሷን ከራሷ ጋር ለማስተማመን ሰት ሞክር አዳገታት ።

ሌሎቹ ሴቶች ስለአገር መውደድና ስለዓላማ የሚያወሩት ሁሉ የማይረባ ነገር ነው ። ወንዶቹም ዋና ዋና ጉዳዮች እያሉ ስለአገሮች ነባነት የሚዘላብዱት ነገር ያው እንደሴቶቹ የማይረባ ነው ። እስካር ሌት እሳራ ሐሚልተን ብቻ ፣ እሷ ብርቱዋ ብቻ ናት በጠንካራ አየር ላንዳዊ ሞንቅላት ፍሬ ያለው ነገር የምታስብ ። ይሄን ዓላማ የሚባል የጅል ነገር አጥንት እንደያዘ ውሻ መገዝገዝ ብላ ይዛ አታላገንም ። በእንጀሩ ግን የራሷንም እውነተኛ ፍላጐት ተቅብላ ጅል መሆን የለ ባትም ። ራሷን አታታልልም ። ስለሁኔታው እቅጯን አውቃ አንድትረዳ የሚያደርግ ማስር ሞንቅላት አላት ። ያም ሆኖ የምታስብ የምታልመ ውን ማንም ሰው ማወቅ አይኖርበትም ። አሁን እሷ የምታስበውን ይሄ ለባዛር የተሰበሰበ ሕዝብ ቢያውቅ መቼም የጉድ ያለህ ብሎ ራሱን ይይዛል ፣ አሁን ደንግጥ ብድግ ብላ አርኬስትራው ያለበት መድ ረክ ላይ ቆማ ጠርነቱ ፍፊ — ቤስ ስለሆነ መቆም እንዳለበትና ሰው ሁሉ ወደቤቱ ተመልሶ ወደ ጥሞ አርሻው መሄድ እንደሚገባው ብታ ስረዳቸው ምን ይሉ ይሆን ? እንደዱሮው የፓርቲ ዳንስ መጀመር ፣ እንደ ጥንቱ ዳንጅ ማግኘጥና ጥሩ ጥሩ አረንዓይ ቅሚሶችን መልበስ እን ደሚያሻ ብትነግራቸው ምን ይሉ ይሆን ?

ለእንዲት ቅጽበት ራሷ ለራሷ ያስረዳችው ንግር ገባት ። ግን እሁ ንም አዳራሹን በመከፉት መመልከቱን አልተወችም ። የማከስር ሴት ልጆች ተመድበውበት የንበረው ባንኩ ወ/ሮ ሜሪዌዘር እንዳሉት እውነትም ሰብዙ ሰው ዐይን የሚያጋልጥ አይደለም ። ሰው እየመጣ እየገዛ የሚሄደው በጣም እየቆየ በመሆኑ በመሀል በሚፈጠ ረው ጊዜ እስካርሌት ሁሪያ ገባውን ደስተኛ ሕዝብ በቅንዓት ዓይን ማሬት ቀጥላለች ። ሚላኒ የእርካስሌትን የመከፉት ስሚት ልብ ብላ ለች ። ሆኖም ይሄ መከፋቷ የመጣው ቻርሊ አጠገቧ ባለመኖሩ ነው ብላ ስላመነች ምንም ዓይነት ንግግር እንደማትፈልግ እስባ ዝም አለቻት ። እስካርሌት አካባቢውን በጥላቻ ስታይ ሜላኒ ከባንኩ ሥሬ ያሉትን ዕቃዎች እያነሳች በመደርደር ለዐይን ማራኪ ለማድረግ ትሞ ጣራለች ። እስካርሌት ከደሴቪስና ከስቲፈንስ ፎቶ ግርጌ ያሉት እበቦች እንኳ ደስ አላሷትም ።

"የመስጥዕት ማቅረቢያ ቦታ ይመስላል" አለች በሽሙጥ ፣ "ሁሉ ሰው ስለነዚያ ሁለት ሰዎች የሚያወራውን ለሰማ አባትና

@OLDBOOKSPDF

ልጅ የሆኑ ያስመስላቸዋል ።" እንድ ድንገተኛ የፍራቻ ስሜት እንቅ አደረጋትና ነገሩን በቅን ልቡና ባለማየቷ ይቅርታ መጠየቅ ቃጥቷት ነበር ። ሆኖም በጊዜ ራሷን ገታች ።

"መቼም እውነት ነው" ከራሷ ሕሊና ጋር መጣት ገጠመች። "ሁሉ ሰው የተቀደሱ ሰዎች አድርጉ ያያቸዋል ። ሁሉቱም እንደኛው ሰዎች ናቸው ። እንደው አጋንንው ያወሩላቸዋል እንጂ ። መል ካቸውማ በጣም አስቀያሚ ነው"

እርግጥ ስቲፈንስ እንኳ አይፈረድበትም ። ሕይወቱን ሙሉ ጤና አጥቶ የኖረ ስለሆነ እንዲህ መሆኑ አይገርምም ። ዶቪስ ግን . . . ወደ ዚያ ጽድት ወዳለው ክሩ ፊት ቀና ብላ ተመለከተች ። የፍየል ጺም የሚ መስለው የአገጩ ጺሙ ነው በጣም የሚያናድዳት ። ወንዶች የሚያ ምሩት ወይ ሙልጭ አድርገው ሲላጩ አሊያም የከንፈር ጺማቸ ውን ብቻ ሲያሳድጉ ፣ ያ ካልሆነ ሙሉውን ሳጥም አድርገው ጺም በጺም ሲያደርጉት ነው ።

"መቼም ይሄ ቀጭጫ በሉ ቤት የመጨረሻ ቆንጆ ሆኖ መቅ ረቡ ነው" አለች እስክርቤት በልቧ ። ያ ፊት በውስጡ የአንዲት አገር ሽከም ለመሸከም የሚያስችል የረጋ እውቀት መኖሩን ሳታጤን ።

የሰም ፣ አሠኘስ ምንም ጥረት አይሰማትም ። መጀመሪያ በተሰበ ሰበው ሕዝብ ማህል መሆኗ አስደስቷት ነበር ። አሁን ግን በሕዝብ ማህል መሆኑ ብቻ በቂ እንዳልሆነ ገባት ። ባዛሩ ላይ ተግኝታለች ። ግን ከተሳታፊዎቹ አንዱ ለመሆን አልፈለችም ። ማንም ከጉዳይ አልጣ ፋትም ። ካሉት ባል ከሌሳቸው ሴቶች ሁሉ ወዳጅ ፍለጋ የማትዘዋ ወር ፣ ፍቅረኛ እንኳ የሌለ አሲ ብቻ ናት ። ደሞ ሕይወቷን ሙሉ እን ዲህ ሰው በተሰበሰበበት ቦታ ሁሉ የሰው ፀይን የሚያርፍባት የው በት ማዕከል ሳትሆን ያለፈቻበት አንድም የለም ። ይሄ ደግ ነገር አይ ደለም ። ገና አስራ ሰባት ዓመቷ ነው ። አማሮጅ ዳንስ ፍለጋ መሬት ይጭራሉ ። አሥራ ሰባት ዓመቷ ነው ። በእክላንድ የመቃብር ቦታ የተ ቀበረ ባል የነበራትና ወይዘሮ ፒቲ ፓት ቤት በአንቀልባ የሚታ ዘል ህፃን ያላት በመሆኑ ሰው ሁሉ ለዕድሜዋ በቂ ነገር ነው እያለ ያወራል ። እዚያ ካሉት ወጣት ሴቶች ሁሉ ቀላ ያለ ደረት ፣ በጣም ቀጭን ወገብና ሰዳንስ የሚመቹ እግሮች ያሏት እሷ ብቻ ናት ። ነገር ግን ለነሱ ይሄ ምንም ግድ ሳይሰጣቸው "ውድ ሚስቱ" ከሚል ጽሑፍ በታች ከቻርለስ ጐን እንድትጋደም ይፈልጋሉ ።

ዛሬ እስክርቤት በጥሩ ሁኔታ መደነስ የማትችል ሴት ሆናለች !! ዛሬ እስክርቤት መጨፈር ፣ መላፋትና መጨዋወት የማትችል ሴት

@OLDBOOKSPDF

ሆናለች ። ከቶውንም ከሌላ ሚስቶች ጋር ተቀምጣ ለሚደንስትና ለሚ
ሳቡት ልጃገሮች ቁንጥ ማውጣት የማትችል ሚስት ሆናለች ። የሙት
ሚስት ለመሆን እኮ ዕድሚዋ ገና ነው ። የሙት ሚስቶች ከዕድሚ
ያቸው ገፋ ያደረጉ አሮጊቶች መሆን አለባቸው ። በጣም ከማርጀታቸ
ውም የተነሳ መደነስና መጨዋወት እንዲሁም መደሰቅን የማይፈ
ልጉ ናቸው ። እረ ይሄ ደግ ነገር አይደለም ። ገና በአሥራ ሰባት ዓመቷ
የሙት ሚስትነት ክብርና ባለይዞታነት መታወቂያዋ ሆኖ እዚህ ቁጭ
ማለቷ መቼስ በጭራሽ ደግ ነገር አይደለም ። ድምፄን ቀስ አድርጋ ፣
እንግቷን በትህትና ደፍታ ፣ በጣም ቆንጆና ማራኪ ወንዶች ወደሷ
ባንኪ ሲመጡ እንኳ በባይ አሳምራ መቀመጥ በጭራሽ ደግ ነገር
አይደለም ።

እያንዳንዷ የሴትዮንም ለምገረድ በሰባት ወንዶች ማህል ቁማ
ለች ። የመጨረሻ አስቀያሚውም ለገረዶች እንኳ ወዳጅ ይዘዋል —
ከሁሉም የሚያናድደው ደግሞ የነበሯቸው ቁሚሶች ምርጥ ምርጥ
መሆናቸው ።

እሷ እዘህ እጅጌዋን እጅ እንዳዋ ድረስ ፣ እንግሊዜዋን ለገጯ
ድረስ ቆልፋ ከሸኘች የሠላር ጉንጭ የአንባት ሐብል ማሠሪያ ሌላ
የጌዋ ዘር የሌለበት ጥብር ቁሚስ ለብሳ ፣ ፉራ መስላ ተቀምጣ ፣ ቡሀቃ
የመሰለች አስቀያሚ ሴቶች ቆንጆ ቆንጆ ወንዶች ከንድ ላይ ተንጠልጥ
ለው ሲሳሳቁ እንድታስተውል ተፈርዶባታል ። ይሄ ሁሉ የሆነው ያ
ቻርለስ ሐሚልተን በዝግጅ ተለክፎ በመሞቱ ነው ። ደሞኮ እንደወንዶ
ዎቹ ጦር ማንባር ላይ በጀግንነት ቢሞት ኖሮ እንዲህ ሆኖ ሞት እያ
ሰኙ እንኳ በማውራት ጉዘናና ነበር ።ምን ያረጋል በኩፍኝ ሊልፈስ
ፈለ ሞተ ።

አስካርሌት በእልህና በንዴት እንደተሞላች ማሚ ካስተማረቻት
ሥነምግባር ወጣ የሚሰበኝ ባንኪ በከርኔ ተደግፋ ሕዝቡን ትመ
ለከት ጀመር ። ከርኔ ሞምዶድ ብሎ አስቀያሚ ሆነ ። አስቀያሚ ቢሆኑ
ምናለባት ? ምናልባት እኮ ከእግዚህ ከንዶድን የምታሳይበት አጋ
ጣሚ አይኖራት ይሆናል ። ወዲህ ወዲያ የሚዘዘሩትን በአበባ የተንቆ
ጠቆጡ ቢጫ የሐር ቀሚሶች በተራቡ ዐይኖቿ አየቻቸው ። የተሸነ
ሸነ ጥብጣብ ጠርዝ ያላቸውን ባለአሥራ ስምንት ሽብሸባት ሐም
ራዊ ቀሚሶች ፣ በአሥር ያርድ አርብ የተሰፉ እንደአረፋ የሚኩረፈረፉ
ሰማያዊ ቡፌ ቀሚሶች ሁሉ ታዩዋት ።የተገለጡ ደረቶች ፣ክሩቅ የሚ
ጣሩ አበቦች ያፈሰሰባቸው ቀሚሶች ያልፋሉ ። ያገድማሉ ። ሜይቤል
ሜሪዊዘር ከወገቡ በታች በጣም ሰፊ የሆነ ውሀ አረንጓዴ ቀሚስ
ከመልበሷ የተነሳ ወገቧ ቀጥኖ ቀጥኖ የጠፋ እስኪመስል ድረስ አንሶ

@OLDBOOKSPDF

ወድሚቀጥለው የሚሳብ መከፈያ ባንኮኒ አለፈች ። ቀሚሷ የክሬም ቀለም ባለው ጌዋ የተንቆጠቆጠና ባለፈው ጊዜ ኮንቶሮባንድ ሲገባ ከቻርል ስቶን የመጣ ሲሆን ፣ሚይቤል በእዩልኝ ስታተራምስው ላያት ሬት በትለር ሳይሆን ራሷ በኮንትሮባንድ ያመጣችው ያስመሰላታል ። "እቤት እኔ ይሆን ቀሚስ ብሰብስ ፣ እንዴት ያምርብኝ ነበር ።" አለች እስክርሌት ባሳቧ ያ ቀናተኛ ልጅ እየጋለበ ።"ወገቧ እንኳ የላም ወገብ ነው የሚያክለው ። ያ አረንጓዴ ቀለም ለእኔ የሚስማማ ቀለም ነው ። ያን ቀሚስ ብሰብስ ታዲያ ከነዚህ ውብ ወይኖቼ ጋር . . . እኔኮ እሚገርመኝ ወርቃማ ፀጉር ያላቸው ሴቶች እንዲህ ዓይነት የማይስ ማማቸውን ቀሚስ መልበሳቸው ነው ! አሁን ይቺ ቆሻሻ እንደቆየ አይብ አረንጓዴ የሆነች ሴት ይዟን ትልበስ ፣ በቃ ይሄንን ቀለም ከሐ ዜኔ ለሳቅሞ አልሰብስም ። እንደገና ባገባም ኃክኮ አሳደርገውም ። ከእንግዲህ ያረጁ ሚራሚ ባሳበሳ ቀሚሶችን እለብሳለሁ ።"

እስክርሌት አገር በቂ ሳይ የማደጭን ነገር ለአጭር ጊዜ አሰበች ። ለመጫወት ፣ ሁንጆ ሁንጆ ለመልበስና ለመደነስ እንዲሁም ወደ ግብዣ ቦታ ለመሄድ ጊዜው እንዴት አጭር ነው በሉ ፣ ያሉት ጥቂት በጣም ጥቂት ዓመታት ብቻ ናቸው ። ከዚያ ማግባት ። የጨዋ ልብስ ናቸው የሚባሉ ደብዛዛ ቀለም ያላቸው ቀሚሶችን መልበስ . . . ከዚያ ልጆች መቀፍቀፍና የወግብን ጭጭት ማበለቸት . . ከዚያ ከሌሎች ወሳጅችና የሙት ሚስቶች ጋር እጥፋ ሁቅምጠ የሚደንሱ ሌቶችን ማየት . . . መደነስ ከበፈለን ከባል ጋር ወይም ዳንስ ከማያውቁና እሰው አማር ሳይ እየዘለሉ ከሚወጡ ከማሌዎች ጋር ብቻ መደ ነስ ። ይሀንን ለማድረግ ከአምባችሁ ሴሎች ሴቶች ስለእናንተ እያወሩ ስማችሁን ያጠፉና ከነቤተሰባችሁ ጉድፍ ሳይ ይጥሏችኋል ። የወጣትነት ጊዜያችሁን እንዴት ማራኪ ለመሆን እንደሚቻል በማጥናት ማሳለፉ ችሁ ፣ የልጅገረድነት ዕድሜያችሁን እንዴት ወዳጅ እንደምትመርጡ ስትማሩ መክረማችሁ ከንቱ ይቀራል ። ትምህርታችሁን ግፋ ቢል ለዓ መት ወይ ለሁለት ዓመት ብትጠቀሙበት ነው ። ማሚና ኤለን ያስ ተማሯትን ትምህርት ለታ ለታውስ ሁልጊዜ ፍሬውን ለማየት ትችል እንደነበር አስባ መልካም ትምህርት መሆኑ ታወቃት ። የተወሰኑ ሕግ ጋት ተከተሉ ይሏችኋል ። እነሱ ያሉትን ስትከተሉ በውጤቱ የድል ዘውዳችሁን ትጭናለችሁ ።

ከአሮጊቶች ጋር ስትሆኑ ጨዋና ጥሩ ልጅ እንዲሁም ቀጥተኛ መምሰል ይኖርባችኋል ። ምክንያቱም አሮጊቶች ልጃገረዶችን እንደ ድጠት በቀናተኛ ዐይን ስለሚመለከቱ ከአፋችሁ አለፍ ወይ ከአይ ናችሁ ቆለጭለጭ ካላችሁ ዘልለው ሊያንቋችሁ ገማጅ ናቸው ። ከሽማግሌዎች ጋር ከሆነ ሴት ልጅ ቀልጣፋና ደፋር መሆን ይኖርባ

@OLDBOOKSPDF

ታል ። ድፍረቷ ግን አስከልፊያና አስከመንቲት መድረስ የለበትም ። እንደው ከንቱነታቸውን ለመቀበቅስ ያህል ብቻ አከክ ማድረግ ነው ። እንዲህ ካደረጋችሁላቸው ወጣት የሆኑ ይመስላቸውና ጉንጫችሁን ቆንጠጥ ያደርጉና እንዳንቺ ቀልጣፋ በዓለም አይገኝም ይሏችኋል ። እናንተም እንዲህ ሲሆኑ በታዩ ኩርፍ ምንትር ማለት ይኖርባችኋል። አለበለዚያ ጉንጫችሁን በደስታ ድብን አድርገው ይቆንጥጡና ስት ሙሹ ለልጆቻቸው በጣም ቀበጥ ናት ብለው ይነግሩላችኋል ።

ከወጣት ልጃገረዶችና ፀወጣትነታቸው ከገቡ ሴቶች ጋር ሰመ ሆን ከፈለጋችሁ ባገኛችኋቸው ቁጥር የኔ ቆንጆ እያሳችሁ መሳም አለባችሁ ። በቀን አሥር ጊዜ ብታገኟቸው አሥር ጊዜ መሳሳም ይኖር ባችኋል ። እሺችሁን አወጣባቸው ላይ ጠምጥማችሁ አንሰም እናንተ ወገብ ላይ እንዲያደርጉ — ምንም ያህል ሂርሃችን ብትጠሉት — መጣፋት ይኖርባችኋል ። የሚለበሱትን ቀሚስ አጭሩ አጭሩ ማሩም ልብስ ለብሰሽል ማለት ፡ ባልሽ እንዲት ጨዋ ሰው ነው ሚለትና በትሁትና እየላ ቃችሁ እናንተ ከእነሱ ምን ያህል አንደምታንሱ እናጠቀሳችሁ እነሱን ከፍ ከፍ ማድረግ አለባችሁ ። ከሁሉ በላይም እነሱ ያሰቡትን ከሚ ናገሩት የተሻለ እናንተ ሀሳባችሁን ለመግለጽ እንደማትችሉ በመ ጥቀስ ማስረዳት ማጸት ይሆናል ።

የዱሮ ወዳጆቻችሁ የሆኑ የቤሰቦች ሴቶች ባሎች ካጋጠሟችሁ ምንም ያህል ቆንጆና ማራኪ ቢሆኑ መሸሽና ዞር ማለት አለባችሁ ። ወጣት ባሎችን በታገኙ ያመለጧቸውን ወይም የቀረባችኋቸው ከሆነ ሚስቶቻቸው መርዝ ምሳላቸውን ሠልንሰው በጣም ወይን አወጣችሁ ፡ ልታይ ልታይ አሳችሁ እያሉ ስሜቸሁን በማጥፋት ሁለ ተኛ ጥቅረኛ እንዳታገኙ ያደርጓችኋል ።

ከወጣት ወንደላጤዎች ጋር ክሆነ ማን -አሆሆሆ ! በጣም የተለየ ጉዳይ ነው ! ! እነሱ ያሉበት ቦታ ቀስሰ ብላችሁ ትስቁና ለምን እንደ ሳቃችሁ ለማወቅ መጥተው ሲጠይቋችሁ ምክንያቱን አትንግሯ ቸውም ። ሐየት ብላችሁ እንደገና ሮክ ብላችሁ ትስቃላችሁ ። አሁ ንም ለምን እንደምትስቁ ለማወቅ ሲተርቧችሁ አሁንም ፈቃደኛ ሳትሆኑ ትተዋላላችሁ ። በዚህ ዓይነት የፈለጋችሁትን ጊዜ ያህል በሙ ሪያችሁ ልታቅዩዋቸው ትችላላችሁ ። በዓይኖቻችሁ እያባበላችሁ ወንዱ ብቻችሁን እንዲያገኛችሁ ፍላጎቱን የሚቀሰቅስ እንቅስቃሴ ታሳዩ ታላችሁ ። በዓይኖቻችሁ ታል ትገቡለታላችሁ ። ብቻችሁን አግኝቶ ልሳማችሁ ሲል ደግሞ በጣም እንደተናደዳችሁበትና ስሚታችሁን እንደሳዘው በማስመሰል ትነጫነጫላችሁ ። ታኮርፉላችሁ ። ተጣድፎ ስላስቀየማችሁ ይቅርታ እንዲጠይቃችሁ ካደረጋችሁት በኋላ በጣም

@OLDBOOKSPDF

በሚማርክ አንጋገር ይቅር ይለዋችኋል ብመንገር ለሁለተኛ ጊዜ ሊስማችሁ እንዲምክር ታመቻቹለታላችሁ ። ታዲያ ሁልጊዜ አይሁን እንኂ እንዳንዴ ትሳሙለታላችሁ ። (ኤለንና ማሚ እንኳ ይሄንን እላስ ተማሯትም ማን የሚያዋጣ ዘዴ መሆኑን አጥንታለች) ። ከዚያ ድንገት ለቅሏችሁን ትለቁትና ምን እንደነካችሁ እንደማታውቁ ፣ ከአንግዲህ የጹሮውን አክብሮት ሊሰጧችሁ እንደማይችሉ እየጠ ቀሰችሁ ትንሰቀሰቃላችሁ ። እነሱም እምባችሁን ያዶራርቁና ለትዳር እንደሚመጇችሁ እየገለጡ የጹሮ አክብሮታችሁን እንደሚጠብቁ ላችሁ ይነግሯችኋል ። ከዚያ ደግሞ . . . ኦ ወንደላጤዎች ሳይ ሲደረጉ የሚችሉ ብዙ ነገሮችን ታውታለች ። በማማሽ ጎን ፈገግታ መማረ ከን ፣ በጨዋታ መሀል ፍልቅቅ ማልትን ፣ ዳሌን እያውረገረጉ ቀሚስ እንደደወል እንዲወዛወዝ ማድረጉን ፣ ፅንባን እያዘሙ ማውረድን ፣ ለቅን በማድ ማስረዘምን ፣ የኔ ነፍስ የኔ ከብላላ እያሉ መሸንገልን ፣ ያዘኑ የራሩ መምሰልን ሁሉን አሳምራ ታውታለች ። እነዚህ ዘዴ ዎቹ ፣ እነዚህ ጥበቦቹ አስባ ከተጠቀመችባቸው በጭራሽ ኢላማቸ ውን አይስቱም ። በማንም ወንድ ላይ ይሠራሉ — ከአሽሌይ በስተቀር ። የለም የለም ። እንዚህን ሁሉ ዘዴና ጥበቦች መማር ዋጋም የለው ። ለእንድ በጣም አጭር ወቅት ብቻ ተጠቅማችሁባቸው ለዘለዓለም ትጥሏቸዋላችሁ ። ምን ዋታ አለው ? በጭራሽ አለማግባት እንዴት መታደል ነው ባሉ! ሠብ አፈንዳዴ ቀሚሶች ለብሶ እንዳማሩ መኖር ። ለዘለዓለም ቆንጆ ቆንጆ ወንዶች ሊያስከትሉ መኖር ። ዘለዓለም በፍቅር ባለሚለሶች እንደታጀቡ መኖር ። ሠኖም በጣም ለረጅም ጊዜ በዚህ ሁኔታ እንቆይ ብትሉ እንዶ ኢንዲያ ዊከስ ጭርንቁሳም አሮጊት ትሆኑና "አይ ይቹ ምስኪን" እያለ አገር ይጠቋቆምባችኋል ። የሽ ሙጡ ፣ የአሽሙሩና የሽሮዶላው ብዛት ከላይ ቆዳችሁን ይልጠዋል። ከውስጥ ቆሽታችሁን ፣ ያደብንዋል ። የለም የለም . . . ሴላው ሁሉ ይቅርና በመጣ ማዕረግ አግብት ባይሰቆም ባይጫወቱም ክብርን ጠብቆ ፣ ክብርን አስጠብቆ መሞት ይሻላል ።

እግዚአብ ሕይወት ማለት ምን ወጥንቅጡ የወጣ ነገር ነው በሉ፡ ይሄን ምርለስ የሚባል ሰው አግብታ ሕይወቷን በአስራ ሰድስት ዓመታ ያጨለመችው እንዴት ደደብ ብትሆን ነው ኧል ?

በንዴትና በተስፋ መቁረጥ ታጥራ ትዝታዋን ስታመነጭግ የተሰበሰበው ሕዝብ ወደ ሣድግጻው ሲመጣ ከሀሳቧ አላቀቃት ። ሴት ሴቶቹ በግፊያው መሀል ቀሚላቸው እንዳይገለብ ከሰውነታቸው ጋር ጥብቅ አድርገው ይዘው በጥንቃቄ ይራመዳሉ ። አስካርሌት በእግር ጥፍሯ ቆማ ክስብስቡ በላይ ስትመለከት የሚሊቪያው ሻምበል የአ ርኬስትራውን መድረክ ሲያዘጋጅ አየችው ። ምክ ብሎ ትእዛዝ

@OLDBOOKSPDF

ሲሰጥ ካሉት ሰዎች ግማሽ ያህል የሚሆኑት በአንድ መስመር ሰልፍ ገቡ ። ለጥቂት ደቂቃዎች ላብ በማንባራቸው እስኪንጠፈጠፍ ድረስ የሰልፍ ስልጠና ሲሰሩ የተሰበሰበው ሕዝብ አንድ ጊዜ አወካ ። አጨበጨበ ። እስካርሌትም እንደሕዝቡ ማጨብጨብ ግዴታዋ በመ ሆኑ አጨበጨበች ። ወታደሮቹ ከሰልፍ ሲለቀቁ ወደ መጠጡ ባን ኮኒ ሄዱ ። እስካርሌት ወደ ሜላኒ እየዞረች ፡ እንግዲህ ስለዓላማው ማስመሰሌን ልጀምር መሰለኝ አለችና በልፃ፡-

"በጣም ደስ ይላሉ ፡ አይደል ሜሊ?" አለች ።

ሜላኒ በባንኮኒው ሥር ያለውን ጥልፍ ለማመቻቸት ወዲህ ወዲያ ትላለች ።

"ብዙዎቹ ሻራጫ ዩኒፎርማቸውን ሲሰፉሱና ቨርጂኒያ ሲገቡ ነው በጣም የሚያምርባቸው" አለች ድምጽዋን ሰመቀነስ ምንም ሳትቸገር ።

አብዛኞዎቹ የሚለሽያዎቹ ከሩ አናቶች ወደመድረክ ተጠግ ተው የሚስጠውን ማሳሰቢያ ያሳምጣሉ ። ወይዘሮ ጉዊናን የሃያ አምስት ዓመት ወንድ ልጅዋ ዊሊ ዘማች ስለሆነ በስጋት ጉንጯ አንዴ ቀይ አንዴ ነጭ እየሆነ ይለዋወጣል ።

እስካርሌት ይሄ ከሰው ሁሉ ከሜላኒ በመምጣቱ ደነገጠች ።

"ለምን ሜሊ?"

"እውነት መሆኑንማ ታውቂያለሽ እስካርሌት ። ትንንሾቹን ወንዶች ልጆችና ሽማግሌዎቹን ማስቄ አይደለም ። ከሚለሽያዎቹ ውስጥ አብዛኞቹ መተኮስ ይችላሉ ። ስለዚህ በአሁኑዋ ደቂቃ እዚያ ሄደው መተኮስ ነበረባቸው ። "

"ማን እኮ... ማን እኮ" መናገር ጀመረች እስካርሌት ። እስከዛሬ ይህንን ነገር አስባበት አታውቅም ። "መቼም ሁሉም ወደ ጦርነቱ መሄድ የለባቸውም ። አንዳንዶቹ እዚሁ ቀርተው... " ያ ዊሊ ጉዊናን እዚህ አትላንታ ስለመቅረቱ ይቅርታ ሲጠይቃት ምን ነበር ያላት? "አዎ፡ ከሶማይሉን ከወረራ ለመጠበቅ አንዳንዶቻችን እቤት መቅ ረት ይኖርብናል ። ነበር ያለኝ ። "

"ማንም አይወርረንም ባክሽ" አለች ሜላኒ ቅዝቅዝ ብላ ፡ ወደ አንድ የሚለሽያ ቡድን እያየች ። "ደሞ ወራሪዎችን ለመከላከል በጣም ምርጡ መንገድ ወደ ቨርጂኒያ ሄዶ ያንኪዎቹን እዚያው መደ ምሰስ ነው ። ይሄ ባሪያዎች እንዳያምጹ ሚሊሺያዎች እዚሁ ይቅሩ

@OLDBOOKSPDF

የሚባልው ሁሉ ማለት ነው። የምትሠራው የመጨረሻ ግብ ገንዘብ ነው። የኛ ሰዎች በኛ ላይ ለምን ይነሳሱ ይሄ የፈሪዎች ለበብ ነው። የየዘገሩ ሚሊሺያ ወደ ቨርጂኒያ ከዘመቱ እርግጠኛ ነኝ ያንቺዎቹን ድባቅ እንመታቸዋለን። እዚያው እንዳሉ ነው"

"ለምን ሚሲ ?" አስክርሌት እንደገና ጮኸች፣ ትክ ብላ እያየች። የሚሲ ለስላሳና ጥቁር ዐይኖች በንዴት ቦግ ብለው አበሩ።" ያኔ ባል ለመዝመት አልፈራም ። ያንቺም ባል ሚንባሩን አሳጠፈም። እናም የሁለታችንም ባሎች አንዘምትም ብለው እቤት ከሚቀሩ ብሞት ይሻለኛል። . . . ውይ የኔ አመቤት፣ በጣም አዝናለሁ። እንዴት ጨካኝና ሀሳብ የለሽ ሆንኩኝ ዛሬ!"

የአስክርሌትን እጅ ሞቃ ሞቃ እያደረገች ለመነቻት። አስክርሌት አሁንም ትክ ብላ ታያታለች። የምታስበው ግን ስለሞተው ባሏ ስለቻርለስ አይደለም። የምታስበውም የምታልመውም ስለአሽሌይ ነው። ድንገት እሱም ሞቶ ቢያጋጥመውስ ፣ ወዲያው በጭንቅ ዘወር ብላ ዶክተር ሚድ ወደንሱ ሲመጣ ፈገግ አሉች።

"ታዲያስ ልጆች" አሰና ሰላምታ አቀረበ "ጨርሞ መም ጣታችሁ በጣም ጎሩም ነገር ነው። ዛሬ ግቻ ከቤታችሁ መውጣ ታችሁ በጣም ትልቅ መስዋዕትነት ነው። ሁሉም ነገር ለታላቁ አላማ ሲባል ነው። እናም እሁን አንድ ምስጢር እነግራችኋለሁ። ዛሬ ግቻ ለሠስፒታሉ የገቢ ምንጭ የሚሆን አንድ ትልምር ልፈፃር አስቤ ያለሁ። ሆኖም አንዳንዶቹን ሴቶች እንዳያስደነግጣቸው እሰጋለሁ።"

ንግግሩን አቁርጦ የጭፍል ጨሙን እያሻሸ በትንሹ ሳቀ።

"ውይ ምን ይሆን? እባክህ ንገረን"

"አሁን የመጣልኝ ሃሳብኛ ነገር ደግሞ አናንቲ እንድትገምቱ ማድረግ ነው። ብቻ እነዚያ የቤተክህነት ሰዎች ይህን ሠራህ ብለው ከከተማይቱ እንዳያባርሩኝ አናንቲው ትከሰክሱልኛላችሁ። ያም ሆነ ይህ ዞሮ ዞሮ ድካማችን ሁሉ ለሠስፒታሉ ነው። ታያላችሁ። ከዚህ ቀደም እንደዚህ ያለ ነገር እንኳን ተሠርቶ ተሞክሮ አያውቅም።"

ወዲያው ራመድ ራመድ እያለ አንድ ጥግ ላይ ወደተሰበሰቡት ሞግዚቶች ሄደ። ሁለቱ ሴቶች ያ የነገራቸው ምስጢር ምን እንደሆነ ለመገመት ገና ሲተያዩ ሁለት ጨዋ ሽማግሌዎች ወደ ነሱ ባንኪ መጥተው ጮክ ብለው አሥር ማይል እርዝመት ያለው ጥልፍ ጨርቅ እንፈልጋለን አሉ። አስክርሌት በልቧ መቼም ጨዋ ካለሆኑ ወንዶች ጨዋ ሽማግሌዎች ይሻላሉ አለችና በአግጫ ሥር እየሰካች ጨር

@OLDBOOKSPDF

ቁን ቆርጣ ሰጠቻቸው ። ሽማግሌዎቹ ወደ መጠጡ አካባቢ ሲሄዱ በነሱ እግር ሌሎች ተተኩ ። የነእስካርሌት ባንኮኒ እስከዚህም ብዙ ደምበኞች የለውም ። ይልቁንስ ሚይቤል ሚሪዌዘር የምታስካክበት፣ ሩኒ ኤልሲንግ የምትግስጥበትና የዋይቲንግ ሴት ልጆች እየቁ ቀላጠሩና እየፈነደቁ መልስ የሚሰጡበት ባንኮኒ ሞቅ ብሏል ። ሚሊ በጥሞና ድምጹን አጥፍቶ አንደሚሸጥ ባለሱቅ ፤ ወንዶች የማይጠ ቅሙበትን የጥልፍ ዝባዝንኬ ትሸጣለች ። እስካርሌትም የሷኑ ፀባይ ተከትላ ደምበኞቿን ታስተናግዳለች ።

ከነሱ ባንኮኒ ሌላ በእያንዳንዱ የሚሰበ መክፈያ ባንኮኒ ሳይ የሚ ስቁ ልጃገረዶችና ዕቃ የሚገዙ ወንዶች አሉ ። እነሱ ዘንድ የሚመ ጡት ጥቂት ወንዶችም ከአሽሌይ ጋር ዩኒቨርሲቲ አብረው እንደነ በሩና እንዲት ያለ ቆፍጣና ወታደር እንደነበር ያወሱላቸዋል ። ወይም ደግሞ ስለቻርልስ ክበድ ባለ ቃና ያነሱና አትላንታ እሱን መሳይ ሰው ማጣቷ በጣም ትልቅ ሐዘን መሆኑን ይናገራሉ ።

ሙዚቃው ድንገት ተሞ ብሎ ጀመረና "ጀኒ ቡከር ፣ ሽልፐ ዚስ ኒገር" የተሰኘውን ዘፈን አፈካው ። እስካርሌት የምትጮህ መሰ ላት ። ስመጀነስ ፈሰገች ። ሰመጨፈር ፈሰገች ። አሻግራ ወደ ወለሉ ተመለከተችና እግሯን ከሙዚቃው ቅኝት ጋር መታ መታ ፣ ጥቁ ቁር ውብ አይኖቿን አብራ ስለምለም ስለምለም አደረገቻቸው ። ከወለሉ መውጫ በኩል እስክነሱ ድረስ አተኩሮ የሚያይ እንግዳ ሰውዬ ትክ ብሎ በሚያስፈራና አመፃኛ በሚመስለው ፊቱ ላይ በተ ተከሉ ዓይኖቹ እጅድም ይታኛቸዋል ። ከዚያም ማንም ወንድ ሴቶች ላይ የሚያነበውን ግብዣ በነሱ ላይ አነበበና ለራሱ ፈገግ አለ ።

ጥቁር ሙሉ ልብስ የለበሰው ረጅም ሰው ባጠገቡ የቆሙትን መኩንኖች ድንክዬ አስመስሏቸዋል ። ከትከሻው ስፋ ያለ ነው ። ወገቡ ግን ቀጠን እያለ ይወርዳል ። በተወለወለው ቦት ጫማው ውስጥ የሚሸሸጉት እግሮቹ ያለቅጥ ትናንሾች ናቸው ። የለበሰው ጥቁር ሱፍና ያጣረ ሸሚዝ በሥነሥርዓት ከተተኮሰው ሱሪው ጋር ያለው አለ ባበሰ ከመልክና ከቁመናው አንፃር ሲታይ ጨርሶ አይገናኝም ። መልኩ ጥንቃቄ የበዛበት ይመስላል ። ሰውነቱ ጠንካራ ኃይለኛና ውስጡን አደገኛ የሚመስል ሲሆን የለበሰው ልብስ ግን ለስላሳና ዐይን የማይ ቆረቁር ፣ ሰለ ነው ። ፀጉሩ ድብን ያለ ጥቁር ነው ። የከንፈር ዲሙን ባጭሩ ተቆርጦታል ። ግን በጣም በጥንቃቄ ተስተካክሏል ። በእነ ባቢው ካሉት የተንዣረገገ ዲም ካላቸው የሀገሬው ፈረሰኞች ጋር ሲነፃፀር ከውጪ አገር የመጣ ባይተዋር ሰው ይመስላል ።

ያሀና ምግብ ካገኘ አይምሬ ነው ። ከዱሮውም የምግብ ፍላጎቱ ኃይለኛ ይመስላል ። ምግብ ከቀረበለት ያለፍርሃት ጥበስቅ አድርጎ

@OLDBOOKSPDF

ይበላል ። ስለራሱ በሚነገሩ መጥፎ ነገሮችና ስድቦች የማይረበሽና በራሱ እርግጠኝነት የሚሰማው ሰው ነው ። ወደ እስካርሌት ትኩር ብለው የሚመለከቱት ጠንካራ ዓይኖቹ የአሽሙር ብርሃን ይንፀባረቅባቸዋል ። በጣም ትኩር ብሎ የሰው ቆዳ እስኪሸበላ ድረስ ከማ ስተዋሉ የተንሳ እስካርሌት ወደሱ እንድትዞር ተገደደች ።

በጭንቅላቷ በእንደኛው ከፍለ የሚሰቃወስ ደወል ተንቃጨለ። ሆኖም ለጥቂት ቅፅበት ሰውየው አልተከሰተላትም ። ሰውየው ግን ገና ከወራት በፊት ለመጀመሪያ ጊዜ በሷ ላይ ዐይኑን የጣለ ሰው ነበር ። እጅረትም የደስ ደስ ረግጧቸን ከሩቁ መገበችው ። ለጥ ብሎ እጅ ሲነሳት በአክብሮት እንደመሳቅ አለች ። ካገኑበሰበት ቀና ብሎ በቅጥታ እንደሀንዶች አይነት የሚተጣጠፍ የሚመስል እረማመዱን አሳምሮ ወደ እሷ ሲመጣ ሰውየው ማን እንደሆነ በደንብ ስለገ ባት በድንጋጤ በእጅጉ አፏን ያዘች ።

መብረቅ እንደመታት ሁሉ አጢዋ ጹብ ብሎ ደንግጣና ባለች በት በድን ሆና እንደቆመች እሱ በተሰበሰበው ሕዝብ ማህል አቋ ርጦ ወደሷ መምጣት ጀመረ ። የእውር የድምበሯን ፊቷን አዙራ ወደ ምጣበና መጠጥ ከፍሎች ለመሄድ ስትጣደፍ የባንኩኒው ሚስማር የቀሚሷን ጫፍ አንሶ እንደጥንጠ የሙጥኝ አለባት ። ሚስማሩን ስማላቅቅ ቀሚሷን በኃይል እናትጡሎች እስኪቀደድ ድረስ ስትተና ነቅ ሰውየው አጠገባ ደርሶ ቆሟል ።

"ፍቃድሽ ይሁንና አመቤት" አለና ጭንበስ ብሎ ቀሚሷን አስለቀቀላት ። "ወ/ሮ እስካርሌት ፣ ታስታውቪኛልሽ ብዬ በጭራሽ ተስፋ አላደረግኩም ነበር ። "

ድምጹ እንግዳ ይሁን እንጂ ለጆሮ ደስ የሚል ነው ። በጥሞና የሚወጣ የጨዋ ሰው ድምጽ ለዛ አለው ። በቻርልስተናውያን ዝግ ተኛ ቅላጼ ቀጥ ብሎ የሚፈስስ ቆንጆ ድምጽ ነው ።

ቀና ብላ በለማኝ አይኖቹ ተመለከተችው ። ባለፈው ጊዜ የት እንደተገናኙ ትዝ አላትና ፊቷ ሳምባ መሰለ ። በሕይወቷ አይታ በማታ ውቀው ዓይነት በጣም የጠቆሩ ዓይኖቹ ከአይናቹ ጋር ተጋ ጨ ። አይኖቹ በፍጹም ጨካኝነት ፈንጥዘው ይደንሳሉ ። እዚህ ከሚ መጡት ሰዎች ሁሉ በጣም የምትፈራውና በሕልሟ ሳይቀር የሚመ ጣባት የዚያን ዕለቱን ከእሽሉይ ጋር የፊጸመችውን ነውረኛ ትር ኢት በእማኝነት ያየ በዓለም ላይ አንድ ሰው ቢኖር እሱውም እዚህ ተገኘ ። ይሄ ልጃገረድ የጨረሰና አገር የጠላው ርካሽ ሰው ዛሬ እዚህ ተገኘ ። ጨዋ ሴት እንዳልሆነች ከጥሩ ምክንያት ጋር የነገ ራት ሰው ይሽው እሁን እፊቷ መጥቶ ተገተረ ።

@OLDBOOKSPDF

ድምጼን ሰምታ ሚሳኒ ዞር ብትል ፣ እስካርሌት በሕይወቷ ለመ
ጀመሪያ ጊዜ የባሏ እሆኗ በመሆኗ እግዚኦን አመሰገነች ።

"ኦ . . . እንዴ ይሄ . . . ይሄ እኮ አቶ ሬት በትለር ነው ፣ አይደ
ለም እንዴ እንዴ "እሰኙ ሚሳኒ ፣ ከጭንቅ ረግማ ጋር እጅግ
እያዘረጋች ።" አንድ ጊዜ ተሳሳትን . . ."

"በተከበረውና በደስታ በተሞላው የቅዳሜያት ስነ ሥርዓትሽ ቀን
ነዋ" አለና የጀመረችውን አረፍተ ነገር ጨርሶ ጮንበስ ብሎ እጅግ
ተሰለመ ። "በማስታወቂያሽ በጣም አመሰግንሻለሁ ።"

"ከቻርለስተን ድረስ እዚህ መጥተህ ምን ትሠራለህ አቶ በትለር?"

"አባትሽ በጣም የሚያሰጨኝ የንግድ ሥራ አጋጥሞኝ ነው
ሜላኒ ። ከአሁን ወዲህ እንዳይህ ወዲ ከተማችሁ ብቅ ጥልቅ ማለቴ
አይቀርም ። ዕቃዎችን ማምጣት ብቻ ሳይሆን እንዴት እንደሚከፋፈሉ
ልማ ማየት እንዳለብኝ ተረድቻለሁ ።"

"ዋጣመጣችሁ . . ." ሚሊ ጀመረችና አጸረጠች ። ቆን
ድቦቿን ሽብሽብ አድርጋ ቆምና በደስታ ፈገግ አለች ።" አሃ
ብዙ ሲወራለህ እንሰማ የነበርከው ዜናህው ከፒኮን በትለር እን
ነህ ልክ! የሥውቅዕው ከንቅሮብኝዳስት ። እንዴ ፣ እዚህ ያለች አደ
ንዳችን ልጀገረድ እኮ እንኮ ያመጣቸውን ቅሚስ ነው የምትሰብሰው
እስካርሌት እልገረመች . . . በምትክት ምን ሆነሽል ወዲትእልብ
ሽን ደክመሽ? እስቲ ቁጭ በይ ።"

እስካርሌት እበርጩማዋ ላይ ወገባ ብላ ቁጭ አለች ። ትንፋሿ
ቅሎ ቅሎ ከመውጣቱ የተነሳ የደረቷ ቁልፎች ተበጥሰው የሚበሩ
መሰላት ። ዉ . . . ምን ዓይነት አስደንጋጭ ነገር ነው የገጠማት ፣
ይሄን ሰው ጸጥ አሳ ያስቀመጠው ብላ በልቧ ሚያም በወንድም አላሰበ
ችም ። ጥቅሩን ማሬገ ቢያውን እንቢ በትህትናና በማብረገብነት
በተሞላ እንቅስቃሴ ብለሆላት ያራግብላት ገባ ። ፊቱ አሁንም ጭንጫ
መሬት እንደመሰለ ይሁን እንጂ ዓይኖቹ መደነሳቸውን አሳውረጠም።

"እዚህ በጣም ይሞቃል እኮ" አለ ። "ወይዘሮ እስካርሌት እሃራ
ደክማ መውደቅ ሊያጓሉት ነው ። ወደ መስኩቱ ልውሰድሽ ይሆን?"

"የለም አልሄድም" አለች እስካርሌት በጣም በሚዘገንን የባለጌ
ቃና ፣ ሚሳኒ ምን መሆኗ ነው ብላ ትክ ብላ እስኪታያት ድረስ
ጥንክር አድርጋ ።

"ከአንጣጹህ ወይዘሮ እስካርሌት ኦሃራ መባል ቀርቷል እኮ
አቶ በትለር ፣ በኛ ቤተሰብ የዘር ግንድ ነው የምትጠራው ። ቻርለስ

@OLDBOOKSPDF

ሐሚልተንን በማግባቷ ስሟ ወይዘሮ እስክርሌት ሐሚልተን ሆኗል።" አለች ሚሊ። "አሁን እኮ የእኔ እህት ናት።" ብላ ከንዚያ ተወዳጅ ከሆኑ ፈገግታዎቿ አንዷን ረቂቅ አድርጋ እስክርሌት ላይ ፈነጠቀችባት። እስክርሌት፣ የባህር ወንበዴ ከመሰለው የካፒቴን በትዕር ፊት ላይ የምታየው ብዥል አንቆ የሚገላት መሰላት።

"እርግጠኛ ነኝ ስሁለት ቆንጆ ሴቶች ይሄ ትልቅ ፀጋ ነው" አለ ትንሽ እጅ እንደመንሳት ብሎ። ይሄ አባባል ሚንም ወንድ ደግሞ ደጋግሞ ያለው ቢሆንም እሱ ሲናገረው ግን ሁልጊዜውን የሚያስረሳት መሰለች።

"በዚህ አስደሳች የበዓል ቀን ባሎቻችሁ እዚህ እንዲሞጉ አምናለሁ መቼም ብታስቀሙኝ። ትውውቅን ማደስ ጥሩ በመሆኑ በጣም ደስ ይለኛል።"

"የኔ ባል እንኳ ቨርሚኒያ ነው ያለው" አለች ሚሊ ራሷን በኩራት ቀና አድርጋ። "ምርለስ ግን..." ብላ ድምጿ ተቋረጠባት።

"እጦር ከምጥ ውለዋ እንዳለ ዋቅ።" አለች እስክርሌት በደረቁ። ታልሞችን ይዋል የመታምኮው ያህል ነው የወረወረቻቸው ይሄ በትዕር የሚባል ፍጥረት ከዚህ አይነፍድም ማለት ነው የሚሊ ሚራ በመጋባት እስክርሌትን እያየቻት ቁልቁ ካፒቴኑ እንደመፀፀት አደርጎ።

"እመቤቶቹ በጣም ይቅርታ፣ አላወኩም እንጂ እንዲህ ያለውን ጥያቄም አልጠይቅም ነበር። ያም ሆኖ እባካችሁ ፍቀዱልኝና አንዷት አረፍተ ነገር ላክልበት፣ ለአገር መሞት ማለት ለዘለዓለም መኖር ማለት ነው።"

ሚሳኒ ከብርሃን ጋር በሚያንፀባርቁት እንባዎቿ ውስጥ ፈገግ አለችለት። እስክርሌት በደከማ አቅጣጫ የፈጠረችው ጥላቻና የውርደት ሥቃይ ስሜት ተሰምቷታል። ደሞ ማንም ወንድ የሚለውን እሱ ሲናገረው እኩ ተቃራኒ ትርጉም የሚሰጠውን አስተያየቱን ስንዘረ ማለት ነው። ሚሲ በካፒቴን በትዕር ውስጥ ምን እንዳለ ለማየት የማትችል ጅላ ጅል ሴት ናት። እሱ በእስክርሌት እያሾፈ ነው። ምርለስን ሳትወደው እንዳገባችው አውቋል። ውይ ምነው አምላኬ! ከሱ በቀር ይህንን ነገር ሌላ ሰው ጆሮ እንዳታስገባብኝ፣ ማንም የሱን ገፅ አይቶ እኔ እንደማንበው እንዳያነበው አድርግልኝ። እንድ ከፋ ሀሳብ ወደ አዕምሮዋ እየተሳበ ገባ። ይሄ ሰው ሚስጥሬን ለሌላ ሰው ይነግርብኝ ይሆን? እርግጥ ነው

@OLDBOOKSPDF

ጨዋ ወንድ አይደለም መቼም ። ወንዶች ጨዋ ሳይሆኑ ሲቀሩ መቼም ለሚያወሩት ነገር ወሰን የለውም አሉ ። ጸኃንት ለመስጠት እንኳ ልክ አይገኝላቸውም ። ቀና ብለ ብትመለከቱው በማራገቢያው እያራገበላት እንኳን ፥ አሁን ክዳርና ዳር ወደታች ጐትቶ የአሸሙር ሐሸን እያዘነ ነው ። በመልኩ ውስጥ የሚነበብ አንዳች ነገር መንፈሷን አሸነፈለትና ጉልበት አጣችታ በጥሳ ጕርፍ ተጥለቅልቃ ማራገቢያውን ከእጁ ድንገት ምንጭቅ አድርጋ መሰደቸበት ።

"እኔ በጣም ደህና ነኝ" አለች በእልህ ። "ወራሬን በማራገቢያ መመንጨር ያለብህ አይመስለኝም ። "

"እስክርሌት ፥ የኔ ቆንጆ ምነው ምን ሆንሽብኝ፣ ካፒቴን በትለር እባክህ ይቅር በላት ። የምሰጂኑ ባሏ የጅርሊ ሲም ሲነሳ የምታ ደርገውን አታውቅም ። ከሁሉም በላይ ደግሞ ዛሬ እዚህ ከነጭራሹ መምጣት እንዳልነበረብን መቼም ሳይገባህ አይቀርም ። እየህ ፥ አውንም ሀዘን ላይ ነን ። እሷ ደግሞ ትልቅ ጭንቀት ላይ ናት ። ይሄ ሁሉ ሳቅ ጨዋታ ይሄ ሁሉ ሙዚቃ ልታይ ልትሰማው የማይገባት ነገር ነው ። "

"ብደምብ ይገባኛል" አለ ቀመበለ ባለው አንጋገር ። ዘወር ብሎ አሳሽ በመሰለ ፊት ሚሊኒን ቦርቡሮ ሲመለከታትና የተጨነቁ ፀይኖቿን እጥግ ድረስ ወደ ውስጥ ሲያያቸው ገጽታው ቀስ በቀስ እየተለወጠ ያለፈቃዱ እክብሮትንና ጨዋነትን በጠቆረ ፊቱ ላይ ሜናቸው ። "እንደሚመስለኝ በጣም ደራርና የምትታይ ሴት ነሽ ፣ ወይ ዘሮ ሚላኒ"

እስክርሌት "ስለኔ ምንም አንድትጨነፍስ አልፈልግም ልበለው" ብላ አስባ ነበር ። በማህል ሚሊ ግራ በተጋባ ፈገግታዋ እጅባ መልስ ሰጠች፡-

"ካፒቴን በትለር ፣ የለም እኔ እንደሱ አይደለሁም ። የሆስፒ ታሉ ኮሚቴ በመጨረሻዋ ደቂቃ ላይ እዚህ እንድንመጣና የዚህን የባንኩኒ ሥራ እንድንሸፍን ስለፈለገ ... የትራስ ልብስ ነው ? ይሽው በባንዴራ የተሰጠፈ ቆንጆ የትራስ ልብስ"

ባንኩኒው ዘንድ ወደመጡት ሶስት ፈረሰኞች ዘወር አለች ። ለአንዲት ትንሽ ቅጽበት ሜላኒ ይሄ ካፒቴን በትለር እንዴት ጥሩ ሰው ነው የሚል ሀሳብ አእምሮዋን አቋርጦ አለፈ ። ከዚያ ከጥልቅ ጨርቅና ከአክታ መቀበያ ሳህን የተሻለ ነገር ቢሆን የምሸጠው እንዴት ጥሩ ነበር ብላ ተመኘች ። የትምባሆ መዓት እያኘኩ የሚ መጡት ፈረሰኞች ፍላጎት ገብቷታል ግን ምንም ልትረዳው አልቻ ለችም ። ወዲያው ስለካፒቴኑ ፣ ስለእስክርሌትና ስለአክታ መቀበያ

@OLDBOOKSPDF

ሣህን ማሰቧን ተወች—በርከት ያሉ ደምበኞች ባንድ ጊዜ አጥለቀለቋት ።

አስካርሌት አራሷ እያራገበች በርጩማዋ ላይ በፀጥታ ተቀምጣለች ። ቀና ብላ ለማየት ድፍረት አጥታለች ። በልቧ ይሄ ካፒቴን በትለር የሚባል ሰው መርከቡ ላይ ተሳፍሮ በመጣበት እግሩ እንዲመለስላት ትመኛለች ።

"ባለቤትሽ ከሞተ ቆየ እንዴ?"

"አዎን ። ብዙ ጊዜ ሆነው- ዓመቱ መምጣቱ ነው ። "

"ያማ የትየለሌ ነው ። "

አስካርሌት የትየለሌ ማለት ምን እንደሆነ አርግጠኛ አልሆነችም ድምጹ ውስጥ አንድ ሊያጠምደው የፈለገው ነገር እንዳለ ግን አልተጠራጠረችም ።

"ከተጋባችሁስ ብዙ ጊዜ ሆኗችኋል? መቼም ስለጥያቄ ድፍረቴ ይቅርታ ታደርጊልኛለሽ ። ከእዚህ አካባቢ ከራቅሁ ብዙ ጊዜ ስለሆነኝ ነው ። "

"ሁለት ወር" አለች አስካርሌት ካለፈቃዷ ።

"በጣም የሚያሳዝን ነው ባክሽ" ቀለል ያለ ድምጹ ቀጠለ።

ምን ያለው የተረገመ ሰው ነው አለች በልቧ ፣ በጣም አምርራ ። በዓለም ላይ ከሱ ሌላ ማንም ሰው ቢሆን ኖሮ ውጣልኝ ድራሽህ ይጥፋ እለው ነበር ። ግን ምን ያደርጋል ስለአሽሌይ የደበቀችውን ምስጢር የሚያውቅና ቻርለስን እንደማትወደው የተረዳ ሰው እንዴት ተደርጎ ይባረራል ። እጅ እግሬን አሳስሮኝ ቁጭ አለ ። አሁንም ማራገቢያዋን እያየች ፀጥ አለች ።

"ሕዝብ በተሰበሰበበት ቦታ ስትመጪ ይሄ የመጀመሪያሽ መሆኑ ነው ?"

"በጣም የሚገርም ነገር መሆኑን እንኳ አውቃለሁ ።" ፈጠን ብላ ለማስረዳት ሞከረች ። "ነገር ግን በዚህ ባንኪ ላይ የተመደቡት የማከለር ሴቶች ልጆች ለአስቸኳይ ጉዳይ ተጠርተው ስለሄዱ እኛ እንድንተካቸው በመፈለጉ ስለዘህ ሜላኒ እና እኔ . . . "

"መቼም ለታላቁ ዓላማ ሲባል የሚደረግ መስዋዕትነት ሁሉ ተገቢ ነገር ነው ።" እንዴ፣ ወ/ሮ ኤለሲንግ ይህንኑ መልስ ሰጥተዋት ነበር እኮ ፣ ሆኖም እሳቸው ሲናገሩት እንዲህ እንዳሁኑ ለየት አላለባ

@OLDBOOKSPDF

ትም ነበር። የስድብና የንዴት ተጠሪ የሆኑት ትኩስ ትኩስ ቃሎች መጥተውላት ነበር ግን እስንፈሯ ሲደርስ አፍና አስቀረቻቸው። ደሞምኳ አሷ እዚህ የመጣችው ቤት መቀመጥ ስለሰለቻት ነው እንጂ ለዓላማው ብላ አይደለም።

"እኔ ሁልጊዜ የማስበው" አለ በሻም በሚጥም ቃና ነገሩን እያመሳሰለ። "ይሄ እንዶ ሂንዱ ሱቲ ባህል ሴቲቱን ባሏ ከሞተ ጀምሮ ደስታ የሚባል እንዳትቀምስ፣ እንዳትዝናና በማድረግ እስክእለተ ሞቷ ድረስ ከል ሚልበስ በጣም ትልቅ ጭካኔ ይመስለኛል።"

"ሱቲ ነው ያልከኝ?"

ሳቀባት። እሷም እንደሁልጊዜው በድንቁርናዋ ስትናደድ ፊቷ ቀላ። እሷ የማታውቃቸውን ቃላት የሚጠቀሙ ወንዶችን እንዳንድ ነገር ትጠላለች።

"አንድ እፃር አንድ ሙያ ሲሞት ከመቅበር ይልቅ ያቃጥሉ ታል። ሚስቱም እዚያው የህዝን ሥነሥርዓቱ የሚከሄድበት ቦታ ድረስ ተወስዳ አብራ ትቃጠላለች።"

"እንዴት የሚዘገንን ነው አሰፈ የምን አብሮ መቃጠል ነው እሱ? ፖሊሶች ይሄ ሲሰራ ነበር ይላሉ እንዴ?"

"እሱስ ዝም አይሉም። አብራ አልቃጠለም የምትል ሴት ከማነ በረሰቡ ትገለላለች። ያላሩ ሴት ሂንዱዎች ቡና መጠጫ ያደርጓታል። የጨዋ ሴት አስተዳደግ የሌላትና አሳዳጊ የበደላት እያሉ ሥጋዋን ይከትፉታል። ልክ እሁን አንቺ ዛሬ ማታ ቀይ ቀሚስ ለብሰሽ ዳንስ ብትጫወቺ የሚሉሽን ዓይነት ማለት ነው። በበኩሌ የሙት ሚለቶችን በቂም የመቅበር ያህል የሚሰልሙን የደቡብን ባህልና ልማድ ከሱቲ የባሰ ጨካኝ አድርጌ ነው የማየው።"

"አንዲች ነኝና አስካርሌት! እንዴት አንተ! እንዴት እኔን ከሚች ባሌ ጋር አስከወዲያኛው በቂም ተቀበረሽ ትለኛለህ? ትልቅ ድፍረት ነው!"

"ይገርማል፣ ሴቶች ለባርነት የሚዳርጓቸውን ተመሳሳይ ሰን ለለቶች እንዴት እኩል እንደሚያቅፉ በጣም ይገርመኛል፣ የሂንዱን ባህል ጨካኝ ነው እያልሽ ታወግዣለሽ፣ ነገር ግን ዛሬ ማታ ኮንፌ ዴሬሽኑ ባይፈልግሽ ኖሮ ደፍረሽ ወዲህ ትመጪ ኖሯል?" አስካርሌት እንዲህ ያለው ከርከር ሁልጊዜ ግራ ያጋባታል። የሱ ደግሞ ከሌሎች የባሰ አደናግሯታል። ምክንያቱም የሚናገረው ነገር

@OLDBOOKSPDF

እውነት ይኑርበት አይኑርበት ለመገመት በማትችለው ሁኔታ ድብ ዝዝ ብሎባታል። ያም ሆኖ እሱን ለመርታት ጊዜው አሁን ነው።

"በጭራሽ አልመጣም ነበር። ብመጣ አየሁ... ብመጣ... በጣም ውርደትና... እኔ እንደማላፈቅ..."

አሽሚጣጭ ዐይኖቹ የምትናገራቸውን ቃላት አንድ በአንድ እያጠመዱ ያነጣጥሩባቸዋል። ስለዚህ መቅጠል አልቻለችም። ቻርሊን እንደማታፈቅረው አሳምሮ ያውቃልና ለማስመሰያ የምታዘጋጃቸውን የቃላት ድርድሮች እንድታቀርብለት ዕድል አይሰጣትም። ጨዋ ካልሆነ ወንድ ጋር እንዲህ ያለው ሙግት ውስጥ መግባት እንዴት ያለ አሰቃቂ ነገር ነው በሉ፡ ጨዋ ወንድ ሴት ልጅ መዋሸቷን ቢያ ውቅ እንኳ አምንሻለሁ፡ እውነትሽን ነው አያለ ያመናት ለመምሰል ይሞክራል። የደቡብ ሰዎች ጅግንነት ይሄ ነው። ጨዋ ወንድ ሀቁ ጊዜ ለሕግ ታማኝ ነው። የታዘዘውን ብቻ በመናገር ለሴቷ ሕይወት ቀላልና ጣፋጭ እንዲሆንላት ያደርጋል። ይሄ አሁን እፊቷ የቆመ ሰው ግን ስለሕግ ድንቃ የለውም። ሕግ አያግደውም። ስለዚህ ማንም ተናግሯቸው የማያውቅ ነገሮችን እያነሳ ማውጋት ያስደሰተ ዋል። ሰው የተከለከላቸውን ነገሮች ጥሶ የልቡን መናገር ያረካዋል።

"ትንሹሽ እስኪያጥረኝ ድረስ በትእግሥት እየጠበኩሽ እኮ ነው"

"አንተ በጣም ቀልብ የምትነፍገ ሰው ነህ።" አለች ረዳት በማጣት መሬት መሬት እያየች።

አሱ በሳንኮኒው ላይ ተደግፎ ኦፉ ጆሮዋ ጋ እስኪደርስ ድረስ ዘመም ብሎ ተጠግቶ አንድ ነገር ሹክ አላት። አኳኋኑ ሁሉ በአ ቲናዊያን አዳራሽ መድረክ ላይ የአንድን አልባሌ ሰው ገፀ ባህሪ ወክሎ እንደሚጫወት ቴዋናይ ነው።

"ጨዋዋ ወይዘሮ አትፈሪ! የሠራሽውን መጥፎ ሥራ ምስጢሩማ አጥብቄ ይዣዋለሁ።" አለ።

"ወይኔ ጉዴ" አለች በሹክሹክታ፡ ትኩሳቷ እየጨመረ። "እን ዴት እንዲህ ያለ ነውር ነገር ትናገራለህ? ስድነት ነው።"

"እኔ'ኮ ሕሊናሽን ቀለል ይልሽ እንደሁ ብዬ ነበር የነገርኩሽ ምን እንድል ጠብቀሽ ነበር? ቆንጂት ሆይ የኔ ሁኚ። አለበለዚያ ሚስጥርሽን ሁሉ እዘከዝከዋለሁ ልበል እንዴ?"

ካለፈቃዷ ዓይኖችዋና ዓይኖቹ ተገናኙ። ዓይኖቹ እንደትንሽ ልጅ ዓይኖች ያባብላሉ፡ ያጫውታሉ፡ ያሽኮረምማሉ፡ ያጓጓሉ። በድን

@OLDBOOKSPDF

ገት ሳጅን ለቀቀችው። ምንም ቢሆን ነገሩ ሁሉ ቅጥ አምባሩ ጠፍ ቷል። እሱም ከት ብሎ ሳቅ። በጣም ሮክ ብሎ በመሳቁ የተነሳ አዳራሹ ጥግ የተሰበሰበት ሞግዚቶች ወደሱና ወደሷ አቅጣጫ ተመ ለከቱ። የሚቹ የቻርለስ ሐሚልተን ሚስት ሙሉ በሙሉ ሳገሩ እንግዳ ለስው ባዳ ከሆነ ፀጉረ ልውጥ ሰውዬ ጋር መሳቅ መዳራት ደረጃ መድረሷን በማወ ገዝ ራስ ለራስ ገሞመው ሽመጣቸውን ቀጠሉ።

ከበሮ ደጋግሞ ተመታ። "አሽሽሽ... ዝም በሉ!" የሚሉ የብዙ ሰዎች ድምጾች ተሰሙ። ዶክተር ሚድ እመድረክ ላይ ወጥቶ ስዉ ዝም እንዲል እጁን በመዘርጋት ምልክት ይሰጣል።

"ደክመን ታክተን ሳይሉ ይህንን ባዛር እዚህ ያደረሱትን ታታሪ ሴኖች ከልብ ልናመሰግናቸው ይገባል። እነዚህ በአገር ፍቅር ስሜት የነደዱ ጠንካራ ሴኖች ያስገኙልን የገንዘብ ድል ብቻ አይደለም።" ሲል ንግግሩን ጀመረ። "ገንዘብ ከማስገኘታቸውም ሌላ ይህን ሻካራና ባዶ አዳራሽ ሕይወት ሰጥተው አሁን በዙሪያዩ ለማያቸው እም ቡጥ አበቦች መከማቻ የሚሆን የአትክልት ሥፍራ አድርገውታል። ለምለም ሸረንዓዴ መኖሪያ አሰመስለውታል።"

እያንዳንዱ ሰው ጭብጨባውን አቀለጠው።

"እነዚህ ታታሪ ሴኖች ያሳዩትን ጊዜ ብቻ ሳይሆን እያንዳን ዷን የአዳቸውን ቅንጣት ጉልበት ላያሳዩዙ ስማሰሞል። እነዚህ በየ ባንኩሩው መደርደሪያ ላይ ከዳሮው በእጥፍ ድርብ አጌጠው የም ታዩዋቸው ሁሉ የተዘጋጁት በደቡቦቹ ሴኖች ውብና ጠንካራ እጅች ብርቱ ድካም ነው።"

የተናገርከው ትክክል ነው የሚሉ አያሌ ጭብጨባዎች ፣ አስ ተጋቡ። ሬት በትለር በማይለሽነት ባንኩሂውን እንደተደገፈ እስክ ርሌት አጠገብ ቆሞ "ጉረኛ ፍየል! ፍየል አይመስልሽም?" አለና ጠየቃት።

አትላንታ አለኝ የምትለውን ውድ ዜጋ እንዲህ አቅሎና አዋ ርዶ ሲሰድበው ስትሰማ በመጀመሪያ ደነገጠች፡ ቁይታ ገረማት። በመቃወም ዓይን ተመለከተችው። ግን እውነትም ዶክተሩ በሹል አገጩ ላይ ካበቀለው ግራጫ ጢም ጋር ፍየል ይመስላል። በተና ገረ ቁጥር ጢሙ በክፉተኛ ጭካኔት ይርገበገባል። እስካርሌት ይህን እውነታ ስታይ ሰድ መጣችና እንደምንም ተቃቸው።

"ነገር ግን እነዚህ ነገሮች ብቻ በቂ አይደሉም።" ዶክተሩ ቀጠለ። "የሆስፒታሉ ኮሚቴ ሴኖች በእስታማሚ እጅቻቸው

@OLDBOOKSPDF

አያሌ ያተኮሱ ግንባሮችን አቀዝቅዘሞል ። አያሌ ጀግኖች ልጅ
ችንን አክመውና ጠግነው ከሞት አፋፍ መልሰዋል ። ለታላቁ ዓላማ
ችን ከፍተኛ መስዋዕትነት ከፍለው ሕይወታቸው በመጨረሻዋ
እስትንፋሳቸው ላይ ተንጠልጥላ የነበረች ጀግኖቻችንን በከፍተኛ
ጥረት ተንከባክበው ሕይወታቸውን አትርፈውልናል ። ታዲያ አሁ
ንም ምን እንደሚያስፈልገን ያውቃሉ ። እኔ አልዘረዝራቸውም ። ከአ
ንግሊዝ ብዙ መድኃኒት መግዛት ስለሚያሻን በርከት ያለ ገንዘብ
ያስፈልገናል ። ዛሬ ማታ በመሀከላችን አሥር ዓመት ሙሉ ደክመኝ
ላይል መድኃኒቶች ሲያመጣልን የነበረ ሰው ይገኛል ። ካፒቴን
ሬት በትለር ነው ። ”

ካፒቴን በትለር ሰምቼ አወቁትም አላውቁትም በግርማ ሞገስ
ዝቅ ብሎ እጅ ነሳ ። አስካርሌት ግርማ ሞገሱን ስታይ በጣም
ታላቅ ኩራት አለው አለች በልቧ ። እዚያ ላለ ለእያንዳንዱ ሰው
ያለው ጥላቻ በጣም ክፍ ያለ ከመሆኑ የተነሳ የተለመደ ማሾፉን
በዚህ አጋጣሚ የተወጣ ይመስላል ። እጅ ሲነሳ ከፍተኛ አድናቆት
ጭብጨባና እጥፍ ላይ ያሉት ሴቶች አንገታቸውን መዘዝ አድ
ርገው ሲያዩት እንድ ሆነ ። እሃ! የሚቼ የቻርለስ ሕሚልተን ሚስት
የምታጫውተው ስካ እሱን ኖሯል ፡ ቻርለስ ሞቶ ገና ሙት ዓመቱን
ሳናወጣ ከዚህ ሰውዬ ጋር ትገለፍጣለች ።

“ብዙ ተጨማሪ ወርቅ ስለሚያስፈልገን እሁን የምጠይቃችሁ
እሱን ነው ” አለ ዶክተሩ ቀጠለና ። “የምጠይቀው መስዋዕትነትን
ነው ። መቼም ይህን መስዋዕትነት ከጦር መስዋዕትነት እንበለው
እንጂ ፡ ግሬጫ የለበሱ ቆራጥ ሰምቻችን ከሚከፍሉት መስዋዕት
ነት ጋር ስናወዳድረው በሚያስቅ ሁኔታ ኢምንት ይሆናል ። እናቶ
ቹና እህቶቹ ዛሬ ጌጣ ጌጦቻችሁ ያስፈልጉናል ። እሁን የምጠይቀ
ውም እነሱን ነው ። እኔ ባልሆን ኮንፌዶሬሲው ይፈልጋቸዋል ።
መቼም ኮንፌዴሬሲው ለምኗት እጅጣን የማትዘረጋ ሴት እትኖርም ።
በጣም የሚያምር አመልማስ ጣት ላይ ያሉት ጌጦች እንዴት የተ
ዋቡ ናቸው ? ። መስተዋት በመሰለው የእገር ወጻድ ሴቶቻችን
ሳንቃ ደረት ላይ ያለው የአንገት ሀብል እንዴት ያንፀባርቃል ? ያም
ሆኖ የትኛውም ወርቅ ፡ የትኛውም ዕንቁ ፡ የትኛውም ክቡር ድን
ጋይ ለታላቁ ዓላማችን ከሚከፈለው መስዋዕትነት የበለጠ አያን
ፀባርቅም ፡ ከመስዋዕትነታችን የተሻለ አያበራም ። ወርቁ ቀልጦ ፡
ኩባር ድንጋዮቹ ተሸጠው የሚገኘው ብር መድኃኒት ለመግዛ ይው
ላል ። እህቶቻችን ሆይ ፡ እንግዲህ ሁለት እካለ ስንኩል ጀግኖች የላ
ጠራ ዘመቢል ይዘው ወደ እናንተ ይመጣሉ ። እናም . . . ” ከዚህ

@OLDBOOKSPDF

ወዲያ የተናገረው ቃል ከ[illegible] በመሸት ፡ በሀሳቃው ውስጥ
ገብቶ ሚሙቅ ጠፋ ።

እስካርሌት ስመጀመሪያ ጊዜ ሐዘንተኛ መሆኗ የሠራላትን ውለታ
እስባ ቀመስኔን አሰኛ ። ሐዘንተኛ ባትሆን ኖሮ ይሄኔ . . . በጣም
ውድ ዋጋ ያላቸው የጀሮ ጉትቻዎቿ ፡ እያቷ ወ/ሮ ሮቢላንድ የሰ
ጧት ያ ቡኾላ ወርቅ ክንውፍራም ሠንሠለት ፡ በጥቁር እንቁና በወርቅ
የተነጠረው የእጅ አልቦዋና የአንገት ሀብሏ ፡ ቅልጠው ነበር ።
ያ ቀጫጫ የዙፋቸ ተወላጅ ባልቆሰል እጁ የሳጠራ ዘንቢልን አንጠ
ልቁሎ ሲመጣ አየኾው ። በሷ በኩል ከለው ግድግዳ አካባቢ ያሉት
ሰዎች በዙሪያው ይራኩቱ ጀመር ። ወጣት ሳይባል አሮጊት ሴቶች
ሁሉ እየቅበዘ እያወኩ የጌጅ አልሟሾውን እያወለቁ ሰጡ ። የጀሮ ጉት
ቻቸውን ከጉጅሮዋቸው ቅጠል እንደሚቀጥፉት ሁሉ ሲመንጭቁት
ስታያቸው እንደቀበጨቀ ያህል እየታመሙ ይሰማት ። የእንገት ሀብላቸ
ውን መቆለፊያ ለመፍታት እንጂ ሴት ለሰንጂ ሌት እየተጋፉ ይተጋ
ገዛሉ ። መርፌ ቅልጥ የመሰለውን የአንገት ሐንጣልማይ ሀብሎች ይፈ
ታሉ ። ቤተክታታይ ወርቅ ከወርቅ ፡ ብር ከብር ፡ ብረት ከብረት ሲጋጩ
የሚሰማው ድምጽ ዓይነት ይሰማል ። ከዚያም "ቆይ ቆይ ፡ ኤሀግ
ፈትቻቸሀለሁ ፡ በል እነካ ያውልህ" የሚሉ ድምጾች ይሰሚሰሙ ፡
ሜይቤል ሜሪዌዘር ከከርሮኗ በሳጥና በታች ያጠለቀቻቸውን ውደ
ጥንድ ጥንድ አልበዎች አውልቃ ሰጠች ። ፋሲ አልሲንግ " እማዋ
አንም ልስዋ ?" አያለች ከትውልድ ትውልድ ሲወርድ ሲዋረድ መጣ
አሁን እሷ ሀጥር ላይ የተሰካውን ከውድ ዕንቁ የተሠራና በወርቅ
የተከፈፈ የፀጉር ጌጥ ከራሷ ላይ ምንጭቅ አደረገችው ። እያንዳንዳ
ስጠቃ ዘምቢራ ውስጥ በተጣለ ቁጥር ሚብጨባውና ጩኸቁ ለብቻ
ነው ።

ያ እየሰቀ የሚሾር ትንሽ ሰውዬ አሁን ወደ እነ እስካርሌ
ላንኪኒ እየመጣ ነው ። ቅርጫቱ ክብዶ ከንጹን ሊገነጥለው ደርሷል
ፊት በባለር እንደጥባ ከወርቅ የተሠራ የሊጋራ ማስቀመጫ አለ
ጥጉ ቅርጫቱ ውስጥ ወረወረ ። ስውዬው ወደ እስካርሌት ባንኮ
መጥቱ ቅርጫቱን አስቀመጠ ። እስካርሌት ምንም የምስጠው የ
ሽም በሚል እጅጅን ዘርግታ ራሷን ነቀነቀች ። መቼም ከገር ሕዝ
ሁሉ እሷ ብቻ ሳትሰዋ መቅረቷ የሚያበሽቅ ነገር ነው ። ወዲያው
የሠርግ ቀለበቷ እጣቷ ላይ በሰፈው ተንሰራፍቶ ሲያበራ አየችው ፡

ለአንዴት ግራ ለተጋባች ቅፅበት የቻርለስን ፊት ለማስታወ
ሞከረች ። ቀለበቱን ሲያጠልቅላት መልኩ ምን ይመስል እንደነበ
ለማሰብ ተጣጣረች ። ነገር ግን ሁልጊዜም እሱን ስታስታውስ እንደምት

@OLDBOOKSPDF

ሆነው በላይዋ ላይ የሚጫነው የብስጭት ስሜት በቀለበት ጊዜ ሆነ በረ መልኩን ትዝታ አደብዝዞ አላሳይ አላት ። ቻርለስ — ሕይወቷ ከዛሞ እንድትገታ ያደረገባት ሰው ። ቻርለስ — ገና በወጣትነቷ ፣ ገና በለጋነቷ እንደአሮጊት እግር እጅዋን ታቅፋ እንደትቀመጥ ያደረ ጋት ወንድ ።

በድንገት ቀለበቱን ከጣቷ መንጭቃ ለማውጣት ሳብ ብታደር ገው አሻፈረኝ አላት ። እሳው እጣቷ ላይ ተጣብቆ ቀረባት ። ያም የዙ ፍቫ ተወላጅ ትንሽዬ በው ወደ ሜላኒ አመራ ።

"ቆይ እንጂ" አለች አስካርሌት በጩኸት ። "ቆይ የምሰጥህ ነገር አለ" ቀለበቷ ወለቀላትና በሰንሰለት ፣በሰዓት ፣በቀለበት ፣በወርቅ መርፌ ቁልፍ ፣በእጅ አምባር ወደተሞላው ቅርጫት ስትሄድ እግረ መንገዷን ዓይኗ ከሬት በትለር ዓይን ጋር ተጋጨ ። በትንሹ ፈገግ ብማ ለቱ ከንፈሮቹ ከበታቸው ዝንፍ ብለዋል ።በበቀል ዓይነት ስሜት ቀለበቷን እቅርጫቱ ክምር ላይ ጨመረችው ።

"ውይ የኔ እመቤት" አለች ሜላኒ የአስካርሌትን ክንድ ጭም ድድ አደርጋ ይዛ "ዓይኖቿ ውብጥ ፍቅርና ኩራት ፏ ብለው ዘርታዋል። "አንቺ ጀግና ዋጀግና ጀግና ሴት፣ ቆይ እባክህ ዎሙ እስቃ ፔካርድ፣ እኔም የምሰጥህ ነገር አለኝ!"

ሜላኒ የራሷን የሠርግ ቀለበት ለማውለቅ ትታገል ገባች ። ይህ ቀለበት ዶሮ አሽሊይ ከስቀመጠው ወዲህ ከበታው ሳይነቃነት የቆየ ነበር ። ይህ ቀለበት ለሷ ምን ሚለት እንደሆነ ማንም ሰው እንደሚያ ውቀው ሁሉ አስካርሌትም ታውቃለች ። በሰንት መከራ ከጣቷ ጉላት ቀና ለጥቂት ሴኮንዶች እመዳፏ ላይ ቆየ ። ከዚያ በኩራትና በቅስታ እጌጣ ጌጡ ክምር ላይ ተጨነ ። አስካርሌት የበቀል ስሜት ሜላኒ ደግሞ የዘነጉ እምባ እየታየባቸው እጣጣ ወደ ተከማቹት እሮጌዎች ወደሚ ሄደው የዙፍቫ ተወላጅ ያስተውላሉ ። አጠገባቸው የቆመውን ፈት በትልርን ሁለቱም ዘነጣቱት ።

"እንቺ በድፍረት ባታደርጊው ኖሮ እኔም አልደፋፈርም ነበር" አለች ሜሊ ፣ ከንዲን አስካርሌት ወገብ ላይ ጠምጥማ በቅስታ ጭምቅ እያደረገቻት ። አስካርሌት ለእንዲት ቅዕበት የሜላኒን እጅ መነጭቃ ገፍትራ ባለ በሌለ አቅሟ "በእግዚአብሔር ተይኝ" ብላ ለመጮህ አስባ ነበር ። ጂራልድ ሲናደድ እንደሚያደርገው ሁሉ ልታምባርቅ ፈልጋ ነበር ። ነገር ግን ከሬት በትለር ጋር ዓይን ለዓይን በለተጋጨች ስሚቷን እቀዝቅዛ በትንሹ ፈገግ አለች ። መቼም ሜሊ የውስጥ ስሜቷ ሲፈነቅላት የልቧን በታፈነዳ በጣም ታናድዳለች ።ግን ምናል

@OLDBOOKSPDF

ባት እውነቱን ከምትጠራጠር እንዲሁ የስሜቷን እየተናገረች ብትቀመጥ ይሻላል ።

"እንዴት ደስ የሚል ትርዓት ነው ጃል" አለ ፊት በትለር ረጋ ብሎ ። "እንዲህ እንዲህ ያለው መስዋዕትነት እኮ ነው በመር ሜዳ ያሉትን ግራጫ ለባሽ ልጆች የሚያበረታታቸው"

በስድብ ልትወርድበት ከለበች በኋላ እንደምንም ታስችሎ ካፉዋ ሳይወጡ አሟሟቻቸው ። በሚናገረው ነገር ውስጥ ሁሉ የማሾፍና የአሽሙር ቃና አለበት ።እዚያው እባንኮኒ ጀርባ እየተንሰራደደች በልቧ ጥምድ አድርጋ እንደምትጠላው ታሰባት ።ያም ሆኖ እንድ ስሜትን የሚቀሰቅስ ፡የሚያሞቅ የሚያጋግል ፡ሕይወትን የተሞላና እንደኤሌክትሪክ የሚነዝር ነገር እላዩ ላይ ሰፍኗል ።በጥቁቁር ዓይ ጥቹ የሚታገላትን ይህን ሰው ለመቋቋም እየርሳንዳዊ ደሟን በሙሉ አጠራቅማ ሽንጧን ጎትራ ተነሳች ። ይሄን ሰው እንዴ መይ ሁለቱ ጉድ ልታደርገው ወስኔች ።የሲኝ የማል ምሰጢር ማወቅ ስለጠቀመው እንደልቡ ሊጫወትባት መንገድ አግኝቷል ።እሷ ደማሞ አንድ መላ ፈጥራ ይህን መንገድ ታደናቅፍበታለች ።በሕይወቷ ውስጥ ያለ አቅሟን ሁሉ አጠራቅማ ስለሱ ምን እንደምታስብ ልከ ልኩን ልትነግረው ቆርጣለች ።ማሚ ሁልጊዜ እንደምትለው ክኮምጣጤ ይልቅ ስኳር ብዙ ዝንብ ይሰባሰናይሀንን እፊቷ የቆመ ዝንብ በስኳሯ እጥምጣ ሁለተኛ በእጁ ላይ እንዳይጥላት ማድረግ አለባት ።

"እመለሳናለሁ" ነው ደስ በሚል ቃና ፡ሆነ ብላ ጥረቱ ያልነባት በማስመሰል ።መቼም ካፒቴን በትለርን ከመሰለ ታላቅ ሰው እንዲህ ያለ አስተያየት ማግኘት ትልቅ ፀጋ ነው ።

ሞንትላቱን ወደ ኋላ ጋለል አድርጎ ሳቁን በነባነት ለቀቀው ። እስካርሌት ግን በማላገጥ አምባረቀብኝ ብላ ፊቷ ሳምባ መሰለ ።

"የምትፈልጊውን ነገር ለምን ቢቀጥታ አትጠይቂም?" አለና ጠየቃት ።ድምጹን በጣም ዝቅ ሳላደረገው ፡ሚያወካው ሕዝብ ጩኸት ማሀል ለሷ ብቻ የሚሰማ ነው ። "የማትረባ ሞንጫ ራስና ስድ ነህ ለምን አትይኝም ገለምንስ ባንቺ ጉዳይ እጄን እንዳላስገባ ዓይንህን አልይህ አለበለዚያ እንዴን ግራጫ ለባሽ አንበሳ ጠርቼ ማንቁርትህን አንቆ እንዲያወጣህ አዶርጋለሁ አትይኝም ?"

ለዚህ ምላሽ የሚሆኑ እሳት ያለበሱ ቃላት አምላሷ ጫፍ ላይ መጥተው ነበር ።ሆኖም በጅግንነት ራሷን ገትታ "ምነው ምን አለኩህ ካፒቴን በትለር! ምነው እንዲህ ከፉ ክፉ ያናግርሃል! እንዴት

@OLDBOOKSPDF

ያለህ ዝነኛ ሰው እንደሆንክ አገር አውቆት ዐሐይ ሞቆት ያበቃ ነገር መሆኑን እንደማናውቅ ሁሉ እንዴት እንደዚህ.."

"ባንቺ ቅር የተሰኘህበት ነገር ስላለ ነው ፡አስቀይመሽኛል ።"

"አስቀይመሽኛል ?"

"አም ።በመጀመሪያ ያ ሁሉ ነገር በተከሰተበት ዕለት ሳገኝሽ ፣ የማታ ማታ ቁንጅ ብቻ ሳትሆን ድፍረትም ያላት ማሩም ሴት እገ ኝሁ ብዬ አስቤ ነበር ።አሁን እንደማይሽ ግን ቁንጅና ብቻ አንቺ ድፍ ረቱ የለሽም ።"

"ፈሪ ናት ማለትህ ነው እንዴ ?"እንደዶሮ ተርገፈገፈች ።

"እንዴታ ፡አየሽ በትክክል የምታስቢውንና አልብሽ ውስጥ ያለውን የመናገር ድፍረት የለሽም ።መጀመሪያ ሳገኝሽ እንዲህ ብዬ አስቤ ነበር፡—የዚህች ዓይነት ሴት ከሚሊዮን አንድ ቢገኝ ነው ። እንዶሌሎቹ ጅል ሴቶች ራሷ የሚሰማትን ሳይሆን እናቶቿ የሚሉትን የምታምን ሴት አይደለችም ።እንደሌሎቹ ደደብና ግብዝ ሴቶች አውነተኛ ፍላጐቷን በሆዷ ቁበራ በሚያሞግሩ ሺህ ቃሳት ማር የሳሰ ንግግር የተሸፋፈነ ነገር አትፀፀብድም ።የሚያሳስብ ትልቅ የልብ ቁስል አያ ላቸው በጣም ደስተኛ ልመምስል እንደሚፈልጉት ሴቶች አይደለ ችም ።ይህች የአሃራ ልጅ የትም ምሚገኝ ብርቅ ፀባይ ያላት ናት። የምትፈልገውን ታውቃለች ።የምትፈልገውን አቅጩን ለመናገር ወደ ኋላ አትልም — ከሰፈለገም የአበባ ማስቀመጫ ትመረውራለች ።"፡

"ወይኔ" አለች ጉዴት አየተናንቃት ። "እንግዲያው እልቤ ውስጥ ያለውን ነገር አሁኑ አንግርሀለሁ ።ጨዋ የጨዋ ልጅ አስተዳደ ጨዋ ብትሆን ኖሮ እዚህ መጥተህ አታነጋግረኝም ነበር ።ሁለተኛ ዓይንህን ማየት የማልፈልግ መሆኔ ይገባህ ነበር ፡አንተ ግን ስድ ነህ በጨዋነት ባጠገቡም ደርሰህ አታውቅ፤ የማትረባ ስድ አደግ ፍጥ ረት ነህ ።ደሞ ጎና ለጎና ከያንኪም ደብቀህ የምታስባቸው ጀልባ ዎች አሉልኝ ብለህ እዚህ ስንት የተከበሩና ቆራጥ ሰዎች ባሉበት በታ የማንሳጠጥ መብት ያለህ መስሎህ ሲታላቁ ዓላማ የሚሰጨ ውድ ልጅኛ ላይ በማሾፍ..."

"በታ በታ ።ዘውሽ የኔ እናት ይብታሽ ። "አለ በፈገግታ ልመና። "ንግግርሽን ስትጀምሪ ደህና የልብሽን ተናግረሽ ነበር ።ስለዚህ ስለዓላማ የምታወሪውን ገባዝንኩሽን ግን በፊጠረሽ ተጅኝ ።ስለሱ መስማት በጣም ሰልችቶኛል ።ደሞ ከምላሴ ፀጉር ይነቀል አንቺም እራስሽ ብትሆኚ ።"

@OLDBOOKSPDF

"ምንበ እንዴት ባክህ!? እንዴት ኢንዲህ ብለህ" ለመናገር ከጀመረች በኋላ ሚዛኗን ጠበቀችና እቋረጠች ።ከዚያም በትክክል አመዛዝና ስታየው በሱ ወጥመድ ውስጥ መውደቋ አናደዳትና ከነጭራሹ ዝም ማለቱን መረጠች ።

"እንቺ ሳታይኝ በፊት እዚያ መውጪያው ላይ ቆሜ ሁሉን ነገርሽን በጥሞና ሳዳምጥ ነበር" አለ ።"ሴቶችንም ሴቶች አስተውያቸዋለሁ ።እነሱ ከአንድ ጉብሪካ ተጠፍጥፈው የተመረቱ ይመስል ፊታቸው ላይ የሚነበበው ሁሉ አንድ ዓይነት ነው ። ያንቺ ግን ከሁሉም ይለያል ።ያንቺ ፊት ለማንበብ በጣም ቀላል የሆነ ፊት ነው ።ልብሽ እሥራሽ ላይ አልነበረም — ሌላ ነገር ነው የምታስቢው ደሞ እርግጠኛ ነኝ የምታስቢው ነገር ከስታቋቋ ዓላማችንም ሆነ ስለሆ ስፒታላችን አይደለም ።የምታስቢው ነገር አፈትሽ ላይ ቁልጭ ተደርጐ ተጽፏል — ለመዳንክ ለመሟወት ትፈልጊያለሽ ግን አልቻልሽም ።ስለዚህ ብሽቅ ብለሻል ።ሊሙነቱ ይሻው ነው ።በይ እውነቱን ንገሪኝ ።ቀሳሳትኩ ?"

"ካፒቴን በትለር ከዚህ በኋላ ምንም የምነግርህ ነገር አይኖርም" አለች በተቻላት ሁሉ በሥነ ሥርዓት ለመናገር እየሞከረችና የተረፋትን የክብር ብጥስጣሽ እየሰባሰበች ። "ታላቁ ኮንትሮባንዲስት" ቢሉህ ጊዜ እኮ ሬዶንን ለመሳደብ መብቱ ተሰጠህ መሪን ተለቀቅክ ማለት አይደለም ።"

"ታላቁ ኮንትሮባንዲስት ፣ያ እንኳን ቀልድ ነው ።የእኔ እመቤ ቤት ፣አስቲ ከፊትሽ ከማባረርሽና ጉደል ከመጣልሽ አስቀድመሽ አንዲት ነገር የመተግበሪያ ጊዜ ፍቀጅልኝ ። እንዳንቺ ያለች ቢጥሌ አር በኛ እኔ ለታላቁ ዓላማ ስላደረኩት አስተዋጽኦ የምታውቀው ነገር የቱወናበደ እንዲሆን አልፈልግም ።"

"እኔ ያንተን ጥራ ለማጸመጥ ፍላጐት የለኝም ባክህ ።"

"አየሽ የኮንትሮባንድ ሥራ እኔ ግንዘብ የማገኝበት ንግድ እንጂ ሌላ ነገር አይደለም ።ይገርምሻል ፣ባለፈው ወር ጀልባዬን እኔው ዮርክ ወደብ በቀጥታ ልኬ ጫንኳት ።"

"እረ በጉዴ ወጣሁ! ምን?" ብላ ጮኸች ፣ያለፈቃዷ ፣ነገሩ ፍላጐት እያደረባት ። "አልተከሰተበትም? እንዴት አመለጥክ ?"

"አይ የኔ የዋህ፣ በጭራሽ አልነኩኝም ። ግንዘብ ለማግኘት ብለሽ ለኮንፌዴሬሲው ዕቃ በመሸጥሽ ቅር የማይሰኙ ብዙ የሕብረቱ ቆራጥ አርበኞች አሉ አክ! ጀልባዬን ወደኋው ዮርክ አስገባለሁ ።ሀያንኩ

@OLDBOOKSPDF

ድርጅቶች የምፈልገውን እገዛለሁ (እርግጥ በምስጢር ነው) ከዚያ ወደምፈልበት እሄዳለሁ ። ያ ትንሽ አስጊ የሆነ ጊዜ ደግሞ ወደነሱ እሄድና በነዚያው የጎብረቱ አርበኞች አማካይነት ባሩድ ፣ ጥይትና ምርጥ ምርጥ ቀሚሶችን አመጣለሁ ። ወደ እንግሊዝ ከመሄድ የቀሰለ አመቺነት አለው። አንዳንዴ ወደቻርልስተንና ወደ ቄልሚንግተን ዕቃ ማሻገር አዳጋች ነው ።ነገር ግን ቅንጣት ታህል ወርቅ እዛ ያላት ቀጋ በጣም ይገርምሻል ።"

"ያንኪዎች ምን ያህል ርህሮች እንደሆኑ እንኳን አውቃለሁኝ። እነዚያኞቹ እንደዚህ መሆናቸውን ግን"

"ያንኪዎች የጎብረት ድርጅቱን ከድተው ዕቃ እያወጡ እየ ሸጡ የተቀደሰ ገንዘብ ማግኘታቸውንስ ለምን ትሸሽገዋለሽ ? አንድ መቶ ዓመት ቢያልፍ እንኳን የማይለወጥ ነገር ነው ። ውጤቱ ዞሮ ዞሮ ያው ነው። ቀስ በቀስ ኮንፌዴሬሲው ድባቅ እንደሚመታ፣ እንደ ሚሸነፍ ያውቃሉ ። ታዲያ ዕቃ እየሸጡለት ቢያተርፉ ምናለበት ?"

"ድባቅ እንደሚመታ ?"

"እንዴታ ፡ አሳምሮ ነዋ!"

"በል አሁን ቆጥ ብለህ ነገር ሳይመጣብህ ትተህኝ ትወጣ ለህ እትወጣም ?ነው ወይስ ካንተ ለመራቅ ሠረገላዬን አስመጥቼ ወደቤቱ ልሂድልህ?"

"አመፀኛ ግንፍለተኛ ፍጥረት !" አለ ሴላ ፈጠን ያለች ፈገግታ እያሳየ ።አትም የለሽ ንዴትና ብስጭት ልቧን እንዳንድ ነገር እያስደ ለቀው ደረቷ ከፍና ዝቅ እያለ ቁና ቁና ስትተነፍስ እጅ ነስቷት ጥሏት ሄደ ። የመከፋት ስሜት እውስጧ የቋያ እሳቱን ያነድባታል ። በምኞት የሠራው ፎቅ የተናደበት ህፃን ልጅ አእምሮ ውስጥ የሚፈ ጠር ዓይነት የመከፋት ስሜት እውስጧ ይንቀለቀላል ።ሴሎቹን ኮን ትሮባንዴሰኖች እንዴት ደፍሮ ቢያጭበረብራቸው ነው ዝናን ያተረ ፈው ። ኮንፌዴሬሲው ድባቅ ይመታል ብሎስ እንዴት ደፍሮ ይናገ ራል ። ለዚህ የድፍረት ንግግሩ መቼስ መረሸን አለበት ። እንደ ከሀዲ መረሸን አለበት ።በአዳራሹ ውስጥ ዙሪያ ገባውን የተቀመጡትን ድል እንደሚያደርጉ እርግጠኛ የሆኑ ፡መስዋዕት ለመክፈል የተዘጋ ጀና ጀብድ ለመፈጸም የቆረጡ የምታውቃቸውን የጀግና ፊቶች ሁሉ ተመለከተችና አንዲት ቀዝቀዝ ያለች አየር ልቧን ዳሰስ አደረገቻት ። ድባቅ መመታትን እነዚህ ግንባር አያጥፌ ሰዎች እያሉ እንዴት ሊሆን ይችላል ? በጭራሽ አይደረግም ። እንዲህ ያለውን አኩይ ሀሳብ ማሰቡ ራሱ የማይሞከር ነው ። እምነቱ ቢስነት ነው ።

@OLDBOOKSPDF

"ሁለታችሁ ታንሸዋሹኩ የነበረው ምንድነው?" አለች ሚላኒ ደምበኞቿ ሊሄዱላት ወደ እስካርሌት ዞራ። ወይዘሮ ሚሪዊዘር ዓይኖቻውን እናንተ ላይ ተክለው ስለነበር እኔም ደጋግሜ ሳያችሁ ነበር። ሙቼም የላችውን ምላስ ታቂዋለሽ፣የኔ እመቤት።"

"... ስውየው በጭራሽ አይቻልም እኅቴ፣ የመጨረሻ ስደ አደግ ባለኔ ነው!" አለች እስካርሌት። "እኛሀን ሚሪዊዘር የሚባሉ ነዝናዛ አሮጊት እንኳ ተያቸው ይሰፍልኖ። በዐኩሌ ጎና ለጎና እሳቸው ደስ ይበላቸው ብዬ እንደሀግን መሸቆጥቆጥ ትክት ብሎኛል—የራሳቸው ጉዳይ።"

"ሙይ ምንው እስካርሌት" ሚላኒ ራሀ እንደተዋረደች ያህል እሙሽት።

"ክሽሽሽ" አሰኞ እስካርሌት "ዶክተር ሚድ ሌላ ማላስቢያ ሊናገር ነው።"

ዶክተሩ ወደቃቸውን ለሰጡት ሴቶች ምሲጋናውን በማቅረብ ንግግሩን ሲጀምር ሕዝቡ ባንድ ጊዜ እርጭ አለ።

"የተከበራችሁ ወገኖቹ እሁን ደግሞ እንድ የሚያስገርም ዱብ ዕዳ እጥልባችኋለሁ።ይሄ አስገራሚ ነገር አንዳንዶቻችሁን ላያስደንግጣችሁ እይተርም። ነገር ግን የምታደርጉት እያንዳንዱ ነገር ለዚህ ሆስፒታልና በመር ግንባር ለወደቁ ልጆቻችን ጥቅም የምትውል መሆኗን እንድታስተውሉ አጠይቃሰሁ።"

ሰው ሁሉ ወደፊት ሳብ ሳብ አደለ ይሄ ዶክተር ምን ሊያስደነግጥ የሚችል ነገር ያመጣ ይሆን ነበሚል ጉጉት ልቡ ቆሟል።

"እንግዲህ ዳንሱ ሊጀመር ነው።እንደምታውቁት የመጀመሪያው የሪል ዳንስ ሲሆን ለስላሳ ቫልስ ይቀጥላል።ከዚያ ፀተክታታይ ሌሎች ዳንሶች ይቀጥላሉ። መቼም የመጀመሪያውን የሪል ዳንስ በመሸከር ክር የሚመራው ማን እንደሆነ አውቃለሁ። እናም" ዶክተሩ ጣ ከተሰበሰቡት ምግዚቶችና ደንግጠሮች ማህል ወደተቀመጠችው ሚስቱ ታኘ።" ጭበገ፣ ራሳችሁ ከመረጣችኋት ሴት ጋር በመደነስ የሪል ዳንሱን ለመምራት ትችላላችሁ። ታዲያ የምትመርጧትን ሴት የምታስነሱት እንዲሁ አይደለም። ተጫርታችሁ ነው። የጫረታው ገቢ ለሆስፒታሉ ይሆናል።የማጫርተው እኔ ነኝ።"

ማራገቢያዎች እርግብግብታቸውን መሀከል ላይ አቆሙ።የመረጃምና የመደሰት ሀምሀምታ አዳራሹን ሞላው። የሞግዚቶቹ አካባቢ ጨኸትና ጭብጨባ ዘረከተበት።ወይዘሮ ሚድ ባሏን ለመደገፍ እጁ

@OLDBOOKSPDF

ትበል እንጂ በድርጊት መፈጸሙን አልወደደችውም ። ጨንቋታል። ወይዘሮ ኤልሲንግ ፡ ወይዘሮ ሜሪዌዘርና ወይዘሮ ዋይትንግ በንዴት ፊታቸው ቀልቷል ። ሆኖም በድንገት የክተማ ጠባቂዎች የድጋፍ ጭብጨባ አሰሙ ። ሌሎቹ ዩኒፎርም ለባሽ እንግዶች ተከተሉ ። ወጣት ወጣቶቹ ሴቶች እያጨበጨቡ ከመቀመጫው ተነስተው ዘለሉ።ፍንድቅድቅ አሉ።

"ያዜ ነገር ትንሽ ትንሽ የባሪያ ሣረታ አይመስልሽም ?" አለች ሜላኒ በሹክሹክታ ፡እስክ አሁኗ ደቂቃ ድረስ እንከን አይወጣለትም ትለው የነበረውን ዶክተር በጥርጣሬ ዓይን እያየች ።

እስካርሌት ምንም አልተናገረችም ። ግን አይኖቿ ያበራሉ ። ልቧ ትንሽ ሕመም ቢጤ ተሰምቶት ተኩማትሯል ። አዬ ፡ምነው የመጣ ሚስት ብልሆነች ኖሮ ፡ወይ ነዶ ይሄኔ እኮ የዛሬዋ እስካርሌት የጥንቷን እስካርሌት እ"ሃራ ብትሆን ኖሮ ያንን ውሀ አረንጓዴ ቀሚሷን ለብሳ ደማቅ አረንጓዴ ጥብጣቧ ከጡቶቿ ሥር እየተወዛወዘ በጥቁሩ ዞማ ፀጉሯ ላይ ሮዝ አበባ ሰክታ ፡ወስዱ ላይ ተገኝታ የሪል ጻንሱን ትመራ ነበር ።እሳምራ ትመራው ነበር ።ይሄኔ በያርዘን የሚቆጠሩ ወንዶች ከኔ ጋር ትደንስ — ከኔ ጋር ትደንስ የሚል ጦርነት ከፍተው ለዶክተሩ ገንዘብ ሰመክፈል ይጋፉ ነበር ።ወይኔ! እሷ ከፈቃዴ ውጪ እዚህ የግድግዳ ጌጥ ሆና ተቀምጣ እነሩኒ ወይም እንሜ ይቤል የአትላንታ ቁንጅ ተብለው የሪል ጻንሱን ይከፈቱ ፡ እስቲ ይሁን! ግራር በሌለበት እንቢጮ እድባር ሆና!

ከውካታው ማህል የዛ የዙዌቩ ተወላጅ ሰውዬ ድምጽ ዘለቅ ብሎ ተሰማ ። "እኔ ከሜይቤል ሜሪዌዘር ጋር ለመደነስ ሃያ ብር እሰጣለሁ ።"

ሜይቤል ተሸማቃና ፊቷ በድንጋጤ ደም መስሎ ራሷን በፋኒ ትከሻ ላይ ጫነች ።ሁለቱ ሴቶች አንዱ በአንዱ አንገት ራሷን ደብቃ ይስቁ ጀመር ።ሌሎች ስሞችና ሌላ የገንዘብ መጠን መጠራቱ ቀጠለ። ዶክተር ሚድ የሆስፒታል ኮሚቴው ሴቶች የንዴት ሹክሹክታ ደንታ ሳይሰጠው ሙሉ በሙሉ ፈገግ ብሏል ።

መጀመሪያ ወይዘሮ ሜሪዌዘር ልጃቸው ሜይቤል በእንዲህ ያለው ነገር ውስጥ በፍጹም እንደማትሳተፍ በፊት ለፊት ተናግረው ነበር ። ጨረታው እየተጋጋለ ለሜይቤል የሚከፈለው ዋጋ ወደሰባ አምስት ብር ከፍ ሲል ግን ተቃውሟቸው እየሟሸሸ ሄደ ።እስካርሌት ባንኮኒውን በክንዷ ተደግፋ እጃቸው በኮንፌዴሬሲው ረብጣ ብር ሞልቶ ወደ መድረኩ ለመውጣት እየሳቁ የሚጋፉትን ወንዶች መዓት በስሜት ሰክራ ታስተውላለች ።

@OLDBOOKSPDF

አሁን እንግዲህ ከሲና ከአሮጊቶቹ በስተቀር ሁሉም ሴቶች ሊደ
ንሱ ነው ።እያንዳንዷ ሴት የዓለም የሲሳይ ጊዜ ሊሆንላት ነው—ከእሷ
በስተቀር ።ሬት በትለር ከዶክተሩ ማርጌ ቆሞ አየችው ። ፊቷ ላይ የሚ
ነበበውን ገፅታዋን ለመቀየር ሳትዘጋጅ በፊት ወደሷ ዞር ብሎ እያ
ትና አፉን በእንደኛው ጥግ ወደታች ዝቅ ፡እንደኛውን የአይኑን ሽፋል
ደግሞ ወደላይ ከፍ አደረገው ። አገጩን ወዲላይ አነቃንቃ ፊቷን ከሱ
አዞረች ።ወዲያው ከወደመድረኩ ስሟን ሰማች ።ከህምህምታው ሁሉ
በላይ ጐላ ብሎ በሚሰማ ፡በማያጠራጥርና ጥርት ባለ ቻርልስተናዊ
ድምጽ የገዛ ራሷ ስም ተጠራ ።

"ወ/ሮ አስካርሌት ኦሃራ .... እንድ መቶ ሀምሳ ብር—
በወርቅ የሚከፈል ።"

አንድም በጎንዘቡ ብዛት አንደም ባልታሰበው ስም ምክንያት፡
አዳራሹን ድንጉጥኛ ዝምታ ዋጠው ። አስካርሌት በጣም ከመደንገጧ
የተነሳ "እንደሱዋ ሚስት" በድን ሆና ቀረች ።አትናገር አትጋገር፡
አትላወስ አትንቀሳቀስ ባስችበት ደንገዘ ቀረች ። አገጩን እጆቿ ማህል
ቀብራ ፡የማያዩ ዓይኖቿን በመነፈም እንዳፈጠጠች ተቀምጣ ቅርፅ
መሰለች ።ሰው ሁሉ ወደሷ ዞሮ ያያታል ።ዶክተሩ ከመድረኩ ጐን
በስ ብሎ ሰፊት በትለር አንድ ነገር ሹክ ሲለው አየች ።ምናልባት
ሐዘን ላይ ስለሆነች ወደወለሉ መጥታ መደነስ አትችልም ሊለው
ይሆናል ።ሬት በምንቸገረኝ ትከሻውን ክፍ ዝቅ አደረገ ።

"ምናልባት ከቆንጆዎቻችን መሀል ከሴላ ጋር ለመደነስ ፈቃ
ድህ ቢሆን ?" አለና ጠየቀው ዶክተሩ ።

"የለም።" አለ ሬት ጥርት ባለ ድምጽ ፡ሕዝቡን በማዬለሽ ዓይን
አንዴ ጥርግ አርገው አይቶ ።"ከወ/ሮ አስካርሌት ጋር ነው ።"

"እየነገርከህ ። አሱ የማይቻል ነገር ነው እያልክህ ።" አለ ዶክ
ተሩ እየተፈታተነው ። "ወይዘሮ አስካርሌት በጭራሽ ..."

አስካርሌት በመጀመሪያ የራሷ መሆኑን ያልተገነዘበችውን
ድምጽ ሰማች ።

"አምን ፈቃደኛ ነኝ ።"

ከመቀመጫዋ ዘላ ተነሳች ።ልቧ በመዶሻ የሚቀጠቀጥ ይመስል
እንደ አንዳች ከመምታቱ የተነሳ በእግሯ ችላ የምትቆም አትመስልም፡
እንደገና የሰው ሁሉ ዓይን ማረፊያ በመሆኗ ልቧ ይመታል ።እንደገና
ወንድ ሁሉ የሚፈልጋት ቆንጆ ሴት በመሆኗ ልቧ ይመታል ።ከሁ

@OLDBOOKSPDF

ሉም በላይ ደግሞ እንደገና የመደነስ ዕድል በማግኘቷ ልቧ ጮቤ ይረግጣል ።

"ምናባቱ! የፈለጉትን ይበሏ! እኔ ግድ አለኝ ፡" አለች በሹክሹክታ አንድ ደስ የሚል ጣፋጭ ኣብደት በላይዋ ላይ እየሰፈረ ።ከሀር የተ ሠራ ማራገቢያዋን እስከመጨረሻው ዘርግታ ተረከዟን ጪ—ጨብ ፡ ጪ ጨብ እያደረገች ራሷን ቀና አድርጋ ንፍታ ከባንኩኒው ወጣች ። ለእንዲት ትንሽ ቅዕበት እንዴት ሊሆን ቻለ የሚል የሚመስለውን የሜላኒን ፊት ፡ ድንበርብሩ የወጣውን የሞግዚቶቹን ፊት ፡ የቀኑትን ልጃገሪዶ ችና የሚያበረቷቷትን ወታደሮች ተመለከተች ።

ወዲያው እወለሉ ላይ ታየች ።ፊት በትለር ያን የሚያሾፍ ፈገ ግታውን እያሳየ በተሰበሰበው ሕዝብ ማሀል አቋርጦ ወደሷ እየወጣ ነው ። እሷ ግን ማንም ቢሆን ባሁኗ ደቂቃ ደንታዋ አይደለም ። ለምን ራሱ ኤብ ሊንከን እይሆንም ፡ ቁብ የላትም ። እንደገና ልትደንስ ነው ። የሪል ዳንሱ መሪ ናት ።ሞቅ ባለ ፈገግታ ትንሽ ዝቅ ብላ ተቀ በለችው ።እሱም እንድ እጇን በተዋበ ኮት በተሸፈነው ደረቱ ላይ አድርጐ ለጥ ብሎ እጅ ነሳት ።የሙዚቃ መሪው ሌቪ በሁኔታው ስለ ተደናገጠና ነገሩን ለመሸፈን ስለፈለገ በፍጥነት ጮክ ብሎ አስተዋ ወቀ፡ "አብራችሁ የምትጫወቷትን ንደኛ ያዙና ቦዚህ የሪል ዳንስ ተደ ሰቱ !"

ይሄኔ ኦርኬስትራው ያንን ከሪል ቅኝቶች ሁሉ ምርጥ የሆነ ውን"ዲክሲ"የተባለ ሙዚቃ አንቆረቆረው ።

* * *

"ካፒቴን በትለር ፡ምነው እንዲህ አጋለጥከኝ ?"

"ግን እኮ ውድ ወይዘሮ አስካርሌት ፡አንቺ አራስሽ ይፋ ለመው ጣት መፈለግሽ ለማንም ግልጽ ነው ።"

"በዚህ ሁሉ ሰው ፊት እንዴት ስሜን ትጠራለህ ?"

"ለመቃወም ትችይ ነበር እኮ"

"አይ ለዓላማችን ብዬ ነው...እኔ..እኔ ያን ያህል ወርቅ ስታበረክት ራሴን ሰቼ ነበር ። ደሞ መሳትህን አቁም ሰው ሁሉኮ እኛን ነው እሚ መለከተው ።"

@OLDBOOKSPDF

"ብስቅም ባልስቅም እኛን መመልከታቸው አይቀርም ።ብቻ አደራ ሽን ይሄንን ስለዓላማው የምትቀባጥሪውን ሽፋን አንሺልኝ ። ለመደ ነስ ፈልገሽ ነበር — ዕድሱን እኔ ሰጠሁሽ ። ይሄኛው የዘፈኑ መጪ ረሻ ነው መሰለኝ?"

"አዎ ልጄ ። አሁን መደነሴን አቁሚ አቦታዬ ሂጂ መቀመጥ አለብኝ"

"ምነው? አግርሽ ላይ ወጣሁብሽ እንዴ?"

"አይ አሱስ አልነካሽኝም — ግን ሰዎቹ ሁሉ የሚያወሩት ስለ እኔ ነው እኮ"

"እውነት ይሄ ጉዳይ ከልብሽ አስጨንቆሽ ነው?"

"መቼም... ሀአ"

"ምንም የሠራሽው ወንጀል የለም ።አይደለም እንዴ? የሚቀጥ ለውን የቧልስ ዳንስ ሰምን ከኔ ጋር አትደንሺም ?"

"ግን እናቴ ብትሰማኩ..."

"አሁንም በእናትሽ አንቀልባ እንደታዘልሽ ነሽ እንዴ?"

"አንተ መቼም በጣም ተወዳጁን ግብረገብነት እንኳ ስትናገረው በጣም አስቀያሚ የምታደርግ ሰው ነህ ። መጥፌውን ይስጥህ እቴ!"

"ግን እኮ ግብረገብነት የምትይው ነገር ራሱ አስቀያሚ ነገር ነው ። ሰዎች ቢለፈልፉ ሳንቺ ደንታ ይሰጥሻል እንዴ ?"

"አይሰጠኝም ።..ግን መቼም..በቃ ስለሱ አናውራ ባክህ ። እግዜ ሀር ይስጣቸው የቧልሱም ሙዚቃ ጀመረ ። ይሄ ሪል የሚባል ሙዚቃ ሁልጊዜ ትንፋሽ ያሳጣኛል ።"

"ጥያቄዬን አታረሳሽኝ ።ሌሎች ሴቶች ስላንቺ የሚያወሩት ነገር አንቺን አስጨንቆሽ ያውቃል ?"

"ኤዊ እንደዚህ በጣም ከነዘነዝከኝ እሺ ልንገርህ ።ካልከስ በዋ ራሽ ደንታ አይሰጠኝም ።ግን ሴት ልጅ ደንታ ሊሰጣት ይገባል ፣ እርግጥ ዛሬ ማታ እንኳ እኔ ለምንም ግድ የለኝም ።"

"ብራቮ ፣አየሽ አሁን ሌሎች ሰዎች ለአንቺ እንዲያስቡልሽ ማድ ረጉን ትተሽ ፣እራስሽ ለራስሽ ማሰብ ጀመርሽ ማለት ነው ። የጥበብ ሁሉ መጀመሪያ ይሄ ነው...."

@OLDBOOKSPDF

"እሃ...ግን እኮ..."

"አየሽ ወደፊት ሰዎች በኔ ላይ ያወሩትን ያህል ሲወራብሽ ምንም ለውጥ እንደማያመጣብሽ ትገነዘቢያለሽ ።እስቲ አስቢው ፣ አሁን እትውልድ አገሬ ቻርልስተን ውስጥ እኔን የሚቀበል ፣ እኔን ቤቱ የሚያሳርፍ አንድም ሰው አይገኝም ።ለተቀደሰውና ለሀቀኛው ዓላማ ሽን ያደረኩት አስተዋጽኦ እንኳን እገዳውን አላስነሳልኝም ።"

"....እንዴት አሊቃቂ ነገር ነው!"

"በጭራሽ አይምሰልሽ ።ስምሽ ጠፍቶ መልካም ሥራሽን ሁሉ በመጥፎ ሲወስዱት ፣ ያ የሰራሽው ነገር ሁሉ ምን ያህል ሸከም ምን ያህል ጫና እንደነበረ ትገነዘቢያለሽ ። ነፃነት ማለትም በእርግጥ ምን ማለት እንደሆነ ቅረጽለሽ ።"

"በጣም ቅሌት የተሞላ ነገር ነው የምታወራው ።"

"አዎ ።ቅሌት የተሞላና ሰውነት የሆነ ነገር ነው ።ምንጊዜም ድፍረት ወይም ገንዘብ ካለሽ ጥሩ ስም ባይኖርሽም ጥሩ ኑሮ መኖር ትችያለሽ ።"

"አይ ገንዘቡኩ ሁሉን ነገር አይገዛም ።"

"ይሀንን አንድ ሰው ነግሮሻል ማለት ነው ። እንዲህ ያለ ርካሽ ነገር አንቺ ራስሽ ልታስቢ አትችይም ።ደሞ ገንዘብ ምን የማይገዛው ነገር አለ?"

"አይ ፣ መቼም ሌላውን እንጃ — ደስታን ወይም ደሞ ፍቅርን ግን አይገዛም ።"

"በጠቅላላው ስታይው ሊገዛ ይችላል ። በማይችልበት ጊዜ ደግሞ የማይገዛውን ነገር ያሚተኩ በጣም ግሩም ግሩም ነገሮችን ይገዛል።"

"ካፒቴን በትለር ፣ አንተ ሁሉን የሚገዛ ገንዘብ አለህ?"

"ምን ዓይነት የአይን አውጣ ጥያቄ ነው ፣ወይዘሮ እስካርሌትን ትገርሚያለሽ ግን እሺ ልንገርሽ ።መቼም ገና በልጅነቱ ቤሳ ቤስቲን ሳይዝ ከቤተሰቡ ለተነጠለና ካገሩ ለተባረረ ሰው በጣም ብዙ የሚ ባል ገንዘብ አፍርቻለሁ ።ደሞ እርግጠኛ ነኝ በዚህ አሁን በምሠራው ኮንትሮባንድ በሚሊዮን የሚቆጠር የተጣራ ገቢ ይኖረኛል ።"

"አትለኝም!"

"አትጠራጠሪ ብዙ ሰዎች ልብ የማይሉት ነገር ቢኖር ፣ ገንዘብ

@OLDBOOKSPDF
የሚገኘው አንድም አገር ስትለማ አንድም አገር ስትጠፋ መሆኑን ነው ።"

"ይሄ ሁሉ ምን ለማለት ነውን?"

"ያንቺ ቤተሰብ ፣የኔም ቤተሰብ እንዲሁም ዛሬ ማታ እዚህ የም ታይው እያንዳንዱ ሰው ገንዘብ ያገኘው ኋላ ቀርነትን ና ጥሬነትን ወደ ስልጣኔ በመለወጥ ነው ። ይሄ እንግዲህ አገር ማልማት ፣ አገር መገ ንባት ማለት ነው ።አገር በማልማት ብዙ ብር ይገኛል ።አገር በማጥ ፋት ግን የበለጠ ብር ይገኛል ።"

"የምን አገር ነው የምታወራው?"

"ይሄንን እኛ የምንኖርበትን አገር ነዋ — ደቡቡን..ክንፈዶሬሲ ውን... የጥጡን ማዛት በአይናችን በብረቱ እያየነው እግራችን ሥር ተንኮታኩቶ ሲወድቅ አታይውም እንዴ ። ይህን ለማየት የማይችሉና በሚደርሰውም ጥፋት ምክንያት የሚፈጠረውን አመጯ ሁኔታ ለመጠ ቀም የማይችሉ ጅሎች ብቻ ናቸው ። እኔ አዱኛዬን እያፈራሁና እየበለፀግሁ ያለሁት ይህን ጥፋትና መንኮታኮት እጥቅም ላይ በማ ዋሌ ነው ።"

"በዚህ አይነት ድባቅ እንመታለን ብለህ በእርግጥ ታምናለህ ማለት ነውን?"

"እንዴታ ።ምነው አስካርሌት በአይንሽ በብረቱ እያየሽው ። ለምን እንደሰጮን አንገትሽን አሸዋ ውስጥ ቀብረሽ አላየሁም ትያ ለሽ ?"

"ው..አሁንስ አንዲህ ዓይነቱ ወሬ አንገሸገሸኝ ።ካፒቴን በት ለር እንደው እግዚሀር ሲፈጥርህ ካፍህ ደህና ነገር አይወጣም ማለት ነው?"

"በወርቅ ነፀብራቅ የተሞላው የጥቁር ጉልላት ማረፊያው እንጂ ከል የጠራው ዓይንሽ የሰውን ልብ ጥፍት በሚያደርግ ሁኔታ ሲጓ ንስ ነብስን ያስሸልባል — ብልሽ ደሰ ይልሽ ነበር እንዴ?"

"አጭ እንደሱ አልፈልግም ፤ ይሄ ሙዚቃ ነፍስ አይደል? ዉ . . . መቼም ሕይወቴን ሙሉ ሻልስ ብደንስ የምጠግበው አይመሰ ኝም ፣ እንደዚህ ተርቤው እንደነበር አላውቅም ነበር ።"

"መቼም በሕይወቱ እቅፌ ውስጥ ካስገባኋቸው ሴቶች ሁሉ በጣም ግሩም የምትደንሽ አንቺ ነሽ ።"

@OLDBOOKSPDF

"ካፒቴን በትሰር እንደቪህ ጉብቅ አድርገህ አትቀፈኝ ። ሁሉ ሰው የሚያየው እኛን ነው ።"

"ማንም ሰው ባያየንስ ኖሮ ትጨነቂ ነበር ?"

"ካፒቴን በትሰር እራስህን ረስተህል ።"

"አይምሰልሽ ።ለእንዲት ደቂቃም እራሲን አልረሳም ።እንዴት ብዬ ፣ ያወም አንቺ እጮፌ ውስጥ እያለሽ፣ እንዴ ይሄ ቅኝት ያት ኛው ነው፣ አዲስ አይደለም እንዴ ?"

"እም አዲስ ነው ። ነፍስ የሚያጠፋ አይደለም እንዴ ፣ ከያን ኪዎቹ የወሰድነው እኮ ነው ።"

"ምን የሚባል ዘፈን ነው?"
"አስከፊው ጦርነት ሲያበቃ የሚል ነው ።"
"ቃሎቹ ምንድነው የሚሉት እስኪ ዝፈኝልኝ"

ውድ ፍቅረኛዬ
ታስታውስ የለም ወይ
ያኔ ስንገናኝ

ተምበርከክህ ከእግሬ
የፍቅርህን መጠን
ልኩን ስትነግረኝ

እንዲያ ኮርተህ ቆመህ
በግራጫ ልብስህ
አምረህ ተሽልመህ

ከእኔና ከአገርህ
መቼም ላትራራቅ
ከልብህ ቃል ገብተህ

ብቻህን አልቅሰህ
ብቻህን አምርረህ
የብቻ እንባ አንብተህ

እወልያለሁኝ
አስከፊው ጦርነት
ሲያበቃ እንዳገኝህ!

"እርግጥ መጀመሪያ እንኳን ዩኒፎርሙ ሰማያዊ ነበር ። በኋላ ግን ወደ ግራጫ ለወጥነው ። ካፒቴን በትለር ፣ ቫልስ መቼም ከንተ

@OLDBOOKSPDF

ጋር የተፈጠረ ነው የሚመስለው ። በጣም ግሩም ትደንሳለህ ። ብዙ ትላልቅ ሰዎች ዳንስ አይችሉም እንተ ግን ግሩም ነህ ። ደሞ ሀሳ ተኛ የምንደንሰው እኮ ገና ከብዙ ዓመታት በኋላ ነው የሚመስለኝ»

«እይሽ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ትደንሻለሽ ። የሚቅጥለው ንም ሪል ዳንስ የምጫረተው ላንቺው ነው ።ከዚያ የሚቅጥለውንም ....የሚቀጥለውንም»

«ዉ... አልችልም እባክህ እንደሱ ባታደርግ ይሻላል ። ስሚ ይጠፋል ።»

«ምን ስም አለሽና ከእንግዲህ ወዲያ ፡ሮድ ጨቅይጥ ትቢያ ገብቶ ሚናልባት አንድ አምስት ሰድስቴ ከደንስኩ በኋላ ለቤሎት ወንዶች ፅድል እስጣቸው ይሆናል ። የመጨረሻውን ግን ለራሴ እንዲ ሆን እፈልጋለሁ ።»

«እንደሱ በጣም ጥሩ ነው ።መቼም አብሻለሁ ።ግን የራሳቸው ጉዳይ ።ስሚት አይሰጠኝም ።ግንም የፈለገውን ይበል ደንታዬ አይደለም ።እኔ እንደሆን ቤት መቀመጥ እንገናግርኖል ።ልቤን ደክሞኛል ከእንግዲህ በደንብ እደንሳለሁ...እደንሳሰሁ...እደንሳለሁ... ነፍሴ እስኪ ወጣ እደንሳለሁ »

«ጭር መልዩለም ትተቻልሽ ።የሐዘን ልብስ ስጠላ እንዳንድ ነገር ነው ።»

«እንዴ የሐዘን ልብሱንማ ማውለቅ አልችልም ።ካርቱን በት ለር ኳንደሱ ጥብቅ አድርገህ እትቀፈኝ ባክህ ።እንደዚህ የምታቅፈኝ ከሆነ በጣም ነው የምኖደደው ።አብዳለሁ ።»

«ስታብጀኝ አይደል እንዴ ጡበትሽ የሚመጣው ።እንደገና ሞምቅ አድርጌ አቅፍሻለሁ ። እንደዚህ እቅፍ እቅፍቅፍ አደርግሻለሁ ። በንዴት እብድ ስትይ ማየትማ በጣም እፈልጋለሁ ። የዚያን ዕለት በ«አሥራ ሁለቱ ዋርካዎች» ሽርሽር ቦታ በተደግለው ግብግ ሳይ ተናደሽ ዕቃውን ሁሉ ስትወረውሪ እኮ እንዴት ታምሪ እንደነበር ልነግርሽ አልችልም ።»

«ውይ ምነው ባክህ ምናለ አሱን ብትረሳው ።»

«የለም ።አሱስ የምረሳው ነገር አይደለም ። እንዳወም በሕይወቴ ከጋጣሙኝ ነገሮች ሁሉ በጣም ውድ ትዝታዬ እሱ ነው ።በጥንቃቄና በጣም ልዩ በሆነ እንክብካቤ ያደግኩ ቆንጆ ደቡባዊት ፣ አየርላንዳዊ ንድ ሴያይል ማየት በጣም ግሩም ነገር ነው ።በጣም የጠለቀ አየርላንዳዊነት አለብሽ እስክርሌት ።»

@OLDBOOKSPDF

“ውይ የኔ ጌታ ሙዚቃው አለቀ ።እኒያው ወይዘሮ ፒቲፓት ከጓሮ እየመጡ ነው ።መቼም እኒያ ወይዘሮ ሜሪዌዘር ሄደው ሹክ ብለ ዋቸው መሆን አለበት ።እረ በአግዚሀር እንሂድና በመስኮቱ ወደ ውጪ እንመልከት ። እዚህ እንዲይዙኝ አልፈልግም ። የሳቸው አይኖች ሲጉረ ጠረጡ እኮ ፍንጀል ፍንጀል ያክክላሉ ።”

@OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ 10

ጠዋት የኬክ ቁርስ እየበሉ ሳሉ ወ/ሮ ፒቲፓት እንባቸው ይወ ርዳል ።ሚላኒ ፀጥ ብላ ትቀምጣለች ።እስካርሌት በተከላካይነት ኮስ ተር ብላለች ።

"እኔ ያሻቸውን ቢያወሩ ቁብ የለኝም ።እርግጠኛ ነኝ ለሦስቲ ታሉ እዚያ ከነበረች ከማንኛዋም ልጃገረድ የበለጠ ገንዘብ አስገኝ ቻለሁ ።እዚያ የተሸጠውም ትርኪ ምርኪ ነገር ካወጣው የበለጠ ገንዘብ አስገኝቻለሁ ።"

"ምንው የኔ ቆንጆ ፣ ገንዘቡ ምን ያረጋልሽ?" አሉ ወይዘሮ ፒቲፓት እየተንጫነጩና እጀቻቸውን እያወናጨፉ ። "እኔ መቼም ያየሁትን ማመን ነው ያቃተኝ ።ምስኪኑ ቻርሊ ሞቶ ዓመት ሳይሞላው....ያ አስቀያሚ ካርቱን በትለር እንደዚያ እንድትጋለጪ አድርጎ ተጫ ወተብሽ ። በጣም አደገኛ ፣ በጣም ታይለኛ ሰው ነው ፣አስካርሌት ። የወ/ሮ ዋይቲንግ ያክስት ልጅ ወ/ሮ ኮሌማን ባሏ ከቻርልስተን የመጣ ነው። እሷ በደንብ ነግራኛለች ። ከደሀና ቤተሰብ ተባርሮ የወጣ ነው ። ወይ ጉድ ከበትለሮች ጨዋ ዘር ማህል እንዲህ ያለ የመርገምት ፍሬ ይብ ቀል ። በድፍን ቻርልስተን አይንህን ላፈር የተባለ ነው ። በዚያ ላይ የዚያች የልጃገረዷ አስነዋሪ ታሪክ አለ ። ታሪኩ በጣም አስፀያፊ ከመሆኑ የተነሳ ወ/ሮ ኮሌማን እንኳ አታውቀውም...." "ዉይ አስከዚህ እንኳን መጥፎ ሰው አልመሰለኝም" አለች ሚሊ በቀስታ ። "መቼም ምንም የማይወጣለት ጨዋ ሰው ይመስላል ። ደግ ሞም የኮንትሮባንዱን ሥራ በእንዴት ያለ ጀግንነት እንደተወጣው ስታዪ..."

"እሱ ጀግና አይደለም ባክሽ ፣" አለች አስካርሌት ነገሩን ለማፋ ለስ ፣እኬክ ላይ ቅባት እየጨመረች ። "ለገንዘቡ ብሎ ነው የሚለ ፋው ። እራሱ ነግሮኛል ። ስለኮንፌዴሬሲውም እቺን ታህል አይጨነ ቅም ። እንዲያውም ድባቅ እንመታለን እያለ ያወራል ።ያም ሆኖ ሲደ ንስ ልዩ ነው ።"

የሚያዳምጧት ሴቶች በድንጋጤ እጢአቸው ዱብ አለ ።

"እኔ በበኩሌ እቢት መቀመጡ እጅ እጅ ብሎኛል ። ሁለተኛ አላደርገውም ። እኔ ትላንት ማታ ስላደረኩት ነገር የሚያወሩና ስሜን

@OLDBOOKSPDF

የሚያጠፉ ከሆነ ከእንግዲህ እንዴ ሰሜ ጠፍቷልና ምንም ሰውኛ አያ መጣም ።"

ይሄ አሁን የተናገረችው ሬት በትለር የነገራት መሆኑን ልብ አላለችም ። ከምታስበው ጋር በትክክል ተጋጥሞላታል ።

"እቤት ፣ እናትሽ ስትሰማ ምን ትል ? እኔንስ ምን ትለኝ ?"

እስካርሌት የደረሰባትን ቅሌት እናቷ ኤለን ስትሰማ እንዴት እንደምትሸማቀቅ ታያትና አንድ ቅዝቃዛ የሕሊና ወቀሳ ጉሮሮዋን አነቃት ።ሆኖም በአትላንታና በታራ ማህል ያለውን የሃያ አምስት ማይል ርቀት አስባ ልብ ገዛች ። ያለጥርጥር ወይዘሮ ፒቲ ለኤለን አይነግሩባትም ። እንደባለአደራነታቸው ራሳቸውን ጭምር ያስጠይቃቸዋል ። ደሞም ወይዘሮ ፒቲ በገዛ አፋቸው ክላወሩ ችግሩ ሁሉ ይወገዳል ።

"እኔ እንደሚመስለኝ..." እሱ ወይዘሮ ፒቲ ፣ "እኔ እንደሚመስለኝ ምንም ነገሩን ብጠላው ስለዚህ ጉዳይ ለሔንሪ ደብዳቤ ልጻፍ ለት...ያለን ወንድ ዘመድ እንድ እሱ ብቻ ነው ።እሱ ሄዶ ለካፒቴን በትለር ያደረገው ሁሉ ትክክል እንዳልሆነ አስረድቶ ይውቀሰው።.. እሴ..እንደው ቻርሊ ቢኖር እኮ...እስካርሌት ኧእንደው በፈጠረሽ ይገፍ ሻለሁ ከዛ ሰው ጋር ሁለቴኛ እንዲት ቃል እንዳትነጋገሪ ።"

ሚላኒ እጆቿን እጭኖቿ ላይ አድርጋ ዝም ብላ ተቀምጣለች ። ዜኣ እሳሀኑ ላይ ቀዝቅዟል ። ቲንሰታ በእስካርሌት ጀርባ ቆማ እንገቷን በክንዷ አቀፈቻት ።

"የኔ ቆንጆ" አለች "አትበሳጪ ። ትላንት ያደረግሺው ሁሉ የጀግና ሥራ ነው ።ሆስፒታሉን በጣም ይረዳል ።እናም ማንም ስላንቺ ክፉ ቢናገር እኔ ልክ ልኩን እነግርልሻለሁ ።አክስቴም አታልቅሺ። እስካርሌት ከቤት ባለመውጣቷ እንዴት እንደተቸገረች ተመልከቺ ። ትንሽ ልጅ እኮ ናት" ጣቶቿ በእስካርሌት ፀጉር ይጫወታሉ ። "ምናልባት ወደፊት አልፎ አልፎ ወደ ፓርቲ ድግስ ብንሄድ ጥሩ ነው ። ምናልባት ሐዘናችንን በማስታመም ራሳችንን መቅበራችን በጣም ራስን መውደድ ላይሆን አልቀረም ። የጦርነት ጊዜ እንደሌላው ጊዜ አይደለም ። ከቤታቸው ርቀው ጦር ግንባር ያሉትን በየማታው ጠያቂ የሌላቸውን ወታደሮች ሳስብ ሆስፒታል ተኝተው ካገገሙ በኋላ ለመውጣት ሲችሉ ግን ከሠራዊቱ ለመቀላቀል በቂ ጤና ሲያጡ ላይ ፣.. እንዴ የኛ ነገር በጣም ራስን መውደድ ይመስለኛል ። በዚች ባሁኗ ደቂቃ ቢያንስ ሦስት ያገገሙ ቁስለኞች ቤታችን ውስጥ ሊኖሩ ይገባ ነበር ። አንዳንዶቹን ወታደሮችም ራት ልንጋብዛቸው ይገባ ነበር። አይዞሽ እስካርሌት ፣ ምንም አትፍሪ ። ሰው እኮ ችግርሽ ቢገባው ስለ

@OLDBOOKSPDF

እንቺ እንዲት ቃል አይትንፍሽም ።ቻርሊን ታፈቅሪው እንደነበር ሁላችንም እናውቃለን ።”

እስካርሌት ለራሷ ፍርሃት ምንባል አልፏ ውስጥ የለም ።እንዲያውም ሚላኒ ዐጉሯን በመደባበሷ ተናዳለች ። ጭንቅላቷን ምንጭቅ አድርጋ “ድራንዳንዳን” ለማለት ፊልጋ ነበር ። ትላንት ማታ የከተማ ጠባቂ ዎቹ ፡ ሚሲሺያዎቹና ወታደሮቹ ለመደነስ እንድትችል እንዴት እንደታገሉላት የምታስታውሰው ስዕል ገና ከአዕምሮዋ ያልጠፋ ትኩስ ትዝታ ነው ። በዓለም ላይ ካለ ከማንም ሰው ይልቅ ሚላኒ ለእሷ ስትከራከር በጭራሽ ያስጠላታል ። እራሷ ለራሷ መከራከር ትችላለች። እናም እነዚህ አሮጊት ድመቶች እንጉሚንጉለን ቢሉ የራሳቸው ጉዳይ ብላ በራሷ መንገድ ትሄዳለች ። የአሮጊቶችን ንዝንዝ እየሰሙ የሚጨነቁ በዓለም ላይ በርካታ ጥሩ ጥሩ መኩንኖች ሰላሉ እነሱ ይጨነቁላቸው ።

ሚላኒ በምትናገራቸው የማዕናኛ ቃላት ወ/ሮ ፒቲፓት ዓይናቸውን ሲያቹ ፕሬሲ ድነት ትልቅ ደብዳቤ ይዛ ዘው አለች ።

“ለእሶ ነው እትዬ ሚሊ ።አንድ ትንሽ ኔግሮ ነው ያመጣልዎት”

“ለእኔ!” አለች ሚላኒ ፖስታውን ተቀብላ እየከፈተች ።

እስካርሌት ኤሾርቅራ ከኬኬ ጋር ስትታገል ምንም ሳታይ ቆይታ የሚላኒ ለቅሶ አነቃት ። ዘወር ስትል ወ/ሮ ፒቲፓት እጆቿውን እሚላኒ ደረት ላይ ሲያስቀምጡ አየች ።

“አሽሌይ ሞተ!” ጮኹ ወ/ሮ ፒቲፓት ጭንቅላታቸውን ወደ ኋላ ጋለል ፣ እጆቸውን ዝልፍልፍ አድርገው ።

“ወይኔ አምላኬ!” አለች እስካርሌት በጩኸት ፡ ደሟ እንደበረዶ ቀዘቀዘ ።

“የለም! የለም!” ጮኸች ሚላኒ ። “ዶሎ በሉ! የሚሸተተውን ጨው ዶሎ በሉ! እስካርሌት ባክሽ ዶሎ በይ..ይሄውልሽ አክስቴ በይ አሽቺው ። አሁን ተሻለሽ? ወደ ውስጥ ተንፍሺ ። አሽሌይ እኮ ምንም አልሆነም ። ስላስደነገጥኩሽ በጣም አዝናለሁ ። አለቅስ የነበረው በጣም ስለተደሰትኩ ነው።” ወዲያው ጭብጧን ዘርግታ አንድ ነገር ከመዳፏ ወደአፏ ገፋች ። “በጣም ነው ደስ ያለኝ” አለችና እንባ በእንባ ሆነች ።

እስካርሌት ዐይኗ ከአፎቱ ወጥቶ እስኪንቀል ድረስ አፍጣ አንድ ነገር ላይ ተከለችው — በጣም ትልቅ የጣት ቀለበት ።

@OLDBOOKSPDF

"እንብቢው" አሰኝ ሜላኒ በጣቷ ወሰሉ ላይ መዳለው ደብዳቤ እያመለከተች ። "ጨ . . እንዴት ያለ ግሩም ሰው ነወ! እንዴት ያለ ደግ ሰው ነው!"

እስካርሌት በንገሩ ግራ ተጋብታ ነጠላወን ወረቀት ከወለሉ እን ስታ እንደልቡ በተጻፈ እጣጣል በጥቁር የተጻፈውን ደብዳቤ ማን በብ ጀመረች ፡— "ኮንፌደሬሲው የወንዶች ልጆቹን ደም ይሻ ይሆ ናል ።የሴቶቹ ልብ ይድማልኝ ፡ደሙም ለስርየቱ ይፍሰስልኝ ግን አላ ለም ።ስለዚህ ውድ እመቤት ፡ለፈጸምሽው የጀግንነት ተግባር የእከብ ሮቱ መግለጫ እንዲሆን ይሆን እቃ ትቀበይኝ ዘንድ እንሆ ። ቀለበቱን ለማስመለስ ከዋጋው አሥር እጅ ከፍ አድርጌ የከፈልኩ ስለሆን መስ ዋእትነትሽ አልባከነም።...ከፒቴን ሬት በትለር ።"

ሜላኒ ቀለበቱን እጣቷ ውስጥ አስገብታ በፍቅር ዓይን ተመለ ከተችው ።

"ትልቅ ሰው ነው ፡ጨዋ ሰው ነው ብያችሁ አልነበረምን?" አለች ወደ መይዘሮ ፒቲፓት ያራ ። ፈገግታዋ በፊቷ ላይ ባለት የአንባ ነጠ ብጣቦች ውስጥ በርቶ ይታያል ። "መቼም ዋና አስተዋይ ሰው ካልሆነ በስ ተቀር ይህንን ቀለበት መስጠት እንዴት ልቤን እንደሚያደማው . . . በዚህ ፋንታ የወርቅ ሰንሰለቴን አልካለሁ ። አክስቴ እንድ ማስታ ወሻ ልትልኪለት ይገባል ። ለእሁድ እራት ጋብዣውና ምሥጋናዬን ላቅርብለት ።"

ሦስቱም በስሜት ከመጥለቅለቃቸው የተነሳ ካፒቴን በትለር የእስካርሌትን ቀለበት አለመመለሱን ያሰቡበት አይመስልም ።እስካ ርሌት ግን አስታውሳቸለች ።ያወቁም ብስጭት ብላ ። ደሞ ይሆን እነሱ የተጸነቁበትን ቆራጥ ተግባር እንዲፈጽም የገፋፋውም የካፒቴን በት ለር ጨዋ መሆን እንዳልሆነም ታውቃለች ። ወ/ሮ ፒቲፓት ቤት ለመ ጋበዝ ስለሚፈልግና ለዚህም መግቢያው በር የትኛው እንደሆነ እሳ ምሮ ስለሚያውቅ ነው ።

* * *

"እስካርሌት ፡ የሰሞኑን ወባይሽን ነባር ሰምቼ በጣም ተረብሻ ለሁ ።" ይላል የኢለን ደብዳቤ ። ጠረጴዛ ላይ ቁጭ ብላ ይህን ደብዳቤ የምታነበው እስካርሌት ሽምቅቅ አለች ።መጥፎ ወሬ ያለጥርጥር በፍ ጥነት ነፍሷል ማለት ነው ። ቻርልስተንና ሳቫና ላለች ፡ ከደቡቡ ሕዝብ ሁሉ እነዚህ የእትላንታ ሰዎች ሐሜተኞችና በሌሎች ሰዎች ጉዳይ

@OLDBOOKSPDF

ጣልቃ የሚገቡ መሆናቸውን በተደጋጋሚ ሰምታ ነበር ። ዛሬ በደንብ አመነች ። ባዛሩ የተካሄደው ሰኞ ለት ነው ። ዛሬ ገና ሐሙስ ነው ። ለመሆኑ የትኛዋ አሮጊት ድመት ትሆን ለኤሰን የጻፈችላት ? ለትንሿ ጊዜ ስብቀኛዋ ፣ ወ/ሮ ፒቲፓት ይሆናሉ ብላ ጠርጥራ ነበር ። ግን ይህን ጥርጣሬ ወዲያው ተወችው ። ምስኪኗ ጣ/ሮ ፒቲፓት ለራሳቸው በእስ ካርሴት ዓይን ያወጣ ፀባይ እወቀሳለሁ ብለው ስለሰጉ ለኤሰን ለጣ ላበቅ የመጨረሻዋ እንደሚሆኑ አይጠረጠርም ። ምናልባት አሳባቂዋ ወ/ሮ ሜሪዊዘር ሳይሆኑ አይቀሩም ።

"የጨዋ አስተዳደግሽ ሁሉ ገደል ገብቶና እራስሽን ረስተሽ እንዲህ ስድ ያደረገሽ ምን እንደሆነ ሊገባኝ አልቻለም ። ምንም እንኳ ሐዘን ላይ ብትሆኚ ሆስፒታሉን የመርዳቱ ነገር በልጦብሽ ወደ ባዛሩ መሄድሽ ባልከፋም ነበር ። ነገር ግን መደነስሽ—ያውም እንደ ክሮቴን በትለር ካለው ባለጌ ሰው ጋር — በጣም የማላምነው ነገር ነው ። ስለሱ የሚወራውን በሙሉ ስምቻለሁ (ማንስ አልሰማም ?) እንኳን በሌላ ፣ በገዛ ቤተሰቡ እንኳን (እርግጥ መከረኛዋ እናቱ አላገለለችውም ። እናት ናታ) የተጠራ ሰው መሆኑን ፖሲን የፃፈችልኝ ገና ባለፈው ሣምንት ነው ። በጣም መረጃ ፣ የመጨረሻ ባለጌ ሰው በመሆኑ ልጅነትሽንና የዋህነትሽን በመጠቀም እንድትጋለጪና በሕዝብ ፊት አስነዋሪ ተግባር ፈጽመሽ ላንቺም ለቤተሰብሽም ሐፍረት እንድትሆኚ ያደርግሻል ። ወ/ሮ ፒቲፓት እንዴት እንዲህ መረን እንደለቀቅሽ አልገባኝም ።"

እስካርሴት በጠረጴዛው አሻግራ ወደ አክስትየዋ ተመለከተች። አሮጊቷ የኤለንን እጅ ጽሕፈት አብታውሰውታል ። ልክ ስድብ እንደ ሚፈራና ከስድቡ ለማምለጥም ዕንባዎቿን ለመከላከያ እንደሚያቀርብ ትንሽ ልጅ ከንፈራቸውን ሽብሽብ አድርገው ኩፍ ብለው ተቀምጠዋል ።

"ያን መልካም አስተዳደግሽን እንዲህ ባጭር ጊዜ መዘንጋትሽ ቅሰሜን ስበር አድርጐታል ። ባንድ አፍታ ወደቤት እንድትመጪ ላደርግሽ አስቤ ነበር ግን ተውኩት ። ያው አባትሽ እንደፍጥርጥርሽ ያድርግሽ ። ካርቱን በትለርን ለማንጋገርና እግረ መንገዱንም አንቺን ወደቤት ይዞ ለመመለስ አርብ እለት ወደአትላንታ ይመጣል ። ቤተኛ ለኝ ሁሉ እንዲምርሽ ብለምነውም በጀ አላለም—እንጃ አምርሮብሻል ። መቼም ይህን አጉል ፀባይሽን ወጣትነትሽና አሳብ የለሽነትሽ ያመጣው ነው ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ ። እበልያለሁ ። ለታላቁ ዓላማ ማገልገልን እንደኔ የሚፈልገው ፣ እንደኔ የሚመኘው ከቶ የለም ። የገዛ ልጅሽም በእኔ እንዲወጠ ምኞቱ ነው ። ነገር ግን እንዲህ እንዳሁኑ ከብርን እጉድፍ ላይ የሚጥል ተግባር "

@OLDBOOKSPDF

እደብዳቤው መጨረሻ በዚህ የንጹሑና የእልህ ቃና ፡ሚቀጥል ብዙ ነገር አለበት ።እስካርሌት ግን አልጨረሰችውም ።አንድ ገጼ እፍረሀት ባህር ውስጥ ሰምጣለች ። አሁን የመከላከልም ሆነ የማዴል ሽንት ስሜት የለባትም ። በልጅነቷ ፡ ገና የአሥር ዓመት ልጅ ሳለች ቅቤ የጠጣ ብስክት ስዌለን ላይ በገበታው አሻግራ ስትወረውር ይሰማት የነበረውን ዓይነት የህፃንነትና የጥራትኝነት ስሜት ቱሰ ማት ። እሪ በበለስ ፡ ያቺ ሩህሩህ ፡ ቅድስትና ድምጿ የማይሰማ እናቷ እንዲህ ሞክን ብላ ትውቅሳት ፣ አባቷስ ከሬት በትለር ጋር ለመነጋ ገር እዚህ ድረስ ይምጣ፣ የነጉሩ አሳሳቢነት ቀስ በቀስ በውስጧ ክን ፉን ዘረጋ ። ጂራልድ አምርሮ ሊመጣባት ነው ። ይሄ ያሁኑ ጫን ያለው ነው ። እንደወትሮዋ እገልበቱ ላይ ቁጭ ብላ በጣፋጭ ቃላት እየተማ ጠነች በቅልጥፍና አጭበርብራ ሰማምለጥ አትችልም ።

"መጥፎ ነገር አለበት እንዴ፣ የሰበትም አይደል ?"አሉ ወ/ሮ ፒቲፓት በሚንቀጠቀጥ ድምጽ ።

"አባባ ነገ ሊመጣ ነው ። መጥቶ ማጅራቱ ላይ ሊቆም ነው ።" ብላ መለሰች እስካርሌት—በሀዘን ።

"ፕሪሲ ያን ጨዌን አምጪልኝ"አሉ ወ/ሮ ፒቲፓት እየተርበ ተበቱ ፡ማሻሽ የጥበላለትን ገበታ አርቀው ወንበራቸውን ወደኋላ እየገፉ ። "እኔ... እኔ ልቤ ፈሰሱ መውደቂ ነው ።"

"በቀሚስ ኪስዎ ውስጥ ነው ያለው ።" አለች ፕሪሲ ፡ ከእስካር ሌት ኋላ እያንገዠበበችና በድራማው እየተዝናናች ። ጂራልድ ሲናደድ ማየት ደስ ይላታል ። ሆኖም ከንዴቱ የሚመነጨው ጩኸት የሚወረወ ረው ቁርንጭድ ፀጉር ወደተሸከመው ሞንቅላቷ ከሆነ አትፈልገውም ። ወ/ሮ ፒቲ የቀሚስ ኪሳቸውን ፈታተሹና ብልቃጣቸውን አፍን ጫቸው ሥር ያዟት ።

"አደራችሁን ሁላችሁም ከአጠገቤ እንዳትጠፉ ። ለሱ ጥላችሁኝ እንዳትሄዱብኝ አደራ ። "ብላ ጮኸች እስካርሌት ። "ሁለታችሁንም በጣም ስለሚወዳችሁ እናንተ አጠገቤ ካላችሁ አይቆጣኝም ።"

"እኔ አልችልም ፡አይሆንልኝም"አሉ ወይዘሮ ፒቲ በደከመ ድምፅ ፣ ከመቀመጫቸውአየተነሱ ። "እኔ እኔ ሕመም ተሰምቶኛል ። ሂጂ መተኛት አለብኝ ። እንዲያውም ነገ ቀኑን ሙሉ ተኝቼ ነው የምውለው ። 'ይቅርታ አድርግልኝ አሞኝ ነው' ትሉልኛላችሁ ።"

"ፈሪ በቅባቃ ፡"አለች እስካርሌት በሆዷ ።

ሚሊ ምንም እንኳን አራስ ነብር ሆኖ የሚመጣውን ጂራልድን ነገር አስባ ገና ካሁኑ ፊቷ እሸቦ ቢመስል ከእስካርሌት ጉን ለመ

@OLDBOOKSPDF

ቆም ቆርጣለች ። "ማዬለም አይሆንሽ ፡ እኔ ለሆስፒታሉ ስትይ ያደረግሽው መሆኑን በደንብ አስረዳልሻለሁ ። እርግጠኛ ነኝ ይገባዋል ።"

"እሄሄ ፡ በፍጹም አይገባውም ባክሽ" አለች እስካርሌት ። "ዒ . . መቼም እማማ እንዳስፈራራችኝ በእርግጥ ወደታራ ተዋርጄ ከሞሄድ ሞቲን እመርጣለሁ ።"

"እንዴ ፡ በጭራሽ መሄድ የለብሽም" ብለው ሙሁ ወ/ሮ ዊቲ ፓት ፡ ድንገት በእንባ ገንፍለው ። "አንቺ ከሄድሽ ሐኒሪ መጥቶ ከኛ ጋር እንዲኖር ማድረግ ሊኖርብኝ ነው ። ግን እንደምታውቂት ከሐኒሪ ጋር ለመኖር በጭራሽ አልችልም ። እኔ ሰራሴ ከሜላኒ ጋር ብቻዬን በጭለማ ሰቀመጥ በፍርሀት ልሞት እደርሳለሁ ። አበሺ አበሺ ይል ኛል ። ከተማዋ ለራሷ በባይተዋር ስሞት ተጥልቅልቃለች እናቴ ። እንቺ ካለሽ ግን በጣም ጉበዝ ከመሆንሽ የተነሳ ወንድ ኖረ አልኖረ ግዴ ለኝዘ"

"ሙይ አይሆንም ፡ወደታራ ይኮሽ መሄድ ያለብትም ።" አሰች ሜሊ ፡ አሷም በአንድ አፍታ የምታስቅስ መስላ ። "አሁን እኮ ይሄ ቤትሽ ነው ። ሙይ እንቺ ከሄድሽ ምን ይመጠናል?"

"መቼም ሰላንቺ የማስበውን ብታውቂ ኖሮ መሄዴን እንዴት በአልልታ በተቀበልሺው ነበር" ብላ አሰበች እስካርሌት ፡ ምነው ከሜላኒ ሌላ ከጂራልድ የሚያድነኝ ሰው በኖረ ኖሮ በሚል የመከፋት ስሜት ። በጣም የምትጠሉት ሰው መድህናችሁ ሲሆን ፡ በጣም ያምት ጠምዱት ሰው ከችግር የሚያወጣችሁ ሲሆንኮ እንዴት አንጀት የሚያቆስል ነገር ነው ።

"ምናልባት ካፒቴን በትለርን የመጋበዛችንን ነገር ብንተወውስ . . ." ብለው ጀመሩ ወ/ሮ ዊቲፓት ።

"እንዴ ፡እንዴት ብለን፣ በጭራሽ አይሞከርም ፡ትልቅ ነውር ነው" አሰች ሜሊ ክፍት ብሏት ።

"እባካችሁ ወደአልጋዬ ጠብሱኝ ።እሊያ ሊያመኝ ነው መሰ ለኝ ።" አለ ወይዘሮ ዊቲፓት እያቃሰቱ ። "ምነው እስካርሌት ምን አልኩሽ ምን በደልኩሽና ይሀን ጣጣ አመጣሽብኝ ?"

በሚቀጥለው ቀን ከሰዓት በኋላ ወይዘሮ ዊቲፓት ታመው አልጋ ላይ እንደተኙ ጂራልድ መጣ ። ከባቢታው ጠረጴዛ የተቀመጡትን በጥርሃት የተሞጠ ሁለት ሉዶች ትተው ከተዘጋው የመጓታ ቤት በር ጀርባ ተሳተው ጂራልድን ይቅርታ ይጠይታሉ ።ጂራልድ ምንም እንኳን እስካርሌትን ቢለማትና ሚላኒንም ጉንጯን ቅንጠጥ አድርጉ

@OLDBOOKSPDF

"የአክስቱ ልጅ" ብሎ ቢጠራት ክፉ ነገር ባረገዘ ዝምታ ተውጧል። እስካርሌት ከዚህ ክፉ ሙልክ ይልቅ እንድ ሺህ ቁጣዎች ፣እንድሺህ ወቀሳዎች ይሻሏት ነበር ። ሜላኒ የገባችውን ቃል ጠብቃ ከእስካርሌት ቀሚስ ጋር የተሰፋች ይመስል እንደሚንቀሳቀስ ጥላ ተጣብቃ ባታለች ።ጀራልድ እስካርሌትን በሜላኒ ፊት እንዳይሳደብ ጨዋነቱ አግዶታል ።እስካርሌት ፣ሜላኒ ምንም ችግር እንደሌለ በማስመሰል የምታሳየው እንቅስቃሴ እንደተዋጣላት አውን ማመን አለባት ። በዛ ላይም የእራት ገበታ ከፍ ካለ በኋላ ጀራልድን በሌላ ወሬ መጥመዷ ዓላማዋ በደንብ እንዲሳካ አድርጓታል።

"ስለመንደራችሁ ሁሉንም ነገር ንገረኝ ፣ማወቅ አፈልጋለሁ" አለች ወደሱ እያየች ። "ኢንዲያ እና ሐኒ እኮ መልዕክት እንኳ መናገር አይችሉበትም ። አንተ ግን እዚያ የተደረገ የተፈጠረውን ነገር እንድ ሳይቀር እንደምታውቅ አሳምሬ አውቃለሁኝ ። እስቲ ስለ ጆ ፎንቴን ሠርግ ንገረን ።"

ጀራልድ በአታላይ ጥያቄዋ ተሸንፎ ሞቅ አለውና ሠርጉ ቅዝ ቅዝ ያለ እንደነበር አስረዳት ። "እንደእናንተ ሰርግ የደመቀ አልነበረም ። ጆ ለጥቂት ቀናት ብቻ ስለሆነ አስፈቅዶ የመጣው ብዙ ጊዜ አልነበራቸውም ። ያቺ ደቃቃዋ የመጨረሻዋ የሙንሮ ልጅ በጣም አምሮባት ነበር ።" የለም ፣ ምን ዓይነት ልብስ እንደለበሰች እንኳ ትዝ አይለውም ። ሆኖም "የሰርግ ሜጣስት ቀሚስ" የላትም እያሉ ሲያ ወሩ ሰምቷል ።

"ውይ ፣የላትም"አሉና ጮሁ ሲጮኹ ፣ የሚያሳፍር ነገር መሆኑን እያመለከቱ ።

"እውነቴን ነው ።ለምን እንደሌላት ታውቃላችሁ? የሰርግ ማግስት ግብግ ከሌለ ልብሱ ምንም አያደርግማ ።" አለና አስረዳቸው ጀራልድ ፣ በከፍተኛ ጩኸት እየሳቀ ። እንዲህ ያለውን ወሬ እሴቶች ጆሮ እንዲደርስ ማድረጉ ተገቢ እንዳልሆነ እስኪሰማው ድረስ ሳቁን ቀጠለ ። እስካርሌት በመሳቁ ልቧ ከፍርሃት አገር መለስ ብሎላት መንፈሷ ስለተነቃቃ ለሜላኒ ጥበብ ምስጋና ይግባው አለች ።

"ጆ በሚቀጥለው ቀን ተመልሶ ወደ ቨርጂኒያ ሄደ — በሠርጉ ማግስት" በፍጥነት ጨመረበት ጀራልድ ። "ዘመድ ጋ መልስ ተጠርቶ መሄድም ሆነ መደነስ ቀርቷል ። የታርሌተን መንትያ ወንድማማች ኾችም እቤት መጥተዋል ።"

"እዎን ሰማን ። ተሻላቸውን?"

@OLDBOOKSPDF

"አይ ይሄን ያህልም ለጉዳት በሚሰጥ ሁኔታ አልቆሰሉም። ስቱዋርት ጉልበቱን ነው፡ ብሬንትም አንዲት ትንሽ ጥይት ትከሻውን ለኩፍ አድርጋው ነው። በጀግንነት ስማቸው መጠራቱን መቼም ሳትሰሙ አልቀራችሁም፡ ሰምታችሁ የለ?"

"አረ እንደውም አልሰማን። እስቲ ንገረን።"

"የአንበሳ ልብ ነው ያላቸው ሁለቱም። የአየርላንዳዊ ደም እንዳላቸው አምናለሁ።" አለ ጂራልድ በአድራጐታቸው በመርካት። "ምን እንዳደረጉ እንኳን አላስታውስም። ብቻ ብሬንት አሁን ሙቶ አለቃ ሆኗል።

እስካርሌት ወንድማማቾቹ ባጉት ድል ተደሰተች። የራሷ ድል ሆኖም ተሰማት። ማንም ወንድ ከዕለታት አንድ ቀን ወዳጅዋ የነበረ ከሆነ ምንጊዜም የራሷ አድርጋ ማየቱን አትተውም። ስለዚህም የሱ መልካም ሥራና ስም የሷም ድርሻ ይሆናል።

"ሁለታችሁን የማመሰክት ወሬም አለኝ እኮ" አለ ጂራልድ። "ስቱዋርት አሁንም በ"አሥራ ሁለቱ ዋርካዎች" ሴት ማሳደዱን ቀጥ ሏል አሉ።"

"ሐኒን ነው? ኢንዲያን?" ብላ ጠየቀችው ሜላኒ ጉጉት ብላ። እስካርሌት ከሞላ ጐደል ተናዳ ትኩር ብላ ታስተውላለች።

"እንዴ ወይዘሪት ኢንዲያን ነው እንጂ። ይቺ የኔዋ ውዳቂ ጠቅላ እስከታወናበደው ድረስ ቅልጥፍ ብላ ይዛው አልነበረም እንዴ?"

"ወይኔ" አለች ሜላኒ በጂራልድ ልቅ ንግግር እየተበሳጨች።

"በዛ ላይ ወጣቱ ብሬንት ታሪ መጥቶ ያንሣበባል—ባሁኗ ደቂቃ እንኳ"

እስካርሌት መናገር አልቻለችም። የወዳጅዋን ዓይኑን ሌላ ሴት ላይ መጣል፡ የወዳጅዋን መክዳት እንደስድብ ቆጠረችው። በተለይም ቻርለስን ላገባ ነው ብላ ስትነግራቸው እንዴት እንደበረገጉ አስታወሰች። ስቱዋርትማ ወይ ቻርለስን ወይ እስካርሌትን ወይ እራሱን አሊያም ሦስታቸውንም እንደሚገድል ነግሮ አስፈራርቷት ነበር። በጣም ያስደስታት ነገር ነበር።

"ሱዌለንስ?" ብላ ጠየቀች ሜሊ፡ አዲስ የፈጣታ ፋይል እየከፈተች። እኔ እንደሚመስለኝ አቶ ኬኔዲ..."

@OLDBOOKSPDF

"እ፡እሱ?" አለ ጂራልድ። "ያ የራሱን ጥላ እንኳ የሚፈራው ፍራንክ ከእዲማ አሁንም እግር እግሯ ሥር ያነፈንፋል። ደሞ ራሱ ከልተናገረ እኔ በእርግጥ ምን እንደሚፈልግ አጠይቀዋለሁ። እሱን ለኔ ተዉልኝ።"

"ካሪንስ?"

"እሷ እንኳ እምንም ውስጥ አትገባ-ሕግን ናት።" አለች እስካርሌት ቀልጠፍ ብላ፡ አንደበቷን ፈታ።

"አንቺ ስታገቢ የአንድ ዓመት ታናሽሽ ነበረች እኮ አሜቱ" ተቃወማት ጂራልድ "በለሽ ብለሽ በዱሮ ወዳጅሽ ጉዳይ ከታናሽ እህትሽ ጋር እሰጥ አገባ ልትገጥሚ ነው እንዴ?"

ሚለ ከእንዲህ ያለ ግልጽነት ጋር ያልተላመደች በመሆኗ በድንጋጤ ፊቷ ቀልቶ፡ ፒኮር የስኳር ድንች ጥበስ እንዲያቀርብ በእጅዋ ምልክት ሰጠችው። በአእምሮዋ ውስጥም እንደዚህ እንዳሁኑ የግል ጉዳዩን የማይመስክት ግን ጂራልድን በጨዋታ የሚይዝና የመጣበትን የሚያስረሳ ወሬ ለማምጣት የሀሳብ አሰሳ ታካሂዳለች። ምንም ወሬ አልመጣ አሳት። ጁግኑቱ አንዴ ወሬ ከጀመረ በድጋሚ ቀስቃሽ አያስፈልገውም። እሱ የሚፈልገው አድማጭ ብቻ ነው። በየወሩ ገንዘብ አዋጡ የሚለውን የኮሚሽኑን ጽ/ቤት ሉበነት፡ የጂፈርሰን ዱቪስን ነፈዝነትና በገንዘብ ተገዝቶ ለያንኪዎች ቅጥረኛ የሆነውን አየርላንዳዊ ከሀዲነት በስፈው አወራ።

የወይን ጠጅ ሲቀርብ ሁለቱ ሴቶች ተነሰተው ብቻውን ትተው ሊወጡ ሲሉ ጂራልድ ቅንድቦቹን ሰብሰብ አድርጎ ሴት ልጁን ኮስተር ብሎ ተመለከተና ለትንሽ ደቂቃ ከሷ ጋር ለመቆየት እንደሚፈልግ ተናገረ። እስካርሌት፡ መሀረቧን በረዳት ማጣት ስሜት የምታራግፈውንና ተንሸራታቹቹን በሮች ጭትታ የምትወጣውን ሚላኒን፡ ተስፋ በቆረጠ ዓይን አየቻት።

"እንዴነሽ አሁንስ እሜቱ" መደንገጥ ጀመረ ጂራልድ፡ ከወይኑ እየቀዳ። "ጥሩ ሥራ ነውፒ ሌላ ባል ፍለጋ ላይ ነሽ እንዴ? ገና ትኩስ የመጣ ሚስት መሆንሽ ቀረ እንዴ?"

"ቆይ ጮክ አትበል አባባ፡ ሠራተኞቹ..."

"አይ እነሱማ ካወቁት ሰንበቱ። እረ ያገሩ ሰው ወርደታች ንን አውቆልናል። ምስኪን እናትሽን እንትልጥ ያሳጣት ነገር ነው። እሷንም ጭንቅላቱን በጥበጠኛለ። በጣም የሚያሳፍር፡ በጣም የሚያ ዘፍጥ ነውር ሥራ ነው። አሄሄ፡ እንደዱሮው በእንባሽ የምታታልይኝ

@OLDBOOKSPDF

አይምሰልሽ ፥ ሞሽሳቂት ። ለስ ተባይፎ ። ወዲያው የእስክርሌት ቅን ድቦች መጨማደድ አፏም ቅርፁን ማጣት ሲጀምር አይቶ ደነገጠ ። "አውቅሻለሁ ። ከባልሽ ጀርባ ትዳሪያለሽ ። አታልቅሺ ። ስለዚህ ጉዳይ ዛሬ ማታ ምንም አልናገርሽም ። ይልቅዩ ያንን የሴት ልጂን ስም ያጉደፈውን ክብሯን ያዋረደውን ካርቱን በትሰር የሚባል ሰው ሄጂ አናግረዋለሁ ። ጠዋት ይሻላል ፥ ጠዋት ሄጂ አገኘዋለሁ ። አንቺም አሁን አታልቅሺ ። ምንም አይረባሽም ። እንባ ምንም አይረባሽም ። ደግመሽ ሁሳችንንም ከትቢያ ሳትጥይንና ጭቃ ሳትለውሽን ነገሁት ወደተራ ይገርሽ እመለሳለሁ ። አታልቅሺ ፥ እምዩሳዬ ምን እንዳመጣሁልሽ ተመልከቺ ፥ ቆንጆ ስጦታ አይደለም ? እዩው ተመልከቺው እንጂ ፥ ስንት ሥራ ያለብኝን ሰው እዚህ ድረስ እንድመጣ ለምን ታደርጊያለሽ ? የሆነ ያልሆነ ችግር እየፈጠርሽ ለምን ሥራ ታስፈቺኛለሽ ? እ ደሞ ምን ያክለቅስሻል ?

ሚሳኒና ፒቲፓት ከተኙ ቆይተዋል ። እስክርሌት ግን በወበቃ ማው ጨለማ ውስጥ አይኗን እንዳፈጠጠች ናት ። ልቧ እንዳች ነገር ተጭኖት ክብድ ብሏል ። ጡቷቿ ፍርሃት አግተዋል ። ወቸ ጉድ ! ምን እርግማን መጣባት ፥ ግና ኑሮዋን ሀ ብሎ እንደገና ከመጀመሯ ወደ ቤትሽ ተመልሰሽ የኤለንን ዓይን አይ ትባል ! መቼም የእናቷን ፊት ከምታይ ሞት ይሻላታል ። ብዚችው ባሁኗ ደቂቃ ድብን መትት ብትልሳቸው እኮ አዳ ሚ ስምን ጠላኋት ይል ነበር ። የሞቀ ትራሷ ላይ ከአንድ ፊቷ ሠራ በሌሳኛው ስትገላበጥ ሳትችል ፥ ፀጥ ካለው ካጥር ውጪው መንገድ አንድ ድምጽ ጆሮዋን ያዘው ። እንደአንግዳም አንደተለመደም የሚመስል ውጅብርብር ያለና በትክክል ተለይቶ የማይሰማ ነው ። ከአልጋዋ በፍጥነት ወርዳ ወደ መስኮቱ ሄደች ። የከብ ንጠብጣብ ጠቃጠቆ ባረገው ደብዛዛ ሰማይ ሥር ከአናት ቅር ንጫፎቻቸውን ያቆላለፉት ዛፎች ያቀፉት መንገድ ፥ ረጋ እንለስ ጥቁር ጽልመት ወርታል ። ያ ድምጽ እየቀረበ መጣ ። የኀማምችና የፊረስ ኮቴ ድምጽ ። ወዲያው የምታውቀው "ፔግ ኢን ኤ ሰው ባክድ ካር" የሚለው ዜማ በውስኪ በጉረኑን ድምጽ ሲዘመር ስትሰማ ደነገጠች ሳቋን ለቀቅችው ። ምንም እንኳ የጀንስቦሮው የችሎት ቀን ባይሆን ጀራልድ ወደቤት የሚመጣው በዛው በተለመደው ሁኔታ ነው ።

አንድ ግዙፍ ጋሪ እደጃፉ ሲቆምና ማንነታቸው የማይለይ ሰዎች ሲወርዱ አየች ። አንድ ሰው አብሮት አለ ። እበሩ ላይ ሁለት

@OLDBOOKSPDF

ስምች ቆሙና የበሩ መክፈቻ ድምጽ ተሰማ ። የጂራልድ ድምጽ ግልጽ ሆነ ።

"አሁን 'ላሚንት ፎር ሮበርት ኢሚት' የተሰኘውን ዘፈን አሰማ ሀለሁ ። ልታውቀው የሚገባህ ዘፈን ነው ወዳጄ ። አስተምርሀ ለሁ ። "

"እኔም መማር እፈልጋለሁ" አለና መለሰ የጓደኛው ጥልቅት ያለው ቀጥተኛ ድምጽ ፤ ትንሽ ሳቅ ተቀላቅሎበት "ግን አቶ ጂራ ልድ ፡ አሁን አይሆንም "

"እረ የሰማያቱ ያለህ! ያው አገር የጠላው በትለር የተባለ ሰው ነውና !" ብላ አሰበች በመጀመሪያ ። ከዚያ ልብ ገዛች ። ተመስ ጌን ፡ ቢያንስ አልተጋደሉም ። ያሞም አብረው እቤት ሲመጡ የቻ ሉት ኋይኝነቱን አጥብቀው ቢይዙት ነው ። ያውም በዚህ ሰዓትና በዚህ ሁኔታ ።

"እኔ እዘፍነዋለሁ ። አንተ ማጸመጥ ይኖርብሀል ። አለበለዚያ አሬንጅ ማን ነህና እገድልሀለሁ ። "

"የለም አሬንጅ ማን አይደለሁም ። ቻርልስተናዊ ነኝ"

"ከዚያኛው አይሻልም ። እንደውም ይብሳል ። የሁለት ወንድሞቼ ሚስቶች ቻርልስተናዊያን ስለሆኑ ስለቻርልስተን አውቃለሁ ። "

እስካርሌት ደንግጣ "ለመንደሩ ሁሉ ነው እንዴ እሚያወራው ?" አለች የአንባት ልብሷን እያነሳች ። ግን ምን ማድረግ ትችላለች? በዚህ በጭለማ እምድር ቤት ወርዳ አባቷን ከመንገድ ጉትታ ማስ ገባት አትችል ነገር ።

ጂራልድ የውጪው በር ላይ ተንጠልጥሎ ቆይቶ ያለምንም ማስጠንቀቂያ ጭንቅላቱን ወደ ኋላ ጋለል አድርጎ "ላሚንት" የሚለውን ዘፈን በወፍራም ድምጹ አምባረቀው ። እስካርሌት የመስኮቱን ደፍ በክርኗ ተደግፋ እያጸመጠች ያለፈቃዷ ትስቃለች ። አባቷ ቃናውን ቢያስተካክለው ኖሮ ቆንጆ ዘፈን ይሆን ነበር ። ለትንሽ ቅጽበት የዚያን ዜማ አስደሳች የግጥም መጀመሪያ ተከተለች፡-

ወዳጅዋ ካለበት
ጀግናው ከተኛበት
ሩቅ ነው ቀዬዋ

@OLDBOOKSPDF

ስንቱ ይገመጣል
ምራቁን ይውጣል
ሲያያት ሰብቻዋ

ዘፈኑ ቀጠለ ። አስካርሌት ከወ/ሮ ፒቲፓትና ከሜላኒ መኻል በት የመቀስቀስ ድምጽ ሰማች ። ምስኪን ነገሮች ። ያለጥርጥር በጣም መባ ሰጨታቸው አይቀርም ። አንዲጂራልድ ያለ ደመ-ሙቅ ወንድ አይተው አያውቁምና አልለመዱም ። ዘፈኑ ሲያበቃ እነዚያ ሁለት የነበሩ ቅር ጻኞ ተዋህደው አንድ ሆኑና ያው አንዱ ደረጃውን ወጣና ቆየት ቆየት እያለ በሩን ያንኳኳ ጀመር ።

"እታች ልውረድ መሰለኝ" አለች አስካርሌት በልቧ ። "ሌላው ቢቀር የገባ አባቴ ነው ። ወ/ሮ ፒቲፓት እንደሆኑ እዚያ ልሂድ ቢሉ ከመሄዳቸው በፊት ልባቸው ፈሰሰ ይሞታሉ ። በዛ ላይ ጄራልድ በዚህ ሁኔታ እያለ ሠራተኞቹ እንዲያዩት አይፈለጉም ። ፒተር አስ ገብቹ ላስተኛው ቢል ደግሞ ያልአግባብ ያስቸግረው ይሆናል ። እንዴት ደግሮ እንደሚያስተኛው የሚያውቅና የሱን ጠባይ የተረዳ ፖርክ ብቻ ነበር ።"

የአንገት ልብሷን ጉርሮዋ አካባቢ በስፒል አያያዘችና አልጋዋ ጐን የሚቀመጠውን ሻማ አብርታ በጥድፊት በጨለማው ደረጃ ወርዳ ወደፊት ለፊቱ አዳራሽ ሄደች ። ሻማውን በሩ አጠገብ ባለው ቋሚ ላይ አስቀምጣ በሩን ከፈተች ። በሚውለበለበው የሻማ ብርሃን ውስጥ ጥቂት እንኳ ወልገድ ሳይል ፣ አጭሩንና ፍርጥም ያለውን የሰከረ አባቷን ደግፎ አንደቆመ ሬት በትለርን አየችው ። "ላሚ ንት" የሚለው ዘፈን በዓደባው ክንድ ላይ የተንጠለጠለው የራሱ የጄራልድ መሆኑ ገባት ። ባርሜጣው ራሱ ላይ የለም ። ኮሳውና ሉጫ ረጅም ፀጉሩ ተመሳሜጭሯል ። አንደኛው የክራባቱ ቅርንጫፍ በአ ንድ ጆሮው በኩል ሄዷል ። ሸሚዙ ወደደረቱ ላይ በመጠጥ ረጥቦ እርጥበቱ ቁልቁል ወደ ሆዱ ይወርዳል ።

"አባትሽ ይመስለኛል ፣ አይደል?" አለ ካፒቴን በትለር የሚ ዝናኑ ዓይኖቹን እጠይም ራቱ ላይ እያጫወተ ። ድንገት ልብሷን ዘልቆ የሚገባ በሚመስል አስተያየቱ ግዴለሽ አለባበሷን አንዴ ጠረግ አድርጎ አየው ።

"አስገባው ወደ ውስጥ" አለች ፣ በአለባበሷ በማፈርና የዚህ ሰው መሳቂያ ያደረጋትን ጄራልድን በመርገም ።

ሬት ጄራልድን ወደፊት ገፋው ። "ደረጃውን ይዘ መውጣቱን ላማዝሽ ይሆን? ደግፈሽው መውጣት ያስቸግርሻል ፣ በጣም ይከ በዳል ።"

@OLDBOOKSPDF

በለሊት አመኘ። በብርሃን አማካይ ዘሎ በድፍረት ጥያቄ በማቅረቡ ደንግጣ አፏን ከፍታ ቀረች። ካፒቴን በትለር ፎት መውጣቱን አልጋቸው ላይ እንዳሉ ፒቲፓትና ሚላኒ ቢሰሙ ምን ይሉ!

"እረ የሰማያቱ ያለህ! እንዴት ተብሎ! እዚሁ አልፍኝ ድረስ ይበቃል ፤ እዚያ ሶፋ ላይ።"

"ሱቲ ነው ያልሺኝ?"

"አፍህን ብትዘጋልኝ በጣም አመሰግንሀለሁ። እዚህ ጋ። በታ እዚህ ጋደም ይበል"

"የቆሳ ቦት ጫማውን ላውልቅለት እንዴ?"

"የለም ፡ ከዚህ በፊትም አደርጉት ተኝቶ ያውቃል።"

አሁን ሳታውቅ ለፈጠረችው የምላስ ወለምታ ምነው ምላሴ በተቆረጠ ኖሮ አለች። ምክንያቱም የጂራልድን እግሮች እያጣመረ ሳለ ትንሽ ሳቅ ሲል አይታዋልችና ሰምታታል ማለት ነው።

"ባክህ ሂድልኝ አሁን"

በደብዛዛው አዳራሽ ውስጥ ሄዶ እበሩ እጀታ ላይ አስቀምጦት የነበረውን ባርሚጣውን አነሳ።

"እሁድ ማታ በእራት ሰዓት አገኝሻለሁ" አለና በሩን ከኋላው ያለድምጽ ዘግቶ ሄደ።

እስካርሌት ሠራተኞቹ ቁርስ መሥራት ሳይጀምሩ በፊት ጠዋት በአሥራ አንድ ተኩል ተነስታ ድምጽ ሳታሰማ ወደ ምድር ቤት ወረደች። ጂራልድ ነቅቶ አገኘችው። ሶፋው ላይ ተቀምጦ በመዳፎቹ ጭንቅላቱን ለመደፍጠጥ የፈለገ ይመስል ራሱን በእጁ ይዞ ይጫነዋል። ስትገባ በደበዘዙ ዓይኖቹ ቀና ብሎ አያት። ዓይኖቹን ማዘዋወር እንኳ ከባድ ሆኖ የሚሰማው ሕመም ያስታስተዋል።

"ወይ አጉል ቀን! ጐደሎ የቀን ጐደሎ!"

"ያደረግኸው ሁሉ ጥሩ ነገር ነው አባባ" አለች ኮስተር ብላ በቁጣ እንደበት። "በዛ በወድቅት ሰዓት መምጣትህ ሳያንስ በጨኸት ዘፈን እየዘፈንክ ሰፈር ጐረቤቱን ሁሉ መቀስቀስህ ባለ"

"ዘፈንኩኝ እንዴ?"

"መዝፈን ነው አስነካኸው እንጂ! "ላሚንት" የሚለውን ዘፈን የሰፈሩ ማሚቶ ጸር እስከ ጸር እስኪያስተጋባ አደል እንዴ እየጮህክ የዘፈንከው።"

@OLDBOOKSPDF

"ምንም ትዝ የሚለኝ ነገር የለም ።"

"ማዬለህም የጐረቤቱ ሰው ሁሉ እስክእለተ ሞቱ ያስታውስ ሀል ። ወይዘሮ ፒቲፓትና ሚላኒም አሳምረው ያስታውሳሉ ።"

"እረ የጭንቅ አማላጅዋ!" አለ ጄራልድ በማቃሰት ፡ በወፍራም ምላሱ የደረቀ ከንፈሩን እያራሰ ። "ቁማር ከተጀመረ ወዲያ የማስ ታውሰው በጣም ጥቂት ነው ።"

"ቁማር?"

"ያ በትለር የሚባል ሴት አውሬ ሰውዬ በካርታ ቁማር የሚያ ከለኝ የለም ፤ ሁሉን ሙልጭ የማስወጣ ነኝ እያለ ሲደነፋ . . ."

"ምን ያህል ተበላህ?"

"እንደ እንደልማዱ አሸነፍኩ እንጂ ። አንድ ወይም ሁለት ከመ ጠጡ ከወሰድኩ ቁማር የሚያርሰብኝ የለም ።"

"እስቲ ቦርሳህን ተመልከት."

ጄራልድ እያንዳንዷን እንቅስቃሴ ከስታይ ማህደር የሚያ ወጣት ይመስል እያስታስተችው ቦርሳውን በመክራ አውጥቶ ከፈ ተው ። ባዶ ነው ። በድንጋጤ እይት ፈጠጠ ።

"አምስት መቶ ብር ነበረኝ ።" አለ ። "ያውም ለኤለን ከኮንትሮ ባንዲስቶች ላይ ዕቃ እገዛለሁ ብዬ የያዝኩት ነበር ። አሁን እን ኳን ለሷ ዕቃ መግዣ ወደታራም መመለሻ ቤሳ ቤስቲን የለኝም ።"

እስካርሌት ባዶውን ቦርሳ በንዴት እያየች ሳለች አንድ ሃሳብ ቀስ በቀስ ወደ አእምሮዋ ገብቶ ቅርጽ መያዝ ጀመረ ። እየቆየም ግዘፍ መልክ መልክ ያዘ ።

"እኔ መቼም ከእንግዲህ ወዲያ እዚች ከተማ ውስጥ አን ገቴን ቀና አድርጌ አልንቀሳቀስም ።" ብላ ጀመረች ። "ሁላችንንም አዋርደኸናል ።"

"እንግዲህ አፍሽን ያዢ አንቺ ። ጭንቅላቴ ሲፈርጥ ደርሶ እይ ታይሽም እንዴ?"

"እንደካፒቴን በትለር ካለ ሰው ጋር ጥምብዝ ብለህ እቤት መምጣት ። ማምባህ አየር ሊያወጣ በሚችለው መጠን እየ ጮህክ ጐረቤት ሁሉ መቀስቀስ ። ያንን ሁሉ ገንዘብ መክሰር ።"

"ሰውየው እንደጨዋ ካርታ መጫወት እያውቅም ። ሲበዛ ጮሌ ነው ። እሱ . . ."

@OLDBOOKSPDF

"አሁን እማማ ስትሰማ ምን ትላለች?"

በላም በደነገጠ ሰው ዓይን ቀና ብሎ አየ።

"ለእናትሽ ነግረሽ ደሞ እንዳታበሳጪያት። አትነግሪም አይደል?" እስካርሌት ምንም ሳትናገር አፏን ዝግታ ጭጭ አለች።

"እሷን የመሰለች ጨዋ ሴት ይህን ስትሰማ እንዴት ስሜቷ እንደሚጎዳ አስቲ አስቢው።"

"ትላንትና ማታ የቤተሰቡን ክብር አጐደፍሽ ያልከኝንስ እማማ ብትሰማ እንዴት ስሜቷ እንደሚጎዳ አስበኽዋል አንተስ? ያውም እኔ ለሚዋጉት ወታደሮች መርጃ ገንዘብ ለመሰብሰብ ትንሽ ስለደ ነስኩ ነው። ወ. . . . እኔ መጨሚ ነው።"

"የለም፡ ባክሽ አትጨሚ።" ልመና ገባ ጂራልድ። "ደካማ ጭንቅላቱ ከሚሸከመው በላይ ይሆንብኛል። ለራሱ አሁንም መፈ ንዳቱ ነው።"

"እና አንተ ስለኔ ያልከው. . ."

"የኔ ቆንጆ ምስኪን አባትሽ በተናገረው ነገር ስሜትሽ አይ ጐዳ ባክሽ። የሚናገረውን አያውቅም፡ አልገባውም፡ አንቺ የታ ነጽሽ አስተዳደግ ጨዋ ልጅ ለመሆንሽ እርግጠኛ ነኝ።"

"እና ከነውርደቱ አቤት ይዘሽኝ ልትሄድ ትፈልጋለህ?"

"አ የኔ ቆንጆ እሱንስ' አላደርገውም። እንደው ላስፈራራሽ ነው። እናትሽ በወጪ ጉዳይ እየጨቀጨቅሽኝ ነበር። ለእናትሽ አትነግሪም አይደል?"

"አልነግርብህም" አለች እስካርሌት በልቧ። "ነገር ግን አንድ ነገር ካደረክልኝ ነው። እዚህ እንድቆይ ከፈቀድክልኝና ሄደህ ለእማማ የሰማችው ሁሉ የአሉባልታ ወሬ መሆኑን ካስረዳህልኝ ነው።"

ጂራልድ ሴት ልጁን በሐዘኔታ ዓይን ተመለከታት።

"መቼም ከማጭበርበር ያላነሰ ሥራ ነው የሰራሽው"

"ትላንት ማታ የተሠራውም ከትልቅ ቅሌት ያላነሰ ሥራ ነው።"

"እሺ እንግዲህ" ማወነባበድ ጀመረ። "በቃ ሁሉንም እንር ሳው። እኔ እምልሽ፡ እንደወይዘሮ ፒቲፓት ያለች ቆንጆ ሴት ወይ ዘሮ ቤት ውስጥ፡ ብራንዲ ይጠፋ ይመስልሻል? የፀጉራም ውሻ. . ."

@OLDBOOKSPDF

እስካርሌት ድምጿ እንዳይሰማ በእጣር ጣቷ እየረገጠች በፀጥተኛው አዳራሽ አድርጋ ወደምግብ ቤት ገብታ ፡ ወ/ሮ ፒቲፓት የልብ መፍሰስ በሽታቸው ሲነሳባቸው ትንሽ ትንሽ የሚጎነጩትንና እሷና ሚሲ በድብቅ "ማደንዘዣ ጠርሙስ" ብለው የሰየሙትን ብራንዲ ልታመጣ ሔደች ። ድል አራቷ ላይ ተጽፏል ። ጀራልድን በሚገባ ወጥመዱ ውስጥ ስላስገባችው ምንም ሀፍረት አይሰማትም ። ከእንግዲህ ማንም የወሬ ቀበኛ ሰኤለን ቢጽፍላት ማባበያውን ፡ ማርከሻውን ፈጥራለች ። አሁን አትላንታ ውስጥ ከርታ ትቀመጣለች ። ወ/ሮ ፒቲፓትም በሷ ጸፋ የገቡ ስለሆነ እንደፈለገች መደሰት ትችላለች ። ቢፈውን ከዘጋች በኋላ ጠርሙሱንና ብርጭቆውን ደረቷን አስጠግታ ይዛ ለጥቂት ጊዜ ቆመች ።

ከዚያ ጊዜ ወዲያ በፒችትሪ ክሪክ አካባቢ ባሉት ምንጮች ሁሉ ሽርሽር ትሄዳለች ። በስዋን ማውንቴን ላይ በሚያረግ ግብግ ላይ ትገኛለች ። በሪሲፕሺን ግብግቦችና የምሽት ጸንሶች ላይ ትካፈላለች ። የፈረስ ጋሪ መንዳት ፕሮግራም ይኖራታል ። የአሁድ አሁድ የቢፈ እራት ምሽት አያመልጣትም ። የዝግጅቶች ሁሉ ቁልፍ ፡ የዝግጅቶች ሁሉ እምብርት በመሆን በቅድሚያ ትሰለፋለች ። ሰው በተሰበሰበበት ቦታ ሁሉ እመሀከል ቦታ አታጣም ። መቼም ሆስፒታል ውስጥ ትንሽ ውለታ የዋለችላቸው ወንዶች ሁሉ በፍቅር ይወድቁላታል ። አሁን ሆስፒታሉንም እንደአዲያፊ ቦታ ማየቱን ቀንሳለች ። ወንዶች በታመሙ ጊዜ በቀላሉ ስሜታቸውን መቀስቀስ ፡ ልባቸውን ማነሳሳት ይቻላል ። ታራ ውስጥ የሚገኙት የበሰሉ ፍሬዎች ዛፉ በቀስታ ሲነቀነቅ እንደሚረግፉ ሁሉ ቀልጣፋ ሲትም ወንዶቹን በእጅዋ ልታገባቸው ትችላለች ። ታረግፋቸዋለች ።

የገነኛው ጀራልድ ጭንቅላት የትላንት ማታውን የዘረ ድምር ለመቋቋም ባለመቻሉ እግዚሀርን እያመሰገነች ማገገሚያውን ሕይወት መልሰ መጠጥ ይዛ ወደአባቷ ተመለሰች ። እማሬ መንገዷንም ትላንት ማታ አባቷ ላይ የደረሰው ነገር ሁሉ የሬት በትለር እጅ ይኖርበት ይሆን የሚል ጥርጣሬ አሳድሮባታል ።

@OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ 11

በተከታዩ ሳምንት ውስጥ በአንደኛው ቀን ከሰዓት በኋላ እስ
ካርሌት ድክም ብስጭት ብላ ከሆስፒታል ወደ ቤት ተመለሰች ።
ጠዋቱን በሙሉ ቆማ ስለዋለችና ወይዘሮ ሚሪዊዘር አንድ ወታደር
አልጋ ላይ ለምን ቁጭ አልሽ ብለው ሙልጭ አድርገው ስለሰ
ደቧት ብሽቅ ብላለች ። ወይዘሮ ፒቲና ሜላኒ የፀሐይ መከለያ
ባርሜጣዎቻቸውን አድርገው እበረንዳው ላይ ከዋድና ከፕሪሲ ጋር
ተቀምጠዋል ። የተለመደውን የሳምንቱን ዘመድ ጥየቃ ለመጀመር
ተዘጋጅተዋል ። እስካርሌት አብራቸው ለመሄድ ባለመቻሏ ይቅርታ
ጠይቃቸው ፎቅ ወጣለው መኝታ ቤቷ ሄደች ።

የመጨረሻው የሰረገላ ድምጽ መሞቱንና ቤተሰቡ በሙሉ
ለአይን ርቆ መሄዱን ስታረጋግጥ በቅስታ ወደሜላኒ መኝታ ቤት
ሄዳ የበሩን ቁልፍ ከፈቸች ። ብዙ አግር ያልበዛበት በዕቃ ጢም
ያለ ቆንጆ ክፍል ነው ። አግድም የምትገባውን የአራት ሰዓት ፀሐይ
በፀጥታ የሚሞቅ ክፍል ። አልፎ አልፎ ከሚታየው ደማቅ ነጠብጣብ
በስተቀር ወለሉ ያብረቀርቃል ። ሜላኒ የዕቃ ማስቀመጫ ብላ ባንደ
ኛው ግድግዳ ላይ ትንሽ መደርደሪያ ብጤ ባትሰቅልበት ኖሮ የቤቱ
ግድግዳ በሙሉ ምንም ነገር የሌለበት ነጭ በነጭ ይሆን ነበር ።

ከኮንፌደሬሲው የተጌጠ ባንዲራ በታች ደግሞ የሜላኔ አባት
አሚከሲኮው ጦርነት ላይ ሲዘምቱ ታጥቀውት የነበረውና በኋላም
ቻርለስ ወደጦር ግንባር ይዞት የሄደው ሰይፍ ፣ የቻርለስ የአንገት
ርጣ ፣ ዝናሩና እንዲሁም ሽጉጡ ከነማህደሩ ተሰቅሏል ። በሰይፉና
በሽጉጡ መካከል ከብር የተቀረጸው የቻርለስ ፎቶም በማራጫ
ዩኒፎርሙ እንደኮራ ፣ ቡናማ አይኖቹ እያንፀባረቁና የጭምት ፈገግ
ታው እከንፈሩ ላይ እንደወዛ ይታያል ።

እስካርሌት ቀና ብላም ወደ ፎቶግራፉ ሳታይ ከፍሉን ማህል
ለማህል አቋርጣ አልጋው አጠገብ ካለው ጠረጴዛ ላይ ወደሚገኘው
የደብዳቤ ሳጥን ሳታመነታ ሄደች ። በሰማያዊ ጥብጣብ የታሠሩ ከአ
ሽሌይ ለሚሰኙ የተላኩ ደብዳቤዎች ከውስጡ አወጣች ። ከደብዳ
ቤዎቹ ሁሉ በላይ በኩል ያለው ዛሬ ጠዋት የተላከው ደብዳቤ
ነው ። እሱን ከፈተችው ።

@OLDBOOKSPDF

ከዚህ ቀደም እስካርሌት ለመጀመሪያ ጊዜ ደብዳቤዎቹን በምስጢር ልታነብ ስትል ባንድ ወገን የሕሊና ወቀሳው በሌላ ወገን እያዛለሁ የሚለው ስጋት ወጥሮ ይዟት ከፍርሀቷ የተነሳ እጅዋ በመንቀጥቀጡ ፖስታውን መክፈት እንኳ አቅቷት ነበር። አሁን ግን ያ ጠለቅ ብሎ የማይዘልቅ ክብሯ በምትሠራው ጥፋት ተደጋጋሚነት ስለደበዘዘ ብትያዝ እንኳን ደንታ የማይሰጣት ሆናለች። እማሪ መንገዷን በተሸማቀቀ ልቧ እንዲህ ብላ አሰበች፦ "አሁን እናቴ ብታውቅ ምን ትለኝ?" መቼም በእንዲህ ያለ ክብርን በሚያደማ ቃላቱ ልጅዋ መርከሷን ከምታውቅ አለን እዚያው ድርቅ ብላ ብትቀርላት ይሻላታል። ይሄ ሐሳብ በመጀመሪያ አስካርሌትን አስጨንቋት ነበር። ምክንያቱም በማንኛውም ረገድ እናቷን የመምሰል ፍላጎት ስለነበራት ነው። ዳሩ ምን ያደርጋል ደብዳቤዎቹን ለማንበብ ያላት ፍላጎት ከዚህ ሀሳብ እየለሰና የእናቷን ነገር ከአእምሮዋ ገፍትራ አስወጣችው። ዛሬ ዛሬ፣ ደስ የማይላትን ሐሳብ ከአእምሮዋ እየገፈተሩ ማስወጣቱን በጣም ተሳምዳዋለች። እንደሚከተለው ያለውን ፊሊጥ በጣም ሠልጥናበታለች፦ "ይሄንን ሁሉ አላስብበትም። ያኛውን አሁን ባልጨንቅበት ይሻላል። ነገ አስብበታለሁ።" በአጠቃላይ ግን ነገ ሲመጣ ወይ ያ ሀሳብ ከናካቴው እይታወሳትም አሊያም በመቆየቱ ምክንያት የሚያስጨንቃት ጉዳይ መሆኑ ይቀራል። ስለዚህ የአሽሊይን ደብዳቤዎች ሰርቃ የማንበቧ ነገር ሕሊናዋን የመውቀሱም ጫና እያደር ተቃልሎላታል።

ሜላኒ የአሽሊይን ደብዳቤ በከፊል ለፒቲፓትና ለእስካርሌት በማንበብ ረገድ ለጋስ ናት። ሆኖም በከፊል ሳታነብላቸው የምታስቀረው ክፍል አስካርሌትን እረፍት ይነሳታል። የባሏን እህት ደብዳቤ እየሰረቀች እንድታነብም ልቧን ያቆመዋል። አሽሊይ ሚስቱን ካገባት በኋላ ማፍቀር ጀምሮ እንደሆን ለማወቅ በጣም ትፈልጋለች። ማፍቀሩ ቀርቶ የሚያፈቅራት ለመምሰል መሞከሩን ማወቅ አለባት። በጣም የሚወዳት መሆኑን በጽሑፍ ይገልጽላታል? የፍቅሩን መጠን በምን ዓይነት ሁኔታና በእንዴትስ ያለ ሙቀት ይነግራት ይሆን? በጥንቃቄ ደብዳቤውን ከፖስታው ውስጥ አወጣች።

በማስመሪያ የተሰመሩ የሚመስሉት የአሽሌይ ቆሎ የመሰሉ ፊደላት ወደ አይኖቿ ዘለሉና "ውድ ባለቤቴ" ብለው ጀመሩ። በእፎይታ ተነፈሰች። ጐሽ ለካ ገና "የኔ ፍቅር" ወይም "የኔ ማር አሸት" ማለት አልጀመረም።

"ውድ ባለቤቴ ሆይ የልቤን ሐሳብ የምደብቅሽ አይምሰልሽ። እንደምትሰጊና አሁን ምን እያሰብኩ እንደሆነ ለማወቅ እንደምትፈልጊ የገፍሺው ደብዳቤ..."

@OLDBOOKSPDF

"ኧረ በማርያም" አሰች እስካርሉት በልቧ ፥ ሕሊናዋን በሚወቅስ የመሸማቀቅ ስሜት ። "የልቡን ሐሳብ እየደበቃት ፣ ። ለመሆኑ ሜሊ የእሱን ጭንቅላት ማንበብ ትችላለችና ነው እንዴ? ኧረ እሱ ቀርቶ የኔንስ ጭንቅላት ታነባለች እንዴ? እኔና እሱን ትጠረጥረን ይሆን?"

ደብዳቤውን በጣም እያስጠጋች ይዛ ሳለች እጆቿ ይንቀጠቀጡ ጀመር ። ሆኖም የሚቀጥለውን አንቀጽ ስታነብ ዘና አለች ።

"ውድ ባለቤቴ ሆይ ፣ የልቤን ሐሳብ ካንቺ የምደብቀው ባንቺ ላይ ምንም ዓይነት ሽከም እንድጭንብሽ ስለማልፈልግ ነው ። አእምሮዬ ውስጥ የሚጉላላውንና የሚንጫጫውን ሀሳብ አንቺ ላይ በማራገፍ የራሴን ደህንነት ጠብቂ አንቺን በጭንቀት ማጥ ውስጥ ልዘፍቅሽ አልሻም ። ሆኖም ካንቺ የምሸሽገው ቅንጣት ነገር እንደሌለ አንቺም በቅጡ ታውቂዋለሽ ። ምንም የሚያሰጋሽ ነገር አይኖርም ። አልቆሰልኩም አልታመምኩም ። በቂ ምግብ አገኛለሁ ። አንዳንዴ የምተኛበት ቦታም አላጣም ። ወታደር ከዚህ በላይ የሚጠይቀው ነገር ፣ ከዚህ በላይ የሚፈልገው ነገር ሊኖር አይችልም ። ግን ሚላኒ ለልቤ ጫና የሆነብኝ ሀሳብ አለ ። ልቤን ከፍቼ ይህንን ጫና አሳይሻለሁ ።

"በነዚህ የበጋ ምሽቶች ሁሌ ማታ ማታ የጦር ሰፈራችን ሰው ሁሉ ከተኛ በኋላ እኔ እንቃና በጀርባዬ ተንጋልዬ የሰማይን ከዋክብት ደግሜ ደግሜ እያየሁ፡ አሽሌይ ዊክስ ፣ እዚህ ምን ትሠራለህ? ለምንድ ነው የምትዋጋው ? ለማን ነው የምትዋጋው? እላለሁ ።

"መቼም ለክብርና ሰገነና ብዬ እንደማልዋጋ በትክክል አውቃለሁ ። ጦርነት መጥፎ ነገር ነው ። እኔ ደግሞ መጥፎ ነገር አልወድም ። ወታደር ስላልሆንኩኝ ከመድፍ እፍ መንጭቴ የማገኘው ቢሆን እንኳን ስምና ሽልማትንም አልሻም ። አየሽ ሜላኒ ፣ እኔ ጥሩምባና መለከት ደሜን የሚያሞቀው ፣ አታሞና ነጋሪት ሐሞቴን የሚያመረው ሰው አይደለሁም ። አንድ ደቡባዊ ብቻውን አንድ ደርዘን ያንኪ ጠርጐ ይጥላል ሲሉን እውነት መስሎን ፣ የጥጥ ንጉሥ የዓለም ገዥ ይሆናል ሲሉን እውነት መስሎን ተታለልን ። ገደል ገባን ። ከበላያችን ሥልጣን ላይ ያሉ ሹሞቻችን ያማሩ ቃላትና የሽንገላ ዲስኩሮች በሰረዉብን የሀሰት ጥላቻና ስሜታዊ ፍቅር ተሞኘን ። ቅዱስና ብፁዕ የምንላቸው ባለሥልጣኖቻችን በሚሰነዝሯቸው 'የጥጥ ንጉሥ ፣ ባርነት ፣ የሀገሮች ነፃነት ፣ ያንኪዎችን ማውገዝ ' በሚሉ ባዶ መፈክሮች ተሸነገልን ።

@OLDBOOKSPDF

"ስለዚህ አብርድ ልብሴ ላይ ተንጋልዬ ዓይኖቼን አቅንቼ ከዋክብትን እያስተዋልኩ ፣አሽሊይ ለምንድነው የምትዋጋው?' እያልኩ ራሴን ስጠይቅ ፡ ስለአህጉሮች ነባነት ፡ ስለጥጥ ፡ ስለባሪያዎች እና ከልጅነት ጀምሮ እንደጠመጠመብትን ስላደግነው የያንኪዎች ጥላቻ አስብና ከነዚህ ከዘረዘርኳቸው ሁሉ ለአንደኛውም ስል እንደማልዋጋ እገነዘባለሁ ። በዚህ ምትክ የ"አሥራ ሁለቱ ዋርነዎች"ን መንደር ማሰብን እመርጣለሁ ። በአጫጮቹ የበረንዳው ምሰሶዎች ላይ የጨረቃ ብርሃን ለምን በአግድም እንደሚፈስስ መመራመር ይበልጣል ። የማግኖሊያዎቹ ዛፎች ሰጪረቃ ልባቸውን ሲከፍቱ ለምን እንዲህ ግኑታዊ ተፈጥሮ ኖራቸው እያልኩ እጠይቃለሁ ። በበረንዳው ላይ የሚድሁት የሐረግ አበቦች በጠራራው የቅትር ሰዓት እንኳን ለምን ጥላ ያጠላሉ ማለት ያረካኛል ። በልጅነቴ ላያት እንደነበር ሁሉ እናቴን ስፈት ስትሰሩ አሁንም አያታለሁ ። ወደ አመሻሹ ላይ በየማሳው እያቋረጡና ያከሚቸው እየዘፈኑ ለእራት ዝግጁ ሆነው የሚመጡት ባሪያዎች ድምጽ ይሰማኛል ። እየተተረተረ ወደውሀው ጉድጓድ የሚወርደው ባልዲ የሚፈጥረው ድምጽ አሁንም ይሰማኛል ። ። በጥጥ እርሻዎቹ አሻግሮ ወደወንዙ የሚወርደውን ረዥም ቁልቁለት መንገድ ማየት ፡ ከዚያ ሰረ ጠርዝ የለሽ ምድር ወዲያ መቼትሽት ሲል የሚነሳውን ጭጋግ መመልከት ፡ አሁንም ይናፍቀኛል ። እንግዲህ ምን የሚልቸው ፡ ስታይን የምጠላው ፡ ዝናን የማልፈልገውና ስማንም ጥላቻ የሌሸኝ ሰውዬ እዚህ የመጣሁበት ምክንያት ይሄ ነው ። ምናልባት አርበኝነት ፡ ጀግንነት ፡ የሀገርና የቤት ፍቅር ስሜት የሚባለው ይሄ ላይሆን አይቀርም ። ግን ሚለኒ ነባሩ ከዚህም ጥልቀት ያለው ነው ። ምክንያቱም እነዚህ ሁሉ አሁን ሕይወቴን በሞት አፋፍ ላይ የጣድክብት ሰበብ ምልክቶች ናቸው ። እኔ የምወደው አይነት ኑሮ ፡ እኔ የማፈቅረው ዓይነት ሕይወት ማስታወሻዎች ናቸው ። እኔ የምዋጋው ለጥንቱ ቀናት ብዬ ነው ። ለዳሮው አናናር ለዳሮውና ለማፈቅረው የሕይወት ዘይቤ ብዬ ነው ። ነገር ግን በማም አሰጋለሁ ። ምንም ያህል ብንዋደት ፡ የቱንም ያህል መስዋዕትነት ቢከፈል የጥንቱ አናናር አይመለስም ብዬ እሰጋለሁ ። አሸንፈንም ተሸንፈንም የምንፈልገውን አናገኝም ። ሁለቱም እንድ ዓይነት ውጤት ያለው ነው—ረታንም ተረታንም የምንፈልገውን ማጣት ።

"ይህንን ጦርነት ብናሸንፍና የጥጥ ግዛት ህልማችንን ዕውን ብናደርግ ከጥንቱ የተለየን ሰዎች ስለምንሆንና የዳሮው እርጋታ የነበረው ሕይወት ስለማይኖር የፈለግነውን ነገር አናገኝም ። ያመ ከማጣት አንድ ነው ። ዓለም በራችንን እያንኳኳ የጥጥ ያለህ ይላል፣ እኛም ያሻንን የሽያጭ ዋጋ ለመተመን እንችላለን ። ይሄ ማለት እን

@OLDBOOKSPDF

ሚዲህ አስካሁን ስንከራከራቸው ፣ ስናሸማቅቃቸውና ስንረግማቸው የነበሩትን ያንኪምሾ በጎንዘብ ፍቅር መስከር ፣ ለትርፍ ንግድ መስ ገብገብና ማጋበስ እኛው መልሰን ተገፈቅንበት ማለት ነው ። እና ሚለኒ የፈሰግነውን ማጣት ፣ናፈለግነውን ማጣት ፣ እንጀ ሚላኒ እንጀ ብቻ !

"በበኩሴ አደጋ ወይም መምጣና መጋዝ ፣ብቆስል ወይም ሞት እራሱ ቢመጣ እንኳ አያስፈራኝም ። እኔን የሚያስፈራኝ ይሄ ጠር ነት ቢቆም እንኳን የጥንቱን ቅናት መልሰን ለማግኘት አለመቻ ላችን ነው ። እኔ የዚያ ዘመን ሰው ነኝ ። የሱሮውቹ ቅናት ባልደረባ ነኝ ። ያለህ ያሁኑ ያዘይ ጊዜ ፣ የዚህ የማድያ የኤልቂት ጊዜ ፣ የዚህ የእረመኔያዊ ጭጥጨሩ ጊዜ ሰው አይደሰሁም ። ሰወደፊትም ቢሆን ምንም ዋስትና ከሌለኝ የቻልኩትን ያህል እንኳን ጥረት ባደርግ ከነን ጋር የምጣጣም አይመስለኝም ። አንቺም ብትሆኚ ያው ነሽ ። አንቺም ሆንሽ እኔ ከአንድ ወንዝ የተጠለቅን ፣ ካንድ ዘር የበቀ ልን ሀንድ ደም የተጠመቅን ነን ። አንድ ነን ። ነገ ምን እንደሚመጣ የፈታችን ቀን በኩያው ምን አንዳዘለ ጣላውቅም አንደትሰንት ያሚ ያመረቃ ፣ አንደትሳንት ሰዘ ያሉውና አንደትሳንት ውብ እንደማ ይሆን ይሰማኛል ።

"እዚህ እትጋደልኩበት ዘመን ሆኜ እንኴ የተኙት ወጣቶች ማለ ትም መንትዮቹም ሆኑ አለቀሰ ወይም ካድ እኴ እማስበውን ያስቡ ይሆን አላለሁ ። የሚዋጉት ሲሞን እንደሆነ ያውቁ ይሆን? የሚዋ ጉለት ዓላማ ግና የመጀመሪያዋ ጥይት ስትተኮስ ከንቱ የቁሪ መሆኑን እያወቁት ይሆን ? በእርግጥም የኛ ዓላማ የጥንቱ አኗኗራችን የትላንት ያሞቁ ሕይወታችን ሰልነበረ ግና የመጀመሪያዋ ጥይት ስትተኮስ መደናረሰብ አላዩት ይሆን እያልኩ ይገርመኛል ። ጫሩ ግን እንዚህን የሚያስቡ አይመስ ለኝም ። ባሰማሰባቸው ታድለዋል ።

"እኔ አንቺ እንድታገቢኝ ስጠይቅሽም ይሆንን ነገር ባእኛ አን ኳር አላሰብኩበትም ነበር ። የ"አሥራ ሁለቱ ዋርክምቾ" መንደር ኑሮ እንደወትሮው ይቀጥል መስሎኝ ነበር ። እንደተለመደው በሰ ላም ፣ በእርጋታ ፣ እንዴሁም ምኣም ሰማይዛባና በማይለወጥ ሁኔታ ይፈስስ መሰለኝ ነበር ። ሚላኒ ፣ እኔና አንቺ በጣም እንመሳሰላለን። የምናፈቅራቸውም ነገሮች እንደዚሁ አንድ- አይነትና የረጉ ነገሮች ናቸው ። እናም ከጀርባችን የነበሩ ያለተጣደፉ ፣ ግርግር ያልበዛባቸውና ዛዙ ክንዋኔ የማይታይባቸው ፣ በውስጣቸው የማንበቢያ ፣ መጊቻ የማጸጠጫና የማለሚያ ቀናት ይዘው በረሻው የተዘረጉ ዓመታት ይታዩኝ ነበር ። አሁን ግን እሲያ ሁሉ አልፈው ይሄ ጊዜ መጣ ፣ በቅ ሬሽ ይጠጣል ያላልነው ይሄ ወቅት መጣ ። ይሄ የጥንቱን ደግ

@OLDBOOKSPDF

ነገር የሚያመሰሰ ክፉ ቀን ፣ ይሄ በደም ጐርፍ የተጥለቀለቀ በሬና አራጅ የበዙበት የአረመኔያዊ መተራረድ እስከፊ ቀን ፣ ይሄ በጥ ላቻ የተሞላ ጨካኝ ጊዜ በሁላችንም ላይ መጣ ። ሚላኒ እውነቱን ነው የምልሽ ያጣነውን ቀን የሀገሮች ነፃነትም ሆነ የባሪያዎች መኖር ወይም የጥቃ ሰብል መንጣለል አይተካውም ። በሞራሽ እኩያ ዋጋ አናገኝለትም ። አሁን የሚደርስብንንም ቁጣ የምናገኘው ፍሬ እይክሰውም ። ያንኪዎቹ ክሽነፉን የሚያርሰው ጥፋት ደግሞ ለማሰብ የማይቻል ነገር ነው ። ያም ሆኖ ሠዲት ድባቅ ሊመ ቱንም ይችላሉ ።

"ይሄን እንኳ በቃላት ልገልፀው አልሻም ። አረ ከነሞራሹም ባላስበው ይሻለኛል ። ልቤ ውስጥ ምን እንዳለ ስግውቅ መፈለግሽን ነግረሽኛል ። ልቤ ውስጥ ያለው ፍርሃት ነው— የመሸነፍ ፍርሃት ። ድባቅ የመመታት ስጋት ። ያኔ ቀሰበት ማሰራችን ይፋ የወጣበት ቀን እግብገው ላይ የነበረ ፣ በእንጋገር ዘይቤው ቻርልስተናዊ የሚመስል ፣ ስለደቡባዊያን ድንቁርና በሰጠው አስተያየት ከሞላ ጐደል ትልቅ የጭቅጭቅ ጦርነት አስነስቶ የነበረ ፣ በትሰር የሚባል ሰው ትዝ ይልሻል ? ያሉን ጥቂት የብረት መጨፍለቂያዎች ፣ ፋብሪካዎች ፣ ወፍጮ ቤቶችና መርከቦች ብቻ ናቸው ፣ ብሎ በመናገሩ መንትየቹ ወንድ ማማቾች በጥይት ካሳልነው ብለው ሲጋበዙበት እንደነበር ታስታ ውሻለሽ ? ጥጣችንን ወደ ውጪ ለመላክ መውጪያ መግቢያውን አጥረው ያንኪዎቹ እንደሚያፍኑን የተናገረው ትዝ ይልሻል ? ሰውየው ትክክል ነበር ። እቅጯን ነው የተናገረው ። ያንኪዎቹ የሚዋጉት በአዳዲስና ዘመናዊ የጦር መሣሪያዎች ነው ። ስለዚህ በጥቂት ጊዜ ውስጥ መድኃኒት እንኳ እንዳናስገባ መፈናፈኛ ሊያሳጡን ይች ላሉ ። የሚሰማቸውን እየተናገሩ ገደል ከሚጨምሩን የጦር መሪ ዎች ይልቅ እንደበትለር ያሉት በእሽሙር ቋስላችንን የሚጠቁሙ ተቺዎች የሚያውቁትን እውነት ሲናገሩ በሰማን ይበጀን ነበር ። አሱ በትክክል እንደገለጸው ደቡቡ ከትዕቢትና ከጥጥ በስተቀር ምንም የሚዋጋበት እቅም የለውም ። ጥጣችን ዋጋ ቢስ ሆኗል ። ከእንግዲህ የሚቀረን ያ አሱ ትእቢት ያለው ነገር ብቻ ነው ። እኔ ግን ያንን ትእቢት እኩያ የማይገኝለት ድፍረት ነው ብዬ ጠር ቼዋለሁ ። እና ምንም ቢሆን . . ."

እስካርሌት ያብዳቢውን ማንበብ በጣም ሰልችቷት በጥንቃቄ አጥፋ ወደ ጎስታው መለሰችው ። በዛ ላይ እየደጋገመ ስለመሸነፍ የሚለፍፈው ጅላጅል ወሬ ስሜቷን አቁዘቀዘባት ። እሷ የሜላኒን ያብዳቢ ሰርቃ የምታነበው እኮ የአሽሌይን እንቆቅልሽ የበዛባቸ ውንና የማይጥሙ ሀሳቦች ለማወት ፈልጋ አይደለም ። ያኔ ታራ በራ ንዳ ላይ ከሱ ጋር ተቀምጣ ስለነዚህ ነገሮች በበቂ ነግሯታል ።

@OLDBOOKSPDF

እሷ ለማወቅ ያህል ያልሆነ ቢሆንም ፍቅሩን ይገልጽላት እንደ ሆነ ብቻ ነው። እስካሁን መቼም ምንም ትንፍሽ አላለ። በደብዳቤ ማስቀመጫው ላጥን ውስጥ ያሉትን እንድም ሳታስቀር አነበበች። ወንድም ለእህቱ ከሚጽፈው ደብዳቤ የተሻለ እንድ እንኳ ለመሀላ የለባቸውም። የሚወዳዳና የሚያስቱ ካንዱ ወደአንዱ ርዕስ የሚዘልሉ እንጂ እንድም ፍቅረኛ ለፍቅረኛ የሚጽፈው ዓይነት ደብዳቤ የለባቸውም። እስካርሴት አስኳሀፌ መጫት ዓይነት የፍቅር ደብዳቤ ስለ ተጻፈላት ፣ ከልብ የሚፈነቅለ የፍቅር ስሚት ያለበትን ደብዳቤ ገና ስታየው ታውቀዋለች። የዘይ ዓይነት እንድም የለባቸውም። እንደተ ለመደው በድብቅ የእሽሌይን ደብዳቤ ካነበበች በኋላ የሚሰማት የሚ ያጽናናና አርኒ ስሜት እንደሁሉት ጀቦናት። ይሄ ንባብ አሽሌይ አሁ ንም እንደሚያፈቅራት ስለሚያረጋግጥላት ያስደስታታል። እስካርሴት ፣ እቺ ሜላኒ ፡ አሽሌይ እንደተራ ጓደኛ እንደሚወዳት እንዴት አትገነ ዘብም ብላ እንደውልጊዘው ተገረመች። በእርግጥ ሜላኒ ግን ከባሏ ደብዳቤ መልእክት ውስጥ ምንም የሚያድልባት ነገር የለም። ዳሩ ሜላኒ የአሽሌይን የፍቅር ደብዳቤ ከሌሎች ጋር እንዳታወዳድር ሌላ ጥቅርም ሆነ ሌላ ፍቅረኛ ከታመቅ ፡ ከየት ታምጣ።

"ምን ዓይነት የእብድ ደብዳቤ ነው የሚጽፍላት" አለች አስካ ርሴት በልቧ። "አኔ መቼም ባሌ እንዲህ ያለ አርቲ ቡርቲ ነገር ቢጽፍልኝ አፍንጫው ድረስ ነው የምነግረው ! እንዴ ፡ ቻርሊ እንኳን ከዚህ የተሻለ ደብዳቤ ይጽፍ ነበር።"

ደብዳቤዎቹን [illegible] ጠርዝቸው ላይ የተጻፈ ቀናቸው ንና ያዘታቸውን ለማ[illegible] ከየ ኮመለከትች ተራ በተራ ወደፓ ስታው መለሰቻቸው። ፡ ፓ ዳርሲ ሚድ ለቤተሰቡ እንደሚጽፋቸው ወይም ያ ምስኪኑ ጴላስ ማክለር ለነዛ ለሞርንቄሳም እሀቶቹ ለወይዘ ሪት ሬይዝና ሲፎት ሆኖ እንደሚጽፋቸው ያሉ ፡ አዲስ የጦር ሰፈር ሲከተም ስለሚደረገው እንቅስቃሴና ስለወታደራዊ ሕግጋት የሚያ ወሱ እንድም የለባቸውም። የሚደና የማከለር ቤተሰቦች በየመን ደሩ ስለ እነዚያ ደብዳቤዎች ሲያወሩ ይውላሉ። እስካርሌት እንዲህ ያለ በስፈት ከበብ ለንበብ የሚችል ዓይነት ደብዳቤ አሽሌይ ለሜላኒ የማይ ጽፍላት መሆኑን አስባ እንደማሪር አለች።

አሽሊይ ለሜላኒ የሚጽፈው ደብዳቤ ላይ ስለጦርነቱ ምንም ነገር ካለማንሳቱ የተነሳ ፎርት ሰምተር የዘመኑ ወሬ ከሆነበት ቀን ጀምሮ ያለውን የጦርነት ታሪክ ቸል የሚልና ጊዜ የማይገድበው በሁለቱ ሠሪያ ብቻ የሚሰመር ከብ መስመር ለማስመር የሚፈለግ ይመ ስላል። ከሞላ ጎደል መርነት የለም የማለት አዝማሚያም ያለው

@OLDBOOKSPDF

ይመስላል ። እሱና ሚላኒ ስላነበቧቸው መጻሕፍት ፣ ስለዘፈኗቸው ዘፈኖችና አብረው ስለጠየቋቸው የዱሮ ጓደኞች እንዲሁም በታላቁ ሽርሽር ወቅት ስለሄዱባቸው ቦታዎች ይጽፋል ። ወደ "አሥራ ሁለቱ ዋርካዎች" መንደር ተመልሶ ለመሄድ ያለውን ጽኑ ጉጉት ይጽፋል ። አብዛኛዎቹን ገጾች የሞላው ግን ስለአደን ፣ በዝምተኛዎቹ ጫካ ዎች ውስጥ አቋርጦ ስለሚሔድበትና በሀጋይ ወቅት እጭጋግ ውስጥ ካሉ ከዋክብት ሥር ስለሚገዘው የፈረስ ጉዞ ፣ ስለ ግብዣዎቹ ፣ ስለዓሣ ጠመዳ ፣ ስለዐጥቂኞቹ በጨረቃ ብርሃን የፈኩ ምሽቶች ፣ የዮንቱ ቤቱን ለዛና ውበት ፣ በመጻፍ ነው ።

አሁን ባነበበችው የመጨረሻ ደብዳቤ ውስጥ ያሰፈራቸውን ቃላት አስታወሰች፡- "እኒያ ሁሉ አልፈው ይሄ ወቅት መጣ ! በጭራሽ ይመጣል ያላልነው ይሄ ወቅት መጣ !" መጋፈጥ ያለበትና መጋፈጥ ያልቻለው ነገር ነፍሱን ቪ ቢታ ያቆሰላት ይመስላል ። ጨክኝትና ወዮታ የሞላባቸው ቃላት ይሯሯጡበታል ። መቁሰልንና መሞትን ካልፈራ ምንን ሲፈራ ነው ታዲያ ? ብሳ ነገሩ እንቆቅልሽ ሆነባት ። ለራሷ ነገርን መተንተን አይሆንላትም ከዚህ እግርና እጅ ከሌለው ድፍንና ውስብስብ ሀሳብ ጋር ትግል ገጠመች ።

"ጦርነቱ ረብሾታል . . እኖ . . እሱ . . እሱ ደግሞ የሚረብሸውን ነገር አይወድም . . እኔን ለምሳሌ ያፈቅረኛል ግን እንዳያገባኝ አስተሳሰቡንና የአኗኗር ዘይቤውን እንዳላዛባበት ይፈራል ። የለም ፣ በእርግጥ ፈርቶ እንኳን አይደለም ። አሽሌይ ፈሪ አይደለም ። ደሞ ሊሆንም አይችልም ። በየጋዜጣው ሁሉ ስሙ ሲጠቀስና ኩሎኔል ስሎን ራሱ ለሚላኒ በጻፈው ደብዳቤ ስለአሽሌይ ቆራጥነትና የመምራት ችሎታ ተናግሮ የለ እንዴ ። እንድ ጊዜ አንድ ነገር ለ መሥራት ቆርጦ ከተነሳ አኮ እንደሱ ጀግና እንደሱ አይበገሬ የለም ። ነገር ግን . . . በሰፊው የውጪ ዓለም ከመኖር ይልቅ በራሱ ጭንቅላት ጎጆ ቤት ውስጥ መኖርን ይወዳል ። ወደ ዓለም ብቅ ማለት ያስጠላዋል ። እናም . . . ኤጭ ምን እንደሆነ በጭራሽ አይገባኝም ። ይህንን ጉዳይ ገና ከዓመታት በፊት ተረድቼ ቢሆን ኖሮ እንደሚያገባኝ አውቅ ነበር ። "

ስለአሽሌይ በናፍቆት እያሰበች ደብዳቤዎቹን እደረቷ ላይ ይዛ ለትንሽ ጊዜ ቆመች ። መጀመሪያ ከሱ ጋር ፍቅር ከያዛት ቀን ጀምሮ እስካሁን ድረስ ስለሱ ያላት ስሜት አልተለወጠም ። ያኔ ፣ ገና በአሥራ አራት ዓመቷ እታራ በረንዳ ላይ ቆማ ፣ አሽሌይ በፀሐይዋ ብርሃን ፀጉሩ እንደብር እያብረቀረቀ በፈገግታ እየጋለበ ሲመጣ ያየችው አለት የተለከፈችው የፍቅር ልክፍት ዛሬም ቅንጣት አል

@OLDBOOKSPDF

ተለወጠም ። ፍቅሯ ፣ ልትረዳው የማትችለውን ወንድ ያፈቀረች ልጃገረድ ዓይነት ፍቅር ነበር ። ያ ፍቅሯ እሷ የሌላትንና የምታደንቀውን ግሩም ባህሪ የተጎናጸፈን ወንድ ያፈቀረች ልጃገረድ ዓይነት ፍቅር ነበር ። ያኔ እሱ ፣ ማንም ወጣት ሴት ፍፁም ሙሉ ወንድ ብላ የሀልሚና የምኞቷ ማረፊያ የምታደርገው ሰው ነበር ። የልጅነት ልቧ ይጠይቀው የነበረውም ጥያቄ ፍቅሯን እንዲያረጋግጥላት ብቻ ነበር ። ማረጋገጫው ደግሞ እንዲስማት ተስፋ ከማድረግ የበለጠ ርቆ አይሄድም ።

ደብዳቤዎቹን ካነበበች በኋላ እንደሚያፈቅራት አርግጠኛ ሆነች ። ምንም እንኳ ሚላኒን ያገባ ቢሆን እሷ የምትፈልገው ይሆን ማረጋገጫ ብቻ ነበር ። አውንም እንደዱሮዋ ሰጋ ፣ እንደዱሮዋ ወጣት ናት ። ያ ቻርለስ በእርብትብት ቅጥየለሽነቱና በተደናገጠ አቀራረቡ በሷ ውስጥ ያለች እንዲት የፍቅር ደም ሥር እንኳ ነክቶ ቢሆን ኖሮ ፣ ፍቅራቸው ለአሽሊይ ያላት ሕልም አስኪሰማት ብቻ አደሆንም ነበር ። ነገር ግን በዚያ ጥቂት የጨረቃ ምሽቶች አብራው በተቀመጠች ጊዜ ቻርለስ የፍቅር ስሜቷን ቅንጣት ታህል እንኳ አልቀሰቀሰባትም ። ስለዚህም ብስለቱን እግኝታ የፍቅር አዋቂነቱንና የመውደድ አስተዋይነቱን ለማዳበር አላስቻላትም ። ቻርለስ የፍቅርን ስሜት ፣ የመዋደድንም ሆነ የዕውነተኛ ጓደኝነትን ሀሳብ በስጋም ሆነ በመንፈስ ሊቀርጽባት ቀርቶ አክክ እንዲያደርጋት ሊያደርግ አልቻለም ።

እንግዲህ ለእስካርሌት የፍቅር ስሜት ማለት ለማይገባትና ልትገልፀው እንዲሁም ልትጋራው ለማትችለው የወንድ ፅበደት ተገዢ መሆን ማለት ነው ። ለሷ የፍቅር ስሜት ማለት በጣም የሚያምና የሚያበሳጭ ውሰ አድሮም ወደ ባሰውና ወደሚያደክመው ልጅ የመውለድ ሕመም የሚሰድ የሕይወት መንገድ ማለት ነው ። ትዳር እንደዚህ መሆኑ ለሷ የሚገርማት ነገር አይደለም ። ኤለን ገና ከሠርጉ በፊት ፣ ትዳር ፣ ሴቶች በክብርና በወግ ሊሸከሙት የሚገባ ነገር መሆኑን ትነግራት ነበር ። ሌሎች ሞግዚቶችም ከሷ የሙት ሚስትነት ወዲህ በሹክሹክታ የሚሰጡት አስተያየት ይሄንኑ አረጋግጦላታል ። እስካርሌት የፍቅርንና የትዳርን ጣጣ ማለፍ ደስስ ይላት ነበር ።

ትዳርን አልፋለች ። ፍቅርን ግን ገና እያዘገመችበት ነው ። ይህ የሆነበት ምክንያት ለአሽሊይ ያላት ፍቅር በጣም ለየት ያለ ስለሆነ ነው ። ለሱ ያላት ፍቅር የመውደድን ስሜትም ሆነ የትዳርን ሕግ የሚጥስ ነው ። ለሱ ያላት ፍቅር ፣ የተቀደሰና ውበቱ ትንፋሽ አስ

@OLDBOOKSPDF

ጨራሽ የሆነ ነው ። ለሱ ያላት ፍቅር ፣ የጥንት ትዝታንና ተስፋን እየተመገበ ፣ የግዷን በተጫኑባት የዝምታ አዝጋሚ ቀናት ውስጥ እየተ ንገዳገደ ያደገ ትኩስ ስሜት ነው ።

አስካርሌት ለአንድ ሺኛ ጊዜ አሽሌይ ሰምን አይገባኝም እያ ለች በመገረም የደብዳቤዎቹን ከምችት በጥበጣበ አሰረች ። ጉዳዩን አንድ አጥጋቢ ምክንያት እስከምታገኝ ድረስ ለማብሰልሰል ሞከ ረች ። ነገር ግን እንደሁልጊዜው ግልጽና ቀጥተኛው አእምሮዋ ውሰ ብስቡን ጥያቄ ማለጥ እንጂ መፍታት አቃተው ። ደብዳቤዎቹን መልሳ ሳጥኑን ዘጋችው ። ድንገት ሽምቅቅ አለች ። አእምሮዋ ደብዳ ቤው ላይ በመጨረሻ ወዳነበበችው ነገር ተመለሰ ። የካፒቴን በትለርን ስም ማንሳቱ ትዝ አሳት ። ያ የማይረባ ሰው ከአንድ ዓመት በፊት የተናገረውን ነገር እንዴት አሽሌይ ሊደነቅበት ይችላል ። ምንም ጉበዝ ደናሽ ቢሆን ያለጥርጥር ካፒቴን በትለር የማይረባ ሰው ነው ። ያንን ባዛሩ ላይ ስለኮንፌደሬሲው የተናገረውን ነገር መቼም ማንም የማይረባ ርካሽ ሰው እንጂ ጨዋ አይናገረውም ።

ከፍሉን አቋርጣ መስታወቱ ወዳለበት ሄዳ የፀጉሯን ውበት ለማየት ያህል ላማ ላማ አደረገችው ። ሁልጊዜ መስታወት ፊት ቆማ የራሷን መልክና ገደም ያሉትን እንዶ ኩል የጠሩ ዓይኖቿን ስታይ እንደምታደርገው ሁሉ መንፈሷ መጋለብ ጀመረና የጉንጯን ስርጉድ ለማውጣት ፈገግ አለች ። እነዚህን የጉንጯን ስርጉዶች አሽሌይ እን ዴት እንደሚወዳቸው አስባ ካፒቴን በትለርን ከአእምሮዋ ገፍታ አስወጣችው ። በዚህ ወጣትነቷ ፣ በዚህ ሰጋ ቁንጅናዋና የአሽሌይ ፍቅር መታደሱን ባረጋገጠላት ስሜቷ ውስጥ የተፈጠረ ደስታዋን የሌላ ሴት ባል የማፍቀርም ሆነ የሴትዮዋን ደብዳቤ ሰርቃ የማን በብ የሕሊና ወቀሳ አላደፈረሰባትም ።

በሩን ከፍታ በደብዛዘው ጠመዝማዛ ደረጃ ስትወርድ ልቧን ቀለል ብሏታል ። ግማሽ መንገድ እንደወረደች "አስከፊው ጦር ነት ሲያበቃ" የሚለውን ዘፈን መዝፈን ጀመረች ።

@OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ 12

ወርኑቱ በእብዛኛው አየተሰበሰበ ተጥሷል። ሆኖም ሰዉ ያንኪዎች ፈሪዎች ናቸው የሚለውን አባባል እንደተወ ሁሉ "እንዴ ድል ከመታን ወርኑቱ ያነቅሳል" ማለቱንም ትቷል። አሁን ያንኪዎቹ ፈሪ እንዳልሆኑም ሆነ ወርኑቱም በእንድ ድል ብቻ እንደማይነቃ ለሞንም ግልጽ ሆኗል። ለሚንኛውም በጂኤራል ቸርጋንና በጂኤራል ሮሰክራ መሪነት የኮንፌዴራሲው ወታደሮች ሁንሲ ላይ ድልን ተጐናጽፈዋል። በዚህራን በሰቲኛ ወርኑት ላይም ያገኙት ድል የያንኪ ሞንቅላት ይዘው የሚዘራበት ዓይነት ነው። ሆኖም እንዚህን ማዳይ የተጣሉ ሞንቅላቶች ከፍ አድርጎ ለማሳየት ከፍተኛ የሕይወት ዋጋ ተከፍሏል። የእሳሰንታ ሆስፒታሎችና መኖሪያ ቤቶች በበሽተኞችና በቁስለኛ ተሞልተዋል። ጥቁር የሚለብሱ ቤቶች ቁጥር ከቀን ወደ ቀን እየጨመረ መጥቷል። በእክላንድ የመታብር ቦታ ላይ የሚደረደረው የመታብር መሸመር ክሩለት ወደ አለት ዓይን አስክሚያደክም ድረስ እየረዘመ ሂዷል።

የኮንፌዴሬሲው ፕንዘብ ምንዛሪ በጣም ዝቅ እያለ የምግብና የልብስ ዋጋ ደግሞ በዚያው መጠን ሽቅብ እየናረ መጥቷል። የኮሚ ሳሪያት ጽ/ቤት በምግብ ሸቀጣ ሸቀጥ ላይ ከፍተኛ ግብር በመጠ የቁ የእሳሳንታ ግበታዎች እየተራጩ ነው። የፋርኖ ጹቂት ጠፍ ቷል። ከተግነያ በጣም ውድ ነው። በብስኩትና በኬክ ፋንታ የበ ቆሎ ቂጣ መብላቱ በድፍን አገር ተለምዷል። የሥጋ ቤቶች ማን ጠልጠያዎች የበሬ ሥጋ ካዩ ሰንብተዋል። የዘማ ሥጋም እንደዚሁ ላመል የተንጠለጠለ ቢገኝ ነው። የተገኘውንም ሲገዙ የሚችሉት ሀብታሞች ብቻ ናቸው። ብቻ ደግሉ በርከት ያለ የእሳማና የጫ ጨት ሥጋ እንዲሁም ቅጠላ ቅጠል መኖሩ ነው።

በባህር ወደቦች አካባቢ የያንኪዎች የዕቃ እገዳና ቁጥጥር በጣም ጠብቋል። እናም እንደሻይ ቅጠል፣ ቡና፣ የሐር ጨርቅ፣ ሽቶዎች የራሽን መጽሐፍችና መጻሕፍት ያሉ የቅንጦት ዕቃዎች በጣም ውድና የማይገኙ ነገሮች ሆነዋል። የመጨረሻ ርካሽ የሆነው የጥጥ ልብስ ዋጋው ሰማይ በመነካቱ ሰዎቹ ያለታ ልብሳቸውን ለሚመጣው ዓመት እንዲሆናቸው ጣጥፈው ለመጠቀም በወዘን መስነዋል። ሽረራት ድር ያደራቸው የሸማኔ ዕቃዎች ከየጓራንጉሩ እየተፈለጉ እየወጡ ከሞላ

@OLDBOOKSPDF

ጐደል የእያንዳንዱ መኖሪያ ቤት አልፎኝ የሸማኔ ጉድጓድ ሆኑዋል። ወታደሮች፡ ሲቪሎች፡ ሴቶች፡ ሕፃናትና ኤግሮዎች እያንዳንዱ ሰው የቤት ሽመና ፋብሪካ ያወጣውን ልብስ ለመልበስ ተገዷል። የኮን ፌዴሬሲው ዩኒፎርም ግራጫ ቀለም፡ አውን ከናካቴው ጠፍቶ የቤት ሽመና ያፈራው ነጣ ያለ ልብስ ቦታውን ተክቶታል።

ገና ካሁኑ ሆስፒታሎች የኪኒን፡ የክሎሮፈርምና የአዮዲን እጥረት እያስጨነቃቸው ነው። ከጥጥ የተሠሩ ፋሻዎች በጣም ውድ ከመሆናቸው የተነሳ አንዴ የተጠቀሙበት ፋሻ የማይጣልበት ደረጃ ተደርሷል። በሆስፒታል ውስጥ የሚሠሩት ሴቶች ብዙ በደም የተበከሉ የፋሻ ቁርጥራጮችን በዘመቢል እየ ሞሉ ወደቤታቸው በመውሰድ እጥበው ተኩሰው ደሞ ለሌሎች ስቃይተኞች መጠቀሚያ ያደርጓቸዋል።

ገና ከሀዘን ክል ውስጥ ወጥታ አዲስ ሰተፈጠረችው ለእስካር ከርሌት እግራ ግን አውን ቁርኑቱ የሚሰጣት ትርጉም ቢኖር መደ ሰትና መፈንደቅ መቻሏን ብቻ ነው። እንደገና ወደ ዓለም በመመ ለሷ ባገሩ የሰፈነው የልብስና የምግብ ችግር አላበሳጫትም።

እስካርሌት አንደኛው አሰልቺ ቀን የሌላው ቀን ትክክለኛ ግልባጭ እየሆነ የጎሳደበትን፡ ያለፈውን ዓመት ጉታታና ደብዛዛ ትዝታ እስታውሳ ያሁኗ ሕይወቷ በከፍተኛ ጥድፊያ ላይ መሆኗን አሰበች። ዛሬ እያንዳንዷ ቀን በስሜት ሰተሞላ ጀብዱዋ ጉጎ መቅ ደኟ ሆናላታለች። ዛሬ እያንዳንዷ ቀን፡ የሚጋብዟትን አዳዲስ ሰዎች የምታገኝባት፡ እንዴት ቆንጆ እንደሆነች የሚነግሯትን ወንዶች የምታጫውትባት፡ ለቢ ቢሱ መታገልና ምናልባትም አስፈላጊ ከሆነ መሞት ትልቅ መብት ነው ብለው የሚምሉላትን ሰዎች የምታና ግርባት ናት። አሽሌይን በመጨረሻዋ አስትንፋሰዋ ልታፈቅረው ትችላለች፡ አጥቅራውማለች። ሆኖም አሱን ማጥቀሯ ሌሎች ወን ዶች አናግባሽ እያሉ ደጅ እንዲጠኗት ከማድረግ አያግዳትም።

ለመቼም የማይቆመው ጦርነት ከጀርባ ሆኖ እየገፋፋቸው ማኅ በረሰባዊ ግንኙነቶችም ሁሉ ወግና ሰባቸውን አጡ። እኒህን ለዛ ቢስ ግንኙነቶች ሽምገል ሽምገል ያሉት ሰዎች ጠልተዋቸዋል። እናቶች ብዙ ባይተዋርና ዘር ነገጸቸው የማይታወቅ ወንዶች ማንነ ታቸውን ሳያሳውቁ ሴት ልጆቻቸውን ሲያናግሩ ደርሰውባቸዋል። እንዲያውም እጅ ለእጅ ተያይዘው እይተዋቸው በድንጋጤ ነብሳ ቸው ልትወጣ ደርሳለች። ወይዘሮ ሚሪዊዘር፡ ለራሳቸው ከሠርጋቸው ቀን በፊት የገዛ ባላቸውን ስመው አያውቁ፡ ሴት ልጃቸው ሜይ ቤል ከዚያ ከዝንጀሮ ፊቱ ከራኔ ፒካርድ ጋር ስትሳሳም ይዘዋት

@OLDBOOKSPDF

ዓይናቸውን ማመን አልቻሉም። ሚይቢል በነገሩ አጥራ ክባር ትጠ
ፋለች ብለው ሲያስቡ እሷ ምንም ነውር እንዳሌለበት ሁሉ በሠራ
ችው ሥራ ሳታፍር ስትቀርማ ጭራሽ ትንፋሽ አጠራችው። ሬቴ
ልጅዎን ይጸሩልኝ ብሎ በትሕትና መጠየቁ እንኳ ሁኔታውን ሊያሻ
ሽልላቸው አልቻለም። ወይዘሮ ሜሪዌዘር ደበቡ ከፍተኛ የሞራል
መንኮታኮት እየደረሰበት መሆኑ ተሰምቷቸዋል። አንዳንዴም አስው
ፈት በይፋ ይናገሩታል። ሌሎች እናቶችም ከሳቸው ጋር በመስማማት
ለዚህ ሁሉ ጦስ የሆነው ጦርነቱ መሆኑን አውስተው ይደመድማሉ።

በወር ወይም በሳምንት ጊዜ ውስጥ ምትን የሚጠባበቁ ወን
ዶች አንዷን ልጃገረድ ወ/ት የሚል ቅጽል አስሚ ላይ ጨምረው
ሳይለምኗት ለአንድ ዓመት መክረም በጭራሽ አይችሉም። ከጦር
ነቱ በፊት ይጠኑመቡት የነበረውም ሴትን የማጫወትና የማግባባት
ጨዋ ልማድ አሁን ጋጠ—ወጥ ሆኗል። በሦስት በአራት ወር ጊዜ
ውስጥ ዓይን አውጥተው ላግባሽ ይሳሉ። ሴቶቹም ወንድ ለወዳጅ
ነት ሲጠይቃቸው አስክሶስተኛው ጊዜ ድረስ መግደርደርና መቃ
ወም እንደሚገባቸው አያወቁ ገና በመጀመሪያ ጥያቄ ተንሰፍስፈው
እጅ ይሰጣሉ።

ይሄ የማኅበራዊ ግንኙነት መዛባት ለእስካርሌት ጦርነቱን እንደ
ጥሩ መገናኛ እድርገሳታል። ቁስለኛ ማከምና ፋሻ መጠቅለ
ሉን ከመሰልቸቷቷ በስተቀር ጦርነቱ አስክ ዘለዓለም ቢቀጥል አሁን
ግድ የላትም። በእርግጥ የሆስፒታሉን ነገር በረጋ አእምሮ እንድታይና
እንድትታዘብ ያደረጋት፥ ሆስፒታል ጥሩ የወንድ ማደኛ ቦታ ስለሆነላት
ነው። እነዚያ ረዳት የለሽ ቁስለኞች ያለአንዳች ትግል የደምግባቷ
ተገዢ ይሆኑላታል። ፋሻቸውን መቀየር፥ ፊታቸውን ማጠብ፥ ትራሳ
ቸውን ማመቻቸትና በማራገቢያ ማናፈስ ብቻ ይበቃታል፤ ወዲያው
በፍቅር ይወድቃሉ። አቤት ካለፈው አስፈሪ ዓመት በኋላ ይሄ እንዴት
ያለ ገነት ነው በሉ።

እስካርሌት ቻርለስን ከማግባቷ በፊት ወይንበረችበት ሁኔታ ዳግም
ተመለሰች። ከነጭራሹም ቻርለስን እንዳላገባችው፥ መሞቱ የሐዘን ድን
ጋጤ ላይ እንዳልጣላትና ዋድን እንዳልወለደች መሰለች። ጦርነት፥ ትዳ
ርና ልጅ መውለድ እውስጧ ጠልቀው አንድም የስሜት ደም ሥር
ሳይነኩ ያለፉ ስለሆነ ምንም አልለወጧትም። ልጅ አላት። ነገር
ግን በቀዩ ሸክላ ቤት ውስጥ የሚኖሩት ሰዎች በሚገባ ስለሚንከባ
ከቡት ልትረሳው ምንም አልቀራትም። በሥጋም በነብስም የጥንቷን
እስካርሌት እሪ መሆኗ ታያት—የመንደሯ ቆንጆት። ሃሳቦቿና ድርጊ
ቶቿ ሁሉ እንደዚያው እንደጥንቱቹ ቀናት ሆኑ። ሆኖም የእንቅስ

@OLDBOOKSPDF

ቃሴዋ መስክ አሁን በጣም ሰፍቷል ። ምንም እንኳ የወ/ሮ ፒቲፓት ወዳጆች ደግ አይደለም ፡ ሰብሰብ በይ ቢሏት ከሠርጓ በፊት ታደርግ እንደነበረው ማድረጓን ቀጠለች ። ፓርቲ ስትጋበዝ ትሄዳለች ፡ዳንስ ትደንሳለች ፡ከወታደሮች ጋር ፊረስ ግልቢያ ትሄዳለች ፡ ትሳፋለች ። ብቻ በልጃገረድነቷ ትሠራው የነበረውን ሁሉ ትሠራለች—ጥቁር ከመልበሷ በስተቀር ። ይሄ አድራጐቷ የፒቲፓትንና የሜላኒን ቅስም የሚነካ መሆኑን ታውቃለች ። በልጃገረድነቷ በደም ግባቷ ትማርክ እንደነበር ሁሉ አሁንም ማራኪ ሆናለች ። በልጃገረድነቷ ራሷ በመ ረጠችው መንገድ ትሄድ እንደነበር ሁሉ አሁንም ያንኑ በመ ከተል ትደሰታለች ። ዝነኛነቷንና የመልኳን ማማርም እንደልጃገረድ ነቷ ታዝበታለች ።

ከጥቂት ሳምንታት በፊት ተጭሳቁሳ የነበረችው እስካርሌት አሁን በመዳኗ ብዛባና አድናቂዎቿን እየሰማች ሜላኒን አማብ ቶና አዶን ላይ ወድቆ ካለው አሽሌይ ጋር ብትሆን የምታገኘውን ደስታ ተገናጽፋለች ። ብቻ እንዴት እንደሆነ እንጃ አሽሌይ የሴላ ሴት ባል የመሆኑን ሃሳብ አሱ በሌለበት መሸከም ይተላል ። ደሞም በአትላንታና በቨርጂኒያ መሀከል በመኖ ማይል የሚቆጠር ርቀት መኖሩን ስታስተውል አሽሌይ የሚሳኒ የሆነውን ያህል የእሷም እን ደሆነ ይሰማታል ። ለሀሰት የሚጋሩትም ይመስላታል ።

በዚህ ዓይነት የ1862 የሠጋይ ወራት በነርስ ሥራ ፡ በጻንስ ፡ በፊ ረስ ግልቢያ ፡ በፋሻ ጥቅለላ እንጁተሞሉ በጥጥነት ሄዱ ። እስካርሌት ለአጭር ጊዜ እናቷን ጥየቃ ወደ ታራ ሄዳ ነበር ። ይህ አጭር የዘመድ ጥየቃ ጊዜ እስከዚህም አላስደሰታትም ፡ ምክንያቱም አትላንታ እያ ለች በጣም ትናፍቃት የነበረችው እናቷን ለረጅም ሰዓት እንድታና ግራት ሰደል ስላሳገኘች ነው ። እንዲድሮው ኤለን ስፈት ስትሰፋ እንኗ ተቸምሰ በተንተሳቱሰች ሎጥር ከተሚስጥ የሚወጣውን የለመ ሽታ ማሽተት አልተቻለም ። በቀስታ የእስካርሌትን ጉንጭ ቆንጠጥ አድርጋ ስታልፍ ትሬጥር የነበረውንም አስደሳች ስሜት ማግኘት አልተቻለም ።

ዛሬ ኤለን ከጠዋት ጀምራ የአርሻው ጎብረተሰብ እስከሚያ ሳላፋበት ሰዓት ድረስ ወዲህ ወዲያ ስትል በሥራ ተጠምዳ ትውላለች። ከስታለች ። የኮንፌዴሬሲው ከሚሳሪያት የሚያቀርበው የጥጥ ጥያቄ በየዕለቱ እየበዛ በዚህ ወር በጣም አጨናንቋታል ። ታራ እንድታመ ርት ያለባትን ግዴታ የተቭከመችው ኤለን ናት ። ጀራልድ አራሱ እንኳን በሥራ ተወጥሯል ። ከበዙ ዓመታት በኋላ ዘንድሮ በሥራ ተጠመደ ። የምስለኔውን የጀናስ ዊልከርሰንን በታ የሚተካለት ስው

@OLDBOOKSPDF

ስላላገኝ የሚሯሯጠው ራሱ ነው ። እስካርሌት ኤለንን የምታገኛት ደህና እያረ ብላ ለመሳሳም ብቻ ነው ። ጂራልድም እርሻ ውስጥ ነው የሚውለው ። ስለዚህ ታራ ለልችት አለቻት ። ሌላው ቀርቶ እህቶቹ አንኳ የየራሳቸውን ጉዳይ ይዘው ከፒ. ጋር የመጫወቻ ጊዜ አላገኙም ። ሱዌለን ከፍራንክ ኪኬዲ ጋር "እመግባባት ደረጃ" ስለደረሰችና "አስ ከፊው ጦርነት ሲያበቃ" ን መዝፈን ስለጀመረች እስካርሌትን ትሰለቻ ታለች ። ካሪንም በብሬንት ታርሌተን ህልም ተጠቅልላ ስለምትውል ጥሩ አጫዋች ልትሆንላት አልቻለችም ።

እስካርሌት ምንም እንኳ በየጊዜው ወደታራ ስትሄድ ከፍተኛ ደስታ ቢሰማት : ወ/ሮ ፒቲና ሚላኒ ወደ አትላንታ እንድትመለስ ደጋግቢ ሲጽፉላት ቅር ሳይላት ትመለሳለች ። ኤለን ደግሞ የበኩር ልጅዋና የልጅ ልጅዋ ከአጠገቧ ሲሄዱባት ይከፋታል ።

"አትላንታ ሆስፒታል ውስጥ ስንርስነት እየተፈለግሽ እኔ ዘንድ ቅሪ ማለት ራሴን መውደድ ይሆንብኛል ።" አሰች ኤለን ። "ብቻ . . . ብቻ የኔ ቆንጆ በጣም በሥራ ስለተጠመድኩኝ ጊዜ አግኝቼ ሳላጫ ውትሽና ናፍቆቴን ሳልወጣ ተመልሰሽ መሄድሽ በጣም ተሰምቶኛል"

"ሁልጊዜም ያንቺው ነኝ" ትላለች እስካርሌት ፤ ራሷን ኤለን ደረት ላይ ቀብራና ጎልናሞ ሊወቅሳት እየጀመረ ። ወደ አትላንታ እን ድትመለስ የሚያደርጋት ኮንፌዴሬሲውን ለማገልገል ያላት ፍላጎት ሳይሆን ዳንስና ቆንጆዎቹ የአትላንታ ወንዶች መሆናቸውን ለእናቷ አልነገረቻትም ። ዛሬ ጊዜ ከእናቷ የምትደብቃቸው ነገሮች እየበረከቱ መጥተዋል ። ከሁሉም በላይ ግን በትለር ወይዘሮ ፒቲፓት ቤት ድረስ እየመጣ እንደሚጠይቃት አለመናገሯ ዋነኛው ሚስጥር ነው ።

* * *

ከባሃሩ ድግስ በኋላ በተከታታይ ወራት ሬት ከተማ ውስጥ ካለ፡ እስካርሌትን ይጠይቃታል ። በሠረገላ ያንሸራሽራታል ። ዳንስ ቦታ ይወ ስዳታል ። ባህር ሲደግስም አብሯት ይዝናናል ። ከሥራ ስትመለስ ከሆ ስፒታሉ ደጃፍ እየጠበቀም ወደቤቷ ይመልሳታል ። ከእንግዲህ ሚስተ ሬት ያጋልጥብኛል የሚለው ስጋቷ ተወግዶላታል ። ያም ሆኖ ግን ከአሽሊይ ጋር የሆነችውን ነገር ያየና በመጨረሻ የውርደቷ ሰዓት የነበረ እማኝ በመሆኑ ከኅሊናዋ ጓሮ አንድ የሚቆረቁራት ነገር አለ ። ስላም ያሳጣታል ። ባበሳጫትና ባናደዳት ቁጥር ሁሉ ምላሷን ሰብሰብ እንድ ታደርግና በስድብ እንዳትወርድበት የሚያደርጋትም ይሄው ሚስጥ ሯን ማወቁ ነው ። ሲያበሳጫት ደግሞ ልክ የለውም ።

@OLDBOOKSPDF

በሠላሳ ዕድሜ አጋማሽ ላይ ያለ በመሆኑ ከሌሎች አፍቃሪዎቿ ሁሉ ጠና ያለ ነው። ስለሆነም በራሷ ዕድሜ አካባቢ ያሉትን ወንዶች እንደምትይዛቸው አድርጋ እሱን እንዲልሷ ለመግራት አልቻለችም። በሱ ዓይን እንደሕፃን ልጅ ናት። በሕይወቱ አንድ ጊዜም የሚያስደንቀውና የሚያስገርመው አንዲሁም የሚያገናናው ነገር ያጋጠመው አይመስልም። እሷን አበሳጭቶ ስትናደድ የምታደርገውን ሲያይ ግን የሚገረምባት ይመስላታል። እንደውም በዓለም ላይ እንደሷ የሚያስደንቀው ማንም የሌለ መስሎ ይሰማታል። በጥበቡ እየተነኮሰ ንዴትን ሲጭርባት ምንም ከኢለን የወረሰችው ሁሉን ውጠ ጭጭ የሚል ፊት ቢኖራት የጂራልድ እየርላንዳዊ ደም ከውስጧ ቶሎ ገንፍሎ ሰለሚወጣ ባንዴ ቱማ ብላ አራስ ነብር ትሆና ለች። ለዛውም ካሁን ወዲያም በኢለን ፊት ካልሆነ በስተቀር ራሷን መቆጣጠሩንና ንዴቷን መደበቁን ትታዋለች። ገና ለገና በመግረም ያሾፍብኛል ፣ ገና ለገና ይስቅ ይጎልትብኛል ብላ ልትናገራቸው ያሰበቻቸውን ቃላት በመጠባቸው እግራቸው ወደ ልቧ መመለሱ አልተቻላትም። ደሞኮ እሱም የሚናደድ ዓይነት ሰው ቢሆን ኖሮ ባልከፋ—አጅሬ ንቅንቅ የለም። ስለዚህ ሁልጊዜ ተሸናፊዋ እሷው ናት።

አንዳንዴ ድል ከምታረግባቸው ሙግቶች በኋላ ስድ አደግ መሆኑን ፣ ጨዋነት የምትባል ስንዝር ታህል ጠባይ አውለጡ አለመኖሯን ምንም የማይቻል አስቸጋሪ ሰው መሆኑንና ከእንግዲህ ከሱ ጋር ምንም የምትፈጥረው ነገር እንደማይኖር እየጠቀሰች ልክ ልኩን ነግራ ትለያየዋለች። ነገር ግን ቆይቶም ሆነ ወዲያውኑ ወደአትላንታ ሲመለስ ወይዘሮ ዊቲፓትን በመጠየቅ ስበብ ሲመጣ ከናሱ ድረስ ከጦርነት መንጋጋ ነጥቆ በቆራጥነት ያመጣውን አንድ ባክ ሙሉ ከረሜላ ይዞላት ከች ይላል። አሊያም ሰተት ብሎ ቤቷ ይገባና ወይ የመዚቃ ድግስ ላይ አብራው እንድትቀመጥ ወይም ደግሞ አብራው ዳንስ ቦታ እንድትሄድ ሲጠይቃት እሷም እይጠና ሆዱ ናትና በዓይን አውጣነቱ እየተገረመች ፣ ትላንት የተባባሉትንና የሠራትን ሥራ ረስታ ሌላ ጊዜ እስኪያበሳጭት ድረስ እሺ ብላ ትሄዳለች።

ፊት በትለር ምንም ያህል አስከፊ ጸባይ ቢኖረው እስካርሌት እንዲጠይቃት መፈለጓና መናፈቋ አልቀረም። ተንትናና ተመራምራ ልትደርስበት ያልቻለችው አንድ የሚያስደስት ነገር አለው። እስከዛሬ ከምታውቀው ማንም ወንድ ላይ ያላየችው ነገር እሱ ዘንድ አለ። በሙሉ ቁመናው ላይ የሚታይ ግርማ ሞገሱ ገና ወደቤቷ ሲገባ ቤቱን በድንገት ሕይወት ይዘራበታል። በሞቀ ስሜት ይሞላዋል። በጥቋቁር ዓይኖቹ ውስጥ የሚነበበው የማሾፍ የማላገጥና በድፍረት ዓይን የማ

@OLDBOOKSPDF
ውጣት ባህሪው መንፈሷ እንዲረታና እንድትንበረከክለት የሚያደርግ አንድ ምትዋት አለው ።

"እንደነለክ ያፈቀርኩት ያህል አኮ ነው እሚሰማኝ" ትላለች በልቧ ፣ ግራ በመጋባት ። "ግን ደሞ አሳፈቀርኩትም ። ኤጭ ይሄ ነገር በጭራሽ አይገባኝም ።"

በውስጡ እየጋለ የሚያጭነከንካት ስሜት ግን ጭራሽ እየጠነከረ ጭራሽ እየበረታ መጣ ። ሬት ሲጠይቃቸው ሲመጣ ያ ግዙፍ ወንዳ ወንድ ሰውነቱ የወይዘሮ ፒቲፓትን ያማረ የጨዋ ቤት ትንሽና ዓይን የማይሞላ ያስመስለዋል ። ከቢተሰባቸው አባላት ውስጥ የሱ መምጣት የማድ እንድትቀበለው የሚያደርጋት አስካርሌትን ብቻ አልነበረም ። ወይዘሮ ፒቲፓት እራሳቸው ሳይወዱ እየተርበተበቱ እጃቸውን ከለው ቆይተዋል ።

ወይዘሮ ፒቲ ፣ ምንም እንኳን ኤለን ፣ ሬት ልጅዋን መጠየቁ እንደሚያበሳጫት ቢያውቁ ፣ ምንም እንኳ ከቻርልስተን ጨዋ ጎብረተሰብ የተገለለ ሰው መሆኑን ቢያውቁ ፣ በመጣ ቁጥር የሚያሳያቸው ሰፊ እድፍቅትና እጃቸውንም መሳሙ የማር ማሰሮ እንዳየች ንብ ሊላቀቁት የማይችሉት ነገር ሆኖባቸዋል ። በዛ ላይ በመጣ ጊዜ ሁሉ እንዳንድ ትናንሽ ስጦታ ይዞላቸው ይመጣል ። የሚያመጣላቸውንም ስጦታ ለላቸው አስቦ የገዛላቸው መሆኑንና በጦርነት ማህል ነብሱን ሸጦ ያሳለፈው መሆኑን ሲያረጋግጥላቸው ያ የእሮጊት ልባቸው እንደት ንሽ ልጅ ይጨፍራል ። አስፕል ፣ መርፌ ፣ መርፌቁልፍ ፣ የልብስ ቁልፎች ፣ የሐር ክርና የጸጉር ማስያዣ በየዓይነቱ ያመጣላቸዋል ። በአሁኑ ጊዜ እነዚህ ትናንሽ ነገሮች እንኳ የትንጦት ዕቃ ሆነዋል ። ሴቶቹ ጸጉራቸውን የሚያስይዙት አኮ ከእንጨት በተሠራ ጸጉር ማስያዣ ነው ። ለልብስ ቁልፍም የሚጠቀሙት እንጨት በጨርቅ እየጠመጠሙ ነው ። ታዲያ ወይዘሮ ፒቲ እነዚያን ስጦታዎች ላለመቀበል ምን ሐሞት ይኖራቸዋል ። በዛ ላይ የተጠቀለለ ነገር ሲያዩ ለመክፈት ችኩላቸው እንደሕፃን ልጅ ነው ። መቼም አንዴ ከከፈቱት ደግሞ ውስጡ የሚያዩት እምቢ የሚሉት ነገር አይደለም ። ስጦታውን ከወሰዱ ደግሞ ሰጪውን ፣ ወንድ እሉለበት የሦስት ሴቶች ቤት መምጣት ባለጌ ነህ ብለው መጥፎ ስሙን አስታውሰው ውጣልኝ እንዳ ይሉት ድፍረቱን ያጣሉ—እንዴት ብለው፣ ወይዘሮ ፒቲ ሬት በትለር እቤታቸው ሲመጣ ዘልለው የሚያንቃቸው ይመስል ሌላ ወንድ እጎና ቸው እንዳኖር ይፈልጋሉ ።

"እሱ ሰውዬ እንጀ ከብድ የሚለኝ እንድ ነገር አለው" ይላሉ ሬዳት ያሻናል በሚል የብቸኝነት ታና ። "እንጀ ግን . . . መቼም እልቡ

@OLDBOOKSPDF

ውስጥ ለሴቶች አክብሮት ያለው ጨዋ ሰው ሊሆን ይችላል—ብዬ ባስብ እንኳ ደህና ነበር ። ሆኖም . . . እንጃ ብቻ ። ”

ሚላኒ ተለበቷን ከመለሰላት በኋላ እንደበትለር ያለ ጨዋ ፡ እን ደሱ ያለ ግሩም አስተዋይነት ያለው ሰው በድጥን አገር ሲሄዱ ሲሄዱ ቢውሉ የማይገኝ ነው እያለች በምታስብበት ሰዓት አክስቲ ስለሱ የሰጡት አስተያየት በጣም አስደንጋጭ ። ከሷ ጋር በደምብ ይሟገታል ፡ ይታለዳል ። ሆኖም ከልጅነቷ ጀምሮ የማታውቀውን ወንድ በጣም መቅረብ ስለምትፈራ ትንሽ ጨመት ትላለች ። በልቧ በጣም ታዝንለታለች ። እሱ መቼም ይሄንን ቢያውቅ ተገርሞ ይሞ ታል ። በኑሮ ውስጥ ያጋጠመው አንድ የፍቅር ታሪክ ሕይወቱን እን ጻጨለመበትና ደመ መራራ እንዳደረገው አርግጠኛ ናት ። ስለዚህም እሱን ወደደስተኛ ሕይወት ለመመለስ አንድ በጣም አስተዋይ እና ታሪ ሴት እንደምታስፈልገው ይሰማታል ። የቤት ልጅ ስለሆነች ከፉ ሥራ መሥራት ቸርቶ ከርካቤው መኖሩንም የማታምን በመሆኗ ስለፈት በትለርና ስለቻርለስተናዊቷ ልጃገረድ የሚነግረውን ሐሜታ ስትሰማ ድንጋጤና አለማመን ተረዳድተው ተናነቋት ። ይህ በሱ ላይ የተወራ መሬ ከፍተኛ ሥቡ ሥራ ነው ብላ ስላሰበችም በሱ ላይ ፊቷን ከማዞር ይልቅ በሞምትነቱ ሰጋሥና ጨዋ ልቧን እንድትሰጠው ተገ ደደች ።

አስካርሌት በፀጥታ የወ/ሮ ፒቲፓትን አስተያየት ተቀበለች ። በሷም ሣምት ራት በትለር ለሜላኒ ዘስተቀር ለሴላ ለማንም ሴት አክብሮት የለውም ። በነዚያ ጥቃቅንና እንደመርፌ የሾሉ ዓይኖቹ ከላይ እስከታች አትኩሮ ሲያያት አስካሁን ድረስ እርቃኗ ሥጋዋን የቆመች ይመስላታል ። አልለመደችውም ። አስከዛሬ ምንም የሚያስቅይ ማት ለድብ ሰድቧት አያውቅም ። ያ ቢሆን እንኳ ምላሹን አዘጋጅታ በስ ድብ ድራሹን ታጠፋው ነበር ። የለም ፡ እሷን ያስቸገራት ይሄ በዓለም ላይ ያሉ ሴቶች በሙሉ የሱ ገንዘብ እንደሆኑ ሁሉ ፡ ለሱ ዘመን መጠቀሚያና መዝናኛ እንደተመደቡ ሁሉ ፡ ከጥቁር ጠይም ፊቱ ላይ ያሉ ዓይኖቹ በአሽሟጣጭ አስተያየት ማየታቸው ነው ። ይሄ አስተያየቱ ከሜላኒ ጋር ሲቀመጥ ብቻ አይታይበትም ። ከሜላኒ ጋር ሲሆን ያ ቀዝቃዛ አሽሙር ፡ ያ ዓይኖቹ ውስጥ የሚሯሯጥ ሽሙጥ ሁሉ ድራሹ ይጠፋል ። ይልቁንም የተጨዋችነቱ ፡ የሰው ማክበሩ ለሰው ታዛዥ የመሆኑ ልዩ ምልክት ይጐላል ።

አንድ ከሰዓት በኋላ ፡ “ለሷ እንደዚህ ደግና ታዛዥ እንደምትሆ ንላት ለኔም ቅን የማትሆንበት ምክንያት አይታየኝም ። ” ብላው ነበር አስካርሌት ፡ ሚላኒና ወ/ሮ ፒቲ የእንቅልፍ መትሰስ ልማዳቸውን ሊወጡ ሄደው ፡ እሷና እሱ ብቻ ሲቀሩ ።

@OLDBOOKSPDF

ሚላኒ በሁራት ስለአሽሌይና ስላገኘውም ሹመት በረኻው ስታ ወራለት ሬት የሚላኒን የስፌት ጨርቅ እንደያዘ ለአንድ ሰዓት ያህል ፊቱ ላይ ምንም ሳይነበብበት መቀመጡን እስካርሴት ልብ ብላለች ። ሬት ስለአሽሌይ የተጋነነ ስሜት የለውም ። ሻለቃ በመሆኑም ምንም ስሜት አልሰጠውም ። ያም ሆኖ መልስ የሚሰጠው በትህትና ሲሆን ስለአሽሌይ ቆራጥነትም በሹክሹክታ የተናገረው ትክክለኛ ነገር ነው።

ይሄኔ እኔ የአሽሌይን ስም አንስቼ ቢሆን ኖሮ ፡ አለች በሀሳቧ ንዴት እየተናነቃት ፡ ቅንድቡን ከፍ ከፍ እያደረገ ያን የሽሙጥ ፈገ ግታውን ይጅምር ነበር ።

"እኔ ከሷ የተሻለ ቁንጅና አለኝ" ብላ ቀጠለች "እና ለምን ለሷ ጥሩ እንደምትሆንላት በጭራሽ አይታየኝም ። "

"ትንሽ እንደመቅናት ይታጣሻል ልበል?"

"ውይ! በጭራሽ!"

"አንድ ሴላ ተስፋ ተንኮታኩተ ማለት ነው ። እኔ ለወ/ሮ ሚላኒ ጥሩ እምሆንላት ጥሩ ሊኮንላት የሚገባ ማሩም ሴት ስለሆነች ነው ። በሕይወቴ ካየኋቸው በጣም ሩሀሩህና ራስ ወዳድ ካልሆኑ ጥቂት ሰዎች ውስጥ አንዷ እሷ ናት ። ምናልባት እነዚህን ማሩም ማሩም ባህሪዎቿን አንቺ ልብ አላልሽም ይሆናል ። በዛ ላይ የማወቅ ዕድል አግኝቼ ካወቅኋቸው በጣም ጥቂት ታሳላቅ ሴቶች ማህል ፡ ምንም ገና ወጣት ብትሆን ፡ አንዷ እሷ ናት ።"

"ይሄን ስትል ፡ እኔስ ታላቅ ሴት አይደለሁም ማለትህ ነው እንዴ?"

"ምነው መጀመሪያ የተገናኘን እለት ጨዋ ሴት እንዳይደለሽ ተማምነን ።"

"ኤጭ! እንደዚህ ስድ የምትሆን ከሆነና ያንን ወሬ ደግመህ የምታመጣ ከሆነ በቃን! እንዴት እንደዛ ያለ በልጅነት የተፈጸመ ጉዳይ እንደ ደህና ነገር አኔን ለመታወሚያ ታቀርባለህ? ያ የተፈጸመው ከስንትና ስንት ጊዜ በፊት ነበር ። ከዛ ወዲያ እኔ እንዴት እንዳደግሁ ማየት ነበረብህ ። አንተ በየጊዜው እንደመጫ ባንድ ነገር ላይ ተጣብቀህ ትነዘንዘኛለህ እንጂ እስካሁን እረስቼው አርፍ ነበር ።

"አይ ፡ በልጅነት የተፈጸመ ነው ብዬ አላምንም ። አንቺ አሁን ተለውጠሻል ብዬም አላምንም ። አንቺ ፡ አሁንም ቢሆን እንደምትፈልጊው አልሆን ባለሽ ሰው ላይ የአበባ ማስቀመጫ የመወርወር ችሎታ አለሽ ። ደግነቱ ባሁኑ ጊዜ በአብዛኛው የፈለግሽው ነገር ይሆንልሻል። ስለዚህ የአበባ ማስቀመጫ መስባበሩ አስፈላጊ አይሆንም ። "

@OLDBOOKSPDF

"ወይኔ፡ እንተኮ . . . ምነው ወንድ በሆንኩኝ ኖሮ፣ ገፍትሬ ከዚህ አስወጥቼ ከዚያ . . . "

"ከዚያ በራስሽ ጦስ መገደል። አስታውሽ ፡ እኔ ከሃምሳ ያርድ ርቀት ላይ ተኩሼ ሳንቲም የምበሳ ሰው ነኝ። እንዛኑ የገዛ ራስሽን መሣሪያዎች ይዘሽ ብትቀመጪ ይሻልሻል —የጉንጭሽን ስርጉድ፡ የአ በባ ማስቀመጫሽንና የመሰሳሉትን ማለቴ ነው።

"እንተ እኮ በጣም እርኩስ ሰው ነህ"

"አሄሄ፡ ይህን ስላልሽ ይናደዳል ብለሽ እንዳይሆን ብቻ ? ስላስ ቀየምኩሽ ይቅርታ። እውነተኛ ማንነቴን በሚያሳዩ ስሞች ስለጠራሽኝ ስደብሽኝ ብዬ ፀጉሬን አልነጭም። በእርግጥ እርኩስ ሰው ነኝ፤ ደሞስ ለምን አልሆንም ? ይሄ ነፃ አገር ስለሆነ ማንም የፈለገውን ነገር መሆን ይችላል። ምናልባትም ደስ ካለው እርኩስ ይሆናል። ምርጫው የራሱ ነው። አየሽ ሄ ውድ ወይዘሮ፡ እንዳንቺ ያሉ ልባቸው የሐዘን ማቅ የለበሰና እሱን ለመሸፈን በመሞከር የለበጣ ኑሮ የሚኖሩ አስመሳ ዮች ብቻ ናቸው ብትከክሰኛ ስማቸው ሲጠሯቸው ያዙኝ ልቀቁኝ የሚሉት።"

እስካርሌት ድምጽ ለሌለው ፈገግታውና ከልብ ለመነጨው አስ ተያየቱ የምትመልሰው ጠፍታ አፍጣ ተቀመጠች። ከዚህ ቀደም እንደሱ ያለ በጭራሽ የማይረታ ሰው አጋጥሟት ስለማያውቅ በጸጥታ ከመቀመጥ ሌላ አማራጭ አልነበራትም። የስድብ፡ የመቀዝቀዝና ሰውን የመዝለፍ መሣሪያዎቿ ሁሉ ሊያሳፍሩት ባለመቻላቸው ከፊ ለቸው በከንቱ ባረቁ፡ ከፊለቸው በእጅጥ እንዳሉ ከሸፉ። እሷ ከል ምድ እንደምታውቀው፡ ውሸታሙ ስለእውነተኛነቱ ሽንጡን ገትሮ እንደሚከራከር፡ ፈሪው ስለድፍረቱ እንደሚለፍፍ፡ ስድ አደጉ ስለጨ ዋነቱ እንደሚሰብክና መሪዳው ስለክብሩ እንደሚያወራ ነው። ሬት በትለር ግን እንደዚህ አይደለም። ያለችውን ሁሉ አምኖ በመቀበል እየሳቀ ሌላ እንድትጨምር ያደፋፍራታል።

ሬት በትለር በነዚህ ወራት ውስጥ በዚህ ቀን እመጣለሁ ሳይል ይመጣል። ደህና ስንብቱ ሳይል ደሞ ይሄዳል። ከዳር አገር እስከ አትላንታ ድረስ የሚመጡት ጥቂት ኮንትሮባንዲስቶች ብቻ ስለ ሆኑ እሱ ለምን ዓይነት ንግድ እንደሚመጣ ለእስካርሌት አልነ ባሽ ብሏታል። እንዚያ ኮንትሮባንዲስቶች ያስጫኑትን ዕቃ ወይ ዊል ሚንግተን ወይ ቻርልስተን ድረስ ይወስዱና ከደቡብ የሚመጡና ተጫርተው የሚገዙ ወፈ ሰማይ ነጋዴዎችና የአቦ ሰጡኝ ሻጭ ገሾ ዎች ተጋፍተው ይወስዱላቸዋል። መቼም ሬት በትለር የሚመጣው

@OLDBOOKSPDF

እሷኑ ለማየት ቢሆን ደስታዋ ነበር ። ነገር ግን ያ ከልኩ ያለፈ ከንቱ ልቡናዋ እንኳ ይህንን አላምን አላት ። ከዚህ ቀደም ካገኘችው ጊዜ ውስጥ አንድ ቀን እንኳ የፍቅር ምልክት አሳይቷት ቢሆን ወይም በዙሪያዋ በሚሰበሰቡት ወንዶች ላይ የቅንዓት ስሜት አድሮበት ቢሆን ወይም ደሞ እጅዋን የመያዝ አዝማሚያ አሳይቷት አሊያም ፎቶግራፏ ንም ሆነ መሀረቧን ለማስታወሻ ልውሰድ ብሏት ቢሆን እንኳ ፤ በሷ ደም ግባት ተስቦ መመላለሱን በድል አድራጊነት ታምን ነበር ። ሆኖም እሱ እንዲህ ያለ ነገር ማድረግ ቅርቱ ስማድረግ ቃጥቶትም እያውቅ ። በጭራሽ የአፍቃሪነት ሁኔታ አይታይበትም ። እንዲያውም ከሁሉ በላይ የሚያበሳጨው ነገር ደግሞ በእጅዋ ልታገባው ፣ የፍቅር ባለሟል ልታደርገውና ልታንበረክከው የምታደርጋቸውን ጥረቶች ሁሉ ገና ስትጀምር ማወቁ ነው ።

እሱ ወደ ኩጣ በገባ ቁጥር ሴቱ ሁሉ ስለሱ ማማት ይጀም ራል ። በሱ ላይ ስለሚያንጣጥበበው የፍቅር ስሜት ብቻ ሳይሆን እርኩ ስነቱንና ነውር ሥራውን ሁሉ አያነሱ ቆዳውን ይልጡታል ። ስሙን ያጐድፉታል ። እንዲህ ያለ ስመ ጥሩ ሰው ነው! የአትሳፃታ ሞግዚቶች ለሐሜታ በተሰበሰቡ ቁጥር የሱ ስም የበለጠ እየጎ ደፈ ፣ የበለጠ እየጠሩ ይሄዳል ። ዳሩ ግን ስሙ በጠሩ በጐደፈ ቁጥር አትላንታ ወጣት ሴቶች ፊት ይበልጥ ዝነኛ ፣ ይበልጥ ዕውቅ ሰው እየሆነ ይመጣል ። አብዛኞዎቹ ወጣት ሴቶች የሞሆኝ በመሆናቸው "በሴቶች ጉዳይ ሰላ ያለ ነው ። ግድ የለውም" ከሚባለው በላይ አይ ሰሙም ። ወንድ ልጅ በሴቶች ጉዳይ እንዴት "ሳላ" ሊል እንደሚ ችል ግን በትክክል አይገባቸውም ። ልጃገረድ ከሱ ጋር ሄዳ በሰላም አትመለስም ሲባልም ሰምተዋል ። ይሄ ሁሉ አኩይ ተግባር እየተ ወራበት ፣ ይሄ ሁሉ አይምሬነት እየተነገረበት ፤ አትላንታ ከረገጠባት ቀን እስከዛሬ ድረስ የማንንም ያላገባች ሴት እጅ እንኳ ያልሳመ መሆኑ በጣም ግር የሚል ነገር ነው ። ያም ሆኖ ግን ይበልጥ ሚሥ ጥራዊና ይበልጥ አስደሳች ሰው እንዲሆን አድርጎታል ።

ሠራዊቱ ውስጥ ካሉት ጀግኖች ቀጥሎ አትላንታ ውስጥ ስሙ የሚነሳው የሱ ብቻ ነው ። በጠጪነቱና "ስለሴቶች በሚታማ በት ነገር" ምክንያት ከዊስት ፖይንት እንደተባረረ የማያውቅ ማንም ሰው የለም ። ያቺን ቻርልስተናዊት ልጃገረድ የሠራትን ሥራና ወን ድማንም የመግደሉ የቅሌት ወሬ ድፍን አገር ቡና የሚጠጣበት ጉዳይ ነው ። ሰው ቻርልስተን ካሉ ዓደኞቹ ጋር እየተጻጻፈ ስለፊት በትለር ወሬ ስለሚሰበስብ ስለሱ የሚታወቀው ነገር እየሰፋ ሄዷል ። አባቱ ጨዋና ልበ ሙሉ ሽማግሌ ሲሆኑ ገና በሃያ ዓመቱ ቤሳ ሳንቲም ሳይሰጡ ከቤታቸው አባረውታል አሉ ። ከቤተሰቡ የስም

@OLDBOOKSPDF

ባሀረ—መገገብ ዳዊት ላይ ሳይቅር ስሙን ሰርዘውታል ። ከዚያ ጊዜ ወዲህ በ1849 በነበረው የወርቅ ንግድ ሽሚያ ጊዜ ካሊፎርኒያ ሄዶ ተሳትፏል ። ከዛም ወደ ደቡብ አሜሪካና ኪዩባ ሄዷል ይባላል ። ታሪኩ ግን ይሄን ያህልም በአመርቂ ሁኔታ አይታወቅም ። የእትላ ንታ ሕዝብ የሰማው ከሴቶች ጋር ስለመጻራቱ ፣ ስለመታኮሱ ፣ በማዕ ከላዊ አሜሪካ ለሚገኙ አብዮታውያን ጠመንጃ ስለመሸጡ ፣ ከሁሉም የከፋው ደሳሞ እውቅ ቋማርተኛ መሆኑና ቋማርን እንደሙያ መያዙ ነው ።

ጆርጂያ ውስጥ በሚገኝ በማንኛውም ቤተሰብ ውስጥ ቢያንስ አንድ ወንድ ልጅ ወይም ዘመድ የሆነ ሰው ፣ ንብዘብ ፣ ቤት ፣ መሬትና ባሪያ በቋማር እያስያዘ የማይበላ የለም ። ሆኖም ይሄ የተለየ ነው ። ሰው ቋማር ተጫውቶ ከስሮ ዶሀይኦም ቢሆን ጨዋ መሆን ይችላል ። ቋማርን እንደሙያ የያዘ ሰው ግን ካነር የተባረረ ፣ ከቤተሰብ የተተፋ ከመሆን ሌላ ምን ሊሆን ይችላል ።

ፅድሜ ለጦርነትና ፅድሜ ለኮንፌዴሬሲው መንግሥት ለሚ ሰጠው አገልግሎት ይበል እንጂ ሬት በትሰርን አትላንታም ሪፏ ብትሆን በሯን ትዘጋበት ነበር ። ኤሁን ግን የመጨረሻው ጠባብ ዜጋ እንኳ በሀገር ፍቅር ምክንያት ሆዱን ሰፍ አድርጎ ሬትን ተቀብ ሎታል ። እሱን በጣም የወደዱት ደግሞ ፣ የበትሰር ቤተሰቦች እሱን ማባረራቸው ጸጽቷቸው ሰራው የሚሉትን ኃጢአት ለማስተባበል እየሞከሩ ነው ፣ እያሉ ያወራሉ ። ስለዚህ የአትላንታ ሴዶች ይቺን ጫፍ ይዘው በዚያ በኩትሮባንዲስት ላይ የሚወራውን መጥፎ ወሬ ማስተባበል ጀምረዋል ። ዛሬ እያንዳንዱ አትላንታዊ በጦር ግንባር ያሉት ወታደሮች ሕልውና ኮንትሮባንዲስቶች በሚያስገቡት መሣሪያና ፅቃ ላይ የተመሠረተ እንደሆነ እንደሚያውቅ ሁሉ ፣ የያንኪ የጦር መርከቦችን ለመደምሰስም ኮንፌዴሬሲው በኩትሮባንዲስቶች ጀልባ ላይ ፅምነቱን የጣለ መሆኑንም ያውቃል ።

ካፒቴን በትሰር በደቡብ ውስጥ አሉ ከሚባሉት መርከበኞች አንዱ ስለመሆኑና ለምንም ግድ የሌለው ፣ ምንም ሥጋት የሌለበት ኃይለኛ ሰው ስለመሆኑ ጭምጭምታ ወሬ አለ ። ቻርልስተን ውስጥ ጥርሱን ነቅሎ ያደገ በመሆኑ ፣ በወደቡ አጠገብ ያለውን የካሮላይና የባህር ዳርቻ አያንዳንዱን ስርጥ ፣ አያንዳንዱን ቋጥኝ ፣ አያንዳንዱን የቦይ ውሃ ፣ ዓዳ ጐድጓዳዋን ሳይቅር ያውቃታል ። በዊልሚንግተን አካባቢ ያለውንም የውሃ ዳርቻ እንደዚሁ እንደቤቱ ዓዳ ያውቀዋል ። አንድም ጀልባ ሰምጣበት አታውቅም ። የጫነውንም ፅቃ አባህር ለመጣል ተገዶ አያውቅም ። ጦርነቱ ሲጀመር የአንድ ፈጣን ጀልባ መግዣ

@OLDBOOKSPDF

ጎንበብ ብቻ ይዞ ዓይኑን ጨፍኖ ንግድ ጀምሮ ፡ እንዲህ ንግድ ተሩ ቀም ከመዶ ሁለት ሺህ እጅ ከሚተርፍበት ጊዜ ደርሶ ዛሬ የአራት ጀልባዎች ጌታ ሆኗል ። ጥሩ ጥሩ የመርከብ ነጂዎች ስላሉትና ደህና ደሞዝ ስለሚከፍላቸው ከቻርልስተንና ከዊልሚንግተን በድፍን ጨለማ ጥቂ ሞኑ ያወጡና ፤ ናሱ ፡ እንግሊዝና ከናዳ ውስጥ ያራግፉ ። የእንግሊዝ የጥቂ ፋብሪካዎች ያለሥራ ስለያመና ሠራተኞቻቸውም ስለተራቡባቸው ማንም የያንኪዎችን የባህር ጦር ሥፈር በዘዴ አሳልፎ ጥቂ ሞኖ እንግሊዝ የባህ ነጋዴ ሊሸር ፑል ገበያ ላይ የፈለገውን ዋጋ ተምኖ ሊሸጥ ሊለውጥ ይችላል ። እንግዲህ የሬት በትለር ጀልባዎች አንድም የኮንፌዴሬሲውን ጥጥ ይዘው በመውጣ ታቸው ፣ አንድም ደቡቡ እንደእህል እንደውሃ የሚፈልገውን የጦር መሣሪያ ይዘው ስለሚመለሱ ብቸኛ ተጠቃሚዎችና አድለኞች ናቸው ። ታዲያ እንዴህ ያለውን ጀግና ሰው ፡ ሴቶቹ ይቅር ማለትና የሠራውን ሥራ መርሳት ብይኖርባቸው ኖሯል ?

ሬት በትለር ሰውነቱ ሙሉና የሚታይ ወንድ ነው ። ሁሉ ሰው እየነረ ያየዋል ። ገንዘብ እገዳልቡ ይረጫል ። በጥቁር ሠንጋ ፈረስ ተን ሰራፍቶ ተቀምጦ ይታያል ። እጅግ በመናዊና እንከን የለሽ ስዴት ያስዋባቸው ሽክ ያሉ ልብሶችን ይለብሳል ። ይሄ ኦስባበሉ ራሱ እንዲታይ እንዲደነቅ ያደርገዋል ። ዛሬ የወታደሮች ዩኒፎርሞች ከመደብዘዛቸውም አርጅተዋል ። ሲቪሎቹም ቢሆኑ በጣም ማሩም የሚሉት ልብስ በስውር ስዴት የተጣጣፊ ነው ። ስለዚህ የሱ ልብሶች የሰው ሁሉ ዓይን ማረፊያ ናቸው ። እስክርሌት እሱ የሚለብሳቸውን ዓይነት ቦላሌዎች በጭራሽ አይታ አታውቅም ። በጥሚ ቀለም ያላቸው ባለ ዲዛይን ምርጥ ሱፎችና ተከሳቸው ጥራት ያለው ነው ። የሰደርያምቹ ነገ ርማ እይነሳ ። መማለድ ከሚቻለው በላይ ቆንጆዎች ናቸው ። በተለይ ሐምራዊ የሮዝ እምቡጦች ጣል ጣል ያለበት ውሃ የመሰለው ሀር ሰደ ርያው ትንፋሽ ያሳጣል ። የሚገርመው ደግሞ እነዚህን የመሳሰሉ ልብሶች ለብሶ ሽክ ብሎ ፎጣ ትከሻው ላይ ጣል ያደረገ ያህል ግድ ሳይሰጠው ሲገናና በቀላል አየር ላይ የሚንሳፈፍ ይመስላል ።

መቼም እሱ ላማባባቸው ብሎ ከሞከራቸው ሴቶች እምቢ ብለው የሚቀሩ በጣም ጥቂቶች ናቸው ። በመጨረሻያማ ወ/ሮ. ሚሪዌዘር እንኳ ሳይቀሩ አሜን ብለው ተቀብለው እሁድ ማታ ራት ጋበዙት ።

ሜይቢል ሚሪዌዘር ያን ሁጫሜ የዙዌቭ ተወላጅ ልታግባ ነው ። ያውም ግና የሚቀጥለውን አረፍት አማኝቶ ከሶር ሜዳ ሲመጣ ነው ። እቢ ልታግባ የምትፈልገው በብልጭልጭ ነጭ የሳቲን የሙሽራ ልብስ ነው ። ዛሬ በኮንፌዴሬሲው ግዛት ውስጥ ሲለፉ ቢውሉ ነጭ ሳቲን

@OLDBOOKSPDF

እይገኝም ። ስለዚህ ባሰበችው ቁጥር ታለቅሳለች ። ደሞ እንዳትበደር እንኳን ከአመታት በፊት የነበሩት የሳቲን ጨርቅ የሙሽራ ልብሶች ዕቦር ስፈር ባንዲራ ሆነው አልቀዋል ። በሀገር ፍቅር ስሚት የተሞሉት ወ/ሮ ሚሪዊዘር ፣ የኮንፌዴሬሲው ሙሽሪት እቤት በተሸመነ የሙሽራ ልብስ እኮ ነው የምታገባው—ቢሷትም በጀ አላለችም ። እሷ የምትሻው የሳቲን ጨርቅ ነው ። ሲታሳቁ ዓሳማ ሰትል ያለ ፀጉር ማስያዣ ጸጉሯን ብትለቀው ፣ ያሰቱልና ቀሚሷን ከትከሻዋ ብትከፍተው ፣ ቆንጆ ሚማ ባታደርግ ፣ ከረሜላና ሻዩ ቢቀርባት ፈቃዷ ነው ። እንዲያውም ኩሯቷ ነው ። የሙሽራ ልብሷ ግን የግድ ብልጭ ልጭ ሳቲን መሆን አለበት ።

ሬት ይህንን ወሬ ሚስኒ ስታወራ ስለሰማ ፣ ከኢንግሊዝ አገር በብዙ ያርድ የሚሰላ ውትት የመሰለ ብልጭልጭ የሳቲን ጨርቅና በጌጥ ያሸበረቀ ቬዋል እምጥቶ ለማይቤል የሠርግ ስታጡ ሰጣት ። ሲሰጣት ደግሞ ግንዘቡን መክፈል የማይታሰብ ነገር መሆኑን ሂልዩ ነበርና ሜይቤል ከደስታ ብዛት ልትስመው ምንም አልቀራት ። ወ/ሮ ሚሪዊዘር እንዲህ ያለ ውድ ስጦታ— ያውም የልብስ ፣ መቀበል አግባብ እንዳልሆነ ቢያወቁም ሬት በትለር ከጀግኖቻችን ማህሉ የአንዱን ሴት ልጅ በእንዲህ ያለ የሙሽራ ልብስ ከማንቆጥቆጥ የበለጠ ምንም ነገር እንደሌለ ፣ በጣፈጠ ቋንቋ ሲነግራቸው ከቶም ለመታወም ወኔ አነሳቸው ። እሺ ፣ ይሁን አሉ ። በዚህ ዓይነት ወ/ሮ ሚሪዊዘር የስጦታውን ዋጋ ለመክፈል ብለው ሬት በትለር ላይ ያላቸውን ጥላቻ ሁሉ ፍቀው እራት ጋበዙት ።

ሬት ለሚይቤል ስጦታውን መስጠት ብቻ ሳይሆን ስፈቱ እንዴት መሆን እንዳለበት ጭምር የባለሙያ አስተያየት ሰጠ ። በዛሬ የአለባበስ ፈሊጥ ፓሪስ ውስጥ በቱንቲዎቹ ሰፋ ፣ ቀሚሶቹ አጠር ይላሉ ። ሽንሽን መሆናቸው ቀርቶ በትላልቁ ሽብሽብ ሽብሽብ ተደርገው ይሰሩና ከሥር የተጠለለፉትን ትናንሽ ቀሚሶች የሚያሳዩ ናቸው ። ከዚህ ጨመር አድርጎም ከግርጌያቸው ሽብሽብ ያላቸውን የሴት ሠሪዎች በፓሪስ መንገዶች ላይ አሰማየቱንና ምናልባት ዘመን አልፎባቸው ይሆናል ብሎ እንደሚገምት ነገራቸው ። ወ/ሮ ሚሪዊዘር ሌላ ጊዜ ለወ/ሮ ኤለሲንግ ሲያወሩ ፣ ትንሽ ፈት ቢሰጣት ኖሮ ሴቶቹ ምን ዓይነት ቡታንቱ እንደሚለብሱ ጭምር ያስረዳቸው እንደነበር ነገሩ ዋቸው ።

መቼም ሬት በትለር የወንድነት ባህሪው አነስ ያለ ሆኖ ቢታይ ኖሮ ፣ ስለቀሚስ ፣ ስለፀጉር ጌጥና ስለፀጉር ሥራ ዝርዝር ነገሮችን ማወቁ በሴትነት ያስጠረጥረው ነበር ። ሴቶቹ ስለአለባበስ እሱን መጠየቅ

@OLDBOOKSPDF

ትንሽ የሚያሳፍር ነገር ሆኖ ቢሰማቸውም ከመጠየቅ አልቦዘኑም። ስለአለባበስና ስለጸጉር ሥራ የሚያወሱት በኩንትሮባንድ የሚገቡ መጽሔቶች በጣም ዋቂት ስለሆኖባቸው፣ ሴቶቹ— እባህር ማህል መርከብ እንደተበላሸባቸው መርከበኞች ከዓለም ተነጥለዋል። የፈረንሳይ ሴቶች ፀጉራቸውን ቢላጩና ከአውሬ ፀጉር የተሠራ ባርኔጣ ቢያደርጉ እንኳ፣ እነዚህ የአትላንታ ሴቶች በምንም መንገድ ሊሰሙ አይችሉም። ስለዚህ የሬት የማስታወስ ችሎታ የሩግ*ይስ ሌዲስ ንጽሕፍ ተክቶላቸዋል። በሴት ልጅ ልብ እጅግ የሚወደድ ዝርዝር እንስታይ ጉዳዮችን ለማስታወስ ስለሚችል ከየ አንዳንዱ ጉዞው በኋላ በሰዎች ተከቦ—ዘንድሮ የሴት ባርኔጣ መጠኑ አነስ ማለቱንና ከፀጉር በላይ ብቻ ጣል መደረጉን፣ ስፋቱም የፀጉርን ስፋት በሙሉ እንደሚሸፍንና ለክፈፍ ማስጌጫው አበባ መጠቀም ቀርቶ የዶሮ ሳባ መጭካቸን፣ የፈረንሳይ ንግሥት ማታ ማታ ፀጉሯን ከኋላ መሸጠሯን ሳታ፣ ጀሮዋን ሙሉ በሙሉ እንደሚያሳይ አድርጋ እራሷ ላይ እንደምትከምረው፣ የማታ ቢሾማዎች እንደገና ማጠራቸውንና እማበደንገጥ ደረሽ እንደደረሱ ይነግራቸዋል።

ለጥቂት ወራት ዝንጉንቱና ጭቅር አሞቂነቱ የሚነገርለት ሬት በትለር ብቻ ሆነ። ከዱርው ስሙ ጥፉነቱና ከዕቃ ኮንትሮባንድም አልፎ የምግብ ሽቀጥ ማምታታት ጀምሯል ከሚለው ሹምሹምታ ወሬ በስጥቅር ታዋቂነቱ ገንኗል። የሚጠሉት ሰዎች እሱ አንድ ጉዞ ጨርሶ ወደ አትላንታ ሲመለስ የሰቃ ዋጋ በአምስት ዶላር ይጨምራል እያሉ ያስወሩበታል። ሆኖም ይሄ የውስጥ ለውስጥ ሀሜታ እየተወራበት እንኳ እሱ ከፈለገ ዝናውን እንደጠበቀ መኖር ይችላል። እሱ ግን ይህንን ከሚድረግ ራንታ በአርበኝነትና በሀገር ፍቅር ስሜት የተሞሉትን ዜጐች በደምብ ከተወጻጀቸውና አክብሮታቸውንም ካገኘ በኋላ በአንድ እውስጡ ባለ የተገላቢጦሽ አመል ተገፋፍቶ አስከዛሬ ያደረገውና ያሳያቸው በባይ ሁሉ ለማስመሰል መሆኑን እየገለጠ ያለውን ጥላቻ ያሳውታቸዋል።

ለእያንዳንዱ ሰውና በደቡብ ውስጥ ሳለ ለማንኛውም ነገር በተለይም ለኮንፌዴሬሲው፣ በጣም የመረረና ቂም ያዘለ ጥላቻ ያለው ከመምሰሉም በላይ ይህንኑ ጥላቻውን ለመደበቅ አይጨነቅም። ድጥን የአትላንታ ሕዝብ በመጀመሪያ በመደናገጥ ዓይን፣ ቀጥሎ በቀ ዘቀዘ ዐይን በመጨረሻ እሳት በጐረስ ቁጣ የተነሳበት ስለኮንፌዴሬሲው በሰጠው አስተያየት ነበር። ገና 1862 ወደ 1963 ሳይሸጋገር ወንዶቹ ቀዝቀዝ ሰላምታ ሲሰጡት፣ ሴቶቹ ደግሞ እሱ፣ ሰው ወደተሰበሰበበት ቦታ ሲመጣ ልጆቻቸውን ወደራሳቸው አስጠግተው በመያዝ ያሳልፉት ጀምረዋል።

@OLDBOOKSPDF

የኢትላንታን ታማኝነትና እንደእሳት የሚንቀለቀል ቅንነት መፈ ታኑት ብቻ ሳይሆን ሰውን ያስተይማል የሚለውን መጥቦ መንገድ ሁሉ እየተጠቀመ መቅረብ የሚያስደስተው ይመስላል ። በጣም ደህና ደህና የሚባሉት የከተማይቱ ሰዎች የኮንትሮባንዱን ሥራ በመሥ ራቱ ጀግንነቱን ሲያደንቁለት ፡ በጦር ግንባር ያሉት ጀግኖች እንደሚ ፈሩ ሁሉ አሱም በእደታ ማህል ሲሠራ እንደሚፈራ ፤ አፍ አውጥቶ ይነግራቸዋል ። መቼም በጦር ግንባር ያሉት ማናቸውም ወታደሮች ጥርሃት የሚባል እንደማያውቃቸው ግንም ያምናል ። ስለዚህ ወታ ደሮቹ ፈሪ ናቸው ብሎ መናገሩ ከየትኛውም ከተናገረው ነገር የበ ለጠ ደማቸውን የሚያፈላ ነገር ነው ። ስለወታደሮቹ ባወራ ቁጥር "ጀግኖች ልጆቻችን" እና "ማራኪ ሰባቸ ጀግኖቻችን" ብሎ ይጀም ርና አንጀት በሚያላርር ሁኔታ ይደመድመዋል ። ዘልባቸው አሱን የሚመኙ ደፋር ወጣት ቤቶች እንዲያጫውታቸው ሲፈልጉ ፡ ለነሱ ሲሉ ከሚዋጉት ጀግኖች አንደአንዱ ሙሆኑን ገልፃው ሲያመሰግኑት እጅ ይነሳና ጉዳዩ እነሱ እንደሚሉት አለመሆኑን ፤ አሁን የሚያገኘ ውን ያህል ግንዘብ ቢያገኙበት ለያንኪዎቹ ሉቶችም ይህንኑ ነገር ያደርግላቸው እንደነበር ይነግራቸዋል ።

ለእስክርሉትም አትላንታ ውስጥ የባዛሩ ጌለት ሚታ ካገኘችው ጊዜ ጀምሮ የሚያወራለት በዚሁ ሁኔታ ነበር ። ብቻ አሁን ከማንም ጋራ ሲያወራ እንግግሩ ውስጥ ትግሽ ቸፈን አድርጎ አሽሙሩን ይነሰ ንስበታል ። ለኮንፌዴሬሲው የሰጠውን ግልጋሎት በሚመለከት አድ ፍቶት ሲያደርግለት ለሱ ንግድ እንጂ ሌላ ትርጉም እንደሌለው ሳያ መነታ ይገልጽላቸዋል ። ከመንግሥት ክንትራት ወስጂ አሁን የማገኘ ውን ያህል ግንዘብ የማገኝ ከሠኑ ፡ ይላል በዐይኑ የመንግሥት ኮንት ራትኞችን እያየ ፡ የኮንትሮባንድ ሥራዬን አቁሚ ሙራጅ ለብስ እንዳዲስ አዘጋጅቼ ፡ ሰኳር ውስጥ አሸዋ ደባልቼ የተላ ዱቄት አሽጌና የበሰበሰ ቆዳ ፋፍቼ ለኮንፌዴሬሲው እሸጥ ነበር ይላል ።

የሚሰጣቸው አስተያየቶች ሁሉ መልስ የሚሰጣቸው አለመሆና ቸው ነገሩን ያብሰዋል ። የመንግሥት ክንትራት ወስደው የሚሠሩ ሰዎች ስለሚፈጽሙት ትናንሽ ደባ የሚወራ ጭምጭምታ ወሬ አለ ። ጦር ሜዳ ያሉ ወታደሮች በሚጽፏቸው ደብዳቤዎችም በተከታታይ ከሚጠቀሱ አቤቱታዎች ውስጥ፡ በሳምንት የሚያልቁ ጫማዎች ፣ በማይተኩስ ባሩድ የተሞሉ ጥይቶች ፣ ገና ሲስቧቸው የሚበጠሱ ልን ሞች ፣ የበሰበሱ ሥጋዎችና ነተዝ የሞላበት ዱቄት ዋና ዋናዎቹ ናቸው። የአትላንታ ሰዎች እንዲህ ያሉትን ሽቀጣ ሽቀጦች የሚሸጡት ባለቦ ንትራቶች ወይ ከአላባማ ወይ ከቨርጂኒያ አለያም ከተንሲ የመጡ እንጂ ጆርጂያውያን አይደሉም ብለው ለማሰብ ይሞክራሉ ። ምነው

@OLDBOOKSPDF

ያርጂያውያን ባለኮንቶራት ከደሆነ ቢተበብ የወጡአይደሉም እንዴ፣ ለሆስፒታሉ መዋጮና ሰሞቱ ወታደሮች ልጆች ማሳደጊያ ገንዘብ በመጀመሪያ ያዋጡስ እነሱ አይደሉም እንዴ፣ በ"ዲክሲ" ሙዚቃ ላይስ የመጀመሪያዎቹ ተደሳቾችና የዎንኪዎችን ደም ለመምጠጥ —ቢያንስ በዲስኩር ደረጃ፣ መጀመሪያ የተነሱ እነሱ አልነበሩም እንዴ፣ ከመንግሥት ኮንትራት ወስደው የትርፍ ትርፍ በማካበት ላይ የሚገኙ አሳግባብ ቢልዮኔዎች ላይ የሚሰነዘረው ቁጣ ገና ሙሉ በሙሉ አልዘነበም። የሬት በትለርም ማንጓጠጥ እንደራሱ የአስተዳደግ ጉድለት ተመስጂል።

ሬት በከፍተኛ ስልጣን ላይ ያሉትን ሹማምንት ጉቦኝነት መሸሞሩና በጦር ግንባር ያሉትን ወንዶች ወኔ ቢስነት መግለጽ ብቻ ሳይሆን የተከበሩትን ቢጎች የሚያበሳጭ ሁኔታ ላይ መጣል ያስደስተዋል። በአርበኝነትና በሀገር ፍቅር የተሞሉ በማስመሰል የሚፈነጩትን በዙሪያው ያሉትን ሰዎች ሀሊና ጠቅ አድርጎ መውጋት፣ ሕያን ልጅ የተነሳ ሬኛ አይኑ በአስፒል ሳይወጋ ማለፍ እንደማያስችለው ሁሉ አሳስቸል ይለዋል። ጉረኞችንና የሚደነፉትን ማዋረድ፣ ደንቆሮዎቹንና እኝኝ ብለው አላማ አሳማ የሚሉትን ማጋለጥ ደስ ይለዋል። ሲያዋርዳቸውና ሲያጋልጣቸው ደግሞ እነሱን መስሎ፣ እንደሚወዳቸው ሁሉ ቀርበው ከመሆኑ የተነሳ በአደባባይ እርቃናቸውን እስኪቀሩ፣ ወናፍነታቸው እስኪታይና መሳቂያ እስኪሆኑ ድረስ ምን እንደተሠራ ምን እንደተደረገ አርግጠኛ አይሆኑም።

የክትማው ሰው ሁሉ ሬትን በተቀበለው ጊዜ አስካርሌት ምንም አልተወናበደችም ነበር። የሠራቸው የጀግንነት ሥራዎችና የሚኩራባቸው ያማሩ ጉማሮች ሁሉ ምሳሉን እጉንጩ ውስጥ ቀብሮ የሚሠራቸውና የሚናገራቸው መሆናቸውን አሳምራ ታውቃለች። የድፍረትና የአርበኝነት የኮንትሮባንድ ሥራዎቹን ሁሉ እንደመዝናኛ እንደሚቆጥራቸው ይገባታል። አንዳንድ ጊዜ እንደአብሮ አደጎቿ የሠፈር ልጆች ይመስላታል። ቀልድና ፌዝ እንደሚወዱት የታርሌተን መንትያ ወንድማማቾች ይመስላታል። እንደሠይጣኖቹ የርንቴን ወንዶች ልጆች ተንኮልና ሸር የሚተበትብ ይመስሳታል። ሴሊቴን ሙሉ ሰነን በሰው ላይ የመቀስጀ ሴራ ሲያውጠነጥኑ እንደሚያድሩት እንዳካልቨርት ወንዶች ልጆችም ሆኖ ይታያታል። ግን እንድ መሠረታዊ ልዩነት አለው። ከሬት ቀላል መሳይ ተግባር ሥር እንድ ከራ ነገር አለ —ከሞላ ጐደል የእርኩሰነትና የጭካኔ ልቡና።

አስካርሌት፣ ምንም እንኳን ቅን ልቡና የሌለው ቢሆን በዚህ በአስደሳች የኮንትሮባንድ ሥራው በጣም ወዳዋለች። ምክንያቱም

@OLDBOOKSPDF

በመጀመሪያ ከሱ ጋር ከነበራት ግንኙነት ይልቅ አሁን የተሻለ ግንኙነት ስለሚኖራት ነው። ስለዚህ ይሄ ሰሞኑን ሆነ ብሎ በአትላንታ በነፈቃድ ላይ የከፈተውን ግልጽ ጦርነት መጀመሩ በጣም አበሳጭቷታል። ያበሳጫት አንድም የጅል ሥራ ስለሆነባት፣ አንድም አልፎ አልፎ በሱ ላይ የሚሰነዘረው መራራ ትችት እሷንም ስለሚነካ ነው።

ፊት በትለር በአትላንታ ሕዝብ ዘንድ የመጨረሻ ፍርዱን ተቀብሎ የፈረመው በወይዘሮ ኤልሲንግ ቤት በተዘጋጀው ያገጠሙ ቁስለኞች መርጃ የሙዚቃ ድግስ ላይ ነበር። የዚያን ዕለት ከሰዓት በኋላ የወ/ሮ ኤልሲንግ ቤት በፍቃድ ብሙጡ ወታደሮች፣ ከየሆስፒታሉ በመጡ ሰዎች፣ በከተማ ጥበቃ አባላት፣ በሚሊሺያ ጦር አባላት፣ በሞዛዞች፣ በሙት ሚሰቶችና በወጣት ሴቶች ተሞልቶ ነበር። በቤቱ ያለ እያንዳንዱ መንበር ተይዟል። ሴቶቹ ቀርቶ የሚጠግዘዘው ረሽቦም ደረጃ እንኳ በመቀመጫነት በእንግዶች ተይዟል። የወ/ሮ ኤልሲንግ አሽከር ተሸክሞት የቆመው ያ ከመሰቱዋት የተሠራ ትልቅ ገበቴ ሁለት ጊዜ በብር ሳንቲም ከተሞላ በኋላ ተጋብቶ አሁንም እየተጨመረበት ነው። ይሄ ራሱ አንድ ድል ነው። ምክንያቱም በዛሬ ተመን አንድ ዶላር በኮንፌዴሬሲው የወረቀት ገንዘብ ስልሳ ብር ማለት በመሆኑ ነው።

ታስመስልም ትመንበት እያንዳንዷ ልጃገረድ ዝግጅቱ እንዲሳካ ወይ ትዘፍናለች ወይም ጊያኖ ትጫወታለች። ከየጠረጴዛው ጭብጨባና ጩኸት እንደጉድ ይፈልቃል። እስካርሌት በራሷ ተደስታለች። እሷና ሜለኒ "ዊን ዘ ዲው አዝ አን ዘ ብሎሶም" የተባለውን ዘፈን ለሁለት የተጫወቱት ሲሆን ከዚያ ተከትሎ በጣም የሚደምቀው "አላው-ድ፣ ሉዲስ፣ ዶንት ማይንድ ስቲፈን!" የተሰኘው ዘፈን በመቀጠሉ ብቻ ሳይሆን በመጨረሻው ጠረጴዛ ላይ የኮንፌዴሬሲውን መንፈስ ምስል ወክላ የተቀመጠች በመሆኗ ነው።

እስካርሌት ነጭ በነጭ የሆነ የግሪክ መጐናፀፊያ በቀይና በሰማያዊ መቀነት ሸብ አድርጋ ባንድ እጅዋ የኮከቦችና የሠንደቆች ምስል በሌላኛው እጅዋ ደግሞ የወርቅ ጌጥ ያለውን የቻርለስንና የአባቱን ሰይፍ ይዛ እፊቷ ወደተንበረከከው የአላባማውን ካፒቴን ቤሪ አሽበርንን ወደሚወክለው ምስል ዘርግታዋለች።

የምታሰየው ትርኢት ሲያበቃ ፊት ቆንጆ አድርጋ ያቀላጠፈችውን ትርኢት እንዴት እንደሚያደንቅ ለማየት ከወይኖቹ ጋር መጋጨት ነበረባት። እሱ ለራሱ አንድ ሞት ያለ ከርከር ይዞ ከናካቴውም ወደሷ ሠሮ ማየቱን እንጂ። በጣም ከፋት። እስካርሌት በዙሪያው የከበቡትን ሰዎች ፊት በማየት የሚናገረው ነገር እንዳበሳጫቸው ገባት።

@OLDBOOKSPDF

ወደነሱ መንገድ ጀመረች ። በተሰበሰበው ሰው ማህል አልፎ አልፎ በሚሰፍነው ፀጥታ ውስጥ የዘለቀውን የሚሊሽያውን የዊሊ ጉዊናንን ግልጽ ድምጽ ሰማች፡-

"ጀግኖቻችን የወደቁለት አላማ የተቀደሰ አይደለም ነው የምትል፣ ጌታው ?"

"እባቡር ሐዲድ ላይ ተኝተህ ባቡር ቢድህህ የባቡሩን ኩባንያ የተቀደሰ የሚያደርገው ይመስልሃል ?" ብሎ ጠየቀ ሬት ። ድምፁ ከምር ለማወቅ የሚፈልገውን የጠየቀ ያስመስለዋል ።

"ጌታው ፣" አለ ዊሊ ድምፁ እየተንቀጠቀጠ "እንደው በዚህ ጣር ሥር ባንሆን ኖሮ እ...ወይ ነዶ!..."

"የሚከተሰውን ንገር ሳስበው ያንቀጠቀጠኝ ጀመር ባክህ" አለ ሬት ። "ጀግንነትህ በጣም የታወቀ በመሆኑ ካሁኑ እንቀጠቀጠኝ ።"

ዊሊ ሬቱ ደም መሰለ ። ንግግር ሁሉ ቆመ ። እያንዳንዱ ሰው በሽቋል ። ዊሊ ጠንካራና ጤናማ እንዲሁም ለወታደርነት በቂ የሆነ እድሜ ያለው ይሁን እንጂ ጦር ግንባር አልሄደም ። በእርግጥ ለእናቱ አንድ ነው ። ሆኖም ማንም ሰው ለሚሊሽያነት ተመልምሎ አገር መጠበቅ አለበት ። ንግር ግን ከሚያገማሙት መኰንኖች መሀል ሬት ስለጀግንነት ሲናገር የድብቅ ሳቅ የሚስቁ ጥቂት ቅድስና የሌላቸው ነበሩ ።

"ኡፍ ምነው አፉን ቢዘጋ ፣" አለች እስካርሌት ብግን ብላ ። "ዝም ብሎ እየለፈለፈ የፓርቲውን ድግስ ሊያበላሸው ነው በቃ ።"

የዶክተር ሚድ ሽፋሽፍቶች እንደመብረቅ ተርገበገቡ ።

"ምናልባት ላንተ ምንም የተቀደሰ ነገር ላይኖር ይችላል ! አንበሴ" አለ የአደባባይ ንግግር በሚያደርግበት ድምፁ ። "ሆኖም ለጀግኖች የደቡብ ወንዶችና ሴቶች ብዙ የተቀደሱ ነገሮች አሉ ። አገራችንን ከወራሪ ነፃ ማውጣት ፣ የሀገሮችን ነፃነት እና ደሞ..."

ሬት ድክም ያለውና ድምፁ ሁሉ መስልቸትን የተላበሰ ሆኗል ። "እሱማ አለና ጀመረ" መዋጋት ላለባቸው ሰዎች ጦርነቶች ሁሉ የተቀደሱ ናቸው ። ጦርነት የፈጠሩት ሰዎች ጦርነቶቹን የተቀደሱ ናቸው ካሉ ወደጦር ሜዳ የሚሄዱላቸውማ ጅል ይኖራል! ሆኖም ማንም ተናጋሪ ሄደው ለሚዋጉት ደደቦች የማነቃቂያ ዲስኩሩን ቢደሰኩር ፣ ምንም ዓይነት ከቦር ዓላማ እንዳላቸው ቢናገር ፣ መቼም ቢሆን መቼ ለጦርነት ምክንያቱ አንድና አድርጎ ቢናገር ፣ መቼም ቢሆን መቼ ለጦርነት ምክንያቱ አንድና አንድ ብቻ ነው ። ይኸውም ግንዘብ ነው ። ጦርነቶች ሁሉ

@OLDBOOKSPDF

የሚካሄዱት ለገንዘብ ሲባል ነው። ይህን የሚያነዘቡ ግን በጣም ጥቂት ሰዎች ብቻ ናቸው። በየቤታቸው ቁጭ ብለው ስለመርነት በሚለፍፉ አፈ— ቅቤዎች ቃላት፣ በመለከትና በነጋሪት ጩኸት ጆሮአቸው የደነቆረው አብዛኞቹ ሰዎች የሌሎችን ሀሳብ በፍፁም አያጸምጡም። አንዳንዴ ወደመርነት የሚያስሮጣቸው ጩኸት "የክርስቶስን መቃብር ከአረመኔዎች ጠብቁ" ይሆናል። አንዳንዴ ደግሞ "የጳጳሶች ሥርዓተ መንግሥት ይውደም!" ይባላል። አንዳንዴም "የነፃነት ያለህ!" ተብሎ ይጮሃል። ደሞ ሌላ ጊዜ "ጥቃ፣ የባርያ ሥርዓትና የሀገሮች ነፃ ነት!" ይባላል።

"አሁን እዚህ ውስጥ ጳጳሱን ምን አገባቸውና ነው? የክርስቶስን መቃብር ከኛ ጋር ምን ያገናኘዋል?" አለች እስካርሌት በልቧ።

እስካርሌት ወደተናደዱት ሰዎች እየተጣደፈች ሳለች ሬት በትህትና እጅ ነስቶ ብሕዝቡ ማህል ወደበሩ ሲያመራ አየችው። ልትከተለው ሞክራ ነበር። ነገር ግን ወይዘሮ ኤልሲንግ ቀሚሷን ጐትተው አስቀሯት።

"ተይው ይሂድ" አሉ ወጥ ያለውን ከፍል በሚሞላ ግልጽ ድምፃቸው። "ተይው ይሂድ። ይሄ ክሀዲ፣ ስግብግብ ነጋዴ! አጠቃችን መህል የትኛ አባብ አት ነው!"

ሬት አፈራሹ ውስጥ ባለበት ቆም ብሎ ባርኔጣውን በእጁ እንደያዘ፤ እንዲሰማ ጮክ ብለው የተናገሩትን ነገር በታዛዥነት ካዳመጠ በኋላ ሬትን እዙሮ ቤቱን እንድ ጊዜ በዐይኑ ገርመም አድርጎ ጠረገና ወደወይዘሮ ኤልሳ ጡሮች ተመልከቶ ድንገተኛ ሳቅ እየሳቀ እጅ ነሰጎ ወጣ።

ወይዘሮ ሚሪዌዘር በወይዘሮ ፒቲፓት ሠረገላ ወደቤታቸው እየሄዱ ሳሉ፤ ሌሎቹ ሶስቱ ሴቶች ግና በደንብ ተደላድለው እንኳ ሳይቀመጡ፤ አንድ ጊዜ አምባረቁ፡-

"ያውልሽ እንግዲህ ወ/ሮ ፒቲፓት ሐሚልተን፣ ጥጋሽን አገኘሽ አይደለም ታዲያ!

"ለምኑ?" አሉና ጮኹ ወይዘሮ ፒቲ ነገሩን ለማወቅ በመፈለግ ስሜት።

"ስለዚያ በትለር ስለምትይው ርካሽ ሰው ፀባይ ነዋ! ጨዋ ነው ስትይው አልነበር?"

ወይዘሮ ፒቲፓት እንዳንድ ነገር ተርገፈገፉ። ወ/ሮ ሚሪዌዘር፤ እራሳቸው ሬት በትለርን ደጋግመው ራት እንዳልጋበዙት ሁሉ አሁን

@OLDBOOKSPDF

በሱ ጉዳይ ያርሶ መቃሸና ክሳሽ ሆነው መሳደባቸው ወ/ሮ ፒቲፓትን ከፉኛ አናደዳቸው። እስክርሌትና ሚሳኒም ያሰበት ይሄንኑ ነበር። ነገር ግን በታላላቆቻቸው ጉዳይ ውስጥ ጣልቃ እንዳይገቡ የጨዋ አስተዳደጋቸው ገታቸው። በዚህ ምትክ አቀርቅረው የእጅ ጓንቲም ቻቸውን ዝም ብለው ይመለከታሉ።

"የሰደበው እኛን ሁላችንንና ኮንፌዴራሲዎንም ነው" አሉ ወ/ሮ ሚሪዊዘር። ከሚደብለጨልጨው የእንባት ጊጣቸው ሥር ያለው አጭሩ ደረታቸው በትንፋሻቸው ኃይል ከፍ ዝቅ ይላል። "የም ንዋጋው ስንበብ ብለን ነው ይበል! መሪዎቻችን ዋሽተውናል ይበ ሉን፣ እወሀኒ መግባት አለበት። መታሠር አለበት። አምን አሥራት ይገባዋል። ስለዚህ ነገር ዶክተር ሚድን አነጋግረዋለሁ። ወይኔ አቶ ሚሪዊዘር በህይወት በኖረ ጥሮ ያሳየው ነበር! አሁን ፒቲ ሐሚልተን ስሚኝ። ሁሉተኛ ያ ጥጋ ቢስ ሰውዬ በርሽን እንዳይረግጥ!"

"እዬ" አሉና አጉተመተሙ ወ/ሮ ፒቲ፣ ረዳት በማጣትና ምነው ሞቼ ባረፍኩት የሚል ስሜት እየታየባቸው። ዘወር ብለው ወዳቀረቀሩት ሁለት ሴቶች በሉመና አይን አዩና እንደገና ሌላ ተስፋ ፍለጋ መደአጎት ጥቁር ቀጥ ያለ ጀርባ ተመለከቱ። እያንዳንዷን የውይይቱን ቃል እንዳያመልጠ ስለሚደውቁ ዘወር ብሎ ውይይቱ ውስጥ ገብቶ እንደወትሮው ይናገራል ብለው ተስፋ አድርገው ነበር።

"አሁን እንግዲህ ወ/ሮ ዶሲ፣ ወ/ሮ ፒቲን ሰቀቅ ያርጓት" ብሎ ይናገራል ብለው ተስፋ አደርገው ነበር። ጥቁር ግን ካለበት ቅስቀስም አላለ። ፊት በትለርን ይቃወመዋል። ወ/ሮ ፒቲም ይህን ያውቃሉ። በረሸው ተነፈሱና "መቼም ዶሲ፣ እንዲህ ካሰብሽ..."

"አስባለሁ እንጂ" አሉ ወ/ሮ ሚሪዊዘር ፍርጥም ብለው። "ግና መጀመሪያም እንዴት እሺ ብለሽ ቤትሽ እንዳስገባሽው አልገ ባኝም። ከዚህ ከዛፊው ከሰዓት በኋላ ወዲያ ግን ይሄን ሰውዬ የሚ ቀበል እንድም ጨዋ ቤተሰብ አይኖርም። በይ ሐሞትሽን ስብሰብ አድርጊና ድርሽ እንዳይል አድርጊው።"

ዘወር ብለው ወይናቸውን ሴቶቹ ልጆች ላይ ጣል አደረጉ። "መቼም ሁለታችሁ የምለውን እያስተዋላችሁ ነው።" አሉ ቀጠሉና "ምክንያቱም በክፊል ጥሩቱ የናንተም ነው። ስታችሁ ተቸብላችሁ ታል። በትህትና ግን ጠበቅ አርጋችሁ የሱ መምጣትና ዕምነተቢስ ወሬው እቢታችሁ እንደማይፈለግ ንገሩት።"

ይሄኔ እስክርሌት እንግዳና ሻካራ እጅ ኮርቻውን እንደነካው ፈረስ እመር ብላ ለመዝለል ፈልጋ ነበር። ለመናገር ግን ፈራች።

@OLDBOOKSPDF

ወይዘሮ ሜሪዌዘር ለእናቷ ሌላ ደብዳቤ ቢጽፉስ የሚለው ሥጋት አቆን ያዛት ።

"እንቺ አሮጌ አጋሰስ !" ብላ አሰበች ፤ ፊቷ በታፈነ ንዴት ቀልቶ ። "ስላንቺና ስለእመቤታዊ አስተያየትሽ ምን እንደማስብ መናገር ብችል እንዴት ያለ ፀጋ ነበር !"

"ስለአላማችን እንዲህ ያለ ስድብ ሲነገር እስከምሰማ ድረስ ፅድሜ ይኖረኛል ብዬ ፈጽሞ አላስብም ነበር ።" አሉ ወ/ሮ ሜሪ ዌዘር ፤ በጣም እየተናደዱ ። "አላማችን ትክክለኛ አላማ አይደለም ብሎ የተናገረ ማንም ሰው መስቀል አለበት! እናንተ ሁለታችሁ ሁለተኛ ከዚህ ሰውዬ ጋር ተንጋግራችኋል የሚል ወሬ ብሰማ ወዮላ ችሁ ። በእግዚሃር ሜሲዮ ምን ሆነሽል?"

ሜላኒ ጨው መስላች ። ዐይኗ ፈጥጧል ።

"እኔ ሌላ ጊዜም አናግረዋለሁ" አለች ሜላኒ በገለቅተኛ ድምጽ ።" "ከፉ ቃልም አልናገረው ። ቤቱም ቢመጣ አልከለክለውም ።"

ወይዘሮ ሜሪዌዘር በቡጢ ሆዳቸውን የተመቱ ይመስል ትንፋሻቸው ከሳንባቸው ተሟጦ ወጥቶ መተንፈስ አቃታቸው ። ወ/ሮ ፒቲ ወፍራም እሩቸውን ከፍተው ቀሩ ። አጎት ፒተርም ዘወር ብሎ በትክታ ሴቶቹን ተመለከታቸው ።

"እኔስ ሜላኒ የተናገረችውን እንዳልናገር ምን ዘጋኝ ፣ ምን ሐሞት አሳጣኝ ?" ብላ አሰበች አስካርሌት ቅናትና አድናቆት ተቀላ ቅለውባት ። " ይቺ ኮሳሳ ጥንቸል እንደወይዘሮ ሜሪዌዘር ያሉትን ሞዛዛ አሮጊት እንዴት ደፈረቻቸው ?"

የሜላኒ እጆቿ ይንቀጠቀጣሉ ፤ ነገር ግን ድፍረቷ ከዘገየች የሚ ጠሩባት ይመስል በጥድፊያ ቀጠለች ።

"ያንን በመናገሩ እኔ ክፉ አልናገረውም ምክንያቱም . . . እር ግጥ ጮክ ብሎ መናገሩ ብልግና ነው— የማይገባ ነገር ነው . . . ነገር ግን የሱ ሀሳብ . . . የአሽሌይም ሀሳብ ነው ። እናም ባሌ የሚያ ስበውን ሀሳብ የሚያስብን ሰው ቤቴን አልከለክለውም ። ትክክል አይሆንም ። "

የወይዘሮ ሜሪዌዘር ትንፋሽ ወደሳምባቸው ተመለሰና መናገር ጀመሩ ።

"ሜሊ ሐሚልተን ፤ እኔ እግዚሃር ሲፈጥረኝ እንዲህ ያለ ሸፍጥ ሰምቼም አላውቅ ፣ ከዊክስ ዘሮች ውስጥ እንድም ፈሪ ሰውኖሮ አያ ውቅም . . . . "

@OLDBOOKSPDF

"እኔ አሽሌይ ፈረ ነው አላልኩም" አለች ሚላኒ ፥ ዐይኖቿ ማብራት ጀምረዋል" እኔ ያልኩት አሽሌይ ፥ ያገላለፁ መንገድ ይለይ እንጂ የሚያስበው ካፒቴን በትለር የሚያስበውን ነው ሀሳባቸው አንድ ዓይነት ነው ማለቴ ነው ። ደሞም በየሙዚቃ ድግሱ እየዘረ ፀሳቡን እንዲማይናገር ተስፋ አደርጋለሁ ። ሆኖም ይሄንን አውን ያልኩትን ጽርልኛል ። "

አስክርሌት ሚላኒ እንዲህ እንድትል ከደብዳቢው ውስጥ የነ ፋሉት ወረጥ ነገር የትኛው እንደሆነ ስታስብ ሀሊናዋ ወቀሳውን ጀመራት ። ዴፋ ያነበበቻቸው አብዛኛዎቹ ደብዳቤዎች ነና እንደጨ ረሰች ከእለምሮዋ ጠፍተዋል ። ሚላኒ ትእምሮዋ ታውሯል ማለት ነው ብላ አምናለች ።

"አሽሌይ ያንኪዎቹን መዋጋት አልነበረብንም ብሎ ጽፎ ልኛል ። በቦር መሪዎችና በአፈቅቢ ደስኳሪዎች ተታልለን ገደል ገብተናል ብሏል ። " አለች ሚላኒ በጥድፊያ ። "ይሄ ጦርነት እኛ ላይ የሚያደርሰውን ጥፋት የሚተነ ምንም ነገር አይኖርም ብሏል ። ታላቅና ዝነኛ የሚባል ምንም ነገር የለውም—እዚህ ያለው ስቃይና እድጥ ብቻ ነውም ብሏል ። "

"እሄ ፣ ያ ደብዳቤ ፥ ለኳ ያሄንን ማልቀ ፍሯል!" አለች አስካር ሌት በሀሳቧ "እሴ እኔ በሚራሽ አላምንም " አሉ ወ/ሮ ሚሪዌዘር ፍርጥም ብለው ። " ያለውን በትክክል መተርጎም አቅጥሽ ነው ። አልገ ባሽም ። "

"እኔ አሽሌይ የሚለኝ ሳይገባኝ የቀረበት አንድም ጊዜ የለም ። ለነገረኝም ነገር የተሳሳተ ትርጉም ሰጥቼ አለውቅም ። " ብላ መለሰች ሚላኒ ፥ በቀስታ ፥ ከንፈሯ ግን ይንቀጠቀጣል ። "የሚለኝ በትክክል ይገባኛል ። እሱ የተናገረው በትክክል ካፕቴን በትለር ያለውን ነው ። የሱ ልዩነቱ የተናገረው በባለጌ ልማን ሳይሆን በጨዋ አንደበት መሆኑ ነው ። "

"እንደ አሽሌይ ያለውን ድንቅ ሰው እንደ ካፕቴን በትለር ካለው ወሮበላ ጋር ማወዳደርሽ ሳንቺ ትልቅ ሐፍረት ነው ! እንደሚመስለኝ አንቺም አላማችን ከንቱ ነው ሳትይ አትቀሪም ። "

"እኔ . . . እኔ የማስበውን አላውቅም " አለች ሚላኒ በጥርጣሬ አንጋገር ፥ ቁጣዋ እየበረደና መሸማቀቅ እየሰፈነባት ። በድፍረት ንግግሯ መፍራት ጀመረች ። "እኔ . . . እኔ ለአላማችን ልክ አሽሌይ እንደ ሚሞት ሁሉ እሞታለሁ ። እኔ እኔ እምለው ግን . . ማለቴ ይሀንን ማሰ ቡን ለወንዶቹ አተዋለሁ ። ምክንያቱም እነሱ ከኛ የተሻለ ያስባሉ ። "

@OLDBOOKSPDF

"እኔ እንዲህ ያለ ነገር በቅንጭ ብዬ አላውቅም" አሉና ወ/ሮ ማሪዌዘር ተሳለቁ "አቁም አጉት ፒተር ቤሩን አስፍከው!"

አጉት ፒተር ከጀርባው በተቀመጡት ሴቶች ውይይት ተመስጦ ከወይዘሮ ሚሪዌዘር የሠረገላ ማቆሚያ አልር ሄዶ ኖሮ ፈረሱን ወደ ኋላ መመለስ ጀመረ። ወይዘሮ ሜሪዌዘር እሳት እንደመሰሉ፣ የሴት ባርሜጣቸው ጥብጣብ ንፋስ እንደሚያዋሽቃት መርከብ ይርገበገ ባል።

"ወደረት ታዝኛለሽ" አሉ።

እጉት ፒተር ፈረሱን መጭ አሰና በአለንጋው ነረፈው።

"ወይዘሮ ፒቲን ስላናደዳቸው እናንተ ሁለት ወጣት ሴቶች ልታ ፍሩ ይገባችኋል።" አለና በለሆሳስ ተነደበ።

"እሬ አልተናደድኩም" አሉና መለሱ ወ/ሮ ፒቲ። ከዚህ ቀደም ከዚህ ባቱላል ነገር ልባቸው ረክሳ ተዘለፍልፈው የወደቁ ስለሆነ ዛሬ እስገራሚ ሆነዋል። ሚሲዮ ማርአቸት፣ እኔ እንዳልወቀስ ብለሽ ሽንጥሽን ንትረሽ ተከራክርሽ። በእውነት ወ/ሮ ዶሲን ንትሮ የሚ ይሳ ሰው ማየቴ ደስስ ብሎኛል። በሁላችንም ላይ ኤመቤት ሆናብን ትዘር አኮ። እንዴት ድፍረቱን አጣሽ እናቴ ግን ስለአሽሌይ የተና ሂደሽውን መግገር ነበረብሽ!"

"እንዴ እውነት እኮ ነው" አለች ሜላኒ ስትመልስ። ወዲያው ግልጭስ ጀመረች "እሷ እሱ እንደዛ በማሰቡ አለፍርበትም። ጦር ነቱ በሙሉ ስህተት መሆኑን ያስባል። ያም ቢሆን ለመዋጋትና ለመ ሞት ፈቃደኛ ነው። ያ ደግሞ በትክክል አምናችሁ ክምትዋጉበት ጦርነት ፣ሰለጠ ድፍረትን ይጠይቃል።"

"አረ በእግዚሃር ወ/ሮ ሚሊ፤ እዚህ ፒች ትሪ ጐዳና ላይ አይለቀስም እኮ።" አለ አጎት ፒተር በጐርናና ድምፁ ፈረሱን በፍ ጥነት እያበረረው። "ሰምኛ አንዳንድ ቅሌት ነገር መናገራቸው አይ ቀር መቹም። እስቲ እቤት እስክንደርስ ታገሱ።"

እስካርሌት ምንም አልተናገረችም። ሌላው ቀርቶ ሜላኒ እንድ ታጽናናት ብላ እጆዋ ውስጥ የከተተችውን እጅዋን እንኳ ጨመቅ አላደ ረገችውም። እሷ የአሽሌይን ደብዳቤ ያነበበችበት ምክንያት አንድ ብቻ ነው — ያፈቅራት እንደሆን ለማረጋገጥ። ሜላኒ ታዲያ እሷ እንደዋዛ ላለፈቻቸው የደብዳቤ መልእክቶች ሁሉ አዲስ ትርጉም ትሰጣለች። እንዶ አሽሌይ ያለ ፍፁም ሰው እንደሬት በትለር ከለ ወሮበላ ጋር መወዳደሩ አስደነጣት። እንዲህ ብላም አሰበች፡- "ሁለ

@OLDBOOKSPDF

ቱም ስለጦርነቱ ዕውቀነኛውን ነገር አይተዋል ። ሆኖም አሽሌይ ሊሞት ፈቃዱ ነው ፤ ሬት ግን ንክች አያደርጋትም ። በኔ ግምት የሬትን አስተዋይነት የሚያሳይ ነገር ነው ብዬ አምናለሁ ።" ስለ አሽሌይ እንዲህ ያለ ነገር ማሰቡ አስደንጋጧት ለጥቂት ቅጽበት አረፍ አለች ። "ሁለቱም ስለ ጦርነቱ አስከሬውን ዕውነት ተረድተዋል ። ሆኖም ሬት አውነቱን ግንባር ለግንባር ተፋጦ ጨበጠ ሰዎችን ለማበሳጫ ይጠቀምበታል— አሽሌይ ከዩውት ሊጋፈጠው አልቻለም ። "

በጣም እንቆቅልሽ ነገር ነው ።

@OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ 13

በወ/ሮ ሜሪዌዘር ውትወታ ዶ/ር ሚድ የሬትን ስም ሳይጠቅስ እሱን መሆኑ ግን ግልጽ በሆነ ቋንቋ ፡ በደብዳቤ አስመስሎ ጋዜጣ ላይ አወጣው ። የጋዜጣው አዘጋጅ ማህበረሰባዊ ድራማው ገብቶት ፡ ምንም እንኳ ለወትሮው የጋዜጣው የመጀመሪያ ሁለት ገጾች የባሪያ ዎች ፡ የበቅሎዎች ፡ የግረሻዎች ፡ የሬሳ ሳጥኖች ፡ የሚከራዩ ወይም የሚሸጡ ቤቶች ፡ የሻል ሕክምናዎች ፡ የማስወረጃ መድኃኒቶችና የመ ሀንነት መድሀኒቶች ማስታወቂያዎች የሚወጣባቸው ቢሆኑ ፡ የዶክ ተር ሚድን ደብዳቤ ፊት ለፊት በነዚህ ገጾች ላይ አወጣው ።

የዶክተሩ ደብዳቤ በድፍን ደቡብ በስግብግብ ነጋዴዎች ፡ በእት ራፊዎችና የመንግሥት ኮንትራት ወስደው እያምታቱ ገንዘብ በሚያ ካብቱ ሰዎች ላይ የተነሳውን ሕዝባዊ ቁጣ ያዘለ ፡ የመጀመሪያ በር መክፈቻ ነው ። ያንኪዎቹ የቻርልስተኑን የባህር ወደብ መውጫ መግ ቢያውን ስለዘጉት በሞናዋ የባህር በር በሚልሚንግተን በኩል ዕቃ ዎችን በማስገባት ፈንድ የሚሠራው የነጋዴዎች ደባና ቅሌት ጣራ ነክቷል ። ስግብግብ ነጋዴዎች የተጠራቀመ ረብጣ ብራቸውን ይዘው ወደ ዊልሚንግተን ወደብ ይመጡና በዕቃ ጠም ብለው የተሞሉትን ጀልባዎች ገና ዕቃቸው ሳይወርድ ተስማምተው ይገዙና የዕቃ ዋጋ እስኪንር ድረስ ደብቀው ያስቀምጡታል ። የተፈላጊ መሠረታዊ ዕቃ ዎች ፍላጎት እየጨመረ ስለሚሔድ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የዕቃ ዋጋ ወዲያውኑ እንደሚያሻቅብ ግልጽ ነው ። ሲቪሉ ሕዝብ ወይ ከነጭራሹ ላለመግዛት መወሰን አሊያም ነጋዴዎቹ በተመኑት ዋጋ የግድ መግዛት ይኖርበታል ። በዚህ ማህል ደሀው የሕብረተሰብ ክፍል ከፉኛ ይመታል ። ይማቅቃል ። ዋጋ በናረ ቁጥር የኮንፌዴሬሲው ገን ዘብ ምንዛሪ አዘቅት ይወርዳል ። ምንዛሪው በወረደ ቁጥር ደግሞ የቅንጦት ዕቃዎች ፍላጎት የትና የት ይደርሳል ። ኮንትሮባንድ ነጋዴ ዎች የታገዱ የእለት የሰርክ መገልገያ መሠረታዊ ዕቃዎችን እንዲያ መጡ ኮሚሽን ይቀበላሉ ። ጉቦ ይበላሉ ። አሁን ጀልባዎቻቸውን የሚ ሞላው ግን ኮንፌደሬሲው የሚፈልገው መሠረታዊ ዕቃ ሳይሆን በጣም ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው የቅንጦት ዕቃዎች ናቸው ። ሰውም ምርጫ ስለሌለው ነገ ዋጋዎች የበለጠ እንደሚንሩና የገንዘቡም የመግዛት

@OLDBOOKSPDF

አቅም ስለሚደክም ከናካቴውም ዋጋ ሊያጣ ስለሚችል ያለ የሱስ ገንዘቡን አውጥቶ የቅንጦት እቃዎቹን በውድ ዋጋ ይገዛል።

ነገሩን የበለጠ ያከፋው ደግሞ ከዊልሚንግተን ወደብ ወደሪች ሞንድ የሚሔድ አንድ የባቡር ሐዲድ ብቻ መኖሩ ነው። በቪ የሚ ቆጠር የበርሜል ዱቄትና የታሸገ የአሳማ ሥጋ በትራንስፖርት እጥረት በየመጋቢ መንገዱ አቅራቢያ በስብሶ ሲቀር፤ የነጋዴዎቹ የወይን ጠጅ፣ ውድ ጨርቅና ቡና ግን ዊልሚንግተን ወደብ በገባ በሦስት ቀን ጊዜ ውስጥ በየት እንደሚመጣ ሳይታወቅ ሪችሞንድ ይገባል።

ዱሮ ውስጥ ውስጡን ሲታማ የነበረው ሁሉ አሁን ይፋ ወጣ። ሬት በትለር የራሱን አራት ጀልባዎች ማንቀሳቀስና የጫነውን ሸቀጥ ታይቶ ተሰምቶ በማያውቅ ዋጋ መሸጡ ብቻ ሳይሆን የሌ ሎች ጀልባዎችን ዕቃ እየገዛ በማስቀመጥ ዋጋው እስኪንር እንደሚ ጠበቅ በይፋ ደመራ ጀመር። የዊልሚንግተንን ወደብ እንደዋና የን ግድ መናኸሪያ አድርጎ የታገዱ ዕቃዎችን ጥና ከተጫኑበት ሳይራ ገፉ ለመጣት ከአንድ ሚሊዮን ዶላር በላይ የሚገመት ገንዘብ የነጋዴዎች ጣምራ ሽርክና መሪ ሆኖ አስቀምጧል የሚለው ወሬ እየ ገነነ ሄዷል። በዚች የወደብ ከተማና በሪች ሞንድ በደርዘን የሚቆ ጠሩ መጋዘኖች ያሏቸው ሲሆን የዋጋን መናር የሚጠብቁ በርካታ ልብሶችና የምግብ ሸቀጣ ሸቀጦች ጢም ብለው ሞልተውባቸዋል። ካሁኑ ወታደሩና ሲቪሉ ሕዝብ የችግሩ ቁንጮ እየተሰማው ስለመጣ በሬት በትለርና በመሰሎቹ ላይ ማጉረምረምና ጥርስ መንከስ ጀም ሯል።

"በኮንፌዴሬሲው የባሀር ኣገልግሎት በኩል ባለው የታገደ ዕቃ የማሻገር ሥራ ብዙ ጀግኖችና በአርበኝነት ስሜት የተሞሉ ሰዎች አሉ" ይላል የዶክተሩ ደበዳቤ የመጨረሻ ክፍል። "የኮን ፌደሬሲውን ሕልውና እስካቆዩ ድረስ ሕይወታቸውንና ሀብታቸ ውን በሙሉ አደጋ ላይ ጥለው የሚጣጣሩ ራስ ወዳድ ያልሆኑ ሰዎች አሉ። እነዚህ ሰዎች በሁሉም ታማኝ ደቡባዊያን ልብ ውስጥ ታትመው የሚኖሩ ናቸው። እንዲህ ሕይወታቸውን ከሞት አፋፍ ጥደው እየለፉ ማንም ቢሆን የገንዘብ ከፍያቸው ላይ ጭቅጭቅ አይ ፈጥርባቸውም። ራስ ወዳድ ባለመሆናቸው እናከብራቸዋለን። ስለ ነዚህ ሰዎች ምንም የምናገረው የለኝም።

"ይልቁንስ የታገደ ዕቃ በማሻገር ስም የራሳቸውን ጥቅም የሚ ያሳድዱ ወሮበሎች አሉ። ሰዎቻችን በየጦር ሜዳው የእንዲት ኪኒን እንክብል ጠፉ ይዟቸው ሲንጨፈረሩ፣ እነሱ የሙሽራ ልብስና ጌጣ

@OLDBOOKSPDF

ጌጥ የሚያመጡ፡ ወገኖቻችን የቁስል ማዶንዘኛ አጥተው ሲያልቁ ለአውነተኛ አላማችን ሲወድቁ ፡ እነሱ ጀልባዎቻቸውን በሻይ ቅጠ ልና በወይን ጠጅ ሞልተው ሲመጡ የሚታዩ የሰው ጥንብ አንላዎች ላይ የበቀል እርምጃ እንዲወሰድባቸው እጠይቃለሁ ። ከሮበርት ሲ ጋር የዘመቱ ጀግኖቻችንን ደም እንደጭራቅ የሚመጡና የታገደ ዕቃ የማሻገርን የኮንትሮባንድ ሥራ እንዲጠላ የሚያደርጉ ሌቦች እንዲ ባረሩ አጠይቃለሁ ። ልጆቻችን በባዶ እግራቸው በየጦር አምባው ሲባዝኑ እነዚህ ነጋዴዎች የተወለወለና ሬት የሚያሳይ የቆዳ ቦት ጫማ አድርገው እማህላችን ሲዘባነኑ እንዴት ያስችለናል? ወታደ ሮቻችን እሳት አጥተው በብርድ ሲንቀጠቀጡ እነዚህ በላኤለቦች ሻምፓኝ እያፈሰሱ ሲዝናኑብን እንዴት ችለን እንቀመጥ ? እነዚህን ወሮበሎች ከአገር እንዲያስወጣቸው እያንዳንዱን የኮንፌደሬሲ አባል በትክክለኛው ዓላማችን ስም አጠይቃለሁ ። ”

የአትላንታ ሕዝብ ጋዜጣውን እንብቦ ትንግርቱ መነጉሩ ገባው። እንደማንኛውም ታማኝ የኮንፌደሬሲው አባልም ሰው ሁሉ ሬት በትለርን ሚገለል ጀመረ ።

በ1862 ከረምት ተቀብለው ያስተናግዱት ከነበሩት ቤተሰቦች ሁሉ በ1863 በሩን ያልዘጋቤት አንድም የለም— ከወ/ሮ ዊቲፓት ቤት በስተቀር ። ወ/ሮ ዊቲፓት ቤት አሁንም እንደልቡ ይገባል ይወ ጣል ። እዛም ቢሆን ሚሳኒ ባትኖር ኖሮ ተቀባይ አያገኝም ነበር ። ወ/ሮ ዊቲፓት አሱ ከተማ አለ በተባለ ቁጥር ጨና አይሰማቸውም ። አሱ ወደ ቢታቸው እንዲመጣ በጋበዙት ቁጥር ጓደኞቻቸው ምን እንደሚሏቸው አሳምረው ያውቃሉ ። ነገር ግን ወይድ አንተን የሚ ያስተናግድ ሰው ከእንግዲህ አይኖርም እንዳይሉት አሁንም ድፍረቱ ያንሳቸዋል ። አሱ አትላንታ ከተማ ገባ በተባለ ቁጥር ሣሬስ እቤቱ አሳስገባውም ከበር ነው የምመልሰው እዚያው እደጃፉ ላይ ሰላም ብዬ እመልሰዋለሁ እያሉ ለሴቶቹ ያወራሉ ። አሱ በእጁ ትንሽ የተ ጠቀለለ ነገርና በአፉ ቁንጮና ቸውንና ደም ግባታቸውን የሚያሞካሹ ቃላት ይዘሳቸው ብቅ ሲል ፉከራቸው ሁሉ ይሚሟጠጥባቸዋል ።

“እንደው ምን እንደማደርግ ቸግሮኛል” ይላሉ እያቃሰቱ ። “ዝም ብሎ አትኩሮ ሲያየኝ፡ እንደው አቡዬን ፤ ብናገረው መቃብ ሬን የሚያቀርበው እየመሰለኝ ፍርሃት ይወረኛል ። ለራሱ አርጉም ጥሩረት እንደሆነ ታውቃላችሁ ። ግን ብናገረው የሚመቃኝ ወይም... ወይም ውይ የኔ እመቤት ምነው ቻርሊዬ በሕይወት በኖረ ኖሮ! አስካር ሌት ሁለተኛ እንዳይመጣ አስቲ አንቺ ንገሪው ። እንደው ጥፍጥ ባለ የጨዋ አማርኛ ቀስስ ብለሽ ንገሪው ። ወይኔ ጉዴ! መቼም እንቺው

@OLDBOOKSPDF

እያበረታታሽው እንዲሚመጣ አምናለሁ ። ከተማው በሙሉ ነው የሚያወራብሽ ። አሁን እናትሽ ብትሰማ ምን ትለኝ ሚለ ለሱ ሰውዬ ፊት ባትሰጭው ጥሩ ነው ። ፊት ነስተሽ ራት ብትይው ይገባዋል ። ሜሊዬ ፡ ለሐንሪ ካየቱን በትለርን አነጋግረው ብዬ ልፃፍለት ይሆን ?

"የለም እኔ አላደርገውም" አለች ሚላኒ ። "ክፉ ቃልም አልናገረውም ። እንደሚመስለኝ ሰዉ የካፒቴን በትለር ነገር ሲነሳ እንደታረደች ዶሮ ይንደፋደፋል ። እርግጠኛ ነኝ እሱ ፡ ዶክተር ሚድ እንደሚለውም ሆነ ወ/ሮ ሜሪዌዘር እንደሚሉት መዋፎ ሰው አይመስለኝም ። ምግብ ከተራቡ ሰዎች አይነጥቅም ። አይደብትም ። እንዲሌላው ቀርቶ ለሰዉት ልጅች ማሳደጊያ መዋሪ መቶ ዶላር ሰጥቶ ኖል እኮ ። እሱም እንደኛው ታማኝ እንደኛው የአርበኝነት ስሜት ያለውና አራስን በክራት ስመከላከል የሚችል ሰው ነው ። ወንዶች ሰው ሲያማቸውና ከጅርባ ሆኖ ሲሸረድዳቸው የሚሰማቸውን ስሜት አስቡ ።" ወይዘሮ ፕሪቻት ስለወንዶች የሚያውቁት ነገር ስለሌለ ከጅርባቸው ሲታመም ሆነ በፊት ለፊት ሲነገራቸው ምን እንደሚሰማቸው ስለማይረዱ እንደው ዝም ብለው ቁፋፍር እጅጎቸውን ያወራጫሉ ። እስካርሌት ጌና ዱሮ የሚላኒን ቢሰው ሁሉ ደህና ነገር አያለሁ እያሉ መፍጨርጨር ስላለመኖሯት ነገር ዓለሙን ትታዋለች ። ሚላኒ ጅል ናት ። ነገር ግን ግንም ምንም ሊያደርግ የማይችለው ነገር ነው ።

እስካርሌት የራትን የአርበኝነት ስሜት ያለመኖር አሳምራ ታውቃለች ። ምንም እሳኳን ይሆን ከምታምን መሞትን ብትመርጥ ለጉዳዩ ግን ደንታ የላትም ። ስሕሏ ደንታ የሚሰጣት ከናሱ ድረስ የሚያመጣሉት ትሩንሽ ስዘታዎችና ስሌት ልጅ አስፈላጊ የሆኑት ዕቃዎች ናቸው ። እውነት አሁን ጅልነት ካልሆነ በስተቀር ብትፈርጥ ብትነሳ የማታገኛቸውን እንደ መርፌዎች ፡ ከረሜላና የፀጉር ማሲያገር የመሳሰሉትን ነገሮች የሚያመጣሉትን ሰው እቤቱ አትግባ ብላ በዛሬ ኑሮ ውድነት ከየት አባቷ ልታመጣ ነው ? የለም ይሆንን ጉዳይ የቤቱ ባለቤት ፡ ሞዝቤትና የግብረገብነት ዳኛ ለሆኑት ለወይዘሮ ፒቲ ፓት አስተላልፉ ብታርፍ ይሻላታል ። እስካርሌት ከተማው በሙሉ ስለፊት በትለር እቤቷ መምጣትና ስለእሷም ጭምር እንደሚያማና እንደሚያወራ በደንብ ታውቃለች ። በአንፃሩ ግን በእትላንታ ሕዝብ ዓይን ሚላኒ ዊክስ ምንም ዓይነት ስህተት ትሰራለች ተብላ የማትጣ መት ናት ። ስለዚህም ፊት በትለርን ሚላኒ የምትከላከልለት ከሆነ የሱ እቤት መምጣት የክብር ተቀባይነት እንዳገኘ ይቆያል ።

ወጣም ወረደ መቼም ፊት ከጎተረባው ከነአሽሙሩና ከነስድቡ አጠገቧ ቢኖርላትና ይሄን በግልጽ አገር የሚያውቀውን ነገር ቢተው

@OLDBOOKSPDF
እሷ የበለጠ ደስታን ታገኛለች ። በፒትሪሪ ጉዳና አብራው ስትሄድ በግልጽ ሲሰደብ የሚሰማትም ብስጭት ይቀርላት ነበር ።

"እንደዚህ ያሉትን ነገሮች ማለቡን እስብ ፡ ግን ለምን ትናገራ ቸዋለህ?" አለችው በስድብ ዓይነት ቃና ። "የፈለግኸውን ደስ የሚል ህን ነገር ለማሰብ ትችላለህ ነገር ግን አፍህን ዘግተህ ብትቀመጥ ሁሉ ነገር ተስተካክሎ በጣም ግሩም ኑሮ እንኖራለን ። "

"ያ እንኳ ያንቺ ሥርዓተ ማኅበር ደንብ ይመስለኛል ፡ የኔ ዓይ ናማ አስመሳይ ፤ አይመስልሽም ? አስካርሌት ፡ አስካርሌት ከዚህ የተሻ ለና በድፍረት የተሞላ በሳይ እኮ ነው ካንቺ አገኛለሁ ብዬ ተስፋ የማደርገው ። እንደሚመስለኝ የእየርላንድ ተመላጆች የሚሰማቸውን ፊት ለፊት ይናገራሉ ። ዴቪሎች ደግሞ የተነገራቸውን ሁሉ ይቀ በላሉ ። እስቲ እውነቱን ንገሪኝ አስካርሌት ፡ አንዳንድ ጊዜ አፍሽን ዘግተሽ በመቀመጥሽ ምክንያት ልትፈነጂ አትደርሺም ?"

"እሱስ አዎ" አሰኙ አስካርሌት ያሳትን ያለፈቃዷ በማመን ። "ስለአላማችን ሴት ተቸን ሲያወሩ ስልችት ይለኛል ። ግን ፊት በትለር ፡ እንደታከተኝ ብነግራቸው አንዳቸውም ከኔ ጋር አያወሩም፡ ማንኛዎቹም ወንዶች ከኔ ጋር አይደንሱም ። "

"አዎ ፡ መደነስ ደግሞ የሚድ ነው ። ራስሽን ለመቆጣጠር መቻል ሽን እደንቃለሁ ። ካንቺ እኩል መሆን አልችልም ። ስለ አገር ፍቅርና ስለ ጀግንነት የምቆረቆር እንዲሁም መልካም ፍቅር አሞቂ በመሆ ሰል የበግ ለምድ መልበስም አልችልበትም ። እርግጥ እያንዳንዷን ሳንቲም መስዋዕት እያደረጉ በማሻገሩ ንግድ የተሰማሩና ከጦርነቱ በኋላ ከስረው ሙልጫቸውን የሚወጡ በቂ ግብዝ ጀግኖች አሉ ። እኔ አላስፈልጋቸውም ። እኔ ከጀግኖቹ ጋር በመጻፍም የአገር ወዳዶ ቹን ቁጥር ለማብዛትም ሆነ የመናጢ ድሆቹን ቁጥር ለመጨመር አስፈላጊ አይደለሁም ። እንደፍጥርጥራቸው ብድሩ ይድረሳቸው ፡ ዋጋ ቸው ነው ። አንድ ጊዜ በጣም በቅንነት ሳገለግል ነበር ግን ወርቅ ላበደረ ጠጠር እንዲሉ ዋጋዬ ያ ሆነ ። እናም ምን አለ በይኝ በዓ መት ውስጥ ዋጋቸውን ያገኛሉ"

"ውይ በጣም የማትረባ ነህ ፤ እንግሊዝና ፈረንሳይ ከኛ ጎን በቆመበት ባሁኑ ሰዓት ይሄን መናገርህ በጣም ያስጠላል . . . "

"እየሽ አስካርሌት እስኪ አሁን ጋዜጣ ላይ ማንበብ ነበረብሽ ፡ ትገርሚኛለሽ !ለሁለተኛው በደንብ አንብቢ ። ጋዜጣ የሴቶችን ጭንቅ ላት ያሾረዋል እኮ ፡ ለማንኛውም እንድታውቂው ያህል ከወር በፊት እንግሊዝ አገር ነበርኩና ልንገርሽ ። እንግሊዝ ብትሞት ኮንፌደሬሲውን

@OLDBOOKSPDF

አትረዳም። እንግሊዝን እንግሊዝ ያደረጋትም ይሽው ነው። በዚህ ላይ የእንግሊዝ ዙፋን ላይ የተቀመጠችው የድኾ ሴት ፈሪሃ እግዚ አብሄር ያደረባት በመሆኑዋ የባሪያ ግሾን አትደግፍም። የእንግሊዝ የፋብሪካ ሠራተኞች ቢሻቸው በረሃብ ይሙቱ፣ ጥጡም ባይጣ ይትር እንጂ ለባሪያ ግዝ ቅንጣት ድጋፍ አይሰጡም። ፈረንሳይንም ካነሳሽ ያ በናፖሊዎን የወጣ መሪያኞው ሚክሲኮ ውስጥ የሚያ ሰሯቸውን ፈረንሳዮች በማረጋጋት ሥራ ተጠምዷልና ስለኛ ለመ ጨነቅ ጊዜም የለውም። እርግጥ ጦርነቱ መሞሩ ደስ ይለዋል። ምክ ንያቱም ሠራዊቶቹን ከሚክሲኮ እንዳናስወጣበት ይረዳዋል። የለም የለም እስካርሌት ፡ የውጪ ኦርዳታ ነገር የሞተ ጉዳይ ነው። ጋዜጣ ቻኙሁ የደቡቡን ሕዝብ ሞራል ለመጠበቅ የሚነዙት ፕሮፓጋንዳ ነው። ኮንፌዴሬሲው አልቆለታል። እንደማመል ሻኛውን እየበላ ነው እስትንፋሱ የቆየው። እንደምታውቂው ደግሞ በመጨረሻ ትልቁ ሻኛ ውስጥ የተከማቸ ምግብ እንኳ አሳቂ ነው። እኔም ከእንግዲህ ወዲያ ማፋ ቢል ለፅ ወራት ነው የማሸገሩን ሥራ ብሠራ። ከዚያ በኋላ እተዋለሁ። ምክንያቱም ከዚያ በኋላ በጣም አስጊ ሁኔታ ይፈ ጠራል። የንግድ ጀልባዎቹንም ላንዱ ምሌ ኑኛ ስሚል ጅል እንግሊዛዊ አሸጥና እገላገላለሁ። ብቻ ያም ሆነ ይህ፡ ይሄ የሚያስጨንቀኝ ጉዳይ አይደለም። በቂ ገንዘብ ያውም በወርቅ እንግሊዝ ባንክ ውስጥ አከ ማችቻለሁ። ችግር የለም። ይሄ የወረቀት ብር አይረባኝም።"

እንደተለመደው ሚድ የለሽ ሆኖ ነው የሚናገረው። ሌሎች ሰዎች የሚናገረውን ነገር ሸፍጥና ሌብነት ነው ይላሉ። ለእስካርሌት ግን እውነትነቱና ቁምነገርነቱ ይታያታል። ግን ተገቢው መን ገድ እንዳልሆነ አውቃለችና ደንግጣለች። ከልቧም ባይሆን ታስመስ ላለች። እንደጨዋ ሴት እንድታስብ ግን አድርጓታል።

"ዶክተር ሚድ ስላንተ የጻፈው ልክ ነው ማለት ነው ካፕቴን ሬት። ራስህን ለማዳን የምትችለው ጀልባዎችህን ከሸጥክ በኋላ ወደ እኛ በመመለስና የበደልከውን በመክሰ ነው። የምዕራብ ሰው ስለ ሆንክና ...."

"እስካርሌት፣ ምዕመናን ለመመልመል የሚሰብክ የባፕቲስት ካህን መሰልሽኝ አሁንስ። ራሴን ለማዳን ንስሀ አልገባም ብልስ ባይተዋር ያረገኝን ሥርዓት፣ ያልተቀበለኝን ሥርዓት የምቀበልበት ምን ምክንያት አለኝ? እንደውም ድምጥማጡ ቢጠፋ ደስታዬ ነው።"

"እኔ እንዲህ ያለ ሥርዓት አላየሁም" አለች በመስቀልያ መንገድ።

"እረተይ ባታይውም በውስጡ እየኖርሽ አግልሎሻል። እን ደኔ ማለት ነው። እኔ ከምጠላው ያነሰ አትጠይውም ደግሞ። ከበት

@OLDBOOKSPDF

ልር ቤተሰብ የተባረኩት እንጂ ያመለጣቸልን ለቻርልስተን ሥር
ዓት ማኅበር እጅ አልነሳም አልጣጣምም ብዬ ነው። ቻርልስተን
ደግሞ ከዚህ ከደቡቡ የባሰ ነው። ምን ያህል እንደሚታክት አውንም
የተረዳሽው አይመስለኝም። ብዙ ሲሠሩ የነበሩና የተለመዱ ነገሮ
ችን የሚድሽን ቱቀበይ ይሉሻል። ጉጂ ያልሆኑ ብዙ ነገሮች አሉ።
ግን ማንም ያለምክንያት እንዳይሠራቸው ተደርጓል። ምንም እርባና
የሌላቸውና ሲሠሩ ሳይ የሚያናድዱኝ ሞልተዋል። ያቺን ቤትዮ
ኤላንባም በማለቴ የደረሱብኝም ከነዛ ሁሉ በጣም ትንሹ ነው። ሽር
ሽር ከወሰድኳት በኋላ ባጋጣሚ ምክንያት በማዜ መደቤቷ ስላልመለ
ሰኳት ብቻ የማትሞመኝን ጅላጅል ሴት የማገባበት ምን ምክንያት
አለ፣ ደሞስ አንጣጣሪ ሆኜ ሳለ ያ እንድ አይና ወንድሚ ልግደልሀ
ብሎ ሲቃጣ እንዴት ዝም ብዬ ልሙት ነ እርግጥ ባንሩ ባሀል ደንብ
ገሎኜ ባርፍና ስሜን ብጠብቅ ደህና ነበር ይባል ይሆናል። ግን መኖር
እፈልጋለሁ። ስለዚህ በተድላና በደስታ ኖርኩ . .

"ወንድሜ በቻርልስተን የሞሀ በጎች ማሀል ተጥዶና ተግባብቶ፣
ሚስትና ቤት አበጅቶ፣ የሩገ እርሻ አስቱፍቶ መሞሩን ሳይ ክሲቸዋል
እላለሁ። አየሽ አቨባርሴት፣ የዚህ የደቡቡ አኗኗራችን ያረጀ ያፈጀ
በመከከለኛው ክፍለ በመን የንበረና የፊውዳል ዓይነት ነው። የሚ
ገርመው እስኩን መቆየቱ ነው። አውን ግን በቅቶታልና መፍረሱ
ነው። ያም ሆኖ እኔ ዶክተር ሚድ ዓለማችን ትከከለኛና የተቀደሰ
ነው እያሉ ሲደሰኩሩ ከለመንክ ትይኛለሽ፣ ደግሞስ መለከትና ሞሩ
ምባ በተነሱ፣ አቃም በተደሰቀ ግንባል ብዬ የጦር ልብስ ለብሼ
ወደ ቨርጂኒያ ሄጀ ደሜን የማፈሰ ይመስልሻል፣ ያውም እንማርስ ሮበ
ርት ከሚመሩት ጦር ጋር ነሞኜ እመስልሻለሁ ልበልነ የነከሰኝን መሳም
በዘራም የለብኝ። እምኑቴም አይደለም። ይልቅስ ደቡብና እኔ አቻ ለአቻ
ነን። የደቡቡ ሥርዓት ማህበር አገልግሎት ለረሀብ አጋልጦኝ ነበር።
እኔ ግን አልተራብኩም። እንደውም ደቡቡ እየወደቀ ሲሄድ ከመቃ
ብሩ ሳይ በቪህ የሚቆጠር ገንዘብ በማኳበት የተኔፈገኝን የዜማነት ብድር
ከፈልኩኝ።

"እኔ የማትረባና ትጥረኛ ነህ ብዬ አስባለሁ" አለች እሰካ
ርሴት። የሰጠችው አስተያየት በጣም ፈጣን ነው። አብዛኛው የተና
ገረው ነገር ሞንትላኒ ጉብቷል። ማናቸውም አሷን የሚመለከት ነገር
ሁሉ እንደሚገባት ሁሉ ይሄም ቶሎ ገባት። ስሜት የለጣት ግን
በጣም ጥቂቱ ነው። በሕይወት ላይ የሚከሰቱ በጣም ብዙ ጅላጅል
ነገሮች አሉ። ለምሳሌ ልቧ እመቃብር የገባና በጣም ያዘንች በመ
ምሰል መታየት አንዱ ነው። እያንዳንዱ ሰው እነዛሩ ላይ ሰት
ደንስ ድንጋጤ ሊገድለው እንደነበር ማየትም ሌላው የየይስሙላ

@OLDBOOKSPDF

ነገር ነው ። ማንኛዋም የአገሩ ሴት ከምታደርገውም ሆነ ከምትና ገረው ነገር የተለየ ማድረጓና መናገሯ ሕዝቡን ከመቀመጫው ማስ ነሳቱም አንዱ ልዩ ጉዳይ ነው ። ያም ሆኖ ግን እስካሁን እሷን የሚ ያናድዳትን ባህልና ልማድ ሲተች እንኳ ከመበሳጨት ወደኋላ አላ ለችም ። እሷ የምታስባቸው ነገሮች በቃላት ሲገለጹ በመስማት እንዳ ይረበሹ ከሚፈልጉ ሰዎች ማህል ለረጅም ጊዜ ኖራለች ።

"ቅጥረኛ አልሽ ? የለም ፣ ምንም እንኳን የቅጥረኝነት ምልክት ቢሆን አርቆ አስተዋይ ብትይኝ ይሻላል ። ቢያንስ እንደኔ አርቆ አስ ተዋይ ያልሆኑ ሰዎች ሊሉ የሚችሉትን በይ ። ማንኛውም የኮን ፌዴሬሲው አባል በ1861 በሺህ የሚቆጠር ብር ቢኖረው ኖሮ እኔ ያደረኩትን ነው የሚያደርገው ። ግን ይህን የቅጥረኝነት ዕድል የተጠቀመበት አፍኝ አይምሰም ። ለምሳሌ ፎርት ሰምተር እንደወ ደቀና የዕቃዎች አገዳ ከመጀመሩ በፊት በጣም በርካሽ ዋጋ ጥጥ ገዝቼ ወደ እንግሊዝ ላክት ።

እስካሁን በሊቨርፑል መጋዘኖች ውስጥ ታምቆ ይገኛል ። አልሸ ጥኩትም ። ዋጋው እስኪወደድና የእንግሊዝ ኢንዱስትሪዎች እስክ ሚፈልጉት አቅየዋለሁ ። እንዴን ታውንድ በእንድ ብርም ብሸጠው ግድ የለኝም ። "

"እንድ ታውንድ በእንድ ብር ሂሳብ የምታገኘው ውቅያኖስ ሲደርቅ ነው ። እይምሰልህ" አለችው ።

"እንደማገኝ አልጠራጠርም ። አሁን እንኳ አንዱ ታውንድ ሰባ ሳንቲም ገብቷል ። ይሄ መርጎት ሲያልቅ በብር የበሰበሰ ባለፀጋ እሆ ናለሁ ። ይኸውም አርቆ አስተዋይ ፣ ይቅርታ ቅጥረኛ በመሆኔ ነው ። ገንዘብ የሚገኘውና መከበር የሚቻለው አንድም አገር ስትለማ አን ድም አገር ስትጠፋ ነው ። አገር ስትለማ ቀስ በቀስ መከበር ይቻ ላል ። አገር ስትጠፋ ግን በአንድ አፍታ መከበር ይቻላል ። ይህንን ቃሌን አትርሺ ። ምናልባት አንድ ቀን ይጠቅምሽ ይሆናል ። "

"ጥሩ ምክር መስማት ደስ ይለኛል ። አደንቃለሁ ። " አለች እያ ሾፈች ። "ግን ያንተ ምክር አያስፈልገኝም ። ለመሆኑ አባቴ ደሀ መሰ ለህ እንዴ ? የምፈልገውን ያህል ገንዘብ ካባቴ አገኛለሁ ። በዛ ላይ ከቻርለስ የወረስኩት ንብረት አለ ። " አለች ።

"እንደመሰለኝ የፈረንሳይ መሳጭነትም ተንኮታኩተው እስኪ ወድቁ ድረስ ልክ እንዳንቺ ነበር የተመጻደቁት " አላት ።

ሬት አልፎ አልፎ በማጎበረሰቡ የአገልግሎት ሥራ ስትጠመድ ጥቁር መልበሱን ቅተወው እንደነበር ጠቅሶ ነግሯታል ። ሬት ፈካ ያለ

@OLDBOOKSPDF

ቀለም ስለሚወድ ይህን የሐዘን ልብስዋንና ከራስ ፀጉሯ እስከ እግር ጥፍሯ ማቅ ለብሳ ሲያያት ታስቀይመዋለች ። ትገርመዋለችም ። እሷ ከጥቁር ልብሷ ጋር የሙጥኝ ብላለች ። እንዳትተወው ከባሷ ሞት ወዲያ ጥቂት ዓመታት ሳትቆይ ካወለቀችው ሰራሷ አውንም ስማ አላማረ አገር ጉድ ይላታል ። ደሞስ የሌላውስ ይቅር ለእናቷ ምን ብላ ልታስረዳ ነው ?

ሬት ግን ይሄ የሐዘን ልብሷ ቁራ እንዳስመሰላት ግልጽ ኦዲ ርጎ ከመንገሩም በቀር ጥቁር ልብስ ከአሁኑ ዕድሜዋ በአሥር ዓመት አ ያረጀች እንደሚያስመስላት አስረድቷታል ።

ልክ ይሄን ሲላት ከፉኛ ስሜቷን ነካትና በእርግጥ የአሥራ ስምንት እመቷ ኮረዳ የሃያ ስምንት ዓመት ሴት ሆና እንደሆን ለማረጋገጥ ወደ መስተዋቱ በረረች ።

"እንደሚመስለኝ እንደወይዘሮ ሜሪዌዘር አሮጊት ለመምሰል የም ትሞክሪበት ምክንያት አይታየኝም ።" አለ ። "ይልቅ ላልተቀበልሽውና ከልብሽ ላላወጋሽለት ባልሽ የሐዘን ማስታወቂያ ለጥፈሽ ከምትሠሪ ሌላ ልብስ ብትሞክሪ ይሻላል ። እኔ አተባበርሻለሁ በዚህ በኩል ። ምን አለ በይኝ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ይህንን በጥቁር የተከፈፈ የፀጉር ጌጥሽንና የሐዘን ልብስሽን ከራስሽ አውልቂ ፓሪስ የተሠራ አዲስ ጌጥ አንሳድፍሻለሁ ።"

"እሱ እንኳ አጅሬጣም ። ምነው ይሄን ወሬ ብንተወው ሬት ።" አሰኝ አስካርሌት ስለቻርለስ የተናገረው አያናደዳት ። ሬት ለሌላ ጉዞ ወደ ዊልሚ ንግተን ለመሔድ ተዘጋጅቶ ስለነበር ማንባሩን ኮስትሮ ወጥቶ ሄደ ።

ከጥቂት ሳምንታት በኋላ አንድ ቀን በበጋ ብራ ንጋት አንድ የተጠቀለለ ነገር በእጁ ይዞ ሲመጣ አስካርሌት ብቻዋን ነበረች ገና የተጠቀለለውን ነገር ሲገልጠው "ውይ እንዴት ያምራል?" ብላ ወደሱ እንድትሮጥ ያደረጋትን ልዩ የፀጉር ጌጥ አወጣ ። ለማየት ጓጉ ታና አዲስ ልብስ ለመንካት ባላት ጥማት ስታየው በሕይወቷ አይታ የማታውቀውን የራስ—ጌጥ ተመለከተች ። ስስ ቀይ ቀለም ባለው ሀር ዙሪያውን የተከበበ ደማቅ አረንጓዴ ጐፈር አክል የፀጉር ጌጥ ነው ። ወደ አገጭ የሚወርደው ማሰሪያውም ወፃ አረንጓዴና ሠፊ ነው ። በዚህ የፀጉር ጌጥ ክፈፍ ዙሪያ ያማረና ብን ብን የሚል ላባ አጅቦታል ።

"እስቲ አርጊው" አለ ሬት እየሳቀ ።

@OLDBOOKSPDF

ምን ጊዜ ሮጠች ሳይባል ወዶ መስተዋቱ ሄዶ የጀሮ ጉትቻዋ እንዲ ታይ በጉርዋን ወደኋላ ገፍታ ፀጉር ጌጡን ሰካችና ማሰሪያውን አጎ ጭኖ ላይ ለማስተካከል ትጣጣር ጀመር ።

"እምሮብኛል?" ብላ ጠየቀች ፣ ምስጋናውን እየጠቀሰችና ላባ ውን ለማውለብለብ ራሷን እየነቀነቀች ።

እሱ ባያረጋግጥላትም ቆንጆ እንደሆነች ገብቷታል ። አረንጓ ዴዉና ከሉል የመሰለ ዓይኗ እምሮ ተጣጥሞ የሸጋዎች ሸጋ እድርጓ ታል ። "ውይ ፈትዬ የማን ጌጥ ነውን እጠዋለሁ ። ያለኝን ገንዘብ ሁሉ እሰጠሀለሁ ። "

"ጌጡ የራስሽ ነው ።" አለ ። "እንዲህ ያለው አረንጓዴ ጌጥ ካንቺ ሌላ ማንን ይስማማ ይመስልሻል? ለመሆኑ የአይንሽን አንፀባራቂ ቀለም ዘአክሮዬ ይገዙ እንደምሆር አታውቂም ?"

"ስሞትልህ ራት እውነት ለኔ ነው ያመጣኸው?"

"አዎ ፣ ሉክስ የሆነ የፓሪስ ባርኔጣም አሳጥኑ ውስጥ አለልሽ። ምናልባት ከጠቀመሽ እዴው ። "

ባርኔጣው ምንም ስሜት አልሰጣትም ። መስተዋት ውስጥም ሰልዋን እያየች ፈገግ ትላለች ። ባሁኑ ሰዓት የሷ ቁምነገርዋ ሁለት ዓመት ሙሉ የተለየችውን የራስ ጌጥ ስታደርግ ምን ያህል ቆንጆ እንደምትሆን ምን ያህል እንደምትዋብ ፣ ማሰብ ብቻ ነው። በዚህ የራስ ጌጥ ምን የማትሠራው ነገር ይኖራል ! ወዲያው ፈገግ ታዋ ቀስ በቀስ ከሰመ ።

"ወደድሽው?" አላት ።

"ዉ . . . ህልም እንዳይሆንብኝ . . . ግን ይህን የመሰለ አረንጓዴ ጌጥ በጥቁር መሸፈንና ሳባውን ጥቁር የማስቀባቱን ነገር እንዴት ብዬ እንደማደርገው እንጃ!"

ወዲያው ተንደርድሮ ማሠሪያውን ከአንጭዋ ላይ አውልቆ ጌጡን ነጠታትና በአንድ አፍታ ወደ ሣጥኑ መለሰው ።

"ምን ማድረግህ ነው? ያንቺ ነው አላልክም እንዴ?"

"ያንቺ ቢሆን ታዲያ የፀጉር ጌጡን የሐዘን ሸማ እንድታደ ርጊው አይደለም እኮ ። ሌላ ዐይነ ጉልላት ሴት ፊልጊ አሰጣታለሁ ። አንቺ ከጠላብሽ ። አይታ የምታደንቅልኝን እፈልጋለሁ ። "

"በፍጹም አታረገውም ! ሞቼ ነው ቆሚ አባክህ ፈት ከፉ አት ሁንብኝ አባክህ እኔ ላድርገው ?"

@OLDBOOKSPDF

"እና እንደሌሎቹ ባርኔጣዎችሽ ልታበላሺው?አሉ"

ሣጥኑን እንቅ አርጋ ያዘች ። ያ እንደዚያ ያስዋባትን
ዣትን እቃ ለሌላ ሴት ሊሰጥባት? ሞታለች !!

ለትንሽ ጊዜ ዊቲና ሚላኒ ምን ይሉኝ ይ
ያው ተወችው ። ስለእናቷ ኤለንም አሰበችና አ
ብኩንነቷ ከሥጋቷ አየሰባትና ፍርሃቷን አረሳች

"አላበላሺውም ። ላላበላሺው ቃል እገባ
ስጠኝ" አለች ። ሣጥኑን ሰጣትና ፈገግ እ
ስታሞካሽ በትዝብት አስተዋላት ።

"ስንት ነው ዋጋው?" አለች እንገትዋን ያ
ዜው ሃምሳ ብር አለኝ ፣ በሚቀጥለው ወር ግን

"በኩንፈዮፊሲው የወረቀት ምንዛሪ ሁለ
አለ የጄነጠ ፊቷን በፈዝ እየተመለከተ "ውይ የኔ
ሀምሳውን ብሰጥህና ሳጥኝ ደግሞ . . ."

"ካንቺ ምንም ገንዘብ አልሻም ። ስጦታ ነው" አ

እስክርቢቶት እፍግን ከጉታ ቀረች ። ከወንዶች ስጦታ በመቀበሬ
ላይ የንበራት እንቢተኝነት ድራሹ ጠፋ ። ብቻ እናቷ ስለዚህ ጉዳይ
ስትመክራት " አየሽ የኔ ኦመቤት ሴት ልጅ በስጦታ መልክ መቀ
በል ያለባት ከረሜላ ፡ አበባ ፡ ምናልባትም የማጭም መጽሐፍ ወይ
የፎቶግራፍ ማስቀመጫ ካልሆነም ትንሽ ብልቃጥ ሽቶ ነው ። ለምን
እጨሻሽ አይሆንም ፣ ውድ እቃ በስጦታ መልክ እንዳትቀበይ ። ወርቅና
ጌጣ ጌጥ ወይም የኪስ ሳንቲም ሆነ መሐረብ በጭራሽ መቀበል የለ
ብሽም ። እንዲህ ያሉትን ውድ ውድ ስጦታዎችን ከተቀበልሽ በምን
ከቸው መንዶች ያሻቸውን ነገር ካንቺ ከመውለድ አይመለሱም ፣
ያ ደግሞ ጅል አይደለም ፣ ልጄ ። "ያለኦት ትዝ አላት ።

"አ ፈራት" አለች እስክርቤት በልቧ አንዴ ራሷን በመለተዋት
ውስጥ አንዴ የፊትን የማይነበብ ፊት እያየች ። "መቼም አልቀበልም
ልለው አስችልም ። በጣም የሚያምር ጌዋ ነው ። ጌጡ ትንሽ በ
እንኳ ወሰጇ የፈለገውን እንዲያደርግ ነጻነት እሰጠው ነበር ።
ደሄን በማሰቢ መልሳ ጉደናጠችና ፊቷ ሁሉ ተለዋወጠ

"ሃምሳ ብሩን ልስጥህ ቢቃ . . . . ."

"ገንዘብ ልትሰጪኝ ብትሞክሪ አሽቀንጥሬ ነው የምወረውርሽ
እንደውም ለነብሰሽ ይሆንሻል ለቁርሣን አድርጊው ። እርግጠ
ከገንዘብሽ ጋር ብትቆርቢ ለነበስ ይሆንሻል ። '

@OLDBOOKSPDF

ፈቃዴ ሳቀርብ አላውቅም በአረንጓዴ ጌጣጋር ሲያንፀባርቅ
አንድ አፍታ አላየባት ። "ምን ልታደርገኝ ፈልገህ ነው ?"

ጠባይሽንና ሐሳብሽን አርግጥ አርገሽ ትኮሽ በእጅ
ነታ እያባበልኩሽና እየተፈታተንኩሽ ነው ፣ የኔ
አበባ ብቻ ከወንድ ልጅ ልቀበል ማለት አያዋ
ጋጠጠ ሳቀባት ።

ተ ልበ ክፉና ጮሌ ሰው ነህ ። ስለዚህም
ግንም እንቢ እንደማይል በደንብ አውቀሃል ።"

ን ቢያደንቁም ያሸፉባታል ።

የፊቢርቁንና የሐሩን ናሙና ሰጥቼው የጌጡን
አሳይቼው አመጣልኝና በሐምሳ ብር ገዛሁት
ሮ ፒቲ ትነግሪ ይሆናል ።'

ሐሳቡ ብር ገዛሁት አላትና ለኩተማው ሰው ሁሉ ስትነግር
አይነት ዝራው ናት ይለኛል ። ግን ሬት አደራህን ከእ
ንግዲህ ወዲህ ሌላ ውድ ዕቃ አንዳታመጣልኝ ። እርግጥ በጣም ደግ
ነህ ፣ ግን እኔ ለመቀበል አልፈልግም ።"

"እረባክሽ! በበኩሌ እኔን ደስ ካለኝና ያንቺን ውበት የሚየ
ደምቅ ከሆነ ማንኛውንም ስጦታ አመጣለሁ ። እንዲያውም ደማቅ
አረንጓዴና ውሃ የመሰለ ሐር ቀሚስ ያውም ከፀጉር ጌጥሽ ጋር
መልክ በመልክ የሚጣጣም አመጣልሻለሁ ። ሆኖም ደግ ሰው እን
ዳልሆንኩ እንድታውቂ አሁንም አስጠነቅቅሻለሁ ። በጌጥና በመ ጫ
ወቻ እየተፈታተንኩ አሻንጉሊት ላደርግሽ ነው ። ሁልጊዜ እንድ
ታስታውሺ የምፈልገው እኔ ያለ ምክንያት ምንም እንደማልሰራና
አንድ ነገር የምሰጠው በምትኩ አንድ ነገር ለማግኘት እንደሆነ ነው።
ደግሞ ያዋጣኛል ፣ ሁልጊዜ አገኝበታለሁ— አተርፋለሁ ።"

ጥቂቱር አይኖቹ ፊቷን ፈለጉ ፈለጉና ሲያገኙት ወደ ከንፈርዋ
። እስካርሌት ሁኔታው ልቧን አሸበራትና ዓይኖቿን ወደ መሬት
። ልክ እናቷ ሌለን እንደተነበየችው የፈለገውን ጉዳይ ሊፈ
ያሻውን ነጻነት ሊጐናፀፍ ነው ማለት ነው ። ወይ ሊስማት
። ወይ ለመሳም ሊሞክር ነው ። ከሁለቱ የቱን ሊያደርግ እንደሆን ግራ
ጋባው አእምሮዋ ለይቶ ሊያውቅ አልቻለም ። ምን ታድርግ ይሆን?
ወመሸችና እምቢ ካለችው የፀጉር ጌጡን አልሰጥ ሊላት
ብቻ አይደለም ። ወስዶ ለሌላ ልጃገረድ ሊሰጠው ነው ።

@OLDBOOKSPDF

እሺ ካለችውና ዛሬ ከተሳመችለት ደግሞ ሌላ ጊዜ ሌላ የፀጉር ጌጥ ሊያመጣና ሳሚኝ ሊላት ነው። ወንዶች ሰምን እንደሆነ እንጂ እንኚ መሳሳምን በጣም ይናፍቃሉ። ብዙዎቹ ደግሞ እንዴ ኮ ሳሳሙ በኋላ የወረ ፍቅር ይይዛቸውና በተቻላቸው አምረው ለመቅረብ ይጥራሉ። ልጅቷ ግን እንዴ ከተሳሙኝ በሚተኙለት ጊዜ ቀልጣፋና ተማደርዳሪ መሆን አለባት። ሬት ከሲ ጋር መሳቀሩንና እንደተስመው ሲለምናት ወይም እንደተስቅለት ሲጠይቃት ማየት የሚገርም ነው። አም ፣ ይሁን እንግዲህ። ይሳማትና ይለይ። እንደተሳመለት ወሰነች።

እሱ ግን እንኳን ሊስማት ንትንትም አላለ። በጭኗ ላይ ገደም አድርጋ እያየችው አንድ ነገር እተተመችው።

"እና ሳደረግኸው ውለታ ሁሉ ጥቅም ታጣኝበታለህ ማለትህ ታዲያ ከኔ ምንድነው የምትጠብቀው?" አለች።

"እሱንማ እናያለን ወደፊት ፤" አለ።

"የፀጉር ጌጡን ውለታህን ለመክፈል ብዬ ሳግባህ የምለፋልህ ታዲያ!" አለች በመሽኮርመም ፀይን እያየችው።

ከከንፈር ጸሙ በታች ጥርሱን ፍልቅቅ አድርጎ ፈገ

"እሜቱ እራስሽን አትሸንግይ። አንቺን ሆነ ሌላ ሴት ማግ አልፈልግም። እኔ የተዳር ሰው አይደለሁም።"

"እውነትክን ነው!" አለችና ሙሽች ጋለል ብላ የፈለች እንዲያደርግ ነጻነት እየሰጠችው "እኔ ልስምህ እንኳ ፈቃደኛ ይደሁም።"

"ምነው ታዲያ አጭሽ በጣም አሞጠሞጠ?"

"እንዴ!" አለች ምን እመስል ይሆን ብላ አሰበች። በኋላ ብታየው ከንፈሮችዋ ለመሳም በሚገባ እንጸኩበኩበ ታወቃት። "ወይኔ!" አለች በቱጭት መሬቱን በእግርዋ እየደበደበች። "በጣም ባለጌ ሰው ነህ። ካሁን ወዲያ ባይኔ እንዳይህ አልፈልግም!"

"በእርግጥ እንደሱ የምታስቢ ከሆነ የፀጉር ጌጡን አምጪና ትነግሪኛለሽ። ምን አይነቱ የመውደድ እዳ ገጠመኝ የኔ ቆንጆ። ይሄንኑም መደበቅ አልቻልሽም። ደግሞ እንደምታውቂው... ነይ እስካርሌት ፤ የፀጉር ጌጡን አምጪና ስለ እኔና ስለጠባዬ የምታስቢውን ትነግሪኛለሽ።"

@OLDBOOKSPDF

"ይሆን የፀጉር ጌጥ እንዲህ ብለህ እንዳትነካ!" አለች ጌጡን እንቅ አድርጋ ይዛ እያፈገፈገች ። ቀስ እያለ እየሳቀ ተከተለና እጅዋን ያዛት ።

"አይ እስክርሌት ፣ ገና ወጣት በመሆንሽ አንጀቴን ትበይዋ ለሽ "አለ ። "እንድስምሽ ከፈለግሽ እስምሻለሁ " ብሎ ዘመም አለና በጺሙ ጉንጯን ታከከ አላት ።

"አሁንስ ፣ የስጦታውን ዕቃ ለማቆየት ብለሽ በጥፊ ትመቺኝ ይሆን ?"

ከንፈሩ ዝም ቅዝቅዝ ሲልባት በመገረም በንዴት ቀና ብላ ፕሯቁር ጠሲት አይኖቹን አየችና ምን ያለው ተስፋ አስቆራጭ ፡ ሰጥድ የፈጠረው ሰው ነው!! አለች ። ካልሳማትና ሊስማት ካል ፈለገ ጥቅርም ይዞት ካልሆነ ስጦታ የሚያመጣላትና የሚመላለሰው ምን ልሁን ብሎ ነው ?

"ይሄ ይሻላል ።" አለ "እስክርሌት መቼም ዕዳ ሆኜብሻለሁ ። ውን መተው በጣም አስቸጋሪ ይሆንብሻልና ከቻልሽ አሽገሽ ኝ ። እኔ ላንቺ መጥፎ ነኝ መቼም ። "

ነህ እንዴ?"

"ራስሽ አታይውም እንዴ? ከባዛሩ ቦታ ካገኘሁሽ ወዲያ የሠው ሁሉ ዕጢ ዴብ የሚያደርግ ነው ። እና ለዛ ሁሉ እኔ ተጠ ዯ ሆኛለሁ ። ለመሆኑ እንድትድንሽ ማን ገፋፋሽ? አላማችን ታላ ነና የተቀደሰ አይደለም ብለሽ እንድታምኚ ማን በግድ ያዘሽ? ወን ዶች ሞኞችና የሚ,ያሚያሩ መመሪያዎች ያሉዋቸው ናቸው ብለሽ እንድታምኚ ማን ገፋፋሽ? ሐሚታውን ሁሉ ማን አትስሚ ፡ ማን እርግፍ አርገሽ ተይው አለሽ? ከሐዘንሽስ ማን በግድ ተላቀቂ አለሽ? ማንም ሴት የማትቀበለውንና ባትቀበል ምንም የማያጐላትን ስጦታ ተቀብለሽ ሁሉን ነገር እንድትደመድሚ ማን አማከረሽ?"

"ካፒቱን በትለር ራስሀን አታታል ። እኔ እንዲህ ያለ ቅሌት አይነካካኝም ። ደግሞም ይሀን ያልከውን ሁሉ ያላንተ እርዳታ ልሠራው የምችለው ነው ። "

"ያን እንኳን አጠራጠራለሁ" አለና ዝም አለ ። ረጋ ብሎ ተቀመጠና አርግጥ በሐዘን ልቧ የቆሰለው የቻርልስ ሐሚልተን የመታሚስት እየተባልሽ ቁስለኞችን በማከምሽ ዝናን አትርፈሽ ለጥቂት ጊዜ ትቀመጪ. ይሆናል ። ውሎ አድሮ ማን . . . . "

@OLDBOOKSPDF

እሷ ልቧ ሲላጋ ሄዷል። መስታወት ውስጥ ራስዋን እየተመለ ከተች ዛሬ ከሰዓት የፀጉር ጌጧን አድርጋ ሆስፒታል ሄዳ ለእርዳታ መኮንኖቹ አበባ ስታበረክት እያታሰባት የሚያወራውን አትሰማም።

በተናገረው ነገር በተለይ ወደ መጨረሻው ላይ እውነትን ያዘለ ነገር እንዳለበት ልብ አላለችም። ምተብኝ ብላ ጥቁር የለበሰችለትን ሰው እንድትረሳውና እንዳሳዝኑ ሴቶች ሁሉ እንድት ጊያጌጥ እንዳደረጋት አላየችም። አልፎ ተርፎም በሰው ግራት እናቷ ኤለን ካስተማረቻት ውጪ የትና የት እንደሄደች አላስተዋ ለችም። ሳታውቀው ቀስ እያለና አንዱ ካንዱ ጋር ምንም ግንኙነት እንደሌለው ሁሉ ትንሽ በትንሽ የለወጣት ከመሆኑም በላይ በዚህ ለውጥ ረገድ ሬት እጇን ያስገባ አይመስላትም። ውስጥ ውስጡን እየገፋፋት እናቷ ስለሰውታ ፅታዎች ያስተማረቻትንና መልካም ሴት ለመሆን የቀሰመችውን ክብድ ትምህርት ሁሉ አዘናጋት።

እስካርሌት እስከዛሬ ድረስ ካገኛችው ነገር ሁሉ የፀጉር ሽፋኗ ዋነኛው ነው። ኤምስት ሳንቲም አላወጣችበትም። ደምም ሬት ይመንም አይ መጣ ያፈቅራታል። እሷም እንድ መላ ፈጥራ እንዲያምን ታደርገዋለች።

በንጋታው እስካርሌት በእጅዋ ማበጠሪያ፣ በአፏ ሙሉ የፀጉር ማስ ያዥ ይዛ ከመስታወቱ ሬት ሲሬት ቃጣ ሜይቤል ሪችሞንድ ያለ ውን ባሏን ለመጠየቅ ሄዳ ስትመለስ የዋና ከተማዋን ሴቶች ያሳ በዶ አዲሱ የፀጉር አሠራር ብላ የንገሪቻትን ለመሥራት ትሞክ ራለች። አዲሱ የፀጉር አሠራር 'ድመት፣ አይጥና አይጠመጉጥ' የሚባል ሲሆን በጣም አስቸጋሪንት አለው። ፀጉር አመሀከል ላይ ይከፈልና በማራና በቀኝ በሶስት በሶስት ደረጀ እየተጠለለ ይሠ ራል። ወደ ፀጉር መከፈያው አጠገብ የሚጠቀለለው በጣም ትልቅ ሲሆን "ድመት" የሚባለው ነው። "ድመት" እና "አይጥ" ለመሥ ራት በጣም ቀላል ነው። "አይጠመጉጥ" የሚባለው ግን ከፀጉር ማስያዣው እያመለጠ በጣም አስቸገራት። ያም ሆኖ እሠራዋለሁ ብላ ቆርጣለች። ምክንያቱም ሬት ማታ ለእራት ሲመጣ ባየው አዲስ የፀጉር አሠራር ላይ አስተያየት ከመስጠት አይቆጠብምና ነው።

አዲሱን የፀጉር አሠራር ካልቻልኩ ብላ ላብ በግንባሩዋ ላይ ችፍፍ እስኪሚል ድረስ ከጥቅሉ ፀጉር ጋር ስትታገል ከታች ኛው አዳራሽ ቀለል ያለ የእግር ኮቴ ስትሰማ፣ ሜላኔ ከሆስፒታል መመለስዋን አወቀች። ወዲያው ሜላኒ በጣም በፈጠነ እርምጃ ሁለት ሁለቱን ደረጀ እንዴ እየዘለለች ስትመጣ እስካርሌት ልትሰካ የያ ዘችውን የፀጉር ማስያዣ ማሠል ላይ አቱማ እንድ ችግር መኖሩን

@OLDBOOKSPDF

ትጠራጠር ጀመር ። ሚላኒ ትግር ካልገጠማት በስተቀር አካሄዷ እንደ ወራሽ ሚስት በጥሞናና በዝግታ ነው ። እስክርሌት ወደበሩ ሮጣ ብርግድ አድርጋ ከፈተችው ። ሚላኒ ጥፋቱ እንደተገኘበት ልጅ ፊቷ ቀልቶ እየፈራች ዘው ብላ ገባች ።

ሚላኒ እንባ በጉንጮቿ ይወርዳል ። የዐሐይ ባርሜጣዋ አንገቷ ላይ በጥብጣብ ተንጠልጥሏል ። በራፉው ቀሚስ ዳሌዋ ላይ በጋይል ይተራመሳል ። በእጅዋ የጨበጠችው ነገር አለ ። ርካሽና ከባድ መዓዛ ያለው ሽቶ አብሯት ገባ ።

"ወይኔ እስክርሌት ጉድ ሆንኩልሽ" ብላ ጮኸች ፡ በሩን ዘግታ አልጋው ላይ ዘፍ ብላ ወደቀች ። "አክስቴ እስካሁን እቤት አል መጣችም፣ አልደረሰችም፣ እቤት ፡ እግዚሀር ምስጋና ይግባው ፡ እስክር ሌት መቼም ልጥት ምንም አልቀረኝ ፡ ተዘለፍልፌ ልወድቅ ነበር። እስክርሌትዬ ያ አጭት ፒተር እኮ ሰ/ሮ ፒቲ እናንራለሁ እያለ እያስፈራራኝ ነው!!"

"ምንድነው እሚናገረው?"

"ስዛች ልመ/ት ነው ወ/ሮ ግናት እቴነ ያወራሁኝ መሆኔን . . ." ሚላኒ በመሀረብ ፊቷን እራገበች ። "ያቺ ቀይ ፀጉር ያላት ቤል ዋት ሊኔማ የምትባል ሴት !"

"ለምን ሚ ሲ" ብላ ጮኸች እስክርሌት ፡ በጣም ከመሸበርዋ የተነሳ ትክሮ ብላ በመመልከት ።

ቤል ዋትሊንግ እስክርሌት በመጀመሪያ ወዴ አትላንታ ስትመጣ መንገድ ላይ ያየቻት ባለ ቀይ ፀጉር ሴት ናት ። መቼም በዚች ከተማ ውስጥ በጣም አስቸጋሪዋ ሴት ይቺ መሆን አለባት ። ብዙ ሴተኛ አዳሪዎች የወታደሮችን እግር ተክትለው ወደአትላንታ መጥተዋል ። ቤል ዋትሊንግ ከሴትኛ አዳሪዎች ሁሉ በጣም ተወዳጅ ናት ። እንደነበልባል አሳት የሚንበለበል ቀይ ፀጉር ስላላትና የምት ለብሳቸው ዘመናዊ ቀሚሶች በጣም ስለሚያማምሩ የወንድ ዓይን ማረፊያ ናት ። አብዛኛውን ጊዜ በፒችትሪ ጐዳና ወይም በአንዱ ደሰ በሚል ሳረቢት መንደር ትታያለች ። ሆኖም እሷ በምትታይ በት ሰዓት በአጠገቧ ያሉ የተከበሩ ሴቶች ሁሉ ከጐኗ ላለመታየት መንገድ አቋረጠው ይሸሻሉ ። ያዜ ሁሉ እየሆነ ላለ ሚላኒ ከዚች ኔት ጋር ስታወራ ታየች ። አጎት ፒተር በሷ መናደዱ መቼም የሚደ ነት ነገር አይሆንም ።

"መቼም አክስቴ ከምትሰማ ብሞት ይሻለኛል! እንደምታውቂው ሸሷ ከሰማች እንደልማዷ ታለትስና ለሰው ሁሉ ወሬውን ስለምታ

@OLDBOOKSPDF

ጸርሰው ስሚ ይጠፋል አይደለም ወይ እያለችሰቀሰቀች ። "ያ እኮ የእኔ ጥፋት አልነበረም ። እኔ . . . እኔ ከፊቷ ሮጬ ማምለጥ አልችል፡ በጣም ብልግና ይሆንብኛል ። እስካርሌት እኔ . . . እኔ በጣም አዝኜ ላታለሁ ። ሰፊ ማዘኔ ትክክል አይደለም ትያለሽ ?"

እስካርሌት የዚህ ዓይነት ማብረግበጎት ጉዳይ አይገባትም ። እንደማንኛዋም የዋህና አስተዳደግ ጨጥ ሴት ስለሴትኛ አዳሪዎች የማወቅ ጉጉት አላት ።

"ምን ፈለጋ ነውን ስታወራስ እንዴት ነው?"

"እ የምትናገረው ሰዋሰው እንኳ እስከዚህም ነው ። ነገር ግን በጣም ጥሩ ለመናገር ስትጣጣር አይቼ እዘንኩላት—ምስኪን ነገር ። ከሆስፒታል መውጣቱ ነበርና አጎት ዊተርንና ሠረገላውን ስፈልግ አጣሁ ። ስለዚህ ወደቤቱ በእግር ሰመሄድ ወሰንኩ ። በኤመርሰን ደጅ ሳልጥ አንድ ጥግ ተደብቃ አገኘኋት ። ብቻ እግዚሀር ሲረዳኝ የኤ መርሰን ቤተሰቦች ወደግዛን ሄደዋል ። እናም "እባክሽን ወይዘሮ ሚላኒ ለአንድ ደቂቃ አነጋግረኝ" አለችኝ ። ስሚን እንዴት እንዳሰብኝ ቀች እኔ አንጃ ። አርግጥ በምችለው ጥቃት ሁሉ መሄድ እንዳለብኝ ባውቅም... ግን እስካርሌት ይገርምሻል ። በጣም ተጐሳቁላ ስለነበር . . . ያው መቼም . . . ስለሰመኝኝ ሁምኩኝ ። ጥቁር ቀሚስና ምንኔሌላ ቀለም የሌለበት ድፍን ጥቁር የራስ ገጥ አድርጋለች ። ያ ቀይ ፀጉ ባይኖር ኖሮ በእውነት ጨጥ ሴት በሆነች ነበር ። እና ገና መልስም ሳልሰጣት በፊት "እኔ ካንቺ ጋር መነጋገር እንዳሌለብኝ አውቃለሁ፡ ነገር ግን እዚያን ሲከፋ ዶሮ ወ/ሮ ኤልሲንግን ሳነጋግራቸው ብሞ ከር ከሆስፒታሉ አባረሩኝ!"

"እንዴ በፅሙነት ሲከፋ ዶሮ ብላ ጠራቻቸው ?" አለች እስካር ሌት በደስታ እየሳቀች ።

"ውይ አትሳቂ ። ምንም የሚያስቅ ነገር የለበትም ። ለነገሩማ ይግረምሽ እንጂ ይቺ ወ/ሮ ማናት እቲ ፡ ስሆስፒታሉ መዋጮ ያላ ትን ልትሰጥ ፈልጋ ነው ። ይሄን ከሷ ትጠረጥሪያለሽ ታዲያ? በየጠዋቱ የነርስ ግልጋሎት ልታበረክት እንደምትመጣ ቃል ግባች ። መቼም ወ/ሮ አልሲ ይሄንን ቢሰሙ ሞቱ እንኖለፁ ብለው ወዲያውኑ ከሆስፒታሉ ያባረሯት ነበር ። ከዚያም ቀጠል አድርጋ እንዲህ አለች። "አንድ ነገር ለመሥራትም እፈልጋለሁ ። እኔስ እንዳንቺ የኮንፌ ዴሬሲው አባል አይደለሁም ?" እናም አስካርሌት ፡ ስመርዳት ያላ ትን ጥላቶት ሳይ ልቤን ነክቶው ። እንደምታውቂው የኮንፌዴሬሲውን አላማ ልርዳ ካለች መጥፎ አይደለችም ማለት ነው ። እንደዚህ ማሰቤ መጥፎ ይመስልሻል ?"

@OLDBOOKSPDF

ሥራ የለማያት ያለህ ሚሊዮኔር ሆነች ብሎ ማን ይጨ
ነቃ? ሌላስ ምን አለች?"

"ወይ ሆስፒታል የሚሔዱትን ሴቶች በሙሉ አጠና ነበር አለች። ከሁሉ ሁሉ የኔ ፊት ደማ ፊት ነው ብላ እንዳመነችና እንዳስቆ ጫችኝ ነገረኸኝ። ጥቂት ገንዘብ እንዳሳትና ያንን ገንዘብ ለሆስፒታሉ መርጄ እንዳውል ልትሰጠኝ እንደምታስብና ለማንም ምንም እንዳል ነገር አለጠነቀቀኸኝ። ወይዘሮ ኤልሲንግ ገንዘቡን ከየት እንደተገኘ ካውቁ እሺ ብለው አይቀበሉኝም። ገንዘቡ ከየት እንደተገኘ ፥ ይህን ነገር ሳስብ ተዝለፍልፌ ልወድቅ ደረስኩ ፥ እኔ በጣም ከመበሳጨቴ የተነሳ ሸሽቻት ልሄድ ፊለኩኝና እንዲህ አልኳት 'እንዴት ግሩም ሴት ነሽ'። ሌላም የማይረባ ነገር ብያታለሁ። እሷም ሳቅ ብላእው ነቸኛ ክርስቲያን እንቺ ነሽ' አለችኝና ይዤንን ቆሻሻ መሀረብ ወደ እጇ ላይ ገፋ አደረገችው። ኡፍ ሸቶው ፥ አሸችው አስቲ?"

ሚላኒ አንድ ፍራንክ የተቋጠረበት የቆሸሸና የሸቶ መዓት የጠጣ መሀረብ ከፍ አድርጋ አሳየች።

"አያመሰገነችኝና ወደፊት በየጣምንቱ ገንዘብ እንደምታመጣ ስነግራችኝ ሳለች እግሯ ፒተር ወረገላውን አያበረረ አጠገቤ ከች አለ። አየኝ" ሚሲ ቹንትሳቷን እትራሱ ውስጥ ቀብራ ትንሰቀስቅ ጀመር። "ከማ ጋር እንደቆምኩኝ ሲያይ . . . አስካርሌት ፥ እንዳንድ ነገር አምባረቀብኝ ፥ በሕይወቱ ማንም እኔ ላይ አምባርቆብኝ አያ ውቅም። ከዚያ ቀጥሎም 'በይ ቶሎ ብለሽ እዚህ መረገላ ላይ ውጪ' አለኝ። በእርግጥ እሺ ብዬ ወጣሁ። እቤት እስክምንደርስ ድረስ እንደረገመኝ ፥ እንደጨቀጨቀኝ ለፒተርም እናገራለሁ እንዳለኝ መጣ። ምናልባት አስቲ አንቺን ይሰማሽ እንደሁ ንገሪው። መቼም አብሪያት መቆም ቀርቶ ቀና ብዬ እንኳ እንዳየኋት እክስቴ ብትሰማ እራሷን ትሰቅላለች። ታዲያ ታናግሪዋለሽ እስካርሌት?"

"እሺ አናግረዋለሁ። ግን አስቲ ምን ያህል ገንዘብ እንዳለበት እንያ። ብዙ ይመስላል" እስካርሌት ቋጠሮውን ስትፈታው እንድ እፍኝ የሚያህል ወርቅ አልጋው ላይ ተበተነ።

"እስካርሌት ፥ ሀምሳ ዶላር ፥ ያውም በወርቅ!" ብላ ጮኸች ሚላኒ፤ የሚያብለጨልጨውን ላንቲሞች ስትቆጥር እየደነገጠች። "እኔ እም ለው በአንዲህ ያለ ሁኔታ የተገኘን ገንዘብ . . እ . . እንደዚህ ተደርጎ የተገኘን ፍራንክ . . በሷ ዓይነት ኑሮ የተገኘን ላንቲም . . ለጀግኖቻ ንን ማሞል ተገቢ ይመስልሻል? ወይስ እግዚሀር ክልሷ ለመርዳት ፣ሰቧን ስለሚያውቅ በምንም መንገድ ቢመጣ ይቅርታ ያደርጋል? መቼም ሆስፒታሉ የሚፈልጋቸውን ነገሮች ብዛት ሳስብ . . ."

@OLDBOOKSPDF

እስካርሌት ምንም ሕሳዳመጠቻትም ። አሷ የቀሽሽውን መሀረብ እያስተዋለች ሐፍረትና ንዴት ይተናነቃታል ። በመሀረቡ አንደኛው ጫፍ ላይ "ሬ ክ በ" የሚሉ የስም መጀመሪያ ፊደላት ተጠልፈውበታል ። እላይኛው የኮሞዲኖዋ መሳቢያ ውስጥ ባለው ትላንት አበባ ቆርጣ መያዣ ስታጣ በዚህ ያሻው ብሎ ሬት በትለር የሰጣት መሀረብ ላይም እነዚህኑ ፊደላት አይታለች ። ዛሬ ግታ ለአራት ሲመጣ ልትመልስለት ወስናለች ።

እንግዲህ ያ ሬት ከዚህች ዋትሊን ከምትባል ፍጥረት ጋር ያመሻል ፣ ይዳራል ማለት ነው ። ንጉዘቡንም የሰጣት እሱው ነው ማለት ነው ። ለሆስፒታሉ ያደረገችው መዋጮ ከሱ የመጣ ነው ። በኩንትሮ ባንድ ፣ የታጣደ ዕቃ በማሻገር የመጣ ወርት ። ወቸጉድ ከእንዲህ ያለችው ፍጥረት ጋር ቆይቶ ሲያበቃ ሬት የጨዋ ሴት ዓይን ለማየት እንዴት ሐሞት ይኖረዋል ጀል! ደሞ አፍቅሮኛል እያለች እያመነች ልቧን ማውለቋ ይባስ ። በቃ ሲያፈቅራት አይችልም ማለት ነው ።

እነዚህ መጥፎ ሴቶችና እነሱ እጃቸውን ያስገቡበት ነገር ሁሉ እስካርሌትን የሚያበሳጫት የተደበቀ ምስጢር ይኖረዋል ። ወንዶች እነዚህን ሴቶች ለምን እንደሚፈልጓቸው ሠዊም ጨዋ ሴት የምትገረው ጉዳይ አይደለም ። ብትናዝርም በሹክሹክታና ሽፍን ባለ የእንጋገር ፈሊጥ መሆን እንዳለበት እስካርሌት አሳምራ ታውቃለች ። ወደነዚህ ሴቶች የሚሄዱ ወንዶች በጣም ዝቅ ያሉ ተራ ተርታ ሰዎች ናቸው ብላ ትገምት ነበር ። ከዚህ በፊት ትላልቅ ወንዶች ፣ ከሷ ጋር ደህና ደህና ቦታ የሚገናኙ ወንዶች ፣ ከሷ ጋር የሚደንሱ ወንዶች ፣ እንዲህ ያለ ነውር ቦታ ይዟዟሉ ፣ እንዲህ ያለ ነውር ሥራ ይሠራሉ ብላ በጭራሽ አስባም አልማም አታውቅም ። አንድ አዲስና አስደንጋጭ የጥርጣሬ መንፈስ አሳደረባት ። ምናልባትኮ ወንዶች ሁሉ ወደዚህ ቦታ ይሄዱ ይሆናል ። ሚስቶቻቸውን እየፈቱ ወደዚህ ሕይወት መገሩሩታቸው መዋፎ ነገር ነው ። ዝቅ ወዳሉ ሴቶች ዘንድ ሄደው ማደርና ለመስተንግዶው ገንዘብ መክፈል ግን በጭራሽ ስም የሚያሳድፍ ነገር ነው ፣ አቤት! ወንዶች ማለትኮ ከንቱ ነገሮች ናቸው ። ሬት በትለር ደግሞ የመጨረሻው የከንቱ ከንቱ ነው ።

እስካርሌት ከእንግዲህ ወዲያ ሬት በትለርን አይኑን አታየውም። ይህንን መሀረብ አፍንጫው ላይ ወርውራ ከቤቷ ታባርረዋለች። ሁለተኛ ከሱ ጋር ንግግር አይኖራትም ። እሱ ግን እንደዛ ማድረግ እኮ አትችልም ። እንኳንስ እሱ ወደ ሴቶች እንደሚሄድ ቀርቶ ሴቶቹ መኖራቸውን ማወቋንም ልትነግረው አትችልም ። እንዴት ብላ ። ሴት ልጅ የምታደርገው ነገርኮ አይደለም ።

@OLDBOOKSPDF

"ወይኔ" አለች በንዴት። "ወይኔ ሴት ባልሆንኩኝ ኖሮ፡ይህ ንን እባብ አሳየው ነበር!!"

መሀረቡን በእጅዋ ጭምድድ አድርጋ ይዛ ደረጃውን ወረደችና አጮት ጥቁርን ልትፈልግ ወደማድቤት ሄደች። ምድጃውን እያለ ፈች ሳለች መሀረቡን እሳቱ ውስጥ ወረወረችው። በአቅም የለሽ ንዴቷ እንደበሳች ቆማ ሲንድ ተመለከተችው።

@OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ 14

የ1863 በጋ እየቀረበ ሲሄድ ተስፋ በእያንዳንዱ ደቡባዊ ልብ ውስጥ ከፍ እያለ እየመጠቀ ሄደ ። እያንዳንዱ ቤተሰብ ላይ ጠባሳ የተወው ችግርና ብቸኝነት ቢኖርም ፡ የእያንዳንዱን ቤተሰብ በር ያን ኳኳው ሰማብማብ ኑጋዴዎች የፈጠሩት የምግብ እጥረትና ተንኮል ቢኖ ርም ፡ ሞትና በሽታ እንዲሁም ሲቃ ሰቀቃ በየቤቱ እንጥቡን ያስነ ባበት ጊዜ ቢሆንም ፡ ደበብ አንደኅና ንብስ ዘርቶ "አንድ ድል ብቻ ከዚያ ጦርነቱ ያበቃል" የሚለውን መፈክር አንግቦ ተነስቷል ። ከለ ፈው በጋ በተሻለ ደስተኝነትና እርግጠኝነት ልባቸውን ሞልተው መፈክሩን ያሰሚሩታል ። ያንኪሞቹ የማይፈረክስ ቋጥኝ ሆነው ከርመው በመጨረሻ እየተፈረካከሱ ነው ።

የ1862 ግና በዓል ሲከተላንታም ሆነ ለመላው ደቡብ በጣም የሚያስደስት ነበር ። ኮንፌዴሬሲው ፍሬድሪክስበርግ ላይ ከፍተኛ ድል አግኝቷል ። በሺ የሚቆጠር የያንኪ ፈሳና ቁስለኛ አገር ምድ ሩን አልብሶታል ። የገና በዓል ወቅት ሀገር አቀፍ ደስታን አዝሎ ከርሟል ። የጦርነቱ ሚዛን ለኮንፌዴሬሲው እያደላ በመምጣቱ አገር በደስታ ተጥለቅልቋል ። ገና ጥሬ የነበረው ሠራዊት አሁን በቂ ልምድ አግኝቶ የበሰለ ተዋጊ ሆኗል ። ጀኔራሎቹ ችሎታቸውን አስመስክ ረዋል ። ከብራቸውን ጠብቀዋል ። ስለዚህም በፀደይ ወር ዘመቻው እንደገና ሲጀመር ፡ ያንኪዎች ለእንዴም ለሁለትም ድባቅ ይመታሉ ። ድባቅ ይገባሉ ።

የፀደይ ወር መጣ ። ውጊያው ተጀመረ ። በማንበት ወር ኮንፌዴራ ሲው ቻንስለርስቪል ላይ ድልን ተጐናፀፈ ። ደቡቡ ደስታን እንደ ርችት ተኮሰ ። እንደ ችቦ ለኮሰ ። ያድል ጩኸትም ሰማይ ጠቀሰ ።

ወደ ጅርጂያ ሲገሰግስ መጥቶ የነበረው የኅብረቱ ፈረሰኛ ጦር በኮንፌዴሬሲው ሠራዊት ድል ተመታ ። ሰው ሁሉ ይስቃል ፡ ያጨ በጭባል ። ትከሻ ትከሻውን እየተመታታ "እህስ ጌታ! ሽማግሌው ናታን ቡድፎርድ ፎሬስት ያገኛቸው ለታ መዮላቸው!" ሚያዚያ ወር መጨረሻ ግድም ኮሎኔል ስትሬት በተባለ የጦር መሪ የሚመራ ስም ንት መቶ የያንኪ ፈረሰኛ ጦር ከአትላንታ ስልሳ ማይል ርቀት ላይ ያለችው ሮም ከተማ ላይ ድንገተኛ ወረራ ለያካሂድ ጅርጂያ ገባ ። በአትላንታና በተነሲ ማህል ያለውን የባቡር ሐዲድ የመቱረጥ በጋይ

@OLDBOOKSPDF

ለኛ ጥንት የተነደፈ እቅድ ያላቸው ሲሆን ከዚያ ቁልቁል ወደ ደቡብ ወርደው አትላንታ በመግባት ሩብሪካዎቹንና በኮንፌዴሬሲው ቁልፍ ከተማ የተከማቸውን የጦር ቁሳቁስ ለማውደም ይፈልጋሉ ።

በጣም ከፍተኛ የማጥቃት እርምጃ ስለሚሆን ደቡቡ ትልቅ ጥፋት ይደርስበት ነበር—አድሚ ለፎሬስት ነገሩ ሁሉ የተገለጠለት ሆነ ። የያንኪዎችን አንድ ሶስተኛ ብቻ የሚሆን ኃይል — ግን እጅግ ኃይለኛ ሰዎችና እጅግ ፈጣን ተዋጊ ፈረሰኞች ያሉበት ኃይል ይዟል! ግን ይደፍረዋል! እያሳደደ ሮም ከመግባታቸው በፊት ተገተጋቸው። ሌትና ቀን አራወጣቸው ። በመጨረሻም ሙሉ ሠራዊታቸውን በቁ ጥጥር ሥር አዋለ !!

ወሬው አትላንታ ሲደርስ የቻንስለርስቪሉም ድል ወሬ እኩል ደረሰ ። ከተማዋ በደስታ ከመሠረትዋ ተናጋች ። በሳት ተጥለቀለቀች የቻንስለርስቪሉ ሽንፈት ለያንኪዎች ከባድ ጥቃት ነው ። ለአትላንታ ሕዝብ ግን ብዙ ሳት ስላት ያፈራው የኩሎኔል ስትሬት ሠራዊት በቁ ጥጥር ሥር መዋል ነው ።

"የስም ቲታዬ ፡ ከሽማግሌው ፎሬስት ጋር መቀለድ በእሳት መጫ ወት ነው" አሰ የአትላንታ ሕዝብ ፡ የጦርነቱ ወሬ በተደጋጋሚ በተ ወራ ቁጥር ።

የኮንፌዴሬሲው የድል ዕጣ ገርፍ ወደሚጎርፍበት አቅጣጫ ሕዝቡን እያንሳፈፈ እየበረታና እየሰፋ ሄደ ። በግራንት የሚመራው የያንኪ ጦር ከግንቦት አጋማሽ ጀምሮ ቪክስበርግን መውረሩ እው ነት ነው ። እስቶንዌል ጃክሰን ፡ በቻንስለርስቪል ጦርነት ላይ በቆ ሰለ ጊዜ ደቡቡ ከፍተኛ ውድቀት ደርሶበት መዳከሙ እውነት ነው። በፍሬድሪክስበርግ ጦርነት ላይ ጄኔራል ቲ.አር.አር. ኮብ ሲሞት ጆር ጂያ በጣም ቆራጡንና የጦር ስልት አዋቂውን ልጅዋን ማጣቷ ዕው ነት ነው ። ያም ሆኖ ግን ያንኪዎች እንደ ፍሬድሪክስ በርጉና እንደ ቻንስለርስቪል ፡ ሽንፈት የደረሰባቸው ቦታ የለም ። በበቃኝ እጃቸ ውን መስጠት አለባቸው ። ከዚያ አስከፊው ጦርነትም ያበቃል ።

ሐምሌ መጀመሪያ ላይ ጂኔራል ሊ ወደ ፔንሲልቫንያ እየገሰገሰ መሆኑ በመጀመሪያ ጭምጭምታ ወሬ ተጥሎም በሪፖርት መልክ መጣ ። ሊ በጠላት ግዛት ገባ! ሊ በጦርነት እየገፋ ሄደ! ይሄ የጦ ርነቱ ማከተሚያ ፡ የመጨረሻው ውጊያ ነው!

አትላንታ የፍንደቃ ስሜት ሞልቷታል ። ደስታ መላ ሰውነ ቷን ወርሯታል ። ትኩስ የበቀል ጥማት ይዟታል ። ጦርነት በገዛ እገራ ቸው ውስጥ መካሄዱን ሲያዩ ያንኪዎቹ የጦርነት ጣጣ በደምብ

@OLDBOOKSPDF

ይገባቸዋል ። ለም መሬት ጠም ማደሩ ፡ ፈረሶችና ከብቶች መሰረቃቸው ቤቶች መቃጠላቸው ፡ ሽማግሌዎችና ልጆች እስር ቤት መጋዛቸውና ሴቶችና ሕፃናት በረሀብ አለንጋ መገረፋቸው ምን ማለት እንደሆነ አሁን ይገባቸዋል ።

ያንኪዎች ፡ ሚዙሪ ፡ ኬንተኪ ፡ ተነሲና ቨርጂኒያ ውስጥ ምን እን ደሠሩ ማንም ያውቃል ። ትናንሽ ልጆች ሳይቀሩ ያንኪዎች በወረራ በያዟቸው ግዛቶች ውስጥ የዘሩትን ሽብር በጥላቻና በጥርሃት ያወ ሱታል ። ግና ካሁኑ አትላንታ ፡ ከምሥራቅ ቴነሲ በመጡ ስደተኞች ተጣባለች ። እናም እነዚህ ስደተኞች ምን ዓይነት አበሳና መከራ እንዳዩ ለከተማው ሰው አሰረድተዋል ። በነዚያ ግዛቶች ውስጥ ያሉ የኮንፌዴሬሲው ደጋፊዎች በጣም ጥቂት በመሆናቸው የቁጣው ጩኄ በከባዱ ያረፈው እንቱ ሳይ ነበር ። በየድንበር አገሮች እንደሆ ነው ሁሉ ጦረቤት በጦረቤቱ ላይ እየጠቆመ አስገደለ ። ወንድምም ወንድሙን ገደለ ። እንዚህ ስደተኞች ፔንሲልቫንያን አቆን እሳት ቢለቁባት ይወዱ ነበር ። የመጨረሻዋ ጨዋ አሮጊት እንኳ ፔንሲልቫንያ ድምጥማጧ ቢጠፋ ደንታቸው አይደለም ።

ጸሩ ግን ጄኔራል ሊ ፡ ፔንሲልቫኒያ ውስጥ ያለ የማንም ሰው የግል ንብረት እንዳይነካ ፡ ቤት ንብረት ማቃጠል በሞት እንደ ሚያስቀጣና ወታደሩ ላጠፋው ለማንኛውም ንብረት ከፋይ እንደሆነ ትእዛዝ ማስተላለፉ ከተነገረ በኋላ ወሬው ሁሉ እየቀዘቀዘ መጣ ። ይሄ ትእዛዝ የጄኔራሉን ደግነት በማስመስከሩ ዝነኝነቱን ያረጋገጠ ለት ጉዳይ ሆኗል ። በዚያች ባለፀጋ አገር ሀብታም መጋዘኖች ውስጥ ያሉትን ሰዎች አታደሀዮዋቸው አሰ፣ ጄኔራል ሊ ምን አስቦ ነው፣ የኛ ልጆች በጣም መራባቸውንና ለእግራቸው መጫሚያ ለገላቸው ልብስ ማጣታቸውን አረሳው እንዴ ?

ጳርሲ ሚድ ለዶክተሩ የላከው የመጀመሪያ ዜና ሐምሌ መጀመ ሪያ ላይ ለአትላንታ የደረሰ ሲሆን ሰዉ በንዴት ሲቀባበለው ከረመ ።

"አባባ ቦት ጫማ ልታጫልኝ ትችላለህ ይሽው ከዛሬ ሁ[illegible] ሳምንት ጀምሮ ባዶ እግሬን ነበርኩ ፡ ወደፊትም የማማኘት ተሳፋ የለኝም ። እግሬ ትልቅ ባይሆን ኖሮ እንኳ እንደሌሎቹ ልጆች ከሞቱ ያንኪዎች መስጂ አደርግ ነበር ። እስካሁንም የኔን እግር የሚያህል ያለው የሞተ ያንኪ አላጋጠመኝም ። ካገኘህ በፖስታ ቤት በኩል እንዳትልክ—እንዴ ይመነትፈኛል ። ቢመስድብኝ አልወትሰውም ። ፊልን በባቡር አሳጥረህ ጫማውን አስያዘህ ላከው ። ወደፊት ወዴት እንደ ምንሄድ እጽፍልሀለሁ ። አሁን ለጊዜው ምንም የማውቀው ነገር የለም

@OLDBOOKSPDF

—ወደ ሰማን ከመሸሙ በፍጥነት ለስተኋላ ። እሁን ያለነው ሜሪላንድ ውስጥ ነው ። ሁሉ ሰው ወደፔንሲልቫኒያ ነው የምንሄደው ይላል . . .

"አባባ ፣ ያንኪዎቹን እነሱ ያደረሱትን ጥፋት እኛም ማድረስ እንደምንችል ፣ በሰፈሩት ቁና እንደምንሰፍራቸው እናሳያቸዋለን ብለን ነበር ። ጄኔራሉ ግን አይሆንም አለ ። በበኩሌ እንኳ ያንዱን ያንኪ ቤት ሳቃጥል ብረሸን ደስታዬ ነው ። አባባ ፣ ዛሬ በሕይወትህ አይተህ በማ ታውቀው ሰፊ የበቆሎ እርሻ ውስጥ አቋርጠን አለፍን ። እኛ በቤ ታችን አካባቢ እንደዚህ ያለ የበቆሎ እርሻ የለንም ። መቼም በጣም ተርበን ስለነበር በበቆሎው እርሻ ላይ በማል ያደረስነው ጥፋት አለ ። ጄኔራሉ ስለማያውቅ ምንም አይሳዳውም ። ያም ሆኖ ግን ያ አረን ጓዴ አሸት ምኑም የጠቀመን ነገር አልነበረም ። ልጆቹ ሁሉ ተቅማጥ ይዞቸው ስለነበር በቆሎው አባሰባቸው ። ተቅማጥ ይዞህ ከምትጓዝ በቆሰለ እግር መጓዝ ይሻልሀል ። አባባ ፣ አባከህ ቦት ጫማ ከገኘህ እንደምንም ብለህ ሳክልኝ ። አሁን ሻምበል ሆኛለሁ ። እንድ ሻም በል ምንም ዩኒፎርም ባይኖረው ቦት ጫማ ግን ሊኖረው ይገባል ። "

ሠራዊቱ ግን ያለው ፔንሲልቫንያ ውስጥ ነው ። ዋናው ጉዳይ ይሄው ነው ። እንድ ድል ብቻ ፣ ከዚያ ጦርነቱ ያከትማል ። ከዚያ ጸርሲ ሚድ ቤት መግጠን ያዩርጋል ። ልጆቹ ሁሉ ወደ የቤታቸው ይመለ ሳሉ ። ከዚያ እያንጓንዱ ሰው በደስታ ይዋጣል ። ወይዘሮ ሚድ ወታ ደሩ ልጆዋ ከድል በኋላ ሲመለስ ታይቷት ወይኖቹ በደስታ እንባ ረጠቡ ።

ሐምሌ ሰላሳኛውን ቀን እንደያዘ ከሰሜን የሚመጡትን የስልክ መልዕክቶች ዝምታ ዋጣቸው ። በአትላንታው ዋና ጦር ሰፈር የሚመ ጡት ብጥቅጣቂ ወሬዎች በስተቀር እስክ አራተኛው ቀን ተሲዓት ድረስ ዝምታው እንደተንሰራፋ ቆየ ። ፔንሲልቫንያ ውስጥ በምትገኝ ጌትስበርግ የምትባል ትንሽ ከተማ ውስጥ ጄኔራል ሊ ሠራዊቱን ሁሉ አሰባስቦ ከፍተኛ ውጊያ አክሄዶል አሉ ። ጦርነቱ የሚካሔደው በጠላት ግዛት ውስጥ ስለሆነና ሪፖርቱ ወደ አትላንታ የሚመጣው ደግሞ በሜሪላንድ አቋርጦና በሬችሞንድ ተሻግሮ በመሆኑ ወሬው ፡ ዲጣሪና ዝግተኛ ነው ።

"ልብ መስቀሉ እየበረታ መጣ ። ፍርሃት ቀስ በቀስ እየዳኸ እከተ ማይቱ አናት ላይ መውጣት ጀመረ ። መቼም ጦርነት በሚካሔድበት አገር ስለጦርነቱ ምንም ካለማወቅ የበለጠ መጥፎ ነገር የለም ። ልጅ ቻቸው ጦር ግንባር ላይ ያሉ ቤተሰቦች ምነው ፔንሲልቫንያ ውስጥ ባልሆኑ እያሉ ይፀልያሉ ። ልጆቻቸው ጸርሲ ሚድ ያለበት ከፍለ ጦር ውስጥ ያሉ ወላጆች ግን ጥርሳቸውን እየነከሱ ያንኪዎቹን ላን

@OLDBOOKSPDF

ዴም ለሁሌም ደባቅ የሚመቱበት ጦርነት ውስጥ በመሆናቸው ክብር ይሰማናል ይላሉ ።

በወ/ሮ ጊቲ ታት ቤት ያሉት ሶስቱ ሴቶች ሊሸፍኑት ባልቻ ለት ፍርሃት ተውጠው እርስ በርስ ይተያዩ ጀመር ። እሸሌይ እኩ ያለው ዳርሲ ባለበት ክፍለ ጦር ውስጥ ነው ።

ሐምሌ በገባ በአምስተኛው ቀን ከሰሜን ሳይሆን ከምዕራብ የክፉ ወሬ ጮርፍ መጣ ። ቪክስበርግ በጠላት እጅ ወደቀች ። ከረኽርምና ከመራራ ጦርነት በኋላ የሚሲሲፒ ወንዝ ሙሉ ያንኪ ሱዊስ እስከ ነው ኦርሊያንስ ድረስ ያለው አካባቢ በመሉ ያንኪዎች እጅ ገባ ። ኮንፌዴሬሲው ሁለት ሳይ ተከፈለ ። በሉላ በማንኛውም ጊዜ ቢሆን ይሄ የጥፋት ወሬ አትላንታ ላይ ፍርሃትና ድንጋጤን ይነዛ በት ነበር ። አሁን ግን የቪክስበርግን ሁኔታ ጉዳዩ ያሉት በጣም በትንሹ ነው ። እነሱ በህልማቸውም በወሬቸውም የሚያስቡት ጂኔራል ሊ ፒንሲልቫንያ ውስጥ ግፋ መደፊት የሚለውን ጦር ነው ። ጂኔራል ሊ በምሥራቅ ድልን ከተጐናፀፈ የቪክስበርግን ሽንፈት ከመጠፍ አይቆጥሩትም ። ፊላዴልፊያ ፡ ኒው ዮርክና ዋሽንግተን አሉ ። የነዚህ አገሮች መያዝ ሰሜኑን ሽባ ከማድረጉም በላይ የሚሲሲ ፒን አካባቢ ሽንፈት ያካክሳል ።

ሰዓታት እየተሳቡ በሄዱ ቁጥር የዝምታ ጥቁር ጥላ ከተማይቱ ላይ የማጥላቱም መጠን እንዲሁ እየሰፋ ሂደ ። ሰምቹ ፡ ሰማዩ በጸመና የከበደ መሆኑ ቀርቶ ጥርት ያለ ሰማያዊ እንደሆነ አድርገው አስኪያ ያስቡ ድረስ ግራ በሚያጋባ ሁኔታ ጠራራዋ ፀሐይ በዝምታ ድባብ ሥር ተደበቀች ። በየቦታው ሴቶቹ ተሰብስበው ይታያሉ ። በየበረንዳው በየአግር መንገዱ ፡ በጕዳና ማህል ሳይቀር ተከማችተው እንዲ ላንዲ ወሬው የደግ መልክ እንዲሰለው ይነጋገራሉ ። አንዲ አንዲን ትደግ ፋለች ። ሌላዋ ሌላዋን ታጽናናለች— የራሂን ፍርሃት ደብቃ ሌላዋን ታበረታታለች ። ሆኖም ጭምጭምታ ጭምጭምታ ወሬ እንደሚሰ ማው ጂኔራል ሊ ሞቷል ፡ ጦርነቱ አልቆለታል ይባላል ። የጦር ሚዳ የእለት ሁኔታ መዝገብ የስም ዝርዝሩን ይዞ ይሾጉዲጉድ ጀመር ። ዝርዝሩ በከተማይቱ ዋና ዋና መንገዶች ላይ ሽቅብ ቁልቁል ይላል ። ምንም እንኳን ሳለግመን ቢሞክሩ ጎረቤቶቹ ሁሉ በቁርጠት እንደ ያዙ ወደከተማይቱ ፡ ወደ ጋዜጣ ማከፋፈያ ፡ ወደ ዋናው ጦር ሠፈ እየሄዱ የወሬ ያለህ ይላሉ ። ምንም ወሬ—መጥፎ እንኳ ቢሆን እት ዲሰሙ ይማጠናሉ ።

ባቡር ጣቢያው ውስጥ የሚሰበሰበው ሕዝብ ስፍር ቁጥር የ ውም ። በፖስታ ቤቱ ደጃፍ ፡ በዋናው ጦር አካባቢ ፡ በተዘጉት የጋዜ

@OLDBOOKSPDF

ማከራፊያ መስኩቶች ዙሪያ የሰው ዘር ተጠራቅሚል ። የሚያወራ ሰው ከኛ የለም ። አልር አልር አንድ ሽማግሌ ሰው ይመጣና አባካችሁ አዲስ ወሬ አንዳለ ይላል ። የተሰበሰበውን ሕዝብ ለንግግር ከማነሳሳት ይልቅ ዝምታውን ያበረታዋል ። የወጥመዱን በረዶ ይበሱን ያጠፍ ረዋል ። ምክንያቱም ለጥያቄው ምላሽ የሚሆነው ያው የተደጋገመው አረፍተ ነገር ነው፦"ከሰሚን የተነሣረን ነገር የለም—ጦርነቱ ከመቀ ጠሉ በስተቀር ።" ከፊሎቹ በእግር ከፊሎቹ በሰረገላ እየመጡ የሚሰ በሰበት ሲቶች እያደር ቁጥሩ እየጨመረ ሄደ ። ጥቅጥቅ ካለው ወፈ ሰማይ ሕዝብ የሚወጣው ትንፋሽና ጠረን ፡ ከሚንቀራጠጡ እግሮች ሥር የሚነሳው አቧራ ከወበቅ ጋር ተደባልቆ በጣም ያፍናል ። ሲቶቹ ትንፍሽ አላሉም ። ፊታቸው ላይ የሚነበበው የልመና ድምጽ ግን ከእሪታ የበለጠ ይጮሀል ።

ወንድ ልጅን ፡ ወንድሙን ፡ አባቱን ፡ ፍቅረኛውን ፡ አባ ወራውን ወደዚህ ጦርነት ያልሳክ እንድም በተሰብ አይገኝም ። ሁሉም የሞት መርዶ ወደቤታቸው መምጣቱን እየተጠባበቁ ነው ። ሞትን እየጠበ ቱት ነው ። ሽንፈትን ሳይሆን ምትን ። የመሸነፍን ሀሳብ ከተሰና በቱት ቆይተዋል ። ይሄኔ በፔንሲልቫኒያ ኮረብቶች አናት ባለው ዐሐይ የመታው ሳር ላይ ወጥቻቸው እያለቱ ነው ። በእሁኑ ደቂቃ እንኳን ፡ የደቡቡ ተዋጊዎች በጦርነቱ አሙሉ ነፋስ እንደጠፍ እየረገፉ ነው ። የሚዋጉለት አላማ ግን ክቶውንም አይወድቅም ። አይሞትም ። በሺ የሚቆጠሩ ጀግኖች ይሞቱ ይሆናል ። ነገር ግን ሌሎች በሺ የሚቆ ጠሩ ጀግኖች ልጅች የአመጣ ጨክታቸውን እያስተጋቡ መሬት ፈሶ እልፍ አዘርዝሮ እንደሚበቅል የስንዴ ፍሬ ከመሬት ይፈላሉ ። በእግራቸውም ይተካሉ ። እነዚህ ጀግና ልጆች ከየት እንደሚፈሉ ግንም አያውቅም ። በእርግጥ የሚያውቁት ነገር ቢኖር ልክ እውነተኛና ቀና ተኛ አምላክ በመንበረ መንግሥቱ መኖሩን እንደሚያውቁ ሁሉ ፡ ጀኔራል ሊ ተአምር እንደሚሰራና የቨርጂኒያው ሠራዊት ምንጊዜም የማይበገር መሆኑን ነው ።

አስካርሌት ፡ ሚላኒና ወይዘሮ ፒቲ ፓት የዐሐይ መከለያ ሻሸ ቦውን ተጠልለውና አስረገላው ላይ ሆነው "ዴይሊ ኤግዛምነር" የጫባለው ጋዜጣ ከሚወጣበት ቢሮ ፊት ለፊት ተቀምጠዋል ። እስካ እጅጅ ከመንቀጥቀጣቸው የተነሳ ሻሸ ይርገበገባል ። ወይዘሮ ፒቲ በጣም ከመደንገጣቸው የተነሳ እከብ ፊታቸው ላይ ያለው የጥን ጎል የመሰለ አጥንጫቸው ይንቀጠቀጣል ። ሚላኒ ግን ጊዜ በጣፋ ጥር ጥቂት ዐይኗ የበለጠ እየፈጠጠ ከድንጋይ የተቀረፀች ይመ በድን ሆና ተቀምጣለች ። በሁለት ሰዓት ጊዜ ውስጥ አንዲት ልጅ የት ብቻ ሰጥታለች ። ይሽንኑም የተናገረችው ከዕቃ ማስቀ

@OLDBOOKSPDF

ቀመጫዋ ቦርሳ ውስጥ የሚሸቱት ጨው አውጥታ ለአክስቷ ስትሰጥ ሲሆን በሕይወቷ ለመጀመሪያ ጊዜ ፍቅር በተመላ አንደበት ለአክስቷ መናገሯ ነው።

"እንቺ አክስቱ፣ ልብሽን የሚደክምሽ ከመስለሽ አሽትሻው የማስጠነቅቅሽ ግን ልብሽን ደክሞሽ ተዝለፍልፈሽ የምትወድቂም ከሆነ አንሞት . . . ፒተር ወደቤት ይዞሽ ይሄዳል እንጂ እኔ አብሬሽ አልሄድም። እኔ እንደሆን ዛሬ አንድ ወሬ ስሰ . . . አንድ ወሬ ሳልሰማ አልሄድም ። ከዚህ ቦታ ንቅንቅ አልልም። እስካርሌትም ከእኔ ተነጥላ እንድትሄድ አላደርግም።"

እስካርሌት ከዚህ ቦታ የመሄድ አገማሚያውም የላት። ስለአሽሊይ የመጀመሪያውን ወሬ እማትሰማበት ቦታ ለመቀመጥ በጭራሽ አትፈልግም። በሞራሽ፣ ለምን ወይዘሮ ፒቲ ተዝለፍልፈው መውደቅ ቀርቶ ድብን አይሉም። ከዚህች ሥፍራ እንድ አርምሽ እንኳ አትንቀሳቀስም። ይሄኔ ከጦር አምባዎቹ እንዴ ሥፍራ ይዋጋል። ምናልባትም እየሞተ ነው። ይሄ የጋዜጣ ማደያ ደግሞ እውነተኛውን ነገር የምትሰማበት ቁልፍ ቦታ ነው።

እስካርሌት በአካባቢው የተሰበሰበውን ሕዝብ ሁሉ አንድ በአንድ ታያለች። ጓደኞቿን፣ ጐረቤቶቿን፣ ወይዘሮ ሚድ የፀሐይ ባርሚጣዋን አድርጋ የእሥራ አምስት አመቱን ፊል በእጅዋ ይዛ እንደቆመችና የማክለር ሴት ልጆች በሚንቀጠቀጠው የሳይኛው ከንፈራቸው ዋርሳቸውን ለመሸፈን እየሞከሩ አንዷኑ ታያለች። ወይዘሮ ኤልሲንግ እንደጅብራ ተግተረው የውስጥ ስሚታቸው እንዳይከዳቸውና እንዳ ይታወቅባቸው ከተጫጠረ ፀጉራቸው ብሚወርደው ጥበጣብ ፊታቸውን ለመሸፈን ይሞራሉ። ፋኒ ኤልሲንግም የጨው እምድ መሰላ ቆማለች። (እርግጥ ፋኒ ስለወንድሟ ስለሽማ እትጨነትም። ማንም ያልጠረጠረው ወጻጅ እጠር ማንባር ይኖራት ይሆን እንዴ?!) ወይዘሮ ሜሪዌዘር የሚይቢልን እጅ መታ መታ እያደረገች እሥረኛው ላይ ተቀምጣለች። ሚይቤል ምንም እንኳ ቫሏን በጥንቃቄ ሆዷ ላይ ጣለ አድርጋ ለመሸፈን ብትሞክር እርግዝናዋ ስለሚያስታውቅ አደባባይ መውጣቷ ያሳፍራል። ይሄን ያህልስ ምን አስጨንቃት? የሉዚያናው ሠራዊት ፔንሲለቫንያ ስለመሄዱ ማንም የሚያውቅ የለም። ምናልባት ያ ኮሳሳ ፀጉራም ዙዊቭ ወጻጅዋ በዚች ባሁኗ ደቂቃ በሰላም ሪችሞንድ ውስጥ ተቀምጠ ይሆናል።

ከተሰበሰበው ሕዝብ ራቅ ብሎ እንቅስቃሴ ተሰማ። ሠረገላ የሉላቸው ሰዎች እየተሸጋገጉ መንገድ ለቀቁ። ፊት በትለር በጥንቃቄ ፈረሱን ከወይዘሮ ፒቲ ፓት ሠረገላ ጐን አስጠግቶ አቆመው። አስካ

@OLDBOOKSPDF

ርሴት እንዲህ ብሳ አጠየቀቸ፡ በእንዲህ ያለ ጊዜ መምጣቱ እንዲት ያለው ደራር ነው በሉ! ዩኒፎርም ባለመልበሱ ብቻ እንኳ ይሄ የከ ፋው ሕዝብ እንደወረቀት በጫጭቆ ሲጥሰው እንደሚችል አይታ የውም እንዴ! እየተጠጋ ሲመጣም አሲ ራሺ በመጀመሪያ የምት በጫጭቀው መስሎ ተሰማት ። አሽሌይና ሌሎቹ ልጆች በየጦር ሜዳው በባዶ እግራቸው ፡ ፀሐይ እናት አናታቸውን እየቀጠቀጣቸው፡ በረሀብ እየተቆሉና ፡ በበሽታ እየማቀቁ ከያንኪዎች ጋር ሲተናነቁ እሱ እዚህ የተመለመለ ቆዳ ቦት ጫማ አድርጎ ፡ ሽክ ያለ ነጭ ሱፉን ለብሶ ፡ አወልውሎና ምኞትን ተሳብሶ ፡ ውድ ሲጋሩን እያጨሰ ሰንጋ ፈረሱ ላይ መኮፈሱ ምን አይነት ድፍረት ነወት

ማህል ሰማህል እያቋረጠ ቀስ እያለ ሲመጣ የመረራቸው ሰዎች ፀጉኛ እላዩ ላይ ከንጥላቸው ፈሰሱ ። ሽማግሌ ሰዎች ጠማቸው ውስጥ ያጉተመትማሉ ። ወይዘሮ ሜሪዌዘር ምንም ስለማይፈሩ ሠረገላ ላቸው ውስጥ እንዳሉ ቁም ብለው "ስማብግብ ነጋዴ!" አሉ ፡ ቃሉ መዝገብ ታሳት ውስጥ ካሉት ቃሎች ሁሉ በጣም የተሳሳተና መር ዛም እሰኪመስለ ድረስ እየሳልተው ። እሱ ማንንም ከጉዳይ አልጣፈም ስጄሊና ለወ/ሮ ፕቲ ብቻ ባርሜላውን አንስቶ አጅ እየነሳ ወደ እስካ ርሴት ፈረሱን አስጠግቶ ወደታች ዘመም አለና አንሾካሾከ ፡"ዶክ ተር ሚድ ባንዲራችን ላይ ድል እንደንሥር ከንሱን ዘርግቶ ያርፍበ ታል የሚለውን ከኛ ዓይኮሩን አሁንም ሰምን አይደሰኩርልንም ታዲያ?"

እስክርሴት እንደ አራስ ነብር ተማ ብላ የሚፋጅ ስድብ አዘል ቃላት ወደ ከንፈሯ እየተጋፉ ሲመጡባት ወደሱ ዞረችና ልታዘንብ በት ስትል አድረጣት ።

"ወይዛዘርት ፡ እዚህ ልነግራችሁ የመጣሁት" አለ ድምጡን ዝሳ አድርጎ ። "ወደ ጥናው ጦር ሠፈር ሄጄ እንደ ነበርና የመጀ መሪያው የጦርነቱ የእሰት ሁኔታ ዝርዝር መምጣቱን መስማቴን ነው ። "

ይህ ንግግር ሲሰማ አጠገቡ ከነበሩት ሰዎች ግድም ሀምሀምታ ቁጠሰ ። መዲያው የተሰበሰበው ሰው ሁሉ ቁልቁል በዋይት ሆል ግቢና ጎንጀርድሮ ወደ ሣናው ጦር ሰፈር ስመፈጁ አኮበኮበ ።

"አትሂዱ" አለ ከሰርቻው ብድግ ብሎ እጁን በማንሳት ። "የኢ ስት ሁኔታ ዝርዝሩ ወደሁለቱም ጋዜጣ ማተሚያ ቤቶች ተልኮ እየ ታተመ ስለሆነ በያላችሁበት ቆዩ!"

"ውይ ኳተቴን በትለር ፡" ብሳ ሎኔት ሚሊ ፡ ዐይኖቿ እንባ

@OLDBOOKSPDF

እንዳዘሉ ወደሱ ዞራ ። "መጥተሀ ለኛ መንገርህ ፣ እንዴት ደግ ሰው ነህ! ዝርዝሩ መቼ ይለጠፍልን ይሆን!"

"በየትኛውም ደቂቃ ሊለጥፉት ይችላሉ ፣ እመቤት ። ሪፖርቶቹ ወደ ዋናው ቢሮ የመጡት ከግማሽ ሰዓት በፊት ነው ። ለዚህ ጉዳይ ኃላፊ የሆነው ሻለቃ ፣ ሰዉ ወሬውን ለማጣጣት ሲጋፉ ቢሮዎቹን ይሰባበራቸዋል ብሎ ስለሰጋ በየጋዜጦቹ አስኪታተም ድረስ እንዳይ ለጠፍ አዟል ። አሃ! ተመልከቱ!"

የጋዜጣ ማደያው ቢሮ መስኮት ተከፈተና አንድ እጅ ከውስጥ ወደ ውጪ ተዘረጋ ። በርካታ የሰም ዝርዝር የያዙ ወረቀቶችን ይዟል ። በአዲስ ቀለም ተሰምሮበታል ። የሰም ዝርዝሮቹ በጣም ተጠጋግተው አጣበውታል ። የተሰበሰበው ሕዝብ ይጋፋ ፣ ይተራመስ ጀመር ። በማህል የሚቀደዱ ወረቀቶች ሁሉ ይታያሉ ። ወረቀቱን ያገኘ ያገኘው ወደ ኋላ ወጥቶ ለማንበብ ይታገላል ። ከኋላ ያለው ደግሞ "አሳልፉኝ!" እያለ ወደፊት ይገፋል ።

"ልጓሙን ያዝልኝ" አለ ሬት ባጭሩ ፣ ወደ መሬት ወርዶ ልጓሙን ለአጎት ፒዮር እያቀበለ ። በግራያው ማህል እየሰነጠቀ በጭካኔ ወደፊት እየገፋ ሲገባ ሰፊ ትከሻው ከሰው በላይ ይታያል ። ባንድ አፍታ ማማሽ ደርዘን የሚሆን ወረቀት ይዞ ተመለሰ ። አንዱን ለሜላኒ ሰጠና ያቀረውን በአቅራቢያው ሠረገላዎች ላይ ላሉት ለወ/ሮ ማክለር ፣ ለ/ወ/ሮ ሚድ ለወ/ሮ ሚሪዌዘርና ለወ/ሮ ኤልሲንግ ሰጣቸው ።

"ፈጠን በይ ሜሲ" ብላ ጮኸች አስካርሌት ። ልቧ ጉሮሮዋ ላይ ተቀርቅራለች ። የሜላኒ እጆች በጣም ስለሚንቀጠቀጡ ለማንበብ አስቸግሯታል ።

"ውስጂው" አለች ሜሲ ። አስካርሌት መንጭቃ ወሰደችው ። በ"ወ" የሚጀመረው የታሰ ። "ወ" ። አሃ ፣ እነዚያው ግርጌው ላይ ቀለም አጨመላልቋቸዋል ። "ዋይት" ማንበብ ጀመረችና ድምጿ ተንቀጠቀጠ ። "ዊከንስ . . . ዊን . . . ዜቡሎን . . . " ወይኔ ሜሊ ፣ የሱ ስም የለም! እሱ የለበትም! እረ በእግዚሃር ሜሊ ፣ ወይዘሮ ፒቲን እያቸው፣ አባክሽ የሚሸተት ጨው ቀና አድርጊያቸው ሜሊ ። "

ሜሊ ፣ ከደስታ ብዛት በግልጽ እያለቀሰች ፣ የወይዘሮ ፒቲን ጭንቅላት ደግፋ የሚያሸቱት ጨው ወደ አፍንጫቸው ሥር ቀረብ አደረገችላቸው ። አስካርሌት አሮጊቷን በወዲያኛው ወገን ደግፋ ልቧ በፈንጠዝያ ተሞላ ። አሽሌይ በሕይወት አለ ። እንኳን ሊሞት የመቁሰልም አደጋ አልደረሰበትም ። እሱን ማትረፉ እግዜር እንዴት ቸር ነው! እንዴት . . . ፣

@OLDBOOKSPDF

እስክርሌት ዝግተኛ የማታስት ድምጽ ስምታ ዘወር ብትል ፋኒ ኤልሲንግ ራስዋን እናቷ ደረት ላይ አንጋላ አየቻት ። የእለት ውኔታው የስም ዝርዝር ሠረገላው ላይ ወደቀ ። ወይዘሮ ኤልሲንግ ሴት ልጃቸውን ደግፈው ለማቁፍ ሲሞክሩ ከንፈራቸው ይንቀጠቀጣል ። ለሠረገላ ነጂው "ቶሎ በል ፤ ወዴ ቤት" አሉት ። እስክርሌት የስም ዝርዝሩን በፍጥነት ማተረት ። ዝግ ኤልሲንግ ከዝርዝሩ ውስጥ የለም ። ፋኒ አንድ ወዳጅ ጥሯት አሱ ሳይሞትባት አልቀረም ። የተ ሰበሰበው ሕዝብ ገለል ብሎ የመ/ሮ ኤልሲንግን መረገላ በሕዘን ዐጥቃ አሳለፈው ። ከዚያ ተከትለው የማክለር ሴት ልጆች በጋሪያቸው አለፉ ። መ/ሮ ፌይዝ እየነዳች ነው ። ጥርሷ አንድ ጊዜም በከንፈሯ አልተከደነም ። እንደ ድንጋይ በድናለች ። መ/ሮ ሆፕ ሞት ፊቷ ላይ እንዳረበበ ከጐኗ ቁጭ ብላ የእህቷን ቀሚስ ጭምድድ አድርጋ ይዛ ለች ። ኤሮኒቶች መስለዋል ። ትንሹን ወንድማቸውን ዳላስን በጣም ይወዱታል ። እነዚህ ሴቶች በዓለም ላይ ያላቸው ዘመድ ዳላስ ብቻ ነበር ። እሱም እንደኛውን ሄደ ።

"ማሲ! ማሲ!" ብላ ጮኸች ሜይቤል ፤ ደስታ ድምጽዋ ውስጥ ይሰማል ። "ሬኔም ደህና ነው ። እሽሌይም ሰላም ነው!ው! እግዚ ሃር ይመስገን ፤" ቫዕ ከትከሻዋ ወርዶ ወደታች በመሄዱ የእርግዝና ውጌታዋ እውን በግልጽ ይታያል ። ሆኖም እፏም ሆነች መ/ሮ ሚሪዌ ዘር አልተጨነቁበትም ። "ሠይ ፣ መ/ሮ ሚድ! ሬኒ" ድምጿ ባንድ እፍታ ተሰመጠ ። "ሚሲ ተመልከቺ! . . . መ/ሮ ሚድ እባክሽን ! ዳርሲ እንጃ . . . !"

መ/ሮ ሚድ ወደጭኗ እየተመለከተች ስለነበር ስሟ ሲጠራ እን ደሌም ቀና አላለችም ። ከጐኗ ያለው ትንሹ ፊል ግን ለማንም የሚነ በብ መጽሐፍ ነው ።

"ያው ፣ ያው እማማ" አለ ረዳት በማጣት ስሜት ።" መ/ሮ ሚድ ቀና ስትል ከሚለኒ ጋር ፀይን ለዐይን ተጋጨ።

"እነዚያን ቦት ጫማዎች አውን አይፈልጋቸውም" አለች ።

"ሠይ ውዴት!" አለች ሚለኒ በጩኸት ፣ መንሰቅሰቅ እየጀ መረች ። መ/ሮ ሂዙን ወደ እስክርሌት ትከሻ አሻገረቻትና ከሠረገላው ተስፈንጥራ ወርዳ ወደ ዶክተሩ ሚሰት ሄደች ።

"እማማ እኔ አየሁልሽ" አለ ትንሹ ፊል እንኑ ያለችውን አሸቦ ፊት ሴት ለማጽናናት ። "እናም ብትፈቅጂልኝ ያሉትን ደንኪዎች በመሉ እገድላቸው ነበር ።"

@OLDBOOKSPDF

ወይዘሮ ሚድ ሁለተኛ የማትለቅቀው ይመስል ጥብቅ አድርጋ ይዛው "አይሆንም!" አለች በታፈነ ድምጽ።

"ፊል ሚድ፣ አንተ ደግሞ አፍህን ዝጋ!" አለች ሜላኒ ልጁን ወጥ ለማሰኘት፣ ወደ ሠረገላው ወጥታ ከወ/ሮ ሚድ ጎን ተቀምጣ ከን ዷን በክንዱ አቆላለፈች። "ደሞ አንተም ሄደህ ተገድለህ ጠብትቀር የእናትህን ሐዘን ትቀንስላት መሰለህ? እንዲህ ዓይነት ደደብነት አይቼም አላውቅ። በል ሯሎ ወደቤት አድርሰን!"።

ፊል ልጓሙን ሲያነሳ ሜላኒ ወደ አስካርሌት ተመለሰች።

"አክስቴን እቤት እንዳደረስሽ ወደ ወይዘሮ ሚድ ቤት እንድ ትመጪ። ካፕቴን በትለር ለዶክተር መልእክት ታደርስልኛለህ ሆስፒታል ነው ያለው!"

ሠረገላው እየሳሳ በሚሄደው ሕዝብ ማህል አቋርጦ ሄደ። አን ጻንዶቹ ሴቶች ከደስታ ብዛት ያለቅሳሉ። አብዛኞቹ ግን የደረሰ ባቸውን ክፍተኛ ጥፋት ስማሰብ እንኳ ደንገዘቦል። አስካርሌት ደብ ገዘ ሊጠፋ የተቃረበውን የአለት ሁኔታ ዝርዝር ለማንበብ ራስዋን ደፋች — ጓደኞቿን ባገኝ ብለ። አሁን እሽሌይ ስለተገኘ የሌሎች ሰዎችን ስም መፈለግ ይዘለኝ። የስም ዝርዝሩ እንዴት ረዥም ነው! ከአትላንታ የመጡት ሰዎች፣ እንዴት መዓት ናቸው። ገ! ከድፍን ጆርጂያ የመጡትስ ቢሆኑ ገ!

ኧረ የሰማይቱ ያለህ "ካልቨርት..ሬፎርድ፣ መቶ አለቃ" ሬፍዬ! በድንገት ያ ቀን ትገ አላት፡- ከረዥም ጊዜ በፊት፣ አብረው የሄዱ በት አብረው የጠፉበት ጊዜ ታወሳት። አብረው ያመሹና ስለሚ ርባቸውና ጨለማውን ስለሚፈሩ ይመለሱ ነበር።

"ፎንቴን — ጆሴፍ ኬ፣ ተራ ወታደር" ውይ ግልፍተኛው ጆሲ! ሚስቱ ሳሊ ልጅ ከወለደች ገና ቅርብ ጊዜዋ እኮ ነው!

"ሙንሮ—ላፋዬት፣ ሻምበል" አቤት ላፉዬ! ከካትሊን ካልቨ ርት ጋር ቀለበት አስሯል እኮ! ምስኪን ካትሊን! የሷ ደግሞ እጥፍ ጉዳት ነው—ወንድሟንም ፍቅረኛዋንም ባንድ ጀምበር መነጠቅ። ቢሆንም የሳሊ እጦት ይብሳል—ወንድሟንም፣ ባሏንም።

ዉ...በጣም አስከፊ ነገር ነው። ቀጥላ ለማንበብ ልሷ እምቢ አላት — ፊራች። ወ/ሮ ፒቲ ከትከሻዋ በላይ ቁና ቁና ይተነፍሱ ታል። አስካርሌት ገፋ አድርጋ በሠረገላው መቀመጫ ጥግ አስቀመ ጠቻቸውና ንባቧን ቀጠለች።

@OLDBOOKSPDF

በእርግጥም "የታርሴሉን ቤተሰብ ልጅኽ" ስም ሶስት ሲሆን አይችልም። ምናልባት . . . ምናልባት አታሚው በስህተት ስም ደግሞ መሆን አለበት። ግን አይደለም። እንዚሁና፡—" ታርሴሉን — ብሬንተን፣ ሙቶ አሰቃ "፡" ስቱዋርት ፡ አሥር አሰቃ ፡" ታርሴሉን — ቱማስ ፡ አሥር አለቃ" ። ቦይድ ምስኪኑ ጠርነቱ ገና ሲጀመር ሞቷል ። የተቀበረው የት እንደሆን አማዚሀር ይወቅ—ቨርጂኒያ ውስጥ አንዱ ጋ ተጥሏል ። ሁሉም የታርሴሉን ቤተሰብ ልጆች ሂደዋል ። ቱምና ቅል ጭማም መንትያ ወንድሞቹ ሐሚታና ትርጉም የለሽ ቀልድ ይወዱ ነበር ። ቦይድ ደግሞ የጸንስ አስልጣኝ ማርማ ሞገስና መንታ ምላስ ነበረው ።

ከዚህ ወዲያ ሰማንዘብ አልቻለችም ። አብራ የደነሰቻቸው ፡ የተላ ፋቻቸው ፡ የተሰባመቻቸው ሴሎች አብሮ አደጐቹ ይመጡ ይኑር ሰማወቅ አልቻለችም ። ብታስቅስ ፈታዴ ነበር ። ጉርሮሞን የያዘች ባቸው እንደብረት የጠነከሩ ጣቶቹ ሊያንቋትና ሰጋሞን በስተው ሊገቡ ምንም አልቀራቸው ።

"በጣም አዘናለሁ እስካርሴት" አለ ፈት ። ቀና ብላ አየችው። እስካሁን እዚያው መሞሩን ዘንግታለች ። "ብዙ ጓደኞችሽ የሉምን?"

አራሲን ንቅንቃ ለመፍገር ሞከረች፡—"ዝመንደራችን ምን ሰው ቀረ ብለህ ነው . . . እናም ሁሉም . . . ሁሉም የታረሴትን ልጆች አሉበት"

ፊቱ እርግት ብሎ መታበር መስሏል ። ወይኖቹ ሙስጥም የማሾፍ ስሜት የለም ።

"ገና ይቅራል እኮ—ይቀጥላል" አለ ። "እንዚህ የመጀመሪያ ስም ዝርዝሮች ናቸው ። አጨሞጁሉም ። ነገ በዛ ያለ ዝርዝር የያዘ ይወጣል ።" በእቅራቢያው ሠረገላምች ላይ ያሉት ሰዎች እንዳይ ሰሙ ድምፁን ዝቅ አደረገ ። "እስካርሌት ፡ ጀኔራል ሊ ድል ተመትቶ መሆን አለበት ። ወደ ሚሪላንድ ማፈግፈጉን ዋናው ጦር ሠፈር ሲወራ ሰማሁ ።"

የፊሩ ወይኖቹን ወደሱ ቀና አደረገች ። ፍርሃቷ ከጀኔራል ሊድል መሙታት የመነጨ አልነበረም ። ነገ ሲላ የሰም ዝርዝር ይመ ጣል ስለተባለ ነው! ነገ እንዴ ፡ በዚች በአሠሩ ደቂቃ እንኳ ሞቶ ሊሆን ይችላል እኮ ! አለዘ ነገ ደግሞ ምንም ለማወቅ አትችልም ። ምናል ባትም የነገ ሳምንት ድረስ ሳታውቅ ትችላለች ።

"ወይኔ ፣ሬት ! ጦርነቶች ባይኖሩ ምናለበት! ያንዚያቹ የባሪ ያምቹን ጉልበት በገንዘብ ተምነው ቢከፍሉላቸው ይሻል ነበር ።

@OLDBOOKSPDF

ወይም እኛም ብንሆን ፣ ይሄ አስከፊ ነገር ሲፈጸም ከማየት ባሪ ያዎቹን በነፃ ብንለቅላቸው ይሻል ነበር እኮ ።"

"እስካርሌት የባሪያዎቹ ጉዳይ አይደለም እኮ ። እነሱ ሰበብ ሆኑ እንጂ ነገሩ ሌላ ነው ። ወንዶች ጦርነትን ስለሚያፈቅሩ ምን ጊዜም ጦርነት ይኖራል ። ሴቶች አይፈልጉም . . . ወንዶች ግን ነብ ሳቸው ነው . . . አዎን . . . ከሴት ፍቅርም የበለጠ ጦርነት ያፈቅ ራሉ ።"

አፉ እንደተሰመደው ተጣመመና ሽሙጡን ጀመረ ። ያ የአሽ ሙር ፈገግታው ብቅ አለና የምር ተኮሳትሮ የነበረ ገጽታው ፣ ወደ ተንኮል አገር ተሰደደ ። ሰፊውን የፓናማ ባርሜጣውን ብድግ አደ ረገ ።

"ደህና ሁኚ ። ዶክተር ሚድን ልፈልግ መሄዴ ነው ። የልጅን መርዶ ነጋሪው እኔ መሆኔ አሁን አይሰማው ይሆናል ። ውሎ አድሮ ግን የጀግናን ሞት መርዶ አንድ ሰማብሳብ ነጋዴ ይዘ መምጣቱን ማሰብ እንኳ ያስጠላው ይሆናል ። ይቆጨዋል ።"

እስካርሌት ወ/ሮ ፒቲን ውሃና ኤልኮል አድርጋ ካስተኟቻቸው በኋላ ፕሪሲና ኩኪ እንዲጠብቋቸው አድርጋ ወደወይዘሮ ሚድ ቤት ለመሄድ ቁልቁል መንገዱን ይዛ ወረደች ። ወይዘሮ ሚድ እፎቅ ከፈል ጋር ተቀምጣ የባሏን መምጣት ትጠብቃለች ። ሜላኒ እልፍኝ ተቀምጣ ሊያስተዛዝኑ የመጡትን የጐረቤት ሰዎች ድምጿን ዝቅ አድርጋ ታነጋግራለች ። ወይዘሮ ኤልሲንግ ለወ/ሮ ሚድ ያዋሏትን ጨርቅ በመቀስ እየቆረጠች በመስፋት የሐዘን ልብስ ስታዘጋጅ ቆይታለች ። ማድቤት በማቅለሚያ ውስጥ የሚነከረው ጨርቅ ሽታው ቤቱን ሞልቶታል ። የምትንሰቀሰቀዋ ወጥ ቤት በትልቅ ማጠቢያ ውስጥ ለሀዘኑ የሚሆን ጨርቅ በጥቁር እየነከረች ነው ።

"አሁን ወ/ሮ ሚድ እንዴት ናት?" አለችና ጠየቀች እስካርሌት፣ ለስለስ ብላ ።

"አታለቅስም እንባዋ እምቢ አላት" አለች ሚላኒ ። "ሴቶች ማልቀስ ሲያቅታቸው በጣም ያሰቅቃል ። ወንዶች ሳያለቅሱ ችግሮ ቻቸውን እንዴት እንደሚቋቋሙ ይገርመኛል ። እነደሚመስለኝ ከሴ ቶች የተሻሉ ጠንካሮችና ቆራጦች ስለሆኑ ነው ። ፔንሲልቫንያ ድረስ

@OLDBOOKSPDF

ሄጄ ፈሳውን አመጣለሁ ነው አምትለው ። ዶክተሩ ሆስፒታሉን ጥሎ መሄድ አይችልም ።''

''ለዚ በጣም አስፈሪ እኮ ነው ! ለምን ፈል አይሂድም ?''

''እሱ አንዴ ከዚ ከመሰጠ ከሠራዊቱ ጋር ይቀላቀላል የሚል ሲጋት አሳት ። ምንም ዕድሜው ትንሽ ቢሆን ትልቅ ነኝ ብሎ ያስ ባል ። አሁን ወደጦር ሚዳ የሚወሰዱቸው ወጣቶች የአሥራ ስድስት ዓመት ልጆች ናቸው ።''

አንድ በአንድ የዓረቢቱ ሰው ሁሉ እየተሰናበተ መጣ ። ዶክተሩ ሲመጣ እዚያ ለመገኘት ፈቃደኛ የሆነ ሰው የለም ። አስካርሴትና ሚላኒ ብቻ እልፍኝ ውስጥ ስፈታቸውን እንደያዙ ቀሩ ። ሚላኒ ሐዘን ይነበብባት አንጄ ረጋ ብላለች ። እንባዋ ግን በጅዋ የያዘችው ጨርቅ ሳይ ዱብ ዱብ ይላል ። ወርነቱ አሁንም አንዴ ቁጠለ ነው የሚል እርግጠኛ ግምት የላትም ። አሽሌይ ሞቶ ሊሆን ይችላል ። አስካር ሴት ፣ ፈት የነገራትን ሆኗን የሚያርጣትን ከራ ወሬ ለሚላኒ ነግራ የስቃይዋ ተከፋይ ታርጋት አታርጋት ግራ ገብቷታል ። በመጨረሻ ገዛ ብላ መቀመጡን መረጠች ። ለለአሽሌይ በጣም የተጨነቀች መሆኗን ሚላኒ ማወቋ ደግ አይደለም ። መቼም ሚላኒና ወይዘሮ ፒቲን ጨምሮ እያንዳንዱ ሰው በገዛ ራሱ ጭንቀት ውስጥ ስለስጠመና የሷን የዛሬ ጠዋት ሁኔታ ስላሰየባት እግዚሃርን አመሰገነች ።

ለጥቂት ጊዜ በዝምታ ስፈታቸውን ሲሰሩ ከቆዩ በኋላ ከደጅ ድምጽ ሰሙ ። በመጋረጃው አሻልተው ሲመለከቱ ዶክተር ሚድ ከፈ ረሱ ሲወርድ አዩት ። ትከሻው ተከማችሏል ። አንገቱን በጣም ከማ ቀርቀሩ የተነሳ የአንጭ ጢሙ እደረሱ ሳይ የተዘረጋ ማራገቢያ መስ ሏል ። ቀስስ እያለ ወደቤት ገብቶ ባርሚጣውንና ቦርሳውን አስቀ መጠና በፀጥታ ሁለቱን ሴቶች ሰማቸው ። ከዚያም በደካማ እርምጃ ወደፎቅ ለመሄድ ደረጀውን ወጣ ። ወዲያውኑ ፈል ቅጥ ባጣ ሁኔታ እየተደነባበረ መጣ ። ሁለቱ ሴቶች መጥቶ ይቀላቀለናል ብለው ሲጠ ብቁ ወደፊት ለፈቱ በረንዳ ሂዶ ላይኛው ደረጀ ሳይ ተቀመጠና ሚንቅላቱን እመዳፎቹ ውስጥ ቀበረ ።

ሚሲ በጋይል ተነፈሰች ።

''ሂዶ ያንኪዎቹን እንዳይዋጋ ስለተከለከለ ተናድዶ ነው ። ግና በአሥራ አምስት ዓመቱ ! ወይኔ እስካርሴት ፣ እንዲህ ያለ ወንድ ልጅ ቢኖርሽ እኮ ገነት መግባት ማለት ነው !''

''እናም ጦር ሚዳ ልከሽ ማስገደል'' አለች እስካርሴት ፣ ዳርሲን በልቧ እያሰበች ።

@OLDBOOKSPDF

"ምንም ልጅ ሳይኖርሽ ከሚቀር መቼም፣ አንድ ወንድ ልጅ ኖሮሽ ሲዋጋ ቢሞት ይሻላል።" አለችና ሚሳኒ ትንሩሿን መዶ ውስጥ ሳበችው "እንቺ ሊገባሽ አይችልም እስካርሌት። ትንሹ ዋድ ስላለልሽ ሊገባሽ አይችልም። እኔ ግን . . . ሙይ እስካርሌት ልጅ መውለድ እንዴት እንደምፈልግ መቼም፣ ልነግርሽ አልችልም! እንዲህ ፊት ለፊት በመና ገራ ብልግና ነው ትይኝ ይሆናል! ግን ከልቤ ነው። ደሞም ግንም ሌት የምትፈልገው ነገር ነው።"

እስካርሌት እንዳያስነጥሳት ትታገላለች።

"የእሽሌይ መሄድ የእግዚሃር ፈቃድ ከሆነ መቼስ እችለዋለሁ። ከመሞቱ በፊት ግን እንዲያስቀድመኝ አፈልጋለሁ። የምጸናናበት ልጅ እንኳ ሳይኖረኝ ሞቶ ከሚሉኝ አዚያው ድብን ብል ይሻለኛል። ወይኔ እስካርሌት፣ አንቺ እንዴት ፅድለኛ ነሽ! ምንም ቆር ሲን ብታጪ ወንድ ልጅን ተክተሻል። እኔ ግን አሽሌይን ባጣ ያስ ምትክ መቅረቱ ነው። እስካርሌት፣ እትታዘቢኝና ባንቺ በጣም እቀ ናአለሁ። . . ."

"በኔ ትቀኚለሽ!" ብላ ፎገች እስካርሌት፣ የሀሊናዋ መቀሳ እየጮሰማት።

"እንቺ ልጅ ስላለሽና እኔ በለቤሰኝ አቅናለሁ። አንዳንድ ጊዜ ልጅ ሳይኖረኝ መቅረቱ በጣም ስለሚያሰቅቀኝ ዋድ የኔ ልጅ እን ደሆነ አድርጌ ሰጣስመስል እሞክራለሁ።"

"ድራንደንዴን ሂድ እንግዴህ!" አለች እስካርሌት በልቧ፣ በራ ጅሙ እየተነፈሰች። ፊቷ ቀልጥ የምትሰኙው ጨርቅ ላይ የተደፋ ችውን ቀሚን ሴት ለአንድ አፍታ አስተዋለቻት። ሚላኒ ልጅ ትፈልጣ ይሆናል። በውነቷ ግን የወላድ ዓይነት አይደለም። ልጅ የሚ ሸከም ሆድ ያላትም አትመስል። ከአሥራ ሁለት ዓመት ልጅ የበለጠ ቁመት የላትም። ዳሌዋ የሕየን ዳሌ ነው የሚያክለው። ጡት የሚ ባል ደረቷ ላይ አያታይም። ጅው ያለ ሜዳ ነው። የሜላኒን የልጅ እናት መሆን እስካርሌት አትሻውም። ልትሸከማቸው የማትችላቸውን ብዙ ሀሳቦች በአእምሮዋ ውስጥ ያተረማምስባታል። ሚላኒ ከአሽ ሌይ ልጅ ብትወልድ እኮ፣ እስካርሌት አንድ የራሷ የሆነ ነገር ተነ ጥቆ የተወሰደባትን ያህል ይሰማታል።

"ስለዋድ የተናገርኩትን ነገር ይቅር በይኝ። በጣም ስለምወደው ነው። አላበላጨሁሽም አይደል?"

"እንግዴህ ደደብ አትሁኝ" አለች እስካርሌት ባጭሩ። "ይልቅ ወደበረንዳው ሂጅና የፊልን ነገር አንድ በይው። እያለቀሰ እኮ ነው።"

@OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ 15

ሠራዊቱ ከቨርጂኒያ ከተባረረ በኋላ ራፒዳን ላይ ባሉት የከረ ምት ጦር ሰፈሮች ውስጥ ገብቶ ተቀመጠ። ይህ ሠራዊት ከጊት ስበርጉ ሽንፈት በኋላ የደከመና ኃይሉ የነጠፈ ሆኗል። የገና በዓል ወቅት እየተቃረበ ሲመጣ አሽሌይ እረፍት ተቀብሎ ወደ አትላንታ መጣ። አስካርሌት ከሁለት ዓመት በላይ ሳታገኘው ቆይታ አሁን ስታየው ስሚቷ ሁሉ ንጉፍ ፍርሃት ፍርሃት አላት። ያኔ በ"አሥራ ሁለቱ ዋርካሞች" መንደር በረንዳ ላይ ቆማ ሚላኒን ሲያገባ ባየች በት ወቅት በዚያን ጊዜ ከፈቀረችው የበለጠ ወደፊት በምንም ዓይ ነት ልታፈቅረው እንደማትችል አበባ ነበር። አሁን ግን ያ ሁሉ ፍቅር አንድ ቅምጥል ሕፃን ለአሻንጉሊቱ ከሚኖረው ስሜት የበ ለጠ እንዳልነበረ ታያት። ስለሱ ሰረጅም ጊዜ በማለሚ፣ እሱን ለረ ጅም ጊዜ በመናፈቋ፣ ስለሱ ለረጅም ጊዜ ስትጭነር በመቆየቷ ስሚቷ ሁሉ ሽሮ የእሱኑ ከምንጊዜውም ባለ።

ይሄ የአሁኑ አሽሌይ ዊክስ፣ ይሄ የንጣጣና የተቀዳደደ ዩኒፎርም የለበሰ አሽሌይ ዊክስ፣ ይሄ ቡናማ ፀጉሩ በዐሀይ ብዛት ግራጫ የሆ ነው አሽሌይ ዊክስ፣ ከዚያ ከጥንቱ ክጠዋቁ ከወርንቱ በፊት እንደነ ፍቢ ታፈቅረው እንደነበረው ተጫዋችና ቀዝገ ያሉ ዓይኖች ያሉት ሸጋ ሰው በጣም የተለየ ነው። ያኔ ድምፁ ሁሉ ካሁኑ ሺማዜ ልብ የሚሰርቅ ነበር። በፊት ቀላ ያለና ሎጋ ለማለጋ የነበረው አሁን ከሲ ታና ጠሚጋ ሆኗል። በአራ ጳርና ጳር ይወርድ የነበረው ወርቅማ ጢሙ በፈረሰኛ ጦር ጢም አለጫጨት በዴ ተሳጭቶት ትክክለኛ ውን እንከን የለሹን የወታደር አጭሞና ገጽታ ያከለበት የመጨ ረሻው ጥበብ ነበር።

የጥንቱን ዩኒፎርሙን ለብሶ በሚሊተሪ ቆጥማና አጭቋም ቆሟል። ሽጉጡ በተቀዳደደ ማኅደሩ ውስጥ እንደነገሩ ተሸጉጧል። የጐራ ዴው ሰገባ ቀስ እያለ ቅርፁን ጠብቆ እየወረደ የቡት ጫማውን እፍ አየታከከ ይቀለበሳል። አርጅተው የደበዘዙት የፈረስ መኮልኮያዎቹ ሻሲቃ አሽሌይ ዊክስ። ሲ ኤስ ኤ የሚለውን ጽሑፍ እንደያዙ ናቸው። አሁን የአዛዥነት መንፈስ ከሁኔታው ይነበባል። በጥ ያለ በራስ የመተማመን አየር ይንጭስበታል። የባለሥልጣንነት ስዕል ተሰሙበታል። በአራ ግራና ቀኝ ጨምደድ ያሉ መስመሮች መታ

@OLDBOOKSPDF

ፅት ጀምረዋል ። በማዕዘናማ ትከሻውና ቀዝቃዛ ብርሃን በሚያመ
ነጩት ዓይኖቹ ላይ እንድ አዲስና እንግዳ ነገር አለ ። ዱሮ ዘና ያለና
ማዴለሽ የነበረው ሰውዬ አሁን አሁን አይጥ አይታ ልትዘል እን
ተዘጋጀች ድመት ንቁና ቀልጣፋ ሆኖ ነርቮቹ ሁሉ እንደከራር ከር
የተወጣጠሩ ይመስላሉ ። በዓይኖቹ ውስጥ በሥራ የመታከትና የጭ
ንቀት ሁኔታ ይታያል ። የፊቱ ቆዳ ከፀሐይ ብዛት ጥቁርሻ ከመምሰ
ሉም በላይ ቆዳው አጥንቱ ላይ የደረቀ ይመስላል ። ያ የሷ ው፤ የእስካርሌት
አሽሌይ ፤ የራሷው ቆንጆው አሽሌይ ነው ። ግን ተለውጧል ። የተሰየ
ሆኗል ።

እስካርሌት የነናን በዓል ታራ ሄዳ ለማሳሰፍ አቅዳ ነበር ። የአ
ሽሌይ ቴሌግራም ከመጣ ወዲያ ግን በዓለም ላይ ያለ አንዳችም ኃይል
ሌለን እራሷ እንኳ ተበሳጭታ ብታዛት ከአትላንታ የምትነቃነቅ
አልሆነችም ። አሽሌይ ወዴ "አሥራ ሁለቱ ዋርካዎች" መንደር የመሄድ
አዝማሚያ ቢኖረው ኖሮ እንኳ ወዶሱ ጠጋ ለማለት ያህል ወደተራ
ትሬድ ነበር ። ነገር ግን አሽሌይ ለቤተሰቡ በየፈው ደብዳቤ እዚሁ
አትላንታ ድረስ መጥተው እንዲያዩት ስለንገራቸው አባቱ ጆን ዊከስ
ሐኒና ኢንዲያ ቀድመው አትላንታ ንብተዋል ።

ደሞ ብላ ብላ ስሁሰት ረዣዥም ዓመታት ሳታየው ቆይታ ወደ
ታራ ትሂድ እንዴ፣ ያንን ልብ የሚያጠፉ ድምጹን ትጣው፣ በዓይ
ዋቹ ውስጥ እንዳልረሳት የሚናገረውን ትርኢት ሳታይ ትቅር፣ በጭ
ራሽ እይሞከርም ፣ በጭራሽ ! ለምን በዓለም ላይ ያሉ እናቶች በሙሉ
ትሰብስበው አይጠሯትም እንዴት ጋት እንኳ አትንቀሳቀስም ።

አሽሌይ ወደቤት የመጣው የነና በዓል ከመድረሱ ከአራት
ቀናት በፊት ነው ። ከጌትስበርግ ሽንፈት በኋላ የአሽሌይ መንደር
ልጆች ቁጥር በጣም ተመናምኗል ። አሽሌይ የመጣው ከዚሁ
ከተመናመነው ቁጥር ቀንሶ ጥቂት የመንደሩን ልጆች ይዞ ነው ።
ካድ ካልቨርትም አብሮ መጥቷል ። ከስቶ ጉስቁልቁል ብሷል ። ደግሞ
ደጋግሞ ያስላል ። የሙንሮ ቤተ ሰብ ሁለቱ ልጆች ከ1861 ወዲህ
የመጀመሪያውን እረፍት አግኝተው በመምጣታቸው በደስታ ተጥ
ለቅልቀዋል ። አሌክስና ቶኒ ፎንቴን በጣም ይጠጣሉ ፣ ጉራ ይነ
ዛሉ ፤ ይደባደባሉ ። ቡድኑ አንድ ባቡር አሳልፎ ሌላ ባቡር እስኪ
መጣለት በሚጠባበቅባቸው ሁለት ሰዓቶች ውስጥ የፎንቴን ልጆች
አርስ በእርስ እየተጣሉና በባቡር ጣቢያ ያሉትንም እንግዳና ሰላማዊ
ሰዎችን ለማረጋጋት የረጋ አእምሮና ዲፕሎማሲ ያለው ሰው በማ
ስፈለጉ አሽሌይ ሁሉንም ወዶ ወይዘሮ ፒቲፓት ቤት ይዟቸው መጣ።

"ቨርጂኒያ ውስጥ ብቻ ተደባድበው የበቃቸው መሰላችሁ!"
አለ ካድ ፣ ሁለቱ ወንድማማቾች ወ/ሮ ፒቲፓትን መጀመሪያ ማን

@OLDBOOKSPDF

ጅሉም ነው፡፡ ሚለው ጉዳይ እንዴአውራ ዶሮ ሲጣሉ አይቶ ምርር ብሎት ፥ “ማን አየይደለም ። ከሪችሞንድ ጀምሮ እንዲሁ ጠብ እንደጫሩ አለ። የአሥር ቤቱ ዘበኛማ ጋማ ጋማቸውን ይዞ መሸጂቸው ነበር አድሚ ለአሸሌይ ዝቅናና በሰላ አንደበቱ አስገዶ ለመነሳቸው እንጂ የጣና በዓል አስሮቤት ይከርሚት ነበር ።”

አስካርሌት ካድ የሚለፈልፈውን አንዱንም አልሰማች ። እሷ ለራሷ ከስንት ጊዜ በኋላ ከአሽሌይ ጋር ብእንድ ክፍል በመቀመጫ በደስታ ሰክራለች ። ለመሆኑ እስከዛሬ ሴሎች ወንዶች ማሩም ናቸው ወይም ቆንጆዎች ናቸው አሊያም አስደሳች ናቸው ትል የነበረው በምን ሂሳብ ነውየ እንወድሻለን ፥ እናፈቅርሻለን የሚሏትንስ ወንዶች እንዴት ብሎ በትእግሥት ሁሉበለቻቸውየ አሽሌይ በዓለም ላይ እያለ እንዴት ሊጥሚት ይችላለችብቻ እንኳን እንደገና ወደቤት መጣ ። እን ኳን እንደገና ዓይኑን አየችው ። ይገርማል አሁን እኮ ከአሽሌይ ርቃ ኖትቅመጠችው የአልፍኖን ምንጣፍ ርዝመት ያህል ብቻ ነው ፥ አሽሌይ ሚላኒን በአንድ ጉኑ ፥ ኢንዲያን በሌላ ጉኑ ፥ ሐኒን በሰተ ጀርባው አድርጎ ቡፉው ላይ ተቀምጠ አስካርሌት ስታየው የደ ስታ እንባዋን ለማፍሰስ ያለ የኩለ አቅሟን እንድትጠቀም ትነደዳለች ። ምነው ከንጂን በከንፉ አቆላልፎ እሳኑ ሻጥ ማለት በቻለች እንዴት ዓለም ነበር ። ምነው በየደቂቃው የሴታውን እያስቱካከለች አጠገቧ መኖሩን ሚረጋገጥ በቻለች ። ምነው እሱን ይዛ ሰመሀረቡ እንባዋን የማድረቅ ዕድልን በተገፍፀጌች ፥ ይቺ ሚላኒ እኮ እነዚህን ሁሉ ነጎ ሮች ያለ ፀፍረት ታደርጋለች ። በጣም ክመጀስቱም ብዛት ቄምትን ቷንና ቆጠብ ማለቷን ሁሉ ትታ እባቧ ከንድ ላይ ተንጠልጥላ በዓይ ኗም በፈገግታዋም በእንባዋም ታጫውተውቅለች ። አስካርሌት ደግሞ ጀሄን ሁሉ መቃወሟን ትደስትበታለች ። በዚህ መቅናቷን ችረካበ ታለች ። እነሆ በመጨረሻ አሽሌይ ቤቱ ገባ ።

አስካርሌት አሁንም እጅዋን አሽሌይ የሳማት ቦታ ላይ አድርጎ ጉንጯን እያሻሸች በወቅቱ ተሰምቷት የነበረውን የልብ መሸበር ፥ የከንፈሩን ንክሪትና ሙቀት እንደገና በሀሳቧ ታጣጥምና ወደሱ ዞራ ፈገግ ትላለች ። እርግጥ መጀመሪያ የመሳሙን ዕድል ሚላኒ ኑጥቃ ታለች ። ሚላኒ እጅና እግር የሌለው የተምታታ ጨቨት እየጮቨች በላዩ ላይ ስትጠመጠም እስከዘለዓለም የምትላቀቅ አትመስልም ነበር። ስለዚህም አስካርሌትን በመጀመሪያ አልላማትም ። ከሜሊ ደግሞ ኢንዲያና ሐኒ ተሻምተው ከሚላኒ እቅፍ መንጭቀው ተቀራመቱት ። ከዚያ ደግሞ ካባቱ ጋር ተጨማጨሙ ። በአባትና ልጅ ማህል ያለ ውን ጠንካራና ረጋ ያለ ስሜት በሚያሳይ ኩሩ መውደድ ተሞልቶ አባቱን ሳማቸው ። ቀጥሎም እኒያ ለጽላ እማራቸው የሚችሰውን ያህል

@OLDBOOKSPDF
ሙቤ የሚረግጡት ወይዘሮ ፒቲዎት ተራ ስለገቡ አሳቸውን ሳመ። በመጨረሻም በዙሪያዋ ከበው "አ! እስካርሌት ፡ አንቺ ውብ ነገር! ነፍስ ነገር" እያሉ በሚጮሁት ወንዶች ሚሀል ወደቆመችው ወደ እስካርሌት መጥቶ እጉንጯ ላይ ሳማት ።

እስካርሌት ለእንኳን ደህና መጣህ የደስታ መግለጫ ያዘጋጀቻቸው ቃላት በሙሉ ግና ሊሰማት ከንፍ አውጥተው በረሩ ። ከንፈሯን እንዳልሳማት ያስታወሰችው ከብዙ ሰዓታት በኋላ ነው ። ወዲያው ትኩሳት እየተሰማት በመገረም እንዲህ ብላ አሰበች ፡—ለመሆኑ ብቻዋንስ ቢያገኛት ኖሮ ከንፈሯን ይስማት ነበር እንዴ? ያንን ረጅም ቁመቱን በማጐንበስ ዝቅ አድርጐና እሷም በእግር ጣቷቋማ ተንጠራርታ ከንፈር ለከንፈር ሊገናኙ በእጁ ጥበቅ አድርጎ ይሏት በጣም ለረጅም ጊዜ ይቆይ ነበር እንዴ? ይህንን ነገር ቢያደርገው ሊሰጣት የሚችለውን ወደር የሌለው ደስታ አሰበችና ያደርገዋል ብላ አመነች ። ወጣም ወረደም ለእንደዚህ ያለው ነገር ግና አንድ ድፍን ሳምንት እሰ ፡ በእርግጥም ደግሞ እንደምንም ብላ ለብቻው ታገኘውና "እንዚያን በምስጢር በፈረስ እየጋለብን ተፈናጠን እን ሄድባቸው የነበሩ ጉዞዎች ታስታውሳለህ?" "አንድ ቀን ማታ ታራ ደረጃው ላይ ቁጭ ብሰን አንተ ያኔን ግጥም ስትጠቅስ (ኧረ የለማ ያቱ ያለህ ምን ምን ነበር የዛ ግጥም ርዕስ? ምን ቸገረኝ ይቅር) ጨረቃዋ እንዴት ደምቃ እንደነበር ትዝ ይልሀል? አንድ ቀንስ ጀምበር ከጠለቀች ወዲያ ቁርጭምጭሚቱ ግድም እግሬን ወለም ብሎኝ በክንድህ ታቅፈህ እቤት ያገባኸኝ ትዝ ይልሀል?" ትለዋለች ።

አቤት ፡ ትዝ ይልሀልን እንደመግቢያ በመጠቀም ልትነግረው የምትችለው ነገር ብዛቱ ። እንደሀሳፍት ያለሀሳብ እየፈነጩ በየመን ደራ የሠሩባቸውን እነዚያን ውድ ቀናት እንዲያስታውስ ትዝ ይል ሀል ትለዋለች ። ሜላኒ ሐሚልተን ወደቲያትሩ መድረክ ሳትገባባቸው በፊት የነበሩትን የትዝታቸውን ቀናት ትዝ ይልሀል እያለች ዳግም እንዲያስታውስ ታደርገዋለች ። እናም እየተነጋገሩ እያሉ ስሜቱ በፍጥነት ጋልቦ ወደሷ እንደሚመጣ ፡ ለሜላኒ በባልነቱ የሚለማሳት ፍቅር የሠራውን ግድግዳ አልፎ አሁንም እሷን እንደሚያፈቅራት ፡ በዚያ የድግስ ቀን የሆዱን አውጥቶ አውነቱን እንደነገራት ሁሉ አሁንም እንደሚጨነቅላት ፤ ዓይኖቹ ውስጥ ለማየት ትችል ይሆናል ። አሽሌይ አፈትርሻለሁ ብሎ ይሩ የፍቅር አዋጁን በግልጽ ቢነግራት ምን እንደ ምታደርግ አታውቅም ። ብቻ እንደሚጨነቅላት ከነገራት ይበቃታል። አም እስካርሌት ለመታገስ ትችላለች ። ሜላኒ ከንዱን እየጨመቀች በማልቀስ የፍቅር ጊዜዋን ስትጨርስ ጠበቃ ታገኛዋለች ። ትታገሳ

@OLDBOOKSPDF

ለች ። የሷም ጊዜ ይመጣል ። ለዛውስ እንደው ለወጉ ነው እንጂ አሁን እንደሚላኒ ያለች ሴት ምን ፍቅር ታውቅና ነው ?

አሽሌይ እቤት የመምጣቱ ደስታ የፈጠረው ረብሻ ጋብ ሲል "የኔ ቆንጆ ፡ ቡቲታም መሰልክ እኮ" አለች ሜላኒ ። "ዩኒፎርምህን የሰፋልህ ማነውን ደሞ ለምንድነው በሰማያዊ ጨርቅ የጣራህን"

"እኔ እኮ በጣም ሽክ ብዬ ልቤ ወልቋል" አለ አሽሌይ ምን እንደሚመስል እያሰላሰለ ።" እዚያ ካሉት ሞርንቁሳሞች ጋር ብታወዳድሪኝ ኖሮ እንዴት እንደማምር ይገባሽ ነበር ። ሙሴ ነው የሰፋልኝ ። ዘመርነቱ በፊት መርፌ በእጁ ጨብጦ ስለማያውቅ ቆንጆ አድርጎ ሰፍቶታል ብዬ ነበር ። ለምን በሰማያዊ ጨርቅ ሰፋው ላልሺው የነበረን ምርጫ ወይ በተማረኩ የያንኪ ሰማያዊ ዩኒፎርሞች ቅጻጅ ማስጣፍ አሊያም የተቀደደውን ለብሶ መሄድ ስለሆነ ምን ማድረግ እንችላለን ? ባፕኝነው ጨርቅ መጣፍ መደረት ነበረብን። ስለቡቲታምነቱም ለጠየቅሽኝ ባልሽ ባዶ እግሩን ስላልመጣ ኮከብ ሽን አመሰግኛው እሺለሁ ። ባለፈው ሳምንት ቦት ጫማዬ ከጥቅም ውጪ ሆኖ በባዶ እግሬ ቀርቼ ነበር ። መቼም እግዜር ሳይጠግን አይሰ ብርም ሁለት ያየንኪ እስከወጡኞ ገድለን የነሱን ጫማ ባንወስድ ኖሮ ይሄኔ ትናንሽ ከረጢቶችን እግሬ ላይ አስሬ እመጣልሽ ነበር ። ያንደኛው ያንኪ ቦት ጫማ በእኔ እግር ልክክ ብሎ ገባ ።"

ረሣሾም ቅልጥምሹን ዘርግቶ ጫማዎቹን እንዲያደንቁለት ከፍ አድርጎ አሳያቸው ። "የሌላኛው አስካውት ቦት ጫማ ለኔ ላደርገው ብለው ብሠራው እምቢ አለና በግድ ገባ ። በጣም ስላነሰኝ እግሬን ሊቆርጠው ደርሷል ። ብዙ ከፋም ለማም እቤቱ ያደርሰኛል።" አለ ካድ ።

"አራስ ወዳፅ አሳማ አልሰጥ አለን እንጂ ለእኛ ይሆንን ነበር" አለ ቶኒ ። "በእነዚህ መሳጭንታዊ የሮንቱን ቤተሰብ ትናንሽ እግሮች ልክክ ብሎ ይገባ ነበር ። መቼም እግዚሀር በሚያውቀው ይሄን ዝተት ጫማ አድርጌ እናቱ ጋ መሄድ በጣም ያሳፍረኛል ። ከመርነቱ በፊት ባሪያዎችዋ እንኳ እንዲያደርጉት አትፈቅድላቸውም ነበር ።"

"አትጨነቅ" አለው አሌክስ ወደካድ ቦት ጫማዎች እያየ ። "ወደ ቤት ስንሄድ ባቡር ላይ እናስወልቀዋለን ። እኔ እንኳን እናቴን አልፈራትም ነገር ግን እኔ . . . ማለቴ . . . እኔ ያ ዲሚቲ መጎር የእግር አውራ ጣቱ በተቀደደ ጫማዬ አፍጦ ብቅ ሲል እንዲያይበኝ አል ፈልግም ።"

@OLDBOOKSPDF

"እንጂ ፥ እሳማ የኔ ቦት ጫማዎች ናቸው ። እመልሳለሁ ያልኩት እራሴ ነኝ" አለ ቶኒ ወንድሙ ላይ እየጮኸ ። ሜላኒ ይሄ ግጭት ወደዝነኛው የርንቱን ልጆች ድብድብ ያመራ ይሆናል ብላ ሰግታ እንኮም ተው እንተም ቱው አለችና ሰላም አወረደች ።

"ለሲሶቹ የማሳያቸው ሙሉ ጠም አለኝ" አለ አሽሌይ ፥ የእነጭ ጠሙን እየነካካና ምላሱ የቆረጠውን ግማሽ የዳነ ቁስል እያሸ ። "በጣም ቆንጆ ጠም ነበር ። እኔው ራሴ ላረጋግጥላችሁ የምችለው የጅብ እኩቦርትም ሆነ የናታን ቢድፎርድ ፎሬስት ከኔ የተሻለ ቆንጆ እንዳልነበረ ነው ። ነገር ግን ሪችሞንድ ሰንደርስ እንዚያ ሁለቱ ጹርዬዎች "አለ ወደ ፎንቱኖች እያላየ" ጠማቸውን ለመላጨት መወሰናቸውንና የኔም እንዲሳሙ እንደፈለጉበት ነገሩኝ ፥ ላፈልልኝ ። አለጫጨታቸውን መቼም ልነግራችሁ አለችልም ። ሞንትላቱ አብሮ ከጠሚ ጋር ክሰመሙደቁ ቱአምር ነው ። ኢባንና ክድ ጣልቃ ባይገቡ ኖሮ የክንፈር ጢሜም ኢይተርፉቸውም ነበር ።"

"እረ ሙሽቱን ነው መይዘሮ ሜሴ እንዲያውም ልታመሰግኗን ይገባል ፥ ጠሙ ችፍርግ ብሎ ኅድን በሞራሽ ማን እንደሆነ ለመለየት አትችይም ነበር ። በርሽንም ኢታሳልፈው" "አሰ አሌክስ ።" የአስር ቢቱን ሐላፊ አንጋግሮ ከአስር ቤት ሰሰግኳለን ውለታውን ላለማባ ከን ጪሙን ላጭኮን የጹሮውን አሽሌይ መልክ ፈልፍሰን አመጣ ንለት ። አውንም ፈቃድሽ ከሆነ የክንፈር ጢሙን ላፍ ልናደርገው እንችላለን ።"

"የለም የለም አመሰግናለሁ" አለች ሜላኒ በጥድፊያ ፥ አሽሌይን በፍርሀት ጭምድድ አድርጎ ይዛ ። እነዚህ ሁለት ጎረምሶች በጉል በት ሊላጩት ሰለሚችሉ ፈርታቸዋለች ። "አሁን እንዳለው ቆንጆ ነው ያምራል ።"

"ይሄ ነው ፍቅር ማለት" አሉ የፎንቱን ልጆች ፥ አርስ በእርሳቸው እየተያዩና ራሳቸውን እየነቀንቁ ።

አሽሌይ በወይዘሮ ፒቲ ሠረገላ ልጆቹን ባቡር ጣቢያ ድረስ ሊሸኛቸው ሲሄድ ሜላኒ የአስካርሌትን ክንድ ይዛ ፥

"ዩኒፎርሙ ለአይን የሚያስጠላ ነገር አይመስልሽም ? አሁን ኮቱን ብሰጠው ጉድ አይልም ? እሱ ምንው ለመጣሪያና ለሱሪ የሚሆን ብዙ ልብስ ቢኖረኝ ።"

ለአሽሌይ ይሰጥ የተባለው ኮት ነገር አስካርሌትን አላስደሰታ ትም ። ሜላኒ ሳትሆን እራሷ እስካርሌት ኮቱን የገና ስጦታ አድርጋ ብት ሰጠው በጣም ደስ ባላት ነበር ። ዛሬ ግራጫ ሱፍ ለዩኒፎርም ቀርቶ

@OLDBOOKSPDF

ለክት ልብሰም አይገኙ። ከናቢ የዘለጠ ተወዲሉ። አሽሴይ የሚለብሰው የተለመደውን አቤት የተሰፋ ሱሪ ነው። በኖ አይንት ጨርቅ አንኳን ሀፊ በብዛት አይገኝም። ስለዚህም አብዛኞቹ ወታደሮች የሚለብሱት የሚያዙ የያንኒ ዩኒፎርሞችን ቡኖ አይነት ተሰም እየነከሩ ነው። ሞኖም ሚላኒ በአጋጣሚ ሰፊ ሣራጫ ጨርቅ አግኝታ ረዥም አይባል አጠር ያለ ኮት ሰፍታለች። ሠለፔታል ወብጥ ስትሠራ አንድ ቻርልስተናዊ ልጅ ሊታከም መጥቶ እዚያው በመሞቱ በጉሩን ቁርጣ ሰብስባ በኪሱ ያገኘችውን ዕቃ አንድ ላይ አምራ የመጨረሻ ሰዓት የአሟሟቱን ሁኔታ ከማለስጥ ማስረጃና የማጽናኛ ደብዳቤ ጋር ለእናቱ ልካላት ነበር። እዚያ ጊዜ መዲያ ደብዳቤ መሰዋወጥ ጀመሩ። ቤትየዋ ሚላኒ ወር ግንባር ያለ ባል አንዳሰት ስለተረዳች ለሚቹ ልጅዋ ሃዘኑው የጎበረውን ሰፊ ሣራጫ ጨርቅና ከነሕብ የተሠሩ ቁልፎች ላከችላት ። ቆንጆ ሰቅ ነው ፤ ወፍራ ምና የሚምት ። ባለ ፈርጥ ጌጥም አለው ። መቹም ያለጥርጥር በቆንጆ ዕቃዎች አሸጋሪ ኮንትሮ ባንዲሰቶች የተገዛ ነው። በጣም ጠያ መሆን አለበት ። አሁን ለልብስ ሰፊ ተሰጥቷል ። ሚላኒ ለብስ ሰፊው ስጣና አሰት ጠዋት እንዲያደርስ አጣድፋ ንግራዋለች ። አወነርሴት አዩኒፎርሙ የሚቀረውን ነገር ማሟላት ብቻችል ደስ ይሉት ገቢ ። ነገር ግን ዛፊ ተራኒ ዕቃዎች አትለንታ ውስጥ አይገኙም ።

አሰካርሰት ስአሽሰይ የገኛ ስጦታ አዘጋጅታለት ነበር ። ነገር ግን ሚላኒ አዘጋጅትለት ግራጫ ኮት ግርማ ሞገስ አንጸር የሷ ስጦታ በጣም ያንሳል። ያዘጋጀችለት ስጦታ ፣ ሬት ከናሱ ካመጣለት መሀ ረቡኽ ሙስጥ ሶስቱን ፣ በጣም ውድ መርፌዎችን የያዘ የቤት እመቤት ዕቃ ማበጭመጫ ነው ። ሆኖም ንሷ ልትሰጠው የምታ ፈልገው ሚስት ለባሷ ልትሰጠው የምትችለውን እንደ ሸሚዝ ፣ እንደጓንቲ ፣ እንደባርሜጣ ያሰ ነገር ነው ። አሃ ፣ አምን አምን እንደ ምንም ብዬ ባርሜጣ ብሰጠው ጥሩ ነው ። አሽሴይ ያረገው ጠጥጣፋ አናት ያለው ባርሚጣ በጣም የሚያስቅ ዓይነት ሆኗል። አስካርሰት እንዚህን የመታዶር ባርሚጣዎች ከዱሮውም ትጠሳቸዋ ለች ። ገና ለገና ሰሎንዶል ጃክሰን ዘሰፌዎች ቆንጆ ባርሚጣዎች ሩንታ ይሸጣ የመረጠ እንደሆነ ስው ሁሉ ማድረግ አለበት እንደ፣ እሱ ስሳዶረጋቸው ግርማ ሞገስ ይኖራቸዋል ያለ ማነውየ ጸሩ ምን ያደርጋል አትለንታ ውስጥ የሚሰራት ባርሚጣዎች በሙሉ እንደው ድሬት ብቻ ናቸው ።

የባርሜጣ ነገር ስታስብ ሬት በትለር ትዝ አላት ። እሱ በጣም ብዙ ባርሚጣዎች አለት ። ለቢጋ ጊዜ የሚያረግ ስፊ የፓናማ ባርሚጣ። ሰተለመደ ዓይነት ጣብሀ የሚደረግ ባርሚጣ ፣ የአደን ባርሜጣ ፣

@OLDBOOKSPDF
ጥቁርና ሰማያዊ ተሻጣፊ ባርሜጣ አለው ። የሷው አሽሌይ በዝናብ ወዲህ ወዲያ ሲል ከባርሜጣው የሚንጠፈጠፈው ውሀ ኮሌታውን እያረሰረሰው ተቸግሮ ሳለ ሬት ይሄ ሁሉ ባርሜጣ ምን ሊያደር ግለት ሰበሰበው?

"በቃ ሬትን ያንን አዲሱን ጥቁር ባርሚጣ ስጠኝ አለዋለሁ" ብላ ወሰነች ። ጠርዝ ጠርዙ ላይ ግራጫ ሪባን አሰሩበትና የአሽሌይ ስም ያለበት ፊደል አጠልፍበታለሁ ። ከዛ በጣም ቆንጆ ይሆናል ።"

ቆም ብላ አሰበችና ባርሚጣውን ያለምክንያት ማግኘት እንደ ማትችል ገባት ። ዝም ብላ ሄዳ ለአሽሌይ የምሰጠው ባርሚጣ ስጠኝ ልትለው እትችልም ። እንኳን ለአሽሌይ የምሰጠው ነው ብላ ቀርቶ የአሽሌይን ስም ስትጠራ እንኳ ቅንድቦቹን ከፍ ከፍ አድርጎ የሚያ ሾፈው ሰውዬ እንዴት እሺ ብሎ ይሰጣታል? በቃ ዝም ብላ ሬት ዘንድ ቅሄድና ሆስፒታል ውስጥ አንድ የተቸገረ ወታደር ባርሚጣ ይፈል ጋል ብላ የመሸት አሳዛኝ ታሪክ ፈጥራ ታሳምነዋለች ። ሬት በጭ ራሽ ሊያውቅባት አይችልም ደሞ ማወቅም አይፈለግም ።

የዚያን ዕለት ከሰዓት በኋላ ቢያንስ ለጥቂት ደቂቃዎች ከአሽ ሌይ ጋር ለብቻዋ ለመሆን ብዙ ጥረት አደረገች ። ዳሩ ምን ያደርጋል ያቺ ሚላኒ በጭራሽ ከአጠገቡ የምትለይ አልሆነችም ። በዚያ ላይ እነዚያ ቅንድብ የለሾቹ ኢንዲያና ሐኒ ዓይናቸውን ከሱ ላይ አንነ ቅል አሉ ። በሱ የሚኮራው አባቱ ጆን ዊከስ እንኳ ለግል ቆይታ ጊዜ አላገኘም ።

ራት ላይም ቢሆን ያው ነው ። ሁሉም ስለጦርነት ይጠይቁታል፡ ይነዘንዙታል፡ ጦርነት ። ሰጦርነት ማን ይጨነቃል ? እስካርሌት አሽሌይም በዚህ ጉዳይ ላይ እንደሷ እንደማይጨነቅ ገመተች ። የሚያወራው የማ ያስርጥ ነገር ነው ። አልፎ አልፎ ይስቃል ። ከዚህ ቀደም አይታበት በማታውቀው ሁኔታ ወሬውን በመምራት መድረኩን የያዘው እሱ ሆነ ። ግን የሚናገረው ትንሽ ነገር ይመስላል ። ቀልድ ይነግራቸዋል ። ስለጓደኞቹ ታሪክ ያጫውታቸዋል ። ወታደሮች ተራ በሚያቀያይሩ በት ጊዜ ስለሚፈጠር አስቂኝ ነገር ያወራላቸዋል ። ረሀብንና በዝናብ ረጅም መንገድ መጓዝን ቀለል አድርጎ ያወጋል ። ከጌትስበርግ ሲያ ፈገፍግ ጄኔራል ሊ ምን ይመስል እንደነበርና የሚከተለውን ጥያቄ ይጠይቅ እንደነበር በዝርዝር አስረዳቸው ። "ጎበዝ ፣ የጀርጂያ ሠራዊት ውስጥ ናችሁ፣ መቼም እናንተን ጀርጂያውያንን ሳንይዝ መጓዝ አን ችልም ። "

እስካርሌት ይህን ሁሉ ዝባዝንኬ የሚያወራላቸው ለመሞላስ የማይፈልገውን ጥያቄ እንዳይጠይቁት ብሎ ነው ብላ አሰበች ። አባቱ

@OLDBOOKSPDF

በትክታ ለረጅም ጊዜ በተጨነቅ ዓይን ሲመለከተው ሲያይ ወዲያው መሬት መሬት አየ። እስክርቤት ይሄ ሁኔታው በልቡ ውስጥ ምን የተደበቀ ነገር ይኖር ይሆን የሚል የድንጋጤ ጥያቄን ፀነሰባት። ሀሳቧ ግን ወዲያው ተነነ። ለራሷ አሁን እንደጨረር ከሚፈነጥቅ ደስታና ከሱ ጋር ብቻዋን ከመሆን ፍላጎት ሌላ ጭንቅላቷ ምንም ሀሳብ አያስተናግድም።

በእሳቱ ዙሪያ ተሰብስቦ የነበረው ሰው ወደ ማደሪያው እስከ ሚሄድ ድረስ ይሄ ሀሳብ ከአእምሮዋ አልወጣም። ሰው ማዛጋት ሲጀማምር ጆን ዊክስና ሴቶቹ ልጆች ወደሆቴላቸው ሄዱ። በኋላም አሽሌይ፣ ሜላኒ፣ ፒቲፓትና እስክርቤት አጎት ፒተር ፋኖስ እያበራላቸው ደረጃውን ሲወጡ አንድ ቀዝቃዛ ሀሳብ መንፈሷ ላይ ጭጋጉን ጣለ። ፎቅ ያለው አዳራሽ ውስጥ እስክቆመባት የመጨረሻዋ ደቂቃ ድረስ ምንም ከሱ ጋር የማለ ጭውውት ለማድረግ ከሰዓት በኋላ ውን ሙሉ ባትችልም፣ አሽሌይን በልቧ የራሷ አድርጋ፣ የግል የብቻዬ ብላ ቆይታ ነበር። አሁን ግን ደህና እደሩ ብላ ተሰናብታቸው ወደ ማደሪያዋ ስትሄድና ወደማደሪያቸው ሲሄዱ፣ የሜላኒ ፊት በስሜት ተሞልቶ ወደሮዝነት ሲያደላና እንዳንድ ነገር ስትንቀጠቀጥ አየቻት። አይሞኟ ምንጣፉ ላይ ተሰክተዋል። ምንም እንኳን አንድ የሚያስፈራ ስሜት የተሰማት ብትመስል በአይን አፋርነት የተጠቀለለ ደስታን ሳትሳናፀፍ አልቀረችም። አሽሌይ የመኝታ ቤቱን በር ሲከፍት ሜላኒ ቀና ብላ እታይም ነበር። በሩን ሲከፍትላት ግን በፍጥነት ዘው ብላ ገባች። አሽሌይም ቃሉን ሳያስበው እንዳገኘው ሁሉ እስክርቤትን ድንገት ደህና እደሪ አላት። እንደ ሜላኒ የአሱም አይኖች የእስክርቤትን ዓይን አላዩም።

በሩ ከጆርባቸው ተዘጋ። እስክርቤት አፏን እንደከፈተች ብቻዋን ቀረች። ባዶ ምድረበዳ ላይ ድንገት ብቻዋን የቀረች መሰለ። ለካ አሽሌይ የፏ አይደለም። የሜላኒ ነው። ሜላኒ በሕይወት እስካለች ድረስ ደግሞ ከአሽሌይ ጋር መኝታ ቤት ገብታ በሩን ለመቆለፍ ትችላለች። የትኛውም ክፍል ከአሽሌይ ጋር ገብታ በሩን መዝጋት ትችላለች— የቀረውን ዓለም እውጭ ትታ በሩን መቀርቀር ትችላለች።

* * *

አሁን አሽሌይ ተመልሶ ወደ ቨርጂኒያ መሄዱ ነው። ሀሩርና ቁር ወደሚፈራረቁበት፣ የበረዶው ቅዝቃዜ ወደሚናከስበት፣ ሕመምና ችግር ጥርሳቸውን አሹለው ወደሚጠብቁበት፣ ወርቃማው ራሱና

@OLDBOOKSPDF

ሸንቃጣ ሰውነቱ ቅልጥፍ በሙ ተጀክሎ ሥር እንደገባች ጉንጻን
ወደሚረገጥበት ቦታ ተመልሶ ሊሄድ ነው ። ያለፈው ሳምንት ከነአስ
ደሳችነቱ እያንዳንዷን ሰዓት እየሰሰተ ከደመቀበት ትዥስሉቱና እንደ
ሕልም እንደቅዠት ውልብ ካለ ውበቱ ጋር ሳይጠገብ አለፈ ።

ሳምንቱ ሳይታወቅ በፍዋነት በማራርና በነና ዛፍ ሽታ እንደታ
ወደ ፣ በሻማና በማሾ ብርሃን እንደፈክ አስደሳች ሕልም ፣ ደቂቃዎች
እንደልብ ትርታ እንደሚበርሩበት አንድ አስደሳች ሕልም ሆኖ አለፈ።
አስካርሌት በሕመምና በደስታ በተመሰታቀለ ስሜት እያንዳንዷን
ደቂቃ ከተፈፀመባት ድርጊት ጭምር እንድትመዘግብና አሽሌይ ከሄደ
በኋላ በትዝታዋ ማሀደር እንድታቆይ የነፋፋትና ትንፋሽ ያላጣት
ሳምንት በችኮላ ከነፈ ። ወደ ፊት ጊዜ ስታገኝ ከተፈጸመው አስደሳች
ድርጊት ትንሽ በትንሽ እየቀንጠበች ወስዳ ፣ አሽሌይ ባስፈለገው ሰዓት
በሂደበት እየተከተለች ሲስቅ እየሳቀች ፣ ሲናገር ፀጥ እያለች የአ
ይኑን የቅንድቡን እንቅስቃሴ እየማተረች ፣ ያፉን የከንፈሩን ንቅ
ናቱ እያስተዋለች ፣ አርካታ ያገኙበትን ጸንሱን ፣ ዘፈኑንና ሳቁን
ሁሉ አጣፍጣ ልታቀርብለት የወሰነችበት ሳምንት በጥድፊያ አለፈ ።
ጦርነቱ ደግሞ በዚያ ዓይነት ሰዓሰም ለዘለዓለም ይቀጥላል ። ዕለ
ነው ።

ሚላኒን ተሰናብቶ እስኪወጣ ድረስ እበረንዳው ላይ ተቀምጣና
የመሰናበቻ ስጦታዋን በእጅዋ እየጠበቀች ይዛ ብቻውን እንዲመጣና ልቧ
ያሰበውን እንድተፈጽም ትበልያለች ። ጀሮዋን ወደፎቅ ሰከታ እ
ንዳንዷን ኮሽታ ታዳምጣለች ። ነገር ግን ቤቱ ፀጥ ከማለቱ የተነሃ
ከራሷ የልብ ትርታ በስተቀር የሚሰማት ነገር የለም ።

ወይዘሮ ፒቲን ከሰላሳ ደቂቃ በፊት ስለተሰናበታቸው ትራሳ
ቸው ላይ ተደፍተው ያለቅሳሉ ። ከተዘጋው መኝታ ቤት አቅጣጫ
የሹክሹክታ ድምጽ እንኳን አይሰማም ። አስካርሌት እዛ መኝታ ቤት
ውስጥ ለብዙ ሰዓታት የቆየ መስላት ። እያንዳንዷን ሚስቱን ለመሰ
ናበት የሚቆይባትን ሴኮንድ ረዛመቻት ። ሴኮንዶች ባለፉ ቁጥር
ከእሷ ጋር የሚቆይበትን ጊዜ እያሳጠሩ በመሆናቸው ረዛመቻቸው ።

በዚህ ሳምንት ውስጥ ለሱ እንግራቸዋለሁ ያለቻቸውን ነገሮች
ሁሉ ታስብ ጀመር ነገር ግን ልትነግረው የምትችልበት ምንም እጋ
ጣሚ አላገኘችም ። ምናልባት ወደፊትም ቢሆን ፈጽሞ እድሉ ላይኖ
ራት እንደሚችል አሁን ታወቃት ።

"አሽሌይ ትጠነቀቃለህ አይደል? እግርህን እርጥበት እንዳታስ
ነካው ፣ ብርድ በሽታ ይይዝሀል ። ከሸሚዝህ ሥር እደረትህ ላይ

@OLDBOOKSPDF

ጋዜጣ ማድረግ አትርሳ—ንፋስ ይከላከልልሀል።" እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉት ጅላጅል ነገሮች ነበሩ ። ነገር ግን ከነዚህ ይልቅ በጣም አስፈላጊ የሆኑ ሊነገሩ የሚገባቸው ነገሮች ነበሯት ። እሱ ሲናገራቸው ልትሰማቸው የምትፈልገው በጣም አስፈላጊ ነገሮችም አሉ ። ባይ ናገር እንኳን አይኖቹ ውስጥ ልታነባቸው የምትፈልጋቸው በጣም ብዙ ነገሮች አሉ ። ግን ያላት ጊዜ በጣም አጭር ነው ። ያኗት ጥቂት ደቂቃዎችም ቢሆኑ ሚላኒ ተከትላው ከመጣች ሲሰረቁባት ነው ። ለምን ባለፈው ሳምንት አጋጣሚ ፈልጋ አልነገረችውም፣ ግን በየት በኩል ፣ ሚላኒ ከኮኑ አትሰይ ፡ አይኗን ከአይኑ አትነቀል ። በዛ ላይ ዘመድ ወዳጁ ጐረቤቱ ይንጋጋል ። ከጧት አስከማታ ከበውት ይውላሉ ። በየት በኩል ታናግረውና ሲመሽ ደግሞ እሱና ሚላኒ መኝታ ቤት ገብተው ቀርቅረውባት ይተኛሉ ። እስካርሴትን ያየበት ጊዜ ቢኖር እንኳ አይኖቹ ሚላኒን እንዳይነኩ ፡ ስሜቷንም እንዳይጐዱ ተጠንቅቆ ፡ በወንድምነት ፡ በረጅም ጊዜ ዓደኝነት ዓይን ነው ። ታዲያ እንዴት ብላ ታግናውና ያም ሆነ ይህ ዛሬ ትሞታታለች እንጂ ይመዳት አይመዳት እንደሆነ ሳትጠይቀው አይሄዳትም ። ግን ያውቃል ላንዴም ለሁሌም ይሆናል እኮ የሚሔደው ። ቢሞት እንኳን የም ስጢር ፍቅሩን እያስታመመች መውቱን እንድትጋራ ዛሬ ማወቅ አለባት ።

አሽሌይን ለዘመናት ስትጠብቀው እንደቆየች ሁሉ ሲቆርጣት ቆይቶ ሮቅ ካለው መኝታ ቤት የኮቴ ድምጽና በር ክፍት ዝግት ሲል የሚያስማው ድምጽ ይሰማል ። ደረጃውን ሲወርድ ሰማች ። ተመ ስገን! ብቻውን ነው ። ሚላኒ ከሠዘንጥ ብዛት ከአልጋዋም አልተነሳ ነቀችም ማለት ነው ። አሁን እንግዲህ ለጥቂት ደቂቃዎች በግላጭ ብቻውን ልታገኘው ነው ።

ደረጃውን ቀስበ እያለ እየወረደ መጣ ። እንቅስቃሴው በደምብ ይሰማል ። ከቤቱ ውስጥ ወደ ደረጃው ሲወጣ አይኖቹ ቀዘዘ ብለዋል። ፈገግ ለማለት ይሞክራል ግን ፊቱ አሸቦ መስሎ ጭር በማለቱ ውስጥ ውስጡን እንደቆሰለና ደም እንደሚፈሰው ሰው ያለ ስሜት ይነበብ በታል ። እሰከ ዛሬ ካየኋቸው መታደሮች ሁሉ እሱን መሳይ ቆንጆ አጋጥሚት እንደማያውት ሁሉ በባለመብትነት ኩራት ተሞልታ ሲመጣ ብድግ ብላ ተቀበለችው ። የሸኮኖ ማህደሩና ቀበሮው በቦታው ውሎ ያበረቀርቃል ። አጎት ፒተር በሚገባ ስለወለወላቸው ፎደራ ወና ጐራዴው እንዲሁም መኮልኮያው በጣም ያንፀባርቃሉ ።

አዲሱ ክት ፣ ልብስ — ሰፊው የደድረስ ይድረስ ስለወሻሸለው የመጋጠሚያው ስፌት ተዛብቶ አልተቀበለውም ። አዲሱ ግራጫ

@OLDBOOKSPDF

ኩቱ ከመድመቂ የተነሳ የታጠፈ አሮጌ ቦላሴውንና ተመላልጠ ጠባሳ የወረሰውን ቦት ጫማውን የበለጠ አስረጅቷቸዋል ። ዳሩ ለምኑ ነው። በብር ጥሩር ቢጥለቀለቅና ቢያበራ እንኳን እንደዛሬው እስካርሴትን ልቧን ሊነካት ፡ እንደዛሬው ያማረ ወታደር ሊሆንላት አይችልም ።

"አሽሌይ" አለች በልመና ድምጽ ። "ባቡር ጣቢያው ድረስ አብሬህ ልሂድ?"

"እባክሽ ይቅር እዚሁ ሁኚ ። አባቴና ሌሎቹም ሴቶቹ ስለሚ ኖሩ ባትሄጂ ይሻላል ። ብቻ ለማንኛውም እባ ሄደሽ ብርድ ከሚመ ታሽ እዚሁ ደህና ዋል ብትይኝ ይሰስ ይለኛል ። ትዝታውንም አል ችለው ። "

"ወዲያው እቅዷን ተወችው ። ኢንዲያና ሃኒ ከሄዱማ ምን ይመ ቻል ፤ የግል ሚስጥሯንም ለማውራት አትችልም ። ደሞ ሲጠሉዋት እንዳንድ ነገር ነው ። ስለዚህ ያቀደችውን ትቢ ሰረዘችው ።

"እንግዲያው አልሄድም ። ይመልሀ አሽሌ! ስጦታ አዘጋጅቼ ልሃለሁ ።" ብላ ስጦታውን ማቅረቢያዋ ሰዓት ሲደርስ ትንሽ አፈር አለችና የተጠቀለለውን ዕቃ ጠግኖ ጀመረች ። ከቻይና ከሚመጣ ሐር የተሰራ ዙሪያውን ዘርፍ ዘርፍ ያለው ጌጠኛ የአንገት ልብስ (ስካርፍ) ነው ። ራት በትለር ሐሻና ሄዶ ሲመጣ ካመጣላት ሰፊ መቅ ለሚያ ለወንድ በሚሆን መጠን ቆርጣ ባለፈው ሳምንት ለአሽሌይ ያዘጋጀችው ስጦታ ነው ።

"በጣም ቆንጆ ነው እስካርሌት ። ራስሽ ነሽ የሰፋሽው መሰ ለኝ ። በጣም ማራም ነው ። እነዚያ ጓደኞቹ አዲስ ኮትና አዲስ እስ ካርፍ አድርጌ ሲያዩኝ ቀንተው ይሞታሉ ። እስቲ አርጊልኝ የኔ ቆንጆ አላት ። ወገቡ ላይ ከቀበቶው በላይ የፍቅር ቋጠሮ በሚባለው ዓይነት አሠራ ሸብ አደረገችለት ። አዲሱን ኮት የሰጠችው ሜላኒ ልት ሆን ትችላለች ፤ ስካርፉ ግን የእስካርሌት የራሷ ልዩ ስጦታ ነው ። ጦር ሜዳ ሄዶ ባየው ቁጥር ያስታውሳታል ማለት ነው ። ቀጥ ብላ ቆመችና ትኩር ብላ ተመለከተችው ፤ ቆንጆ ነው የሚባለው ጀም አስቱዋርት እንኳ የለበሰው ልብስ ፊቷ ቢቆም ይህን የሷን ያህል አይተካከልም ።

"በጣም ቆንጆ ነው" አለ ዘርፉን በጣቶቹ እየዘረዘረ ።" ግን እርግጠኛ ነኝ ወይ ቀሚስሽን ወይ መቅለሚያሽን ቀድደሽ መሆን አለበት የሠራሽው ። እንደዛ ማድረግ አልነበረብሽም እስካርሌት ። በዛሬው ጊዜ ውድ እቃዎችን በቀላሉ ማግኘት አይቻልም ። "

@OLDBOOKSPDF

"ውይ አሽሌይ እኔ . . . "ብላ አቋረጠች ። ልትል የፈለገችው ግን" ለመልበስ ከፈለክ ልቤንም ቆርሼ ብስጥህ ፈቃዴ ነው" ለማ ለት ነበር ። በመጨረሻ " ማናቸውንም ነገር አደርግልሃለሁ!" አለ ችው ።

"እውን ታደርጊያለሽ?" አለና ጠየቃት ፡ ፊቱ ላይ የነበረው ቅሬታ እየጠፋ ። "እንግዲያው እንድታደርጊልኝ የምፈልገው አንድ ነገር አለ ። ይህ ነገር ጦር ሜዳ ሆኘ እንዳላስብና እንዳልጨነቅ ሐሳቤን ቀልል የሚያደርግልኝ ነገር ነው ። "

"ምንድነው እሱ?" አለች ሙሉ ፍቃደኝነቷን ለመግለፅና ታል ለመግባት ቸኩላ ።

"እስካርሌት ፤ የሚላኒን ነገር አደራ ። "

"ሚላኒን እደራ?"

ወሽመጧን ቆረጣት ። አስቲ ሌላ ስንት አድርጊልኝ የሚባል ፡ ስንት ቃል ግቢልኝ የሚያሰኝ ጉዳይ እያለ ፡ ስንት የሚያስደስት ስንት የሚያስረሳድቅ ነገር እያለ ፤ ሰው ባሁኑ ሰዓት ስለሚላኒ ያነሳል በሉ! ተበሳጨች ። ንዴት አሳት አረጋት ። ከአሽሌይ ጋር የብቻዋ ፡ የማ ሉዋ የሆነ የመነጋገሪያ ሰዓት ይሄ ብቻ ነው ። ይሄም በዛ ብሎ ሚላኒ በሌለችበት ጥላዋ ማህላቸው ጉብቶ ይበጠብጣል ። አሽሌይ ደግሞ፤ በዚች የመጨረሻ የመለያያቸው ሰዓት የሚላኒን ስም ማንሳቱ ይባስ እንዴት እንዲህ ያለ ጥያቄ ይጠይቃል?

በበኩሉ መበሳጨቷንም ሆነ በብስጭት ፊቷ መለዋወጡን ልብ አላለም ። እንደወትሮው በአይኖችዋ ውስጥና ከአይኖችዋ ባሻ ገር አንድ ነገር ያስተውላል ። እሷን በጭራሽ አላያትም ።

"አዎ ካይንሽ አታርቂያት አደራ ። ቡቡ ናትና እሷ አታስተው ለውም ። በነርስ ሥራዋና በስፌት ሙያ ተጠምዳ እራሷን ትጐዳለች። ጭምትና ዝምተኛ ናት ። ከፒቲፓት ከሄንሪና ካንቺ በስተቀር በዚህ አለም ላይ ዘመዷ የምትለው ፡ ይቀርበኛል የምትለው አንድ ሰው የለም ። ማከን ያሉት የበርር ቤተ ሰቦችም የሶስት ቤት ዝርያ ያክ ስት ልጆች ናቸውና ይሄን ያህል አትቀርባቸውም ። እንደምታውቂው ወ/ሮ ፒቲፓት እንደ ሕዛን ልጅ ናቸው ፤ ነገረ ሥራቸው ሁሉ የትንሽ ልጅ ነው ። አጐት ሔንሪም እንደሆነ ሽማግሌ ነው ።

ሚላኒ እንደሀቷ አድርጋ ትወድሻለች ። የቻርለስ የወንድሟ ሚስት በመሆንሽ ብቻ ሳይሆን እንደው አለ አደለም . . . አንቺ በመሆንሽም ጭምር በጣም ትወድሻለች ። እስካርሌት እኔ ብሞትና የሚደግፋት

@OLDBOOKSPDF

ብታጣስ ብዬ አስብና ድንጋጤ እንደሀልም ይመስደኛል ። እና ቃል ትገቢልኛለሽ ?"

እስካርሌት "እኔ ብሞት" ያለውን ክፉ ቃል ሰምታ በመደናገጢ ከዚያ ወዲያ የተናገረውን አልሰማችም ። ለራሷ ሁልጊዜ የሞትና ያል ሞታ ሰው የተዳፈረበትን ባህረ መዝገብ በተመለከተች ቁጥር ክፉ እንዳይነካው በመመኘት ልቧን እንጥሏ ላይ ሰቅላ ነው የምታነባው እንኳንስ እኔ ብሞት ብሏት ቀርቶ ። ያም ሆኖ እንደው በደመ —ነብሷ የኮንፌዴሬሲው ወታደሮች ድባቅ ቢመቱ እንኳ አሽሌይ እንደሚተርፍ ለውስጠ ቅሰቧ ይታወቃታል ። ታዲያ አሁን እራሱ አፍ አውጥቶ የምትፈራውን ነገር ነገራት ። ፅጨዋ ዶብ አለ ። ፍርሃት ሞጣት ። በእጉል አምልኮ ተጥሰቅለታ ትይዘው ትለቀውን አጥታ ልቡናዋ ከሚያወቀው ይልቅ ይሄ የሰማችው ነገር አይሉ ክፉኛ ተናነቃት ። እንደ አየርላንድ ተወላጅነቷም ሁለተኛውን አይታ ከመጀመሪያው ይልቅ አመነችበት ። ብጉሰይ የሞት ነገር ሲነሳ የምታይ የም ትሸሻዉን ማመኑ ይቅላታል ። አሽሌይ ሐዘንተኛ ዓይኖቹ ውስጥም የምታየውና ጠቅሳሳ ሁኔታው ጥላ ሞት ያንዣበበበት ዓይነት ነው ።

"እንዲህ ማለት የለብህም ። ኧረ ከኑሯራሹ ማሰብም የለብህም። ስለሞት ማውራት ደግ አይደለም ፣ ይቅር ይበልህ እንደውም ይቅር ይበልሽ በልለ"

"እሱን እንቺ ትፀልይልኛለሽ ፤ ወዲያውም ሻማ ታበሪልኛለሽ" አለ እያላቀ ፣ የመንፈስ ሥጋቷ እንዴት በፍጥነት እንዳናገራት እያየ ።

እሷ ግን ለተናገረው እንኳን ልትመልስ ያሰውንም አልሰማች ። አሽሌይ በሽርሺኒያው ጦር ሜዳ ላይ ከሱዋ ስንትና ስንት ርቆ በረደ ላይ ሬሳው ተንጋሎ ስፅሉ እየታያት በሀሳብ ታምጣለች ። መናገሩን ሲቀጥል የድምፁ ማማር ፣ የመለስለሱና ሁሉ ነገር በቃኝ የማለቱ ሁኔታ ይብሱን እያስፈራት ሄደ ። ንዴትና ተስፋ መቁረጥ ሲለቋት ደሞ ፍርሃት ይቀበላታል ።

"ለዚህ ብዬ ነው አደራ የምልሽ እስካርሌት ። በኔም ላይ ሆነ በሌሎቹ ላይ የሚደርሰብን አይታወቅም ።በመጨረሻም ቢሆን ሕይወቱ ቢተርፍ እንኳ ሚላኒን ለመንከባከብ በጣም ሩቅ ቦታ እሠ ናለሁና አልችልም ።"

"በመጨረሻ በመጨረሻ ነው ያልከው?"

"አዎ በጦርነቱ መጨረሻ አለም ሲጨልምብን ማለቴ ነው ።"

@OLDBOOKSPDF

"ግን አሽሌይ ያንኪዎች ሊያሸንፉን ይችላሉ እንዴ? ምነው ሳምንቱን ሙሉ ስለ ጂኤራል ሊ ጀግንነትና የጦር ሥልት አዋቂነት ስትናገር . . . ."

"አየሽ በዚህ ሳምንት ማንም በፍቃድ የመጣ ወታደር እንደሚ ያደርገው ሁሉ ዋሽቻችኋለሁ። ደሞ ልክ ነኝ። ሜላኒንና ወ/ሮ ፒቲን በምን እጻቸው ሳስፈራራቸውና አዎ እስካርሌት ያንኪዎች ድል መት ተውናል። ጌትስበርግን መያዛቸው የጉዳሜው የመጀመሪያ እርምጃ ነው። እዚህ ያለ ሰው ይሄን ሁሉ አያውቅም። እዚህ የተመለሱትም ቢሆኑ ብዙዎቹም ልብ አላሉም። የኛን ችግር ሊያዩልን ሊገነዘቡልን የቻሉ አይመስሉኝም። ግን . . .እስካርሌት አንዳንድ ጓደኞችሽ ባዶ እግራቸውን ናቸው። በረዶው ደግሞ ቨርጂንያ ውስጥ የሰው ቁመት ያህል አድጓል። እናም ቀዝቃዛና የደነዘዘ እግራቸው፣ ባሮጌ ጨርቅና በተቀዳደደው የእግር ሹራብ ተሸፍኖ ሳይና ዱካቸው በረዶው ላይ እየነጠበ የሚያልፈውን ደም ሳስተውል ባንጻሩ እኔ ደህና ቦት ጫማ እንዳለኝ ሳስብ ጫማዬን ወዲያ ወርውሬ እንደነሱ ሁን ሁን ይለኛል።"

"ውይ አባክህ አሽሌ እንደሱ ሕታድርግ እንዳውም ቦት ጫማ ዬን አልጥልም ብለህ ቃል ግባልኝ!"

"ይሄውልሽ ይሄንን ሳይና ያንኪዎቹን ደግሞ ስመለክት ነው አለቀልን፣ ዓለም ሁሉ ጨለመብን የምሰው። ያንኪዎቹ በሺ የሚቆጠሩ ወታደሮች ከአውሮፓ እየገሡ ያማሉ። ይሄን ሰሞን የማ ረክናቸው ወታደሮቻቸው አብዛኞቹ እንግሊዝኛ አይናገሩም። ጀርመ ኖች፣ ፖላንዶችና የጋሊክ ቋንቋ የሚናገሩ ጥሬ አየርላንዳዊዎች ናቸው። እኛ ግን አንድ ሰው ቢሞትብን መተኪያ እናገኝለትም። ጫማዎቻ ችን ሲቀረደዱ ሌላ ጫማ እናገኝም። ሁሪያችንን ተከበናል እስካር ሌት። ከመላው አለም ጋር መዋጋት በጭራሽ አንችልም።"

በልቧ እንዲህ ብላ አሰበች። "ካንፌዴሬሴው ተንኮታኩቶ፣ ትቢያ ይላስ! ቢሻው አለም በሙሉ ጀሀነም—ይግባ እንተ ግን መሞት የለ ብህም። አለኝታዬ አንተ ነህና ከምትክብኝ መኖር አልችልም!"

"እስካርሌት አደራሽን አሁን የነገርኩሽን ለማንም ነግ ረሽ እንዳታስደነግጪ። ላንቺም ቢሆን የነገርኩሽ ለምን ሜላኒን አደራ እንዳልኩሽ ለማስረዳት ስል ነው። እሷ ደካማና ቡቡ ናት። አንቺ ግን ጠንካራ ነሽ እስካርሌት። የፈለገው ነገር ቢደርስብኝ እንኳ እናንተ አንድ ላይ መሆናችሁ ያጽናናኛል። ቃል ትገቢልኝ የለ?" አላት።

@OLDBOOKSPDF

"እንዴ ! ታዲያስ !" አለች እየጮኸች አሽሌይ ከሞት አፋፍ ላይ ሆኖ ምንም አድርጊልኝ ቢላት ከማድረግ አትመለስምና ። "አሽሌይ !አሽሌይ ! ጥለኸኝ መሄድህን ልቋቋመው አልችልም! በጭራሽ አልችልም! ድፍረት ያንሰኛል?! " አለች ።

"የለም ደፋር መሆን አለብሽ ።" አለና ድምጹን በመሠርነት ለወጥ አድርጎ መስጥ ፈጠን ባለ ሁኔታ ቀጠለ ። ከውስጥ አንድ ነገር ፍጠን ፍጠን የሚለው ይመስላል ።" ደፋር መሆን አለ ብሽ አለበለዚያማ እኔስ እንዴት አድርጌ ልቋቋመው ነው?"

ይህንን ሲላት ልክ የእሷ ልብ እንደቆሰለው ሁሉ በመለያየታ ቸው ምክንያት የእሱም ልብ አልችል ብሎ መስላትና በደስታ ተሞ ልታ ፊቱን ለመፈለግ አይኖችዋ ይቅበዘበዙ ጀመር ። ሚላኒን ተለ ናብቶ ሲመጣ ጭማሪ ብሎ የመጣው ፈተ ያው እንደከፋው ከመሆኑ በቀር አይኖቹ ውስጥ ምንም ነገር ማንበብ አልቻለችም ። ጐንበስ አለና በእጁ ፊቷን ቀና አድርጉ ቀስ ብሎ ማንባሩዋ ላይ ሳም አደረጋት ።

"እስካርሌት! እስካርሌት! በጣም ጠንካራ ፡ አመለ ሸጋና ጥሩ ሴት ነሽ ። ቆንጆው መልክሽ ብቻ አይደለም የኔ እመቤት ። ሁለመናሽ ፤ ስውነትሽ ፡ ጭንቅላትሽ በጣም ቆንጆ ነው ።"

"ው . . . ይ አሽሌይ" አለች በተናገረውና ፊቷን በመዳሰሱ ክልክ በላይ ተደስታ ። "እንዳንተ ማንም . . ."

"እንደሚመስለኝ ማንም ከማያውቅሽ በላይ ጠልቄ አውቅሻ ለው ። ቆንጆ ቆንጆ የሆኑ ነገሮች በውስጥሽ ተቀብረው መቀመጣ ቸውንም ሌለሞች ሳይገነዘቡ እኔ ስማስተዋል ችያለሁ ።" መናገሩን አቁሞ እጆቹን ከፊቷ ላይ አውርዶ ዝም ብሎ አይን አይኑዋን ያያት ጀመር ። ትንፋሽ አጥታ ንግግሩን እንዲቀጥልና እነዚያን ለሪ ዥም ጊዜ የናፈቅቻቸውን ሶስት ቃላት በመጣደፍ (እኔ—አንቺን—እወድሻለሁ) እንዲላት በእግር ጥፍሩዋ ቆማ ትጠብቃለች ። ግን እነዚህ ቃላት አልመጣ አሉ ። መናገር ማቆሙን ስታይ ዓይን ዓይኑን በጉጉት እያስተዋለች ከንፈሮቹዋ ተንቀጠቀጡ ።

ይሄ ሁለተኛው ተስፋ አስቆራጭ ነገር ሲገጥማት ልቧ ሊሸከ መው ከሚችለው በላይ ሆነባትና "ው-ይ!" ብላ እንደህፃን ልጅ እምባዋ ይወርድ ጀመር ። ከውጪ አንድ የአሽሌይን መሄድ መርዶ የሚ ያረዳ ድምጽ ተሰማት ።

ብቻውን በሠረፌ ውሃ ላይ የሚቀዝፍ የጫካ ሰው የሷን ያህል ብቸኝነት አይሰማውም ። ለካ አጐትዬው ፒተር አሽሌይን ወደ ባቡር ጣቢያ ሊወስድ ሲመጣ የሰማችው ድምጽ ነው የረበሻት ።

@OLDBOOKSPDF

አሽሌይ "ደህና ሁኚ" በቁጣ ተሰናብታት ከሬት ወስዳ ለት የሰጠችውን ባሮሜጣ ከጠረጴዛው ላይ አንስቶ ወደፊት ለፊቱ እዳራሽ መንገ ጀመረ ። የበሩን እጀታ ይዞ ዞር አለና ተስፋ መቁረጥን አገለሎና ሁሉ ነገርዋን በጭንቅላቱ ለመቅረጽ እንደፈለገ ሁሉ ለረኽም ጊዜ ትኩር ብሎ አያት ። በእንባዋ ጭጋግ ውስጥ ቀና ብላ አስተዋለችው ። ሕመም ጉረሮዋን እየተናነቃት ያን ያህል በናፍቆት የጠበቀቻቸውን ቃላት ሳይተነፍስ ከሄ ርቆ ፣ ከሞቀ ቤቱ ርቆ ፣ ከሷ ሕይወት ውስጥም ተመንጭቆ ምናልባትም እስከማዕዜኑ መንዙ ነው ። ጊዜ እንዳንድ ነገር ይጋልባል ፤ አሁንማ ምንም ነገር ለማድረግ ረፈደ በቃ ። ተንደርድራ አልጭኝ ተአዳራሽ አጽርጣ የልብሱን ጫፍ ያዘችና "ሳሙኝ ፤ የመሰናበቻ" አለችው ። ቀስ አድርጎ ከንዶቹን በገላዋ ዙሪያ ጠምጥሞ ወደ ፊቷ ጐንበስ አለ ። ግና ከንፈሩ ከንፈሩዋን ሲነካ በፍጥነት እግኑቱ ላይ የማንቅ ያህል ተጠመጠመችበት ። ለማይለካ የግዜ ርዝመት ሰውነትዋን ወደ ሰውነቱ አስጠግቶ ይዟት ቆየ ። ወዲያው ጡንቻው ሲግተረተርና ገላው ሲቆጣ ተሰማት ። ከመቅጽበት ባርሚጣውን ወለሉ ላይ ጣለና እጅዋን ከን ግቱ ፈልቅቆ አላቀቀው ።

"ተይ እስካርሌት ፤ የለም አይሆንም ተይ" አላት በቀስታ እጅና እግሩዋን በመስቀልያ አጠላለፎ ይዞ ። "አፈቅርሃለሁ" አለች እያስ ጐሰበተች ። "እስከዛሬም ሳፈቅርህ ነበር ። እንዳንተ ማንንም ማንንም አፍቅሬ አላውቅም ። ቻርለስን ያገባሁትም አንተን የጐዳሁ መስሎኝ ነው ። አንተን በጣም ከማፍቅሬ የተነሳ ቨርጂንያ ድረስ በእግሬ ተጉዤ አጠገብህ ብሆን ፈቃዴ ነውዘ እዚያ ሄጀ ምግብህን ባበስል ልህ ፣ ጫማ ምትህን ብሰፋ ፣ ልህና ፈረስህን ባጥብልህ . . አሽሌይ ብቻ አፈቅርሻለሁ በሰኝ ፤ ብቻ ተሪፈ እድሜዬን አኖርበታለሁ!"

አጐንብሶ ባርኔጣውን አንስቶ ቀና ሲል ፊቱን በስላች አየችው ። መከፋት የወረረውና በጭራሽ የመራቅ ፣ የመለያየት ጣጣ የሌለበት ፊት ነው ። ያም ሆኖ ለእሷ ያለውን ፍቅርና ስላፈቀረችው የተጐናፀፈውን ደስታ ፣ ሐፍረትና ተስፋ መቁረጥ የሚያሳይ ስዕል ሰፍሮበት ይታያል ።

"ደህና ሁኚ" አለ በሻከራ ድምጽ ።

በሩ ተከፈተ ። ቀዝቃዛው አየር በእንግድነት ገብቶ ቤቱን ሞላው ። መጋረጃዎችንም እየገለበ አውለበለባቸው ። እስካርሌት ብራማው ዝናሩን በክረምቱ ፊዛዛ ፀሐይ ውስጥ እያብረቀረቀ የሰጠችውን የአንገት ልብስም ዘርፍ ዘርፉን እያስደነሰ ወደጋሪው ሲሄድ እያየች ባለችበት እየተንቀጠቀጠች ቀረች ።

@OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ 16

የ1864 ጥርና የካቲት ወራት በዝናብና በአውሎ ንፋስ እንደ ተሞሉ ፡ የደስታና የመሸማቀቅ ጸመናዎች ተደበላልቀው እንደሰፈ ነባቸው አለፉ ። በጌትስበርግና በቤክስበርግ ላይ ደቡቦች ድል ከተመቱ ወዲያ መቼም ዳሩ ሲነኪ መሀሉ ዳር ይሆናል ነውና የደ ቡቦች አማካይ መስመር ተባባ ። ከከባድ ውጊያም በሁዋላ ተነሲ ከሞላ ጐደል በያንኪዎች የተባበረ ሠራዊት ተያዘች ። ይሂም ሆኖ የደቡቦች ቅስም ግና አልተሰበረም ። አውነተኞና መራር ቁርጠኝነት አላቸው ። ባለሙሉ ልብ ተስፈኝነታቸውም ከጸመና እንቁ እንዲ መኙ ያደርጋቸዋል ። ይህን የተመኙት ያለምክንያት አይደለም ። ያን ኪዎች መስከረም ላይ ተነሲን ሲይዙ ፣ በተከታታይ ድል ለማግኘት ወደፊት ገፍተው ጅርጂያን ለመያዝ ሲጥሩ ፣ ድል መመታታቸው ለደቡቦች የተስፋ ጭላንጭል ሆኖላቸው ነበር ።

እዚህ በአገራቱ ሰሜን ምዕራብ ጠረፍ በጅርጂያ ምድር የተካ ሄደው ከባድ ውጊያ ከዚህ ሁሉም ታይቶ አይታወቅም ። ጦርነቱ የተ ካሄደው ቺካማውጋ ላይ ነበር ። ያንኪዎቹ ቻታኑጋ የተባለችውን በታ ይዘው በጅርጂያ ተራሮች ላይ ሲገሰግሱ ቆይተው ከባድ ውድቀት ደርሶባቸው ተመለሱ ።

የአትላንታ ባቡር መንገዶች ለቺካማውጋው ታላቅ ድል ከፍ ተኛ አስተዋጽኦ አደረጉ ። ከቨርጂኒያ ወደ አትላንታ በሚወስደውና ወደሰሜን ዘልቆ ተነሲ በሚገባው ባቡር መንገድ በኩል የጂኔራል ሎንግ ስትሪት ጦር ጐርፎ ገብቶ ውጊያ ገጠመ ። ብዙ መቶ ማይሎች ርዝመት ባለው መንገድ ላይ ግራ ቀኙ ጠድቶ ለጦር መሳሪያም ሆነ ለሌላ ዕቃዎች ማጓጓዣ ተመቻቹ ።

ባቡር ከባቡር ሲከታተል ፡ በየሰዓቱ መንገደኛው ይግተለተላል። ድፍን መኪናዎች ዝርግ አውቶሞቢሎች በሚጨሁ ሰዎች ተሞል ተው በየደቂቃው እየተትመከመኩ ያልፋሉ ።

የአትላንታ ከተማ ይህንን ሁሉ ታስተውላለች ። ሰምቼ ያለም ግብ ያለአንቅልፍ ፡ ያለፈረስ ያለአንበላንስና ያለምንም ዕቃ ባዶ እጃቸውን ከባቡር እንደወረዱ ትንፋሻቸውን ለመዋጥ እንኳ ጊዜ

@OLDBOOKSPDF

ሳያግኙ መርኑቱ ወላፈን ውስጥ ምስማ ይላሉ ። እንዲህ ሁኖ ጀር ሺያ የባቡትን ያንኪዎች ወደ ተነሲ ለማባረር ተቻለ ።

የመርኑቱ ታላቅ ዕጣ ነው ። አትላንታም የባቡር መንገዶችዋ ለመርኑቱ በዋለት ውለታ ኩራትና እርካታ ተሰማት ።

የደቡብ ሕዝብ ግን አሁንም በናፍቆት የሚጠብቀው ከቺካማውጋ ይነኛል ብሎ የሚገምተውን የድል ምሥራች ነው ። ያንኪዎች ብርቱ ተዋጊዎች መሆናቸውን ግንም አይክድም ፣ ያም ብቻ አይደለም— የማታ ማታ— ደህና ደህና የጦር ጀኔራሎች አግኝተዋል ። ጀኔራል ግራንት ድሱን ያማኝ እንጂ ስፍር ቁጥር የሌለውን ሕዝብ የሩሲካ በማ አድርጎ ለእርድ ቢያበቃ ደንታ የማይሰጠው በላኤሰብ ነው ። ግና ስሙ ሲነሳ የደቡቦች ልብ የሚርድለት የሚንቀጠቀጥለት በተደጋጋሚ ስሙ በየጦርሜዳው የሚነሳለት ሼርማን የተባለው ጀኔራልም አለ ። በተነሲውና በምዕራቡ ዘመቻ ቀንደኛና ቆራጥ የጦር አለቃነቱን ያስመሰከረ ጀግና ነው ።

እርግጥ ከንዚህ አንዱ ኤንኳ ከደቡቡ ጀኔራል ሊ ጋር አይተካ ከልም ። በዚህ ጀኔራልና በሠራዊቱ ሳይ ያለው እምነት ለጉድ ነው። የማታ ማታ ድሉ የነሱ መሆኑን ሳያጠላውሉ በኩራት ልባቸውን ነጥተው ይናገራሉ ። ጸሩ ግን ጦርነቱ እየተራዘመ ሄደ ። ብዙዎቹ ሞቱ ። ብዙዎች ቆሰሉ ። በርከት ያሉት ሞተው ሚስቶቻቸው ያለባል ቀሩ። አያሌ ሞተው ልጆቻቸው ያለ አባት ቀሩ ። ጦርነቱ ገና ይቀጥላልና ብዙዎች ሊቆስሉ ፣ ብዙዎች ሊደሙ ብዙዎችም ሊሞቱ ነው ። በዛ ውም ሥፍር ቁጥር የሌላቸው ሚስቶች ያለባል ፣ አያሌ ጮርቃ ልጆች ያለአባት ያሳሳቢ ሊቀሩ ነው ።

ይባስ ብሎ ደግሞ መንጋው አውራውን የሚጠራጠርበት ፣ ምንዝር አለቃውን የማያምንበትና ሕዝቡ መሪዎቹን በክፉ አይን የሚያይበት ሁኔታ ተፈጠረ ። ብዙ ጋዜጦች በይፋ ፕሬዚዳንት ዴቪስንና የጦር እቅዱን ማውገዝና ዓይንህን ላፈር ማለት ጀመሩ ። በኮንፌዴሬሲው ካቢኔ አባላት ማህል እርስ በርስ መጠራጠር በፕ ሬዚዳንት ዴቪስና በጀኔራሎች ማህል አለመግባባት መፈጠሩ ተባ ባስ ።

የግንዘብ ምንዛሪው አሽቆለቆለ ። ጫማና ልብስ ዋርሱት ጠፉ ። ለሠራዊቱ የሚሆን ትጥቅም ሆነ መጻኢት ለሽታ እንኳን እየጠፉ ሄደ ። የባቡር መንገዶቹ የእደላ መኪናዎች ይሻሉ ፣ የባቡር ሐዲዶች ያንኪዎቹ በሰበሩዋቸው ምትክ አዳዲስ ሐዲዶች ይፈልጋሉ ። ጀ ኔራሎቹ አዲስና ትኩስ የጦር ኃይል እንዲላክላቸው ይጠይቃሉ።

@OLDBOOKSPDF

የደረሰላቸው የእርሻ ሐይል ግን ከጣም አነስተኛ ነው። ከዚህ የከፋው ደግሞ አንዳንዶቹ ሀገረ ገዢዎች እንደነ ብራውን ያሉት የሚለሽያ ሰራዊት ትጥቅም ሆነ ስንቅ ከግዛታችን ውጪ እንል ክም ብለው ከጆርጂያ አናስወጣም ባይ ሆኑ። መንግሥቱ ከቁጥር አል ጽፍ አላቸው እንኳ ሠራዊቱ የሚተማመንባቸው፣ መመኪያዱ የሚላ ቸው ስትንና ስንት የጦር ሰዎች ነበሩ። ምን ያረጋል የትም ባክነው ቀሩ።

አዲሱ የብር ምንዛሪ ሲያሽቆለቁል ዋጋዎች ያለቅጥ ናሩ። የበሬ ሥጋ፣ ያሳማ ሥጋና ቅቤ አንዱ ፓውንድ ሰላሳ አምስት ብር ገባ። አንድ በርሜል ዱቄት አንድ ሺህ አራት መቶ ይሸጥ ጀመር። ዕዳ (ጨው) ፓውንዱ መቶ ብር አወጣ። ሻይ ቅጠል አንዱ ፓውንድ አምስት መቶ ብር ገባች። ለመቅት የሚሆን ልብስማ ሙሪሽ አይገኝም እንኳ ቢገኝ ዋጋው ሰማይ ጠቀስ ከመሆኑ የተነሳ የአትላንታ ሴቶች ቀሚ ሳቸውን በአራፊ ጨርቅ እየሠፉ በጋዜጣም ሙምር እየደረቱ መል በስ ግድ ሆኖባቸዋል። ጫሚ አንዱ ጥንድ ከሁለት አስከ ስምንት መቶ አወጣ። ይኸውም ጫማው ከእውነተኛ ቆዳ ወይም ከክርታስ ድብልቅ መሠራቱ እየታየ ነው። ሴቶቹ ከመቅለሚያ ዕቃቸውና ከምንጣፍ ቁራጭ የተሠራ ገምባሱ ያደንጋሉ። የጫማ ሰፊዎችም ከእንጨት የተሠሩ ናቸው።

እንግዲህ ይህ ዕውነት የሚያሰየው ሰሚሞቹ ደበቦቹን ያለ ምንም ጥርጥር በቅጥፕር ሥር እንዳዋሉ ነው። ሰጪ ግን ይህን ሁሉ የተገነዘበው አይመስልም። የያንኪዎቹ የጦር ጀልባዎች የወ ደቡን ኬላ በጥብቅ በመያዛቸው የታገዱ እቃዎችን እንደልብ ማሻ ገር አስቸጋሪ ነው።

አስከዛሬ ደቡቡ የሚኖረው ጥጥ በመሸጥና የሚያመርተውን ሸቀጥ በመግዛት ነበር። አሁን ግን መግዛትም መሸጥም አልተ ቻለም። ጂራልድ ኦሃራ እንኳን የሰላት ዓመት የጥጥ ምርት ዘመ ጋዙ ጉን አጥፍ ሰር እንዳጀለው ሊበሰብስበት ነው። ምንም አልፈ የው። ሊቨርፑል ውስጥ በባሬ ገበያ መቶ ፃምሳ ሺህ ብር ያወጣል።

ግን በምን ተአምር ሊሸርፑል ይድረስ። ችግር ነው። ጂራ ልድ ያ ባለፀጋ ሰው ዛሬ ቤተ—ሰዐቹንና ኤግሮ ባሪያዎቹን ምን አብ ልቶ ከረሙትን እንደሚያመጣቸው የጨነቀውና ግራ የተጋባ ሰው ሆኗል።

በድጥን የደቡብ ክፍል ያሉ የጥጥ አምራቾች ዕጣቸው ይሄው ሆነ። ከላው የማይጣስና ጥብቅ ቦታ በመሆኑ የደቡቡን ጥጥ ምርት

@OLDBOOKSPDF

ወደ እንግሊዝ ገበያ ልኮ ለመሸጥ መንገዱ ተዘጋ። ሌላው ቀርቶ ወደ እንግሊዝ ከዚህ ቀደም ተልኮ በነበረው ጥጥ ሺያጭ የተገዛው አስፈ ፈላጊ ቁሳቁስም መመለሻ መንገድ አጣ። በእርሻ የሚተዳደረው ደቡብ በኢንዱስትሪ ከሚተዳደረው የሰሜን ክፍል ጋር ጦርነት በገጠመበት ባሁኑ ሰዓት ጹሮ በደኑ ጊዜ ያልገዛቸውን በርካታ ዕቃዎች አሁን መግዛት አስፈለገው።

ጊዜው የተመቸው ለምግብ ጅምላ ነጋዴዎችና ለአትራፊዎች ነው። ብልጥ ብልጡ ሰው ይህን እጋጣሚ አላለፈውም። ምግብና ልብስ እያጠራ ሲሄዱና ዋጋቸው ሳራ እየተላካ ሲመጣ በነዚህ ሸቃጣ ነጋዴዎች ላይ የሕገቡ ጩኸትና ምሬት የትየለሌ ሆነ። በ1864 ይወጣ የነበረ አንድም ጋዜጣ ርእስ አንቀጹ ላይ እነዚህን ነጋዴዎች ጥንብ አንሶች እያለ የማያወግዝ፥ ደም መጣጭ እያለ የማይሰድብና መን ግሥት ከባድ እርምጃ እንዲወሰድባቸው ያልተማፀነ የለም። መንግስት የተቻለውን ሁሉ ሞክረ፤ ግን ምንም ፍሬ አልተገኘም። መንግሥት በየአቅጣጫው የተወጠረበት ጊዜ ነውና ስንት ቦታ ይሁን?

መቼም በነጋዴ ላይ ሁሉ ከወረደው የምሬት መዓት የሬት በት ለርን ያህል የቀመሰ የለም። ዕቃ የማሸጋገር ሥራ አጉል እየሆነ ሲመጣ ጀልባዎቹን ሸጠ የምግብ ሸቀጣ ሸቀጥ መነገድ ይዟል። ከሪችሞንድና ከዊልሚንግተን ስለሱ የሚወራው ወሬ በመጀመሪያው ሰሞን ሬትን ያስተናገዱትን ሰዎች ሁሉ ሀጥረት በሀጥረት አደረ ጋቸው።

ከዚህ ሁሉ የጦር ፈተናና መሕት በላይ ደግሞ የአትላንታ አስር ሺህ ሕዝብ ቁጥር በመርኀቱ ወቅት በእጥፍ ጨመረ። የታሃደ ዕቃ የማሻገሩ ሥራ እንኳ ለአትላንታ ከብር ተጨማሪ ሆኑዋታል። ከረ ሹም ጊዜ ጀምሮ የዳር አገር ከተሞች ከደቡብ ይልቅ በንግድ ልቀ ውና ውጠው ት ይታዩ ነበር። አሁን ግን ወደቦቹ በመዘጋታቸውና ብዙዎቹ የወደብ ከተሞች ወይ በመያዛቸው ወይ በመወረራቸው ምክንያት ይህንነት በአትላንታ ጫንቃ ላይ አረፈ። የመሀል አገር እንትስቃሴ ለጦርነት የደጀን ኃይል መሆኑ ታወቀ። አትላንታ ደግሞ የደቡቡ እምብርት ላይ ያለች ከተማ ናትና የሁሉ ነገር አንቀሳቃሽና መሽከርከሪት ሆነች።

የከተማው ሕዝብ በመከራው ላይ መከራ ተደራርቦበታል። ብት ንትኑ ወጥቷል። እንደ ሌላው የኮንፌዴሬሲው ክፍል ሁሉ በሽታና ሞት ከፋኛ ይደቁሰዋል። ነገር ግን አትላንታ ከተማ በጦርነቱ አገኙት እንጂ አላጣችም፤ አተረፈች እንጂ አልከሰረችም። የኮን ፌዴሬሲው ልብ የሆነችው አትላንታ በሚገባ ደክመኝ ሳትል —ትር

@OLDBOOKSPDF

ታዋን ቀጥላለች ። የሷም ታሪክ ሁሉንም የባቡር መንገዶች ማለ ቲያ መዝለቂያ የሌለውን ወፈ ሰማይ ሕዝብ ፡ የጦር ፡ መሣሪያና ስንቅ በሙሉ ጉልበት ያዘዋውራሉ ፡ ያስተሳልፋሉ ።

ዴሮ ዶሮ አስካርሌት አሮጌ የተቀደደ ቀሚስ መልበስና የተጠነ ጫማ ማድረግ ሞቷ ነበር ። አሁን ግን ያየኛል ፡ አይቶ ይንቀኛል የምትለው ስው ባለመኖሩ ምክንያት ግድ አይሰጣትም ። በነዚያ ሁለት ወራት በእድሜዋ አግኝታ የማታውቀውን ደስታ አግኝታ ነበር ። ከንዲን በአንገቱ ዙሪያ ስትጠመጥም የአሽሌይን የልብ ትርታ አዳምጣ የለ እንዴ ? ቃላት ችለው ከሚገልፁት በላይ እፊቱ ላይ የነበረውን ተስፋ መቁረጥ አንብባ የለም እንዴ? እሱ አፍቅሯታል ። በዚህ ባለመጠራጠሩዋና ልቧን መለስ ባደረገላት ደስታ ተገፋፍታ ለሚለኒ ደግ ልትሆንላት አሰበች ። እም ለሚለኒ ታዝንላታለች ። ለእውርነቷና ለደደብነቷ ቀላል ጥላቻ ቢኖራትም ታሳዝናታለች ።

"ይሄ ጦርነት ሲያበቃ!" ብላ አሰበች" ብቻ ይሄ ጦርነት ይለቅና . . . ቆይ . . ." ብላ ዘለች ። እንዳንድ ጊዜ እንዲህ ብላ ታስብና ልቧን ፍርሀት ፍርሀት ይላታል ። "ከዛስ ምን ይሆናል?" ደግነቱ ይህን አሳብ ቶሎ አሽቀንጥራ ትጥሰዋለች ። ጦርነቱ ሲያበቃ እንደ ምንም ነገሩ ሁሉ እንደሚሆን ይጸረጋል ። አሽሌይ እጭቅሯት ከሆነ ከሚለኒ ጋር መኖሩን አይቀጥል- መኼስ ።

ወዲያው ደግሞ የዚህ ናመፋታት ነገር አስደነገጣት ። ኤለንና ጇራልድ ፡ በዚያ ደረቅ ካዮሊክ እምነታቸው አግብቶ የፈታ ሰው እንድታገባ አፈር ከልተጫናቸው በቀር አይፈቅዱላትም ። ቤተክርስቲያን መተው ይሆንባቸዋል! አመጣች አመረደችውና ስታበቃ ምና ባቱ እንግዲህ ከቤተክርስቲያንና ከአሽሌይ ምረጪ ቢሏት አሽሌይን እንደምትመርጥ ጠስና ተፈጠመች ። ጪ . . ግን መቼም ቅሌት ነው የተፋቱ ሰዎችን በሕግ የሚያግዳቸው ቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን ራሱ ሀብረተሰቡም ጭምር ነው ። አንድም አግብቶ የፈታ ሰው ተቀባይነት አያገኝም ። ግን በአሽሌይ የመጣ ነገር ነው ። የፈለገው ቢሆን በድፍረት ትጋፈጠዋለች ። ለአሽሌይ ማንኛውንም መስዋዕትነት ትከፍላለች ።

ብቻ ጦርነቱ ሲያልቅ እንደምንም ይስተካከላል ። አሽሌይ አፍቅሩዋት ከሆነ አንድ ዘዴ ይፈልጣሊታል ። እሷም ብትሆን ዘዴ እንዲፈልግ ትገፋፉዋለች እናም እያንዳንዷ ቀን ባለፈች ቁጥር ፡ ከ ልቡ እንደሚያፈቅራት እርግጠኛ እየሆነች ያንኪዎች ድል ከተመቱ በኋላ ሁሉን ነገር እንደሚሆን አርጎ እንደሚያበጀው ያለም ንም ጥርጥር ባሳጊ ጠናች ። እርግጥም ያንኪዎቹ "በእጃቸው አስ

@OLDBOOKSPDF

ገብተውናል" ብሏታል ። ያ እንኳን ሞኝነት ነው አለች በልቧ ። ስለደከመውና ተናዶ ስለነበር ነው ያንን የተናገረው ብላ ተጽናናች። ለዛውም እኮ ያንኪዎች አሸነፉ አላሸነፉም ደንታዋ አይደለም ። ዋናው ቁምነገር ፣ ጦርነቱ እንደምንም ሆኖ ቶሎ ባለቀና አሽሌይ ወደቤት በመጣ ብቻ ።

የመጋቢት አልቂት ሰውን ሁሉ በየቤቱ መክተቱ አለፈ ። ሚላኒ አይኖችዋን ደስታ እንዳጥለቀለቃቸው ፣ ጭንቅላቷን ኩራት እንደተ ጫነው መጥታ በሆዲ ጽንስ እንዳለ ነገረቻት ።

"ዶክተር ሚድ ወይ በነሐሴ ወይ በመስከረም ትወልጃለሽ አለኝ ። እስከዛሬ ሳስብበት ነበር ግን ዛሬ ነው እርግጠኛ የሆንኩት ። ኦፍፍ ፣ እስካርሌት ግሩም አይደል? በልጅሽ በዋድ አቀና ስለነበር ልጅ ባገኘው እያልኩ ስመኝ ነበር ። እስከ ዘላለሜ ልጅ የማልወልድ እየ መሰለኝ በጣም ሰግቼ ነበር ። ስምን ደርዘን አልወልድም ደስታዬ ነው!" አለች ።

እስካርሌት ወደወንድሟ ስመሄድ ፀጉሯን ትልግ ነበር ። ሚላኒ ይሀን ስትነግራት ማበጠሪያውን ማህል ላይ እንደያዘች ማበ ጠሩዋን ቀጥ አደረገች ።

"ወይኔ አምላኬ!" አለችና ለጥቂት ጊዜ የሆነው ሁሉ አልዋጥ አላት ። ወዲያው ያ ተዘግቶ ያየችው የሚላኒ መኝታ ቤት መዝጊያ ፊቷ ድቅን አለባትና አሽሌይ ባሉዋ እንደሆነና ከሌላ ሴት ጋር እንደማገጠ ሁሉ አንዳች ቁርጠት እንደሰለት ሰነጠቃት ። ልጅ ። የአ ሽሌይ ልጅ ። ጉድ እኮ ነው ። እስቲ ሚላኒን ሳይወዳት እንዴት እንዲህ ያለ ነገር ያደርጋል?"

"እንደተገረምሽ አውቄያለሁ" አለች ሚላኒ ትንፋሽ እያጠራት ። ግን አይገርምም! ውይ እስካርሌት እንዴት አድርጌ ለአሽሌይ እንደ ምጽፍለት እንጃ ! እንደው ዝም ብዬ ብነግረው እየሸ ያን ያህል አይሆንም ወይስ . . . ዝም ልበለውና ቀስ በቀስ ይወቅ . . . ታውቂ ያለሽ . . . "

"ወይ አምላኬ" አለች እስካርሌት እምባ እየተናነቃት ማበጠ ሪያዋን ጥላ ኮመዲኖው እምነበረድ ደጥ ላይ እየተደገፈች ።

"የኔ እመቤት እንደሱ አትሁኚ! ልጅ ማግኘት መጥፎ እንዳ ልሆነ ታውቂያለሽ ። ደሞም አንቺው ራስሽ ተናግረሽዋል ። ይሄን ያህል ፊትሽ እስከሚለዋወጥ ድረስም ለኔ መጨነት የለብሽም ፤ ምንም እንኳን ለኔ ማሰብሽ መልካም ቢሆን ። እርግጥ ዶክተር ሚድ

@OLDBOOKSPDF

ማዘወንሽ ጠባብ ነው ግን ምንም ችግር አይገጥምሽ ይሆናል ብሏል . . . ግን እስካርሌት ዋድን ማርገዝሽን ለቻርሊ ለመንገር እን ዴት ብለሽ ጻፍሽለት ? ወይስ እናትሽ ወይም አባትሽ ናቸው የነገ ሩልሽ ? ወገ የኔ እመቤት እዴም ቢኖረኝ ኖሮ! ኡ...ውይ እንዴት እንደማያርግ . . . ”

“ዝም በይ!” አለች እስካርሌት ተቆጥታ “ዝም በይ!”

“ወገ እስካርሌት ይቅርታ አርጊልኝ ። ምን ደደቢ ነኝ ፣ እንደ መሰለኝ ደስ ያላቸው ሰዎች እኮ አራሳቸውን በጣም ይወ ዳሉ ። ስለ ቻርሊ ረስቼ . . . ”

“ዝም በይ!” አለች እስካርሌት ድጣችና የራቷን መለዋወጥ ለመቆጣጠር እየሞከረችና ግንባሯ ቁጣዋን ለማረጋጋት እየጣ ረች ። መቼም ወናዴዲን ሜላኒ በፍፁም ማወት የለበትም ።

ሜላኒ መለኛዋ ሴት በመጨከኑዋ ተወጅታ እንባዋ ዱብ ዱብ አለ ። ቻርለስ ሞቶ ገና ጥቂት ወራት ከማለፋቸው እንዴት ዋድ ስለ መወለዱ እንስታ ያላትን አስክፊ ትዝታ ትቀሰቅስባታለች ? እንዴት ይሄን ያህል ሐላብ የለሽ ሆነሽ?

“ቆይ ልብስሽን ላውልቅልሽ የኔ እመቤት” አለች በሩሀሩህ አንደበት ። ” ቆይ አጉርሽነም እኔ ሳበቦርልሽ ”

“ተይኝ አልፈልግም” አለች እስካርሌት ፊቷን ኮሶ አስመስላ። ሜላኒም ራሷን እየረገመችና እንባ እየተናነቃት እስካርሌትን ጥላት ሄደች ። እስካርሌት ዓይኑዋ እንደደረቀ፡ ከብሩዋ እንደቆሰለ ፡ ነገሩ ሁሉ ድንግርግር እንዳለባትና አልጋ ላይ በሚተኙ ሰዎች እንደ ሩናች አልጋዋ ጋ ቁጣትራ ቀረች ።

የአሽሌይን ልጅ በሆድዋ ከያዘች ሴት ጋር እንድትቆይ መቀ ጠሟ ምት መሰላት ። ስለዚህም ወዲያውኑ መሄድ ይሻላል ብላ አሰ በች ። አም ሁሉም ነገር ቤት ሄዳ ብታደርገው ያምራል ።

ከአንግዲህ የሜላኒን ዓይን ማየትና ያሰበችው ነገር እፊቷ ላይ እንዳይነበብባት ማድረግ የማይገሩ ዳነት ሆነባት ። በአጋታው ጠዋት እታዋን ጠቅልላ ቁርቢን በልታ ወዲያውኑ ለመሔድ ወሰነች ።

ነገር ግን እስካርሌት ዝም ድበር ብላ ፡ ፒቲፓት ተደነጋግሳ ሜላኒ በሀሳብ ተጉሰቁቁላ ጠረጴዛ ከበው እንደተቀመጡ አንድ ቴሌ ግራም መጣ ።

ለሜላኒ ከአሽሌይ አሽከር ከጦር ሜዳ የተላከ ቴሌግራም ነው።

@OLDBOOKSPDF

"ያልፈለክበት ቦታ የለም ። ግን አላገኘሁትም ። ወደቤት ልመ ለስ ወይ?" ይላል ።

ማንኛቸውም ምን ማለት እንደሆን አልገባቸውም ። ብቻ ገዘም ብለው እርስ በርስ በመደንገጥና በመሸበር ይተያያሉ ። እስካርሌት ወደቤት የመሄዱን ነገር እርስት አረገችው ። የጀመሩትን ቱርስ ሳይጨርሱ የአሽሌይን አዛዥ ኩሎኔሉን በቴሌግራም ለማነጋገር ወደ ፖስታ ቤት ተነስተው በረሩ ። ገና ሲገቡ ለካስ ራሱ ኩሎኔሉ ቴሌግራም አድርገው ኖሮ ሲጠራ ደረሱ ።

"ሻለቃ አሽሌይ ክሶስት ቀናት በፊት የአስካውት ጉዞ እየ መራ እንደወጣ አልተመለሰም ። እዝናለሁ ። በየጊዜው ያገኘነውን ወሬ እናስተላልፍላችኋለን" ።

በጣም እንደከፋቸው ወ/ሮ ፒቲ ስመሀረባቸው ላይ እየተንሰቀሰቁ ሚሳኔ ድሮቅ ድርቅርቅ ብላ ነጭ ኖራ ራሱን መስላ እስካርሌትም ፍዝዝ ድንዝዝ እንዳለች በሠረገላው ጥላ ተቀምጣ ጉዞ አይበለው መቼም ተጉዘው እቤት ደረሱ ። እቤት እንደገቡ እስካርሌት እየበረረች ደረ ጀውን ወጥታ መኝታ ቤት ገብታ መቁጠሪያዋን አወጣችና ተንበር ከካ ለመፀለይ ሞከረች ። ግን ፀሎት የሚባል ዘሩ ጠፋ ። እግዚሐር ሐጢአቷን አይቶ ፊቱን ያዞረባት ስለመሰላት ከፍተኛ ፍርሃት ገባት ። ባለትዳር ወንድ በማፍቀሩዋና ከሚስቱ ነጥላ ልታፋታው በመሞከ ርዋ እግዜር አሽሌይን ገድሎ ሲቀጣት ያስበ መሰላት ። ለመፀለይ ቃጣች ። ግን ዓይኑዋን እንኳ ወደሰማይ ማቅናት አልቻለችም ። ልታስቅስ ከጀላት ፤ ግን እንባዎችዋም አደሙባት ፤ ጠብ አልል አሉ ። መቃ አንገቷን ማንቃ ደረቷን እንደፍል ውሃ እየቃጠሉ ይገርፋሉ ያለቻቸው ውስጥ ውስጡን እንደገሞራ የሚያቃጥሏት እምባዎ ችዋ ጨክነው እምቢ አሉ ።

በሩ ተከፈተና ሚሳኔ ገባች ። ፊቷ ከነጭ ወረቀት ተበጭቆ እንደተሠራ ልብና በዘማ ፀጉር ዳር ዳሩን እንደተከፈፈ ሁሉ ጨው መስላለች ። ዓይኖችዋ እንደፈራ ሕፃን በሰፊው ፈጠው የገሽ ግት ሸስለዋል ።

"እስካርሌት" አለች እጆችዋን ዘርግታ "ትላንት ስለተናገርኩት ይቅርታ አድርጊልኝ ። ከእንግዲህ ያለሽኝ አንድ አንቺ ነሽ ። እም እስካርሌት ፤ ውድ ባሌ እንደሞተ ታውቆኛል!"

እንዴት እንደሆነ እንጃ እስካርሌት ከንድ ላይ ወድቃ ጡቶቿ በሲቃዋ ከፍ ዝቅ ይላሉ ። ሳያውቁት አልጋው ላይ ተጠጋግተው ተቃቅፈው ይላቀሱ ጀመር ። እስካርሌትም ሞራሽ ሆድ ባሳትና ፊቷን

@OLDBOOKSPDF

ሚላኒ ፊት ስር ቀብራ ስትንሰቀሰቅ ያንዲ እንባ ያንደኛዋን ጉንጭ አረጠበው ። ማልቀስ ሰውነት ይጐዳል ። ማልቀስ አለመቻል ደግሞ የበለጠ ይጐዳል ።

"አሽሌይ ሞተ! ሞተ በቃ ። አፍቅሬ ገደልኩት!"

አለች በልቧ ። እንደገና ትኩስ እንባ ፈንቅሏት አለቀሰች ። ሜላኒ የእስካርሌት እንባ ጥናቱን ሰጣትና እንገቱዋ ላይ ተጠመጠመ መሸባት ።

"ቢያንስ" አለች በማንሾካሾክ መልክ" ቢያንስ ልጁን እሳኝ ቻለሁ ። "

"እኔ ግን" አለች በልቧ እስካርሌት ትንሿ ቅናት እንደትልቅ ገሞራ እያታለለቻት ። "እኔ ግን ሲሰናበተኝ ካየሁት መልኩ በስ ተቀር የቀረልኝ ነገር ምንም የለም ። "

* * *

መጀመሪያ የተሰማው በጣም እሚለመዱ የጠፉ— ተገድሏል ተብሎ የተገመተ" ነበር ። ሜላኒ ወደ ኪትኤል ስሎን አሥር ጊዜ ቴሌ ግራም ታደርጋለች ። በመጨረሻ አንድ የማስተባበሪያ ደብዳቤ መጣ ። አሽሌይና አንድ ቡድን ለእስካውት ጉዞ እንደወጡ አልተመለሱም ይላል ። በያንዘያቹ ከልል ይኖር ይሆናል በሚል ጭምጭምታ ወሬ አነሳሽነት ሞስ የተባለ ሰው በሐዘን ልቡ ተንክቶ ለሕይወቱ ሳይ ሳስ ሄዶ ፈልጐ ፈልጐ አጥቶት ተመለሰ ። ሜላኒ ወዮ ብላ ቆይታ ገንዘብና መመሪያ እንዲልኩላት ቴሌግራም አድርጋለች ።

በመጨረሻ በባህረ— መገባበ ላይ"የጠፉ— ምርኩኛ ሆኑዋል ተብሎ የተገመተ " የሚለው ሲታይ የሐዘን ሽረሪት አድርቶበት የነ በረው ቤት እንደገና ነፍስ ዘራ ። ሜላኒ ክቴሌግራሙ ቢሮ ተጐትታ ወጣች ። ባቡር በመጣ ቁጥርም ደብዳቤ አገኘሁ ብላ ትዋ ትታለች። ሆኗ እየገፉ የእርግዝና ምልክት የሆኑትና— የመውለጃዋን ቀን የሚናገሩት የመታወክ ዓይነቶች ይሰሟት ጀመር ።

አሷ ግን አልጋ ላይ መቆየት እንደሚገባት ዶክተር ሚድ የነ ገራትን አሻፈረኝ ብላ ትዘዋወራለች ። መንፈሷ አልረጋጋ አላት ። እስካርሌት ወደ መኝታዋ ከሄደች በሁዋላም ስትንቆራጠጥ ይሰ ማል ።

አንድ ቀን ከሰዓት በኋላ ድንገጡ የአሽሌይ አጐት ፒተር እየሾፈራት ፊት በትለር ደግሱት ከከተማ ወደ ቤት በመከራ ደረ

@OLDBOOKSPDF

ሰች ። እዛው ቱሉግራም ቢሮ ደጃፍ እንደቆመች ልቡዋ ፍስሷ —ድክ ምክም ብላ ስትማትቅ ሬት በዚያ ሲያልፍ አይታት ደረሰላትና ደግፎ አመጣት ። ደረጃውን ተሸክሞ አውጥቶ መኝታ ቤቷ አደረሳት ። ቤተ ሰቡ ሙቅ ውሃ ፣ ብርድልብስና ዊስኪ ፍለጋ ሲራኮት ሬት አልጋዋ ላይ አስተኝቶ ትራሷን አመቻችቶላት ጨርሷል ።

"ወይዘሮ ሚላኒ" አለና በፍጥነት ጠየቃት "የመውለጃ ቀንሽ ደርሶ የለ?" ሚላኒ ታማ ባይሆን ኖሮ ይህን ጥያቄ ሲጠይቃት በድንጋጤ በወደቀች ነበር ። እንኳን ወንድ ቀርቶ ሴቶች ጓደኞችዋ ስለእርግዝናዋ ሲያወሩባት አትወድም ። ዶክተር ሚድ ጋ እንኳ ስትሄድ በሰንት ጣጣ ነው ። እና ከሰው ሁሉ ይልቅ ሬት በትለር ይህን ጥያቄ ሲጠይቃት በጭራሽ የማይታሰብ ነገር ሆነባት ።

ግን እንዲህ ደክማ እያቃሰተች ምን ማድረግ ትችላለች ። ቢቸ ግራት በአምንታ አራስዋን ነቀነቀች ። ራስዋን ከነቀነቀች በሁዋላ ሁኔታው ርህራሄ የሞላበት መሆኑን ስታይ ጭንቅትዋ ቀለል አለላት።

"ለራስሽ ጥንቃቄ መውሰድ አለብሽ ። ይሄ ሁሉ መሯሯጥና መጨነቅ ምንም አይረባሽ ። ልጁንም ሊጐዳው ይችላል ። ፈቃድሽ ከሆነ እንደምንም ብዬ ያሰኘን እቅም ተጠቅሜ ከዋሽንግተን ተነ ጋግሬ የአሽሌይን መጨረሻ አጣራልሻለሁ ። በኔ ጣይው ። የምር ኮኛ እስረኛ ሆኖ ከሆነ የፈዴራሉ መዝገብ ላይ ስሙ ይገኛል ። ስሙ ከሌለ ግን መቼስ ምን ይደረግ እርግጠኛ ካለመሆን የበለጠ የከፋ ነገር የለ ። ግን ቃል እንድትገቢልኝ እፈልጋለሁ ። አለበለዚያ እንዲኾ ብዬ እጀን አላስገባም ። " አለ ሬት ።

"ውይ! በጣም ደግ ሰው ነህ ።" ብላ ጮኸች ሚላኒ ። "ሰዎች ስላንተ እንዲት መጥፎ ነገር ሊያወሩ ይችላሉ ታዲያ" "ብቻ ወዲያው ሁኔታውን ገልጣ ከሱ ጋር በማውራቷ መላ ቢስ መሆን ዋን ተገንዘበችና እንባ እንባ አላት ። እስካርሌት እየበረረች ደረጃ ውን ወጥታ እንዳሸረጠች ስትገባ ሬት የሚላኒን እጅ በቀስታ ሲመታ አገኘው ።

ከዚያ ወዲህ ልክ እንደሚናገረው ፣ እንደቃሉ ጥሩ ሰው ሆኖ ተገኘ ። ምን እየሠራ እንደሆነ አንዳቸውም አያውቁ ። እንዳይጠይቁት ደግሞ ከያንኪዎች ጋር ያለውን የቅርብ ግንኙነት የሚነካ ጉዳይ ሊሆን ይችላል ብለው ፈሩ ። ከዚያ በኋላ ከወር በፊት የሰማውን ነገር እነሱ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲሰሙ ወደ ስማይ ዘለሉ ። ውለው አድረው ግን በጉጉትና በናፍቆት ስሰት ልባቸው ደማ ።

@OLDBOOKSPDF

አሽሌይ አልሞተም! ቅስሙ ምርኮኛ ሆኗል—እስረኛ። መጣ
ጩ እንደሚያስረዳው ኢሊኖይስ ውስጥ በሚገኝ ሮክ አይላንድ ከሚ
ባል ቦታ ክለ የእስር ካምፕ ውስጥ እንደታሰረ ይናገራል። በመጀመ
መሪያ ከደስታቸው ብዛት በሕይወት ከመኖሩ በቀር የፈለጉት ነገር
አልነበረም። ጉበሱ መትረፉ ብቻ አስፈንደቃቸው። የኋላ ኋላ እየተ
ረጋጉ ሲሄዱ እርስ በርስ እየተያዩ "ሮክ አይላንድ!" አሉ በአንድነት
ልክ" ገሐነም ውስጥ!" ከማለት አዙል ነበር አባባላቸው። ምክን
ያቱም በሰሜን ውስጥ አንደርሰን ቪል የከረፋ ስም እንደመሆኑ ሁሉ
ሮክ አይላንድም በማንም ደቡባዊ ልቡና ውስጥ ሀዘት የሚፈጥርና
እዚያ የታሰረ ዘመድ ካለው የሚያስደነግጥ እስር ቤት ነው።

ሊንከን የምርኮ እስረኛ አልለዋወጥም ባለበትና የሕብረቱን
ወታደሮች ኮንፌዴሬሲው እየቀለበ አኮኖሚው ሲዳክም የጦር
ቱን ፍጻሜ ያፋጥነዋል ብሎ ባመነበት ሰዓት፣ በሺ የሚቆጠሩ ባለ
ሰሚያዊ የደምብ ልብስ እስረኞች አንደርሰን ቪልና ጆርጂያ ውስጥ
ታጅለው ነበር።

ኮንፌዴሬሲው እንኳንስ ለምርኮ ወታደሮች ቀለብ ቀርቶ ለራ
ሱም ቂስለኛና ሕመማን ይቀልበው ነገር አያጠረው ነው። ለእስረ
ኞች የሚሰጡዋቸው ወይ የሚያጋሩዋቸው በጣም አነስተኛ ነው።
እስረኞቻቸውን የሚመግቧቸው ወታደሮቻቸው ጦር ሜዳ የሚበሉትን
ምግብ ነው። ይሄ ምግብ ደግሞ ሲያንኪዎቹ ስለማይስማማቸው በየ
ቀኑ መቶ ያህሉ እንደ ቅጠል ይረግፋሉ። ይህንን የሰሙት ሰሜናው
ያን አሳት ጎርሰው አሳት ለብሰው በበኩላቸው በምርኮ በያዙዋቸው
እስረኞች ላይ የከፋ የበቀል እርምጃ በመውሰድ "እዛም ቤት እሳት
አለ" ይላሉ። በዚህ አንባር ሲታይ ደግሞ በእስር ቤቶቹ ሁሉ በመጥ
ፎነቱ የታወቀው የሮክ አይላንድ እስር ቤት ነው። ለምግብ ፍርፋሪ
እንኳ እየጠፋ ነው። አንድ ብርድ ልብስ ለሶስት ነው የሚሰበሰው።
የፈንጣጣ፣ የሪህ የታይፎይድ መርቢያ ከመሆኑ የተነሳ ቦታውን የበ
ሽቶች መናኸሪያ የሚል ስም አስጥቶታል። እዚያ ከሚጋዙት ሰዎች
ሰባ አምስት በመቶው በሕይወት አይወጡም።

እንግዲህ አሽሌይ እንዲህ ያለው እርኩስ ሥፍራ ነው የተጋ
ዘው! አሽሌይ በሕይወት አለ፡ ግን ቂስለኛ ነው ያውም ኢሊኖ
ይስ ውስጥ። የኢሊኖይስ በረዶ ደግሞ አሽሌይ በሄደበት ሰዓት በጣም
ጠሊቅ ነው። ሬት የሱን ወሬ ከሰማበት ጊዜ አንስቶ ቂስሉ እንዴት
አድርጎት ይሆን? ለሞት ጸርገጦስ እንደሁ ከጥኝ ይዞት ይሆን?

"ካፕቴን በትለር፣ ባለህ መንገድ ገፋጥተህ በሌላ እስረኛ
እንዲለውጠት ማድረግ አትችልም?" አለች ሚላኒ እየጮኸች

@OLDBOOKSPDF

"እየሽ ፥ ሊንኮን ሚስቱ ወይዘሮ ቦኮስቢ ለወለደችለት አም ስት ልጆች የሚያስቅስ ሩሀሩህና ትክክለኛ ሰው ቢሆንም እንኳ አንደርሰንቪል ውስጥ ለሚረግፉት እልፍ አእላፍ ያንኪዎች ቅኝ ጣት ያህል አዘኔታ የለውም" አለ ሬት አፉን እያጠላለፈ ።" ሁሉም ቢሞቱ እንኳ ቁብ የለውም ። ትእዛዝ ተላልፏል ። የኢስረኛ ልውውጥ የለም ። ወይዘሮ ሚላኒ ፥ ከዚህ ቀደም አልነገርኩሽም - ባልሽ አንድ ዕድል አግኝቶ እምቢተኛ ሆኖዋል ። "

"አላምንም" አለች ሚላኒ በጩኸት ።

"አዎ ፥ አሻፈረኝ አለ ። ያንኪዎቹ ከሀንዶች ጋር ለሚያደርጉት ጦርነት ወታደሮች የሚመለምሉት ከምርኮኛ የኮንፌዴሬሲው ሰዎች ማህል ነው ። ማንም እሥረኛ ይህን የወዳጅነት ውል ተቀብሎ ለሀ ንዱ ጦርነት አገልግሎት ለሁለት ዓመታት ሊሰራ ምሎ ቃል ከገባ ከአገልግሎቱ በኋላ ተሰቆ ወደ ምዕራቡ ክፍል በነፃ ይላካል ። ይህንን አሽሌይ ተቃወመ ።

"እንዴ! እንዴት እንቢ ይላል "ብላ ጮኸች አስካርሌት ። " ለምን መሀላውን ተቀብሎ ሲያበቃ ከወህኒ ሲያወጡት ከድኑ ወደ ቤት አይመጣም ነበር?"

ሚላኒ ከመትጽበት በንዴት ወደኋ ዞረች ።

"ምን ማለትሽ ነው? እንዴት እንዲህ ያድርግ ትያለሽ ? ኮንፌ ዴሬሲውን ለያንኪዎች ውል ብሎ ሲክድ ፤ ለነሱ የገባውን ቃል ደግሞ ከዱ ቃለ በላ ይሁን ! አ! ምነው ምን በወጣው !ያንን ውል ከሚገባ እሣው ርክ አይላንድ ውስጥ ለምን ክርር አይልም? እሥር— ቤቱ ውስጥ ቢሞት ለኔ ክብር ነው ፤ እኮራበታለሁ ። ያኛውን ቢያደርግ ግን አፈር ነስንሹ ሁለተኛ አይኑን ላላይ እምላለሁ ። በጥዱም! እርግጥ ነው አሳምሮ ተቃውሚል ። "

አስካርሌት ሬት ወደበሩ ማምራቱን ስታይ ተቻኩላ "አንተ ብት ሆን ኖሮ ሬት ከያንኪዎች ተስማምተህ ሕይወትህን ካተረፍክ በኋላ አትከዳም ነበር ?" ብላ ጠየቀችው ።

"መጠርጠሩስ " አለ ሬት ከከንፈር ጢሙ ሥር ጥርሱን ብልጭ አረገና ።

"ታዲያ ለምን አሽሌይ እንደዛ አያደርግም?"

"እሱ ጨዋና ኩሩ ሰው ስለሆነ ነዋ" አለና ወጣ ። አስካርሌት ማሽሟጠጥና ጥላቻን እንዴት አንድ ላይ ባንድ ቃል መግለጽ እንደ ሚቻል ገረማት ።

@OLDBOOKSPDF

ክፍል ሦስት

ምዕራፍ 17

የ1864 ግንቦት መጣ። የሚያቃጥልና ደረቅ የአየር ጠባይ ያለው ግንቦት አበቦቹን ሁሉ በዕንቡጥነታቸው የተወነሰብትን ማጎፀን አሳ ርሮ ባጭሩ ቀጭቷቸዋል። የግንቦት ወር የአረንጓዴ ሕይወት ወር ነው። በጂኔራል ሼርማን የሚመሩት ያንኪዎች ደሞ ከአት ላንታ በስተሰሜን ምዕራብ አንድ መቶ ማይል ርቀት ላይ ከሚ ገኘው ከዳልተን ከተማ ከፍ ብለው በጆርጂያ ግዛት ውስጥ እንደገና ተንሰራፍተዋል። በጆርጂያና በተነሲ ድንበር ላይ ከበድ ያለ ውጊያ ይካሄዳል የሚል ሞምሞምታ ወሬ አለ። አሁን ያንኪዎች ኃይላ ቸውን እያሰፈሩ ያሉት ከዚህ ቀደም የደቡቡ ሠራዊት የቺካማውጋ ውን ድል ሲጎናፀፍ ሦ ብስ ያረፈበት መስመር ሲሆን በስተምዕ ራብ ወደአትላንታ የሚወስደውን የባቡር መንገድ ተከትሎ አትላ ንታንና ቱንሲን ከምዕራቡ አካባቢ ጋር የሚያገናኘው መንገድ ነው።

ዳልተን አቅራቢያ በሚካሄደው ጦርነት አትላንታን በአብዛኛው የሚነካት ነገር የለም። ያንኪዎቹ የተከማቹት ከቺካማውጋው ጦር ሜዳ ወደደቡብ ምሥራቅ ሲል የጥቂት ማይል ርቀት ብቻ ካለው ቦታ ላይ ነው። አንድ ገዚ ከዚህ ቦታ በተራራማው ወገን አሳብ ረው ጥሰው ለመግባት ሞክረው እንዳይሆን ሆነው ተመልሰዋል። አቋ ንም ዕጣቸው ያው ይሆናል።

ይሄ ቦታ ለኮንፌዴራሲው በጣም ቁልፍ የሆነ ቦታ በመሆኑ ጂኔራል ጆ ጆንስተን ያንኪዎቹ ብዙ እንዲቆዩ እድል መስጠት እንደሌለበት አትላንታም ሆነች ጆርጂያ አሳምረው ያውቃሉ። ጆር ጂያ ምንም ሳትታወክ ሥራዋን ማካሄድ ስላለባትና የብዙ ነገሮች ክንዋኔ በሲ ጫንታ ላይ ያረፈ ስለሆነ፤ ሽማግሌው ጆ እና ሠራ ዊቱ አንድም ያንኪ ከዳልተን በስተደቡብ በኩል ወደሷ እንዳይገባ ማድረግ ይኖርባቸዋል። ይቺ አገር በጣም ትላልቅ የእህል መጋዘኖችና የፋብሪካ ዕቃ መሸጫ ሱቆች እንዲሁም ግምጃ ቤቶች ያሉባት ናት። ሠራዊቷ የሚገለገልበትን አብዛኛውን ባሩድና የጦር መሳሪያ ጥሩ

@OLDBOOKSPDF

ከሱጥ ከር የሚሰኙ ፈለክንና የምታመርትም እሷ ናት ። በእትላንታና በዳልተን ከተማ ማህል የመድፍ ፋብሪካና ሌሎች እንዱስትሪዎች ያሉባት ሮማ ከተማ ትገኛለች ። ከሪችሞንድ በሰቱ ደቡብ በሀገሪቱ በጣም ትልቁ የብረታ ብረት ሥራ የሚከናወንባቸው የኢኖዋ እና የአላቱና ከተሞችም አሉ ። እትላንታ ውስጥ የሚገኙት የሽጉጥ ፣ የክርቻ ፣ የድንኳንና የሴሎች የጦር መሳሪያዎች ፋብሪካዎች ብቻ ሳይሆኑ በደቡብ ውስጥ በጣም ትልቅና ሰፊ የሚባሉት የመጻመጫ ፋብሪካዎች ፣ የቁና ዋና መንገዶች ቡቆችና እንዲሁም በጣም ትላልቆቹ ታዋቂ ሆስፒታሎች ይገኛሉ ። ፣ የነንፈዴሬሺው ሕይወት ዋስትና የሆኑት የእራቱ ትላልት የባቡር መንገዶች መገናኛም እትላንታ ናት ።

ከለዚህ ከወትሮው በተለየ ሁኔታ የተጨነቅ ሰው ያለም ። በዛ ሙም እኩ ሻልተን ከቴነሲው መስመር በላይ በኩል በጣም ሩቅ ስፍራ ላይ ያለ ነው ። ቴነሲ ውስጥ ሰላሰት ዓመታት ጦርነት ሲካሄድ የቆየ በመሆኑ ሰው ያዚያ ከፍለ ኤገር የሚኸዴውን ጦርነት በጣም ራቅ አድርጎ ከማየቱ የተነሳ ቨርጂኒያ ወይም ሚሲሲፒ ወንዝ ላይ እንደሚከሄድ አድርጎ ይቆጥረዋል ። ከዚህም በላይ ሽማሴው ጂኔራል ጆ ጀና የሱ ሰዎች ብቸትላንታን ቢያንኪዎቹ ማህል ናቸው ። መቼም እስዮንዎል ኳነበግ አሞኋ ወዴዘ ቴጂኔራል ሲ ቀጣሎ ያለ ንበግ ጂኔራል ሽማሴው ጋዘ መሆኑን ማንም ያውቃል ።

በማቦት ወር አንድ ቀን ምሽት ላይ ወ/ሮ ዊቲ ቤት በረንዳ ላይ ቤተሰቡ ተቅምጠ ሳለ ዶ/ር ሚድ ጂኔራል ጆንስተን በተራራዎቹ ማህል እንደዘረት ግድግዳ ሉም አብላትታ ምንም የምትፈራው ነገር እንደማይኖር የሲቪል አስተያየቱን ስጥቶ ነበር ። እዚያ በተወሳቸኸር ወንበር ላይ ተቀምጠው በሰውታ የምትጠልቅዋን ጀንበር የሚያ ስተሙሲትና የወትቱን የአሳት ኤፊዎች እንቅስቃሴ የሚያዩት አድ ማረጮቹ በየአእምሯቸው የሚመላለሰው ነበደ ያሉ ነገሮች ስላሏቸው የሚያዳምጠት በተለያየ ሰሚት ነበር ። ወ/ሮ ሚድ እጅዋን ፈል ከንድ ላይ ጣል አደርጋ ያለተፉ የሚናገረው ትክክል እንዲሆን በልቧ ትመኛለች ። ጦርነቱ እየተቃረበ ከመጣ ልጇዋ ፈል እንደሚሄድ ታውቃለች ። አሁን የአስራ ሰደበት ዓመት ሲጅና ከተማ ጥበቃ ምድብ ውስጥ ያለ ነው ። ፋኒ ኤልሲንግ ከጌትስበርጉ ሽንፈት ወዲህ ከበል ጥዝዘ ብሳ ባለራት ወራት አእምሮዋን እንደ እንድ ነገር ካቆሰለው አሰቃቂ ትርኢት ለማሸሽ ትጠጣራለች ። ይህ ትርኢት መቶ አለቃ ዴላስ ማዘበር በረቫሙና በአስፈሪው መደሚሪላንድ በተደረገው ማፈ ግፈግ ላይ በበፈ የሚሰብ ጋሪ ተገልብጠበት የመሞቱ ትርኢት ነው። ከአእምሮዋ አልወጣ ብሏታል ።

@OLDBOOKSPDF

ሻምበል ከሪ ስለ ሴቶች ያላቸው ምልከታ የሆነ ክንዱ እያመመው ነው ። በዚያ ላይ እስካርሌትን ለመወዳጀት ያደርግ የነበረው ጥረት ሁሉ አንድ እርምጃ ፈቀቅ አልለ ስላሰው አዝኗል ። ምንም እንኳ የሁለቱ ጉዳዮች ማንኙነት ባያጣባው ከአሽሌይ ዊከስ መያዝና መታዝ በኋላ ወሬው ይሽው ሆኗል ። እስካርሌትና ሜላኒ ሁልጊዜ ውይይቱ የማይሰብ ሲሆንባቸው እንደሚያደርጉት ሁሉ የሚያስቡት ስለ አሽሌይ ነው ። እስካርሌት ምርር ብላና በሐዘን ተውጣ ሞቶ ቢሆን ነው እንጂ እስካሁን አንድ ነገር እንሰማ ነበር ትላለች ። ሜላኒ ለማ ያልቁ ሰዓታት የሚመሷለስባትን የፍርሀት ጉርፍ ለመገደብ እየጣረች "ሊሞት አይችልም ። ቢሞት ይታወቅኝ ነበር ። ለእኔ ይሰማኝ ነበር" ትላለች ። ሬት በትለር የማይነበብ ጠይም ፊቱን ባዶ አድርጎ የሚያምር በት ጫማው ውስጥ የገባ እግሩን ያለሀሳብ አጣ ምሮ ዛፍ ጥላ ሥር ዘና ብሎ ቆሟል ። እስካርሌት ይሄ አይን አፋር ልጅዋ ሬት በትለርን ስለሚቀርውና ሬትም ልጁን በጣም ስለሚወደው ሬት ብትለር ማታ የሚመጣ ከሆነ በጣም ቢመሽም ዋድ ቶሎ እንዳይተኛ ታደርገዋለች ። በእጠቃላይ አስካርሌት የልጅዋ መኖር ቅር ያሰኛታል ። ልጁ ግን በሬት ክንድ ላይ ሲሆን ሀጥ ይላል ። ግሩም ልጅ ይሆናል ። ወይዘሮ ፒቲ ፓት ለእራት የተሰራው ያረጀ ዶሮ ሆዳቸውን ስለረበሻቸው ተጨነቀዋል ።

በንጋታው ወይዘሮ ፒቲ ፓትሪያርኩን ሲረግሙ አረፈዱ ። ይሄ ውጉዝ ናቸው አይበሉም የሚሏቸው እንሰት ቢሆኑ ኖሮ ወ/ሮ ፒቲ ሆዳቸውን አያማቸውም ነበር ። ፓትሪያርኩን እርጅና ሳይገድላቸው በሬት እሳቸው ቢገድሏቸው ይመዱ ነበር ። በተደጋጋሚ የዶሮ ጫፈጩት መብላት ቁራ እንደመብላት ነው አያሉ ዘላበደዋል ። ደግነቱ አትት ፒተር የአውራ ዶሮውን አንገት ከቀነጠሰው ወዲያ ወ/ሮ ፒቲ በቤተሰብ ደረጃ መበላቱ ጥሩ ነው ብለው በማሰባቸው ፣ እማሬ መንገዳቸውንም ለሰምንታት ዶሮ ቀምሰው የሚያውቁ ወዳጆቻቸው ዶሮ ይቀምሳሉ አሉና ነገሩን ወደዱት ። ስለዚህም ራት ጋበዙ ። ሜላኒ ከፀነሰች አምስት ወራት ስለሆነና ከቤት ስላልወጣች ሰው የሚጋበዝበትን ይህንን እራት ጠልታዋለች ። ወይዘሮ ፒቲ ግን ነገሩን ኮሰተር ብለው ገፉበት ። ዶሮ ለብቻ መብላት እጉል መስገብገብ ነው ። ለሳውም ሜላኒ ጉርድ ቅሚሷን ከወገቧ ከፍ አድርጋ ብትታጠቅው እርግዝናዋ ይሄን ያህልም እያስታውቅባትም ። ጡቷም ትልቅ አይደለም ።

"ው-ይ አክሰቱ ፣ እኔ ማንንም ማየት አልፈልግም . . . አሽሌይ እዛ . . . "

@OLDBOOKSPDF

"አሽሌይ እዚህ አለሁ ብዬ ወይዘሮ ጥቲ ፣ አሽሌይ ሞቷል ብለው ስለሚያምኑ ድምጻቸው እየተንቀጠቀጠ ። "ልክ አንቺ በሕይወት እንዳለሽ ሁሉ እሱም በሕይወት አለ ። ደሞኮ አብሮ የሚበላ ፣ አብሮ እሚጠጣና አብሮ እሚኖር ሰው መኖሩ ጥሩ ነው ። እኔማ ፋኒ ኤልሲ ንግንም እጠራታለሁ ብያለሁ ። ወይዘሮ ኤልሲንግ 'እባክሽ ጋብዣ ትና ከሰው ትተላቀል ስሚኝ እንዲነቃቃ ይረዳታል ። 'ብላኛለች' "

"ውይ አክስቱ ፣ ገና ምስኪኑ ዳላስ ሞቶ ጥቂት ጊዜ ሳያልፍ እቺን አሰገድደሽ እንድትመጣ ማድረግ ጭካኔ ነው . . . "

"እንግዲህ ሜሲ አናደሽ እንዳለቅስ አታድርጊኝ እንደመሰለኝ እኔ አክስትሽ ነኝ ። ምን ማድረግ እንዳለብኝ አውቃለሁ ። ግብግ እፈልጋለሁ ብያለሁ እፈልጋለሁ "

ወይዘሮ ጥቲፓት ግብግቡን አዘጋጇ ። ብቻ ግብግቡ ሊጀመር ጥቂት ይቂቃ ሲቀር አንድ ያልተጠበቀና ያልተጋበዘ እንግዳ መጣባቸው ። የዶሮ አርቢዋው ሽታ ገና ቤቱን ሲያውድ ፤ ከነዚያው ከተለመዱ ምስጢራዊ ጉብኝቱ አንዱን ፈጽሞ ሲመለስ ሬት በትለር የወይዘሮ ጥቲን በር አንኳኳ ። በትልቅ የካርቶን ሳጥን ሙሉ ከረሜላ በብብቱ ሥር ይዞና ባለቡለት ስለት ምላሱን አዘጋጅቶላቸው ከች ብሏል ። ሆኖም ወይዘሮ ጥቲ ምንም እንኳ ይከተሩና ወ/ሮ ሚድ እንዴት እንደሚጠሉትና ፋኒም ዩኒፎርም ያለበሰ ወንድ እንዴት እምርራ እንዶምትጠምድ ቢያውቁ ፣ ምንም ነገር ለማድረግ ባለመቻላቸው ግብቱ እንዲጋበዝ አደረጉት ። ሙቹም ወንጌድ ላይ ቢያነጉት የሚድ ቤተሰቦችም ሆኑ የእልሲንግ ቤተሰቦች አያነጋግሩትም ። ነገር ግን በጓደኞቹ ቤት ውስጥ ከሆነ ግንጋግሩ የጨዋነት ግዴታቸው ነው። በዚያ ላይ አውን ሬት በለፈለፉለሞ ሚላኒ ጠንካራ ጋሻ መከታነት ሥር ስለሚጠለል ጥስትናው ይጠበቅለታል ። የአሽሌይን አድራሻ ለማግኘት እጇን ካስገባ በኋላ ፤ ሚላኒ ቤቷ ቤቱ መሆኑን በይፋ ተናግራ ማንም የፈለገውን ቢል እሱ በሕይወት እስካለ ድረስ በሯን ክፍት የምታደርግለት መሆኗን አውጇለች ።

ወ/ሮ ጥቲፓት ፤ ሬት ጠባዩን አሳምሮ መቀመጡን ሲያዩ የነበራቸውን ተታውሞ እየቀነሱ ሄዱ ። እብዛኛውን ሰዓት ፋኒን በማጽናናት ላይ በማዋል መስዋዕት ያደረገው ሲሆን በጣም ግሩም አድርጎ ያስተዛዘናት ከመሆኑ የተነሳ ሬገማ ማለት ደረጃ አድርሷታል ። የአ ራት ግብግቡ በስንሥርዓት ቀጠለ ። የነገሥታት ፈሽታ ዓይነትም ሆነ ። ካሬይ አሽበርን በእንደርሰንቪል መንገድ ላይ ከአንድ የተማረከ ያንኪ የትንባሆ ማስቀመጫ ውስጥ ያገኘውን ትንሽ ሻይ ቅጠል ይዞ መጥቶ

@OLDBOOKSPDF

ለለንበር ሰው ሁሉ አንድ አንድ ጥንጅል ጠጣ ። ሻዩ ትንሽ ትንሽ የትምባሆ ጣዕም ነበረው ። ለእያንዳንዱ ሰው ደህና ደህና የዶሮ ሥጋ ደረሰው ። በሽንኩርት የተሠራ የበቆሎ ምግብ ፣ጣፔቴ ሙሉ የደረቅ አተር ፣ በርከት ያለ ሩዝና መረቅ (ይሄ አንኳ የማወራሪያ ዱቄት ስለ ሌለ ሙሀ ሆኗል) ቀርቧል ።ከምግብ በኋላ የሚቀርበውም የድንች ጥብስ ሬት ካመጣው ከረሜላ ጋር ቀረበ ።በዚህ ላይ ሬት ለወንድች ለወንዶቹ የጋበዛቸው እውነተኞው የሐሻና ሲጋር ከሚጠጡት የእን ጀሪ ወይን ጋር ሲጨመር ግብግቡው የሮማውን ሀብታም የሱኩላንን ግብግ መሰለ ።

ወንዶቹ እፊት ለፊቱ በረንዳ ላይ ወደተቀመጡት ሴቶች መጥ ተው ተቀመጡ ። ሙይይቱ ሁሉ ወደጠርጎት ወሬ አመራ ። ዛሬ ጊዜ እያንዳንዱ ሙይይት የሚያመራው ወደ ጠርጎት ነው ። ሟሙውቶች ሁሉ ወይ ከጠርጎት ይጎሳሉ አሊያም ወደ ጠርጎት ይመለሳሉ ። ያለ ጥርጥር ግን ለሁሉም ሙይይት ፍሬ ሀሳብ ጠርጎት ነው ። በሀዘን ሊወሳ ይችላል ።በደስታም ሊወራ ይችላል ።ብቻ ሀሮ ሀሮ ወሬው ስለጠርጎት ጊዜ ፍቅር ፣የጠርጎት ጊዜ ሠርግ ፣በሆስፒታል ውስጥ የሚ ሞቱ ሰዎች ጉዳይ ነው ። ስለጠፒ ግንባር ከሆነም በየጠር ሠፈሩ ስለሚፈጠሩ ነገሮች ፣ስለወጊያ ፣ስለዘመቻ ፣ ስለቆራጥነት ፣ስለፍራቻ ፣ ስለአስቂኝ ቀልድ ፣ ስለሀዘን ፣ ስለብቸኝነትና ስለተስፋ ይነገራል ። ሁል ጊዜ ተስፋ ።ምንጊዜም ተስፋ ። ባለፈው በጋ የደረሰው ሽንፈት ቢኖ ርም እንኳ ጠንካራ ተስፋ ምንጊዜም ይኖራል ።

ሻምበል አሽበርን ከአትላንታው ሠራዊት ወደዳልተኑ ሠራ ዊት እንዲቀየር ጠይቆ የተሳካለት መሆኑን ሲገልጽ ሴቶቹ ሁሉ የተ ዘረጋ ክንዱን በዓይኖቻቸው እየሳሙ እሱ ከሄደ የሚያጫውታቸው እንደሚያጡ በማሰረዳት የኩራት ስሜታቸውን ሸፍነው መሄድ እን ደሌለበት ይገልጹለታል ።

ወጣቱ ካሬይ እንደ ወይዘሮ ሚድ ፣ እንደሚኒላ ፣ እንደ ወ/ሮ ፒቲና እንደፋኒ ያሉ ያገቡና በተለይ የተደላደሉ ሴቶች እንዲህ ያለውን ነገር ሲናገሩ ሲሰማ ግራ የመጋባትም የመደነትም ስሜት ተሰማው ። በተለይ አስካርሌት ከልባ የምትናገረው እንደሚሆን ተስፋ አደረገ ።

"እንዴ ቶሎ ይመለሳል እኮ" አለ ዶክተር ፣ በካሬይ ትከሻ ላይ እጁን ጣል አድርጎ ።"እንግዲህ አንድ ወጊያ ብቻ ቢኖር ነው ። ከዚያ የያንኪ ዘር በሙሉ ጭራውን ሸጉጦ ወደ ተንሲ ይፈረጥጣል" እዚያ ሲደርሱ ደግሞ ጄኔራል ፎሬስት ያስተናግዳቸዋል ። እናንተ ሰዎች ያንኪዎቹ ወደዚህ ይቃረባሉ የሚል ስጋት ጨርሶ እንዳይ ሰማችሁ ። ጄኔራል ጆንስተንና ሠራዊቱ በተራራዎቹ ማህል እን

@OLDBOOKSPDF

ግድግዳ ቆሟል ። አም እንደብረት ግድግዳ ቆሟል ።" አለ ደገመና ቃላቱን አጣጥሞ ። "ቬርማን በጭራሽ አልፎ አይመጣም ። ሽማግሌ ውን ጆ በፍጹም ሊያነቃንቀው አይችልም ።"

ሴቶቹ ሁሉ ንግግሩን በመደነቅ ሰቁ ። መቼም እሱ የተነፈሳት ቃል መሬት ጠብ የማትል ዕውነት ናት ። እንዲህ ያሉትን ነገሮች እኮ ከሴቶች የተሻለ ወንዶች ያውቋቸዋል ።ስለዚህ እሱ ጀኔራል ጆን ስቱን የብረት ግድግዳ ነው ካለ ጀኔራል ጆንስተን የብረት ግድግዳ መሆን አለበት ።ሬት ብቻ የተለየ ሀሳብ አለው ።መናገር ጀመረ ። ከራት ሰዓት ጀምሮ ምንም ሳይናገር ቆይቷል ። የሚያንቀላፋውን ልጅ ደረቱ ላይ አስተኝቶ ስለጦርነቱ የሚያወሩትን አቶን አጣሞ ሲያዳምጥ ነበር ።

"ጭምጭምታ እንደሰማሁትና እንደማምነው ቬርማን ሙዶቪ ወታደሮች አሉት ። ተጨማሪ ኃይል እንዳስመጣ ታውቁ የለም?"

ዶክተሩ ባጭሩ መለሰለት ።ሲመጣ ጀምሮ ዶክተሩ ቅፍፍ ብሎት ነበር ።ከዚያ ጭራሹኑ አብረውት ራት ከሚበሉት ሰዎች ማህል አንዱ ሬት ሆኖ አገኘው ። ይህን ሰው ሲጠላው ለብቻው ነው ። የጥላቻ ስሜቱን ይፋ እንዳያወጣ ያገደው ለመ/ሮ ፒቲ ያለው አክብሮ ትና በሳቸው ጣራ ሥር መሆኑ ነበር ።

"ታዲያስ ጌታውን"ዶክተሩ በምላሹ አምባረቀ ።

"ከትንሽ ጊዜ በፊት ቫምበል አሽበርን ሲናገር አንደሰማሁት ባለፈው ድል ተበረታትው ወደጠሩ የተቃላቀሉትን ከሀዲዎች ጨምሮ ጀኔራል ጆንስተን አርባ ሺህ ወታደሮች ብቻ ናቸው ያሉት ብሏል ።"

"ጌታ" አለች መ/ሮ ሚድ በንዴት "በኮንፌደሬሲው ሠራዊት ውስጥ ምንም ከሀዲዎች የሉም ።"

"ይቅርታ እመቤቴ"አለ ሬት ፤ በሽሙጥ ሐፍረት ። "እኔ ከሀዲ ያልኳቸው ከጦሩ ፈቃድ ተቀብለው መጥተው ወደጦር ክፍላቸው መመለሱን ረስተው የቀሩትን ፤ በቁስለኝነት ሲታከሙ ስድስት ወር ቆይተው ከዳኑ በኋላ ግን ቢታቸው ተቀምጠው የወትሮ ሥራቸውን የቀጠሉትን ወይም የዐደይ አርሻ የጀመሩትን ነው ።"

ዓይኖቹ ማብራት ጀመሩ ። ወይዘሮ ሚድ ከንፈሯን በንዴት ትነ ከሳለች ።ሬት ወይዘሮ ሚድን በቀላሉ ስለረታትና እፀም ኩርፍ ስላለች እስካርሌት ልትስቅባት ታጥቷት ነበር ። በየፈፋውና በየጉድ ባው ፣ በየረግረጉና በየጨለቅላታው በቅጣት የሚማትቁ ወደ ሠራዊቱ ጸግመኛ እንመለስም ፣ እንዋጋም ብለው የእስር ቤቱን ሹም ያስቸገሩ

@OLDBOOKSPDF

በመቆ የሚቆጠሩ ሰዎች አሉ እኔም የሚሉት "ጦርነቱ የሀብታሞች ፣ ውጊያው ግን የድሆች ነው" ስለሆነም እስካሁን የተዋጋነው ይበቃናል ነው ።ሆኖም እነዚህን በቁጥር የሚበልጡ ፤ በከሀዲነት ተራ ገብተው የነበሩ ፤ ነገር ግን እስከዘለቂታው ያልከዱ ሰዎች አሉ ። እነ ዚህኞቹ ፈቃድ ለማግኘት ሰስት ዓመት ሙሉ የጠበቁና በጥበቃ ላይ እንዳሉ ከቤተሰባቸው በአግባብ ያልተጻራ ደብዳቤዎች የደረሳቸው ናቸው ። ደብዳቤዎቹ እንዲህ የሚሉ ናቸው—"እኛን ርበናል—" በዚህ ዓመት እህል አይኖርም ። የሚያርስ ሰው የለም ።" "እኛን ርበናል ። ከሚሰሪያቱ የአሳማ ጥጃዎቻችንን ወስደውብን ለወራት ካንተ የተላከም ገንዘብ አልደረሰንም ።የደረቅ አተር እየበላን ነው የከረምነው ።"

ሁልጊዜ ጎበረ ዜማው "ሚስትህ ፣ ልጆችህ ፣ ቤተሰቦችህ በሙሉ ተርበናል ፣ጦርነቱ የሚያልቀው መቼ ይሆን ?ወደቤትስ መቼ ትመጣለህ እኛ ተርበናል ።ተርበናል" በየሰለቹ እየመነመነ የሚሄደው ሠራዊት ፍቃድ በመከልከሉ ያለፈቃድ ወደቤቱ እየሄደ መሬቱን ያርስ ፣ እህሉንም ይዘራና ቤቱን ያድስ እጥሩንም ያጥር ጀመር ።ወደፊት ያለ ፈሰው ጦርነት መምጣቱንና ይህንን ሁኔታ የተረዱ የነፍስ ጦር መሪ ዎች ለሄዱት ወታደሮች ደብዳቤ በመጻፍ ተመልሰው ወደጦሩ እንዲ ቀላቀሉና እስካሁን ላደረጉት ምንም ጥያቄ እንደማይጠየቁ ይነ ግሯቸዋል ።አብዛኞውን ጊዜ ሰዎች ይመለሳሉ ።ረሀብ ለጥቂት ወራት ከቤተሰባቸው ላይ ጥርሱን ነቅሎ ከለሚርቅ ወደጦር ከጥላቸው ይቀ ላቀላል ።"ለማረስ ሲባል የተመለሱ ፈቃዶች" ሠራዊቱን ከድቶ ከጠ ላት ጋር እንደመቀላቀል አይቆጠሩም ነበር ። ሠራዊቱን የሚያጸ ሙት ግን እንደነዛው እንደከዲዎቹ ነው ።

ዶክተር ሚድ ምኞት የማይሰጠውን የዝምታ አጥር ጥሶ በቀዝ ቃዛ ድምጽ ለውይይቱ ድልድይ በመዘርጋት "ካፒቴን በትለር ፤ በኛ ወታደሮችና በያንኪ ወታደሮች ማህል ያለው የቁጥር ልዩነት የሚያስጨ ንቅ ጉዳይ አይደለም ። አንድ የኮንፌደሬሲው ወታደር ለአንድ ደርዘን ያንኪዎች ይበቃል ።"

ሴቶቹ ራሳቸውን በመነቅነቅ ትክክልነቱን አረጋገጡ ። ይሄ መቼም ማንም አሌ የማይለው ጉዳይ ነው ።

"ጦርነቱ ገና ሲጀመር ይሄ አሁን ያልከው እውነት ነበር" አለ ሬት ።"ምናልባት አሁንም እውነት ይሆን ይሆናል ። የኮንፌደሬሲው ወታደር ለጠመንጃው ጥይት ፣ለእግሩ ጫማ እና ለሆዱ ምግብ እስካ ገኘ ድረስ አውነት ይሆን ይሆናል ። አይደለም እንዴ ሸምበል አሽበርን ?"

@OLDBOOKSPDF

ድምጼ አሁንም ለስላሳና የማፈር ቃና ያለበት ነው ። ካፊይ አሽ በርን ያለጥርጥር ፊትን የሚጠላ በመሆኑ በተናገረው ነገር ከፍቶ ታል ። ዶክተሩን በደስታ ይደግፈው ነበር ። ነገር ግን ለመዋሸት አይ ኾልም ። ምንም እንኳ ጥቅመ ቢስ ከንዱ ሰምኔም የማይበጅ ቢሆን ሌላው ሲቪል ሕዝብ ያልተረዳውና እሱ የተረዳው የሁኔታው መነ ባስ ፤ ወደ ጦር ግንባር ለመሄድ እንዲያመለክት ያደረገው ምክንያት ነበር ። ክኮሚሳሪያቱ ጽ/ቤት ፡ ከሠለጢታል ግዳጅ ከፖስታና ከባቡር ጣቢያ አገልግሎት ተዛውረው ወደጥንቱ የወጊያ ግንባር በቅያሬ የሚመለሱ በእንጨት እግር የሚሄዱ ፣ አንድ ዓይናቸውን ያጡ ፣ ጣቶቻ ውን የተቆረጡ ፣ አንድ ከንዳቸውን የተገረዱ እያሉ ሰዎች አሉ ። ሽማግሌው ጀ እያንዳንዱን ሰው እንደሚፈልግ ያውቃሉ ።

ቫምበል አሽበርን ሀለመናገሩ ዶክተር ሚድ ትዕግሥትን ጨርሶ አምባረቁ፡—"የኛ ሰዎች ለእግራቸው መጫሚያ ፣ ለሆዳቸው እህል ውሀ ሳይኖራቸው ከዚህ በፊት ድልን ተጐናፅፈዋል ። ወደፊትም ይዋ ጋሉ ። ያሸንፋሉ ። ጀኔራል ጀንስተን እንደማይነቃነቅ ኢረጋግጥልሀለሁ፤ የተራራ መወጣት ሠሙረድ ልምድ ከጥንት ጀምሮ ለአንድ ሠራ ዊት ምሽግ ነው ። መጠለያው ነው ። ጠንካራ መከላከያው ነው ። በታ ሪክ ውስጥ ቱርም ፓይሌን አስታውሰሀ?"

እስካርሌት የተሸላትን ያህል ብታስብም ቱርሞፓይሌ ሊመጣ ላት አልቻለም ።

"ታዲያክ ቱርሞፓይሌ ላይ እስከመጨረሻው አንድ ሰው ድረስ ሞተው አልቅው ነበር ፤እይደለም እንዴ ዶክተር?" ብሎ ጠየቀ ሬት ሳቁን ለማፈን ጉንጮቹን እየነፋ ።

"እየተሳደብክ ነው እንዴ ሰውዬ ?"

"ዶክተር! ይቅርታ አድርግልኝ! አልተግባባንም ነእኔ መረጃ መጠየቄ ነበር ።ስለየንቱ ታሪክ ያለኝ የማስታወስ ችሎታ ደካማ ነው ።"

"ያንኪሞች ወደጀርሺያ አንዳይገቡ ለማድረግ ካስፈለገ የኛ ሠራ ዊት እስከ መጨረሻው አንድ ሰው ድረስ ይሞደታል ።" አለ ዶክተሩ ነጠቅ አድርገ። "ግን ያ አያስፈልጋቸውም ። በአንድ ወጊያ ብቻ ከጀ ርሺያ ያባረሯቸዋል ።"

ወይዘሮ ፒቲፓት ከተቀመጡበት ተነስተው በጢያኖ የሚዘፈን ዘፈን ምርጫ እንዲያደርግ እንድትጠይቅ ለእስካርሌት ነገሯት ። ውይ ይከ እየጠነከረ ከፉ አውሎ ንፋስ ሊያስነሳ መሆኑን ተመልክተዋል ። ሬትን እራት ከጋበዙ ችግር ሊፈጠር እንደሚችል አሳምረው ያውቁ

@OLDBOOKSPDF

ነበር ። እሱ ካለ ሁልጊዜ ረብሻ ይኖራል ። እንዴት እንደሚጅምረው ግን በትክክል ሊረዱት አልቻሉም ። የመድሀኒአለም ያለህ! እስካር ሌት እዚህ ሰው ላይ ምን አይታለች? ሚላኒስ የምትደግፈው ለምንድ ነው?

እስካርሌት በታዛዥነት ወደ እልፍኙ እየሄደች ሳለች በበረን ዳው ላይ ፀጥታ ነገሰ ። የፀጥታው የልብ ትርታ ሬት ላይ የሚዘንበው የጥላቻ ስሜት ነው ። ሰው ምንም ቢደነቁር የጂኔራል ጆንስተንና የሠራዊቱ አይበገሬነት እንዴት አይታየውም? እንዴትስ አያምንም ። ይሄን ማመን መቸም የተቀደሰ ተግባር ነው ። የመጨረሻ ከሀዲ ሆኖ የማያምን ሰው እንኳ ቢሆን በዚህ ጉዳይ ላይ ቢያንስ አፉን መዝ ጋት መቻል አለበት ።

እስካርሌት ጥቂት የፒያኖ ቁልፎች ተጫንችና ጣፋጩንና ሐዘን የተቀላቀለበትን ድምጹዋን ከወደእልፍኙ ለቀቀችው ።የዘነኛው ዘፈን ስንኞች ፈሰሱ፣—

"ለቦምብ ቁጣ ተጥደው
በጥይት አረር ተቆልተው

ግድግዳው በነጣ አስር ቤት
ሚችም መተም በተጉበት

ሰቆቃ እየተዘራ ፡ መከራ እየታጨደ
ያንዲ ወጻጅ ተወለደ ።

ያንዲ ውበ ሽጋ ፍቅረኛ
ያ ጅግና ወጣት ምርኩዛ

ለዛው ያማረ ፊት ገፁን
ልጅነት ግርማ ሞገሱን

ዐዳሱን እንደለበሰው
የመታብር ሲሳይ ሲሆን
ትቢያ ሊለብስ ምን ቀረው"

"ወርቃማው ፀጉር በደም ተነከረ"አለ ሐዘንተኛው የእስካር ሌት መዘቃ ። ሩኒ በማማሽ እንደመነሳት ብላ በደከመና በታፈነ ድምጽ "ሌላ ዘፈን ዝፈኝ" አለቻት ።

እስካርሌት በመገረም በድንጋጤ በመዋጧ ፒያኖው ድንገት ፀጥ አለ ። ወዲያው ፈጠን አድርጋ የሌላ ቅኝት ቁልፎችን በመንካት "ጃኬት አፍ ግራይ" የተሰኘውን ዘፈን ጀመረችና ይሄ ምርጫዋ ምን ያህል ልብ እንደሚያባባ አስታውሳ ወዲያው አቋረጠችው ። የምትዘፍ

@OLDBOOKSPDF

ነው በማጣቂያ መሀል ስትቀር ፒያኖው እንደገና ፀጥ አለ ። ሁሉ ዘፈኖች ከሞት ፣ ከመለያየትና ከሐዘን ጋር የተያያዙ ናቸው ።

ፊት ድንገት ብድግ ብሎ ዋድን እፉኒ ሞን ላይ እስተኛውና ወደአልፍኝ ሄደ ።

"ማይ አልድ ኬንተኪ ሆም" የሚለውን ተጫወቺ" አለ ለስለስ ብሎ ። እስካርሌት እያመሰገነችው ወደዚህኛው ዜማ ተሸጋገረች ። የፀድምጽ በፊት ግሩም ወፍራም ድምጽ ታጀበ ። ሁለተኛው ግጥም ላይ ሲደርሱ የተስዘሰዘው ሰው ሁሉ እፎይ ብሎ በቀላሉ መተንፈስ ጀመረ ። ዘፈኑ እስከዚህም ነበር ። ሰውን ምን ዘና እንዳደረገው እግዚሀር ይመቅ ።

ጭጋር ይኑረው እንጂ ፡ ከቢድ ሜና ጭንቀታችን ፣
መቅለሉ አይቀርም አድሮ ፡ መንገድ ለመንገድ ኑሯችን ፣
የጥንት ኬንተኪ ዜቱ ደህና አደሪ እስከዚያ ቀን ፣"

* * *

ነገሩ እስከዘለቀበት ድረስ የዶክተር ሚድ ማምት ትክክል ነበር ። መቶ ማይል ርቅ ከሚሃየው ክዳለቱን ከተማ ብላይ ጀንበቱን በተራ ራምች መሀል እንደ ብረት ሚድማስ ቆመ ።

ጀኔራል ጆንስተን ቢጣም በቆራጥነት በመጣሩ ፤ በጣም አምርሮ በመዋደቁ ፣ ቪርማን በሸለቆው ወርዶ እትላንታ ሰመግባት የንበረው ፍላጐት በመቀጨቱ ፤ ያጎኪዎቹ ኒንዲያፈገፍጉና መከረው ሠከረው እንዲመጡ ተግደዱ ። ግራጫ ለባሽ መታደሮችን ግንባር ለግንባር ተፋጠው ጥሰው ለማለፍ በለመጅላቸው ክዳለቱን ግርጌ አሥራ አምስት ማይል ላይ ጣታ ጣታ በጨለማ ሽፋን ቸገብው በማሻሽ ክብ ሠራያውን ጠምደው ከጀንስተን ጀርባ ሬሳክ ላይ የባቡር ሀዲዱን ለመቁረጥ ዘመቱ ።

የመንታምቹን የሐዲድ ብረቶች አደጋ ላይ መውደቅ የሰሙት የነንፌደሬሲው መታደሮች ፤ ይዘውት የንበረውን ቁልፍ ምሽግ ለቅቀው ፤ በጠፍ ጨረቃ አጭሩን አጯራሜ መንገድ መርጠው ፤ ወደ ሬሳክ እንዲገሰግሱ ተገደዱ ። ከየኮረብታው ሥር እንደጉንዳን እየተርመሰመሱ ያንኒዎቹ ሲመጡ ፤ የደከቡ መታደሮች ምሽጋቸውን ሠርተው ፈንጂያቸውን ቀብረው ይጠብቁዋቸውና ጥይት እንደአሸን እያፈሱ ጸልተን ላይ እንደሠሩላቸው አዚህም ሠሩላቸው ።

ከጸልተን ቆስለው የመጡ መታደሮች ሽማሌው ጆ ወደ ሬሳክ የማፈግፈጉን ወሬ ይዘው ሲመጡ ድፍን እትላንታን ዛረመው ሰቢመ ጠኑም ተረበሸ ። በሰሜን ምዕራብ ሰማይ ላይ አንድ ትንሽ ጥቁር

@OLDBOOKSPDF

ይመና የሚያንዣብብ መስለ—የበጋ አውሎ ንፋስ ያዘለ የመጀመሪያ ጥቁር ደመና ። ጂኔራሉ ምን እያሰበ ነው ነያንኪዎቹ አሥራ ስምንት ማይል ወደ ውስጥ ዘልቀው ጆርጂያ ይግቡ ነው እንዴ እሚለው ፣ ዶክተር ሚድ ያለው እንኳ ቢሰላ ተራራዎቹ ምሽጐች ናቸው ፣ ታዲያ ሸማግሌው ጆ ያንኪዎቹን አዚያው ተራራ ላይ ገትር ያልያዛቸው ለምንድነው ?

ጆንስቶን ሬሳካ ላይ ያንኪዎቹን አሥጠ ይዞ ወደኋላ እንዲመለሱ አድርጓቸው ነበር ። ነገር ግን ሼርማን ያንኑ የማጥሽ ክብ የሚጥቃት እርምጃ ወስዶ ፣ አልቆ መሰናክርት የሌለው ሠራዊቱን አሰማርቶና የአሰ ታናሳት ወንዝ አቋርጠ ፣ እንደሳና በኮንፌዶሬሲው ክለል ያለውን የባ ቡር ሐዲድ መታ ። እንድነና ግራጫ ልባሾቹ ከየጉበሮ ጉድንዳቸው እየወጡ የባቡር ሐዲዱን ለመከላከል በጥድፊያ በረሩ ። እንቅልፍ ሳያ ኖራቸው ፣ በዘመቻና በወጊያ ብዛት ሰውነታቸው ዝሎ ፣ ርሃቸው (ሁል ጊዜም ይርባቸዋል) ሌሳ ረጣን ዘመቻ ለማድረግ ቁልቁል ሸለቆውን ይዘው ወረዱ ። ከያንኪዎቹ ቀድመው ከሬሳካ ለድስት ማይል ዝቅ ብላ ወደምትገኘው ካልሁን ወደተባለች ጭንሽ ከተማ ገቡ ። መሽግውና እድ ፍጠውም ያንኪዎቹ ዝቅብ ሲመጡ ለ,ተገትጓቸው ይጠብቁ ጀመር ። ውጊያው ተፋፋመ ። ከባድ ፍልሚያ ተጋጠሙ ። ያንኪዎቹ ድል ተመ ተው ወደኋላ አፈገፈጉ ። የኮንፌዶሬሲው ወታደሮች ከደካም ብዛት ክንዳቸው ላይ ተንጋለው አረፍት አንዲያገኙ ይፀልያሉ ። አረፍት ግን በጭራሽ አልተገኘም ። ሼርማን ቀበ በቀበ የአጠቃቅ ስልቱን በሰፊ ከበባ አደራጅቶ እንደ ግኖ እንዲያፈገፍጉና እንደሳና የባቡሩን ሐዲድ ጥበቃ ላይ እንዲሰማሩ አደረጋቸው ።

የኮንፌዶሬሲው ወታደሮች መንገድ ለመገንድ እያንቀላፉ ይጓ ዛሉ ። አብዛኞውን ጊዜ ሰማዕብ እንኳ ይደክማቸዋል ። ትንሽ ትንሽ ማሰብ ቢችሉም ሸማግሌው ጆን አምነው ይቀመጣሉ ። እንደሚያፈገ ፍጉ ገብቷቸዋል ። እንዳልተቸነሩም ያውቃሉ ። የቂቋ ሰው ስለሌላቸው ምቾጋቸውና የመከሰከያ ሰፈራቸውን ለቀቁ እንጂ የሼርማንን ተወ ርዋሪ ጦር ማሸነፍ አያቅታቸውም ነበር ። በየሄዱበት ያንኪዎቹን ጠራ ርገው ያባርሯቸዋል ። ያንኪዎቹ ደም መልሰው ይቀጋሉ ። መልሰው ሽንጣቸውን ገትረው ይቆማሉ ። የዚህ ሁሉ ማፈግፈግ መጨረሻ ምን እንደሚሆን አያውቁም ። ሸማግሌው ጆ ግን የሚሠራውን ያውቃልና ለንሱ የሱ ማወቅ በቂያቸው ነው ። የማፈግፈጉን ስልት በጣም ረቂቅ አለሥረገው በወገን ላይ የደረሰው ጉዳት በጣም ጥቂት ሲሆን ከጠ ፋት በኩል ግን በርካታ ሞተዋል ። በርካታ ተማርከዋል ። አንድም ጉሽ ክርካሪ አልተመታባቸውም ። ጠመንጃም ቢሆን አራት ብቻ ነው የጠ ፋባቸው ። ከጀርባቸው ያለውንም የባቡር ሐዲድ ቢሆን አድነውታል ።

@OLDBOOKSPDF

ሄርማን ያንን ሁሉ የግንባር ማጥቃት ፣ ያን ሁሉ የፈረሰኛ ግፍጫና ያን ሁሉ የከበባ ተወርዋሪ ጦር ተጠቅሞ የባቡር ሐዲዳቸው ላይ እንዲት ጣቱን እንኳ አላሳረፈባትም ።

የባቡር ሐዲድ ። ያ እንደእባብ እየተምዘገዘገ በወሐያማው ሸለቆ ውስጥ እጅርመ ወደአትላንታ የሚዘልቅ ቀጭን ብረት ፣ ያ ውዱ የባቡር ሐዲድ አሁንም የነሱ ነው ።ሰዎቹ በከዋክብት ብርሃን ውስጥ በስሱ የሚያበራትን የሐዲድ መስመሮች ለማየት በሚችሉበት አቅጣጫ ትንጋልው ይተኛሉ ። እነዚህ ሰዎች እዚህ ጥጋድመው የሚጠብቁት ሞትን ነው ።ከመሞታቸው በፊት ለመጨረሻ ጊዜ የሚያዩትና ግራ የተጋቡ አይኖቻቸውን የሚያሸፉት ጨክኔ ወሀይ ብርሃን ሰት ሰድባቸው ከሙቀቷ ጋር እሚበሰጨለጭት የባቡር ሐዲዶች ላይ ነው ።

በሸለቆው ቁልቁል ሲዶ በርካታ የሰዶቶች መንጋ እሬታ ቸው ከች አለ ። አራሽ ከቀጥታው ሠብሶም ከድሀ ጥቁር ከጎጭ ፣ሴት ከሀዛን ሳይል ይርመሰመሳል ። ሽማግሌዎች ፣ በሞት አፋፍ ያሉ በሽተኞች ፣አሳስ ስንኩላን፣ ቁስለኞች፣ በእርግዝና የጎፉ የደረ ሱሴቶች ፣ የአትላንታን ጐዳና አጣበው ከፊሉ በባቡር ፣ ከፊሉ በእግር ፣ ከፊሉ በፈረስ ጀርባ ፣ግማሹ በሰረገላ ፊላሙ በጋሪ ከንጓዝ ጉዘንዙ ይጓዛል ።እንደ ጉድ ይፈስሳል ። ከሚያፈገፍገው ሠራዊት እምበት ማይል ቀደም ብሎ እጾተኞው ይታምማል ። በየቦታው ይሞማል ። ፊሳፃ ሲጾርስ ቆም ብሎ ያንኪዎች ወደኋላ ተባርረው መጀቢቱ መመለስ ይችል እንደሆን ይጠይቃል ። ደም ካልሁን ላይ ቆም ይላል ። የያንኪዎቹን መባረርና ወደ ቤት የመመለሱን ነገር ይጠይቃል ። መንገዱን ይቅዋለል ። ቀጥሎ ኪን ግስተን ላይ ያርፋል ። ያንኑ ጥያቄ ይጠይቃል ። መንገዱን ይይዛል ። በቆመበት ቦታ ሁሉ በተበሳ ይሳሳል ።ይሄ ሁሉ ሆኖ ግን ያንን ፀሀ ያማ መንገድ መልሶ ማግኛ አይችለም ። ግራጫ ለባሹ ሠራዊት አና ቤቶችን ያልፋል ። እርቃናቸውን የቀሩ እርሻዎችን ይሻገራል ። በራቸው የተከፈት ብቸኛ ትናንሽ ቤቶችን ጥሎ ይሄዳል ። አልፎ አልፎ አንዳንድ ብቸኛ ሴቶች በፍርሃት ከሚርዱ ባሪያዎቻቸው ጋር እዚህም እዚያም ጠብ ጠብ ብለዋል ። ወደ ወታደሮቹ መጥተው አበረታቷቸው ። ለተጠሙት በባሊ የጉድንድ ውሀ አመጡላቸው ። የቆሰሉትን በጨርቅ አሰሩላቸው ። የሞሉትንም በገዛ ቤተሰባቸው የመቃብር ቦታ ቀበሯቸው ። ፀሀያማው ሸለቆ በአበባቸው ነዋሪዎቹን ተራቁቷል ። መና ቀርቷል ። ያልታረመ ፣ ያልተከተከተው ሰብል በሰፊ እርሻ ማሳዎች ላይ የሰብሳቢ ያለህ እያለ ይጮሀል ።

ካልሁን ላይ የተጠቃው የጆንስተን ሠራዊት አፈግጥሞ አዴርስ ቪል ገባ ። አዴርስቪል ላይ ከባድ ውጊያ አካሂቦ ወደ ካስቪል ሸሸ ። ከዚያ ከካርተርስቪል በስተደቡብ ሄደ ። አሁን እንግዲህ ጠላት ከጓል

@OLDBOOKSPDF

ተን ሃምሳ አምስት ማይል ዘልቆ ጉብቷል ። ወጊያው ከተጧጧፈበት አስራ አምስት ማይል ርቀት ላይ በምትገኛው የኒው ሆፕ ቸርች አካባቢ ግራጫ ለባሾቹ ክአንግዲህ ንቅንቅ ላይሉ ወስነው እግራቸውን ተከሉ ። ታዲያ በኋላቸው የሚመጣው ሰማያዊ ለባሽ ተዋጊ ያለ ርህራሄ እየገሰገሰ ፣ እንደተናዳፊ እባብ እየተወረወረ ፣ ሲያስፈልግ እየተጠቀለለ ፣ ሲያስፈልግ ያለልክ እየተዘረጋጋ ፣ በነከሰበት ሁሉ መርዙን እየተፋ ፣ የቆሰለ አካሉን ወደኋላ እያጣራ ፣ ምንጊዜም ወደፊት እያገፋ ፣ ማጥቃቱን እየደጋገመ ቀጥሏል ። በኒው ሆፕ ቸርች አምባ ላይ እያንዳንዱ ያንኪ የመጨረሻውን አቅሙን ፣ የመጨረሻውን የደም ጠብታውን የሰገሰበት የአሥራ አንድ ቀናት ያላሰለሰ ጦርነት ተካሄደ ። ጀነራል እንደገና ተጠቅሶ ፣ እንደገና ተመትሶ ፣ እየመነመነ ያለ የውጊያ መስመሩን ጥቂት ማይል ራቅ አድርጎ አሸጋ ።

በኒው ሆፕ ቸርች አምባ የምቅት የኮንፌደሬሲው ወታደሮች ቁጥር ጭራሽ እየበረከተ መጣ ። ቁስለኛው በባቡር እየተራገፈ እትሳንታን እጥለቀለቃት ። ከተማዋ ጭንቅ ጥብብ አላት ። እንዲህ ያለ የቁስለኛ ጉርፍ ከጅክማውጋው ጦርነት በኋላ በጭራሽ አይታ አታውቅም ። ሆስፒታሎቹ ከአፍ እስከገደፉቸው ጢም ብለው በመሙላታቸው ቁስለኛው ግማሹ ቧልዶ መጋዘኖች ወለል ላይ ፣ ግማሹ የጥጥ መጋዘኖቹ ባዶ ከረጢቶች ሊይ ተኝቷል ። እያንዳንዱ ሆቴል ፣ እያንዳንዱ ሆስቴል ፣ እያንዳንዱ የግል መኖሪያ በቁስለኛ ተጨናንቋል ። በስታይተኛ ታጭቋል ። ወደዘር ፒቲ ሜላኒ አርግዝናዋ ከገፋ በኋላ እንደዚህ ያሉ ጉስቁላ ሰዎች ማየቷ ትርፉ የሰባት ወር ልጅ ነው እያሉ ቢነሚነጩም አገር የደረሰውን ያህል ቁስለኛ ተካፍለው ያስተናግዳሉ ። ሜላኒ ግን ቀሚሷን ከወገቧ በላይ ክፍ አድርጋ ቤቱን የወረሩትን ቁስለኞች ቦታ ቦታ ለማስያዝ ወደላይ ወደታች ትላለች ። የማያልቅና አታካች ምግብ ቅቀላ ፣ የማያልቅና አታካች የቁስለኛ አንገት ማቅናት ማገላበጥ ፣ ማናፈስ ፣ የማያልቅና አታካች ቁስል አጠባ ፣ ፋሻ ቅየራ ፣ የማያልቅና አታካች በበሽተኞች ማቃሰት የተሞላ እንቅልፍ አልባ ሌሊት ። በመጨረሻ ከተማዋ የምትችለውን ያህል ቁስለኛ ከተሞላች በኋላ ተርፎ የፈሰሰው ቁስለኛ ወደ ማከን እና ወደ አውጉስታ ተላከ ።

እርስ በእርስ የሚጋጩ የተዛቡ ሪፖርቶችን ይዘው በሚመጡት ቁስለኞችና የተደናገጡ ስደተኞች መቆሚያ መቀመጫ ያጣችው የአትላንታ ከተማ ፤ በምጥና በጣር እሪ ብላ ልትጮህ ምንም አልቀራት ። ያ ትንሽ የነበረ ጥቁር ጭሙና እየሰፋ እየተስፋፋና እየተንሰራፋ መጥቶ የሰማዩን አድማስ ሞልቶ ከውስጡ ከአውሎንፋስ ሳንባ የሚወጣ ቀዝቃዛ የሲቃይ አየር የሚተነፍስ መሰለ ። በሠራዊቱ አይበገሬነት ላይ እምነቱን ያልጣለ ማንም የለም ። በጀኔራሉ ላይ ግን ቢያንስ ሊቨሎቹ

@OLDBOOKSPDF

ሙሉ በሙሉ እምነታቸውን ነጥፏል ። ኒው ሆፕ ቸርች አምባ ከአትላንታ የምትርቀው ሰላሳ አምስት ማይል ብቻ ነው ። ጂኔራሉ በሦስት ሳምንት ጊዜ ውስጥ ስድሳ አምስት ማይል ወደ ኋላው ተንሏቋል ። እስከመጨረሻው ከማፈግፈግ ለምን ያንኪዎቹን ገትሮ አይይዝም ነበር?ጅል ነው ። እረ ክጅልም የባሰ ጅላጅል ነው ። ሸበቶ ያገኙ ጠም ያላቸው የከተማ ጠባቂዎችና የሚሊሽያ አባላት በሰላም አትላንታ ቁጭ ብለው ከሱ የተሻለ እንሠራ ነበር እያሉ የተታውሚቸውን ትክክል ነት ለማረጋገጥና ለማሳየት በየጠረጴዛ ልብሱ ላይ ካርታ እየነደፉ ያስረዳሉ ። ጂኔራሉ ኃይሉ እየተመናመነ ሲመጣና ማፈግፈጉ በጣም ሲበዛበት በመጨረሻ አገረ ገዥው ብራውን እነዚህን የከተማዋን የመ ጨረሻ ምልምሎች እንዲልክለት ተማጠነ ። የመንግሥቱን ሠራዊት ግን የተጨማሪው ኃይል መምጣት በጣም አረጋጋው ። ሴላው ቢቀር እኮ አገረ ገዥው ጄፍ ዴቪስ ተጨማሪ ኃይል ቢጠይቀው እምቢ ብሎ ነበር ። ታዲያ ጂኔራል ጆንስተን ሲጠይቀው ምን እሺ አሰኘውና

መዋጋት ማፈግፈግ ፣ መዋጋት ማፈግፈግ ። በሰባ አምስት ማይል ርቀት ውስጥ የኮንፌዴሬሲው መታዩር ከሞላ ጎደል በየቀኑ ለሐያ አምስት ቁናት ተዋጋ ። ኒው ሆፕ ቸርች አሁን ከግራጫ ለባሹ ኃላ ቀርቷል ። ኒው ሆፕ ቸርች አስገራሚ ሁለ ዕብደት የሞላበት ቅዝታ ነው ። ወበቅ ፣ አቧራ ፣ ረሀብ ፣ ዝለት ፣ በቀይ አፈር ላይ መደርደር ፣ በቀይ ጭቃ ላይ መጻለዮ ፣ ማፈግፈግ ፣ መመሸግ ፣ መዋጋት ፣ ደግሞ ማፈግፈግ ፣ ደግሞ መመሸግ ፣ ደግሞ መዋጋት ። ኒው ሆፕ ቸርች የሌሳ ሕይወት ቅዠት ነበር ። ቢግ ሻንቲም እንደዚያው ነው ። ዘረው ለመዋጋት ሲሞክሩ እነዚያ ዴያቢሎስ ያንኪዎች እሳት የሚተፉበት የቅዠት ሕይወት ። ሆኖም የውጊያው መሬት ሁሉ በሰማያዊ ለባሽ ያንኪ ፊሳ እስ ኪሞላ ድረስ ነበር ። ጸሩ በየጊዜው አዲስ ያንኪ ይፈለፈላል ። አዲስ ያንኪ ይመጣል ። ያ በደበብ ምሥራቅ በኩል በማማሽ ከብ የሚሠራ የያንኪዎች እኩይ የውጊያ መስመር የኮንፌዴሬሲውን ክልል ይከ ባል ። የባቡሩን ሐዲድ በመርዝ ክንዱ ያጥራል ፣ አትላንታን ያፋ ጥጣል ።

ከቢግ ሻንቲ የሚሸሹት የሳሉ እንቅልፍ የለሽ ተዋጊዎች ቁል ቁል መንገዱን ተከትለው ከትንሿ ማሪየታ ከተማ አጠገብ ወደሚገ ኘው ወደ ኬኔሳው ተራራ አፈገፈጉ ። እዚህ የውጊያ መስመራቸ ውን በአሥር ማይል ርቀት ከበባ አዘጋጁት ። በተራራው ጠርዝ ላይ የጠመንጃ ምሽግ ሠሩ ። በከፍታው ቦታ ላይ የመሳሪያ ክምችታቸውን አሰፈሩ ። መልዕክተኞችና ቁስለኞች የማዕናኛ ሪፖርታቸውን ለተደ ናገጠው የአትላንታ ሕዝብ አስረከቡ ። የኬኔሳው ኮረብታዎች የማይ ደፈሩ ናቸው ። በአካባቢያቸው ባሉት የፓይንና የሎስት ተራሮችም

@OLDBOOKSPDF

ላይ ተመሽጓል ። ያንቺም ወዳጆች ከእነሱ ጋር የተመገቡሙ ጀን ሰምት ንቅ እያደርጓቸውም ። በተራራዎቹ አናት ላይ የተጠመጡት መሳሪያ ዎች በረዥም ማይል ርቀት ላይ ያሉትን መንገዶች ጭምር ለመቆ ጣጠር የሚችሉ ናቸው ። እትዛንታ ጥቂት ተንፈስ አለች ። ነገር ግን . . .

ንጋር ግን የኬኔሳው ተራራ የሚገኘው የሃያ ሁለት ማይል ርቀት ላይ ነው ። ከኬኔሳው ተራራ የመጡ ቁስለኞች አትላንታ በገቡበት ቀን የወጋዘሮ ሜሪዌዘር ሰረገላ ወ/ሮ ፒቲፓት ቤት ደጃፍ ከንጋቱ አንድ ሰዓት ላይ ቆሞ ነበር ። ጥቁሩ እግሮች ሴቪ እስካርሌት ቁሱ ለብሳ እንድትመጣና ወይሆስፒታል እንዲሄዱ ነግሯት በመጣበቅ ላይ ነው ። ፋቲ ኤልሲንግና የቦኔል ሴት ልጆች በጠዋት በመቅሰቀሳ ቸው እያዛኑ ኋለኛው የሠረገላ መቆመጫ ላይ ጭምጠዋል ። የወይ ዘሮ ኤልሲንግ ቤት ሞግዚት ፣ ታጥቦ የተዘጋጀውን ፋሻ በዘምቢል ሙያ ላይ አስቀምጣ እሷ ብጥን ላይ ተቀምጣለች ። እስካርሌት ባለ ፊው ፊሊት ጉሀ እስኪቃጭና ድረስ የቸኮማ ጠባቂዎች ባዘጋጁት ፓርቲ ላይ ስትጸንበ ሰላደረች ያለፈቃዱ የደከሙ እማሮቷን በማድ እያነሳች ወጣች ። ፕሪሲ የእስካርሌትን አሮጌ የሆስፒታል የሥራ ልብስ ስታለ ብሳት ላለች እስካርሌት ዕጥ ብላ ነበር ።በዝሆታዋ ጭሰጥ ደክመኝ የሚሉትን ታታሪ ሠራተኛ ወ/ሮ ሚሪዌዘርን ፣ ቁስለኞችንና የደቡ ቡን ኮንፌዶሬሲ ተራዎችች ። ያረፈወን ጥብስ ብቆሱና የደረቀ ስኳር ሲንፎን ጥጥ ጥጥ እያደረገች በጥሞት ጠጣጣችና ደጅ የሚጠብቁትን ሴቶች ተጭለተለች ።

ይሄ የነርስነት ሥራ ክፉኛ ለፀጉን አሚታል ። እንገሽማቿታል ። ኤለን መደታራ መጥተሽ እንድታደኝ ብለኛለች ብላ ሀሬውት ለወ/ሮ ሚሪዌዘር ኮንግራቸዋለች ።ይሄ ግን ምንም አልረዛትም ። እሷ ደንዳና ሰውነታቸውን ሰሬ ሽርጥ ውስጥ ከትተው እጅጌያቸውን ጠቅልለው ወዲህ ወዲያ የሚሉ የነርሶች ኃላፊ ወ/ሮ ሚሪዌዘርን ትክ ብለው አይተዋት ሲያበቁ "እስካርሌት ሐሚልተን እንዲህ ያለ እጉል ነገር ሁለተኛ ከፍሽ ሲወጣ እንዳልሰማ ። እሬው ራሴ ለእናትሽ ደብዳቤ ፅፌ እዚህ ምን ያህል እንደምንፈልግሽ እነግራታለሁ ። መቼም እርግ ጠኛ ነኝ ችግራችን ንብቷት እዚሁ እንድትቀሪ ታደርግሻለች ። በይ አሁን ሽርጥሽን አድርጊና ወደዶክተር ሚድ ሩጪ ። ቁስለኞችን ለማ ከም የሚያግዘው ሰው ይፈልጋል ።"

"ወይኔ አምላኬ" አለች እስካርሌት በፍርሀት ። "ይሄው ነው ችግሩ እንግዲህ ። እማማ እዚህ ቆይ ትለኛለች ፣ የቁስሉ ሽታ ደማም ከእንግዲህ ልቋቋመው የምችለው አይደለም ፣ ምንው አሮጊት በሆን ኩና እንደዚህ እንደበግ ከምንዳ ሌሎችን ወጣቶች እንደልቤ ባዘዝ

@OLDBOOKSPDF

ኳቸው ፣ እንደበግ በነዳኋቸው ፣ እንዚህንም አሮጊት ድመኖች ጀሀነም ግቡ ባልኋቸው ።

አምን ሆስፒታል አንገሽግሾታል ። የሚከረፋው ሽታ ፣ ተባዩ ፣ ውጋት ቁርጥማቱ ፣ ያልታጠበው ሰውነት ቅርናት አንገፍግፉታል። የነርስነት ሥራ የተከበረ ሙያ ነው የሚባልበት ጊዜ እንኳን ገና ዱሮ አለፈል ። በዛ ላይ እንዚህ የአሁኖቹ በማረግፈጉ መርነት ላይ ቆስ ለው የሚመጡ ወንዶች እንደዱሮዎቹ ቃንጅዎች አይደሉም ። እሷ ንም የማፍቀር ምንም ዓይነት ክሽሎት አያሳዩም ። የሚናገሩትም ቢሆን "ውሊያው እንዴት ነው ?" ምን ደረሰ ! ሽማሌው ጀ አሁን ምን እያደረገ ነወሳ ጀግናውና ብልሁ ሽማግሌ ጆ" ከማለት አይዘለም። እሷ ይሄ ሽማግሌ ጆ የሚሉት ሰው ጀግንነቱም ሆነ ብልሀነቱ አይ ታያትም ። እሱ ያደረገው ነገር ቢኖር ያንኪዎቹን ወደጀርጂያ ሰማ ኔያ ስምት ማይል ዘልቀው እንዲገቡ ዕድል መስጠት ብቻ ነው ። የለም እዚህ ቁስለኞች ምንም ደስ የሚል ነገር የሰባቸውም ። በዛ ላይ አብዛኞቹ እየሞቱ ነው ። በፍጥነት እየተረፈረፉ ነው ። በፀጥታ ከሕ ይወት እየተሰናበቱ ነው ። የደማቸውን ሙሙረዝ ፣ የበድን ሰውነታ ቸውን ድኅዘቤ ፣ ታይፎይድን ፣ የብርድ በሽታውን የመቋሚያ አቅም ኖሯቸው አትሳኝታና ዶክተር ዘንድ ለመድረስ አይችሉም ። ሳይደርሱ ይሞታሉ ። ቢደርሱም እልቂው ነው እሚደርሱት ።

ቁስ ይሞታል ። ግንቦች በመስኩት እንደትድ ይገባሉ ። የንዚህ ትሳልት ጥቋቁር ግንበኞ ወረራ ፣ ሞትነት ያልሰበረውን የበሽተኞቹን ቅስም ያንኮታኮተውል ። እሰክርሴት የመዋር ሽታ ጠረንና የሰው ስቃይ በውስጧ ፍጭቱ በጠበጣት ። አዲስ ሽቶ የተጎሰጎሰበትን ቀሚ ሷን ላብ እያኮቀው በአጃዋ የቀለል ማጠቢያ ሳህን ይዛ ዶክተር ሚድን ትከተላለች ።

አቢት ያሰማይ ያለህ ሀኩክተሩ የሚጥቁን ሥጋ በቢላ ሲሰነጥ ቀው ሳያስታውክ ስሜትን መቆጣጠር መቻል እንዴት ከባድ ነው በሉ! የሰው እግር እንዶቨንኮራ አንዴ ከሚቆረጥበት የእጥራሲዮን ክፍል የሚመጣው የስቃይ ድምጽ ጀሮ ከሚጥለው በላይ አኮ ነወ! ፊታ ቸው ዋራ የመሰለውን በሀም የተገዳዱ ሰዎች ፣ ዶክተሩን በሞትና በሕይወት አፋፍ ሆነው የሚጠብቁትን ሰዎች ፣ ጀሮዋቸው በሰቆቃ ድምጽ የተሞላውን ሰዎች "አዝናለሁ የኔ ልጅ ይሄ እጅህ መቆረጥ ይኖርበታል ። አዎ አዝናለሁ ። ግን ተመልከት እነዚህ ቀያይ የተበከሉ ሥሮች ይታዩሀል? መቆረጥ ይኖርበታል ።" የሚለውን የዶክ ተሩን አስፈሪ መልስ የሚጠባበቁት ሰዎች ሲታዩ የሚሰማው በጣም አሳ ዛኝ ምንም ፈውስ የሌለው የሕመም ስሜት እንዴት አሰቃቂ ነው በል !

@OLDBOOKSPDF

የከሰሮፎርም ማደንዘዣ በጣም ከማኑሱ የተነሳ በጣም የተገዛውን ሰው እግር ወይም እጅ ሲቆርጡ ካልሆነ በስተቀር ለመጠቀም አልተቻለም። አፒየምማ በጣም ውድ ስለሆነ ሟቹን ከሕይወት ለመገላገል እንጂ ኗሪውን ከሥቃይ ለማላቀቅ መገልገልያ መሆኑ ቀር ቷል። ኪኒንና አዮዲን ድራሻቸው ጠፍቷል። አምን አስካርሌት የዚህ ሁሉ ነገር አማኝ በመሆኗ ልቧን አመጣት። ምነው እሷም እንደሜላኒ የእርግዝና ሰበብ አቅርባ መቀረት በቻለች እንዴት ግልግል ነበር። በዛሬው ጊዜ ከነርስ ሥራ ለመላቀቅ አንድ ምክንያት እርግዝና ብቻ ነው።

ምሳ ስዓት ሲደርስ ወ/ሮ ሚሪዌዘር ለአንድ ረሽጥ ማይም ከቀራረው የመጣ ቁስለኛ ደብዳቤ እየፎሰሰች ሳሉ አስካርሌት ሹልክ ብላ ከሆስፒታል ወጣች። አስካርሌት ከእንግዲህ ልትቋቋመው የማትችለው ነገር ሆኖባታል። መቼም ከላይ የተጫነባት ሰዳ እንጂ በፈቃዷ የምትሠራው ሥራ አይደለም። የስድስት ሰዓት ባበር ሲመጣ እስከ ማታ ድረስ የምትሠራውን ሥራ ይዘሳት እንደሚመጣ ታውቃለች — ምናልባትም ያለምጣበ የምትሰፋበት ሥራ ሊሆን ይችላል።

ሳንባዋ በሚፈቅድለት መጠን ቁና ቁና እየተነፈሰች ተቻኩላ በሀሳት ሕንጻዎች ማህል ሽቅብ ወደ ፒችትሪ ጐዳና ሄደች። አንድ ጥግ ይዛ እንደቆመች ቀጣላ ምን እንደምትሠራ ግራ ገባት። ወደ ወ/ሮ ፒቲ ቤትም እንዳትሄድ አጥራ ፡ወዴ ሆስፒታል ግን በቂራሽ ላትሄድ ወስና ተገትራ ቀረች ።እንዲህ ቅው ጠፍቷት እንደቆመች ሬት እየገሰገሰ መጣ ።

"ዛሬማ የቆሻሻ ለቃሚ ልጅ መስለሻል ።" ልብሷ ተጣጥፎ በላብ ሽቆና የውሀ ጭንጣቂ አረስርሶት ስታይ አስካርሌት በድንጋጤና በሲቃ ተሸማቃለች ። ለምንድነው ሁልጊዜ የሴቶች ልብስ ላይ አይኑን የሚጥለው ? ደሞ እንደዚህ መቆሸሿን በግልጽ እየተናገረ የሚባልገውስ ለምንድነው? ምን ይጠቅመዋል አሁን ?

"ምንም ነገር ካንተ መስማት አልፈልግም ። ይልቅስ ወርደህ ወደ ጋሪው አውጣኝና ሰው ወደማያየኝ ቦታ ውሰደኝ ። ከእግዲህ ወዲያ ባንገቴ ቢያንጠለጥሉኝ እንኳ ተመልሼ ወደ ሆስፒታል አልሄድም ። ወይ ጉድ እኔ ጠርነቱን አልጀመርኩ ፡ ምን በወጣኝ ነው እሰ ከዚህ እበሳ ጣጣዬን የማየው ?"

"እሪ በሞቴ! ታላቁን ዓላማችንን ልትከጂ ነው እንዴ ?"

"ማሰሮ ጀበናን ጥላሸት ትመስላለህ አሰው አሉ — አመድ በቆቴት ሰቀ !ይልቅስ አጋሪው ላይ አውጣኝ ። ወዴት ትሄድ እንደነበር ነውቅልህም ፤ ብቻ እኔን ውሰደኝ ።"

@OLDBOOKSPDF

ከጋረው ዱብ ሲል ስታየው ከመቅጽበት ወይ አንድ አይን ወይ አንድ እጅ ወይ አንድ እግር አጥቶ አካለ ስንኩል ያልሆነ ፡ በበ ሽታ ፊቱ አሸቦ ያልመሰለና ያልነጣ ያልገረጣ ፡ ዘወላ ያልመየበ ሙሉ ሰው በመሆኑ ደስስ አሳት ።

ከቶውንም ደህና በልቶ ጠጥቶ ጤናማ የሆነ ሰው ሆኖ ስላገኘ ችው በጣም አመረቃት ።አለባበሱም በጣም ማሩም ነው ። በገዙው ሳይጨማደዱ ጠበበው ሳይወጣጠሩና አላራምድ ሳይሉት ክትና ሱሪው ወጥ ሆነው በልኩ ተሰፍተዋል ። በሀ ላይ አዳዲስ ናቸው ፤ ተቀዳድ ደው እንደሌሎቹ ያደፈ ግላና ፀጉር እንደ ጉንዳን የወረረው እግር አያሳዩም ። በጭራሽ ስለሌለው አለም ኪፕ ያለው አይመስልም ። እቺን ታክል አይጨነትም ። በተለይ ኤሁን ሰው ሞንቀት ጉስቁልናና ሐሳብ በሚያናውዘው ሰዓት የእሱ ሀሳብ የልሽነት የሚገርም ነው ። ቡናማ ፊቱ ጥርት ብሎ ያበራል ። አፍ ከቀያይ ከናፍሩ ጋር እንደሌት ከንፈር ቅልብጭ ብሎ እንደተሠራ ሆኖ ስሜት የሞላበት ፈገግታ እያሳየ ፤ ብድግ አድርጉ ጋሪው ላይ አወጣ ት ።

እጮንዋ ጉብ ሲል የግቡጥ ሰውነቱ ጡንቻ በልኩ የተሠራ ልብ ሶቹን ሞላ አደረጋቸው ። እንደተለመደውም ባለግርማ ሞገሱ ሃያል ትክለ ሰውነቱ አንዳች ሰሚት ስረበባት ።ለፋሬ ትክሻዎቹ እንደኮ ርማ ሸኛ ተነፋፍተው ስታይ ይሄ መንዲስ አጭሙ ረበሻት ። በመጠ ኑም ፍርሃት ገባት ። ግላው ሲኔክት ክብድ ያለና እንደ ሞንቅላቱ ኃይለኛ ማፊት ሆነባት ። ይገርማል ። ቢያዩት ላይን የማይከብድ ፀጋን የተገናጸፈ ጉልበት ያለው ፡ዛል ብሎ ፀሐይ እንደሚሞቅ ነብርና ንቁ ነቱም ለማነቅ እንደተዘጋጀ አይነት ነው ።

"ምን አይነት ሸሩጭ ነሽ" አለ ፈረሱን መጭ እያለ ። "በየማ ታው ሴሊቱን ሙሉ ከወታደሮቹ ጋር ስትደንሺ ፡ የአበባና የማጊጫ ጥብጣብ ስጠታ ስትሰጪያቸውና ለዓላማው እንደምትሞቺ ስትምይ ስትገዙቺ ከርመሽ አሁን ጥቂት ቁስሎች የመጠንኑ ግዜ ፡ ትሸሺያቸ ዋለሽ ። አትረቢም ።"

"እንዴ ሌላ ወሬ የለህም ? ይልቅ ቶሎ ቶሎ ንዳ ደሞ አያት ሚረዊዘር ድንገት ከመደብሩ ሲመጣ ያየኝና ላሮጊቶቹ ማለቴ ለነ ወይዘሮ ሚሪዊዘር ይነግርብኛል ።"

ፈረሱን በአለንጋ እንዴ ሳጥ ሲያደርገው በላይ በፖወንድ ጉዳና አቋርጦ ከተማውን ማህል ለማህል የሚሰነጥቀውን የባቡር ሐዲድ ተሻግሮ ፈረጠጠ ።ቁስለኞች የጫነው ባቡር ገና መግባቱ በመሆኑ የባቡር ጣቢያው ሠራተኞች በጠራራው ፀሐይ ቁስለኞቹን ከባቡር ወደ አምቡላንሱና ወደ መሣሪያ መጫኛ በመኪናዎች በማ

@OLDBOOKSPDF

ጋባት ሥራ ይጥደፈደፋሉ ። እስክርስቶቱ በቃ ያቸው የመንፈሷን እረፍት ነስቷታል ፤ ብቻ ከዚህ ሁሉ አምልጣ የመሄድዋ እርይታ አመዝኖ አረጋጋት ።

"አፍ ያ አሮጌ ሆስፒታል እንደሰለቸኝና እንደታከትኝ ነገር" አሰኝ ቁሚስዋን እያስተካከለችና የፀጉር ጌጥ ማንጫዋን አጣጭቃ በታች አጥብቃ እያሠረች ። "በየቀኑ ቁስለኛ በቁስለኛ ላይ ይጨም ራል ። ይሄ ሁሉ የጂኤራል ጀንስትን ጥፋት ነው ። ያንኪዎቹን ዳል ቶን ላይ ጉትሮ ይዘዋቸው ቢሆን ኖሮ ይሄኔ . . ."

"አንቺ ደደብ ልጅ በሚገባ ተቆጭሚቸዋል ግን አይገባሽም ። ከዚያ ወዲያ ግትሬ ልያዝ ቢል ኖሮ ቬርማን ሁለት ቦታ ንጥሎ ሕይሉን እሠላት ላይ ይዘጥስስት ነበር ። እናም የባቡር መንገዱ በተነ ጠቀ ነበር ። ባቡር መንገዱ ደሞ ጀንስትን ስማጸን የሚጣጣር ለት ዋናው ኢላማ ነው ።

"እሣ" አለች እስክርስቶት ስለጦር ስትራቴጂ ምንም በማያውቅ ማይም እንደበት ። "ያም ሆኖ ይህ የራሱ ጥፋት ነው ። እንድ ንገር ማድ ረግ ነበረበት ። እንደሚመስለኝ እሱ ሰው መነሳት አለበት ። ከማሬ ግፈግ ለምን ጠንክር አያቆማቸውም ?"

"እንርም እንደለስቱ 'እንባቱ ይቆረጥ' ማለት ጀመርሽ ። ለምን የማይቻለውን ነገር አላረገም ብሳችሁ ይጠት ትላላችሁ ። ጳልቶን ላይ ድል ሲያደርግ ዒታ እየሱስ የእለም መድሀን ብላችሁት ነበር ። አሁን ሰድስት ሰምንት ባልሞላ ግዜ ውስጥ ኬኒሳ ተራራ ላይ ያልተ ሳካለት ሊመስላችሁ ደግሞ 'ይሁዳ ክሐዲወስ' አደረጋችሁት ። ይሄም ሆኖ አሁን ትንሽ ቆይቶ ያንኪዎቹን ሂያ ግይል እንኳ ቢያባ ርራቸው መልሳችሁ "እየቡስ" ትሉታላችሁ ።በዛ ላይ የኔ እምቦሳ ሼርማን የጀንስትንን እጥፍ ሐይል ሠራዊት ያለው ነው። ለኛ ለያንዳንዱ ቆራጥ ተዋጊ ሁለት ፣ ሁለት በነብስ ወከፍ መድቦ ቢሞቱበት እንኳ ግድ የለውም ።ጀንስትን ግን አንድ ሰው እንኳ ቢሞትበትና ቢያጣ ምትክ አያገኝለትም ። የእርዳታ ኃይል በጣም ይፈ ልጋል ፣ግን ምን አገኘ ፣የጂዎብራውን በኩሎ"ናቸው የቀሩት። እና ምን ትልኩለት !"

"ሚሲሺያዎቹም ሊሄዱ ነው እንዴ? የከተማ ጠባቂዎችም ሞምር ሊሄዱ ? አልሰማሁም እኮ ።አንተ በምን አወክ?"

"የሞምሞምታ ወሬ ይነፍሳል ። ዛሬ ጠዋት ከሚሲጅፒል በ ባው ባቡር ነው ወሬው የመጣው ።ሚሲሺያዎችና የከተማ ጠባቂዎች ጀንሰንን ለማገዝ ሊላኩ ነው ።የአገሪ ንዥው የብራውን የግል አጃቢዎ

@OLDBOOKSPDF

ችም ቍምር ዘመጨረሻ ባሩድ ሊያሸቱ ነው ።መቼም ብዙዎቹ ግራ—ይጋባሉ ። እንዲህ ይሆናል ብለው በጭራሽ አልጠረጠሩም። አገረ ገሹው እንደማይሄዱ ቃል ገብቶላቸው ነበር ። ያሀና አርገው ቀለደባቸው ።ሁኔ ገሹው ጂኖይቪሰን ተሟግቶ ቨርጂኒያ መታደሮቼን አልከም በማ ለቱ ቦምብ የማይበሳ ጥይት የማይዘልቀው ጋሻ መከታ ሆኗቸው ነበር ።የራሳችንን ማዛት እንጠብቃለን በዮች ነበሩ ።ጠርነቱ የገፋውን ያህል ቢገፉ እነሱ ማዛት ፣ እነሱ ሂጀፍ ይመጣል ብሎ ማን አስቦት! ውነትም አሀን ማዛታቸውን ላለማስደፈር መራወጥ ሊኖርባቸው ነዋ !።"

"ምን ያስትሃል ፣እንተ ጨላሻ አረመኔ እዚህ የቀሩትን አረጋ ውያንና በከተማ ጠባቂነት የተመጠሩትን ልጆች አታስብም !ትንሹ ፊል ሚድ ፣ ትልቁ ኢያት ሚሪዌዘርና አጐት ሐንሪ ሠሚልተን ሁሉ ሊሄዱ እኮ ነው ማለት ነው ።"

"እኔ ስለትናንሾቹ ልጆችና ስለእንጋፋዎቹ የሚጨነኩ ጦርነት አባቶች አልተናገርኩም ። እኔ የማወራው እንደ ዊሊ ግሪናን ስለመስ ለት ቆንጆ የደምብ ልብስ ስለሚያማርጡትና ጐራዴ ስለሚያወና ጭኑት ጀግኖች ነው..."

"እንተ ራስህስ!"

"አይ የኔ ቆንጆ ፣ እኔን እንትፍ ታህል አይጐዳኝም ! እኔ የደ ምብ ልብስ ሐልስብስ ፣ ጐራዴ አሳወናጭጭምና የኮንፌዴሬሲውም ዕጣ ከኔ ገዕ ጋር አ ጥናም ።በዚህ ላይ በከተማ ጠባቂዎቹም ውስጥ ሆነ በሌላ ከማናቸውም ጋር ሞቼ አልገኝም ። ዌስትፓያንት ውስጥ የተማርኩት በጭ የወታደራዊ ስልት ትምህርት ስላለኝ ቀሪ ውን ሕይወቴን ለማቆየት እችላለሁ ። ለማንኛውም ሽማግሌው ጀ እንዲቀናው ምኞ ነው ። ጂኔራል ሊ እንደሆን ያንኪዎቹ ቨርጂኒያ ውስጥ ፋታ ስላልሰጡት እርዳታ ሊልክለት አይችልም ።ስለዚህ ለጀ ንስተን ሊደርሱለት የሚችሉት የጀርጂያ ወታደሮች ብቻ ናቸው ። በጣም ታላቅ የጦር ስልት አዋቂ ሰው በመሆኑ ሌላም እርዳታ ባገኘ ተገቢው ነበር ።ሁልጊዜ ያንኪዎች ከመያዛቸው በፊት ቦታዎ ችን በቁጥጥር ሥር ማድረግ ያውቅበታል ።ነገር ግን የባቡር መንገ ዱን ላለማስነካት ሲል ወደኋላ ያፈገፍጋል ።ደሞ ምን አለ በይኝ ከተ ራራው ካባረሩትና ወደዚህ አካባቢ ወደሚዳው ገፍተው ከመጡ ያለ ጥርጥር ያርዱታል ።"

"እዚህ አካባቢ ሊመጡ!" ብላ ጮኸች እስካርሌት ። "ያንኪዎች ይሄን ያህል ገፍተው ሊመጡ እንደማይችሉ አጥተኸው ነው እንዴ ።"

@OLDBOOKSPDF

"ምን ነካሽ ፥ ኬኔሳው ከዚያ ሃያ ሁለት ሚዶል ብቻ እኮ ነው የሚርቀው . . . እና"

"ሬት ወደ መንገዱ ተመልከት፤ ባጅብ የሚመጣ ሰው ፣ ወታደሮች አደደሉም ። ምንድን ይሆን? አጡ ባሪያዎች ናቸው"

ሁዩ አቢራ እየተንቧለለ ጸጥና መስሏል ። ከደመናው ማህል የብዙ ሰዎች ኩቴና በመጥ የሚቆጠሩ አሞሮዎችው ትርርዋቸው እስኪነቃ እየጮሁ የሚዘምሩት ሀሳብ የለሽ ድምጽ ይሰማል ። ሬት ጋሪውን ጥግ አስይዞ አቆመ ። አስካርሌት በጉጉት ታስቲውላሰች ። ትከሻ ትከሻቸው ላይ አነፋና ይጣ ያዘው ጥርር ፊታው ላይ ሳባቸውን እያን ጠፈጠፉ በአንድ መኮንንና የመር መሐንዲስ ልብስ በለበሱ ሰዎች ቡድን እየተንጹ የሚመጡ አሞሮዎች ናቸው ።

"እረ በሶላሰ ምንድነ ጥቃት"አለች አንደገና ።

ከዚያ አይኖቿ ፊት ለፊት ገናዝመሩ ከሚመጡት ማህል አንዱ ጠቋሪ ድነ ላይ አረፉ ። ቁመተ ለድስት ጫማ ተኩል ይሆናል ። አሳር የሚያክል ወጠምሻና እንደሪነኝ የጠቆረ ሰው ነው ። አንድታይለኛ አውሬ ባለማነስ ነጭ ጥርሱን ሕያበራ "ሙሲያውያን ተንዙ" የሚለውን መዝሙር እየዘመረ መንጋጠጎ ይመራል ።

ከታራው ክበ ከትልቁ ሳም በስተቀር አንደዚህ ያለ ግዙፍና ጉልህ ድምጽ ያለው አሞሮ በምድር ላይ የለም ። ትልቁ ሳም የጂራ ልድ ቁኝ እጅ ሆኖ በአርሻው ቦታ ምስለኔ በሌለበት ባሁኑ ጊዜ ከሸ ቤት ይሀን ያህል ርቆ መጥቶ ምን ያረጋል ?

ዘመቀመሪጫዋ በግማሽ መነሳት ብድግ ብላ ቀረብ በማለት ሰማ የት ስትሞክር ግዙፉ ሰው ኢየትና አሲን በማስታወሱ ተደሰቶ ያባል ጨት የመሰለው ጠቋራ ፊቱ ሁለት ላይ ተከፈለና ፈገግ አለ ። ቆም አለና ያማውን ልሬት ጥሎ ወደሷ እያመራ አጠገቡ ያሉትን ነግሮ ምንም እየተጣራ "እረ በየሀው ! እትዮ እስካርሌት እኮ ናት ። ሌሊሻ ! አንቺ እጋስል ! ፕሮፌት ! ውድ አመቤቱ እስካርሌት እኾትላችሁ ።"

በሰምቹ ማህል ግራ መጋባት ተፈጠረ ። እየተተራመስ የሚሄደው ሕዝብ ቆም ብሎ በጥርጣሬ ፈገግ አለ ። ትልቁ ሳም ሌሎች ሶስት ግዙፍ አሞሮዎች እየተከተሉት ወደ እስካርሌት ሰረገላ ሲመጣ አንድ የሚጣደፍና የሚጮህ መኮንን ወደሱ እየመጣ ፦—

"ተመለስና ስልፍ ግቡ እናንተ ! ነግሬያችኋለሁ ተመለሱ እሰበ ለዚያ እኔ የማደርገውን . . . ወይኔ ! ወ/ሮ እስካርሌት ነሽ እንዴ ? እንደ ምን አደርሽ አመቤት ? አንተም ሰውዬ ተመለስ ። እዚህ አመጽ ልት

@OLDBOOKSPDF

ፈጥሩና ስሙን አልታዘዝ እንዲል ልታነሳሱ ነው እንዴ ! እግዚሀር በሚያውቀው እነዚህ ጐረምሶች ከጥቅ ጅምር እንደ በጠበጉኝ አሉ ።''

''ውይ ሻምበል ራንጻል አባከሀ አትስደባቸው! የኛው ልጆች እኮ ናቸው ። ይሄ ካቦቸን ትልቁ ሳም ነው ። አሊያም ፡ አፖስልም ፡ ፕሮፌትም የታራ ልጆች ናቸው ። ያናግሩኝ እንጂ ፡ እንዴት ናችሁ ልጆች ?''

እስካርለት ሁሉንም ጨበጠቻቸው ። ትንሿ ቀይ እጅዋ በትልቅ ጥቁር መዳፍ ውስጥ ተሞጠች ። አራቱም እፀኝ በማግኘታቸው ፈነ ደቁ ። አብረዋቸው ሲሚቀመጡት ፡ደጅዋቸው እንዴት ያለች ቆንጆ እመቤት እንዳለቻቸው እያሳዩ ተኩራሩ ።

''ከታራ ይዟን ያህል ርቃችሁ መጣችሁ እዚህ ምን ትፈጥራ ሳችሁ ልጆች ? መቼም ጠፍታችሁ እንደሆነ አምናለሁ ። ተቆጣጣሪ ዎቹ እንደሚያሳጧችሁ አታውቁም ?''

ከለደስቱኛ አስተያየቷ ተጥከሰከሱ ።

''ጠፍታችሁ ?'' አለና መለሰ ትልቁ ሳም ። '' የሰም እመቤቱ እኛስ ጠፍተን አይደለም ። እኛን አይጎዳኩም ፡ ምክንያቱም ታራ ውስጥ ኃይለኛ ሠራተኛ ነበርን ።'' ትሜሚው ጥርሶቹ ብልጭ አሉ '' በተሰይ እኔን ያስጠሩኝ ጐበዝ ዘራኝ ስለሆንኩኝ ነው ። አምን እመቤቱ አባባ ናፈንክ ኪኔዲ ናቸው መጥተው የወሰዱን ።''

''ለምን ትልቁ ሳም ?''

''እንዴ እመቤቱ አልሰማሽም እንዴ ! ያንኪዎቹ ሲመጡ ጨዋ ዎች ነፍሶች የሚያበቁበትን የምሽግ ጉድጓድ እንድንቆፍር ተጠር ተን እኮ ነው ።''

ሻምበል ራንጻልና ሠረገላው ላይ ያሉት ሰዎች የመሣሪያ ማጥ መጂ ጉድጓዶችን ይዛ ኔግሮ እንዴት እንደሚገነቡ ሲሰሙ ፡ ተጠቃ ቅሰው ሳቁ ።

''ጌታዬ ጀራልድ እንኳን እሱን ከወሰዳችሁብኝ ሥራዬን እንዴት ብቻዬን ለመሥራት እችላለሁ ብለው ነበር ። እመቤቱ ኤለን ግን 'ውሰደው አቶ ኪኔዲ ። ትልቁን ሳም እኛ ከምንፈልገው የበለጠ ኮንፌ ዶሬሺው ይፈልገዋል' አሉ። እናም አንድ ዶላር ሰጡኝና ጨዋዎቹ ነፍሶች ያዘዙህን እንድትሠራ ብለው አስጠነቀቁኝ ። ይኸው እዚህ መጥተናል ።''

@OLDBOOKSPDF

"ይሄ ምን ማለት ነው ሻምበል ራንዳል ?"

"ነገሩስ ቀላል ነው ። ጀኔራሉ ጦር ግንባር ያሉትን ሰዎች አንዳች ወሬም ለማንቀሳቀስ አልችልም ስላለ የአትላንታን ምሽጐች ረዘም ባለ ማይል ርቀት ላይ ተክለን ለመጠበቅ አስበናል ። በዚህ ምክንያት ከገጠሩ አካባቢ ጠንከር ጠንከር ያሉትን ወጠምሻ ባሮች አመጣ ናቸው ።"

"ነገር ግን ..."

እንዲት ቀዝቃዛ የፍርሀት ስሜት አስካርሌት ጡት ሥር መንፈራፈር ጀመረች ። ረዘም ባለ ርቀት ላይ የሚሠራ የመሣሪያ መጥመጃ ቦታ ! ለምን ተጨማሪ አስፈለጋቸው ? ባለፈው ዓመት ውስጥ ከኩ ማይሉ እምበርት አንድ ማይል ርቀት ላይ በአትላንታ ዙሪያ የመሣ ሪያ ማጥመጃ ምሽጐች በተርታ ሲሠሩ ከረሙ ። ከተማይቱን እንደመ ቀኑት የሚያስታጥቁ ጉድጓዶችን ከማይል ማይል ሳያስተጓጉሉ ቆፈሩ — ተክክ ! አሁን ደግሞ ተጨማሪ የማጥመጃ ጉድጓዶች !

"ግን አስካሁን ከመሸማነው በላይ ተጨማሪ ምሽግ ለምን ያስ ፈልገናል ? ያሉትን እንደገና የምንፈልጋቸው ለምንድነው ? እርግጠኛ ነኝ ጀኔራል ማናቸውንም የማያሰልፍ ..."

"ያሁኖቹ ምሽጐቻችን ከኩጣዋ አንድ ማይል ብቻ የሚርቁ ናቸው" አለ ሻምበል ራንዳል አጠር አድርጐ ። "ያ ደግሞ ምኞታችን ሆነ ዋስትናን ለመጠበቅ ምንም አስተማማኝ አይደለም ። እነዚህ አሁን የሚቆፈሩት ከዱሮው ራቅ ተደርገው ነው ። አየሽ አንድ ሌላ ማፈግ ፈግ ከተደረገ ሰዎቻችን አትላንታ መምጣታቸው የማይቀር ነው ።"

የመጨረሻ ንግግሩ በፍርሀት ዓይኗን አንጻስፈጠጣት ሲያይ ወዲያው ፀፀት ገባው ።

"ግን በእርግጥ ሌላ ማፈግፈግ አይኖርም ።" አለና በፍጥነት ጨመረበት ። "የኬኔሳው ተራራ አቅራቢያው የማይበገር ምሽግ ነው ። የተራራዎቹ አናትና ጠርዝ ሁሉ ተጠምዶባቸዋል ። ስለዚህ መንገዱን ይቆጣጠራሉ ።ያንኪዎች ምናልባት ዘልቀው ሊያልፉ አይችሉም ይሆ ናል ።"

ሆኖም አስካርሌት ሻምበል ራንዳል የሬትን ጥቅል አስተያየት ሲያይ ማቀርቀሩን ልብ ብላ ስጋት ገብቷታል ። የሬትን አስተያየት አስታወሰች፡—"ያንኪዎቹ ገፍተው ከተራራው አስወርደው ስጥ ያለው ሜዳ ውስጥ ካስገቡት ያኔ ቢታው ያርዱታል ።"

"ዉ...ይ ሻምበል ፡ባንተ ሀሳብ "

@OLDBOOKSPDF

"እንዴ በቁራሽ ! ምን ሲደረግ ! ለእንዲት ደቂቃ እንኳ ሀሳብ አይግባሽ ። ሽማግሌው ጥንቃቄ በማድረግ ያምናል ። ተጨማሪ ምሽግ የምንቆፍርበትም ብቸኛ ምክንያት አሉው ነው ። አሁን ግን እኔ መሄድ አለብኝ ። እንቺን ማነጋገሬ በጣም ደስስ ብሎኛል ። በሉ እመቤታችሁን ይህና ሁኚ በሷትና እንሂድ ልጆች ።"

"ይህና ሁኑ ልጆች ።ከታመማችሁ ወይም ጉዳት ከደረሰባችሁ፣ ብቻ ማንኛውም ችግር ሲገጥማችሁ ሳነጋግኝ ።የምኖረው በፒችትሪ ጐዳና ወረድ ብሎ ነው ።ጐዳናውን ይዛችሁ ስትሄዱ ከሞላ ጐደል የከተማዋ የመጨረሻው ቤት ውስጥ ነው የምኖረው ። ቆይ እንዴ ይዩ " ቦርሳዋን ደባበሰች ።" ውይ ጊታዩ ምንም ሳንቲም የለኝ ። ሬት እስቲ ጥቂት ሳንቲሞች ስጠኝ ። እንካ ትልቁ ሳም ፡ ለእነሱም ለልጆቹም ትምባሆ ግዛበት ። ጥሩ ልጅ ሁን ። ሻምበል ራንዳል የሚያገሀን በትክክል ፈጽም ።"

የተዘበራረቀው የሰልፍ መስመር እንደገና ተስተካከለ ። መንቀሳቀስ ሲጀምሩ የቀዩ አዲራ ዳመና እንደገና ብድግ ብድግ ይል ጀመር ። ትልቁ ሳምም ዘፈኑን ጀመረ ፡

"ሙሲውያን ተንቡ ! ምድረ ግብፅን አስክትረግጡ
ከፈርኦን የማሩ ቀንበር ሕዝቦቹን ነፃ ይውጡ !"

"ሬት ሻምበል ራንዳል እኮ ልክ ሌሎች ወንዶች ፡ ሲኖች እውነቱን ከክሙ ተገለፍልፈው ይወድቃሉ ፡ የሚሉትን ስለሚያምን እኔንም ጥሸኝ ! ሞሽረል አይደል ? ውይ ሬት ፡ እደጋ ባይኖር ኖሮ ምሽግ ይቆፍሩ ነበር እንዴ ? ሠራዊቱ ያዘን ያህል የሰው እጥረት ደርሶበት ነው እንዴ የባሪያዎች ጉልበት ያስፈለገው ?"

ሬት ፈረሱን መጭ አለው ።

"ሠራዊቱማ የሰው ያለህ እያለ ነው ። ያ ባይሆን ኖሮ የከተማ ጠባቂዎች ወደ ጦር ግንባር ይጠሩ ነበር እንዴ ? ስለምሽጉም ላልሺው መቼም ምሽጉ በጣም የሚጠቅሙት በወረራ ጊዜ ነው ። ጂኔራል የመጨረሻ መቆሚያውን እዚህ ለማድረግ እየተዘጋጀ ነው ።"

"ወረራ ! በል ፈረስን አዙረው ወንድሜ ፡ አሁኑኑ በቀጥታ ወደ ታራ እሂዳለሁ ።"

"ምኑ አስጨንቋሽ ነው ?"

"ወረራው ! በእግዚሀር ወረራው ነዋ ! ስለወረራዎች በደንብ ሰምቻለሁ፡ አባባ ነግሮኛል ። እሱ በአንድ ነው በሁለት ወይም እንኳ ብቻ ቁጥሩን የወረራ ዘመን ኖሯል እና አባባ ሲነግረኝ"

@OLDBOOKSPDF

"የምን ወረራ?" ስል እየጠየቅሽኝ ነው ?"

"ከሮምዌል አየርላንዶችን ሲይዝ ድሮጌዳ ላይ ያካሄደው ወረራ። ያኔ እነአባባ ምንም የሚበሉት አልነበራቸውም። ቃራቡ፥ በረሀብ ጥርስ እየታኘኩ በየመንገዱ እየተገለለፈለፉ እየወደቁ አለቁ። ቢቸግራቸው ያገሩ ድመትና አይጥ አንድ አልቀራቸውም —ቅርጥፍ አደረጉ። ሴላው ቀርቶ እንደበረሮ ኳንኩዬና የመሳሰሉትን ሳይቀር በልተው ሕይወታቸውን እንዳተረፉ አባባ ነግሮኛል። እንደውም እርስ በርስም ይበላሉ ነበር አለኝ። እጆቻውን ከመስጠታቸው በፊት ወገን ወገኑን ይበላ ነበር ብሎኛል። ብቻ ያንን እንኳ ልመን አልመን ቸግሮኝ ነበር። ከሮምዌል ከተማይቱን መሉ ስመሉ ሲይዝ ሉኖቹ በሙሉ... ወረራ! ውይ የጭንቅ አማላጅዋ!"

"አንቺ መቼም በሕይወቱ ካየኋቸው ሁሉ የመጨረሻ ጥሬ ደን ቆሮ ነሽ። የድሮጌዳ ወረራ በሺ ስድስት መቶ ምናምን ግድም የነበረ ነው። አባትሽ ኤቶ ጄራልድ ደግሞ ያኔ ከነመፈጠሩም እንኳ። በዛ ላይ ደግሞ ሼርማን ማለት ከሮምዌል ማለት አይደለም።"

"ውይ ይሄኛው ግን ይብሳል ! እንደሚሉትማ ..."

"አየርላንዳዊያን ይበሉ ነበር ስላልሺው ምግብ ነገርም ቢሆን በቅርበቱ ሞቴል ውስጥ ከሚያቀርቡት ምግብ ይልቅ ጥሩ መረቅ ያላት አይጥ ቢቀርብልኝ እኔ ራሴ ግጥም አድርጌ እበላለሁ። እንደሚመስለኝ ኮመልሺ ወደ ሪችመንድ መሄድ አለብኝ። ግንዘቡ ካለኝ እዚያ ቆንጆ ምግብ አላቸው።" ሚዩኖቹ ፊቷ ላይ የሚታየውን ስጋት ያሽሚጥጣሉ።

ፍርሀቷን በማሳናቷ ብስጭት ብላ ጮሀ ተናገረችው፡—

"እስካሁን ድረስም እዚህ ለምን እንደቆየህ እንጂልህ ! ሁልጊዜ የምታስበው ስለምኞት ብቻ ነው። ስለመብላት እና ስለመሳሰሉት ነገሮች"

"በበኩሌ ከመብላትና ከመሳሰሉት ነገሮች የተሻለ ጊዜ ማሳለፊያ አላውቅም" አለ። "ለምን እስካሁን ቆየህ ላልሺው ግን ስለተመዘበሩ ከተሞች፥ ስለተያዙ ከተሞችና ስለወረራ የሚያወሱ በቂ መጻሕፍት እንብበይለሁ። ባይኔ ያየሁት ወረራ ግን አንድም የለም። ስለዚህ እዚሁ ቆይቼ ባይ ይሀና ነው። ተዋጊና ተፋላሚ ስላልሆንኩ የምገዳበት ነገር አይኖርም። በዛ ላይ ልምዱን ማግኘት በጣም አፈልጋለሁ። እስካርሌት አዲስ ልምድ ሲያጋጥምሽ በፍጹም አትለፈው። እንዳያመልጥሽ። አዳዲስ ልምዶች አእምሮን ያዳብራሉ።"

@OLDBOOKSPDF

"የኔ አእምሮ የጻበረ ነው—ይበቃኛል ።"

"ምናልባት ስለሱ በደንብ ታውቂ ይሆናል ። ግን ልንግርሽ የሚገባኝ ፤ ያ ሐሞት የለሽ መሆኑን ነው ። ምናልባት እዚህ የምቆይ በት ሌላው ምክንያት ወረራው ሲመጣ አንቺን ለማዳን ሊሆን ይች ላል ። ሴት ልጅ መከራ ውስጥ ባለችበት ሰዓት አድኜ አላውትም ። ያም ሌላው አዲስ ልምድ ይሆናል ።"

እያግባባና እያጫወታት መሆኑን ብታውቅም ከቃላቱ ሥር ኮስ ተር ያለ ቁምነገር እንዳለበት ይሰማታል ። ሙንቅላቷን ሽቅብ ከግራ ወደቀኝ ወርውራ ፀጉሯን አዘናፈለችና፡—

"እኔ አንተ እንድታድነኝ አልሻም ። ራሴን በራሴ ልጠብቅ ስለ ምችል ስለመልካም አስተሳሰብህ አመሰግናለሁ ።"

"እንደዚህስ አትበይ እስካርሌት ፤ ብትሪልኒ አሰቢበት እንደ ፣ ግና ። ግን በምንም ዓይነት ሰውንድ ልጅ እንደዚህ ማለት የለብሽም። ፈጽሞ ። የያንኪ ሴቶች ችግር ይሄ ነው ። ስለራሴ እኔ አውቃለሁ ፣ ራሴን በራሴ አጠበቃለሁ ያንተን እርዳታ አልፈልግም ፣ አመሰግና ለሁ ባይሉ ዋሮ እንዴት ማራኪ ይሆኑ ነበር ። በአጠቃላይ ሰታ ያ ችው ዕውነቱን ይናገራሉ ፣ እግዚርም ይረዳቸዋል ። ስለዚህም ወንዶቹ፣ ሴቶቹ እራሳቸውን እንዲጠብቁ ሰራሳቸው እንዲጠነቀቁ ያደርጓ ቸዋል ።"

"እንዴት እንደዚህ ያለ ጋጠወጥ ንግግር ትናገረኛለህ ።" አለች ቀዝቀዝ ብላ፣ ከያንኒ ሴት ጋር ከመመሳሰል የበለጠ ስድብ የሰም በሚል ዕምነት ። "ስለወረራ የነገርከኝ ውሸት መሆኑን አምናለሁ ። ያንተ ዎች በጭራሽ አትሳኃታ እንደማይነቡ አሳምረህ ታውቃለህ ።"

"እውነት እውነት አልሻለሁ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ እዚህ ታግኛቸዋለሽ ። ብትፈልጊ እንወራረድ ። ከረታሽኝ አንድ ካርቶን ከረሚላ አመጣልሻለሁ ።" ጥቂቱር ዓይኖቹ ከንፈሮቿ ላይ ተንሸራሸሩ ። "አንቺ ከተረታሽ አንዴ ትሰሚኛለሽ ።"

ለመጨረሻ አጭር ትጽበት የያንኪዎቹን መረራ የመጥራት ስሜት ከፉኛ ጨመደዳት ። ግን "መሳም" የሚለውን ቃል ከአፉ ሰ,ያወጣ ገና ሁሉንም ረሳችው ። ከወታደር የጦር ስልት ይልቅ የምታውቀውና የሚያስደስታት ነገር ይህ በመሆኑ በስንት መከራ ፈገግ ከማለት ተቆ ጠበች ። ያኔ አረንጓዴውን የፀጉር ጌጥ ከሰጣት ወዲህ ሬት ማናቸው ም ያፈቀረ ሰው እንደሚያደርገው አድርጉ ምልከት ሰጥቷት አደ ውቅም ። አስከዛሬ በግል ወሬያቸው ማህል እንኳ ወደዚህ አርዕስት ነገር ለማጋደል ስትሞክር እሱ ላመል እንኳ ወሬውን አይቀርሳትም

@OLDBOOKSPDF

ነበር ። ብሬ ግን አፍ አውጥቶ ሳትጠይቀው ስለመሳሳም ይናገር ጀመር ።

"እኔ ለዚህ ዓይነቱ የግል ጭውውት ጉብ የልኝም ።" አለች ቅዝቃዝ ብሳ መሸበርዋን ሳታስነኩ ። "ደም ለዛውም አንተን ከምስጭ አሳማ ብስም ይሻለኛል ።"

"የሚሉምሽን አንቺ ታውቂያለሽ ። በዛ ሳይ አየርላንዳዊያኖች አሳማ ከመውደዳቸው የተነሳ አልጋቸው ሥር እንደሚያኖሩዋቸው ሰምቻለሁ ። ግን እውነቱን እንናገር ከጉባስ በጣም ነው መሳም ያማረሽ ። ስሀተትሽ አዛ ሳይ ነው ። ወዳጂሽ ሁሉ በጣም ያከብሩሽ ነበር ፣ ስምን እንደሚያከብሩሽም አማዚሀር ይወቅ ። ወይም በጣም ስለሚፈሩሽ የፈለግሽውን አያደርጉልሽም ። ዘሀሁ ምክንያት ሰረጅም ጊዜ የማትችይውን እኾል ብለሽ ጥሎ በረታህብሽ ። እና በድንብ መሳም የሚችል ሰው ደህና አድርጉ ሊስምሽ ይገባል"

ጨዋታቸው እሰ ወደምትፈልገው አቅጣጫ አልሄደ አሳት ። ደም ሁልግዜ እኮ ነው ። ከሱ ጋር ስናሀን በፍፁም እንዝነት ማድረግ አይሆንላትም ። ሁሌ የምትረታበት ግሞኟ ነው ። መሳም እኾላ ለሁ ብለህ ራህን እጩ ማድረግህ ይሆን ?" አለችው በማንጓጠጥ ንዴቷን እንደምንም ተቆጣጥራ ።

"እንዴታ ! ከተጠቀቅኩ ግን ይደርስብኛል ፣ ስው ማሩም አር ግህ ትስግለህ ይለኛል" አለ በቸልታ ።

"እ" አለች በደም—ግባድ እየተከራከረች "ያውም እንት" ብላ አይኖቿ ድንግርግር አለባቸውና እቆመች ። እሱ ፈገግ ብሏል ። በሃቁር የአይኑ ጥልቀት ውስጥ እንዷት የብርሃን ጮራ እንደ ወላፈን ብልጭ አለች—ሳንድ አፍታ ።

"አርግጥ የፀጉር ጌጣን የሰጠሁሽ አለት ያሳየሁሽን የመሳም ምልክት ለምን አዳር እንዳላደረስክት ሳይገርምሽ አልቀረም ። "

"እኔ በጭራሽ..."

"አስካርሉት ጥሩ ልጅ አይደለሽም ። በጣም አዝናለሁ ። አየሽ ጥሩ ሴቶች ሁሉ ወንዶች አልሰም ሲሏቸው ወይም ሊስመጥቸው ካልሞከሩ ይገርማቸዋል ። እንዲህ እንዲያደርጉ አይፈልጉም ፤ ሲያደርጉ ደግሞ እንደተሰደቡ ሁሉ ይከሳቸዋል ። ያም ሆነ ይህ ወንዶቹ ስመ ሳም እንዲሞክሩ ይመኛሉ ። ይህንን ልብ በይ የኔ ቆንጆ ። አንድ ቀን እስምሻለሁ ። ትወጂዋለሽ እርግጠኛ ነኝ ። ግን አሁን አይደለም ፤ ስለ ዚህ ትግስቱን ይስጥሽ እያልኩ ፤ እንድትታገሺ አለምንሻለሁ ።"

@OLDBOOKSPDF

እንደሚቀልድባቸው ታውቃለች። እንደሁልጊዜው ፈዙ አብድ አረጋት። እርግጥ የተናገረው ብዙው እጅ አውነት ነው። ለማንኛውም ነውረኛ አድርጐታል። ከአንግዲህ የአስተዳደግ ጉድለቱን፣ ዋልጌነቱን አይታለችና እንዲሸ ብሎ ከዕ. ጉዳይ ቢፈልግ፣ ሲደፈራትና ነጻነት ሲያ ገኝባት ቢሞክር ታሳየዋለች።

"ባክህ ፈታድህ ከሆነ ፈረሱን አሠርልኝ፣ ካፕቴን በትለር። ወደ ሆስፒታል መሄድ አፈልጋለሁ።"

"አውነት አሰኘሽ? የኔ ቅዱስ መላክ? አውን ከኔ ንግግር ተባ ይና ቁስል መርጠሽ ነው? ደህና። ታሳፍን አላማችንን ከግልገል በጭራሽ እጂን አልሰበሰብም" ፈረሱን አዞረና ተመልሰው ወደ ሩይቭ ፓይንት ገሰና ጉዞ ጀመሩ።

"ለምን መስለሽ ያኔ ልንፋቡት ያልፈለከውት" አለ ንግግሩን አብ ቅቷል ብሳ መገመቷን ልቧ አያወቀ። "ልንፋቡት ያልፈለከውት ትንሽ አስክታድጊ ድረስ ነው። ትንሽ እደጊ ብቤ ነው። አየሽ አሁን አን ቺን መሳም ይሄን ያህልም አያበደስተኝምና ደስታዬን ሰስቼ ነው። ሕጻናትን መሳም በፍጹም አያረክሽም።

እንደማሾፍ ብሎ የጐሪጥ ሲያያት እንዳንድ ነገር በትተኑ ፍስ ደረቷ ከፍ ዝቅ ሲል ተመለከተ።

"እግረ መንገዴንም" አለና ለለለስ ብሎ ቀጠለ። "ትመኝው የነበረው የአሽሌይ ዊክስ ትዝታ ከልብሽ አስኪከስም ነው የምጠብቀው።"

ግና የአሽሌይን ስም ሲያነሳ ድንገተኛ ሕመም በሥራ አካላ ትዋ ተናኘ። ትኩስ እንባ ቅንድቦቿን ተጫጫናት። እስኪከስም? የአ ሽሌይ ትዝታ እንዴት ከልቧ ይከሰማል? እንዴት ተደርጐ? ለምን ከሞተ ከሺህ አመታት ወዲያ አይሆንም? አሽሌይ ቆስሎ ሩቅ አገር ወዳለ የያንኪ አስር ቤት ተግዘ ያለ ብርድ ልብስ ተኝቶ እጁን ያዝ ደገፍ የምታደርግለት ፍቅረኛ እጦት ሳትኖር ሲሰቃይ አሰበች ውና ይሄ አዘሀ ጐኗ ቁጭ ያለ ደህና የተመገበ፣ ደህና የለበሰ ሰው ዝግ ዘለግ ካለው ድምፁ ሥር እንዲሚያላግጥበት አስባ ንዴትና እልህ ተናነቃት።

በጣም በመናደዷ የንግግር ታላት አልታዘዝ ብለዋት ለጥቂት ጊዜ በዝምታ ተጓዙ።

"አሁን ስለአንቺና ስለአሽሌይ እያንዳንዷን ጉዳይ ከሥር ከመሠ ረቷ በተግባር ተረድቻለሁ።" አለ ሬት ያቋረጠውን ንግግር ቀጥሎ

@OLDBOOKSPDF

"በአሥራ ሁለቱ ወንጌል መጽሐፍ ውስጥ አስቀያሚ ትርጓሜሽን ነገሩን ማስተዋል ጀመርኩ ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ዓይኖቼን ከፍቼ በማየት ብቻ ብዙ ነገሮችን ለቀምኩ ። ምን ዓይነት ነገሮች አትጂኝም ነ ለዚህ ምላሹ—አንቺ አሁንም ትምህርት ቤት ያለሽ ልጃነ ረድ የሚኖራትን ዓይነት ፍቅር ለሱ አንደምትለማሺና እሱም የተከ በረ ተፈጥሮው የሚፈቅድለትን ያህል ምላሹን አንደሚሰጥሽ መረ ጻቴ ነው ። ወ/ሮ ሚለኒም ብትሆን ምንም የምታውቀው ነገር የለም ። አንቺና እኔን በሚመለከት በጣም ማሩም ዘዴ ተጠቅመሽ ጥሩ አድ ርገሽ አታለሻታል ። የማወቅ ፍላጐቴን ከሚቀሰቅስብኝ አንድ ነገር በስተቀር ስላንቺና ለለአሽሌይ አያንዳንዱን ዝርዝር አውቃለሁ—ከአ ንድ ነገር በስተቀር። ይህ ላውቀው የምፈልገው ነገር፡— "ለመሆኑ የተከ በረው አሽሌይ አንቺን በመሳም ሀያው ነፍሱን ተፈታትኗት ይሆን፣ የሚለው ነው"

የዝምታ በረዶና የተደፋ አንባት ብቻ ሆነ መልሷ ።

"እሀ ፣ በቃ ስምሻል ማለት ነው ። እንደምገምተው የሳመሽ ፈቃድ ተቀብሎ በመጣበት ጊዜ ነው ። አሁን ታዲያ ምናልባት ሞኙ ይሆ ናል ብለሽ ስለሰጋሽ ፤ ልሱ ያዘጋጀሽውን ፍቅር የሐዘን ማቅ አልብ ሰሽ ለገዛ ልብሽ እየመሰከሽው ነው ። ግን እርግጠኛ ነኝ ይህኛውንም ሀዘን ትወጪውና ትረቪጥልሽ ። እናም እንዴት እንደሳመሽ እያሰብሽ የምታመነዠጊውን ትዝታ ስትጥይውና የሱን መሰም ስትረቪው አሌ ደግሞ ..."

አሳት ለብሳ አሳት ጐርሳ ወደሱ ዞረች ።

"እንቱ ጀሀነም ግባ !" አለች ፍርጥም ብላ ፤ እንደኩል በጠሩ ዓይኖቿ ውስጥ ንዴት እየተንቀለቀለ ። "ደሞ በጐማዎቹ ላይ ዘልዬ ከመውረዴ በፊት አውርደኝ ከዚህ ሠረገላ ፤ ሁለተኛ ካንተ ጋር አን ዴት ቃል አልነጋገርም ። "

ሠረገላውን አቁሞ ወርዶ ደግፎ ከማውረዱ በፊት እመሬት ዱብ አለች ። ሰትዘል የጐማው ፈረፋንጎ ቀሚሷን ስለያዘባት ፋይቭ ፓይ ንት ላይ የተሰበሰበው መንገደኛ የውስጥ ልብስና የሱሪ ትርኢት ቦማ ብልጭ ሲል አየ ። ሬት ጎንበስ ብሎ ቀሚሷን በፍጥነት አስለቀ ቀላት ። እስካርሌት አንድ ቃል ሳትናገር ፤ ወደኋላ እንኳ ዞራ ሳትመለከት እየተመናቀረች ሄደች ። ሬትም በስሱ እየሳቀ ሠረገላው ላይ ወጣ ።

@OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ 18

ጦርነቱ ከተቀሰቀሰ ጀምሮ አትላንታ ገና አሁን የወጊያ ድምጽ ሰማች ። ማለዳ ገናከተማይቱ ዓይኗን ሳትገልጽና የነዋሪዎቿን ድምጽ ሳትሰማ በፊት እንደበጋ መብረቅ ድክም ያለ ከሩቅ የሚመጣ የኪን ተኪ ተራራ የመድፍ ጩኸት ይቀሰቅሳታል ። አንዳንዴ ቀትር ላይ ከሚተራመሰው የተሽከርካሪ ድምጽ ከፍ ብሎ ወድፍ የሚሰማበት ጊዜም አለ ። ሰዉ ሃያ ሁለት ማይል ርቀት ላይ ያሉትን ያንኪዎችእን ደሌሉ ለመቁጠር የመድፉንም ጩኸት ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎ በመ ሰቅ ፣ በመጫወት ፣ የዕለት ሥራ በመሥራት እንዳልሰማ ለመቁጠር ሞከሮ ነበር ። ጆሮ ግን ወዴ ኪንተኪ አቅጣጫ ታምቡሩን እየወጠረ እያንዳንዷን ድምጽ ከመስማት አልታቀበ አለ ። ከተማይቱ በሌላ ሥራ የተጠመደች ትምስል እንኗ ፡ እጅዋ ሌላንዣር ያንሳ ይጣል እንኗ ጆሮዋ ማዳመጡን አላቋረጠም ። ይዳምጣል ። ያዳምጣል ። ያዳምጣል ። ልቧም እንደድንገት ፍንጥር ኢያለ በተን ሙቶ ጊዜ ይበረግጋል ። ያሁኑ መድፍ ጎላ ያለ ይሆን ፣ ወይስ ሰዉ ጮላ ያለ ኢያረገው ነው ? ጄኔራል ጆንስተን አሁን ቀጥ ያረጋቸው ይሆን ፣ ልክ ያገባቸው ይሆን ፣ ያደ ርገዋል ?

ከአየሩ ላይ ቁርጠት ይንሳፈፋል ። በየቀኑ ማፈግፈጉ በጨመረ ቁጥር እያተጨነቁና በምጥ እየተወጠሩ የነበሩት ደም ሥሮች የሚ በጠሱበት ሰዓት ደርሷል ። ማንም ሰው ስለፍርሃት አይናገርም ። ይህ ርዕስ እንደነውር ተቆጥሯል ። ሆኖም በጭንቅ የተወጠሩት ደም ሥሮች ሊረግቡ የሚችሉት በጄኔራሉ ላይ በሚወርደው ትችት ብቻ ሆኗል ። የሕዝቡ ስሜት ከፍተኛ ትኩሳት ላይ ፡ ከፍተኛ ንዳድ ላይ ተጥዷል ። ሼርማን አትላንታ በር ላይ ደርሷል ። ከእንግዲህ ሌላ ማፈግፈግ ከተደረገ የኮንፌዴሬሲው ሠራዊት ወዴ ከተማይቱ መግ ባት ሊኖርበት ነው ።

የማያፈገፍግ ጄኔራል ስሙን ! ጠላትን ገትሮ ይዞ ፡ ቆሞ እሚ ጋፈጥ ፣ ቆሞ እሚዋጋ ሰው ስሙን !

"የጀ ብራውን አምበሶች" በመባል የሚታወቀው የመንግሥት ሚሊሺያና የከተማ ጠባቂዎች ፡ ከሩቅ የመድፍ ጩኸት ጆሮዋቸው ላይ እያስገመገመባቸው ከአትላንታ ወጥተው ድልድዮችንና ትናንሽ

@OLDBOOKSPDF

ወንዝ መቸጋገሪያ[illegible] ከመጠለያ ከሚሰሩት ጀርባ ወጣለው ወደ ቻታሁቸ ወንዝ ሄደዋል። ጭጋግና ጸሙና የሠረሰው ቀን ነበር። ሆኖም በፋይቸ ፖይንትስ መግድ አሠርጠው በማሪየታ ሠንሳይ በኩል ወጥተው ሲዘምቱ ዝናብ መጣል ጀመረ። የከተማይቱ ሕዝብ በሙሉ አንሰሱን ለመሸኘት ንቅሎ ሲወጣ እነሱ በጥሻ ትሪ ጫፍና ጸር ጸር ባሉት መታዘሮች የእንጨት ጣራ ሥር ተጠልለው ደስተኛ ቤመምስል ይጣጣራሉ።

አስካርሌትና ሚይሊል ሜሪዊዘር ስምንን ስመሸኘት ከሠስ በጥታል ፈቃድ ወስደዋል። ፈቃድ የወሰዱበት ምክንያት አትት ሄነሪ ሕሚልተንና እያት ሚሪዊዘር ከተማ ጠባቂዎች ውስጥ ስለንበሩ ሲሠን: ሁለቱ ሴቶች ከወ/ሮ ሚድ ጋር ከተሰበሰበው ሕዝብ ማህል ተጨ ናንቀው በእግር ጣታቸው ቆመው እየተንጠራሩ በተሻለ ሁኔታ ለማየት ይፍጨረጨራሉ። አበካርሌት ምንም እንኳ ድጥን ደበብ ስለ ጠርንት ደማ ደማ ወሬና ሙሂያውም የተሰክ እንዲሠን የሚኖረውን ፍላንት ዓይነት በአዕምሮ ውስጥ የሚኑር ቢሆን፣ አሁን የሚዘም ቱስን ጉስቱል ስምኞ ከታይ ስሜታ ከመጋል ይልቅ ቀዝቀዛታል። በአርግጥ እንደነዚህ ያሉ ሽማግሌዎችና ትናንሽ ልጆች ፊንጂ መር ማሪ መሃንዲስ ተብለው መመደባቸው ጦርነቱ በጣም አሳሳቢ ደረጃ ላይ መድረሱን ያሳያል። እወጎት ለመናገር ወጣቶችና ጠንከር ጠንከር ያሉ ደማቅ የሚቢቪያ ልብስ የለበሱና የባርሜጣቸው ዘርፍ የሚደግበብ ሰዎች በዚህ መስመር ላይ ተሰማርተዋል። ንግር ግን ብዙ ሽማግሌዎችና ልጅ እማሮች ስሰራባቸው እነሱን ማየት ልቧን ከሀዘንና በፍርሃት ሞላው። ከአባቷ በዕድሜ የሚበልጡ ግራጫ ፂም ያበቀሉ ሽማግሌዎች በዚያ ዶፍ ዝናብ ውስጥ ከታምቡሮቹ ቅኝት ጋር የግዳቸውን ለመራመድ ሲፍረመረሙ ይታያሉ። አያት ሚሪዊዘር የወ/ሮ ሜሪዊዘርን የአንባት ፎጣ ከዝናቡ ለመከላከል ትከ ሻው ላይ አጣፍተው ከመጀመሪያዎቹ ዘማቾች ጋር ሰልፍ ገብተው ሲሄዱ ወደ ሴቶቹ ዘወር ብለው ሰላምታ ሰጡ። እነሱም መሃረቦቻ ቸውን እያውለበለቡ የደህና ሰንብት ጨኸታቸውን አሰሚቸው። ሜይ ቤል ግን የአስካርሌትን ከንድ ጭምድድ አድርጋ ይዛ እንዲህ ስትል አንሾካሾከች፡— "ወይኔ እጂህ ምስኪን ሽማግሌ! ዝናቡ፣ ንፋስ ቀላ ቅሎ ደህና አድርጎ ቢዘንብ እኮ አንድያውን የሚጨርሳቸው ደካማ ሽማግሌ ናቸው! የሪህ በሽታቸውም ..."

አጎት ሄነሪ ሃሚልተን የረሻሙን ጥቁር ኮቱን ኮሌታ ወደ ጆሮው አቁሞና ሁለት በሚከሲኮ ጦርነት ላይ ያገለገሉ ሽጉጦች ቀበ ቶው ላይ ታጥቆ በሹራብ ከር የተሠራ ትንሽ ቦርሳ በእጁ አንጠ ልጥፏል። ከጐኑ የአጎት ሄነሪ ያህል ዕድሜ ያላቸው ጥቁር አሽከሩ

@OLDBOOKSPDF

ጥንጥላቸውን ለሁለት እከፍላለሁ ብለዋል። ወጣቶቹ ልጆችም ከታላቆቻቸው ጎን ትከሻ ለትከሻ ተለካክተው ተሰልፈዋል። ዕድሜው ከአሥራ ስድስት ዓመት በላይ የሚሆን አንድም ወጣት የለባቸውም። አብዛኞዎቹ ከሠራዊቱ ለመቀላቀል ከት/ቤት ጠፍተው የመጡ ናቸው። እዚህም እዚያም የሚሊተሪ አካዳሚ የካዴት ዩኒፎርም ለብሰው ተስማሽተዋል። ጠባቃ ባርኔጣዎቻቸው ላይ ያሉት ጥቁር ዶሮ ላባዎች በዝናብ ረጥበዋል። በደረታቸው ላይ አሜሪም የሚሄዱት ንጭ ጨርቆችም ረስርሰዋል። ፊል ሚድም ከነሱ ማህል አለ። የሞት ወንድሙን ኮሬዴና ሽጉጥ ታጥቆ ባርሚጣውን ወደ አንድ ወገን ጋደድ አድርጎ በሰፒል አስይዙታል። ወ/ሮ ሚድ ፈገግ ለማ ለት ችላለች። እስኪያልፍ ድረስ አጅዋን ሰታውለበልብለት ቆይታ እስካርሌት ትከሻ ላይ ከኋላ በኩል ሞንቅለቷን አንጋስለች—ሞንካሬዋ ድንገት ጥሏት እንደሄደ ሁሉ።

ኮንፌዴሬሲው ጠመንጃም ሆነ ሌላ የጦር መሣሪያ በለሌለው ሰዎቹ ምንም የታጠቁት ነገር የለም። እነዚህ ሰዎች የሞቱና የሣማረኩ ያንኪዎችን ትጥቅ ወስደን እንታጠቃለን የሚል ተስፋ ይዘው ባዶ እጃቸውን የሚዘምቱ ናቸው። አብዛኞቻቸው በቦት ጫማዎቻቸው ውስጥ ትላልቅ የእድን ሰንጢዎችን ይዘዋል። በእጆቻቸውም "የጆ ብራውን ሰንሽዎች" በመባል የሚታወቁት ሹል የብረት ጫፍ ያላቸው ረዣዥም ዘንጎችን ይዘዋል። የታዴሱት ያረጁ ናስማሰር ጠመንጃዎችን አንግበዋል። ዝናሮቻቸውም በጥይት ጢም ያሉ ናቸው።

ጆንስቦን በማፈግፈግ ላይ እያለ ቪ ሰዎች ግድም አለቁበት። ስለዚህ አሥር ቪህ አዲስ ምልምል ወታደሮች ያስፈልጉታል። የቀላ ኩሰት እነዚህ ናቸው ማለት ነው! አለች እስካርሌት በሃሣቧ።

የመድፈኛው ጦር በተሰበሰበው ተመልካች ሕዝብ ማህል አቋርጠ ጭቃውን እየፈጨና እያፈነጣጠቀ ሲግተለተል አንድ በበቅሎ የሚሄድ ኔግሮ ከመድፉ ጐን ጐን ሲሄድ የእስካርሌትን ዓይን ሳበው። ወጣትና የተቀመጠበትን ኩርቻ የመሰለ ቁሰም ያለው ኮስታራ ፊት አለው። እስካርሌት ስታየው ግና፡—"መሴ እኩ ነው! የአሽሌይ ሙሴ! ደሞ እዚህ ምን ይፈጥራል?" ብላ ሮሽች። በትርምስምሱ ሕዝብ ማህል እንደምንም እየተጋፋች የፈረሰኞ ማሠሪያ ምሰሶው ድረስ መጥታ "ሙሴ! አቁም!" አለችው።

ልጁ ሲያያት በደስታ ተሞልቶ ልጓሙን ሳበና ከበቅሎው መውረድ ጀመረ። አንድ ከኋላ የሚመጣ ያላበው ዓምላ አለታ "ስማ እዚያው እበቅሎህ ላይ አርፈህ ቁጭ በል። አለዚያ ተኩሼ እቀልብሃለሁ! ወደ ተራራው በግዙ መድረስ አለብን።" አለው።

@OLDBOOKSPDF

ሙሴ በጥርጣሬ አንዱ ሃምሣ አለቃውን ኦንዴ እስካርሌትን አየ። እሷ ጭቃወን እየረጨች ከሚያልፉት ተሽከረካሪዎች ጐማ ጋር ትጋፍታ የአርካቡን ገመድ ያዘች።

"ውይ አንድ ጊዜ ቆይ ሃምሣ አለቃ! ሙሴ እዚያው ሁን! እት ሙረድ። ደሞ እዚህ ምን ትሠራለህ?"

"ወደ ጦርነቱ ተመልሼ መሄዴ ነው እመቤቴ። እንዳስፈቀዱ ጊዜ ከጌታ አሽሌይ ጋር ሳይሆን ከጌታቹ ጆን ዊልክ ጋር መገመቴ ነው።

"ከጆን ዊክስ ኮ" እስካርሌት በድን ሆና ቀረች። አዎ ጆን ዊክስ ወደ ሰባ ዓመት ገደማ ይሆነዋል። "የት አለ አሁን?"

"እሷላ ካለው ከመጨረሻ መድፍ ጋር ናሻው፡ እመቤቴ አሰላር ሌት። መጻያ ናቸው ኮ"

"ይቅርታ የኔ እህት። ሂድ አንተ!" ፬ አለቃው ተቆጣ፡

እስካርሌት ባለ ጠመንጃዎቹ ሁሉ እያለሷት እየሄዱ ሳሉ እሷ ቁር ጭሚቷ ድረስ ጭቃ ውስጥ ሰምጣ ቆማለች። ው.... አይሆንም! አለች በሃሣቧ። ሊሆን አይችልም። በጣም አደጅቷል እቱ። ደሞ አሽሌይ ጦር ነት እንደማይወድ ሁሉ አሱም አይወድም! ወድኋላ ጥይት እርምጃ ዎች ተራምዳ ወዶፈረስ ሣመሪያው ምሰሶ እያመራች እያንዳንዱን የሚያልፍ ፊት ታስተውሰ ጎሳች። የመጨረሻው መድፍ ጐማውን እያስቃሰት ሲመጣ ጆን ዊክስን አየችው። የሳቲን ሙሽራ ልብስ እን ደለበሰች ሴት በመጣምሩ ተሸምንሙና፡ በዝግታ ጭቃወን የምትራ መድ ትንሽ ቀይ በቅሎ ላይ ተሳድሞ። ያን ብርማ በዝናብ የራሰ ጸጉ ሩን እንጉቱ ላይ ከምሮ። ተጭን ሰውነቱን ቅጥ እድርጐና ዘና ብሎ ይሄዳል። አሃ... ይቺ በቅሎ እኮ ኔሊ ናት! የወ/ሮ ታርሌተን ኔሊ! ቢት ሬስ ታርሌተን እንደውድ ሀብት የምትጨነቅላት ኔሊ!

ጆን ዊክስ እስካርሌት ጭቃ ውስጥ ቆማ ሲያያት በደስታ ፈገግ እያለ ልጓሙን ሳብ ረገብ አደረገና ወርዶ ወደሷ መጣ።

"እስካርሌት አንኳላለሁ ብዬ ተስፋ አድርጊ ነበር። ያንቺ ሰዎች መዓት መልዕክት ጭነው ሊልኩኝ ነበር። ነገር ግን ምንም ጊዜ አል ነበረኝም። እዚህ የጣነው ዛሬ ጠዋት ነበር። እንደምታዩው ይኸው እያጣደፉና እያከሰሱ አስወጡን።

"ውይ አቶ ጆን ዊክስ" ብላ ጮኸች እስካርሌት በተስፋ መቁ ረጥ አጽን በእጅዋ ይዛ። "እትሂድ መሄድ ያለብህ ሉምንድን ነው?"

"አሃ! ሰላ አርጅቷል ብለሽ ነው የምታስቢው!" አለ ፈገግ ብሎ ፈገግታው በአረጀ ፊት ላይ የሚታይ የአሽሌይ ፈገግታ ነው። "ምናልባት

@OLDBOOKSPDF

ለእማር ጉዞ አረጅ እንደ ሆን አንጂ ስግልቢያና ለተኩሰ እንኳ ገና ቆፍ ጣና ነኝ ። ወ/ሮ ታርሌተን በደግነቷ ኔሊን ስለሰጠችኝ እንደምታይኝ ኮርቼ ተቀምጫለሁ ። መቼም ኔሊ ምንም እንደማትሆንብኝ ተሰፋ አለኝ ። አሰበለዚያ ወደቤቴ ተመልሼ የወ/ሮ ታርሌተንን ዓይን አላ ይም ። ከፈረሶቿ ሁሉ የተረፈችላት ኔሊ ብቻ ናት ።" አሁን ፍርሃቷን ሁሉ ያስረሳትን ሳቁን እየሳቀ ነው ። "እናትና አባትሽ እንዲሁም አህቶችሽ የከበረ ፍቅራቸውን ልከውልሻል ። አባትሽ ዛሬ ከእኛ ጋር ሊመጣ ምንም አልቀረውም ነበር !"

"ውይ ያባባስ ይቅር ! ምን በወጣው እናቴ !" ብላ ሙሽሯ አስካርሌት በመሸበር ። "አባባስ አይሆንም ። ወደ ጦርነቱ አይሄድም ፣ አይደል ?"

"እሱ ሊሄድ አስቦ ነበር ። በእርግጥ በማይታጠፍ ጉልበቱ ብዙ ርቀት በእግሩ ለመጓዝ ባይችልም በፈረስ ከኛ ጋር ለመሄድ ወስኖ ነበር ። እናትሽም በፈረስ መኬድ ያለበት ብዙ ወጣ ገባ መንገድ ስላለ የግመሹን አጥር ሊዘል የሚችል ከሆነ እንደልብ ሊገሰግስ ይችላልና ቢሄድ ግድ የለኝም ስትለው አባትሽ ይሄኔ ማን ያቅተዋል በሚል የፉከራ ስሜት ተነስቶ ነበር ። ነገር ግን— ታምኚልሽ አስካርሌት ? ፈረሱ አጥሩ ጋ ሲደርስ ቀጥ አለና ቆመ ፣ አባትሽም ወደፊት ተስፈንጥሮ ከፈረሱ አልፎ ወደቀ ፣ የሚገርመው አንገቱ እንኳ አለመቁመጡ ነው ። እንደምታውቂው በጣም ግትር ሰው ነው ። ተነስቶ እንደገና ሞከረው ። መቼስ ምን ይደረግ አስካርሌት ሶስት ጊዜ ሞክሮ ሶስቴም ወደቀ ። ወ/ሮ አለንና ፖርክ ደግፈው ወደ አልጋው ወሰዱት ። ስለነገሩ ደጋግሞ ያወራ ነበር ። እናትሽ እንዳሚረቱኝ በትና እሱ ግን ሊዘለው ይችል እንደነበር ዛት ። ለእንዲህ ያለ ቅልጥ ፍናን ለሚጠይቅ አትልግሎት እንደሱ ያለሰው አይሆንም ። ይሄ ልታፍ ሪበት የሚገባ ነገር አይደለም ። ስሳውስ አንድ ሰው እቤት ቀርቶ በደ ጀንነት ለሠራዊቱ እህል ሙዝራትና ምርቱን መላክ አለበት አይደል ።"

አስካርሌት የመገላገል ፈጣን ስሜት እንጂ ፍርሃት የሚባል አያ ታትም ።

"ኢንዲያና ሐኒ ከበርር ቢተሰብ ጋር እንዲተመጡ ወደ ማዘን ልኪያቸውሞለሁ ። ጄራልድ እንግዲህ ታሪንም የ "አሥራ ሁለቱ ዋርክምኞ" መንደርንም ይቆጣጠራል በይ እንግዲህ ልሂድ የኔ ልጅ ። ውብ ጉንጭሽን ልሳምና እንለያይ ።"

አስካርሌት ከንፈሯን ቀና አደረገች ። ጉሮሮዋን እንደሳማ ያለ ስሜት አንቋታል ። ጆን ዊከስን በጣም ትወደዋለች ። ከረሃም ጊዜ በፊት ፣ ከዕለታት አንድ ቀን ፣ የልጁ ሚስት ልትሆን ትመኝ ነበር ።

@OLDBOOKSPDF

"ይሄንን ለፒቲፓት ነው የሳምኩሽ ። እሷን ሳሚልኝ ። ይሄንን ደግሞ ለሚላኒ ነው ። መስደሽ ለሷም ስጪልኝ ።" አለ ፡ ሁለት ጊዜ በስሱ ሳም ሳም አድርጎ ። "ለመሆኑ ሚላኒ እንዴት ናት ?"

"ደህና ናት"

"እሰይ" ! አለ ። ሩቅ ሳሪጫ ዓይኖቹ እሷን ይዩ እንጂ በሱዋ ውስጥ እሷን አልፈው የአሽሌይ ዓይኖች ያዩ ነበረው ሌላ ዓለም ያስተውላሉ ። የመጀመሪያውን የልጅ ልጅ ባይ አወድ ነበር ። ደህና ሁኚ ፡ የኔ ልጅ ።"

ጆን ዊክስ ባርሚጣውን በእጁ ይዞ ፡ ብርማ ፀጉሩን ለዝናብ እንዳጋለጠ ኬሊን ኮልኩሎ ፈረጠጠ ። አስካርሌት በመጨረሻ የተና ገራቸው ቃላት ራሷን ከመምታታቸው በፊት ሚይቤልና ወ/ሮ ሚድ ጋ ደረሰች ። ከዚያም በተፈጠረባት ሥይጣናዊ ሽብር ምክንያት ራሷን በራሷ በመፈታተን ለመሸሸይ ብሞክር ይሻላል አለች ። አሽሌይ እንደ ነገራት ሁሉ አባትዬውም ስለሞት ነገራት ። ይሄኔ አሽሌይ . . . የሰም ማንም ቢሆን ስለሞት ማውሳት የለበትም ! ሶስቱ ሴቶች በዝናብ ወደ ሆስፒታል በመመለስ ላይ እንዳሉ አስካርሌት መጸለይ ጀመረች ፡ "እሱንም አደራ አምላኬ ፡ አትግደለው!! እሱንና አሽሌይን ጠብቅ ልኝ ! !"

ከዳልተን እስከ ኬኔላው ተራራ የተደረገው ማፈግፈግ ከማንቦት መጀመሪያ እስከ ሰኔ አጋማሽ ፈጀ ። ሞቃቶቹ የማንቦት ዝናባማ ቀናት ከለፉ በኋላ ሼርማን የኮንፌዴሬሲውን ወታደሮች ከሚላጣው ስለታማ የተራራው ጠርዝ ማባረር ስለአቃታው ፡ ተስፋ እንደገና አንገቱን ቀና ማድረግ ፡ እንደገና ማቆጥቆጥ ጀመረ ። አያንዳንዱ ሰው በማም ተደስቶ ስለጄኔራል ጆንስተን ደግ ደግ ነገር ማውራት ጀምሯል ። እርጥቦቹ የሰኔ ቀናት በጣም እርጥበት ወዳለው ሐምሌ ሲሸጋገሩ የኮንፌዴሬሲው ወታደሮች መሣሪያ በተጠመደባቸው ኮረብታዎች ዙሪያ የሞት የሽረት ውጊያ አካሂደው ሼርማንን ባለበት ገተሩት ። አትላንታ አንዳች የደስታ ስሜት አናወጣት ። ተስፋ እንደሻምፓኝ በአትላንታውያን ራስ ላይ ወጣ ። ዘራፍ ! እሰየው ! እልል ! ተባለ ። ግትረን ያገናቸው ተባለ ። የፓርቲና የዳንስ መረርሽኝ ነባ ። ከውጊያ የመጡ ሰዎች ወደከተማ ማታ ማታ ከገቡ በቡድን በቡድን እራት ይጋበዛሉ ። ዳንስ ይዘጋጅላቸዋል ። ሴቶቹ ከወንዶቹ በአሥር እጅ ስለሚበልጡ ወንዶቹን እየተሻሙ ይደንሳሉ ።

አትላንታ ሰው በሰው ሆናለች ። ዘመድ ጠያቂዎች ፡ ስደተኞች ፡ በየሆስፒታሉ የተኙ ቁስለኞች ቤተሰቦች ፡ በተራራው ላይ እየተዋጉ ያሉ ወታደሮች ሚስቶችና እናቶች አጨናንቀዋት መተንፈሻ ቦታ

@OLDBOOKSPDF

እጥቃለች ። ከየክ/ሀገሩ የመጡ ቆንጆ ቆንጆ ሴቶችና ሞዛዚቶች ከዘመቻ የተራ ከአሥራ ስድስት ዓመት በታች የሆኑ መጣቶችና ከሰልሳ ዓመት በላይ የሆኑ አረጋውያን በሙሉ ከተማዋ ውስጥ ፈለሰዋል ። ወረ ፕሬታት እንዚህን የመፈረሻዎቹን ቆንጆ ቆንጆ ሴቶች መምጣት አልወደዱትም ። ምክንያቱም እነሱ የሚመጡት ባል ፍለጋ ነው የሚል ሪምኒት ስላላቸው ነው ። የነዚህ ሴቶች ተማባር የፈጠረባቸው ሀፍረት ያዜ ዓለም ወያኔት እየዘከጠ ነው አሸማቷቸዋል ። እስከርሌትም ነገሩን ጠልታዋለች ። የአሥራ ስድስት ዓመት ዕድሜ ያሉቸው ወጣቶች ፡ ትምቡኬ ጉንጮቻውና ያማረ ፊገ ማታቸው ፡ ሁለት ሶስቱ ተገልብጠው የተለበሱ ጭሚሰኖቻውንና የተጠጋነ ሚማምኖቻውን ለሰሚያለረሳ ፡ ባል ለማግኘት የሚያደርጉት ውድድርና ሽሚያ እስከርሌትን ጉስበዚህም አሳስጨንቃታል ። የዓ ልብሶች ሁድሜ ሰፊት በትሰር ፡ በለፈው የጅልባ ጉዞ ካመጣሉት ጨርቆች የተሰሩ ስለሆኑ ከሁሉም የተሻሉና የበለጡ ሠቦች ናቸው ። ጸሩ ግን እዓ. አሥራ ዘጠነኛ ዓመታን የያዘች በመሆኗና ወንዶቹ ደሞ ትንንሾቹን ሴቶች ማሳደድ ስለማመርጡ ቅሬታ ተሰምቷታል ።

ባለልጅና የመሳ ሚሰት መሆኗ ለውድድሩ የሚያበቃኝን የመበት ማማያ አጓድሎብኛል ፡ ብሳ አሰበች ። ደግሉ በዚህ በደስታ የተሞላ ጊዜዋ እናትነቷም ሆነ የመሳ ሚሰትነቷ ይሄን ያህልም ሽክም አልሆነባትም ። ቀን ቀን በሆስፒታሉ ሥራ በመጠመዷና ማታ ማታ የጸንሰ ምሽት በመሥራቸው ዋድን የምታይበት ጊዜም የላት ። አንጸንድ ጊዜማ ለረቡዕም ሰዓታት ልኟ እንጸሳትም ትዘነጋለች ።

በሞቃቶቹና ንፈጥበት ባላቸው የበጋ ማታዎች የአትሳንታ ቤቶች ለነብስ አደን ወታደሮች ብሚነሰባበት መብራቶች ፏ ብለው ደምቀ ዋል ። በምሽግ ጉድጓዶችና በተጠመዱ መሣሪያዎች ክልል የዋሉት አቧራ ባቧራ የሆኑ ወታደሮች የሚዝናኑት እንዚህ ቤቶች ውስጥ ነው ። የባንጆ ሙዚቃ ጨኽት ጭጻና ድረስ ይሰማል ። ጻንሱ እንደ መዓት ይቀልጣል ። ሳቅና ውክታ በምሽቱ አየር ላይ ይንሳፈፋል ። ወጣቶች በቡድን በቡድን ሆነው ፒያኖዎቹ ላይ ሰፍረዋል ። በጉጉት የተሞሉ ድምጾች "ዩር ሌተር ኬም በት ኬም ቱ ሌት" (የላክሽው ደብዳቤ ዘግይቶ መጣ እንጂ መምጣቱንስ መጥቷል) የተሰኘውን አሳዛኝ ዜማ ይጫወታሉ ። የተበጫጫቀ ልብስ የለበሱት ቆራጥ ወታደሮችም ከየማራገቢያው ሥር በሳቅ የሚፍለቀለቁትን ሴቶች እያ ስተዋሉ በጊዜ ጋብቻቸው እንዲፈጸም ይለምኑዋቸዋል ። ሴቶቹም ቢሆኑ ጋብቻቸው መቆየቱን አይወዱትም ። ከተማይቱን ደስታና ፌሽታ ባዋለቀለቃት ባሁኑ ሰዓት ለመጋባት ያላቸው ጥድፊያ ለብ ቻው ነው ። ጀኔራል ጆንስተን ኬኔሳው ተራራ ላይ ያንኪዎቹን ወጥሮ

@OLDBOOKSPDF
በያዘበት ወር ውስጥ በርካታ ጋብቻዎች ተፈጸሙ ። አያሌ ሠርጎችም ተደገሱ ። ሙሽራዋ ከብዙ ጓደኞችዋ ተበዳድራ ባመጣችው ልብስና ጌጥ ተሞሽራ በደስታ እየዋኘች ፡ ሙሽራውም ጐራዴውን ጉልበቱ የተጣጣፈ ሱሪውን እየገጨበት ይቀመጣሉ ። በደጉ ጊዜ ስንትና ስንት ነገር እንዳልተደረገ ሁሉ በዚሁ ሁኔታ ብቻ ይጋባሉ ። ያም ሆኖ ደስታቸው ልክ የለውም ። ወሰን የሌው ደስታ ፡ ድንበር የሌለው ፌንጠዝያ ፡ ቁጥር ስፍር የሌላቸው የዳንስ ድግሶች ፡ መጠኑ የማይለካ የሰውነት ንዝረያ ! አልል በይ ወፌ አልል በይ አሞራ ! ጀንስተን ከዚህ ሃያ ሁለት ማይል ርቀት ላይ ያንኪዎችን ግተሮ ይሠል ። እሰይ እንበሳዬ ፣ ከወለዱ አይቀር የሱን አልፍ ነበር !

ትክክል ነው ። የኬኔሳው ተራራ መስመር ኬላው የማይሰበር ፡ ወሰኑ የማይዶፈር ነው ። ከሀያ አምስት ቀን ውጊያ በኋላ ሼርማን ራሱ እንኳን ያለቀበት ሠራዊት ብቁጥር የሚያስቸግር በመሆኑ ሀቁን ተረድቶታል ። ስለዚህም ማንባር ልማንባር ከመጋፈጥ ይልቅ ሠራዊቱን በሰፊው እንዲከብ አድርጐ በኮንፌዶሬሲው መታደሮችና በአትላንታ መሀከል ተሸብልቆ ማጥቃት ጀመረ ። ይህ ዘዴው አሳምሮ ጠቀመው ። ጀንስተን ሚዳማውን አከባቢ ሰመከላከል ሲል ኮረብታውን እንዲለቅቅ ተገደደ ። በዚህ ውጊያው ካለው ኃይል አንድ ሶስተኛ ያህሉን አጣ ። የተረፈውም በድክም እየተጎተተ ፡ በዝናብ እየበሰበሰ ገጠር ገጠሩን አዳርሶ ወደ ጆታውቺ ወንዝ አመራ ። የኮንፌደሬሲው ጦር ከእንግዲህ እንዲመጣለት የሚጠብቀው የማጠናከሪያ ኃይል የለም ። በአንጻሩ ግን ከተኔሲ በስተደቡብ ጀምሮ እስከሚጊያው ቦታ ድረስ የተዘረጋውን የባቡር ሐዲድ በእጁ ያስገባው የሼርማን ጦር በየዕለቱ አዳዲስ የጦር መሣሪያና አዲስ ምልምል ወታደሮች በባቡር ይጓጓዙለታል ። ስለዚህ የግራጫ ለባሾቹ የውጊያ መስመር በየማጡና በየአረንቋው ማህል እየፈገፈገ መሸሽ ግድ ሆነበት ። ሽሽት ወደ አትላንታ ። ጉቦ ወደ አትላንታ ። ሩጫ ወደ አትላንታ ። ይቺ አትላንታ ስንቱን ትችለው ይሆን?

ያ አይደፈፈው ተራራ ሲለቀቅ ፡ ያ ኬላው የማይሰበር ተራራ ሲጣስ ፣ ያ አይበገሬው የተፈጥሮ ምሽግ ጠላት እጅ ሲወድቅ ፣ ከተማይቱን የሸብር ማዕበል አናጋት ። ለሃያ አምስት የፈንጠዝያ ቀናት ፡ ለሃያ አምስት የፌሽታ ቀናት ፡ ለሃያ አምስት የእሸሽ ጎዳሚ መሳለትና ሌሊት ፣ እያንዳንዱ ሰው ይሄ አሁን የደረሰው ነገር በጥዱም ሊሆን የማይችል ነገር እንደሆነ ፣ ላገኘው ሰው ሁሉ ሲነግር ነበር ። አሁን ይሄ ወሬ አይሆንም የተባለው ሁሉ ሆነ ! አይደረግም የተባለው ተደረገ !

@OLDBOOKSPDF

ጀኔራሉ በወዲያኛው የወንዙ ዳርቻ ሆኖ ያንኪዎቹ እንዳይገፉ ግትር መያዙ የሚያጠራጥር ጉዳይ ነው። እማዘሀር በሚያውቀው ወንዙ እኩ በጣም ቅርብ ነው— ሰባት ማይል ብቻ ነው!

ቬርማን ግን ሻረቱን በላይ በኩል አቋርጦ አውንም እያተራመሰ አሳደጓቸው ። ግራጫ ልባሾቹ መታደሮች ወንዙን ሰንጥቀው በፍጥነት መሸሽ የማይቀርላቸው ጉዳይ በመሆኑ በወራሪዎችና በአ ትላንታ ማህል ግብተው የውጥር የስንጥር ተያዙ ። ከስተማይቱ በስተ ሰሜን ባለው የፒችትሪ ክሪክ ሽለቆ ውስጥ ቀረብ ቀረብ ያሉ ጉድጓ ዶችን ቆፍረው መሣሪያቸውን አጥምደው የሞት ሽረት መከላከል ለማድረግ የጥድፊያ ዝግጅት አደረጉ ። አትላንታ ቁርጠት ያዛት ። አት ላንታ ምጥ አጣደፋት ። አትላንታ ጣር አንዘፈዘፋት ።

መዋጋት ግፈግፈግ ! ደም መዋጋት ደም ግፈግፈግ — ደም መሸሽ ! እያንዳንዱ ግፈግፈግ ፡ እንደነዳንዱ ሽሽት ያንኪዎችን ወደ ከተማይቱ እየቀረበቻቸው ነው ። ፒችትሪ ክሪክ ከአትላንታ የሚርቀው አምስት ማይል ብቻ ነው ! ጀኔራሉ ምን ያስብ ይሆን ?

"ሸንጠን ግትሮ የሚዋጋ ሰው ስጠን !" የሚለው ጩሽት ሪች ሞንድ ድረስ ተሰማ ። አትላንታ እጠላት እጅ ከመደቀች የጦርነቱ ክፉ ፍጻሜ መሆኑን የሪችሞንድ ከተማ ታውታለች ። ጠሩ የቻታኑጋን ወንዝ ካቋረጠ በኋላ ጀኔራል ጀንስተን ዘጠር አሣሸነቱ ተነሳ ። የኮን ፌደሬሲው ጦር የአንደኛው ሠራዊት አዛዥ የሆነው ጀኔራል ሁድ በሱ ቦታ ተተካ ። ከተማይቱም ትንሽ ተንፈስ አለች ። ሁድ በጭራሽ አያፈገፍግም ። ያ ጢሙ የተንሻረገገውና አይኑ ፈላጭ ቆራጭ የሆ ነው ረሻሙ የኬንተኪ ተወላጅ ከግፈግፈግ ጋር ጠበኛ ነው ! እንጂ ኔራል ጀንስተን ያፈግፍጉ እንጂ አጅፊስ ንክች አያደርጋትም ! እንደ አዳኝ ውሻ እያሳደደ መግቢያ መውጫ ሲያሳጣ የከረመ ጀግና መሆኑ የተመሰከረለት ነው ። ያንኪዎቹን ከክሪክ ሽለቆ መልሶ ያባርራቸዋል ። አዎን በመጡበት እግራቸው ይመልሳቸዋል ። ወንዙን አቋርጠው ሽቅብ መንዴን ተከትለው እያንዳንዷን እርምጃቸው ወደ ዳልተን እንድታ መራ ያደርጋቸዋል ። የመልስ ምቱን ያሳያቸዋል ። ሠራዊቱ ግን "ሸማ ግሌውን ጀ መልሳችሁ ስጡን !" እያለ ነው ። ከዳልተን ጀምሮ ያለፋ ቸውን የመከራ ማይሎች ሁሉ የዘለቀው — ከሸማግሌው ጀ ጋር ሰለነበርና ሲቪሉ ሕዝብ አይወቀው እንጂ የዋህ ባላንጣ እንዳልገ ጠመ አሣምሮ ስለሚያውቅ የሸማግሌው ጀ ያለህ ! ሸማግሌውን ጀ መልሳችሁ ስጡን ! መልሳችሁ ሹመልን ! ይላል ።

ቬርማን ለጀኔራል ሁድ የዝግጅት ጊዜ አልሰጠውም ።እንደተቅ ግጥ በላይ በላዩ አጣደፈው ። የጦር አዛዥ ሹም ሽር በተካሄደ ማግ ስት የያንኪው ጀኔራል ከአትላንታ ሰድስት ማይል ታልፎ በምትግ

@OLDBOOKSPDF

ኘው በደኅተር ከተማ ላይ አጣዳፊ የማጥቃት አርምጃ ወሰደ ። ከተማ ዋን በእጁ አስገባ ። የባቡር ሐዲዱን ቆረጠ ። ደሄ ሐዲድ አትላንታን ከአውጉስታ ፡ ከቻርልስተን ፡ ከዊልሚንግተንና ከቨርጂኒያ የሚያገናኝ መስመር ነው ። ሼርማን የኮንፌደሬሲውን ሠራዊት በአንብርክኩ አስ ኪደው ፡ እሽመደመደው ። ሽባ አደረገው ። ምላሽ ለመስጠዉ መደረግ ያለበትን ሁሉ የማድረጊያው ጊዜ አሁን ነው ! አትላንታ የመልስ ምቱ ይመታ ፡ የሚደረገው በአስቸኳይ ይደረግ ! አያለች ትምህለች ።

ከሐምሌ ወቢኃማ ከሰዓት በኋላዎች በአንደኛው አትላንታ ምሮታ ተሳክቶ የለቢ ደረሰ ። ጀኔራል ሁድ ከመቋቋምና ከመዋጋትም በላይ ተማምር ሠራ ። የሱን ሰዎች ከጉድጓዳቸው አስወጥቶ ከሱ ኃይል በእጥፍ የሚበልጠዉ የሼርማን ወታደሮች ሰማያዊ የውጊያ መስመር ላይ በጥድፊያ አሰማራቸው ።

ሰው በፍርሃት እየተናጠ የሁድ የማጥቃት አርምጃ የያንኪዎችን ቁጣ እንዲመልስለት ይጸልያል ።የመድፉ ሚሰግምግምና በሺ የሚቆጠሩ ጠመንጃዎች ማጉረምረም ምንም ከከተማዋ እምብርት የአምስት ማይል ርቀት ላይ ቢሆን ጨኸቱ ምድር ሰማይ የሚያናጋ ከመሆኑ የተነሳ ሰዉ ከሚቀጥለው ጐረቤቱ አጥር ማዪ የሚተኮስ ይመስለዋል ።ቦምቡ ከምድር ማጎጸን እየገሰገሰ የሚያወጣው ጭስና አቧራ ፡ ከዛፎቹ አናት በጣም ቀርበ እንደሚጠቀለል ደመና አየር ላይ ይንጠለጠላል ።ይሄ ሁሉ ሲሆን ግን የጦርነቱን ሁኔታ የሚያውቅ ማንም ሰው አልነበረም ።

ከሰዓት በኋላው እየተማሸ ሲሄድ የመጀመሪያው ወሬ መጣ ።ነገር ግን ወሬውን ያመጡት ግና ወዒያው ሊጀምር የቆሰሉ ሰዎች በመሆናቸው አጠራጣሪ ነአንዱ ከንዱ የሚቃረንና የሚያስፈራ ሆነ ። እነዚህ ሰዎች በጣም ያልተገዱ ቁስለኞች በአስጊ ሁኔታ የቆሰሉትን እየረዱ በኑጠላም በቡድንም እየተጋዙ የሚጓዙ ናቸው ። በጥቂት ጊዜ ውስጥ ተጠራቀሙና በባሩድ ጪስ ፡ በአቧራና በላብ የጠቆረ ፊታቸው የኔግሮ መልክ ይዘ ፡ቁስለኛው በመጠቅለያ እጦት አፉን ከፍቶ ፡ ደማቸው በላያቸው ረግቶና ገምብ ሁሪያውን ወሯቸው ወደ ሆስፒታሉ አቅጣጫ የስታይ ጉዟቸውን ሲጓዙ በረኸመ የሚፈስ የጉስቁልና ጅረት መሰሉ ።

ከከተማይቱ በስተሰሜን የመጡት ቁስለኞች ፡በመጀመሪያ የደረሱት ወ/ሮ ፒቲ ቤት ነበር ።አንዱ አንዱን እየተከተለ እያቃሰቱ ውጪው በር ጋ ሲደርሱ በአረንጓዴው ሜዳ ላይ እየተሽመደመዱ ዘፍ ብለው ወደቁና፡—

@OLDBOOKSPDF

"ውሃ!" አሉ በጣር ድምጽ ።

በዚያ አናት በሚበሳ የከሰዓት በኋላው ጠራራ ጸሐይ የወ/ሮ ጢቲ ቤተሰብ በሙሉ ዋቁር ንጭ ሳይባል ውሃ በባልዲ ፡ ፋሻ በቅር ጫት ይዞ ውሃ ሲያድል ፡ቁስል ሲያሽግ ዋለ ።ፋሻው አልቆ የአንሶ ላና የፎጣ ቅድዳጅ ሳይቀር ቁስል ታሽገበት ። ወ/ሮ ጢቲ ደም ሲያዩ አስከሮና አዝለፍልፎ አንደሚጥላቸው አንኳ ረስተው በትናንሽ ጫማዎ ቻቸው ውስጥ ያሉ ትናንሽ እግሮቻቸው አብጠውና ዝለው ሰውነታቸውን መሸከም እስኪያቅታቸው ድረስ ሰለፉ ፡ ሲያረተርቱ ዋሉ ። ሚላኒ እንኳ ራሷ ምንም ሆኗ በጣም ወደፊት ቢገፉ ፡ የጨዋ ልጅ ወንን ትታ ከጥ ሬሷ ከኩኪና ከእስካርሴት ጐን ኮስተር ብላ ስትሰራ ፊቷ እንደቁስለ ኞቹ ፊት ጭንቀትና ስቃይ ሰፍኖበት ይታያል ።በመጨረሻ ተዝለፍ ልፋ ስትወድቅም ቤቱ ውስጥ ያለ እያንዳንዱ አልጋ ፡እያንዳንዱ ወን በር ፡እያንዳንዱ ሶፋ በቁስለኞች በመያዙ ምክንያት ያስተኟት ማድ ቤት ካለው ጠረጴዛ ላይ ነበር ።

በጣርማሩ ማህል የተረሳው ሞድ በሽብር የተሞሉ ዓይኖቹን አፍጦ ፡ አውራ ጣቱን እየጠባና እያሳሰ ፡ በወጥመድ እንደተያዘች ጥን ቸል አሾልቆ ወደሜዳው እያየ ፡ በራት ለፈቱ በረንዳ ላይ ካለው የደረጃ መድገፊያ ጀርባ ይድባል ።እስካርሴት አይታው "ሞድ ሐምፕተን! ሂድ ጓሮ ሜዳው ላይ ተጫወት!" ብላ ፊሣበት ነበር ።እሱ ግን በሚ ያየው ትርዒት በጣም ከመደናገሩና ከመገደናገጡ የተነሳ ሊታዘዝ አልቻለም ።

ሚጓውን የወዳደቁ ቁስለኞች ሸፍነውታል ። ለመራመድ አቅም የላቸውም ። ለመላወስ እንዳይችሉ ቁስላቸው ቁስፎ ይዟቸዋል ። እግት ጢተር በየተራ እየተሸከመ ሰረገላ ላይ ጭኖ ወደ ሆስፒታል ወሰዳ ቸው ። ያረጀው ፈረሱ እስኪያለከልከና አረፋ እስኪደፍቅ ድረስ አመ ላለሳቸው ። ወ/ሮ ሚድና ወ/ሮ ሚሪዊዘር ሰረገሎቻቸውን ልከው ቁስለኞች ሲያመላልሱባቸው ከብደት በዝቶባቸው አታሰቱ ።

ውለው አድረው በረሃቦቹ ሞቃት የበጋ ምሽቶች ከጦር ሜዳ የሚመጡ አምቡላንሶችና ሽፊቸው አዟራ የጠጣ የኮሚሲርያቱ ተሽ ከርካሪዎች ይመላለሱ ጀመር ። ከዚያ ሰንበትበት ብሎ የእርሻ መኪ ናዎች ፡ በበሬ የሚሳቡ ጋሪዎች የግል ሰረገላዎች ሳይቀሩ በሕክ ምና ክፍል መኰንኖች ትእዛዝ ሠመቻ ላይ ተሰማሩ ። እነዚህ ተሽከ ርካሪዎች በቁስለኛና በሬሳ ተሞልተው ቀዩ አፈር ላይ ደም እያንጠ ባጠቡ በኮረኮንቹ መንገድ እየተንገጫገጩ የወ/ሮ ጢቲን ቤት አል ፈው ይሄዳሉ ።

@OLDBOOKSPDF

አምቡላንሶቹና ተሽከርካሪዎች ባልዲና መዋለቂያ የያዙትን ሴቶች ሲያዩ ቆሙ። ከመሰየም ጐላ ባለ የስታዩ ጎብረ ዚማ እሱ ዕቱ—

"ውሃ!"

እስክርሌት የሚዝለፈለፉ አንጥሮች ላይ የተሰኩትን ጭንቅ ላቶች ደማቁ የተከፈተ አፍ እንዲረጥብና እንዲለጣ፣ በትኩሳት የነደዱ ሰውነቶች ቀዝቀዝ እንዲሉና የተከፈቱ ቁስሎች ለጊዜውም ቢሆን ደንዘዝ ብለው እርይታን እንዲያገኙ በባልዲ ውሃ ታፈሰባቸዋለች። በእግር ጫቲ እየቆመች ለአንበሳንስ ሹፈሮች መዋለቂያውን ባቀበለች ቁጥር ልቧን እጥሮርሞ ላይ ሰክታ— "ምን ወሬ አለ? ምን አዲስ ንገር አለ?" ብሳ ትጠይቃለች።

ከሁሉም የሚያጠቃት አጋድ ዓይነት መልክ ነው፡—"በእርግጥ የሚታወቅ ነገር የለም እመቤት። የሚሆነውን ለመናገር ጊዜው ገና እኮ ነው።"

ሊመሽ ማታው ወበቁን ይዞ ከተጉ ይላል። ኤማርዎቹ የሚይዙት የሚጎድ እንጨት ደግሞ ይበሰን ሞቃት ያረገዋል። የአስካ ርሌት አፍንጫ አፀራ ምልኮ ኩፈናት። ከንፈሮችዋም ደራረቁ። ያ ያማረውና ሽቱው የሚያውድ ሎሚሏ በደም ፣ በቆሻሻና በሳብ ተለዋወሰ። ለክ አሽሉይ ወርነት ከብር አይደለም ቆሻሻና ስታይ እንጂ፣ ብሎ የማፈው ይሄን ጥሯል።

ድካም ፣ የሚከናወነውን የሕይወት ትርኢት ሁሉ ተጨባጭ ነት የሌለው ቅዠት አድርጎታል። ተጨባጭ ሲሆን አይችልም። ወይስ ተጨባጭ ነው። እንግዲያው ዓለም አብዷላ ፣ ተጨባጭ ካልሆነ ደሞ እዚህ አመ/ሮ ፒቲ ቤት ሰላማዊ ድጅ ሆኖና በሚውለበለበው ብር ሃን ውስጥ ቆማ በሚሞቱ ወጣቶች ላይ ውሃ እምትጨምረው ምን ዕዳ አለባት? ብዙዎቹ የሲ ወዳጅ የነበሩ ስለሆኑ ነና ሲያይጥት ፈጣ ሊሉላት ይሞክራሉ። በዚህ ኮረኮንቻማ ቁልቁለት መንገድ ላይ በቁ ለማው ውስጥ እግጭ እገው እያሉ ከሚሔዱት ማህል አብዛኛዎቹ የምታውቃቸው ወንዶች ናቸው። በዚህ አቧራማ መንገድ ከሚ ሄዱት አብዛኛዎቹ አሳምራ የምታውቃቸው ናቸው። እዚህ ሲሞቱ ባይኗ በብረቱ የምታያቸውና ትንንና ዝምቦች በደም የተበከለ ፊታ ቸውን ሲወሩት የምታስተውለው ፣ አብራቸው የደነስችና ያሳላቀቻ ቸው ፣ ሙዚቃ የተጫወተችላቸውና ዘፈን የዘፈነችላቸው ፣ የቁላፉቻቸ ውና የተንከባከበቻቸው እንዲሁም ያፈተረቻቸው ትንሽም ብትሆን/ ወጣቶች ናቸው።

@OLDBOOKSPDF

ካፊያ እሽበርን በአንድ የዘረፈ ጋራ ላይ ከብከመሩ ዙስለኛች ክምር በታች በጭንቅላቱ በገባች ጥይት ምክንያት ሊሞት ጥቂት ቅጽበት እንደቀረው ኢማኜታሞለች ። ሆኖም የሱን ዙስለኛ ሰውነት ጐትቼ ላወጣ ብትል ሌሎች ስድስት ዙስለኛችን ለስታይ መዳረግ ስለሚሆን ዝም ብላ ወደ ሆስፒታል ሊሄድ ተመለከተችው ። በኋላ ስትሰማ የሚያክመው ዶክተር እጥፍ እንደሞተና የት እንደተቀበረ እንኳ የማይታወቅ መሆኑን ተረዳች ። በዚያ ወር እንደነገሩ ጫር ጫር በተዶረገ በአክላንድ መታሰር የተጣሉ ወንዶች ቁጥር እጅግ ብዙ ነው ። ሚሳኒ ፡ አላባማ ስምትገኘው የካፊያ እናት ጸጉሩ እንዲላ ከላት ተሪልን መጥፋቱን ሰምታ ክፍተኛ ቅሬታ ተሰምታታል ፡

ያ ወዘቃማ ሴሊት እየገፋ በሄደ ቁጥር ቆመው የቆዩበት መገባ ቸው ታሞ ፡ ከይነም ብዛት ጉልበታቸው ዝሎ እንኳ አስካርሌትና ሚላኒ እያነጻነጹት እንግዳ ሰው "ምን ወሬ አለ ምን አዲስ ነገር አለ ? " እያሉ ጮኸው ይጠይቃሉ ።

በዚህ ሁኔታ ረኽሙ የመነሪ ሰዓት ተለ በቀለ አየተሳበ ሲሄድ የጥይቂያቸውን መልስ አገኙ—አርስ በርሳቸው ሲተያዩ አንዷ ለአ ንዷ አመድ የነዛባት መስላ ትስዝትታያት ድረስ የሚያስደነግጥ መልስ ።

"እያፈገፈግን ነው ።" "ማፈግፈግ ይጥርብናል ። " "በሺ በሚቆጠር ኃይል ይበልጠናል ። " "ያንኪዎቹ የሚልርን ፈረሰኛ ጦር ይኸተር አትራቢያ ከሞናው ጦር ቅረውት ። ነጠሉት ፡ እሱን ማጠ ናከር ይኖርብናል ። "" የኛልጅች በሙሉ በትርቡ ከተማ ይገባሉ ።

አስካርሌትና ወ፡ሮ ሂዲ ለመደጋገፍ ክንድ ለክንድ ተሳሰሩ ።

"ያንኪዎች ነየመጡ ነው እንዴ?"

"አዎ እመቤቱ ፡ መምጣቱንስ እየመጡ ነው ፡ ነገር ግን የትም አይደርሱ እመቤት ። " አይኮሽ እመቤቱ አትላንታን ሊመስጂት አይችሉም ።" "የለም የኔ እመቤት በዚች ከተማ ሀሪያ በሚሊዮን ማይል ርቀት ላይ መሣሪያ ጠምደናል ።" "ሸማግሌው ጅ አት ላንታን ለዘለዓለም አላስነኳትም ነ"ሲል እኔ ራሴ በጀርዩ ሰምቼዋለሁ ። "ግን አሁን ሸማግሌው ጅ ነኛ ጋር የለም—አሁን ያለው . . . "ዘመቱል አንተ ሴቶቹን ለማስፈራራት ፊልሃል እንዴ?" "ያንኪ ዎች ኑቺን ምድር በቁሪሽ አያዛትም የኔ አመቤት ። " "እናንተ ሴቶች ሰምን ወደ ማዘን ወይም መጀሌላ ሰላም ወደ ሆንበት አካ ባቢ. አትሄዱም ? እዚያ ምንም ዘመድ የላችሁም ?" "ያንኪዎች አትላንታን በቁሪሽ አይነኳትም ። ያም ሆኖ መሞከራቸው ስለማይ

@OLDBOOKSPDF

ቀር ለሴቶች እዚህ መቀመጡ ጥሩ አይሆንም።" "እዚህ መዓት ተኩስ ይኖራል።"

በሚቀጥለው ወበቃማና ዝናባማ ቀን በሺ የሚቆጠር የተሸ ነፈ ሠራዊት ወደአትላንታ ይግተለተል ጀመር። በረሀብና በድካም የዛሉ በስባ ስድስት ቀናት ውጊያና ማፈግፈግ ብዛት የተጉሰቁሉና ከሰውነት የወጡ፣ ፈረሶቻቸውም አጥንታቸው ወጥቶ ማስፈራሪያ የመሰሉ፣ መድፋቸውን በሲባንና በእርጥብ ጠፍር አስረው የሚጉ ትቱ በሺ የሚቆጠሩ ሰዎች አትላንታ ገቡ። አመጣጣቸው ግን ከተሸነፈ ሠራዊት እንደሚጠበቀው ሸጥ ባጣና በተመሰቃቀለ ሁኔታ አልነበረም። የተቀደዱ ቀይ ባንዲራዎቻቸውን በዝናብ ውስጥ ከፍ አድርገው፣ ቡቱቶም ቢሆን የኒፎርማቸውን በወጉ ለብሰው በት ክክል ተሰልፈው ነበር። የማፈግፈግን የመር ስልት ወደ ፊት ዜማ ጥቃት እኩል ከሚቆጥረው ከሸማግሌው ጀ ጋር ማፈግፈግን በሚገባ ስለሰለጠኑበት አሁን አልተቸገሩም። ጠማሞቹ የምድር ጉስቋሎች ሜሪላንድ! የኔ ሜሪላንድ! ከሚለው ዜማ ጋር እኩል እየተራመዱ በፒችትሪ ጉዳና ቁልቁል ይተምማሉ። የከተማዋ ነዋሪዎች በሙሉ በጭብጨባ ተቀበሏቸው፣ እንዚህ ልጆች በድልም ሆነ በሽንፈት ወቅት የነሱው ልጆች ናቸው።

በቅርቡ በአዳዲስ የኒፎርም አምሮ ሂዶ የነበረው የሚሊሺያ ሠራዊት እንዳልሆነ ሆኖ ጨትይኖ በመምጣቱ ማ ከማን አይለይም። አሮጌው ሠራዊትና አዲሱ ሚሊሺያ በአቧራና በጉስቁልና ጋይል አንድ ዓይነት ሆነዋል። ዓይናቸው ውስዮ አዲስ ነገር ይነበባል። እን ማዳ ነገር ይታያል። ያ ሶስት ዓመት ሙሉ ክልዘመትን እያሰኘ ያስ ወተውታቸው የነበረው፣ ያ ለምን እንደማንዘምት ይገለጽልን አያሉ እንዲጨታጨቁ ያደርጋቸው የነበረው፣ ያ አለመገመታቸውን በሀዘን እንዲዐዐቱበት ያደረገው፣ ያ ያልዘመቱበት በዚህና በዚያ ምክንያት ነው አያሉ ያስረዱበት የነበረው የስሜት ማፊት ሁሉ ዛሬ ከጀርባ ቸው ቀርቷል። የመርኑትን የቋያ እሳት ካዩ በኋላ አገር ሰላም የሆነ በትን ጥግ፣አገር ጠና የሆነበትን መጠለያ ቢታ አንጂ ሌላ ምንም አይ ይፈልጉም። አብዛኛው የነሱ ሕባል ከሞት ያልተ ምንም ዓይነት ኑሮ ይሁን መኖርን ይፈልጋልና። እነዚህ ሚሊሺያዎች አሁን አንጋፋዎች ሆነዋል። በአጭር ጊዜ የመር አገልግሎት አንጋፋ ጦር ለመባል በቅ ተዋል። ነገር ግን ሀሮ ሀሮ ያው እንደማንኛውም አንጋፋ መር ናቸው። እንደማንኛውም አንጋፋ ጦር ጠባይ ገዝተዋል። ግዳጃችንን ተወጥተናል ብለውም አምነዋል። ከተሰበሰቡት ሰዎች ማህል ቻሉ ሞቻቸውን እየፈለጉ በኩራትና በአይበገሬነት ዓይን ያዩዋቸዋል።

@OLDBOOKSPDF

ቋቅሳታቸውን ቀና ፡ ልባቸውን ሞላ አድርገው ለመሄድ ችለዋል— ለመዋጋት ስለበቁ ።

የከተማ ጠባቂዎች አባላት ሆነው ዘምተው የተመለሱት ሽማግሌ ዎችና ትናንሽ ወጣቶች ተመለሱ ። ጠሚሞቹ ሽማግሌዎች አገራቸ ውን ማንሳት አቅቷቸዋል ።ወጣቶቹም ከደነገ ብዛት ፡ ጥና በልጅነቱ ችግር እንደገጠመው የተጸከመ ሕዝን መስለዋል ። አስካርሌት ፊል ሚድን አየችው ።መልኩን ለማስታወስ ግን በጣም ተቸገረች ።በባሩድ ጭስ የበለዘውና የጠቆረው ፊቱ ፡ በሚንቀሳቀስና በድካም የተዝለፈለፈ ፈው ሰውነቱ ጨርሶ የሱ አይደለም ። እጅት ሐንሪም እየተንቀሳቀ መጣ ።ባርሜጣ የለሽ አራሱ ለዘፍዛ ተጋልጧል ። አንገቱ ከአንድ በዘይትና በግራሰ ከራሰ ኮት ውስጥ ብቅ ብሏል ። አያት ሚሪዊዘርም በእንድ መሣሪያ ጫኝ ሰረገላ ላይ ተኮምጠዋል ። አግራቸው በብጥስጣሽ ጨርቅ ተሸፍኗል ። ደሃ ሁሉ ሰው አለፈ ። አስካርሌት በተ ቻላት ሁሉ ለማየት ትፈልገው የነበረው ጅን ዊከስ ግን አልነበረም ።

የጅንስተን አንጋፋ ጦረኞች ከዚህ ሁሉ በኋላም በድካም የለሽና ቁብ የለሽ አረማመድ ይጓዛሉ ። ደሃ አረማመድ ለዩስት ጎመታት ሲጠበቁት የኖረ ነው ። አሁንም ለቆንጆ ሴቶች ፊገግ ለማለት ይሞ ክራሉ ።አሁንም የኒሮርም ያልለበሱ ወንዶች ያሽሚጥላሉ ። የሚሄ ዱት ከተማዋን በቀለበት መደከበት መሣሪያ ያተጠመደባቸው ጉድጓዶች ነው ።እነዚህ ጉድጓዶች እንደዱሮም ትርጠና የይድረስ ይድ ረስ የተቆፈሩ አይደሉም ።እደረት ድረስ የሚያሰምጡ በአሸዋ በተጠ ቀጠቁ ከረጢቶች የተከለሉ ናቸው ። እነዚህ ጉድጓዶች ከተማይቷን ማይል እስከ ማይል አጥረዋታል ። ቀደ ጉድጓዶች ከሁዩ አፈር ከምር ጋር ተደርድረው የሚሞላቸውን ይጠብቃሉ ።የሚገባባቸውን ይጠባበቃሉ ። የቀበሮ ጉድጓዶች ተሰልፈው የጅግና ያለህ ይላሉ ።

የተሰበሰበው ሕዝብ እንዚህን መታደሮች በድል ሲገቡ ጉሮ ወሸ ባዩ ብለው እንደሚተበሳቸው ሁሉ በሞብጨሀዩ በሆታ አሳለፋቸው ። በየአንዳንዱ ሰው ልብ ውስጥ ፍርሃት አለ ። ይሁን እንጂ ሀዙን ሳያወ ቁት ፡ ይደርሳል የተባለው የመጨረሻ አስከፊ ነገር ስለደረሰ ፡ ጠረን ቱም ዐይናቸው ሥር የሚነሃይድ ስለሆነ ፡ ነተማጀቱ ላይ ለውጥ ይታ ደል ። አሁን ቱርጠት የለም ። አሁን የስሜት ውጥረት የለም ። በየልብ ውስጥ ያለው ነገር በየፊቱ ላይ መታየቱን ትቷል ።ምንም በውጥረት የታፈነ ደስታ ቢሆን እያንዳንዱ ሰው ደስታ ይታይበታል ። እያንዳንዱ ሰው ስሜራዊቱ ጅግና ልበ ሙሉ ፊት ለማሳየት ይጣጣራል ። እያንዳንዱ ሰው ያ ሽማግሌ ጅ ከአዛቨንት ከመነሳቱ በፊት ይለው የነበረውን ይላል፡—"አትላንታን ለዘላለም አሳስነትም"

@OLDBOOKSPDF

አሁን እንግዲህ ጂኔራል ሁድም እያፈገፈገ ስለሆነ አብዛኞቹ ወታደሮች ሽማግሌው እንዲመለስላቸው ይመኛሉ ። ይህን ማለቱም ስለሚያጽናናቸው ከሽማግሌው ጀ አባባል ድፍረትን ያገኛሉ፡—

"እትላንታን ለዘለዓለም አላስነካትም !"

* * *

ሁድ እንደጂኔራል ጆንስተን ጥንቃቄ የተሞላባቸው ዘዴዎችን አይጠቀምም ። ከዚያ ይልቅ በቀጥታ መጋተርን ይመርጣል ። ያንኪዎችን በምሥራቅ ገትሮ ይዟል ። በምዕራብም እንደዚያው ነው ። ሼር ማን ተጋጣሚውን አዲስ ቦታ ሳይ ለማጥቃት እንደሚጣጣር የነባ ትግል ተጋጣሚ ከተማዋን ይዞራታል ። ሁድም ቢሆን ያንኪዎች ጥቃት እስከሚያደርሱበት ድረስ የጠመንጃውን ታታ ሳይሰብ አለ ጠበቀም ። በቀጥታ በማንባር ወጥቶ ደም እንደጠማው አውሬ እየተ ወረወረ በድፍረት ጥይቱን ያዘንብባቸዋል ። በጥቂት ቀናት ውስጥ የአትላንታና የአዝራ በተስኪያን ጦርነቶች ተካሂደው አበቁ ። ሁለ ቱም እጅግ ቁልፍ የሆኑ ቦታዎች በመሆናቸው ፔችትሪ ከሪክን የአሜር ውጊያ መናኸሪያ አደረጉት ።

ያም ሆኖ ያንኪዎቹ ጭራሽ አየዘዙ ፡ ተመልሰው መምጣ ቸው አልቀረም ። ብዙ እጦት ብዙ እልቂት ደርሶባቸዋል ፤ ነገር ግን የበለጠም ቢያጡ ፡ የበለጠም ቢያልቁ ፡ በቲ ኃይል ስላላቸው አይቸግራቸውም ። አትላንታ ላይ የፈንጂ ዝናብ አውረዳባት ። ሰው በየቤቱ እንዳለ ተታጠለ ፡ ነደደ ፡ አለቀ ። የቤት ጣሪያዎች ንፋስ እንዳነ ሳው በርሚጣ በረሩ ። መንገዶች ተበዳደሉ ። ሰዉ በየስርቻው ፡ በየጉድባውና በየኮረኒሱ ሥር ተሸሸገ ። የውሀ መውረጃ ቦዮችና ተቦ ዎች ሳይቀሩ መደበቂያ ሆኑ ።አዎ ፡አትላንታ ተወረረች ።ተፈጀች ። ተለበለበች ።

ጂኔራል ሁድ እዙን በያዘ በአሥራ አንድ ቀናት ውስጥ ያጣ ቸው ሰዎች ቁጥር ጆንስተን በሰባ አራት ቀናት ማጥቃትና ማፈግ ፈግ ያጣቸውን ሰዎች ቁጥር ያህል ሆነ ። አትላንታ ከሶስት አቅ ጣጫ ልቧን ተወጋች ።

እንግዲህ ከአትላንታ ወደ ተነሲ የሚወስደው መንገድ ሙሉ በሙሉ በሼርማን እጅ ገባ ማለት ነው ። ሠራዊቱንም ወደ ምሥራቅ የሚወስደውን የባቡር መንገድ ተቆጣጥሮ እንዲሄድ አድርጐ እሱ በሶ ቡላ ምዕራብ በኩል ወደአላባማ የሚወስደውን የባቡር መንገድ

@OLDBOOKSPDF

ቆርጠ ይዘታል ። ወደ ደቡብ (ማለትም ወደማክንና ወደላሻና) ከሚወ ስደው የባቡር መንገድ በስተቀር አንድም ክፍት መንገድ የለም ።

ከተማዋ በወታደር ተጥለቀለቀች ። በዝሰለኛ ታጨቀች ። በስደተ ኞች ከአፍ እስከ ገደፍዋ ተሞላች ። ያለችው አንዲት አውራ መን ገድ በመሆንዋ የቀሰለችውን ከተማ ጨሽትና ጥማት ለማርካት በወ ርዱም በቁመታም ብትዘረጋጋም እንኳ በማሞ ጠበበች—አልቻለችም ። ያም ሆኖ ይች መንገድ በሕይወት እስካለች ድረስ የአትላንታ እስት ንፋስ ይኖራል ።

እስካርሌት ይች መንገድ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነች ለታ ስብ ፡ ዌርማን ለመያዝ ምን ያህል ጠንክሮን ወጥሮ እንደሚታገል ስታይና ፓኔራል ሁድ ጁማሞ ላለ በሴለ የመጨረሻ እስትንፋሱ ምን ያህል ለማጸን እንደሚፋለም ስታስላ በድንጋጤ ናላዋ ዞረ ። ይቺ የባ ቡር ሀዲድ በየመንደሩ ኤጀርጣ በጅንስቦሮ ቢላቲ ነች ። ጅንስቦሮ ደማሞ ከታራ አምስት ማይል ብቻ ነው ርቀቷ ፤ መቼም በሰውታና በጣ ዕር በተሞላው በአትላንታ ገሀነም ዓይን ስትታይ ፡ ታራ ሰላማዊ ፕነት ናት — የወጥታ ምሽግ ሆሚይሰሀነው ግን ከጅንስቦሮ ታራ ድረስ አምስት ማይል ብቻ መሆኑ ወቸኮጅ ፤

× × ×

እስካርሌትና ሉሎች በዝኳታ ሰዓት መይዘውምች ጠጣሩ ጣራ ባሳቸው መጋዘኖች አናት ላይ ስስ ሽፕቸውን አጥልቀው ተቀምጠው የአትላንታን የምጥ ቀን ያኮተሙሉ ነበር ። ሆኖም በየመንገዶቹ ላይ ለመጨመሪያ ጊዜ ፈንጂ እንደ አሸን መፍላት ሲጀመር ወደየኮርኒሱ ወረዱ ። የዚያኑ ዕለት ማታ ሽፅትና ስደት ተጀመረ ። ጉዘው ወደ ማክን ነው ። ሴኖች ፡ ሕፃናትና አረጋዊያን እንደኤሲ ይሰባሉ ። ማታ ወን በባቡር የዘለቱ አምስት ስድስት ቡድን ያህል ማዘን ገብተዋል ። ፊት ወደአትላንታ ሲመጣ ከተታኩተት አጣቢልተሉ የያዘ ሁሉ አሁን ሽሹቱ ጊዜ አልሰጥ ብሎት ጓዝ ጉሙኑን ፡ ቅሌን ፈሌቹን ሳይል እየ ተጣደፈ ይወጣል ። ጓዙ ግፉ በሌ አንዲት የማትከበድ ቦርሳ ወይም አንስተኛ ሻንጣ ብቻ ናት ። የተመጢ ቀን ለጆሮ ጉትቻ ለአ ንገት ዐብል ፡ ለእጅ አምባር ፡ ለጌጣር አልቦ አያስችም ። ልጨና ገረ ዶች ተድናግጠው ዚላ ፡ ማንኪያ ፡ ሹካና ካለፉት ቀናት የተረፉ የጌ ቶቻቸውን ርቆግራፍ ብቻ ይዘው ጉግሬ አወጪኝ አሉ ።

ወይዘሮ ሚሪዊዘርና ወይዘሮ ኤልሲንግ አንዳድም ብለው አሻ ፈረሻ አሉ ። ሆስፒታል ለምሪ እንደለጋሰን ባሎች ሆኑ ። በዚህ ላይ

@OLDBOOKSPDF

ደግሞ የማናባቱ ያንቺ ነው ከገዛ ቤታችን የሚያስወጣን ፣ ደሞ ለያ
ንቺ ፊት መስጠት በሚል ኩራት ባለው ንግግር ትዝሃቸውን ነፉ ።
ሜይቤልና ሕፃን ልጅዋ እንዲሁም ወይዘሮ ፋኒ ኤለሲንግ ማን አይናቸ
ውን ሳያዩ ወደ ማዘን ሄዱ ። ወይዘሮ ሚድ ደግሞ በሕይወቷ ለመ
ጀመሪያ ጊዜ የዶክተር ትእዛዝ አላከብርም ባይ ሆና 'ከጥሩት ውሻ
መጻኛው መርከብ ላይ ውጪ' ፣ በባቡር ተሳፍረሽ ሂጂ ብትባል አል
ሞክረውም አሉች ። ዶክተሩ ይፈልጉኛል የሚል ፈሊጥ አመጣች ። በዛ
ላይ ፈል ችግር ሊገጥመው ስለሚችል ሰምኖልባቱም ቢሆን እገኑ
መሆን እንዳለባት አጠንክራ ገለጠች ።

ያም ሆኖ ወይዘሮ ዋይቲንግና ሴሎች አያሌ የእስካርሌት ቡድን
አባል ቤቶች ሄደዋል ። የሽማግሌው ጆን የማፈግፈግ ፖሊሲ እሪ
ብለው ይቃወሙ የነበሩት ወይዘሮ ፒቲ እንኳ ሻንጣቸውን ጠቅልለው
ለመነሳት የመጀመሪያዋ ነበሩ ። ነርቬ አይችልም ፣ ጩኸት ከበዛ
ያመኛል አሉ ። ቦንብ ሲፈነዳ ከሰሙ ልባቸው ሥራውን እንደሚያ
ቆም ፣ ኮርኒስ ላይ ወጥቶ መደበቅ እንደማይሹሉና ሌላ ዓይነት ፍርሃት
ግን በጭራሽ እንደሌለባቸው አስረዱ። ሰለወታደራዊ ነገሮችም ጨምረው
ለመናገር ፈልገው ነበር ፣ ከነዚያ የአሻን ልጅ ከሚያነክሱ ከንፈሮቻቸው
ግን ምንም ቃል ሊወጣ አልቻለም ። እዚያው ማዘን ሄጻው ከእክ
ስታቸው ልጅ ከአሮጊቷ ከወይዘሮ በርር ጋር መቆየት ይቻልኛል አሉ ።
ሴቶቹ ልጆችም አብረውኝ መሄድ አለባቸው ባይ ሆኑ ።

እስካርሌት ወደ ማዘን መሄድ አልፈለጎችም ። ምንም እንኳ የፈ
ገጇ ጩኸትና የጥይት እሩምታ ቢያስፈራራት ከአሮጊቷ ከወይዘሮ
በርር ጋር ከመኖር አትሳንታ መቅረትን ትመርጣለች ። አሮጊቷን ስት
ጠላቸው እንዳንድ ነገር ነው ። ከዓመታት በፊት በዊክሶች የቤተ
ሰብ ግጭት ድግስ ላይ ከአሮጊቷ ልጅ ከዊሊ ጋር እስካርሌት ስት
ሳሳም ወይዘሮ በርር ድንጣት ደርሰው 'ፍየል ከመድረሷ ቅጠል መበ
ጠሷ' እያሉ እስካርሌትን ሙልጭ አድርገው ሰድበዋታል ። ስለዚህ
ብትሞት ማዘን እንደማትሄድ ለወይዘሮ ፒቲ ተናግራለች ። ከአትላ
ንታ መውጣቷ በጣም አስፈላጊ ከሆነም—እኔ ወደ ቃሬ ፣ ሜሊ'ክንቺ
ጋር ወደ ማዘን መሄድ እንችላለን· ብላ በግተርነት አስረድታለች ።

ይሄን ስትሰማ ደግሞ ሜላኒ ፍርሃት በተሞላና ልብ በሚነካድምጽ
ተንሰቅሰቀች ። ወ/ሮ ፒቲ ዶክተር ሚድን ሊጠሩ ተነሰተው ሄዱ ።
ሜላኒ የእስካርሌትን እጅ በእጅዋ ጭምቅ አድርጋ ለመናዋን ጀመ
ረች ።

"የእኔ እናት ስለእግዚሀር ብለሽ ጥለሽኝ ወደታራ አትሂጂ!
እኔስ ያለአንቺ ማን አለኝ ? ብቻዬን መቅረቴ እኮ ነው ። እስካርሌት

@OLDBOOKSPDF

ልጂ ሲወለድ እንቺ ከጐኔ ባትኖሪ መሞቴ ነውነ ልክ ነው ወይዘሮ ፒቲም አለች ጥሩ ሴት ናት። ነገር ግን እሷ ልጅ ወልዳ አታውቅም። እንዳንዴም ስለምታበሳጨኝ ጩቪ ጩቪ ነው የሚለኝ ። እባክሽ ውዴት ሜዳ ላይ አትትይኝ ። እንቺኮ ልክ እንደሕፃኔ ነሽ፤ በዛ ላይ " በስሱ ፈገግ ብላ፥ "የአሽሌይ አደራ አለብሽ ። እንደምትጠብቂኝ ቃል ገብተሽለታል ። ቃል እንድትገቢለት እንደሚጠይቅሽ ነግሮኛልኳ ። "

እስካርሌት በመገረም ተመለከተቻት ። ለራሷ ጥሳቻዋን መደበቅ እስከያቅታት ድረስ የምትጠላት ሴት እንዴት እንዲህ ልትወዳት ትችላለች ? ሚሊ እንዴት ያለች ደደብ ብትሆን ነው የአሽሌይ ንና የእስካርሌትን ፍቅር ምስጢር መጠርጠር እንኳ ያቃታት? መቼም ባለራት ወራት ውስጥ የሱን ወሬ ለማወቅ ስትንሰፈሰፍ መዓት ጊዜ ራሷን አጋልጣለች ። ሜላኒ ግን ምንም ያየችው ነገር የለም ። ምስኪን ሜላኒ ! የወደዷትውን ሰው ጥሩ ጥሩውን ብቻ እንጂ እንዲት ክፉ ነገሩን ለማየት የማይቻላት ምስኪን ሜላኒ ! ምስኪን የሰው አርማብ . . . እውነት ነው ። ሜላኒን እንደምትንከባከባትና እንደምትጠብቃት ለአሽሌይ ቃል ገብታለት ነበር ። ወይ አሽሌይ! አሽሌይ ! መቼም ሞተህ መሆን አለበት ይሄን ሁሉ ወር በሕይወት አለህ ብዬ አላምንም! ደሞ አሁን ወስዶ እድሮ የገባሁልህ ቃል ይሽው መልሶ አሰረኝ ።

"እሺ መቼም" አሰኝና ቀጭሩ "ያንን ቃል ገብቻለሁ ። ቃሌን የምበላ ሰው ደሞ አይደለሁም ። ወጣም ወረደ ግን ወደማከን ሄጂ ከዛች ወ/ሮ በርር ከምትባል የጠነዛች ድመት ጋር አልቀመጥም ። በአምስት ደቂቃ ውስጥ አይኗን ጐልጉቡ አውጥቼ ነው የማሳርፋት ። እኔ ወደታራ ነው የምሄደው ። አንቺም አብረሽኝ መምጣት ትችያለሽ እማማም ያንቺ መምጣት በጣም ያስደስታታል ። "

"ኤስይ ! ያማ በጣም የምወደው ነገር ነው ። እግዚሀር ይስጥሽ አስካርሌት ። እናትሽ ኮ በጣም ግሩም ሴት ናቸው ። ነገር ግን እንድችግር አለ- አየሽ እኔ በምወልድበት ሰዓት አክስቱ አብራኝ ካልኖቸረ እሞታለሁ ነው የምትለው ። ታራ መሄድ እንደማትፈልግ ደግሞ አሳምሬ አውቃለሁ ። በጣም የሚያጋጭ ነገር ነው ። አክስቱ መቼም እልነካ ባይ ናት ። "

ዶ/ር ሚድ ፣ ወይዘሮ ፒቲ ነፍሱን አስጨንቃ ካልመጣሀ ምጪ መጥቷል ። ባሉት መሠረት ሜላኒ ቢያንስ የመጀመሪያ ደረጃ ምጥ ላይ ትሆናለ ችብሎ በመገመት ከመጣደፉ የተነሳ ትንሩሹ ቁርጥ ቁርጥ እያለ ደረሰ ። እዚህ ያጋጠመው ነገር ግን የተለየ በመሆኑ በጣም ተናዶ

@OLDBOOKSPDF

ትናገረ ። የሚለኒንን ችግር ቆይቶ ሲረዳ ግን ምንም በማያከራክር ሁኔታ ቁርጥ ያለውን ነገር ነገራቸው ።

"ወ/ሮ ሚሊ ፤ ያንቺ መደማከን መሄድ እንደሆነ የማይሞከር ጉዳይ ነው ። መደዚያ ንቅንቅ እላለሁ የምትይ ከሆነ እኔና አንቺ አን ጻችም ንግግር አይኖረንም ። ባቡሮቹ በሙሉ ሰው በሰው ላይ የሚ ጭኑና ቸው ። በዚያ ላይ ምንም አስተማማኝነት የላቸውም ። በማንኛ ውም ጊዜ መንገደኛውን ሙሪድና ሞክ ግባ ሲሉት ይሸላሉ ። ወሳኙ ባቡሩ ስወታደሮች ወይ ለቁስለኞች አሊምም ሰዕቃ ማጓጓዣ መፈ ለግ እለመፈለጉ ነው ። አሁን አንቺ ባለሽበት ሁኔታ . . ."

"ታራ ከእስካርሌት ጋር ብሄድ ግን እኮ . . ."

"እንግዲህ ነገርኩሽ ። ልትሸኟም ብደለሁ አትሄጂም ። ታሪም የሚሄደው ሆነ ማከን የሚሄደው ባቡር ያው አንድ ነው ። ስለዚህ ሁኔ ታው እንድ ነው ።ከዚያም በለይ እሱን በትክክል ያንቺምቹ የት እን ዳሉ የሚያውቅ ማንም የለም ። ሁሉ ቦታ ይዘሞወራሉ ። እናንተ የምት ሄዱበት ባቡር አራሱ ሊያገ ይችላል ። ደግም ጆንስቦሮ እንኳ በሰ ላም ብትገቡ እለክታራ ያረሰ ገና የእምለት ማይል ኮረኮንች መን ገድ ይጠብቃችኋል ። ነፍሰጡር ቤት የምትሄድበት መንገድ አይደለም ። በዛ ላይ ሽማግሌው ዶክተር ፎንቴን ከሠራዊቱ ከተቀላቀለ በኋላ በመንደሩ ዶክተር የሚባል የለም ።"

"ግን እኮ እሞላጆች እሉ...."

"እኔ ዶክተር ነው ያልኩት ያእኔ እመቤት" ብሎ ፈርጠም ብሎ መለሰና ሳያውቀው ዓይኖቹ በቀጭኑ የሰውነቷ ቅርፅ ላይ ተንሸራ ሸሩ ። "እንድትሄጂ በጭራሽ አላደርግም ። አደገኛ ሲሆን ይችላል ፣ መቼም ህፃኑን ወይ ሠረገላ ላይ ወይ ባቡር ላይ አንዲወለድ አትፈልጊም፣ ትፈልጊያለሽ ?"

ይሄ በግልጽ የተናገረው የባለሙያ አስተያየት ሴቶቹን ሁሉ ወደ ድንጋጤና ወደ ዝምታ አገር ሰደዳቸው ።

"እኔ እራሴ ሁኔታሽን ልቆጣጠር በምችልበት ቦታ ፣ ማለትም እዚሁ አርፈሽ መቀመጥ አለብሽ ። ወደላይ ወደታች ማለት በጭራሽ የለብሽም ። ደረጃ መውረድ ወይም መውጣት የለም ። ለምን ጥይት በም ስኮት አይገባም በፍፁም መነቃነቅ የለብሽም ። ለዛውም እዚህ ይህን ያህል አደጋ የለም ። ያንቺዎቹን በጥቂት ጊዜ ውስጥ ላንውል ስና ድር እንመልሳቸዋለን...እ...ወይዘሮ ፒቲ አንቺ ወደማከን ሂጪ ባልሽ እዚህ ይቅሩ ።"

@OLDBOOKSPDF

"ያለ ምግዚትን ያለምንም ጠባቂ ሰውን ማንም አጠንቧ ሳይ ኖርን" ብለው ጮኹ ወ/ሮ ፒቲ ።

"ራሳቸው ምግዚት ናቸው።" አለ ዶክተሩ ። "ደሞም የወይዘሮ ሚድ ቤት ከዚህ አንድ ሁለት ደቻፍ አልፎ ነው ። ብቻ ያም ሆነ ይህ አሁን ወይዘሮ ሚሊ ባለችበት ሁኔታ ማንም የወንድ ጓደኛ ስለማይጠ ይቃት ምንም ችግር አይኖርባቸውም ። እሪ የሰማያቱ ያለህ! ወይዘሮ ፒቲ- የጦርነት ጊዜ እኮ ነው ፤ አሁን ስለምግዚትና ደንገጡር የምና ስብበት ጊዜ አይደለም ። ለወይዘሮ ሚሊ ብቻ እናስብላት ።"

ከክፍሉ ወጥቶ እስካርሌት አስከትመጣ ድረስ ፊት ለፊቱ በረ ንዳ ላይ ቆሞ ጠበቃት ።

"ወይዘሮ እስካርሌት ፤ ላንቺ በግልጽ ልነግርሽ አፈልጋለሁ ።" አለና ጀመረ ፤ ግራጫ ጢሙን እያንቀጠቀጠ ።"ቁም ነገረኛና ወጣት ሴት ነሽ ።ስለዚህ ትንሽ ጊዜሽን ልውሰድብሽ። ስለወይዘሮ ሚሊ ከዚህ መሄድ ከአንግዲህ እንዲነሳብኝ አልፈልግም ። ጉዞውን ልትሰቀም መቻሏ ያጠራጥረኛል ። አየሽ እንደምታውቂው ጸሴዋ በጣም ጠባብ ነው ። ምናልባትም በፎርሲፕስ መገላገል ይኖርባት ይሆናል ። ስለሆነም በደህናው ጊዜ እንኳን ችግር የሚኖርባት ሴት ናት ። እና የማንም ደንቆሮ ባሪያ አዋላጅ ነኝ ብሳ መጥታ እንድትጫወ ትባት አልፈልግም ።እንደእሷ ያሉ ሴቶች መውለድ አይገባቸውም ነበር ። ብቻ ሆነ...ለማንኛውም የዚህችን የወይዘሮ ፒቲን ሻንጣ ቶሎ አዘጋጅተሽ እሷን ወደማከን ላኪያት በጣም ደንጋጣ ስለሆነች ወ/ሮ ሚሊን ታበሳጫትና ኃላ ደግ አይሆንም ። እና አሁን የእኔ አመቤት" ትክ ብሎ የሚወጋት በሚመስል ዓይን እያስተዋላት "ስለአንቺም አብረሻት ወደ ቤት መሄድ ቢሆን ምንም መስማት አልፈልግም ። ወይ ዘሮ ሚሊ እስክትገላገል ድረስ አብረሻት ቆዪ ። እትፈሪም ፤ አይደል ?"

"እሪ በጭራሽ!" እስካርሌት ሽምጥጥ አድርጋ ዋሸች ።

"በጣም ጀግና ልጅ ነሽ ። ወይዘሮ ሚድ አስፈላጊውን ነገር ሁሉ ከመሊድ እስክ እርሳት ያለውን ትረዳሻለች ። ድንገት ወይዘሮ ፒቲ አገልጋዮቹን ሁሉ ይዤ እሄዳለሁ ካለችም አሮጊቷን ቤት ሲን ምግብ እንድታበስልሳችሁ አልካታለሁ ። ብዙ ጊዜ እኮ አይ ደለም ልጁ በአምስት ሳምንት ጊዜ ውስጥ ይወለዳል ። ብቻ የመጀ መሪያ ጊዜ ስለሆነ ስለመጀመሪያ ልጅ እርግጠኛ ሆኖ መናገር አዳጋች ነው ያውም ይሄ ሁሉ የጥይት ገናብና የቦምብ ውርጅብኝ በሚወርድበት ጊዜ ። በየትኛውም ቀን ሊወለድ ይችላል ።"

@OLDBOOKSPDF

የመሄድና የመቅረቱ ጉዳይ በዚህ ሁኔታ አከትሞ ወይዘሮ ጢቲ ፓት ዕንባ በዕንባ ሆነው ፡ አጐት ጢቮርንና ኩኩን ይዘው ወደማከን ሄዱ ። ከመሄዳቸው በተጨማሪ ሲያስቡት ለቅሶዋቸውን ያጠናከረባቸው ደግሞ ከዚህ ቀደም በአርበኝነት ግንፋሎት ተገፋፍተው ለሆስፒታሉ በስጦታ መልክ ያበረከቱት አንድ ሠረገላና አንድ ፊረስ ናቸው ። ያኔ ወዲያውኑ የዐዕታቸው ቢሆንም አሁን ሆድ የሚያስብሳቸው ነገር ሆነ ። እስካርሌትና ሜላኒ ከትንሹ ዋድና ከፕሪሲ ጋር እቤት ቀሩ ። ቤቱ ከቀድሞው ይልቅ አሁን ብርቱ ሀጥታ ውጦታል ። የውጪው ቀኩስና የመጀ ጩኸት ግን እንደቀጠለ ነው ።

@OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ 19

በነዚያ የወረራው የመጀመሪያ ቀናት ያገራቱን መከላከያ ለማዳከም ያንኪዎች አዚህና አዚያ ሲሮጡ ፣ አስካርሌት ከፍርሃትዋ ብዛት ተኩሱን ላለመስማት እጆቹዋን ጆሮዋ ላይ አድርጋ ያለ ረዳት እየተ ወራጨች ከአሁን አሁን ለእንዴም ለሁሌም በታተኑኝ እያለች ስጋቷ ሰማይ ነካ ። የወርነቱን መቃረብ የሚያሰማውን የተኩስ አሩምታ ስትሰማ ፣ እየበረረች ወደ ሜላኒ ክፍል ገብታ አልጋው ላይ ተዘረረችና ከሜላኒ ጋር ተቃቅፈው ዋይ ዋይ ማለት ሆነ ። ፕሪሲ እና ዋድ ጓዳ ተደብቀው ሙለማው እንደሸረሪት ድር ተብትቧቸዋል ። ፕሪሲ ላንቃዋ እስኪሰነጠቅ ታጓራለች ። ዋድ ሕጭ እንቅ እያረገው አያስጉረ ለቅሶውን ያስነካዋል ።

ከላባ ከተሰራው ትራስ ላይ ተደፍታ ፣ ትንፋሽ እያጠራት ፊቷን ደፍታ ፣ ሞት አናቷ ላይ ያፏጫል ። እምድር ቤት ደህና በለላም እን ዳትቀመጥ ያቺን መከረኛ ሜላኒን ለማስታመም ፎቅ እንድትመጣ ስላደረገቻት ውስጥ ውስጡን እረገመቻት ። ግን ምን ይደረግ — ዶክተሩ እንዳትንቀሳቀስና አብራት መሆን እንዳለባት ነግሯታል ። ደሞ ገና ለገና እንደጨርቅ ይበላሳኛል ብላ ከፈራችው የጥይት አሩምታ አኩል ፣ የሜላኒ ልጅመጣ አልመጣ ስጋት ያሸብራት ጀምሯል ። ይሄ ሃሣብ በመጣባት ቁጥር ሆዷ ባናቷ ይንቀረቀራል ፣ እንደመአት ይንዘቀዝቃል ። ለመሆኑ ምጥ ቢጀምራት ምን ሊውጣት ነው ? መቼም እንደሐምሌ ዝናብ ከሚወርደው ጥይት መሃል ሄዳ ዶክተር ከምትፈልግ ሜላኒ ብትሞት ይሻላታል ። ነፍሷን አልጠላች በዚህ ተኩስ መሃል የምትሄድ ። ፕሪሲንም እንዳትልካት ነፍሷን ስትወድ እንደጉድ ነው ። ታዲያ ምጡ ቢመጣ ምን ልታደርግ ነው ?

አንድ ቀን ማታ የሜላኒን ራት እያዘጋጁ ሳሉ ጉዳዩን ለፕሪሲ ብታዋያት ፤ ያልጠበቀችውን መልስ ሰጠቻትና በጣም ተረጋጋች ፣ እፎይ አለች ።

"እትዬ ወ/ሮ አስካርሌት ፣ ዶክተሩን እንኳ በምጢ ሰዓት ባናገኘው አትጨነቂ ግደለሽም ፣ እኔ አዋልዳታለሁ ። ስለማዋለድ በደንብ አውቃለሁ ። እናቴ አዋላጅ ነበረችና እኔንም አዋላጅነት አስተምራኛለች ። እሱን ለኔ ተይልኝ ።" አለች ፕሪሲ ።

@OLDBOOKSPDF

ንስክርሌት ሦጣው ተለል አለሳት ።ማዋለድ የሚያውቁ እጆች አጠገብዋ በመኖራቸው ጭንቅትዋ ተቃለለ ።ግን ዶክተሩን ባንኖች እንዴት ጥሩ ነበር ።ከሚዘንብው የጥይት መዓት ለማምለጥ በጥድፊያ ዕብድ ሆና ፣ ወደ ሰላሙ አገር ወደ ታሪ ለመሄድ ከልክ በላይ በመ ቸኩልዋ ልጅ እንዲወለድና ለአሽሌይ የገባችውን የታል ዕዳ ተወ ጥታ አንድያዋን ለመሄድ እንደትችል በየማታው ትጸልያለች ።ታሪ ከዚህ ሁሉ ስቃይ መላላጊያ ሆና ታየቻት ።

እስክርሌት ታሪ ለመሄድ ፣ እናቷን ለማየት እንደጓጓች ለምንም ነገር ግዙታ አታወቅም ።ከእናቷ ከሌለን ጐን ከሆነች አለም ቢገለበጥ ማድ የላትም ።በየማታው ከልሰታቂው ቀንና ጀሮ ከሚሰነጥቀው የፈ ንጂ ጩኸት በኋላ ፣ "ቆይ ነገ ሚላኒን ፣ አትላንታ ለመቆየት ባለመ ቻሌ ፣ ወደ ታሪ እሄዳለሁ ።አንቺም ወደ ወ/ሮ ሚድ ቤት ሂጂ እላታ ለሁ ።" ብላ ታስብና ትተኛለች ።ግን ገና ትራስዋ ላይ በራስዋ ጋለል ስትል አሽሌይ የተሰናበታት ዕለት ፊቱ ላይ የንበረው ሀመም የተጫ ነው ፣ ሆኖም ፈገግታ ያላጣው —ሁኔታው ትዝ ይላታል ። "ሜ ላኒ አደራ አንቺ ጠንካራ ነሽ እና ታል ግቢልኝ" ያለው ያን ቃጭልባታል ።ታል ጣብታለች ።እንድ ቦታ አሽሌይ ሞቶ ተጋድሞ ይሆናል ።ባለበት ቦታ ሆኖ ቃሏን መጠበቅዋን በዓይነ ቁራኛ እያየ ይከተላታል ።ፍርም ይሁን ሞቶ ፣ የሆነችውን ትሁን እንጂ ቃሏን አትበላም ፣ አትክዳውም ።ስለዚህም የመሄድዋን ነገር ትታ ትቀመጣ ለች ።

ሌለን ፣ እስክርሌት ወደ ታሪ እንድትመጣ ለጸፈችላት ደብዳቤ ሁሉ ወረራውን አቅላና የሚላኒን ነፍስ ጠርነትና ወሩዋ መግባቱ ንም ጠቅሳ መልሳለች ።ሌለንም የሥጋም ይሁን የጋብቻ ዝምድናን አክብዳ ስለምታይ እስክርሌት እንደትተር ዋድና ፕሪሲ ግን ወደ ታሪ እንዲመጡ መስማማትዋን ጸፈችላት ።ይሄ ሃሣብ ከፕሪሲ — ኮሽ ባለ ቁጥር መደንገጥ ጋር ሲታይ ፣ ያለማወላወል ተቀባይነት አገኘ ። የወ/ሮ ሚድ ገረድ እቤት ባትኖር ኖሮ ልጆቹን ሁሉ ረብሻ አመጻ ቸውን አዙናው ነበር ።

እስክርሌት ልክ እንደእኗቷ ዋድን ወደ ታሪ የመላኩን ነገር በጣም ፈልጋዋለች ።ለልጇ ደህንነት ብቻ ሳይሆን እየፈራ ሲጮህ ስለ ሚያናድዳት ለመገላገልም "ሙምር ነው ።ዋድ ተኩስ በስማ ቁጥር በድን ይሆናል ።ሌላው ቀርቶ ተኩስ ሲያባራ እንኳ ሎሚሲን ጨም ድዶ ለማልቀስ ምንም አይቀረው ።ያንኪዎች ይመጡብኛል እያለ ፣ ወደ አልጋው መሄድ እንኳን ያስፈራዋል ። በየማታው በቱስታ የሚያ ሰማው የትገትና የድንጋጤ ድምጽ ከምትችለው በላይ ሆነባት ።

@OLDBOOKSPDF
አሷም ደብታ ነው እንጂ እንደሱው ትፈራለች ።ነገር ግን ይህንን የፈራችውን ፍርሃት የሚያስታውሳትን ፊቱን ስታይ ትጠላለች ። እም ፣ ለዋድ የሚሆን ቦታ ታራ ነው ። ፕሪሲ ይዛው ትሂድና ወዲያው ስማዋ ለዱ ሥራ ትመለስ ።

እርግዋ የፈንጂ ድምጽ ስትሰማ በድንጋጤ መዘለሏን ባታቋር ጥም እሚላኒ ትራስ ሥር እየጮኸች ሂዳ ራስዋን መቅበርዋን ትታለች ። አሁን ትንሽ ምራቋን ዋጥ አርጋ "ይሄኛው ቅርብ ነው አይደል ?" ማለት ችላለች ።

ሕይወት በሞራሽ ሲታመን የማይችል ሕልም እየመሰላት ስለ መጣም ፍርሃትዋ ቀነስ ብሏል ።እስካርሌት ኦሃራ ሞት በየደቂቃ ውና በየሰዓቱ ያዝኩሽ እያላት እሷ እዚህ ችላ መቀመጡዋ በሞራሽ ሊሆን የማይችል ነገር ነው ።የሕይወት ቅንጣት ክዝምታና ከሰላም ወደ ጩኸትና ረብሻ በዚህ ባጭር ጊዜ ተለወጠ ቢባልስ ማን ያምናል ።

ይሄ እንደሰመመን ያለ ፣ አሙንንት የሌለው ነገር ነው ። ጥርት ያለ የጠዋት ጭሀ ቅዳጅ ፣ ሰማያዊ ሰማይ እንዴት ባንድ ጀንበር በጋዝ ጢስ ታፍኖ መብረቅ ያዘለ ጥቁር ደመና ሲመስል ይችላል? እንዴትስ በእንቡጥ ድጌራዳና አንገታቸውን ቀና አድርገው እጅብ ብለው በሚታዩ ሮዝ አበቦች የታጀበ ሞታትና ብራ ቀን ፣ አሩምታ በግሪሳ የሚተምበት ፣ወዮታና ጩኸት የመላበት ፣የቦምብ ፍንጣሪና የብረት ስብርባሪ በሙቱ ሚትር ርቀት አየር ላየር የሚተራመስበትና ምድር ቀውጢ ሆና የሰውና የአራዊት ገላ እየተበጫቀ የሚፈናጠቅበት አስፈሪ ዕለት ሊሆን ይችላል ።

ምንም እንኳ ከጊዜ ጊዜ ጦርነቱ ጋብ ቢል የፒችትሪ ጉዳና አላረፈም ። ሕይወት ይላወስበታል ፣በየሰዓቱ ጩኸት ይሰማበታል ። የጠር—መኪናዎችና አምቡላንሶች ይተራመሱበታል ። ቁስለኞችን ከየ ምሽጉ ይጭናሉ ። ጦር ሠፈሮች በእጥፍ ፍጥነት ከቦታ ቦታ ይከተማሉ ። ከአንዱ ጉድጓድ በመጣ ትዕዛዝ ሰላ አካባቢ ጉድጓድ ይቆፈራል ።ወደዋናው የጦር ሠፈር የሚያቆስቁሉት መንገዶች የኮንፌዴሬሲው ሕልውና በነሱ ላይ የቆመ ይመስል ይስተካከላሉ ። ይደለደላሉ ።

የሞቀው ጨለማ ጸጥታማ ቢሆንም ለነገ ያረገዘው ስለማይታመቅ ማበፈራቱ አልቀረም ።ጨለማው ጸጥ ከማለቱ የተነሳ እንቁራሪቶችና የሌሊት ወፎች እንኳን ትንፍሽ ለማለት የፈሩ ይመስላል ። አሁንም አሁንም ከራቅ ጨለማውን የሚሰነጥቅ የተኩስ ድምጽይሰማል ።

ብዙ ጊዜ ሌት ውድቅት ላይ ፋኖስ ሁሉ ከጠፋፋና ሜላኒ ከተኛች በኋላ ከተማውን ዝምታ ሲጫጫነው ፣ አስካርሌት እንደተደመች

@OLDBOOKSPDF
እንቅልፍ አልወስድ ብሏት ስታጫንጭ ፣ የፊት ለፊቱ በር ሲከፈትና ፈጠን ያለ እርምጃ ሲመጣ ይሰማታል ።

ነገር ግን እስካርሌት ሁለቱን ወደ ታራ ከመላኳ በፊት ፣ያንኪ ዎቹ በአትላንታና በጆንስቦሮ መሃከል ዞረዋል የሚባል ወሬ ሰማች። ድንገት ዋድና ፕሪሲን ይዞ የሚሄደውን ባቡር ቢይዙትስ?...ያንኪ ዎች በሴቶች ላይ ካላቸው ጭካኔ ይልቅ በሕጻናት ላይ ያላቸው ጭካኔ ይከፋል ሲባል ሰምተው ስለነበር ይሄ ወሬ በጠበሳቸው። ስለዚህ ፈራችና ዋድ እዛው አትላንታ እንዲቆይ አደረገች ። በጣም የተደናገጠና የእናቱን ቀሚስ ለደቂቃ እንኳ መልቀቅ የሚያስፈራው ትንሽ ጣረ ሞት ልጅ ነው ።

የወረራው ጦርነት በሞቃቶቹ የሐምሌ ቀናት — ቀን ቀን ይካሄዳል ።ቀንቀን የመድፍ ሙዚረቅ ይድብለቀለቃል ፣ የባሩድ እሳት ይነበለበላል ።ማታ ማታ ጸጥ አርጭ ይላል ።ከተማው ሁኔታውን አይቶ ማታ ማታ መደላደል ጀምሯል ።የመጨረሻው አስከፊ ነገር ማለፉ እንደሆነ ሁሉ ፣የመጨረሻው አስቃቂ ቁጣ መሄዱ እንደሆነ ሁሉ ፣ ሌላ ይመጣብናል ብለው የሚፈሩት ነገር አልነበረም ። ወረራን ይፈሩ ነበር — ይሸው እያዩት ነው ፣ግን ይሄን ያህል ክፉ አልነበረም። ሮኑ እንደወትሮው ከፋም ለማም ቀጥሏል ። እሳተ ገሞራ ላይ እንደተቀመጡ ያውቃሉ ፣ግን እስኪፈነዳ መጠበቅ እንጂ ምን ማድረግ ይች ላሉ ? ስለዚህ ለምኑ ነው ጭንቀቱ ?ወይ ክንጭራሹ አይፈነዳ ይሆናል ።ጀኔራል ሁድ ያንኪዎቹን እንዴት ከከተማው ውጪ እንዳቆያቸው ማየት ነው ።ጀግኖቻቸው ወደ ማዝን የሚወስደውን ባቡር መጎንድ እንዴት ጣትረው እንደያዙ ማየት ነው ።ቬርማን በጭራሽ አይነ ካትም ።

ጸሩ ግን ምንም እንኳን የጥይቱ ጋጋታና የስንቁን ማጠር ቸል ቢሉት ፣ምንም እንኳን ከማማሽ ማይል ርቀት ላይ ያሉትን ያንኪዎች ቢንቁ ፣ ምንም እንኳ በተበታተኑትና ምሽግ ውስጥ ባሉት ግራጫ ለባሽ ወታደሮቻቸው ላይ ወደር የሌለው እምነት ቢኖራቸው ፣ አትላንታ ደጃፍ ፣አትላንታ ቆዳ ሥር ነገ ምን ይመጣ ይሆን የሚል ጥር ጣሬ ያፏጫል ። የልብ መንጠልጠል ፣ ጭንቀት ፣ ሐዘን ፣ረሃብና...እንዴ የመውደቅ — እንዴ የመነሳት...ደሞ መልሶ የመንደባለል ፣እንደገና ቀና የማለት ተስፋ ውጋት ፣ የእትላንታን ቆዳ እየገፈፉት ነው ።

ቀስ በቀስ እስካርሌት ከጀግኖቹ ፊት ድፍረትን እየወሰደችና ተፈጥሮ ደግ — መድሀን የሌለውን ነገር መቻል ብቻ እንደሚያቀል — አሳምሮ ሲያሳያት ፤ ጸናቱን አገኘች ።

@OLDBOOKSPDF

ሁሉ ጊዜ ፊታቸው የማይታይ ወታደሮች በረንዳው ላይ ጥቁር ለብ ለብ ይቆሙና ድምጽ ያሰማሉ ።አንዳንዴ የሠለጠነ ትሁት ድምጽ ከጨ ለማው ውስጥ —"እመቤት ረበሽኩዎት በጣም ይቅርታ እጠይቃለሁ... እባክዎ ለእኔና ለፈረሱ የሚሆን ውሃ እንዳለዎት?" ይላታል ። አንዳ ንዴ እንደተራራ የከበደ ድምጽ ይሰማታል ። አንዳንዴ ከሩቅ ደቡብ የሚመጡ ጥሬ ባላገሮች ድምጽ ፣ አልፎ አልፎም ከዳር አገር የመጡ ሰዎች ለብ የሚነካ ንግግር ፣ የእናቷን ድምጽ ያስታውሷታል ።

"እመቤት ይሄ ጓደኛዬ እፈረሱቹ ማርማም ድረስ ይዞኝ እንዲ ሄድ ነበር ግን አልቻለም ፣ሊያስገቡልኝ ይችላሉ ?"

"የኔ እመቤት እንደሚረዱኝ ተስፋ አለኝ ።ትንሽ የበቅሎ ጥሬ ቢለግሱኝ ይገዳዎ ይሆን?"

"እሜቴ ሰላስችገርኩዎት ይቅርታ ፣ ይህን ሌሊት እግቢዎ ባርፍ ይፈቅዱልኛል ? የደጅዎን ሮዝና ጽጌረዳ አይቼ እቤቴ እንዳለሁ ሁሉ ቱጽናናሁ.....።"

የለም እነዚህ ግታዎች እውን አይመስሉም ። አዎ ፊታቸውና ማንነታቸው የማይሰይ በደከመ ድምጽ የሚያታስቱ ሰዎች ያሉበት የሕልም ምሽት ይመስላል ። ውሃ ማጠጣት ፣ ምግብ ማብላት ፣ ትራስ ማቀበል ፣ቁስል መጠገን ፣ የሚጎዙን የተበሳሰ አራስ መያዝ... በፍፁም ፣ የሱዋ ሥራ ሊሆን አይገባውም ነበር ።

አንድ ቀን በሐምሌ ወር መጨረሻ ግድም አገኘት ሔንሪ ሀሚል ተን በውድቅት መጣ ። አገኘት ሔንሪ ጀንጥላውንና ሻንጣውን ይዞ አልመጣም ።ያ ትልቁ ቦርሳውም ቢሆን በጣም ቀንሷል ።መሉ የነበረ ው የፊቱ ቆዳ አሁን ተጨማዶ ተንጠልጥሏል ። ረዥም ነጭ ጸጉሩም ቢሆን ለመግለጽ ከሚቻለው በላይ አድጏል ። ከሞላ ጎደል ባዶ እግ ሩን ነው ለማለት ይቻላል ። ተባይ ከላይ እስከታች ይፈላበታል ። ርበ ታል ።ይሄ ሁሉ ሆኖ ጠንካራው መንፈሱ ፍንክች አላለም ።

ምንም እንኳ "እኔን የመሰሉ አሮጌ ሰዎች የሚዋጉበትና ጠመ ንጃ የጨበጡበት ምን ጦርነት ነው! የጅል ውጊያ ነው!" ቢልም ቅሉ የተደሰተበት ይመስላል ። ልክ እንደወጣቶች ሁሉ እሱም ለጦርነቱ በማስፈለጉ እንደወጣቶቹ ሊዋጋ ፣የወጣቶችን ሥራ ሊሠራ ሄደ ። ከዛም በላይ ደግሞ እንደሽማግሌዎቹ ከንአያት ሚሪዊዘር ይልቅ እሱ ከወጣቶቹ ጎኩል ሊዋጋ እንደቸሚል ይናገራል።...የአያት ሚሪዊዘር ሪህ በጣም አስ ቸግሯቸው ስለነበር የጦር አዝማቹ ሻምበል ሊያስወጣቸው ነበር ። እሳ ቸው ግን በጀ አላሉም ። ከአማቾቹው ልጅት ጫሚታ ይልቅ የሻምበሉ ስድብና ማመናጨቅ ይሻለኛል ባይ ሆኑ ። ሲጋራ አታጭስ ፣ ጠጅህን

@OLDBOOKSPDF

ተላጭ ፣ እያለች የልጃቸው ሚስጥ በሚስጢሎቻቸው ፣ ጠር ሚያ መቆየቱን መረጡ ።

የአገኟቸው የሄንሪ ጉብኝት አጭር ነበር ። ያራት ሰዓት ብቻ ፍቃድ ተሰጥቶአቸው ነው የመጣው ።ለሀውም ከሰዓ ውስጥ ከፈሉን በየ ጉድጓዱ ውስጥ ለሚዘዋወርበት የአግር ጉዞ ቅጥበ ነው ።

"ልጅት እንግዲህ ብዙ አልቆይም" አሰ ፣ ሚሳኒ መኝታ ቤት ቁጭ ብሎ እግሩን አስካርሌት ያቀረበችለት ሞዝቃዛ ውሃ ውስጥ ነክሮ እያወዛወዘ ።

"የኛ ቡድን ነገ በጠዋት ይንቀሳቀሳል ።"

"የት?" አለች ሚላኒ በድንጋጤ ከንዱን ጭምድድ አድርጋ ።

"እጅችሽን ተይ" አለ ሄንሪ በንዴት ። "ተባይ በተባይ ሆኛለሁ ። ተባይና ተቅማጥ ባይኖርበት ኖሮ ጦርነት የሽርሽር ጉዞ በሆነ ነበር ። የት ነው የምትሄደው? ሳልቪው ግን እርግጥ አልተነገረንም ፣ ግን አሳምሬ መገመት እችላለሁ ። እንዳው በጣም ተሳስቼ ካልሆነ ነገ ጠዋት ወደ ደቡብ ማለትም ወደ ጅንስቦሮ ነው የምንሄደው ።"

"እንዴ ? ለምን ወደ ጅንስቦሮ?"

"ምክንያቱም እዚያ በጣም ከባድ ውጊያ ይኖረናል እትዓለም ። ያንኪዎቹ ከቻሉ ያንን ባቡር መንገድ ለመያዝ ነው የሚጣጣሩት ። የባቡሩን መንገድ ከያዙ ደግሞ አትላንታ ደሀና ሁኝ ማለት ነው!"

"በጉዴ — ወጣሁ! ግን መያዝ ይችሉ ይሆን?"

"ኤይ ወዲያ ዝምበሉ! እንዴት ብለው ? እኔ እያለሁ" አለ ወዲ ተደናገጠ ፊታቸው ኮስተር ብሎ እያየ ። ከዚያ የባስ ተኩሳተረ "በጣም ከባድ ውጊያ ይሆናል ፣ ልጅት ማሽነፍ አለብን ። መቼም ወደ ማክን ከሚወስደው አውራ ጐዳና በቀር ሁሉንም መንገዶች ይዘዋል ፣ ያ ብቻ አይደለም ።እናንተ አታውቁ እንደሁ እንጂ ፣ ያንናንዷን ጠባብ መንገድ ፣ እያንዳንዷን የከባድ መኪና መንገድና ናቢቡት መን ገድ ሳይቀር ፣ የማክደኑን መንገድ ትተው ፣ ሌላውን ይዘዋል ። እና ያን አውራ መንገድ ከነጠቁን አለቀልን ማለት ነው ።አትላንታ በትልቅ ቦርሳ ውስጥ ነው ያለችው ። የቦርሳው ማሰሪያ ጣመድ ውስ የተሸመ ረው ጅንስቦሮ ላይ ነው ። የጅንስቦሮውን ጐዳና ከያዙብን ጣመዱን እንደልብ መሳብ ስለሚችሉ የስቅላቱ ሽምቀቆ አንገቱ እንደገባ ሰው ያደርገናል ። ስለዚህ ያንን ላለማስያዝ የሞት የሽረት አልሞት ባይ ተጋዳይ ውጊያ እናካሂዳለን ።...እንግዲህ በትንሽ ጊዜ ውስጥ እሄ

@OLDBOOKSPDF

ለሁ ልጅች ። ሚለ ፡ የመጣሁት ልስናበታችሁና እስካርሌት ካንቺ ጋር መኖሩዋን ለማረጋገጥ ነው ።

"እንዴ ፡ ከኔ ጋር ለመሆንዋ ምን ጥርጥር አለው ፡ብቻ እጮት ሄንሪ በተቻለህ ራስህን ጠብቅ ።"

እጮት ሄንሪ እግሩን በብጭቃጫቂ ጨርቅ አጾራረቀና ጉሮሮ ውን እያጠራ የተቀዳደደ ጫማውን አጠለቀ ።

"መሄዴ ነው ፡ ልሂድ እንግዲህ" አለ ። "ነና አምስት ማይል የኤ ግር ጉዞ አለብኝ እስካርሌት ። እሰቲ ቤት — ያፊራውን እንዴሚሆን አርገሽ ስንቂን ስንቂልኝ ፡ ምንም ይሁን ይሆነኛል ።"

ሚላኒን ስም ደሀና ሁሂ ካለ በኋላ ወደ ማድቤት ሄዶ እስካር ሌት የበቆሎ ሽልጦና ጥቂት በመሀረብ ቢጠ የተጠቀለሉ ፍራፍሬዎች ስታዘጋጅ አገኛት ።

"እጮት ሄንሪ . . . እውነት . . . ይሄን ያክል . . ይሄን ያክል አስገ. ነው እንዴ?"

"አስገ. ነወይ ሽረ በየሃው!— እንዴታ ! ጅል አትሁኚ ! የመጨረሻው ገደል አፋፍ ላይ ነው ያለነው ። አልቆልናል እኮ !"

"ታራ የሚደርሱ ይመስልሃል?"

"እንዴት ብለው" አለ እጮት ሄንሪ ስንት ትልቅ ጉዳይ እያለ ስለራሷ. ቤት መጨነቋም አይ የሴት ጭንቅላት ፡ አይ የሴት ነገር እያስኘው ። ብቻ የተደናገጠ ፊቷን ሲያይ ለስለስ አለ ።

"በጭራሽ አይደርሱም ። ታራ ከአውራ ጐዳናው አምስት ማይል ይርቃል ። ያንኪዎቹ ለመያዝ የሚፈለጉት ደግሞ አውራ መንገዱን ነው ። እንዳው አታስቢምና የኔ አመቤት ። " ከዚያ በፍጥነት ቀጠለ" ይሄን ሁሉ መንገድ በእግሬ ተጉዤ የመጣሁት እንዳው ደሀና ሁኑ ለማለት አይደለም—ለሜላኒ መርዶ ይገፎ ነው ። ብቻ እንዴት እንደምነግራት ቸግሮኝ ዝም አልኳት ። ስለዚህ ላንቺ ጨንገርሽና አንቺው ንገሪያት እንግዲህ ። "

"አሽሌይ ደሀና አይደለም እንዴ? ምን ሰማህ? ሞ... ሞተ አሉህ እንዴ?"

"ምን ሆንሽብኝ በተበሮ ጉድጓድ ውስጥ እስከ ሙታኑታዬ ድረስ በጭቃ ተዘፍቆ ከርሚ እንዴት ብዬ ነው ስለአሽሌይ የምሰማው ?" አለ ሽማግሌው ሄንሪ ። "የለም አባቱ ነው ። አባቱ ጆን ዊክስ ሞተ ። "

@OLDBOOKSPDF

አስካርሴት ለምሳው የሠላቀችውን ስንቅ ግማሽ እንደጠቀለለች እቁማ ውዝፍ ብላ ቁጭ አለች ።

"ለሚላኒ ላረዳት ነበር አመጣጤ ፣ ግን ወሬዬ ከዳኝ ። እንቺ ንግሪያት ። እንቺ ይሄንንም ስጪያት ። "ከኪሱ ማህተምና የሚቹ ባለ ቤት የወ/ሮ ዊክስ ጉርድ ፎቶ ያለበት ትልቅ የወርቅ ሰዓት አወጣና ሰጣት ። የሰዓቱ ማስቀመጫም ከነቁልፉ አብሮት አለ ። ያንን ጅን ዊክስ እጅ ላይ ሺ ጊዜ ያየችውን ሰዓት ስታይ የአሽሊይን አባት መሞት ማረጋገጫ ሆኖት ። ለማናገርም ሆነ ለማልቀስ ተሳናት ። አፍዋ ተሳሰረ ። አጎት ሄንሪ ኡሁ ኡሁ እያለ ፣ ስታለቅስ እንባዋን አይቶ እንዳይረብሸው ቀና ብሎ ሳያያት፡—

"ጅማና ሰው ነበር ፣ አስካርሴት ። ይህንንም ለሚላኒ ንገሪያት። ለልጆቹም ትዳፍላቸው ። በዚህ ዕድሜው መቼም ማሩም ወታደር ነው። አንድ ፈንጂ እሱን ከነፈረሱ አገኘው ። ፈረሱ አልሞተም ነበር ። እኔው ነኝ የጨረስኩት ። የሚያሳዝን ፍጥረት ። ደህና ፈረስ ነበር ። ለወ/ሮ ታርሌተን ስለሱም ጸፊላት ። መቼም ስትሰማ ታዝናለች ። በይ ስንቁን ጠቅልይልኝ የኔ ልጅ ። መሄድ አለብኝ ። ይሄን ያህል አትጨነቂ ። የወጣት ሰው ሥራ ሲሰራ ከመሞት የበለጠ ለሽማግሌ ምን የተሻለ ሞት ይገኛል ። ?"

"ዉ ፣ መሞት አልነበረበትም ። ወደ ጦርነትም መሄድ አይገባውም ነበር ። በሕይወት ቆይቶ የልጅ ልጁን እያየ አልጋ ላይ እንዳለ በሰላም መሞት ነበረበት ። አዬ ሰምጌ ሄደን በመጓጠል አያምን ። ጦርነቱንም ይጠላው ነበር ። . . . ሆኖም . . . " ስትል አጎት ሄነሪ አቋረጣት፡—

"ብዙዎቻችን የምናስበው ይሄንኑ ነው ግን ምን ይደረጋል" አፍንጫውን ተናፍጦ ቀጠለ ። "ለመሆኑ ስታስቢው በዚህ የእርጅና ዳዬ ሰዓት ራሴን ለያንኪዎች ጥይት ኢላማ የማደርገው ወድጄ ይመስልሻል ? ግን እንደምታይው ዛሬ ጊዜ ለወንድ ልጅ ምን ምርጫ ይኖረዋል ? በይ ሳሚኝ የኔ ልጅ . . . አይዞሽ ፣ ስለኔ በጭራሽ አትጨነቂ ይህን ጦርነት በሰላም እንደምወጣው አምናለሁ ።"

አስካርሴት ሳመችውና ቁልቁል ደረጃውን ወርዶ ጨለማ ሲለብስ የደጃፉ በር ሲከፈት ተሰማት ። ባዶ እጅዋን ግትር ብላ ለተወሰኑ ደቂቃዎች ቆመች ። ከዚያ ለሚላኒ ለመንገር ደረጃውን ወጣች ።

* * *

ሐምሌ መጨረሻ ላይ አጎት ሄንሪ እንደገመቱው ያንኪዎቹ እገዳና ወደ ጅንስቦሮ ተመልሰዋል የሚለው መጥፎ ወሬ ተሰማ ። ከከተማው ግርጌ አምስት ማይል አካባቢ የባቡሩን መንገድ ቆፍ

@OLDBOOKSPDF

ጠውት ነበር ። ሆኖም የኮንፌዴሬሲው ፈረሰኞች ተጋትረው አጥ ቅተው አባረሩዋቸው ። የመሐንዲስ ክፍል ወታደሮችም እንደዚያ እናት በሚበሳው ጠራራ ጸሐይ ሳባቸውን እያንቆረቆሩ የባቡሩን መን ገድ ጠገኑት ።

እስካርሌት በድንጋጤ መንፈሷ ተዘበራርቆባታል ። ለሶስት ቀናት ያህል ፍርሃት እየናጣት ወሬ ስትጠብቅ ከርማለች ። እግዚሀር ይስ ጠው እንድ የሚያጽናናት ደብዳቤ ከጂራልድ ተልኮላት ኖሮ ደረሳት። ጠላት ታራ አልደረሰም ። የወርነቱን ድምጽ ከሩቅ ይሰማሉ እንጂ እንድም ያንኪ አይተው አያውቁም ።

ጂራልድ ያንኪዎች የባቡር መንገዱን እንዲት እንዲበቁ እንደ ተደረጉ ሲጽፍ ፡ ስድብ ፡ ጉራና ድንፋታ ከማብዛቱ የተነሳ አራሱ በገዛ እጁ ጠራርጎ ያባረራቸው ይመስላል ። በተከታታይ ባሉ ሶስት ገጾች ላይ የወገንን ጥንካሬና ጀግንነት ሲተነትን ቆይቶ ወደ ደብዳቤው መጨረሻ ላይ ባጭሩ የካሪንን መታመም ይገልጻል ። ወ/ሮ አሃራ እንዳ ለቸው በሽታው ታይፎይድ ነው—የእንጀት ተበቦ ። ብቻ በጣም አልታመመችም ። እስካርሌትም በሙራሽ መጨነቅ የለባትም ። ያም ሆነ ይሀ ግን መንገዱ እንኳን አያሲጋም ቢባል በምንም ዓይነት ወደ ቤት የመምጣት ሃሳብ እንዳይኖራት ያስጠነቅቃታል ። እናቷን ወ/ሮ አሃራንም በዚህ በወረራ ሰዓት እስካርሌትና ዋድ አለመምጣታቸው በጣም አስደስቷታል ። እስካርሌት እዛው ባለችበት ወደ በተከሲያን እየሄደች ለካሪን መፀለይዋ አስፈላጊ መሆኑን ወ/ሮ አሃራ አደራ ብላለች ፡ ይላል ።

እስካርሌት ቤተክርስቲያን ከሄደች ወራት ያለፉ በመሆኑ ይሄ የመጨረሻው ጥያቄ ሕሊናዋን ገረፋት ። ዱሮ ከቤተክርስቲያን መራቅ የመጨረሻው ሃጢያት ነው ስትል ነበር ። እየዋለች እያደረች ግን እንደዱሮው ሃጢያቱ በርክቶ አይታያትም ። ያም ሆነ ይሀ የእናቷን ትእዛዝ አክብራ ወደ ክፍሏ ገብታ ጸሎት ጀመረች ። ጸሎቱን ጨርሳ ከተንበረከከችበት ስትነሳ እንደወትሮው ከጸሎት በኋላ የሚሰማት ምኞትና የመንፈስ አፎይታ አሁን አልተሰማትም ። ለጥቂት ጊዜ ፡ ምንም እንኳ በሚሊዮን ለሚቆጠር ጊዜ ቢጸለይም ፡ እግዚሀር በየቀኑ የሚላ ኩትን ልመናዎች አልሰማቸውም ። እሷንም ፡ ኮንፌዴሬሲውንም ሆነ ደቡቡን ቸል ብሏል ።

የዚያን ለት ማታ ከፊት ለፊቱ በረንዳ ላይ የጂራልድን ደብ ዳቤ ደረቷ ላይ ጥበቅ አድርጋ ይዛ ተቀምጣ ነበር ። ደብዳቤውን ወደ ደረቷ ጥብቅ አድርጋ በያዘች ቁጥር ታራንና ኤለንን ወደርሷ የበለጠ ያቀረበቻቸው ይመስላታል ። ከእልፍኙ በመስኮት በኩል የሚመጣው

@OLDBOOKSPDF

የፋኖስ ብርሃን በወይን ሐረግ በተሸሳለሙው ደብዛዛ በረንዳ ላይ እንግዳና ልዩ የሆነ ወርቃማ ጥላውን አጥልቷል። በወይን ሐረግ ላይ እየተንጫለሉ የሚወጡ የሚመስሉት ቢጫ አበቦችም የሚያምር ጥንጥቅ ጥቅ ቀለም ባለው ግድግዳ የተከበበች አስመስሰዋታል። ምሽቱ ወጭ አርጭ ያለ ነው። ጀምበር ከጠለቀች ጀምሮ አስካሁን ድረስ አንዲት ጥይት እንኳ ጠሽ ስትል ባለመሰማቷ ዓለም በጣም ሩቅ ቦታ ያለ ይመስላል። አስካርሌት ወንበሩ ላይ ወደራት ወደኋላ እየተወዛወዘች ያን ከታራ የመጣ ደብዳቤ ካነበበች ወዲህ የሚሰማትን የብቸኝነት ስቃይ ስሜት ታስተናግዳለች። ምነው ዛሬ አንድ ሰው፣ ማንም ይሁን ማ ብቻ አንድ ሰው፣ ወ/ሮ ሜሪዌዘር እንኳ ብትሆን፣ አጠገቧ በኖረች እንዴት ደስ ባላት፣ ጸሩ ምን ያደርጋል ወ/ሮ ሜሪ የሆስፒታል የሰሊት ተረኛ ናቸው። ወ/ሮ ሚድ ደግሞ ፊል ከጦር ግንባር ስለመጣ ለሱ የደስደስ ጣብጣ እያዘጋጀች ነው። ሜላኒም ተኝታለች። ባጋጣሚ እንኳን እግር የሚጥሰው ሰው ጠፋ። ይህን ሰሞን ጠያቂ ምጅ ሁሉ የሉም። ምክንያቱም ዜአግሩ የሚጓዝ ሰው ሁሉ ወይ በጥይት መሃል መጓዝ ይኖርበታል፣ አሊያም ጀንሰቦሮ ከለለ አካባቢ ያንዜ ምችን ሊያሳድድ ገጠር ገብቷል።

እንዲህ ያለ ብቸኝነት ሁልጊዜ በለማይገጥማት የዛሬውን አል ወደደችውም። ብቻዋን ከሆነች ማሰብ አይቀርም። ዛሬ ጊዜ ደግሞ ምንም ደስ የሚል የሚታሰብ ነገር የለም። እንደማትኝውም ሰው ልማድ አድርጋ የምታስበው የጥንቱን፣ ያለፈውን ቀን ነው — የሞተውን።

ዛሬ ማታ በዚህች ጸጥታ በዋጣት ዝምተኛ አትላንታ ውስጥ ቁጭ ብላ፣ ዓይኖቹዋን ከድና፣ ራሷን በታራ የገጠር እርጭታ ውስጥ ከታ፣ ስለዚያኛው ሕይወት ታልማለች። ጉሮ እንዳልተሰወጠ ሆኖ ይታ ያታል። የማይለወጥም ሆኖ ይሰማታል። ሆኖም የመጀር ጉሮ እንዳ ጥንቱ እንደጠዋቱ ሆኖ እንደማይቆይ ኅሊ ልቡዋ ያውቀዋል። አራቱን የታርሌተን ቤተሰብ ሰዎች፣ ባለቀይ ጸጉሮቹን መንትዮች፣ ቶምና ቦይድን፣ አሰላሰለቻቸውና እንድ ጉሮሮዋን የሚያንቅ አሳዛኝ ስሜት አስጨነቃት። ወይ ጉድ! ወይ ስቱዋርትን፣ ወይ ብሬንትን ማግባት ነበረባት እኮ። ከእንግዲህ ወደ ታራ እንኳን ብትመለስ በአርዘሊባኖስ ዛፎች ማህል ባለው የግቢዋ መንገድ እየጋለበ መጥቱው የሚጠይቃት፣ እንዴት ነሽ የሚሏት ጉሪምሶች ድምጽ አይኖርም። ደሞም ሬይፎርድ ካልቨርት፣ ያ — ተዓምራዊ እንቅስቃሴ ባለው ለዛ የሚደንስ ልጅ — ከእንግዲህ ከሴቶቹ ሁሉ መርጦ ነይ እንደንስ አይላትም። በዛ ላይ እነዚያ የሙንሮ ቤተሰብ ልጆች፣ ትንሹ ጀ ፎንቴንና . . .

"ወይኔ አሽሌይ! ወይኔ አሽሌይ!" ጭንቅላቷን በመዳፎቿ ውስጥ

@OLDBOOKSPDF

ቀብራ ተንሰቀሰቀች ። "ካንተ ተለይቼ መኖርን በጭራሽ ልለምደው አልችልምኮ!"

የውጪው በር ሲከፈት ሰማችና በፍጥነት ቀና ብላ አይኑዋን ጠራርጋ ተመለከተች ።ተነስታ ብታይ ሰፈ ባርኔጣውን በጁ ይዞ ሬት በትለር ደረጃውን ሲወጣ አስተዋለች ። ባለፈው ጊዜ ከጋሪው ላይ ወርዳ እየተመናቀረች ጥላው ከሄደች ወዲያ አማኝታው አታውቅም። በሩይቭ ፖይንት ገዳና ላይ ከሃችው ወዲያ በጭራሽ አላየችውም ። ያኔ አይንህን እንዳላይ ብላው ነበር ። አሁን ግን አንድ ሰው አጠገቧ እንዲኖር ስትመኝ ፡ ስለአሽሊይ ከማሰብ የሚያድናት አንድ ሰው ባገኘሁ ስትል ፡በመምጣቱ ተደስታ ያለፈውን ውሳኔዋን አጎሳችው ። እሱም ያለፈው ጥላቻውን ፣ ረስቱም ይሁን የረሳ በማስመሰል እንጃ ፣ እፊቷ ተደላድሎ ቆመ ።

"ወደማክን አልተሰደድኽም ሰካ! ወ/ሮ ፒቲ ማፈግፈግሞን ሰምቼ እንቺም የሄድሽ መሰለኝ ነበር ። የቤትሽ መብራት ሲበራ አይቼ መኖር አስመኖርሽን ለማጣራት ነው የመጣሁት ።ለምን ቆየሽ!"

"ከ ሜላኒ ጋር እንድሆን ብዬ ነው ። አየህ . . .አሁን እሷ... ተሰድዳ መሄድ በምትችልበት ሁኔታ ላይ አይደለችም ።

"ኧረ ጉድ ፈልቷል" አለ ። በፋኖሱ ብርሃን ከባድ ድንጋጤ እንደያዘው ይታያታል ። "ወ/ሮ ሜሊ እስካሁን እዚሁ ናት እንዳትይኝ ፣ እንደዚህ ዓይነት የማይረባ ነገር ፡ እንደዚህ ያለ ድንቁርና አይቼም ሰምቼም አላውቅ ። በዚህ ሁኔታዋ እንዴት እዚህ ትቆያለች ። በጣም አደገኛ ነው ።"

እስካርሌት ስለሜላኒ ሁኔታ ከወንድ ጋር መወያየት እንደማይ ገባ በማሰብ ትንሽ ተደናገራት ። ሬት ፣ ለሜላኒ አደገኛ ነው ሲል ገረማት ።እንዴት አንድ ወንደላጤ ይህን ሊያውቅ ይችላል ?"

"ስለእኔ ደህንነት ባለመጨነቅህ ግን ታሳዝናለህ" አለች ። በት ዝብት በመገረም ዓይን አያት ፣

"ለአንቺ እንኳን መቼም ቢሆን ከያንኪዎች ጋሻ እሆንልሻ ለሁ ።"

"ምን ያህል በእርግጥ ልትደግፈኝ እንዳሰብክ ለማመን ያስ ቸግራል" አለች በመጠራጠር ።

"አስተማማኝስ አይደለም።"አለና መለሰ"ግን አንቺ መቼ ነው ለአስተማማኝ ድጋፉቸው ማረጋገጫ ከወንዶች አፍ መጠበቅ የምት ተይው ?"

@OLDBOOKSPDF

"ልሞት አልኝ ላይ ሰማጥር ነው የምሁመው" ብላ መለሰች ፣ ራት እንኳን እምቢ ቢላት ሊያማቅጥት የሚችሉ ብዙ መንገዶች ይኖራሉ ብላ በመተማመን ።

"ከንቱነት ፡ ከንቱነት ነው ሁሉም ቢያንስ ቢያንስ እትጨን መጥገርሽ ጥሩ ነው "አላት ።የሰጋራ ጎኑውን ከፈተና አንድ ሲጋር አውጥቶ ወደ አጥንጫው አስጠግቶ ለጥቂት ጊዜ ያዘው ።ወደ ጭሳ ቆሞም ከብሪት ጭር በአጄ ብርሃኑን ከለለው አቀጣጠሰና ዝም ብሎ ማጨስ ጀመረ ። እስካርሌት እመንበሩዋ ላይ እንዳለች ወደራት ወደ ኋላ ትላለች ። የማታው ጨለማ ያዘለው ዝምታ ዋጣቸው ። የሉሊት ወፍ በሮዝና በጽጌረዳ አበባዎች አናት ከአንድ አበባ ወደሌላ እየዘለለች ድምጽ ታሰማለች ።ወዲያው አካባቢውም እንደነሱ በነጉሩ ላይ የሚያርብ ይመስል ጾም አርጭ አለ ።

ራት ጨለማው እንዳጠላበት በለዘብታ ሳቀና ፣

"እና ከወሮ ሚሲ ጋር ቆየሽ እዛ ይዜ መቼም አጋጥሞኝ የማያ ውቅ እንግዳ ነገር ነው ።"

"አውን ምን አዲስ ነገር አየህ አዲስ ነገር የለውም" አለች ፣ ምኞቷን አጥቃ ግን ነቃት ሳይነጋስላት ።

"ነው እንዴ፣ እንግዲያው ከሰብአዊነት ውጭ የሆነ አመለካከት ያንሰራል ማለት ነው ።ለረሻሆም ጊዜ ፣ከሚሳኒ ጋር መቀመጥ አያስችልሽም የሚል ግምት ነበረኝ ፤የማትረባ ልጅ ነሽ ብለሽ ስለም ታስቢና ስለጀግንነት የምታወራው ያታክትሽ መስሎኝ ስለንበር ትዕግስትሽ ያልቃል ባይ ነበርኩ ።መቼም ባጥንቸው ቀጭጨ ሁሉ እሷን ከማነጋገሰስ ወደ ኋላ አትይምና በዚህ የተከሰስ ወርጅብኝ ማህል አብረሻት መቀመጡን ትመርጣለሽ ለማለት ያስቸግራል ። ስለዚህ ነው እንግዳ ነገር የሆኑብኝ ።ግን እንዴት እንዲህ ልታደርጊ ቻልሽ?"

"የቻርሲ እህት በመሆኑዋና... ልክ እንደእህቱ ስለማያት ነዋ!" ብላ መለሰች በክራት ፤ ምንም ጀሮ ግንድዋ ቢማል ።

"የአሽሌይ የጠጉት ሚስት ስለሆነች ማለትሽ ነውን?"

እስካርሌት ንዴቱዋ እየተናነቃት ከመቀመጫዋ ብድግ አለች "ላለፈው አጉል ጠባይህ ይቅርታ ላደርግልህ ስሞክር ደግሞ ታጥቦ ጭቃ ሆንክ ።በጭራሽ ደጀን እንድትረግጥ መፍቀድ አልነበረብኝም እንደው ሀሳብ ልቤን ባቆሰለው ስዓት በመምጣትህ ነው እንጂ..."

"ቁጭ በይና ተረጋጊ ።" አላት ድምፁን እየለወጠ ። ወደኋ ተመጋና መልሶ መቀመጫዋ ላይ ሳብ አድርጎ አስቀመጣት ።" ለምን ድንው ሐዘን የጣሽ" አለና ጠየቃት ።

@OLDBOOKSPDF

“አይ ከታራ ይህቺ ከሆነች ነው። ያንኪዎቹ ወደ እኛ ቤት እየተቃረቡ ከመሆናቸውም በላይ ትንሿ እህቴ የአንጀት ተስቦ እንደያዛት ነገሩኝ ። እናም እኔ እንደፈለኩት ወደ ቤቴ ብሄድ እንኳ በሽታው ይይዛታል ብላ አናቴ አትፈቅድልኝም ። ዉ. . . ወደ ቤቴ መሄድ አለብኝ የኔ ጌታ ።”

“በቃ አታልቅሺ እንግዲህ” አለ በሩህሩህ አንደበት ። “ያንኪዎቹ ቢመጡ እንኳን ከታራ ይልቅ አትላንታ ውስጥ መቀመጥ ይሻል ሻል ። ያንኪዎቹ አይነኩሽም - ይምሩሻል ። ተስቦው ግን ምሕረት አያውቅም — ይይዝሻል ።”

“ያንኪዎቹ አይጎዱሽምበ ምን ማይጎ የሰለው ውሸት ነው የም ትዋሸኝ”

“የኔ ቆንጆ ያንኪዎች ይሄን ያህል አረመኔዎች አይደሉም ። ጨካኞች አይደሉም እኮ ። አንቺ እንደምታስቢው ቀንድና ሽሆና ያላቸው አውሬዎች አይደሉም ። ከድምፃቸው ቃና ማጣትና ጸባያ ቸው ትንሽ ከማስቀየሙ በቀር ከደቡቦች በምንም አትለ’ያቸውም።”

“እንዴ ያንኪዎች ካፕ. . . ”

“አስገድደው ይተኙኛል እንዳትይ አይመስለኝም ። እንዲህ ለማ ድረግ ይፈልጉ እንጂ በግበር ለመፈጸም ግን እንኛ አይመስለኝም።”

“ኤዊ እንዲህ ያለህ ባልጌ ከሆንክ እንግዲህ ወደ ቤቴ መግባቱ ነው ። ” ብላ ፎከች ። በንዴት ፍም የመሰለ ፊቷን ጨለማው ምስ ጋን ይግባውና ሬት እንዳያይባት ከልሎላታል ።

“እውነቱን ንገሪኝ ፡ እውን ያሰብሽው ያን አልነበረም?”

“በፍጹም! ምነው አንተ!”

“ተይ ባክሽ ያሰብሽው ይሄንኑ ነው ። አየሽ ያሰብሽውን ነገር ፡ የልብሽን ስላወኩብሽና ስላነበብኩብሽ መናደድ አይገባሽም ፡ አይረ ባሽም ። አስተዳደገ ጨዋ የሆኑትና ድንግል አእምሮ ያላቸው የደ በብ ሴቶቻችን የሚያስቡት ይሄንኑ ነው ። ዛሬ ሲያስቡ ጭንቅላታቸው ላይ የሚመጣው ይሄው ነው ። እንደ ወ /ሮ ሚሪዌዘር ያሉት የሙት ሚስቶች ሳይቀሩ የሚያስቡት ይሄንኑ መሆኑን አልጠራጠርም . . . ”

እስካርሌት ፡ ቨርጂኒያ ወይ ተነሲ ወይም ሉዚያና ውስጥ ከቤታ ቸው ርቀው ሁለት ሶስት ሴቶች ተሰብስበው ከተቀመጡ ካለዚህ ጉዳይ እንደማያወሩ ታሰባትና ምራቁዋን ውጣ ጭጭ አለች ። ያንኪ ዎች ሴቶችን አስገድደው እንደሚተኙዋቸው ፡ ሕፃናት ሆድ ላይ

@OLDBOOKSPDF

ጠመንጃ ደግነው ወጥተው አንድ ሺህ ሰዎችና ሽማግሌዎችንም ቤተ ውስጥ አጉረው እንደሚያቃጥሏቸው የታወቀ ነው ። ማንም ቢሆን በየ መንገዱ ጮክ ብሎ አይናገረው አንጂ ልቡ ያውቀዋል ። ሬት ትንሽ ትህትናና ቅንነት ቢኖረው እውነት መሆኑን ባወቀ ባልሰደለፈም ነበር ። ደሞ ይሄ ጉዳይ ቀልድ አይደለም መቼስ ። በማሾፍ ሲስትባት ይሰማታል ። አንዳንድ ጊዜ ነገረ — ሥራው ሁሉ እንዳይሆን ነው ። ኧረ ብዙ ጊዜ ነው ነገረ—ሥራው እማይጥማት ። መቼም ወንድ ሆኖ ሴቶች የሚያስቡትንና የሚያልሙትን ማወቅ ነውር ሥሪ ነው ። ሴቷ እንዳወቀባት ከወቀች ቀሚሷን ገልቦ እርቃንዋን የሚያያት ነው የሚመስላት ። ከጨዋ ሴቶች እንኳ ቢሆን ማንም ወንድ ይሄን ጉዳይ ሊያውት አይችልም ። ጭንቅላትዋ ውስጥ ያለውን ነገር ስላነበበባት እስክርሴት ክብርዋ እንደተነካ ሁሉ ነደጻት ። እሷ ሚስጥሬ ፡ የግል ጉዳዬ የምትለው ፡ መቼም ትንሽም ቢሆን ከወንድ የምትደብቀው ነገር አላት ። ይሄ ሬት የሚባል ሰው ግን ውስጡን ሊያሳይ እንደሚችል መስታወት ቁልጭ አድርጎ ያያታል ።

"ለመሆኑ ይሄን ስናወራ ቤት ውስጥ ማን አላችሁ ? ማን ይጠብቃችኋል ? ተደናቂዋ ወሮ ሚሪዌዘር ናት ወይስ ወሮ ሚድ ናት ያለችውን መቼም እነሱ እዚህ ባዩኝ ቁጥር ዝምብዬ ያለጉዳይ የምመጣ ነው የሚመስላቸው ። "

"ወሮ ሚድ ብዙውን ጊዜ ማታ ማታ ነው የምትመጣው ።" አሰኝ አስክርሴት የንግግራቸው አርእስት መለወጡ ደስ አያላት ። ዛሬ ማታ ግን ልጅዋ ፊል በመምጣቱ ምክንያት ወዲህ አትመጣም ። "

"አብቻሽን ማግኘቱ እንዴት ዕድለኛ ነኝ አባክሽ" አለ ሰስለስ ብሎ ።

ከደምቡ ውስጥ አንድ ነገር ልቧን ኮለኮለውና መጋለብ ጀመረ ። ፊቷ ሁሉ ባንዴ ቦግ ብሎ ፈካ ። ብዙ ጊዜ እንዲህ ያለው አባባል ያዘለው ታና የፍትር መግለጫ ፡ የፍትር አዋጅ መሆኑን ከልምድ ታው ታለች ። ምን ዓይነት ቀልድ ነው ። አሁን እንደው አፍ አውጥቶ አፉ ቅርሻለሁ ቢሳት ሶስት ዓመት ሙሉ እያፈዘ ሲናገር የከረመውን ሁሉ ውጣ ብድሯን ሳትመልስ እንዴት ብላ ልትቀበለው ነው ። ሌላው ቀርቶ አሽሌይን በጥፊ የመታች እለት ያፈረችውን ማፈር እንኳ እንዴት ረስታ ተከተለኝ ልትለው ነው ። ስለዚህ ለስለስ ብላ በጥሞና እንደእሁቱ እንዲያያትና እንደው ስለጦርነቱ ነብር ብሎ ያሰበውን እንዲተው ልትነግረው አሰበች ። በደስታ ተጥለቅልቃ ሳቀች ።

"አትገልፍጪ እንግዲህ " አላትና እጅዋን ያዝ አድርጎ መዳፍዋን ወደላይ አዙሮ በከንፈሮቹ ተሳለመው ። ጫን ብሎም ሳመው ። ይሄኔ እንድ ሕይወትን የተገናፀፈ ፡ እንደ ኤሌክትሪክ የሚነዝር ፡

@OLDBOOKSPDF

ሰውነቱዋን ውብጡን የሚወርር ነገር ከእሱ ከንፈሮች ወደእሷ እጅና በተላለፈው መሳም ውስጥ ፡ በእሽላትዋ ሰርጎ ገባ ። ከመዳፍዋ ወደ ሰዓት ማሰሪያዋ አካባቢ የተንሸራተቱት ከንፈሮች ፥ እሱን በፍጥነት የሚንዘረዘውን የልብ ትርታዋን ግልቢያ ፥ ለማወቅ ይችላሉ ። ይህን ዕድል ለመንፈግ ብላ እጅዋን ሳብ ለማድረግ ሞከረች ። መቼም ይሄ የሠራ—አከላትዋ ላይ እየፈሰሰ ያጋላት ትኩስ ስሜት ፥ ይሄ በእጅዋዋ ጠጉሩን እንድትደባብስ በይ በይ የሚያሰኛት ትኩስ ግለት ፥ ይሄ—ምነው ከንፈሩን አፌ ላይ ባዋለው የሚያሰኛት የትኩሳት ጮርቃ ፥ የሚያጠራጥር ነገር አይደለም ።

ከሱ ጋር ፍቅር እንዳልያዛት አስባ ተምታታባት ። ከአሽሌይ ጋር ነው ፍቅር የያዛት ። ታዲያ ይሄ እጅዋን የሚያንቀጠቀጠው ንና አንጀቷን የሚያላውሰትን ብርቱ ስሜት ምን ይሉታል ፤ በቁስታ ሳቀና

“እጅሽን አታርሂው አደጋሽ አልጐዳሽም ።”

“አልጐዳሽም፣ ፊት በትለር አንተንም ሆነ ማንንም ሱሪ ያጠለቀ ወንድ አልፈራም !” አለችና ፎገች ፤ እጅዋም እማሯም ሲንቀጠቀጡባት ፍርሃት ቤቱን ሰራባትና ።

“ጥሩ የመንፈስ ጥንካሬ ነው ፤ ግን ድምጽሽን ዝቅ አድርጊው ወ/ሮ ሚሲ, ልትሰማ ትችላለች ። ደሞ ረጋ በይ በሞቴ ።” በንግግሯ እንደረክ ሁሉ በደስታ ነው የሚናገረው ።

“አስክርሌት ቱመጀኛለሽ አይደለም?”

ይሄ እንኳ የጠበቀችው ይመስላል ።

“መቼም ... አንዳንዴ ...” አለች በጥንቃቄ ። “አንዳንዴ ተንኮለኛ ሳትሆን ስትቀር አም” እንደገና ከት ብሎ ሳቀና መዳፉን ከጉንጯ ጋር አስታከ ። “አየሽ ፥ እንደሚመስለኝ ግን የምትወጂኝ ተንኮለኛ በመሆኔ ነው ። በዚህ በቤተሰብ ሥር — በኖርሽበት ዕድሜሽ ውስጥ እንደኔ ማርማ ሞገስ ያለው ሽረኛና ተንኮለኛ ለው እጋጥሞሽ ስለማያውቅና ከሌሎች ሁሉ የተለየሁ በመሆኔ ልዩ ለዛና ቁመናዬ ሳያሸንፍሽ አልቀረም ።”

የጠበቀችው መልስ ይሄ አልነበረምና እንደገና እጅዋን ለመሰብ ሰብ ትሞክር ፥ ልታስለቅቀውም ትጣጣር ጀመር ።

“በጥጨም ያልከው ውሸት ነው ።እኔ ጥሩ ወንዶችን ፡ጨዋነትን የተላበሱ ወንዶችን ነው መመኪያዬ ብዬ የምወዳቸው” አለች ።

“አሀ እንደበሬ አፍንጫቸውን ሰንገሽ የምትገሰትቺያቸውን ማለ ትሽ ነው ።እሱ እንኳን የትርጓሜ ጉዳይ ነው ።ግን ግዴለም ይሁን ።”

@OLDBOOKSPDF

መጻፍሞን እየጀማመ ሲስመው አንድ ነገር ማጅራቷን አየዳሽ ሲጨመድዳት ተሰማት ። "መውደዱን እንኳ ትወጂኛለሽ ግን ልታረ ቅሪኝ ትችይ ይሆን እስካርሲት?"

"ይሂ ነው ።" አለች በልቧ በድል አድራጊነት ስሜት ። "እሱን እገኘሁት" ትጥላም በተጠና እርጋታ "አርግጥ አይደለም ። ይህን ጠባይህን ካላረምክ በስተቀር የሚሆን አይመስለኝም ።"

"አይዱ ለማረምስ በፍጹም አልፈልግም ። እና አታፈቅሪኝም ማለት ነውን እንደጠበቅሁት ሆነ ማለት ነው። እንግዲያውስ ምንም እንኳ ከልቡ በላይ ብወድሽም ስለማላፈቅርሽ ለሁለተኛ ጊዜ በማያሞጣሽ ፍቅር መቁሰል ስለሚሆን ብሽ ትርፉ ሐዘን ነው ። አይመስልሽም ቀንጂት ! ቀንጂ ልበልሽ ወይስ ጠ/ሮ ቮርለስ? እንግዲህ ወደድሽም ጠላሽም "ቀንጂት" እልሻለሁ ፣ ብቻ ባሰመብትህ አይነፈጓኝ ።

"አታፈቅሪኝም ማለት ነውን"

"አላፈቅርሽም ። ግን ያፈቅረኛል ብለሽ ገምተሽ ፣ ተስፉ አድርገሽ ነበር እንዴ?"

"ይሂን ያህል ተስፈኛ አትሁን ።"

"አንቺው ራስሽ ተስፉ አድርገሽ ነበር ማለት ነው ።ተስፋሽ የለ መሆሙ ይሁን— እንኳን ቀናሽ ። ስለዚህ ላፈቅርሽ ይገባኛል ። አዎ ፡ በብዙ የማይረሱና ተራ ነገሮች ላይ እንኳ ያልቀናሽ ሴትዮ እሁን ስለሆነልሽ ላፈቅርሽ ይገባል ። ብዙ ሴቶች መልክ መልካም ይዎ ግባትን የተላበሱ ፣አያሌ ነገሮችም የተሳክላቸው ይሆኑና ግን ልክ እንዳንቺ የማይረቡ ናቸው ።አላፈቅርሽም ።ነገር ግን ስወድሽ ግደን የለኝም ።የጎሰናሽን ግትር አሰመሆንና አንዳንዴ ልትደብቂው የምት ሞክሪውን ራስ ወዳድነትሽን አወደሞሰሁ ።ምናልባት ከአየርላንዳዊዎቹ ገበሬ አያት ትደም አየቶችሽ ወስደሽዋል ብዬ የምሰጋበትን በተግባር የሚታይ መሠረትሽንም ስወደው አንዳንድ ነገር ነው ።"

ገበሬ ? ምንው እንዴህ አርጉ ባይሰድባት ። ቃላት አስከሚደጥራት ድረስ በስድብ ልትወርድበት ስታነበንበው "አታቋርጪኝ በሞቱ" ብሎ እጅጥን ጭምት አድርጉ ለመናት ''አየሽ እኔ ውስጥ ያሉት ልቡ ጠባዮች አንቺም ውስጥ ስላሉ፡ ተመሳሳይ በመሆናችን፡የሚመሳሰሉ ሁሉ ይጣጣማሉና አወድሻለሁ ።የዚያ እንደጣኦት የምታመልኪበትን እን ጨት ራስ አሽሉይን ትዝታ አውንም እንደምታሰላስይ ተጣንዝቤያ ለሁ ።ምናልባት በዚህ የስድስት መር ጊዜ ውስጥ መታብር ጉብዮ ሊሆን ይችላል ። ትዝታው ግን ካንቺ ጋር አለ ።ደም ሆኖ ለኔም ትንሽ ቦታ አልብሽ ውስጥ ማስተረፍ አስብሽ ። አስካርሉት ፡ አትቁነጥጭብኝ!

@OLDBOOKSPDF

መግለጫ እየሰጠሁሽ ነው። በቅሬታ ወረቀትሽ ጥርጣሬዎች" የመኖሪያ ቦታ አዳራሽ ውስጥ ፤ ቻርለስ ሐሜልተንን እያባበልሽ ስትሸነግይው አይ ኔን ከጣልኩብሽ ጀምሮ እንደወደድኩሽ አለሁ ። ግንንም ሴት ከፈለ ኩት የበለጠ ፈለኩሽ — ግንንም ሴት ከጠበኩት የበለጠም ለረጅም ጊዜ ጠበኩሽ ።"

የመጨረሻዎቹ ቃላት ትንፋሽ እስኪያጥራት ድረስ አስደነቋ ዋት ።እንደዛ ሲሰድባት ቢከርምም ለካ አፍቅሯታል ።ልክ የሷ ተቃ ራኒ በመሆኑም ማፍቀሩን ገልጦ ቢነግራትና አጥ አውጥቶ ቢያሳውቃት ትስቅብኛለች ብሎ ፈርቷል ።እንግዲህ አሁን ታሳየዋለች ።

"እንዳገባህ መጠየቅህ ነው እንዴ"ነአለች ።

እጆችዋን ሰቅቅ ወደ መሬት አወረዳቸውና ወንበሩዋ ላይ እንዳ ለች እስክትሸማቀቅ ድረስ ጣራ የሚሰነጥቅ ሳቅ ሳቀ ።

"እረ በፈጣሪ! ምነው የትዳር ሰው እንዳልሆንክ ነግሬሽ?"

"እንዴ ...ግን ምን...?.."

ከመቀመጫው ተንስቶ አንድ እጁን እዶራቱ ላይ አደረገና ሰዋ ብሎ በቁንጥ እጅ ነስቶ "ቁንጂት" አለ ዝማ ብሎ"መጀመሪያ ሳልለማመጥሽና ሳላባብልሽ ወዳጅ እንድትሆኚኝ በፅውቅ ትሽ ላይ ተጨማሪ ዕው ቅት ማከሌ ነው ።"

"ወዳጅ?"

ጭንቅላቷ ይህንን ቃል በጮክታ ተናገረው ። በስድብ ከትቢያ እንደ ተቀላቀለች ኅሊናዋ ሙቹ ተናገረ ። ገና ሲናገር የተሰደበች አልመ ሰላትም ነበር ።እንደዚህ ጅል ናት ብሎ መገመቱ ደሟን አፈላው ። ውርደት መሰላት። እሷ በወጉ በማረጉ ትዳር እይዛለሁ ብላ አሰበች እንጂ እንዲህ እንዲህ ያለ ጥያቄ ያቀርብልኛል ብላ በጭራሽ አላሰበችም ።

ንዴት ፡ የብኩንነት ውጋትና መከፋት አንጐልዋን እሳት ላይ ጣዱት ። እናም ገና ምን ብላ እንደምታዋርደው አስባ ሳትጨርስ በንዴት አፍዋ እንዳመጣላት ተናገረችው ።

"ያንተ ወዳጅ በመሆን ማቲ — ከመፈልፈል ፡ ልጅ ከመቀፍቀፍ በቀር ምን አገኝ መሰለህ ?"

በኋላ ግን የተናገረችውን ስታስተውለው በድንጋጤ ግንጭሏ ተነ ሥቶረ ።በጭለማው ጥላ ውስጥ አትናገር አትጋገር በድን ሆና በመሐ ረቡዋ አፍዋን እንደያዘች ሲያያት ተንከትክቶ ሊሞት ።ሳቀ ።ሳቀ ። ድምጹ እስኪዘጋ ድረስ በሳቅ ፈነዳ ።

@OLDBOOKSPDF

"አየሽ ለዚህ ነው እኔ እምወድሽ ። አስከዛሬ ድረስ ካየሁዋቸው ሴቶች ሁሉ እንዳንቺ ግልጽ ሴት አላጋጠመኝም ። ስለግበረገብ ነትና ስለስነሐት በማውራት ጉዳዩን ላታደበስብሺ ነገሮችን ሁሉ ተጨባጭ ተግባራዊ ገፍቸውን ለማየት የምትችይ አንቺ ብቻ በመ ሆንሽ አወድሻለሁ ። ሌላ ሴት ብትሆን ደንፍታ ደንፍታ ከቤቱ ወጣልኝ ባለችኝ ነበር ።"

አስካርሌት ፊቷ በፍርሃት እንደተላ ከመሬት ዘለለች ። እንዴት እንዲህ ያለ ነገር ተናግራ እራሷን ታቀልላለች? እንዴት እሷን መሳይ አስተዳደግ — መልካም ያውም የአለን አሳራ ልጅ እንዲህ ስትዋረድ ዝም ብላ አዳምጣ ስታበቃ እንደዛ ያለ ሐፍረተ — ቢስ መልስ ትሰ ጣለች ? አሉ ማለት ነበረባት ። ልቧ መጥሰስ ነበረበት ። ፊቷን ከዘረን ዳው መልሳ ፡ ጀርባዋን ሰጥታው በጨዋ ድንብ መኝታ ቤት መሄድ ነበረባት ።አሁን ግን ግዜው አለፈ ፡ረፈደባት ።

"እኔም በሩን አሳይሃለሁ!" ብላ ፈጠነች ፤ ሚለኒም ሆነች ሚድ መንገድ ላይ ሆነው ቢሰሙዋት እንኳ ግድ ሳይሰጣት ። "ውጣ!" እንዴት እንዲህ ደፍረህ ትናገረኛለህ ? እንዲህ የልብ ልብ የሰጠህ ህና...እኔን እንዲህ አድርገህ...ብቻ ውጣልኝ ሁለተኛ ድርሽ እንዳ ትል ። ዛሬ የመጨረሻ ነው — ከምሬ ነው ። ከዛሬ ወዲያ ይቅርታ ታደ ርግልኛለች ብለህ መርፈና የጌጥ ጥብጣብ ይዤ እመጣለሁ ብትል ውርደት ይጠብቅሃል ። ሁዋላ ላባቱ ነግሬ አስገድልሃለሁ!"

ባርሚጣውን አንስቶ እጅ ነሳና ወጣ ። በፋኖስ ጭላንጭል ብር ሃን ከከንፈር ጠመ በታች ጥርሶቹ በፈገግታ ፍልቅቅ ሲሉ ይታየ ታል ። በሆነው ነገር ሁሉ አላፈረበትም ። ይልቁንም በተናገረችው በመ ገረም በጎቱ አስተያየት ያስተውሳታል ።

አው . . . በጣም የሚያስጠላ ሰው ። ተሽከርክራ ወደቤቷ መጣባት ጀመረች ። በሯን ኃ አድርጋ ልትዘጋው ሞከረች ፣ ግን አቅሚ ከበሩ ማጠፊያ ጥንካሬ ሳያይል ቀርቶ አልዘጋ አላት ። ብዙ ታገለች ፡ አለ ሆነም ።

"ልርዳሽ እንዴ" ብሎ ጠየቃት

ከእንግዲህ ለአንዲት ደቂቃ ልቆይ ብትል የደም — ጋንግ የሚፈነዳ ስለመሰላት ደረጃውን ተንደርድራ መውጣት ጀመረች ። የመጨረሻው ደረጃ ላይ ስትደርስ በሩን በታላቅነት ሲዘጋላት ሰማች ።

@OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ 20

የንሐሴ ወር ፀሐያማ ቀናት ፣ ከነረብሻቸው እየቀዘቀዙ ሲሄዱ ፣ የቦምቡ ጩኽትም ድንገት ፀጥ አለ ። በከተማይቱ ላይ የሰፈነው ፀጥታ ጭራሽ የሚያስደነግጥ ነው ። ጎረቤት ከጎረቤቱ መንገድ ሲገናኝ ወደፊት ምን እንደሚከተል ካለማወቅ ሥጋት የተነሳ ፣ እርስ በርስ መተያየት ፣ እርስበርስ መጠራጠር አንዱ ላንዱ ከብዶና አስፈሪ ሆኖ መታየት ብቻ ሆነ ። ጩኽትና ትርምስ ከበዛባቸው ቀናት በኋላ ይሄ ድንገት እርጭ ያለው አየር ፣ ታውቅ የነበረውን የሰውን ነርቭና አእምሮ ማረጋጋቱ ቀርቶ ጭራሽ ጭንቀት የሚናኝበት ዓይነት ሆኗል ። የያንኪዎች የመድፍ እሩ ሰምን እንደተዘጋ ያወቀ ማንም የለም ። ስለራሳቸው ሠራዊትም ቢሆን የሚያውቁት በከተማው ዙሪያ ካሉት ምሽጎች በብዛት ወጥቶ ፣ የባቡሩን ሀዲድ ለመጠበቅ ወደ ደቡብ የማፈግፈጉ ወሬ ብቻ ነው ። ሙሊያ ቢኖር እንኳ የት ቦታ እንደሚከዜድ የሚያውቅ የለም ። ከብድ ሠርጎችም ቢኖር የት ቦታ እንደሚከዜድ የሚያውቅ አንድም ሰው የለም ።

ባሬ ጊዜ ያለው ወሬ ከእንዱ አፍ አንዱ አፍ የሚያልፈው ተባራሪ ወሬ ብቻ ነው ። የወረቀት እጥረት አለ ። የቀለም እጥረት አለ ። የሰውም እጥረት አለ ። ስለዚህም ወረራው ከተጀመረበት ቀን ወዲህ ጋዜጦች ሥራቸውን አቁመዋል ። ማንኛውም ዓይነት ወፍ ዘራሽ ወሬ ካንዱ ኃ ይፈላና ከተማውን ባንድ እፍታ ያጥለቀልቀዋል ። በዚህ ወሬ በተጠማ ዝምታ ውስጥ የሰው መዓት ጀኔራል ሁድ የሚያዝበትን ጠቅላይ መምሪያ ዙሪያውን ከቦ የዜና ያለህ ፣ የወሬ ያለህ ይላል ። ሴላ በርከት ያለ ሕዝብ ደግሞ የቴሌኮሙኒኬሽኑን ጽ/ቤትና የባቡር ጣቢያውን ካፍ እስከገደፉ ሞልቶ አጣበታል ። ሠራዊታችን ምን ደረሰ ? ጦርነቱ እንዴት ሆነ ? የወሬ ያለህ ። የሼርማን መድፍ አፉን ከያዘ ወዲህ የሰው ሁሉ ግምት ያንኪዎች እየሸሹ ፣ የኮንፌዴሬሲው መታደሮች እያሳደዱ እስከ ዳልተን ድረስ እንደሚገፉዋቸው ነው ። ታዲያ ምን ያደርጋል ከተስፉ በቀር ወሬ የለም ። የተጨበጠ ነገር ጠፍቷል ። የቴሌግራፍ መስመሮች ፀጥ—እርጭ ብለዋል ። በቀረችው አንድ የባቡር ሐዲድ ላይ ከደቡብ የሚመጣ አንድም ባቡር የለም ። የፖስታ አገልግሎት ከናካቴው ሽባ ሆኗል ።

@OLDBOOKSPDF

የሐጋይ መቅት እሢራውንና ትንፋሽ—አልባ ጠራራ ፀሐዩን ታጥቆ ድንጥት እርጭ ያስችውን ከተማ ሊያፍን አድብቶ መጥቷል ። የከ ተማውን ሕዝብ ጉጉ ልቦች ደረቅና በሳል የሚያፍን አየሩን ጭንቅ ሲጨምርባቸው በድካም ላይ ድካም ፣ በመልፈስፈስ ላይ ተዝለፍልፎ መውደቅ ሊያክልባቸው ነው ።

ሰለ ታራ ምንም ነገር ባለመስማቷ ልታብድ ለደረሰችው — ነገር ግን በጀግንነት ለመወጣት ለምትጥጨረጨረው — ለእስካርሌት ፣ ወረራው ከተጀመረ እስካሁን የዘለዓለም ያህል ጊዜ አልፏል ። ያሁኑ አስፈሪና ሰይጣናም ዝምታ እስከመጣ ድረስ ሕይወቷን በሙሉ ከመ ድፍ ጨኸት ጋር የኖረች መሰላት ። ያም ሆኖ ወረራው ከተጀመረ ገና ሰላሳ ቀኑ ነው ። ሰላሳ የወረራ ቀናት! ከተማዋ በጥይት በተበሳሳ ቀይ ሸክላ ተሞላች ። መድፍ ያሰማሩረጥ ፡ እስኪለለች ድረስ ያገ ሳል ። አምቡላንሶችና በበሬ የሚጎተቱ ጋሪዎች ወደ ሆስፒታል በሚሄ ደው እሢራማ መንገድ ላይ ትኩስ ደም እያዘሩ በረሻም ሰልፍ ይጓዛሉ ። ሰውነታቸው የዛለ ፣ የሰለቻቸው መታብር ቆሩሪዎችና ቀባ ሪዎች ፣ ሬሳ እስኪቀበቅዝ መጮሁ ሳያስጨንቃቸው ርቅት በሴላ ቸው ጉድጓዶች ውስጥ የሰውን ልጅ እንዴ እቃ ይወረውሩታል ። ይሄ ሁሉ በሰላሳ ቀን ውስጥ የታየ ነገር ነው ። በሰላሳ ቀናት ውስጥ!

ያንኪዎቹ ከዳልተን ወደ ደቡብ ከተንቀሳቀሱ ገና አራት ወራ ቸው ነው! አራት ወር ብቻ! እስካርሌት ፣ ወደ ጥንቶቹ ቀናት መለስ ብላ ሴላ ኑሮ ይኖርበት የነበረና ሌላ ዓይነት ሕይወት ሞቆበት የነበረ ቀን ማለፉን አሰላስለች ። እሬ የለም !የለም የለም! አራት ወር ብቻ አይደለም—ያንድ ሰው ዕድሜ ነው ።

ከአራት ወር በፊት!እንዴ ፡ ከአራት ወር በፊት' ኮ ዳልተን ፣ ረሳካና ኬኔሳው ተራራ በባቡር መንገዱ ዳርቻ የነበሩ ቦታዎች ስሞች ነበሩ ። ዛሬ ጦር ሜዳ ሆነዋል ። የሞት የሽረት ጦር ሜዳ ! ጆንስተን ወደ አትላንታ ሲያፈገፍግ በአልሞት ባይ ተጋዳይነት የሚሟሟቁባ ቸው የውጊያ ቦታዎች ! ጥንት የደስታ ምልክት የነበሩት ፣ የፈሽታ ስሞች የነበሩት የጥቂ ትሪ ከሪክ ፣ የዲካተር ፣ የእዝራ ቸርች እና የኑ ቶይ ክሪክ መጠሪያዎች ዛሬ የሐዘን ማስታወሻዎች ሆነዋል ። ከእን ግዲህ ከጓደኞቿ ጋር የምትግናኝባቸውና የምትስቅ የምትጫወትባቸው ፀጥ ያሉ መንደሮች አይሆኑም ። ከእንግዲህ በቀስታ ከሚፈስሱት ጅረቶች ዳርቻ ከቆንጆ—ቆንጆ ወንዶች ጋር የምትንሸረሸርባቸው ለም ለም መናፈሻዎች አይሆኑም ። እነዚህ ሥፍራዎች ዛሬ ከመርጎት በስ ተቀር የሚሰጡት ትርጉም የለም ። እነዚያ በምኞት ትቀመጥባቸው የነበሩ ለስላሳ የሣር ሜዳዎች ዛሬ የመድፍ ጉማ ድቂቾዋል ። መ

@OLDBOOKSPDF

ንጄ ለጠመንጃ ሲፋጠጥ በሚራወጡ እግሮች ተረምርመዋል ። በመጨረሻ የጣር ድምጽ በሚወድቁ ሚኞች ሰውነት ተደምድመዋል ። . . . እናም ዝግተኞች ጅራቶች ቀያዩቹ የጀርጅያ ሽክላዎች ከሚያቀሏቸው በላይ በደም ተነከረዋል ።

ያንኪዎች አሜርጠውት ከለፉ በኋላ ፒችትሪ ክሪክ ቀይ ቀለም የፈሰሰበት መስሏል አሉ ። ፒች—ትሪ ክሪክ ፡ ዴካተር ፡ እዘራ ቸርችና አቶይ ክሪክ—ከእንግዲህ የቦታ ስሞች መሆናቸው አከትሟል ። ከእንግዲህ ወዳጆች የተቀበሩባቸው የመቃብር ስሞች ናቸው ። ከእንግዲህ ከግርጌያቸው ፈሳ የተጣለባቸውና የበሰበሰባቸው የተጠላለፉ ቁጥቋጦዎችና ጥቅጥቅ ያሉ ጫካዎች መጠሪያ ስሞች ናቸው ። ከእንግዲህ ጀኔራል ሁድ ፡ ሼርማን አትላንታን በአራት ወገን ጥሶ ለመግባት ሲጥር መክኑ የመለሰበት የጦር ሜዳ ስሞች ብቻ ናቸው ።

በመጨረሻ ወሬ ተገኘ ። በመጥረት ላይ ወዳለችው ከተማ አዲስ ወሬ መጣ ። ይህ ወሬ በተለይ ለአስካርሌት እጅግ አስደንጋጭ ነው ። ሼርማን ከተማይቱን እንደገና በአራተኛው አቅጣጫ እንደውጋት ቀስፎ ለመያዝ የጀንስቦሮውን ባቡር መንገድ እያጠቃ ነው ። አሁን እንግዲህ በአራተኛው አቅጣጫ ያንኪዎች በብዛት ፈሰዋል። ተወርዋሪ እግረኛ ጦርም ሆነ ፈረሰኛ ሠራዊት ለምልክትም አይታይ ። ዙሪያ ገባውን የያንኪ ጦር እጥለቅለቅታል ። በሺ የሚቆጠር የኮንፌዴሬሲው ሠራዊት ለከተማው ቅርብ ከሆነው የውጊያ መስመር ተነስቶ ወደ ዚሁ እየገሰገሰ ነው ። ድንገት በከተማዋ ላይ የሰፈነው እርጭታ አሁን ምክንያቱ ታወቀ ።

“ለምንድነው ጀንስቦሮን የሚያጠቁት?” ብላ አሰበች አስካርሌት ፤ ለታራ ምን ያህል ቅርብ እንደሆን አሰልታ ልቧን ሽብር እያፈናት ። “ሁልጊዜ ጀንስቦሮን የሚደበድቡት ለምንድነው እሱ? ምነው ሐዲዱን ከሌላ አቅጣጫ ቢመቱ? ”

ለሳምንታት ያህል ስለታራ ወሬ አልሰማችም ። ባለፈው ጊዜ ጀራልድ ልኮላት የነበረው አጭር ደብዳቤ ደግሞ ሙራሽ ስጋቷን የሚያብስ ነበር ። ካሪን በጠና ታማለች ። ደብዳቤ ከመጣ ብዙ ቀን በመሆኑ ትመት ትዳን አይታወቅም ። እዴ ፤ ምነው ከሜላኒ ጋርም ሆነ ብቻዋን ገና ወረራው ሲጀምር ወደቤቷ ሄዳ በሆነ ኖሮ?

ጀንስቦሮ ላይ ውጊያ እየተካሄደ ነው— አትላንታ የምታውቀው ይህን ብቻ ነው ። ውጊያው ምን እንደደረሰ ግን የሚያውቅ ማንም የለም ። ብቻ ከራ ወሬ በመጣ ቁጥር ከተማይቱን ልቧን ያቆስለዋል ። የጣታ ማታ ከጀንስቦሮ የመጣ መልክተኛ ያንኪዎቹ ወጓሪራቸውን

@OLDBOOKSPDF

ናሚያረጋጣዋ የምሥራች ወሬ አሰማ ። ታዴያ ምን ያደርጋል ፡ የያንዚ ወታደሮች ለቀው ሲወጡ ጀንበሮ ላይ ያላደረሱት ጥፋት የለም ። የነዳጅ ማጠራቀሚያ ዴፖዎችን አቃጠሉ ። የቴሌግራፍ ገበዮችን በጣ ጠሉ ። ዕስት ማይል የሚሆን የከባድ መኪና መንገድ ቆርጠው ከጥቅም ውጪ አደረጉ ። የመሐንዲስ መምሪያው መሃንዲሶች የተበላ ሸውን መንገድ ለመጠገን እንዲ አብድ ይሯሯጣሉ ። ሆኖም ያንኪዎቹ ጥፍ ጥናዎቹን መሳናቸ መንገዶች አመዳቸው እስኪወጣ አበላሽተውና የተነታኮሉ ሐዲዶች አያጋሉ ከዕልክ እንዲዶች ጋር እያቀላለፉ ስላሰሯቸው ለማስተካከል በጣም ብዙ ጊዜ ይፈጅባቸዋል ። ዛሬ ጊዜ እንኳን የባቡር ሐዲድ መልሶ ለመሣጠም ማሳቸውንም ከበረት የተሠራ ነገር መልሶ ፀመተካት በጣም አዳጋች ነው ።

ያንኪዎች ታራ አልደረሱም ። የጀኔራል ሁድን ጦር የድል ወሬ ይሆ የመጣው ያው መልክተኛ ያንኪዎች ታራን እስመን ኪታቸውን ለእስካርሌት አረጋገጠላት ። ከጦርነቱ በኋላ ጀራልድ ወደ አትላንታ ሊሄድ ሲነሳ ጀንበሮ ውስጥ አማሾት ነበር ። አናም ጀራልድ ለእስ ካርሌት ደብዳቤ ይዛት እንዲሄድ በጣም ለምኖ ነ ጥያት ነበር ። ‹‹ግን አባባ ጀንበሮ ምን ያደርጋል?›› መልዕክተኛ ሻው መልስ ለመ ጠት ትንሽ ቸገረው ። ጀራልድ ወደ ታራ ይሆት የሚሄድ የጦር ሠራ ዊት ይኸተር እየፈለገ ነበር ።

እስካርሌት በረንዳው ላይ ፀሐይ እየመታት ፉማ መልዕክተኛ ው ስላደረገው ሁሉ አመስግና እየሸች ሳሰች ፡ ጉልበቷ የሚሚ መሰ ላት ። ካሪን ፡ ከኤለን የህክምና አትም በላይ ሆና ጀራልድ ይኸተር ፍሰጋ እስከ መሠር ከደረሰ መቹም ፡ ከሞት አፋፍ ላይ ናት ማለት ነው! መልክተኛው በጠመዝማዛው ቅይ አፈር መንገድ ሠር ካይን ሲጠፋ ፡ እስካርሌት የጀራልድን ደብዳቤ በሚንቀጠቀጡ ጣቶቿ ከፈ ተችው ። ዛሬ ኮንፌዴሬሲውን የፀረቅት ጉጥረት መድረኽ አሳጥዳታል ። በመሆኑም ጀራልድ ማበታወቂውን የጨለላት ከዚህ ቀደም ጽፋለት በነበረው ደብዳቤ ከመስመሮቹ ማሀል ማሀል እያስገባ ነው ። ለማን በብ በጣም አስቸጋሪ ነው ።

‹‹ውድ ልጄ ፡እናትሽና ሁለቱም እህቶችሽ በእንጀት ተለቦ በሽታ ተጠምደዋል ።በጣም በጠና ታመዋል ፡ ግን መቹም ይሻላቸዋል ብለን ተስፋ እናደርጋለን ። እናትሽ በየቀኑ ማታ ማታ — አደራ — እደራ እንቺም ሆንሽ ዋድ ወደዚህ እንመጣለን ብላችሁ በዚህ በሽታ እንዳ ትለከራ — ብለህ ጸፍለት እያለች ትወተውተኛለች ።እንደምነሽ ብላ ሻለች ። እንድትፀልይልኝ አደራ ብላሻለች ።››

@OLDBOOKSPDF

"ወይኔ ፀልይልኝ አለች። አስካርሌት ደረጃውን ወጥታ ወደክ ፍሏ ሄደች። አልጋዋ አጠገብ ተንበረከከችና ከዚህ ቀደም ፀልያ በማታ ውቀው ዓይነት በከፍተኛ ተመስጦ ፀለየች። የተለመደውን የፀሎት ሥነሥርዓት ባትከተልም፤ በተደጋጋሚ የምትሳቸው ቃላት — "እመ ቤቴ ማርያም ሆይ፤ እናቴን አትግደያት፣ እናቴ አትሙትብኝ፣ አሷን ከልገደልሻት እኔ በጣም ጥሩ ልጅ እሆናለሁ። እባክሽ አትግደያት።"

የሚቀጥለውን ሣምንት ሙሉ አስካርሌት እንደቆሰለ አውሬ በቤቱ ዙሪያ እየሠረች ወሬ ትጠብቃለች። የፈረስ ኮቴ በሰማች ቁጥር ትበረግጋለች። ወታደሮች በር ባንኳኩ ቁጥር በአኩሶ ሌሊት ደረጃውን እየተንደረደረች ወርዳ ትወጣለች። ዳሩ ግን ወሬ አሚባል ጠፋ። የታራ ወሬ የክራ ቀን አህል ሆነ። በሷና በቤቷ ማህል ያለው የሃያ አምስት ማይል የቀይ አረር መንገድ የአንድ ከፍለዓለም ያህል ሰፊና ረዥም ሆነባት።

የፖስታ መልዕክት ነገር አሁንም አንደተባባ ነው። የኮንፌዴሬሲው ወታደሮች የት እንዳሉ አይታወቅም—ያገኪዎቹም ምን እየሠሩ እንደሆነ አይታወቅም። የሚታወቅ አንድ ነገር ቢኖር በሺ የሚቆጠሩ፣ ግራጫና ሰማያዊ የለበሱ ወታደሮች በአትላንታና በጆንስቦሮ ማህል አንድ በታ መኖራቸው ብቻ ነው። በአንድ ሣምንት ጊዜ ውስጥ ስለታራ አንድም ነገር ሳይሰማ ተከረመ።

አስካርሌት — የአንጀት ተሰቦን ነገር አትላንታ ሆስፒታል ውስጥ በደንብ ስለምታውቅ በዚህ በሽታ ለተለከፈ ሰው አንድ ሣምንት ምን ማለት እንደሆነ ይገባታል። ኤለን ታማለች፤ ምናልባትም ከሞት ጋር እየተሟገተች ናት። እዚህ ደሞ አስካርሌት ያለአንድ አጋዥ፣ ያለአንድ ረዳት ነብሰጡር ሴት ተሸክማ፣ በሷና በቤቷ ማህል ሁለት ተባራሪ ሠራዊቶች አስቀምጣ ቁጭ ብላለች። ኤለን ታማለች — ምናልባትም ከሞት ጋር መግት ሳይ ናት፣ ግን እኮ ኤለን ልትታመም አትችልም፣ በሀይወቷ ታማ አታውቅም። ይሄ ሀሳብ በጣም አደገኛ ነው። የአስካርሌትን ሀልውና ከሥር ከመሠረቱ የሚያናጋ ሀሳብ፤ ሁሉ ሰው ይታመም—ኤለን ግን እንዴት ተደርጎ። ኤለን የታመመችን እያከመች ትፈውሳለች። እሷ ልትታመም አትችልም። አስካርሌት ባሁኑ ሰዓት ቤቷ ለመሆን በጣም ፈለገች። መጻኛ ጥማ እንደሚፈልግ፣ የመጨረሻ ሀልውናዬ የሚለውን መጠለያ እንደሚፈልግ የደነገጠ ሀሣብ፤ ታራን የሙጭኝ ልትል በመጨረሻ የፍላጎት አቅሟ ተመኘች።

ቤትዋ እንደበጐን አንገቱን መዞ የቆመ፣ መስኩቱ ላይ ነጭ መጋረጃዎች የሚውለበለቡበት—ቤት። ግቢው በአበባ የተንቆጠቆጠ፤

@OLDBOOKSPDF

ንቦች በሥራ ተጠምደው የሚሯሯጡበት—ቤት ። ዳክዬዎችንና ተርኪ ዎችን በአበባው ከልል ለመጠበቅ ሬት ሰፊቱ በረንዳ ላይ ተቀምጠ የሚጠብቅ ልጅ ሁልጊዜ የሚታይበት—ቤት ። ፏ ባሰ ቀይ ምንጣፍ የተሸፈነ የሚመስል መሬትና ከፀሐይዋ ጋር የሚስቅ በስንትና ስንት ማይል ርቀት ላይ የበቀለ ጥጥ የተንጣለለበት ቤት! ቤት!

ሰው ሁሉ በሚሰደድበት በወረራው ጊዜ ወደ ቤቷ ሄዳ ቢሆን እንዴት ጥሩ ነበር! ይሄኔ ሚለኒን ሞምር ይዛ እዚያ ደርሳ ለማረፊያም ትርፍ ማምንታት ይኖራት ነበር ።

"እቺ የተረገመች ሚላኒ!" በልባ. ሸ ማዜ ረገመቻት ። "ምነው ከወ/ሮ ጥቱ ጋር ወደ ማከን ሄዳ ቢሆን ኖሮ ። እዛው ከዘመዶቿ ጋር ተቀላቅላ እርፍ ትል ነበር ። ከኔ ጋር አሁን ምን ትፈጥራለች ። እኔ የሷ ዘር ጠብታ ደም እንኳ የለበኝ ። እንዲህ እንደመጫ እኔ ላይ ጥበቅ የምትልብኝ ሰምንድነው? እሷ ወደ ማከን ብትሄድልኝ ኖሮ እኔም ወደ እናቴ እሄድ ነበር ። አሁንም ቢሆን—አሁንም፤ ይሄ የሚ ወለደው ሀጻን ልጅ እዚህ ባይኖር ምንኪም እንኳ ቢኖሩ የመሄድ እድሉ ነበረኝ ። ማን ያውቃል ጂኔራል ሁድም ወደቤቱ ሊሸኘኝ ይች ላል ። በጣም ሚሩም ሰው ነው እኮ ። ጂኔራል ሁድን ፤ አጃቢና የሰላም ባንዲራ ሰጥቶ እንድሄድ እንዲያደርገኝ ላስረዳው እችላለሁ ። ዴሩ ምን ያደርጋል ይሁንን ሀጻን እስኪወለድ መጠበቅ ይኖርብኛል ። ወይኔ እናቴ! እማምዬ! ባክሽ አትሙቺብኝ! ይሄ ሀጻን ለምን ቶሎ አይወለ ድም! በቃ ዛሬ ሄጂ ዶክተር ሚድን ልፈልግና ሀጻኑ ተፋጥኖ እንዲ ወለድ የሚያደርግ መድሃኒት ካለ እንዲረዳኝና እሚሸኘኝ ካገኘሁ ወደ ቤቱ እንድሄድ ልጠይቀው ። ዶ/ር ሚድ መሄድሽ ጥሩ አይደለም ብሏታል ። ወይኔ አምላኬ! ብትሞትብኝስ! ሚላኒ ሞታ ስትጋደም ። ሚላኒ ሞታ ። እና አሽሌይ. . . የለም የለም እንዲህ ያለ ነገር በጭራሽ ማሰብ የለብኝም ። ደግ አይደለም ። ግን እኮ አሽሌይ. . . የለም የለም፣ ስለሱም ማሰብ የለብኝም—ምና . . . ልባት ሞቶ ሊሆን ይችላል ። መት ወቃሽ እሆናለሁ ። ያም ሆነ ይህ ግን እሷን እንድጠብቅለት ቃል አስገብቶ ፣ አደራ ብሎኝ ነው የሄደው ። ቃሉን ሳላከብርና እኔ ሳልጠፋ ቃት ይቺ ሰው ብትሞት—አሽሌይ በህይወት ካለ. . . የለም የለም ስለሱ ማሰብ የለብኝም ። ሐጢአት ነው ። እናቴን ከጠበቀልኝ ጥሩ ሰው እሆናለሁ ብዬ ደሞ ለእግዚአብሄር ቃል ገብቻለሁ ። ዉ! ምነው ሀጻኑ ቶሎ በተወለደና በተገላገልኩ ። የትም ይሁን ብቻ ከዚህ በቃ እግሬን በነቀለውና ወደቤቴ በሄድኩ ።"

አስካርሌት አንድ ጊዜ እንደነበሷ ትወዳት የነበረችውን ይሽን ከተማ ዛሬ ላይዋ ላይ ከሚያንጎበጎበው ፀጥታ ሞምር ላይኗ እንኳን ጠላቻት ። አትላንታ ዛሬ ያቺ የጥንቷ የጠዋቷ ደስተኛዋ ፣ ሳቂታዋና

@OLDBOOKSPDF

የምታፈቅራት አትላንታ አልሆነችም ። ከወረራው በኋላ በጣም የሚ
ያስፈራ ያደፈጠ እርጭታ የጥላት ከመሆኑዋ የተነሳ አንድ ወረርሽኝ
በሽታ የነባባት በሽተኛ ከተማ መስላለች ። ድምፅ ሁሉ የሚቀሰቅሰው
ነገር አለ ። የቦምቡ ውርጅብኝ የሚነሳ ይመስላል ። በፀጥታው ውስጥ
እንኳ ሽብር አርግዟል ። ከተማይቱ ፍርሃትን ፣ መጠራጠርንና ትዝታ
ዎችን በፀፀት ስታመነሻሻ ትውላለች ። የሰው ሁሉ ፊት የቆነጠጡት
ይመስላል ። እስካርሌት ትንሽ የምታውቃቸው ወታደሮች—ሙድድር
ውስዮ የነባ ሯጭ ባላንጣው ከቀደመው ወዲያ ሮጠ ሮጠ አቅመን
ሁሉ ሟጦ ጨርሶ ሲደርስ—ያለውን መልክ ይዘዋል ።

የነሐሴ ወር የመጨረሻው ቀን መጣ ። አብሮትም የአት
ላንታ ውጊያ ከተጀመረ ጀምሮ ታይቶ እማይታወቅ የመጨረሻ
ከባድ ውጊያ መካሄዱን የሚያሳምን ጭምጭምታ ወሬ ተሰማ ። በስተ
ደቡብ ሲል አንድ ቦታ ላይ ነው ። አትላንታ ፣ የጦርነቱን ደግ ወሬ
ስትጠብቅ ለመሳቅና ለመጫወት መሞከሩንም እርግፍ አድርጋ ትታ
ዋለች ። ወታደሮቹ ከሁለት ሳምንታት በፊት ያወቁትን ነገር ፣ አሁን
አገር በሙሉ አወቀው— አትላንታ ገደል አፋፍ ላይ ተንጠልጥላለች ።
የማከኑ ባቡር መንገድ እጠላት እጅ ከወደቀ ፣ አትላንታ አለቀላት ፣
ገደል ገባች ማለት ነው ።

* * *

መስከረም አንድ ቀን ጠዋት ፣ እስካርሌት ማታ በጭንቅላቷ
ተሸክማ ወደ ትራሷ ያመጣችው አስፈሪ ስጋት ፣ እንደተናነቃት ነጋ
ላት ። እንቅልፍ ባልጨረሰ ልቧ እንዲህ ብላ አሰበች—"ትላንት ማታ
ስተኛ ያስጨንቀኝ የነበረው ነገር ምን ነበር? . . . አሃ ፣ ትዝ አለኝ —
ውጊያው ነው ። ትላንት ፡ የሆነ ቦታ ጦርነት ተካሂዷል! እንዴ ፣ ማን
አሸንፎ ይሆን?" በፍጥነት ቀና ብላ ቁጭ አለችና አይኗን ታሻሽ
ጀመር ። ያ የተጨነቀ ልቧም የትላንትናውን ጫናውን እንደገና ተሸከመ ።

አየሩ ፣ ምንም እንኳ ገና ማለዳ ቢሆን ፣ ያፍናል ። ሰማያዊ ብሩህ
ሰማይና ምሀረት የሌላት የምታነድ ፀሐይ እንደምትወጣ ተስፋ የሚ
ሰጥ ሙቀት ይኑር እንጂ ፣ አየሩ ይተነፍጋል ። የደጁ መንገድ እርጭ
ብሏል ። የሚያልፍ ጋሪ የሸከም ስቃይ አይሰማም ። በፈጣን እርግጫ
እየተራመዱ ሲያልፉ ቀዩን አፈር የሚያቦኑ ወታደሮች የሉም ። ጐረ
ቤት ባለው ማድቤት ውስጥ የሰነፍ ሬግሮዎች ድምፅም ሆነ ቁርስ
ሲዘጋጅ የሚሰማው አስደሳች ድምፅ የለም ። ከወ/ሮ ሚድና ከወ/ሮ
ሚሪዌዘር ሬግሮዎች በቀር ቅርብ ጐረቤት ውስጥ የሚሠሩት ሬግሮዎች
ሁሉ ወደማዘን ተሰደዋል ። ከነሱም ቤት የምትሰማው ነገር የለም ።

@OLDBOOKSPDF

መንገዱን ይዞ ወደታች ሲሄድ የሚገኘው የንግድ አካባቢም አፉን ይዟል ። ዞኖ ብሏል ። ብዙዎቹ መጋዘኖችና ቢሮዎች ተዘግተዋል ። ውስጣቸው ይሠሩ የነበሩትም ሰዎች ጠመንጃ ጠመንጃቸውን አንግበው ገጠር አንድ ቦታ ተቀምጠዋል ።

ይሄ ዛሬ እስካርሉትን እንዴት አድርሽ ያሳት የጠዋት ፀጥታ ከዚህ ቀደም በተከታታይ ዝምታቸውን እየታቀፉ መጥተው ከነበሩት ጠዋቶች ሁሉ ፣ የከፋና የሚያስፈራ ነው ። በፍጥነት ተነስታ ፣ እንደ ወትሮው ሳትንጠራራና ሳታዛጋ ፣ ልቧን የሚያረጋጋላት ፣ አይዞሽ የሚላት የጐረቤት ሰው ፊት ባይ ብላ ተስፋ አድርጋ ወደ መስኮቱ በረረች ። መንገዱ ግን እንኳን ሰው ወፍ ዝር አይልበትም ። የዛፎቹ ቅጠሎች እንዴት አሁንም ጥቁር አረንጓዴ እንደሆኑና ቀይ አባራ እንደነዛባቸው ተገነዘበች ። በፊት ሰፊድ ደሽፍ ያሉት ተኩትኩተው የማ ያውቁ ሳቂታ አበቦች በሀዘን መቆራመዳቸውን አስተዋለች ።

እዚያው እንደቆመች በመስኮቱ አሻግራ ማዶ ማዶውን እያየች ሳለች ፤ ከሩቅ እንደሚሰማ የንፋሳማ ዝናብ መልዕክተኛ መብረቅ የመሰለ ድክም ያለ ድምፅ ሰማች ።

“ዝናብ” አለች በመጀመሪያ ግምት ። ያ የገጠሬ አስተዳደግ ያለው አዕምሮዋ ጨመር አደረጎትና “በአርግጥ ዝናብ ያስፈልገናል” አለች። ሆኖም በዛችው ቅፅበት ሀሳቧ ተሰወጠ “ዝናብ? ኧረ የምን ዝናብ! ዝናብ አይደለም! መድፍ ነው!”

ልቧ እንዳንድ ነገር እየበለሰ መስኮቱ ላይ ዘመም ብላ ከየት አቅጣጫ እንደሚተኩስ ለማወቅ ጆሮዋን ለሚያስገመግመው ድምፅ አሳልፋ ሰጠች ። የመድፉ ድምፅ ግን በጣም ሩቅ ከመሆኑ የተነሳ ትንሽ ትንሽ ብቻ ስለሚሰማት አቅጣጫውን ለይታ ለመናገር አልቻለችም ።

“ምነው አምላኬ! ከወደ ማሪየታ ብታደርገው!” ብላ ፀለየች ። ወይም ከወደ ዴካተር ። ወይም ከፒችትሪ ከሪክ ። ብቻ ከወደ ደቡብ አታድርገው ጌታዬ! ብቻ ከደቡብ አታድርገው የኔ ጌታ! መስኮቱን አሠንም የባሰ ጥብቅ አድርጋ ይዛ ጆሮዋን የምትችለውን ያህል በድምፁ አቅጣጫ ወጠረች ። የጆሮዋ የድምፅ ማርገብገቢያ ታምቡር ግን የራሷን የልብ ትርታ በቀር የሩቁን የመድፍ ተኩስ አሳስተላልፍ አላት ። የለም ፤ አሁኑኑ ጆንስቦሮ አይደርሱም ። እዚያ ድረስ ከመጡ ድምፁ የባሰ ድክምክም ያለ ይሆን ነበር ። ያም ሆነ ይህ ግን ምናልባት ወደ ጆንስቦሮ ከሚወስደው መንገድ በታች አሥር ማይል ርቃ በምትገኘው በራፍና ሬዲ ሰፈራ መንደር ሊሆኑ ይችላሉ ። ግን እኮ ጆንስቦሮ ራሱ ከራፍና ሬዲ በታች ከአስር ማይል በላይ አይርቅም ።

@OLDBOOKSPDF

መድኃ በስተደቡብ ከሆነ ምናልባት የአትላንታን የመጨረሻ የሞት ደወል እየሰሙ ሊሆን ይችላል ማለት ነው ። ለእስካርሌት ግን ለታመመችው እናቷ በጣም ከመጨነቋ የተነሳ ወጊያው ወደደቡብ ነው ማለት ከታራ አጠገብ ጦርነት እየተካሄደ ነው ማለት ነው ። አጅዋን በእጅዋ ጭምቅ እንዳደረገች በወለሉ ላይ ስትንጐራደድ ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ነገሩ ሁሉ ከሁሉም አቅጣጫ ሲገባት ግራጫ የኒፎርም የለበሰው ሠራዊት ሊሸነፍ እንደሚችል ታያት ። ታራ ደጃፍ ያሉት በሺ የሚቆጠሩ የቬርማን ወታደሮች ብዛት ነው ይህንን ሀሳብ የፀነሰባት ። ይህ ሀሳብ የጦርነትን ሽብር ሙሉ በሙሉ ግልፅ ያረገላትን ያህል ፣ የመስኩቶችን መስታወት ብትንትናቸውን ያወጣው የወረራ ተኩስ አላስረዳትም ። ይሄ ሀሳብ የጦርነቱን ሰቆቃ ግልፅ ያደረገላትን ያህል ፣ መራብና መታረዝ ግልፅ አላደረገላትም ። ይሄ ሀሳብ የጦርነትን እስከፊ ውጤት ግልፅ ያደረገላትን ያህል ፣ በሺ የሚቆጠሩ እንደሀረማ የሚጐትቱት ረዥም መስመር ላይ የተጋደሙ የወገኖቿ ሬሳዎች አላስረዷትም ። የቬርማን ጦር ከታራ ጥቂት ማይል ርቀት ላይ! ያንኪዎች ቢሸነፉ እንኳ የሚያረገግጉት በታራ በኩል ነው ። ጂራልድ ደሞ ሶስት የታመሙ ሴቶች ይዞ ሸሽቶ መሄድ አይችልም ።

እዩ! እንዳው ያንኪዎቹ ኖሩም አልኖሩ አሁን እዚያ ብትሆን እንዴት ጥሩ ነበር ። ፒሸማዋን መሬት እያንዘረዘረች ፣ በባዶ እግሯ ስትንጐራደድ ፣ ብዙ በተራመደች ቁጥር መጪውን ክፉ ነገር የማሰቢ ነገርም እየበረታባት ሠጣ ። ቤቷ መሆን ትፈልጋለች ። ኤለን አጠገብ መሆን ትፈልጋለች ።

ከታችኛው ማድቤት ፕሪሲ ቁርስ ስታዘጋጅ የሚፈጠረው የሳህን ኳኳታ ይሰማል ። የወይዘሮ ሚድ ሠራተኛ የቤትሲ ድምፅ ግን ዙሩም የለ ። ፕሪሲ በአይጥ ድምፅዋ “ከባዱን ሸክም ለማቅለል ጥቂት ቀናት ይቀሩናል. . .” የሚለውን መዝሙር ስትዘምር ይሰማል ። መዝሙሩ ያንን የምትፈራውን ነገር ደግሞ በአእምሮዋ ቀረፀባትና አንገት ልበሷን ትክሻዋ ላይ ጣል አድርጋ ባዳራሹ ተንደርድራ ወደ ኋለኛው ደረጃ ሄደችና “አንቺ ፕሪሲ! ይሄን መዝሙር ተይና እፍ ሽን በማሪሽ ተቀመጪ!”

በጣም ደብዘዝ ባለ ድምፅ “እሺ እመቤቴ” ብላ ስትመልስላት ፣ ጠለቅ ያለ ትንፋሽ ተነፈሰችና ባደረገችው ሁሉ ሐፍረት ተሰማት ።

“ቤትሲ የት ሄደች?”

“እኔ እንጃ ፣ አልመጣችም ።”

አስካርሌት ወደ ሜላኒ ክፍል ሄዳ በሩን ጥቂት ከፈት አድርጋ በፀሐይ ብርሃን የሚንበለበለውን መኝታ ቤት አየልቃ ተመለከች ።

@OLDBOOKSPDF

ሚለኒ የማታ ቢጃማዋን እንደለበሰች አልጋው ላይ ተንጋላለች ። ዓይኖቿ ተዘግተው ዙሪያዋውን እንደማድያት ያለ ጥቁር ቀለበት ከቧቸዋል ። የልብ—ቅርፅ ያለው ፊቷ ልስላሴውን አጥቶ ብልዝ ብሏል። ያ ለስላሳው ስውነቷም የቅርፅ ቅጡን አጥቷል ። እስካርሌት በውስጧ ምንው አሽሌይ እንዲህ ሆና ባያት ብላ ተመኘች ። ከማንም አርማዝ ካየቻት ሴት የባሰ ተበላሽታለች ። እዚያው ቆማ እያስተዋለቻት ሳለች ሚለኒ ዓይኗን ገለጠች ። ፊቷንም እንደልብ ያለች ለስላሳ ፈገግታ ሞላችው ።

"ማቢ" አለች የማይን ባንድ ጐኗ ገልበጥ ብላ ። "ፅሐይ ከወጣች ጀምሮ ነቅቼ ሳስብ ነበር ። እስካርሌት አንድ ልጠይትሽ የምፈልገው ነገር አለ ።"

ወደ ከፍሉ ገብታ የጧት ፀሐይ ፏ ብሎ በበራበት አልጋ ላይ ተቀመጠች ።

ሚለኒ የማይን እጅዋን ዘርግታ በቅስታና ምሥጢር በሚናገር ሰው አያያዝ ረጋ ብላ የእስካርሌትን እጅ ያዘች ።

"የኔ እናት" አለች ሚላኒ "ስለታንኩ ጨኽት በጣም አዝናለሁ ። ወደ ጆንስቦሮ አይደል ድምፁ?"

እስካርሌት "እም" እያለች የልብ ትርታዋ ጨመረ ። ይሄ ሀሳብ በድጋሚ ሲመጣ እንደገና አሳሰባት ።

"ምን ያህል እንደተጨነቅሽልኝ ይገባኛል ። ለኔ ብለሽ ባይሆን ኖሮ ስለ እናትሽ ስትሰሚ ገና ባለፈው ሳምንት ወደቤትሽ በሄድሽ ነበር ። አይደል እስካርሌት?"

"አም" አለች እስካርሌት ደስ ሳይላት ።

"እስካርሌት የእኔ እመቤት ፤ እስከዛሬ ብዙ ውለታ ሠርተሽልኛል ። የገዛ እህቴ እንኳ እንዳንቺ ደግ ፥ እንዳንቺ ጠንካራ አሳቢ አት ሆንልኝም ። ስለዚህ ከልብ እወድሻለሁ ። ከመንገድሽ ስላቋረጥኩሽ አዝናለሁ ።"

አስካርሌት ትክ ብላ ተመለከተቻት እውነት ትወዳታለች እንዴ? ምን ጅል ናት ጃል ።

"እና እስካርሌት ፤ አሁን ተኝቼ ሳስብ ነበር ። አንድ ውለታ እንድትሰሪልኝ እለምንሻለሁ ።" እጅዋን ጨበጠች ። "ድንገት ከሞ ትኩኝ ልጄን ታሳድጊልኛለሽ?"

@OLDBOOKSPDF

የሚላኒ ዓይኖች እስክሚችሉት ተከፍተው በጥድፊያ ታዲያስ ይላሉ ።

"እና እሺ ትይኛለሽ?"

እስካርሌት ጥርሃት እያጥለቀለቃት ሲሄድ እጅዋን አርገበገበች ። ጥርሃት ድምፅዋን አሻከረው ።

"ሜሲ ምነው ምን ነካሽ ። ልትሞች የምትችይበት ሁኔታ የለም ። ማንም ሴት የመጀመሪያ ልጅዋን ልትወልድ ስትል የምትሞት ነው የሚመስላት ። እኔም እንደዛው ብዬ ነበር ።"

"አይ . . . አንቺ እንኳን አትይም አላምንም ። አንቺ ምንም ነገር አስፈርቶሽ አያውቅም ። እኔን ሰማዕናናት ብለሽ ነው እንጂ አንቺ እትፈሪም ። እኔ መሞቴ አላስፈራኝም ። ግን ሀዳኑን ልጅ ጥሎ መሞት አሸሌይ እንኳ የለ . . እስካርሌት ልጄን እንደምታሳድጊልኝ ቃል ግቢ ልኝ ። እንደዛ ካረግሽልኝ በፍፁም አልፈራም ። ወ/ሮ ዊታፓት አሮጊት በመሆንዋ ልጅ ማሳደግ አትችልም ። ሐኒና ኢንዲያም ጥሩ ናቸው እሪ ግን ልጄን አንቺ እንድታሳድጊልኝ ነው የምፈልገው ። ቃል ግቢ ልኛ አስካርሌት ። የኔ እመቤት የሚወለደው ልጅ ወንድ ከሆነ በአሽ ሌይ እንዲወጣ አድርገሽ አሳድጊልኝ ። ሴት ከሆነች ግን—የኔ እመ ቤት—አንዳንቺ እንድትሆን ነው የምፈልገው ።"

"አረ በፈጠረሽ!" አለች አስካርሌት በጩኸት ካልጋዋ እየዘለ ለች ። "እንዴ ካለሞትም ወሬ የለሽ ዛሬ!"

"አዝናለሁ የኔ እመቤት" ብቻ ቃል ግቢልኝ ። እንደሚመስለኝ ዛሬ ሳልወልድ አልቀርም ። እርግጠኛ ነኝ ዛሬ እገላገላለሁ ። እባክሽ ቃል ግቢልኝ ።"

"ጢ—እሺ በቃ ቃል እገባልሻለሁ ።" አለች አስካርሌት በመደ ናገጥ ቁልቁል እያየቻት ።

ወይ ጉድ ይቺ ሚላኒ የምትባል ሴትዮ አስካርሌት ለአሽሌይ ምን ያህል እንደምትጨነቅለት አታውቅም እንዴ? ምን ጅሏ ናት? ወይስ ሁሉን ነገር አውቃ ያው ስለ አሽሌይ ባላት ጥቅር ለልጁ ትጠ ነቀቅለት ይሆን? አስካርሌት ብዙ የሚያስጨውቃት ነገሮች አሉዋት ። ግን ሚላኒ እጅዋን ይዛ ከጉንጩዋ ጋር አስታካ ስታሻሽላት ሁሉም ሀሳቦቿ አፍዋ ላይ ይመሞሙዋሉ ። ዓይኑዋ ላይ መረጋጋት ይታያል ።

"ሜሊ ፣ እንዴት ዛሬ ይሆናል ብለሽ አሰብሽ?"

@OLDBOOKSPDF

“ጠዋት ጐሳ ሲቀይድ ሲምባ ሲመጣ ሲሰማኝ ነበር—እርግጥ በኃይል አልተጫነኝም”

“እሞሽ ነበር እንዴ? ለምን አልጠራሽኝም ነበር? ቆይ ፕሪሲን ዶክተር ሚድ ጋ እልካታለሁ።”

“እስካርሌት ቆይ ገና ነው፤ እሱን መጥሪያው ሰዓት አሁን አይደለም። አሁን ምን ያህል በሥራ እንደሚጠመድ አታውቂም። ሁሉስ ቢሆኑ መች ሥራ ይፈታሉ። ዝም ብለሽ ዛሬ አንድ ጊዜ ልናስጠራው እንደምንችል ብቻ ንገሪው። ለወይዘሮ ሚድም መጥታ ከእኔ ጋር እንድትሆን ላኩባት። እሷ መቼ እንደምንልክባት አሳምራ ታውቃለች።

“እንዴ ይሄን ያህልም ራስሽን ቸል ማለት አይገባም። ሆስፒታል እንዳሉ ሰዎች ሁሉ አንቺም ዶክተር ያስፈልግሻል። አሁኑኑ ነው የምልክበት።”

“አይ ተይ ባክሽ አይሆንም። አንዳንድ ጊዜ ወሊድ ቀኑን ሙሉ ይፈጃል። እና ዶክተሩ እዚህ ተገልቶ እኔን ሲጠብቅ አይውልም ስንት ሚስኪኖች ሆስፒታሉ ውስጥ ያቃስታሉ እኮ። ዝም ብለሽ ወይዘሮ ሚድን አስጠሪያት። እሷ ታውቃለች ለማንኛውም።”

“እሺ እንግዲያው” አለች እስካርሌት።

@OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ 21

እስካርሌት የሚላኒን የቁርስ ትሪ ከላከችላት በኋላ ፕሪሲን ወደ ወይዘሮ ሚድ ሰድዳ ከዋድ ጋር ቁጭ ብላ የራስዋን ቁርስ ለመብላት ቀረበች። ግን የምግብ ፍላጐቱ ከየት ይምጣ። እንድም የሚላቷ የምጥ ሰዓት መቃረብ፡ እንድም ካሁን አሁን የታንኩን ድምፅ ለመስማት ያላት ጭንቀት፡ ተደራርቦ ሲያስምጣት፤ የምግብ ፍላጐትዋ ተዘጋ። የልብ ምቷ ተዛብቶ አንዳንዴ ጊዜ ጊዜ እየለየ ሲመታ፤ አንዳንዴ በፍጥነት እየጋለበ ሆዱዋን እስኪያምማት ድረስ ሲመታ ይሰማታል። ያ የበቆሎ ዱቄትና በወተት የላመ የወትሮ ቁርሷ እንኳ ከጉረሮዋ አልወርድ አላት። እንደመጫ ላንቃዋ ላይ ይጣበቅ ጀመር። ከዚህ ቀደም ይሄ ለመቅሰስ ስትውጥ—ስትሰለቅጠው የነበረ ገንፎ መሰል ምግብ፡ አልበላ ማለት ቀርቶ ጠግባው እንኳን አታውቅም ነበር። ያለስኳር ወይ ያለክሬም አልሞከር አላት። ሰማጣፊጫ ተብሎ የተጨመረበት ማሽላ እምብዛም ምሬቱን አልቀነሰውም። እንዴ ዋጠችና ገበታውን ገፋችው። ያንኪዎቹን ከምትጠላበት አንጹ ቡና ያለስኳርና ያለቅቤ እንድትጠጣ ስላደረጉዋት ነው።

ዋድ ዛሬ ጠዋት በቁርሱ አለመጣፈጥ እንዴ ወትሮው አልተነጫነጨም። ወዳፉ በማንኪያ የምትልከውን ሁሉ ፀጥ ብሎ እየጐረሰ በወታ ያወራርደዋል። አይኖቹን አፍጥጦ ፍርሃትዋን ያጋባችበት ይመስል አብሮዋት ክርትት ክርትት ያደርጋቸዋል። በልቶ ሲያበቃ ወደ መጫወቻ ቦታው ላክችውና እየበረረ ሣር ወዳቆጠቆጠበት ሜዳ ሲሄድ በእርጋታ ተመለከተችው።

ምን እንደምታደርግ ቅጡ እየጠፋት ተነሳችና ከደረጃው ግርጌ ቆመች። ሚላኒ ጋ ሄዳ ይሄ ጭንቅላትዋ ውስጥ የሚምታታውን ሀሳብ ልታቃልል ፈለገች። ግን ጭንቀቱ አየለና አልገፋ አላት። እንዳው ከቀን ሁሉ የሚላኒ ምጥ ዛሬ ይምጣ፡ እስቲ ካልጠፉ ቀን መውለጃዋ ዛሬ ይሁን! እስቲ ስንት ቀን እያለ ዛሬ ስለሞት ይወሳል!

ከደረጃው ግርጌ ተቀመጠችና ራሷን ረጋ አድርጋ የትላንት ውጊያ እንዴት እንዳለፈና የዛሬውስ እንዴት እንደቀጠለ በጥሞና ለማሰብ ትሞክር ጀመር። ትልቅ ጦርነት ከጥቂት ማይሎች ባሻገር ሲካሄድ አንዳችም ነገር ለመስማት አለመቻል እንዴት ያለ እንግዳ

@OLDBOOKSPDF

ነገር ነው፤ ፒቾት ሰውነቱ ሁሉ ወደ ሚያምር አይን ፥ ይቺ ባዶዋን ከመንገዱ ጫፍ ላይ ያለች ከተማ ፀጥ ማለት እንዴት የሚገርም ነገር ነው፤ የወ/ሮ ፒቲ ቤት ከመንገዱ መጨረሻ ካሉት ቤቶች አንዱ ነው ። ወጊያው ከከተማው ደበብ ሆኖ ሳለ ለእርዳታ በፍጥነት የሚሄድ ኃይልም ሆነ የአምቡላንሶች መራወጥ ፥ ወይም የቆሰሉ ሰዎች የመልስ ጉዞ አይታይም ። እንዲህ ያለውን ትርዒት ወደ ደበብ ይታይ ይሆን ብላ ገረማትና እዛ ባለመሆንዋ እግዚርን አመሰገነች ። እዚህ እስሜኑ ክፍል ፥ ከሚድና ከሜሪዌዘር ቤተሰብ በስተቀር ፥ ሁሉ ሰው ሄዶ ብቻዋን ብትቀር እንዴት ጥሩ ነበር ። ምነው አጐት ፒተር በኖረና ወደ ከተማ ሄዶ ወሬ ይዞላት በመጣ ። ሜሳኒ እንዲህ ሆና እንዴት ብቻዋን ጥላት እንደምትሄድ ቸግሯት ነው እንጂ እራሷም ብትሆን ሄዳ ሁሉን ነገር ሰምታ በመጣች ነበር ። ግን እንዴት ብላ ወይዘሮ ሚድ እስክምትመጣ መቆየት አለባት ። ወይዘሮ ሚድ ምነው አልመጣችም ታዲያ፣ ፕሪሲስ ወዴት ሄዳ ነው?

ተነሳችና ወደደጅ ወጣች ። ትዕግስቷ እስክሚያልቅ ብታይ ብታይ የሚሄድበት ቤት እመንገዱ መጠምዘዣ ላይ ቢሆንም ማንንም አጣች ። አልቻለችም ። ከብዙ ጊዜ በኋላ ፕሪሲ ቀኑን ሙሉ ስትንቀሳቀስ ወላ እየተቅለሰለሰችና ቀሚስዋን ወዲያና ወዲህ እያማታች ፥ ከትከሻዋ በላይ ቀሚሷን ቁልቁል በመመልከት ምን እንደሚመስል እያስበች መጣች ።

"ምን እንደ ኤሲ ያንቀረፍፍሻል አንቺ" አለች እስካርሌት፥ ፕሪሲ በሩን ከፍታ ስትገባ ።

"የሱም አጣሁዋቸው" አለች ፕሪሲ
"የት ሄዳለች፣ መቼ ትመለሳለች?"

"አይ እሜቴ" ብላ አንገራገረች ፕሪሲ ፥ ለጥዳዩ ከብደት ለመስጠት ። "አሽከሩ እንደነገረኝ ወይዘሮ ሚድ ጠዋት የወጡ አልተመለሱም ። ልጃቸው ሚስተር ፊል በጥይት ተመቶዋል ተብሎ ተነግሮዋቸው አሮጊቷን ታልቦትንና ቤትሲን ይዘው ፍሊጋ ሄደዋል ። አሽከር የው እንደሚለው ልጁ በጣም ስለተጐዳ እሜቴ በጊዜ የሚመለሱ አይመስልም ነው ።"

እስካርሌት ከመናደዷ የተነሳ ልታጋጫት ከጅላት ነበር ። እነዚህ ኤግሮዎች መኖር ወሬ ይዘው ሲመጡ ኩራታቸው አይጣል ነው ።

"ታዲያ ምን እንደ ሐውልት ይገትርሻል ። ወደ ሚሪዌዘር ጋ ሂጂና ወይ አራሷ እንድትመጣ ወይ ሞግዚቷን እንድትልክልን ንገሪያት ። በይ ቶሎ ሩጪ ።"

@OLDBOOKSPDF

"እነሱም ሶሉም ። ወደዚህ ስመጣ ከሞግዚቷ ጋር እየተጫወተ ትሁ ጊዜ ሳሳልፍ እግረመንገዴን ጐራ ብዬ ነበር ። ቤቱ በሙሉ ተቆልቷል ። ሁሉም ሂደዋል ። ወደ ሆስፒታል ነው የሄዱ የመሰለኝ ።"

"እና እሳ ገብተሽ ነሞ ይሂን ያህል ስዓት የቆየሽውን ቆይ ብቻ ከሣሪ ወዲያ እንዲህ ስታደርጊ ባይሽ እኛ በየመንገዱ እንደአመለኛ በቅሎ እየቆምሽ ጊዜዬን ሳሳልፍ ስትይ ባጎንሽ ነግሬሻለሁ ። ሂጂና . . ."

ቆም አለችና ታስብ ጀመር ። በክብማው ሊረዳት የቀረ ሰው ማን አለ እንግዲህ አሃ ወይዘሮ ኤልሲንግ አሉ ። እርግጥ ወይዘሮ ኤልሲንግ እንኳን አያመዷትም ግን ሚሳኒን ሲመዷት ለጉድ ነው ።

"በይ ወይዘሮ ኤልሲንግ ጋ ሂጂና ሁሉን ነገር በጥሞና አስረድተሽ እዚህ እንዲመጡ ንገሪያቸው ። እይሙ በደንብ አሜምጪ ፕሪሲ ፣ እንደምትይ ፣ የወይዘሮ ሜሲ ልጅ መሙለጀያው ሰለተቃረበ አውን ባንድ አፍታ ድረሱ ትፈልግዎታለች በያቸው ። በይ በቀጥታ ሂጂ ።"

"እሺ እመቤቴ" ብላ ፕሪሲ ፊቷን አዙራ ቁስ እያለች እንደ ቀንድ አውጣ ትሰብ ጀመር ።

"ኧረ ፈጠኜ በይ እንች ቀርፋፋ ቀረፈፍ!"

"እሺ እመቤቴ ።"

ፕሪሲ ተጣድፋ ወጣች ። እስካርሌትም ወደቢቷ ተመልሳ ገባች ። ወደሚኒላ ከመሂድዎ በፊት ግን ትንሽ አመነታች ። ወይዘሮ ሚድ እንዴት እንደቀረችና ልጅዋ ፊሊም መቁሰሉን ማሰረዳት ሊኖርባት ነው ። ምናባቱ ፣ እንግዲህ ዎሽታ የሆን ሰበብ ትፍጠር በቃ ።

እሚሳኒ መኝታ ቤት ሰትገባ የቁርስ ትሪው እቺን ታህል ሳይነካ እንዳለ ቁጭ ብሳለ ። አልበላቺውም ። ሚሳኒ በጐንዋ ተኝታለች ።

"ወይዘሮ ሚድ ወደ ሆስፒታል ሄዳለች አሉ ። ወይዘሮ ኤልሲንግ ግን አውን ይመጣሉ ። ጠናብሽ እንዴ?" አለች እስካርሌት ።

"አይ እስከዚህም ነው ።" ብላ ዋሸች ሚሳኒ ። "እስካርሌት ዋድን ለትወልጂ ምን ያህል ቆየብሽ?"

"ውይ ባንድ አፍታ ነዋ" አለች የማይሰማትን ደስታ የተሰማት በማለመሰል ። እውጪ ሚዳው ሳይ ስለነበርኩ እቤት እንኳ ለመግባት ጊዜ አልሰጠኝም ። ማሚ እንደባሪያ ሚዳ ሳይ መውለድ ነውር ነው ብላ ተቆጣችኝ ።"

"አዬ አውንስ እኔም እንደባሪያዎቹ በሆንኩኝ" አለች ሚሳኒ ፣ ፈገግታዋን እያሳየች ። ወዲያው የህመም ስሜት ፊትዋን አጨማደደውና ፈገግታዋ ጨለመ ።

@OLDBOOKSPDF

እስካርሌት ቁልቁል ወደ ሜላኒ ዳሌ ተመለከተችና ተስፋዋ ቢሟ ጠባትም ለማጽናናት ብላ "አይ ምንም አይልሽ ደህና ነሽ እኮ" አለች ።

"እሱስ ደህና አይደለሁም ። በጣም ሰማቻለሁ ። ወይዘሮ ኤልሲ ንግ በቅጥታ አይደል ወዲህ የሚመጡት?"

"አዎ አሁን በቅጥታ ይመጣሉ" አለች እስካርሌት ። "ቆይ ታች ወርጄ አስፖንጅና ውሃ ይዤልሽ ልምጣ ። ዛሬ በጣም ይሞቃል።"

ካሁን አሁን ፕሪስ መጣች አልመጣች እያለች ወደበሩ ስትመላ ለስ ፤ ውሃውን ወደ ሜላኒ ይዛ የምትሄድበትን ጊዜ አስረዘመችው ። የፕሪሲ መምጣት ምልክቱም ጠፋ ። ስለዚህ ወደ ሜላኒ ተመልሳ ያላበውን ገላዋን በስፖንጅ ታደራርቅላት ፣ ረሽም ጥቁር ፀጉርዋን ታበጥርላት ጀመር ።

አንድ ሰዓት ያህል እንዳለፈ የኔግሮ ኩቴ ሰምታ በመስኮት ስት መለከት ፕሪሲ እንደቅድመ ቀስ እያለችና ተመልካች ያላት ይመስል ጭንቅላትዋን ግራና ቀኝ እያወዛወዘች—በቤቷ መዘነጓ ነው—ስትመጣ አየቻት ።

"ቆይ ብቻ ይቺን አመዳም ሳላሳያት ብቀር" አለችና በልቧ እስካርሌት ቁልቁል ደረጃውን ተንደርድራ ወረደች ።

"ወይዘሮ ኤልሲንግም ወደ ሆስፒታል ሄደዋል ። በጠዋቱ ባቡር በርከት ያሉ ቁስለኞች ገብተዋል አሉ ። ገረድየዋም ወደሃው ለመሄድ ስትሰናዳ ነው ያገኘሁዋት ። ቮርባ ይዛ ልትሄድ ትዘገጃጅ ነበር ። እንዲህ አለች . . ."

"እሷ ምንም ትበል" እስካርሌት እየተሳቀቀች አቋረጠቻት ። "በይ ደህና ልብስ ልበሺና ወደ ሆስፒታል ሂጂ ። መልዕክት ጽፌ እሰ ጥሻለሁ ፤ ወስደሽ ለዶክተር ሚድ ስጪው ። እሱን ካጣሽው ለዶክተር ጆን ወይም እዛ ላገኘሽው ለየትኛውም ዶክተር ስጪው ። ደሞ ፊጥ ነሽ አትሂጂና ዋነ የውስጥ ቆዳሽን ነው ወደ ላይ የምገለብጠው!"

"እሺ እመቤቴ"

"ደሞም ያገኘሽውን ሰው ውጊያው ምን እንደደረሰ ጠይቂ ። እነሱ አናውቅም ካሉሽ ወደ ባቡር ጣቢያ ሂደሽ ቁስለኛ የሚያጓጉዙ ትን መሃንዲሶች ጠይቂያቸው ። ውጊያው ጅንስቦሮ ላይ ወይም እዚያ አቅራቢያ መሆኑን አረጋግጪና ነይ ።"

"ወይኔ አምላኬ ፣ አትዬ እስካርሌት !" አለችና ፕሪሲ ጥቁሩን ፊቷን ፍርሃት ወረረው ። "ያንኪዎቹ ታራ ናቸው እንዴ?"

@OLDBOOKSPDF

"አላውቅልሽም። እሱት አይደል እንዴ ጠይቂ የምልሽ"

"ውይ አምላኬ! እትዬ እስካርሌት! እንዴት ያደርጉን ይሆን!"

ፕሪሲ በፍርሃት እየጮኸች ስትናገር ጭራሽ የአስካርሌትንም ጭንቀት አባባሰችባት።

"እንግዲህ አትጩኺብኝ! ሚላኒ ትሰማለች። በይ አሁን ቶሎ የረባ ልብስ ቀይሪ።"

ፕሪሲ እየተጣደፈች ወደ ማድቤት ስትሄድ አስካርሌት በቤቷ ያጣጋቻትን ብጣሽ ወረቀት—ከጂራልድ ደብዳቤ ላይ ያልተጻፈበትን ቀጳ ነው ያውም—ቶሎ ቶሎ ጫር ጫር ማድረግ ጀመረች። የጻፈችውን ስታነብ ከሰሩ ጂራልድ የጻፈውን..."እናትሽ... የእንጀት ተስቦ... እንደ ምንም ብለሽ... እቤት መምጣት አለብሽ..." የሚለውን አየችና እንባዋ አነቃት። የሚሰኒ ነገር ሆኖባት ነው እንጂ በእግሯም ቢሆን ወደ ቤቷ መሣነድ በቀጠለች ነበር።

ፕሪሲ ወረቀቱን ተቀብላ ብን ብላ ስትሄድ፣ አስካርሌት ደግሞ ተመልሳ ወይዘሮ አልሲንግ ስምን ቀሩ እንደምትልና ለሚላኒ እንደምትሞሽ እያሰበች ደረጃውን ወጣች። መቼም ዛሬ አበሳ ጣጣዋን ነው ያየችው። ደግነቱ ሚላኒ ምንም ጥያቄ አልጠየቀች። በጀርባዋ ተንጋሳ ዝም ያለውና ያማረ ፊቷ ያሳዝናል። አስካርሌት ይሄን የፊቷን ገምታ ከቷይ ስትንሽ ጊዜ ፀጥ ብላ ቆመች።

ቁጭ አለችና የማይገናኙና ውል የሌላቸውን ነገሮች እንዲያውለማውራት ያህል ብትቁበጣየርም፣ ያ የታራ ሃሳብና በያንኪዎች ድል የመመታት ሥጋት እያየለ ጭንቅላትዋን ከራኛ በጠበጣት። የኤሰን ልትሞት መቃረብና የያንኪዎች ወደ አትላንታ መጥቶ ዛር ቅጠሉን ማጋየት፣ ሰዉንም እገሌ ከገሌ ሳይሉ መግደል፣ አስካርሌትን በጣም አሳሰባት። በዚሁ ውስጥ ከሩቅ ይሰማ የመሰላት የመድፍ ጩኸት በፍርሃት ማዕበል እየተገፋ እየሰረገ ጆሮዋ ውስጥ ምስማ ይል ጀመር። በመጨረሻማ ማውራቱም እምቢ አላትና በመስኮቱ አሻግራ በጠራራ ፀሐይ የነደደውን ባዶ አውራ መንገድና አቧራ ለብሰው በየዛፉ ላይ ያሰአ ንዳች እንቅስቃሴ የተንጠለጠሉትን ቅጠሎች ታስተውል ገባች። ሚላኒም ፀጥ ብላለች፣ ብቻ አልፎ አልፎ ሀመሙዋ ፊቷን ያደፈርሰዋል።

ከእያንዳንዱ ቁርጠትዋ በኋላ "ይሄን ያህልም አላመመኝም እስከዚህም ነው" ስትል፣ አስካርሌት መዋሸትዋ ይገባታል። ዝም ብላ ስቃይዋን ከመቻል ይልቅ ጮክ ብላ በመኸች ይሻላት ነበር። አስካርሌት ለሚላኒ ማዘን እንዳለባት ብታውቅም፣ በጭራሽ አታታት። ጭንቅላቱዋ በገዛ ራስዋ ምጥ ተወጥሮ በጭራሽ ለሌላ ማዘን አልቻ

@OLDBOOKSPDF

ለችም ። መክራ የሰፈነበትን የሚላኒን ፊት ትክ ብላ አየችና ከማንም ሰው ይልቅ እሷ ብቻ ከሚላኒ ጋር ባሁኑ ቀውጢ ሰዓት አብራ መቀመጣዋ ገረማት ። ያወም አሷ ። ከሚላኒ ጋር የሚያመሳስላት ምንም ነገር ሳይኖር ። እየጠላቻትና ብትሞት እንኳ ትደሰት የነበረች ሴትዮ እንደዬት አሁን ከሷ ጋር ተቀመጠች ። ገረማት ። ምናልባት ቀኑ ሳያልቅና ሳያልፍ ታስ ኑዛዜዋን ትቀበል ይሆናል ። ብቻ ቆይታ የዘልማድ እምነቷ እንዲህ በማሰቧ አስደነገጣት ። መቼም እንድ ሰው ይሙትልኝ ብሎ መመኘት የመራገምን ያህል የከበደ ነው ። ደግ አደለም ። እርግማን ደሞ ማሚ እንዳለችው በራስ ይደርሳል ። ወዲያው ፈጥና ሚላኒ እንዳ ትሞት በልቧ ወለየችና ምን እንደምታወራ እንኳ ልብ ሳትል ወሬ ጀመረች ።

በመጨረሻ ሚላኒ ያተኮሰውን እጅግን አስከርሌት እጅ ላይ አስቀ መጠችና "ባለማውራቱ አትጨነቂ የኔ እናት ። ምን ያህል እንደተ ጨነቅሽልኝ ገብቶኛል ። ስላስቸገርኩሽ አዝናለሁ" አለች ።

አስከርሌት ዝም አለች ፣ ግን መረጋጋት አልቻለችም ። ልቧ አላ ርፍ አላት ። ለመሆኑ ዶክተሩም ሆነ ፕሪሲ በማዜ ካልመጡ ምናባቷ ሊውጣት ነው፣ ወደ መስኩ ሄዳ አይታ ተመለሰችና ቁጭ አለች ። ደሞ ተንስታ በመስኩ አሻግራ ወደ ሰላኛው የቤቱ አቅጣጫ አየች ።

አንድ ሰዓት አለፈ ። ሌላም ተከተለ ። ጥሲያት ሆነ ፣ ፀሐይዋ አናት አናት የምትመታበት ቦታ ሆነች ፣ ጎራው ትንሽ እንኳ ትንፋሽ ሰለሌለው ቅጠሎች በያሉበት አቧራ እንደለበሱ ቆመዋል ። ሚላኒ ምጧ እየበረታ መጣባት ። ረኽሙ ጠጉሯ በላብ ጮቅ ፣ ልብሷ ሁሉ ከገላዋ ጋር ተጣበቀ ። ላብ በላብ ሆነች ። አስከርሌት በስፖንጁ ልታ መጥላት ትሞክራለች ፣ ግን ፍርሀት መጣሁብሽ ይላታል ። እረ በበለስ! ዶክተሩ ሳይመጣስ ልጁ ቢመጣ፣ ምን ልታደርግ ነው፣ ስለማዋለድ ምንም አታውቅ ። እንዲህ ድንገት ከች ቢልስ እያለች ነበር ሳምንቱን ሙሉ ስትጨነቅ ፣ ስትጠበብ የቆየችው ። እንግዲህ ዶክተርም ቢጠፋ ያለቻት ያቺው አንድ ፕሪሲ ናት ። አዎ ፕሪሲ ስለማዋለድ በቅጡ ታውቃለች ። አራሷም ደግማ ደጋግማ ተናግራለች ። ታዲያ ፕሪሲስ የታለች፣ ምነው ቀረች? ዶክተሩስ ለምን አልመጣም፣ እንደነና ወደ መስኩ ሄደችና ወደውጪ አየች ። እስከምትችለው ድረስ ለማዳመጥ ብትጥር ከሽ የሚል ድምጽ ጠፋ ። የታንኩ ድምፅ እንኳ ከሩቅ ይሰማ የነበረው አንደኛውን ጠፋ ። የሷ ግምት ይሆን ወይስ ከጆሮዋ ነው፣ ገረማት ። እርቆ ሄዶ ከሆነ ፣ ከጆንስቦሮ ሄደዋል ማለት ነው ። ያ ማለት ደግሞ. . .

@OLDBOOKSPDF

በመጨረሻ ፕሪሲ ቁልቁል አየርሀት ለትመጣ አየቻትና በመስኩት አንገሯዋን አውጥታ አጎነበሰች ። ፕሪሲም ቀና ብላ አየቻትና ለመጮህ ታጥቂት አፍዋን ከፈተች ። በጥቁር ፊቷ ላይ የሚታየውን ጭንቀት አንብባ ፤ እስካርሌት ፤ ከጮኽች ሜላኒ ትሰማለች ብላ ሰግታ እጇዋን አፏ ላይ አድርጋ በምልክት ዝም በይ እለቻትና ከመስኩቱ ተነስታ ሄደች ።

"ቀዝቀዝ ያለ ውሃ ላምጣልሽ" አለች ፤ ቁልቁል የሜላኒን ከብ ጥቁር አይኖች እያየች ፈገግ በማለት ። ከዛ በሩን ከሁዋላዋ በርጋታ ዘግታ ተቻኩላ ወጣች ።

ፕሪሲ ከደረሷው የመጨረሻ እርከን ላይ ተቀምጣ ታለከልካ ለች ።

"እትዬ እስካርሌት ፤ ጆንስቦሮ ላይ ውጊያ አለ አሉ ። የኛ ሰዎች እየተረቱ ነው ። ወይኔ አምላኬ! እኔንና ፖርክን ምን ይውጠን ይሆን! ወይ አምላኬ! እትዬ እስካርሌት ያንኪዎቹ እዚህ ቢመጡስ ምን እንሆን ይሆን! ወይ አምላኬ! "

እስካርሌት የሚንተባተብውን አፍዋን በእጇዋ አፈነቻትና "ኧረ በፈጠረሽ ዝም በይ!"

እውነት ያንኪዎቹ ቢመጡባቸው ምን ጉድጓድ ሊገቡ ይሆን ? ታራስ እንዴት ትሆን ይሆን፣ ይሄን ሃሳብ ወዲያ ገፍትና ይልቅ አሁን ያፋጠጣትን ችግር እንዴት እንደምትወጣው ታስብ ጀመር ። እነዚህን ነገሮች ሁሉ ካሰበችማ እሷም እንደ ፕሪሲ አፍዋን ከፍታ ልታንባርቅ ነው ።

"ዶክተር ሚድ የታል? መቼ ነው እሚመጣው?"

"በጭራሽ አላየሁትም እትዬ እስካርሌት ።"

"ምን!"

"የለም እመቤቴ ዶክተሩ ሆስፒታል ውስጥ የለም ። ወይዘሮ ኤልሲንግም ሆኑ ወይዘሮ ሜሪዌዘርም የሉም ። ይህንን የነገረኝ ሰውዬ እንደሚለው ከጆንስቦሮ ብዙ ቁስለኛ ወታደሮች መጥተው ቡቾሙ መኪናዎች ሥር ተዘርረዋል ። ዶክተሩ እዛ ነው የሄደው አሉ ። እዛ እንዳልሄድ ፤ እትዬ እስካርሌት ፤ በጣም ፈራሁ ፤ ሰዎቹ እየሞቱ ነው ። እኔ የሞተ ሰው ማየት በጣም ያስፈራኛል . . .

"ሌሎቹስ ዶክተሮች?"

@OLDBOOKSPDF

"እትዬ አስካርሌት መሄዳቸውን ያመንኩበለኝን አንዱን እንኳን ማግኘት አልቻልኩም ። እነ ሆስፒታል ውስጥ ሁሉም ነብሳቸው እስክ ትወጣ ድረስ ይራወጣሉ ። ይዋከባሉ ። እንደ እብድ ነው የሚሩጥሩ ዋጡት ። ከማህላቸው አንደኛውን ዶክተር ብገኘው 'አንቺ የማትረቢ! ነብር አየኝ በይ! ስንትና ሰንቱ ሰዎች በሞት አፋፍ እያቃሰቱ አንቺ ስለሚወለድ ልጅ ታወሪልኛልሽ—ጥሬ ከፊቴ! የሆነች ሴት ፈልጊና ትርዳሽ' አለኝ ። ከዚያም እንደነገሩኝ በየቦታው እየሠርኩ ያገኘሁትን ሰው ስለመርነቱ ጠየኩ ። ያገኘሁት መልስ ግን 'ጆንስቦሮ ላይ ውጊያ አለ' ነው ። እኔም. . . "

"ዶክተር ሚድ ባቡር ጣቢያ ነው ፤ ነው የምትይው?"

"እዎ እመቤቴ. . . እሱ. . . "

"አሁን ስሚ የምልሽን ። ዶክተር ሚድን ልፈልግ መሄዴ ነው ። አንቺ ከወደዘሮ ሜላኒ ጭን ሆነሽ የምትልሽን ፈጽሚላት ። ታዲያ ስለመርነቱ ትንፍሽ ትይና ጓላ ነግሬሻለሁ! ሥጋሽን ነው እምሽጠው! ሌሎቹ ዶክተሮችም እንደማይመጡ ትነግሪያትና ዋ! ትሰሚ የለም?"

"እሺ እመቤቴ"

"በይ አይንሽን ጠርገሽ ንጹህ ውሃ ያዢና ወደ ላይ ውጪ ። ላቧን አደራርቂላት ። ዶክተር ሚድን ልጠራ መሄዴን ንገሪያት ።"

"መውለጃቸው ደርሷል እንዴ ፤ እትዬ አስካርሌት?"

"እኔ አላውቅም ። ደርሷል ብዬ ሰግቻለሁ ፤ በእርግጥ ግን አላውቅም ። አንቺ ማወቅ አለብሽ ። በይ ቶሎ ወደ ላይ ሂጂ ።"

አስካርሌት ባሰላባውን የፀጉር ሽሩንዋን አንስታ በችኩላ እራሷ ላይ ደነቀረችና መስታወቱ ጋ ቆማ ከመቅጽበት ፀጉርዋን ገፋ ገፋ አርጋ አስተካከለች ። የራስዋን ምስል እንኳ መስተዋት ውስጥ አላየችም ። ትንሽ በትንሽ ሆድዋን ሲቆርጣት የነበረው ፍርሃት አሁን በመላ ሰውነቷ ተሰራጭቶ ሌሎቹ የሰውነቱዋ ክፍሎች በላብ ቢጠመቁም ፤እጅዋ ብቻውን በረዶ መሆኑን ጉን ጨዋን ስትነካ ቅዝአዜው አረጋገጠላት ። ከቤቷ ፈጥና ወጥታ ጠራራው ፀሐይ ውስጥ ገባች ። በጣም በጣም ያቃዮላል ። እንዲያውም ዓይን ያጭበረብራል ። የጢች ትሪን ጭዳና ስትያያዘው የፀሐዩ ቃጠሎ ጆሮማንዲን አነደደው ። ከመንገዱ ግርጌ የብዙ ሰዎችን ድምፅ ከፍና ዝቅ ሲል ትሰማለች ። የሌይ ደን ቤተሰብ ቤት አካባቢ ስትደርስ ልብሱዋ በጣም ጥብቅ አድርጎዋት ስለነበር ያማት ጀመር ፤ ግን ርምጃዋን አልቀነሰችም ። የድምፁ ጉርምርምታ እየጨመረ ሄደ ። ከሌይደን ቤት ወደ ፋይቭ ፖይንት የሚወ

@OLDBOOKSPDF

ስደው መንገድ ፣ ተብያቸው ፈርሶ ሰመንባት እንደሚጣጣሩ ምስክች ፣ በሚራወጡ ሰዎች ተሞልቶዋል ። ሰው ወደላይ ወደታች ይላል ፣ ይንቀሳቀሳል ። እግሮዎቹ ከወዲህ ወዲያ ከላይ እታች ፊታቸውን እንደከፋው ይሩዋሩዋጣሉ ። በየደጃፉ በየበረንዳው ሀዛናት ያለጠባቂ ቁጭ ብለው እሪ ይላሉ ፣ ያለቅሳሉ ። መንገዱ ቦርሳና የቤት ዕቃ በያዙ ሰዎች በተሞሉ ጋሪዎች ፣ ቁስለኞች በታጨቁባቸው የጦር ተሽከርካሪዎችና አምቡላንሶች ተጥለቅልቋል ። በፈረስ በፈረስ ያሉ ሰዎችም ከየእግር መንገዶቹ ወደ ዋናው አውራ ጐዳና እየገቡ ፣ በፒችትሪ ጐዳና አድርገው ቁልቁል ወደሁድ የጦር ሰፈር ይተምማሉ ።

ከቦኔል ቤት ፊት ለፊት ሽማግሌው አሞስ የጋሪውን ፈረስ ይዞ ቆሟል ። አይኖቹን እያንከራተተ ሰላምታ አቀረበላት ።

"ወይዘሮ አስካርሴት ፣ እስካሁን አልሄድሽም፣ እኛ መሄዳችን ነው ። አሮጊቷ እናታችንም ዕቃዋን እያሳሰረች ነው ።"

"መሄዳችን? ወዴት ነው የምትሄዱት?"

"እሱን እማዜር ያውቃል ። እንዱጋ ነዋ ። ያንኪዎቹ እየመጡ እኮ ነው!"

ደሀና ዋልም ሰትሰው ተንሰታ በረረች ። ያንኪዎች እየመጡ ነው! ዌስሊ ቻፕል አጠገብ ስትደርስ እንደመዶሻ የሚመታውን ልቧን ለማርጋትና ትንፋሽዋን ለመዋጥ ቆም አለች ። መቼም አረፍ ካላለች ልቧ ፈስሳ መውደቁ ነው ። የመብራት ምሰሶ ይዛ እንደቆመች ፣ አንድ መኩንን በፈረስ ሽቅብ ፒችትሪ ጐዳናን ይዞ ሲገሰግስ አይታ ፣ ሮጣ እጅዋን አውለበለበችና ትጣራ ጀመር ።

"አቁም! አቁም! አቁም!"

ወዲያው ልጓሙን በፍጥነት ከመሳቡ የተነሳ ፈረሱ ሁለት የፊት እግሩን አየር ላይ አውጥቶ በኋላ እግሩ ቆመ ። መዳከምና መቻኮል አፈቱ ላይ ቢነበቡም የተቀዳደደች ባርኔጣውን ብድግ አደረገላት ።

"እኔን ነው እመቤት?"

"አዎ ፣ ያንኪዎቹ እየመጡ ነው የሚባለው እውነት ነው?"

"እውነት ነው ብዬ አፈራለሁ"

"በእርግጥ ታውቃለህ? "

"አዎ እመቤቱ ። አውቃለሁ ። ከጆንስቦሮው ጦር ሜዳ ገሚሱ ጠራችን ወደጦር ሰፈር ከማማሽ ሰዓት በፊት ገብቷል ።"

@OLDBOOKSPDF

"እርግጠኛ ነህ ከጀንስቦሮ ነው?"

"እርግጠኛ ነኝ። ከእንግዲህ መዋሸት ምንም ዋጋ የለውም። ከጂኤራል ሐርዲ ነው መልዕክቱ የመጣው፡ — 'በሠርጉቱ ሙሉ በሙሉ ድል ስለተመታው በማፈግፈግ ላይ እገኛለሁ' ይላል።

"ወይኔ አምላኬ!" አለች።

የደከመው ሰውዬ የጠቆረ ፊት ቁልቁል ያለምንም እንቅሥቃሴ ያስተውላታል። ልጓሙን አስተካክሎ ያዘና ባርሚላውን አደረገ።

"ዉ—የኔ ጌታ እባክህ ላንዲት ደቂቃ ቆይ። ምን ብናደርግ ይበጀናል ታዲያ?"

"እመቤቴ ምንም ማሰት አልችልም። ሠራዊቱም አትላንታን ጥሎ መውጣቱ ነው።"

"እኛን ለያንኪዎቹ ጥሎን ሊሄድ?"

"ይኸው ነው ብዬ እሰጋለሁ።"

በወንጭፍ እንደተወነጨፈ ሁሉ በቋፍ የነበረው ፈረስ ሽምጥ ፈረጠጠ። እስካርሌት ተረከዝዋ በቀዩ አፈር እንደተለወሰ እሚዳው ማህል ብቻዋን ቀረች።

ያንኪዎቹ እየመጡ ነው። ሠራዊቱ አገር ለቆ እየወጣ ነው። ያንኪዎቹ እየመጡ ነው፡ ምን ብታደርግ ይሻል ይሆን? ማን አዘሏት ይጥፋ! ወይኔ ትሩጥ? የለም መሮጥ አትችልም። ሚላኒ ክምጥ አልጋዋ ላይ እያለች እንዴት ብላ? አፍ ለምንድነው ሴቶች የሚወልዱት? እን ዲያው ምን እዳ ነው? ሚላኒ ባትኖር እኮ ዋድና ፕሬሲን ይዛ ያንኪ ዎች ከማያገኙዋት ጫካ ውስጥ መደበቅ በቻለች ነበር። ሚላኒን ጫካ ይዛ መሄድ መቼም አይሞከርም። ያውም አሁን እንዴት አድርጋ። በትርቡ ወልዳ ቢሆን፡ ትላንትና እንኳን ወልዳ ቢሆን አንድ አንቡ ላንስ እንደምንም ፈልጋ ይዛት አንዴጋ ትደበቅ ነበር። አሁን ግን ዶክተር ሚድን ይዛ ወደ ቤት መሄድ ብቻ ነው እሚሻለው።

ቀሚሷን ሰብስባ ቁልቁል መንገዱን ይዛ መሮጥ ጀመረች። የእግርዋ ቅኝትም "ያንኪዎቹ እየመጡ ነው! ያንኪዎቹ እየመጡ ነው!" ይላል። ራይቭ ፖይንት ላይ ሕዝቡ ወዴህ ወዲያ ሲል ዓይን የለውም። የተሸከርካሪው ብዛት፡ የአንቡላንሱ፡ የበሬ ጋሪውና ቱስለኛ የጫኑ የፈረስ ጋሪዎች ትርምስምስ ለጉድ ነው። ከዚህ ሁሉ ድብል ቅልቅ የሚወጣው ልዩ እስማምጣምታ ምድር ያናውጣል።

@OLDBOOKSPDF

ከዚያ አንድ ንጉሥ ከሌላ ንጉሥ ጋር ጦርነት ገጠመ። በርከት ያሉ ሴቶች ከባሎቻቸው መንግሥ እትጣጫ እህል ውኃ ተሸክመው ይመጣሉ። ትንንሽ ልጆች ከሥር ከሥራቸው በዘምቢል ምግብና ቅጠላ ቅጠል ያቋጣሉ ይዘው ይንቀሳቀሳሉ። ወጣት ወጣቶቹ ድንኳንና በቅሎ በከረጢት ተሸክነው ነበር። አንድ ሽማግሌ ሰውዬ በከርቸር ኩንታል ጨው ይጭኖ ይጭተራተራል። ወንዱ ፡ ቤቱ ፡ አባን ሽማግሌው ፡ ጥፏራም ንጣፉም ፊቱን ሞንትት እንደሞጠፋ የቲጠቀለለ እቃ ፡ ቦርሳ ፡ ሰንዴቅ ሙሉ ምህብ ፡ ሰዓመታት አይታው የማታውቅው የምግብ ዓይነት ፡ በሽከምም በአንተልተልም ይዘ ይግተለተሳል። ያ ሁሉ ሰፍር ቁጥር የሌሰው ሕዝብ ማራኛ ቸኝ አሮተሸጋሸገ አንዲት ቀሚን መንገድ ለቀቁ። በቀ ጭሎ መንገድ ግዙታና ጉልሁጥ እመቤት ወይዘሮ ኤልሲንማ ፣ ባንድ እጃቸው የፈረስ ጋሪውን ለጓም ፣ ባንድ እጃቸው አለንጋ ይዘው ብቅ አሉ። ሰራሰቸው ለጠጉራቸው ማሠሪያ የለቸውም። ፈታቸው ንጭ ሆኑ ዋል። ረኽሙ ማራኛ ዐነራችሙ በጀርባቸው ላይ እንደ ጅረት ይፈስሳል። ፈረሱን መጭ ይሉታል። ከጋሪው ኋላ መቀመጫያ ላይ እየንጠረች ያቀመጠቸው ሞግዚቱም ሚሲ,ሲ. ፡ በዘይት የራስ ጥቅልል ንገር ዘንድ እጅዋ ፡ በሌላው እጅዋና በተልበሱችዋ ማህል ፡ ሣጥኖቹንና ጉንዋ የተከመሩትን እቃዎች ለመያዝ እየሞከረች ነው።

በማህል አንድ የእተር ከረጢት ፈነጣና እገር ምድሩን የእተር ፍሬ አሰበሰው። አስካርሌት ይሰሙኝ ብሳ ይጣ ተጣራች። ግን ድም ፅዋ ዘእነባቢው እስዛሙግዎታ ተዋጠና ጩኸትዋ መና ቀረ። ወይዘሮ ኤልሲንግም ሳይሰሟት አለቁ።

ለትንሽ ጊዜ ይሄ ሁሉ ምን እንደሆነ አልገባ አላት። ወዲያው ብቻ የወታደሩ የልብስ መጋዘን ወደታች መኖሩን ብታሰታውስ ፡ ሰራዊቱ ሁሉ በዶውን ትጥቅ ለምነኪዎቹ መጠለያ እንዲሆን በሩ ወለል ተደርጎ መከፈቱን ልብ አለች።

በሚትመከመክው ጅምላ መንገደኛ ማህል በፍጥነት እየተሽሎክ ለስችጥቅጥቅ ያለውን እየሳፉች ፡ ቀለል ወዳለው የሩይቭ ፖይንት ጉዳና ከፍል ስትደርስ ፡ በፍጥነት ወደ ባቡር ጣቢያው ተሽቀለቀለች። በአም ቡላንሱቹ ትርምስና በአባራው ጉም ውስጥ ዶክተሮችና የቃሬዛ አልጋ የተሸከሙ ሰዎች ፡ ጉንበስ ፡ ቀና ፡ ብድግ ፡ ቁጭ እያሉ ሲጥደፉ ይታዩዋታል። እግዚሃር ምሥጋና ይግባው አሁኑኑ ዶክተር ሚድን ታግኘዋለች። በአትሰንታ ሆቴል በኩል ተጠምዝዝ ባቡር ጣቢያውን ሙሉ በሙሉ አየችው። ከሳድ መኪና ዎችም አሉ። የየምታየው እንዳንድ ነገር አለደነጣጣትና ባለችበት ደርቃ ቀረች።

በዚያ ርህራሄ በሌለው የፀሐይ ሀሩር ፡ ትከሻ ለትከሻ ተጣብቀው ፡ እግር ከራስ ተሰካክተው ፡ ቢሙቆ የሚቆጠሩ ቁስለኞች ፡ በየመኪናው

@OLDBOOKSPDF

ገመጃ ሥር ፡ በየእግር መንገዱ ላይ ሁሉ ፡ የመኪናዎቹን ጥላ ተጠልለው ፤ ላይን በሚያታክት ተርታ ተዘርረዋል ። አንዳንዶቹ ከርር ድብን ብሰው እንደ እንጨት ደርቀዋል ። ብዙዎቹ ጠራራው ፀሐይ እያንቃቃቸው ያቃስታሉ ፤ ያጓራሉ ። በሁሉም ቦታ ዝንቦች በኪሀ ቁስለኞች ፊትና ገላ ላይ እያንገዳበቡ ፡ እያረሩ ጥዝዝዝ እያሉ ይሸመዋቸዋል ። ሁሉ ቦታ በደም ተበክሏል ። የንተቡ የሩሻ ጥምጥሞች ሞልተዋል ። ማስ ጓሮር ፡ መጮህ ፡ ሌሎችም የሰቃይ ልጅ ልጆች ሁሉ ይሰማሉ ። ቁስ ለኞቹ ፤ ቃሬዛ እንሺዎቹ ሲያንሱዋቸው ሰቆቃቸውን ይተነፍሳሉ ። የሳቡት ትንፋግ ፡ የደሙ ክርፋት ፡ ያልታጠበ ሰውነት ቅርናት ፡ ሽንቱና ሰገራው በፀሐይ መቀት ሲቃጋ ይዞ የሚነሳው ጠረን ፤ አፍንጫዋን ሲሰነጥጣት ሊያስመልሳት ምንም አልቀራት ። የአንቡላንሱ ሠራተኞች ወዲህ ወዲያ ሲሩጥሩዋጡ ፤ ከተዘረሩት ሰዎች ብዛትና ጥቅጥቅ ማለት የተነሳ ፤ ሰው በሰው ላይ እየረገጡ ፡ የደነዙ ፡ የበደኑ ሰዎችን እየተራመዱ ነው የሚሄዱት ። የባሰ የባሰበትን የሳኒላ ሲያንሱ ሌሎቹ ምድር ነክሰው የቀሩት ከርቸት ከፎትት እያሉ ተራቸውን ይጠብቃሉ ።

ከሱኛ ሽምቅቅ አለች ። እጅዋን አፍዋ ላይ አደረገች ። ትውከት ትውከት አሳት ። ወዶሐት ሙሄድ ተሳናት ። አንዴ ከዚህ ቀደም ሆስፒታሉ ውስጥ ቁስለኞች እይታለች ። ጥቂቶች ደጀፍ ሜዳው ላይም ቁስ ለኞች እይታለች ። እንደዚህ የሚያሰቅቅ ግን በጭራሽ አላየችም ። እንዲህ የሚገማ የሚገለማ ጠረን ፡ ደም በደም የተበከሉ ሰዎች ከፀሐይ ግለት ጋር የሚያመጡት ሽታ ፤ በጭራሽ አላየችም ። ይሄ ልዩ የሕመም ሰቆቃ ፡ የጠረን እጅልና የድምፅ ጣዕር የተከማቸበት ፤ ቶሎ በል! ቶሎ በል! ብቻ የሚሰማበት ቦታ ነው ። ያንኪዎች እየመጡ ነው! ብቻ ነው የሚሰማው ።

በትከሻዋ እየታከከች ፤ ከቆሙት ማሀል ዶክተር ሚድን ለመፈለግ ዓይኑዋን እያጨናቆረች ፤ መሀል ለመሀል አቋርጣ ሄደች ። በጭራሽ ልታየው አልቻለችም ። ቀና ብላ ማየት አልሆነላትም ፤ ምክንያቱም በጥንቃቄ ካለተራመደች እንዱ ምስኪን ወታደር ላይ ትወጣለች ። ቀሚሷን ወደላይ ሰብሰብ አድርጋ አንድ ቦታ ወደተከማቹና ሲቃሬዛ እንሺዎቹ ትዕዛዝ ወደሚለጡት ሰዎች አመራች ።

በተራመደች ቁጥር የሚያተኩሱ እጆች የቀሚስዋን ጫፍ ይዘው እየጐተቱ በጣር ድምፅ "እመቤት ውሃ! እባክሽ እመቤት ውሃ! ስለ እግዚአብሔር ውሃ !" ይሳሉ ።

ቀሚሷን ከጨመደዷት እጆች ለታስለቅቅ ላቧ እንደጐርፍ እየ ወረደ ይንጠፈጠፋል ። አቤት ከነዚህ ሰዎች ባንዱ ላይ እንኳ ብትወ

@OLDBOOKSPDF

ጣበት ጨኸትዋን ነው የምትሰጠው ። ልቧ ትፈስሳለች ። በሞቱ ሰዎች ላይ ትራመዳለች ። የደምብ ልብሶቻቸው ላይ ተለውሶ የደረቀ ደም ጨርቆቹን ሳይቀር ከቁስል ጋር አጣብቆባቸው ፣ አይኖቻቸው አንድ ቦታ ተሰክተው የቀሩ ሰዎችን ትራመዳለች ። እጆቻቸው ሆዳቸው ላይ ተጣጥፈው ደርቀዋል ። ጢማቸው በደም ተነባብሮ የደረቀና ከአፋቸው የሆነ ድምፅ—በማምት "ውሃ! ውሃ!" ሊሆን የሚችል—ድምፅ ይወጣል ። ዶክተር ሚድን ቶሎ ካላገኘ ችው በጭንቀት እሪ ልትል ነው ። በመ ኪናው ጥላ ሥር ካሉት ሰዎች ባገኘው ብላ "ዶክተር ሚድ! ዶክተር ሚድ እዚህ ይኖሩ ይሆን?" ብላ ጮሃ ጠየቀች ።

ከዚያ ክምር አንድ ሰው ነጠል ብሎ ወጥቶ ወደሷ ያይ ጀመር ። አዎ ዶክተሩ ነው ። ኮት አልለበሰም ። እጅጌውን ትከሻው ድረስ ጠቅልሏል ። ሸሚዙና ቦላሌው በደም ተበክሎ የቂራ አራጅ አስመሰሎ ታል ። ሲላው ቀርቶ የግራጫው ያገጭ ጢሙ ጫፍ ጫፍ ቀይ ተነክ ሯል ። ፊቱ ጥምብዝ ብሎ የሰከረ ፡ ድክምክም ብሎ በንዴት የከሰለና በሐዘን የነደደ ሰው ፊት ሁኑዋል ። ግራጫና አቧራ ባቧራ ሆኖ በጀሮ ማንዱ የወረደው ሳብ ጉንጭና ጉንጩ ላይ ደርቆ ቦይ ሰርቷል ። ብቻ ድምፁ ረጋ ያለና ቁርጠኛ ሆኖ ነው እሷን ሲጠራት ።

"እግዜር ምሥጋና ይግባው ። እንኳን መጣሽ ። የማንንም የእርዳታ እጆች ሁሉ እጠቅምባቸዋለሁ ።"

ለትንሽ ጊዜ በመደናገጥ ትኩር ብላ እያየችው ቀሚሷን ወደታች ለቀቀችው ። እግሩዋ ሥር ከተዘረረ ካንድ ቁስለኛ አዳፋ ፊት ላይ ወደቀ ። ሰውየው በደካማ አቅሙ ከቀሚሷ ጫፍ ለማምለጥ ዘወር አለ ። ዶክተሩ ምን ማለቱ ነው? አንቡላንሶቹ ሥር የሚቦነው አቧራ ባፏ ገብቶ ሲያፍናት ሳል ለቀቀባት ። በዛ ያለ የቁስለኛው ጠረን እንደቆሸሸ ውሃ ባፍንጫዋ ገባ ።

"የኔ ልጅ ቶሎ በይ ባክሽ ፣ ፈጠን በይና ነይ!"

በሰዎቹ ማህል በተቻላት አቋርጣ ቀሚሷን ሰብስባ እየተጣደፈች ሄደች ። በእጅዋ ከንዱን ያዘችው ። እጁ ከድካም ብዛት ይንቀጠቀጣል ። ፊቱ ላይ ግን ምንም ድካም አይነበብበትም ።

"ውይ ዶክተር!" አለችና ጮኸች ። "መምጣት አለብህ ፣ ሚላኒ ምጥ ላይ ነች ።"

የተናገረችውን አዕምሮው አልቀበል እንዳለው ሁሉ ትኩር ብሎ አያት ። እግሩዋ ስር ከንዱን ተንተርሶ የተጋደመ አንድ ሰው በንደኝ ነት መንፈስ "አነሱ ይሰሩታል" አለ ፣ ፈገግ ብሎ ።

@OLDBOOKSPDF

እሷ ጐንበስም ብላ ሳታይ የዶክተሩን እጅ መነቅነቋን ቀጠለች።

"ሚሳኒ እኮ ናት። ል.ል.ልጅ ልጅ ልትወልድ እኮ ነው። ዶክተር መምጣት አለብህ እሷ.." መቼም የመለሳለሻ ጊዜ አይደለም። ግን በሙቶ የሚቆጠሩ ያሰፈሰፉ ጀሮዎች ማህል ቃሎቿን ለማውጣት በጣም ቸገራት።

"ምጡ እየጠናባት ነው አባክህ ዶክተር!"

"ልጅ፣ ኧረ በፈጣሪ!" አለና አምባረቀ ዶክተሩ ፊቱ በጥላቻና በንዴት ልውጥውጥ አለ። ንዴቱ በሷ ወይም በሌላ ሰው አልነበረም። የለም። እንዲህ ያሉት ግራ የሚያጋቡ ተቃራኒ ነገሮች ባንድ ጊዜ የሚፈልቁባትን ይህቺን አለም ነው የጠላው።

"አብደሻል ልበል? እነዚህን ሰዎች ትቼ መሄድ አልችልም። በሙቶ የሚቆጠሩ ሰዎች እየሞቱ ነው። ለአንድ ለሚወለድ ህፃን ብዬ እነዚህን ሁሉ ለስቃይ ትቼያቸው አልሄድም። አንድ ሴት ፈልጊና ትርዳሽ። ሚስቴንም ቢሆን ይዘሻት ሂጂ።"

ወይዘሮ ሚድ ልትሄድ እንደማትችል ልታስረዳው አፍዋን ከከ ፈተች ወዲያ መልሳ ዘጋችው። የገዛ ልጇ መቁሰሉንም አልሰማም እኮ። ቢሰማ ይህን ቦታ ጥሎ ይሄድ ይሆን ብላ አሰበ ገረማት። ብቻ ወዲያው ፊል—የገዛ ልጇ፣ ሊሞት ነው ቢሉት እንኳ ብዙዎቹን ጥሎ ወደ አንዱ "ዘጠና ዘጠኙን በኮሾ ጥሎ አንዱን በማ ፍለጋ" በሚራሽ ንቅንቅ እንደማይል አንድ ነገር ከውስጡዋ ነገራት።

"የለም ዶክተር መምጣት አለብህ። እንደምታውቀው ስትወልድ ችግር ይገጥማታል ብለሃል እና..."

ወይ ጉድ፣ ይቺ ገሃነም እሳት ማህል ላንቃዋ እስኪሰነጠቅ እየ ጮኸች አስፈሪና አስከፊ ቃላትን የምትናገር ፅውኔት አስካርሌት ናት፣ የማይታመን ነገር ነው።

"ካልመጣህ መሞትዋ ነው" አለች።

እጅዋን በታይል መንጭቆ አላቀቃት። የምትናገረውን እንደማይ ሰማት ሁሉ፣ በሚራሽ እንደማይገባው ሁሉ መናገሩን ቀጠለ።

"መሞትን መሞትማ እነዚህ ሁሉ ይሞታሉ። እኔ ሁሉ ሰዎች ይሞታሉ። ፋሻ የለም። ዉርቅ የለም፣ ኪኒን የለም። ማደንዘዣ የለም። ምነው እግዜር ትንሽ ማደንዘዣ፣ ለባለባቸው የሚሆን እንኳ ትንሽ ማደንዘዣ ቢሰጠን ኖሮ፣ ትንሽ እንኳ ማስታገሻ! ኡ እነዚህ ያንኪዎች ይውደሙ! ከይሲዎች! እግዜር ይንቀላቸው!"

@OLDBOOKSPDF

"ደውደመ! ዶክተር" አንድ ድምፅ ፡ መሬት የተጋደመ ቁስለኛ ድምፅ ፤ በጨሙ ማህል ጥርሱን ብልጭ እያረገ ተናገረ ።

አሰካርሴት ትንቅጠቅጥ ጀመረ ። አይኖቹዋ ፍርሃት ባመነጫ ቸው ፍል ዕምባዎቹዋ ተለበለቡ ። ዶክተሩ አብሮዋት አይሂደም ማለት ነው ። ሚላኒ መሞቱዋ ነው ። ለነገሩ መሞቱዋንም አንድ ጊዜ ተመኝታው ነበር ። ዶክተሩ በቃ አይመጣም ።

"ኧረ በእግዚአብሔር ዶክተር! አባክህ ዶክተር እባክህ !"

ዶክተር ሚድ በእጁ ከንፈሩን ትም ትም እያደረገ ፊቱ ቅዝቀዝ ሲል ግንጭሉ ኩምትር ጥንከር አለ ።

"የኔ ልጅ እሞክራለሁ ። ታል አልገባልሽም ። ግን ለመሞጣት እሞክራለሁ ። እንዚህን ሰዎች እንደምንም ቢታ ቦታ አስይዝ ለመሞ ጣት እጣጣራለሁ ። ያንኪምቹ እየመጡ ነው ። ወታደሮቻችንም ከተማ ውን እየለቀቁ እየወጡ ነው ። የቆሰሉትን ምን እንደሚያደርጓቸው አለወቅም ። ምንም ባቡር የለም ። የማከው መስመርም ተይዟል ። ለማንኛውም እሞክራለሁ ። አሁን ሩጪና ሂጂ ። እሩጎ አታስቸግሪኝ ። ልጅ ማዋለድ ይሄን ያህል አስቸጋሪ አይደለም ። የእትብቱን ገመድ መቋጠር ብቻ ነው . . . "

ወዲያው ከጮኮ እጅጌ ነካ መዳረገው ሰው ዞሮ ጣቱን አንዴ ወደዚህኛው አንዴ ወደዘያኛው ቁስለኛ እየጠቆሰ ትዕዛዙን ያዥጎደጉ ደው ጀመር ። ከአሰካርሴት እሣር ሥር ያለው ቁስለኛ አሰካርሴትን ከማሳዘን ዓይን ያያታል ። ዶክተሩ ስለዘነጋት ሁሬ ሄደች ።

ከቁስለኞቹ ማህል አቋርጣ ተመልሳ ወደ ፒኾትሪ ጉዳና አመ ራች ።

ዶክተሩ አይመጣም ። ስለዚህ አራስዋ መወጣት ሊኖርባት ነው ። እግዚሃር ምሥጋና ይግባው ፕሪሲ ስለሞዋለድ አሳምራ ታውቃለች ። ወሐዩ ሚንቅላቷን አሳመጣች ። ላብ በላብ ከመሆንዋ የተነሳ ልብሷ ይረትዋ ላይ ይጣበቅ ጀመር ። አዕምሮዋ ጭዝዝ ድንዝዝ ፡ እግሩዋም ላም ዛል ብሎ ፡ እንደህልም እሩጫ ፡ ልንቀሳቀስ ብትል እስርስር አለች ። ወደቢት የመመለሻዮን ረጅም መንገድ ስታስበው የሚይዘለቅ መሰ ላት ።

ከዛም "ያንኪምች እየመጡ ነው!" የሚለውን ቅኖት አዕምሮዋ መምታቱን እንደገና ጀመረ ። ልቧም ትርታውን ሲያያዘው እጅ እግ ሩዋ ደግሞ ነበሰ ዘራ ። ራይቭ ፖይንት ላይ ወደተከማቸው ጥቅጥቅ ያለ ወፈ ሰማይ ህዝብ ገስገስች ። ግራና ቀኝ ያሉት የእግር መንገ

@OLDBOOKSPDF

ድኾ ካፍ እስከገደፋቸው ሞልተው አሳላውሰ ቢሏት ማህል ጐዳና ገባች ። የቲክሱ ፣ የደከሙና አፏራ የንፋባቸው መታደሮች በረሽም ሰልፍ ጎብተው ያልፉሉ ። እንዲህ ያሉ የተጐሳቆሉ ጢማሞችና የቆሸሹ ጠመንጃዎቻቸውን በየትከሻዎቻቸው የተሸከሙ ሺ በሺ የሚቆጠሩ ንና የሚመጡ ይመስላል ። አውቶሞቢሎች ከበቅሎዎችና ከፈረሶች ጋር ወረቀት የሚያስገባ በማይመስል ቀዳዳ እየታከኩ ያልፉሉ ። ባለሽሬ የጦር ተሽከርካሪዎች የተበጫጨቁ ሽራቸውን እንደነገሩ ሰብሰው ይንጭጭጫሉ ። ፈረሰኞች አፏራውን ወደሰማይ እያንፏለሱ ማለቂያ የሌለው ረድፍ ይዘው ይጓዛሉ ። እንዲህ ብዛት ያላቸው መታደሮች ከዚህ ቀደም አይታ አታውቅም ። ማረማረማ ! ማፈግፈግ ! ማፈግፈግ ሠራዊቱ እየወጣ ነው ።

ይሄ የጥድፊያ ሠልፍ ወደ ጸር ከተፋፈነው ህዝብ ጋር እስክት ቀላቀል ጎፋት ። በርከሽ የሚሸጥ ሙሰኪ ሽታ ሸተታት ። በዲከተር ጐዳና አጠገብ የምታያቸው ደህና ደህና የለበሱ ፡ የተጊያጊያጠና የተኳኳሉ ሴቶች ያመት በእል ፈሽታ ላይ ያሉ ይመስላሉ ። ብዙዎቹ ሰክረዋል ፤ ያቀፏቸው መታደሮችም ጥምብዝ ብለዋል ። በጨረፍታ አየልታ ስታይ ቀያይ ጥቅልል ፀጉር ካሳቸው ሰዎች ማህል ያቺ አስቀያሚ ፍጥረት ቤል ዋትሊንግን እያሰኳኳች አንድ እጅ የሌለው መታደር ላይ ስትለጠፍ አየቻት ። እሱም ይንገዳገዳል ። ሰክረዋል ። ያን የተከማቸ ህዝብ ገፍታ ከፋይቭ ፖይንት ወዲያ ወዳለው ሀንጻ ስትሄድ ፡ የሰዉ ብዛት ሳሳ እያለ ስለመጣ ቅሚሷን ሰብሰባ ደሞ ሩጫዋን ተያያዘችው ። ዌስሊ ቻፕል ስትደርስ ትንፍሽ አጠራት ። ደነማት ። ሆድዋን አመማት ። የቅሚስዋ ወገብ ማሰሪያ ጐንና ጐንዋን እየሰረሰረ አሳመማት ። ቤተ ክርስቲያኑ ደረጀ ላይ አረፍ ብላ ፊቱዋን እጆቹዋ ውስጥ ቀብራ እፎይአለች ። ምነው እንድ አስትንፋስ ማንን ገደለ እንዴ እንኳ ወደ ሆድዋ ሰባ ትተነፍሰው አየር ብታጣኝ ምናለ ! ልቧ እንዲህ እንደ ከበሮመደለቁን ቀንሶ እፎይታን ቢሰጣት እንዴት ሰላም በወረደላት ። እንዲህ ያለው የእብድ ዓለም ላይ አንድ መከታዉ የምትሰው ፡ ምርኩዝ ይሆናት ሰው ብታጣኝ ምን ነበረበት ።

ምነው ለእስካሁኑ እኮ ብቻዋን ምንም ነገር ሠርታ አታውቅም ነበር ። ሁል ጊዜ አንድ ሰው ከጐንዋ ሆኖ ይደግፋት ፡ ጋሻ ይሆናት ፡ አለሁልሽ ይላት ነበር ። አሁን እንዲህ መሆኑዋ የሚገርም ዱብ ዕዳ ነገር ነው ። አንድ ጓደኛ ፡ አንድ ጐረቤት እንኳ የሚረዳት ትጣ ! እንዴ ሁልጊዜ ፤ ጓደኛዋ ፡ ጐረቤትዋ ወይ ታታሪ ባሪያዎቹዋ ይደርሱላት ነበር እኮ ! አሁን በዚህ በሞንቋ ሰዓት ግን አንድ እንኳን ጠፋ ። እንዲህ ባዶዋን ፡ ብቻዋን ፡ በፍርሃት ተውጣ ከቤቷ ስንትና ስንት እርቃ መገኘቱዋ የጉድ ነው መቼም !

@OLDBOOKSPDF

ቤቷ! ወየው ቤት ሠፊ ቢሆን፣ ያንዲዎች ኖሩ አልኖሩ ቤቷ ቢሆን! ኤለን ታምማ እንኳ ቢሆን ቤቷ ብትሆን! የኤለንን ጣፋጭ መልክና የማሚን ጠንካራ እጆች ከፉኛ ናፈቀቻቸው ።

ከተቀመጠችበት እየቀፈፋት ተነስታ መንገድ ጀመረች ። እቤቷ ፊት ለፊት ስትደርስ ዋድ እሚጸው ላይ ሲጫወት አየችው ። ገና ፊቷን ሲያያት ፊቱን ከፋ ከፋ አለውና ማልቀስ ጀመረ ። ጣቱን ይዞ ማልቀስ ጀመረ ።

"እመመኝ!" አለ "እጇን እመመኝ" አላት ።

"ዝም ትል እንደሁ ዝም በል አለዛ አጋጭሃለሁ ። ሂድ ጓሮ ሂድና ጭቃ እያቦካህ ተጫወት ። ከዚያ ንቅንቅ ትልና ዋ!"

"አላበኝ" አለና የቱቀጠቀጠ ጣቱን አፉ ውስጥ ከተተ ።

"እንጃልህ! ሂድ አሳሮኝ . . ."

ቁና ስትል ፕሪሲ ከፎቁ ላይ ሆና ቁልቁል አጐንብሳ ስታይ አየች ። ጭንቀትና ፍርሃት ፊቷ ላይ ተጽፏል ። ግን እመቤቷን ስታይ ባንድ አፍታ ከፊትዋ ጠፋ ። አስካርሌት እንድትወርድ እየነገረቻት ወደቤት ገባች ። አዳራሹ እንዴት ቅዝቅዝ ያለ ነው ! የራስ ሽፋንዋን አጠረጴዛው ላይ ወረወረችው ። ላቧን ከግንባሯ ላይ በአይበሉባዋ ጠራረገች ። የፎቁ ቤት ክር ሲከፈት የምጥ ጣርና ጩኸት ቀስ ብሎ በጆሮዋ ገባ ። ፕሪሲ ሶስቱን ደረጃ አንዴ እየዘለለች ወረደች ።

"ዶክትሩ መጣ?"

"አይ ! ሊመጣ አይችልም ።"

"ወይ አምላኬ! አትዬ አስካርሌት! እሜቴ ሚላኒ እኮ ምጡ በጣም ጠንቶባቸዋል !"

"ዶክተሩ ሊመጣ አይችልም ። ማንም አይመጣም ። አንቺ ነሽ የምታዋልጂት ፣ እኔም አረዳሻለሁ ።"

የፕሪሲ አፍ ተከፍቶ ምላሷ ያለታል ይነቃነቅ ጀመር ። ወደ አስካርሌት አግድም እያየች እግሯን እያነቃነቀች ቀጭን ሰውነቷን አወዛወዘች ።

"ይህን ያህል አትቅለይ!" ብላ ጮኸች አስካርሌት በሁኔታዋ ተበሳጭታ ! "ምን ሆነሻል ?" ፕሪሲ ወደ ደረጃው የኋሊት መውጣት ጀመረች ።

@OLDBOOKSPDF

"አረ በእግዚአብሔር አጥፍ አስኪሉት!" ፍርሃትና ሐፍረት ዓይኑዋ ላይ ወጡ ።

"ምን ሆንሽ ?"

"በእግዚአብሔር እትዮ አስካርሌት ! ይከተሩ መምጣት አለበት። እኔ—እኔ ስለማዋለድ እንድ ነገር አላውቅም ! እናቴ ይሀንን እንዳልማር በቅራሽ አታስጠጋኝም ነበር !" አለቻት ።

ከመናደድዋ በፊት የአስካርሌት ትንፋሽ በድንጋጤ ከሳንባዋ ተሟጠጠ ። ፕሪሲ ቁና ቁና እየተነፈሰች ልትበር ቃጣት ። ግን አስ ካርሌት አፈፍ አድርጋ ያዘቻት ።

"እንቺ ሙሽቃም ጠቂራ ! ምን ማለትሽ ነው ? ስለማዋለድ የማ ላውቀው ነገር የለም ስትይ ከርመሽ አሁን እንዲህ ትመልሻለሽ ? እንች ሞሽላታ—ቆይ እውነቱን ሳላስወጣሽ ብቀር ! እውነቱን ንገ ሪኝ!" ብላ ሽምብራ ፀጉሩዋን ጨምድዳ አስኪበቃት ነቀነቀቻት ።

"ዋሸቼአለሁ እትዬ አስካርሌት ! እንዴት እንዴት እንደዋሸሁ ዎት እኔ እንኛ ! አንድ ልጅ ብቻ ሲወለድ ነው ያየሁት ፤ እናቴም ስታ ዋልድ እንዳላይ ታስወጣኛለች ።"

አስካርሌት አሳት ሆነች ። ፕሪሲ ተሸማቅቃ ወደ ኋላ እያየች ለማ ለፉት ትሞክራለች ። ለትንሽ ጊዜ አፅምሮዋ እውነቱን አልቀበል አላት ። በኋላ ግን ልብ ስትገዛ 'ፕሪሲ ስለማዋለድ ከእሱዋ የበለጠ እንደማታውቅ ተገነዘበችና እንደቋያ አሳት ተንቀለቀለች ። በሕይወ ትዋ ባሪያ መትታ አታውቅም ፤ ዛሬ ግን የፕሪሲን ጥፋር ፊት ባለ በሌለ ጉልበቷ ተንጠራርታ በጥፊ ድርግም አደረገችባት ። ፕሪሲ ጉሮሮዋ እስኪሰነጠቅ ጩኸትዋን ለቀቀችው ። ከሀመሙ ይልቅ ፍርሀት ነው ያስጮሃት ። እናም ከአስካርሌት እጅ ለመውጣት ወደላይ ወደታች ብላ ተወራጨች ።

እንዲህ ጣራው እስኪበሳ ስትጮህ ፎቅ ላይ ይሰማ የነበረው ማቃሰት ፀጥ አለ ። ድክምክም ያለ ቀጭጭጣ ድምፅ "አስካርሌት ! አንቺ ነሽ ባክሽ ነይልኝ ! ባክሽ !"

አስካርሌት የፕሪሲን እጅች ወደመሬት ስትወረውራቸው ተሽሞ ድምጻ ያረጀው ላይ ውዝፍ አለች ። ለትንሽ ጊዜ አስካርሌት ቁና ብላ አየች ። ከፎቁ የሚወጣው ማቃሰት እንደገና ቀጠለ ። እሣው እንዶ ቆመች አንጎላዋ ላይ አንድ ገመድ ያነቃትና ገመዱ ላይ ከባድ ነገር ታስሮ በተራመደች ቁጥር አንጎላዋን የሚሸመቅቃት መሰላት ።

@OLDBOOKSPDF

አሷ ዋድን ስትወልዲ አሳንና ሚሚ ምን እንዳደረጉላት ለማስ ታመስ ብትሞክር ያኔ አንቺ የነበረው ያ የምጥ ሥንቅ ትዝታውን ሁሉ ድፍንፍን አድርጎባታል ። ትንሽ ትዝ ያሏትን ነገሮች ወዲያው ለፕሪሲ በትዕዛዝ መልክ አስተላለፈቻቸው ።

"እሳቱን አንድጂና ውሃ ወገች ። ያለ-ትን ፎጣዎችና የተጠቀለለ ጨርቅ እንዲሁም መቀስ አምጪልኝ ። አጣሁት ትይኝና ወዮልሽ ። ቶሎ ብለሽ ይዘሽ ኑይ ። በይ ፍጠኝ እኮ !"

@OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ 22

እንደባሬው ከሰዓት ረኾም በሙራሽ የሰም ። ሙቀቱስ ቢሆን ። በጠገቡ ገምቦች የመሞላቱም ነገር ሌላ አድርጎታል ። እስካርሌት በማራገብ ልትከሳከላቸው ብትሞክርም ሚላኒ ላይ ያንጣጥብባሉ ። እቤት የተተከለውን አትክልት ቅጠል እስክምታኝቅኝ ድረስ ለማራገብ ትጥራለች ። ሆኖም መከራዋ ሁሉ መና የቀረ ይመስላል ። ከሚላኒ ፊት ላይ ስታበርራቸው ወደ ራሱዋ እግርና ባት ላይ እየወጡ ዘላ እስክት ጮህ ድረስ አስመረሩዋትና "ውይ ምነው እማሬ ላይ!" አለች ።

ከፀሐይና ከሙቀቱ ስመከላከል ብላ እስካርሌት ተሸምቃቂውን የመስኩት ግርዶሽ ወደታች ሰባው ስለነበር የቤቱ ብርሃን ድብዝዝ ብሏል ። በየጠርዙና በጥቃቅን ቀዳዳ ዎቹ የሚወረወሩት የፀሐይ ጨረሮች ይፈነጣጠቃሉ ። ቤቱ ራሱን የቻለ የጋለ ምድጃ ሁኑዋል ። የእስካርሌትም በላብ የሸቀ ልብስ መድረቱ ቀርቶ ይብስ እየራሰ ገላዋ ላይ ተጣበቀ ። ፕሪሲም እጥፋ ቆማ በላብ ተጠምቃለች ። ጠረንዋ ወጠጤ ወጠጤ ይላል ። እስካርሌት በዛው ወጥታ ትቀርብኛለች ብላ ሰግታ ነው እንጂ ከቤት ባባረቻት እንዴት በወደደች ። ሚላኒ በላብ በራሰው አንለላዋ ላይ ተጋድማለች ። እስካርሌት ውሃ ያፈሰሰችበት ቦታ በጣም ረጥቧል ። ወደ ግራ ወደ ቀኝ አንዴ በደረትዋ አንዴ በጀርባዋ ትገላበጣለች ።

አንዳንዴ ቀና ብላ ልትቀመጥ ትሞክርና መልሳ ትንጋለላለች ። በመጀመሪያ በተቻላት ከንፈርዋን ነክሳ ላለማልቀስ ሞከረች ። የነክሰችው ከንፈርዋ ግንትር አለ ። እስካርሌትም ሀዋስዋ ገንትሮ "ሚሊ በፈጠረሽ የማትችይውን አትሞክሪ ። መጮህ ካስፈለገሽ ጩሂና ይውጣልሽ ። ከኛ በቀር የሚሰማሽ የለም ። አይዞሽ ።"

ሰዓቱ እየገፋ ሲሄድ ሚላኒ ምጡ ከአቅሙዋ በላይ ሆነባትና ወደዱ ችም ጠሉችም መጮህ ግድ ሆነባት ። እንዳንዴም እሪ ትል ጀመር ። እንደዚህ ስትጮህ እስካርሌት እጆቿን ጀሮዋ ላይ አድርጋ ላለመስማት በመጣር ሰውነቱዋን እያንቀጠቀጣት ቆመች ። ይህን ከምትሰማ ብት ሞት ፈቃድዋ ነው ። ለዚህ ሰቆቃ ምስክር ከመሆን መቼም ምንም ይመረጣል ። እንዲህ ሀዳን ተወለደ አልተወለደ እያለች ለረኾም ግዜ ከመጨነቅ ሌላ ምንም ይሻላታል ። ያንኪዎቹ ሩይቭ ፖይንት መድረሳቸውን እያወቁች ከመጠበቅ ምን አይመረጥምና ነው ። ስለወሊድ

@OLDBOOKSPDF

አሮጊቶች የሚያወሩትን ሁሉ ቢሆን እንጂ ት በጀት ። እንዲህ ያለ ውን ወሬ ማዳመጥ የምትወድ ቢሆን ኖሮ እንጄት በጠቀማትና የሚ ላኒ ወሲድ ምን ያህል እንደሚፈጅ ባወቀች ነበር ። ወይዘሮ ፒቲ ፓት ከዚህ ቀደም በምጥ ሁለት ቀን ስለተያዘች ሴት ያወሩትን ለማስ ታወስ አልቻለችም ። ያውም ሁለት ቀን አምጣ አምጣ ልጁንም ሳትወ ልድ ስለሞተች ሴት ነበር ። ግን እረሳችው ። ሜላኒ ሁለት ቀን ሙሉ ብታምጥ ምን ሊኮን ነው! ግን ሜላኒ እኮ ለስላሳ ናት ። ሁለት ቀን ሙሉ ማማጥ በጭራሽ አትችልም ። ልጁ እሁኑኑ ካልመጣ መሞቷ ነው መሼም ።

ለመሆኑ ሜላኒ ብትሞትባት አሽሌይን እስካርሌት በሕይወት ብታገኘው ምን ልትለው ነው? በኔ ጣለው ብላ ቃል ከገባች ወዲያ ምን ልትል ነው?

በመጀመሪያ ሜላኒ ምጡ ሲጠናባት የእስካርሌትን እጅ ያዝ ማድረግ ብቻ ነበር ። እሁን ግን በጣም ሲብስባት አጥንቷ እስኪሰበር ጥብቅ አድርጋ ያዘቻት ። በዚህ ሁኔታ ለአንድ ሰዓት ያህል እንደቆየ እስካርሌት እጁዋ አበጠ ፣ ማነቃነት ሁሉ አቃታት ። ሁለት ሮጣዎች ከአልጋው አጣር ጋር አሠረችና ለሜላኒ አስጨበጠቻት ። ሜላኒ እነዚህ ሮጣዎች የሕይወት ገመዱዋ እንደሆኑ ሁሉ ጭምቅ አርጋ ያዘቻቸው። ገተተቻቸው ። እላያቸው ላይ አነባችባቸው ። ይሄን ከሰዓት በሙሉ በወጣመድ ተይዞ እንደሚሞት አውሬ አቃሰተች ። ወዲያው ሮጣዎቹን ለቀቀችና እጆቿን በድኩም አቅሟ እየጠራረገች በሀመም ብዛት ከፎታቸው ወጥተው ቅትት ቅትት የሚሉ አይኖችዋን እስካርሌት ላይ ጣለች ።

"አውሪልኝ ። እባክሽ አንድ ነገር አውሪልኝ ።" ብላ ተነፈሰች ። እስካርሌት የሆነ ነገር ታወራላትና ደሞ ሮጣዋን ይዛ ማቃሰቱዋን ትቀጥላለች ።

ደብዛዛው ክፍል በሙቀትና በሀመም እንዲሁም በዝምቦች እንደ ተሞላ ቀኑ ከመጣተቱ የተነሳ እስካርሌት ጠዋቱን ማስታወስም አል ቻለች ። በዚህ በሳቦትና በተን በታፈነ ጨለማ ከፍል ውስጥ ሕይወ ቷን ሙሉ የተቀመጠች መስላት ። ሜላኒ ስትጮህ አብራት ልትጮህ ይቃጣታል ። በመከራ ከንፈርዋን እየነከሰች ነው ጩኸትዋን ገትታ ጭንቀትዋን የምታሳልፈው ።

እንዴ ዋድ በጣቱ ጫፍ እየረገጠ መጣና ከክፍሉ ውጪ ቆሞ አለቀሰ ።

"ዋድን እልቦታል!" ሲል እስካርሌት ወዶሱ ልትሄድ ከተነሳች

@OLDBOOKSPDF

በኋላ "ጥሰሺኝ አትሂጂ ። አባክሽ አጠገቤ ሁኚ ። እዚህ ስትሞኚ ልቋ ቋመው እችላለሁ!" ስትላት ቀረች ።

ስለዚህ እስካርሌት ፕሪሲን ለዋድ ቁርሱን እንድትሰራለት ላከ ቻት ። ሰራዩ ግን ከዚህ ከሰዓት በኋላ ወዲያ በጭራሽ እህል የሚሉት የምትቀምስ አልመሰላትም ።

የግርማዳው ሰዓት ቆሚል ። ጊዜውን ለማወቅ አልቻለችም ። የቤቱ ሙቀት እየበረደ በመሄዱ ብቻ የመስኮቱን ተሸምቃቂ ግርዶሽ ወደ አንድ ወገን ሰባ ብታይ ወደ ምሽቱ ነው ። ዕሕይም ከአድማሱዋ ግርጌ ቀይ ስጋሽ ለብሳለች ። እስካርሌትማ ይሄ ሞቃት ከሰዓት እስከዘለዓለም የሚቆይ ነበር የመሰላት ።

በከተማው ምን ይሠራ እንደሆን አታውቅም ። ሠራዊቱ ሁሉ ለቅቆ ወጥቶ ይሆን? ያንኪዎቹስ መጥተዋል እንዴ? የኮንፌዴራሲው ወታደሮች ያለወጊያ ሰቀው ሊወጡ ነው እንዴ?

ወዲያው የኮንፌዴሬሲው ወታደሮች ማንስ ፡ የቬርማን ወታደሮች ብዛትና በልተው የጠገቡ ድልብ ድልብ መሆናቸው ትዝ አላትና ሆድዋን ቆረጣት ። ቬርማን! የዴያብሎስ ስም እንኳ የሱን ያህል አያስ ፈራትም ። አሁን ግን ይህን ሁሉ ለማሰብ ጊዜ የለም ። ሚላኒ ውሃ ትላለች ፤ ቀዝቃዛ ፎጣ ግንባሬ ላይ አድርጊልኝ ትላለች ። ገምቦቹን ከፊትዋ ላይ እሽ እንድትልላትና እንድታራግብላት ትፈልጋለች ።

ድንግዝግዝ ብሎ ዓይን ሲይዝና ፕሪሲ ፋኖሱን ስታበራ ሚላኒ አንደኛዋን ደከመች ። በህልም ሰመመን ውስጥ ያለች ይመስል እሽ ሉይ! አሽሌይ ትላለች ፤ ትጣራለች ። እስካርሌት ጥሪውን ከመሰልቸ ትዋ ብዛት በትራስ አፍና ድምፁን ብታስቀረው ፈቃድዋ ነበር ። ምናልባት ዶክተሩ ይመጣ ይሆናል ። ምነው ቶሎ በመጣ! ተስፋዋ እንደገና ለመለመና ፕሪስን ወደ ሚድ ቤተሰብ ሄዳ እዛ መኖሩን እንድታይ ወይዘሮ ሚድም ካለች እሷን እንድትጠራት አዘዘቻት ።

"ጌሱ ከሌለም ወይዘሮ ሚድንም ሆነ ሠራተኞዋን ምን ማድረግ እንዳለብን ጠይቂያቸው ። እንዲመጡም ለምኚዋቸው ።"

ፕሪሲ በጥሞነት ወጣች ። እስካርሌት ስትሮጥ እያየቻት ከዚህ ቀደም እንዲህ መሮጥ የምትችል አይመስላት ስለነበር ገረማት ። ከረኻርም ጊዜ በሁዋላ ብቻዋን ተመለሰች ።

"ዶክተሩ ወደቤት አልተመለሱም ። ከወታደሮቹ ጋር ሳይሄዱ አልቀሩም ። እትዬ እስካርሌት ሚስተር ፊል ሞተ"

"ሞተ!"

@OLDBOOKSPDF

"እም እትዬ" አለት ፕሪሲ ነገሩን ለማከበድ እየብራራች። "ጋሪ ነጂው ታልቦት ነው የነገረኝ። የተገደለው . . . "

"በታ እሱን ተይው።"

"ወይዘሮ ሚድን አላየሁዋቸውም። ገረድየዋ ስትነግረኝ እሬሳውን እያጠቡ ለቀብር ሊከፍኑት ሄደዋል። ያንኪዎቹ እየመጡ ነው። ደርሰዋል አሉ። ገረድየዋ እንዳለች ምጡ በጣም ከጠናባት ከራስ ጌዋ ካራ ወይም ስለት ብጤ አትሩላት፤ በሽታውን እሁለት ላይ ይከ ፍልላታል፤ ብላለች።"

ፕሪሲ ይሄንን ጥሩ ወሬ ብላ በማምጣቱዋ አስካርሌት በጥፊ ልትላት ነበር። ብቻ ሚላኒ ዓይኑዋን በጣም ከፍታ በሥጋት "የኔእናት ያንኪዎቹ እየመጡ ነው እንዴ?" ስትል . . . ሐሳቡን ተወችው።

"አይ" አለች አስካርሌት "ፕሪሲ ስትዋሽ ነው!"

"እም እመቤቴ ውሸቴን ነው!" አለች ፕሪሲ።

"እየመጡ ነው ማለት ነው!" አለች ሚላኒ አልታለል ብላ፤ ፊቷን ትራስዋ ውስጥ ቀብራ። ድምፅዋ እየተሰባበረ ወጣ።

"ወይኔ ልጄን። ወይኔ ልጄን። "ከዚያም ከረዥም እረፍት በሁዋላ

"ውይ . . . አስካርሌት እዚህ መቆየት የለብሽም። ዋድን ይዘሽ መሄድ አለብሽ።" አለች።

አስካርሌት የሰማችው በልብዋ ያለውን ነው። ግን ከሌላ አፍ ስትሰማው የውስጥ ፍርሃትዋ እፊትዋ ላይ ተጽፎ የተጋለጠባት መስላትና ሐፍረትና ፍርሃት ዋጡዋት።

"ተይ እንጂ እንዲህ አትሁኚ። እኔ አልፈራም። እንደማልተውሽ ደሞ ታውቂያለሽ።"

ብትተይኝ ምንም አይደል። መሞቴ ነው።" "እንደገና ማቃ ሰቱዋን ቀጠለች።

* * *

አስካርሌት ቀስ እያለች ግርግዳውን በዳበሳ እየታከከች ጨለማውን አቋርጣ እንዳትወድቅ እየተጠነቀቀች ትወርዳለች። እግሮችዋ ከበዱዋት። ከድካምና ከጭንቀት ብዛት ይንቀጠቀጣሉ። ሰውነትዋን አልቧት ስለነበር ብርድ ሲነካት በጣም ቀዘቀዛት። በቀስታ እበረን

@OLDBOOKSPDF

ጸው ወለል ላይ አረፈች ። እበረንጸው ምሰሶ ላይም ተደገፈችና በሚር በተበቡ እጆቹዋ የደረትዋን ቁልፍ ፈታች ። ማታው ለብ ባለ ለስላሳ ጭለማ ተሞልቷል ። ፍዝዝ ቅዝዝ እንጸለ በሬ ፤ ድንዝዝ ብሳ ታሰተው ለለች ።

ኡፍ አረፈች ። ሁሉ ነገር አበቃ ። ሚሳኒ አልሞተችም ። እንደ ድመት ግልገል ሚያው ሚያው የሚለውም አራስ ሀጻን በፐሪስ እጅ እየታጠበ ነው ። ሚሳኒ ለጥ ብላ ተኝታለች ። ከዚያ ሁሉ የስቃይ ድምፅ ከዚያ ሁሉ የምጥ ሲታ ፣ ከዚያ ሁሉ ያለዋቂ አዋላጆች ያዝ ለቀቅ ፣ ከጥቅሙ ጉዳቱ ከሚያመዝን ማሞለድ በሁዋላ ፣ እንዴት መተኛት ቻለች ልጄ ? እንዴት አልሞተችም ! እስካርሌት እራስዋ እንዲህ ቢሆን የወለደችው ትሞት ነበር ። ሚሳኒ ፣ ከተገላገለች በሁዋላ እንኳ አቅም እያነሳት እንደምንም ተንጠራርታ ወደ እስካርሌት ጆሮ ተጠግታ "እመሰግናለሁ" ብላ ነው እንቅልፍ የወሰዳት ። እንዴት እንቅልፍ እሺ አላት እስካርሌት ዋድን ከወለደች በሁዋላ እንቅልፍ ጭልጥ አድርጎ እንደወሰዳት ረስታለች ። ምን ሁሉንም ነገር ረስታለች ። ጭንቅላትዋ ባዶ ቅል ሁኖዋል ። ዓለም ሁሉ ባዶ ሁኖዋል ። ከዚያ ማለቂያ መዛለቂያ ከሌለው ቀን ወዲያ ምን ዓለም ምን ኑሮ አለ ? ከእንግዲህስ ምን ኑሮ ሊኖር ነው ? የሚጮቅ ምሽት ፤ ሻካራ የማቃሰት ድምፅ ፤ ከብብት ወገብ ድረስ የሚንዠቀዠቅ ፣ ከዳሌ ጉልበት ድረስ የሚወርድ የሾቀ የሚያጣብቅና የረጋ ላቡት ። ይሄው ነው ።

የገዛ ድምፁዋ ከሙሉ ቅኝቱ ወጥቶ ጊዜ እየለየ ቁርጥ ቁርጥ እያለ ሲመጣ ፤ ዓይኖቹዋ ግን ድርቅ ብለውና የሚያቃጥሉ ሁነው ሁለተኛ እንባ የሚያፈልቁ አይመስሉም ። ቀስ አለችና በስንት ድካም ጐንበስ ብላ ከባዱን ቀሚስዋን ጭኑዋ ድረስ ሰበሰበችው ። ባንድ ጊዜ ለብ ያለችም ፣ ቀዝቃዛም ፤ የሚያጣብቅ ገላ ያላት ሆናለች ። የማታው አየር እግርና እጅዋን ሲዳስሳት ተሐድሶ ሆናት ።

እስካርሌት እበረንጸው ወለል ላይ ቀሚሷን ሙታንታዋ እስኪ ታይ ድረስ ሰብስባ ወ/ሮ ፒቲ ቢያዩ ምን ይሉኝ ብላ ላትጨነቅ ያለሃሳብ ተዘረጋግታ ተቀምጣለች ። ስለምንም ነገር አትጨነቅም ። ጊዜው መሄዱን እንጸፉመ ሁሉ ረጋ ። ግና መሽቶ መጨለሙም ይሁን እኩለ ሌት ይሁን አታውቅም ፣ አትጨነቅም ። ግድ አልሰጣትም ።

ከፎቅ የሚንቀሳቀስ ኩቴ ለማችና "ያቺ የተረገመች ፕሪሲ እንጸ ትሠን" ብላ አይኑዋን እንደጨፈነች አንድ አንቅልፍ የመሰለ ነገር ተጫጫኗትና ሸለብ አደረጋት ። ከዚያ ካልተወሰነ የጭለማ እረፍት በሁዋላ ፕሪሲ በደስታ እያስካካች እጐንዋ ቆማ አየቻት ።

@OLDBOOKSPDF

"እትዬ እስካርሴት ከማን ጥሩ ነው ያደረግነው ። እናቲም ብት ሆን ከዚህ የተሻለ ማድረግ አትችልም ።"

እጭለማው ውስጥ እንዳለች እስካርሴት በጣም ስለደከመች ዝም ብላ አፍጥጣ ታያለች ። ለመሳደብ ደክሟታል ። ለማንቋሸሽም ደክሟ ታል ። ያጠፋችውን ለመዘርዘር ድከም ብሏታል ። የማትችለውን ማቁ ለድ ሙያ አለኝ ማለቷን ፣ ፍርሃትዋን ፣ ብልግናዋን የሚለኒ ምጥ በጣም ሊባባስ ቅጂ መጥፌቱን ፣ መቀሱን ያልሆነ ቦታ ማስቀመጥዋን ፣ አል ጋው ላይ ውሃ መርጨትዋን ፣ አራሱን ልጅ ከእጅዋ መጣልዋን ሁሉ አንድ ባንድ እንዳትንገራት ደክሟታል ። ያ አንሶ ደግሞ እዚህ መጥታ ስለመልከም ሥራዋ ማናፋትዋ ይባስ ።

ያንኪዎቹ እንዚህን ነው እንግዲህ ነፃ እናውጣ የሚሉት! ብቻ ምን ያረጋል ያንኪዎቹን በደስታ ይቀበለዋቸዋል ።

ምስሶውን መደ ኋላ ተንጋሳ ተደግፋ ዝም ብትል ፕሪሲ ከሁኔ ታዋ ስሜትዋን ተረድታ መደ በረንዳው ጭለማ በረረች ። ትንፋሽዋን ለመዋጥ መንፈስዋን ለማረጋጋት ከሚበቃ ረዥም እረፍት በሁዋላ ፣ ከወደሰሜን በኩል በርክት ያሉ ሰዎች የኩቴ ድምፅ ሽቅብ መንጓጓን ይዞ ይሰማል ። ወታደሮች! ቀስ ብለ ቀና አለችና ቀሚስዋን ወደታች አውርዳ ተቀመጠች ፤ ሰው ከጭለማው ውስጥ ያያት ይመስል በምን ተእፍረት ። በቤቱ አኳያ ለቱጦር የሚያስጥሩ አያሌ ሰዎች እንደጥላ ሲያልፉ አይታ ተጣራች ።

"ቁሙ! እባክችሁ ቁሙ!"

አንድ ጥቁር ጥላ ከአጀቡ ተንጥሎ ወደ በሩ መጣ ።

"መሄዳችሁ ነውንጥላችሁን መዚዳችሁ ነው እንዴ?"

ጥላው ባርሚጣውን የሚያወልቅ መሰለና ከጭለማው ለስለስ ያለ ድምፅ መጣ ።

"እምን እመቤቱ ኪያረግን ያሰነው ይዜንኑ ነው ።ከሰሜን በኩል አንድ ማይል እርቀት ላይ ካለው ምሽግ የመጨረሻዎቹ ነን ።

"እናንተ! እውነትም ሠራዊቱ እያፈገፈገ ነዋ?"

"እምን እመቤቱ ።እየሽ ያንኪዎቹ እየመጡ ነው ።"

ያንኪዎቹ እየመጡ ነው ።የረሳችው ቅኝት ። ጉሮሮዋ ደረቀባት ። ምንም ነገር በተጨማሪ ማውራት አልቻለችም ።ያም ጥላ ከሱዋ ርቆ ሄደና ከመሰል ጥላዎች ጋር ተቀላቀለ ። እግሮቻቸውም እጭለማው ውስጥ ገቡ ። "ያንኪዎቹ እየመጡ ነው! ያንኪዎቹ እየመጡ ነው!"

@OLDBOOKSPDF

ይላል የእግሮቻቸው ቅኝት ።የእሷም የልብ ትርታ ይህንኑ ተቀበለና "ያንኪዎቹ እየመጡ ነው!" ይል ጀመር ።

"ያንኪዎቹ እየመጡ ነው እንዴ!" ብላ ፕሪሲ በጣም ተጠግታ ቆመች ።" ወይኔ እትዬ አስካርሌት ይገሉናል እኮ !ጠመንጃዎቻቸውን በሆድ ዕቃችን ነው የሚለቁብን! እንሱ.."

"በቃ ዝም በይ!" እነዚህን ቃላት ሳይንቀጠቀጥ ሰምቶ መቻል ግንም አይችል ። ፍርሃትዋ ታደሰባት ። ምን ልታደርግ ትችላለች ?እንዴት አድርጋ ልትሸሽ ነው ? የማን ያለህ ትበል ? ጓደኞችዋ ሁሉ ጥለዋት ሄደዋል ።

ከመቅዕበት ስለፊት በትለር አሰበችና ፍርሃትዋን አረጋግቶ ቦታ አስለቀቀው ።ዛሬ ጠዋት እንደዛ አጉረጥ ተቆርጦ እንደወደቀ ጫጩት ስትንፈራፈር እንዴት ሬትን አላስታወሰችም! ትጠላዋለች ግን ጠንካራና ጥሩ ሰው ነው ። ደግሞም ያንኪዎችን አይፈራቸውም ። እስከአሁን ከተማ ውስጥ ይኖር ይሆናል ። በእርግጥ ዶሚን አፍልቷት ይቅርታ የማይደረግለት ፣ ምህረት የማያሻው ነገር ተናግሯት ነው የሄደው ።ግን እንዲህ ባለው ክፉ ግዜ መቼም ማንንም ቢሆን መጥፎ መጥፎ አመሉን ቸል ብሎ ደግ ደጉን ማየት ያስፈልጋል ።በዛ ላይ ፈረስም ጋሪም አለው። አይ...!ምነው ቅድሙኑ ብታስበው ኖሮ! ከዚህ ጭለማ ቦታ ሁሉንም ይዟቸው ይሄድ ነበር ። ከያንኪዎቹ አድኖ — አንድ ቦታ የትም ይሁን ይዟቸው ይሄድ ነበር ።

ወደ ፕሪሲ ዞራ በጥድፊያ ተናገረች ።

"ካፒቴን በትለር የት እንደሚኖር ታውቂ የለም ? —አትላንታ ሆቴል ውስጥ"

"አም እመቤቴ ግን..."

"በቃ እዛ እየሮጥሽ ሂጂና እንደምፈልገው ንገሪው ። በፍጥነት እንዲመጣ አፈልጋለሁ ።ፈረሱንና ጋሪውን ወይም ከቻለ አምቡላን ስም ካገኘ ይዞ እንዲመጣ ንገሪው ።ስለ አራሱ ልጅም ንገሪው ።ከዚህ ይዞን እንዲሄድ መፈለጌን አስረጂው ። በይ ፈጠን በይ ፣ ሂጂ!"

ቀና አለችና ፕሪሲን ገፈተረቻት ።

"በእግዚአብሔር እትዬ አስካርሌት ! በጭለማ መሄድ አፈራለሁ! ያንኪዎቹ ቢያገኙኝስ ?"

"በደምብ ከሮጥሽ እንዚያን ወታደሮች ትደርሺባቸዋለሽ ።እንሱ ያንኪዎቹ እንዳያገኙሽ ማድረግ ይችላሉ ። በይ ፍጠኚ ።"

"እኔ ፈርቻለሁ! ካፒቴን በትለር ሆቴሉ ውስጥ ከሌለስ!"

@OLDBOOKSPDF

"ታዲያ የት እምሸ ተጠይቂያለሽ ።ምንም ሞራል የለሽ ልበልሽ ከሦቱሉ ውስጥ ከሉለ በዲካተር ጐዳና ካሉት ምግብ ቤቶች ውስጥ ፈልጊው ።ጠይቂያቸው ። ቤል ዋትሊንግ ቤትም ፈልጊው ።

በተቻለሽ የገባበት ገብተሽ ፈልጊው ።አንቺ ጅላንፎ ፈጥነሽ ከልሄድሽ ሁላችንንም ያንከዎቹ እንደሚይዙን አታውቂም እንዴ ?"

"እትዬ እስካርሌት ፤ እናቴ ምግብ ቤትና ሴተኛ አዳሪ ቤት ከገባሁ ትደበድበኛለች ።" እስካርሌት በርግጫ ልትላት ቃጣት ።

"እትሂጂና ዋ! ቆዳሽን ነው የምገፈው ።ብትፈልጊ ማህል መንገድ ላይ ቆመሽ እየጮህሽ እሪ የበትለር ያለህ በይ!ወይም ውስጥ መኖር አለመኖርሩን ሰው ጠይቂ ።በይ ሂጂ ።"

እየተቆነነች እየተገተተችና እያጉረመረመች ስትሄድ እስካርሌት እንደገና ደህና አድርጋ ስትረግጣት ቁልቁል ከደረጃው ጫፍ ባፍጢሙዋ ልትደፋ ምንም አልቀራት ።

"ሂጂ ሁዋላ ። አለበለዚያ ወንዝ አሻግሬ ነው የምሸጥሽ ። እናትሽን ሁለተኛ አታያትም ።ምን አለፋሽ የምታውቂውን ሰው ሁሉ አታይም ። ደሞ እምሸጥሽ ሰቅጌ ሠራተኛ ነው ። በይ ፈጠን !"

"ውይ በእግዚአብሔር እትዬ እስካርሌት..."

በእመቤቷ የእጅ ግፊት ደረጃውን ተንደርድራ ወረደች ። የፊት ፊቱ በር ተከፈተና እስካርሌት ጮኸች ።

"አንቺ አመጻም ፈጠን አትይም አሁን!" አለች ።

የፐሪሲ ኩቴ በመንገዱ ስታቆለቁል ይሰማል ።እየቆየ ኩቴ እሚባል በለስላሳው መሬት ተዋጠና ጠፋ ።

@OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ 23

ፕሪሲ ከሄደች በሁዋላ አስካርሴት ወደ ታችኛው አዳራሽ ደረጃውን ወርዳ ሄደችና ፋኖሱን አበራች ።ቤቱ የከሰዓት በሁዋላውን ሙቀት ተረክቦ ያቆየ ይመስል ተን የሞሳበት ወበቅ አገለሞዋል ።ቀን ቅፍፍ ድብር ያረጋት መንፈስ ለቅዱት ሆድዋ እህል ይሻል ።ከትላንት ማታ ጀምራ ከእንድ ማንኪያ ገንፎ በቀር እህል ባፍዋ እንዳልዞረ ትዝ ይሳትና ፋኖሱን ይዛ ወደ ማድቤት ሄደች ።የምድጃው እሳት ጠፍቷል ።ቤቱ ግን እንደ አንድ ነገር ይሞቃል ።ያገኘችውን ግማሽ ያህል የበቆሎ ዳቦ ተስገብግባ እየጐረሰች ሌሳ ምግብ መፈለግዋን ቀጠለች ።እማሰሮው ውስጥ ከጠዋቱ የተረፈ የወተት ገንፎ አየችና እሣሀን ላይ ስመገልበጥም ጊዜ ሳትሰጥ በጭልፋ ገባችው ። ጨው እንሶታል ግን ጨው ፍለጋ ስመሄድ ረሃቡዋ አሳስቻሳትም ።በዛ በጭልፋ አንድአራቴ ደህና ዋጠችና የቤቱ ሙቀት ሲያይልባት ባንድ እጅዋ ፋኖሱን በሌላው እጅዋ ቁራሽ የበቆሎ ዳቦ ይዛ ወደ አዳራሹ ሄደች ።

ፎቅ ሄዳ እሚላኒ ገመን መቀመጥ እንዳለባት ታውቃለች ።ድንገት ቢያማት እንኳ ጮክ ብላ ስመጣራት አትችልም ።ነገር ግን ያንን ሁሉ የህልም መዓት ያየችበትን ክፍል ተመልሳ የማየቱ ሀሳብ ያስጠላት ጀመር ።አሁንስ ሚላኒ መሞቷ ነው ቢሏትም አትሄድም ። ያንን ክፍል ደግማ ማየት በፍፁም አትፈልግም ።

ፋኖሱን በሻማው ማስቀመጪያ ላይ አኑራ ወደ ሬት ስፊቱ በረንዳ ሄደች ።ማታው በመጠኑ ሙቀት ቢኖረውም እዚህ ነፋሻ ነው ።እደሪ ሸው ላይ በፋኖሱ ውጋጋን ውስጥ ተቀምጣ ከዳቦዋ ጋር መሙዋገድን ቀጠለች ።

ስትጨርስ ትንሽ ትንሽ ጉልበት ተሰማት ። ብቻ ከጉልበቱ ጋር አብሮ ያ ፍርሃቱዋም መጣ ።ከመንገዱ ወደታች የሚመጣ የቻቻቻታ ድምፅ ይሰማል ፤ምን እንደሆነ ግን አልገባትም። ከፍና ዝቅ እያለ ከሚመጣው የድምፅ ሀምሀምታ በስተቀር ምንነቱን መለየት አልቻለችም ። ጆሮዋን በተቻላት ወደዚያው አቅጣጫ ለማዳመጥ ሞከረችና እንደገና የሥጋት ውጥረት የሠራ አካላትዋን አሳመማት ። በዚህ አለም ላይ ካለ ማናቸውም ነገር ይልቅ የፈረስ ኮቴ ድምፅና በፍርሃትዋ የሚሰቅባት ፤በራሱ የሚተማመነውና ሀሳብ የለሹ ሬት በት

@OLDBOOKSPDF

ለር ቢናገር መስማት ከሚችሉ ጋር ስትቀመጡ ንገር ሆነ ። ፊት እንድ
ቦታ ይዞዋቸው ይሄዳል ። የት እንደሆነ አታውቅም ። ለዛ ደሞ ግድ
የላትም ።

ጀሮዋን ወደ ከተማው እቅጣጫ ሰክታ እንዳለች ከዛፎቹ በላይ
የብርሃን ውጋጋን ብቅ አለ ። ጎረማት ፣ እንቆቅልሽ ሆነባት ። ትኩር ብላ
ተመለከተች ብርሃኑ ጭራሽ እየፈካ መጣ ። ሰማዩ መጀመሪያ ወደ
ወይን ጠጅ ፣ ከዚያ ፈዘዝ ወዳለ ቀይ ተለወጠና ከመቅፅበት ከዛፎቹ
አናት ምላስ የመሰለ የእሳት ነበልባል ወደሰማይ ብድግ አለ። ከመቀ
መጪያዋ ዘለሰች ። ልብዋ ድው ድው ማለቱን ፤ ፈጣን ግልቢያውን
ጀመረ ።

ያንኪዎቹ መጡ እንደሚመጡና ከተማዋን እንደሚያጋዩዋት ታው
ቋታል ። ከከተማዋ እምብርት ወደ ምሥራቅ የሚሄድ ይመስላል —
እሳቱ ። ወደ ሳይ እየተፈናጠረ ፣ በወርድም በቁመትም እየሰፋ ፣ ደም የመ
ሰለ ቀይ ቀለሙን እያሰራጨ ፣ ከደንገጡና ካፈጠጡ አይኖቹዋ ፊት
ቦግ አለ ። ትልቅ ሀንጻ እየነደደ መሆን አለበት። እንድ ጠባብ እስትንፋ
ላፍንጫዋ የጭስ ሽታ ይዞላት መጣ ።

ወደ ግዛ ከፍልዋ ሰመጌድና በመስኮት ደህና እድርጋ ለማየት
እንዲያመቻት ወደፎቁ በረረች ። ሰማዩ ድብልቅልቁ ወጥቷል ። ከሚን
ቀለቀለው እሳተነበልባል በሳይ እንደ ጅራፍ እየተጥመለመለ የሚወ
ጣው ጥቁር ጭስ ጥቅጥቅ ደመና ሠራ ። የጭሱ ሽታ የአሁኑ ከቅድሙ
በረታ። አዕምሮዋ እዚህም እዚያም እያለ ፣ እንዴ ነበልባሉ በምን ያህል
ግዜ ውስጥ የፒችትሪን ጦዳና አዳርሶ ያለችበትን ቤት እንደሚያቃ
ጥል ፤ እንዴ ያንኪዎቹ ምኔ መጥተው እንደሚያንቋትና እንደሚረባረ
ቡባት ፣ እንዴ ወዴት እንደምትሸሽ ፤ እንዴ ምን እንደምትሠራ ፣ የተመ
ሰቃቀሉ ሰሳቦችን ያከማቻል ። የገሃነም አራዊት ሁሉ የሚጮሁባት
መሰላት ። የተምታታ የሀሳብ ቁርጠት ናዳ ተጭኗት ናላዋ ዞረና የመ
ስኮቱን ደፍ ተደግፋ ዳነች ።

"ማሰብ አለብኝ" አለች እራሷ ለራሷ ፤ ደግማ ደጋግማ "ማሰብ
አለብኝ ።"

ዳሩ ግን ሐሳቦቹዋ ሁሉ በፍርሃት እንደሚበሩ አዕዋፍ ወደ ውስጥ
ወደውጪ እያሉ አልጨበጥ አሉዋት ። እዚያው እደፉ ላይ ተንጠልጥላ
እንዳለች ፤ ከዚህ ቀደም ከማናቸውም የመድፍ ላንቃ ሰምታ የማታው
ቀው ምድር ሰማዩን የሚያደበላልቅና ጆሮ የሚያደነቁር የፈንጂ
ድምፅ ሰማች ። ሰማዩ በተምዘግዛጊ የቋያ ነበልባል ደማ ። ተሸፐራፐረ ።
ሴላ ፈንጂ ተከተለ ። ምድሩዋ ተናወጠች ። ከበባይዋ ያሉት መስተዋ
ቶች እየረገፉ ቁልቁል እሷ ወዳለችበት ወደቁ ።

@OLDBOOKSPDF

እንዴ ፈንጂ ሕሳውን ቢሰማል ዓለሙ ሁሉ ጆሮ በሚሰነጥቅ ጩኸት ፣ በነበልባልና በሚናወጽ ምድር የተሞላ የሥቃይ አምባ ሆነ። ወደሰማይ የሚወረወረው የእሳት ብልጭታ ደም የተረጨበት በሚመስለው የጭስ ደመና ማህል ሰንጥቆ ይወጣና ተመልሶ በዝግታ ይወርዳል። አንድ ደካማ ድምፅ ጉኑዋ ከሰው ከፍል ብትሰማም ግድ አልሰጣትም ።አሁን ለሜላኒ ግዜ የላትም ።ጊዜ ያላት ፣ እንደምታየው የእሳት ጨረር በፍጥነት በደም ስርዋ የሚያልፈውን ፍርሀት ለማሰላሰል ነው ።በፍርሃት የተሞጠችና በናቱዋ ደረት ላይ ፊቷን ቀብራ ይሀንን የእሳት ትርዒት ላለማየት የምትፈልግ ትንሽ ልጅ ናት ። እቤት እቤቷ ብትሆን! ከእናትዋ ጋር እቤቷ ብትሆን!

ህዋስ በሚነዝረው በዚህ ጩኸት ማህል ፣ በፍርሃት የሚሮጥ ሰው ኮቴ ሶስቱን ደረጃ ባንዴ እመር እሚል ኮቴ ፣ ሲመጣ ሰማች የድረሱልኝ አይነት ጩኸት ተከተለው ። ፕሪሲ በሩን በርግዳ ወደ ከፍሉ ገባችና ወደ እስክርሌት በርራ በቁንጮዉ ሥጋዋን የምትበጭቅ ይመስል እጅዋን እንቅ አረገቻት ።

"ያንኪምቹ.." ብላ ጮኸች እስክርሌት እራሷ ።

"የለም እትዬ ያኛ ሰምች ናቸው እኮ!" አለችና ጮኸች ፕሪሲ፣ በጥፍሩዋ የእስክርሌትን እጅ እየቆፈረች ። "የጥይት መጋዘኑን፣ የመሣሪያ ግምጃ ቤቱንና የልብስ መጋዘኑን እያቃጠሉ ነው ።በእግዚአብሔር አትዩ እስክርሌት ሰባ የሚሆን የጦር ተሽከርካሪዎች የባሩድ ከረጢቶች እንዲያዙ ተቃጠሉ።ወይኔ አምላኬ እኛም መንደሻችን ነው እንግዲህ።

እንደገና እየጮኸች እስክርሌት እሚት እስክትጮህ ድረስ ሜን ብላ ቆነጠጠቻት ። እስክርሌት በንዴት የፕሪሲን እራስ ነቀነቀቻት ።

ያንኪምቹ ግና አልደረሱም! ለመሸሺያ ጊዜ አለ!! ያሏትን በፍርሃት ያዳነማቸው ኃይሎች ሁሉ በራስዋ ላይ አሰማራች ።

"እራሴን ማሸሽ ካልቻልኩኝ" አለች በልቧ ። "እንዳበረሩት ድመት መሸማቀቂ ነው!" ብቻ የፕሪሲ መሸበር ትንሽ አፅናናት ። ትከሻዋን ይዛ ሰበቀቻት ።

"ይሀን ጩኸትሽን አቁሚና ደህና ነገር አውሪ ።ያንኪምቹ ግና አልመጡም አንቺ ሞኝ! ከጢቴን በትለርን አግኝቼው ለመሆኑ! ምና ለሽ? እጨጣለሁ አሉ ?

ፕሪሲ መጮሁዋን ታቁም እንጂ ጥርሱዋ ይንቀጫቀጫል ።

"አዎ እትዬ በመጨረሻ አግኝታት ። አንድ ሆቴል ውስጥ አግኝቼ ነገርኩት ። እሱ.."

@OLDBOOKSPDF

"የት እንዳገኘሽው መቼ ጠየኩሽ? ይመጣል ወይ ፈረሱን ይዞ እንዲመጣ ነግረሺው የለም?"

"በእግዛቤር እትዮ እስካርሌት የኛ ሰዎች ፈረስ ጋሪውን ለአን ቡላንስ ብለው ወስደውብኛል ብሎ ነገረኝ።"

"ኧረ የሰማይ እምላክ!"

"ግን ይመጣል..."

"ምን አለ?"

ፕሪሲ ትንፋሽዋን ዋጠችና አይኖችዋን ከብልል ከብልል እያረገች ለመረጋጋት ሞከረች።

"እም እትዮ እንዳዘዙኝ ቡና ቤት ውስጥ አገኘሁት። እደጅ ቆሜ ተጣራሁና ወጣ። እሶኝና በቀጥታ መጣ። እኔም በዴካተር ጐዳና ወታ ደሮቹ መጋዘኖቹን ሚቃጠሳቸውን ስነግረው ነይ አለኝና ወደ ፋይቭ ፓይንት ጐዳና እጄን ይዞ ወሰደኝ። በይ ምንድን እንደሆነ የምት ይው ፈጠን ብለሽ ንገሪኝ አለኝ። እኔም እርሶ እንዳሉኝ ካፒቴን በት ለር ፈረስህንና ጋሪህን ይዘህ ቶሎ ድረስ ብለውሃል አልኩት። ወይ ዘሮ ሜላኒ ልጅ ስለወለዱ ይዘኸን ከከተማ እንድትወጣ ይፈልጋሉ አልኩት። እሱም ወዴት ለመሄድ እያሰበች ነው? አለ። እሱን በርግጥ አላውቅም ግን ያንኪዎቹ እዚህ ከመድረሳቸው በፊት መጥ ተህ ከአንተ ጋር አብሮ ለመሸሽ ነው ብለው! የእኔን ፈረስማ ወሰ ዱት ብሎ እየሳቀ ሄደ።

የእስካርሌት አንጀት ተቆረጠ። የመጨረሺያው ተስፋዋ መነመነ። ሠራዊቱ በማፈግፈግ ሲሸሽ ማናቸውንም በከተማው ያለ ተሽከርካ ሪና አንሰሳ ይዞ እንደሚሄድ እንዴት አጣችው? ምን ጅል ናት? ለትንሽ ግዜ ፕሪሲ የምትሰውን ሳትሰማ በድን ሆነች። ብቻ በሁዋላ ሴሳውን ወሬ ለመስማት ጓጉታ ልቧን መለስ አረገች።

"ከዛም ወይዘሮ እስካርሌትን አትጨነቂ በያት አለኝ። ባጣ እንኳ ከሠራዊቱ አንድ ፈረስ ሰርቂ እመጣለሁ። ከዚህ በፊትም ፈረስ ሰርቄ ነበር። ቢተኩሱብኝም ይግደሉኝ እንጂ አንድ ፈረስ ይገፎ እመጣለሁ። ከዛ እንደገና ሳቀና፤በይ አቋራጭ ፈልገሽ ወደ ቤትሽ ሩጪ። እና መን ገድ ከመጀመሬ በፊት አንድ ነገር ፈነዳ! ድምፁን ስሰማ ባለሁበት ውሃ ሆንኩ። እሱ ግን አይዞሽ ምንም አይደል ሰዎቹ የጦር መሣሪያ ዎቻቸውን ያንኪዎቹ እንዳይጠቀሙበት ሲያፈነዱ ነው አለኝ እና.."

"ብቻ ይመጣ የለ? ፈረስ ይዞ ይመጣ የለም?"

"ብሏል።"

@OLDBOOKSPDF

በከባዱ ተነፈሰችና እፎይ አለች ።መቼም ፈረስ የማግኘ እንድ እንኳን ዘዴ ካለ ሬት በትሰር ያገኘዋል ።ወ...ሬት በጣም ግሩም ሰው ነው ።ከዚህ ጣጣ ያውጣት እንጂ ይቅርታ ታደርግለታለች ። መሸሽ ነ ብቻ !ሬት ካለ ደግሞ በሞራሽ አትፈራም ።ሬት መከታ ይሆናቸዋል። እግዚሃር ይመስገን ሬት ተገኘ! ደህንነቱዋ ፍንትው ብሎ ታያትና ወደ እለት ተጣባሩዋ ተመለሰች ።

"ዋድን ቀሰቅሽውና አልብሺው ። ሰኛም ልብሶቹን ሁሉ ሰባሰ በሽ አዘጋጂና በትንሹ ሻንጣ ከተቺያቸው ።ደሞ ልንሄድ መሆኑን ለሚላኒ እንዳትነግሪያት ።ነና ነው ፤ ቁርጡ እልታወቀም። ወፈር ወፈር ባሉት ፎጣዎች ተጠንቀቂና አራሱንም ጠቅልይው ።ልብሶቹንም ከተ ችለት ።"

ፕሪሲ እስካሁን ፍርሃትዋ አልበረደላትም ። ቀሚስዋን በእጅዋ እንደያዘች ናት ።ክነሙቹ ያንኪዎች በቀር ምንም የሚታያት ነገር የለም። አስካርሌት ገፈተረቻትና ጭብጧን አስለቀቀቻት ።

"እኮ ፍጠኝ !" አለቻት ። ፕሪሲ እንደጥንቸል በረረች ።

አስካርሌት ወደ ሚላኒ ሄዳ ፍርሃትዋን ማቃለል አለባት ። መቼም እንደመብረቅ የሚጮኸውን ፈንጂና የሚንቀለቀለውን ሰማይ ጠቀስ ወላፈን ስታይ ድንጉት ቀልቧን ትስታለች ። ሁኔታው ሁሉ የዓለም ፍጻሜ ይመስላል ።

ነገር ግን ወደህ አሣረኛ ክፍል ተመልሳ ለመግባት ገና አላገነ መችም ።ወደ ምድር ቤት ወርዳ ወይዘሮ ፒቲ ፓት ወደ ማከን ሳይ ሸሹ ጥለውት የሄዱትን ሣህንና ከብር የተሠሩ ዕቃዎች ለማሰናዳት አሰበች ።ዳሩ ግን ገና ወደ ምግብ ቤት ስትደርስ እጅዋ ከመንቀጥቀጥ የተነሳ ሶስቱን ሣህን ለቀቀችውና ተከሰከሰ ። ወደ በረንዳው ሮጣ ስማዳ መጥ ሞከረችና እንደገና ወደ ምግብ ቤት ተመልሳ ከብር የተሰራው ንም ሳህን አንካክችው ።የያዘችው ነገር ሁሉ ከእጅዋ ይወድቅ ጀመር። ወዲህ ወዲያ ስትጣደፍ ብጭቅጫቂ ጨርቅ ሳይ እረገጠችና እረብ ብላ ወደቀች ። ብቻ ወዲያው ምኔ ተነሳች ሳይባል ብድግ አለች ።የወ ደቀችበትም አላመማት ።ከበላይዋ ፕሪሲ እንደዱር አውሬ ስትጋልብ የሚሰማው ድምፅ አስካርሌትን አንሙል አረጋት ።

ለአስራ ሁለተኛ ጊዜ ወደበንረዳው ሄደች ። አሁን ግን ወደ አታ ጥቅለላ አልተመለሰችም ። እባው ቁጭ አለች ። ዕቃ መጠቅ ለል ምን ዋጋ አለው ። በሞራሽ አይቻልም ። ልብ ድውድው እያለ የሬትን መምጣት ከመጠበቅ በቀር ሌላ ነገር መሥራት አይቻልም። ሳይመጣ ሰዓታት ያለፉ መሰለ ። በመጨረሻ ግራሶ ያነሰው ተሽከር

@OLDBOOKSPDF

ርካሪ ሲጥጥ ሲጥጥ ሲልና የፈረስ ይሁን የሌላ የማይለይ በደ ንብ የማይሮሀ ዱካ ተሰማ ። ምነው ፈጠን ቢልን ለምን ፈረሱን አያስ ሮጠውም ?

ድምፁ ወደ አፅ. እየተጠጋ ሲመጣ ከተቀመጠችበት ተንስታ የሬ ትን ስም ጠራች ።ከዚያም እንዲያው በደብዛዛው ከእንድ ትንሽ ጋሪ ሲወርድ አየችው ።የውጪው በር ተከፈተና ወደ እሱዋ መጣ ።እሁን በደንብ ይታያት ጀመር ።በፋኖሱ ብርሃን ቁልጭ ብሎ ታየ ።መቼም የልብሱ ነገር አይነሳ ። ወደ ግብገባ እንደሚሄድ ሁሉ ሽክ ብሏል ። በእውቅ ልብስ ሰፊ የተሰፋ ነጭ በነጭ ሱሪና ኮቱ ውሃ ከመሰለው ግሬጫ ሰደሪያውና አንገቱ ላይ ሸብ ካደረገው አስካርፉ ጋር ሙሽራ አስመስሎታል ።ሠፊ ባርኔጣው ወዳንድ ወገን ጋደል ብሏል ።ቀበቶው ላይ ከግራና ከቀኝ ሁለት ባለቀንድ እጀታ ሽጉጦች ተንጠልጥለዋል ። የኮቱ ኪስ በቦምብ ተሞልቶ ተነፋፍቷል ። ባልሰለጠነ ሰው አካሄድ እርምጃውን ጨርገድ ጨርገድ እያደረገ ሲመጣ ያማረ ጭንቅላቱ ያል ሰለጠነ ልዑል መልክ ይታይበታል ።ያ ማታ ቁርጠት የለቀቀባት እደጋ አሱን ያሳከረው ይመስላል ።በጨለማ ፊቱ ላይ ከጥንታቂ የሚ መጣ ቁርጠኛነትና ሞጋ ማጣት ይነበባል ። ይህንን ማስተዋል ብት ችል ኖሮ አስካርሌት ድንጋጤውን ባልቻለችውም ነበር ።ጥቁር አይ ኖቹ በሚሆነው ሁሉ የተደነቁ ይመስል ወዲህ ወዲያ ይንቀዋለላሉ። ያ ምድር የሚያናጋ የፈንጂ ድምፅ እየተሰማና ያ ሁሉ እቶን እየፈላ የህጻናት ማስፈራሪያ እንደሆነ ሁሉ ቁብ አልሰጠውም ።ደረጃውን ሲወጣ ወደሱ እየተንደረደረች ፊቷ ነጥቶ አይኑዋ በብርሃን እየነደደ መጣች።

"እንደምን አመሸሽ" አለ በውስጡ ታይል ባለው ድምፁ ባርኔ ጣውን ሰሰላምታ እያነሳ "በጣም ጥሩ ሰዓት ነው ።ሊመጓዝ እንደምት ፈልጊ ሰማሁ ።"

"ከእንግዲህ ወዲያ ብትቀልድ አላናግርህም" አለች በሚርበተ በት ድምፅ ።

"ፈራሁ እንዳትይኝ ብቻ!" የተገረመ አስመስሎ ሲስቅባት ከደ ረጃው ጫፍ ልትገፈትረው ምንም አልቀራት ።

"አዎን ፈርቻለሁ! እግዜር ሰፍየል የሰጠውን ያህል እንኳ ጭን ቅላት ካለህ አንተም ትፈራለህ ።አሁን ለወሬ ጊዜ የለንም ። ከዚህ ወጥተን መሄድ አለብን ።"

"ኧረ ታዛዥ ነኝ የኔ እመቤት ።ለመሆኑ ወዴት ለመሄድ ነው ያሰብሺው ? ወደዚህ የመጣሁት ወዴት እንደምትሄጂ የማወት ጉጉት ይዞኝ ነው። ወደ ሰሜንም ሆነ ወደ ደቡብ ፤ ወደ ምሥራቅም ሆነ ወደ

@OLDBOOKSPDF

ምዕራብ ሠላጠሰ አይቻልም ።ያንኪዎቹ በድጥን አገር ሁሪያውን ናሻ ተዋል ። ያንኪዎቹ እስከሁን ያላገኙትና ሠራዊቱም የሚያፈገፍግበት ከከተማው የሚያስወጣ መንገድ አንድ ብቻ ነው ።ያም ቢሆን ክፍት እንደሆነ የሚቆየው ለጥቂት ጊዜ ነው ።ኖጂኔራል ስቲቨሰ ጦር ዳር ያሉን እየተዋጋ መንገዱን ነጻ አድርጐ ሠራዊቱ እንዲያፈገፍግ ለማድረግ በመጣጣር ላይ ነው ያለው ።ሠራዊቱን ተከትለሽ በዚሁ በሚከደኑ መንገድ ቢትሂጂ ደሞ ፈረሱን ይነጥቁሻል ። ፈረሱን መንጠቁ እንኳ ባልከፋ እኔንም በሌብነት ጣጣ ውስጥ ይከተኛል ።እና ወዴት ለመሄድ ታስቢያለሽ ?"

እየተንቀጠቀጠች የሚናገረውን ትሰማለች ፣ ግን አንዴንም ልብ አላለችም ።ጥያቄ ሊጠይቃት ያት እንደምትሄድ ታውቃለች ።ቀኑን ሙሉ በትጨነቅ ስትጠበብበት የዋለችው ጉዳይ ነውና ያት እንደም ትሂድ ታውቃለች ።እንድ ቢታ ብቻ ነው ።

"ወዴ ቤቴ ነው የምሄደው ።" አለች

"ባቢት ? ወደታራ ማለትሽ ነው ?"

"ኤም፣ እም፣ ወደታራ፣ አባክህ ፌት ፈጠን እንበል !"

አበጸ እንጂው ብሎ አያት ።

"ታራን በፈጠፈሽ እስካርሴት፣ ጅንሰቦሮ ላይ ሌት ተቀን ወጊያ መሆኑን አታውቂም እንዴ ? ከራፍና ሬዲ ጀምሮ ቁልቁልና ሽቅብ እያሉ ጀንሰቦሮው መንገድ ሙስጥ ሙሉ እንደሚዋጉ አታውቂም? ባሁኑ ሰዓት ያንኪዎቹ በድጥን ታራ መንገደር ላይ እንደሆኑ አታውቂም ? እርግጠኛ ቦታቸውን ማንም ለማወቅ ባይችልም እዛ አካባቢ ናቸው ። ወደ ቤት መሄድ አትችይም፣ በያንኪዎቹ ሠራዊት ማህል ለማለፍ አትችይም ።"

"የሰም እሄዳለሁ!" ብላ ጮኸች "እሄዳለሁ፣ እሄዳለሁ!"

"አንቺ ሞኝ ልጅ" ድምፁ ቁጣ ያዘለና ፈጣን ነው "በዛ በኩል ለመሄድ አትችይም ነው እኮ የምለው ።ያንኪዎቹ እንኳ ባያገኙሽ ጫካዎቹም ቢሆኑ ከሁለቱም ወገን በከዳ መንበደዎች ተሞልተዋል ።ብዙዎቹ የኛ መታደሮች ደሞ ገና ከጅንሰቦሮ በማፈግፈግ ላይ ናቸው ።እነሱም ቢሆኑ ልክ እንደያንኪዎቹ ፈረስሽን ይነጥቁሻል ። ያለሽ አንድ ምርጫ የኛኑ ጦር እየተከተልሽ ሙለማ ለብስሽ መጣዘ ነው ።የማክደኑን መንገድ ይዘሽ መሄድ ብቻ ነው የሚያዋጣሽ ።ወደ ታራ መሄድ አትችይም ።እዛ ብትሄጂ እንኳ በእሳት ጋይዩ ድምጥ ማጡ ጠፍቶ ነው የምታገኘው ።እንቺን ወደቤት ሂጂ ብሎ መልቀቅ ጭካኔ ነው ።"

@OLDBOOKSPDF

"ወደቤቴ እሄዳለሁ!" ብላ ሙቅጥጥ ድምፅዋ ጭራሽ ወደ አሪታ ተለወጠ ። "እሄዳለሁ ። እንተ ልትከለክለኝ አትችልም ። እሄዳለሁ! እናቴ ጋ መሄድ አለብኝ! እናቴን አፈልጋለሁ! ልታቆመኝ ብትሞክር እገልሃለሁ! ወደታራ እሄዳለሁ!"

ከፍርሃትና ከሞንቂት የመነጨ እንባዎቹ በመጨረሻ መንገድ ስትሰጣቸው ወረዱ ። በእጅዋ ደረቱን እየመታች "በአግራም ቢሆን እሄዳለሁ እንጂ አልቀርም ፣ እሄዳለሁ!" ብላ እንደገና ጮኸች ።

በመጨረሻ እቅፉ ውስዋ ገባች ።በእንባ የራሰ ጉንጩ ከሸጉርጉሩ የሸሚዙ ኮሌታ ላይ አረፈ ።የሚማቱት እጅቹዋም አቆሙ ።በእጅቹ ፀጉሯን እየደባበሰ ድምፅን ረጋ ለስለስ አደረገው ።እንዴህ ያለው ግርማ ሞገስ ያለው የረጋ ፣ምንም ፈሪ ያልተቀላቀለበት ድምጽ የሬት በትለር ሆኖ አያውቅም ።የብራንዲ ፣የትንባሆ እንዴሁም የፊረስ ጠረን የተቀላቀለበት የእንድ ጠንካራ ሰው ሽታ አለ ። አባቷን ጄራልድን አስታወሳት ።

"በቃ በቃ ያኔ ቆንጆ" አለ ለስለስ ብሎ ። "በቃ አታልቅሺ ። ያኔደፋር ልጅ ፣ ሠይቤትሽ ትሄጂለሽ ። ትሄጂለሽ በቃ አታልቅሺ ።"

አንድ ነገር ፀጉሩዋን ሲታከካት ተሰማትና ከንፈሩ ይሆን እንዴ ብላ ገረማት ። ዉ... አቅሱ በጣም ይመቻል ። በጣም ደስ ይላል ። ይሞታታል ። ምነው እዛው በቆየሁ አሰኛት ። በእንዴህ ያሉ ጠንካራ ክንዶች ማህል ሆኖ ምን ሊነካት ፣ ምን ጉዳት ሊደርስባት ይችላል ። ኧረ በጭራሽ ።

እጇን እቢሱ ከተተና አንድ መሀረብ አውጥቶ እንባዋን ከአይኖቹዋ ላይ ጠረገላት ። "በይ እንደጥሩ ልጅ ተናፈጪ" አለና አዘዛት፣ ቅንሽ ፈገግ ብሎ ።" እና ምን ማድረግ እንዳለብኝ ንገሪኝ ።ቶሎ ቶሎ ማለት አለብን ።"

አፍንጫዋን በትዕዛዙ መሠረት አጸዳች ። መንቀጥቀጡ መቼም አልተዋት ።ምን እንደምትለው ማስብ ግን አልቻለችም ።ከንፈሮቹዋ እንዴት እንደሚንቀጠቀጡና ዓይኖቹዋ እርዳታ ፍለጋ ወደሱ እንዴ ሚመለከቱ አየና ታዘዛት ።

"ወይዘሮ ሚሲ መለደች አይደል? እቧን ይዞ መሄድ በጣም አደ ገኛ ነው ።ሃያ አምስት ማይል ሙሉ ፣ እሱዋን በዛ በአጥንቱ በሚሄድ ጋሪ መውሰድ አደገኛ ነው ።ወይዘሮ ሚድ በንድ ብተዋት ይሻላል ።"

"የሚድ ቤተሰቦች እቢታቸው የሉም ።እና ልተዋት አልችልም።"

@OLDBOOKSPDF

"ጥሩ እንግዲህ ። በይ እጋሪው ላይ ትውጣ ።ያቺ ሀሳብ የለሽ ደቃቃ ፍጥረት የታለች ?"

"አላይ ፎቅ እቃችንን እየጠቀለለች ናት ። በሰንዱቅ አድርጋ እያዘጋጅች ነው ።"

"ሠንዱቅ? በዛ ጋሪ ላይ ምንም ሠንዱቅ መጫን አይቻልም ። እናንተን ለመጫን እንኳ መቻሉን እንኛ ።ማሀል መንገድ ላይ ፣ ጉማውን ባንጫነው እንኳ ራሱ ወልቆ ይበርራል ።ንገሪያትና በጣም ቀላል የሆ ነውን በቤቱ ያለውን አልጋ ትያዝና ጋሪው ላይ ይጫን ።"

እስካርሌት አሁንም አልተንቃነቀችም ።በጠንካራ እጆቹ ክንዷን ሲይዛት በስውነቱ ያለው የህይወት ሙቀት ወደሱዋ ተላለፈ ። ምነው እሷ እንደሱ አርጋታና አለመለወጥ ቢኖራት !ምነው እሷ እንደሱ ጠንካራ ብትሆን! እየገፋ ወደ አዳራሹ ወሰዳት ፣ ግን አሁንም እምታ ደርገው ጠፍቷት ቆመች ።እንደለማዱ አራን በማሽሟጠጥ አጣመ መና "ሰውንም ሆነ እግዚአብሔርን አልፈራም ትለኛ የነበረችው ጀግና ሴት ትሆን !" አለ ።

ከት ብሎ ሳቀና እጆቿን ወደታች ገፋቸው ።ግትር ብላ አይን አይኑን አስተዋለችው ። ጠላችው ።

"አልፈራም" አለችው ።

"አሱማ ጀግና ነሽ አትፈሪም እም ።ትንሽ ቆይተሽ ደግሞ በፍር ሃት ስትንቀጠቀጪ ትገኛለሽ። ባንቺ ላይ ምንም እምነት የለኝም ። እኔ የለሁበትም ።"

በደካማነቷ መራቱን በእግሩዋ መታችና ትይዘው ትለቀው ነገር ማሰብ ባለመቻሏ ፣ ቃል ሳትናገር ፋኖሱን አንስታው ደረጃውን መው ጣት ጀመረች ።ከሁላዋ ተጠግቶ ራሱ ለራሱ ይስቃል ። ትሰማለች ። ድምፁ መቼም አንጀቷን ነው ያሳረራት ። ወደ ዋድ መኝታ ቤት ብትሄድ እጁን ቆፈን እንደያዘው ሁሉ አቆላልፎ ፕሪሲ ግማሽ እንዳለበሰችው ደረሰች ። ያስለዋል። ፕሪሲ በፍርሃት የመራድ ጩኸት ታሰማለች ። የዋድ አልጋ ቀለል ያለ በመሆኑ ደረጃውን እየገፋች ወደ ጋሪው እንድትወስደው ፕሪሲን አዘዘቻት ።ፕሪሲ ልጁን ከአልጋው አወረደችና እንደታዘዘችው አደረገች ።ዋድ ኋላ ኋላዋ ተከተላት ። አዲስ ነገር ሲያይ ሳሉም ተወት አረገው ።

"ና"አለች እስካርሌት ወደሚላኒ መኝታ ቤት በር እየዞረች ። ሬት ባርሜጣው በእጁ ይዞ ተከተላት ።

@OLDBOOKSPDF

ሚላኒ አገጭዋ ድረስ አንሳፍፋ ለብሳ በፀጥታ ተጋድማለች። ፊቷ አሸቦ መስሏል ። ጉድጉድ ብለው ጥቁር ክብ የሰሩት አይኖቿ በተጠቀቀት ቆመዋል ። ሬት መኝታ ቤቷ ድረስ መግባቱ ይሄን ያህል አላስገረማትም ። ያለ ጉዳይ እንዳልገባ ታውቃታል ።ፈገግ ለማ ለት ሞክራ ነበር ግን ፈገግታዋ አፉዋ ጥግ ሳይደርስ ከሰመ ።

"ወይቤት ፣ ወይታራ መሄዳችን ነው"አለች እስካርሌት ፈጥና ለማስረዳት ። "ያንኪዎቹ እየመጡ ነው ። ሬት ይዞን ሊሄድ ነው ። ያለው መንገድ ይሄው ብቻ ነው ሚሲ"።

ሚላኒ ራስዋን በቀስታ በመነቅነት አዎ ለማለት ሞከረችና ወደ ሕፃኑ ዝቅ ብላ ማየት ጀመረች ።እስካርሌት ህጻኑን አነሳችና በወፍ ራም ፎጣ ጠቀለለችው ።ሬት ወደ አልጋው ተጠጋ ።

"እንዳልገዳሽ ቀስሰ ብዬ ነው" አለ ድምፁን ዝቅ አድርጎ፣ አን ሶላውን ሳይዋ ላይ ጣል ጣል እያደረገ ። "እስቲ በከንድሽ አንገቴን ልታቅፊ ትችይ እንደሆነ ምክሪ"

ሚሲ ሞከረች ፣ ግን ክንዶችዋ ዝለው ወደቦታቸው ተመለሱ ። ጐን በስ አለና አንድ እጁን በብብትዋ በኩል አንድ እጁን ከጉልበትዋ ሥር አደረገና ዝግ ብሎ አነሳት ። አልጮኽችም እንጂ ከንፈሩዋን ስት ነክስና ፊቷ ሲንጣ እስካርሌት አስተውላለች ።እስካርሌት ሬት እንዲ ታየው ፉኖሱን ከፍ አድርጋ ያዘችለትና ወደበሩ ስታመራ ሜላኒ አንድ ነገር እንደቀራት ሁሉ ወደ ግድግዳው አይኑዋን ሰቀለች ።

"ምንድነው ፣ ምንፈለግሽ" አለ ሬት ልስልስ ብሎ ።

"አባክህ" ሜላኒ በሹክሹክታ በጣቱዋ ለማሳየት እየሞከረች "ቻርለስን" አለ ።

ሬት ቁልቁል ተመለከታት ። በሰመመን የምትናገር ነው የመሰ ለው ። እስካርሌት ግን ነገሩ ገብቷት ብስጭት አለች ። ሚላኒ ከሽጉ ጡና ከጐራዴው በታች እግርግዳው ላይ የተሰቀለውን የቻርለስን ፎቶግራፍ (አሮጌ ፎቶ) ነበር አውርዱ የምትለው ።

"አባክህ" አለች ሚላኒ እንደገና በሹክሹክታ ፣ "ጐራዴውንም"።

"ዉ እሺ እሺ" አለችና እስካርሌት ፣ ሬት መንገዱ ጥርት ብሎ እንዲታየው ከአበራችለት በኋላ ፣ ተመልሳ ጐራዴውን ሽጉጡንና ዝናሩን አውርዳ ያዘች። እነዚህን ሁሉ ፣ ህጻኑንና ፉኖሱንም ባንድ ላይ መያዝ ያስቸግራል ። አይጣጣምም። አለዚያማ ልክ እንደ ሜላኒ መሆን ነው ። ሚላኒ ለራስዋ ልትሞት እያጣጣረችና ያንኪዎቹ አይኑዋ ሥር ደርሰው ፣ አፀ. ለቻርለስ ንብረት ትጨነቃለች ።

@OLDBOOKSPDF

ፎቶግራፉን ስታወርድ የቻርለስን መልክ በጨረፍታ አየችው። እነዚያ ቡናማ ትላልቅ አይኖቹ አይኑዋ ገቡና ቆም ብላ ፎቶግራፉን ትኩር ብላ በጉጉት አየችው። ይሄ ሰው ባሏ እኮ ነው። ጥቂት ማታ ምች አብሮዋት ከጉኑዋ ተኝቱዋል። እንደሰው ለስላሳና ቡናማ አይን ያለው ልጅም ወልዶላታል። ግን ትንሽ ትንሽ ነው የምታስታውሰው።

በክንዱ የታቀፈችው ህጻን እጆቹን አወራጨና በለስላሳው ሃአሀዩ ሲል ጮንበስ ብላ ተመለከተችው። ሰመጀመያሪ ጊዜ ይሄ ልጅ የአሽሌይ ልጅ መሆኑን ተገነዘበች። ባላት የመመኘት አቅም ሁሉ የሷ ልጅ እንዲሆን፤ የሱዋ ብቻም አይደል፤— የሱዋና የአሽሌይ ልጅ እንዲሆን ተመኘች።

ፕሪሲ ደረጃውን እመር እመር እያለች መጣች። እስካርሌት ልጁን አቀበለቻትና ፈዋነው መውረድ ጀመሩ። ፋሞሱ ቅርስ የለሽ ጥላዎችን ግር ማጻው ላይ ይወረውራል። አሻራቹ ሲደርሱ እስካርሌት የራስ ሽፋን አየችና በፍጥነት ሰከንታ ጥብጣቡን አነጨሙዋ ላይ አሠረች። የሚላኒ የሐዘን የራስ ሽፋን ነው። ስእስካርሌት አይሆኖትም፤ ነገር ግን የራሷን የት እንዳረገችው ስለማታስታውስ ዝም ብላ አደረገችው።

ከቢት ወጣችና በፊት ለፊቱ በረንዳ ተንደረደረች። ፋሞሱን እን ደያዘች ከግርግዳው እንዳትላተም እየተጠነቀቀች ወረደች። ሚላኒ ከሁ ዋለሟው የጋሪው ክፍል ሙሉ ለሙሉ እግሩዋን ዘግታ በጀርባዋ ተጋ ድማለች። ከነጋንዋ ዋድና በርጣ የተጠቀለለው ሕፃን አሉ። ፕሪሲ ጋሪው ላይ ወጣችና አራሱን ታቅፋ ቁጭ አለች።

ጋሪው በጣም ትንሽና ጠባብ ነው። ከግራና ከቀኝ ያሉት መደገ ፊያዎችም በጣም ዝቅ ያሉ ናቸው። ጉማምቹ ጎና መጀመሪያ ሲሠሩ ወልቱው የሚወድቱ ይመስል እንደሽባ እግር ወደ ውስጥ ወደውጪ ይላሉ። ፈረሱን አንዴ አየችውና ስቅቅ አለች። ግጥብጥቡ የወጣ ባጥ ንቱ ያለ እንስሳ ነው። ቅስሙ እንደተሰበረ ሁሉ አንገቱን ቁልቁል ደፍቶ በፊት እግሮቹ ማህል ሊከተው ምንም አልቀረው። ከሲታ ጀርባው ላይ ልጓም ያረፈበት ቦታ ጉድጉዶ ቦይ ቦይ ሠርቷል። ሲተ ነፍስ ድምፅ እንደሌለው ፈረስ ነው።

"እንደው ሰስሙ ነው ፈረስ የሚባለው አይደል?" አለ ሬት። "አግዳሚዎቹ እንጨቶች ማህል የሚሞት ይመስላል። ግን ላገኝ የቻ ልኩት ይሀንኑ ብቻ ነው። አንድ ቀን ከየት እንደሰረኩትና እንዴት እንደሰረኩት፣ እንዴት የተተኮሰብኝ ጥይት እንደሳተኝ በዝርዝር አጫ ትሻለሁ። ላንቺ ስል በዚህ ደረጃዬ የፈረስ ሴባ —ያውም ከፈረስም የዚህ ዓይነት ፈረስ—ሴባ ሆንኩኝ። ለሴላ ለምንም ስል አይደለም —ለአንቺው ስልነው። ነይ ልያዝሽና ውጪ።"

@OLDBOOKSPDF

ፋኖሱን ተቀበላትና ወለሉ ላይ አኖረው ።የጋቢናው መቀመጫ አንድ ጠባብ አግዳሚ እንጨት ነው ። ሬት እስክርሌትን ብድግ አድርጎ አግዳሚው ላይ አስቀመጣት። ወንድ ከሆኑ አይቀር እንዲህ ጠንካራ መሆን እንዴት መታደል ነው አለችና በልቧ ፣ የተሸበሸበ ቀሚስዋን ሳብ ሳብ አደረገች ።ሬት አጠገብዋ እስክለ ድረስ አሳቱንም ሆነ ጩኸቱን ወይም ያንኪዎቹን አትፈራም ።

ጋሪው ላይ ወጥቶ ተቀመጠና ልጓሙን ያዘ ።

"ውይ አንዴ ቆይ!" ብላ ጮኸች። "የሬት ሰፊቱን በር ሳልቀ ልፈው!" ከት ከት ብሎ ጣራ የሚሰነጥቅ ሳቅ ሳቀና ልጓም መሳቢ ያውን ሳብ — እረገብ አደረገ ።

"ምን ያስቅሃል? በግነው የምትስቀው ?"

"ባንቺ ነዋ ። በሩን ቆልፈሽ ያንኪዎቹ ውጪ ሲቀሩ ታየኝ!" አለ ።ፈረሱ ያለፈቃዱ ቀሰስ እያለ ሮጠ ። ከመንገዱ ግራና ቀኝ ያለው መብራት ቢጫ ክብ ውጋጋን በራቁ ቁጥር እያነሰ ሄደ ።

* * *

ሬት ቀርፋፋ ፈረሱን ከፒኞትሪ መንገድ ወደ ምዕራብ ጠምዝዞ ኮረኮንቹ መንገድ ሲገባ ያ ቆሽቋሻ ጋሪ ብድግ ቁጭ ሲል ሚላኒን ከፉኛ አስቃሰታት ።ግራና ቀኝ ያሉ ጭለማ የለበሱ የዛፍ ቅርንጫፎች ከበላያቸው ተቆላለፈዋል ።ከግራና ከቀኝ ዝምታ የወረራቸው ቤቶች እንደሸማኔ መወርወሪያ አልም ይላሉ ።የየአጥሮቹ ነጫጭ ማገሮች በተርታ እንደተደረደሩ የመቃብር ሐውልቶች በደብዛዛው ብልጭ እያሉ ያልፋሉ ።ጠባቡ መንገድ ፈዛዝ ብርሃን ያለው አሸንዳ ሆነ ዋል ።ብቻ ፣አልፎ አልፎ በተሸፈነው ኮርኒስ ጭላንጭል ቀዳዳ፣ ፍም የመሰለው የሰማዩ እሳት ወላፈን ሰንጥቆ ሲገባ ፣ የአንዱ ጥላ አንዱን እየተከተለ ያበዱ ጣረ —ሞቶችን ይመስላል ።የጭሱ ሽታ ከጊዜ ጊዜ እየበረታ መጣ ።በወበቁ ትንፋሽ ክንፍ ላይ ተንጠልጥሎ ከወደከተማው ማህል የድምፅ ድብልቅልቅ መጣ ። ጩኸት፣ ከባድ የጦር ተሽከርካሪዎች ኳኳታ ፣ የሰልፈኞች የእግር ኮቴ አንድ ላይ ታጅሎ ይነዳል ። ሬት የፊረሱን ጭንቅላት ደሞ ወደ ሌላ አቅጣጫ መልሶ ሌላ መንገድ ሲገባ ፣ እንደመብረቅ አየሩን የሚሰነጥቅ የፈንጂ ድምፅ ተሰማና የነበልባልና የጭስ ሰማይ — ሰበር ርኬት ፣ ብው ብሎ በስተምዕራብ ወጣ ። "ይሄ የመጨረሻው ፣ ፈንጂ ማዓንጎው ባቡር ሲፈነዳ መሆን አለበት ።" አለ ሬት ዝግ ብሎ ። "ለምን በጪት ይዘው አልወጡም ጅሎች!—በቂ ጊዜ ነበራቸው እኮ ብቻ ለኛ መጥፎ ነው ። ከከተማው ዳር ዳር ውስጥ ውስጡን እየሄድን እሳቱና በዴክተር

@OLDBOOKSPDF

ጐዳና የሚሯትቱው የተሣከረ የህዝብ መንጋ ሳያገኘን ከከተማው ርቀን ወደደቡብ ምዕራብ ያለ አደጋ እንደርሳለን ብዬ አሰቤ ነበር። ነገር ግን ዞሮዞሮ የማሪያታን መንገድ ማቋረጥ ሊኖርብን ነው ። ከል ተሰላትኩ ያሁኑ ፈንጂ ማሪየታ አካባቢ ነው ። አልተሳካልንም ።''

''ታዲያ —ታዲያ በእሳቱ ማህል መሄድ ሊኖርብን ነው እንዴ ?''አለች አስካርሌት እየተርበተበተች ።

''በሻም ከፈጠንን ላይገጥመን ይችላል'' አለና ሬት ፣ ከመቀመጫው ብድግ ብሎ ዘለለና መጠነኛ ርቀት ያለው ጨለማ ውስጥ ሰመጠ።

ከሄደበት ሲመለስ በእጁ አንድ የዛፍ ቅርንጫፍ ይዞ መጣና ያለ ርህራሄ የፈረሱን ጀርባ ገረፈው ። ፈረሱ ሰውነቱን አስቆጥቶአያለክ ለክ ሮጠ ።ጋሪው ወደፊት ሲሳብ ብረት ምጣድ ላይ እንዳለ እንደሚ ታመስ ጥፊ አንገረገባቸው ።ሀዳኑ ዋይ ዋይ አለ።ዋድና ፕሪሲ ከጋሪው ጉንና ጐን ጋር ሲያላጋቸው ጮሁ ።ከሜላኔ ግን ምንም የሚሰማ ድምፅ የለም ።

ወደ ማሪዬታ ጐዳና ግድም ሲቃረቡ ዛፎቹ እየሳሱ ሄዱ ። ረዣዥ ሾሮሞቹ የእሳት ወላፈኖች ከሠንጋዎቹ በላይ ብልጭ እያሉ መንገዱንና ቤቶቹን ቀን በብርሃኑ ከሚታዩት የበለጠ ብሩህ አድርገው ያሳዩዋቸዋል ።እሣር እሣር የሚያክሉ ጥላምታቸውም ፣በአውሎ ነፋስ እንደሚ ውለበለብ የሚስሞጥ መርከብ የተቀዳደደ ድንኳን ፣ይርገበገባሉ ።

የአስካርሌት ጥርሶች ይንቀጨቀጫሉ ፣እሷ ግን ከመሸበርዋ የተ ነሳ አይታወቃትም ።የእሳቱ ወላፈን ፊታቸውን የሚገርፋቸው ቢሆ ንም በርዱዋት ትንቀጠቀጣለች ።ይሄ መቼም ምድራዊ—ሲኦል ነው። እውስጡ ነው ያለችው ።የሚንቀጠቀጠው ጉልበትዋ ባይከዳትና ዳግም ቢጠናሳት ኖሮ ከጋሪው ዘሳ ወደ መጡበት ጨለማ መንገድ እንደዕብድ እየጮኸች ተመልሳ ወደ ፕቲታት መመሸጊያ ቤት በሄደች ነበር ። ሬት ላይ ልጥፍ አለችና በሚንቀጠቀጡ ጣቶቿ ክንዱን ይዛ ቀና ብላ፣ እንዲያና ግራት፣ እንዲያቅፋትና ማረጋገጫ እንዲሰጣት ትማጠን ገባች። እላያቸው ላይ በሚፈስሰው የቀይ እሳት ጨረር ውስጥ ጥቁር ምስሉ ተጠርቦ ወጥቶ ስታየው ፣ አሮጌ ፍራንክ ላይ ያለ ቆንጆ ጨካኝና ያረጀ የሰው ምስል ይመስላል። ስትነካው እንደእሳት የሚያስፈሩ ብልጭልጭ ዓይኖቹን ወደ ሱዋ ዘወር አደረገ ። ለአስካርሌት ግን ገና ነበስ እየዘራ ያለ ፣ ጉቀት ያደረበትና ከሁኔታው ደስታን እንዳገኘ ሁሉ ይህን የሰቆቃ ገሃነም ያለቅሬታ የተቀበለ ሰው ነው ።

''ይሄውልሽ'' አለ እጁን ከረዣዥሾሞቹ ሽጉጥ ባንደኛው ላይ አድርጐ ።ማንም ሰው ነጭም ይሁን ጥቁር ወደ ጋሪው አካባቢ ከመ

@OLDBOOKSPDF

ጣና በአጯ ፈረሱን ደግፋ አለ ተኩበጠ ።ጥያቄ ከዚያ በኋላ እንጠይ ቀዋለን ።ግን በፈጠረሽ ተሳስተሽ በድንጋጤ ፈረሱን እንዳትገይው።"

"እኔ...እኔ እኮ ሽጉጥ አለኝ ።" አለች በማንሾካሾክ ፣ መሳሪያውን በእጅዋ ጨብጣ ። ሁኔታዋ ሞት ፊት ለፊት ቢያፋጥጣት እንኳን በጣም ስለምትፈራ ታታ መሳቡዋን የሚያጠራጥር ነበር ።

"አለሽ፣ ከየት አመጣሽው"

"የቻርለስ ነው" አለችው ።

"የቻርለስ ?"

"አዎ —የቻርለስ —የባሌ"

"ለመሆኑ በእርግጥ ባል ኖሮሽ ያውቃል ፤ የኔ እመቤት?" ብሎ እንሾካሾከና ለስለስ አድርጐ ሳቀባት ።ምነው ቀልዱን በተወና ኮስ ተር ቢል !ምነው ፈጠን ብሎስ ቢነዳ !

"ልጄን እንዴት ያገኘሁት ይመስልሃል ታዲያ?" አለችና ጠንከር ብላ ጮኸችበት ።

"እ ከባል በስተቀር ልጅ የመውለጂያ ሴላም ዘዴ አለኮ"

"ዝም አትልምና ፈጥነን እንሄድም?"

በልጓም ፈረሱን ኮለኮለና ወደ ማሪየታ መንገድ ሲያመራ አሳት ያልነካው አንድ ቤት አገኙ ። "ፍጠን!" በአዕምሮዋ ያለው ቃል ይኸው ነው ። ፍጠን! ፍጠን ብቻ!

"ወታደሮች!" አለ ።

ከሠራዊቱ ተገንጥለው የቀሩ ወታደሮች የማሪየታን መንገድ ይዘው ፤ በተቃጠሉ ፣ ሀንጻዎች ማህል እንደቀንድ አውጣ እየተሳቡ ፤ ድክምክም ብሏቸው ፤ ጠመንጃቸውን እንደነገሩ አንከርፍፈው ፣ አንገታ ቸውን ደፍተውና ለመፍጠን አቅም አንሱዋቸው እየተገለፈለፉ ፤ ከማራና ከቀኝ ዛፎች ሲገነደሱ ደንታ ሳይሰጣቸው ፣ ጭስ ቢያፍናቸው ሳይገ ዳቸው ፤ እየተጥመለመሉ ይጓዛሉ ። ሁሉም የተበጫጨቀና ብትን ትኑ የወጣ ልብስ ከመልበሳቸው የተነሳ ወታደርና መኮንኑ ፣አለቃና ምንዝሩ አይለይም ። ያው ልዩ ምልክት ትከሻ ላይ ከሴለ በቀር ። ሁሉም ባዶ እግራቸውን ናቸው። ወይ እጅ ወይ እራስ በነተበ ፋሻ ተጠ ቅልሎ እዚህም እዚያም ይታያል። አንገታቸውን እንዳቀረቀሩ ወደ ግራም ወደ ቀኝም ዞር ብለው ሳያዩ በፀጥታ ከመሄዳቸው የተነሳ ኩቴያቸው ባይሰማ ኖሮ ጣዕረ — ሞት ይመስላሉ ።

@OLDBOOKSPDF

"በደንብ እዩያት" አለ የፎሉ በተባለ ድምፅ "ሰልጅ ልጆችሽ የታላቁ አላማ ተዋጊዎች ሲያፈገፍጉ ማየትሽን እንድትጠብቂ አጠንክረሽ አስተውያቸው።"

ወዲያው ከመቅጽበት ጠላችው።ከጥርሃትዋ ሁሉ ባየለ ጥርሃትዋን እንደትንሽ ነገር ባሳነሰ ጥላቻ ጠላችው።የሱዋ ሕይወትም ሆነ ከጋሪው ጀርባ ያሉት ሰዎች ሀይወት በእሱ ጫንቃ ላይ ያለ ቢሆንም እንኳ በእኒህ በተጠላቆሉ ሰዎች ሲያፌዝ ስታይ ክፉኛ ጠላችው። ስለሞተው ቻርለስ አሰበች።ሞቶ ሊሆን ስለሚችለው አሽሌይም አሰበች።ቆራጠቹንና ጀግኖቹን በየመቃብሩ የተኙ ልጆች ሁሉ አሰበች። ግን እሷ አራሷ ጅሎች ናቸው ትላቸው እንደነበር ረሳች።

ለመናገር ባትችልም ትኩር ብላ ባየችው ቁጥር ጥላቻና ምሬት ባይኖችዋ ላይ ሲነዱ ይታያሉ።

የመጨረሻዎቹ ወታደሮች ከጥል ሲያልፍ አንድ ትንሽ ደቃቃ ሰው ከሁዋላ የጠመንጃውን ሰደፍ መሬት ለመሬት እየጐተተ አመነታና ቆመ።በዛ በፈዘዘና በቀዘቀዘ መልኩ የሀልም ተንሸራ መስሎ ሌሎቹን ከሁዋላ ሆኖ አያቸው።እንዶ እስካርሌት አሟር ነው—ቀጫጫ። ከትንሽነቱ የተነሳ ቁመቱ ከጠመንጃው ጋር እኩል ነው።መክራና ጉስቁልና ያቸረቸፈው ፊቱ ጪም አልባ ነው።አሥራ ስድስት ዓመት ቢሆነው ነው፤ አሰች እስካርሌት በልቧ።ከከተማው ጠባቂዎች ወይም ከትምህርት ቤት ጠፍቶው ሠራዊቱ ውስጥ ከገቡት አንዱ መሆን አለበት አለች በሀሳቡዋ።

ትኩር ብላ ስታስተውለው የልጁ ጉልበት ሽበርክ አለና ተገለፍጦ ከአቡዋራው ተደባለቀ።ታል ሳይተነፍሱ ሁለት ሰዎች ከሁዋለኛው ረድፍ ተለይተው ወደሱ መጡ።አንደኛው ጢሙን እቀበቶው ድረስ ያንገረገገ ጥቁር ረዥም ነው።ቀስስ ብሎ የወደቀውን ልጅና የራሱን ጠመንጃ ለዓደኛው አቀበለው። ከዚያ አንከበከበና ልጁን እትከሻው ላይ በቀላሉ ጫነው።ከሚያፈገፍገው ሠራዊት ሁዋላ ጓላ ተሸክሞ ትከሻው በጭንቀቱ ጉበጥ ብሎ ሲከተል፤ ልጁ፤ ታላቆቹ እንደተቆጠት ሕፃን፤ አኩርፎ በደካማ ድምፁ "አውርደኝ! የተረገምክ! ልቀቀኝ በእግሬ እሄዳለሁ!" ብሎ ጮኸ። ጢማሙ ሰውዬ ግን ቃልም ሳይመልስ እመንገዱ መጠምዘዣ ሲደርስ ላይን ተሰወረ።

ሬት ልጓሙን በእጁ ረገብ አድርጐ እንደያዘ በጉጉትና በስጋት ትርዒቱን እያስተዋለ ሪጋ ብሎ ተተምጧል።

ወዲያው ከጐናቸው ዛፍ እየተገነደሰ ይወድቅ ጀመር።እስካርሌት፤ ጥላው ሥር ከተቀመጠበት ቤት ጣራ ሦስት የመሰለ የእሳት ነበልባል

@OLDBOOKSPDF

ወደ ሰማይ ሲጮሁ ነበር ። ከዚያ ከሚሄዱ ወፎችና የጠር ሜዳ ባን ዳሪዎች በአሳት እየተለበለቡ ወደ አየር ጭሱ ።ጭስ አፍንጫዋን አቃ ጠላት ። ዋድና ፕሪሲ ያስላቸው ጀመር ። ሀዳትም ልጅ በትንሹ እንዳ ትሙ አስነጠሰው ።

"አ... ውይ እምላክ ነፌት በፈጠረህ !አብደሀል እንዴ ፍጠን እንጂ ኧረ ፍጠን !"

ፌት ምንም አልመለሰ ።ብቻ ከዛፍ የቆረጠውን አርጩሜ መከ ረኛው ፈረስ ላይ ያለ ርህራሄ ቢያሳርፍበት እንስሳው ወዴት ዘለለ ። ፈረሱ ባለው አቅሙ እየሮጠ በማሪያታ መንገድ ገሰገሱ ።

ከፌት ሰፈታቸው ባለው የእሳት አሸንዳ ግራና ቀኝ ያሉት ሀንጪ ምች ቦጣ ብልጭ ይላሉ ።ያ ጠባብና አጭር መንገድ ወደ ኮረኮንቹ መንገድ የሚያወጣ ነው ።በዚህ መንገድ ነጮዴ ።ከያርዘን ቦሐይምች የፈካ ብርሃን ዓይናቸው ላይ ይንቀለቀላል ።ሙቀቱ ቆዳ ይልጣል ። ወላፈኑ ይንጣጣል ፡ያስነጠሳቸል ፡እንዴ ከንዱ እየተላጋ ይጮሃል ። የእሳት ማን በል ይተምማል ።ለማያልቅና ጊዜ ሰማይስካው ጊዜ እንዳስንጋ በሚ ጋረፍ ወላፈን ማህል ሄዱ ሄዱና አሁን ደግሞ ከፈል ጭስማ ዋጣ ቸው ።

እንዲሁ ጉያቡ አባቡሩ መንገድ ሲገቡ ፌት በጥንት አለንጋ ውን ይጠቅም ጀመር ።ፊቱ የተበሳጨና ያለበትን የረሳ ይመስላል ። ሰፊ ትከሻውን ወደፊት አስቀድሞና አገጩን አሹሎ ሲሄድ አዕም ርው ውስጥ የሚገለባው ሃሳብ ያላስደሰተውም ይመስላል ።የእሳቱ ወበቅ ላብ በጉንጩና በጆሮ ግንዱ ያወርድበታል ። ኤሱ ግን አል ጠርገውም ።

ከአንድ መታጠፊያ ወደ ሴላ ፡ ከአንድ ጠባብ መንገድ ወደ ሴሳ እያሉ አስክርሌት ትዕግስቷን አጥታ በስንት መከራ የነበልባሉ ማስን ምገም አጓላቸው ቀረ ።አስካሁን ድረስ ፌት ቃል አልተነፈሰም ። እያለፈ እያለፈ አለንጋውን ያወናጭፋል ። የሰማዩ ቀይ ቀለም እየሰፋ ከስሞ ለአስፈሪው ጭለማ ቦታ በመልቀቁ አስካርሌት ፈራች ። ተንገፖረገ ረች ።ስለዚህ ፈገም ፡ይሁን ሳቅም ይሁን አረ ለምን ስድብ አይሆ ንም ብቻ ንግግር ትፈልጋለች ።እሱ ግን ምንም አልተናገረም ።

ይናገርም ዝምም ይበል አጠገቡዋ መሆኑ ግን ትልቅ ድጋፍ፣ ትልቅ ምኞት ሆንዋታል ።ከጐንዋ አንድ ሰው መኖሩ ፣ ዘመም ብላ የምትደገፈው ፣ ጠንካራ ከንዱን የምትመረኩዘውና በእጇና በስም — አይጠሩው አስደንጋጭ ሽብር ማህል ጋሻ ጀግሬ እንደሆነላት የምታ ውቀው ሰው መኖሩ ብቻ ፣ በጣም የሚያስደስት ነገር ነው ።

@OLDBOOKSPDF

"ውይ ሬት" አለች በሹክሹክታ ክንዱን እንቅ አድርጋ ይዛ። "እንተ ባትኖር ምን ማድረግ እንችል ነበር? ሠራዊቱ ውስጥ አለመግባትህ ደስስ አለኝ!"

እራሱን ዘወር አድርጐ ክንዱን በሚያስለቅቅና በሚያሸማቅቃት አስተያየት አያት። በዓይኖቹ ውስጥ ምንም የፌዝ መልክ አይታይም። እርቃናቸውንና ንዴትን ያዘሉ እንዲሁም ብስጭት የለበሱ ናቸው። ከንፈሩን አጣመመና ፊቱን ከሱዋ አዞረ። ለረዥም ግዜ ባልደፈረሰ ፀጥታ ውስጥ ሲጓዙ አልፎ አልፎ የሀጻኑ ድምፅና የፐሪሲ ሹክሹክታ ከመስማቱ በቀር ሙሉ ዝምታ ነው። እስካርሌት የፐሪሲን ማንኳረፍ እስከምትችል ታግሳ ታግሳ ቢቸግራት ዞራ ቆንጠጠቻት። ፐሪሲ ደን ግጣ ጮኸች። ከዚያም የድንጋጤ ዝምታ ዋጣት።

በመጨረሻ ሬት ፈረሱን ወደ ቀኝ ጠመዘዘና ሰፋ ካለ ለስላሳ ሜዳ ገቡ። የቤቶች ድብዛዛ ቅርጽ ሩቅ ሰሩቅ እየታየ ሄደ። ጥቅጥቅ ያለው ጫካ ከግራና ከቀኝ እንደግርማ መሰለሰለ እያለ ያልፋል።

"እሁን ከከተማው ውጪ ወጥተናል። ወደራፍና ሬዲ የሚወስደው ዋና መንገድ ሳይነን" አለ ሬት አጠር አድርጐ ነልጓሙን ረገብ አደረገና።

"ፍጠን ፍጠን አታቁም!" አለች እስካርሌት።

"ቆይ እንጂ ፈረሱ ጥቂት ይተንፍስ።" ከዚያ ወደሱዋ ዞረና ለስ ለስ ብሎ "እስካርሌት እሁንም ያንን የአብድ ሥራ ለመሥራት ቆር ጠሻል ማለት ነው?"

"የቱን የአብድ ሥራ?"

"ይሄ ወደታራ እዘልቃለሁ ብለሽ ያሰብሽውን? መቼም ራስን የመግደል ያህል ነው። የስቲቭ ሊ ጦርና የያንኪዎቹ ሠራዊት በእንቺና በታራ ማህል ናቸው።"

እሪ ጉዴ! ወደ ቤቷ ላያደርሳት ፤ ይህን ሁሉ የመከራ ቀን ከተጉ ዋዙ በኋላ ወደታራ አላዘልቅሽም ሊላት ይሆን እንዴ!

"አዎ! ሬት ባከሀ እንፍጠን! ፈረሱ አልደከመም። እንሂድ!"

"ቆይ ትንሽ—ለአንድ ደቂቃ ያህል። በዚህ መንገድ የባቡሩን ሐዲድ እየተከተልሽ ወደ ጆንስቦሮ መሄድ አትችይም። ቀኑን ሙሉ በራፍና ሬዲ ላይና ታች እያሉ ወደ ደቡብ ሲዋጉ ነው የሚውሉት። በራፍና ሬዲ ውስጥ ላያልፍና ጆንስቦሮን ላይነካ የሚሄድ የከባድ መኪና ወይም የእግር መንገድ ታውቂያለሽ?"

@OLDBOOKSPDF

"እንዴ ፤ አዎ!" አለች አስካርሌት በጩኸት ። "ወደ ራፍና ሬዲ ከተጠጋን ከጆንስቦሮው መንገድ ርቆ እየተጠማዘዘ ውስጥ ውስጡን የሚሄድ ኮረኮንች መንገድ አውቃለሁ ። አባባና እኔ በዛ ብዙ ጊዜ እንመላለስ ነበር ። በማኪንቶሽ በኩል ብቅ ይላል ። ማኪንቶሽ ከታራ አንድ ማይል ነው እርቀቱ ።"

"በጣም ጥሩ ።ራፍና ሬዲን ያለችማር ማለፍ ትችያለሽ ማለት ነው ። ጄኔራል ሊ ዛሬ ከሰዓት በህ በኩል ለሚያፈገፍገው ሰራዊት ሽፋን ሆኖ ነው የሞለው ። ምናልባት እስካሁን ያንኪዎቹ እዛ አይኖሩ ይሆናል ።" የስቲቭ ሊ ሰዎች ፈረሱን ካለወሰዱብሽ በዛ ማለፍ ትችያለሽ ።

"እኔ ... እኔ የምችል አይመስለኝም — በዚያ እለፊ ነው የምትለኝ?

"አዎ አንቺ ።" አለ ድምፁን ሻክር አድርጎ ።

"ግን ሬት...አንተ...አንተ አትወስደንም ማለት ነው እንዴ?"

"አዎ ። እዚሁ ጥያችሁ መሄዴ ነው ።"

ወደ ኋላዋ ዙራ ፤ጥቁር ሰማያዊውን ሰማይ ፣ከጉንና ከጭን እንደ እሾር ቤት ማድማዳ ያነቁዋትን ዛፎች ፣ ጋሪው ጀርባ ያሉትን አስፈሪ ፍጥረታት ሁሉ ዙሪያ ገባውን አስተውላ ስታበቃ ፣ በመጨረሻ ወደ እሱ ፊት ዞረች ።እባዶለች ወይስ ጀሮዋ ነው?

ያሽሚጥጣታል ።በፈዛዛው ብርሃን ውስጥ ነጫጭ ጥርሶቹ ይታዩ ዋታል ።የዳሮው ፈዙ ደም ዓይኖቹ ላይ ተመለሰ ።

"እኛን ልትተወን ?...ወዴት ልትሄድ ነው?"

"የኔ ቆንጆ ከሠራዊቱ ጋር መሄዴ ነው ።"

በእርጅታም በንዴትም ተነፈሰች ።የሌላው ጊዜስ ይቅር እንዴት በአሁኑ ሰዓት ያፈሀል? ሬት ሠራዊቱ ውስጥ ሊገባ! —ጉድ እኮ ነው ። ሌላው ቢቀር በአታጥና በዲስኩሪኖች ጩኸት ተግፋፍተው ወደ ጦር ሜዳ እየሄዱ ፤ ህይወታቸውን በከንቱ የሚሰዉ ጅሎች ራሳቸውን በራሳቸው እንደሚገድሉና ጥበበኛ ሰዎች ግን ገንዘብ እንደሚያካብቱ ሲናገር አልነበረም እንዴ !

"እንደዚህ ስላስፈራራሽኝ ቆይ አላይህለሁ ብቻ አሁን እንሂድ።"

"የምሬን ነው የኔ እመቤት ። እስካርሌት ፤ በቆራጥነት ልከፍል ያሰብኩትን መስዋዕትነት በቅን መንፈስ ባለመቀበልሽ አስቀይመሽ ኛል ። ጀግንነትሽና ለታላቅ አላማችን ያለሽ ፍቅር የት ዶረስነ ፊቱን በጋሻዬ ላይ ወይም ወደ ጋሻዬ የማዞርበት ጊዜ ስለሆነ ይህ እድል

@OLDBOOKSPDF

እንዳያመልጥሽ ።ወዶ ጠርጥሮ በመጀመር በሙት ረሽም የጀግንነት ዲስ ኩር ማድረግ ስለምሽ ፈጠን ፈጠን እያልሽ ትናገሪ ።"

የተመለጠ ድምፁ በጀሮዋ ሰተት ብሎ ገባ ። በእሷ እያሾፈ ነው። ግን በራሱም እንደሚያሾፍ ነው የቀጠረችው ።

ስለምንድን ነው የሚያወራውን የሀገር ፍቅር ወኔ ፣ ጋሻ ፣ የጀግን ነት ዲስኩር የሚናገረውን ከልቡ መናገሩ እውነት ሊሆን አይችልም። በዚህ በጭለማ መግጊድ ላይ እንዳለች ለመሞት ከምታጣጥር ሴት ጋር ፣ አዲስ ከተወለደ አራስ ጋር ሕንዴት ይደብ ጥቁር ጋርና ከተደና ገጠ ሀጻን ጋር ጥሎሞት እንደሚሄድ አፍ እውጥቶ መናገር ፣ ያውም በጦርነት ፣በማጅራት መቺ ፣በያንኪዎች ፣በእሳት ማህል እንድትሸሽር ሲፈርድበት ፣ ምንም የሚታመን ነገር እይደለም ። እማዘር ያውቃለ እን ግዲህ ።

ጹሮ የስድስት ዓመት ልጅ ሳለች ከዛፍ ላይ ባጥጢሙዋ ተደ ፍቃ ነበር ።ታዲያ ያንን ህመሙ ከመሰማቱ በፊት የነበረ ትንሩሽ ማጣት ታስታውሳለች ። አሁን ወደ ሬት ስታይ የተሰማት ስሜት ልክ እን ደዛው ትንሩሽ የሚያላጣ ብድን የሚያደርግና አጥንቄ የሚያሩን ነው ።

"ሬት ትቀልዳለህ መሰለሽ!"

ክንዱን አቀፈች ። ክፍርሃት የመነጨ እንባዎችዋ እጁዋ ላይ ጠብ ጠብ ሲሉ ተሰማት ።እጅዋን ብደግ እድርገ ጥሩ አድርጉ ሳመዉ።

"ክልኩ በላይ ራስሽን መደድሽ እኮ የኔ ቆንጆ! ስለራስሽ መደበ ቂያ ስታበላበይ ኮንሌዴሬሲውን ረሳሺው ሠራዊቱ በመጨረሻው ሰዓት ላይ በአሥራ—አንደኛው ሰዓት ስደርስለት እንዴት እንደሚ ወደኛ ይታይሽ" አንድ—ዓይነት የማሸፍ ለዛ ድምፁ ውስጥ አለ ።

"ሬት" አለች በማሳዘን "እንዴት እንዲህ ትሠራኛለህ ለምን ድንነው ጥለሽኝ የምትሄደው?"

"ለምን?" የቆተታ ላቅ ሰቀ ። "ምናልባት በኛ በደቡባውያን ልብ ውስጥ ባለው የመከዳት መንፈስ ምክንያት ሊሆን ይችላል ። ምናልባ ትም ደግሞ አፍሬ በምንሥ—እፍረት ሊሆን ይችላል ፤ ማን ያውቃል።"

"አጥሬ አልክ በሐጥረት ልትሞት ይገባህ ነበር ። እዚህ ባዶ ሜዳ ላይ እኛን ያለ ረዳት ጥለሽን ስትሄድ ..."

"ውድ አሰካርሴት ! ረዳት አጥና ብቸኛ አይደላችሁም ። ማንም እንዳንቺ የቆረጠና ክፉኛ ራሱን የወደደ ረዳት አያጣም ። ያንኪዎቹ እንዲያገኙሽ እማዜር ይርዳቸው ።"

ከጋሪው ሳይ ዘሎ ወረደና ሰላምታ ሰጣቸው እንደጋለ እሰዋ መዳሰች በት ከፍል ወጥቶ

@OLDBOOKSPDF

"ሙሪጂ" ብሎ አዘዛት ።

ትከ ብሳ አየችው ።ተጠጋጥ በክንድና በክንዱ ማህል ይዞ አንጠ ልጥሎ ወደ መሬት ጹብ አደረጋት ።ጠበቅ አድርጉ ይዞ እየጮሁት ከጋሪው አርቆ መሰዳት ።አቧራና ጠጠር ነጠላ ጫማዋን ዘልቆ ሲቆረ ቁራት እግሩዋ ላይ ጉዳት ተሰማት ።የረጋው ወበቃማ ጭለማ እንደሀ ልም ዋጣት ።

"እንዲገባሽ ለማድረግ ወይም ይቅርታ አንድታደርጊልኝ አይደ ለም የምፈልገው ።ቢገባሽም ባይገባሽም ግድ አይሰጠኝም ።ምክንያ ቱም ከንቱነቱን ስመረዳትም ሆን ለራሴ ይቅርታን ለማድረግም አል ሸምና ነው ።እንዴህ ያለ ከጥቅም ይልቅ ክብርን መውደድ እስካሁን በእኔ ውስጥ መኖሩ ብስጭት ያደርገኛል ።ያም ሆነ ይህ ይቺ የደቡብ ምድር የእያንዳንዱን ሰው እርዳታ ትጠይቃለች ።ጀግናው አገረ ገዥ ይሀንኑ አልነበር የቋናገረውን ብቻ ምንም ይሁን ምን ወደ ጦርነቱ መሄዴ ነው ። "እሰና ከትከት ብሎ ሲስቅ የጫነው ማጫቱ አብሮት በመሣቅ ተቀበለው ።

"ውድ ሆይ ! ክብርን የበለጠ ባልወድ ኖሮ አንተን ባላፈቀርኩ ህም ነበር..." አለ ። ሁለገብ አባባል ነው ።እኔም አሁን ከዚህ ሌላ የተ ሻለ ነገር ማሰብ አልችልም ።እና ምንም እንኳን ባለፈው ወር ያንለት ማታ በረንዳው ላይ የተናገርኩት ሌላ ቢሆንም እስካርሴት አፈቅርሻ ለሁ ።"

ድምፁ ደስስ የሚል አርጋታ አለው ።እጆቹን ራቁት ከንዱዋ ላይ ሽቅብ አንሻተታቸው ። መቁት የተሞሉ ከንዶች ናቸው ።

"እስካርሉት በጣም ስለምንመሳሰል አፈቅርሻለሁ ። ሁለታችንም ክዳተኞች ነን ። ሁለተችንም አጭልግ ራስ ወዳዶች ነን —ወሮበ ሎች ። ስለዚህ አፈቅርሻለሁ ። ሁለታችንም እኛ ደህና እስከሆንና እስከተመቸን ድረስ ዓለም ቢገለባበጥ ደንታችን አይደለም ።"

በጭለማ ውስጥ ድምፁ መሰማቱን ቀጠለ እሷ ግን ምኑንም ልብ አትል ።ጭንቅላትዋ ሥራዩ ብሎ ማሰብ የያዘው ጥሎዋት የመሄ ዱንና ያንኪዎቹን ብቻዋን መጋፈጥዋን ብቻ ነው ።ጭንቅላትዋ አሁ ንም አሁንም "ጥሎኝ መሄዱ ነው ፤ ጥሎኝ መሄዱ ነው" ይላል ። ግን ምንም ሰሚትዋን አላገኘፈለው ።

ከዚያ ክንዶቹን በወገቡዋና በትከሻዋ ዙሪያ ጠመጠማቸው ። የትላልቅ ጭኖቹ ጠንካራ ጡቻዎች ጎላዋን ሲጫኑዋትና የኩቱ ቁል

@OLDBOOKSPDF

ርች ጠቆችዋን ሲቆረቁሩባቸው ትስማለች ። አንድ ልዩ ትኩሳት ያለው ስሜት በመስፈራራትና በመደናገጥ የተሞላ ስሜት እንደወራጅ ውሃ ጊዜውን ፣ቦታውንም ሆነ ሁኔታውን ጥርግርግ አድርጐ ከአዕምሮዋ አወጣው ። አተኮሳት ። ደስማት ። ምርኩዝም አስፈለጋት ። ከጨርቅ እንደተሰራ አሻንጉሊት ተሽመደመደች ። ስለዚህም የደገፉዋት ሞቃት ክንዶች በጣም ደስስ አሉዋት ።

“ባለፈው ወር ስለተናገርኩት ነገር ሃሳብሽን ለመለወጥ አትፈልጊም ማለት ነው ? ከአደጋና ከሞት የበለጠ የሚያሳፍር ነገር አይገኝም ። ጀግናና ቆራጥ ፣ ሁኚ እስካርሌት ። አንድን ወታደር ከመልካም ትዝታ ጋር ወደ ወር ሚዳ እንዴት እንደምትልኪው ፣ እንዴት ወደሞት እንደምትሸኚው አስቢ ።”

ወዲያው ያዝ አደረገና ይስማት ጀመር ።የከንፈር ዱሙ የአፍዋን ጸርና ጸር ጠቅጠቅ ያደርጋል ።ጊዜ ያሳቸው ይመስል ፣ያ ምሽት በሙሉ ትርፍ መዝናኛ ይመስል በሚያቃዋል ከንፈሩ ቀስስ እያለ ይስማታል። ቻርለስ እንዲህ አድርጐ ስሞዋት አያውቅም ።የታርሌትን መንትዮችም ሆኑ የካለቨርት ልጆች እንደዚህ እንጀትዋ እስኪላወስ ፣ እየሞቀችና እየቀዘቀዘች እስክትንቀጠቀጥ ስመሞት አያውቁም ።ሰውነቱዋን ወደሁዋላዋ አንጋሎ ከከንፈሩዋ ወርዶ በትሮሮዋ አድርጐ እጡት መያዢያዋ ድረስ እየሳማት ዘለቀ ።

“ጣፋጭ” አለ በሹክሹክታ “ጣፋጭ ነሽ”

በጭለማው ውስጥ ጋሪውን አየችው ።የዋድ ኮልታፋ ድምፅ ከወደጋሪው መጣ ።

“ማ...ማ! ዋድ ፈሳ !” አለ ።

በናወዘው ጭለማ አዕምሮዋ ፣ ቅዠቃዛው ሀሳብ እንደገና ዘው አለ ።ለጊዜው ረስታው የነበረውንም ነገር አስታወሰች ።ፍርሃትዋ መጣባት ።ሬት ፣ይሄ የተረገመ ራት ጥሎዋት ሊሄድ እኮ ነው ።ደሞ እኮ ይባስ ብሎ አሳማዬ እያለ የማይረባ ነገር እያወራ ይሰድባታል ። ጥላቻና ኀዬት ቤታቸውን ሠሩባት ።ሐሞትዋን አመረሩት ።ባንዴ ምንጭት አድርጋ ከአቅፉ ወጣች ።

“አንተ ከሃዲ!” ብላ ጮኸች ።ሌላ የከፋ ስድብ ለመፈለግ አባቷ ፎራልድ ሊንኪንን ፣ የማኪንቶሽን ቤተሰቦችና አልገራ ያለችውን በቅሎ ምን ብሎ እንደሚሳደብ አሰበች ።ስድቦቹ ግን በጭራሽ አደሙባት ፣አልመጣ አሉ ።“አንተ ወራዳ ፈሪ! አስቀያሚ !ከርፋታም !” አለችው ።ከዚህ የበለጠ የሚጐዳ ስድብ አጣችና እጅዋን ወደኋላ አግተ

@OLDBOOKSPDF

ርትራ ተንጠራራችና በተረፈው ጉልበቷ አፋ ላይ ደረገመችበት ። ወደኋላ አፈገፈገና ጉተተ በሩ ተከፈ ።

"አሃ" አለ በቀስታ ። ለአንድ አፍታ ተፋጥጠው ይተያዩ ጀመር ። በዘባዱ ሊተነፍስ ትሰማዋለች ።እሷም ብትሆን ስትሮጥ እንደቆየች ሁሉ ቁና ቁና ትተነፍሳለች ።

"ልክ ናቸው! ሁሉም ልክ ናቸው በፍፁም ጨዋ ሰው አይደለህም ! ሰው አይደለህም !" አለች ።

"ወይ የኔ ቆንጆ ፡ ያም ሲያንስኝ ነወ!" አለ ።

እንደሚስትባት ሰላወቀች ያው ሃሳብ እንደገና መጣባት ። "ሂድ! ሂድ በል! ቀዋሰ ፈጥነህ እንድትሂድ እፈልጋለሁ! ሂድ ሁለተኛ አይ ንህን ለማየት አልፈልግም ።ሬንጂ አናትህ ላይ እንዲወድቅ ምኞቴ ነው ። ሚሲዮን ቦታ ቢበቃትንህ ደስታዬ ነው ።እኔ..."

"ግድየለም የቀረውን ተይው ባገሬ ምድር ሞቼ ስወድቅ ወደ ወደፊት ሀሊናሽን ይፀፅትሽ ይሆናል ።" እየሳቀ ወደጋሪው ሲመለስ ታየሞለች ።ከጋሪው ገን ቁመና ሲናገር ድምፁ ይሰማ ጀመር ።የወጻ ጅነትና የአከብሮት አትጋገር ነው ። ሁልጊዜ ከሚሳኒ ጋር ሲያወራ በዚህ መልክ ነው ።

"ወይዘሮ ሚሳኒ" አለና ተጣራ ።

የፕሪሲ ድንጉጥ ድምፅ መልስ ሰጠው ።

"ኧረ በእግዚአብሄር ካፒቴን በትለር ! ወይዘሮ ሚሊ ገና ቅድም ደክመው የወደቁ ናቸው ።"

"አልሞትችም! ትተነፍሰ የለም"

"አዎ መተንፈስ ይተነፍሳሉ"

"እንዲያው እንዲሁ እንዳለች ብትቀጥል ይሻላል ።ነብሷን ካወ ቀች ይህን ሁሉ ስቃይ ችላ የምትቋቋመው አይመስለኝም ። በጥንቃቄ ጠብቂያት ፕሪሲ ።ፋሻና ፕላስተር ይሄውልሽ ። አሁን ከሆንሽው የበ ለጠ ጅል ላለመሆን ሞክሪ ።"

"እሺ ጌታዬ አመሰግናለሁ ።"

"እስካርሌት ደህና ሁኚ ።"

@OLDBOOKSPDF

ወደሱዋ ቦሮ እንደሚያናግራት ብታውቅም ፡ምንም አልተናገረች። ጥሰታዋ እንደቤትዋን ቆሰፈው ።ኩቴው በጠጠሩ መንገድ ላይ ኮርቻም ኮርቻም ሲልና ለአንድ አፍታ በሙለማው ውስጥ ትከሻው ብድግ ሲል አየሻው ።ከዚያ ላይን እየራቀ ተሰወረ ።ሄደ በቃ ።ኩቴውን ለጥቂት ጊዜ ትሰማው ነበር በኋላ ግን ቀስ በቀስ እየሳሳ ጠፋ ። ጉልበትዋ እየተብረከ ረከ ወደ ጋሪው መጣች ።

ለምን ሄደ፣ ወደ ሙለማው ለምን ተባ፣ ወደጦርነቱስ ለምን ይሄዳል፣ ሰው ላለቀለት ለሞተ አላማ ብሎ እንዴት ይሄዳል፣ ወደዚያ ዕብድ ዓለም ሄዶ ምን ይሰራል ፣ የሴቶች ወዳጅነትና የመጠጥ ትፍስህት የሚያረካው ሬት ፡መልክም ምግቡና ምቹ አልጋን የሚወደው ሬት ፡ሸጋ የሆነ ሐር በሐር ልብስና ምርጥ ቁሳ ጫማ የሚያማርጠው ሬት ፡ደቡብን እንዳንድ ነገር የሚጠላውና በሚጥጉት ሞቅኹ ላይ ይስቅ ይሰለቅ የነበረው ሬት ዝምን ሊያደርግ ይሄዳል፣ አሁን የተወለ ወለ ቦት ጫማውን መራራ መንገድ ላይ ሄደበት ።ረሃብ በሚይታክት አግሩ ወደ ሚገዝበት ፡ ቱበል ፡ ሥታይ ጉብቁልናና የልብ ደካም እንደ ተናክሽ ተኩላ ወደሚያስፈሰፍበት መራራ መንገድ ሄዶ ።የዚህ መን ገድ መጨረሻ ደግሞ ሞት ነው ። መሄድ አልነበረበትም ። እዚህ ደህን ነው የተጠበቀ ፡ህብታም ፡ የደለውና የተመቸው ነበር ። ነገር ግን ጥቅጥቅ ባለው እውር ጭለማ ፡ በቤትዋና በሱዋ ማህል ያንኪዎቹ ባሉበት መንገድ ላይ ብቻዋን ጥሎዋት ሄደ ።

አሁን ልትሰድበው የፈለገችው የነድብ አይነት ሁሉ ትዝ አላት፣ ግን አልፈ ፡ረፈደ ።ራስዋን ከቀረቀረው የፈረሱ ራስ ጋር ዘመም አድ ርጋ አስታከ ስቅስቅ ብላ አለቀሰች ።

@OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ 24

ከእናት ባሎት የተቆላለፉ ሀፍኛ ማሀል ድምት ብለው የጪት ፀሐይ ብርሀን ፍንጥቅጣሪዎች አይኑዋን ሲወጉዋት እስካርሌት ከእን ቅልፍዋ ነቃች ። ለትንሽ ጊዜ በአጉል አቅጣጫ በመታኛትዋ ደን ግጣ ድርቅ ብላ ቀረች ። የት እንዳለች ትዝ አላላትም ። ፀሐዩ አይኑዋን አሞበረበራት ። የተኛችበት የጋሪው አግዳሚ ጣውላ ጎላዋን ቆረቆራት ። አንድ ከባድ ነገር እግሩዋ ላይ ተጋድሟል ። ቀና ለማለት ስትሞክር ለካስ የከበዳት ቸኩም ዋድ ጉልበትዋን ተንተርሶ ተኝቶ ነው ። የሚለኢ አሜር አፍዋ ሲገባ ምንም አልቀረው ። ከጋሪው አግዳሚ መቀመጫ ሥር ፕሪሲ እንደ ጥቁር ድመት ተጠቅልላ ተኝታለች ። አራሱን ልጅ በእሷና በዋድ ማሀል ይዛዋለች ።

ይሄኔ ሁሉም ነገር ትዝ አሳት ። በጥጥነት ቀና ብላ ቁጭ አለችና ዙሪያውን ተመለከተች ። እግዚአብሔር ምሥጋና ይግባው ያንኪ እሚባል አይታይም ። የተያበቁበትም ቦታ አልተገኘም ። የሬት ኩቴ—ድምፅ ከጠፉ በውሃላ የተጓዙት መንገድ ሁሉ እንደ ሀልም ገብ ውል አላት ። ያ የማያልቅ ማታ ፡ዳገት ቁልቁለት የሞላው እንቅፋት የበዛው እግሯ እገው እያሉ ያረተረቱበት መንገድ ፡ ጥልቀት ካላቸው ከጫራና ቀኝ የነበሩ ጉድባዎች ውስጥ የጋሪው ጐማ መቀርቀሩና አሱን ገፍቶ ለማውጣት እያን ፕሪሲ ያዩት ፍዳ ሁሉ ፤ ፍንትው ብሎ ታያት ። የወታደሮች ኩቴ በሰማች ቁጥር ወዳጅ ይሁን ጠላት ባለማወቋ ጋሪውን ወደ ጫካውና ወደሚዳው ስንትና ስንት ጊዜ ጠምዝዛ አቆመች። በዛ ላይ ግልም ሆነ ማስነጠስ ወይም የዋድ ትክትክ ስሚያልፈው ሠራዊት ያሉበትን እንዳያጋልጥ የተሰቀቀችው መሰቀቅ ! ! አቤት የጨለማ መንገድ! ሰዎች እንደጣሪ ሞት የሚሳቡበት ፡ከእግር ኩቴ በቀር ኩሽታ የማይሰማበት ከኮርቻ ጨፍጨፍና ከቆዳ መተሻሸት በቀር ድምፅ የሌለበት መንገድ ! አቤት ያ ከፉ ሰዓት — በሽተኛው ፊረስ የሚያለከልከበት ፤ ፊረሰኛውና ተሽከርካሪው የሚራኩትበት የጭለማ ጊዜ ፡ትንፋሽ አጥታ በተቀመጠችበትና በክንድ ርቀት ልትነካቸው በምትችልበት ሁኔታ ባጠገብዋ ሰዎች ሲያልፉ ፡ሳብ በሳብ የሆነ ገላቸውን ጠረን የምታሽትበት ክፉ ሰዓት !

@OLDBOOKSPDF

በመጨረሻ በ[illegible]የመጨረሻው የስቲቭሊ መከላከያ በብ ለማፈግፈግ ትዕዛዝ የሚጠብቅበት ካምፕ ውስጥ እሳት ይበራል ።በታረሰው ሜዳ በሪያ ለአንድ ማይል ያህል ፤ ከሁዋላዋ የሚነደው እሳት ሳያንን እስኪጠፉ ድረስ ተጓዘች ። ቆይቶ ግን በንት ግዜ የተመላለሰችበትና የምታውቀው መንገድ በጭለማው ውስጥ ሊለወርባት ሲታ ያዛት ።ከዚያ መንገዱን ስታገኘው ደግሞ ፈረሱ ጉልበት ታጠፈና አልነቃነቅ አለ ። ከፕሪሲ ጋር ሆነው እንግ ፋህ ቢሉትም አሻፈረኝ አለ ።

ስለዚህ ልጓሙን እወለቅችና ወደሁዋላ ሄዳ እግሩን በርግታ ድክም በሁኔው ሁኔታ ተዘረረች ።እንቅልፍ አሸነፋት ። ዓይኖችዋ ከመዝጋታቸው በፊት በጨረፍታ የሚሰማት የሚለኔ ያክማ ድምፅ ጆሮዋ ገባ ። የለመና ድምፅዋ እንኳ በጣም ደክማ ነው ። "አስክርሴት ሙሃ ሳሳኝ እሾል ይሆን?"

"ምንም የለም" ብላ ሞልሳለት ታራሹ እፍዋን ሰትው ሳይሄዱ እንቅልፍ አያፋት ። አሁን ነጣቂስ ።እስሙ ሁሉ የረጋ ፣የፈላ አረንጓ ዴና ሠርታ ፣ የጠዋት ፀሐይን የተሳበሰ ነው ።እንድም መታደር በአካ ባቢው ዝር አይልም ።ርሃብታል ፣ሞርሙሩዋታል ።ጠምቱዋታል ፣አፍዋ ደርቋል ።እናም ያቺ በሐር ፈትል እንሰላ ማህል ካልተኛሁ የምት ለው ፣ያቺ በአርማብ ሳብ በተሠራ አልጋ ላይ ካልሆነ አይመቸኝም ትል የነበረችው አስክርሴት አሃራ እንደ ባሪያ ጥርብ ጣውላ ሳይ መተኛትዋ በጣም ነው የገረማት ።

በወሐዩ ጨረር መሀል አይኑዋን አየጨናቅረች ሚለኔን አየቻትና ድን ግጥ አለች ። ሜለኔ ድርቅ ብላ ነጭ ፍራ መስላ ተጋድማ ስታይ እስክ ርሴት የሞቱች መስሎዋት አመደዋ በነ አለ ። እውነትም የሞቱች ትመ ስላለች ።እንደአሮጊት ፊትዋ ተጨማድዶ ፣ ጥቁሩ ፀጉርዋ ምስቅልቅል ብሎ ተንጨባሮ ፤ ሕይወት አልባ ሙት ትመስላለች ። ብቻ በመጨረ ሻዋ በትትንፍስ ልቡዋ ክፍ ዝቅ ሲል ስታይ በእርይታ ተነፈሰች ።

ሜለኔ ሌሊቱን ሰትሞት አድራለች ማለት ነው ።

አስክርሴት እጅዋን አቅንድቡዋ በላይ አድርጋ ጨረሩን እየ ከለለች ሜለኔን ታስተውላለች ።ትላንት ማታ ሲሄዱ ውለው በዋድ የታጀበው የጠመርና የኩረኩንች መንገድ ፊት ለፊታቸው መታየት ሲጀምር እስው ደስፍ ካለ እርሻ ላይ አድረዋል ። "ወይኔ የማሎሪ ቤት ሰብ መንደር እኮ ነው የሚታየኝ" ብላ ልብዋ በደስታ ተሞ ልቶ ወዳጅትና ረዛቦች ማግኘትዋ ታሰበት ።

@OLDBOOKSPDF

ንፁር ግን እምቅ ላይ የተንጠለጠለ የሚመስል አርጭታና አር ጋታ በአርሻው ላይ ... ዋራጭ ... ሚሩን የፈረስ ኮቴ ፡ የተሸከረካሪ ጉማና የሰው እግር ተመላልሶ ስለረመረመው አዚያም አዚያም ተስባብሮ መጻድቋል ። ሚዳጠል አፈሩ ተሚጠ ቁጫጭን መንገድ ሠርቷል ።ወደቤቱ ብታይ ያ ንጭ ቪላ ሕንፃ ከቦታው ጠፍቶ ረሻም አራት ማዕዘናማ ጨንጫ የመሰረት ድንጋይ ካብና በሞስ በጠ ቆሩ ሸክላዎች ታይለ ነብስ የዘሩ ሁለት የጭስ ማውጫዎች በደራረቁና ጥላሸት በወረሳቸው ቅጠሎች ማህል ቆመው ነው ያሉት ።

አርድ አንቀጥቅጦ ንፁር ሁኖ አስተነፈሳት ።ታራንም አንዲሁ ወድማ ትቢያ ሆና ፣እንደሙት በድኖ ታማኞት ይሆን እንዴ ?

"ከሰዚህ አሁን ማሰብ አይገባኝም" አለች ፈጥና አራስዋ ለራሷ። "ይህንን እንጸለብ ማድረግ የለብኝም ደም ያስፈራራኛል ካሰብኩት ግን ከሱዋ ቁምዋር ሙጪ ልቡዋ እንደከበሮ በፍጥነት ድው ድው እያለ "ወደቤት ፍጠኚ፣ ወደቤት ፍጠኚ" ይሰል ።

ወደቤት መሄጓድ መቅጠል አለባቸው ።ከሁሉም በፊት ግን ምግ ብና ሙሃ ያስፈልጋቸዋል ።ዘሁሉይ ውታ ። ፕሪሊን ንቅንታ ቀ ሰቀሰዎት። ፕሪሲ ኢይኑጥን እያሻሸች ወደሱዋ ተመለከተች ።

"እረ በእግዚአብሔር እትዬ አስካርሴት ከተስፋዋ ምድር ካልደ ረስን በቀር የምንኖ አልመሰልኝም ንበር ።"

"ከሱዋ በጣም ሩቅ ነው ያልሽው" አለች ቆሻሻ ፀጉሩን ወደ ሁዋላዋ በእጅዋ እየሳገች ። ፊቱዋ እሹቅ መስሎዋል ። ሰውነትዋ ላብ በላብ ሆኑዋል ። የቆሸሸች ቅጥ ያጣችና ሰውነቱዋ በማጣበቁም መጥፎ መጥፎ የምትሸትት መሰላት ። ልብሶችዋ ለብሳቸው ስለምታድር ሙም ድድ ብሰዋል ።እንደዚህ ደክሞዋት አያውቅም በሕይወትዋ ። እንደ ዚህ መርሮዋት በጭራሽ እታወቅም ። ማታ ላይታወታት የተጐዱ ጡንቻዎቹዋ አሁን ስትንቀሳቀስ ያሚት ጀመር ።

ወደሚሊኒ ቁልቁል አስተዋለች ። ጥቂቱር አይኖችዋ ተከፍተው የሀመምተኛና ትኩሳት ያስፈጠጣቸው ከሥር ከሥር ማዲያት የወረ ሳቸው ሁነዋል ።በመከራ ከንፈሮችዋን አልላቃ "ውሃ" አለች ።

"ፕሪሲ በይ ተነሺ ወደጉድጓዱ ሄደን ውሃ እናመጣለን" ብላ አዘዘቻት ።

"ግን እትዬ አስካርሴት ፣ ምናልባት እዛ አካባቢ ሰው ሞቶ ያንኪ ዎቹ ሊኖሩ ይችላሉ እኮ !"

@OLDBOOKSPDF

"ከዚህ ጋሪ ላይ አትውረጂና ዛሬ አሳርሺን ነው የማሳይሽ ።" አለች አስካርሌት ለመሣት ፍላጎት ላይኖራትና ተንሸራታ ከጋሪው ወርዳ ።

ከዚያ ቀስ ፈረሱ አለበች ።እሪ በፈጣሪ ነማታውን ሞዮስ አድሮ እንደሆነ! ሐንሞን ስትፈታለት ሊምት ደርሶ ነበር ።ጋሪውን ሁራሂዳ ብታየው በጉጉ ተጉተዋል ። መቼም ሞቶ ብታገኘው እግዚአብሔርን እረግማ ራሷም በሞተች ነበር ።ዘመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ውስጥ ይህን ያረገ ሰው አለ ።እግዚአብሔርን ረገመ ።እሱም ሞተ ።ያ ሰው ምን እንደተሰማው በደንብ ታመቃት ።ይሄኛው ፈረስ ግን አልሞተም — ቁና ቁና እየተነፈሰ ህመምተኛ ዓይኖቹን ግማሽ በማሽ ከፍቶ በህይወት ይታያል ።እንግዲህ ሰአሉም ቢሆን ጥቂት ውሃ ይጠቅመዋል ።

ፕሪሲ ያለፈቃድዋ ከጋሪው ወርዳ የአካርሌትን እግር ተከትላ መንገዱን ይዘው ሄዱ ።ድምጣማጡ ከጠፋው መንደር በስተጀርባ አመዱ የቀረው የበፈያሞች መንደር ጭር ሳሙ ብሎ ዛፍ የነበ ዘው በረሀ መስሎዋል ።ዘዚህ መንደርና ጭስ በጠጡት የመሠረት— ደንጊያዎች ማህል የውሃ ጉድጓዱን አገኙ ።ባልዲው አሁንም በገመድ እንዲተንጠለጠለ ጅው ብሎ ጉድጓድ ውስጥ ወርዷል ።ገመዱን ወደ ላይ እየሳቡ ሲጠጡዋቸው ከሁል የመነለው የጠራ ውሃ ባልዲውን ሞልቶ ከሙለጣው ጉድጓድ ብቅ አለ ። አስካርሌት ከንባልዲው ወደ አፍዋ አስጠግታ ስትጭነጨው ታላቅ ድምፅ አስኪፈጠር ድረስ ጉርጉሮ ጉርጉሮ ስታደርግ ውሃው ከላይ አስክታች መላ ሰውነትዋ ላይ ፈሰሰ ።

ፕሪሲ ከፍቶዋት "እኔም ጠምቶኛል እትዬ አስካርሌት" ብላ የሌሎችን ችግር አስከታስታውሳት አስካርሌት አላቋረጠችም ።

"በይ የተዳጠረውን ፍቺና ባልዲውን ወዲጋሪው መስደሽ ትንሽ ስጫቸው ።የተረፈውን ለፈረሱ ስጪው ። ወይዘሮ ሜላኒ ልጁን ማጥ ባት እንዳለባት ረሳሽ እንዴ! ይራባል እኮ ።"

"ቆይ እትዬ አስካርሌት ፡ ወይዘሮ ሜላኒ ምንም ወተት የላቸውም። ደሞ ምንም አይኖራቸውም ።"

"በምን አወቅሽ?"

"የአሳቸው ዓይነት ብዙ አይቻለሁዋ ።"

"ከኔ ጋር ሁለተኛ እንደዚህ ያለ ነገር እንዳታወሪ ። ስለልጅሽ አውቃለሁ በትይ ቆይተሽ ትላንት ጉድሽ ታየ ። በይ ፈጠን በይ አሁን እኔ የሚበላ ነገር ልሂድና ልፈልግ ።"

@OLDBOOKSPDF

በዛፎቹ ሥር ጥሩት ፍሬዎች ከማግኘትዋ በቀር ልፋትዋ ሁሉ ከንቱ ነበር ። ዛፎቹ ሁሉ ፍሬዎቻቸውን ተራቁተዋል — ወታደሮች እዚህ ነበሩ ማለት ነው ። ከመሬት የለቀመቻቸውም ቢሆኑ አብዛኛዎቹ የበሰበሱ ናቸው ። ደሀና ያዘናዎቹን ለይታ በቀሚስዋ ታቅፋ በነጠላ ጫማዋ ጠጠር እየነዳ ፡ ለስላሳ ለስላሳውን መንገድ እየመረጠች ተመለሰች ። ምንው ትላንት ግታ ጠንክር ያለ ጫማ ብታደርግ ኖሮ የፀሐይ ባርኔጣዋነስ ብታደርግ ምን ነበረበት ? እሚበላስ ብትይዝ ? ጅልኮ ነበር የሆነችው ። ግን ሬት ያስብ በታል ብላ ነበረ ።

ሬት ነገና ስሙን ስታውቅ እንግሸግሻትና ቱ ብላ ወደ መሬት ተፋች ። እንዴት ጨላችው ! ምን ያለ የሚያስጠላ ሰው ነው የሆነው ! ደም አውላላ ሚዳ ላይ ሲሰግት ዝም አለችው — እርግጥ አሳሳሙን ፈቅዳዋለች ። ትላንት ጠፈጥ አድርጓት ነበር ። ዉ... ምን የማይረባው ነው አሱ !

ተመልሳ ስትመጣ ፍሬውን አከፋፈለችና የተረፈውን እጋሪው ውስጥ ዘረገፈችው ። ፈረሱ በእግሩ ቆሟል ። የጠጣው ውሃ ግን እምብዛም ተሃድሶ አልሠነውም ። በቁን ስታየው ከማታው የባሰ ጉስቁላ እንስሳ ሆነ ። የጀርባው አጥንት እንደአሮጌ ላም ሁሉ ግጥጥ ብሏል ። ጉድኑ ምርጊቱ እንደለቀቀ ማገር ተደርድሮ ይቆጠራል ። ለመንካትም ቀፈፋትና ልጓሙን ስታጠልቅለት ሁሉ ራቅ ብላ ነው ። ግመዱን እቆ ውስጥ ስታስገባ ጥርስ የሚባል ለበስመኣብ ወልዱ እንደሌለበት አየች ።

እንደ ጋሪዎቹ እንደከረብታዎቹ ሁሉ ኣርጅት ብሏል — የነሱን ያህል ነው ዕድሜው ! አይ ሬት ፡ ከሰረቀ ምነው ደሀናውን ቢሰርቅ ?

መቅመጫውን በቦታው አስተካክላ ሁለቱን ተወርዋሪ እንጨቶች በፈረሱ ግራና ቀኝ አወላ አሰረች ። እንደመጮህ ብሎ መንገድ ጀመረ ። ወደ መንገዱ ስታስገባው መንቀርፈፉን ቀጠለ ። አዬ ! ከሱስ በእግርዋ ብትሄድ ያፈጥናታል ። ለሜላኒ ፡ ለዋድ ፡ ለአራሱ ልጅ ብላ ነው እንጂ ወይኔ ! እንዴት ሮጣ እቤቷ በገባች ነበር ! ወደእናቷና ወደታራ በሚያደርሳት መንገድ ሁሉ ሳታርፍ በሮጠች ነበር !

አሁን ካሉበት ቦታ ታራ አስራ አምስት ማይል እንኳ አይርቅም ግን ይሄ ኮስማና ፈረስ በሚራመደው ዓይነት ቀኑን ሙሉ ሊፈጅባቸው ነው ። ምክንያቱም እሱን ለማሳረፍ በየግዜው መቆም ይኖርባቸዋልና ነው ። ሙሉ ቀን ! ምን እዳ ነው ! የሚያበራውን ቀይ መንገድ ፡ ተሽከርካሪዎችና አምቡላንሶች እዚያም እዚያም የበዳይሱትን ቀይ መንገድ ቁል ቁል ተመለከተች ። እቤት ፡ ታራ ደሀና መሆኑዋንና ኤለን መኖሩዋን

@OLDBOOKSPDF

ለማወቅ ገና ሰዓታት ይፈጀል ። በዚህ በታሀሳስ የፀሐይ ሐሩር እየነደ ደሹ ይሄን ጉዞ ጨርሳ ልመጣላቸል ገና ሰዓታት ያስፈልጋሉ ።

ወደ ሚለኒ መለስ ብላ የህመምተኛ ዓይኖቹን ከፀሐዩ ለማጸነ ጨጥና አየቻትና የራስ ሽፋኑን ላሳ አድርጋ ሕመጥታ ለፕሬሲ ሰጠቻት ።

"እፊቲ ላይ አድርጊላት ፀሐዩን ያክላልላታል ።" የሱዋን የራስ ዋን ያልተሸፈነ ሙንቅላት ፀሐዩ ከአናት እየመታት" ነው ጪ.. ይሄ ቀን ከማለቱ በፊት መቼም እንደ እንብ ላል ነው የምሰባብረው" አሰች ።

በእድሜዋ ያለ ባርኔጣ መዶም ያለነጠላ በጠራራ ፀሐይ ወጥታ ፣ ለብሳለ አጅዋን ቢያማትም የፈረስ ልጓም ያለንጉቲ ይዛ በሙራ አታውቅም ። ሆኖም አሁን በቆሽዋ ጋሪ ቆሽዳ ፈረስ እየ ነዳች ቁሽሽሽ ብላ ፣ ሳብ በሳብ ሆናና ፈሀብ አንጀትዋን አያሄክት ግልጥጥ ላለ የሐይዩ ሐሩር ሳጋለጠች ።ያለንዳች ረዳት በቀ ወረረች ከተማ ማዘል አንዱዋንኛ አውጣ ቅሳባለች ።ወይ ጉድ ከጥ ቂት ሳምንታት በፊት አቡ በማም ደሀን አብሮችዘበጥቂት ቀናት በፊት እቡ ነው እያንዳንዱ በው አትሳንታን ማን ይነክታል ፣ጀርሚያን ማን ይወርራታል ይል የነበር የነገር ማን ከአራት ወራት በፊት ከወደሰሜን ምዕራብ ይነፍስ የነበረው ንፋስ ፣ አውለጎራስ ቀላቅሎ ነጮድጓጮ ሆነና አለሙዋን ሁሉ ጠራርጎ ዘሰጎም ከተዋመጠቸበት ቤት አስወ ጥቶና መጠጊያ አሳጥቶ ፣ይወን በመሰል ባዶ ምረድ በዳ ውስጥ ጣላት።

ታራ አሁንም ቅኖር ይሆን ፣ ወይስ ታራም በጀርሚያ ላይ ካለ ፈሙ ከነፋሱ ጋር በነጎች ፣ አለንጋዋን እፈረሱ ጀርባ ላይ ትወረው ራለች ።ወደፊት ፈጥኖ እንዲሄድ ሙጭ ትለዋለች ።የጋሪው ጉማዎች እንደለከረ ሰው ከወዲያ ወዲህ ይንገዳገዳሉ ።

* * *

አየሩ ሞት ሞት ይሸታል ። በከሰዓት በኋላው ጨረር ውስጥ ለታይ አረንጓዴው አሰዋትና አጠንከራ ታብታቁሰው የነበረው የአርሽ ሚለ ሳሙሳ እርጭ ብሎ አስነርሉትን በልፀ ሽብር ነዛባት ።እያንዳንዱ ቃሬውን የቆመ በት ውያንዳንዱ በነሰለ በወደመ ፍርስራሽ ላይ የተገ ኑረ ያጭስ ማውጫ ባለፉት ቁጥር ያስፈራት ጀመር ።በሕይወት ያለ ሰውም ሆነ እንሰሳ ለምልከት እንኳ አይታይም ።እርግጥ የሞተ ሰው የሞተ ፈረስ መሄም በቅሎ በየመንገዱ ጻር ተዘርር አብጠ ዝምብ እንደወረረው አይተዋል ።በሕይወት ያለ ግን አንድ አላዩም ። የሚግጡ ከብቶችና የሚዘምሩ ወፎች የሉም ። ንፋስ የሚያወሳውሳቸው ዛፎች አይታዩም ።በመንገዱ ከፈረሱ ኮቴና ከሚላኒ ልጅ ለቅሶ በቀር የዐ ጥታውን ኪላ የሰበረ የለም ።

@OLDBOOKSPDF

ገጠሩን የሚያስፈራ ቁጣ "እኩ ዝም!" ብሎ እንደተቆጣው ሁሉ እርም ብሏል ።እስክርሌት ድንዝዝ ብላ ከጣር በሁዋላ እንደረጋ የእናት መልክ ሬድን ጭው እድርጋ የክፉም ነገር አስባለች ።ዳሮ እምታውቀው ጫካ በጣረ ሞቶች የተሞላ መሰላት ። በሺ የሚቆጠሩ ሰምኮ ጀንስቦር አጠገብ በተኪያዬደው ወሚያ አልቀሞል ። ለወትሮው የነበሳት በሁሮሳዊ ፀሐይ አግድም በምታበራበት በዚህ ጫካ ውስጥ ፣ በማይንቀሳ ቀሱ ትጠሎች በተሞላው በዚህ ጫካ ውስጥ የጠላትም የወዳጅም ጣረሞት ዓይን ደም—ለብሶ ቀይ አፀፉ ተሞጅሮበት በከርክሳ ጋሪዋ ስትሄድ የሚያያት መሰላት ።

"እናቴ እናቴ"አለች በሹክሹክታ ።እነደምንም ብላ እናትዋጋ በደረሰች ብዙህ አንዲሆው በአማዚአብሔር ቱአምር ብቻ ታራ ደህና ሁና በዛሮች በታጀበው መንገድ ማህል ሄዳ ፣ የእናቷን ደማና ተወዳጅ ልጅ ብታይ ፣ የአናቷን አንኮብኮቤ የሞላባቸው እጅጉ ብትዳበስ ፣ የእና ቷን ቀሚስ ለጨብጣ ፊቷን እዙያ ሙሉ ብትቅበር ፣ እንዴት በተግሳን ልኝ ። እናቷ ምን መደረግ እንዳለበት ታውታለች ። ሜሳኒና ልጅዋን እንዳ ይሞቱ ትጠብቃቸዋለች ።አኪሀን ሁሉ አእምሮዋ ውስጥ የሚተራመሱ ትን ጥርዮችና ጣረ ሞቶች ታበርዳታለች ።ግን ፅኑ እናትዋ ታማለችነ ሞታም ሊሆን ይችላል ።

እስክርሌት በአለንጋዋ ጀርባ ጀርባውን እየመታች ፈረሱን ሂድ አለችው ።አሁን መሩጠን አለብቸው !! ይሆነን ወበቃማ ቀን ሙሉ በማያልቀው በማይዘለቀው መንገድ ላይ ሲድሁ ዋሉ ። ጥቂት ቆይቶ ይመ ሻል ።ደሞ በዚያ የሞት እኩያ በሆነ ብቸኝነት ሲዋጡ ነው ። ልጓሙን ጠበቅ አድርጋ ወሣ በጽጠረ እጅዋ ይዛ ሳብ— ረንበ እያደረገች የፈረ ሱን ግላ ስትጠቦጥበው እጅዋ አንደአሳት ተቃጠለ ።

አቤት የቃራንና የአለንን ክንዶች እንደናፈቀች ፣ አቤት እነዚ ህን ለጋ ጓንቃዋ ሊሸከማቸው የማይችለውን ማናምች—በሞት አፋፍ ያለችውን ሴት ኡየሚጀሽ የሚሄደውን ህዜን ፣ የራሷን የተራበ ልጅና ጥርኝት ያርበደበዳትን ኔግሮ —እኩሀን ሁሉ ሸክሞጅን ለማራገፍ ብት ችል። ሁሉም ጉልበትን ከአሏ ይሻሉ የመንገድ ምራን ከአሏ ይሻሉ ።የጀርዘ አጥንቷ የሆነውን ድፍረት ።ግን አሁን በለብዋ የሌለ ውን ፣ የጥንካሬዋ ምንጭ የሆነውን አቅሟን — አሁን ግን የነዳትን፣ እንድትለግሳቸው ይፈልጋሉ ።

የደከመው ፈረስ ለአለንጋውም ሆነ ለልጓሙ ሠልስ ሳይሰጥ እግሩን ይጉትታል ።ትንሽ ድንጋይ በስንት ጣር ያልፋል ።ካሁን አሁን ጉልበቱ ዝሎ የሚወድቅ ይመስላል። ድንግዝግዝ እያለ ምሽት ሲመጣ የረዥሙ ጉዞ ማለቂያ ተቃረበ ። የኩሪኮንቹንና የነብሁን መንግድ

@OLDBOOKSPDF

ትኩው መደዋናው አውራ ጐዳና ገቡ ብዘሀ መጪሀ ታራ አንድ ማይል ብቻ ነው የምትርቀው!

እዚህ አካባቢ የማኪንቶሽን ቤተሰብ ንብረት የሚያመለክተው የክምጠጠ ዛፍ በጭልሟው ውስጥ ገዝፎ ጥቁር ሰብሶ ይታያል። ትንሽ ራቅ ብላ ሀዋርክምቹ ዛፎች በተከበበውና ወደ አንገስ ማኪንቶሽ ቤት በሚወስደው ጐዳና ጋ ዝግ አያለች ትንሽች። ጭልማውን ሰንጥቃ ከማ ራና ከቀኙ ያረጁ ዛፎች ያሉባትን መንገድ አለፈች። ሁሉ ነገር ጨለማ ነው። በቤቱ ውስጥም ሆነ በሰፈሩ ጭላንጭል መብራት የለም። ዓይኑ ዋን አስጨንቃ ስታይ ያንኑ በዘሀ ከፉ ቀን ለትመለክት የዋለችውን አይነት ነገር አየች — ሁለትኛው ፎቅ ድምጥማጡ ጠፍቶ በዚሁ ላይ እንደመቃብር ሐውልት የቆመ የሚሰ ማውጫምኝና እንደዕውር አይን ማርማዳው ሰይ የተደመደመ የመስኮት አፎቶች።

"እዚህ ቤት ኮብለለ ሎሽች ያለችን ተለበት አጠራቅማ።

"በቶኮ"አለች ደግመኛ።

ፕሬሲ በድንጋጤ ጭምሩድ አድርጋ ያዘቻት። ዙር ብትል ፕሬሲ አይኑዋ ይቁለጨለጫል።

"እትዬ እስካርሌት አትመጪ፤ አብሽ ደግሜ እንዳትመሪ!" አለች በሹክሹክታ ድምፅዋ እየተቁረበረበ። "ምን እንዳለ አይታ ወቅም አቱ!"

"ወይ አምላኩ!" ብላ አሰበች እስካርሌት እየተንቀጠቀጠች። ወይ ፈጣሪ አውነትዋን አቱ ነው። ከእንዲህ ያለው ቦታ የሚወጣው ምን ይታወቃል!

ልጓሙዋን አርገበገበችና ወደፊትዋ ተሠገሠች። ዩማኪንቶሽን ቤት ማየት የተስፉዋን የመጨረሻ ሙጣጭ አንጠፈጠፈባት። በእሳት ጋይ ኋል ተወድሟል። ከእሱ እንደመጣቻው የእርሻ ቦታዎች ሁሉ ምድረ በዳ ሁኑዋል። ከዚህ ወዲያ እንግዲህ ታራ የማገሸ ሣይል ርቀት ላይ ፍት። ሠራዊቱ በሚጓዝበት በዚሁ መንገድ ሰይ ግማሽ ማይል ተጉዞ ታራ ይደረሳል። ታራም እንደሌለች መልጭ ወጥታለች። ሊሾ ሚለ! የምታገኘው ያረረ ሽክላና የማታ ከዋክብት የሚያበሩበት ጣራ የለሽ ማድማዳ ነው። ኤለንና ጄራልድ በንነው፤ ለጀገረዶቹ እሀትጅና ማሚ በንነው፤ እማሮዎቹ በንነው — የት እንደሆን እግ ዜር ይወቅ — ይሄ መእተኛ ዝምታም እነዚህን ሁሉ መሮዋቸው ነው የምታገኛቸው።

እንዴ እሱቲ ምን ልሁን ብላ ነውን እሱቲ ምን ቅጠጥ አድርጓት በዕውር፤ በድንብር ጉዞ ሚለኒንና ልጆዋን ጉትታ እዚህ ድረስ መም

@OLDBOOKSPDF

ጣር ! ምን ጅል ናት —ዓይን የላትም እንዴ ነየወሐዩ ሐሩር እክሰሎ አሳርሮሞሞ ከርከሣው ጋሪ እንደኳስ እያነጠራቸው የመጡት በዚህ ድምጥማጡ በጠፋ የታራ አፈር ላይ ስመሞት ከሆነ ፣የመሞት የመ ሞት ምነው እዛው አትላንታ ውስጥ ሞተው ባረፉ ?

ግን ያ አሽሌይ ሚላኒን እጅዋ ላይ ጥልባቃል ።"ሚላኒን እደራ" ብሏታል ። ጪ...ያ ልብ በሚሰልብ ሁኔታ ቲሳሰሙበት ቆንጆ የሰንበት ቀን ለአንዴም ሰሁሌም ሲለያት የጉሳሰሙት ሽጋ ቀን! "እሷን ልትጠብ ቂያት ታል — ችግቢልኛለሽ አይደል? ታል ግቢልኝ!" ሲላት እቪ ብላ ታል ግብታለታለች ። በአንዲህ ያለ ታል —ከዳን ለምን አራስዋን አሰረች? አሁማ አሽሌይ በንኖ ሊጠፉ ደርብ እሥር ሆነባት ።በዚህ ዛሁኑ ፣ ስውነቱዋ ሁሉ እልት ባለበት ሰዓት እንኩዋ ሚላኒንና በደክማ ድምፅ ፀጥታውን የሚያደፈርስውን ሚያው ሚያው የሚል አራስ ልጅ እንደ ጠላቻቸው ነገር! ግን የትም ልትጥላቸው አትችል ። አንዱ ታል ግብታ ለያ! ፕሪሲና ጥድ የሏ እንደሆኑ ሁሉ ሜላኒና ልጅዋም የኗ የራሷ ናቸውና ጉልበትዋ እስክልፈረሰ ቅኖሩዋ እስክልቆመ ድረስ ትግል ዋና ጥረትዋ እንሱን ለማትረፍ ይሆናል ። ያማ ባይሆን ኖሮ ሜላኒን ሆስፒታል እስገብታ እዛው አትላንታ ጥሏቸው በከዳቻቸው ነበር ። ያን አርጋ ቢሆን ኖሮ ደግሞ በዚህኛውም ሆነ በወዲያኛው ዓለም የአሽሌይን አደን ማየትና ሚስትህንና ልጅህን በባሰዳን ማህል ጥያቸ ዋለሁ ለማለት በሙራሽ ባልቻለችም ነበር ።

ዋ አሽሌይ ! ሚስቱንና ልጁን ይዛ መንገድ ለመንገድ ስትዋትት እሱ የታለ ዛሬ ማታ የት ጠፋ ታዲያ በህይወት ኖሮ ከርከ አይላ ንድ እሥር ቤት ትጥር ውስጥ ተጋድሞ ያስባት ይሆን? ወይስ በኩ ፍኝ መረርሽኝ የዛሬ ስንት ወር ሞቶ ከሌሎች የኮንፌዴሬሲው ወታ ደሮች ጋር አፈር ተጭኖት ይሆን ?"

ወዲያው አንድ ነገር ከአቅራቢያቸው ቁጥቋጦ ሥር ድምፅ ሲያ ሰማ ባለችበት አመድዋ ቡን አለ ።ፕሪሲ ድብልቅልቅ ያለ ጩኸት ሙሃ ሕፃኑ እሥርዋ እንዳለ መቀመጫው ሥር ተደፋች ።ሚላኒ እም ብ ዛም ሳትሸበር እጆዋን ዘርግታ ዐጸኑን በዳበሳ ትፈልጋለች ።ዋድ እይ ኑን በእጁ ሽጥኖ ለመሙህ እንኳ ፈርቶ ተቸማቆ ተቀምጣል ።ከዚያ እንሳቸው ያሉ ቁጥጋበዎች ተሰባበሩ ። አንድ ኩቴ እየረመረማቸው መጣና እምቡዋ የሚል ድምፅ እጀራቸው ገባ ።

"ውይ ለካ ሳም ናት" አለች አስካርሌት ፍርሃት ባሻከረው ድምፅ። "ለምን ነሆለል ትሆኛለሽ ፕሪሲ ፣ ህጻኑን መጫንሽ ሳያንስ ፣ ሚላኒንና ዋድን አስደነገጥሻቸው ።"

@OLDBOOKSPDF

"የለም ጣረ ሞት ነው" አለች ፕሬሲ የጋሪው መለል ላይ ፊቷን እንደደፋች ።

ሆነ ብላ ወደ ፕሬሲ ቦራ አስክርሌት በአለንጋው ጀርባዋን ላጥ አረገቻት ። ማንንም ከለደኳም የሚያንሳባትን ሰው መታገስ አትችልም ።

"ተነሽ ሀሞላ ! እንቺ ጅላንፊ ! ተነሽ ይህን አለንጋ በላይሽ ሳልጨርሰው !" አለች ።

ፕሬሲ እያማጠች አንገትዋን ቀስስ ብላ ጠምዛ ብታይ እሱን ትም ላም ናትና ። ቀይና ነው ቡሬ ላም ቀና ብላ ሰልሙጣ አይን በፍር ሃት ታያቸዋለች ።አላውን ከፈተችና እንደ ገና እምብዋ አለች ።

"ቁንዶታሌች ልበልህ የጨና ልጅሽት አይመስልም"

ጫኔ የጠቃ ማት ሞልቶ መታለብ የምትፈልግ ነው የመሰለሽ"

አለች ፕሬሲ ራስዋን እየዝነች ። "እንደውም ኦግርምቹ ወደ ጫኳ ነድተው የደበቁዋትና ከምንኪምቹ ያስመለጥዋት የማኪንቶሽ ላም ሳትሆን አትቀርም ።"

"ከኛ ጋር እንውሰዳትና ለሀኪኑም ትንሽ ወተት እናገኛለን ።" አለች አስክርሌት በፍጥነት በመወሰን ።

"እንዴት ልገወስዳት ነው እትዬ አስክርሌት ! ? ምንም ላም ይዘን ለመሄድ አንችልም ። አስካሁን ያልታለበች ላም ወተትዋም ጥቅም አይኖረውም ።ማትጥ ከመጠን በላይ ያብጥና ይፈነዳል ።ለዚህ ነው እምበዋ የምትሰው ።"

" ስለዚህ ጉዳይ ይህና አድርገሽ ስለምታውቂ አሁን ቁንሽና ልብስሽን አውልቀሽ ቀደሽ ከጋሪው ጋር አሰሪያት ።"

"እትዬ አስክርሌት ለአንድ ወር የውስጥ ልብስ አርጊ አላውቅም ። ያለችኝ ይኸው ናት ። እቺን ደግሞ ለማትረባን ላም ብዬ አልቀድድም ። ላም እላ — ክፍሌ አይደለም ፤ ለዛውም አይሆንልኛም ። ላሞች እረራ ለሁ እኮ ።"

አስክርሌት ልጓሙን ለቅቃ አስቀመጠችና የራስዋን ቀሚስ ወደ ላይ ጎትተች ። ከሥር የነበረው የውስጥ ልብስ ፣ አለኝ ከምትለው የመ ጨረሻው ቆንጆ ልብስና ያልተቀደደ ነው ።

ከወገቡ ላይ መርሬ ቁልቋን አስለቅቃ ወደታች ጎትታ በእግሩዋ በከ·ል አወለቀችው ። በሁለት እጆችዋ ውስጥ ጭምድድ አድርጋዋለች ። ይህን የመሰለውን ምርጥ ጨርቅ ሬት ነው በመጨረሻው የፅገዳ ዕቃ

@OLDBOOKSPDF

ማሸገር ሥራው ከነ በርፍ ጌው ክናሱ ይዘላት የመጣው ። ብትኑን ወርቅ ለመስሩት ሳምንት ፈጅቶባታል ።ጠንከር ብላ በቁርጠኛ ውሳኔ ስፈቱ ሥር በጥርስዋ ይዛ ጣራራ እድርጋ በቁጨት ስትተረት ረው እንድ ቀጭን ረዥም ክፍል አወጣችለት ። እንደነና በጥርሱዋ ስትስበወና በእጅዋ ስትቀደው ብዙ የተተለቀለ ጨርቆች እጅዋ ላይ ቀሩ ። ውሃ ቋጥረው በረኑዲትና ከድካም ብዛት በሚንቀጠቀጡት ጣቶቹዋ በደርበቡ ሠጥራ ሠራችው ።

"ይህን ቀንደዋ ላይ አሠሪ ብላ አዘዘች እስክርሌት ።" ፕሪሲ ፈራ ተባ አለች ።

"ኢትዮ እስክርሌት እሬ እኮ ላሞች እፈራለሁ ። አሬ እዘብት አጠ ላብ ደርሽም አላጠቅም ። የጣያ እረኛ ይማሮ አይደለሁም ። የቤት ባሪያ ነኝ ።"

"ምን እጽንድ የቂል ሚንሲል ነሽ ! ምን አይነድ ይማሮ ነሽ ! መቼም አባቱ ያለ ከሰራው ሁሉ መጥፎው አንቺን መጣዛክ ነው" አለች እስክርሌት ሰመናደድ እንኳ አቅም አንቧት ። "ከአንማዲሀ አጀን ክንሳሁ ይሄ አርመኖሚ አላይሽ ላይ ሳይሰባበር አልተውሽም ።"

"እም" አለች በለኗ "እማሮ" አልኳት እኮ ። እማማ በጥውም እን ዳህ ሊባል አትወድም ።"

ፕሪሲ እንዴ ወዶ ሳፍደው የአመሌቷ ፊት ፣አንዴ ወደምትጨ ዝው ላም ሳይታዋን አጥርጠረጠሯው ።መቼም ከሁለቱ ፣ ከአስክርሌት የሚመጣው አደጋ ያንሳል ። ስለዚህ የጋሪውን መደገፊያ የሙጭኔ ብላ ቆመች ።

ግትርትር ብላ አስክርሌት ከጋሪው ወረደች ። እያንዳንዱ እንቅስ ቃሴዋ ጠንቃቃነቱን ሚያድስ እያደረገ ያማታል ። ላም የምትፈራው ፕሪሲ ብቻ አልነበረችም ። እስክርሌት በጣም ገር የምትባለውን ላም እንኳ እንፍሰይማን እድርጋ ትፈራለች ። አሁን ግን ስጥቃትን ፍርሃ ትዋ ሳይሆን እንደመርግ የተሰለለባትን ታሳቅ ሥጋት ነው ጉዳዬ የምትለው ። እንደ እድል ሆኖ ላሟ እትናካም ። ለማዳ ናት ። እናም ባን ደኛው ሩንዱዎ ላይ ማለሪያዋን ስታጠልቅባት የሰው ልጆችን ጓደኛ ነትና እርዳታ የምትሻ ይመስል ምንም አላለች ። ሌላውን የግመዱን ሚዋ ቀጥቃጣ እጅዋ እንደቻለ ከጋሪው ጀርባ ጋር አሠረች ። ወደ መቀ መጪያዋ ስትመለስ ታሳቅ ሚሳቀት ወረራትና በደመነፍስ ተወነወ ዘች ።የጋሪውን መደገፊያ ጨብጣ ከመውደቅ ዳነች ።

ግሳኒ አይኖችዋን ስትከፍት እስክርሌትን አጠገብዋ ቆማ አየቻ ትና በሹክሹክታ

@OLDBOOKSPDF

"ውዴት —አቢት ደረስን ኮ" አለች ።

ቤት ! ግና ታሰን ስታስብ ትኩስ እምባ ወደዓይኑዋ መጣባት ። ሚለኒ ቤት እሚባል ሽታው እንደጠፋና ዕብደት በወረሰው ምድረ በዳ ብቻዋውን እንደቀሩ አለወቅችም ።

"ግና ኑ" አለች ጉሮሮዋን ቃላቱ እያነቁዋት በሰንት መከራ ። ግን እሁን እንዴርሳለን ። እንዲት ላም እማኝኾለሁ ። ላጉቺም ለአራሱ ልጅም ወተት ታጣኛላችሁ ።

"ምስኪን ልጅ" አለች ሚለኒ ቀስ ብላ ፣ አቅሙ ደካማ እጅዋን ወደ ለጅዋ ስትዘረጋ ገለሙ እያጠረባት ።

ወደ ጋሪው ወጥታ ባለ በሴሰ አቅሟ ቱጣጥራ በመጨረሻ ሙስ ሙር አስያዘችው ። ፈረሱ ግን እንጉርጉን ሰብሮ አልሄድ ብሎ ስግም ። እስክርሌት ያለርህራሄ ገረፈችው ። ደካማ እንስሰ በሥጉዴትዋ እማዚ አብሔርን ይቅርታ ጠየቀች ። ይቅርታን ባያረግሳትም መቼስ ምን ይደ ረግ ያሳዝናታል እንጂ ምን ይሆናል ። ታራ እንደሆን ፈት ለፈታቸው ናት ።ይችን የማይል ሩብ ይመሰዳት እንጂ ፈረሱ ቢሻው ብፍጢሙ ይደፋ ።

በመጨረሻ መንገድ ደረሰ ። ጋሪው ሲጠጢጥ ይሳል ።ሳሙዋ በየጊዜው እምቡዋ — እምቡዋ ትሳለች ። እስክርሌት የዚች እንስሰ ማታሰት በሙራሽ ትሚከደን አሰጨርቂት ፈትታ ሌትሰቅታት ምንም አልቀራትም ። ታራ ምንም ሰው ከሴሰ ይቺ ላም ምን ትጠቅማቸዋ ለች ፣ እትታለብ ነገር ፣ ብትታለብ እንኳ ግና መደጡትዋ የተጠጋውን በእርግጫ ነው የምታበነው ። ግን ላሚ አሁን የደ ናት ። ብታስቀም ጣት ምናሌ ። አሁን በአለም ላይ ያሏት ነገሮች በጣም ጉንሽ ናቸው ።

እስክርሌት ኮራ ብሎ ከቆሙው ኮረብታ ሥር በመጨረሻ ስትደ ርስ አይኑዋን ጭጋግ ወረሰው ። ከኮረብታው ወዲያ ታራ አለች ! ! ልብዋ ሰንጥቅ አለ ። ይሄ ደራታ እንስሳ መቼም ኮረብታውን ችሎ አያወጣትም ። ዱር በደጉ ጊዜ ቆፍጣና በቅሎዋን ይዛ በቀላሉ ጋልባ የምትወጣው ጸጋት ነው ። መቼም በዚች እጭር ማዜ ውስጥ ጸጋቱ ለሰት አወጣ ማለት አይቻልም ። ፈረሱ ክንክባድ ጭነቱ አይንክውም ።

እንደተጨጫናት ወረደችና ፈረሱን በኩርኩ ጫነችው ።

"ሙረጂ ጥሪሲ ብላ አዘዘች ። ዋድን ያሻው ። ወይ እዘይው ወይ በእግሩ ይምጣ ። ህጻኑን ሚለኒን አስተጂው ።" ዋድ ማልቀስ ጀመረ ። እስክርሌት ስምን እንደሚያለቅስ አላወቀችም ብቻ ።

"ጭለማ — ጭለማው — ዋድ ይፈራል !"

@OLDBOOKSPDF

"እትዬ አስካርሌት እኔ መሐድ አልችልም ። እግሬ ተላልጧል ። በዛ ላይ እኔና ዋድ አንድ ላይ አንካበድም ። እና . . ."

"ውረጂ ! ጉትቻ ሰላወርድሽ ብትወርጂ ይሻላል ! እንደዛ ካረ ግሁ ደግሞ እዚህ ጭለማ ውስጥ ብቻሽን ጥዬሽ ነው የምሄድ ! በይ ፈጠን !"

ፕሪሲ ወደ ጭለማውና ውሀው ወዳለችት ከጋሪዋ ብትርቅ — መደሚያንጯት ዛፎች እያጉረመረሙ ተመለከተች ።

ያም ሆነ ይህ ህዝቡን ሜላኒ ጉን አስቀኝታ መሬት ዱብ አለችና ዋድን አወረደችው ። ትንሹ ልጅ እያለቀሰ ምላዚክ ላይ ጥብቅ አለ ።

"ዝም በል በይው ! አሁንስ ምርር ነው ያለኝ" አለች የፈረሱን ኮርቻ ይዛ ያለፈቃዱ እየገፋች ። "ዋድ ጥሩ ልጅ ሁን እንግዲህ አለበለዚያ — መጥቼ አርአለሀለሁ !!!"

አግዜር ለምን ህጻናትን ፈጠረ ብላ አሰበች በልቧ ወደ ጨለማው ጨክና ዙራ ። ጥቅመቢስና ጨዋዪ ነገሮች ሁልጊዜ እቀፉን ሁልጊዜ እንቅፋት ! እንደዛ ደክሟት መሸም እልፎ ውስጥ ከፕሪሲ ጉን ጉን ድክ ድክ ለሚለው ለተጨናገጠው ልጅዋ ለማዘን በጭራሽ ቦታ የላትም ። ለምን እንደወደለችው ነው ግራ የገባት ። ጭንቀት ነው የጥረሳት ። ከሱውንም ምርለስ ሐሚልተንን ለምን እንዳገባችው ለታ ከቶ አዕምሮዋ ገረመው ።

"እትዬ አስካርሌት" አለች ፕሪሲ በሹክሹክታ የእመቤትዋን ከንድ ጭምድድ አደርጋ ይዛ ። "ወደታራ ባንሄድ ይሻላል ። እዛ ማንም አይኖርም ። ሁሉም ሄደዋል ፣ በነዋል ። ምናልባትም እማማና ሌሎቹም መጥተው ይሆናል ።"

አስካርሌት የራስዋ ሀሳብ ማሚቶ ለቀቃትና የሚቆነጥጣትን ጣቶች አነሳምሯው ።

"እንግዲያው የጥድን ኒድ አስይዢኝ ። እንቺ እዚሁ ተንልተሽ ቅሪ ።"

"ምንው እትዬ ! ምንው !"

"ታዲያ ዝም በያ !"

አቤት ፈረሱ እንዴት እየተንቀረፈፈ ነው የሚሄደው ። ቆበሩን ሲያጥቅ ኪሉ ወደ እጅዋ ተንጠባጠበባት ። በአእምሮዋ አንድ ጊዜ ከሬት ጋር የዘመረችው መዝሙር በጥቂቱ ትዝ አላት ። ሌላውን አታስታውስም ።

@OLDBOOKSPDF

"ከባዱን ሸክም ልናወርድ ፣ ጥቂት ቀናት ብቻ ቀሩን . . ." ንበር የመገሠሩ ትገዛ

"ከባዱን ሸክም ልናወርድ ፣ ጥሬት እርምጃዎች ቀሩን" አለ የእሷም አእምሮ ደማሞ ደጋግሞ ። መዲያው እከረብታው ሜዳ ላይ ጾረሰ ። ከፊት ለፊታችው እየደበዘዘ ከሚሄደው ሰማይ ማርቼ ጥቅጥቅ ያሉት የታሪ ጥርሞች ጨለማ ልብስው ገዝፈዋል ። አለካርሴት የመ ዝሪት ሙከራቸው ለማየት በቀድፊያ ጥከረኝ ። ምንም ብርሃን የለም ።

" ሁሉም በእነዋል " አለ ልቧ እንደቅዝቃዛ የሚታር ድምፅ ሣይደዋል !"

የፈረሱን ንፈስ ወደ ሠማንዴ አታናት ። ከአናት የአርዘ — ሊባ ኖስ ቅርጫፎች ተቆላለፈው ጣራ ሰርተውባቸው የመድኅት ጽል ሙት ውበቱ ከትቱያቸዋል ። የነጋቷማን አጀንዳ እየሰነጠቁ አያንዣን እያበጨነቁ ፀትህ ! ደታ ያታል — መዴስ አይታንትም ፣ ዓይኖቹ ይከታከተታል እንዴ ! የታሪ ነው ሀንዳ ኩበዘዝ ብሎ ዙጥም አይሰ ይም ። ቤቱ ! ቤቱ ! ሐሩቹ ነጭው ግደግዳዎች ፣ ባሉ ተወለበለበ መን ረጎ መስኩት ፣ ከፈለ ቢረንጋ — ጨለማ ያዘለው አይታወቅ ፣ እዚህ ውስዋ ይኖት ይሆን መዴስ እናድግኒንቶች ቤት ያለ መክፉ የዘንበዩ ቅን ቤት ይሆን ያልርባሉኝ የሸንበበት ! ብሉጣ ያቀፈው አይታወቅ ።

ያ በጀግኒ የምታወጣው አጭሩ ሠማንዴ በጣም አረዘመባት ። በዛ ላይ ፈረሱ ጭራሹን የመሮም ያህል ይንጉታታል ። ዓይንዋ ጭለማ ወሳ ቢገራት ያበባል ። ቤቷ ከጠባቧ ያለ መስኩት ። ይሄ ሊሆን ይች ላል ! ይሄ ሊሆን ይችላለ ! በዋሩም ሊሆን አይችልም ። ጦርነቱ ልሞ ንም ምህረት አያደርግም ። ታራን አንኳ ፣ ልአምለት መቆ አጠቃ ፊድጊ የተገንባቸውን ታራን አንኳ አልማረም ። ዋ ! በ"ታራ ላይ ማለፍ አልነ በረቸችም ።

ከዚያ በዋቱር ጥላ ውስዋ ቅርጽ ያለው ነገር አየች ። ፈረሱን ወደፊት ኮስ ጥስ ትገፉትው ጀመረ ። ነጭ ግርግዳ በጭለማው ውስዋ ብቅ አለ ። በምስ አለነበዘም ። ታራ አምልጣለች ! ቤቷ ! ኮርኦ ውን ጥላ የመጨረሻያምቹን እርምጃዎች በመሮዋ በዛ በአጀም ባዶ ውን ግርግዳ ለማነቅ ምንም አልተራት ። ከዚያ አንድ ጥላ የመሰለ የሰው ቅርፅ ያለው ነገር ከጥቁሩ በረንዳ ብቅ አለ ። ታራ ብሎዋን አለ ቀረችም ። እቤት ውስዋ ሰው አለ !

የደስታ ጩኸት ጉሮሮዋ አፀኪሰነጠቅ ጮኸና ደም ደስታዋ መላት አለባት ። በሩን ጭለግ ወንታለ ። የዝምታ አዘቅት ውጠታለ ። ያ የቆመው የሰው ምስለ ወይ አያንቀላቀስ ወይ አይጣራ ዝም ብሎ

@OLDBOOKSPDF

ሳግትሯል ። ምንድነው ነገሩ የየተበላሸ ነገር አለ እንዴ ! ታራ በሕይወት አለች ። ግን ቀዬውን በሙሉ ያቃሰለው እርጭታ ቤቱንም ተግባራዊ —ዘምታ አልብሶታል ። ከዚያ ያ ቅርጽ መንቀሳቀስ ጀመረ ። ግትር ትር እያለ በቅስታ ደረጃውን ወረደ ።

እሱ ይሆን እይሆን ፣ በሚል የጥርጣሬ ዓይን አያየችው "አባባ" አለች በሹክሹክታ ። "እኔ እዚ ቤቲ አስካርሌት ነኝ ፣ ወደቤት መም ጣት ነው ። " አለችው ። ጂራልድ በእንቅልፍ —ልቡ እንደሚጓዝ ሁሉ ፕታራ እግሩን እየጐተተ ወደ አሏ ተንቀሳቀሰ ። ህልም እንደሆ ነች ሁሉ በሰመመን እያስተዋላት ቀረብ አለ ። እጁን ዘርግቶ እትከሻዋ ላይ አስቀመጠ ። ሊንቀጠቀጥ ይሰማታል ። ከእንቅልፉ ሙሉ ለሙሉ እንዳልነቃ ሰው እጁ ተጥጥቀጥ ይላል ።

"ሜ ልጅ ፣ ልጄ" አለ በጥረት ። ከዚያ ዝም አለ ።

"እንዴት — ምን እንዲህ አስረጀው ?" አለች በልቧ ።

የጂራልድ ትከሻ ተኩማትሮ ወደ ውስጥ ጐብጧል ። በደብዛዛው የሚታያት ፊቱ ጥሙለማልማ ብሎ ፡የጥንቱ ጂራልድ ህይወት የሞላ በት እረፍት የለሽነት የለበትም ። ዓይኖቹም ፍርሃትን ያዘሉትን የሞደን ዓይኖች መስለው እሏን እሏን ያያሉ ። ቅስሙ የተሰበረ ደቃቃ ፍጥረት ሁኖዋል ።

ይሄኔ እንድ ኮማታመቀው ነገር ከሙለማው ዘሎ ሰውነቱዋን ወረራት ።እናም ዝም ብላ ቆማ ማየት ሆነ ሥራዋ ። ለመጠየቅ ያለበ ኛው የጥያቄ ሞንት ሁሉ እፍኖ ላይ እየሚሟ ዲጳ ሆነች ።

ክጋሪው ላይ እንድ የጨኸት ድምፅ መጣ ። ጂራልድ በጥረት ቀና ብሎ አስተዋለ ።

"ግልፂና እራስ ልጅዋ ናቸው "አሰች እስካርሌት በሹክሹክታ ።" በጣም አሟታል ስለዚህ ይሞት ወደቤት መጣሁኝ"

ጂራልድ እጁን ከከንፉዎ ላይ አውርዶ ትከሻውን አስተካከለ ። ወደጋሪው አጠገብ ሲሄድ የታራን የጥቱን የጠዋቱን እንግዳ ተቀ ባይነት ፣ እንደሰመመን ያለ የትዝታ ጥላ አጥልቶበት ፣ እያስታወሰ የሚ ናገር ይመስላል ።

"የአክስቴ ልጅ ሜላኒ ?"

የሜላኒ ደቃቃ አንደ ጉርምርምታ ተሰማ ።

"የአክስቴ ልጅ ሜላኒ — ይሄ ቤትሽ ነው ። "አሥራ ሁለቱ ዋርክ ዎች" በአሳት ጋይቷል ። ስለዚህ ከእኛ ጋር መኖር አለብሽ ።"

@OLDBOOKSPDF

የሚለኒን ያለፈ ስቃይ ስታስታውስ ፣ እስካርሌት ፣ ግድየለ ወደ አልባት እንገብጋቢ ጉዳይ ዞረች ።የአሁኑ ተግባርዋ ሜላኒንና ልጅ ዋን በምቹ አልጋ ላይ ማስተኛትና ወላድን ለማረስ መዶለግ ያለባቸውን ጥቃቅን ነገሮች ሁሉ በተቻላት መረዳም ነው ።

"ካልተመከሙኖት ችላ በእግሩዎ መሄድ አትችልም ።"

የእግር ኩቴ ተሰማ ወዲያው ። አንድ ጥቁር ጥላ ፣ ከፈት ሲራቅ የአ ጸራሽ ዋሻ ብቅ አለ ። ዎርክ ደረጃውን ተንደርድሮ ወረደና

"እትዬ እስኪርሌት ! እትዬ እስካርሌት !" እያለ ጮኸ ።

እስካርሌት ክንዱን ያዙትው ። ዎርክ የታራ የአፈርዋ ብናኝ ፣ የአብ ራኳ ክፋይ ነው ! ! እኒደመከላዎችዋና እንደቀዝቃዛ በረንዳዎችዋ የታራ አካል ነው ! ! እጅዋን እየመታ እንባው ጉብ ጉብ ሲል ገላዋ ሲረጥብ ይሰ ማታል

"በመመኔስሽ በጣም ተደስቻለሁ ! በጣም ነው ደስ ያለኝ ።"

ፕሪሲም በልቅሶ ንፍፈሰች ። ምንም የማይያዙ ቃላትን እያጉ ተመተመች "ጋክ ! ጋክ ! የኔ ቆንጆ ! የኔ ጣር ወስላ !" ስትል ጉንጩ ዋድም ቅልልቆቹ ባብተው ሲያለቅሱ ሲያይ ተደሩፈረና "ዋድን ጠም ቶታል !" ብሎ እየጮኸ አለቀሰ ።

እስካርሌት ሁሉንም ያዘኑትውና፡—

"ወይዘሮ ሜላኒና ልጅዋ ኢጋሪው ላይ ናቸው ። ዎርክ በጥንቃቄ ደረጃውን ይዘሃት ወጥተህ በሁዋላ በኩል እንግዳ መኝታ ቤት አስ ተኛት ። ፕሪሲ ደግሞ ዋድንና ህፃኑን ይዘሽው ግቢና ልዋድ የሚጠ ጣው ውሃ ስጪው ። ማሚ አለች እንዴ ዎርክ ? እንደምፈልጋትንገ ራት ።

የተናገረችው ንግግር እንደሆነው ሁሉ ራመድ ራመድ ብሎ ወጥቶ ወደጋሪው የኋላ ክፍል ገባ ። የላባ ያህል ውፍረት የሌላትን ሚላኒ ለዛን ያህል ሰዓት ከተኛችበት ጣውላ ግማሽ በማማሽ ብድግ ሲያደርጋት አ አ አ የሚል ድምፅ አሰማች ። ወዲያው ጠበቅ አድርጉ ይዞ ብድግ ሲያደርጋት እንደዘጸን ልጅ አራስዋን እትከሻው ላይ ልጥፍ አደረገች ። ፕሪሲ አራሱን ልጅ ታቅፋ ዋድን በእጅዋ እየጉ ተተች ስትከተላቸው ፣ ደረጃውን ወጥተው እጨለማው አዳራሽ ውስጥ ጥልቅ ብለው ላይን ተሰወሩ ።

የእስካርሌት የተሞሸላበቱ እጆች ያባትዋን እጅ ባስክኪይ ይፈል ጋሉ ።

@OLDBOOKSPDF

"ደህና ናቸው ፣ ትላላችው ?" አለች ።

"ልጅቱማ እያገገሙ ነው ፤"

ዝምታ ተጫናት ። በዚህ ዝምታ ውስጥ በቃላት ሊገለፅ የማይችል ከፉ ሐሳብ መጣባት ። በጭራሽ በአፍዋ ልትናገረው አልቻለችም ። አሥር አሥሬ ምራትዋን ትወጣለች ። ግን አንድ ድንገተኛ ድርቀት የጉሮሮዋን ዳርና ዳር ያጣበቀው መሰለ ። ለዚያ የፍርሀት እንቆቅልሽ ለሆነባት የታራ ጭርታ መልሱ ይሄ አሁን ያለው ይሆን እንዴ ፣ አፅምሮዋ ውስጥ ለሚጉላላው ጥያቄ መልስ የሚሰጥ ይመስል ጄራልድ ፡—

"እናትሽ . . ." ብሎ ጀመረና አቆመ ።

"እናቴ ምን ?"

"እናትሽ ትላንትና አረፈች ።"

* * *

ያባትዋን ክንድ እንቅ አድርጋ እንደያዘች ፣ ጭለማ እንኳ ቢሆን እንደገዛ ጭንቅላትዋ በምታውቀው ድፍን ያለ አዳራሽ ውስጥ ፣ ቁል ቁል እያትጮሀተች ስትሄድ ይታወቃታል ። ትላልቅ መደገፊያ ያላቸውን መቀመጫዎች ትታ ባዶውን የጠመንጃ ፎደራ አልፋ ፣ ወደ ፊት እግሮቹን ያወጣውን ከሞጻኖም ዘልቃ ልክ በደመ ነብሰዋ እንደው ቀልበዋ እንደመራት ሄዳ ፤ እናትዋ የእለት ገቢና ወጪ ሂሣብ መዝገብዋን ዘርግታ ትቀመጥበት አነበረው ክፍል ገባች ። እርግጥ ነው ወደ ክፍሉ ስትገባ ለወትሮው እናትዋ መዝገብዋ ፊት ለፊት ቁጭ ብላ ቆይታ ቀና ትልና ፊትዋን ሚዛናዊ መልክ አስይዛ ከግሩም ፈገግታ ጋር መቀነትዋን እያወዛወዘች የደከመች ልጅዋን በናፍቆት ትቀበላት ነበር ። አሁን ልትሞት አትችልም ። አባትዋ ቢነግራትም እንኳ የሚሆን ነገር አይደለም ። አባቷ እንደሰቀቀን አሁንም "ትላንትና አረፈች ... ትላንትና አረፈች ... ትላንትና አረፈች ።" የሚለውን ሐረግ ቢደግምላትም ይህ ሊሆን አይችልም የሚለው ሀሳብ አሸንፋት ።

አሁን መቼም እግርና እጅዋን በብረት ሰንሰለት አስሮ ከሚያንገላታት ጭንቅና ጉልበትዋን ከሚያብረከርከው ረሀብ በቀር የሚሰግት አንዳችም ነገር የለም ። ሰለ እናቷም ቢሆን ቆይታ ታስብበታለች ። የእናቷን ነገር ከአፅምሮዋ ካላወጣችው በቀር ወይ እንደ ጄራልድ ቅጥ የለሽ ንግግር መዘባረቅ ወይም እንደዋይ ሰው እስኪያከት መነፋረቅ ይመጣል ።

@OLDBOOKSPDF

ፖርክ ሰፈሙን ደረጃ ፊጥኖ እየተራመደ ጭስማሙን ጥሎ የበረደው እንሰሳ አሳት ዳር መጠጋት እንደሚሻ ሁሉ አስርዋ ውበቅ ሊል መጣ ።

"መብራቱስ ?" ብላ ጠየቀች ። "ቤቱ ለምን እንዲህ ጨለመ ፖርክ ሻማ አምጣ እንጂ ?"

ጎትዬ አስካርሌት ሁሉንም ጥርግርግ አድርገው መሰዱብን እኮ ። በጭለማ ሥራችን ለመሥራት የምንጠቀምበት አንድ ነበር ፤ እሱ ውም ሊያልቅ ምንም አልቀረው ። ማን እትዬ ከፊንጉና እትዬ ሰቼ ለንን በታስታምም የምትጠቀምበት የሞራ —ሥጣቂ ውስጥ የቀነ ከረ አራፊ ጨርቅ በማንደድ ነበር ።"

"በል የቀረፈውን ሻማ አምጣ ።" ብለ አዘዘችው ። "በል ወደ እማማ . . . ወደ ቢሮው አምጣው ።"

ፖርክ ወደ ምግብ ቤት በረረ ። አስካርሌት ቀስም ቀስም ወደም ትቸኮው ትንሽ ክፍል ነበታ ሶፋው ላይ እረብ አለች ። ያባቷዋ ከንድ አሁንም እስንዱዋ ውስጥ እደቀለለ ሪጳት የለሽ ፣ ተስማማኝ ፣ ሁሉን አማኝ ሆኑዋል ። እንዲህ የሚሆን ከንድ ደግም ወይ የሲጋ ወጣት ወይ የአረጋዊ ሲሆን ነው ።

"አሱ ሽማግሌ ፣ የደከመ ሽማግሌ ነው" አለችኛ እንደገና ባሳብዋ ለምን እንደማትጠነቀቅሰት ገረማት ።

ፖርክ ማማሽ — በማማሽ ነዶ ያለቀ ሻማ አብርቶ ክፍ አድርጉ ይዞ ሲገባ ብርሃን እየተመዘገዘገ ወደ ክፍሉ ተሰራጨ ። ያ የጭስማ ዋሻ ሕይወት ዘራ ። የተቀመጠበት የወለሰት አሮጌ ቦሳ ፣ ጣራ ጀስኪ ነክ ዶሴ የተከመረበት የእግድ መጫሬያ ጠረጴዛ ነኑ ሙልቅሰት ወን በሩ ፣ አሁን በወረቀት የተጠቀጠቀት እናትዋ በገዛ እጅ ክሕፈትዋ የጽ ፈቻቸው ወረቀቶች የተሞሉበት ማህደር ፣ የተቀደደው ምንጣፍ —ሁሉም ዱሮ እንደነበረው ነው ። አሰን ካለመኖርዋ በቀር ሁሉም ነገር አለ ። አዎ ነአለች ። ግና ከሩቅ ሽታዋ እንደሎሚ የሚጣራው አለኝ ገደም አደርገው ከሚያዩ ወጣ ዓይኖቹዋ ጋራ የለችም ።

አስካርሌት ፤ ሕዋሳት ከህመም ለመዳንና አንደገና ለማገም እን ደሚጣጣሩ ሁሉ ፤ የቆሰለው ልብዋም እንዲሁ ይሰማው ጀመር ። ይህ ህመም እንዲያስጨንቃት ማድረግ ግን የለባትም ። ግና ተራፊ እድሜ ዋን ሙሉ ሊያሙዋት የሚችሉ ናቸውና ልቧን የሚያቆስሉዋትን ነገሮች ሁሉ ማግለል አለባት ። አሁን ግን በጭራሽ ዉ . . . አሁንስ አትችልም እግዜር ይርዳት !

@OLDBOOKSPDF

ወደ ፔራልድ ማዲያት የወረሰው ፊት ተመለከተች ። እናም በሕይወ
ትዋ በመጀመሪያ ግዜ ጂሙን ሳይላጭ ሃራጫ ጨኮኒት ወርሶት አየች ።
ፖርክ ሸማውን እማለቀመጫው ላይ አኖረና ወደሱዋ አጠገብ መጣ ።
እስክርሌት ፖርክ ፀጉሳ ውሻ ቢሆን ኖሮ እራሱን እግሮችዋ ላይ አድ
ርጉ በእጅዋ እንድታሻሸው ይፈልግ እንደነበር አሰባ ገረማት ።

"ፖርክ ፣ አሁን ስንት ባሪያዎች አሉ?"

"እትዬ እስክርሌት ፣ እነዛ የማይረቡ እግሮዎች ጥለውኝ ሸሹ ፣
ማሂሰሽም ከያንኪዎቹ ጋር ሄዱ እና . . . "

"ስንት ቀሩ አሁን?"

"እትዮ እስክርሌት እኔና ማሚ ብቻ ነን ። አሷ ትንሽዎን ልጃገረ
ቦች ስታዕዕምም ቀንን ሙሉ ትወሳሰች ።ጲልሲም ምግብ ታበስልላ
ቸዋለች ።እንግዲህ እኛ ሶስታችን ነን የቀረነው ።

"እኛ ሶስታቸን" አለች ጉድም አይደል ፣ አሰቲ ሙት ባሪያዎች
እንሳልነበሩ ሁሉ ሰስት ብቻ ይቅሩ ። አስክርሌት እንሳንድ ነገር የማ
ሳውራትን ጭንቅላትዋን በስንት ጣጣ ከበሽተኛ እንጉትዋ ላይ አቀ
ናች ። ሂምቡጥን በትክክል ማውጣት እንዳለባት ይሰማታል ። ቃላቱ
ግን ይጣረሙ ብለው ጠሩት እንዶሌለና አሥር አሽከሮች ባንድ
ግዜ ኑ ማለት እንደምትሽል ሁሉ ፣ ስትጮኽት ብለው ሳይዘቡ ከአፍዋ
በስሆሳስ ወጡ ።

"ፖርክ ብጣም ርዕኛል ፣ የሚበላ ነገር አለ ይሆን"?

"እይ እትዮ ሁሉንም ዘርፈው ወስዱብን አኩ ።"

"የዳሮው አትክልትስ?"

"እሱንማ ፈረሰኞቹወን ነጫበት ፣ ለቅቁበት ። የስኳር ድንቹንም
አርሻ አጠፉት ?"

በመጥራም ክንፈሮቹ ላይ እንድ የደስታ ፈገግታ የሚመስል
ነገር ታየበት ።

"እትዬ እስክርሌት ፣ እነዚያን የሚበሉ የያም ፍሬዎች በሙራሽ
አልረሳቸውም ። አሁንም እዚያው አሉ ። ያንኪዎቹ ምንም ያም ስላሳዩ
ሥሩ ብቻ የቀረ ነው የመሰላቸው እና . . . "

"ጨረቃዋ አሁት ትወጣለች ። ሂድና በጨረቃዋ ብርሃን ያገኘ
ኸውን ያህል ሰብስበህ ጠብስና አዘጋጅልን ። የበቆሎ ቂጣ እንኳ
የለም ? የደረቀ አተር ? ጫጩቶቹ ሁሉ አለቁ ?"

@OLDBOOKSPDF

"የለም እትዬ አንድ እንኳ አላስተረፉልንም። እዚሁ ያልበሏቸውንም ጭነዋቸው ሄደዋል።

እነሱ—እነሱ—እነሱ ይባል . . . እነሱ ምን ያልሠሩት ነገር አለ፣

አስቲ ማቃጠልና መግደል አልበቃ ብሏቸው ሴቶችና ሕፃናትን በመጨፍጨፉበት ከዚማ ውስጥ የሚላስ የሚቀመስ አሳጥተው ቢጠፉ ይፍጁዋቸው ፣

"እትዬ አስካርሌት ያገኘሁዋቸውን ጥቂት ፍሬዎች እመሬት ቀብሬ ፣ ዛሬም የበላነው እነሱኑ ነው።"

"ከድንቹ በፊት ፍሬዎቹን አምጣልኝ። ፖርክ በጣም ደክሜያለሁ። የወይን ጠጅ ወይም ሚንቺውም የሚመጣ ነገር እንዳለ ይሆን፣

"እይ ጓዳማ መጀመሪያ የመጣበሩበት ቦታ ነው።"

ከረሃብ ፣ ከእንቅልፍ ማጣት ፣ ከድካምና ከውጥረት የመነጨ ፈሰሽ ባፍንጫዋ ፈሳ። በእጅዋ የያዘችውን አበባ ሹምት አድርጋ ፣

"ወይን ጠጅም የለም" አለች በደምሳሳው ፣ መያርያዬው ላይ ይደረደር የነበረውን ሥርር ቁጥር የሌለው የወይን ጠርሙስ አስታውሳ።አንድ ትዝታ ሚንሳል አለባት።

"ፖርክ አባባ ጎሮ ከዛፍ ሥር በበርሜል የደበቀውስ ውስኪ?" ሉላ የፈጣጣ ጣረ ሞት ፣ ሉላ የደስታና የአክብሮት ፈገግታ ጥቁር ፊቱን አደመቀው።

"እትዬ አስካርሌት አርሶ መኖም በጣም አስታዋሽ ነዎት እኔ ያንን ውስኪ ረስቼው ነበር። ግን እትዬ አስካርሌት ያ ዊስኪ ጥሩ አይደለም።እዚያ ሰዓሞት ያህል ነው የተቀመጠው። ደሞም ውስኪ ለሴቶች ጥሩ አይደለም።"

ኔግሮዎች ደደቦች ናቸው፣ ከልተነገራቸው በቀር እይገባቸውም። ምንም ነገር ማሰብ አይችሉም። ታዲያ ያንኪዎቹ ነፃ እናወጣለን የሚሉት እንዚህን ነው። "ግዴለህም ፖርክ ለእንደኔ አይነቷ ወይዘሮና እንደ አባባ ላሉት አዛውንት በጣም ተስማሚ ነው። በል ፈጠን ቢል ፖርክ ቆጥርና አወጥተህ ከሁለት ብርጭቆዎች ፣ ከዴቂትና ከስኳር ጋር ይዘህ ና። ደባልቄ ጁሌፕ አሰራለው።

ፊቱ ከሱ አለው።

"እትዬ አስካርሌት ሰረጅም ጊዜ ስኳር ታራ ውስጥ አልነበረም። እናም ደሞ ፈረሶቹ ሓዲቂሆን ሁሉ በሉት ፣ ብርጭቆዎቹንም ሰባብረዋቸዋል።"

@OLDBOOKSPDF

"እሞ ከእንግዲህ ወዲያ 'እነሱ' ይለኝና መጮሂ ነው። ምንም ልረዳው አልችልም።" ብላ አሰበች። ከዚያም ጮክ ብላ "ደህና፤ ፈጠን በልና ዊስኪውን አምጣ በንፁህ አጥለን እንጠጣዋለን።" ከዚያም ጥና ዞር ሲል "እስቲ ቆይ ፖርክ ለማሰብ ያልቻልኳቸውና መሠራት ያለባቸው ብዙ ነገሮች አሉ። አሃ አዎን —አዎን ፈረስና ላም አምጥቻለሁ። ላሟ ሙታለብ ያስፈልጋታል፤ ፈረሱንም ልንሙን አውል ቅለትና ውሃ አጠጣው። ሂድና ለማሚ ላሟን እንድትጠቢታት ንገራትና አንዱ ጋ እንድታስራት አድርግ። የሚላኒ ልጅ የሚቀመስ ነገር ካላገኘ በረሀብ መሞቱ ነው—እና . . ."

"ወይዘሮ ሜሲ የላቸውም ... ማለቴ ችለው ...?" ፖርክ መናገሩን ዝግ ብሎ አቋረጠ።

"ወይዘሮ ሚሲ ምንም ውተት ጠብ አይላትም።" ኧረ በፈጣሪ እንዴት እናት በእንዲህ ያለው ሁኔታ ትሞታለች!

"በቃ እትዬ እስካርሌት፤ የኔዋ ዴልሲ የወይዘሮ ሚላኒን ልጅ ትጠብቅላቸዋለች። የኔ ዴልሲ በቅርቡ ልጅ ወልዳለች። ስለዚህ ለእሷም ለወይዘሮ ሚላኒም ልጅ የሚበቃ ወተት ይኖራታል።"

"እ ፖርክ እዲስ የተወለደ ልጅ አገኘሃ?"

ሀዲናት፤ ሀኖት በሀዲናት ላይ። ለምንድ ነው እግዜር እኪህን ሁሉ ሀዲናት የሚፈጥረው? እሞ ግን እግዚሃር አይደለም የፈጠራቸው — ደደብ ሰዎች ናቸው።

"አም እመቤቴ ትልቅ ወፍራም ጥቁር ልጅ። እሱ . . ."

"ሂድና ዴልሲን ትላልቆቹን ልጆች ትተሽ ሂጂ በላት። እነሱን እኔ እጠብቃቸዋለሁ። ወደ ሜላኒ ልጅጋ ሂጂና ሊደረግ የሚገባውን አድርጊ በላት። ማሚኒም ላሚቱን አደራ፤ ያንን ምስኪን ፈረስም ወደ ግርግም አስገቢው በላት።

"አይ እትዬ እስካርሌት፤ የምን ግርግም አለ ብለው ነው ማገዶ አደረገት እኮ . . ."

"ከእንግዲህ 'እንዲህ አረጉ' ትለኝና ወየውልህ። ዴልሲን ጠብቂያቸው በላት በቃ። አንተ ደሞ ስማ ፖርክ —ሂድና ጉርንዱን ቆፍረህ ውስኪውን አውጣ —ወዲያውም ድንች ይዘህ ና።

"ግን አትዬ እስካርሌት መቆፈሪያ የለኝም እኮ"

"እንዴ የግዳዩ እንጨትም ቢሆን ፈልጋ፤ እሱ አይሆንም እንዴ?

@OLDBOOKSPDF

"ምንም የማገዶ እንጨት የለም ። እኔስ . . . "

"እንጃለህ . . . የፈለከውን አድርግ — ግዴለኝም ። ብቻ ፈጥነህ ፈጥር ።ብል አሁኑ — ፈጠን ።"

ድምፁዋ እየከረረና እየሻከረ ሲሄድ ፖርክ ከከፍሉ እየበረረ ወጣና እስክርቤትና ጂራልድ ብቻቸውን ቀሩ ። እግሩን ቀስበ ብላ መታ መታ እደረገችው ። ጸር ኮርቻ ላይ ቁጭ ሲል ሠዮርዋር ይሉ የነበሩት ጭሚቹ ዘሬ መሸቬ ማለታቸውን ተገንዘቦች ። ይሆት ጭልጥ ካለው ሀሳብ በማውጣት አንድ ነገር ማድረግ አለባት ፤ ስለ እናቷ ሰመጠየቅ ግን እስካሁን አልደረሰችም ። ምንን ልትጠይመው በምትችልበት ሰዓት ትጠይቀው እንጂ አሁን አትችልም ።

"ታራን ለምን አሊታጠቢኝም?"

ጂራልድ የምትባግረውን እንኳማይሰማ ሁሉ ትኩረ ብሎ ያስት ሠሓታል ። ጥያቄዋን ደግሞ ጠየቀችው ።

"ኒ ..." አለና እያመነታታ ፤ "ቤታችንን እንደዋና የጦር ሠራዊ ሙው አድርገወት ነበር ።" አላት ።

"ያንቺምቹ — አዘሀ ቤት ?"

እነዚያን ያማሩ ግድግዳዎች ሲያበላሿቸው ታያትና ህዋሳቷ ተቆጡ ። ቅድስቷ አለን ኖራበት ተባርኮ የነበረው ቤት እንዚያ — እነ ዚያ — እነዚያ እርኩሶች ይጣቡበት ።

"እና አዚው ነበሩ ፤ የኔ ልጅ ። ግና "አሥራ ሁለቱ ዋርክምኞች" አጠገብ እንዳሉ ሙሉን ከወንዙ ብሻገር ተመለከትነው ። ንጉር ግን ሐኒና ኢንዲያን እንዲሁም እንጸንዶቹን ባሪያዎች ወደ ማክን ልከና ቸው ስለነበር ለነሱ አልተጨነቅንም ። እኛ ግን ወደ ግክን ለመሄድ አልቻልንም ። ልጆቹ በጠና ታምመው ስለነበር ትንሹንም ልጅ ጨምረን ይዘን ለመሄድ አልቻልንም ። ባሪያዎቻችንም ሸሹ ። የት እንደሄዱ አላውቅም ተሸክርክሪዎቹንና በቅሎዎቹን ስርቀውብን ሄዱ ። ማሚ ፣ ጴልሲና ፖርክ ግን አልከዱንም ። ልጆቹንና እናትሽን ለማንቀሳቀስ አልተቻልም ።

"ኧኒ ከአቪ" ። ስለ እናቷ ማውራት የለብትም ። ሌላ ምንም ያወራ ብቻ የሱዋን ወሬ ይተው ።

ያ ጂኔራል ቬርማን እንኳ ይህንን ክፍል ፣ የእናቷን ቤሮ ዋና የጦር ሠራሩ አድርገው ነበር ። የፈለገውን ይንገራት ።

@OLDBOOKSPDF

"ዎንኪዎች መንገዱን ለመዝጋት ወደ ጆንሰቦሮ መሄዳቸው ነበር ። እና ከወንዙ አሸቅበው በሺ የሚቆጠሩት ተሽከርካሪዎችና ፈረሶችም እንዲሁ በሺ የሚቆጠሩ ይዘው መጡ ። እበረንዳው ላይ ቆሜ አገኘሁዋቸው ።"

"ወ...ጅማናው ቶንሹ ጂራልድ !" አለች እስካርሌት በልቧ ፤ ኩራት በትምሳ መንፈስ...ጂራልድ ከሬት ለፈቱ ያሰውን ሰራዊት እበረንዳው ላይ ቆሞ ሲያይ ከጀርባው የራሱ ሠራዊት ያለው እንጂ የጠላት ጦር ብቻ እፈቱ ያለ አይመስልም ነበር ።

"ቤቱን ልናቃጥለው ነውና ሰቅቅህ ውጣ አሉኝ ። እኔም አብራችሁ አቃጥሉኝ እንጂ አልወጣም አልኩ ። ሰቀን መሄድ አንችልም ። ልጆቹና እናትሽ ..."

"ከዛስ?" ሁልጊዜ ወሬውን ወደ እናቷ ማዞር አለበት እንዴ?

"ቤቱን በሙሉ ወረርሽኝ ገብቶታል ። ታይፎይድ ነግሶበታል ። እናም እንሱን ሚንቀሳቀስበት ሬሳ መጫኑት ስለሆነ —ሞቴ ነው አልኩ ። ጣራውን እሳያኙን ላይ ሲያጋዩት ይችላሉ እንጂ ... ብቻ ለማንኛውም ታራን ለቅቴ መሄድ አልችልም ። ታራንና አልተዋትም ።"

ወደውጭ አየች በሐሳቡ ሲሸፍትና ድምጹ ሲመነምን እስካርሌት ነገሩ ገባት ። እም ጂራልድ አያት ቅድም አያቱ ቁራሽዋን መሬት አናስነካም ብለው ሞተዋል ። አትብታቸው የተቀበረበትን ፤ ያረሱበትን ፣ልጅ ያፈሩበትን ቤት — ለቀን እንሄድም ብለው ተዋግተዋል ።

"በሶስት — ሞት ኔፋፍ ባሉ ሴቶች እናት ላይ አሳት ልቀቁ እንጂ ለቀነ እንሄድም አልኳቸው ። አንደኛው — ወጣቱ መኪንን ደህና ሰው ነበር ።"

"እንዴ አባባ ! — ያንኪውን ነው ደህና ሰው የምትለው ?"

"ደህና ሰው ነው ። እየጋለበ ሄደና ከአንድ ሻምበልና ካንድ ሐኪም ጋር ተመለሰ ። የታመሙትን ልጆችና እናትሽን አያቸው ።"

"አንድ የሚይረባ ያንኪ አመኝ ታቤታቸው ድረስ አስገባህ ማለት ነው ?"

"የስታይ ማስታገሻ ነበረው ። እኛ ምንም አልነበረን ። እህቶችሽን አዳናቸው ። ሱዊሰን ከራኛ ደም ይወርዳት ነበር ። ለማዳን የሚችለውን ያህል ደግነትም ነበረው ። በሽተኞች መሆናቸውን አመለከተና ቤቱን ሳያቃጥሉት ቀሩ ። አንድ ጂኔራል ከነአጃቢዎቹ እጅብ ብለው ገቡና ከበሽተኞቹ ክፍል በስተቀር ቤቱን ጢም አድርገው ሞሉት ። እናም ወታደሮቹ ..."

@OLDBOOKSPDF

መናገሩን ለመቀጠል የደከመው ይመስል አቋረጠ ። ያ ሹል አገጭ ዙልዙልቱ ተጣጠፈና እደረቱ ላይ ወደቀ ። እንደገና በጥረት ተናገረ ።

"በቤቱ ዙሪያ ያልሠፈሩበት ቦታ የለም ። በቆሎው እርሻ ውስጥ ሠፈሩ ። እጥጥ እርሻው ውስጥም ሠፈሩ ። ምን አሰፋሽ የማሙሼ ሜዳ በሙሉ በነሱ ሰማያዊ የደምብ ልብስ ቀለም ተጥለቀለቀ ። የዚያን አለት ሜታ ዘጠና ዘጠኝ ቦታ የሠፈር አሳት ነደደ ። አጥሩን እየ ሰባበሩ ለማብሰያ ማገዶ አደረጉት ። ማርማሙን ፣ የዶሮ ርቢውንና ፣ ማድ ቤቱን ሳይቀር አጋዩት ። ከብቶቹን አሳማዎቹንና ዶሮዎቹን ሁሉ — የኔ ተሪኪኒዎችም አልቀሩ አረዱዋቸው ።" አዱ የጂራልድ ውድ ተር ኪዎች — እንሰሳም ሞቱ ። "ያልወሰዱት ዕቃም የለም — ስዕሎቹና የቤት ቁሳቁሶቹ እንዲሁም ሣህኖቹ..."

"ከብር የተሰሩትንስ?"

"እነሱን እንጃ ፣ ምርከና ማሚ ጉድጓድ ውስጥ ከትተዋቸው ነበር መሰለኝ — እንጃ ግን አላስታውስም ።" የጂራልድ ድምፅ ይርበተ በታል ። "እዚህ ታራ ሆነው ነበር ወሊያውን የሚያክሄዱት ፣ ሽቅብና ቁልቁል ይጋልባሉ . . . ይራኩታሉ ። በሁሳማ ጀንበሮ ላይ የሚተኩ ሰው መድፍ እንዳ መብረቅ ይሙሀ ጀመር ። ልጆቹ እንኳ ታምመው በተኙበት እየሰሙ 'አባባ መብረቁን አስቁመው' ይሉኛ ነበር ።

"እማማስ ፣ ያንኪዎቹ እቤት ውስጥ መኖራቸውን ታውቅ ኑራል ?"

"አሄሄ . . . እሱዋማ ምንም የምታውቀው ነገር የለም ።"

"እግዚሃር ምስጋና ይግባው" አለች እስካርሌት ። ያንን አለማወቋ በጣም ጥሩ ነገር ነው ሀሳቧን ያቀለሳታል ። እናቷ የሚሆነውን ሁሉ አታውቅም — እታችኛው ቤት ጠላቶቿ መኖራቸውን አታውቅም ። የጆንስቦሮውን የጥይት ፉጨት አልሰማችም ። ካንድ ልቧ እኩል የምታ ረገውና የሥጋዋ ቁራጭ የሆነው የታራ ምድር ከያንኪዎች እግር ሥር መዋሉንም አታውቅም ።

"እኔም ከልጆቹና ከእናትሽ ጋር እላይኛው ቤት ስለነበርኩ ጥቂ ቶቹን ብቻ ነው ያየሁዋቸው ። ብዙ ጊዜ ያየሁት ወጣቱን ሃኪም ነው ። ደግ ፣ በጣም ደግ ሰው ነው እስካርሌት ። ከቁስለኞቹ ጋር ቆይቶ ከልጆቹና ከእናትሽ ጋር ይቀመጣል ። እንደውም መድሀኒትም ትቶላ ቸው ነው የሄደው እናም ለቅቀው ሲሄዱ ልጆቹ ሊሻላቸው እንደሚችሉ እናትሽ ግን . . . በጣም ደክማ ስለነበር ልትቋቋመው እንደማትች ልና አቅም እያነሳት እንደሄደች ይናገር ነበር . . ."

@OLDBOOKSPDF

አርጭታ መጣ — ዝምታ ። በዚህ ውስጥ እስካርሌት እናቷ በዚያን ሰሞን ምን እንደምትመስል አሰበች ። ሌሎች እንዲያርፉ እሱዋ እን ቅልፍዋን አጥታ እየሰራች ፣ ሌሎች እንዲበሉ እሱዋ ባዶ ሆድዋን ምግብ እያበስለች ፣ልጅ አሳዳጊም እሱዋው ሁና ለታራ ዋንኩር ካስማ የሆነችው ቀጭንዋ ምሰሶ እሷ ነበረች ።

"ከዚያ ሂዱ ።ሂዱ በቃ ።" አለ

ለረሽም ጊዜ ዝም ብሎ ቆየና በእጁ እጁዋን ይፈልግ ጀመር ።

"እቤቅ በመምጣትሽ በጣም ነው ደስስ ያለኝ" አለ ቀለል አድርጉ ።

ከበረንዳው ማዶ ቮጥ — ቮጥ የሚል ድምፅ ይሰማል ምስኪን ፓርክ ፣ የዛሬ አርባ ዓመት የሰለጠነውን ወደቤት ሲገቡ ጫማ መጥ ረግ አሁን እንኳ አልዘነጋም ።ሁለት ጠርሙሶች ይዞ ሲመጣ የሐይለ ኛውና የበሰለው አልኮል ሽታ ቅድሞት ወደቤት ገባ ።

"እትዬ እስካርሌት ብዙ ፈሰስብኝ ። ከጠባብ ጉድጓድ አውጥቶ ወደ ጠርሙስ መቅዳት በጣም አስቸጋሪ ነው ።"

"ምንም አይደል ፓርክ — አመሰግናለሁ ።" ጠርሙሱን የመመን ጨቅ ያሀል ጭብጣ ስትወስድ የዚህ የሰንበተ መጠጥ ሽታ አፍንጫ ዋን ወጋት ።

"ጠጣ አባባ !" አለች ዊስኪውን በአክብሮት ወደ አጁ ገፋ አድ ርጋ ። ሁለተኛውን ጠርሙስ ውሃም ወሰደች ። ጀራልድ እንደትንሽ ልጅ በታዛዥነት ተቀብሎ ከፍ አድርጉ ደቅ—ደቅ—ደቅ እያረገ ይጠጣ ጀመር ። ውሃ እንዲደባልቅ እንጂ ብትሰው በእንቢተኝነት ራሱን ነቀ ነቀ ።

ውስኪውን ጭብጣ ለመጠጣት ወደ አፉዋ ስታስጠጋ መጠጣ ትዋን የማይደግፉ ዓይኖቹ ተከተሏት ።

"ሴት ልጅ አልኮል መጠጣት እንደሌለባት አውቃለሁ" አለች ባጭሩ ። "ዛሬ ግን አባባ እኔ ሴት ልጅ አይደለሁም ፣ ደሞም ብዙ የሚሠራ ሥራ አለ ።"

ብርጭቆውን ጋደል አድርጋ ትንፋሽዋን ዋጠችና ፈጥና ተጉነ ጨች ። ኃይለኛው መጠጥ ቁልቁል በጉሮሮዋ እያቃጠላት ወርዶ ሆዷ ሲገባ አፍን አደረጋትና እንባዋ በዓይኗ ሞላ ። እንደገና ትንፋሽዋን ዋጠችና መጠጡን ከፍ አደረገች ።

"ኪቲ እስካርሌት" አለ ጀራልድ ከተመለሰች ጀምሮ ለመጀመ ሪያ ጊዜ ትዕዛዝን የተላበሰ ድምፅ እያሰማት ።

@OLDBOOKSPDF

"ይቀጥላል ። አልጠይቅም ደስ ይለኛል አታውቂም ። ሞቅ— ያደርግሻል ፤ ደግ አይደለም ።"

"ሞቅ —ያደርግሻል ?" ደስ ምግይል ላቅ ሳቀች ። "ሞት ማድረግ አይደለም እንደሚያስከረኝም ተስፋ አለኝ ። ስክር ለማየትና ሁሉን ለመርሳት እፈልጋለሁ ።"

ደነገጠና ጠጣች ። አንድ የመቀት ብቡር ይም ሥርጥ ላይ ወጣ ። ጀርግንዴዋ ጋለ ፤ ፊትዋ ቂማቂም መሰለ በዚችዋ ሁለ ጣቶችዋ ላይ ሳይቀር ተግተርትረው ወጡ ።ይሄ የልብታ እሳት ምን ዓይነት የተቀደሰ ስሜትን ይሰርጸል እባክችሁ ! ! እንደበረዶ የቀዘቀዘውን ልብዋን እንኳ ዘልቆ ሊያሳለው በሥራ አክሳትዋ ጉልበት ናፕላት ። የጂራልድን ፅንቆቅልሽ የጭብትና የተቀየመ ፊት አይታ ጉልበቱን ችብ ችብ እድርጋ እነደገና የሚወደውን ደግታ ፈገግ ለማሰት ሞከረች።

"እንዴት ለብ ያደርግሻል አባባ ፤ ያንተ ልጅ አይደለሁም እንዴ ! ከከሳይተን ዘር የተወረሰ ጠንካራ ጭንቅላት የሌለኝ መሰለህ ?"

ከሞላ ጐደል ፈገግ አለ — ደክማ ፊት ። ሚስኪው እሮጎፉው ነው ። መልሳ ዊስኪ ሰጠችው ።

"አሁን ልላ መጠጥ ይጌመሐህ ። ከዚያ በሁዋላ መደ ፎቅ ይሄይህ ሄጂ አልጋህ ላይ አስተኛሀለሁ ።"

አራቢን ተጭጣጠረችና ለማሰብ ሞከረች ። እንዴ ይሄክ ዋድን ስታጎጋር የምትጠቀምበት የአጎጋር ዘይቤ ነው ። አባቷን እንዴት ብላ እንዲህ ትናገረዋለች ። ትወር ነው ጋጣወጭነት ። ግን እሱም የምት ናገረውን ያጸምጣል ።

"አዎ ፤ አልጋህ ላይ አስተኛሀለሁ ።" አለች ጨመረችና "ሌላም መጠጥ ምናልባትም በጠርሙሱ ያለጣች ሁሉ እለጥሀና አስተኛሀለ ለሁ ።እንቅልፍ ያሻህል ።ልጅህ ካቲ አስካርሌት እዚህ በመኖሩዋ ስለ ምንም ነገር መጨነቅ የለብህም ። በል ጠጣ ።"

በታዛዥነት እንደገና ጠጣ ። ከንዱዋን በክንዱ ጠልፋ ልታነ ሣው ፈልጋ ጮተችው ።

"ፖርክ . . ."

ፖርክ ጠርሙሱን ባንድ እጁ ጂራልድን በሌላኛው እጁ ያዘ ። አስካርሌት የሚበራውን ሻማ ብድግ አድርጋ ያዘችና ሶስቱም ተያይዘው በጭለማ አዳራሽ ቀስስ እያሉ ሽቅብ በጠመዝማዛው ደረቅ ወጡ። ወደ ጂራልድ ክፍል ሄዱ ።

@OLDBOOKSPDF

ሱዌለንና ካሪን ወንበር ላይ ተቀምጠው የሚያቃስቱበትና በሞራ ተንከሮ ብርሃን የሚሰጠው እራፊ ያለበት ከፍል እንዳንድ ነገር ይሸታል ። መስኮቱ ሁሉ ዝግትግት በግለቱ የመድሃኒቱና የታመቀው አየር እስካርሌት ገና በሩን ከፈት ስታደርግ አፍንጫዋን ወጋትና አጥወለወላት ። ዶክተሮቹ በታፈነ ክፍል ውስጥ ትኩስ አየር ሲገባ ደግ አይደለም ይላሉ እንጂ እሷስ እዚህ ከምትቀመጥ ሞቷ ይሻላታል ። ጓባችና ሶስቱንም መስኮቶች ከፍታ የጥርኳውን ቅጠሎችና የአፈር ሽታ ያዘለውን አየር አስገባች ። ነገር ግን ለሳምንታት ታጅሎ የቆየውን የቤቱን ጠረን ትዴሉ አየር ገፍቶ ለማስወጣት አቅም አነሰው ።

ካሪንና ሱዌለን ገርጥተውና ንጥተው ያረሾሙ ባለአራት ጠርዝ ፣ ከዚህ ቀደም በዴቴ ግዜ ሳንቀው ያንሸካሸኩበት በነበረው አልጋ ላይ ፣ አይናቸው ፈጦ ጣራ ጣራ እያዩ ቀጋድመዋል ። እጥ ላይ ኤለን ከሰሻና ያመጣችው የፈረንሳይ ሥራ ፣ ከራሱና ከአማሩ ጠምዛዛ የሆነ ባዶ አልጋ ይታያል ። ኤለን ቅጭኛ የነበረው እዚህ ላይ ነው ።

እስካርሌት ሁለቱን እህቶችዋን ቁልቁል በመጠየፍ ዓይን ተመለከተቻቸው ። ለረሾም ግዜ ባዶ ሆድዋን ቆይታ የጠጣችው ውሲኪ ሥራውን ሠርቶዋል ። ስጉሰንዴ እህቶችዋ እሩቅ ይመስሏትና ያልተያያዘውና ወጥነት የሌለው ንግግራቸው እንደነብሳት ጥዝጥዝታ ነው የሚሰማት ። እንጾኖና ደግሞ ልቅውና ገዝፈው አይኑዋ ላይ እንደመብረቅ ፈጥነው ድርግም ይሉባታል ። ድነም መቼም አጥንቱዋን ሠር ስር ነው የገባው ። ስግግም የጠዙ ቀን እንቅልፍ የጠዙ ቀን መኾታ ያስፈልጋታል ።

ምነው ጋደም ብላ እንቅልፍ በመሰዳትና እናትዋ ኤለን እንደድሮው በቀስታ ንቅንቅ ፣ ንቅንቅ እድርጋ ቀስቅሳት "እስካርሌት እረፍ ዲል እኮ ። እንደዚህ በንፍ አትብይ እንጂ" ብትላት ምናለ ። ይሄ ግን የአለም እንጀራ ነው ዛሬ ። እዱ ! ከሱዋ ምራቅዋን ዋጥ ያረገችው በጥበብ የምትልቃቅና ጭንቅት የሌለባት ኤለንጋ መሄድ ብትችል ኖሮ ። እራስዋን እደረቱዋ ላይ የምታንጋልልባት አንዲት ሴት ብታገኝ ፣ የትጫናትን ሸክም የምታራግፍበት ጫንቃ ያለው ሰው ብታገኝ ፣

በሩ ተከፈተና ዲልሲ የሜላኒን ልጅ ታቅፋ በአንድ እጅዋ የውስኪውን ጠርሙስ ይዛ ገባች ። ጭስ ባፈነው አጠራጣሪ ብርሃን ውስጥ ዲልሲን ስታያት ከዱሮው ከስት ብላ የሀንድ ዘር ደሙዋ ጠርቶ ይታያል ። የፊትዋ አጥንት ገጦ ወጥቷል ። የተገተረ አፍንጫዋ ይብስ ሾሏል ። የመዳብ ቀለም ያለው ቆዳዋም የንጣት ፍካት ይታይበ

@OLDBOOKSPDF

ታል ። ያለቅ የተቀደደ ተመልሶ ከአይ ኤመገብዋ ድረስ ተከፍቶ የብ
ረት ቀለም ያለው ጠትዋ ፊት ለፊት ይታያል ።የሚላኒ ልጅ የዕም
ቡዋ ሮዝ አበባ ከንፈሩን በስስት ወደ ጥቁሩ የጡትዋ ጫፍ ልኩ
ይመጠምጣል፡ ይጠባል። እናትዋ ጉያ እንዳለች የድመት ግልገል በት
ናንሽ እጅቹ እዚህም እዚያም ጡትዋን ሞቡድ ሞቡድ ያደርጋል ።

እስክርሌት አረፍት በማጣት ተንሳቹና የዲልሲን ክንድ ያዝ አደ
ረገቹ ።

"እዚህ መቅረትሽ የሚያስመሰግንሽ ነው ዲልሲ።"

"አባትም እኔንም ልጂንም ከገዙኅና እናትም እንደዚያ ደግ ሆነ
ውልኝ ከየሁኝ ወዲያ እንዴት ብዬ ከንዚያ ከማይረቡ ኔግሮዎች ጋር
እሄዳለሁ ፤እትዬ እስክርሌት ?"

"ተቅመጪ ዲልሲ ።ልጂ ስመጥባት እንዲሞቹም ብትቀ
መሙ ይሻላል ። ወይዘሮ ሚላኒ እንዴት ነች ?"

"ይሄ ልጅ ከመራቡ በስተቀር ምንም ችግር የለበትም ።እኔ ደሞ
ህጻን መመገብ ያለበትን ነገር ይዣለሁ ። ወይዘሮ ሚላኒ በጣም ደህና
ናቹው ።በፍፁም ሰሞት እያበቃቹውም ።እትዬ እስክርሌት አይዞዎት።
እንደሳቹው የጠቆሩም የገረጡም ብዙ አይቻለሁ ። መድኪማቹውና መበሳ
ጨታቹው እንዲሁም ለአራሱ ልጅ መጨነታቹው ነው እንጂ ምንም
አልሆኑ እኮ ። እኔ ዝም አለኝህዋቹውና እዛ ጠርሙስ ውስጥ ከነበረው
ጥቂት ሰጠሁዋቹው ።አሁን ደህና ተኝትዋል ።

እንግዲህ በዚህ ዓይነት ያንን የህል ዊስኪ የተነለገለበት ቤተ
ሰቡ በሙሉ ነው ማለት ነው ።እስክርሌት ፡ለዋድም በተሰጠውና ትክ
ትኩ ይሻለው እንደሆን ብላ አሰባ ነበር ። ሚላኒ እንግዲህ አትሞትም ።
እና አሽሊይ ቢመጣ...ወደቤት ቢመለስም... አያያይ ! ይሄንን በኋላ
ብታስብ ይሻላል ።አቤት በኋላ የምታስበው ነገር ብዛቱ !አቤት ወደ
ፊት አስብበታለሁ ፡ወደፊት እወስናለሁ ያለችው ነገር ብዛቱ! የሀሳብ
ዋን ሰዓት እስክዘላለሙ ለመማፋት ብትችል እንዴት ማልማል ነበር ።
ወዲያው በተሰባበረ ቅንት መናገር ጀመረች ። ቆይቶ ግን እንድ
ቸር—ቸር የሚል ድምፅ የፀጥታውን ኬላ ሰብሮ ተሰማ ።

"ማዬ ናት- ልጆቹን በስፖንጅ ልታጥብ ውሃ ስታዘጋጅ ነው።
በብዙ መታጠብ ያበፈልጋቸዋል ። " አለች ዲልሲ የውስኪውን ጠር
ሙስ በመድኃኒት ብሮታመች ማህል ከእንድ ብርጭቆ ኤጠገብ እያ
ስቀመጠች ።

እስክርሌት በድንገት ሳቀች ።የጥንቱን ትዝታዋን የሚቀስቀስ የት
ድንድ ውሃ ደምጽ ስትሰማ ሕሞሳትዋ ይርገበገባሉ ። ፊትዋ ኩራት

@OLDBOOKSPDF

እንደተላበሰ ስትስቅ ዲልሲ ትክ ብላ ታያታለች ። እስካርሌት ጉዳ
ዩን ዲልሲ የተረዳችላት ይዘው ነው መስለት ። ወንበሩ ውስጥ ተመልሳ
ቁጭ አለች ። ጥብቅ አድርጎ የያዛትን መቀነትዋን ሊያንቃት የደረ
ሰውን የአንገት ማሠሪያና እግሩን የሞሸለቁዋትን ባቧራና ባቸዋ
የተጣሉ ነጠላ ጫማዎች ብታወልቃቸው ደስታዋ ነው ።

ያ የጎመድ መግተቻ መሽከርከሪት በዝግታ እየተንቀጫቀጨ
ባሊውን ከጉድንዱ ወደ ኧናት ያስጠጋል ። ከትንሽ ጊዜ በሁዋላ እኩ
የእናትዋ ሞግዚት የነበረችውና አሁን የራስዋ ሞግዚት የሆነችውን
ማሚን ታገኛታለች ። ዝም ብላ ተቀመጠች ። ምንም ነገር የምትፈልግ
እትመስልም ። አራሱ ልጅ ወተት ፊቱ ላይ እንደተዝረከረከ የቅርብ
ወዳጁ የሆነውን የጡቱን ጫፍ ለመፈለግ ይወራጫል ። ዲልሲ ጡት
ዋን ወደአፃኑ አፍ እያስተካከለች ፀጥ ብላለች ። እስካርሌት የማሚን
ጹሀ ታዳምጣለች ። አቤት የማታው አየር እርጭ እንዳለ ነገር! እያንዳ
ንዱ ኮሽታ በእስካርሌት ጆሮ እንደባሀር ሞገድ ጮሃ ትጣባለች ።

ማሚ በዛ ሚዛን በሚያኑላ ክብደትዋ የላይኛውን አዳራሽ
ወለል ማም—ማም እያለጎች ወደበሩ ስትመጣ ሕንፃው የሚናድ
መሰለ ። ማሚ ትከሻና ትከሻዋን ቁልቁል የሚጎትቱ ሁለት የእንጨት
ባልዲዎች በማራና በቀኝ እጁዋ ይዛ ወደ ክፍሉ ገባች ። ጥቁሩ ደን
ፊቷ ለምን እንደሆነ የማይታወቅ የሐዘን ሃሳብ ያዘለ የዝንጀሮ ፊት
መስሉዋል ።

ግና እስካርሌትን ሲያዩ አይኖችዋ ቦግ ብለው በሩ ። ባልዲዎቹን
እመፊት ስታስቀምጥ ጥርሱዋ ብልጭ አለ ። ይሄኔ እስካርሌት ተን
ደርድራ ጥቁር ከንጭ ታቅፎ ባሳደገው የማሚ ደረት ላይ ልጥፍ
አለች ። ይሄ ደረት ያረጋጋል ፡ ይሄ ደረት ከዱሮዎቹና ካልተለወጡት
ነገሮቹ ማህል ነው ። ብላ አሰበች ፣ ግን ማሚ ስትናገር ይህን ሀሳብ
በሙሉ ሰረዘችባት ።

"ጐሽ የማሚ ልጅ ቤቷ ገባች !!ውይ እስካርሌት አሁን እማማ
ኤለን እመታብር ገብተው ምንድነው የምንሰራው፣ እስካርሌት ፣ ከሳ
ቸው ጐን እመታብሩ ውስጥ ብተኛ እንዴት በወደድኩ! ያለ እማማ
ኤለን ምንም ለመሥራት አልችልም ። ከእንግዲህ ችግርና ሥቃይ ብቻ
ነው የቀረን —የጭንቀት ሸክም ! ። "

እስካርሌት በማሚ ደረት ላይ እንደተንጋለለች ሁለት ቃላት
ሐሳቡዋን ወሰዱት—"የጭንቀት ሸክም" ። እነዚህ ቃላት ነበሩ ትክት
አስኪላትና እስኪያማት ድረስ የዛን አለት ከሰዓት በኋላ ጭንቅላትዋ
ውስጥ ይደውሉ የነበሩት ። አሁን የቀሩትን የመዝሙሩን ስንኞች
በደከመ ልቦና አስታወሰች ።

@OLDBOOKSPDF

"ሥጣር ይኑረው እንጂ ከቢድ ሜና ጭንቀታችን
መቅለሉ አይቀርም እድሮ፣ መንገድ ለመንገድ ውሏችን፣
ከባዱን ሸክም ልናወርድ፣ ጥቂት ቀናት ብቻ ቀሩን!"

"ሥጣር ይኑረው እንጂ" አለች በአዕምሮዋ በድጋሚ። ይሄ ሸክማ አይቃለልላት ይሆን? ወደ ቃራ መምጣቷስ ጭንቀትዋን የሚያቅሙላት ሳይሆን ይብስ ሸክም የሚጨምርባት ሊሆን ነው እንዴ? ከማሚ ክንድ ወደ ላይ ተንስታ ወየታ በእጁዋ ጥቁር ጉንጩዋን መታ መታ አደረገቻት።

"የኔ እመቤት—አቤት እጅሽ! በሞትኩት" ብላ ማሚ የተሞሸላለቀውንና ደም የቋጠረውን የእስካርሌትን እጅ በከፍተኛ የመደናገጥ መከፋት ዓይን ተመለከተችና

"እስካርሌት ምነው ስንት ጊዜ ልንገርሽ፣ ሴት ልጅ ሴትነትዋ የሚረጋገጠው እጁዋን በማየትና.....አዪ የኔ እመቤት ፊትሽ ደማሞ እንዴት እንዲህ በፀሐይ ተጠባበስ!"

ምስኪን ማሚ ጦርነትና ሞት በእናትዋ አንገቦ ሲያልፍ እንኳ እንደነዚህ ባሉ ጥቃቅን ነገሮች መጨነቋን ግና አልተወችምዘ አሁንም በዚህ ጉዳይ በጣም ጥንቁቅ ናት። እንግዲህ ደሞ ትንሽ ቆይታ እጃቸው የተሳሳጠና የሸከረ ሴቶች ባል አያገኙም ልትላት ነው። እስካርሌት አስቀድማ ተንብያለች።

"ማሚ፣ እኔ የምፈልገው ስለ እማማ እንድትነግሪኝ ነው። አባባ ስለእሷ ሲናገር ማዳመጥም ያስጠላኛል።"

ማሚ ባልዲዎቹን ልታነሳ ጐንበስ እያለች እንባዎችዋ በዓይኑዋ ችርፍፍ አሉ። ዝም ብላ ተሸክማ ወደ አልጋው አጠገብ ወሰደችና የሱዌለንንና የካሪንን የማታ ልብስ እየገፈፈች ማንሳት ጀመረች። እስካርሌት በደብዛዛው ብርሃን ውስጥ ወደ እህቶችዋ አየች ካሪን ተቀዶ የተሰፋ ነው እንጂ ንፁሕ ቢጃማ ለብሳለች። ሱዌለን የአየርላንድ ሥራ በሆነ ወፍራም ጠርዝ ባለው ባረጀ መጐናፀፊያ ተጠቅልላለች። ማሚ ያለቀ አራፊ እንደአሰጋንጅ እየተጠቀመች የልጆቹን ያላበው ገላ ስታደራርቅ እያለቀሰች ነው።

እስካርሌት እነዚያ ዋጋ ቢስ፣ የማይረቡ፣ ውርደታም የሆኑ ነገሮች—እነዚያ የስላተሪ ቤተሰቦች ናቸው እማማ ኤለንን የገደሉዋቸው። እኔ ደግሚ ደጋግሚ ስማይረቡ ሰዎች ውለታ መሥራት አይበጅም ብዬ ነግሬያቸው ነበር። ነገር ግን እሳቸው—እማማ ኤለን

@OLDBOOKSPDF

ልባቸው አልችል አይላቸው በድ ጎጠቅ ቃቸውን ሁሉ እምቢ ማለት እይሆንላቸውም ። ”

“ስላተሪዎችን” ብሳ ጠየቀች እስክርሌት በድንጋጤ ። “እንዴት እዚህ ሊመጡ ቻሉ?”

“ታመው ነበር” አለች ማሚ ሁለቱን ልጆች እርቃን ገላቸውን በእራፊው ጨርቅ እያሸችና ውሃው እየወረደ አንሰላውን እያራሰው ። “የአሮጊቷ የወይዘሮ ስላተሪ ልጅ ኤሚ በእንጀት ተስቦ በሽታ ተለክሱ ነበር ። ወይዘሮ ኤልሲንግ እዚህ መጥተው ሰእማማ ኤለን ከለእርቦ ማኖለኝ እሚቱ ይታችንል ። ሁልጊዜ በመጨረሻ እንዲሁ ነው የሚያድርጉት ። ለዎን ልጅቻቸውን እራሳቸው አያስታምሙምን እማማ ኤለን እዘት ፤ እናም ክባድ ቢሆንም አስብበታለሁ አሉ ። በኋላም እዚያው ድረስ ሄደው ኤሚን ያስታምሙዋት ጀመር ። አየሽ እስክርሌት ፤ እራሳቸው እማማ ኤለንም እኮ ጤነኛ አልነበሩም ። እና ትሽ ለረቹም ጊዜ ታመው ነበር ። ሲዛውም እማማ ኤለን ሲበሱ የወ ፍን ያህል ነው ። እኔ ስንት ጊዜ ነግርኳቸው— ተዉ እነዚህን የማ ይረቡ ነጮች ይራቁዋቸው ብሳቸው አልሰማ አሉኝ ። ታዲያ ኤሚ ተሸሳት ሲባል በሽታው ካሪንን አፈፍ አደረጋት ። አዎ እመቤት ፤ የእንጀት ተስቦ ያዘሽች ገምብ ወደ ካሪን በርራ ሰከፈቻት ። የሱዋ ሲገ ርመን ሱዌለንም ተደገመች ። ስለዚህ ወይዘሮ ኤለን ሁለቱን ልጆች ማስታመም ያዙ ። ”

ያ ሁሉ ጦርነት በየመንገዱ እየተኪያሄደ ፤ ያንኪዎች ወን ዙን አጽርተጠው ሲመጡ ሁሉ እኛ አናውቅ ፤ በዛ ላይ እነዚያ የቀን ጨያቱኞች በየጣታው እየጠሩ ሲጄዱብን እኔ ላብድ ምንም አልቀ ረኝ ። እማማ ኤለን ግን እንደዱባ ፍሬ እርግት ብለው በትእግስት ቀቀምጠው ነበር ። ልጆቹን ማስታመሚያ መድኃኒት ስለጠሩ ከመ ጨነቃቸው በቀር ምንም አልመሰሳቸውም ።

አንድ ቀን ማታ ሰአሥር ግዜ ያህል የልጆቹን ገላ በውሃ በራስ ጨርቅ ከጠረግኳቸው በሁዋላ እንዲህ አሉኝ፡—“ማሚ—ነብሴን እን ኳን ሸጨ ቢሆን ልጆቼ አናት ላይ የማያርገው በረዶ ባገኝ በገዛሁ” ኳን ሸጨ ቢሆን ልጆቼ አናት ላይ የማያርገው በረዶ ባገኝ በገዛሁ ”

“ጌታዬ ጄራልድም ሆኑ ሮዛ ወይም ሚና እዚህ እንዲገቡ አይ ፈቅዱሳቸውም።እኔን ብቻ የእንጀት ተስቦ ይዞ ስለለቀቀኝ እንድገባ ይፈቅ ዱልኛል። ከዚያ በሁዋላ እራሳቸውኑ ያዛቸው ፤ ቀሰፉቸው ። እስክርሌት፣ እንደማይድኑ ወዲያው ነው የገባኝ ። ”

ማሚ ቀና አለችና ነጠላዋን አጣፍታ እንባ ያረጠባቸው ዓይኖ ጅን አደራረቀች ።

@OLDBOOKSPDF

"በሽታው በጣም አጣደፋቸው፣አስካርሌት ። ያ ደግ ያንኪ ዶክ ተር እንኳን ሊረዳቸው ሞከሮ አቃተው ።ምንም ነገር አያውቁም —ድንገ አሉ ። ብጠራቸው ፣ ባናግራቸው አልሰማ አሉ ። የነሣ ሞግዚ ታቸውን እንኳ መለየት አቃታቸው ።"

"ለመሆኑ . . እኔን ጥሩልኝ . . . እጄንስ ጥሩልኝ አላለችም ?"

"አይ ፣ አልጠሩሽም የኔ ቆንጆ ። እራሳቸውን እንደ ትንሽ ልጅ አስበው ወደ ሳቫና ለመመለስ ነበር እቅዳቸው ። ማንንም ስም ጠቅ ሰው አልጠሩም ።"

ዲልሲ ነገሩ ቀስቀሳትና የተኛውን ህጻን ጉልበትዋ ላይ አጣ ድም አስተኛታ

"እንዴ እትዬ፣ ተናግረዋል እንጂ። እንደውም የሰው ስም ጠር ተዋል ።"

"እንቺ የሀንድ ኔግሮ ፣ የሀንድ ዲቃላ አፍሽን ዝጊ !" አለች ማሚ በማስፈራሪያ ኃይለ ቃል ፣ ወደ ዲልሲ አተኩራ ።

"ቆይ እስቲ ዝም በይ ማሚ !! ዲልሲ ማንን ጠራች ? አባባን ነው ?"

"የለም እትዬ ፣ጌቶችን አይደለም ! ነገሩ የሆነው ጥጣችን በእ ሳት የጋየ እለት ነው . . ."

"እንዴ ጥጣችን ሁሉ ወደመ ! እስቲ ንገሪኝ በሞቴ !"

"እምን እትዬ በሙሉ ድምጥማጡ ጠፋ ። ወታደሮቹ ጥጡን ሁሉ ወደ ሜዳው አግዘው ሲያበቁ ፣

"እስካሁን ጂምርጂያ ውስጥ ከታየው የእሳት ቃጠሎ ይህንን የሚያህል የለም ብለው እየተኩራሩ ደንፉና አወደሙት ።"

ሶስት ዓመት ሙሉ የተጠራቀመ የጥጥ ሰብል — መቶ ሃምሳ ሺህ ብር — ባንድ አፍታ እሳቱ በላው! እናም እሳቱ ሲንቦገቦግ የቀን ፀሐይ መሰለ። እኛ በጣም ፈራን። ቤቱ የሚቃጠል መሰለን። እዚህ እፎቱ ከፍል እንኳ ወላፈኑ በደንብ ስለሚበራ የወደቀ መርፌ ማንሳት ይቻል ነበር ። ብርሃኑ መስኩቱ ላይ ሲንፀባረቅ እማማ ኤለንን እንደቀሰቀ ሳቸው ሁሉ ብድግ ብለው ደግመው ደጋግመው "ፌሊፕ! ፌሊፕ !" እያሉ ጮክ ብለው ተጣሩ ።እኔ እንዲህ ያለ ስም ከዚህ ቀደም በፍ ፁም ሰምቼ አላውቅም ።ግን ስም ነው መቼም ፣እና ይጠሩት ነበር ።"

ማሚ የጨው አምድ ሁና ዲልሲን ትክ ብላ ታይ ጀመር ።እስ ካርሌት ግን አንገትዋን ደፍታ በእጅችዋ ውስጥ ቀበረች ። ፌሊፕ"

@OLDBOOKSPDF

ፊሊፕ ማነው አሉ ? ለእናቴስ ምኑዋ ነው ስሙን እየጠራች የም ታችው ?

* * *

ከአትላንታ ወደ ታራ የተጀመረው ረዥሙ ጉዞ አከተመ ። አዎ የጉ ዞው መድረሻ የኤሌን ክንዶች ይሆናሉ ተብሎ የተጀመረው ጉዞ ባያ ግድግዳ ሆነ መቆሚያው ። ከአንግዲህ ወዲያ አስካርሌት ባባ ትዋ ጣራ ሥር የእናትዋን ፍቅር ከልርግብ ላባ እንዳትሰራ ምንጣፍ ተላብሳ እንደ ህጻን ልጅ ተንጋላ መተኛት አከተመ ።ቤቷ ። ቦር ብላ መጠጊያዬ የምትሰውና ቀና ብላ የምትሻው ምንም ነገር የለም ።መጣ ላመጣም ሆነ መጓላበዮ ይህን አሁን የደረሰችበትን የዓለም መጨረሻ ለማለፍ አያስችላትም ።በሚንቃው ላይ ሸክሟን አጣሸኝ ብላ የምት ጭንበት ማነም የለም ። አባትዋ አረጀ ሕጥሉንም አጣ ። እህቶችዋ ታመዋል ።ሜላኒ ደክማ ልፍስፍስ ብላለች ። ህጻናቱ አቅም የለሽ ረዳት የለሽ ናቸው ። ጌግሮምቹም እንደሆኑ የኤለን ልጅ እንደ እናቷ ሁሉ ምሽግ ትሆነናለች ብለው የቀሚስዋን ጫፍ ይዘው እንደ ህጻን ዓይን ዓይንዋን የሚያይዋት ናቸው ።

በመስኩት ሰታይ እየወጣች ባለችው ጨረቃ ደብዛዛ ብርሃን ውስጥ ታራ ዝርግት ብላለች ። እግሮምቹ ሁሉ በንነዋል ። እርሻዎቹ ምድረ —በዳ ሁነዋል ። የዶሮ ማርቢያምቹ ዶጋመድ ሆነዋል ። አይ ነዋ ስር እንደሚደማ ሰውነት ይታዩዋታል ። ልክ እንደገዛ ራሱዋ ቀስስ እያለ እንደሚደማ ገላ ።ዋ፣ የመንገድዋ ሁሉ መጨረሻ ደሄ ይሁን—በእርጅና የሚንቀጠቀጥ ሽማግሌ፣በሽታ፣የተራቡ ጉሮሮዎች፣ቀሚ ስዋን የሚገሙት ረዳት ያጡ እጆች ። በዚህ የመንገድ መጨረሻ ላይ ምንም የለም ። ያለችው የአሥራ ዘጠኝ አመቷ የሙት ሚስት አስ ካርሌት አሃራ ሃሚልተን ካንድ ትንሽ ልጅዋ ጋር ብቻ ናት ።

ይህን ሁሉ ችግረኛ ምን ታድርገው እንግዲህ ወ/ሮ ፒቲና የበር፡ ቤተ ሰቦች ሚላኒንና ህጻን ልጁዋን ወደ ማከን ሊወስዱላት ይችላሉ።

ልጆቹም ሻል ካላቸውና ካገገሙ አለን ቤተሰቦች ጋ ቢፈልጉም ባይ ፈልጉም ይሄዳሉ ። እሷና ጀራልድም አጐት ጀምስና አንድሪው ዘንድ ይሄዳሉ ።

አፊቷ ያሉትን ቀጫጭን ቅርጾች አንሶላቸው አላያቸው ላይ ርሶና በላብ መንቸክ ተመለከተች ።ሱዌለንን አትወዳትም ።አሁን ድን ገት ፍንትው ብሎ ታያት ። በፍጹም ወዳት አታውቅም ። በተለይማ ካረንን በጭራሽ ወዳት አታውቅም —ደካማ ከሆነ ማንንም ሰው አት ወድም—ነገር ግን የሷው ደም ፣ የሷው ቅጅ ፣ የታራ ልጆች ናቸው ።

@OLDBOOKSPDF

የለም ነአክስቱ ቤት ተቀምጠው ሕይወታቸው ማለፍ የበዛትም። እንደ ደግ ፡ ዘመድ ቤት መሞት የለባቸውም ። የአሣራ ሸር እንደ መናጢ ደሃ የደሀልጅ በምዕሞት እንጀራ ተቆራምዶ ሊኖር ነ— ምን ሲደረግ ዘሙራሽ አይሞከርም ነ

ከዚህ የሞት አፋፍ ነሞት ጫፍ ማምለጫም የለም ይሆን ነየኔ ከሙ አዕምሮዋ ተስ እያለ ነው የሚያስበው ።አየሩ ሙሃ እንደሆነና እንደሚነበድ ሁሉ እጅግን በመዘራ ብድግ አደረጎችው ። የመጠጡን ጠርሙስ ኩብርጭቆዎቹ ማዘል ብድግ አድርጋ ተመለከተችው ።ትንሽ ዊስኪ አሙለው አለ ።ምን ያህል እንደሆነ ግን ለመናገር ብርሃኑ በደ ንብ አያሳይም ።ያ ሽታ እንደበፊቱ አፍንጫዋን አልወጋውም ።ይገር ማል ፤ ልመደችግ። ተስስ አያለች መጠጣት ጀመረች። አሁን ግን እንደ ቅድሙ ማቃጠሉን ተት ሰብ እያረጋት ነው የሚወርደው ።

ባያውን ጠርሙስ አስቅመጠችና ሁሪያዋን ትመለከት ገባች። አቤት መቼም ይሄ ሁሉ ሕልም ነው ። ደብዛዛው ሙስ ያፈነው ከፍል፡ በዘሽታ የሚሣትቁት ልሽኘዶች ቅርጽ የለሽ ሁኔታና ግዙፍ ሆኖ የምትደበለበለው ማሚ ፡ መጎብ ሃመስለችው ዲልሲና ጥቁር ጠትዋ ላይ የተኛ ርዝ ሀዛ. . ጠ. . .ይሄ ሁሉ ህለም ፤ ህልም ነው ። እማደብት የሚፈበበሙኑ ሥጋ ለማሽትት ነኤንፎምኙን ጣራ ዘለቅ ሳት ለመሰማት ነበየኢረሽው ላይ ሽትብ ቁልቁል የሚሉትን ተሽከርሪ ምች ድምፅ ለመስማትና የኤለንን በቀስታ የሚቀሰቅስ እጅ ለማ የት የምትጎበት ህልም መሆን አለበት ።

ከዚያ አራስዋ ክፍል ሙስዋ መሆኑዋ ታወቃት ። በግፋ አልጋዋ ላይ ፡ የጨረቃ ጭላንጭል ብርሃን በትንሹ እየገባ ማሚና ዲልሲ ልብሱዋን እያወለቁላት ነው ለካ ። ጥብቅ አድርጎ ይሰዋት የነበረ ውን መቀነትዋን ሲፈቱላት አስከላንባዋ ጫፍ ድረስ በእርይታ ተንፈሰች ።

የእግር ሹራብችዋን ሲያወልቁላት ፤ ማሚ በሹክሹክታ የእንክብካቤ ታላትን እየተናገረች የተላጠ እግሩዋን ላለማስነካት ተጠንቅቃ ሸተት አድርጋ አወጣችላት ። እግሩዋን ያጥቧት ጀመር ። እንዴት ይቅበትባል! እንደሕጻን ልጅ በዚህ ውሃ ውስዋ እንዲህ በምጾት መቆየት እንዴት መታደል ነው ! ተንጠራራችና ዘና አለች ። ከዚያ አንድ ዓመትም አንድ ሰኮንድም ሊሆን በሚችል ገዜ ውስጥ ብቻዋን ቀረች ። የጨረ ቃዋ ብርሃን እየተመመ መጥቶ አልጋው ላይ ሲፈስስ ቤቱ ፉ ክልሎ በራ ።

መስከርዋን አላወቀችም ነበር ። በድካምና በውስኪ መስከርዋ አልገባትም ነበር ። የምታውቀው ነገር ቢኖር የደከመ ሰውነትዋን

@OLDBOOKSPDF

ዝግትግት አድርጋ ጥሏት ከሰጠችኝም በላይ ስለምትፈራኝ ሀሙም በሌለ በት ፣ ሥቃይ በልለበት ሳለም ውበዋ መማባቷንና አእምሮዋ ሥጋዊ ያል ሆነ ፣ አካላዊነት የሌለው የጠራ ዓለም ሲያሳያት መቆየቱን ብቻ ነው ።

ሁሉን ነገር በአዲስ ዓይን ነው የምትመለከተው ። ወደ ታራ በሚያመጣው ረጅም መንገድ ላይ የሴትነት ጠባይዋን ጥላለች ። ወደ ኋላ ትታው መጥታለች ። ከእንግዲህ አዲስ ልምድ የሚቀርጽባትን ሁሉ መክተብ የምትችል የፕላስቲክ ሸክላ አይደለችም ። እንደለብ እት ተጣጠፍምና ። በዚያ የዓመት እስያ በሆነ ከፉ ቀን ውስጥ ውስጥ ፤ ለግላጋና ተጣፊ የነበረው ያ ፕላስቲክ ሸክላ ሰውነትዋ ጥንክር ብሏል። ይች የሚሬዋ ምኽት እንደሰማን እንክብካቤን መሻትዋ የሚያክትም ባት የመጨረሻይቱ ምሽት ናት ። ጠጣትነቱዋ አብቅቶ እንግዲህ መ.ሰ ለት ወይዘሮ መሆንዋ ነው ። ልጅነት አለፈ ።

የለም ፣ ወደ ጀራልድ ም ሆነ ወደ ኤለን ቤተ ሰቦች ፊትዋን መመለስ የለባትም ። የአሻራ ዘሮች ምልክዋት ተቀባይ ሆነው አያ ውቁም ። እሳቶዎች ፊላቸውን ይችላሉ ። ሽክሞቿ የጣዛ ራስዋ ዕዳዎች ናቸው ። ሽክሞች ሁሉ ሊሸከማቸው የሚችልን ጠንካራ ሜንታ ይሻሉ። በራስዋ ላይ ሊደርስባት የሚችሏውን የመጨረሻውን አለቃቂ ነገር በዓይኑዋ በብርቱ ከናቸ ወዲያ ከእንግዲህ የሚመጣባትን ሁሉ በብ ርቱ ሜንታዋ ለመሸከም እንደምትችል በመገረም አሰበች ። ታራን አትከዳም ። እንዚያ ቀያይ አርሻ ቦታዎች የእሱዋ ይዞታዎች ከመሆ ናቸው ይልቅ እሱዋ የነሱ ይበታ መሆኑዋ ይመዝናል ። የቷ የዘር ሐረግ አንደጥዋ ሰብሉ ሁሉ የቀዩን እፈር ደሙን ጠጥቶ ሥጋ ውን በልቶ ያፈራ ነው ። ታራ ውስዋ ጽኑታ ትጠብቃለች ። ታራ ንም ትጠብቃታለች ።

አባቷን ፣ እህቶችዋን ፣ ሜላኒን ፣ የኤሽሌይን ልጅና ኔግሮዎቹን ለመጠበቅ መቻል አለባት ። ነገ ። አዎ ነገ! —ብቻ ይንጋዘ ነገ ሽን ዟን ጠበቅ አድርጋ ትነሳለች ። ነገ ብዙ የሚሰሩ ነገሮች ይኖሩዋ ታል ። ወደ አሥራ ሁለቱ ዋርካዎችና ወደ ማኪንቶሽ ሠፈር ሄዳ እነዚያ የተራቆቱ የእትክልት ቦታዎች የተረሱትው ነገር እንዳለ ታያ ለች ። ወደ ረግራጋው የጠንቡ ጸርቻም ሄዳ ዳክዬዎችና ዶሮዎች ይኖሩ እንደሆን ታረጋግጣለች ። የኤለንን ጌጣ—ጌጥ ይዛ ወደ ጅንስ ቦሮና ወደላቭጀይ ሄዳ የሚበላ ነገር የሚሸጥላት ሰው ትፈልጋለች ። መቼም በድጭን አገር የተረፈ ሰው አይጠፋ ። ጭንቅላትዋ እንደገር ግዳ ሰዓት እጀታ ፤ ነገ—ነገ— እያለ ፤ ትክ—ትክ— ትክ ይላል ። ነገዋ ጥርት ብሎ ታያት ።

ወዲያው ሁልጊዜ እየሰለቻት ትእግሥት እያጣችና ትክት ብላ ታዳምጣቸው የነበሩት የቤተ ሰቧ አፈ ታሪኮች በመጠኑም ቢሆን

@OLDBOOKSPDF

የጥረጓቸው ፍንትው ብለው ፊት መጡባት ። አም ፡ ጄሬ ልድ ቢሳ ቤስቲን ሳይኖረው ታራን መሠረተ ። ኤለን በሐዘን ኀብታ ከነበረችበት አዘቅት ወጥታ ነው ለመግ ለማዕረግ የበቃ ችው ። አያትዋ ሮበላንድ ናፖሊዮን ዘውድ ከጫነ ወዲያ አገር—ለቆ ተሰደ· ሀብት ያፈራና ዕድሉን በጀርሚያ ለም ምድር ላይ ያቀና ሰው ነው ። ቅድመ—አያትዋ ጥሩዶም የግይቲን ጫነ መንጥሮ የሞቱች ግዛት ኳደረገ በሁላ እሷንም አጣና ታፍሮ ተከብሮ ለመኖር ወደሳቫና መጥቶ ቤት ገጀውን የመሠረተ ነው ። እስካርሌቶች የሚባሉትም ዘሮች ከአየርላንድ ሀገር—ወዳጆች ጋር ሰንጸይቱ አየርላንድ ሲሞጉ ፡ ለቆሰለችው አርነታቸው ሲሉ የተሰቀሉ ናቸው ። አግራዎ ችም የራሳቸው የሆነውን ባለማስነካት ጦመው አስከመጨ ረሻው ዳርቻ የተዋደቁ ናቸው ።

እም ፡ ሁሉም ከሞት—አራቱ ደርሰው ያልሞቱ ፡ የመደቡስ እጣ ፣ጥሟቸው ደቅቀው ያልበነኑ ናቸው ። ነገሥታት ሲጋጩ ፡ ባሪያዎች በእምቢተኝነት ሲነሱም ሆነ በጦርነት ፡ በእሙጽ ፡ ባዋጅና በውርስ ሰዓት ያልተበገሩ ዘሮች ናቸው ። አጉል እጣ—ክፉ· እጣ አንገታቸውን ሰብሮዋቸው አንደሁ· ነው እንጂ ልባቸውን አልገደለውም ፤ ቅስማ ቸውን አልሰበረውም ። በታኝ ፡ አንገሸገሸኝ አላሉም ፡ ተዋጉ ፡ ተዋደቁ። ቢሞቱም ሙልፊት ሳይሉ ፡ ከሰዛቸው ሳይፈናቀሉ ነው· የሞቱት ። ሥጋቸው አለፈ ሥራቸው ተረፈ ። እንዚያ ሁሉ ደማቸው በደም ሥሩዋ ሙሰጥ የሚፈስ እንደጥላ ያለፉ ሕዝቦች በዚህ የጨረቃ ብርሃን ቦግ አድርጉ ባበራው ክፍል ውስጥ አንድ በአንድ በቅስታ የሚሄዱ መሰለ ። እስካርሌት እኢሀን ዘር ማንዘሮቹዋን ማየቱዋ አልገረማ ትም ። እኢሀ ቆራጥ ሰዎች አጉል ዕድል የጫነባቸውን ክፉ መከራ አቅልጠውና ቁጥቅጠው አቃንተው እንደሚመች እንደሚያምር ያደ ረጉ ናቸው ። የእስካርሌት ዕጣም ፤ ወጊያም ታራ ናትና ድል መምታት አለባት ።

አንድ ጥቁር ግርጃ አእምሮዋን እየዳኸ ሲያጥነው ጥውልግልግ ብላ በአንድ ጐኑዋ ተገላበጠች ። እኢሀ ሰዎች በእርግጥ አጠገቡዋ መጥተው ታል አልባ ድፍረትን ይሰርፀባታል ? ወይስ ያው ሕል ሙዋ ነው ? "እዚህ ብትኖሩም ባትኖሩም ፤ አመሰግናለሁ ። ደህና እደሩ" አለችና በእንቅልፍ ልቧ አጉተመተመች ።

@OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ 25

በነጋታው ጠዋት ስትነሳ የእስካርሌት ስውነት መቼም የሱዋ አይደለም ። ያ ጋሪ ሲያንገጫግጫት የዋለውና ውጋት የሞላበት የእ ግር ጉሠ ሰውነትዋን ሁሉ ጉንበል አድርጎት አልራመድ አለች ። በሐ ሩር የነደደው ፈትዋ ቀይ ሆነ ። የተሞሸላለቀው እጁዋ ቆሳሰለ ። ምላስዋ ስንጥቅጥቅ ጉሮሮዋ ድርቅርት ብሎ በእሳት የተለበለበ መሰለ። ይሀንን ለማራስ በቂ ውሃ ይጥ አይመስልም ። ጭንቅላትዋ ሊፈነዳ ደረሰ ። ስትሦር እንኳ አይኗን አያጨናበሰች ነው ። ዱሮ በእርግዝ ናዋ ሰዓት ይሰማት የነበረውን ዓይነት ማቅለሽለሽ ተሰማትና ጠረ ጴዛው ላይ ተጠቡሶ የተቀመጠው ያም ፣ እንፋሎቱ ቦለለል ሲል ሽታው አል'ሰማሽ አሳት ። ሠድዋ አልቀበል አለ ። ጂራልድ ከባድ መጠጥ በጠጣች ማግስት እንዲህ ያለ ስሜት ሊሰማት እንደሚችል ሊነግ ራት ይችል ነበር ። እሱ ግን ሁኔታዋን የሚያይበት ዓይንም ሆነ የሚያጤንበት እንምሮ አልነበረውም ። ከጠረጴዛው ፊት ለፊት ተቀምጠዋል ። ግርጅፍ ብሎ አርጅቶ ግራጫ መስሏል ። ዓይኖቹ ከቦታ ቸው ሊጠፉ ደርሰዋል ። በር በሩን ያያል ። ጭንቅላቱን እንደአውራ ዶሮ ቆልመም አድርጎ የኤለንን ልብስ መንሿሿት የሚያዳምጥና ከው ስጡ የሚወጣውን የሎሚ ሽታ የሚያሽት ይመስላል ።

እስካርሌት ቁጭ ስትል "ወይዘሮ ኤለን እስክትመጣ እንጠብ ቃት ዛሬ አረፈደሽ " አለ በማጉተምተም ። ውስጧን የሚቀውራትን ቁና አድርጋ በመገረም ዓይን አየችውና ዞር ብላ ከጀርባው የቆመች ውን የማሚን ጭንቅት ያዘሉ ዓይኖች ተመለከተች ። እረፍት በሚ ነሳ ስጋት ከተቀመጠችበት ተነስታ እጅዋን አንጎትዋ ላይ አድርጋ አባትዋን በጠዋት ፀሐይ ብርሃን አየችው ። ቁና ብሎ ግልጽ ባል ሆነ አስተያየት ያስተውላታል ። ጭንቅላቱን ይነቀንቃል ። እጆቹ ይን ቀጠቀጣሉ ።

እስካርሌት ካሁን አሁን ጂራልድ ትዕዛዝ ይሰጣል ፣ ምን ምን መሥ ራት እንዳለበት ይናገራል ብላ ስትጠብቅ ሳታውቀው ብዙ ጊዜ አል ፏል ። ወይኑድ ትላንትና ማታ እኮ ደህና ነበር ። ትላንትና እንደተለ መደው እንኳ ባይጮሀና ባይጫወት ቢያንስ ውል ያለውና የተያያዘ ታሪክ ሲናገር ነበር ። አሁን አሁን ግን ፣ ኤለን እንኳ መሞትዋን ማስ

@OLDBOOKSPDF

ታወሰ አይችልም ። የያንኪዎች መምጣትና የኤሰን መሞት አንድ ላይ ተጸምሮ ናላውን አ'ስቶታል ። አስክርሌት መናገር ጀመረችና ማሚ እራሰዋን ነቅንቃ ሽማዋን የቀሰ አይኖትዋ ላይ ስታደርግ አይታ አቋረጠች ።

"ወይኔ ፡ አባባ ራሱን ስቷል ማለት ነው!" አለች በልቧ ። የታወከው ሞንቅላትዋ ደሞ በዚህ አዲስ ችግር የተከነከነ መሰላት ። "የለም፡ የለም በሦነው ሁሰ ደንዝዞ ነው ። እንደሀመም አይነት ነው ። አዙን ይሻለዋል ። ሊሻለው ይገባል ። ግን ባይሻለው ምን ላደርግ ነው ? እውይ አሁን ባላስበው ይሻላል ። እኔኑም ሆነ እናቴን ወይም ሌሎ ቹን አስከፊ ነገሮች አሁን አሰስባችውም ። እንዚህን ልትረዳቸው የማ ትችላቸውን ነገሮች ከምታስብ ይልቅ ልትረዳቸው የምትችላቸውን በርክታ ነገሮች ብታስብ ይሻላል ።

የምግብ ቤቱን ፡ ምንም ምግብ ሳትበላ ለታ መጣችና ወደ ጓሮ ሄዳ ፖርክ በባዶ እሣሩ ሆኖ የተጣፈች ቁምጣውን ለብሶ ደረጃው ላይ ተቀምጦ አተር ሲከካ አገኘችው ። ጭንቅላቱዋ ውስጡን ይደው ላል ፡ ይመቅራታል ። የጠዋት በሐይ አይኑዋን ይወጋታል ። ቁጥ ብሎ የመቆሙ ነገር እንኳ በጉ ፍታድናን ጠየቀ ። እናትዋ ሬግሮዎችን ስታ ናግር ሊኖራት የሚገባውን ያክተማረቻትን የማጫወት መሳ ሁሉ እር ግፍ አድርጋ ትታ በተኾሳት አጥር ምጥን አድርጋ ታወራ ጀመር ።

በቀጥታ ዋያቂ መጠየቅና ትዕዛዝዋን ማሸንዲንዱን ተያያዘ ችው ። የፖርክ ሽኑሽፍኑች ግራ በመጋባት ወደላይ ቆሙ ። ወይዘሮ ኤሰን ጫጩትም ሆነ ሁለሀብ ሰርቀው ብታሳኛቸው እንኳ እንዲህ ባጭሩ ማንንም ሁናግራ አታውቅም ። እስካርሌት ስለእርሻው ፡ ስለ አትክልቱ ፡ ስለመጋዘኑ ደማማ ስትጠይቅ ዓይኑዋ ውስጥ እንዲህ ያለ ቃጠሎ ፖርክ በጭራሽ አይቶ አያውቅም ።

"እዎ አትዬ ፤ ፈረሱን ባልዲው አጠገብ እንዳሰርኩት አፍንጫውን ከባልዲው ውስጥ እንደከተተው ሞተ ። የልም ፤ ላሚ ማን አልሞተ ችም ። አላወቁም እንዴ አትዬ ? እንድ ጥሻ ወለደች ትላንት ማታ ። ስለዚህ ነው እምበዋ የምትስው ።

"ያቺ ያንተዋ ፕሪሲ በጣም ጥሩ አዋላጅ ይወጣታል" አለች እስካርሌት በማሾፍ ። "እንደዚያ እምቢዋ የምትለው መታለብ ፈልጋ ነው አለች የኛ አዋቂ ።"

"አይ አትዬ ፡ ፕሪሲ ላም የማዋለድ ሙያ መች አላት-ና" አለ በዘዴ "እና ይሄ ጉዳይ እያከራከርም ፤ ያ ያንኪ ዶክተር እንዳለውም ለልጆቹ የሚያስፈልጋቸውን ወተት ይቺ ጥሻ ሙሉ ጊደር ስትሆን ቅቤም— ወተትም ይወጣታልና እናገኛለን ።"

@OLDBOOKSPDF

"ጥሩ እሺ ቀጥል ።የቀረ በብት አለ ለመሆኑ ?"

"ምንም አልቀረ እትዬ ። እንዲት ያረጀች ላምና ጥጃዋ ብቻ ናቸው ያሉት ። ያንኪዎቹ የመሙ አለት ወደረግረጉ ጫካ ነዳሁ ቀሯው ፤ አሁን የት እንደምናገኛቸው እግዚሃር ይወቅ ።ያቺ አመለኛዋ እኮ ናት ።"

"ግድየለም እናገኛቸዋለን። አንተና ፕሪሲ አሁኑኑ ፍለጋ ጀምሩ፤ ፖርክን ገረመው ፤ ክብሩ የጎንካ ስለመሰለውም ተናደደ ።

"እትዬ እስካርሌት ፤ ያ እኮ የእረኞች ሥራ ነው ። እሄ የቤት ለው የቤት እንስጋይ ኤማሮ ነኝ ።"

ዐይኗ በንዴት ባንዳፍታ ዳም ለበለ ።

"ሁለታችሁ ሂዱና ታገኙዋት እንደሆን አግኙዋት አለበለዚያ እናንተም እንደ እረኞቹ ጥፉ ከቤት" የፖርክ ዓይኖች አንባ አቀረሩ። "አይ ወይዘሮ ኤሰን ኖረው ቢሆንኮ በቤት — እንስጋይ ኤማሮና ሚዳ በሚውል እረኛ ማህል ያለውን ልዩነት አሳምረው ያውቁ ነበር ።

"ውጣ አሉኝ ፣ እትዬ እስካርሌት? ወጥቼ ወዴት አባቴ ልሂድ እትዬ ?"

"አላወቅልህም ፤ ጉዳዬ አይደለም። ብቻ ማንም ቢሆን ታራ ውስጥ አየኖረ ለልሰራም የሚል ሰው ያንኪዎቹን ተከትሎ መሄድ ይችላል። ለሌሎቹም እንዲሁ ብለህ ንገራቸው ።"

"እሺ እመቤት"

"እሺ ፖርክ የበቆሎውና የጥሁስ ነገር ምን ይሻላል ?"

"በቆሎ? ኧረ በእግዚአብሄር እትዬ እስካርሌት ፤ምነው ፈረሶቻቸውን ለቅቀውበት ። ፈረሶቹ ያሳጠፉትንና ያልበሉትንም ሰብስበው ሞነው ሂዱ ፤ እናም ተሽከረካሪዎቹንና ጋሪዎቹን ደግሞ በጥሙ ላይ ነዱበት ።ያላዩትንና ልብ— ያላሉትን ዛሮ የነበረውን ብቻ ሳይነዱ በት ቀሩ ።እሰሣም ቢሆን አራሙቻ የሞላው ስለነበር ሶስት ሸክም ብቻ ወጣው ።"

ሦስት ሸክም ። እስካርሌት ከዚህ ቀደም ታራ ምን ያህል ሸክም ጥጥ ታመርት እንደነበር አሰበችና ይብስ ራስዋን አመ ማት ። ሦስት ሸክም ። ይሄ እኮ ሰነፎቹ ስላተሪዎች ከሚያመርቱት ጥቂት ቢበልጥ ነው ።በዛ ላይ ቀረጡ ደግሞ በእንቅርት ላይ ጆር ደግፍ ነው ።የኮንፌደሬሲው መንግሥት ታክስ በጥሬ ግንዘብ ያስከፍል ነበር ።አሁን የተመረተው ግን በአይነት እንዳይከፈል እንኳ ቅረጡን የሚሸፍን አይደለም ። ሦስት ሸክም ምን አላት ፣ ብቻ ጥጥ ይለ

@OLDBOOKSPDF

ቅሙ የነበሩት ሁሉ ጠፍተው በሽሹበት ባሁኑ ሰዓት ለእሷም ሆነ ለኮንፌዴራሊው ምን የሚገርም ነገር ደንታ የሚሰጥ ጉዳይ ነው።

"እሱ ፣ ይሄንን አውን ባላስብ ይሻላል" አለች ስራሏ። "ደሞም ስለቀረጥ ማሰብ የሴቶች ጉዳይ አይደለም።ስለዚህ ጉዳይ አባባ ነው ማሰብ ያለበት። ዉ...አባባ! ስለሱም ባላስብ ይሻላል። ኮንፌደሬሲው ስለታከሱ ይጨነቅበት።አሁን የምፈልገው የምንበላው ምግብ ብቻ ነው።"

"ፖርክ፣ ወደ "አሥራ ሁለቱ ዋርካዎች"ና ወደ ማኪንቶሽ ሄዳችሁ የተረፈ ነገር እንዳለ አይታችሁ ኑራል? አትክልቱ በታ ምንም የለ ይሆን ?"

"የለም እትዬ፣ያንኪዎቹ ያገኙናል ብለን ፈርተን ከታራ ንቅን ቅም አላልን።"

"እንግዲያው ዴልሲን ወደ ማኪንቶሽ እልካትና እኔ ደግሞ ወደ "አሥራ ሁለቱ ዋርካዎች" እሄዳለሁ። እዛ ሄዳ የሚበላ ነገር ታገኝ ይሆናል።"

"ከማን ጋር እትዬ ? ከሕዝቡ?"

"እኔው አራሴ ብሆንማ እሄዳለሁ። ማሚ ልጆቹን ትጠብቅ። ሚስተር ጄራልድ የሚችል..."

ፖርክ አስደንጋጭ ጩኸት ጮኸ። ከው አደረጋት። ምናልባት ያንኪዎች ወይም ባለጌ ኔግሮዎች ሊያገኙዋት ይችላሉ። ስለዚህ ወደ "አሥራ ሁለቱ ዋርካዎች" በሮራሽ ብቻዋን መሄድ የለባትም።

"በታ አንተዲህ ፖርክ ዴልሲን አሁኑኑ ተነሺ በላት። አንተና ፕሪሲ ደግሞ ላሟንና ጥጃዋን ፈልጋችሁ አምጡ።" አለችና ዞራ መንገድ ጀመረች።

አስክርሌት ፊት ከፖሪስ ድረስ ያመጣላትን ቆንጆ አረንጓዴ የፀጉር ጌጥ እያስታወሰች አበረንጓው ምስለ ሳይ ተንጠልጥሎ ያገኘችውን የማሚን አሮጌና ቀለሙ የለቀቀ የፀጉር ሽፋን አደረገች። ከዋርካ ቅርንጫፎች የተሠራውን ዘምቢል ብድግ አድርጋ በጓሮ በኩል ባለው ደረጃ ስትወርድ ራስ ምታት በተራመደች ቁጥር እስኪጠዘጥዛት ድረስ ይጠልዛታል። የራስ ቅልዋ ተንኳኳ።

ወደወንዙ የሚወስደው ቀይ መንገድ በወደሙት የጦር እርሻ ዎች ማህል እየተጠማዘዘ ይዘልቃል። ጥላውን የሚዎል አንድ ዛፍ እንኳ ስማላ አይታይም። የማሚን የራስ ሽፋን ዘልቆ ሰንጥቆ የሚገ

@OLDBOOKSPDF

ባው ጠራራ ከሠይ ቅመ ከይዘ ከይዘ ከይዘ

@OLDBOOKSPDF

ድንበቅ አደረጓችው ። እዚህ ቀዝቃዛ ውሀ ውስጥ ቀኑን ሙሉ ተቀምጠ ፣ ረጻት የለሽቹን የታሪ ዓይኖች ከማየት ርቆ ፣ የቅጠሎቹ ሽክሽክታና የውሀው በዝግታ መብሰክሰክ ብቻ በጥልጦን ገሌ በሚሰማበት ፣ እንዲህ ባለ ነፋሻ ቦታ መቀመጥ ምንኛ መታደል ነው! ግን ያለፈቃድዋ መጮማቷና ሰውኪንግን አጥልቃ በመንሁ ጸር ጸር በበቀሉት የውሀ አረንጓዴ ሪቦት ማህል ተሰቅሰል ዛርቻውን ይዛ ወረደች ። ዛርቹ ላይዋ ላይ እሞልተውባታል ። ያንኪምቹ ዋናውን ድል ድቡ ቢሰባበሩትም ትንሽ ወረድ ብሎ አንድ መቶ ያርድ ርቀት ላይ አንዲት ጠባብ በእግር የምታሻገር ድልድይ መኖሩዋን ታውታለች ። ድልድይዋን ተጠንትቃ አቋረጠችና ከማማሽ ማይል ወዲያ ወደሚገኘው "አሥራ ሁለቱ ዋርከምች" መንደር ሽቅብ ዳገቱን በዚያ የቀትር በሀይ ተያያዝችው ።

"አሥራ ሁለቱ ዋርከምች" ከሩት ሰዋሩ አንዳታቸውን አስጣው ቆመዋል ። ወሻሮ ከቀይ አንዶች ዘመን ጀምሮ እንደነበሩ ቆመዋል ። ብቻ ቅጠሎቻቸው በእሳት ተለብልበው ቡናማ ሆነዋል ። ቅርጫፎቻቸው አርፎ ድብን ብለዋል። እነዚህ ሁሪያውን የከበቡትን ያኔ ማርሚ ሞገስ የጉብበሰ ቤተ መንግሥት ይመስል የንበረው ፣ ነው በነሙ የተገጠ የጀን ሜነስ ቤት ጠቅሮ ከበለ መልኩን ተነፍቶ ይታያል ። የመጠጥ ማነ ነጋዴ የንበረው ጥልቀት ያለው ጉድጓድ የጠጮቹሩት የመሠረት ድንጋዮችና ሁለቱ ረዣዥም የጭስ ማውጫዎች በቦታው እንደነበር ምልክት ናቸው ። እንድ ረጅም የማይማዳ አምድ በአንድ በኩል ተገንድሰ መድቡ ያሞሩ የንበሩትን አረንጓዴ ቹብቹብ ቁጥቋጦዎች ያቋቁቷቸዋል ። በእሳት ጋይቷል ።

እስክርሊት እዚህ ማጸሁላይ የቱንደመ አምድ ላይ ተቀመጠች ። ዙራ ለማየት ትርኢቱ ልብ አቁስል ሆኗባት ነው ። ይሄ መልጨን የቁረ ምድረባዳ ከመቹውም ጊዜ የበለጠ ልቧን አደማት ። ባለማርማ ሞገሱ የሚከቦች ቤት ትቢያ ለብሶ እማሩዋ ሥር ተንጥፏል — አፈር ። ይህ ቤት በትህትና ይቀበላት የንበረ ፣ ትዝናናበት የንበረና እመ ቤት ለመሆን — ሚስት ለመሆን ያለመችው ሕልም ፣ እውን አልሆን ብሎ መና የቀረባት ፣ ትወደው የንበረ ቤት ነው ። ዛሬ እፊትዋ የመጨረሻ ክርስ መቃብር ውስጥ ገብቶ እመድ ለብሶ አየችው ። አንድ ጊዜ እዚህ ቦታ ደንሳለች ። በልታ ጠዋታለች ። የፍቅር ሳቅ ተሳስቃለች ። ሜሳኒ ለአሽሌይ ረጣ ስትል አይታ በቅናት የተንገበገበችበትም ቦታ ነው ። አዎ እዚሁ ቦታ ቀዝቃዛው የባፍ ጥላ ሥር ነበር፣ ቻርለስ ሐሚልተንን አገባሃለሁ ስትለው በሙጭኝ ስሜት እጁዋን ላምቅ ያደረጋት ።

@OLDBOOKSPDF

ሥጋ አሽሉይ! ሞተሀል ብዬ ነው ተስፋዬ። ይሀን መከራ ፡ ይሀን ጥፋት ባይንህ ብታየው የሚሰማህን ስሜት ልሸከመው አሰኝ ልሞ" አለች በዘሰባ። አሽሉይ የተሠረገው እዚህ ቤት ውስጥ ነበር።ግን ልጁም ሆነ የልጁ ልጅ እዚህ ሠርተን ሊደግስ ከቶ አይችልም።ማንም መሸሪ ከእንግዲህ ወደዚህ ቤት አትመጣም። ጥቅርን መላበስም ሆነ ልጅ መውለድን በዚህ ቤት ጣራ ሥር ልታደርገው ፡ አሸክናህሽ ልትሠንበት የተመኘችው ነገር ሁሉ ፡ ተረ ቢታ ።ቤቱ ሞቷል። ለጓስክርስት ቤቱ ብሄ ሳይሆን የሚከስ ዘር ማንዘሮች ሁሉ የሞቱ ነው የመሰላት።አመድ ውስጥ የተቀበሩ መስሏታል።

"ጓሉን አሠን ባላስባው ደሽሳል። አሠን ልቋቋመው አልችልም። ሌላ ጊዜ አስብበታለሁ።" አለች ድምፅዋን ጮላ አድርጋ ፡ በዓይኑዋ ወደሌላ አቅጣጫ እየጣተረች።

በፈራረሰው አካባቢ ሁሉ የአትክልቱን ቦታ ፍለጋ ተዘዋወረች። የዊክስ ልጆች እንደዛ ያፈቅሯቸው የንበሩት አበቦች ተረምርመው ተረብርበዋል። ከዛ ወደንርም ሄደች። ጭስ ማውጫው የጋየበትን አመድ አቋርጣ በዶቃ ማርቢያውም በዶሮ ቤቱም ውስጥ አለፈች። ከማጅዜቱ ሁሪያ የንበሩትን አትክልቶች ያጠረው የሽቦ ማገር ተዘጣጥሏል።በረድፍ በረድፍ ተተክሰው የንበሩትም አረንንዴ ኔፅዋት እንዳይሆን ሆነዋል። ያ ሰስሳሰውም ምድር የተሸከርካሪዎቹ ጉማና የከብት ዳሌ ጠባሳ ከታበቧታል።ቅጠሳቅጠሎቹም ከእሬር ተደባልቀዋል። እዚህም ሰደ የሚሆን አንዳችም ነገር ጠፉ።

ደሞ ተመለሰችና ቁልቁሰ ነጫቸው ቢወጣው ክፍሎች ጣ ጥጣ ሚዳውን እየሄደች "እዚህ ቤትየ" እያለች ጮሀ ተጣራች።አቤት የሚል አጣች። ወሻ እንኳን 'ዉ' አይልም። የዊክስ አሽከሮች ኔጣሮ ምቹ ሁሉ ነቅለው ሄደዋል ወይም ያንኪዎቹን ተከትለው ከድተዋል ሣለት ነው። እያንዳንዱ ባሪያ አንዳንድ በነፍስ ወከፍ የሚያርም የሚኮተኩተው የአትክልት ቦታ እንደነበረው ታውታለች።ስለዚህም እንደደረሰች እነዚህ ቦታዎች እንኳን ይተርፉሉ ብሳ ተስፋ አድርጋ ነበር።

መከራዋ ከንቱ አልቀረም።ነገር ግን ውሀ በማጣት ከወጣቸው የንበጠትን የጭመን ዘሮችም ሆነ ለያርተ ቢጫ ወርሀቸው አንድ ሐሙስ የቀራቸውን የባቄሳ ተክሎች ብታይም ደክሚት ስለነበር ስመ ጽሰት እንኳን አትም አጣች። አፈሩ ሳይ ጥውልግልግ ብሳ ተቀምጣ ተስፎ እያለች ዘምቢልዋን ትሞላ ጀመር። እንግዲህ ዛሬ ማታ ከጌመን ጋር የሚቀሰ ሥጋ ጠፉ እንኚ ታሪ ውስጥ ጥሩ ምግብ ተበልቶ ሊታደር ነው። ምናልባት ዲልሲ የቤት ዕቃ ለማውጣ የምትጠቀምበት ቅባት ምግ

@OLDBOOKSPDF

ቡን ለማብሰያ ሳይጠቅም አይቀርም ።ስለዚህ ሰመጥበሻ እንድትቀ
ጥብ መንገር አስላት ማለት ነው ።

የመጨረሻው ክፍል አጠንብ ስትደርስ ጥሬውን ሲበላ የሚችል
እንደ ቀይ ሥር ያለ ራዲሽ የሚባል አትክልት አጣጭትና ወዲያ
ውኑ ረሀብ ሆድዋን ቆረጣት ።በቅመም ያበደ ራዲሽ ነበር ለካ ልብዋ
ሊቋምጥ የቀየው ። አልብሏ ሳይ ያለውን አቧራ እንኳ ለማራገፍ ፋታ
ሲታጣኝ ማማሸን ቆረሰችና ባንዳፍታ ዋጥ ስልቅጥ አደረገችው ። የቆ
የና የኮመጠመ እንዲሁም የሚያቃጥል ስለሆነባት በዓይኑዋ እንባ
ሙልት አለ ። እባዶ ሆድዋ ውስጥ ምኔ ገባ ሳይባል ሆድዋ ታውኮ
እቆጣኛው ላይ አጥወልውሏት ተጋደመችና ያስመልሳት ጀመር ።

ያ ኔማሮ ኔማሮ የሚል ጠረን ያለው ከዝጥል የሚወጣ ሽታ ማቅ
ለሽለሹን አዘረታጎባት ። ለመከላከል አቅም አጥታ ቁቅ ማለቷን ስት
ቀጥል ምድር ሰማዩ ተሽከረከራባት ።ከዛራት ።

ከረጅም ጊዜ በኋላ ድክምክም ብላ መሬት በእርግብ ላባ እንደተሠራ
ሁሉ ተመችቷት ፣ ልስልስ ብሏት በማባራው ተደፍታበት ጭንቅላቷ
እዚህም እዚያም ይሮጣል ። ወሾ-ድ ፣ አስካርሌት አሣራ ሰው ሳይ
ሰማት፣ ሰው ሳያያት ጀጣም ታማ ጀጣም ደክማ ከኔግሮዎች መኖታ
ቤት ጀርባ በፍርስራሽና በውሃቂ ማህል ተዘርራ ወድቃለች ። በእርግ
ጥም ሰዉ ዛሬ ስለሱዋ ቢያውቅ በገዛ ራሱ የችግር ማዋ ውስዋ
ሰምጦ ማ ጉዳዬ ብሎ ሊጨንቅላት ነው ። ዋ ፣ ያቺ የወደቁ የእግር
ሹራበጅን ገንበስ ብላ የማታነሳ አስካርሌት አሣራ ፤ ያቺ የተፈታ
ነጠላ ሴማዋን ማሠሪያ ለመቆለፍ ስንፍ የምትለው አስካርሌት
አሣራ ፤ ያቺ ትንሽ አራስ ምታትም ሆን ትኩሳት ሲነካት ዕድሜ
ዋን ሙሉ የምታስታውሰውና የምታወራው አስካርሌት አሣራ ፤ ዛሬ
ይህ ሁሉ መዓት ይወርድባታል ።

እናም እንዲህ ተዘርራ ቢድና እንደተዘረጋጋች ትዝታንም ሆነ
ጭንቅን በጭራሽ ልትዋጋ በማትችልበት ስዓት ፤ ሀሳብና ጭንቀት
ሞተ አለሞተ እያለ ፈሳ እንደሚጠብቅ ጥንብ አንሳ እየገሠገሱ ከበ
ቡዋት ።አሁንስ "ስለእማማ ፣ስለአባባ ፣ስለአሽሌይና ስለዚህ ፍርስራሽ
— ልቋቋመው ስችል አስብቢታለሁ" ለማለት እንኳ በጭራሽ አቅም
አንሳት ።እርግጥ አሁን ልትቋቋመው አትችልም ።ግን ወደደችው
ጣላችም እንሱት ከማሰብ ልትቆጠብ አልቻለችም ። እነዚህ ሀሳቦች
ሹል ኩምቢዎቻቸውንና የተሳለ ሚጫሪ ጥፍሮቻቸውን ቀስረው
ጭንቅላትዋ ላይ ሰፍረው ይተኩትኩዋት ጀመር ። ከዚያም፤ ጊዜ ለማይ
ላከው ጊዜ ፣ሰዓት ለማይቆጥረው ሰዓት እጉዶፈው መሬት ላይ በማን
ባራዋ ተደፍታ የዐሐዩ ሐሩር አራስ አራስዋን እየመታት ፤ ያለቃ የተ

@OLDBOOKSPDF

ረሱ ነገሮችን ፣ የሞቱ የተቀበሩ ሰዎችንና ለእንዴም ለሁሌም የበነነ ኑሮዋን እያስታወሰች የነገውን ጨለማ ሕይወት ማሰላሰል ጀመረች።

በመጨረሻ ብድግ ብላ የከሰለውን የአሥራ ሁለቱን ዋርካዎች ፍርስራሽ እንደገና አሰተዋለችና ራስዋን እንዳቀናች የለጋነት የውበትና የፍቅር አንጻች ስሚት ከፊቷ ላይ ለዝንተ ዓለሙ ተገፍፎ ሲሄድ ተሰማት ።አንድ ጊዜ ያለፈው አለፈ ። እንዴ የሞቱትም ሞቱ በቃ ። በዱሮዎቹ ጊዜያት የነበረው ሀብትና ፀጋ ሁሉ ላይመለስ በነነ ። እናም እስክርሌት ከባዱን ዘምቢል አክንዱዋ ላይ ስታስተካክል እግረ መንገዷን አእምሮዋን ወዲያውም የራሷን ሕይወት አደላድላ አስ ተካከለች ።

ከእንግዲህ ወደኋላ መሄድ ፡ወደኋላ ማየት የለም ። ወደፊት ብቻ ።

በመላው ደቡብ ለሀምሳ አመታት ያህል ወደአለፉ ጊዜያትና ወደአለፉ ሰዎች አንገታቸውን ጠምዝዘው በምሬት ዓይን የሚመለከቱ ሴቶች እንዳሉና ጉስቁልናቸውንና ድህነታቸውንም ባለፈ ኩራታቸው ታቅፈው በትዝታ እየቆሰሉ ፡ብዙቱ ትውስታ እየደሙ የሞቀ መጡ መሆናቸው እውቅ ነው ።እስክርሌት ግን በፍፁም ወደኋላ ላት መለከት ቆርጣ ተፈጠመች ።

ጥላቸት ወደለበሱት ድንጋዮች ተመለከተች ።አሥራ ሁለቱ ዋርካዎች አንድ ጊዜ ፀጋ ተሳብሶ ፡በማርማ ሞገስ ደምቆ ፡የአንድ ነገድ ምልክት የአንድ ዘር የአንድ ቤተሰብና አኗኗር ማስታወሻ ሆኖ ቁሞ ለመጨረሻ ጊዜ ታያት ። ከዚያም ያ ከባድ ዘምቢል የክንድ ቆዳዋን እየሠረሠራት ቁልቁል ወደታራ መንገዱን ተያያዘችው ።

ረዘብ ዳዶ ሆድዋ ውስጥ አዛጋ ።በምሬት ጮክ ብላ እንዲህ አለች፡—

"እግዚሀር ምስክሬ ነው ፤ እግዚሀር ምስክሬ ነው ፤ ያንኪዎች በፍጹም ሊያጠፉኝ አይችሉም ።ከዚህ ሁሉ ማጥ ውስጥ አልፌ እኖ ራለሁ ።ከዚያ በኋላ በጭራሽ አልራብም ።ሕዝቦቼም አይራቡም ። እግዚሀር ምስክሬ ነው ከእንግዲህ ወዲያ ሰርቄ ዘርፌም ንድፍው ቢሆን በፍጹም አልራብም ።"

ከዚያን አለት ወዲያ ባሉት ቀናት ታራ እንደ ክሩሶ ምድረ በዳ ጭር ጭው ብላ ከቀረው ዓለም ተገንጥላ የበረሀ ደሴት ሆነች። ሌላው ዓለም ከታራ የሚርቀው በጥቂት ማይሎች ነው ። ነገር ግን በታራና

@OLDBOOKSPDF

በጅንሰቦሮ ፣ በታራና በጌቶ ከተሞች አገልግሎት በሳቸጀይ መሀከል ፣ እረ ሌላው ቀርቶ በታራና በሌሎች ዋነርሻ ቦታዎች ማህል ፣ በሺ የሚቆ ጠሩ ማይሎች ላይ የተዘረጉ የሚያናውዱ ማዕበሎች ያሉ ይመስላል። እርጌው ፊረሳቸው ዘመኑ ያሳቸው አንድ የመጓጉዣ መንገድ ተዘ ግቷል ። እነዚያን አድካሚ የቀይ አፈር ረሻዎች ማይሎች በእግር እን ዳይጓዙቧቸው እንኳ ጊዜውም አቅሙም አልተገኘም ።

አንዳንድ ጊዜ ወንብ ከሚሰብሰቧቸው እንጀት ከሚቆርጠው የዕለት ምግብ የማግኘት ሥራና ከአታክቹ ሰዎቹን ሌሎች የማስታመም ተግባር ማህል እስካርሴት ጀሮዋን አስጨንቃ የለመድዙትን የዱሮውን ዓይኑት ድምፅ ብሰማ ብላ በንቃት ታዳምጣለች ። እነዚያ የተለመዱ — በሚጸዳው ላይ የሚጫወቱ ሕፃናት ጨዋታ ፡ በአርሻ ቦታ ወደቢት የሚመለሱ ኃሪዎች ድምጽ ፡ ከማለሸ አካባቢ የሚመጣው የጀራልድ ቋጣ ፡ ከባቡር መንገድ የሚሰማው የተሽከረካሪዎች ሁካታና የጐረ ቤቱ ሰው ለምጣ ብጋለ እረፍት ሲመጣ የሚያሰማውን ሁሉ ታማጸመጥ ጣረች ። ነገር ግን መከራዋ ሁሉ ከንቱ ሆነ ። መንገዱ ሁሉ የዘምታ አዘቅት ወጠታል ። ከመንገዱ ላይም እየተንፀለለ የሰዎችን መምጣት ያበሰር የነበረው አቧራ ካለበት አልተነሳም ። ታራ በአረን ጓዴ ከረዛቱዎችና በቀደጉ ሚሻዎች የተከበበች ደሴት ሆናለች ።

በዓለም ላይ አንድ አካባቢ ፣ ሰዎች በራሳቸው ቤት ጣራ ሥር መልካም በልተው ፣ መልካም ጠዋታው ፡ ጥሩ እንቅልፍ ይተኛሉ ። በእንድ አካባቢ ኮረዶች በሰሰት ዙር የታጠሩ ጭሚሶቻቸውን ለብ ሰው እደ ከጥቂት ሰዎችታት በፊት ታደርግ እንደነበረው ሁሉ "እስ ከፊው ጠርነት ሲያበቃ" እያሉ በደስታ ይዘምራሉ ፡ ይጨፍራሉ ። ይሄኔ አንዱን መድፉና መትረየሱ እያስተጋባ ፡ ከተሞች እየጋዩ ጠርነት ተፋፍሞ ሰዎች በየሠፈሮታሉ ቤታቸው ቁስሎች ማህል አቁ ኖ ከ በሚበዙሉ የማማት ዝታዎች ውስጥ እየሞቱ ነው ።ይሄኔ እን ዱጋ አንሱ ሠራዊት በባዶ እግሩ መጠጊያ አጥቶ ሲያተጓዝ ፡ እየተዋጋ፣ እየተራበ እየተኛ ከተስፉ መቁረጥ በሚወለድ ጭንቀት ታንቆ ወድ ቋል ።ይሄኔ በጀርሚያ ተራሮች ላይ በልተው የጠገቡ ሰማያዊ ለባሽ ያንኪዎች ትልብ ፈረሶቻቸው ላይ ሆነው ፎዘባኔናሉ ።

ከታራ ባሻገር ነው ጠርነቱና ዓለም ሁሉ ያለው ። እርሻው ቦታ ላይ ግን አዕምሮን የሚያፋጥጠ የጣቱ ጠርነት ትዝታዎች እንጂ ጠርነትም ሆነ ሌለው ዓለም ፍሱም ። የውጪው አለም በባዶና ከፊል ባዶ በሆኑ ሆዶች ጥያቄ ሥር ተንበርክኳል ። ስለዚህም ሕይ ወት በሁለት ተዛማጅ ሀሳቦች ሁለት ቦታ ተሰንጥቃለች — ምግብና ምግብን የማግኛ ዘዴ ።

@OLDBOOKSPDF

ምግብ! ምግብ ለምንድነው ከአእምሮ ይልቅ ሆድ ቂሙን የማ
ይፈላው? ምንድነው ሆድ ከአእምሮ ይልቅ ረሻም ትዝታ ፣ ረጅም
ትውስታ የኖረው ? እስኪርሲት ልብ ድካምን መቋቋም ትችላለች።
ረሀብን መቻል ግን አይሆንላትም ። በየጠዋቱ ከእንቅልፏ ሙሉ
ለሙሉ ሳትነቃ ፤ ትዝታ ፤ ረሀብንና ጦርነትን ይዞ ጭንቅላትዋ ውስጥ
ከመግባቱ በፊት ፤ አልጋዋ ላይ ጥቅልል ብላ የለጋ ጥብስ ሽታ
ለማሽተት ትሞክራለች ። እናም በየነጋው ስትነቃ ምግብ ለማሽተት፤
እስኪያስነጥሳት ድረስ ታንፈገፍጋለች ።

ታራ ውስጥ እጠረጴዚው ላይ ፍራፍሬዎች ፣ ያም፣ የአተር ፍሬዎችና
ወተት አልጠፉም ።ነገር ግን እነዚህ ቀራ — ተርታ ምግቦች ፣ እነዚህ
ርካሽ ነገሮች እንኳ በበቂ አይገኙም ነበር ።እነዚህን ነገሮች በቀን
በቀን ሶስቴ ባየቻቸው ጊዜ እንዲያን የጭንቀቱን ምግቦች ፣ በሽማ
ብርሃን የደመቀውን ጠረጴዚና አየሩን እንደሽቱ የሚያውደውን
የትኩስ ምግብ ሽታ ያስታውሷታል ።

ስለምግብ ምን ያህል ጥልቅ ነበሩ ።ያኔ!ምን ያህል ብዙ
ነት ነበር! ጥበሰ ስጋው ፣ትክልት ፣ ብስኩቱ ፣ ብስል ከጥሬው ቅቤው
ትርፍርፍ እንዳለበት ፤ ለእንድ ጊዜ ገቢታ ይቀርብ ነበር ። በእንደኛው
የጠረጴዛ ጫፍ ላይ ያም ፣በሌላኛው ጫፍ የተጠበሰች ዶሮ አለች ።
ጥቅልል ሥጋ ቅባቱ በሚያብረቀርቅ የማሰሮ መረቅ ውስጥ ይዋኛል
ባበባ ሳህን ላይ የተንጎሻሸሩ የተሳጠ ሙክክ ያለ ባቄላ ይከመራል ።
ተጠብሶ የደቀቅ ሥጋ ፣ ከሰተክልት የተሠራ ሾርባ ፣ ካሮቱ ሊቆረጥ
በሚችል ውፍረት በተዘጋጀ ክሬም ተለውሶ ፣ ይቀርባል ። ሰላት ከምግብ
በኋላ የሚበሉ ነገሮች—ባለቸኮሌት ክምር ኬኮች አትክልትና ፍራፍሬ
ዎች ፣ ክሬም ከላይ የሚጠፈጠፍበት ድፍን ኬክ ለምርጫ ይቀርባሉ ።
ይገርማል የጊዜ ክፉ ጉሮሮ ዋጠው እንጂ ይሄ ሁሉ ባንድ ገበታ
ላይ የሚደረደር ምግብ ነበር ። ታዲያ የዚህ ሁሉ ጣፋጭ ምግብ ትዝታ
ምትና ጦርነት ገፍትው ያሳመጡባትን እንባ አመጣባት ። በየጊዜው
የሚያዛጋ ሆዳንም ከባድ ጉሮምርምታ ወደ ማጥወልወል ለወጠው
ማሚ እንዲኖራት ትጓጉት የነበረው የአሥራ ዘጠኝ ዓመት ልጅ
የምግብ ፍላጐት ዛሬ ሳታዘውና ላትፈቅደው ሠርታ በማታውቀው
አድካሚ ሥራ ምክንያት በአራት እጥፍ አደገ ።

የሆድ ነገር ታራ ውስጥ የሷ ብቻ አልነበረም ።ረሀብ ያጠወለ
ገው ፊቷን ሠር ባረገች ቁጥር ጥቁር ከነጭ የተራቡ ፊቶች አይናቸ
ውን ሲያቁለጨልጩ ታገኛለች ። ደሞ የእንጀት ተስቦ ቁራኞቹ ሱዌለ
ንና ካሪን በቅርቡ የረሀብ ጥፍር እንደሚቧጥጣቸው ግልጽ ነው ።

ሌሎችም በየበኩላቸው ያጉረመርማሉ፣—

@OLDBOOKSPDF

"እትዬ እስካርሌት ተጨማሪ ምግብ ክላገኘሁ እንዚህን ልጆች እላስታምምም ።"

"እትዬ እስካርሌት ሴላ ምግብ ክልጨመርኩ እንጨት መፍ ለጥ አልችልም ።"

"የኔ እንበላ እትክልት ክላገኘሁ መሞሴ ነው ።"

"የኔ ልጅ ሁልጊዜ ያም ነው እንዴ የምናበላው ?"

እዛ ቤት ካሉት ሰዎች ሁሉ የማታሞረመርም ፣ ከቀን ቀን ነጪቀ የሚወጣው፣ዕለት በዕለት እየመነመነች የምትሄደው ሜላኒ ብቻ ናት። ሜላኒ በእንቅልፍዋ እንኳ ታስትባብላለች ፡—

"እኔ አልራብኝም እኮ እስካርሌት ።የኔን ፋንታ ወተት ለዲልሲ ስጫት ። እሷ ልጆቹን በደንብ እንድታጠባ ይጠቅማታል ።የታመሙ ሰዎች እኮ ረሀብ አይሰማቸውም" ትላለች ።

ይሄ የጭምት ግትርነቷ ነው ከሴራቸው የሚነዘነዙ ድምጾች ሁሉ በላይ እስካርሌትን ያበሳጫት ።ሴራቸውን ሙሀም ፣አፈዛም ፣ ተቆጥታም ትመልሳቸዋለች ። የሜላኒን ፉክ ወዳድ አለመሆን ግን ምንም ልታደርገው አልቻለችም ። ፒፊሊድም ፣ ኔሳርም ዋድም ሚላኒን የሙጥኝ ይሏታል ። ምክንያቱም ሜላኒ ደክሟት እንኳ ቢሆን ደግ ፣ ሩህሩህና አዛኝ በመሆኑዋ ነው ።ይሄን ሰምታ እስካርሌት ራሱዋም እንደነሱው ሆናለች ።

በተለይማ ዋድ በጭራሽ ከሜላኒ ክፍል አይጠፉም ። ዋድ እንድ ነገር ሆኗል ፣ ብቻ እስካርሌት ምን እንደነካው ለማወቅ ጊዜ አላገኝ ችም ። ስለዚህ ማሚ ወለፋት ይዞታል ያለቻትን ተቀብላ ለዚህ መድ ሀኒት የሚሆን ሥራ ሥርና ቅጠል ደባልቃ ጋተችው ። ድንገተኛው መድሀኒት ግን ልጁን የባሰ አገረጣው ። ይሄን ሰምን እስካርሌት ዋድን እንደሰው አታየውም ። ተጨማሪ ችግር ፣ ተጨማሪ ሆድ ሆኖ እንበላው ሳጣ ልጂ ጥርስ አወጣ' አሰኝቷታል ። እንድ ቀን ይሄ ያፋጠጣት መከራ ሲያልፍ አብራው ቁጭ ብላ ልታጫውተው ፣ ልታስተምረውና ኤ— ቢ—ቢሲ— ዲ ልታስቆጥረው ትችል እንደሆነ ነው እንጂ አሁን በፍጹም ጊዜም ሆነ ፍላጉት የላትም ። ደሞም ሁልጊዜ እማር እማሩዎ ሥር እየተከተለ — በተለይ በተጨነቀችና ሀሳብ በያዛት በዓት — ሲያስቸግራት እየተቆጣች ትመልስዋለች ።

ልጁ በተቆጣችው ቁጥር በድንጋጤ አመዱ ቡን ስለሚል ዝም ብሎ ሲቆም ይብሱን ያበሳጫታል ። ያልገባት ነገር ግን ላዋቂና ለታላ ላቆቹ የማይታይ ሽብርና ድንጋጤ ከሱ ጋር ትከሻ ለትከሻ ተጋጥሞ

@OLDBOOKSPDF

እንደሚኖር ነው ። ደመቀ ከሠራው ጥበበ ሥጋውን የሚያሸብር ፍርሃት ፣ ከዋድ ጋር ይኖራል ። አልፎ ተርፎም ሴት ከእንቅል ፉም ያባንነዋል ። ሴሊት ያስመኸዋል ። ማንኛውም ያልጠበቀውድምጽ ያስበረግገዋል ። ቋጣ ሲሰማ ደግሞ ከያንኪዎች ጩኸት ጋር እየተማ ታበት ከፉኛ ይደነግጣል ። የያንኪዎች ድምጽ ከሚሰማ ደግሞ የጥሪ ሲን ቁንጮ ይመርጣል ።

የወረራው ዱብ ዕዳ ከመምጣቱ በፊት ከመደሰት ፣ ከመጫወትና ሰላማዊ ሕይወቱን ከማራመድ በቀር ሌላ ነገር አያውቅም ነበር ። ምንም እንኳን አናቱ ስለሉ ብዙም ግድ ባይኖራት ያ አየሩን ፍም ያለ በሰው የነበልባል ወላፈን ሰማይ ሲቀድና ጩኸቱ ጆሮ ሲያደነቁር ከየው አስፈሪ ምሽት በፊት ከጨዋታና ደስ ከሚል ኮልታፋ አን ደበቱ በስተቀር ከፍኖት አያውቅም ። ከዚያ ምሽት ወዲያ ነው ለመ ጀመሪያ ጊዜ እናቱ ከራ ታል ተናግራው በጥሬ የመታችው ። በፒች ትሪ ጐዳና ዳር ያለው የሸክላ ቤት ውስጥ የነበረውና እሱ የሚያው ቀው ሕይወት የዚያኑ ለት ማታ አንድያውን ጨለመ ። ያንን መሳይ ኑሮ ማጣቱም የማይቋቋመው ጉዳይ ሆነ ። ከኤትላንታ የሸሹ ለት ማታም ቢሆን ያንኪዎች ያሳድዱኛል ከማለት በቀር የሚሆነው ሁሉ አይገባውም ። አሁንም ቢሆን ያንኪዎች ካጎኑኝ ብትንትኔን ያወጡ ታል ። የሚለው ስጋት አልለቀቀውም ። እናም አስካርሌት ጮክ ብላ በቁጣ በተናገረችው ቁጥር የመጀመሪያውን የቁጣዋን ዕለት ያ የልጅ ነት ትዝታው እያመጣባት በፍርሀት ይርዳል ። አሁንም የብስጭት የቁጣ ድምጽና ያንኪዎች ፣ ባንድነት አእምሮው ላይ ታትመውበት እናቱን ከፉኛ ይፈራታል ።

አስካርሌት ልጁ እያራታት መሄዱን ብታይም ምንም ልታደርግ አልቻለችም ።አለፎ አልፎ እንኳ ማሰቂያ መዘለቂያ የሌለው ሥራዋ ፉታ ሰጥቷት የልጁን ሁኔታ ለማሰተዋል ጊዜ ስታገኝ ከልኩ በላይ ያስጨንቃታል ።እቅሚሰዋ ውስጥ ከመደበቁ የበለጠ ጭንቅ ጥበብ የሚያደርጋት ጉዳይ ሆኗል ። ከዚህ አልፎ ደግሞ ወደሚላኒ አልጋ እየ ሄደ ሲጠለልና በአርጋታ ሲጫወት ወይም የምታወራለትን ታሪክ ሲያዳምጥ ስታይ ብሽቅ ያደርጋታል ። ዋድ የ"አክስቱን" ኩሩ ድምጽና በፈገግታ የሚሰቀውን "ዝም አትልም እንተ ዋድኃላ ንግሬሀለሁ እንግዲህ እራሴን አታሳምመኝ ! "ወይም" ዋድ በፈጠረህ አትሞላ ቀቅ !" የማይለውን ንግግር ወድዷል ።

አስካርሌት ዋድን አቅፎ ለማጫወት ጊዜ ባይኖራትም ሜላኒ ከታቅፈው ግየት ያስቀናታል ።አንድ ቀን ከሚላኒ አልጋ ላይ በራሱ ቆሞ ሲወድቅና ሜላኒ ላይ ሲያርፍ አየችውና በጥፊ መታችው ።

@OLDBOOKSPDF

"መታመሚን ሳታውቅ ቀርተህ ነው እንደዚህ የምትወድቅባት ? በል አሁን ከዚህ ቤት ውጣና እደጅ እሜዳው ላይ ተጫወት ፤ እዚኾ ቤት ድርሽ ትልና ኋላ ወየውልህ !" አለችው ።

ነገር ግን ሜላኔ የሚያለቅሰውን ልጅ በደከመ እጅዋ ጐትታ አስ ቀረችው ።

"ሂድ እዛጋ ዋድ ፤አይዞህ ። እኔን ለመጣራት ብለህ አይደለም አይ ደል ? እስክርሌት ታይው ባክሽ ፤ ምንም አያስቸግረኝም ግዴለሽም ። እኔ አጠብቅዋለሁ ። እስከምድን ድረስ ልሥራ የምችለው ይህንን ብቻ ነው ። አንቺ እሱን ከመጠበቅ ሌላ መጓት ሥራ አለብሽ እኮ" አለች ሜላኔ ።

"ተይ እንጂ ሜሊ ፤ይሄን ያህል አራስሽን አትጣይ ። ነና በደንብ አላገገምሽም ። ዋድ እሆድሽ ላይ መውደቁ ደሟም ተስማምቶኛል ልትዪ አትችይም ። ዋድ ፤ ከዚራ መጂያ እነጠትህ አልጋ ላይ ባጎኽህ ቆዳህን ነው የምገፍህ ። ይሄን ለቅሰህኝ ደግሞ አቁም ። ሁልጊዜ ታለቅሳለህ ። ከእ ንግዲህ ትልቅ ሰው መሆን አለብህ ።"

ዋድ እንባ እየተናነቀው መጽሐፉ ለመደበቅ ሄደ ። ሜላኔ ከንፈ ሯን ትም ትም እያደረገች በአይኗ እንባ ማጥም አለ ። ማሚ ጥግ ቆማ ትርጓሜን ሁሉ ትመለከት ስለነበር ብና ሩና ሥንፈሰች ። ሆኖም ይሄን ሰሞን ለእስክርሌት ታል የሚመለስ ማንም የለም ። ሁሉም የተሳሰ ምላስዋንና ልወጣወጥ ያለውን እሱዋንኳን ይፈሩ ጀምረዋል ።

እስክርሌት ዛሬ የታራ ቁንጮ ፤ የታራ እመቤት ናት ። እንዲህ ያለ ቦታ እንዳለ እንዳሌሎች ሰዎች ሁሉ መደባለሥልጣንነት ከፍ ከፍ ብላለች ። እንደልብዋ የማዘዝ ፤ የመፍለጥ የመቁረጥ ፍላጐቷ ፣ ውስጠ ባህሪዋ ሁሉ ይፋ ወጣ ። በመሥረቱ ጨካኝ አልነበረችም ። የለም ፤ በመፍራትዋና በራስዋ ባለመተማመኑዋ ምክንያት ሌሎች የች ቦታ ማነሱዋን አውቀው አልታዘዝ እንዳይሉዋት ፣ ሲሥልጣኑዋ አል ገዛ እንዳይሉዋት በመስጋት ነው እንዲህ ጨካኝ የሆነችው ። ከዚህም በላይ ደግሞ በበታቾች ላይ ቢመጣህ ሲርበተበቱ ማየት ደስ የሚል ነገር በመሆኑም ነው ። እስክርሌት ይህንን ስታግኝ ለደከመ ሕዋሳትዋ እፎይታን ሰጥቷቸዋል ። በእርግጥም ወባይዋና ሰብዕናዋ መለወጡን ሳታይ አልቀረችም ። አንዳንድ ጊዜ በቁጣ ስታዝዘው ፖርክ ለምቦጩን ሲጥልና ማሚ "አቁ ፤ ዛሬ ጊዜ አንዳንድ ሰዎች ከልኩ በላይ ይባልጋሉ" እያለች ስታጉረመርም ስትሰማ ያ መልካም ወባዬ የት ደረሰ ብላ ትገረማለች ። ያ ሁሉ ኤለን ልትቀርፅባት ትጥር የነበረው የአጨዋወት ወግ ፤ያ ሁሉ ልትከትብባት ትሞክር የነበረው

@OLDBOOKSPDF

ኩሩነት የበለጣ ተዝቃዛ ውሽንፍር እንደመታቸው ቅጠሎች ረገፈና ጠፉ ።

አለን ደግሞ ዶጋማ "ልጄ ቁርጠኛ ሁኚ ፣ ነገር ግን በበታችኞ ችሽ በተለይም በባሪያዎች ላይ ኩራት ይኑርሽ "ትላት ነበር ። ዳሩ ምን ያደርጋል ኔልሶራ ብትል ባሪያዎቹ በሙሉ ማድ ቤት ተሰብስበው ፣ እግር የቤት ሠራተኛ እንጂ የሚዳ እረኛ ፣ የቀን ሠራተኛ የማይ ሆንበትን ደግ ግዜ እያሰታወሱ ያማርራሉ ።

"እሀቶቸሽን ጠብቂያቸው ፣ አፍቅሪያቸው ። ለተጨዱ ሩሀሩህ ሁኚ። ለተቸገሩና ለተንሳቅሉ መውደጃሽን ስጫቸው ።" ትላት ነበር ኤለን ።

አሁን ግን እሀቶቿን ማቅቀር አልቻለችም ። እነሱ ለጫጉላ ያ ሽከም የሆኑ በደን ነገሮች ናቸው ። እነሱን ለመጠበቅም ከሆነ በየቀኑ ላላቸውን ታጥባቸዋለች ፣ ቦዩራቸውን ታበጥርላቸዋለች ፣ ሌላው ቀርቶ በየቀኑ ረዥም መንገድ በእግሩዋ እየሄደች ቅጠሳ ቅጠልና አትክልት ፈልጋ ትመገባቸዋለች ። ደግሞስ ያቺ አስፈሪ እንስሳ ጭራዋን ባወዛ ወሸባት ቁጥር ልሂች ጉሮሮዋ ውስጥ ቀብራ አይደለም እንዴ ላም ማለብ የቀጣሪችው ፣ ደግ የመሆኑ ነገር ግን እንደው ጊዜ ማጥፋት ነው ። እሁን ከልኩ በላይ ደግ ልሁንላቸው ብትል ጭራሽ ከአ ልጋቸውም አይነሱ ። ለራሺ መቼ በጥንሱና አራት የእርዳታ እጆች በተጨመሩልኝ ስትል እዛው ብኝተው ይቅሩ ማለት የማይሆን ነገር ነው ።

እነሱ ከቀን ቀን እያማመና እየቃሰቱ አልጋቸው ላይ ተጋድመ ዋል ። እዚያ ነፍሳቸውን ሲያወጡ እንደተኙ አለም ተለዋውጧል ። ያንኪዎች መጥተዋል ። ባሪያዎቹ ሁሉ ሄደዋል ። እናታቸውም ሞታ ለች ። እንዚህ ምስት የማይታመኑ ድርጊቶች ተፈጽመዋል ። ጭንቅ ላታቸው ሊቀበሳቸው አልቻለም ። እንደውም እንዳንዴ እራሳቸው ንክ እንደሆኑና እነዚህ ነገሮች ሁሉ እንዳልተፈጸሙ አድርገው ያስ ባሉ ። እስካርሌትም በጣም በመለዋወጥዋ ፣ ያለጥርጥር የጹሮዋ እስካር ሌት አይደለችም ። አልጋቸው ግርጌ ቆማ ሊሻሳቸው እንዲሠሩ የምት ፈልገውን ነገር ስትደረድርላቸው እንዲት አጭበርባሪ ምስል እንጂ አሰ ይም አትመስላቸውም ። እንዚያ በመቶ የሚቆጠሩ ሥራውን ሊሠሩ የሚችሉ ባሮች የሉም የሚባለው ነገር ፤ በፍጹም የማይጥሳቸውና የማይገባቸው ጉዳይ ነው ። የእሳራ ልጅ ፣ የእሳራ እመቤት የጉልበት ሥራ ትሠራለች ቢሏቸው አይገባቸውም ።

"የኔ እህት" ትላለች ካሪን ያ ጣፋጭ ፊቷ በበሽታ ጥቁርሽ ለጣ "የኔ እህት ፣ እኔ ሽማ አልጭርም እጂ ይበላሻል !"

@OLDBOOKSPDF

"እስቲ የኔን አይውሞ ትሳለች እስካርሌት የተሳጠውንና ሻከሮ የቸረቸፈ እጅዋን ወደቧ ዘርግታ ።

"ለእኔና ለሕጻኑ እንዶዚህ ስታወሪ በጣም ታስጠይቂለሽ ። እንደ መሰለኝ ግን በመዋሸት ልታስፈራሪኝ ነው የምትፈልጊው ። ወይኔ እማማ እዚህ በኖረች እንዲህ ስታወሪ ዝም አትልሽም ነበር ። ወይ ጉድ አሳት እንድጂ ትይኝ እንዴ !" ብላ ጮኸችባት ሱዌለን ።

ሱዌለን ቅስሰ እንዳለች ወዶታላቅ እህቷ ተመልከታ እስካርሌት እንደው ለሸር ብላ እንጂ ከልቧ እንዳሰለችው ገመተች ። ሱዌለን ከሞት አፋፍ ነው የተረፈችው ። እናቷን አጥታለች ። ስለዚህ ብቸኛ ሁናለች፣ ፈርታለች። የሚንከባከባት ፣ አይዞሽ የሚላት ትሻለች ። እስካርሌት ግን በየቀኑ እየመጣች ፣ ተሸፈቸው እንደሁ ማየት ፣ እንደ ኩል የጠሩ ዓይኖቿን እግድም ወርውራ ወደከልጋው እግር እያስተዋለች፣ ስለጨንነታቸው ማበረታቻና ስለአልጋ ማንጠፍ ፣ ምግብ ስለማብሰል ፣ ውሀ በባሲ ስለመሸከም እንዲሁም እሳት ስለመሞር ታወራለች ። ዶሞ እንዲህ ያለ አስቀያሚ ነገር እያወራች ደህና ነገር እንዳደረገች ውሲ መደሰትዋ ይባስ ።

እም ፣ እስካርሌት ይሄ ነገር ያስደበታታል ። ባሪያዎቹን እንደክብት መን ዳት ፣ እህቶቿን ማጣደፍ ፣ ስሜታቸውን ማንከታከት ፣ ራስዋ በመጨነ ቅዋ ብቻ ሳይሆን ፣ ራስዋ በጭንቀት በመወጠርዋና በመድከምዋ ብቻ ሳይሆን ፣ ምሬትዋን ፣ የኑሮ ዓለትዋን ስለሚያስረሳትና እናትዋ ስለሕይ ወት የነገረቻት በሙሉ መሳሳዝን ለማረጋገጥ ሰትል ደስስ ይላታል ።

እውን እናቷ ያስተማረቻት ነገር ሁሉ ዋጋ ቢስ ሆኖዋል ። የእስ ካርሌት ልብ ኮምጣጣና በፅንቀቅለሽ የተሞላ ነው ። ኤለን ልጆቿን ያሳደገችበት ሥልጣኔ ይንኳታኰታል ብላ እንዳልተነበየች እስካር ሌት አውታለች ። ልጆቿ ይውድበታል ብላ የገመተቻቸውም የማህ በረሰቡ ቦታዎች ይጠፉት ብላ እንዳልጠረጠረች ግልጽ ነው ። ኤለን እንደሱዋ ዘመን ያሱ የክፉ ጊዜዎች ወደፊት እያጋጥሚትም ብላ መሆን አለበት እስካርሌትን ኩሩ ፀጋን የተላበሰች ፣ የተከበረችና ሩህ ሩህ ትሁትና እውነተኛ ሁኚ ያለቻት ። እነዚህን ከተማሩ ፣ ሕይወት ራሷ ሴቶችን ትቀበላቸዋለች ፣ ታቅፋቸዋለች — ትል ነበር ኤለን ።

እስካርሌት ተስፉ በመቁረጥ እንዲህ ብላ አሰበች ። "እሷ ያስተ ማረችኝ ነገር አንዱ እንኳ አይበጀኝም ! አሁን ደግነት ምን ይረባኛል ! ኩራትስ ምን ዋጋ አለው ! ልክ እንደ ባሪያዎቹ ጉንበስ ብዬ መቀ ፈር ወይም ጥጥ መልቀም ብማር የበለጠ ይጠቅመኛል ! ዋ እማማ ! ምንኛ ተሳስትሽ ኑሯል !"

@OLDBOOKSPDF

የኤለን የተደላደለ ዓለም አልፎ በቦታው ጨካኝ ዓለም መቱ ካቱን ፣ በቦታው ዋጋውና ሚዛኑ ሁሉ የተለወጠ ዓለም መተካቱን ከማ ለብ አልተቆጠበችም ። ለሷ የታያት ወይም የታያት የመሰላት እናቷ መሰላቷና ይህን ያልተዘጋጀችበትን ዓለም በፍጥነት መጋፈጥ እን ዳለባት ነው ።

ለታራ የነበራት ስሜት ብቻ ነው ያልተለወጠው ። ወደቤቷ ስት መጣ አይጫጫናትም ። ሚዳውን አድርጣ ነጩ ሕንጻ አንገቱን እሰግ ስታይ ልቡዋ በፍቅር ማበጡንና ወደቤት በመመለስ ደስታ መዋ ጠን በጭራሽ አልተወም ። በመሰኩቱዋም ብቅ ብላ አረንጓዴውን መስክ ፣ ቀዩን ሚዳና ጥቅጥቅ ያለውን ረግረግ ጫካ ስታይ የውበት ስሜት ሳያጥለቀልቃት አልቀረም ። ለዚህ ምድር ያላት ፍቅር ፣ በቀይ አፈር ለተሞሉት ጥቅልል — ጥቅልል ላሉት ኮረብታዎች ፣ ደም የመሰለ ቀለም ለለበሰው ለዚህ የተዋበ መሬት ፣ ቀይ ማዕድን ከሚያፈል ቀው ማህፀኑ ለሚወጣው ሸክላ አፈር ፣ ለቀዩ ሠፈፍ ንጥረ ነገርና ነጭ ነጭ ለጣለባቸው ደማቅ አረንጓዴ ቁጥቋጦዎች ያላት ፍቅር ፣ ሁሉ ነገር ሲለወጥ ያልተለወጠ ፣ የአካሉዋ ቁራሽ ነው ። በየትኛውም ዓለም እንዲህ ያለ መሬት አይገኝም ።

ታራን ስትመለከት ጦርነቶች ለምን እንደሚካሄዱ በከፊል ተገ ንዝባለች ። ሬት ሰዎች ጦርነቶችን የሚያካሂዱት ለገንዘብ ሲሉ ነው ይላት የነበረው በዘተት ነው ። የለም ሰዎች የሚዋጉት ለተንጣለሉ ጋሻ መሬቶች ፣ በማረሻ በለስላሳው ለተኳለ እርሻ ቦታዎች ፣ ማር ለለመ ለመባቸው አረንጓዴ መስኩች ፣ በእርጋታ ለሚተሙ ወንዞችና በአ ረንጓዴ ሣሮች ማህል ወለል ብለው ፈክተው ለቆሙ ነጫጭ ቪላ ቤቶች ነው ። አዎ ለነዚህ ሲሉ ነው የሚዋጉ ።የነሱ ለነበረው ቀይ አፈር ነገ ማን ለልጆቻቸው ለሚሆነው ቀይ አፈር ፣ ነገ ለልጆ ቸውና ለልጅ ልጆቻቸው የሚሆን የጥጥ ሰብል ለሚያፈራው ምድር ሲሉ ነው የሚዋጉት ።

ከእንግዲህ የተረፋት የተረጋገጠና የተበዳደሰ የእርሻ ቦታ ነው ። አሁን አሽሌይም ሆነ ኤለን የሉም ። በንነው ጠፍተዋል ። ፒራልድም ከድንጋጤ ብዛት እራሱን ስቷል ። ግንዘብና ባሪያዎች ፣የሕይወት ዋስት ናና መቀመጫ ሥፍራ ባንድ ጀንበር ከሰመባት ። ዱሮ ካባትዋ ጋር ስለመሬት ትንጋገር የነበረውን ፣ ሌላ ዓለም ውስጥ ሁና እንደሰማችው ሁሉ ታስታውሰው ጀመር ።ምን ያህል ልጅነት ያጠቃት እንደነበር ፣ ምን ያህልስ ካለማወቅ ተጭኗት እንደነበር የገረማት ፣ አባቷ በዚህ ዓለም ሳይ ሊሞትላት የሚገባ አንድ ነገር ቢኖር መሬት ነው — ሲላት ለመረዳት አለመቻልዋ ነበር ።

@OLDBOOKSPDF

"እዚህ ዓለም ላይ ዕድሜ ያለው ነገር መሬት ነው... እናም የኢ የርላንዶች ደም እውስጡ ላለ ማንም ሰው እናቱ ይሄው ነው... ሲለ ቃለትና ሊሠሩለት የሚገባ ፡ሊዋጉ ለትና ሊሞቱለት የሚገባ አንድዩ ነገር መሬት ነው... "ይላት ነበር ።

እም ታራ ሊዋጉላት ሊዋደቁላት የሚገባ ናት ። ስለዚህም እስካ ርሌት የመጊያውን ጥያቄ ያለማመንታት ተቀበለች ። ማንም ታራን ከሷ ሊነጥቃት አይችልም ። ማንም አሷንም ሆነ ሕዝቦቿን አለው አጅ ላይ እንዲወድቁ ሊያደርግ አይችልም ። እያንዳንዱ በታራ ላይ ያለ ሰው ወገቡ ይጉበጥ ፣ አንጀቱ ይታጠፍ እንጂ እስካርሌት ታራን ቀጥ አድርጋ በሁለት እግሩዋ ታቆማታለች ።

@OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ 26

አስካርሴት ከአትሳንታ ከተመለሰች ታራ ውስጥ ሁለት ሳምንት ሆንዋታል ። እማሯ ሳይ የተላጠው ቅልቅ ቁስል ጫማ አላስደርግ ብሏታል ። ላድርግ ብትል እንኳ በተረከዟ ነው የምትሄደው ። እማሯ አብሏል ። በተለይ እውራ ጣቷ ላይ ውሀ የቋጠረው ቁስል ተስፋ አስቆርጧታል ። ወይ ጉድ ! ወር ሜዳ ቆስለው እንደሚመጡት ወታደሮች አመርቅዞ እዚህ ዶክተር በሌለበት ምድር ቢገድላትስ አሁን ? ይገርማል ህይወትዋ እንዲህ መራራ ህይወት ሆናባት እንኳ ጥላት ለመሄድ ትሳሳለች ። ደግሞስ እሷ ከሞተች ታራን ማን ሊጠብቃት ነው ?

ወደ ታራ የመጣች ዕለት ሽማግሌው ጂራልድ መንፈሱን አረጋግቶ የቤተሰቡን ጣጣ ይሸከማል የሚል ተስፋ ነበራት ። አሁን ግን በነዚህ ሁለት ሳምንታት ውስጥ ያ ተስፋዋ ሁሉ ተሟጦ አልቋል ። ስለዚህም ወደደችም ጠላችም እርሻውም ሆነ በእርሻው ላይ ያሉት ሰዎች በእሷ ያልሰለጠኑና ልምድ የሌላቸው እጆች ላይ መውደቃቸው ታውቋታል ። ጂራልድ እንደሆነ በህልም ዓለም ውስጥ እንዳለ ሰው በድንጋጤ ተሸማቆ ከታራ ውጭ ሐሳቡን አስሸፍቶ በፀጥታ ተቀምጧል ። ልታማክረው በሞከረች ቁጥር "እንደመሰለሽ ሥሪ የኔ ልጅ" ይላታል ። ወይም ባስ ካለበት "እናትሽን አማክሪያት የኔ እንቦሳ" ይላታል ።

ከእንግዲህ ምንም ሊሻለው ፣ ምንም ሊለወጥ አይችልም ። ይህን እውነት አስካርሴት ያለ አንዳች መሸበር ተቀበለች ። ጂራልድም እስከሞት ድረስ ኤለንን ይሰማ ፣ ለሷ ታዛዥ ይሆን እንደነበር ተገነዘበች ።አሁንም ባንድ ጻር አገር ውስጥ የሚኖርና ሁል ጊዜ እጮኑ ባለው ክፍል ኤለን አለች ብሎ የሚገምት ሰው ነው ። ለሱ አገር አማን ነው ። እሷ ስትሞት ዋናዋ የህይወቱ መሸከርከሪት ተበጠሰች ። የኑሮ ዋስትናው ፣ ታታሪነቱና ደከመኝ ታከተኝ የማይለው ሀልውናው አብሮ በነነ ። የጂራልድ እሳራን ጨክት የሞላበት ቴአትር ተመልካች የነበረችው ኤለን ነበረች ። አሁን ግን የግርጌ መብራቱ ጠፍቶ ፣ መጋረጃው ተዘግቶ ተመልካቹ ሁሉ በድንገት ወጥቶ ቲያትር አብቅቶ አሮጌው ተዋናይ በባዶው መድረክ ላይ ይናገረው ነገር አጥቶ ፤ የቃላት ቁልፍ እንዲያስጨብጠት እየጠበቀ ብቻውን ቀርቷል ።

@OLDBOOKSPDF

የዛን ዕለት ጠዋት ከእስካርሌት ፣ ከዋድና ከሦስቱ ሕመምተኛ ሴቶች በቀር ሰው ሁሉ ወደ ረግረጉ ጫካ የአሳማ ግልገል ፍለጋ በመሄዱ ቤቱ ፀጥ እርጭ ብሏል ። ጀራልድ እንኳ በአንድ ለጁ የተጠቀለለ ገመድ በሌላው እጁ የፖርክን ከንድ ይዞ እንደምንም ተበራትቶ ወደሚጸው ሄዷል ። ካሪንና ሱዌለን ሁልጊዜ በቀን ሁለቴ እንደሚያደርጉት ሁሉ እናታቸውን ኤለንን አስታውሰው እንባቸውን በጉንጫቸው እያወረዱ አልቅሰው መኝታቸው ላይ ተጋድመው ቀር ተዋል ። ሚላኒ ያን ዕለት ለመጀመሪያ ጊዜ ቀና ብላ ትራስዋን ተደ ግፋ ተቀዶ በተሰፋ አንሶላ ተጠቅልላ በሁለት አራስ ሕፃናት — በአንድ ወገን ገና እርጥብ ህፃን በከንድዋ ታቅፋ ፣ በሌላው ወገን የዲልሲን ቆርጫጫ ፀጉር ልጅ እንደራሷ ልጅ ተንከባክባ ታቅፋ— ማህል ተኝታለች ። ዋድ ከልጋው ግርጌ ተቀምጦ ተረት ያዳምጣል ።

እስካርሌት ታራን የወረራትን ዝምታ አልወደደችውም ። ያንን ወደቤቷ ከአትላንታ ስትመጣ ያየችውን ሬሳ የወጣበት ቤት የመሰለውን አቋርጣው ያለፈችውን መንደር ስለሚያስታውሳት ልቷ ሸከመው አልቻለችም ። ሳሚና ጥጃዋም ለረጅም ሰዓታት ድምጽ አላ ሰሙም ። ከመስኮትዋ ውጪ የሚበርሩ ወፎች አይታዩም ። ሌላው ቀርቶ ለብዙ ጊዜ ከዓመት ዓመት ዛፎቹ ላይ ሰፍረው ይዘምሩ የነበሩት ተጫዋች ወፎች እንኳ ዛሬ ማዝሙራቸውን አቁመዋል ። አጠር ያለች ወንበር ወደ መስኮቱ ስባ ተቀመጠችና ወደ ዶጅ —ከመኝታ ቤቷ መስኮት ውጪ — መትነጹን ፣ የማጠሽ ቦታ ውን ፣ ባዶውን የተዘረጋውን ሜዳ ታይ ጀመር ። አሳጩዋን እከንዱዋ ላይ አሳርፋ እመስኮቱ ደፍ ላይ ተደግፋለች ። ቀሚስዋ ተሸብሽቦ ከጉልበትዋ በላይ ጭኖችዋን ያሳያል ።አወላለሉ ላይ የጉድጓድ ውሀ የያዘ ባልዲ ተቀምጧል ። በየጊዜው የተሞሸለቀ እግርዋን ዝቅ ከፍ እያደረገች እዚሁ ውሃ ውስጥ ትነክራለች ። እግርዋ ሲጠዘጥዛት ፊትዋን ታኮማትራለች ።

እየቀፈፋት ፊትዋን እመዳፍዋ ላይ ትፈትጋለች ። ጉልበት በም ትፈልግበት በአሁኑ ሰዓት ይሄ የእግር እውራ ጣትዋ ደማሞ ቆሰለ ። እነዚህ ጅሎች መቼም አሳማውን ማጥመድ አይሆንላቸው ። ከዚህ ቀደም ሳምንት ሙሉ ለፍተው አሳማዎቹን ይዘው ነበር ። በሁለት ሳምንታት ውስጥ ይኸው እንደገና ጠፋ ። እስካርሌት ብትሆን ቀሚስ ዋን ወደላይ ሰብስባ ገመዱን ይዛ ጆከሮቢንሰን ከመጠራቱ በፊት እንደምታጠምድ ታውቃለች ።

ነገር ግን የአሳማዋ ግልገል ከተያዘች በኋላስ ፣ እሷን በልቶ ደማሞ ሌላ ምግብ መፈለጉ ይቀጥላል ። ከረምት መግባቱ ነው ። ሌላው ቀርቶ ከጉረቤት የሚገኘው የጉመን ጭማቂ እንኳ ሊጠፋ

@OLDBOOKSPDF

ነው። የደረቅ አተር፣ የማሽላ ምግብ፣ ሩዝ፣ ወዘተ... ምን የሚ ፈልጉት ነገር ሥፍር ቁጥር የለውም። ለሚቀጥለው መከር የሚሆን የበቆሎና የጥጥ ዘር እንዲሁም አዲስ ልብስ ያስፈልጋቸዋል። ይሄ ሁሉ ከየት ሊመለስ ነው። በምን ገንዘብ ልትገዛው ነው?

በድብቅ የጄራልድን ኪስና ካዝና በረበረች። የኮንፌደሬሲ ደረ ሰኝና የኮንፌደሬሲ የምስት ሺህ ብር ቼክ ነው። እያፈዘች ለአንድ ኩር ማን ፣ ዘር መግዣ ይበቃን ይሆን ? አለች። ዛሬ ጊዜ የኮንፌዴሬሲው ገንዘብ ረክሶ ከሁሉ ነገር ቢታች ሁኗል። ያ ፊት ያመጣላቸው ጭስ ቋላ ፈረስ እንኳ በዛሬ ገቢያ ሰንትና ስንት ጥቅም ነበረው። በዓለም ላይ ብዙ ልዩነት ያመጣ ነበር። ዋ ! እነዚያ ያነጠነጡ ግጦሹ ላይ በእግራቸው መራቱን ሲፎክሩ ይሙሉ የነበሩ በቅሎዎች ፣ የሚያምሩት ለጋሪ የሚሆኑ ያወለወሉ ፈረሶች ፣ የቧ ትንሽ በቅሎ ፣ የሴቶቹ ልጆች ውርንጭሎች ፣ ያባቷ መሬት ንቅንቅ ሰንጋ ፈረስ እሪ እንሱ ቀርተው ከሳሳዋ በቅሎ እንኳ ብትገኝ !

ብቻ ግዴለም ... አግሯ ሊድን ወደ ጀንሰ ቦሮ ትገሰግሳለች። በሕይወትዋ ሂዳ የማታውቀው ረጅም የእግር ጉዞ ነው። ነገር ግን ለመጓዝ ቆርጣለች። ምንም እንኳን ያንኪዎቹ ከተማውን አጋይተው ድምጥማጡን አጥፍተውት ቢሆን ፣ ምግብ ያለበትን ቦታ የሚመራት አንድ ሰው አታጣም። የዋድ በቁንጮ የደቡን ሬት አይኑዋ ላይ ድቅን አለ። ያም እንደማይወድ በተደጋጋሚ ተናግሯል። ስኳር ድንች ፣ ሩዝና አንዳንድ ሥራሥር ያስፈልገዋል።

ቦማ ብላ በርታ የነበረችውን ፀሐይ ጉም አፈናትና ወዲ ያው ላሮቹ እንባ በእንባ ሆኑ። እስካርሌት አንገቷን ሰብራ ላለማልቀስ ትታገላለች። ማልቀስ አሁን ምንም አይረባትም። ማልቀስ የሚጠቅምበት ጊዜ ቢኖር ባቅራቢያው ውለታ የሚውል ወይም የሚሰጥ ሰው ሲገኝ ብቻ ነው። አሳስወጣም ብላ ከእንባዋ ጋር በትግላት ፣ አይኑዋን ስታጨናቁር ከደጅ የፈረስ ኮቴ ሰማችና ገረማት። ሆኖም አንገቷን ቀና አላደረገችም። የእናትዋ የኤለን ቀሚስ የሚንሿሿ ይመስላት የጀመረበት ሰሞን በመሆኑና በተለይ ይህን ሁለት ሳምንት ፣ ቀንም ሆነ ማታ ፣ እንዲህ ዓይነቱን የፈረስ ኮቴ ድምጽ በሀሳቧ ትሰማ ስለነበር ቀናም አላለች። ልቧ እንዲህ ያለ ሁኔታ ሲያጋጥመው እንደሚሆነው ሁሉ ድው ድው ሲልባት "እንግዲህ ጅል አትሁን" ብላ እንደተለመደው ገታችው።

ብቻ ያ የፈረስ ኮቴ ቀስ በቀስ ወደ እግር ጉዞ ተለወጠና በመጣኑ ከፍ ከፍ ይል ጀመር። ፈረስ ነው። ወይ የታርሌተኖች ፣ ወይ

@OLDBOOKSPDF

የርንዙኖች መሆን አለበት ! ኧረ የለም ። አንድ ፈረሰኛ ያንኪ ነው ። ጉድ ፈላ!

ከመቅጽበት መጋረጃው ውስጥ ዘላ ገብታ ተደበቀች ። በሹል ቅታ በመጋረጃው ማህል በደብዘዛው ብርሃን ውስጥ ስትመለከተው ትንፋሽዋ ከሳንባዋ ወጥቶ አለቀ ። ትንፋሽ አጠራት ።

በኮርቻው ላይ ተደላድሎ ተቀምጧል ። ወፍራም ነው ። ፊቱ ጨካኝ ይመስላል ። ጥቁር ጢሙ ተንዠርግጎ በሰማያዊው የደንብ ልብሱ ኮሌታ ላይ ተኝቷል ። ጥብቅ እድርጎ ማንባሩን ከያዘው ሰማያዊ ባርኔጣው ሥር ያሉት ጥቃቅን ዓይኖች በፀሐይ ሃሩር እንደ ደከሙ በቀስታ ቤቱን ይፈትሻሉ ። ቀበሌ ብሎ ከፈረሱ ወርዶ ኮርቻውን ትቅጥ እምስሶው ላይ ሲሰቅል እስከርሱት ከሆድ ቁርጠት በኋላ እንደሚተኙ ትንፋሽ ላንባዋ አየር ሳበና እስትንፋስዋ ተመለሰ። ወይ ዕዳዋ ! አዳሌው ላይ ረጅም ሽጉጥ ያንጠለጠለ ያንኪ እኮ ነው የመጣ ባት! እሷ ደግሞ ምስት ሔመሞቷ ቢኖርና ወንድ ይዛ ብቻዋን ያለች ሴት ናት! ምን ይዋጣት !

እጅን እሽጉጡ ማህደር ላይ እድርጎ ጉርዶድ ጉርደድ እያለ በጥቃቅን ዓይኖቹ እቤቱ ወዶ ግራ አንዴ ወደ ቀኝ ሲቃኝ ፣ እሰካር ሴት ሞንቅላት ውስጥ የሚተራመሱ ስዕሎች ፣ ጥዮፓት ትዝግራት የነበሩት ታሪኮች እየበረሩ መጡብት ። ሴት ልጅን ብቻዋን ሲያገኙ የሚደበድቡ ፣ እንጎት የማቆርጡ ፣ ቤት የሚያጋዩ ሕየኖት ሲያለቅሱ በጥይት ወንፊት የሚያደርጉ ስዎች ታሪክ ፣ ብቻ በአጠቃላይ እጅግ አስደንጋጭ የያንኪ ታሪክ እሞንቅላትዋ ውስጥ ተጥራመሰባት ።

መጀመሪያ ቁም ሳጥን ውስጥ ለመደበቅ አሰበች ። ቀጥላ እየዳበሸች አልጋ ሥር ልትባባ አሰበች ። ከዚያ በጀርባ በኩል ደረጃውን ተንደርድራ ወርዳ ውፅታዋን እያሳለጠች ወደ ጓክው ሮጣ ልታመልጠው ፈለገች ። ከዚያ በዝግታና በጥንቃቄ እየተራመደ ሲመጣ ኩሬውን ሰማች። ወደ አዳራሹ ሲባባ ቀበቶውን አየችና ሮጣ የማምለጡዋ ነገር የሞተ ጉዳይ ሆነ ። በድንጋጤ ቁዝቅዝና ደንዝዛ ባለችበት ከክፍል ክፍል እየተዘዋወረ ሲመጣ ከታች በት ድምጽ ይሰማታል ። ሰው እያጣ በሄደ ቁጥር ኮቴው እየጎላ እረማመዱ ድፍረት እየተሞላ መጣ። አሁን እምግብ ቤት ደረሰ ። ጥቂት ቆይቶ ወደ ማድ ቤት ሊሄድ ነው ።

ወደማድቤት የመሄዱን ነገር ስታስብ በሰለት ልቡዋን እንደተወጋች ሁሉ ፍርሀትዋ ሁሉ ቀረና ንዴት በጡትዎችዋ መሀል ፈላ። ማድቤት ! አዎ ። ማድቤቱ ውስጥ እኮ አምድሽው ላይ በፍራፍሬ

@OLDBOOKSPDF

የተሞላ አንድ ማሰርኛ ከጠንቸ ድካም ከአሥራ ሁለቱ ዋርካዎችና ከማኪንቶሽ ያመጣቻቸው ፣ ለአራት ፣ ዘጠኝ የተራቡ ሰዎችን የሚመ ከቱ ቅጠላ ቅጠል ሕትክልቶች ተጥደዋል ። ለሁለት ደህና ሰዎች የሚትረፈረፍ ነው ። እስክርቤት እውጭ ያሉት የቤት አባላት መቼ ተመልሰው በልቼው አያለኝ ምራቁዋን እየዋጠች የቋመጠችለትን ምግብ ይሄ ያንኪ ሲበላው መሆኑን ስታስብ ደምዋ ፈልቶ ጣቶችዋ ሁሉ ይንቀጠቀጡ ጀመር ።

እግዚሀር መቅመቅ ያውርዳቸውና ታራ ላይ እንደአንበጣ ሠፍ ረው አራቁተው ልጠኔ ጥለዋት የሄዱት አልበቃ ብሏቸው አሁን ደግሞ ተመልሰው የድሀ ጓዳ ይመዘብራሉ !! ባዶ ሆድዋ እንደዘንዶ ተገላበጠባት ። እረ በፈጣሪ ! ያንኪ አይደለም አንዴ መዝረፉ የት ይቀራል ።

አሮጌ ጫማዋን ከአግሩዋ አወለቀችና ጣለችና በባዶ እግሩዋ ፈጥና ወደ ቢሮው ሄደች ። ያ የኩሜር አውራ ጣትዋ ቁስል በጭራሽ አልተሰማትም ። ድምጽ ሳታሰማ ከላይኛው የኮሞዲኖወ ኪስ ቻር ለስ ያነሳጠው የኃበረውንና ተኩሰበት የማያውቀውን ከሕትላንታ ያመጣችውን ከባድ ሽጉጥ አወጣች ። ከዝናሩ ሥር የተሰቀለውን የቆዳ ቦርሳ ፈተሸችና አንድ የጥይት ካርታ አወጣች ። ጠንከር ባለ እጅዋ ካርታውን በቢታው ሰነጠቸ ። ቸኩላና ኮሽ ሳታደርግ ወደ ላይኛው አዳራሽ ወጥታ ቁልቁል ዶረጀውን እየወረደች የደረጃውን እጅ መደ ገፊያ ይዛ በሌላው እጂዋ በቀሚስዋ ሽጉጡን ጠቅልላ እሙንዋ ላይ ይብቃ ይዛ አረፍ አለች ።

"ማነው እዚያ ያለው ?" አለ አንድ ባጭጫው የሚናገር ድምጽ ። ጆሮ ግንድዋ እንደአንድ ንገር ግለሰ የሚናገረውን እንኩዋ ለመለ ማት እየከለከላት ከደረጃው ማህል ቁጥ ብላ ቆመች ።

"ቁም! አለበለዚያ እገልሀለሁ" አለ ያው ድምጽ ቀጠለና ።

አሱ ባንድ እጁ ሽጉጡን ይዞና ሽምቅቅ ብሎ ምግብ ቤቱ ወለል ላይ ቆሞዋል ። በሌላው እጁ- እውስጡ የወርቅ እጀታ ያለው መቀስ የወርቅ ጌጣ ጌጥና ከዳኑ በወርቅ የተከፈፈ የስፈት ሳጥን - ይዟል ። አስክርሌት እግርዋ እጉልበትዋ ድረስ ቅዝቅዝ ይበል እንጂ ፈትዋን ንዴት ኮሶ አስመስሎዋታል ። ወይጉድ የኤለንን የስፈት ሳጥን እኮ ነው የያዘው ። "አንተ አስቀያሚ እድፋም ያንኪ ቁሞ አድርግ . . . " ብላ ልትሙህበት ታጥቷት ነበር ። ንገር ግን ቃላት አልወጣ አሉዋት ። ዝም ብላ ከደረጃው መደገፊያ በላይ ታስተውለዋለች ። ፊቱ ከኩም ታራ መከማጨጭ ወደ ግማሽ ጥላቻና የምን ልርዳሽ ፈገግታ ተለ ወጠ ።

@OLDBOOKSPDF

"እህ ፣ ለካ እቤት ውስጥ በሙ አለ" አለ ሽጉጡን ወደ ግሀ ደሩ እየመለሰና አዳራሹን ማጎል ለማህል በንጥቅ አስርዋ አስከሚደርስ ድረስ ተራምዶ እየቆመ ። "ብቻሽን ነሽ እንዴ ፣ አመቤት ?"

ወዲያው መሣሪያዋን እንደመብረቅ ፈጥና መዛ ከደረጃው መደ ገፊያ ላይ ደግና በተደናገረው ጢማም ጭንቅላቱ ለቀቅችበት ። ግና እጁን እቀበቶው አጠገብ እንኳ ሳያስጠጋ ነው ቃታውን የሳበችበት። ሽጉጡ የኋሊት ሲገፋት ክንድዋን ነቅነቀው ። ጮኸቱ ጀሮዋን አደ ነቆረው ። ጭሱም አፍንጫዋን አፈነው ። ሰውየው የምሳብ ቤቱ ዕቃ እስኪንቀጠቀጥ ድረስ ተንፈራግጦ በጀርባው ተዘረረ ። በእጁ ይዞት የነበረው ሳጥን ወደቀና ተንካካ ። ወስጡ የነበረው ዕቃም ተቢታኑን ። እስካርሴት ምንም ሳይታወቃት ደረጃውን ወረደችና እፊቱ ቁጣ ቁልቁል ትክ ብላ ታስተውለው ጀመር ። ከዚሙ በሳይ ፊቱን ብታ የው አፍንጫው እንበረበት ቦታ በደም የተበከለ ቃዳዳና ባሩድ የተ ረጨባቸው ያፈጠጡ ግይኖቹን ተመለከተች ። ሠሪት ቀጫጭን የደም ሽረቶች — አንዱ ከፊቱ አንዱ ከማጅራቱ እየመነጨ ወለሉን ሲያ ቀልጥ አስተዋለች ። አም ያለ ጥርጥር ሞቷል ። ድብን ብሏል ። አንድ ሰው ገደለች ማለት ነው ።

ጭሱ እየቀጣመለመለ ወደክፍቱቱ ሲወጣ ቀዩ ጅረትም ወለሉ ላይ እየሰፋ ሄደ ። ጊዜ ለማይለክው ጊዜ እዛው ቆማ ቆየች ። እርግት ባለው የቢጋ የጪት ፀጥታ ማህል እያንዳንዷ ዋጋ የለሽ ኮሽታ ሁሉ የልብዋን ትርታ እንደከበሮ ምት ታጉላባት ጀመር ። የማግኖሊያ ዛፎች የቅጠል ሹክሹክታ ፣ የውሃ ጸር ወፎች የሩቅ ጪውጪታና የደጹ አበቦች ሽታ ሁሉ ጐልቶ ይታወታታል ።

ሰው ገደለች ።በአደን ላይ ከማድያው ቦታ ለመኖር የማትፈቅ ደው ሴትዮ ፥ አሳማ በሚታረድበት ጊዜ ሲያንራ የሚዘገንናት ሴትዮ ፣ ወጥመድ ሲይዛት ሲጪጥ የምትል ጥንቸል ጩኸት የሚረበሻት ሴትዮ ፣ ዛሬ ሰው ገደለች ። ግድያ ! ፍዝዝ ብላ አሰበች ። ግድያን ፈጸ ምኩ ። ጪ ! አንዲህ ያለው ,ነገር እኔን ሊያጋጥመኝ አይገባም ነበር ። እንደገና አይኖችዋን ወደ ተዘረረው ሰው ፥ ሳጥኑ አጠገብ የተዘረጉ ፀጉራማ ግትር እጆች ፣ ወረወረችና ዳግም ህይወት ዘራች ። ግዳይ ጥሎ እንደሚፈነድቅ ንብር ፈነጠዘች ። ከጥቂት ጊዜ በፊት አፍንጫ በነበ ረው ፣ እፊቱ ላይ ያለ ጉድጓድ ውስጥ ተረከዙዋን ተክላ በማሽከርከር ትኩስ ደሙን ራቁት ገላዋ ቢነክት በወደደች ነበር ። ሰታራና ለሌ ለን አንድ የበቀል እርምጃ ወሰደችላቸው ። ተበቀለችላቸው ።

አሳይኛው ቤት አንድ ፈጠን ያለ ኮቴ ይሰማል ። ፈጠን ብሎ ይራመድና ደግሞ ዝግ ይላል ። አሁን በደከመ ሁኔታ የሚጮተት የሚ

@OLDBOOKSPDF

ያስመለሰው የብረት ቅጭልታ ይሰማል ። የጊዜና አካባቢውን የሙን ህብ ስሜት ልብ እንድ ተብሎ ይጠራ የነበረችው አስካርሌት ቀና ብላ ብትመ ለከት ፣ ሜላኒ እንደቢጃማ የምትጠቀምበትን ሸሚዝ ለብሳ በደከማ እጅዋ የቻርለስን ጐራዴ ይዛ ከደረጃው ጫፍ ላይ ቆማለች ። የሜላኒ አይኖች ከማርጌዋ ያለውን ትርዒት ሙሉ በሙሉ ተመለከቱ ። በደሙ እየዋኘ የተዘረረውን ሬሳ ፡ አጠገቡ ያለውን የስረታት ሳጥን ፡ በባዶ እግሩዋ ፊቷ ላራጫ መስሎ ረጅም ሽጉጥ የያዘችውን አስካርሌት — ሁሉንም አንድ በአንድ አዩ ።

እንዲሁ ዝም እንዳሉ ዓይኖችዋ ከአስካርሌት ዓይኖች ጋር ግጥም አሉ ። አተነፋፈው ኩሩ ፊትዋ ላይ ግርማ ሞገስ የተላበሰ ኩራት እንደፍም ያበራል ። ገድሉን ጉሽ የማለትና ጥንካሬ የተሞላ ደስታ— ልክ አስካርሌት ልብ ውስጥ እንዳለው ዓይነት — በአደም ውስጥ ተቀረፀ ።

"ለካ አደም እንደኔ ናት ። ምን እንደተሰማኝ ታውቂታል !" አለች አስካርሌት ፌልፏ ። "በእኔ ቦታ ብትሆን ኖሮ እደም ይህንኑ ነበር የምታደርግ !"

ወደዛች ከጥላቻና ከክፋት በቀር በፀጉ ዓይን አይታት ወደማታ ውቀው አቅመ ልፍስልስ ሴት ልብ በሚሰነጥቅ ስሜት ተመለከተች ። አሁን ለአሽሌይ ሚስት ያላትን ጥላቻ እየተናነቀ ከልብዋ የሚወጣው አድናቆትና ወዳጅነት ነው ። ያለአንዳች ስሜታዊነትና ችግር በሜላኒ ኩሩ ድምጽና የርጉብ ዓይን በመሰሉት ዓይኖችዋ ውስጥ የማይሰበርና የማይበጠስ ቀጭን ለሰት መኖሩን ተመለከተች ። በሜላኒ ቀዝቃዛ ደም ውስጥም የድፍረት ባንዲራና እምቢልታ እንዳለ ተገነዘበች ።

"አስካርሌት ፣ አስካርሌት !" የሚለው የበሽተኞቹ የካሪንና የሱዌለን ድምጽ በተዘጋው በር ታፍኖ ተሰማ ። ዋድም "አክሽፍ ! አክሽፍ !" ብሎ ጮኸ ። ሜላኒ ጣቶችዋን አፍዋ ላይ አድርጋ ፣ ጐራዴውን እደረጃው ላይ በፍጥነት አስቀምጣ በጓመታቱኖ አቅሟ ደረጃውን ወርዳ ወደበሽተኞቹ ክፍል ገባችና ፤

"ልጆች ፡ ልጆች አይዟችሁ አትፍሩ"አለ በደስታ የታሸ ድምጽዋ ። "ትልቋ እህታችሁ የቻርለስን ሽጉጥ ስትወለውል ባርቆ በጣም አስበርግጓት ነው ፣ ዋድ እናትህ ያባትህን ሽጉጥ ተኩሳለች ። አንተ ትልቅ ልጅ ስትሆን ደግሞ ትሰጥሀና ትተኩሳለህ" አለች ።

"ምን ዓይነቷ ምስጥ ዋሾ ናት" አለችና አስካርሌት በልቧ ተገረመች ።

"እኔ ብሆን እንዲህ በፍጥነት አይመጣልኝም ነበር ።ግን ምን ያስጥሻታል ፣ እኔ እንዳደረግሁት ማወቅ አለባቸው እኮ"

@OLDBOOKSPDF

ወደሞተው ሰው አንደገና ተመለከተች ። ንዴቷን ፍርሀትዋ ሚሙተው እንድ ሥጋት ልብዋ ገባና ጉልበትዋ ተብረከረከ ። ሚላኒ እንደገና እየተሳበች ወደ ደረጃው አፋፍ መጣችና የታችኛው ከንፈርዋን በጥርስዋ ነክሳ የደረጃውን መደገፊያ ይዛ ቀስ እያለች መውረድ ጀመረች ።

"ምን መሆንሽ ነው ሂጂና ወደመኝታሽ ተኚ ፣ እራስሽን መጣደል አምሮሻል እንዴ ?" ብላ ጮኸችባት እስካርሌት ። ያቺ ግማሽ እርቃኑዋን ያለች ሚላኒ ግን አቫረረኝ ብላ ቀሰሰተኛ ጉዞዋን ቁልቁል ወደእዳራሹ ተያያዘችው ።

"እስካርሌት" አለች በቹኩሹክታ "ከዚህ ቦታ ወስደን መቅበር አለብን ይሄን ሰው ። ብቻውን ሳይሆን ስለሚችል ጓደኞቹ እዚህ ካገኙት . . . " ብላ ንግግሩዋን እስካርሌት ከንድ ላይ በመደገፍ ገታችው ።

"ብቻውን መሆን አለበት ። ከፎቅ ሆኜ በመለኩት ስመለክት ብቻውን ነው የመጣው ፣ ማንም አብሮት አልነበረም ። ከሮሩ ከድቶ የመጣ ይሆን ይሆናል ።"

"ብቻውን ቢሆንም እንኳ ማንም ስለእሱ ማወቅ አይኖርበትም ። ኔግሮዎቹ ካወሩ ያንኪዎቹ ይመጡና ይይዙሻል ። እስካርሌት ፣ ሰዎቹ ከሜካ ከመምጣታቸው በፊት ፈጥነን መቅበር አለብን ።"

በሚላኒ ውትወታ የእስካርሌት አዕምሮ ወደ ተግባር ስመሰማራት ክሩኛ ያስብ ጀመር ።

"በአትክልቱ ቦታ ማሀል ፖርክ ውስኪውን ካወጣበት ጉድጓድ ውስጥ እቀበረው ነበር ግን ችግሩ እንዴት አድርጌ እዚያ አደርሰዋ ለሁ ።"

"ግዴለም አንቺ እንድ እግሩን እኔ አንድ እግሩን ይዘን ገት ተን እንወስደዋለን" እስካርሌት ያለፈቃድዋ አደነቀቻት ።

"እንዴ አንቺ እኮ ድመት እንኳ መጐተቻ አቅም የለሽም ። እኔ እጐትተዋለሁ ። ሂጂና ተኚ ይልቅ ። ራስሽን ትጐጂለሽ ። እኔን ለመርዳት እሞክራለሁ ትይና ኋላ አንቺን ተሸክሜ ነው ወደ አልጋሽ የምወስድሽ ። "

የሚላኒ ነጭ ፊት ነገሩን ከመረዳት ወደመጣ ፈጣጣ ተለወጠ ፣

"በጣም ተወዳጅ ነሽ እስካርሌት" አለችና የእስካርሌትን ጉንጭ የመታከክ ያህል ሳም አደረገችው ። እስካርሌት በሁኔታው ተገርማ

@OLDBOOKSPDF

ሳይበቃት ሜላኒ ቀጠለች፡—"አንቺ ገ•ትተሽ ልታወጪው የምትችይ ከሆነ ፡ እኔ ሰዎቻችን ሳይመጡ በፊት ወለሉን አፀዳልሻለሁ ፤ እና እስካርሌት . . . "

"ሺ"

"ቦርሳውን መፈተሽ ብልግና ይሆንብኝ ይሆን እንዴ ? ምናል ባት የሚበላ ነገር ይኖር ይሆናል ።"

"አይመስለኝም" አለች እስካርሌት ይህንን አስቀድማ ሰማስብ ባለመቻልዋ እየተበሳጨች ። "አንቺ ቦርሳውን እዪ ፤ እቤ ኪሱን እፈ ትሻለሁ ።" አለች ።

ወደ ሞተው ሰው በጥላቻ ተጠግታ የቀሩትን የጃኬቱን ቁል ፎች ፈትታ ቀስበ ብላ መፈተሹን ቀጠለች ።

"ውይ አምላኬ" አለችና በጩርቅ የተጠቀለለ ያበጠ የኪስ ቦርሳ አወጣች ። "ሜላኒ- ሜሲ በጣንዘብ ጤም ያለ ነው መሰለኝ!" አለች ። ሜላኒ ምንም ሳትመልስ ወለሉ ላይ ቁጭ ብላ ግድግዳውን ደገፍ አለች ።

"እየሽ ፤ ትንሽ ድካም ተሰማኝ እኮ" አለች በደካከመና በሚን ቀጠቀጥ ድምጽ ።

እስካርሌት ጨርቁን ቀዳደድችና በሚንቀጠቀጡ እጆቿ የተጣ ጠፈውን ቦርሳ ከፈተች ። "እዪ ሜሲ . . . በሞቴ ተመልከቺ" አለች ።

ሜላኒ አየችና አይኗን ጭፍን ዝግት አደረገች ። የጣንዘቡ የቼኩ ፡ የተባበሩት መንግሥታትና የኮንፌዴሬሲው ገንዘብ ድብልቅልቁ ፡ ከዚህ ማህል ደግሞ አንድ አሥር ብር የሚያወጣ ወርቅና አንድ አምስት ብር የሚያወጣ ወርቅ ብልጭ አለ ።

"አሁን ገንዘቡን መቁጠሩን ተይ" አለች ሜላኒ ፤ እስካርሌት ጣቱዋን እነባብራ ለመቁጠር ስትዘጋጅ ። "ጊዜ የለንም እስካርሌት ቶሎ ቢይ እንጂ . . ."

"ሜላኒ ይሄ ገንዘብ ማለት መብላት እንችላለን ማለት መሆኑን ተገንዝበሻል ?"

"አዎን ፤ አዎን የኔ እመቤት ። እሱን አውቃለሁ ግን አሁን ጊዜ የለንም ሌሎቹን ኪሶቹን አንቺ ፈትሻቸው እኔ ቦርሳውን ልውሰድ ።"

እስካርሌት ከደስታዋ ብዛት ቦርሳውን ለመመለስ አልቻለችም ብሩህ ዕድል ከፊቷ ተዘርግቷል— እውነተኛ ገንዘብ ! የያንኪው ፈረስ!

@OLDBOOKSPDF

ምግብ እቤት ሰጅተሽ አማዚሪር ነበር ምንም እንኳ ያስጣሙ መንገድ ግራ ቢሆንም ይሰጣል። እግሩም ላይ ትቅምጣ የነበስ በርሳ ዋን በደጣታቱ ተመዳትሽው። ምግብ ሚሳኔ መጥታ ከእጅዋ መጣ ጭታ ወስደሽብኝ።

"ቤድ ሩወኔ እንጂ" አለሳሙ።

የበረሬም ትስ ጨሪና ከአንዲት እሳቲ ሻማ፣ ከቢሳና ከፒንሳበስ ተቀር ምንም የልም። ሚሳኔ ከበርሳው ውስጥ አንድ የቡና ከረጠት አውጥታ ፣ ቪና ዘልታ ኑንሆን ሁሉ አስነሰሳት። ትጥንሽ ብስኩ ጥቂጥ አብረው ኢሉ። እኖም ሉሙዋ እየተሳዋወጠ በወርቅ የተከ ፈረ የአንዲት ልጅ ጉጅ ሱት ሚራፍ፣ ያንገት ሀብል ከኑሰንስለቱ፣ ጌጣጌጥ፣ ከብር የተሠራ የሕማ መጠጫ ክብያ፣ በጠርቅ የተቀባ መቅለ ከአልማዝ የተሠራ ጉንጉን ጥልበት ፣ ትጥንሽ አልማዞች የተገጠለመ ስብሻው። ኑሄቱ የሚያውሰው ሳይናቸው እንኳ ፈፊር እንጂሚ ችለው በጣም ከብድ ሳዝን ያሳችው የጀሮ ጉትቻዎች አየች።

"ሴባ ሴባ ንወተ" አለች ሚሳኔ አቅም እየተለማት። "እስካርሌት፣ ከአጉዱ ጋ ለርሱት መሆን አለበት።"

"ቃዲያስ" አሮች እሰካርሌት። "እዚህ መጥቶ ደማም ከአኛም ዘርፎ ሊጨምርበት ነዋ።"

"ጪ! በሰንዴልሽው በማም ነው ደኑ ያሰኛ። ብዎ እሁን ጥሎ መስያሽ ቀብረው።"

እስካርሌት ጉግበት አሰችና ዙት ጫማውን ይዛ ልትነ ሳ-ሁው ሞክረች። አቤት እንዱት ይከብዳል፣ እንዱት ደክማ አስመ ሰሳት! አሁን ሚንቀሳቀስ ቢያቅታት ምን ሊሆን ነው፣ ለራሳው ጅሮባሞን ስጠችና ብአንድ እጇዋ አንዲኖወሳ እግሩን በሌሳው እጇዋ ሰሳሻውን ይዛ ታዴሷ አጠራቅማ መዲሬት ስትል ጉንቀሳቀ ስሳት። እራሱዋም ጉንገዳደች። ይሄኔ ያ የተረሳው የአማር ቁስሎ ይጠዘዋት ጀመር። ሞርሱዋን ነክሳ ያስ የሌስ አቅጣጫ ሁሉ ወደ ቁስ ሉ አዛወረች። እንደምንም እየተጭጨረጨረች ፣ ሳቢ በሚንባ ርዋ እየተንቀረቀረ ቁልቁል በእዳራሹ እየቱተች ስትሄድ፣ ደመ እወለሉ ላይ ቀጭን መንገድ ሠራ።

"ዉ! እንደዚህ መድማቱ ከቀጠለ ሚዳው ሁሉ በደም ይለወስና በጭራሽ ልንደብቀው አንችልም። ሜሊ ልብስሽን ስጪኝና እራሱ ላይ ልጠምጥመው።"

ሜላኒ መልከዋ ከነጭነት ወደቀይነት ተለወጠ።

@OLDBOOKSPDF

"ሂያዛ አትሠሪ ሚስት ሆነሽ ይሄን ታደርጊያለሽ" አለች እስክርቤቶ። "ሂያ ከሰይ የደረሰበትን ማንኛውም ጥፋቱ ቢኖረኝ ኖሮ እጠቀም ዘንድ ነበር።"

ሚስቱ ወደማያጣጥመው የንጹሕ ሂያ የሁከትና ስብሰባን ቢያጋ ጉም ብሎ 'ኮብራ' ከሙቦይ በአክብሮትና መረጠረትነት፣ በተሸናቱ ከንጹሞች ደራሽ ላይ ኦሳቄና ከብረሉ ነሳሽ ሌመከሰከሰ ጦጣዎር ያመሩ።

"እማዘሀር ይመጣሀን ልስሰና ትሁት አይደለውም" አለች እስ ክርቤቶ ዝኳ፣ የሚሉን ሞንቀት በማይገዋ ከማየት ይልቅ በልቡዋ እየተሰማት። በድም እሰብአአው ፈት ሳይ ጨርቁን ለመጠመች።

ቤትጽጋጋሚ እያመጣሽ ከመጮሁት ቁልቁል በአዳራሹ አድ ርጋ በሳር በእሱ ከሰው በረንዳ አጠብ ስትደርስ የሚሰራዎን ሉሆ በአይበሀሀዋ ሊመጥረግ ቆም አሰኙና ወደ ሚሳኒ ዞራ ብታይ ሚሰኒ እማይጉሀሀ ጦጣ ሃሊዝትዋን ታቅፋ ከርቻት ብሳ ጉቀም ጣሰኙ። እሷ ሚላር አንጌት በአሁኑ ጉንት ነበ ትህትና ጉሐኑታ ለኛ ብሳ አስክርሉት አበበች። የማፅኒ መልነም ከነ ምጣበር ነው ሁል ጊዜ እስክርሌትን የሚያጀግዱት። ወዲያው ሀፍረት ያዛት። ሌሳው ጺቮር — ሌሳው ጺቮር እኮ ሚሰኒ ከመሰደኟ ጥቂት ቀን ሳያልፋት ነው ከአራስ ቤትዋ መጥታ ለማጎሳት እንኳ አቅመዋ የማይፈቅድሳ ትን መሣሪያ ሳቸዝንግ ልትረዳት የመጣችው። እንዲህ ማድረግ ጉልቅ ድፍረትን ያጠይቃል። ድፍረትም ቢሉ ራሱዋ አስክርሉት እንኳ የሌሳትን ዓይነት ድፍረት። ይህንን ደማም ልቡዋ ያጨቀዋል። ምር እንደቸረራት ድር የሳትኟ ፣ማን ከበራት የጠኔከረኟ ቀጭኑዋ ሚሰኒ እጉሳንታ የወደቀኟት አለት በነበረው ረጅም አድካሚ ጉዞ ያስመሰከረ ችው ድፍረት እኮ ነው። ያሰ የዊከስ ዘሮች ያላቸው የማይጨበጥና ልታይ ልታይ ያልበዛበት — አስክርሉት እስካሁን ያልተረዳቸው ግን አስተዋጽኦ ያደረጎችሉት —ድፍረት ነው።

"በይ ወደአልጋሽ ሂጂ" አለች ከትከሻዋ በላይ እየተመለከተ ቻት። "ሂጂ አለበለዚያ ትሞቻለሽ።እኔ እጠራርግሻለሁ ወለሉን ይህን ከቀዘርክ በኋላ"

"ማይሰኽም በእራሴ ጨርቅ እኔ አጠራርጎዋለሁ።" አለች ሚሰኒ ወለሉ ላይ ያለውን ደም በመጠየኳ መልክ አያየች።

"ምን ጥሩኛ ማደይ አራስሽን ፤ ደንታዬ መስለሽ! እና ለዎቻችን ከተመለሰ ከሌት እንዳይወጡና ፈረሱም ከእንዴጋ ጠጭ የመጣ ነው ብለሽ ንገሪያቸው።"

@OLDBOOKSPDF

ሚለኒ በጠዋት ጨረር ውስጥ እየተንቀጠቀጠች የሬሳውን ሙን ቅሳት የበረንዳው ደረጃ እየገጨው ሲወርድ ዘንናትና ጆሮዋን ያዘች ።

ፈረሱ ከየት እንደመጣ ማንም አልጠየቀም ። ከጦርነቱ በታ የመጣ ስመሆኑ ጥርጥር የለውም ። ሁሉም ፈረስ በማግኘታቸው ተደስ ተዋል ። ያ የሞተው ያንኪ አስከሬሉት አሃሪቹ ሥር ሚርጫር ካደረገ ችው መቃብር ውስጥ ገብቷል ። በአካባቢው የነበሩት ቁጥቋጦዎች በስብሰው ስለነበር አስከሬሉት ማታ ከማድቤት ቢለዋ ይዛ ሄዳ ጨፍ ጨፍ ቢታደርጋቸው ባጓጓፍታ መድቀው መቃበሩ ላይ ተረበረቡ ። እንዚህን የጓሮ አዕዋት የመትከሉ ሥራ እንዚያ ኔጣሮዎች ነግሩን እን ዲያውቁ ስለሚያደርግ አስከሬሉት አይሆንም ብላለች ።

ከዚያን ቀን ወዲህ ደስሚት እንቅልፍ ባጣችበት ሌሊት ውስጥ ከዚያ ተመቃበር መጭት ያስጨነቃት ጣረ ሞት የለም ። ትዝታ ውም እንምሮዋን እረፍት አልነሳውም ። ነግሩን ዝፈአመች ወር እንኳ ሳይሆነው ትዝታው መጥፋቱ ዘጣም ገረማት ። ቆንጆዋ ፡ ጉንጨ ስርጉ ዲና ባለጉትቻዋ አስከሬሉት አሃራ ፣ መላ የለ ኽዋ ሴትዮ የያንኪ ሙን ቅሳት በታትና ጫር ጫር ባደረጣችው ኑድንድ ውስጥ መቅበርዋ መቼም ጉድ ጉድ የሚያሰኝ ነገር ነው፤ አስከሬሉት ፣ ከዚህ ቀደም የሚያውቋት ይሆን ሲስሙ ምን ይሉ ብላ ስቅቅ አላት ።

"ከእንግዲህ ስለዚህ ነገር በጭራሽ አላስብም ።" ብላ ወሰነች ። በቃ አንዴ ሆኗል ። ባልገደለው ዋሮ ዋናዋ ጅል በሆንኩኝ ነበር ። መቼም ቤቱ ከመጣሁ ጀምሮ ተለሙሮ እንደሆነ እንጂ ይሄን ነገር አላደርገውም ነበር" አሰች ። ላስበው ብላም ባይሆን አንድ ችግር ወይም ከባድ ሥራ በገጠማት ቁጥር "እንኳን ይሄንን ማድያን ያህል ነገር ፈጽሚያለሁ" የሚለው ነገር አዕምሮዋ ውስጥ ይቀርጽባታል ።

እራስዋን ለማወቅ ከምትችለው በላይ ተለውጣለች ። በ"አሥራ ሁለቱ ዋርካዎች" የባርያዎቹ አትክልት ቦታ ውስጥ ተኝታ ልቡዋ ውስጥ የተፈጠረው ቁርጠኝነት ቀስ በቀስ እየጠነከረ ፡ ቀስ በቀስ እየደነደነ መጣ ።

※ ※ ※

አሁን አስከሬሉት ፈረስ ስላላት የጐረቤት መንደር ሰዎች ሁሉ ምን ሆነው እንደሆን ለማወቅ ትችላለች ። እቤት ከመጣች ጀምሮ ያስ ጨንቃት የነበረው—"ባገሩ የተረፍነው ሰዎች እኛ ነን እንዴ!ሁሉም መንደር ከኛ በቀር ተቃጥሎ ይሆን? ሰው ሁሉ አብሮ ተቃጥሎዋል ወይስ ወደ ማዘን ተሰድዶ ይሆን ?"የሚለው ጥያቄ አሁን ምላሽ ያገኘ ይሆናል ።

የአሥራ ሁለቱ ዋርካዎች ፡የማኪንቶሽ የአትክልት ቦታና የስላ ተራዎች ቤት መጋየትና መፈራረስ ትኩስ ትዝታ ከአእምሮዋ ላይ

@OLDBOOKSPDF

ጠፋ ይህን አዲስ እውነት ስለ ሰው ሁሉ አስፈራት። ብቻ ከመጨ
ነቅ ያየመጨረሻ አስበፈም ነገር ቢሆን አውቆ መጎሳገል ይሻላልና
ወደፎንቱን ቤተሰብ ሄዳ የሆነውን ለማየት ወሰነች። ፎንቱን ይኖር
ይሆናል ብላ ነው። ሚሲሲ ዶክተር ያበፈልጋታል። ልታግማም የሚገ
ባትን ያህል ስላልተሻላትና ድክምክም የማስትዋ ነገር አስካርሴትን
በጣም አሳስቢታል።

እናም የእግሮ ቁስል በዳነ በመጀመሪያው ቀን እዚያ ያንኪ
ፈረስ ላይ ፈጥ አለች። አንድ እግሩን በእጁሩ ኦርኳብ ላይ ሌላ
ውን በሌላው በኩል ባለት የኮርቻ ግምት ዘርግታ ሚዳውን አቋርጣ፣
መቼም ተቻዋለሎ ነጩ የማንነው ብላ ተጠናነፈ። ወደ ሚሞሳ ሂደች።

ይሣረምሽ ብሉ በሚሞሳ ዛፎች ማህል ቢጫው ቤት ድብዝዝ
ብሎ ፊት አንድ ነበረው ቁሚል። ትኩስ ደስታ— ደስታም ቢሉ የእ
ንባ ጉሮሮ የቦቃሳቦለበት ደስታ — ሶስቱ የፎንቱን ቤተሰብ ልጆች
ሲመጡ ስታይ ፈነቀሳት። እሷ ዘአንባ ተረሽ ደስታና ጩኸት ሊስ
ሙዋት ወደሱዋ ሲንደረደሩ ታመሰክቱች።

የመጀመሪያ የእንደምንሽ ስላምታና መላሳም አብቅቶ ወደ ምግብ
ቤት ሄደው ቁጭ አንዳሉ አስካርሴት ልቡዋ ቅዝቅዝ አለባት። ሚሞሳ
ከመንገድ ውጪ ወደ ውስዋ ገባ ያለ በመሆኑ ያንኪዎች አልደረሱ
በትም። ስለዚህም የፎንቱዎች ንብረትና ዕቃ በሙሉ እንዳለ ነው፣
ነገር ግን ታራንና ሴሎቹን የገጠር መንደሮች የወረራቸው ዝምታ
ሚሞሳንም ተጠናወቷቷል። ባሪያዎቻቸው በሙሉ ከአራት ኀረዶች
በስተቀር የያንኪዎችን መምጣት አይተው ፈርተው ኮበልለዋል።
ገና ከሽንት ጨርቅ ያልተላቀቀው ሕፃኑ ጀ እንደ ወንድ ካል
ተቆጠረ በስተቀር ወንድ አሚባል በቤቱ የለም። እቤቱ ውስዋ
ያሉት ትልቋ አያታቸው ፎንቱን፣ የሳቸው የልጃቸው ሚስት—የሃ
ምሳ አመትዋ ወይዘሮ — ግን ወጣቱዋ ወይዘሮ እያሉ የሚጠሩዋትና
ሃያ አመት ሊሞላት የተቃረበችው ሣሊ ናት። ከጉረቤት ሁሉ ርቀው
ያለጠባቂ የተቀመጡ ናቸው እንጂ ፍርሃት ቢኖርባቸውም እፊታ
ቸው ላይ አይነበብም። ምናልባት ብላ አሰበች አስካርሴት፣ የሚሀን
ካክታ ቀርቶ ድምጽ እንኳን ለማሰማት አያታቸው በመኖራቸው ፈር
ተው ይሆናል ሣሊና ወጣቷ ወይዘሮ ዝም ያሉት ብላ ገመተች።
ብኋላም አስካርሴት አራፅም ጭምር የአሮጊቷን እንደበተ ስልነትና
የሚዋጉ ዓይኖች ታውቅ ስለነበር ፈራቻቸው።

ምንም እንኳ የሥጋ ዝምድና ባይኖራቸውና የዕድሜ ክልላቸ
ውም ተቀራራቢ ባይሆን እነዚህን ሴቶች ያስተሳሰራቸው የጋራ ችግ
ርና ልምድ አለ። የመንፈስ ዝምድና አላቸው። ሶስቱም እቤት ውስዋ

@OLDBOOKSPDF

@OLDBOOKSPDF

"እኛስ እንዴት መቆም እንዳለብን አላውቅም ምን ጉድ ነኝ እኮ! ብቻ ባፈጥጥኝ ውሉ ጎልጎታ ቢ ሚያኸው እዚህ የሚሠራ መሳቅ ሥራ ስለነበር ነው በመሐዲ ያልኾኑት ። ግን እንደምንም ጊዜውን ማሸጋገሪ እኛ ብዙ መፍትሔ ሳደርስት የሚሠራው ሥራ አልሠራ ሁም እና ደሞዝ ። ግን ደግሞ ምኑ ምን "አስራ ሁለቱን ዋር ዘምኦንን የመቅኔ" ዓይነት ሲሉ እግዜር ሁሉ ታሪክም ደጋየ ሥራ ብሉን ስለመሆኑ መጀሀ ሰው እኛ ነን ታዋቂም ። ሰምኾ ሁሉ ወዲ ማስኔ የሚሰሥሉ ነባር ንምሉኑ ። በዛ ላይ አሰካርሏሁ ፣ አንቺ እብትሽ መጠ ሁሽቅ የሚል ማጥቅ ይሕልማኾሁም በውኖችንም አልነበረም ። "

"ኔትዬ የሚ ስሙር አሃሪ ባሪያሙኛ ሁሉ በፍርሃት እየራዱ እንዳ ነበን ሣር ብለው መ ሥራ ያኛሙ ታውን ሊያቅጥበሣት ነው ብለ ሙ እንሥራን ንግድ ብለን ሂህና ጥሁ ብለን እንጠርጥር ልኟ?" አለ እሮንትም አሥረጡና ።

"ድማም እኮ ሰማኑ እንደምልነው, , ," ብላ መጣገር ጀመረች ግሊ ።

"ኔባኽሽ እሱ ይሄን የምጣረው አስ ያኛሙቹ ታራን ሁሪ ያጥን ኣበለ ሠራሪያሉ ከሰፋብን ንሳንተም ግሽ ትሽንኣችሁን ለቀቅለሳች ። ወሥጊዜን ለነብሥት አሰሳችኋል ስለተባለ ነው ። ታዲያ የዚ የኔ ነብት ማኮ መኖታሪ እቅጣጫ ከባድ እሰቅ ቀንሳ ። የኛ ባሪያምችም ላይቀሩ ሳሄናሃለው ጥለውን ሸሹ ። ምን ነበር የተ ቀጠለ ልኟ?" አለ አሰንኒ ።

"መቶ ሃምሳ ሺህ ብር ያለጣ የንበረው የጥቅ ሰብሳችን ነበር የተ ሸጥነው" አሉ አስካሊሰት በምሬት ።

"ኧረ ተመስገን ነሙ—አንኳን ቤታችሁ ያልሆነ" አሉ አሮጊ ቅቅ አገጫቸውን መሰቀጣው ላይ አድርገው ። "ምንጊዜም ጥቅ ማብቀል ትኾሳባችሁ ቤተ ማሳቱል ግን ከአንግዲህ አትችሉም ። በነ ገራችን ላይ ጥቅ ሰቀማ ጀመራችሁ እንዴ?"

"እንዳውም አለኛ አሰካርሉት "አብዛኛው ጥሻችን መድ ሚራ ። ሦስት ሽኽም እንኳ አይወጣውም የቀረው ። ለዛውስ እዚያ አገር ዳርቻ ውስጥ ምን አርባና ይኖረዋል ? ባሪያምችችን ሁሉ ኮበ ልለው የሚለቅመው አጥቷል ከናካቱው ። "

"በጐዴ ወጣህ ባሪያምችችን ሁሉ ኮበልለው የሚለቅመው አጥቷል ? "

"ምነው ያኮቪ አመልማሉ ጣቶችና የእሀቶችሽ እጅች የማንን ጐራፊ ያበጥራሉ ባክሽ አ የእኔ ሰት ወይዘሮ!"

@OLDBOOKSPDF

"እኔው እኔ ጥጥ ልሰቅም?" አለች እስክርሌት እያለቀሰች ፤ እሮ ጊቷ ወንጀል የተናገረች ይመስል ። "እንደሚዳ ሰምችገ እንደ ርካሽ ነጮችገ እንደ ስላቱሪ ሴቶችገ እ?

"አም ፤ ርካሽ ነጮች! ወየው ጉድ ፤ የዛሬ ዘመን ሌጆች እኮ ለፈስፋሶች ገልቱምች ናችሁ! ልንገርሽ የእኔ እመቤት — ዱሮ ልጃገረድ ሆኜ አባቴ ሀብቱን ሁሉ ሲያጣ ክጨዋ ልጅ ሥራ በላይ ተራ ሥራና እሚዳ ድረስ እየሄድኩ አባቴ ገንዘብ እስኪያገኝና ባሪያ እስኪገዛ የቀን ሥራ ሁሉ እሠራ ነበር ። ድርሻዬን በዶማ ቆፍሬ ጥጤን ለቅሜ አስገባ ነበር ። አሁንም አለፈሳጊ ከሆነ አሳምሬ እሠራ ለሁ ። ደሞ የሚያስፈልግ ይመስላል ። ሆሆ የርካሽ ነጮች አልሽ!!"

"አይ እማማ ፎንቴን" አለች የልጃቸው ሚስት ወደሁለቱ ሴቶች ዞራ ፤ አሮጊቷን ለማበረድ እርዱኝ የሚል አስተያየት እያ የች ። "እዩ እማማ ያ ዱሮ ነው ስንትና ስንት ዘመኑ ፤ አሁን ጊዜው ተለውጧል . . . " አለች ።

"አይ ወዲያ ፤ ጊዜ ሥራ አትሥሩ ብሎ አልተለወጠም ፤ መልካም ሥራ የሚያስፈልግበት ጊዜ አልተለወጠም" አሉ ባለ ሰላት ዓይኑዋ አሮጊት ማባባልዋን አልቀበል ብለው ። "መልካም የጨዋ ልጅ ሥራ ጥሩ ሰምችን ርካሽ ነጭ ያረጋቸዋል ስትይ እዘህ ተገትረሽ — ለእ ናትሽ አፈርኩላት እስክርሌት! አዳም ጥሮ ግሮ ሲቆፍርና ሔዋን ስት ፈትል . . . "

እስክርሌት ኑገሩን ሰመለወጥ ፈጠን ብላ "ታርሌቶኖችና ካልቨር ቶችስ እንዴት ሆኑ? ተቃጠሉ? ወይስ ወደማክን ተሰደዱ? "

"አይ ፤ ያንኪምች ፤ ታርሌተኖች ዘንድ አልደረሱም እኮ ። እነሱም እንደኛው ከመንገድ ውጪ ነው የሚኖሩት ። ይልቅስ ካልቨርቶች ዘንድ ሄደው ዘረራዋቸው ። ንብረታቸውንና ከብቶቻቸውን ጥርግርግ አድርገው ወሰዱባቸው ። ባሪያዎቹንም ክነሱ ጋር አስኮበለሉዋቸው ።" ብላ ጀመረች ግሊ ። ግን ትልቋ አያት አቋረጧት ።

"አ! እነሱንማ የሐር ቀሚስና የወርቅ ጉትቻ እንሰጣችኋለን ብለው ደልለዋቸው እኮ ነው ። ካትሊን ካልቨርት እንዳለችው እንዳ ንዶቹ ያንኪምችም ባሪያዎቹን አፈናጠው ነው የሄዱት ። ምን ያም ሆነ ይህ ቢጫ ዲቃላ መውለድ ነው የሚተርፋቸው ። ከያንኪ ደም ምንም የተሻለ ዘር አይገኝም ። "

"ወይኔ እማማ ፎንቴን!"

"አይ ፈትሽን እንዲህ ኮሶ አታስመስይ ጂን ። ሁላችንም ያነ

@OLDBOOKSPDF

ባን ሴቶች አይደሰን እንዴ፣ ታዲያ ከዚህ ቀደም ዲቃላ ወይ ክልሰ አይተን እናውቃለን ፣ ምንድነው ግር ያለሽ?''

''ታዲያ የካልቨርትን ቤት ለምን አላታጠልትም ?''

''የሁለተኛዋ ወይዘሮ ካልቨርት የአንጋገር ዘዴና ከዚህ ቀደም ይገ-በኛት በነበረው ያንኪ ሐልሚተን ሙምር ብርታት ነው ቤቱ የተረፈው ።'' አሉ አሮጊቷ ሁልጊዜ ከባሷ ተፋታ ከቤቷ የወጣችን ሴት ወይዘሮ 'ሁለተኛዋ ካልቨርት' ብለው በሚጠሩበት አጠራር ተጠ ቅመው ፤ ምንም እንኳ የመጀመሪያዋ ካልቨርት ከሞተች ሃያ ዓመት ቢሞላት ።

''ጌኛ ቆራጥና የማናወላውል የኮንፌደሬሲው ደጋፊዎች ነን'' አሉ አሮጊትዋ ፤ ቃላቶቹን በቁጭን ረጅም አፍንጫቸው እያዙ ። ''ካትሊን እንዳለችው አንዳችን ሽቅብ አንዳችን ቁልቁል ሰንሮጥ የካልቨርት መጣቢያ መውጪያ በያንኪዎች ተጥለቀለቀ ። ሚስተር ካልቨርትም የትም ዳር ወድቆ ቀረ፤ ሬይፎርድ ጌትስበርግ ውስጥ፣ ካድ አቨርጂኒያ ውስጥ ከሠራዊቱ ጋር ቀሩ፤ ካትሊን ግራ ከመጋባቱዋ የተነሳ በድን ሁና ቤቱ ቢቃጠል እንደምትመርጥ ትናገራለች ። ካድ እቤት ተመልሶ የሆነውን ሁሉ ቢሰማ በቆመበት ደርቆ ይቀራል አለች ። ብቻ የያ ንኪ ሴት ያገባ ሰው ዋጋው ይሽው ነው—ክብር የለ ፣ ትህትና የለ ሁልጊዜ ሰለ እራሳቸው ቆዳ ማሰብ . . . አስካርሌት ለመሆኑ እንዴት ታራን ሳያቃጥሉዋት ቀሩ ?''

አስካርሌት ከመመለሰዋ በፊት ጥቂት ቆየች ። የሚቀጥለው ጥያቄ ''ሰምቻችሁ እንዴት ናቸውነ ውድ እናትሽስ?'' መሆኑ በደንብ ታውቂ ቷል ። ኤለን ሞታለች ብላ ልትነግራትው እንደማትችል ደግሞ ታው ቃለች ። የእናቷን ነገር መናገር ቀርቶ እነዚህ ሴቶች ባሉበት ቦታ ብታስብ በፅንባ ጉርፍ ተጥለቅልቃ እስኪያጣት ጮሀ እንደምታለ ቅሽም ታውቃለች ። ማልቀስ ደግሞ አትፈልግም ። ቤት ከመጣች ጀምሮ አምርራ አልቅሳ እታውቅም ። አንዴ የእንባዎቿን በር ከከ ፈተች ደግሞ ማባሪያም የለቸው ። ያንን ያጠራቀመችውን ድፍረትም ይሰልቧታል ። በአንድ በኩልም እንዲህ ግራ ግብት እንዳላት ዙሪያዋን ከበው ለሚያዳምጧት ፎንቴኖች የእናቷን ሞት ካል ነገረቻቸው ደቅርታ እማይደረግለት ቂም ሊይዙባት ነው ። በተለይ ትልቋ አያት ቅንጣት ታህል ከብር ለማንም የመንደሩ ሰው የማይ ሰጡ ሆነው ለኤለን ግን ልዩ አስተያየት ስለሚያደርጉ እሳቸውን መደ በቅ አያዋጣም ።

''ተናጋሪ እንጂ'' አሉ አሮጊቷ ''የምታውቂው ነገር የለም እንዴ?''

@OLDBOOKSPDF

— 886 —

@OLDBOOKSPDF

አሰበርሱት ልህ ድንገተ እንሰለ አንድ እጁዋን እፈረሱ ሙ ላይ ጣል አድርጎ አያቋ ተመለሸ።

"እሁን" አለ አሮጊትዋ "ምንድነው ታራ ውስጥ ያለው ? ምንድነው የሠሙሽኝ ነገር?"

እስከርሱት ትዝር ብሳ ወደ አረጀት ቫይኖች ተመለከተችና እውነቱን ሳታገላ መናገር አለመምሻሽል ታወቃት። ማ ም ለሙ በስ ልጅ አያት ፀንሱን ሰት ያሉሰቸው ፊታደ ማልቀስ ሊይተልም።

"አማን ሞታሽ" አለች እንዳው በጎረቤ ። ከዛዲን የያዘችው እጅዋ ወደ ዝቅመሌ እጠፌሰው ጀረሰ ተብት አድርገው ያሟት። ከጨርሣታምዝ ቅንድብዋ ሥር ያሉት ዓይኖዋ ተጨናቅሩ።

"ምንድምነ ነገሩሰት?"

"የለሙ በታሽ በጅሩ ምሁሽ። አረፈች። አፄ አቤት ከመድረሴ ከአንድ ቀን በፊት አረፌች።"

"እይሠሽ አታስብ" አለ አሮጊትዋ "አስታሽ—አባትሽስ እንደ ምን ነው?"

"አዩ ፣ አባባን አሳሙ አያዲስ"

"ምን ማለትሽ ነው ሳናገለው እሳጀ ሥጣል እንዲ?"

"ድንጋይና ..... ለሳ አደረጉበት ልብ።ቢጭራሽ አራሱን..."

"አራሱን በጀል አንበይ ... ሥጋትሱ ለስ አይደለም ማለ ትሽ ነጠሳ"

እሱ ሌንደዚህ በመ ... ሲንገር መለማት እፎያታ ነው። አሮጊትዋ የሚያስቸል ነገስን ሠማልሜ—ማለተዛዘኛ ፡ አለ መናገሩዋ እንዲት ማልጣል ነው ጀል።

"እዎ ሙማቅላቱን ስጀል" አለች ቅዝዝ ብላ። "መላ ቅጡ ጥፉ ይለዋል። እማማ መሞትሙን ሳምር ይዘነጋል። ሙይ እማማ አያድርስ ነው። አንዳንዴማ እናቱ የምትመጣ እየመሰለው ለሰዓ ታት ይጠብቃታል። ደሞ እዩ በስንት ትእማሥት መለለዎ የሚጠ ብቃት። ዱሮ ዱሮ እንደሕዎን ልጅ ትእማሥት የለሽ ነበር። መሞ ቱዎን ያስታውስ እንደሆነ ደግሞ ጭራሽ ይበስበታል። በየጊዜው የሰቧን ያመጹ ለመስማት ጀሮውን ሳ ር ይሉይና ብድግ ብሎ ከቤት ወጥቶ ቁልቁል መያመታብር ቢነ ይሮጣል። ከዚያ ፊቱ እንባ በእንባ እንደታጠበ እየተሳተተ ወደቤ ይመለሰና ለልችዎን እስከ

@OLDBOOKSPDF

ሙህ ድረስ "ኬቲ እስካርሌት ወይዘሮ አሃራ እኮ ሞተች ፤ እናትሽ ሞታለች" ይላል ። ልክ ለመጀመሪያ ጊዜ እንደሚያረዳኝ አድርጎ ነው የሚነግረኝ ። ትላንት ማታ ደግሞ ውድቅት ላይ ተነስቶ ሲጠራት ሰምቼ ከአልጋዬ ተነሳሁና እርሻው ቦታ ከአንድ የታመመ ባሪያ ጋር ነው ያለችው ብዬ ነገርኩት ። እሱ ግን ለምን ባሪያዎችን በማስ ታመም ራስዋን ታደክማለች ብሎ ተነጫነጨ ። እሱን ለማስተኛት በጣም አስቸጋሪ ነው ። ነገሬ ሥራው ሁሉ እንደ ሕፃን ልጅ ሆኗል። ዋ ይክተር ፎንቴን በኖረ እንዴት ጥሩ ነበር! ለአባባ አንድ ነገር ያደርግለት ነበር! ሜላኒም ዶክተር ያስፈልጋታል ። እሷም ልጅዋን መውለድ እንደሚገባት ሁና በወቱ አልተገላገለችም ። "

"እሰይ . . . እሰይ . . . ሚሊ ልጅ አገኘች ? . . . እንቺው ጋ ነው የተቀመጠችው?"

"አዎ ፤ አብራኝ ነው ያለችው ። "

"ሜላኒ ምን ታደርጋለች እንቺ ዘንድ ለምን ከአክስቷና ከዘመዶችዋ ጋር ወደግቢን አልሄደችም? የቻርለስ እህት ከመሆንዋ በስተቀር ትወጃት አልመሰለኝም ። በይ ሁለቱንም ከሥረ መሠረቱ ንገሪኝ ። "

"አዩ ፤ ታሪኩ ብዙ ነው እማማ ። እቤት ገብተው ቢቀመጡ አይሻልዎትም ?"

"ግዴለሽም ቆሜ ማዳመጥ እችላለሁ" አሉ አሮጊትዋ ባጭሩ። "አየሽ ልጄ ፤ ሴሎቹ ፊት ከወራሽው ወይ ይስቱብሽ ወይ ጮክ ብለው ሊያወሩብሽ ስለሚችሉ ሐዘን ላይ ይጥሉሻል ። በይ አሁን ንገሪኝ ። "

እስካርሌት ታሪኩን ከወረራው ጀምራ እየቆራረጠች ስለሜላኒ ሁኔታ ማውጋት ጀመረች ። ትክ ብለው ከሚያይዋት የእሮጊትዋ አይኖች ሥር ሁና ታሪኩዋን ስትቀጥል ድፍረት እየዘራች ኃይለ ቃልና የሰቆቃውን ሁኔታ ሁሉ መግለጫ ቃላት እያገኘች ሄደች ። ያ የሚያስፈራው ወበቃማ የወሊድ ቀን ፣ የነበረው ሲቃ-ሰቆቃ ፣ ፍርሃቱዋና ሬት ከድቷቸው መሄዱ ሁሉ እንደገና በሀሳቧ መጡባት ። ስለጫካው ድቅድቅ ጨለማ ፣ የወዳጅ ይሁን የጠላት ስለማይ ለይ የእሳት ውጋጋን ፣ ስለነደዱትና ከሰል ስለለበሱት ፣ በጠዋት ዓይኗ ውስጥ ስለገቡት የጭስ ማውጪያዎች ፣ በመንገዱ ላይ ስለተረፈረፉት ሰዎችና ፈረሶች ፣ ስለረሀቡ ፣ ስለተራቆተው ምድረበዳ ፣ ታራም ጋይታ ይሆናል ስለሚለው ስጋታቸው ሁሉ አወራችላቸው ።

@OLDBOOKSPDF

"እኔማ መቼ እናቱ ጋ ደርቼ ፣ የከበደኝን የኑሮ ጫና ሁሉ ለእሷ ዘርግፌ ፣ እሷው እንደሚሆን ታደርገዋለች ሰል ነበር ። ወደ ቤቱ እየሄድኩ ሳለሁ የመጨረሻው በኔ ላይ ሊደርስ የሚችለው አስከፊ ነገር ደርሶብኛል ፤ ከዚህ የከፋ ምን ይመጣል አለ ነበር ። እቤት ደርሼ የእናቱን መሞት ሳይ ግን የመጨረሻው አስከፊ ነገር በእ ርግጥ የእሷ መሞት መሆኑን ተረዳሁ ። "

አይኖችዋን ወደመሬት ደፋችና አሮጊትዋ እንዲናገሩ ዝም አለች ። ዝምታቸው ቀጥሎ ከመርዘሙ የተነሳ ፤ አሮጊቷ የተና ገረችውን ተስፋ አስቆራጭ መከራ ሁሉ ያልሰሙዋት መሰላት ። በመጨረሻ አሮጊቷ ድምጽኽ- አስካርሉት ከዚህ ቀደም እንዲህ ሩህሩኅ ነው በማታውቃቸው መንገድ - ይመው ጀመር ። ለማንም እንዲህ በልስላሴ ተናግረው አያውቁም ።

"ልጄ ፣ ሴት ልጅ ሊደርስባት የሚችለውን የመጨረሻ አስከፊ ነገር ስታይ ደግ አይደለም ። ምክንያቱም ያን ካየች ወዲያ ምንም የምት ፈራው ነገር አይኖርምና ነው ። ደሞ ሴት ልጅ አፈራዋለሁ የምት ለው ነገር ከሌላት ጥሩ አማይደል ። የተናገርሽው ያልገባኝ እንዳይ መስልሽ ። በምን ማጥ ውስጥ እንዳስገፍሽም ያልተረዳሁ አይምሰልሽ ፤ አሳምሬ ተረድቼያለሁ ። አየሽ ባንቺ ዕድሜ ሳለሁ የፎርት ሚምስ እልቂት በኋላ በተንሳፋ የክሪክ አድማ ዘመን ነበርኩኝ ። እም" አሉ ከሩት የሚመጣ በመሰለ ድምጽ ። "የዛፌ ሃምሳ ዓመት በመሆኑ ልክ በእ ንቺ ዕድሜ ይሆናል ። እኔ እፋጥጬው ውስጥ መደበቅ ችዬ ስለነ በር ቤታችን ሲቃጠልና ሕንዶቹ እህቶቻችንንና ወንድሞቻችንን ራስ ራሳቸውን ሲቆርጡዋቸው አይ ነበር ። ምንም ማድረግ ስለማ ልችል የአሳቱ ውጋጋን የተደበቅኩበትን እንዳያሳይብኝ እፀልይ ነበር። እናቴን ከቤት ጐትተው አውጥተው እኔ ከተሸሸግሁበት ሃያ ሜማ እርቀት ሳይ ገደሉዋት ። እሷንም እራሱዋን ቆረጡዋት ። በየ ጊዜው ሌላው ሕንዳዊ መደሱዋ ይመለስና በረጅም ሾተሉ የራስ ቅል ዋን ይጨቀጭቃል ። እናቴ እንዲህ ያለው ጭካኔ ሲፈጸምባት እኔ ልጅዋ እዚያ ተኝቼ በአይኔ በብረቱ ተመልክቻለሁ ። በነጋታው ጠዋት ከዚያ አቅራቢያ ሰላሳ ማይል ርቀት ላይ ወዳለው መንደር ሄድኩኝ ። በረግራጋው ፣ በሞታው ግጥና በሕንዶቹ ማህል አቋ ርጪ ወደዚያ መንደር ለመድረስ ሦስት ቀናት ፈጅብኝ ። በኋላማ ታብዳለች ይሉኝ ጀመር ። እዛ መንደር ውስጥ ነው እንግዲህ ዶክተር ሮንቲንን ያገኘሁት ። እሱ ይጠብቀኝ ነበር ። ያ እንግዲህ የዛፌ ሃምሳ ዓመት መሆኑ ነው ። ቅድም እንደነገርኩሽ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ጥርሃት የሚባል ነክቶኝ አያውቅም ። ሊደርስብኝ የሚ

@OLDBOOKSPDF

ችሰው አሸነፈ ንጉሥ ደርሶብኛልና። ታዲያ ይህ አሳመራሱት ከብዙ ችግር ላይ ጥሎኛል። የብዙ ደጎታም ሞኝ ልኮናልና። እማዘሃር ቤቶች እንዴጨመቁኝ እንዳፈሩ አያለሁ የፈጠሩትም ነመሠኑ የማይ ፈሩ ሰዎች ከሰ የጥፈጥሮ ኣሣበሩ ያልታደሉና ህሰው ጠፎ የሆኑ ናቸው። አዘነርሱም ፤ እንድ የኮታሪቅረው ሰው እንደምታጥሬ ሁሉ አንድ የሆ ተፈፈው ትር አንዛሳርኝ ኣሣርጊ አሳ።

ድምጽና ሀሴ ጠሩ ኑንሞኝ ሃሳብ ዓመት በፈት መደነበረባ ችው ሞኒሃ የሚሆሳ ነሳ ሳይሆን ከናሥ ፀጥ ብለው ቆመ። ነ አስ ኣሳት ንጉሣሰን የሣመን ነገቅሳቀሰች። አሮጊቷ ችግ ሩዋን ተረጅተው መሳኔሌጠን ያጨለመጥት መሰሎዋት ነበር። ነፃር ግ እሰዘ ሠ ማንም ዘሰው ወሮሜ ሃሳ በው እንደሚያደርገው ውሉ ሩ ከሞ ዝሰሱ ሰ ነገረ ሃሳ ሰው ስሜት የሚኤሠ ነ ሠ ኣሠ ኣ ኣ ኣ

@OLDBOOKSPDF

@OLDBOOKSPDF

ትተኛ እንደነበር ተከራርታ እየተናገረች ወይ ፍንክች አለች። ዴልሲ ብቻ ገም ብላ እይኑዋን ሳታሽ ከቆመችው ከፕሪሲ ጋር ተደምራ ፀጥ አለች።

እስካርሌት የተቃወሙ ዐዐ ግታቸውን ሳትቀበል ሁሉንም እየ ነዳች ወደጥጥ እርሻው አስማራቻቸው። ሆኖም ማሚና ፖርክ በጣም እየለገሙ ስላስቸገሩዋት፡ ማሚኝ ምግብ እንድታበስል ወደ ማድቤት ፖርክ ጥንቸልና አሳማ እንዲያድንና አሣ እንዲያጠምድ መረቡን አስይዛ ወንዝ ወዳለበት ጫካ ላከቻቸው። ጥቂ ለቀማ የፓርክን ከብር የሚነክ እደንና አሣ ጠመዳ ግን የማያዋርዳው ሥራ ነው።

እስካርሌት ቀጠለችና እህቶችዋንና ሜላኔን ለጥጥ ልቀማ ሞከ ረቻቸው። ነገር ግን ምንም የተሻለ ነገር ሊሠሩ ሳይችሉ ከእጅ አይ ሻል ደማ ሆኑ። ሜላኔ ስትለቅም የሚያህላት የለም፡ ፈጣን ና ት-ጥራት እላት- በሙሉ ፈቃደኝነትም ትሠራለች። ግን በጠራራው ፀሐይ ውስጥ ለአንድ ለዓት ያህል ከሠራች በሁዋላ ቀስ በቀስ ልቧ ፍስስ ድክምክም ትልና ለሳምንት ያህል የአልጋ ቁራኛ ትሆ ናለች። ሱዌለን ልዩስፍስና አልታሻ ናት። በዛ ላይ ትልሚማለች። እን ደሜላኔ ልቧ የፊስስ ለማስሞስለ ትሞክራለች ብቻ አስካርሌት ጠር ሙስ ሙሉ ወፀ ፊድ ላይ ስትደረግባት እንደተቆጣች ድመት እንትፍ እያለች ራሱዋን ይዛ ትነሳለች። በመጨረሻ አልሠራም ብላ እቅፉን ተናግራ ተነሣመች።

"እንደባሪያ የሚጸ ሥራ አልሠራም፣ አንቺም ልታሠሪኝ አት ችይም፣ ጓደኞቻችን ይዘን ቢሰሙ ምን ይሉናል፣ ሚስተር ኬኔዲ ቢ— ቢያውቅ ምን ይመጣሻል፣ ወይኔ እማማ ብታውቅ ኖሮ..."

"ከእንግዲህ ወዲህ ሱዌለን አሣራ የእናቱን ስም ታነሽና በየፊ ንው የማሬጨልሽ! "ብላ ፈገሸኑ እስካርሌት" አናቱ ከየት-ኛውም ባሪያ የተሻለ ትሠራ እንደነበር በደንብ ታውቂያለሽ... የኛ ሽትርቅር እ!"

"በቁራሽ! ቢያንስ የሚጸ ሥራ እትሠራም። አንቺ ደግሞ እኔን ልታሠሪኝ እትችይም ቆይ ላባዬ ብልኝማር! እሱ እንዳልሠራ ያደ ርገኛል!"

"ደም በኛ ጣጣ ውስጥ አባሳን ልትከቺው!" አለች እስካር ሌት ባንድ ፊት የእህቷ ጋጠወጥነት እያናደዳትና ባንድ ፊ ለእባቷ እየፈራች።

"ጎኔ እማዝሻለሁ ሱዚ" አለች ኪሪን ቅዝቅዝ ብላ። "የ-ሱንና የእኔን ሥራ ደርቢ እኔ እሠራዋለሁ። ግና ስላልተሻላት ሀሐይ ላይ መዋል የለባትም።"

@OLDBOOKSPDF

እስካርሌት በምሽጋና አንጋገር "በጣም አመሰግናለሁ የኔ ቆንጆ" አለችና ወደትንሽ እህታ በሞንቁት ዓይን አየች ። ያቺ እንደጥከ እበቦች ትንቡከቡከ ያለች ወይን ጠጅና ነጭ ቀለም የፈሰሰባት የመሰለች ትንሿ እህትዋ ካሪን ፣ ወይን ጠጅ መልኩዋ ይገፈፍ እንጂ ሞንቅ ያለው ፊትዋ አሁንም የፍካት ደም ግባት ተላብሷል ። ራሱዋን ከማወቋዋና ልብ ከመግዛቱዋ አስቀድሞ ዝምተኛና ፍዝዝ ያለች የነበረችው ይቺ ልጅ ብዙ ነገር ተለዋውጦ ነው ያየችው ። አሁን ሞታለች ፣ እስካርሌት ጨዋሂና ተሳዳቢ ሆናለች ። ዓለም ሁሉ ግልብጥብጥ ብሎ ተለውጦ የዕለቱ አንገብጋቢ ጥያቄ ደከመኝ ሳይሉ መሥራት መሆኑን ተማንዝባለች ። የካሪን ለስላሳ ተረጥሮ ለወጮን የሚቀበል ዓይነት ፣ ከተለወጠው ሁኔታ ጋር ማሰተካከል የምትችለው ዓይነት አልነበረም ። በትክክል ምን እንደተፈጠረ ለማወቅ አቅቷት ፣ ታራ ውስጥ ፣ በሀልሙ እንደሚጓዝ ሰው ፣ እየዞረች ሥሪ ያሉዋትን መሥራት ብቻ ነው የተያዘላት ። ልፍስፍስ ነበረች — አሁንም ነች ። ሙሉ ፈቃደኛና ታዛዥም አዛዥም ናት ። እስካርሌት የሰጠቻት ሥራ ከሌለ መቁጠሪያዋን ከእጁዋ ሳትለይ ለእናትዋና ለብሬንት ታርሌተን ትፀልይላቸዋለች ። እስካርሌት ፣ ካሪንን የብሬንት ሞት ያን ያህል ያሰጠናት መሆኑንና የሐዘን ቁስሉዋም ያልሻረ መሆኑን አታውቅም ። ለእስካርሌት ካሪን "ሀሣን እህቷ" እና በፍቅር ለመጠመድ ገና ልጅነቷን ያልጨረሰች ናት ።

እስካርሌት በጠራራ ፀሀይ እጥጡ እርሻ ስትውል ፣ ወገቡዋ ከማጉንበስ ብዛት ጉብጠ ሲለበር ያርሶ ፣ በደረቀው የጥጥ ሽፋን እጁዋ ሻክሮ ተቸርችፎ ታይና ምኑው ጉልበትዋና ጥንካሬዋ እንደ ሱዌለን ፣ ፈቃደኝነቱዋና ታዛዥነቱዋ እንደካሪን የሆነች እህት በኖ ረችኝ በላ ትመኛለች ። ካሪን ስትሰቅም በሙሉ ልብና በቅንነት ነው ። ብቻ ምን ያደርጋል ለአንድ ሰዓት ያህል ከሰራች በኋላ ሱዌለን ላት ሆን እያ ነች ለሥራው ብቃት የሌላት መሆኑዋ የሚታየው ። ስለ ዚህ እስካርሌት ካሪንንም ወደቤት ላከቻት ።

እንግዲህ አሁን በጥጡ ተከል ሬድፍ ውስጥ የቀሩት ዴልሲና ፕሪሲ ብቻ መሆናቸው ነው ።

ፕሪሲ በጣም በጸጥኝነት ነው የምትለቅመው ። አንዴ እግሬን ፣ አንዴ ወገቤን ፣ አንዴ ሆዴን ትላለች ። እያረፈች ቆይታ ንጭ ንጯዋ ቆረጠኝ ፈለጠኝ ማለትዋ መዓት ነው ። እናትዋ በጥጥ ልምጭ እስክትመህ ድረስ ካልደበደበቻት አታቆምም ። ከዚያ በኋላ በተቻላት ቁጥ ብላ እየሠራች ማረፍ ከፈለገችም ከእናትዋ ርቃ በጥንቃቄ ትቀመጣለች ።

@OLDBOOKSPDF

ዲልቢ ደህና ነህ ወይ ብሎ ሲጠይቀኝና እንደምትር ነው የምትሠራው ፡ እስክርቤቶ ወግቦኖ ደቅቆኝ የተሸነጠጭው የጥቂ ከፈጢት ትከሻዎ አየላብኝ ፡ ዲልቢን ታታሪነት ታደንና ፡ ዲልቢ የከ ብዙውን ጋህል የሚመስን የመርት ሽልማት ይገባኮል ነላለች-በላቢ።

"ዲልቢ ወደፊት ሥነን ፡ ዘዘ ሲመጣና ቀን ሲወጣልን ይህንን ትጉህ ሠራተኝነትህን አልረሳውም ፡ በጣም ብርቱ ስት ነሽ።"

ያቺ መጻፊ የመስልኝው መንጻጽ ኦገር እንዲሠ ስትባል የደስት ኛነት ደህጣኮ ማለየትም ሆነ ሌሎቹ ኦባሮችኛ ቂምነው እንደሚር ያሰጉት መኮራራት አልቀጣኮም ፡ ብዙ ምነም የማይገኮሳቸዉ ሥላ ዋን ወዲ እስክርቤቶ ዘመር አምናኮ በዜሩኮት "እመለሳሃለሁ እመ ቤቱ ፡ ማስትር ጂራልድና ሚለስ አለን ሰዉ እንደዚሁ ጥሩምኞ ነበሩ ፡ ማስተር ጂራልድ ትንሽን ለጂት ጥሪቤን ቀር እንዳይለየኛኮን ጻለገኝ ነበ ጋር ቤመነሱ ያለቀለኛን ወሰዉ እዘኮመቹም አልረ ሳው ፡ እኔ በእትድ ጉን የሕንድ ዘር እዘቤኛ ፡ ሰዉዲኛ ጀግም ደግ የሰራለኛወኮ የማይረሱ ሰዎች ጎኛው ፡ በፕሪቤ በጣም ልዝናልሁ። የማትረሀ ልኛ ናት ፡ እንዳለኮምኮ እናቷም በጸሎኮ ነው መለሰኛ የመጣኛው ፡ እዮሁም ነንደለት አባቴ ወረዱ ነዘር ፡"

ምንም እነኳን አስክርቤቶ የኮሬት ስው ሆጣትት ነገር ቢኖ ርባትም ፡ ምንም እንዲ የልኮግው ሥራ እዘኔ ማንኮም ሳይ አርፎ ሸክሙ ዘዘባባትም ቀለ በቶስ ጥቡ ከእርኛው ቦታ ወደ ኮተራው ሲያመራ ከታይ መንፈሱም ጎትሳለ የወደቀው ሥራኮ ተጠናከረ። መሥሬም እንደጥሮ ነጣጀጽናና ፡ ናልብን የሚሞላ ሰብል ያለም ፡ ቃራ ባለበጋ የሆነኛው በጥነ ነዘር ፡ መላው ጀቡብ ባሁለት ነገሩ የቆመ ሙም በጥ ነዘር ፡ ሰለዚህም እስክርቤቶ ደህክሚኛነቱ ሰለሚያጠቃት አሁንም ታራና መላው ጀዘብ ነፍስ የሚሰራው አሥዩ የእርሻ ቦታ ላይ ነው ብላ ተፈሠገሰች።

እርግጥ ይሄ እሷ የሰጸሰጸኛው ጥሞ እስክዘህም ነው ፡ ግን ይህም ቢሆን አንደ ነገር ነው ፡ ትንሽም ቢሆን የትንዲሬሰ ግንዘብ ስለሚያፈራላት አረንግዴ ምግባ ምግቢኛ ከያንኪው የመሰደችው ወርቅ እስኪመነዘር መስንበቻ ይሆናታል ፡ ብሚቀጥለው በልግ የኮንፌዴሬሲውን መንግሥት ፡ ጉልቱ ሰምግና ሌሎቹን የቀን ሠራ ተኞች ከመሰደበት ቦታ እንዲመልሰላት ትምክርና ካልሆነ ጥቂት ሠራተኞችን ከያንኪው በመሰደችው ግንዘብ ትተጥራለች ፡ አቤት በሚተገለው በልግ . . . ትዘራለች . . . ትዘራለች . . . ትዘራለች . . .

@OLDBOOKSPDF

የጐበጠ መንፈሳዊ አቅንቃ በቡናማው የፀደይ አፈር አሻግራ አየችና የሚመጣው ዓመት ሰብል ጋሻ ዘጋሳ ዓይ ትንጣሎ ካሁኑ ታያት ፤

ቀ በሚመጣው ፀደይ ምናልባት እኩ በመጪው ፀደይ ጠርነቱ ያበቃና ደኅ ጊዜ ይመጣ ይሆናል ። መቼም ከንፈዳሲው አሸነፈም አላሸነፈም ሃል ያለ ጊዜ መምጣቱ አይቀርም ። መቼስ ምንም ቢሆን ከሁለቱም ወገን በሚሰነዘረው ጥቃት ይሸላል ። ይሔ ጠርነት ሲያበቃ የአርሻ ቦታ እራስ ጉዙ ሰመጋር በቂ ነው ። አቤት ጦርነቱ ሲያበቃ ያማ ቢሆን ሰው ሁሉ የዘራውን ሰማሬስ አርግጠኛ ይሆን ነበር!

አሁን የጉስና ብርሃን ይታያል ። መቼም ጠርነቱ እስከ ዘለዓለም አይክሄድ ። ትንሽ ጥጥ አላት ። ምንዛ አሉት ። አንድ ፈረስ አሉት ። ትንሽም ብትሆን ሀብት ናት ያክማችሁ ግብብ አለቃት ። አሞ፣ የመጨረሻው አስከሬ ነጋር አልፏል ማለት ነው ብቀ!!

@OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ 27

በሕዳር ወር አጋማሽ ላይ አንድ ቀን በምሳ ሰዓት በምግብ ጠረጴዛው ዙሪያ ተሰብስበው ማሚ ያዘጋጀችውን ከፍራፍሬ ፣ ከበቆሎ የተሠራና በማሽላ የጣፈጠ የገበሰ ምግብ ይበሉ ነበር ። አየሩ ቀዝቃዛ ነው ። የዓመቱ ቀዝቃዛ ጊዜ መጀመሩ ነው ። ፖርክ ከእስካርሌት ጀርባ ቆሞ እጆቹን እያሻሸ " የአሳማ መግደያው ሰዓት አልደረሰም እንዴ እትዬ እስካርሌት ?" ብሎ ጠየቀ ።

"እነዚያን ግልገሎቹን ተምሰህ ሞከረሃቸው የለም እንዴ?" አለች እስካርሌት ፍርጥም ብላ ። "አይ ትኩስ አሳማ መቅመስማ እች ላለሁ ፣ አየር ጠባዩ እንዲሁ ከሰነበተ ደግሞ . . ."

ሜላኒ ማንኪያውን አፉዋ ላይ እንዳደረሰች አቆመችና

"የኔ እመቤት አዳምጪ . . . አዳምጪ የሆነ ሰው ከውጭ እየ መጣ ነው!" አለች ።

"እምን—ኧረ የሆነ ሰው ድምጽ ይሰማል" አለ ፖርክም በመ ጨነቅ ።

በበልግ ብርዳማ አየር ውስጥ የፈረስ ኮቴ ጥርት ብሎ ተሰማ ። ፍርሃት እንደያዘው ልብ ፈጠን ብሎ የሚጣራ ድምጽ ነው ። ያን ዲት ሴት ድምጽ በሙክታ "እስካርሌት! ኧረ እስካርሌት!" አለ ።

እያንዳንዱ ሰው ወንበሩን ወደኋላው ገፍቶ ብድግ ከማለቱ በፊት ለሴኮንድ ከፍልፋይ ጊዜ ሰው ሁሉ ዓይን ለዓይን ተፋጠጠ ። እንደው ተደናገጡ እንጂ ለካ ሳሊ ፎንቴን ናት ወደ ጀንስ ቦሮ ስትሄድ እግረ መንገዱዋን አንድ ነገር ሹክ ልትላቸው ታራ ላይ ቆም ብላ የተጣራችው ። አወጅት ወዲያው ። የውጪውን በር ቸኩለው ከፍ ተው ደጃፉ ላይ ግር ሲሉ እሷ መንገዱን ይዛ ባላበው ፈረስ ላዋ እንደሚነፍስ ንፋስ እየከነፈች ስትመጣ አዩዋት ። ፀጉርዋ ወደኋላይ ይፈስሳል ። የፀጉር ጌጥዋ ጥብጣብ ከንፋሱ ጋር ይጫወታል ። ልጓ ሙን እንኳ ሳትስብ በዛው ፍጥነትዋ እየጋለበች ወደነሱ መጥታ ስታበቃ ወደመጣችበት አቅጣጫ በእጇዋ እያሳየች ፡-

"ከወደ መንገዱ ያንኪዎች እየመጡ ነው! እኔ ራሴ ባይኔ ዓይ ምቸዋለሁ! ያንኪዎች . . ."

@OLDBOOKSPDF

ፈረስዋ የፊት ለፊቱ ደረጃ ላይ ከመውጣቱ በፊት በጊዜ አፉን ሸምቅቃ ስትጎትተው ተሽከርክሮ ፊቱን አዞረና ከመንገዱ ጸር ያለውን ሚዳ በምስት እርምጃ ምላው። አደን ላይ ያለች ይመስል በአጥሩ ጥግ ጥግ መጭ አለች። በዓሮ በኩል ሊጋልብ ጠንካራ የገላይ ኮቴውን ስሙና በጎተራዎቹ በኩል ባለችው ቀጭን መንገድ አጽርጣ ቁልቁል ወደሚሞላ እንደጋለበች ተረዱ።

ለትንሽ ጊዜ ሁሉም በድን ሆነው ቀሩ። ሱዌለንና ካሪን እጅ ለእጅ ተያይዘው ያለቅሱ ይንሰቀሰቁ ጀመር። ትንሹ ዋድ ከደንጋጤው ብዛት ማልቀስ እንኳ አቅቶት ባለበት ቦታ ተተክሎ ቆሚል። አትላንታን ለቀው የመጡ ለት ማታ የፈራው ነገር ደረሰ። ያን ኪዎች ሊይዙት መጡ።

"ያንኪዎች!" አለ ጂራልድ ግራ ተጋብቶ። "እንዴ ታዲያ ያን ኪዎች እንዴ እዚህ ቦታ መጥተው ሄደዋል እኮ።"

"ጃሪ በማሪያም!" ብላ ሮቬች አስካርሌት ፣ የሜላኒን የፈሩ ዓይኖቿ እያየች። ለእንዲት ፈጣን ቅጽበት አስካርሌት ጭንቅላት ውስዋ እንድ የትዝታ ስዕል ጥልቅ አለ። ከአትላንታ የወጡ ለት ማታ የነበረው ጭንቅ ፣ በየንጠሩ ውስዋ ያየቻቸው ድምጥማጣቸው የጠፉ ቤቶች ፣ የግድያ ፣ የማሰቃያ ግርፊያና አስገድዶ ሩካቤ ሥጋ የመፈጸም ታሪክ ሁሉ እንድ ባንድ መጠባት። የኤለንን የስፈት ሳጥን በእጁ እንደያዘ ያ የገደለችው ያንኪም አዳራሹ ማህል እንደ ቆመ ታያት። "እሞታለሁ። እሞታለሁ በቃ። መከራውን ሁሉ የተወጣንና ያለፍነው መስሎኝ ነበር። ከአንግዲህ ምንም ልቋቋም አልች ልም። እሞታለሁ።" አለች በልቧ።

ወዲያው ዙር ስትል ፖርክን ወደ ታርሌቶኖች መንደር ይዞ ሊሄድ በኩርቻ የተጫነውንና የተለጎመውን ፈረስ አየችው። ፈረሱዋ! እንድዬ ፈረስዋ! ያንኪዎች እኮ ፈረሱዋንም ፣ ላሚንም ፣ ጥሻዋንም ሊወስዱባት ነው እንግዲህ። እናት አሳማዋንና መኖዋንም አብረው ሊወስዱባት ነው..... አቢት ያቺን እናት አማማና ፈጣን ግልገል እንቦሳዋን ለመያዝ የፈጀው ሰዓትና ድካም እኮ የትየለሌ ነው! አውራ ዶሮውንና ደህና መፈልፈል የያዙትን ዶሮዎች እንጂሁም ፎንቴኖች የሰጡዋቸውን ዳክዬዎች ሊወስዱባቸው ነው። በእህል ጉተራው ውስዋ የተቀመጡት ፍራፍሬዎችና ያሞችም ላይ ቀሩዋቸው ነው። ጹቂቱ ፣ ሩዙና የደረቀው አተርስ ቢሆን። አይተርፍም። ከያንኪው ቦርሳ የተገኘው ገንዘብም ያው ነው። ሁሉን ነገር ጥርግርግ አድርገው ወስደው አናቸውን አስቀርተው ለጠኔ ሊሰጡዋቸው ነው።

@OLDBOOKSPDF

"ዘፍጹም አይመስደኝም።" አለች እስክርሌት ድምጿን ከፍ አድርጋ ጮሀ ። ሁሉም ይንሣርሣር ብለው ወደሱዋ ሠሩ ። ዘአበደን ጋመ ሁኔታ ፊትዋን የሰጥች ነው የመሰለችው ።

"በሞራሽ አልራብም፣ እንድ ነገር ንክሻ እያጽናናኝም።" ኢሉት ደገመችና

"ምንድነው እስክርሌት ፣ ምንድነው የምትይው?"

"ፈረሱን ነሳሚኑን፣ አሳጥሬን ሰፍሬም አይመስደኝም ነሳለ ወለሬሙም።"

አበራ ላይ የሚፈልጉትን ቢደንጋጤ ፊታቸውን ላይ አመድ ሞኑለበትውን ኔሚ ምች በማጥነት ደር ብሉ አየምጮው።

"እረግራጋው በታ።" አሰች ።

"የምን ረጭራጋ ቢያሉ"

"እመንሠ ሰርቻ ያለው አረንሌጋ ቦታ ነሣ እንንት ጅራች እታድርጓኝ እንግዲህ አሳማሪኝ ወድ ረንራጋው በታ ንሔዋችው። ሠሳችውም ። ባሉ ፖርክ ፣ አንሣና ጥሩሲ ሽሌት ብሉችሁ በቤቱ ችግ ጥጣ ፣ ድቃችሁ አሰምችን ክጣል አሰወሰ። ሌሬሰን I አንችና ካሪን ደጣው ዘምቢሉሙን የሚችሉትን ክነሱ ምጣ መሌውችሁና ወደ ጫክው ሂጹ። ማጣ ፣ ክብር የሉሠራሙን ሰሠን ሠወልሰሽ መፈት ቅበ ፊው ። ፖርክ- ሰማ ፣ እስማዲሠ እንዎንጠክ- ፈቶ እትግትርሀ ልባቢንም ክንት ጋር ይዘሽው ሂድ፣ የት ልጄድ እንራሰሽ፣ አንዱ ጋ ሠሰ ደው ፣ አባት ሂድ ከምጡ ጋርሀ ሠሌ አሰዚ።"

እንሊሀ ሙግብምብድ ብሉ እግኪን እሩሂምጣ ሰማያጭ ልባሽ ያንክምች ሲያይ ግራ የተጋባው የኪ ልድ ሞንችሳት ምጣ ሲሆን እያደሚችል ሠውንዝባለችች ። ቆም ብላ እጅጣን ልሳት እንደፈያው ሰው አርገበገበች ። የሠያዳጣጠው ሞድ የሜሳኒን ቀሚሉ ጭምድድ አድ ርጎ ይዙ ክታይ ቅጨማሪ ቋርጠት ሆነባት ።

"አፍለ ምን ላደርግ፣ እስክርሌት፣" አለ የሚሳኒ ዝጣ ያል ድምጽ ጫጫታውን ፣ ሁክታውችና ሩጫውን ዘልቆ ። ምጣም እንኒ ሚሳኒ ራሷ አሸቦ ቢመስልና የሠራ እክልትጥ ቢንቅጠጥጥ የድምጽዋ ረኃ ማለት ሠሉም ትእዛዝንና አመራርን ከእስክርሌት እንደሚኑ ለእስክርሌት ግልጽ እደረገላትና ተረንጋች ።

"ላሚና ተጀመ" አለች እስክርሌት ፈጠን ብላ "አሮጌው ግመሽ በታ ናቹው ። ፈረሱን ያዙና እየንዳኘሁ ወደ ረግራጋው ስፍራ ሠሰ ጹዋሽውና . . ."

@OLDBOOKSPDF

የሷ መሆኗን ስረዳው ነገር ሰቅጠረኝ ሚለኒ ቃሚስዋን የያዙ ዋጋ ነዋድ ፣ ሰላት ጠገግታ አስለቅቃ ፣ ሰፊ ቃማስዋን መያለይ ጠብር ነጭ ፣ እኖ ፣ ጀረጀራች ጠርጎ ወደ ፈረሱ ሮጠች ። እስካ ርኩ ያሮጌብኝት እያኩር የቀጠኑ እግሮች ፣ የሚገለበለብ ቀጫ ጭ ጠሪዮ አብዘ በጨረፍታ ታያለች ። ሚለኒ እፈረሱ ላይ ፊዋ አለ ችና እግሩን ጥሬ ቀኝ አራኩ አንፈራጠጠች ። ልጓሙን አጥ ብው ይዛ ፈረሱን ሆድ ቡጥለጠኖዋ ክስክለችና ፊትዋን ደንጋጤ እንደጠረበው ምሮ ብለ ወደፊት ተገፀች ።

ቀሩኔ ወደ ዘ በዋቸኩሣ ልጂን ያንኳዎች ይገድልብኛል በጪኝ ይገፍው አልድ ፣' ብሎ እሮዋን ኮርጎዋ ቀደማይ ላይ አድርጋ ለመው ረድ ፅተዘጋጅ።

"ሂሽ፣ ሂሺ ላሚ ጋ ልጅን እዩ እጠብቀዋለሁ ። ለመሆኑ የአቸ ሌይን ልጅ ያንኳዎች ሲነኩ ገሎ የሎል ይመለልኛል፣ ይለቅ ሂጂ!" ብለ እበክርሌት እያፋፈቀችላ ።

ሚሲ ልቢ መርኒላ ተበሱ በመቁረጥ ቢቀርባትም ፣ በተረከገዋ ፈረሱን ክልኩሳ አሂፈሳት እያከበሰች ፣ ጠጠሩን እያፈናጠረች መን ገዱን ይዛ ቅስቃስ ጀምራ ቦታ ጎዘለች ።

"ሚሲ ሎሚልሎን ፈረስ ጥጋልባለች ብዩ አልጠረጥርም ነበር" አለችና እበክርሌት ፀሐፊ ፣ መሃሊት በፈራ ጎባች ። ዋድ እያለ ቀበና በሠዋኒ ሎጭለዋ እግር እጥሮዋ ሥር እየሮጠ የሚበር ቀሚ በዋን ሣፍ ለመሆን ታገለግል ። ምትኑን ጀረጀዎች አንድ ጊዜ እመር እያለች ወጥታ ብሎጥ ፣ ሲያንኖ ሱፍለን ከወርክ ቅርንጫፍ የተ ሠራ ቅርጫት ይዘው መጀጅ ቤቱ ሲሄዱ ፣ ፓርከም ምንም ሳይ ሰሳ ዋጀራልጀን እጅ ይህ እሞሳሎ ወንዝሮው በረንዳ አቅጣጫ ሲሄድ ፣ አሃ ዎችሎው ። ሂራልዮ አልሄድ እያለ እንዶሐየን ይነጫነ ጫል ፣ እምቢየው ይለል ።

ከወጀጓር የማሚ ጠንክራ ድምጽ ይሰማል" አንቺ ፕሪሲ! ንግበስ በሄና እዛ ቤት ጎብተሽ ግልግሎቹን አቀብይኝ እንጂ! በኑሎ አጥር ሥር ለመሸለክ እንደጣልኾል አጥተሽው ነው አሁን ዲልሲ አክስሽ ነይና ደሮን ልጅ ጎሳጎኝ....." ቅላለች ።

"አዪ አሰጣዎችን ማንም እንስይነኳቸው እዚሁ ቢቆዮቸው ቢቅ መጡ ይሽል መስሉኝ ነበር እሱ" እያለች በልቧ አስካርሌት ወደ መኝታ ቢትዋ በረረች ። ምነው ረግረኑ ቦታ ጋ የሸበ ቤት በሠራሁላቸው ዋሮ ገ"

@OLDBOOKSPDF

የኮሞዲኖውን የሳይኖውን መሳቢያ ጐሪጥችና ልብሶችዋን አየበ ረበረች የዚያን የያንኪ ቦርሳ እስክታገኝ መፈለግዋን ቀጠለች ። በታገኘው ከፈተችና የማስታወሻ ቁልፎቱንና ክአልማዝ የተሠራ የጆሮ ጉትቻዋን ከደበቀችበት አውጥታ የስፈት ዕቃ ማስቀመጫ ውስጥ ከትታ ሁሉንም ቦርሳው ውስጥ አስቀመጠች ። ችግሩ ቦርሳው የት ይቅመጥ ? ነው ። ፍራሽ ውስጥ ትቅበረው ? ጭስ ማውጫ ውስጥ ትሸጉጠው ? ጉድጓድ ውስጥ ትዘርውረው ? ጡጥጅ ማህል ትደብቀዉ እ! እዛስ እይሆንም ! የቦርሳው ቅርጽ ደረቅዋ ላይ ይታያና ደሞ ጉድ ይፈላል ። አይምሬ ያንኪዎች እርቃኑዋን ነው ግልበው የሚፈትሹት ።

"ጪ! እንደዛ ክሚያደርጉሳስ ሞት ይሻለኛል" አሰኙ በልቧ ሲጋት እየጣባት ።

እታችኛው ቤት የሚራኩቱ አማሮችና የሚያለትሉ ሰምቹ ድምጽ ይሰማል ። እስካርሌት እንዲህ መላው በጠራት ሰዓት እንኳ ያቺ ድምጻ ለስላሳዋ ሜላኒ ፡ ያቺ ደፋርዋ ሜላኒ ፡ ያቺ ያንኪውን የገደለች ሰት ድፍረቱዋን ያየቻት ሜላኒ እንኑር ብትሞርሳት አሰመኖት ። ከሌሎቹ ከሦስቱ ይልቅ ሜል ትሻላታለች ። ሜሊ-ሜል ምን ነዘር ያለቻት! አሃ! ሀሳኑን አደራ ብላታለች ስባ!

ቦርሳውን መያዶረቱዋ አስጠግታ ጭምድድ አድርጋ ይዛ አዳራ ሹን አቋርጣ ትንሹ ኩ ወዶተኛበት አንሰተኛ አልጋ ሄደች ። ብድግ አድርጋ አቅፉ ውስጥ ብታስገባው ከእንቅልፉ ነቃና እጀቹን እያወ ናጨፈ በእንቅልፍ ልቡ ተመፉጨ ።

ትሪን "ባክሽ ኑይ ሱዌለን ! አብክሽ የሚበታገን ያህል ይዘናል እህቴ ፈጠን በይ ባክሽ" ስትል ይሰማል ። ግልብ ጨሽት ፡ የትእዛዝ የሚመስል ድምጽ ከጓሮ በኩል ሲሰማት አስክርሌት ተንደርድራ ወደ መስኩቱ ሂዳ ብታይ ፡ ማሚ በግራና ቨቀኝ እጆችዋ ሁለት የአ ሳማ ግልገሎች ታቅፋ በጥሞ እርሻው ማህል አሳብራ ስትጣያፍ ተመለከተች ። ከእፅ ሁዋላ ፖርክም ሁለት አሳሞች ተሸክሞ ጂራልድን ፊት ፊቱ እየገቱ ይሄዳል ። ጂራልድ በተጣሰው የእርሻ ረድፍ ውስጥ ብቅ ጥልቅ እያለ ይንገዳገዳል ።

አስካርሌት ስንጣትዋን በመሰኩቱ ብቅ አድርጋ "ዴልሲ! እናት የዋን አሳማ አስወጪያት! ፕሪሲን ንጂ በያት ። በእርሻው ውስጥ እያሩዋሩዋጥሽ ልትወስጽት ትችያለሽ ።" አለች ።

ዴልሲ የክፉውን መጻብ የመሰለ ፊትዋን ቅና አድርጋ ተመለ ከተች ። በልብሱዋ ከብር የተሠሩ የገበታ ሳህኖች ታቅፋለች ። ወደ ቤቱ በጣቱዋ እያመለከተች ፡

@OLDBOOKSPDF

ጣሪያ እናት አሞሃሞን እየመታች ከቤትዋ አስወጥታለች ።" "ዜና ለአስማዋ ጥሩ ነው" አለችና እስካርሴት ወደ ክፍሉዋ ፈጥና ሄዳ ከሞተው ያንክ የመሰደቻቸውን ጊማ ጌጣች ፡ ሀበልና ከወርቅ የተሠራ ኩባያ በችኮላ ሰበሰበች ። ግን የተ ትደብቃቸው ፣ ጫኮሰ በአንድ እጁዋ ትንሹን "ባቦ"ን በሌላው እጁዋ ቦርሳውንና ጌጣጌጡን ይዛ መታየት የሚሆን ጉዞ አይደለም ። ልጁን ማስተኛት ጀመረች ። ልጁ ግን ከእጁዋ ዕታወርዶው ዋይ ዋይ ይል ጀመር ። ወዲያው አንድ ጥሩ ሀሳብ መጣላት ። ከሕግን ማለቅለያ ጨርቅ ውስጥ ከመያዘቅ የተሻለ ምን ቦታ ይኖራል ? ልጁን በሥረቱ አስተኝትና መጠቅለያውን ፈትታ ቦርሳውን በጀርባው በኩል አስታክካ መልሳ ጠቀለለችው ። ሀሳኑ አመመውና ጮኸ ። ዘለዓለት ማዕዘንን እራሬ ጨርቅ በሞንና በጭኑ ማሀል አንጠለቸቸት ።

"አሁን እንግዲህ" አለች በልጁ እስካርሴት በከባዱ ተንፍሳ "ይግረኑ ዘታ ቁረኝ" አለች ።

በአንድ እጅዋ ልጁን እያበረገገች አንስታ በሌላው እጁዋ ጌጣጌጡን እንቃ መያዣት አዳራሽ ወጣች ። በድንገት ፈጣን እርም ጀዋ ቀዘቀዘ ። ጉልበትዋ በጥርሃት ራደ ። አቤት ቤቱ እንዴት እርጭ ብሏል! እንዴት የሚያስፈራ ዝምታ ነው የዋጠው ጆል! እንዴ ፣ ሁሉም ብቻዋን ጥለዋት ሄዱ ማለት ነው ? የጠበቃት ሰው የለም እንዴ? እንዴ ፣ ጥላችሁኝ ሽሹ እኩ ማለትዋ አልነበረም ። ዛሬ ጊዜ እኩ ብቻዋን ያለችን ሴት የሚያጋጥማት አይታወቅም ። ያውም ያን ኪዎት እየመጡ . . .

አንድ ድምጽ ኮሽ ቢልባት እንጣጥ ብሳ ዘለለች ። ዞር ብትል ለካ የረሳችው ልጅዋ የደረጀውን መደንፊያ እንደተጠጋ በድንጋጤ ዓይኑ ከፎቱ አለቪወጣ አፍጠ ተቅምጧል ። ሰመናገር ጮከረ ፣ ግን ጉሮሮው አልላቀቅ አለው ።

"ዋድ ሐምፕትን ፤ በል ብደግ በል" ብላ ፈጥና አዘዘችው ። "ተንስና በእግርህ ሂድ ፣ እናትህ እንደሆነች ልታዝልህ አትችልም" አለችው ።

እሱ እየሮጠ ወደሱዋ ሄደና ቀሚስዋን ጭምድድ አድርጎ ይዞ እንደፈራ አውሬ እውለጠ ፊቱን ተበረ ። ትናንሽ እጆቹ እግሩዋን ለመያዝ ሲዳስሱዋት ይሰማታል ። የዋድ እጅ የሁዋሊት እየጎተተ አላለከዱ እያለት ቱልቱል ደረጀውን እየወረዶች፡—"ልቀቅኝ ዋድ! ልቀቁኝና ራስህን ችለህ በእግርህ ሂድ!" ብትልም ልጁ ግን የባሰውን የጨጥኝ አለባት ።

@OLDBOOKSPDF

[illegible]

@OLDBOOKSPDF

የድምጽና ቅላፄ ለውጥ ሳይኖረው ሁሉ ሞኖ ቀና ብሎ አያት። እሰኪ ሬሳት በአጠገቡ ሠብሮ ሠምድ ውስጥ ያለች ግልገል ጥንቸል መልኩ ኦያየባሩና አንድ ተላወሰ።

"ሥጋ እመቤቴ ማሪያምን" አለች በምሀላ። "በያንኪያቹ ፊት ለፎን ያንተን አያድርገው። መሳፈሪያችንን ግልት የለባቸውም ልጅ ግን ሥራቹን ቀሚስዋን አትቅደድርኝ ልጥፍ አለባት። "ምንው ጥይ ጥይ ጅ ኦን ኦንጂ። የማይረቡ ሰንኪያች ናቹው እነ ምን መሰለህ አሰቸጋሪ ዱርዬዎች ሞርን አሳሰን ለማግኘት መሃይጅ ጠጣኙ።

* * *

ቬሮማን ከአቶ አረጋ ኦንሱ ግጅዝያዎ ኦይርሳ መቀባይሩ ሊሆን አደነጣው ነው። ኩሮሰሰ አረጋንት እየዉለኛ ነው። አቅላኒታ ሩጅ ንሳን ለኢሮ ቀመጣው ሚለው የሸሪሙን ሠፈሚት ነው። ከፊት ቦይ በሰዘረኒው የሰዉት መሃ ማይድ ከልሶ ከጥቂቶቹና ቁጥር ኑማይሩ የማይሸሽ ሥራዎች ከሸማችና ከሸማሳሎች በቀር ከሰ ሰንቂ እነሱ ተከላካይ ሳው ቀሰም።

እውን እዚህ ያሰችው አደር አልፍ እርሻ ጣል ጣል ያረገባትና ዝማሬዎችን ኦሳንትን ኦሳይሆኑ ኦቅራ የያዘች ሰም ምድር፣ ዝሰመት አገር ናት። ሰማንያ ሣያስ ልፉት የለመሳ ክፉ ሰ.ያነዱና ሰ.ያ ጋዩ ነው ያንኪያች ገጅዱ። በመሬ የሚቆጠሩ ቤቶች በአሳት ተያ ይዘዋል። ኗሪው ሳሚቆጠር በሱች ከወራሪው መንጋ ኮቴ ጋር አብረው በእሳት እየተያያዙ በንድ ቅኖት ድምጽ አሰምተዋል፤ እሬ ብለው ሮሽዋል። ሰማንያ ኩያቸውን ለብሰው ክፉት ለፉት በፀረንጻዋ ጀንፍ በማሬሰ የሚሃዙትን ያንኪዎች ላየኛው ለእስካርሌት አሣፉሣን ጭጩዙ ሰገር አሰው ንሳጅ አልሠነም። ሰ.ሀ. የግል ጉዳይ፣ ባቲና የአወጥ በሠነ ነገሮች ላጅ የታሰመ አስዘፊ ነገር ነው።

ከፍረጋው ሣን ሰ.ሀንን እንዲ.ኦፊኙና ጥድ ፊሉን በሱሚሰዎ ቸናዋ ሜምሮቲ እየርን ኢንዲያሣን ብጹመችበት ያንኪዎቹ በጥድ ፊያ እሰን ሣስ.ኦ.ው ጠያ ሃረጀው በመዘጣት ቤሉን እሄደአንባጣ ወርረው የቢሉን ኢኑ ኑያመሰሰቀሉ ወደበረንጻው መረመሩት። የቤሉን ንብረት፣ ምንጣኒና ከርኒሱን ሣጅማጻው ያዘለውንም ሆነ ወሰሱ የተ ሸከመውን በተመኢረ ሳንሽና ፈዘኒ እየዘንጣጠሉ መሬቱን ሳይቀር አየቀደዱ ኑደቀኽሙን አዘጣ፣ የዘሸግሸውን ሙለድ ይሉት ጀመረ። እርቁ ሳያልቅ ወጥረው ኑፈሃ እየተያያ። ከሳባ የተሠራውን ኦልጋ ዛትኑትን እያመጡ ሳለታቸውን ሲቅጥሉ ቤቱ በሳበና በመኝ ተሞ ልጭ ሞፈሳ ወኢመፈት እሰቢን እስኮርሌት ሀጥር ላይ ይሰነሰጥ ጀመረ።

@OLDBOOKSPDF

በዚህ ሁኔታ ሲመዘብረቅ ቢዘልቅና ወደ ቤቱ ቢመለስ የነበረው ትንሽ ፍርሃት ፣ አቅመ ቢስነቱዋና ደካማነትዋ ሁሉ ምርጫ በማጣት ሙጥጥ ብሎ አለቀ ።

ለዚህ ዘረፋ አልፍናውን የወሰደው ፀጉረ ጉበስማውና እግረ ወረሃው ቅጭር ያለው ሃምሳ አለቃ በጉንጩ ትንባሆውን ሞልቶ ይታያል። ሌሎቹ የሱ ሰዎች ሳይጠጉዋት በፊት ይዝው ሃምሳ አለቃ ምራቁን ወደመሬት ተፍቶ ቀሚስዋም ላይ ጭምር ጠቅ ብሎ ወደ እስካርሌት ቀረበና፡-

"በእጅሽ ያለውን በሙሉ አስረክቢኝ ወይዘሮ" አላት ። ሰካ እደ ብቃቸዋለሁ ያለቻቸውን ጌጣ ጌጦች በእጅዋ እንዲያዘች ረስታቸው ኑሯል ። አያትዋ ሮቢላንድ ፎቶ ላይ ያየችው ዓይነት የማሸፍ ፈነግታ ፈገግ ብላ አወለቀ ላይ ዝርግፍ ስታደርጋቸው ሲንክታክቱ አየ ተደሰተች ነበር ፡ እንከትክት ስብርብር ቢሉ ፈቃድዋ ነው ።

"ያንን ቀለበትና ጆሮ ጉትቻሽንም ላስቸግርሽ" አላት ።

እስካርሌት የሚያሌቅለውንና ፊቱ ቂጣቂም የመሰለውን ሕፃን ጭንቅላቱን ወደ ታች መልሳ በቅዘቅ አደረገችና ጌራልድ ኤሰንን ሲያገባ የሠርግ ጥሎሽ አድርጎ ለእሰን ስጥታቸው የነበሩትን ቀያይ የጆሮ ጉትቻዎች አወለቀች ። ቀጥሎም ቻርለስ ሲያገባት አጥልቆላት የነበረውን ከሚያበራ ሰማያዊ ክቡር ጽንጊያ የተሠራ ቀለበት ከጣቷ መንጭቃ አወለቀች ።

"አትወርውሪያቸው ። ለኔ አጥልቂልኝ ። " አለና ጣቶቹን ወደ ሱዋ ዘረጋ ሃምሳ አለቃው ። "እንዚያ ደደቦች የሚበቃቸውን ወርቅ ወስደዋል ። ሌላስ የልሽም" ብሎ አይኖቹን ደረትዋ ላይ ጣል አደረገ ።

ለትንሽ ጊዜ እስካርሌት ልቡዋ ፍስስ አለች ። ለራስዋ ቀድሞውኑ በሻካራ እጆቻቸው ባትዋንና ጭንዋን እንዲሁም ጡቶችዋን ቀደም ብሎ ሲደባብሷት በማሰብ ብቻ ከፍቷታል ፣ ደሞ አሁን ይሄ ጡትዋን ያያል ።

"በቃ ። ሌላ የለኝም ። በእጃችሁ የወደቀን ሁሉ መፈተሽ ልማድ ካልሆነባችሁ በቀር- ምንም የለኝም " አለችው ።

"አይ ማዴለም ያልሽኝን አምናለሁ ። " አለና ሃምሳ አለቃው በጨዋ ሰው አነጋገር ፣ ወለሉ ላይ ጢቅ እያለ በመጣበት መንገድ ፊቱን አዙሮ ሄደ ። እስካርሌት ልጁን አስተካክላ ታቀፈችና ጀርባውን ተም ተም እያደረገች ፣ በእጅዋ እቃውን የደበቀችበትን የልጅ

@OLDBOOKSPDF

መጠቅለያ ጨርቅ ሳይኖረው ይሞት እንደም ሚላኒ ልጅ በመውለዱዋ እንድም ልጁ መጠቅለያ ጨርቅ ያለው በመሆኑ አምላክን አመሰ ገነች ።

እፎቅ የቦት ጫማ ኩቱ ፡ እንኑቀልም ብለው የሚታገሉ ወለሉ ላይ የተኮለከሉ ዕቃዎች ሲጠጥታ ፡ የሳህኖች ካካታ ፡ የሚሰበሩ መስ ታወቶች ክሽክሽታና በጠቅላላውም በማናቸውም ነገሮች ላይ የሚመጣ እርግማን ሲፈጸም የሚኖረው ዋጋ ቢስ ነገር ሁሉ ይሰማል ። ከወደ ሚጻው ‘‘እረጸቸው ክሳቡበት አታስወጣቸው! ’’ የሚል የሬክታ ድምጽና ተስፋ የቆረጡትን ዶሮዎች ማስካካት ፡ የዳክዬዎቹም ቋቋታ ይሰማል ። የአንድ የታነቀ ነገር የማጓራትና የሰቆታ ድምጽ ሰማችና ልቡዋ ለንጥቅ አለባት ። ወዲያው የሽጉጥ ድምጽ ስትሰማና ሰቆታው ሲቆም እናት አሳማዋ መሞትዋን አወቀች ። ያቺ ደደብ ፕሬሲ! ሰራ ሱዋ ሸሽታ አሳማዋን ጥላት ሄዳለች! አዬ ግልገሎቹ እንኳ ድነው ቢሆን ! ቤተሰቡ ሁሉ ወደ ረግራጋው ቦታ ሄዶ ቢሆን ! ግን በምን ማረጋገጥ ይቻላልን!

ያንኪዎቹ ቢዘብቱባት ፡ ሲሙሁባትና ሲረግሙዋት ፡ ገም ብሳ አዳራሹ ውስጥ ቁሞ ብላለች ። ዋድ ቁሚስዋን በጣቶቹ በኃይል ጭምድድ አድርጎ ይሂል ። ሲነካት መንቀጥቀጡ ይሰማታል ። ነገር ግን ሠር ብሳ እይዘህ ልትሰው አልቻለችም ። በያንኪዎቹ ፊት የስድ ብም ሆነ የተታውሞ ወይም የንዴት አንድም ቃል መተንፈስ አልሆነላትም ። ብቻ ገም ብሳ ጉልበትዋ ሰውነቱዋን አስካሁን ቢጥ ንካሬ ለመሸከም በመቻሉ ፡ እንጉቱዋም አራሱዋን ችሎ በመቆሙ አምላክዋን ታመሰግናለች ። ይህን ሁሉ ችላ ከተቀመጠች በኋላ ግን ከደረጃው ጫፍ የዘረፉትን ንብረት ታቅፈውና ተሸክመው የሚወ ርዱትን ጠማም ሰዎችና በማህልም ባንደኛው እጅ ላይ የቻርለ ስን ጉራዴ ስታይ ፤ ፍሀ አለቀሰች ።

ያ ጉራዴ የዋድ ነው ። ያያቱ ክዛም በኋላ ያባቱ ሆኖ ፤ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣና ለልጁ ባለፈው የልደት ቀኑ እስካርሌት ሰጥታው የነበረ ጉራዴ ነው ። በትልቅ ሥነ ሥርዓት ነበር ለዋድ የሰጡት ። ሚላኒማ ሐዘንንና ክብርን በተላበሰ የኩራት ትዝታ እንባ በእንባ ታጥባ አልቅሳ ፤ እንዳያቱና እንዳባቱ ሁሉ አድጎ ጀግና ወታደር መሆን አለበት ስትል ነበር ። ዋድም ይወደውና ይኮራበት ነበር ። እንዲያ ውም ይህ ጉራዴ ከተሰቀለበት ግድግዳ ሥር ካለው ጠረጴዛ ላይ እየወጣ የአፎቱን ጫፍ ይነካካ ነበር ። እስካርሌት የራሱዋን ዕቃ ግናቸውንም ቢወስዱት ትችለው ይሆናል .... የትንሽ ልጁዋን ክብር ግን ፣ ይህንን ጉራዴ ግን ባእድ እጆች ሲወስዱ እያየች መቻል በጭ

@OLDBOOKSPDF

ራሽ አይሆንብኝም ። ዋድ እቀ·ሂለሁ ወዲህ እንኦተ·ይበቀ ለምን እንደ·ወሸኝ ለማወቅ አቸልቀ ቢመለከት ታሳነ·ም ድፍረትም አጣ ችዩ ሥጋ ኦሰቀሰ።እንደ እኛን መዩጠጭ እሙሞቱ ሂደና አሰቀሰ።—

"የኔ ነው፣" አለ ።

"አሰን ልትወስዱ አተችለም ሥ" ስለኅ እዚህርሱት እሱን ዘርማቱ ። "አልችልም እንዱ ፣ ኧረ ባህቸ !" አለ ፕሩኖሙነ የያዘው ደቃቃ ወታደር በጋጠ-ወጥነት እያ·ሬሰት ። "እነ·ግበልሽ! ለእኛ አችላሁ፣ ይሄ ለኦ የአመዘኝ ጉራፌ ሥ·!" አሳ ።

"ኧ . . .እ- አይደለም ። ሥሃ የመነሰ ኮሙ ጠጥት ጉራፌ ትሙ ለትወልያ·ው እችኦለሙ ። የትኒቹ ልጅ ነሙ ። ያዉሁ የኅበረ ነው!" "እነ ሸምበል" አለች ወደ ሃምሳ አለቃው ዞራ "እባክህ እንዲመልስ ልኚ አድርግሙ!"

ሃምሳ አለቃው ፕማዕረግ ሳይግት ሰማሣኘት ደስ ብሏት ወደ ፊት ራመድ አለና "አስቲ አምጣ ጉራፌማን ለየው" አለ ። ያም ጀሌ ወታዳር ያለፈሁት ሰጠውና "ጌታሌ ኒጀታሙ ኮወይት ሃተሠራ ነው" አለ ። ሃምሳ አለቃውም በእጁ እሰዛለበጠ ቅይት እጅታውን ወደ ፀሐይ በዙዉ ኒኦርግ ከሉ ላይ የተጻፈውን ቅኩር ብሎ እያየ ማንበብ ጀመረ ።

"ለክሎኔል ዊሊያም ኢር ሠ"ሬስተን ከሥራ ባልደረቦቹ የተሰጠ ። የ"ማንት ማስታወሻ ። በኖቬስቃ ። ፣ሰላግ ። " አፅና አንበበው።

"ኦ! ወይዘር ፣ ንጌም አራሌ ቦናቪስቃ ሳይ ንበርኩኝ"

"እውነት!" አሰኙ አሳዛርሌት ቅንቅዝ ብሉ ።

"እንዴታ! ልንገርሽ እንማሂያው ፣ እንደዘ ያለ የሞቀና የተሩፉመ ጠርነት አይቼ አላውቅም ። በዚህ ባሁኑ ጠርነት እንኳ የዛን ዓይነት ሙጊያ አላየሁም ። እና ይሄ ጎራዴ የዚህ ልጅ አያት ነው ፣ ነው የም ትይ ?"

"አዎ"

"እንግጺያው ሊመስዩበት አያቸልም" አለ ሃምሳ አለቃው ራሱ በወሰደው በመሃረቡ በኳጠረው ጌጣጌጥ ሐብል በመርከት ።

"ማን እኩ ባለወርቅ አጀታ ነው" አለ ያ ጠያቂር መ·ዝገብ ብሎ ።

"ግጿለም አሞን እንድ·ስታ·ውሰን ጉራጌው·ን እን ኮመሳታ ለን" አለ ሃምሳ አለቃው ። እስክርሌት "እመሰማናለሁ·" እንኳ ሳትል

@OLDBOOKSPDF

ጭራዴውን ወለደኛ [illegible] ለመለሰላት ቤቦት ምን አይን ብላ ምን በመጣትና ምሊጋና ታቅርብ! ጭራዴውን ወደ ሐሰት ሳይሰጠው እንደያዘች ያ ጀል መታደር ከሃምሳ አለቃው ጋር ወጣት ጥያቄ ያሙኛ ልቀቂኝ ይላል ።

"ቆይ ግዴለም እናዚህን አመጣጭት እንዲያስቅውሉኝ የሚያ ያርጎሳው ሥራ ሰለመራለሽው ብቀር!" አለ የው መታደር በጭ ኩሉ ሃምሳ አለቃውም በጣም ጮኖገሩን ኑቆመር —" ብትፈለግ ያሙም ሚዛ ከልንግዲህ ታል እነዳትመልስልኝ " አለው ። ደነቃው ሰው ወደጎሮ ሲገድ አስከርሌት ሃሳቧ ቀለል አሰላት ። ቤቱን ስለማ ታጠል ምንም አልተሳነንም ። እናታዮለሞልንና ለቀሽ ሙጫም አሳ ለሞትም ። ምነልባት ምናልባት ማን ያውቃል ። ከላይኛው ፎቅና ከዘር ውጨም ማርር ብሰው መጀአራሹ መጡ ።

"ምንድነው ነ ምን ተነሣ" አሰኑ ጠየቅሹው ሃምላ አለቃው

"እንድ አሳማ ፣ ጥቂት ሚሰጠትኑና ዳክዬዎች አሉ"

"ቅንሽ በቹስና ያምም አለ ፣ ያሽ አውሬ ድመት የሆነች ዘፈ ሰስ ያናፍት ቤትዮ መጥኑ ተናግራ መሆን አለበት"

"የጉለመያው ጋል ፈሽር ነጠ"

"እንግዲህ አዘህ ምነም የለ-ያምላ አለቃ የሚወሰደውን ወስ ደናል ። የመምጠታችን ወሬ ሌላው አካባቢ ሳይዛመት ፈጥነን አንሂድ ። "

"ዳሽ አሰኪ ማድበታችሁን ቆፍር ። ብዙ ጊዜ ዕቃ የሚደብቁት እዚያ ነው ። "

"አዬ ማደቢት የታላችሁ!"

"ዲሽ እንግዲያው የአግሮዎቹን ቤት ቆፍር!"

"አዛም ከጥዮ በሰተቀር ምንም የለም ። እሱንም እሳት ለቅቀ ንበታል ። "

እስክርሌት ለአጭር ቅጽበት ያ ረጅም የጥዋ ተከላ የጠራራ ፀሐይ ሥራ ትውስ አላት ። ያገኑበሰችበት ወጣቱና በሸክም የተሞሸላለቀ ትከሻዋ ሀመሙ ተሰማት ። ለፍቶ መና ። ያ ሁሉ ጥረት ውሀ በላው ። ጥዋ ሁሉ በንኖ ጠፍቷል ።

"ብዙ ንብረት የለሽም ? አይደል ወይዘሮ?"

@OLDBOOKSPDF

"ሠራዊታችሁ ከዚህ ቀደም እዚህ መጥቶ ነበር እኮ" አለች ቅዝቅዝ ብላ ።

"እሞኝ ልክ ነሽ ። በታህሳስ ወር እዚህ አካባቢ ነበርን" አለ ከሰዎቹ አንደኛው ፣ በእጁ የሆነ ነገር እያሽከረከረ ። "አሞ ፣ እረስቼው ነበር ። "

እስካርሴት ፣ በእጁ የሚያሽከረክረው የኤለንን ከወርቅ የተሠራ የእጅ አምባር መሆኑን ተመለከተች ። እስካርሴት ፣ ሁሉ አለን ሥራ ስትሠራ እጅዋ ላይ ብልጭ ድርግም ሲል ለስንት ዓመት ያህል ስታ የው የነበረ ነው ። የእጅ አምባሩን ማየትዋ ያንን የአናቱዋን አመ ልማጭ ጣት በርካታ ትዝታ ቀሰቀሰባት ። ወይኑድ ፣ እዚህ ባዕድ ሰው ሻካራና አድፋም እጁዋ ውስጥ ገባ እነዛ ደሞ ምንም ሳይቀይ ወደ ሰሜን ይወስደውና ለአንድዋ የዘረፋ ንጉዘብ ለሚያካፍሉትና ለሚጥማት ያንኪ ሴት ሊሰጠው ነው ። ወይ የኤለን የእጅ አምባር !

እስካርሴት ፣ የጠላት ወታደሮች እንዳያዩዋት አንጉቱዋን ደፍታ ስታለቅስ እንባዋ ሀፃኑ ራስ ላይ ዱብ ዱብ አለ ። በእንባዋ ሙታማ ውስጥ ወታደሮች ወደ ውጪው በር ሲያመሩ አየች ። ሃምሳ አለ ቃውም በቁጣ ድምጽ እየደመሽ ትእዛዝ ሲሰጥ ተሰማት ። መሄዳ ቸው ነው ። እንግዲህ ታራ ድናለች ። እስካርሴት ግን የኤለን ትዝታ ስላልለቀቃት እምብዛም መደሰት አልቻለችም ። ሥራዬዎቻቸውን ሲያጋልጭ የሚሰማው ድምጽና የፊረሰቻቸው ኮቴ ትንሽ እፎይታን ሰጣት ። ትንሽ ስላምን ዘራባትና ብድግ አለች ። እያንዳንዱ ሰው በተ ዘረፈ ዕቃ ብልብስ ፣ በብርድ ልብስ ፣ በአንሶላ ፣ በሮቶግራፍ ፣ በዶሮ በጻክዬና በእናትየዋ አሳማ- ሽኔም ተሙሮ ፣ ቁልቁል ገዳናውን ይዘው ሲሄዱ ስታይ ድክምና ህማስ የሰሽነት ተሰማት ።

ወዲያው የሞስ ሽታ አፍንጫዋን ወጋትና ቢደክም ና በውጥ ረት ብዛት ስለጥሙ ለመጨነቅ አቅም እያነሳት ዞር አለች ። በም ግብ ቤቱ ክፍት መስኮት ውስጥ ስታይ ሞስ በዝግታ እየተጦመለመለ ከኔግሮዎቹ መኝታ ቤት ሲወጣ ተመለከተች ። ጥጡ የበነነው ከዚያ ነው ። አብሮም ከሱ የሚገኘው የቀረጥ ንጉዘብና ለመጪው መሬራ ከረምት መሙጪያ ይሆናቸው የነበረው ንጉዘብ በክፌል በነን ። ወደመ ምንም ማድረግ አትችልም ። ገም ብላ ማየት ብቻ ። ከዚህ ቀደም ጥጥ በእሳት ሲያያዝ አይታለች ። ብዙ ሰዎች እየተረዳዱ እንኳ የጥጥ እሳት ለማጥፋት በጣም አስቸጋሪ ነው ። ዋናዎቹ ማከማቻዎች እሩት መሆ ናቸው በጅ ። ተመስጌን ነው !! ዛሬ ንፋስ አለመኖሩና ወደ ታራ ጣራ እሳቱን አለማስተላለፉም ሌላው ተመስጌን የሚያሰኘው ጉዳይ ነው !!

@OLDBOOKSPDF

ከመቅጽበት እያየቸው ተከፈነቀረች ግትርትር እያለች በድን ጋጤ አይኑዋ እንደፈጠጠ በአዳራሹ አድርጋ ወደ ማድቤት በሚመ ስደው ቀጭን መንገድ ቁልቁል ወረደች ። ከወደማድቤትም የሚመጣ ጭስ ይታያል ።

በማድቤቱና በአዳራሹ ማህል አንዱጋ ልጇን አጋድማ ፣ አንዱጋ የሞድን እጅም ከቀሚስዋ አስለቅቃ ከማድማዳው ጋር አላግታው በሮስ እታፈነው ማድቤት ውስጥ ጥልቅ አለችና ወዲያው እያላ ለችና እይኖችዋ እንባ ተንቸርፍርባቸው ወደኋላዋ አፈግፍጋ ተመ ለሰች ። እንደገና በቀሚስዋ አፍንጫዋን ሸፍና ገባች ።

ቤቱ ጭልም ብሷል ። ብርሃን የምታስገባው እንዲት አነስተኛ መስኮት ናት ። ጭሱ ጥቅጥቅ ብሎ አይን ቢወጉ አይታይም ። ዳፍንት ያስይዛል ። አስካርሴት ችስስስ ሲልና አልፎ አልፎ ወላፈኑ ጣጣጣጣ ሲል ብቻ ነው እሚሰማት ። እጁዋን አይኖቹዋ ላይ አማድም ሸፍና እንደምንም ተጨናቂራ ስታይ አንድ ቀጭን እሳት ከወለሉ ወደ ግድ ግዳው ሲድህ ተመለከተች ። የሆነ ሰው የምድጃውን የማገዶ ጉርድ ራጅ እንጨት እየነደደ ሳሰ ወለሉ ላይ ስለበታተነው የወለሉ ደረቅ ሣንቃ እሳቱን እየተቀበለ ነዶ ነበልባሉን ሽቅብ እንደውሀ ይተፋዋል።

በፍጥነት ተመልሳ ወደምግብ ቤት ገብታ ሁለት ወንበሮች እስ ኪሰባበሩ ድረስ ወርውራ ከመለሉ ላይ ቁርጥራጭ ጨርቆች ትለቅም ገባች ።

"በጭራሽ! በጭራሽ ላጠፋው አልችልም! ምነው አምላኬ አንድ የሚያግዘኝ ሰው ባገኝ ኖሮ! ታራ በነነች—ነፋስ ያየው ዱቄት ሆነች ። ወይኔ አምላኬ! ያ ደቃቃ ወታደር - እንድታስታውሱኝ የማደርገውን እውቃለሁ ሲል ለካ ይሄን ማለቱ ነሮዋል! ምነው ጐራዴውን በሰ ጠሁት ኖሮ!"

በአዳራሹ አቋርጣ ስትሄድ ልጅዋ ጐራዴውን እንደያዘ ወለሉ ላይ ተጋድሞ አየችው ። ዓይኖቹ ተከድነዋል ። ፊቱ ቅፍፍ እንዳለው ምድራዊ ያልሆነ ሰላም ይታይበታል ። "ወይኔ አምላኬ! ሞቷል እንዴ! በድንጋጤ ገደሉት!" አለች በጭንቀት ። ብቻ ትታው እየበረረች ምን ጊዜም እበሩ ሥር ወደሚቀመጠው ውሀ የሞላ ባልዲ ሔደች ።

የጨርቁን ጫፍ እዚህ ባሊ ውሀ ውስጥ ነክራ ስታቢቃ በከባዱ አንዴ ተነፈሰችና ጭስ ከዋጠው ማድቤት ጥልቅ ብላ በሩን ከሁዋላዋ ድርግም አደረገችው ። ይህ ወሰንህ ይህ ዴካህ ለማይባል የጊዜ እር ዝመት ከፊት ለፊቱዋ እየተወንጨፈ የሚዘለውን የእሳት ነበል ባል በራስዋ ጨርቅ እያፈነች ስታጠፋ ፣ ወደኋላ እያፈገፈገች ጭሱ

@OLDBOOKSPDF

ባፍ ባጥንቷም እየገባ ስትስል ፥ ደግሞ ወደፊት ስትል ቆየች ። በጉሮሮዋ ከማስያዣው ላይ እየተላተቀ በእሳቱ እየተንጨረጨረ ትከሻዋ ላይ እየተሞመለመለ ሲወድቅ የሚሰጠው ጢና የሚነሳ ሽታ አፍንጫዋን ሊበዪበው ደርሷል ። ራድም ቀሚስዋ ሁለት ጊዜ እሳት ይዞ በእጅዋ አጥፍታዋለች ። ነበልባሉ ልታቆመው በማትችለው ሁኔታ እፊት እፊቷ እየጋለበ በሩ መዳለቢት ሳይሳ ይሮጣል ። እንደቆሳ እባብ እያቆጠጠ ያመረመራል ። ድካምና ተስፋ መቁረጥ ተንባብረው ተጫጉጉዋት ። ተበፋ የሌሰው ነገር መሆኑ ታወቃት ። ከንቱ ልፋት ።

መዲያው በሩ ብርሃድ ብሎ ተከፈተና ከውጭ የገባው ደረቅ እየር እሳቱን ወደላይ ብድግ አደረገው ። እንደገና ግም ብሎ ተዘጋበሩ ። እስክርሌት ግግሽ እውር ሆና ፥ በሚጅመለመለው ጭስ ማህል ሜላኒን አየቻት ። በእግሩዋ እሳቱን እየረመረመች ባንድ ከባድ ጥቁር ነገር ትጨፈጭፈዋለች ። ታነፋዋለች ። ስትስል ሰማቻት ፤ በውኑቱዋን ጎንበስ ቀና እያደረገች ስትንገዳገድም አየቻት ። ብልጭ ባለ የእሳት መላፈን ውስጥ ነጭ ፊትዋንና ባጭሱ ብዛት ትናንሽ ስንጥቅ የመስሉትን ዓይኖችዋን አየች ። የያዘችውን ትልቅ ሰፊ ወደ ላይ ወንጭፋ እሳቱን ለመደብደብ ስትታገል አካልዋ መደፈትና ወደኋላ ይላል ። ለስላሳ ግምት የለሽ ረጅም ጊዜ ግን ሰጡኑ ሆነው እሳቱን ለሚጥፋት ሀይ በል ሲሉ ጥያና እስክርሌት እሳቱ እየሳሳና እያጠረ ሲሄድ ተመለከተች ። መዲያው ሚሳኒ ወደሱዋ ዞረችና ባለ በሌለ ጉልበቱዋ ትክሻዋን ትመታት ጀመር ። እስክርሌት ቢታፈነውና በሚትሳለገሌው የጭስ ሰዴማ ውስጥ ጥምልምል ብላ ደክማ መደቀች ።

በኋላ ዓይኑዋን ስትክፍት ጎሮ ሚጻው ላይ የሜላኒን ጭን ተጋርሳና በምኽት ተንጋላ የክሰዓት በሁዋላዋ ፀሐይ እፊቱዋ ላይ ስታበራ አየች ። እጅዋ ፥ ፊቱዋና ትክሻዋ በእሳት ታጠሎ ከሚቻለው በላይ ተጠቡበሏል ። ከዋናው ማከማቻ ቦታ ጭስ እየተጠቀለለ ዳመና እክሎ ዳመና መስሎ ጎተራዎቹን ማፈኑን አሁንም ቀጥሏል። አሁንም የሚታጠል ጥጥ ሽታ ጠንክሮ ብሎ ይሸታል ። እስክርሌት ከማድቤት የሚወጣውን ቀጫጭን የጭስ መስመር አየችና ልትነሳ ታጣት ። ነገር ግን "ረጋ በይና ተኚ የኔ እናት ። እሳቱ ጠፍቷል በቃ" የሚለውን የሜላኒን ዝግተኛ ድምጽ ስትሰማ ተመልሳ ተኛች ።

ለትንሽ ጊዜ አይኖችዋን እንደከደነች በእርይታ እየተነፈሰች ተንጋላ ቆየችና በአቅራቢያው የሚሰማውን የአራሱን ሕፃን እንግንግን የሚል ድምጽና የዋድን ስርቅታ ስትሰማ የልጆቹን ደህንነት አረጋገጠች ። ዋድ አልሞተም ማለት ነው ፥ እግዜር ምስጋና ይግባው ! አይኑዋን ከፈተችና ቀና ብላ ወደ ሜላኒ ፊት ተመለከተች ።

@OLDBOOKSPDF

ጥቅሉ ሥግ ሠኅ ሠኅ ሠኅ

@OLDBOOKSPDF
አቅም ስለሌላት ፣ አንደም የሙገሳ ቃሉቸዉ የመንፈስ ተሀድሶና የመ
ንፈስ ፈውስ ስለሆኑዋት ዝም ብላ ታቁፈችላት ። ዝም ብላም ተሳ
መችላት ።

ወዲያውም ያ በጭስ የታፈነ ጨለማ ማድቤት የወለደው ለባ
ሉዋ አህት የምትሰጠው ክብርና የቅርብ ወዳጅነት በመፈጠሩ ዝም
ማለት ነበረባት ።

"ቆይ እንዲህ ልበላት" አለች በልቧ ያለፈቃድዋ "እሷ
በተፈለገችበት ሰዓት ደራሽ ናት- የልብ አውቃ!" አለች ።

@OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ 28

መቅቱ ቀዝቃዛና ብርጭ አዘል እየሆነ መጣ ። ቀዝቃዛው ንፋስ በበር ቀዳዳ ውስጥ ሳይቀር ይገባል ። የመስኮቱንም የረገበ መያዣ ጀሮ በሚያደነቁር ድምጽ ያንኳኳዋል ፣ ዛሮቹ ቅጠሎቻቸውን ተገፈው ከደብዛዛው ሰማይ ጋር ሲታዩ እርቃናቸውን የቀሩ ጥቋቁር አጽሞች መስለዋል ። የተበጫደሱት ቀያይ መንገዶች በቅዝቃዜ ብዛት ጥርር ብለው ድንጋይ ሆነዋል ። ረሀብም ንፋሱን በጅርጀያ በኩል ይነዳዋል ።

አስካርሌት ከትልቋ አያት ፎንቲን ጋር የተጋገረችውን ሁሉ በምሬት አስታወሰች ። ያኔ ሰዓት ከሰዓት በኋላ - የዛሬ ሁለት ወር ግለት ነው ፤ ምንም ሣመታት ያለፉት ቢመስል ፤ ለአሮገቷ የመጨረሻ ውን አስከፊ ነገር ማየቱዋን ከልቡዋ ነግራቸው ነበር ። ሆኖም አሁን ያ ሁሉ የተማሪ ቤት የጭጋነነ ጠፊ ትይነት ሆኗል ። የሼርማን ሰዎች ለሁለተኛ ጊዜ ወደታሪ ከመምጣታቸው በፊት ፤ አነስተኛም ቢሆን የምግብና የገንዘብ ፀጋ ፣ ከፊ የተሻሉ ጐረቤቶችም ነበሩዋት ። እስከ መጪው ፀደይ የሚያስንበታት ጥቂም ነበራት ። አሁን ግን ጥጡ በንኖ ጠፋ ። ምግቡም በነኔ ። ሊገዛበት የሚችለው ምግብ ባለመ ኖሩ ገንዘቡም ዋጋ ቢስ ሆኗል ። ጎረቤቶቹዋም እንደሆኑ ከፊ የከፉ ሁኔታ አጋጥሟቸዋል ። ቢያንስ አንዲት ላም ከነጓዋ ፣ ጥቂት የአሳማ ግልገሎችና አንድ ፈረስ አላት ። ጐረቤቶቿ ግን ሊደ ብቁት ከቻሉትና ጫካ ሊያስቀምጡ ከቻሉት ጥቂት ንብረት በስተ ቀር ምንም የለቸው ። ፈይፎሊል የተባለው የታርሌተኖች መና ሪያ የነበረው ቦታ ከመሠረቱ ጀምሮ ድምጥማጡ በመጥፋቱ ታርሌ ተኖችና አራቱ ሴቶች ማንም ባዳ በት ተጠግተው ነው ያሉት ። ላቫጆይ አጠገብ ያለው የመኑሮዎች ቤትም ፈርሶ ፈራርሶ ከምድር ተስተካክሏል ። ሚሞሳም ቢሆን እንጨት እንጨቱ ነዶ ዋናው የብ ረት ምሰሶና ፎንቴኖችና ባሪያዎቹ በእርጥብ ብርድልብስ ተጣጥረው ያዳኑት ብቻ ነው የተረፈው ። የካልቨርዮች ቤት ብዙ በዛ በያንኪ በሒልተን ጣልቃ ገብነት ምክንያት ድኗል ። ያም ሆኖ አንድ ከብት ፣ አንድ አሳማ ፣ አንድ ራስ በቀሎ እንኳ አልተረፈም ።

ታራ ውስጥም ሆነ በመላው አገር ችግሩ ምግብ ነው- እህል ው ። ብዙዎች ቤተሰቦች በየጫካው ከሚለቅሙት ፍራፍሬ ፣ ከተረፈ

@OLDBOOKSPDF

ላቸው ያም እና አተር በቀር ይበሉት ነገር የላቸውም ። ያችንም ቤት ያፈራትን በደህናው ጊዜ እንደሚያደርጉት ሁሉ ለባሰባቸው ያካፍ ላሉ ። ጸሩ ግን ተካፍለው ይበሉት ነገር አንደኛውን የጠፋበት ጊዜ መጣ ።

ታራ ሙስጥ ፖርክ ቀንቶት ከሞለ ጥንቸልም አሳማም አሳም ይበላል ። ሌላ ጊዜ ከተገኘ ወተትም ፣ እንደገንፎ ያለ ነገርም፣ የተቆላ የተጠበሰም ነገርና ያም ይበላል ። ሁልጊዜ ግን ረሀብተኞች ናቸው ። እስካርሌት ዙር ባለች ቁጥር የተዘረጉ እጆችና የሚቁለጨ ልጩ ዓይኖች የሚያጥሙዋት ይመስላል ። እራሷም የተራበች በመ ሆኑዋ ሁኔታቸው እብድ ያደርጋታል ።

ጥጃው ብዙ ወተት እየጠጣ ስለተሻማቸው እንዲታረድ አዘዘ ችና የዚያን ዕለት ግታ ቤተሰቡ ሁሉ ብዙ የጥጃ ሥጋ በልቶ ታሞ አደረ ። ክልሳማ ግልገሎቹ ማህል አንዷን ማረድ እንዳለባት ብታ ውቅም ከነገ ዛሬ አደግው ትልቅ ይሆናሉ በማለት ስታመነታ ቆየች። በጣም ትናንሾች ናቸው ። ታርደው ምግብ ይሆናሉ የሚባሉ አይደ ሉም ። ይልቅስ ትንሽ ቢሰነብቱ ደህና ይጠቅማሉ ። በየማታው ፖር ክን ጎንዘብ ሰጥቼ ምግብ እንዲገዛ በፈረስ ካልላኩት እያለች ከሚላኒ ጋር ትጨቃጨቃለች ። ብቻ ፈረሱንም ሆነ ጎንዘቡን ይነጥቁታል የሚ ለው ሥጋት ገታቸው ። ያንኪዎቹ የት ይሁኑ የት አያውቁም ። ምናልባት በሺ ማይሎች የሚቆጠር ርቀት ላይ ወይም እዚችው ወንዟን ሻገር ብለው ይሆናል ያሉት ።

አንድ ቀን እንጸወጮ አስካርሌት እራሷ ምግብ ልትፈልግ ፈረ ሱን ቋና ከተነሳች በሁዋላ ነው ቤተሰቡ ሁሉ ያንኪዎች ይገድሉ ሻል ብሎ ሲጨነቁበት የነበሩት ሐሳቡን የተወችው ።

ፖርክ አንጻንዴ እሩት ቦታ ሄዶ ቆይቶ ወድቅት ላይ ይመለ ሳል ። እስካርሌት ግን የት ዋልከ ብላው አታውቅም ። አንጻንዴ ቅጠላ ቅጠል ይዞ፣ አንጻንዴ አንድ ሦስት ራስ በቆሎ ወይም አንድ ከረጢት አተር ይዞ ይመለሳል ። አንድ ቀንማ ከጫካ አገኘሁኝ ብሎ አንድ አውራ ዶሮ ይዞ መጣ ። ቤተሰቡ ሁሉ ፖርክ በቆሎውንና አተ ሩን እንደሰረቀው ሁሉ ፣ ይሄንንም ሰርቆ መሆኑን ልቡ እያወቀ ጥርቅም አድርጎ በላ ። አንድ ቀን ማታ ቤተሰቡ ሁሉ ከተኛ በሁዋላ እስካርሌት መኝታ ቤት ገባና በቀላል ሁኔታ በጥይት የተመታውንና በደም የተበከለውን እግሩን እንደበግ ጉተት አድርጎ አሳያት ። ተነ ስታ ስትጠግንለት ፈይትቪል ውስጥ አንድ ዶሮ ቤት ውስጥ ለመግ ባት ስሞክር ነቁብኝና እንዲህ አረገኝ አላት ። እስካርሌት የማን ዶሮ ማርቢያ ነው ብላም አልጠየቀች ፣ ብቻ ትከሻውን በእጅጥን መታ

@OLDBOOKSPDF

መታ እያደረጎች እንዘጋ በኋላ ሻማው አለ ። ኤጣሮምኛ እንዳንድ ጊዜ ጽኑዋችና ድድብ ያሉ ናቸው ። ነጭናሮችም ናቸው ። ነገር ግን በግንዘብ ሊገዛ የማይቻል ታማኝነት ያላቸው ሲሆን ፤ ከኤጮኛ ጋር ባለችው አጣዳቡ ምክንያት እወረጲዛው ላይ ገበታ እንዲኖር ለማድረግ ሕይወታቸውን ጭምር ለመስዋእትነት አትርበው ይጣጣራሉ ።

አንዛንዴማ ቢያዩት ይሄ የፖርክ እየቆንጠረ መሰረቅ መጀመር ሙሉ አድሮ ከባድ ጉዳይ ይሆንና የሚያስገርፈውም ጭምር ሊሆን ይችላል ። በሌላም ጊዜ ፍርጥም ብላ እንድትገሰፀውና ማስጠንቀቂያ እንድትሰጠው ትነደፃለች ። "ሁልጊዜ የነዚህን እግዚሀር በእጅችን ላይ የጣለቸውን ባሪያሞች ሞራሳዊና አካላዊ ደህንነት የማስጠበቅ ሐላፊነት እንዳለብሽ ልትረሺ ጠዲት ። ማስታወስ ያለብሽ እነሱ እኛ ሰዎች መሆናቸውንና እንዲሕጎንም መንከባከብ እንደሚያስፈልጋ ቸው ነው ። መልካም አርአያም ልትሆኛቸው ይገባሉ ። " ብላ ሌለን የነገረቻት ትዝ አሳት ።

አሁን ግን እስካርሌት ይህንን ምክር ቸል ብላ ከአእምሮዋ አው ጥታዋለች ። ሉብነትን እየደነፋችና እየገፋራች ናት ። ደማሞኑ የሚ ሰረቁት ሰምኛ ከእሷ የባሰ ጠናጪዎቹ ናቸው ። ይሄ መቹም ሕሊ ናነ የሚነካ ጉዳይ ነው ። እርግጥ ይህ የሞራል ግዴታ እምብዛም አሳ ሳሰባትም ። በመስጎጣትና እቦል ነገር ነው ያደረግሽው በማለት ሱንታ በመቁሰሉ አዘነችለት ።

"ፖርክ ፤ ያበሰበ ማጠንቀቂያ ይኖርብሃል ። አንተን እንድናጣ አንፈልግም ። ካለንሱ ምን መሥራት እንችላለን? በጣም ጥሩ ሰውና ታማኝ ነህ ። እንድ ቀን ሲመጣልንና ገንዘብ ስናገኝ አንድ የወ ርቅ ሰዓት ገዝቼልህ አለዩ ላይ 'ጦልካም አድርገሀል ። ጥሩና ታማኝ ሎሌ' የሚል የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል አስቀርፅበታለሁ ። "

ፖርክ በመመስገኑ እየተኩራራና የታሸገ አማሩን እያከከ ፣

"በጣም ጥሩ ነው እትዬ እስካርሌት ። ግን ገንዘቡን መቼ አገኛለሁ ብለሽ ታስቢያለሽ?"

"መቼ እንደማገኘው አላውቅም ። ግን አንድ ቀን እንዴትም ይሁን አገኛለሁ ። " ጭንበስ ብላ በማያዩት አይኖቹዋ ትኩር ብላ ሲታስ ተውል አቁነጠነጠው ። አንድ ቀን ይሄ ጦርነት ካበቃ በሁዋላ ግን ዘብ አገኛለሁ ። ከዚያ በኋላ ረሀብም ሆነ ብርድ ሁለተኛ አይነካኝም ። አንዳችንንም ብድርና ረሀብ አያግኘንም ። ከዛ በኋላ የሞቀ ልብስ እን ሰብሳለን ። በየዕለቱም የተጠበሰ ዶሮ እንበላለን ። እና . . . "

@OLDBOOKSPDF

ከዚያ መናገሩዋን አቆመች። የታራ ጥብቅ ህግና እራሰዋም መሆን አለበት ብላ ስትገፋፋ የነበረው ፤ ማንም ሰው ባለፈው ጊዜ ይበሉ የነበረውንም ሆነ አሁንም ካገኙ ሊበሉ የሚችሉትን ጥሩ ምግብ እን ስጥ ማውራት አይገባውም የሚል ደንብ ትውስ አላት ።

እሩቅ እሩቅ እያየች በስሜት ተውጣ እንዳለች ፖርክ ሹልክ ብሎ ወጣ ። አሁን የሞተውና በንኖ የጠፋው ያለፈው ጊዜ ኑሮ ፡ ምስ ቅልቅል ያለና ችግር የሞላበት ነበር ። ያኔ አሽሌይን የመማረክና የማሸነፍ እንዲሁም ሌሎች በዶርዘን የሚቆጠሩ ወዳጅችዋን የመሳ ብና በዙሪያዋ እንዲያንጎራብቡ የማድረግ ሀሳብ ነበረባት ። ከታላላቆ ቹዋ የምትደብቃቸው የልጅነት ጠባዮቹዋ ፡ ከሴቶች ጋር የነበረ መቀ ናናት ፡ ልብስ ማማረጡ ፡ ብዙ ቅለሞችን ማንሳትና መጣሉ ፡ ወ . . . በጣም ብዙ ውሳኔ የሚፈልጉ ነገሮች ነበሩ ያኔ !

አሁን ኑሮ ቅልል ብሏል ። የሚያስፈለግ ነገር ቢኖር ፡ ረሀብን ለመቋቋሚያ ያህል ምግብ ፡ ክብርድ ለመጸን ያህል ልብስና እንቅልን ማስገቢያ የሚሆን ጣራው የሚያፈስ ቤት ነው ።

እንግዲህ በእነዚህ ቀናት ነው አሽካርሌት ለዓመታት ሲቆጠቁጡዋት የነበሩትን ነገሮች ደግማ ደጋግማ ማለም የጀመረችው ። ሁልጊዜ አንድ አይነት ሕልም ፡ ሁልጊዜ ዝርዝር ሁኔታቸው እንኳ የማይለያይ ነገሮችን ነው የምታይ ። በእእምሮዋ የሚነዙባት ሽብር ግን ከቀን ቀን እየጨመረ ከመምጣቱ የተነሳ እንደገና አየዋለሁ የሚለው ስጋት እንኳ ከእንቅልፉዋ ያባንናት ጀምሮዋል ። መጀመ ሪያ ያለመች አለት የቀኑን ድርጊቶች ሁሉ ጥርት አድርጋ አስታ ውሳ ነበር ።

ቀዝቃዛ ዝናብ ለብዙ ቀናት ጣለ ። የነሱን ቤት ግን ድርቅና ቅዝቃዜ ውጠውታል ። በምድጃው ዳር ያሉት የማገዶ እንጨቶች እርጥበት ስላላቸው አልነድ ብሰው መቀታቸውን ነሱ ። ከቁርስ ጊዜ ጀምሮ ከወተት ሌላ የሚላስ የሚቀመስ ይጠፋል ። ያሉት የያም ፍሬ ዎች እያለቁ ነው ። የፖርክ አደንም ሆነ አሣ ጠመዳ ፍሬ ቢስ ሆነ ። እንግዲህ መብላት ካለባቸው ከማልገሎቹ አንዱን ነገ ጠዋት ማረድ ነው የሚያዋጣው ። የተራቡትና የተጨነቁ ጥቁር ከነጭ ፊቶች ምግብ ፍለጋ ዓይን ዓይኑዋን እያዩ ቃል ሳይተነፍሱ ክርትት ክርትት ይላሉ ። ፈረስዋን ብታጣም ትጣ እንጂ ፖርክን ልካ ምግብ እንዲገዛ ማድረግ አለባት ። ደግሞ ይባስ ብሎ ዶክተርም ሆነ መድሀኒት በሌለበት ሰዓት ዋድ የጉሮሮ ሕመምና ኃይለኛ ትኩሳት ያዘው ።

ልጅዋን በመጠበቅና በረሀብ ድክም ስላለች አስካርሌት ልጹን ለሚላኒ ሰጥታ ለአሮር እንቅልፍ ጋደም አለች ። እግሩዋ በረዶ ሆኗል ።

@OLDBOOKSPDF

ቅሳባሰሳች። አንዱ ወደቀኝ አንዱ ወደግራ ትላለች። ተስፋ መቁ
ረጥና ፍርሀት እየተጫነዋት እንቅልፉ እንቢ አለት። ደግማ ደጋግማ
አሰበች፣ አወጣች አወረደች "ምን ላድርግ ወዴት ልሂድ እንደው
ባንሩ እሚረዳኝ ሰው ቢጠፋ ! እውነት ያሀንኑዋን ሊሰጣት የሚ
ችለው፣ ዋስትና ሊሆናት የሚችለው ዓለም ያት ጠፋ! ይሀን ሽክሚን
የሚያቃልልላት እንዴት እንድ ብልሀና ጠንቅራ ሰው ይታጣ እሷ
አፈጣጠሯ ሁሉ ለሽክም አይሆን። እንዴት እንደምትሸከመውም እታ
ወቅ። ወዲያው ድንዝዝ አለችና ሸለብ አደረጋት።

እንድ የማታውቀው ነገር ውስጥ ሙጋግ እናን ካደረገው በታ
ሃና ታያለች። እጄዋን እንኳ ከፈት ለፈትዋ ሊያላይ የማይችል
ጭጋግ ነው። ከአግሩ ሥር ያለው ምድር ሞንቀት የሌለበት ነው።
አልም ያለ ምድረ በዳ ነው። ዝምታ የወረረው። እዚህ ውስጥ ነው
የጣሰችው። ጭለግ ውስጥ ድንጋጤ እንደዋጠው ሕፃን ሆናለች።
በጣም ይቅበጠበጣል፣ በጣም ርቧታል፣ መጮህ አታታት እንጂ ዙሪ
ያዋን በሚጋው ውስጥ የነበሀት ነገር በድርሃት የሚያስመህ ነው።
በዚያ በጉም ውስጥ ቀሚስዋን ለመያዝና እቅመችቡት የሚንቀጠ
ቀዋ መሬት ላይ ለጥለዋት የሚጭረጨረጩ ሬጋ ያሉ፣ በጣም ታታ
ሬና ብዙ እጆች ታያለች። ወዲያው ዙሪያዋ ከለ ከግይታይ ድንግዝግዝ
ያለ አካባቢ ውስጥ ልትሸሽግበት ልትጠጋበት ልትረዳበት የምት
ችል በታ መኖሩ ይታወሰታል። የት ይሆን እንዚያ እጆች ገላት
ተው ካደር ሳያደላልኝት ብፈት አዘያ ቦታ ትያርስ ይሆን!

ከመቅጽበት አንዳበይ ሰው በዚያ ሙጋግ ውስጥ መሮዋ ጀመ
ረች። ትመህለች። አሪ ትላለች = እጅቹዋን ብትዘረጋ ላይ አየርና ቀዝ
ቃዛ ሙጋግ ብቻ ነው የምትጨብጠው። ያ መሸሸጊያ ቦታ የት ይሆን!
ይታያታል ግን ልትደርስበት አልቻለችም። አቤት እዛ ለመድረስ
ብትችል። ከዚያ ብትደርስ ትድን ነበር! ነገር ግን ሽብር እግሩዋን
አዛሳት። ረሀብ አቅመ-ዋን አዳሽቃት። አንድ የተሰፋ መቁረጥ ጨኸት
ጮኸችና ብንን ብትል የሚለኒ ፈት ጉጨንቆ ሲጠቢቃትና እጅዋ
ቢቀሰቅሳት አየች። ያ ሕልም ባዶ ሆድዋን በተኛች ቁጥር ደግሞ
ደጋግሞ ይመጣባታል። ያ እግጣዚህ አልፎ አልፎ ቢሆን ቦቲ ነው።
ምንም እንኳን እንዲህ ግይነቱ ሕልም ውስጥ ምንም የሚያስፈራ
ነገር እንደሌለ ልቡዋ ቢያውቅ መተኛት ሁሉ ያስፈራት ጀመር።
ሰለ ጉም የሚታይ ሕልም ያሚያስፈራ አልነበረም። ምንም አልነበ
ረም። ምንም አልነበረም- ነገር ግን እዛ በጭጋግ የተሞላ ሀገር ውስጥ
የመግባት ሀሳብ ከሚሰኒ ጋር እንድገተኛ አደረጋት። ስለዚህ ገና መታ
ገስና መጮህ ሰትጀምር ሚሰኒ ትንቀጉትና ትቀሰቅሳት ጀመር።

@OLDBOOKSPDF

በዚህ ሞንቀት ነጣች ፡ ከሳች ፡ መነመነች ። ያ ያማረ የተዋበ ክብ ፊትዋ ገርሽሽ ብሎ የጉንጩዋን አጥንት አስገጠጠው ። ዘመም ያሉ እንደኩል የጠሩ አይኖቹዋም ተጐልጉለው ወጡ ። በጠቅላላውም እየ ጻሽች የምትሄድ የተራበች ድመት መሰለች ። "የቀን ሀልጫ ይበቃ ነበር እኮ" እያለች በሀሳብዋ ፡ ተስፋ በቆረጠ መልክ ቀን የሠራችውን ሁሉ ከመተኛትዋ በፊት ታመነዠጋለች ።

* * *

የገና ጊዜ ነው ። አንድ ቀን ፍራንክ ኬኔዲን ጥቂት ወታደሮች ከሠራዊቱ ተነጥለው የሚበላ ፍራፍሬና የሚታደኑ እንሰሳት ያገኙ መስሎአቸው እየተንቤራተቱ ሠለው ወደታራ መጡ ። የተጎሰቁሉ ፡ የተደራረቱ ልብስ የለበሱና ከመሸከም በቀር ቀልጠፍ ላለ ሥራ የማይሆኑ ልቁጣና አንካሳ ፈረሶች ላይ የተቀመጡ ናቸው ። ሰዎቹም እራሳቸው እንደፈረሶቻቸው ሁሉ ከጥቅም ውጭ ሆነው ከሠራዊቱ የተነጠሉና ከፍራንክ ኬኔዲ በስተቀር ወይ አንድ አማር የሌላቸው ፡ ወይ አንድ አይናቸው የጠፋ ወይም መጋጠሚያዎቻቸው እልታጠፍ ብለው እጃደንጨት የተጣሉ ናቸው ። አብዛኞቻቸው ከተማረኩ ያንኪዎች የወሰዱዋቸውን ሰማያዊ ኩቦች ከላይ የደረቡ በመሆናቸው የታራ ሰዎች የቨርግን ወታደሮች የመሰሉ መስሎዋቸው ስጊዜው ተደናግጠው ነበር ።

ያን ማታ ታራ ውስጥ በረንዳው ላይ እርይ ብለው ተገናኙ ። በርክት ላሉ ሰዎችና ከሚቆረቆር መሬትና ከሚዋጋ የእንጨት በንጣሪ ላይ ሁኔው የከረሙ በመሆናቸው ከዚያ የተሻለ ሚናቸውም ሙኝታ እርየው የሚያስኝ ፡ ምቹ አልጋ በመሆኑ በጣም ተመችቶዋቸው ነው ያደሩት ። ከጣራ ስርም አድረው ስለማያውቁ ተስማምቷቸዋል ። ዱሮ እንደሚያዩርጉት ሁሉ ትልቅ አዳራሽ ውስጥ ሆነው በሁነኛጅት ሴኖች ተከበው እየሳቁ እየተጫወቱ የገናን ዋዜማ በመዋላቸው ተደስተዋል ። ከቆሻሻ ጢማቸውና ልብሳቸው በቀር ደስስ የሚሉ ሰዎች ናቸው ። ስለመርነቱ ጐስቁር ብለው ለማውጋት ፈቃደኞች አይደሉም ። ይልቁንስ አይን የሌለው ውሽት እየዋሹ ሴቶቹን ያስቋቸዋል ። ያም እርቃኑን የቀረውና ገምታ የዋጠው ቤት ለረጅም ጊዜ ተርቦት የነበረውን ሳትና ጨዋታ አውን አገኘ ።

"ልክ ዱሮ የቤት ፓርቲ እንደምንደግሰው ዓይነት ሆነ እኮ" አለች ሱዌለን ተደስታ ፡ ለእስካርሌት ። ሱዌለን የጣዛ መዳጅዋ ቤቷ እንደገና መጥቶ በማየቱዋ ደስታዋ ሰማይ ጠቀስ ሆኗል ። እናም በጭራሽ አይኑዋን ከፍራንክ ኬኔዲ ላይ አልነቅል አለች ። እስካርሌት ሱዌ

@OLDBOOKSPDF

ለንን አይታ ከዚያ ከገመምተኝነት ከሳትዋ በስተቀር ቆንጆ ልትባል ምንም ያልቀራት መሆኑዋን አስተውላ ግርም አላት ። ጉንጮቹዋ ጥኩት አሉ ። ዓይኖቹዋም ለስላሳና የሚያበሩ ሆኑ ።

"ሆይ ! በጣም ትጨነቅለታለች ማለት እኮ ነው" አለች እስካርሌት በጥላቻ ። "ደሞም ማንንም ታግባ ፡ ለምን ይሄንን ትርኪ ምርኪውን ከሬዴን አይሆንም ፡ ብቻ ባል ይሁናት ፡ ሰው ትሆናለች ብዬ እገምታለሁ ።" አለች በልቧ ።

ካሪንም ብትሆን ትንሽ ፈገግ ብላ ያ በእንቅልፍ ልቧ ያለች ያለመስላት የነበሰረ መልኳ ፈክቷል ። ከመጠት ሰዎች መካከል እንደኛው ብሬንት ታርሌተንን የሚያጠቅና ሲገደልም በቦታው የነበረ በመሆኑ ከራት በሁዋላ ብቻቸውን እንዲያወሩ ቀጥራዋለች ።

አራት ላይ ሚላኒ ከጭምትነቱዋ ወጥታ የግዴዋን ስትስቅ ስት ጫወት ሲያዩዋት ጉድ አሉ ። ተገረሙ ። ትስታለች ፡ ትቀልዳለች ። እንደውም በጣም ግልጽ አይደለም እንጂ አንዱን አንድ ዓይና ወታደር ከሞላ ጎደል ስታሳስቀው ፡ እሱም ስለ ጀግንነት ከልኩ በላይ እየተናገረ ሲመልስላት ነበር ። እስካርሌት ይሄ ሁሉ የአእምሮም ሆነ የአካል ጥረት ሚላኒ እወንድ ፊት ከማፈሩዋ ብዛት ሰሽ ፋን የሚደረግ እንደሆነ ታውቃለች ። በዛ ላይ ጨነኛ እንኳን አይደለች ። እርግዋ ጨነኛ ነኝ ብላ በግድ ከዴልሲ የበለጠ ሥራ ሁሉ ትሥራ እንጂ ሙታመጡዋን እስካርሌት በደንብ ታውቃለች ። እንድ ሰቃ ባኑሳች ቁጥር ፊቱዋ ይነጣና ጉልበቶቹዋ ሊሽ ከሙዋት እንዳልቻሉ ሁሉ ድንገት ዘፍ ብላ ትቀመጣለች ። ዛሬ ግታ ማን ልክ እንደሱዌለንና እንደካሪን ወታደሮቹ የጣና በዓል ዋዜማ ቸውን በደስታ እንዲያሳልፉ የተቻላትን ሁሉ ታደርጋለች ። በእንግ ዶቹ ደስ ያልተሰኘች እስካርሌት ብቻ ናት ።

ወታደሮቹ የዕደላ ምግባቸውን ማለትም ድርጓቸውን ማሚ ካቀ ረበችው የደረቀ አተርና ፍራፍሬ እንዲሁም የአተር እሸት እራት ጋር ደባልቀው እስከዛሬ እንዲህ ያለ ምግብ በልተን አናውቅም እያሉ በሉ ። እስካርሌት አበላላቸውን እያየች ጭንቀት ይሰማታል ። እያንዳ ንዱን ጉርሻቸውን ከመጥላትዋም ሌላ ከትላንት ወዲያ ፓርክ ያሳማ ዋን ግልገል ማረዱን አወቁ አላወቁ እያለች ሰጋቱን አልቻለችውም ። አሁንም ሥጋው እዶሮው ቤቱ ውስጥ እንደተሰቀለና ማንም የቤቱ ሰው መኖሩን ቢናገር አይኑን እንደምታወጣው ፡ እንዲሁም የታ ረደው አሳማ ወንድሞችና አህቶች በቤታቸው መቀመጣቸውን ማንም ትንፍሽ ይልና አላሩን እንደምታሰቀው አስጠንቅቃለች ። እነዚህ የተራቡ ሰዎች ግልገሎቹ መኖራቸውን ቢያዩ በአንድ ራት እንደማ

@OLDBOOKSPDF

ጨርሷቸውና ትልቅ አላማ ከዩም ወደሠራዊቱ እንደሚነዱ ጥርጥር የለውም። ለላሚቷና ለፈረሱም በጣም ነው የሰጋችላቸው። ከግጦሹ በታች አጫካቸው ውስጥ ከሚታሰሩ ይልቅ ወደ ረግራጋው ሥፍራ ቢደበቁ ጥሩ እንደነበር ይሰማታል። እነዚህን ከብቶቹዋን ይዘው ባት ከሄዱ ታራ ከረምቱን መውጣት አትችልም። ምንም ዓይነት መተ ኪያ መንገድ እይገኝላቸውም ደግሞ። ሠራዊቱ ምን ይበላ ምን ደን ታዋ አይደለም። ቢሻው ፣ ሠራዊቱ ሠራዊቱን ይመግበው። ለራሷ ራሷንም መመገብ በጣም አዳጋች ሆኖባታል።

ሰምቹ ፣ ከምግብ በኋላ እንደሚበላ ፍራፍሬ እንዲሆናቸው ፣ ከዚህ ቀደም የተባይን ያህል ይነገርለት ፣ ብዙ ይቀልድበት የነበረ ውንና አይታው የማታውቀውን ጠምዛዛና ጠፍራ "ራምሮድ" የሚ ባል ፣ የኮንፌዴሬሺው ወታደሮች የጦር ግንባር ምግብ ፣ ሰምቹ ከቦ ርሳዎቻቸው ውስጥ አወጥተው ሲጨምሩ ተመለከተች። ከለሎ ያረረ ጠምዛዛ እንጨት ይመስላል። ሰምቹ አበረታቱዋትና አንዴ ገመ ጠችለት። ስክ ካረረው ቅፈሬት ሥር ጨው የሌለው የበቆሎ ጸቦ ቡጥ ነው ያለው። ወታደሮቹ ውጪ ሳሉ እንዚህን ነገሮች ቅርፊ ታቸውን ይልጡና በጨው በውሀ ቡጡን ለውሰው በእሳት ዙሪያ ጨዋታ ጊዜ ይጠብሷቸው ነበር። እንዲ ድንጋይ ከረሜላ የጠነከሩ አፈር አፈር የሚሉ ነገሮች ናቸው። እሰክርሌት እንዴ ገመጠችና ደማሚ እልነካው ስትል ሰምቹ በሳቅ ገነፈሉ። ከሜላኒ ጋር አይን ለአይን ተጋጨና ..."ይሄንን እየበሉ እንዴት ይዋጋሉ?" የሚለው ጥያቄ በሁለቱም እእምሮ ውስጥ ተቀረፀ።

ዓበታው ደስስ የሚል ነበር። ሴላው ቅርጹ በሀሳብ ሳይሆን በእ ካል ዋናው መቀመጫ ሳይ ጉብ ያለው ጄራልድ እንኳን በእንግ ዳ ወሳ ተቀምጠ ጥርጣሬ የተሞላበት ፈገግታ ያሳያል። ወንዶች ወንዶቹ ያወራሉ ፣ ሴቶቹ ይስቃሉ ፣ ተሸንግለው ይዝናናሉ ... እስ ካርሌት ብቻ ወደ ፍራንክ ኬኔዲ ዞራ ስለ ፒቲፓት ወሬ ልትጠ ይቀው ከታጣች በኋላ ፊቱ ላይ አንድ ነገር አይታ ተወችው።

ኬኔዲ አይኖቹን ከሱዌለን ላይ አንስቶ ቤቱን በሙሉ ትኩር ብሎ አንድ በአንድ ይመለከታል። የጂራልድን የሕፃን የሚመስሉ ግራ የተጋቡ ዓይኖች ፣ ወለሉን ፣ የተበጫጨቁትን ጨርቆች ፣ ጌጦቹን ያጣውን የፎቶ ማስቀመጫ ፣ በያንኪዎች ሳንጃ የተበሳሱትን የቤትዕ ታዎች ፣ የተሰቀለውን የተሰነጣጠቀ መስተዋት ፣ እስካሁን ቸለሙ ያልለቀቀና ፎዮግራፎች ይንጠለጠሉበት የነበረ ግርግዳው ላይ የሚታይ አራት ማዕዘን ቅርጽ ፣ የተራቆተውን የግቢታ ጠረጴዛ በወጉ የተሰራትን ግን እርጅት ያሉትን የሴቶቹን ቁሚሶች ፣ ዱሮ የማቡ

@OLDBOOKSPDF

ኪያ በህቃ የነበረና ዛሬ ግን የሞድ ገላ መታጠቢያ የሆነውን ሰፋ መልል ነገር ሁሉ ተመለከተ ።

ፍራንክ ከመረራው በፊት የነበረችውን ታራ አስታውሶ በንዴትና በቅጭት ፊቱ ተለዋወጠ ። ሱዌለንን ያፈቅራታል ፣ እህቶቹዋን ይወ ድዳቸዋል ። ጂራልድን ያከብረዋል ። የእርሻ ቦታውንም ከልቡ ይወ ዳል ። ሸርማን ያራቆታቸውን ብዙ አካባቢዎች ምግብ ፍለጋ ሲዞር አይቷቸዋል ። ነገር ግን እንዴታራ ልቡን የነካው አንድም ቦታ የለም። ለእሷም በተለይም ለሱዌለን አንድ ነገር ቢያደርግ ፣ አንድ ውለታ ቢውል እንዴት በወደደ ። ዳሩ ግን ሊሠራ የሚችለው አንዳችም ነገር የለም ። ሲያው ቀውና ሳያስበው በሐዘን እራሱን ሲነቀንቅና ምላሱን በጥርሶቹ ማህል ሲያወዛውዝ ፣ ከእስካርሌት ጋር አይን ለአይን ተጋጨ። በእይኖቹዋ ውስጥ ከዘር የተወረሰ የኩራት አሳት ሲንቀለቀል አየና ተደናግጦ ንይኑን ወደ ሳህኑ ዶቶ ።

ሴቶቹ ወሬ እንዲውሃ ጠምቷቸዋል ። እትላንታ ከጥያዘችና በጠሳት እጅ ከወደቀች ወዲያ ምስታ እሚባል አይተው አያውቁም ። ሙሉ ለሙሉ ተቋርጧል ። በዚህ ሁሉ አራት ወራት አልፈዋል ። ስለዚህም ያንኪዎቹ የት እንዳሉ ፣ የኮንፌዴራሲው ሠራዊት እምን እንደደ ረስ ፣ እትላንታም ሆነች ወዳጆቹው ምን እንዳጋጠማቸው ፣ በጭ ራሽ የሚያውቁት ነገር የለም ። ፍራንክ ሥራው ብዙ ቦታ የሚያዘ ረው በመሆኑና ከማክን በስተሰሜን እስከ እትላንታ ድረስ በዝም ድናም ሆነ በእውቂያ ከጦላ ንደል ከሁሉም ጋር ስለሚተዋወቅ ልክ እንዲጋዜጣ ማለት ነው ። እንደውም ባይበልጥ ። ጋዜጦቹ ሳይ ድቆ ያለፏቸውን በየግል የሚወሩትን ሐሜታዎች ሳይቀር ማውራት ያውቅበታል ። በእስካርሌት ድንገት መያዙን ለመሸፈን ወሬ አመጣ። "ሸርማን አትላንታን ለቆ ሲወጣ የኮንፌዴራሲው ሰዎች መልሰው እትላንታን ይዝው ነበር ። ዳሩ ምን ዋጋ አለው ፡ ድምጥማጡዋ እስኪ ጠፋ ድረስ እጋይቷት ነው የሄደው" ብሎ ነገራቸው ።

"እንዴ እኔ የወጣሁ ለታ እኮ ነው እትላንታ የተቃጠለች የመ ሰለኝ ።" አለች እስካርሌት በመገረም ጮሀ ። "የኛ ሰዎች እቃጥ ልዋታል ብዩ ነበር ።"

"በጭራሽ ። በጭራሽ እንደሱ አይደለም ፡ ወይዘሮ እስካርሌት ።" አለ እየጮኸ ፍራንክም ተደናግጦ ። "የኛ ሰዎች እውስጡዋ ያሉ ዓትን አገር በፍጹም አናቃጥልም ። ያኔ ያኖሽው ያንኪዎቹ እንዲወ ስዱዋቸው የማንፈልጋቸውን የልብስ ጭኖችና የአገልግሎት ፅሕ ፎቶችን ስናቃጥል ነው! ቢቆ ያ ብቻ ነው ። ሸርማን የጣ ለትማ

@OLDBOOKSPDF

ቤቶቹም ሆኑ መጋዘኖቹ እንደ ምትወጂያቸው አምረው ቆመው ነበርና መታደሮቹን በየቤቱ መርቶ ከትሞ ነበር።

"እዚያ የነበሩትን ሰምኾለሽ ፈጁዋቸው!"

"በጥይት አይደለም እንጂ እንዳንዶቹን ገድሏል" አለ አንድ አይናው መታደር ኮምጠጥ ባለ መልክ። "ወደ አትላንታ ገና ከመጣ ባቡ እያንዳንዱ ህይወት ያለው ሰው ከተማውን ለቆ እንዲወጣ ለከ ንቲባው ነገረ። መቼም የእግር ጉዞ የማይችሉ የደከሙ ሽማግሌዎች፣ ሕመምተኞችና ሴቶች ነበሩ። በመቶ የሚቆጠሩትን እነዚህን አቅመ ደካሞች በሕይወትሽ አይተሽው በማታውቂው ዶፍ በሚወርድበት ዝናብ ውስጥ እየንዳ በራፍና ሬዲ አጠገብ ካለ ጫካ ውስጥ ካስገባቸው በኋላ ጂኔራል ዊድንናና ውሰድ አለው። ብዙዎች ይዘርድ በሽታና ያንን የሰደፍ ግፊያ መቋቋም አቅቷቸው አለቁ።"

"አዬ! ምንው ለምን እንደዚያ ያደርጋል? ምን ያደርጉኛል ብሎ ነው?" ብላ ጮኸች ሜላኒ።

"ከቀጣውን ለመታደሮቹ ማረፊያ እደርጋለሁ አለ። እስከ ጎዳር አጋማሽ ድረስ አቆያቸውና ወጥቶ ፈጁ። ሲመጣም አንድ ነገር ሳይተረፈው ከተጣውን አቃጠለው።" አለ ጥራንክ።

"እውይ! እወጎት ምንም አሳስቲረኮ" አሉ ሴቶች በመከፋት።

ያቺ ሕዝብ የሚተራመስባት፣ ሕይወት የሞላባት፣ የሞቃች ከተማ በንና ጠፍታለች ብለው ማመን አቃታቸው፤ የሚጥፍ ነገር አልሆ ነላቸውም። በአንዚያ ያማሩ ዛፎች ጥላ ሥር የነበሩ ቤቶችና ያማሩ ሆቴሎች በንኩ ጠፉ ለማለት የሚቻል ነገር አይደለም!! እንዴት ጉብለ!! ሚላኒ የተወለደችበት አገር በመሆኗና ከዚያች ሌላ አገር ስለማታውቅ እንባ እንባ ያላት ይመስላል። እስክርሌትም ከታራ ቀጥሎ የምታፈቅራት ቦታ በመሆኑዋ ልቡዋ ስንጥት አለባት።

"አም እንግዲህ ከሞላ ጐደል ሁሉንም ነው" አለ ጥራንክ ቀጠ ለና ፊታቸው ላይ በሚያየው ሁኔታ ተረብሾ። ሴቶችን ማስቀየም ስለማይወድ በተቻለው ደስተኛ ለመምሰል ሞከረ። የተናደዱ ሴቶች እሱንም ያናድዱትና ረዳት የለሽ ያደርጉታል። መጥፎ ነገር ሊነግ ራቸው በጭራሽ አይሻም። ቢፈልጉ ከሌላ ሰው ጠይቀው ይስሙ።

መቼም ሠራዊቱ ወደ አትላንታ ሲመለስ ያየውን ሁሉ ሊነግራ ቸው አይችልም። ከጋሻ እስከጋሻ ከሰል መስለው ጥላሸት ለብሰው በአመድ ላይ ስለቆሙት የጭስ ማውጫዎች፣ ግማሽ በግማሽ አር ረው ስለተቆለሉት ቆሻሻዎችና መንገዱ ላይ ስብርብራቸው ወጥቶ

@OLDBOOKSPDF

ስለተበተኑት ሽከላዎች ፣ በእሳት ተለብልበው በድን ስለሆኑና ቅር ንጫሮቻቸው አርር ክስል ብሰው ስለተዘነጠፉና ቀዝቃዛው ንፋስ ስለገነዳደሳቸው ዛፎች ሊንግራቸው አይችል ንገር ። የኮንፌደሬሲው ሰዎች በከተማዋ ላይ የወረደውን እርግማን ሲያዩ የሆኑትን ሁኔታ አይቶ የተሰማውን ሕመም አስታወሰ ። እንዚህ ሴኖች ስለእነዛ መከረኛ መቃብሮች አይሰሙም የሚል ተስፋ አለው ። ቻርሊ ሐሚልቶንና የሜላኔ እናትና አባት የተቀበሩት እዚያ ቦታ ነው ። የዚያ የመቃብር ቦታ ትእይንት ሰፍራንክ እንደሕልም ይታየዋል ። እነዚያ ያንኪዎች ከሞቱ ሰዎች ጋር አብሮ የተቀበረ ጌጣ ጌጣ እናገኛለን ብለው ያፈረሱት መቃብር ና የፈነቀሉት ሐውልት የትየለሌ ነው ። ከሬሳ ሳይ ሳይቀር ዘርፈዋል ። ከሬሳ ሳጥን ሳይ ያገኙትንም በወርቅ የተቀረፀ የሚሸቹን ስም እየነቀሉ ወስደዋል ። ከብር የተሰሩ በደንብ የተበጁ ፈርጣ ፈርጠኞችና እጀታዎችን ሁሉ ፈልፍለው ሰረቁ ። ስለዚህም እጽጥቹና ሬሳዎቹ እዚህም እዚያም ተቆራርጠውና ተበታትነው በወደቁት ማጥኖች ግሃል ተዘርረረው ለፀሐይ ተሰጥተዋል። በጣም የሚያሰቅቅ ትርኢት ነው ።

መቼም ፍራንክ ስለድመቶቹና ውሾቹ አይነግራቸውም ። ሴቶች ለማዳ እንሰሶች ይወዳሉ ። ግን ፍራንክ ወሻና ድመት በጣም ከመ ውደዱ የተነሳ ጌቶቻቸው እንደ ክብት እየተነዱ ካገር ሲባረሩ ያለ ጌታ የቀሩት እንሰሶች የሐውልቶቹን ያህል አሰቅቀውታል ። እነዚያ እንሰሶች ፈርተዋል ። በርዷቸዋል ። እንዱ ሳንዱ እንደማይተኛ የዱር አውሬ ሆነዋል ። ኃይለኛው ደክማውን ያጠቃ ጀመር ። ደክማው ደግሞ ከሱ የባሰ ደክማ አስኪሞትለት ይጠብቃል—ሊበላ ። በዚያች በፈ ረሰች ከተማ አናት ላይ እያንጣጮበቡ ጥንብ አንሳዎች ሰማዩን ማርማ በተላበሱና በተክፉ ሰዎች ሬሳ በከሱት ።

ፍራንክ ለሴቶቹ የሚሆን ሻል ያለና የሚያጽናና ወሬ ይፈልግ ጀመር ።

“አንዳንድ ከቃጠሎው ቦታ ርቀው የነበሩ ያልተቃጠሉ ቤቶ ችም አሉ እኮ ። ቤተክርስቲያኖቹና የማለን አዳራሽም አልተነኩም ። ጥቂት መጋዘኖችም ተርፈዋል ። በፋይቭ ፓይንት ጐዳና መንገዱን ይዘው ሲሄዱ ያሉ ቤቶችና ሱቆች በሙሉ ዶጋመድ ሆነዋል ። ”

“ያስ ቻርሊ የተወልኝ የልብስ መጋዘን ? በመንገዱ ወደታች ሲሔዱ ያለው እንኳን ፣ አሱም አብሮ ጠፋ ?”

“ከመንገዱ ጻር ከሆነ መቼም አይተርፍም ፡ ግን . . .” አለና ድን ገት ፈገግ አለ ። እንዴት እስካሁን ሳያስበው ቀረ ” ደስስ ይበላችሁ!

@OLDBOOKSPDF

እመቤቶች፣ የወ/ሮ ፒቲ ቤት አሁንም አለ ። ትንሽ ፈርዷል እንጂ አለ ። ”

“እንዴ፣ እንዴት አመለጠ?”

“እንጃ እንግዲህ ፣ ብቻ ከሸክላ በመሠራቱና በአትላንታ ውስጥ የድንጋይ ጣራ ያለው ቤት ያ ብቻ በመሆኑ እሳቱ ዘልቆት ባለመግባቱ ሊሆን ይችላል ። በዛ ሳይ በስተሰሜን የመጨረሻው ቤት በመሆኑም እሳቱ እምብዛም አልያረሰበትም ። እርግጥ ያንኪዎች አዚያ አካባቢ ከትመው ነበር ። ሌላው ቀርቶ ዛሮቹንና ከእጨት የተሠሩትን ደረጃዎች ሳይቀር ፈልጠው ማገዶ አድርገዋቸዋል ። ግን አሁንም ደህና ተቀምጧል ቤቱ ። ብሰፈው ሳምንት ወይዘሮ ፒቲን ማክን ውስጥ ሳያት ። ”

“እየሀት? እንዴምነች ባክህ?”

“በጣም ደህና ፡ በጣም ደህና ናት ። እንደውም ቤቷ ደህና መሆኑን ስንግራት ተመልሳ ለመሄድ አስባለች ። ያ እንግዲህ ፣ ሽማግሌው ባሪያ ፒተር ይዟት ለመሄድ ፈቃደኛ ከሆነ ነው ። ብዙዎቹ የአትላንታ ሰዎች በማክን በመግረር ወደ አትላንታ እየተመለሱ ነው ። ቬርማን ማክንን አልያዘም ፣ ግን ከሱ ቪ ጊቢ ጨክኛ የሆነው ዊልሰን ከዛሬ ነግ ይመርራታል እየተባለ ሲጋት ከናተኛ ሆኑዋል ። ”

“እንዴ ፣ ግን ቤት እንደሌለ ሲያውቁ መመለሳቸው ምን የሚ ሉት ጅልነት ነውነ የት ሊኖሩ ነው ። ”

“በድንኳን ፣ ከአንጨት በተሠሩ ቤቶችና ባሉት ጥቂት ቤቶች ውስጥ እምስትም ስድስትም ቤተሰቦች አንድ ላይ እየሆኑ ይኖራሉ ። እንደነና ቤት ለመሥራትም እየተጣጣሩ ናቸው ። እና ወይዘሮ አስክርሌት ፣ ደጀቦች ናቸው አትበይ በሞቱ ። የአትላንታን ሰዎች አኔም አንቺም በደንብ የምናውቃቸው ናቸው ። ከእዛ ከተማ ጋር የተ ጣበቡ ሰዎች ናቸው ። ልክ ቻርልስተናዊያን ለቻርልስተን እንደሚ ሆኑት ዓይነት ማለት ነው ። እኔሱን ከዛ ለመንቀልና ለማላቀቅ ከያን ኪዎችና ከአሳት የበለጠ ነገር ያስፈልጋል ። የአትላንታ ሰዎች-ወይዘሮ ሚለ ይቅርታ አድርጊልኝና እንደበቅሎ ሰውዝዝ ያሉ ደረቆች ናቸው፣ በአትላንታ ጉዳይ ። ሰምን እንደሆነ እንጃ እንጂ ያቺ ከተማ ጠን ካራ የሞተችና ለመኖር የምትስብ ሆና ነው የምትታየኝ ። ያም ሆኖ ባላገር የተወለድኩና ባላገር ያደግሁ በመሆኔ ከተማ ደስስ አይለኝም ። እና አሁን ተመልሰው ወደዛ የሚሔዱት ሰዎች በጣም ብልሆቹ ናቸው ። ወደ መጨረሻ ግሥማ የሚሄዱት እጠነት አልሻለሁ ሰው ሁሉ ሰርቶ ሰርቶ ከጨረሰ በኋላ ስለሚደርሱ ስንጥር እንጨት ፣ የወ

@OLDBOOKSPDF

ደቀ ድንጋይም ሆነ በጣሳ አያተኮም ። በትላንት ወዲያ ወይዘሮ ሜሪቄ ዘር፣ ወይዘሮ ሜይቤልና አንዲት ባሪያ ኩርኩር ይዘው ሸክላ ለቀማ ወጥተው አየሁዋቸው ። ወይዘሮ ሚድም ከእንጨት የምትሠራውን ቤት ጉዳይ ስትነግረኝ ነበር ዶክተሩ የመጣው ። ከዚህ ቀደም ወደ አትላንታ - ዱሮ ማርታስቪል ትባል በነበረበት ጊዜ - መጀመሪያ ስት መጣ በእንጨት ቤት ውስጥ ትኖር እንደነበርና አሁንም ደግማ ብት ሠራ ቅር እንደማትሰኝ ነገረችኝ ። እርግጥ ስትቀልድ ነው ፣ ግን ምን ያህል እንዳሰበበት ያሳያል ።"

"አም ጠንካራ መንፈስ ያላቸው ይመስለኛል ። አንቺስ እስካርሌት?" አለች ሜላኒ በኩራት ስሜት ። እስካርሌትም አዲስ ባወቀ ቻት ከተማ ኩራት ተሰማትና በአምንታ ራስዋን ነቀነቀች ። ፍራንክ እንዳለውም የሞቀና ሕይወት የሞላባት በመሆኗ ነው የወደደቻት ። እንደሌሎቹ አሮጌ ከተሞች ጉራንጉር የበዛባትና ጥቅጥቅ ያለች ባለመ ሆኑዋ የራስዋን ከተማ የመሰለ ፍካትና ሕይወት አላት ። "ልክ እንደ አትላንታ ነኝ አሰች" በልቧ ። "እኔንም ለማጥፋት ከያንኪዎችና ከእሳት ቃጠሎ በላይ የሆነ ነገር ያስፈልጋል" አለች ።

"እስካርሌት ፣ ወ/ሮ ፒቲ ወደ አትላንታ የምትመለስ ከሆነ እኛም እንመለስና ከሱዋ ጋር እንኑር" አለች ሜላኒ ከሠሳቡዋ አቋረጠቻትና። "ብቻዋን ከሆነች ድንጋጤውም ይገድላታል ። "

"እንዴ ሜሊ ምን ማለትሽ ነውን እንዴት ይሄንን ጥዬ እሄዳ ለሁ?" አስካርሌት ጠየቀች በመስቀለኛ "እንቺ በጣም ንጉተሽ ከሆነ እኔ አላግድሽም ሂጂ ። "

"እንዴ እንደዛ ማለቴ አይደለም እኮ ውዲት!" ብላ ጮኸች ሜላኒ በመከራት ። "ውይ ምን ልበ ቢሷ ነኝ! ታራን ትተሽ መሄድ የለብሽም ጭራሽ ፣ ደሞም እትት ፒተርና ኩኪ ካሉ አክስቴን ይጠ ብቋታል ። "

"የለም ከመሄድ የሚከለክልሽ የለም ፣ ሂጂ" አለች እስካርሌት ፍርጥም ብላ እትጨን በመንገር ።

"እስካርሌት ፣ ጥዬሽ እንደማልሄድ ታውቂያለሽ ። ደግሞም አንቺ ከሌለሽ ፍርሃቱ እንኳን ይገድለኛል ። "

"የራስሽ ጉዳይ ነው ። ደሞም እኔን እትላንታ ትሄዳለች ብለሽ እንዳታስቢ ። ምን አለች በይኝ ደግሞ ጎና ጥቂት ቤቶች እንደ ሠሩ ነው ሽርማን ተመልሶ የሚያቃጥልባቸው ። "

"እይ ተመልሶ አይመጣም ።" አለ ፍራንክ ። ጥረት ያደርግ እንጂ እንቱን ማቀርቀሩ አልቀረም ። "በኩመላው አቋርጠ ወደባሀሩ ዳርቻ

@OLDBOOKSPDF

ሄዷል ። በዚህ ሳምንት ሳቫና ተይዛለች ። እና ያንኪዎቹ ሽቅብ ወደ ደቡብ ካሮላይና እንደሚሔዱ ይነገራል ። ”

“ሣቫና ተወሰደች?”

“አዎ ። ምን ነካችሁ እመቤቶች ፡ ሳቫና ከመውደቅ በቀር ሌላ ምርጫ የላትም ነበር እኮ! እሷን ሊያቆዩ የሚችሉ በቂ ሰዎች አላ ገኙም ። ለነገሩማ አንድ እግሩን አራምዶ ሁለተኛውን ለማስከ ተል የሚችል ማንኛውንም ሰው ፡ ከልሂቅ እስከደቂቅ አሰልፈው ነበር። ለመሆኑ ያንኪዎቹ ወደ ሚሌጅቪል እየገሠገሱ እንዳሉ እመር አካ ዳሚ ውስጥ የነበሩትን ካዴቶች በሙሉ እዝሌ ከከሌ ሳይሉ—ወጣቶቹን ሳይቀር እንዳሰለፉና ሌላው ቀርቶ ከጠባይ ማረሚያ እንኳ ለመር ነቱ ትኩስ ተዋጊዎችን ይመለምሉ እንደነበር ታውቃላችሁ? አዎ ጌታዬ እያንዳንዱን አስረኛ መርነቱ ላይ ለማዋል ፈቃደኛ ከሆነ እየፈቱ ያስማሩት ነበር ። ይቅርታ እንደሚደረግለትም ቃል ይገቡለት ነበር ። መቼም እንዚያን ወጣት ካዴቶች ከሴቦችና ከማጅራት መቺ ዎች ጋር ተሰልፈው ማየት እንዴት ጭንቅላቴን ነክኝ መሰላችሁ ። ”

“እስረኞቹን ሁሉ በኛ ላይ ለቀቂዋቸው ማለት ነዋ!”

“ወይዘሮ እስካርሌት ፡ ከአንግዲህ መበሳጨት አያስፈልግም ። ከዚህ ብዙ ርቀው ሄደዋል ። ለዛውም ደህና ወታደር ወጥቷቸዋል ። እንደመሰለኝ ሌላ መሆን ጥሩ ወታደር ከመሆን አያሚድም ። ያግዳል እንዴ!”

“ኡዉ በጣም የሚያሰደንቅ ነገር ነው!” አለች ሜላኒ ለስለስ ብላ ።

“እኔን አያስደንቀኝም” አለች እስካርሌት በደረቁ ። “ከተማ ውስ ጥስ በቂ ሌቦች አሉ አይደለምና ነው እንዴ ፡ አንኳንስ በያንኪዎች ውስጥና . . .” ብላ በጊዜ አፉዋን ያዘች ። ሰዎቹ ግን ሳቃቸውን ለቀ ቋት ።

“እንኳንስ በያንኪዎች ውስጥና በኛስ የኩሚሳሪያት ክፍል ውስጥ ቢሆን ። ” ብለው የጎደለውን ሲሞሉላት በሳቅ ገነፈለች ።

“ግን የጂኤራል ሁድ ሠራዊት የት ደረሰ?” ብላ ሜላኒ በችኮላ ጠየቀች ። “ሳቫናን ሊያድናት ይችል ነበር ። ”

“እንዴት ወይዘሮ ሜላኒ ፡ ከነጭራሹስ ጂኤራል ሁድ በዚያ አቅ ጣጫ መች ሄደና እሱ ተነሲ ላይ ነበር የሚዋጋ ። ያንኪዎቹን ከጆ ርጂያ ለማስወጣት ነበር የሚጣጣረው ። ” አለ በመገረም ።

@OLDBOOKSPDF

"እናስ! ያቺ ኢንስተኛ ዘይው ሠራቻ!" አለች እስካርሌት በአሽሙር አንጎጋር። "እኛን እንዲጠብቁ ተማሪዎቹን ፣ እስረኞችንና የከተማ ጠባቂዎችን ሰጥቶ ባዶ እጃችንን ከያንኪዎች ጋር አጋጨን ሄደ።"

"የኔ ልጅ፡" አለ ጂራልድ ፡ በሀሳብ ከሄደበት እየተመለሰ። "የኔ ልጅ ፡ የተከደሰ ልጅ አልሆንሽም። ባልገሻል። እናትሽ ታዝንብሻ ለች።"

"የተረገመ ያንኪዎች ናቸው።" አለች እስካርሌት ግንፍል ብላ። "ከዚህ ሌላ ስም አላገኙላቸውም።"

የኤለንን ስም ጂራልድ ሲጠራ ሰው ሁሉ ተደናገጠና ንግግር ሁሉ ቆመ። ሜላኒ እንደገና ከፈተችው።

"አንተማከን እያሰብ ኢንዲያንና ሐኒ ዊክሰን አይተሃቸው ኖሯልን ስለአሽሌይ የሰሙት ነገር ይኖር ይሆን?"

"ይሄውልሽ ወይዘሮ ሜለ ስለአሽሌይ ወሬ ሰምቼ ቢሆን ናሮ ዉኒያውኑ ኮማከን ገለግሺ እመጣ ነበር።" አለ ፍራንከ እየፀፀተው።

"ምንም ወሬው የለም። ግን ወይዘሮ ሜሊ ምንም እንኳን ስለሱ ወሬ ከሰማሽ ብዙ ጊዜ እንደሆነሽ ባውቅም ፡ ስለአሽሌይ መጨነቅ የለ ብሽም። አንድ ሰው እስር ቤት ከገባ በኋላ ስለሱ ወሬ ማግኘት አስቸጋሪ መሆኑን አታውቂም እንዴ? ደሞኮ የያንኪ እስር ቤቶች እንደእኛ እስር ቤት ሞተር አይደሉም። ሌላው ቢቀር በቂ ሕክምና የሚለብሱትም ብዙ ሰዎች ይኖራቸዋል። እንደኛ እንኳን ለእስረኞቻቸው ለራሳቸው ምግብ ያጡ አይደሉም።"

"አ ያንኪሞቹማ ብዙ አሳቸው።" አለች ሜላኒ ጮሀ ፡ የምሬት ስሜት እንደያዛት። "ሆኖም ለእስረኞቻቸው አይሰጧቸውም። እንተም እንደማይሰጧቸው ታውቃለህ ፡ አቶ ኬኔዲ። አሁን የምትነግረኝን ሁሉ የምትነግረኝ እንድጽናና ብለህ ነው። የእኛ ልጆች በያንኪ እስር ቤት እንደሚማቅቁ፣ በቅዝቃዜ እንደሚያልቁ ፡ በረሀብ እንደሚቆሱ፣ ያለሐኪምና ያለመድኃኒት በበሽታ እየተሰቃዩ እንደሚሞቱ ታው ቃለህ። ይሄ ሁሉ ያንኪዎች በእኛ ላይ ካላቸው ጥላቻ የመነጨ ነው፤ ዋይ ነዶ እንደው እያንዳንዱን ያንኪ ከምድረ ገጽ ለማጥፋት ብንችል እንዴት ጥሩ ነበርን! አዎ አሸሌይስ . . ."

"በይ ዝምበይ ታል እንዳትተነፍሺ ከእንግዲህ" ብላ ሙቸኞ እስካርሌት ልቧን እንደልማዷ ጉሮሮዋ ላይ ሰክታ። ማንም ስለአሽሌይ መሞት እሰከአሁን የተናገረ ሰው ስለሌለ በልቧ በህይወት አለ የሚ

@OLDBOOKSPDF

ሰው እምነት በስሱም ቢሆን ይኖራል ዲያም ሆኖ አሽሌይ ሞት የሚል ነገር ከሰማች ወዲያው የሚሞት ይመስላታል ።

"አሁን እንግዲህ ወይዘሮ ሜሊ ፣ ስለባልሽ መጨነቅሽን ተይ ።" አለ አንድ ዓይናው ሰውዬ በማጽናናት መልክ ። "በመጀመሪያ ማና ሳስ ውስጥ እኔም ተይዤ ታስሬ ነበር ። አስረኛ ሲለዋወጡ እስከም ፈታ ድረስ እዚያው ቆይቻለሁ ። ታዲያ እስር ቤት ሳለሁ ይመግቡኝ የነበረው ምርጥ ጮማ ፣ ዶሮ አሮስቶ ትኩስ ብስኩት . . . "

"ኤጭ በቃ ። እንደሚመስለኝ አንተ መልካሙ ሰው ነህ ።" አለች ሜላኒ ትንሽ ፈገግ ብላ ። አስካርሌት ሜላኒ ሐሞቷን ኮስተር አድርጋ ወንድ ስታናግር ያየቻት ገና አሁን ነው ። "ምን ይመስልሀል ?"

"እኔም ስለራሴ የማስበው ይህንኑ ነው" አለና አንድ ዓይናው ሰውዬ እየሳቀ እግሩን በጥፊ መታ ።

"ሁላችሁም ወደ አልፍኙ የምትመጡ ከሆነ የገና መዝሙር እዘምርላችኋለሁ ።" አለች ሜላኒ የጭውውቱን አርእስት መለወጫ ደስ እያላት ። "ያንኪዎቹ ዘርፈው ሰመውሰድ ሸክሙ ከብዷቸው የተጨት ጢያኖውን ብቻ ነው ። ድምጼ ተበላሽቶ የለም እንዴ ሱዌለን ?"

"በጣም እንጂ" አለች ሱዌለን ሰፍራንክ የደስ ደስ ያለው ፈገግታዋን እየመገበች ። ሁሉም ከፍሱን ለቅቀው እየወጡ ሳሉ ፍራንክ ወደኋላ ቀረት ብሎ አስካርሌትን ወደ እጅጌዋ ግድም ጐንተል አደረጋትና ።

"ለብቻሽ ላናግርሽ" አላት ።

ለአንድ ግራ የተጋባት ቅጽበት ስለከብቶቹ የሚጠይቃት መስ ሏት ፈራችና ጥሩ ውሸት ለመዋሸት ባጭሩ ታጠቀች ።

ሰው ሁሉ ቤቱን ለቆ ከወጣ በኋላ ሁለቱ ብቻ እሳቱ አጠገብ ቆመው ሳሉ ፍራንክ ኬኔዲ በሌሎቹ ፊት ያሳይ የነበረውን ደስታ ውን ሁሉ አሰናብቶና ከፊቱ ላይ ጭፍፎ ስታየው ሽማግሌ መምሰ ሉን አስተዋለች ። ፊቱ ድርቅ ያለ ጠይም ከመሆኑ የተነሳ ታራ ሜዳ ላይ እየረገፈ የሚወድቀውን ቅጠል ይመስላል ። ዝንጅብል የመስ ለው ጢሙም በቀጭኑ ሾሎ ግራጫ ሽበት ፈንጣጥቆበታል ። በልቡ ሌላ ነገር እያሰላሰለ በጣቶቹ ጢሙን እያሻሸ አከታውን የሚተፋ እስከሚመስል ድረስ ጉሮሮውን አጥርቶ ለመናገር ተዘጋጀ ።

"በእናትሽ መሞት አዝኛለሁ ወ/ሮ አስካርሌት"

"እባክህ እሱን አታንሳብኝ"

@OLDBOOKSPDF

"አባትሽስ . . . ከዚህ ቀደም እንዲህ አርጎት ያውቃል ?"

"አዎ ፣ ብቻ . . . ራሱን አያውቅም እንደምታየው"

"መቼም ኤለን ዋና አለኝታው ነበረች ። "

"ውይ አቶ ኬኔዲ ፣ ምነው ስለሷ ባናነሳና . . . "

"ይቅርታ ወ/ሮ እስካርሌት ።" አለና እግሩን አቀያይሮ አቆላለፈ፣ አንድ ስሚት እየወጠረው ። "ልነግርሽ የፈለኩት ነገር እንኳ ከአባትሽ ጋር ልሠራ የምፈልገው አንድ ሥራ እንደነበርና አሁን ግን ዋጋ የሌለው መሆኑን ነው ።"

"ምናልባት እኔ ልረዳህ የምችለው ነገር ከሆነ አቶ ኬኔዲ፣ ቤቱን የማስተዳድረው እኔ ስለሆንኩ ልተባበርህ እችላለሁኝ ። "

"መቼም እኔ" ብሎ ጀመረና ፍራንክ ጢሙን ማሻሸቱን ቀጠለ። "በእውነቱ . . . ልነግርሽ እንኳ . . . ልጠይቅ እንኳ የፈለኩት ወ/ሮ እስካርሌት . . . እ . . . ልጅን ወ/ት ሱዌለንን እንዲሰጠኝ ላማክረው ነበር ።"

"እንዴ ፣ እስካሁን አባባት ይሄን ጉዳይ አልጠየቅሁትም ነው እንዴ የምትለኝ ?" አለች እስካርሌት በከፍተኛ መገረም ፈሀ ። "ስን ቱና ስንት ዓመት አብረሃት ቆይተህ ስታበቃ ያለ አንድ ነገር ቁጭ ትላለህ ?"

በመከፋት ፊቱ ቀላ ። ቅንድቡ ተኮማተረ ። በጠቅላላው ነገረ ሥራው ሁሉ የአይናፋርና የጅላጅል ልጅ ዓይነት ሆነ ።

"አይ መቼም . . . እንደምታገባኝ አላውቅም ነበር ። ከሷ በእድሜ በጣም ስለምበልጥ . . . ብዙ ቆንጆ ቆንጆ ወጣት ወንዶችም ታራ አካባቢ ስላሉ . . . "

"ኤጭ !" አለች እስካርሌት በልቧ ። " "ደሞ ወንዶች እሷን ሆነ እንዴ የሚከተሉት ፣ እኔን ነው እንጂ !"

"አሁንም ቢሆን ታግባኝ አታግባኝ አላውቅም ። በጭራሽ አን ስቼባት አላውቅም ግን ምን እንደሚሰማኝ ታውቃለች ። እኔ . . . እኔ እንኳ መጀመሪያ የጄራልድን ፈቃድ ለመጠየቅ እቅጩን እነግረዋ ለሁ ብዬ ነበር ። ወይዘሮ እስካርሌት አሁን ቤሳ ሳንቲም የለኝም ። እንደው የጉራ ነው አትበይኝ እንጂ ብዙ ገንዘብ የነበረኝ ሰው ነበርኩ ። አሁን ግን በአለም ላይ ያለኝ ንብረት ፈረሴና የለበስኳቸው ልብሶች ብቻ ናቸው ። አየሽ ለጦርነቱ ስመዘገብ አብሣኛውን መሬቴን ሸጥ ኩና ባገኘሁት ገንዘብ በሙሉ የኮንፌዴሬሲውን ቦንድ ገዛሁበት ።

@OLDBOOKSPDF

አሁን ምን ያህል እንደወረዱ መቼም የምታውቂው ነው ። ከታላ ሙበት ወረቀት ዋጋ በታች ናቸው ። እነሱም ቢሆኑ አሁን በእጄ የሉም ። ያንኪዎቹ የአሀቴን ቤት ሲያቃጥሉ አብረው አቃጠሏቸው ። መቼም እንዲህ ያጣሁ የነጣሁ በሆንኩበት ስዓት ሱዌለንን ላግባ ስጡኝ ማለቱ እጉል ድፍረት ሊመስልብኝ ይችላል ። ግን ያለኝ አማራጭ ይኸው ነው ። ይሄ ጦርነት ሁኔታዎችን ሁሉ እንዴት እንደ ለዋወጣቸው አለመገመታችንን ሳስብ ይገርመኛል ። በበኩሉ የምጽአት ጊዜ የደረሰ መስሎ ነው የሚታየኝ ። ስለምንም ነገር እርግጠኛ መሆን አይቻልም ። እናም ለኔም ሆነ ሰይ ቀለበት ማሰራችን ትልቅ ደስታን ይሰጠናል ብዬ አስባለሁ ። እርግጠኛ ልንሆንበት የም ንችለውም ነገር ያ ብቻ ነው ። ደሞም ወይዘሮ እስካርሌት ላግባትና አብረን እንኑር አላልኩም ። በቂ ሀብት ኖሮኝ እሷን በሚገባ ላኖራት ስችል ብቻ ነው እንድንጋባ የምፈልገው ። ያ ቀን መቼ እንደሆነ ግን አላውቀውም ። ያም ሆነ ይህ አውነተኛ ፍቅር ላንቺ ትልቅ ነገር ሆኖ የሚሰማሽ ከሆነ ወይዘሪት ሱዌለንን የፍቅር ባለፀጋ አደርጋ ታለሁ ። ”

የመጨረሻዎቹን ቃላት ሲናገር የሚታይበት ኩራት አስካርሌትን ስሜቷን ነካት ። በሁኔታው የተነሪመች ቢሆንም እንኳን ስሜቷን ነክ ቷታል ። ግንም ሰው ሱዌለንን ያፈቅራል ብላ ስለማትገምትም ይሄ የሱ ፍቅር ልትረዳው ከምትችለው በላይ ሆነባት ። ለሷ እሀቷ የራስ ወዳድነት ምልክት ፣ የንጭንጭ ሚስታወሻና የግርምቢጥ እመል ሁሉ ግእከል ናት ።

“ምነው አቶ ኬኔዲ” አለች በደግ ልሳን ። “ይሄ ምንም አይደ ለም ። እንደአበባ ሆኜ ሳናግርህ እንደምችል እርግጠኛ ነኝ ። ስለአ ንተ ታላቅ አክብሮት አለው ። ሱዌለንም አንቱን ማግባቷን የሚ ጠብቀው ነገር ነው ።”

“አሁን እንደዛ ያስባል ብለሽ ነው ?” አለ ፍራንክ ጮክ ብሎ ደስታ ፊቱ ላይ እየፈካ ።

“በደንብ ነዋ” ብላ መለሰች እስካርሌት ። በሆዷ ግን ጀራልድ በየጊዜው ገበታ ሊቀርብ ሱዌለንን የሚላትን አስታውሳ ሳቋ መጥ ቶባት ነበር ። እንደምንም ሸሸገችው ። ጀራልድ “አሁንስ እሜቴ ! ያ ወዳጅሽ አሁንም የጋብቻ ጥያቄ አላነሳም ፣ ምን እንደሚያስብ አኔው ራሴ ልጠይቀው እንዴ ?” የሚላት ትዝ አላት ።

“በቃ ዛሬ ማታ እጠይቃታለሁ” አለ ፍራንክ ጉንጩ ሁሉ እየተንቀጠቀጠ ፣ የእስካርሌትን እጅ ጭምቅ አድርጎ ይዞ እየነቀነቀ “በጣም ደግ ሴት ነሽ ወ/ሮ እስካርሌት” ።

@OLDBOOKSPDF

"ወዳንተ እልክታለሁ" አለች እስካርሌት ወደእልፍኟ መን ገድ እየጀመረች ። ሚላኒ ፒያኖ መጫወቷን እያጀመረች ነው ። ፒያኖው አብዛኞቹ ቁልፎች አርጅተው ከጥቅም ውጪ የሆኑ ቢሆ ንም አንዳንዶቹ የሙዚቃ ቃና አላቸው ። ሚላኒ ሌሎቹን እየመ ራች ። "ሐርክ ፡ ዘ ሔራልድ ኤንጅልስ ሲንግ ኮ" የተባለውን መዝ ሙር ጀመረች ።

እስካርሌት አዳረጠች ። የጦርነት ንፋስ ሁለት ጊዜ በላያቸው ላይ መንፈሱ ሊታሰብ የማይችል ነገር ነው ። በተራቆተች አገር በረሀብ ገደል አፋፍ ላይ ተንጠልጥለው ይሄን የነና መዝሙር መዘመራቸ ውም የማይታለም ነገር ነው ። ድንገት ወደ ፍራንክ ዞር አለች ።

"የምጽአት ጊዜ የደረሰ መስሎ ነው የሚታየኝ ስትል ምን ማለትህ ነበር ?"

"እውነቱን እንግርሻለሁ" አለ በቀስታ "ብቻ እኔ የምናገረውን ለሌሎቹ ሴቶች ንግረሽ እንዳታስደንግጫቸው ። ጦርነቱ ከእንግዲህ ለረጅም ጊዜ አይቀጥልም ። የሞቱትን ወታደሮች የሚተኩ አዲስ ምልምሎች የሉም ። የሚከዱት ወታደሮች ቁጥርም በጣም እያደገ መጥቷል ። በጣም ከፍ ከማለቱም የተነሳ ሠራዊቱ በሞራሽ ሊያ ምነው አልቻለም ። አየሽ ውጊያ ላይ ያሉት ወታደሮች ቤተሰቦቻቸው በረሀብ አለንጋ እየተገረፉ መሆናቸውን ልባቸው እያወቀ አስችሏ ቸው ለመቆየት ስለማይችሉ ጠሩን እየክዱ ወደቤተሰቦቻቸው በመ ሔድ ከረሀብ ሊያድኑዋቸው የሚችሉበትን መንገድ ይሻሉ ። በበኩሌ አልፈርድባቸውም ። ሠራዊቱን ግን ያዳክመታል ። ሠራዊቱም ቢሆን ያለምግብ ሊዋጋ አይችልም ። ምግብ ደግሞ የለም ። ይህንን የማው ቀው ምግብ ማቅረብ የእኔ ሥራ ስለሆነ ነው ። እትላንታን ደግመን ከያዝን ጀምሮ ላይ ታች እያልኩ ምግብ ስፈልግ ከርሜያለሁ ። ነገር ግን ድንቢጥ ወፍ የምትመገበው ምግብ ያህል እንኳ አልተገኘም ። ወደ ላቫና ሲል በስተደቡብ ለሶስት መቶ ማይል ያህል ብትሄጂ ችግሩ ያው ነው ። ሕዝቡ ተርቧል ፡ የባቡር ሐዲዶቹ ተቆራርጠዋል ። አዳዲስ ጠመንጃዎችም የሉም ። የጦር መሳሪያው ግምጃ ቤት እየተሟጠጠ ነው ። ለጫማ የሚሆን ቆዳ ከናካቴው የለም ። . . ስለዚህ አየሽ ፍፃሜው ቅርብ ነው ። "

ከተናገረው ሁሉ ለእስካርሌት ሚዛን ያነሳው ነገር የኮንፌዶሬ ሲው ተስፋ መመናመን ሳይሆን የምግብ እጥረቱ ነው ። ፖርክን ፈረስና ጋሪ አስይዛ ወደ ገጠር ልካ ምግብና ልብስ በወርቅና በዩናይትድ ስቴትስ ገንዘብ እንዲገዛ ለማድረግ እቅድ ነበራት ። ፍራ ንክ የሚለው እውነት ከሆነ ግን . . .

@OLDBOOKSPDF

ማከን እስካሁን እጠላት እጅ አልገባችም ። ማከን ውስጥ ምግብ መኖር አለበት ። የኮሚሳሪያቱ ጽ/ቤት ሲደላደል ውድ ፈረሷ በሠራዊቱ በሚጠበቅላት ሁኔታ ፖርክን ወደ ማከን ልካ ምግብ እንዲ ፈልግ ታደርገዋለች ። እንደምንም ትሞክረዋለች ።

"እሺ አቶ ኬኔዲ ፡ ዛሬ ማታ መጥፎ መጥፎ ነገሮችን ባናነሳ ጥሩ ነው" አለች ። "እንተ ሂድና እትንሿ ፡ እማማ ቢሮ ብቻህን ተቀ መጥ ። ሱዌለንን የማግኘት እድል ይኖርሃል ። "

ፍራንክ ፊቱ በደስታ በራ ። በፈገግታ ተንቦለቦለ ። ከክፍሉ ሹልክ ብሎ ሲወጣና ሲሄድ እስካርሌት ተመለከተችው ።

"አሁን ሊያገባት አለመቻሉ እንዴት የሚያሳዝን ነገር ነው ።" አለች በልቧ ። "እሷን ይዞልኝ ቢሄድኮ አንድ የምቀልበው ሆድ — ተቃለለልኝ ማለት ነበር ። "

@OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ 29

በተከታዩ ሚያዝያ ወር ፤ ያለፈ እዙ ትርፍራፊ ሥልጣን ተለ ቃቅሞ የጦር አዛዥ ሆኖ ዳግመኛ የተሾመው ጄኔራል ጀንስተን ፤ ሰሜን ካሮላይና ላይ እጁን ሰጠ ። ጦርነቱም በዚያው አከተመ ። ይሄ ወሬ ታራ የደረሰው ግን በሁለት ሳምንቱ ነው ። ታራ ውስጥ በጣም ብዙ የሚሠራ ሥራ በመኖሩ ማንም ወጣ ብሎ ልምጣ ብሎ ጊዜ የሚያጠፋ የለም ። ለሐሜት ጆሮ ያለው ከኑ የለም ። ጐረቤቶቹም ሁሉ እንደታራ ሰዎች በሥራ የተጠመዱ በመሆናቸው የመጠያየቂያ ጊዜ የለም ። በዚህ ምክንያት ምንም ዓይነት ወሬ ቢሆን የሚጓዘው በጣም ቀስ ብሎ ነው ።

የፀደይ ጊዜ ጥጥ ለቀማ እፍላ ወቅቱ ነው ። ፖርክ ከሚከን ያመጣው ጥጥና የአትክልት ዘር የሚዘራውም አሁን ነው ። ፖርክ ጋሪውን ይዞ ሄዶ ቶሚስ ፣ የዘር እህል ፣ ዳክዬዎች የአማማ ሥጋና ምግብ ይዞ ሊመለስ ነበር ። አልሆነለትም ። እየዶጋገመ ያጋጠመውን ነገር ያወራል ። እንዴት ከጠላት እያለፈ እንደተጓዘ ፣ ወደታራ ሲመለስ የቶቹን መጋቢ መንገዶችና የእግር መንገዶች እንደተጠቀመ ፣ እግር ረግጧቸው ስለማያውቅ መንገዶች ፣ ጥንት ሰው ሲሄድባቸው ስለነበሩና አሁን ስለቆሩ መንገዶችና ስለ በቅሎ መንገዶች ያወራል ። አምስት ሣምንታት ሙሉ ሊጓዝ ነበር ። እስካርሌት ደግሞ እሱ እስኪመለስ ድረስ ስትጨነቅና ስትጠበብ ከረመች ። ስለመዘግየቱም ስትበሳጭ ነበር ። ሲመለስ ግን ሁሉም ነገር ቀርቶ በሰላም በመመለሱና የሰጠችውን ገንዘብ ይዞ በመምጣቱ ቂጣውን ሁሉ ወጣ ተቀበለችው ። ይዟን ሁሉ ገንዘብ ይዞ ለመመለስ የቻለው ግዛ ያለችውን ምግብና ዳክዬዎች ሳይገዛ ቀርቶ ሊሆን እንደሚችል ተጠራጥራለች ። በየመንገዱ ጠባቂ ባለቤት የሌላቸው ዶሮዎች ሞልተው ተትረፍርፈው ገንዘቡን አውጥቶ ዳክዬ መግዛት እንደትልቅ ሐፍረት ታይቶታል ።

አሁን ታራ ውስጥ ያለው ምግብ በጣም ትንሽ በመሆኑ እያንዳንዱ ሰው ከተፈጥሮ ጋር ያለው ግንኙነት ጠንክሯል ። ለየአንዳንዱ እጅ ሥራ አለ ። ለየአንዳንዱ እጅ ከበቂ በላይ ሥራ አለ ። ለየአንዳንዱ እጅ የማያልቅ የማይዘለቅ ሥራ ተቀምጦለታል ። የዘንድሮው ጥጥ እንዲበራ ያለፈው ዓመት የተለቀመ ጥጥ በታውን መልቀቅ

@OLDBOOKSPDF

አለበት። ከእርሻ ጋር የማይተዋወቀው ልማዣ ፈረስ በማሳው ውስጥ ያለፈታዱ ይጎተታል። አራሙቻ ከየእትክልቱ ውስጥ መውጣት፣ በሩ መዘራት ፣ የማገዶ እንጨት መፈለጥ ፣ የዶሮቹ ቤት መታጠር ፣ በያንኪዎቹ የነደደው ያ ሁሉ ቋሚ ፣ ያ ሁሉ አጥር መተካት ይኖርበታል። ፖርክ ስጥንቸል ማጥመጃ ያዘጋጀው ወጥመድ በየሁለት ላምንቱ አንድ ቀን መታየት አለበት። በወንዙ ሸር ያሉት የአሳ ማከማቻዎች መታደስ አለባቸው። አልጋዎች መጠገን አለባቸው። ወለሉ መወልወል አለበት። ምጣብ መቅቀልና ሳህኖች መታጠብ ፣ አላማዎቹና ዶሮዎቹ መመገብ ፣ የተፈለፈለ እንቁላል መሰብሰብ ይኖርበታል። ላሚ መታለብና መታጎድ አለባት። ያንኪዎቹ ወይም የፍራንክ ኬኔዲ አሳሽ ሰዎች እንዳይወስዱት ውሃ ለማጠጣትም ሆነ ለሣር ግጦሽ ስትሰማራ ሰው አብሯት መኖር አለበት። ሴላው ቀርቶ ትንሹ ዋድ እንኳ ሥራና ኃላፊነት ተሰጥቶታል። በየጠዋቱ ቅርጫቱን በኩራት ይዘ ለእሳት መጫሪያ የሚሆን ጭራሮ ሊለቅም ይወጣል።

የጄኤራል ጆንስተንን እጅ መስጠት ወሬ መጀመሪያ ጠዴን ደሩ ያመጡት የፎንቴን ቤተሰብ ልጆች ነበሩ። አሌክስ እሁንም ቦት ጫማ አድርጓል። ቂኒ በብዱ እግሩ ኮርጅ በሌሳት ቅቅሎ ይጋልባል። ከዚያ ቤተሰብ ልጆች ሁሉ ደህና ደህና ነገር ማማኘት የሚችል ቂኒ ነው። አራት እመት ሙሉ ሰፀሐይና ልንፋስ ተጋልጠው በመከረማቸው ስውነታቸው ጥውልግልግ ብሏል። ከስተዋል፣ ጠቁረዋል። ጨጉጊት የመስሉት ጦር ሜዳ የከረሙ ጢሞቻቸውም መልካቸውን ስዋውጠውት የማይታወቁ ሰዎች አስመስለዋቸዋል።

አሌክስና ቂኒ ወደቤታቸው ለመድረስ ሲጣደፉ እማረ መንገዳቸውን ታራቆም ብለው ልጆቹን እንዴት ናችሁ ስማለትና የእጅ መስጠቱን ወሬ ስመንገር ብለው ነው የገቡት። ጦርነቱ ማከተሙን ፣ ሁሉ ነገር ማብቃቱንና ከአንግዲህ ስለዚህ ነገር ስማውራትም ፈቃደኛ እንዳልሆኑ ተናገሩ። እነሱ ማወቅ የሚፈልጉት ነገር ቢኖር ሚሞላ መታጠል አለመታጠሉን ነው። ከአትላንታ በስተደቡብ ወዲህ እየመጡ ሳሉ ፣ ድሮ የጓደኞቻቸው ቤቶች በንበሩባቸው ቦታዎች ላይ የጭስ ማውጫዎች መአት ቆመው ስላዩ ፣ የገዛ ራሳቸው ቤትም ይተርፋል ብለው አለመገመታቸውን ይናገራሉ። እስካርሌት ፣ ሳሲን እየጋለበች መጥታ እንደነበር ስትነግራቸው ግን እፎይ ብለው ተንፈሱ።

"እሷ ቅበጥበጥ ሴት ናት" አለ ቂኒ። "ጆ መገደሉ መቼም ለሷ ትልቅ ዕድል ነው። እስካርሌት የሚታገኝ ትምባሆ ይኖርሽ ይሆን"

@OLDBOOKSPDF

"ያለው ሱረት ብቻ ነው። ለዛውም አባባ በበቆሎ አገዳ የሚያ ጨስው ነው ።"

"አይ እስክሳስ ዝቅ አላልኩም" አለ ቶኒ "ግን ምናልባት ወደ ፊት ወያዛው መሐዴ አልቀረም ።"

"ዲሚቲ ሙንሮስ ደህና ናት ?" ብሎ ጠየቀ አሌክስ በጉጉት ግን ትንሽ በተረበሸ አንደበት ። እስካርሌት የሳሊን ታናሽ እህት ያመሟታት አንደነበር ታውቃለች ።

"እንዴታ ። አሁን ፌይትቲቪል ውስጥ ከአክስቷ ጋር ተቀምጣለች ። ሳቨጅይ ውስጥ ያለው ቤታቸው መቃጠሉን መቼም ታውቃላችሁ ። ሌሎቹ ዘመዶቿ ማነን ወስዋ ናቸው ።"

"የለም አልተግባባችሁም ። እሱ የሚልሽ እኮ ዲሚቲ ከከተማ ጠባቂዎች ማህል አንዱን ጀግና ኮንፌል አግባታለች ወይ ነው ?" አለ ቶኒ በአሽሙር ። አሌክስ በንዴት ጎላመጠው ።

"አንዴ በጭራሽ ። እሷ እቴ ! ማንንም አላገባችም" አለች እስካርሌት በመተረም ፈክ ብላ ። "እረ በጎሀንም ! ይቅርታ አርጊልኝ እስካርሌት እኔ እንኳ ልጠይቅሽ የፈለኩት ይሄን አልነበረም ። ልል የፈለኩት አንድ ወንድ የሚያገቸው ባሪያዎች ነጻ ከመውጡት በኋላ ፡ ቤት ንብረቱ ከጠፋበትና እርሱ ቢሳ ቤስቲን ሳይኖረው ሴትን እንጋባ ብሎ መጠየቅ ይችላል ወይ ? ነው ።"

"አይ ዲሚቲ እኮ ሰዚህ ሰዚህ ግድ የላትም" አለች እስካርሌት ። አሌክስ ፎንቱን ከመላጀጅ አንዱ ስላልነበረ ስለ ዲሚቲ ቅን ነገር መናገርና ለያ ታማኝ መሆን እስከዚህም እስካርሌትን አይጎ ዳትም ።

"ኧረ በጎሀንም ... እንደገና ይቅርታ አርጊልኝ ። ይህንን መሀላ ካልተመከኝ አያቴ ዘልዝላ ነው የምትሰቅለኝ ። እና ማንንም ልጄ ገረድ መናጠ ደሀ አግቢ ብዬ አልጠይቅም ። እሷን ባያስጨንቃት እንኳ እኔን ይጨንቀኛል ።"

እስካርሌት በረንዳ ተቀምጣ ከወንዶቹ ልጆች ጋር እያወራች ሳለች ሚላኒ ፡ ስዊለንና ካሪን የእጅ መስጠቱን ወሬ ሲሰሙ ነፍ ሹልክ ብለው ወደቤት ገብተዋል ። ወንዶቹ ልጆች በታራ ዓሮ በኩል በማሳዎቹ ውስጥ እያቆራረጡ ከሄዱ በኋላ ፡ እስካርሌት ወደ ቤት ስትገባ ፡ ሴቶቹ አለን ቢሮ ውስጥ ሶፋው ላይ ተቀምጠው እየተ ንሰቀሰቁ ሲያለቅሱ አገኘቻቸው ። ከእንግዲህ እነተመ ። ያ የሚወዱት ብሩህና ቆንጆ ህልም ፡ ያ ተስፋቸውን የጣሉበት ብሩህና ቆንጆ

@OLDBOOKSPDF

ህልም ፥ አበቃ ። ያ ጓደኞቻቸውንና ባሎቻቸውን ከነሱ ነጥሎ የወሰደ እላማ ፥ ያ ቤተሰቦቻቸውን ሁሉ ለድህነት አጋልጦ የሰጠ እላማ ፥ ያ እስከማዕዜኑ አይወድቅም ሕያው ነው ይሉት የነበረ እላማ እስከ ማዕዘኑ ተንኮታኩቶ ቀረ ።

እስካርሌትም ሆዬ ምንም እንባ ጠብ አላሳት ። ግና ወሬውን ስትሰማ እንዲህ ብላ አሰባ ነበር፡— እግዚሀር ምስጋና ይግባው ከእንግዲህ ላሜ አትሰርቅብኝም ፥ ፈረሴ አይጠፋብኝም ። ከእንግዲህ እያንዳንዱ ሰው ቢላዋና ሹካ ይዞ እንዲበላ ዕታዎቼን ሁሉ ከጉድጓድ አወጣለሁ ። ከእንግዲህ የሚበላ ፍለጋ በየጠፉ ያለሀሳብ መሄድ አችላለሁ ።

እንዴት ያለ እፎይታ ነው ኧል፤ ዳግመኛ የፈረስ ኩቴ በሰማች ቁጥር ሥጋት አይገባትም ። ዳግመኛ ኮሽታው ሁሉ የፈረስ ኩቴ ጨኸት ፥ የያንኪዎች የትእዛዝ ድንፋታ እየመሰላት ከእንቅልፏ እየ ባነነች ቅዠት ነው እውን? እያለች በእኩለ ሌሊት አትበረግግም ። ከሁሉ በላይ ደግሞ ታራ መዳኗ ። የመጨረሻው አስቀያሚ ሀልሟ ፥ የመ ጨረሻው አስፈሪ ቅዠቷ ከእንግዲህ እውን አይሆንም ። ከእንግ ዲህ የምትወደው ቤቷ በቃጠሎ ሲጨስና ጣራው ነበልባል በል ቶት ሲወድቅ ሜዳው ላይ ሬሣ አታከተውልም ።

አዎ አላማው ሞቷል ። ነገር ግን ምንም ቢሆን ምንም ከጦር ነት ሰላም ይሻላል ። ልእስካርሌት ጦርነት ጅልነት ነው ። ኮክብ ያረ ፈበት ባንዲራ ስንደቅ ላይ ሲሰቀል ፥ እንደሰው ቆሟ በደስታ ዐይን አይታው አታውቅም ። የሥ ዴክሲ ሙዚቃ ሲዘፈን ደግሞ እንደሰው ሰውነቷን አይወራትም ። የግል ጉዳይዋን ለመሥራት ጊዜ አላገኘ ችም ። ያ የሚያማት የነርስነት ተግባር ፥ የወረራው ስጋት ፥ ይሄ አጉል ሙጭጭ ያሉበት አላማ የሚባል ድርቀት ተሳክቶ ሳይሳካ ቤተሰቧ ላይ ባለፉት ጥቂት ወራት ያደረሰው የረሀብ መዓት ፥ ሁሉም ጠሷን ጥምቡሳሷን ይዞ ሄደ ። ተፈጸመ ። ስለዚህ የምታስቅስበት ምክንያት አይታያትም ።

ሁሉ አለፈ ያ የማያልቅ ይመስል የነበረ ጦርነት ፥ ያ ሳትፈል ግውና ሳትፈቅደው መጥቶ ሕይወቷን አሁለት ላይ የከፈለባት ጦር ነት ፥ ያ የተገናኘችበትን ሀሳብ የለሽ ሕይወት አጨልሞ በትላንት ደስታዋና በዛሬ መከራዋ ማህል ያለውን ልዩነት እንኳ እንዳታይ ጋርዷት የነበረ ጦርነት ፥ እነሆ አለፈ ። ወደኋላዋ መለስ ብላ የጥ ቷን የጠዋቷን እስካርሌት ፥ ባለአረንጓዴ የሞርኮ ሞድ ነጠላ ጫማ ታደርግ የነበረችውን እስካርሌት ፥ በሽቱ የታወደ ቀሚሷን ለብሳ ትሞናሞን የነበረችውን እስካርሌት ታስታውስና አሁን እንደዚያ መሆን ትችል እንደሆን አሰባ ይገርማታል ። እስካርሌት እሳራ እኩ የመ

@OLDBOOKSPDF

ንደራ ወንድ ሁሉ ፈጽሞ ይመስለዋል ። ከመቶ የሚቆጠሩ የምታገባ የምትነዳቸው ባሪያዎች የነበሯት ፣ የታራ ሀብት እንደማይጣጸ የከበባትና ያሻት የፈቀዳትን ለማድረግ የማይሳናቸው ደግ ወላጆች ያሏት ነበረች ። እስካርሌት ኦሃራ በጣም ከመሞላቀቋ የተነሳ ጠይቃ የማይፈጸምላት አንድም ነገር አልነበረም ። ፊልጋ ያላገኘችው አንድ ነገር ብቻ ነው—አሽሌይን ።

በአራቱ ዓመታት ውስጥ እየተጠማዘዘ በሚሄደው ረጅም መንገድ ላይ የሸቱ ቦርሳ የያዘችና የዳንስ ነጠላ ጫማ ያደረገች ትምጥል ልጃገረድ አንሸራትታት ብትወድቅ ፣ የሚዋት እንደኩል የጠሩ ሀይኖች ያሏት ፣ ሣጥቷም የምትቆጥር ፣ በርካታ ጉልበት አድቅቅ ሥራዎች የተሸከመችና በዓለም ላይ አለኝ ትለው ከነበረው ሀብት ንበረት ሁሉ የማይሞት የማይነቀል የቆመችበት ቀይ መሬት ብቻ የቀራት ፤ ትልቅ ሴትዮ ሆነች ።

እስካርሌት የሴቶቹን ልቅሶ እየሰማች አዳራሹ ውስጥ ቆማ አዕምሮዋ ያልወጣበት ዳገት ያልወረደበት ቁልቁለት አልነበረም ።

"ወደፊት ብዙ ጥጥ እንተክላለን ። ፖርክን ነገ ወደማከን እልከውና ብዙ የጥጥ ዘር እንዲገዛ እጽፍጋለሁ ። አሁን ያንኪዎች አያቃጥሉብንም ። ሠራዊታችንም አይፈልገውም ። የእግዚሀር ያለህ ! በሚቀጥለው የሰብል ወቅት የጥጥ ዋጋ ሰማይ ይነካል እኮ !"

ወደትንሿ ቢሮ ገባችና ሰፋው ላይ ተቀምጠው የሚያለቅሱትን ሴቶች ከጉዳይም ሳትጥፍ ፤ የድሕረት ጠረጴዛው ላይ ተቀምጣ ያሳት ገን ዘብ ምን ያህል የጥጥ ዘር ለመግዛት እንደሚያስችላት ታሰላ ገባች ።

"ጦርነቱ አብቅቷል" አለች በሀሳቢ ። ወዲያው አንድ ደስስ የሚል ሀሳብ መጣባትና ነበሯ ከመሳቁ የተነሳ የያዘችውን ወረቀት ጣለችው ። ጦርነቱ አብቅቷል እናም አሽሌይ — አሽሌይ በሕይወት ካለ ወደቤት ይመጣል ። ሜላኒ ስለወደቀው አላማ ስታስላስል ይህንን ጉዳይ አስታውሳው ይሆን ? ብላ አሰበች ።

"በቅርቡ ደብዳቤ እናገኛለን—አይ ደብዳቤ አይደለም ። ደብዳቤ ለማ ግኘት አንችልም ። ብቻ በቅርቡ . . . አቤት ! እንደምንም ያሳውቀናል !"

ቀናት ወደ ግምንታት ተሸጋገሩ ። ከአሽሌይ በኩል የመጣ ምንም ወሬ የለም ። በደቡብ ውስጥ ያለው የፖስታ አገልግሎት የማያስተማምን ነው ። በገጠሮቹ ከፍለሀገራትማ ከናካቴው የለም ። አልፎ አልፎ እግር የጣለው መንገደኛ ከአትላንታ ሲመጣ ከወ/ሮ ፒቲ የተላከ ደብዳቤ ይዞ ይመጣል ። አሮጊቷ እነ እስካርሌት ወደ አትላንታ እንዲሄዱና ከእሳቸው ጋር እንዲቀመጡ ደጋግመው ይማጠናሉ ። የአሽሌይ ወሬ ግን ድራሹ ጠፋ ።

* * *

@OLDBOOKSPDF

ከእጅ መስጠቱ በኋላ በእስካርሌትና በሱዌለን መሀከል ያለው የ — ፈረሱን ልጋልብ እትጋልቢም ጭቅጭቅ እየጦሳ መጥቷል ። አሁን የያንኪዎች ስጋት ስለሌለ ሱዌለን በፈረስ እየሠርኩ ጐረቤቶቹን ሁሉ ካልጠየቅሁ ትላለች ። ሌሎቹ ጐረቤቶቻቸውም እንደታሪ ጥፋት ደርሶባቸው እንደሆን ለማረጋገጥም ሆነ ለሌላ ትሂድ እንጂ አሁን ዋናው ሱዌለን ልሂድ የምትልበት ምክንያት ፤ የዱሮ ወዳጆቿንና የጥንቱን ማንኑነቷን በመናፈቋና ብቸኝነት ስላጠቃት ነው ። እስካርሌት ግን አይሞከርም ባይ ሆናለች ።ፈረሱ በጣም ሰብዙ ሥራ ይፈለጋል — ከጫካ እንጨት የሚጫነው በሱ ነው . . . የሚታረሰው በሱ ነው . . . ፖርክ ምግብ ፍለጋ የሚሄደውም በሱው ነው ። አሁድ አሁድ ደግሞ እየጋጠ እንዲያርፍ መብት ተሰጥቶታል ።

ከአምና በፊት ሱዌለን በህይወቷ ከቤቷ ርቃ መቆ ያርድ ያህል እንኳ በእግሯ ሄዳ ስለማታውቅ ይዟን አጋጣሚ በደስታ የሙጥኝ ብላ በታለች ። ስለዚህ እቤት ትቆይና እያለቀሰች እስካርሌትን ትነዘንዛ ታለች ። እየደጋገመችም "ወይኔ እናቴ በኖረች !" ትላለች ። ይህን ስትላት እስካርሌት ተናዳ እበከዛሬ በጥፊ እንዳልልሽ እያለች ትዘት ባት የነበረውን ጥፊ ሁሉ አንድ ላይ አሥራ አንዴ ብትመረግት ባት እየጮኸች አልጋ ላይ ተዘረረች ። በቤቱም ትልቅ ግርግር ተፈጠረ ። ከዚያን ጊዜ ወዲህ እስካርሌት ፊት ሱዌለን ተነጫንጫ አታውቅም ።

እስካርሌት ፈረሱ እንዲያርፍ አፈለጋለሁ ስትል ከልቧ ነው ። ሆኖም በግማሽ ልቧ ነው ። ሌላኛው የልቧ ግማሽ የሚያስበው ነገር አለ ። አንድ ጊዜ ጦርነቱ ባቆመ በመጀመሪያው ወር ላይ በመንደሩ ዞራ ሰዉን ስትጠይቅ የዱሮ ጓደኞቿንና የዱሮ እርሻዎችን በማየቷ ድፍረቷን ከፉኛ ቀስቅሰባት ነበር ።

ዕድሜ ለሳሲ ብርቱ ጥረት ፤ ፎንቴኖች ከሁሉም የተሻለ ይኖራሉ ። ሆኖም ከሌላው የጐረቤት ሰው ጉስቁልናና ድህነት እንባር እንኚ እስከዚህም ትልቅ ኑሮ ይኖራሉ ማለት አይደለም ። አያት ፎንቴን ቤቱን ከቃጠሎ ለማዳን ወዲህ ወዲያ በሚባልበት ጊዜ የጀመራቸው የልብ ድካም አሁንም ሙሉ በሙሉ አለቀቃቸውም ። ሽማግሌው ዶክተር ፎንቴን የተቆረጠ እግሩ ገና በማገገም ላይ ነው ። እሌ ከሰና ቶኒ እጆቻቸው ለእርሻም ሆነ ለቁሩፎ እርፍ አልጨብጥ ፤ ዶማ አልይዝ ብለዋቸዋል ። እስካርሌት ልትጠይቃቸው ስትመጣ የእጥሩን ሽቦ ተደግፈው ጨበጣትና በቆሽሸሽ ደጋን እግር ጋሪዋ ሳቁባት ። ሆኖም ፀይኖቻቸው ውስጥ ሲስቁባት እንኳ ምሬት ይነበባል ። በሷ

@OLDBOOKSPDF

መሰቅ በራሳቸውም ላይ ምሰሶ ነዋሪ የሆኑ ዘር እንደምትፈልግ ንግራቸው እንደሚያንጉ ቃል ከገቡላት በኋላ ውይይታቸው በእርሻ ችግሮች ላይ አተኮረ ። አሥራ ሁለት ዶሮዎች ፣ ሁለት ላሞች ፣ አም ስት አሳሞችና ከጦርነት የተመለሱባት በቅሎ ነበሩዋቸው ። አንዱ አሳማ በቅርቡ ሞተባቸው ። ሴሎቹም ይሞቱብናል ብለው እየሰጉ ነው ።እስክርሌት እንዚህ ዕድሜ ያለፈበት ከረሜላ ላሽ ትውልድ አባ ላት ሆትኛው ክራባት ከዘመኑ ጋር ይሄዳል እያሉ ከማማረጥ በቀር ለህይወት ደንታ የሌላቸው ወጣቶች መሆናቸው ቀርቶ ፣ እንዲህ ያሉ ስለእርሻና ስለዶሮ ቁጥር የሚጨነቁ ሰዎች ሆነው ስታያቸው ፣ ዓረ ማትና ሳቀች — ሆኖም የእብም ሳቅ እንደነሱው መራራ ሳቅ ነበር ።

ሁሉም የሚሞሳ ሰዎች ሞቅ ያለ አቀባበል አደረጉላት ።ለዘር የሚሆነውንም በቆሎ ያለክፍያ ካልሰጠንሽ ብለው ድርቅ አሉባት። የበቆሎውን ከፍያ ጠረጴዛው ላይ ቁጭ ስታደርግላቸው ቁጡዎቹ የፎንቴን ቤተሰቦች ዙሟ አሉና በሞራሽ እንቀበልም አሏት ።እስክርሌት በቆሎውን ወስዶችና ዶላሩን ቀሰ ብላ በምሥጢር ሳሊ እጅ ውስጥ አስቀመጠችው ። ይሄ የዛሬዋ ሳሊ ፣ እስክርሌት የዛሬ ሰምንት ወር ቃራ ስትገባ የተቀበለቻትን ሳለ አትመስልም ። ያኔ የተከፋችና የጠቆረች ሴት ትሁን እንጂ ተስፋ ውስጧ ይፍለቀለቅ ነበር ። ዛሬ የእጅ መስጠቱና የጦርነቱ ፍፃሜ ተስፋዋን ሁሉ አሟጦ የወሰደባት ይመ ስል እና ቀርቃለች ።

"እስክርሌት" እሰኙ ዓንዘቡን በእጅዋ እየጨበጠች "የዚያ ሁሉ ድክማችን ዋጋ ምንድን ነው ፣ ከቦውንም ለምን ተዋጋን ? ወይኔ የኔው ጀነ ወይ ምስኪን ልጄ"

"በበኩሌ ሰምን እንደተዋጋንም አይገባኝም ፣ ደሞም ግድ የለ ኝም" አለች እስክርሌት ።" ምንም አይጥመኝም አልፈልገውም ። ዱሮም አይጥመኝም ፣ አልፈልገውም ነበር ። ጦርነት የወንዶች ጉዳይ እንጂ የሴ ቶች አይደለም ። አሁን እኔ የምፈልገው ጥሩ ጥሞ ማምረት ብቻ ነው ። በይ አሁን ይሄንን ዶላር ውሰጂና ለልጅሽ ለትንሹ ጆ ጥብቆ ግዢ ለት ። እግዚሃር በሚያውቀው ልብስ በጣም ያስፈልገዋል ። ምንም አሌክስና ቶኒ ትህትና ቢያበዙ በቆሏችሁን መገረፍ አይገባኝም ።" ወንዶቹ ልጆች እጋሪዋ ድረስ ሸኟት ። ምንም ቢሆን እነ ዚህ የፎንቴን ዘሮች የደስ ደስና ፍልቅልቅታ አልተለያቸውም ። እስክርሌት ከሚሞሳ ጋሪዋን አንቀሳቅሳ ጉዞ ስትጀምር የእነ ዚያ የፎንቴን ቤተሰቦች የችግር ማጥ ስዕል ወይኗ ላይ መጣባት ። መቼም መከራና ችጋር እንደደከማት ነገር ምንም ደክሚት አያው ቅም ። ከዕለታት አንድ ቀን በጣም ሀብታም የነበሩና አሁን የሚቅ

@OLDBOOKSPDF
ጥለው ምሳ እንኳ ከየት እንደሚመጣ ባለማወቃቸው ትንሽም ጭን ቀት የማይሰማቸውን ሰዎች ማወቅ እንዴት መታደል ነው በሉ!

እስካርሌት ወደ ፓይን ብሉም መጥታ ካድ ካልቨርትን እቤት አገኝ ችው። በደጉ፣ በዓለም በሲሳዩ ጊዜ ትደንስበት ወደ ነበረው አሮጌ ቤት ለመግባት ደረጃውን ስትወጣ ካድ ካልቨርት ፀይሮች ውስጥ ሞት አረብቦ አየች። በአግዳሚ ወንበር ላይ ጋለል ብሎ እያሳለው ፀሐይ ይሞቃል። የአንገት ልብስ ብጤ ጉልበቱ ላይ ጣል አድርጓል። ያም ሆኖ ገና ሲያያት ፊቱ ፈካ። ሰላም ሲላት እየተነሳ ትንሽ ብርድ ወደደረቱ ላይ እንደመታችው ነገራት። ዝናብ ውስጥ ብዙ ከመተኛት የተነሳ የመጣበት ጣጣ ነው። ቶሎ እንደሚሻለውና ሥራ ለመሥራት እጁን እንደሚያነሳ አስረዳት።

ካትሊን ካልቨርት ድምጽ ሰምታ ከቤት ወጣች። ከካድ ራስ በላይ የቢ ፀይንና የእስካርሌት ፀይን ተጋጩ። ፀይኖቿ ውስጥ ዕውቀትና መራራ ተስፋ መቁረጥ ይንሳፈፋል። ካድ አይወቅ እንጂ ካት ሊን በደምብ ታውቃለች። የፓይን ብሉም መንደር ዳሞ ውጦታል፣ አራሙቻ ወርሶታል። የፓይን ተክሰኞች ግቢው ውስጥ እያቆጠቆጡ ነው። ቤቱ ቁሽሽሽ ብሏል። ጣር እንደያዘው ሰው የሚያቃስት ይመስላል። ካትሊን ቁጭንና እንደ ጅማት ጥንከር፣ ከርር ያለች ናት።

ካትሊንና ካድ ከያንኪዋ እንጀራ እናታቸው፣ ባከስት ብቻ ከሚገኙ ጀቸው አራት እህቶቻቸውና ከያንኪው ምስለኔ ከሒልተን ጋር፣ ማሚ ቶውን በሚያስተጋባው ትልቅ ቤት ውስጥ ይኖራሉ። እስካርሌት የታራው ምስለኔ ጆናስ ዊልከርሰንን እንደማትወደው ሁሉ ሒልተንን ም አትወደውም። አሁን ጊዜ ጥሏት እሱ እንኳ ባትሙ እንደ እኩያ መጥቶ ሲጨብጣትማ የባሰ ጠላችው። ዱሮ ዱሮ እንኳ ዊልከርሰን ያለውን ዓይነት የታሣሹነት ስሜት ይሰማው ነበር። አሁን አቶ ካልቨትና አቶ ሬፎርድ ጦርነት ሄደው ከሞቱና ካድም ታሞ አልጋ ላይ ከዋለ በኋላ ታዛዥነቱም ትህትናውም ቀርቷል። እንጀራ እናትየዋ ወ/ሮ ካልቨርት ለራሷ የኔግሮ አሽከሮች እንኳ እን ዲያከብሯት ለማድረግ አልቻለች፣ አክብሮትን በጭራሽ አታገኘውም።

ሒልተን በጣም ደግ ሰው በመሆኑ በአስቸጋሪ ጊዜ ሁሉ አብ ሮን ከረመ" አለች ወ/ሮ ካልቨርት ነደድ ብሏት፣ ዝም ወዳለችው የእንጀራ ልጅዋ ፈጠን ብላ እያየች "በጣም ደግ፣ የደግ መጨረሻ ነው። ሼርማን የመጣ ጊዜ ሁለቴም እንዴት ቤታችንን እንዳዳነ ሳትሰሚ አልቀረሽም መቼስ። እሱ ባይኖር ኖሮ እንዴት እንሆን እንደነበር አላውቅም። ምንም ግንዘብ ሳይኖረንና ካድ..."

@OLDBOOKSPDF

በካድ ቀዩ ፊት ላይ አንጸባች ብርሃን ተማ አለ ። ካትሊን አፏ ድርቅ እስኪል ድረስ ቅንድቦቿ ተሸበሸቡ ። እንዚህ ሁለት ልጆች በምስለ አው ሥር ብመሆናቸው መስጣቸው የሚነድደው ንዴት ለእስካርሌት ተለምቷታል ። መይበሮ ክልኽርት ለማልቀስ የተዘጋጀች ትመስላለች ። መቼም አንድ ጥፋት አጥፍታለች ። ሁልጊዜም እንጸጠፋች ናት ። ምንም ጀርኽያ ሙሰጥ ገፃ ዓመት የኖረች ብትሆን እንዚህን ደቡላ ውያን ለመረዳት አልቻለችም ። ለእንጀራ ልጆቿ ምን መነገር ምን አስመናገር ፣ ምን ማለት ምን አለማለት እንጸለባት ለሚወቅ አልቻለችም ። ያለቻቸውን ሁሉ እሺ ብለው በትህትና ስለሚቀበሉ ግራ ይገባታል ። እንዚህን ግትርና ልዘቸው የማይታወቅ ግሽንኩ ህጌለች እዚሁ ቅቃ ፣ ልጆቿ ይባ ወጥቷ መባለብት ወደጨዌን ለመጼድ ሁል ጊዜ ትከታለች ። ትምላለች ፣ ትገዘታለች ።

ከዚህ ዘመድ ጥያቃ ሥጥሎ አስካርሌት ወደታርሌቶን ቤተሰብ ለመሄድ ፍላጭቷ አልተነሳሳም ። አራቱ ወንድማማቾች ሄደው ቀርተዋል ። ቤታቸው ተታጥሏል ። ቤተሰቡ ወርዶ ተዋርዶ ምስለኔው ጎጆ ውስጥ ተቸራምቷል ። መጀዚህ ቤት ለመሄድ ልሂ እምቢ አሳት ። ስሜለንና ክሪን ሚን ሌሉ ሚ ቢሉምኳትና ሜሳኒም አቶ ታርሌቶንን ኩመር ሚደ እንኪህ ደህና መጣህ አለማለት ጉረቤት በጉረቤት ላይ የሚፈጽመው ድርጊት አይደለም እያለች ስለወተወቱኞት ፣ አንድ እሑድ ተሰብሰበው ሄዱ ።

ይሄንው ደግሞ ከእስክዛፊው ሁሉ እጅግ የከፉ ፣ እጅግ የመ ረረ ሆነ ። በቤቱ ጥርስራሽ ጥሎ ጥሎ ሲሄዱ ፣ ቤትሪስ ታርሌቶን ብዙድ ሥር አለንጋ ይህ ያተቀጸጸደ የሚለቢያ ልብስ ለብሳ ፣ ከፈረሱ ጋማ አጠገብ ክለው አሞር እሳይኛው ገበ ላይ ተቀምጣ አዩዋት ። እይኗ ጉፉድ በተዘረጋው ባዶ ቦታ ላይ ፈጣል ። ግን አታይም ። ከጉሩ ፈረ ሶቿን የሚያስለዋንላት ትንሹ ጁጋን እማር ኔማሮ ፣ እንደእመቤቱ ፊቱን ጥቁርሽ አስመስሎ ቁጥጠ ብሏል ። የፈረሱ ጋማ በሚበርቁ የፈ ረስ ግልገሎችና የተዳቀሉ በቅሎዎች እንጸልሞሉ ሁሉ ዛሬ ከአንዲት በቅሎ በስተቀር ምንም የፈረስ ዘር አይታይበትም ። ይኽውም በቅሎ ብትሆን ከእጅ መስጠቱ በኋላ አቶ ታርሌቶን ይዟት የተመለሰው ናት ። "የምወጻቸው ሁሉ ከሄዱብኝ በኋላ ምን እንደማደርግ እንኳን አላ ውቅም" ።አለች ወ/ሮ ታርሌቶን ከአጥሩ ላይ ዱብ ብላ ስትወርድ ። መቼም የማያውታት ሰው የምወጻቸው ሁሉ ከሄዱብኝ ስትል ኦራሁን ጠር ሚዳ ሄደው የሞቱባትን ልጆቿን ይመስለው ይሆናል ። የታራ ዎቹ ቤቶች ግን ውድ ፈረሶቿን ማለቷ እንደሆነ ገብቷቸዋል ። "ቆንጆዎቹ ፈረሶቼ ሁሉ ሞቱብኝ ወይኔ ፣ ደሞ የምስክኗ አለ. ነገርነ ኔሲ በኖረችልኝ እንዴት ጥሩ ንበርነ አሁን በሷ ቦታ ካንድ ከተረገመች በቅሎ

@OLDBOOKSPDF

በቀር ምንም የለም ። የተረገመች በቅሉ'' አለች ። ''የተረገመች በቅሉ'' አለች ደግመችና ወደ ገጣባዋ በቅሎ እያየች ። ''መቺም ለኔ የጨዋ ዘር ፈረሶች ፤ በቅሎ ጋጣቸው ውስጥ በመግባቷ የሚሰማቸውን ስሜት ሳያዘንና እንሱም ቢኖሩ ኖሮ ተሰደብን ብለው እንደሚቆዘጠበው ሰጩን ይጨንቀኛል ። በቅሎዎች ያለግባቡ የተፈጠሩ በመሆናቸው እንሱን ማርባት ደግ አይደለም ።''

ጂሚ ታርሌተን ጥፍግ ባለው ጢሙ ተጀቡኖና ሲላ ሰው ምስሎ ሌቶቹን ለመሳምና እንዴት ናችሁ ለማለት ከምስለኔው ቤት ብቅ አለ ። የተደራረቱ ቀሚስ የለበሱት አራቱ ቀያይ ፀጉር ያላቸው ሴት ልጆቹ ከጀርባው በሰልፍ ወጡ ። ጥቁርና ቡናማዎቹ አጸፋቸው ውሾች እየጮሁ እንግዳ ድምጽ መጾሰመበት በር ሮጡ ። በቤተሰቡ ላይ የተጠናና በቆራጥነት የተወሰነ የደስተኛነት ስሜት ይታያል ። ከሚጥ ሳው መራራ ገጽታም ሆነ ከፓይን ብሉሙ ጭት የተመነው አየር ይልቅ ፣ ይሄኛው ቀለል ያለ ትዝታዘን እስከርሌት ላይ ፈጥሮባታል ።

የታርሌተን ቤተሰቦች በሞኑን ምንም እንግዳ መጥቶባቸው ስለማ ያውቅ እኑ እስክርሌትን እንዲያዩና አራት እንዲበሉ አጥብቀው ጠየ ቋቸው ። በዘውም አዲስ ወሬ እንዲነግሯቸው ፈልገዋል ። እስካር ሌት አካባቢው በጣም ስላፈናትና ስለተጨማሩናት መቆየቱን አልፈለ ገችውም ። ሚለኒና ሁለቱ የእስካርሌት እህቶች ግን ረሽም ጊዜ ለመ ቆየት በመፈለጋቸው አራቱም ለአራት ቆዩ ። የቀረበላቸውን የጐድን ቢጋና የደረቅ አተር ብዙም ሳያባክኑ ተመገቡ ።

ስለንዘብ እጦት ተወራ ። ተሳቀ ። የታርሌተን ሴቶች ልጆች ቀሚስ የሚለብሱት ተራ ጉበቱው መሆኑን እያወጉ የሚያስቅ ቀልድ እንደተናገሩ ሁሉ በሙሉ ሳቁ ። ሚለኒም እንሱ ላይ ተጨማሪ ነገር በማከል የታራን ችግር ቀለል አድርጋ በክፉው ጊዜ ያደረገችውን መከ ራዎች ሁሉ ተናገረች ። እስካርሌት በሜላኒ ግልጽ ንግግር ተገረመች ። በሷ በኩል ግን ምንም ነገር መናገር አልቻለችም ። እንዚያ አራቱ የታርሌተን ወንዶች ልጆች በመዝናናት የሚንጐራደዱበትና የሚሉፉ በት ቤት እሁን አና ይመስላል ። ለሷ አና ከመሰላት ብጐረቤቶቻ ቸው ሞቅ ያለ ፈገግታ ሲመጣቡ ለቆዩት ለታርሌተኖችስ ምን ይመስል ይሆን ?

ካሪን በምግብ ሰዓት የተናገረችው በጣም ጥቂት ነው ። ራቱ አልቆ ገበታው ከፍ ሲል ግን ሽተት ብላ ሄዳ ወ/ሮ ታርሌተን ጉን ተቀመ ጠችና አንድ ነገር ሹክ አለቻት ። ወ/ሮ ታርሌተን ፊቷ ተለወጠ ። ከንፈሮቿ ላይ የነበረው ፈገግታ ደበዘዘና ጠፋ ። ከንዲን ካሪን ቀሞን ወገብ ላይ ጠመጠመችው ። ከፍሉን ለቀው ወጡ ። ቤቱ ውስጥ

@OLDBOOKSPDF

ላንድ ደቂቃ መቃወም ፣ አቶን ይዘንጋል ብላ ያሰበችው እስካርሌትም ተክትላቸው ወጣች ። ጠባቡን መንገድ ይዘው ፣ በአትክልቱ አጽዕጠው ቁልቁል ሲሄዱ እስካርሌት አዩታ ፣ ወደመቃብር ቦታ እንደሚሄዱ ገባት ። ከአንግዲህ ወዲ ቤት ተመልሳ መሄድ አትችል ነገር ፣ በጣም ብልግና ይሆንባታል ። ወ/ሮ ቢትሪስ ታርሌተን ጠንክራ ለመታገሉ በምትኮራርበት ዓሁኑ ሰዓት ይቺ ካሪን ፣ ታርሌተን ወደ ወንዶቹ ልጅ መቃብር ይዛት መሄዷ ምን ይባላል ?

በእርሠ ሊሳናስ ዛፎች ሥር በቀይ ሸክላ የታጠሩ ፣ በጣም አዲስ ከመሆናቸው የተነሳ ዝናብ ቀይ አፈር ያላለናጠቃቸው ፣ ሁለት የአዲ ነበረድ መቃብሮች አሉ ።

"ያለፈው ማምሻት ነው ያገኘናቸው" አለች ወ/ሮ ታርሌተን በኩራት ። "አቶ ታርሌተን ወደማክን ጄዶ በጋሪ ሞኖ ያመጣቸው ናቸው ።"

የመቃብር ድንጋዮችን አቢት የጥጋቸው ብዛትና እስካርሌት በመ ጀመሪያ ለታርሌተን ልጆች ተስምታት የነበረው ሐዘን አሁን በድ ንገት ቀነሰባት ። እንዲህ ምግብ እንደጉድ ተወዶ ፣ ክሳውራቹም ለማ ግኘት አስቸጋሪ በሆነበት ጊዜ ፣ ለመቃብር ድንጋይ ይሄን ያህል ውድ ገንዘብ የሚያወጣ ማንም ሰው በፍጹም ሊታዘንለት አይገባም ። ደሞኮ በየአንዳንዱ ድንጋይ ላይ የጥቀረጸ መስመር አለበት ። ብዙ በተቀረጸ ቁጥር ብዙ ብር ያስወጣል ። ቤተሰቡ በሙሉ አብዷል ማለት ነው፤ የሶስቱን ልጆች እስከሬን እዚህ ድረስ ለማምጣትም ቢሆን እኮ ብር ያስፈልጋል ። ቦይድን ግን እስካሁን አላገኙትም ። ምንም ጥሜ አልታየም ።

በብሬንት እና በስቱዋርት መቃብር ማህል እንዲህ የሚል ፅሁፍ አለ . . "በህይወታቸው ሳሉ ተወዳጅና የደስ ደስ ያላቸው ንበሩ ፣ ሞትም ቢሆን አልለያያቸውም ።" በሌላው ድንጋይ ላይ የቦይድ እና የቶም ስም ተፅፏል ። ከጐኑ በላቲን ቃላት የሚጀምር ዓረፍተ ንገር አለ "ደልሴ . . ." ። እስካርሌት ግን ላቲን በፈትቪል አካዳሚ የተወችው በመሆኑ ምንም አልገባትም ። ወይ ጉድ ! ይሄ ሁሉ ገንዘብ በመቃብር ድንጋይ ላይ ይፍሰስ! እንዴ! በጣም ጅሎች ናቸው ። የራሷ ገንዘብ እንደባከነ ሁሉ ነደዳት ።

የካሪን ዐይን ያለወትሮው ያንፀባርቃል ።

"በጣም ቆንጆ ይመስለኛል" አለች በሹክሹክታ ወደመጀመሪ ያው ድንጋይ እያመለከተች ። ካሪን የምትወድደው ዓይነት ነው ።

@OLDBOOKSPDF

እንዲህ ያለ ነገር ስሜቷን በቀላሉ ይቀሰቅሰዋል "እምን" አለች ወ/ሮ ታርሌተን ። ድምጿ ለስላሳ ነው ።

"ይሄ ይስማማቸዋል ብለን አሰብን ። የሞቱት ከሞላ ጐደል በተመ ሳሳይ ጊዜ ነው ። በመጀመሪያ አስቱዋርት ሞተ ። ቀጥሎ ይዞት የነበረ ውን ባንዲራ እንደጨበጠ የሞተው ብሬንት ነው ።"

ሴቶቹ ተሰናብተው ወደ ታራ እየተመለሱ ሳሉ ፡ እስክርሌት ዐጥ ብሳ ለአንድ አፍታ በተለያዩት ቤቶች ያየችውን ሁሉ ታሰላስል ነበር ። ሳትፈቅድ ታሳቢ ወደጥንቱ የዝንጉነታቸው ዘመን ወሰዳት ። በትላልቆቹ ቤቶች ሁሉ ጠያቂዎች ጠዎ የሚሉበት ፡ ብር እንዳፈር የነበረበት ፡ እማሮዎች ቤት ውጪውን ያጣበቡበት ፡ መቅቱን ጠብቆ የትዘራ ጥዋ የቱንጣለለበት እርሻ ኮርቡ የሚታይበት ፡ የጥንቱ ጊዜ ትዝ አላት ።

"በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ፡ በአዚህ አርሻዎች ላይ በጣም ጥቂት የክክ ዛፍ ብቻ ይታያል ።" ብዙ አሰባ ሁሪያውን ጥቅጥቅ ያለውን ጫካ አይታ ሰውነቷን ወረራት ። "ባሪያዎቹ ከሌሉ ነብስና ስጋችንን ለማቆየት ልናደርግ የምንችለው ይህንኑ ብቻ ነው ። ማንም ያለባሪያ ሰፊ አርሻ ላይ ጥጥ መትከል አይችልም ። አብዛኞቹ አርሻዎችም ሊታረሙ ሊኮተኩቱ አይችሉም ። ጫካው እንደገና አርሻዎችን ይው ጣቸዋል ። ማንም ብዙ ጥጥ መትከል አይችልም ። ታዲያ ምን ብናደ ርግ ይሻላል ፤ የገጠሩ ህዝብስ ምን ይውጠዋል ፤ የኩሊው ሰው መቼም እንደሆነ ይሆናል ። አስካሄራ አንደምንም ሲወጣው ቆይቷል ። እኛ የገጠሮቹ ሰዎች ግን መቶ ዓመት የኋሊት ሄደን እንደጥንት አባ ቶቻችን በትንሽ ጐጆ እየኖርን ፡ ጥቂት ሁዳድ ጫር ጫር እያደረግን ከእጅ መደልቱ የሆነ ኑሮ ብቻ መኖር ሊኖርብን ነው ።"

"የለም፡ . . ." አለች በታሳቢ ፡ ፍርጥም ብላ ። "ታራ እንደዚያ መሆን የለባትም ። እኔም አራሲ ማረስ የሚገባኝ ከሆነ አርሳለሁ እንጂ ታራ እንደዚያ መሆን የለባትም ።" ይሄ መንደር ፡ ይሄ ሰበካ ፡ ይሄ ደፍን አገር ቢሻው ወደኋላ ተመልሶ የጫካ ኑሮ ይጀምር ፡ ታራን ግን በጭ ራሽ ወደኋላ እንድትሄድ አላስደርጋትም ።ደሞም ግንዘቤን እመቃብር ድንጋይ ላይ በከንቱ አላፈሰም ። ጊዜዬንም ስለሞተ ጦርነት በማል ቀስ አላባክነውም ። እንደ ምንም ልናስተካክለው እንችላለን ። ወን ዶቹ በሙሉ ሞተው ባይሆን ኖሮ ልናስተካክለው እንችል እንደነበር አውቃለሁኝ ። ባሪያዎችን ማጣታችን የነገሩ በጣም የከፋ ገፅ አይ ደለም ። ወንዶቹን — ወጣቶቹን ወንዶች ማጣታችን ነው ጐጂው ነገር ። "እንደገና ስለአራቱ የታርሌተን ልጆች ፡ ስለፎርድ ካለቨርትና ስለሙንሮ ወንድማማቾች ልጆች ፡ እንዲሁም ከፈትቪልና ከጀንስቦሮ

@OLDBOOKSPDF

የመጡትንና ስማቸውን በአጠገቡ ሆኖ ከፍተኛ ዝርዝር ላይ ያየችውን ወጣቶች በሙሉ አስታወሰቻቸው። "ብዙ ወንዶች ተርፈው ቢሆን ኖሮ እንደም ነም ልንወጣው እንችል ነበር . . ነገር ግን . . "

ሌላ ታሳብ ራሷን መታት — አሁን እንደገና ለማግባት ብትፈልግስ። በእርግጥ እንደገና ለማግባት አትፈልግም። አንድ ጊዜ ማግባት ያለጥ ርጥር በቂዋ ነው። በዛ ላይ ላግባ እንኳ ብትል የምትፈልገው አንድ ሰው አሽሌይ ብቻ ነው። እሱ ደግሞ ገና በሕይወት ቢኖር እንኳ ሌላ ሴት አግብቷል። ግን እንደው ለነገሩ ማግባት ብትፈልግስ። ማን ሊያገባት ይችላል ? ማን አለ ? ታሳቡ የሚያስፈራም የሚያስዘፋም ነው።

"ሜሊ" አለች። "አሁን የደቡቡ ልጃገረዶች ምን ሊውጣቸው ነው ?"

"ምን ማለትሽ ነው ?"

"አሁን ያልኩሽን ነኖ። እንደው ምን ይውጣቸው ፥ ምን ይሆኑ ይሆን ! ማንም የሚያገባቸው አይኖርም። መቼም ሜሊ ፥ ወጣቶቹ ወንዶች ሁሉ ሞተዋልና በቪ የሚቆጠሩ የደቡብ ልጃገረዶች ሲጣ ቸውን አያረኟ መምታቸው ነው።"

"እናም ምንም ልጆች አይኖራቸውም" ብላ ጨመረችበት ሚላኒ ፥ ለሷ ዋናው ቁም ነገር ይሄው የልጅ ጉዳይ በመሆኑ። መቼም ያለጥር ጥር ይሄ ታሳብ ከጎላ ስተቀመጠችው ለሱዌለን አዲስ አይደለምና ወዲያው ማልቀስ ጀመረች። ከጥ በዓል ወዲህ ፍራንክ ኪኦዲ ምንም መልዕክት ልከባት አያውቅም። ለዚህ ምክንያቱ የፖስታ አገልግ ሎት ማነስ ይሁን ወይም ስወረት ብቻ ከሷ ጋር ሆይ ሆይ ብሎ አሁን እረስቷት እንደሆን የምታውቀው ነገር የለም። ወይም እኩ በጦርነቱ የመጨረሻ ቀናት ሠስጥ ተገድሎም ሊሆን ይችላል። መቼም ረስቷት ከሚቀር ይሄ የመጨረሻው እማራጭ እውነት ቢሆን ይሻላታል። ቢያ ንስ በያንስ እንኳሪንና እን ኢንዲያ እንዳታጠማቸው ሁሉ ፍቅረኛዋ ቢሞትባት ትመርጣለች። የእርጭ መክዳት ግን የሞት ሞት ነው።

"አጭ ! እረ በእግዚሃር ዝም በይ !" አለች እስካርሌት።

"እ ! እንቺማ አውሪ ምን አለብሽ" አለች ሱዌለን በስቅስቅታ "ስላገባሽና ስለወለድሽ ነው። አንድ ሰው ይፈልግሽ እንደነበር ማንም ያውቃል። እኔ ግን . . . እስቲ ተመልከቺኝ ! እናም እንደዚህ ስድ ሆነሽ ራሴን ለመርዳት ባልቻልኩበት ባሁኑ ሰአት ! ቆሞ ቀር ሆነሽ መቺ ትይኝ ! ቆይ ግደለም ብቻ ! እንቺ እኮ በጣም አስጠሊ ነሽ" "እጭ ዝም በይ ባክሽ! ሁልጊዜ አፋቸውን የሚከፍቱ ሰዎች እን ዴት እንደሚያስጠሉኝ ታውቂያለሽ። ሽማግሌው ባለዝንጅብል

@OLDBOOKSPDF

ጠም ለመዳን እንዳልሞተ እንደሆን አሰምረሽ ታውቂያለሽ ። ተመልሰ መዋጭ ያገኛሻል ። ከዚህ የተሻለ ቁም ነገር ለሚሰብ እንደሆን አይችል ። በዘነጌ ግን አሁን ከናንተ ሥጋ ብቀር ይሻልኛል ።"

ይህችን ነገር ከጋፊው የሷለ መቅመሷን የሚመጣ ድምፅ ጠፋ ። ካሪን ቧምነ በቀር ዝምታብ ሰቹልን አጠገብ አትኮር አገኟ በደመነብበ ጀር በሶን ሙን ሙም እያደረገች ታዕናናታለች ። ካሪን በኃላብ የለስት አመት መግቢድ ተጣባ ብሬንት ታርኬትን ከገኟ ቁጭ ብሎ ታየዋ ለች ። በይሳሂ ውስዋ አንዶዋም የሚንድ ብርሃንና የመንፈስ መንሳ ሳት ይታያል ።

"ቁ" አለች ሚለኒ በዘዘን "እነዘዚያን የመላሳሉ ውንጀ ቁንጀ ሕጀች አጥቶ ደቡቡ ምን ይመክል ይሆን? አንቲ በሕይወት ቢኖሩስ ምን ይመስል ነበር ነመቹም የነሱን ድጥረት ፣ የነሱን ጉስበትና የንሱን ጭን ቅሳት ስመለከም መቻል አለብን ። እስኳርሌት ፣ እኛ ባለ ሕጀ የሆን ነው ሲቆኝ ፣ ለጀጋችን የሚስ ወንዶቻችንን በታ እንዲቀቡ ፣ የሙቱ ወንዶቻችንን ጀግንነት እንዲመርሱ ማድረግ አለብኝ ።"

"እንዳሉ ያሉ ወንዶች ዳግመኛ አይፈጠሩም" አለች ካሪን ለስለስ ብላ "ማንም የነሱን የታ ለመሞላት አያሞክለውም ።"

ከዚህ ወዲያ የቀራቸውን የቢታቸውን ሠማንሥ ፀጥ ብለው ዘለቁ ።

* * *

ይህ ከሆነ ብዙም ላይቆይ ፣ አንድ ቀን ጀንበር ልትጠልቅ ግድም ፣ ከትሊን ካልበርት አየጋለበች ወደታራ መጣች ። ከርቻቀን የሚነችባት በቅሎ እስካርሌት በሕይወቷ አይታ በማታውቀው ሁኔታ ከበቅሎ ነት ገዳና የወጣች አሳዛኝ ነገር ናት ። ጀርዋ እንዶ ጠወለገ ቅጠል የተጨራመተ ፣ አንከሳ ጥጥረት ናት ። ከትሊንም እንደተቀመጠች ባት በቅሎ አሳዛኝ ሆናለች ። ቀሚሷ የቤት ሠራተኞች እንኳ የሚለ ብሱት ዓይነት አይደለም ። ተበሳስቷል ። የፀሐይ ባርሜጣዋ አገፍ ላይ ባሰረችው ሲባጉ እራሷ ላይ ሊቀይ የቻለ የተቀዳደደ ቡቱቶ ሆኗል ። ግቢ ውስጥ ጉበታ እስከሬት ሰፊቱ በረንዳ እየጋለበች ተጠ ግታ ፣ ከበቅሎዋ ሳትወርድ እዚያው ቤተቀመጠችበት ቀረች ። የምት ጠልቀዋን ጀምበር ውበት በረንዳ ቁጭ ብለው ያደንቁ የነበሩት ሜላኒ እና እስካርሌት ፣ሊቀበሏት ደረጃውን መውረድ ጀመሩ ። የካትሊን ፊት እስካርሌት ልትጠይቃቸው ሄዳ ያየችውን የካድን ፊት መስሏል — የበለዘ ቀይ ፣ ጠጣርና ከአጥንቱ የተላቀቀ ቆዳ የተንከረፈፈበት ። ብትናገር ፊቷ ስንጥቅጥቅ ብሎ የሚረግፍ ይመስላል ። ያም ሆኖ ጀር ባዋ ቀጥ ፣ ጭንቅላቷም ከፍ ብሎ ሰላም ልትላቸው ቆማለች ።

@OLDBOOKSPDF

እስካርሌት የዊክስ ቤተሰብ ግብዣ ጊዜ እፏ እና ካትሊን አብረው ሆነው ስለሬት በትለር ያንቦካሹክ እንደነበር ትዝ አላት ። አቤት የዛን እለት ካትሊን እንዴት ቆንጆ ነበረች ! ባለወፍራም ጠርዝ ሰማያዊ ስስ ቀሚሷ ሰብሳ የሚያማምሩ ሮዝ አበቦች ያሉበት መቀነትና ቁርጭምጭሚት ላይ የምትታሰር ትንሽዬ ጥቁር ነጠላ ጫማ አድርጋለች ። የዚያች የምታምር ልጅ መልክና ቁመና አሁን እበቅሎ ላይ የተቀመጠችው እንጨት የሞጠች የምትመስል ሴትዮ ላይ የለም ።

"እግዜር ይስጥልኝ አልወርድም ።" አለች ። "ላገባ መሆኑን ልነግራችሁ ነው የመጣሁት ።"

"ምን!"

"ማንን ልታገቢ?"

"ካቲ እንዴት ጥሩ ነገር ነው !"

"መቼ ነው ?"

"ነገ" አለች ካትሊን በዝግታ ። በድምፏ ውስጥ ያለ አንድ ነገር የእነሱን ትኩ ፈገግታ አክስሞ አበረረው ። "የመጣሁት ነገ ጆንስቦሮ ውስጥ ላገባ መሆኑን ልነግራችሁ ሲሆን ማንኛችሁንም አልጋብዛችሁም ።"

ሴቶቹ ይሄንን ነገር በዕጥታው ውስጥ እያብላሉ ቀና ብለው ሲያዩዋት የመገረም መልክ ይነበብባቸዋል ። ቆይታ ሜላኒ ተናገረች ።

"የምናውቀው ሰው ይሆን ! —ውዲት ! ?"

"አዎን" አለች ካትሊን ባጭሩ ። "አቶ ሒልተንን ነው"

"አቶ ሒልተን?"

"አዎን ፡ አቶ ሒልተን — ምስለኔያችን ።"

እስካርሌት "ወይኔ !" ለማለት እንኳ ድምፅ አጣች ። ካትሊን ግን ቁልቁል ወደ ሜላኒ አሾልቃ እያየች ፡ በዝቅተኛ ድምፅ "ሜሊ ታለቅሽና እኔ በጭራሽ አልቋመውም ። እኔ እሞታለሁ !"

ሜላኒ ምንም አልተናገረችም ። ብቻ የካትሊንን እቤት የተሠራ ጫማ እዚያው እርካቡ ላይ እንዳለ መታ መታ አደረገችው ። አንገቷን አቀርቅራለች ።

"እናም እግሬን አትምችኝ ! እሱንም አልቋመውም !"

ሜላኒ እጅጉን አወረደች ። ግን አሁንም ቀና ብላ አታይም ።

@OLDBOOKSPDF

"እንግዲህ መሄድ አለብኝ ፡ ልሂድ ። የመጣሁት ለናንተ ለመንገር ብቻ ነው" ያቺ አሳዛኝ ጥያቄ ተመልሳ ልትሄድ ልንሚን አንሳች ። "ካድ እንዴት ነው አሁን" ብላ ጠየቀች እሰክርሌት ። አሁንም መና ገር አልሆነላትም ፤ ብቻ የዐጥታውን በረዶ ለመለበር ያህል ቃሳት ፈልጋ ነው የደነገረችው ።

"እፍ ፣ እሱስ መሞቱ ነው" አለች ኳትሌን ዓጭሩ ። ድምጿ ውስጥ ምንም ህያው ስሜት የለበትም — ደረቅ ነው ። "ደግሞ የሚሞተው እሱ ሲሞት ምን ይመጣታል ሳይል ያለኃሳብና በሰላም ነው ። አየሽ ፡ እንጀራ እናቱና ልጆቹ ነገ እስከመጨረሻው ወደ ስሜን ይሄዳሉ ። በሉ ልሂድ እንግዲህ ቆ"

ሚላኒ ቀና ብላ ከክትሊን ጠግር ወይን ጋር ተጋጨች ። ሚላኒ ቅንድቦች ላይ የሚያንዐበርቡ እንባዎች አሉ ። ወይኖቿ ውስጥ ደግሞ ነገርን የመረዳት ስሜት አለ ። ኤፊቷ ያለችው ኳትሊን ግን ከንፈሮ ቿን ስጠጥ ስመጥ አድርጋ ላለማልቀስ እኝሂሚከር ጠንካራ ልጅ ቅጥ የለሽ ፊጠታ አሳየች ። የክትሊን ከልቧርት ምስለኔ ማግባት ለእሰክርሌት በጣም ማራ ነገር ሆኖባታል ። የበለሰሬ እርሻ ባለፀጋ ልጅ የሆነችው ኳትሊን ፡ ከእሰክርሌት ቀጥላ በመጌደሩ በጣም ብዙ ወጻጆችና ጥቅረሞች የነበሯት ኳትሊን ፡ ምን ቆርጧት ምስለኔ ታገ ባለች ።

ኳትሊን ጐንበስ አለችና ሚላኒ ደም በእግር ጣቷ ቀጠራራ ችና ተሳለሙ ። ከዚያም ኳትሊን ለጋጭጥ አወናጭፋ ሳበ ረገብ በቃ ደርግ ለሰላም በቅሎ ሰገረች ።

ሚላኒ ሁመለከተችው ። ዕንባዎቿ ጉንጭ ላይ በይ ሠርተው ወረዱ ። እሰክርሌት አሁንም ፈገግ ታያለች ።

"ሚሊ ፣ አብዳለች አንዴ ፣ መቼስ አፍቅራው እንዳለሆነ እንቺም ታውቂያለሽ" ።

"አፍቅራው ፣ ተይ አንጂ እሰክርሌት እንዲህ ያለ አሰቀያሚ ነገር አትናገሪ ፣ ወይኔ ምስኪን ኳትሊን ! ምስኪን ካድ !"

"ድራንጸንጻን !" ብላ ሙሽት እሰክርሌት ፡ ነገሩ ብሽቅ እያደረ ጋት ። ሚላኒ ከሷ የበለጠ ሁኔታዎችን መረዳት መቻሏ የሚያበሽት ነገር ነው ። የኳትሊን ነውር ሥራ ለእሰክርሌት ግራ መጋባትን ፣ መገ ረምን ሲያስከትል ፡ ለሚላኒ ግን እጥፈነቱ ፡ ክፉ ውጤቱ ነው የታ ያት ። እርግጥ መቼም የማይረባ ርካሽ ነጭ ማግባት ደስ የማይል ነገር መሆኑ ግልጽ ነው ። ነገር ግን እንዲት ልጅገረድ ሰፊ እርሻ

@OLDBOOKSPDF

ላይ ብቻዋን መቀመጥ አትችልም ። ሥራውን እንድታራምድ የሚረ ዳት ባል ያስፈልጋታል ።

ሚሲ ፣ ባለፈው ቀን እንደነገርኩሽ እኮ ነው ። ሴቶቹ የሚያነ ቡት ወንድ አጥተዋል ። ስለዚህ ማንንም ይሁን ብቻ እንድ ሰው ማግባት ይኖርባቸዋል ።"

እንደ ፣ የግድ ማግባት የለባቸውም ! ሴተ ላጤ መሆን እኮ ምንም የሚያሳፍር ነገር የለበትም ። አሁኑ አክሱቱን ፒቲን ተመልከቻት ።

ጨ . . . እኔ ካትሲንን ብሆን መቼም ሞቴን እመርጣለሁ ! ካድም ብት ሞት ይመርጣል ። በቃ ፣ ምኳልቨርት ቤተሰብ አለቀለት ማለት ነው ። አሁኑ የዕ . . . የኑሱ ልጆች ምን እንደሚሆኑ አስቢው ። ውይ እስካር ሌት ስሞትልሽ ፖርክን ፈረሱን ጫን በይውና ከኋላዋ ደርሰሽ መጥቃ ከኛ ጋር እንድትኖር ንገሪያት !"

"ኧረ የመድኃኒዓለም ያለህ" ብላ ሮዝሽት አስካርሌት ፣ ሚላኒ ታራን እንዲህ እንደዋዛ ለሰው መኖሪያነት ስትለግሳት ሰምታ ዘመደ ናንጥ ። አስካርሌት ያለጥርጥር ከእንግዲህ ሌላ አፍ ለመመገብ ከኖ አትፈልግም ። ይሆንን ልትናገር አስባ አፏን ከመክፈቷ በፊት እሜ ላኒ የተንጻ ፊት ውስጥ ያየችው እንድ ነገር ገታት ።

"እሷ አትመጣም ሚሲ," አለችና አከለችበት ። "እሺ ብላ እን ደማትመጣ እንቺም ታውቂዋለሽ ። በጣም ክሩ ስለሆነች እንደምዕ ዋት ትቆጥረዋለች ።"

"እውነትሽን ነው ! ትክክል ነው !" አለች ሚላኒ ታሳቢን ቀይሳ ፣ የመጨረሻውን የአፏራ ጸመና መንገዱ ላይ እያስተዋለች ።

"አንቺ ለወራት ከኔ ጋር ከርመሻል" አለች እስካርሌት በሆዷ ወደባሏ እህት እየተመለከተች ። "እናም እኔ የማደርግልሽ ሁሉ ምዕ ዋት መሆኑን በጭራሽ አልተገነዘብሽም ። እንደመሰለኝ ወደፊትም እድሜ ዓለምሽን አትገነዘቢም ። አንቺ ጠርነቱ ምንም ካልለወጣ ችው ሰዎች ማህል እንዲ ነሽ ። ስለዚህም ምንም በደል እንዳልደረሰ ብሽ ፣ ምንም ነገር እንዳልተካሄደ አሁንም ታስቢያለሽ ።አሁንም እን ከሮሰስ የሞላን የተትረፈረፈን ፣ ያለንን ምግብ እንጥልበት ያጣንና እንግዳ ሠምጣቱ ምንም ችግር እንደማይፈጥርብን አድርገሽ ታስ ቢያለሽ ። ደሞኩ ቀሪውን ዕድሜዬን በሙሉ ሜንታዬ ላይ ተሸከሚሽ ልኖር ነው ። በተጨማሪ ካትሊንን ማን በጭራሽ አል ሸነከም ።"

@OLDBOOKSPDF

ምዕራፍ 30

ሰላም ከሙሰሰ በአላ በነበረው ሞቃት በጋ ታራ በድንገት በሞኝነቷን ገርፋ ጣሰች ። ከዚያ በተከሰሱት መራት ምግብና ማደሪያ ቦታ የሚፈልጉ ፣ ማስፈራሪያ የመሰሉ ፣ ግራጫ ጢም ያንዠረገጉ ፣ ቡቱት ልብስ የለበሱ ፣ በባዶ እግር የሚሄዱና ምንጊዜም የሚራቡ ሰዎች ተከብባ ፤ ሽቅብ የታራን ቀይ ኮረብታ እያቃሰቱ ወጥተው ሄደው ገብሩላን

@OLDBOOKSPDF

ሩቅን እንደገና ይሞንጥሟቸዋል ። ሴሳጊዜ ልጁቻቸውና ሰፊው ሌጆ ቻቸው በስተግኩል ሥራ ፡ ስለድንጀተኛ ወረራ ፡ ስለቅጣቶች ፡ ስለረ ሀብና በግድ ስለመዝመት እንዲሁም ስለ ቁስል ይነጋገራቸዋል ። አሁን ግን አይደለም ። እንደንዶቹ ወይ እኔድ አጅ ወይ አንድ ዐይን የለሳ ቸው ናቸው ። አብዛኛው ጠባሳ አላቸው ። ጠባሳዎቻቸው በዝናብ ጊዜ ያመሟቸዋል — አሰበ ሰባ ዓመት ከሞኑ ። አሁን ግን እነዚህ ሁሉ ትናንሽ ጉዳዮች ናቸው ። መጀራት ደሞ የተለያዩ ነገሮች ይሞ ናሉ ።

ሽማግሌውና ወጣቱ ፡ ልሬኛውና ጭምሳ ፡ ባለሥራ እርሻውና መናጢ ደሀው ሁሉም ተሚጋፈጡት ፡ ሁሉም በእኩል የሚፈሏቸው ሁለት ነገሮች ነበሯቸው — ትግልና ቁስማጥ ። የነጉሬዶፊሊው ወታ ደር ከኮሰቁልናና ከመዘራ ጋራ ብጣም ከመዛመዱ የተነሳ ሲዶኛ ባሉበት ሰውነቱን ቢያዝ ፡ እነዛኑን ቢደክት ማድም አያስጠውም ። የቁስማቱም ነገር ከተነሣ ፡ —የቅል ከመ "ንጹው ጀርተቹ" ሊሆነ ከሁሬ መታደር ጀምሮ እስከ ጀራስ ድረስ ሁሉን በእኩል ያዳር ሳል ። አራት ዓመት ሙሉ ከፊል ረሀብ ፡ አራት ዓመት መሬ ያደ ረቀ ራሽን እየበሉ መጥር አህሳ አድርኮ ሠርቶላቸው ፡ እያንዳንዱ ያራ የንባ መታደር ወይ ገሳ በሚገኝም ላይ ያለ አሲያም በአፍሳው ተይዙ የሚማትት ነው ።

"በአንፈዱራሲው ሠራዊት ሙሱዋ ያልታመመ ሆድ ያሳቸው አንድም የለም" አለች ማሚ ፡ ለአንዲህ ያለው በሽታ ኤስን ዋና መድሃኒት የጥቁር አንጀራ ሙማቂ ነው ብሳለች ፡ ከሚል አስን እየጨ መሩች ። "በበቡሉ የኛን ሰምች ያጠቋቸው ምክኒምች ናቸው ፡ ሽራ አላምነም ። የራሳቸው የወሰጥ ጤና መታመክ ነው ። ማንም ሰንድ ተቅማጥ እያለበት መዋጋት አይችልም ።"

ማሚ ለለሚያማቸው የሰውነት ክፍል ምንም ሳትጠይቅ መድኃኒት ታጠጣቸዋለች ። ከእንዱ ጀምራ ሁሉንም ታጠጣቸዋለች። አንሱም መድኃኒቱን ሲጠጡላት እንጸሀዘቻቸው ነው ። ምናልባት ሩቅ ቦታ ያሉ ሌሎች ክበታራ ጥቁር ፊቶችና የመድኃኒት ማንኪያ የያዙ አይበገሬ እጆችን እያስታወሱ ሊሠን ይችላል ።

ማሚ "በሚመጡት ሰዎች ንፅሕና" ጉዳይም ቢሆን በጣም ማትር ናት ። ማንም ትጣል የጨረሰው መታደር መደታራ መግባት የለበትም ። ሁሉንም ሰብስባ ቁጥጋሮ ጢሻ ጀርባ ትወስዳቸውና ቡቱቶ ዮኒፎር ማቸውን አስወልቃ ፡ ውሃ በትልቅ ሳፋ ከሳሙና ጋር ታቀርብላቸ ውና ራቁት ገላቸውን የሚሸፍኑበት ምንጣፍና ብርድ ልብስ ትስጣቸ ዋለች ። እሷ እማሬ መንገዷን ልብሳቸውን ትቀቅልላቸዋለች ። እን

@OLDBOOKSPDF

ጸሀ ያለውን ነገር ስታደርግ, መታደሮች የናቅሽ ያዋረድሻቸው ይመ ስላቸው ይሆናል ብለው ሴቶቹ ቢነግሯትም እሷ ፍንክች አላለችም። እንዲያውም ከመታደሮቹ ይልቅ እናንተ ልብስ ላይ ቅማል ቢገኝ ትልቅ ውርደት ነው ብላ ትመልሳለች ።

መታደሮቹ ከሞላ ጎደል በየቀኑ መምጣት ሲጀምሩ ማሚ ፤ መኝታ ቤት እንዳይገቡ ትታወም ጀመር ። ሁልጊዜ ተባይ አምልጠ ይዛመ ታል ብላ ትፈራለች ። እሱሀርሌት ግን መከራከሩን ትታ አልፍኮን የወንዶች መኝታ ቤት እደረገችው ። ማሚ በየጊዜው የወ/ሮ ኤስን ምንጣፍ ላይ መታደር ተኛበት እያለች ትጮሃለች ። እስክርሌት ግን ግትር ሆነች ። መቼም አንድ ቦታ መሆኗት አለባቸው ። ከእሮ መስ ጠቱ በኋላ በተከተሉት ወራት ያ ለስለሳው ባለዩጉር ምንጣፍ ዩጉሩ እየተሳጠ የአማኤሚና ቁሚ ከሮቹ መስመሮች እግር ባረፈበት ቦታ ሁሉ ይታያሉ ።

የመጣውን መታደር ሁሉ ስለአሸሉይ ይጠይቁታል ። ሱዌለን ደግሞ በክራት ስለኬኔዲ ትጠይታለች ። ሆኖም ስለሁለቱ ሰዎች የሚናገር ወይም ስለመጥፋታቸው እንኳ የሚያወራ አንድም መታደር ጠፋ ። እራሳቸው በህይወት ካሉ ቤቲ ሆነ ። በቪ ስለሚቆጠሩት ፣ ባልታወቀ መቃብር መሰየም ስለተጋደመትና ወደ ቤታቸው ፈጽሞ ስለማይመለሱ ሰዎች አንጻቸውም ግድ የሉቸውም ።

የመጣው መታደር ተጠይቅ መሬ በጠሩ ቁጥር ሚላኒ እንዳያስ ፋት ቤተሰቡ በመሉ ስማበረታታትና ስማደፋፈር ይሞክራል ። እር ግጥ አቪሌይ አሥር ቤት ውስጥ አልሞተም ። ይሄ እውነት ቢሆን ኖሮ አንዱ ያንኪ ይሰፍ ነበር ። አርማጥ ነው ወደቤት እየመጣ ነው። የተጋዘበት አሥር ቤት ሩቅ ስለሆነ ሊሆን ይችላል ። ደሞኮ እስከ ቡሩ ድረስ በፈረስ ቢዜድ እንኳ ከባቡሩ በኋላ እንደነዚህ ሰዎች በእግር ለመምጣት በጣም ብዙ ቀናት ይፈጅል ። . . . ግን ለምን አል ፃፈም ? አሃ መጂት ዛሬ ጊዜ የፖስታ ነገር የምታውቂው ነው — በጣም አጠፊጣሪና ስንትና ስንት ፖስታ የትም ሾልኮ የሚጠፉበት ጊዜ ነው ። የፖስታ አገልግሎት እንደገና በተቋቋመበት ቦታ እንኳ ምንም አስተማማኝነት የለውም ። ግን ምናልባት . . . ምናልባት ወደ ቤት ሲመጣ እመንገድ ሞቶስ እንደሁ ። አይ እንደዛ ከሆነማ ሚሲ አንዲ ያንኪ ሴት ትፅፍልን ነበር ! . . .የያንኪ ሴቶች ኤሞ ! . . .ሚሲ አንጸንድ ጥሩ የያንኪ ሴቶች አሉኮ ። እሱስ አም አሉ ። መቼም እግዜ ሃር አንድ ድፍን አገር ሠርቶ ሲያበቃ ጥቂት ጥሩ ሴቶች ጣል ጣል ማድረጉ አይቀር ። እስካርሌት ያን ጊዜ ሳራቶጋ ላይ ያገኘናት ግራም የያንኪ ሴት ትዝ አትልሽም ? እስካርሌት ፣ እስቲ ስለእሷ ለሜሊ ንገ ሪያት!

@OLDBOOKSPDF

"ማሩም፣ እሪ በጉዴ ወጣሁ!" ብላ መለሰች እስካርሌት። "እያማ ባሪያዎቻችንን የምናስጠበቀው በምን ያህል አዳኝ ውሾች እንደሆነ ጠየቀችኝ! እኔ ሜላኒ ባለችው አስማማለሁ ወንድም ይሁን ቤት ምንም የያንኪ ደህና አይቼ አላውቅም። አታልቅሺ እንጂ ሜሉ፣ አሽሌይ ወደ ቤት ይመጣል። በጣም ረዥም የእግር ጉዞ ስለሆነና ምናልባትም... ምናልባትም ቦት ጫማ ስለሌው ሊሆን ይችላል።"

እስካርሌት አሽሌይን በባዶ እግሩ አስበችውና ልታለቅስ ምንም አልቀራት። ሴሎች ወታደሮችስ እግራቸው ላይ ቡቶችና የምንጣፍ ብጥስጣሽ ጨርቅ ጠቅልለው ይሄዱ፣ አሽሌይ ግን ምንበወጣው፣ አሽሌይ ባማረ ፈረስ ቆንጆ ልብስ ሰብሶ፣ የሚያበረቀርቅ ቡት ጫማ አድርጐ መምጣት አለበት። የራሱ ባርኔጣም ባለክፈፍ መሆን አለበት። አሽሌይን በንዚህ ጐስታኖችና የቱባይ ማርቢያ በሆኑ ወታደሮች ደረጃ ዝቅ አድርጋ ማሰቡ ራሱ የመጨረሻ ውርደት መሰላት።

አንድ ቀን ከሰዓት በኋላ ታራ ያለ ሰው ጓሮ ተቀምጦ፣ ፖርክ በወቅቱ ግማሽ በግማሽ የበሰለውን ሀብሀብ ሲቆርጥ ሲመለከት ሳለ፣ በፊት ለፊቱ በር በኩል የፈረስ ኮቴ ተሰማ። ፕሪሲ እንደተለመደው እየተጐተተች ወደ ውጪው በር ሄደች። የቀሩት ሰዎች ሀብሀብ በደ ምብ ስላልበሰለ ተደብቆ መቅመጥ አለበት የሰበትም ከርከር ይዘዋ ዋል። ድንገት ከውጪ የመጣው እንግዳ፣ ወታደር ከሆነ እንዳይሻማ ቸው የሰጉ አሉ።

ሜላኒና ካሪን የመጣው ወታደር ተካፍሎን ቢበላ ምናለበት እያሉ ይንሾካሾካሉ። እስካርሌትን ሱዌለንና ማሚ ደግፈዋታል። ፖ'ር ክን አንድ ቦታ ደብቀው እያለች በቀስታ ትነግረዋለች።

"እናንተ ደሞ ጅል አትሁኑ! እንግዲህ የተገኘው ይበላ፣ ይዋጥ ይሰልቀጥ አትበሉ፣ ስራሳችን ለኛም የሚበቃ ምግብ የለንም፣ ከሁለት ወይም ከሶስት ጠኔያም ወታደሮች ጋር በልተን ለሽታም አይደርሰን" አለች እስካርሌት።

ፖርክ ትንሹን የሀብሀብ ፍሬ በጁ እንደያዘ ውሳኔ ላይ መድረስ አቅቶት እንደቆመ ፕሪስ ስትጮህ ሰማት።

"እሪ በእግዚአብሔር! እትዬ እስካርሌት! እትዬ ሜላኒ! እሪ ቶሎ ኑ"

"ማን ሙጣ?" አለች እስካርሌት በጨኸት ከደረጃዎቹ ላይ ተስ ፈንጥራ ተንስታ። ሜላኒ ከእስካርሌት ጐን ጐን ሌሎችም ከኋላ እንደሰልፈኛ እየተከታተሉ በአዳራሹ አቋርጠው ሄዱ።

@OLDBOOKSPDF

እግዚአብሄር ከሱ ይሆን ብሎ አሰበች እስክርቤቱ ። እ ፣ ምናልባት . . . .

"እንት ፒተር ንወላ የመ/ሮ ፒቲፓት እንት ፒተር!"

ሁሉም ወደፊት ለፊቱ በረንዳ ሮጡ ። ጀርባዋ ላይ ጨርቅ ብጤ ጣል ከተደረገባት ፣ የእይታ ጥራ ታህል ጅራት ከለው ትንሽ ፈረስ የሚ ጠርይውን ሲኾሙን የመ/ሮ ፒቲን ፣ ፈለም ቆራጭ የሠረገላ ዥረር አየ ። በዚያ በሰፈ ጥቁር ራኩ ላይ የዱቲ ንጀኛነት የማሣያት ከራት ሲጠናገፀት ይታያል ። ወዲያው የሚንሳሩ ቆሳ ሽብሽብ ፣ ቅንድቡም ሕብለብ አሉ ። አፉ ግን ተከፍቶ ጥርስ የሌለው አርጌ ውሻ መስ ኗለ ።

ሥራ ለው ጥቁር ክንጭ ሳያባል ይሸሹን እየተንደረደረ እየወ ረደ እጁን በመጨበጥ የጥያቄ መዓት አወረዳበት ። ከሁሉም ድምፅ በላይ የሚሰማው ግን የሜለ, ኑ ።

"እክስቱ ደህና ናት ? አላመጣችም ፣ እይዶ ?"

"የለም አመጨት ፤ ይመለሳለው ደህና ጥቮ" አለና መለሰ ፒተር ፣ ትኩር ብሎ እንዴ ሚሊን እንዲ እስክርቤትን ከሚየው የተ ነሳ ሁለቅ ሊሶች የጥሩቸንት ስሜት አሰኪሰማቸው ጀረስ ። "ጠናበ ኑበሩ ። ነገር ግን የሁለታችሁ ኖፍቆት በጣም ጓድኟቸዋል ። ለንሩ እኔም በጣም ኖውጨያችኋለሁ ።ሀ

"እንዴት እንት ፒተር ምነው እንዳህ . . . "

"የለም ለራሳችሁ ይቅርታን ለመስጠት አትሞክሩ ። ወ/ሮ ፒቲ ለንትና ለንት ጊዜ የቆሳችሁ ፣ ለንት ጊዜ ወደቤት እንድትመጡ ጠየ ቋችሁ ፣ ለናንተ ሊፅፉሳችሁ አይቻለው ። እናንተም በዚህ ዓመት በዚህ አርጌ አርቫ ላይ በጣም ሥራ እንደሚበዛባችሁ ገልየችሁ የባ ሩችሁትን ደብዳቤ እያነበቡ ሲያለቅሱም አይቻለሁ!"

"ግን እኮ እንት ፒተር . . ."

"ወይዘሮ ፒቲ እንዲህ በረሩበት ሰዓት እንዴት ብቻቸውን ጥሳ ችኋቸው ትጠፉሳችሁ ? እኔም እናንተም እንደምናውቀው ወይዘሮ ፒቲ አራሳቸውን ችለው ብቻቸውን መቀመጥ አይችሉም ። ስለዚ ህም ይኽው ከማከን ከመጡ ጀምሮ እትንሿ ሚማቸው ውስጥ እንደ ተንቀለቀሉ ይውሳሉ ። እንደዛያው ይኑጋሳቸዋል ። እንዲህ በጣም በሚፈለጉችሁ ሰዓት ሁሳችሁም እንዴት እንደከዳችኋቸው እንድጠ ይቅ ልከውኛል ።"

ማሚ ታራን "አርጌ አርቫ" ሲል ሰምታ ስለተናደደች "በቃ አሁን ዝምበል!" አለች ። አንድ ደንቆሮ ከተማ አደባ ባሪያ በትንሽ

@OLDBOOKSPDF

እርሻና በሰፈሙ በተንጣለለ ጉልቅ እርሻ ማህል ልዩነቱን አስማወቱ ነደጻት። "እኛስ የምንፈልጋቸው ሰዓት አይደለም እንዴ፣ የኛስ ሥራ አይታይም እንዴ፣ እኛስ ወይዘሮ ሚሳኤና አስካርሌትን እዚህ እንፈል ጋቸው የለም እንዴ፣ ወይዘሮ ፕቲ ለምን ወንድማቸውን እርዳኝ አይ ልም ?"

እጮት ፕቲር በቀላሉ ጎላመጣት።

"ኤኛ ከአቶ ሐይሪ ጋር ማናናንት ከተወን አመታት አልፈው ናል። አሁን እንኤ አይበ ለመጀመር ደጣም በጣም አርጅተናል።" መለስ ብሎ ሳቃቸውን ለማፈን የሚጣጣሩትን ሴኖች ተመልከታቸው። "እናንተ ወጣት ሴቶች ምስጢርን ወ/ሮ ፕቲን ብቻቸውን ትታችሁ በመጥፈታችሁ ማፈር ይገባችኋል። ግማሾቹ ንደኛቸው ሞተውና ግማሾቹም ማዜን ሙሰጥ ቀርተው ፣ አትጣንታም በየንኪምኛና በር ክሽ ጉለበት በሚቀጠሩ አናሮምኛ በተመላችበት ዛሁኑ ሰዓት ፣ ብቻቸውን መተዋችሁ ነውር ሥራ ነው።"

ሁለቱ ሴኖች ስድቡንም ወቅሳውንም እንደምንም ችለው ነበር። ነገር ግን የወ/ሮ ፕቲ ፣ ፕቲርን እዚህ ድረስ ስደብልኝ ብሎ መላክና ጉትጉ ወደኤትላንታ የመጀመሻቸው ይመስል ይዘሃቸው ና ማለት ከቋጥራቸው በላይ ሆኖባቸዋል። በሳቅ ተንከተከቱ። እንደኛዋ በአንደኛዋ ትከሻ ላይ ተደጋግፈው መቆም እስኪያስፈልጋቸው ድረስ ሳቁ። ፖርክ ፣ ጴልሲና ማሚ ሙዲ ታሪን የሰደበና ያሳናቀ ስው ሲሰደብላቸው እንደተለመደው ፈንድቀዋል። ሱዌስንና ክሪ ንኖ ይገለማጣሉ። ሴላው ሁርኮ የጂፌልድ ፊት እንኳ ግራ የተጋባ ፈገግታን በብፃል። እዚኛ ከሰዓት ሁኩ የማይስቅ ፣ አማሩን እያለዋ ወጠ በመንቀራጠጥ ንዴቱን የሚገልፀው ፕተር ብቻ ነው።

"ምን ሆነሃል አንተ ኔማሮ ?" ብሳ ጠየቀችው ማሚ ትንሽ እን ደሸመጣ እየታጣት "አረጀህና የነዛ እመቤትህን እንኳ ለመለበቅ ተሳ ነህ እንዴ ?"

ፕተር ግንፈለ።

"አረጀህ! እኔ ነኛ የማረጀው ? በጭራሽ የኔ እመቤት ! አሁን እን ደማደርገው ሁሉ በደንብ እጠብቃቸዋለሁ። ወደማክን ክንሰዶድስ እኔ አይደለሁ እንዴ ጠብቄ ተንከባክቤ ያደረስኳቸው ? ያንኪዎች ከወደ ማክን ሲመጡስ ከፍርሃት ብዛት ልባቸው ስትፈስስ እኔ አልነበ ርኩ እንዴ የደረስኩላቸው ? ዘንድሮስ በቅሎ አምጥቼ ኤትላንታ ድረስ እሳቸውንና ያጠታቸውን ንብረት ጠብቄ ያመጣኋቸው እኔ አይ ደለሁምን" ፕተር ተበቅያለሁ ብሎ ሲያስብ ቀና ብሎ ሙሉ ረኸቦ

@OLDBOOKSPDF

ቁመቱን ያሳያቸው ጀመር ። "እኔ የማወራው ስለመጠበቅና አለመ ጠበቅ አይደለም ። እኔ እምለው ነጣሩ ምን ይመስላችኋል ነው ።"

"ማ ምን ይመስላችኋል ?"

"ሰዉ ወ/ሮ ጢቲ ብቻቸውን መኖራቸውን ሲያይ የሚለው ነገር ምን ይመስላቸኋል ፣ ነው ያልኩት ። ባል የሌላቸው ሴቶች ብቻ ቸውን ሲቀመጡ ሰው በምን ዓይነት ስሜት እንደሚያማ ታውቃላ ችሁ ። "አለና ቀጠለ ጢቱር ። አሁን የሚያዳምጡት ሰዎች እሱ ስለወ/ሮ ጢቲ ያለውን ግምት ያውቃሉ ። በሱ ግምት ወ/ሮ ጢቲ ከሰው መጠበቅ ያለባቸው የአሥራ ስድስት ዓመት ቆንጆ ልጃገረድ ናቸው ። "ሰው ምን እንደሚሉአቸው አልነግራቸውም ። ደሞ እኔ ፊት ማንም አይናገርም ። የለም እመቤት ፣ማንም የሚያማቸውን ነገር የምና ገር ልኩን የማላውቅ ሰው አይደለሁም ። ያንን አልነግራቸውም ።" ነብስና ስጋዎት ከእርስዎ ጋር እያለ ማንም አይናገርዎትም አላቸዋለሁ ። አሁን ግን ነብስና ስጋቸው እየተላተሙባቸውና እየተራራቁባቸው ነው ። ወይዘሮ ጢቲ እኮ እንዳልጅ ናቸው እና . . ."

ይሄንን ሲል አስካርሌትና ሜሊ በሰቅ አደረጃው ላይ ወደቁ ። በመጨረሻም ሜሊ አንባዋን ጠራርጋ ተነሳች ።

"ምስኪን አጐት ጢቱር ! ስለሳችኋት ይቅርታ ክልቤ ነው ። ይሄው፤ ይቅርታ አደረግልኝ ። እኔና ወ/ሮ አስካርሌት አሁን እናንተ ቤት ለመምጣት አንችልም ። ምናልባት በመስከረም ከጥቂ ለቀማ በኋላ እመጣ ይሆናል ። ለመሆኑ አክስት አዚህ ድረስ የላከችህ በዚህ አጥንቱ በገጠጠ ፈረሰ ይዘኸኝ እንድትሄድ ኖሯል ?"

ይሄን ጥያቄ በመጠየቅ ጢቱር ማንጭሉን በንዴት ቋጠረና ጥቁር ፊቱን ኮሶ አስመሰለው ። ኤሊ አንጣቷን ወደድንጋያማ ሰውነቷ እንደምትክት ዓይነት የታሞቸውን ክንፈሩን በፍጥነት በላይኛው ክንፈሩ ልክ ሰበሰበው ።

"ወይዘሮ ሜሊ, አሁንስ እያረጀሁ መሰለኝ ። ሰምገ እንደላኩኝ ሁሉ ዘንጋሁት ። ደሞ እኮ በጣም አስፈላጊ ጉዳይ ነው ። አንድ ደብ ዳቢ አምጥቼላችኋለሁ ። ወይዘሮ ጢቲ ፖስታ ቤቱን ስላላመኑ በእ ጃቸው ለጣቸው ብለው እኔን ላኩኝ ። እናም . . . "

"ደብዳቤ? ለእኔ? ከማ የተላከ ?"

"አየሽ እመቤቴ ደብዳቤው . . ወይዘሮ ጢቲ እንዲህ ብለው ነው የሰጡኝ፡— "አንተ ጢቱር ወይዘሮ ሜሊ ዘንድ ስትደርስ ብቻ በጥንቃቄ ቀድደህ ስጣት" እና እኔም . . ."

@OLDBOOKSPDF

ሚሊ ከደረጃው ላይ ብድግ አለች ። እጅዋን እልፊ ላይ አድርጋ ቀለች ።

"አሽሌይ! አሽሌይ! ሞተ!"

"እረ የለም እመቤቴ! በጭራሽ! አይደለም!" አለና ጮኸ ፒተር ድምፁን ስልል አድርጎ ፡ ከተቀደደ ኮቱ ደረት ኪስ ደብዳቤውን እየፈለገ ። በሕይወት አለ ፤ ይሄ ደብዳቤ ከሱ የተላከ ነው ። ወደቤት እየመጣ ነው ። እሱ . . . እረ በየሀው! ያሣት እንጂ ማሚ ፤ ቆይ እኔ . . .

"ጎክች እንዳታረጋት አንት ጅላጅል ሽማግሌ !" ማሚ አምባረቀችበት ፤ የሜላኒን የተገለፈለፈ ሰውነት እንዳይወድቅ እየደገፈች ። "አንተ አስመሳይ ጥቁር ዝንጀሮ! ቀስ ብለህ ቅደደው ። አንተ ፖርክ፣ ና እግሯን ያዝ ። ወ/ት ካሪን ጭንቅላቷን ደግፊያት ። እልፍኝ ካለው ሶፋ ላይ ወስዶን ጋለል አናድርጋት ።"

ከአስካርሌት በስተቀር እያንዳንዱ ሰው ይራኩት ጀመር ። ተዝ ለፍልፉ በወደቀችው በሜላኒ ዙሪያ ወዲህ ወዲያ ይላሉ ። እያንዳንዱ ሰው ይጮህል ። አንዱ ጨሣ ሲያመጣ ሌላው ትራስ ሲያመጣ ይሯሯጣል ። በቅጽበት ጊዜ ውስጥ አስካርሌትና አጎት ፒተር ብቻ እበረንዳው ላይ ቆመው ቀሩ ። ስለደብዳቤው ከተናገረበት ደቂቃ ጀምራ ከተተከለችበት ቦታ ሳትንቃነቅ በእጁ የያዘውን ደብዳቤ የሚያርገበግበውን ሽማግሌ ትክ ብላ እያየች ቆማለች ። ያረጀ ሰፊ ጥቁር ፊቱ እናቱ እንደተቆጣችው ልጅ ከፍት ብሎታል ። ይታይበት የነበረውም የከብር ሞገስ በንኖ ጠፍቷል ።

ለትንሽ ጊዜ አስካርሌት ፎናገርም መንቀሳቀስም አቃታት ። አእምሮዋ ግን አንዲህ እያለ ይጮሃል "አልሞተም! ወደቤት እየመጣ ነው!" ይህንን ማወቋ ደስታም ሆነ የስሜትን ምልዓት አልሰጣትም ። አለመናገር ፡ አለመጋገር ፡ አለመንቀሳቀስ ብቻ ነው የተረፋት። የአጐት ፒተር ድምጽ ከራቅ እንደሚሰማ ሁሉ ቀስስ ብሎ እየተርገበገበ ወጣ ።

"አቶ ዊሊ በርር ነው ከማክን ያመጣው ። አምጥቶ ለወ/ሮ ፒቲ ሰጣቸው ። እሱና አሽሌይ አንድ አስር ቤት ታስረው ነበር ። አቶ ዊሊ ፈረስ ስለነበረው ቶሎ ደረሰ ። አቶ አሽሌይ ግን በእግሩ እየመጣ ስለሆነና . . . "

አስካርሌት ደብዳቤውን ምንጭቅ አድርጋ ወስደችበት ። ከወ/ሮ ፒቲ ለሚላኑ የተፃፈ አድራሻ አለበት ። ሆኖም ይሄ እንድታመነታ አላደረጋትም ። ፖስታውን ስትከፍተው የወ/ሮ ፒቲ አነስተኛ ማስታ

@OLDBOOKSPDF

ወሻ ወደቀች ። ከፖስታው ውስጥ የታጠፈ ወረቀት አወጣች ። በኪስ ተይዞ የመጣ ስለሆነ ቁሽሽሽ ብሏል ። ጠርዝ ጠርዙ ንትብ ያለ ሆኗል ። በእሸሌይ እጅ ጽሕፈት ተክትቧል ። "ወይዘሮ ሜላኒ ፣ በወ/ሮ ማራ ጀን ሐሚልተን በኩል ። እትላንታ ወይም "አስፊ ሁለቱ ዋርካዎች ።" ጆንስቦሮ ። "

በሚንቀጠቀጡ ጣቶቿ የታጠፈውን ወረቀት ዘረጋግታ ማንበብ ጀመረች፡—

"የኔ ፍቅር ፣ አንቺ ወዳለሽበት ፣ ወደቤቴ እየመጣሁ ነኝ. . ."

እንባ ፊቷን እያጠበ ወደመሬት ከመውረዱ የተነሳ ማንበብ አቃታት ። ልቧም በማም ነምግበጡ የቁጣ ደስታዋን መቻከም አቃታት ። ደብዳቤውን ወደደረቷ ጥብቅ አድርጋ ይዛ ፣ የበረንዳውን ደረጃዎች ወጥታ ፣ ቁልቁል በአዳራሹ ወርዳ ፣ የታራ ቤተሰብ አባላት በሙሉ ራሏን ስታ በተኛችው ሜላኒ ዙሪያ በሚራኩትበት አልፍኝ አድርጣ ፣ ወደኤለን ቤሮ ሄደች ። በፉን ከኋላዋ ዘግታ ቀለፈችው ። በሚያቃስተው ሶፊ መቀመጫ ላይ ቁጭምጣ እየሯጫት ፣ እየሳቀች ፣ ደብዳቤውን እየላመች ፡—

"የኔ ፍቅር" አለች በሹክሹክታ "አንቺ ወዳለሽበት ፣ ወደቤቴ እየመጣሁ ነኝ ።"

* * *

መቼም አሽሌይ ከንፍ አመጣጥ ቁልሆነ በቀር ከኢሊኖይስ ጆርጂያ ድረስ ለመምጣት ሳምንታት አስዚያም ወራት እንደሚፈጅበት አይናቸው የሚያየው ልባቸው የሚፈርደው ጉዳይ ነው ። ያም ሆኖ ግን በታራ ጉዳና ላይ አንድ ወታደር ብዩ ቁጥር ልባቸው አንዳንድ ነገር ይጋልባል ። እያንዳንዱ ማስፈራሪያ ፊትና ጨጐጊት የመስለጠም ያለው ወታደር አሽሌይ ሊሆን ይችላል ። አሽሌይ እንኳ ባይ ሆን ስለአሽሌይ የሚያውቅ ወይም ከወይዘሮ ዊቲፖት አሽሌይን የሚመለከት ደብዳቤ የያዘ ወታደር ሊሆን ይችላል ። የአግር ኮቴ በሰሙ ቁጥር ጥቁር ከኑ የቢቱ ሰው በሙሉ ግልብቁ ብሎ ወደ ውጭው በር ይሮጣል ። ሰውን ከእንጨት መፍለጫ በታ ፣ ከግጠሽ ሚዳ ወይም ከጥጡ እርሻ ውስጥ እያባረረ ለማስወጣት አንድ ዩኒፎርም የለበሰ ሰው መምጣቱ ብቻ በቂ ነው ። ያ የአሽሌይ ደብዳቤ ከመጣ ለወር ያህል ጊዜ ከሞላ ጉደል ሥራ የሚባል አልተሠራም ። አሽሌይ ሲመጣ ማንም እቤት ሳለመኖር አይፈልግም ። ከሁሉም በላይ እቤት መኖር አለብኝ ብላ የምታምን መቼም አስካርሌት ናት ። አስካርሌት የራሷን ሥራ ቸል ያለችበት ሰሞን በመሆኑ ሌሎቹን ሥራ ሥሩ ማለት አልተቻላትም ።

@OLDBOOKSPDF

ማምንታት እየተንቋቀቱ ቢያዝሙና አሽሌይ ግን ድምፁ ሲጠፋ የታራ ጎበራተሰብ ቀስ በቀስ እንደገና ወደተለመደው ሥራው ተመለሰ። የሄደቱ ልቦች ከዚህ በላይ ሲጠብቁ አይችሉም። እስካርሌትም ምርልዛት መንገድ ላይ እንድ ችግር ተጥሞት ይሆን ወይ የሚለውን ሀሳብ ሲታሰላስል እንድ አስፈሪና ነገር አአምሮዋን ጨመደደው። የሮክ አይላንድ እስር ቤት ከዚህ በጣም ሩቅ ነው። ከእስር ቤት ሲወጣ ጎፈበቱ ደክሞ ወይም ታሞ ሊሆን ይችላል። ግንዘብ የለውም። አቋርጦት የሚመጣው አገር ደግሞ የክንፈዶሬሲው መታዶር የሚጠላበት አካባቢ ነው። ምነው የት እንደደረሰ ባወቅኾ—ቤተሰቡንም አስርቦ ቢሆን እያንዳንዱን ሳንቲም አሟጣ ስባቡር መሳፈሪያ ትል ነበር።

"የኔ ጥቅር፥ እንቺ ወዴት ሄደሽብኝ ፤ ወዶ ቤቴ እየመጣሁ ነው።"

ይህንን ጎረጥሳ ነገር መጀመሪያ ሲታነብብ በደስታ ጉርጥ ከመ ጥለቅለቁ የተነሳ፥ የታታት የአሽሌይ ወደቤት መምጣት ብቻ ነበር። አሁን ግን እእምርዋ ቤረጋጋ ነጎሩን ሲታሰለሙ ልክ ወዶ ቤት የሚመጣው እሚለ ኧታ ነው። አዎን፥ የሚመጣው ቤሞኑን በቤቱ ዙሪያ እየተንሳፈደደች በደስታ ዘደምትዘፍነዋ ወዶ ሚለኒ ነው። በዘሁ ቅጽበት፥ ምነው ይቺ ሚለኒ እዛው እትላንታ እያለች በመሲድ ዘሞተች እንዴት ማልግል ነበር የሚል እርኩሰ ሀሳብ መጣባት። ያ ቢሆን ኖሮ ነገሩ ሁሉ ልክ ይመጣ ነበር። ከዛ ጥቂት ቆይታ አሽሌይን ታገባና ፅጉንሹ ባቡ ጥሩ የእንጀራ አናት ትሆነው ነበር። እንዲህ ያሉ ሀሳቦች ሰመጡባት፥ ከልቧ አይደለም ይቅር በለኝ ብላ እግዚሃርን መማጠኑን ትታዋሽ። እግዚአብሔርን መፍራቷን ጨርሳ ክተወች ከራርሳለች።

መታዶሮች በነጠላም፥ በሞንድም፥ በቡድንም ይመጣሉ። ሁሉም የተራቡ ናቸው። እስካርሌት ከነዚህ የተራቡ መታዶሮች ይልቅ የአንበጣ መንጋ ቢወረኝ ይሻል ነበር ብላ አሰበች። ያንን የጥንቱን ባህል፥ ያንን ብር በበላ በተትረፈረፈ ጊዜ የተፈጠረ እንግዳ የመ ቀበል ባህል፥ ያንን ማንም መንገደኛ ሳይበላ፥ ሳይጠጣ፥ ለሱና ለፈ ረሱ ማደሪያ ሳያገኝ ማለፍ የለበትም የሚል ባህል፥ ያንን እንግዳን ቤት ባፈራው ነገር ማስተናገድ ደምብ ነው የሚል ባህል ረግመችው። ወይንሆን ለእፈር አለችው። ያ ዘመን ለእንዴም ለሁሌም ማለፉን ታውታለች። ሌሎቹ የቤቱ አባላትም ሆኑ መታዶሮቹ ይህንን ዕውነት አያውቁም። እያንዳንዱ እንግዳ መታዶር ሲጠበቅ የተከረመ ይመስል በተቻለ ሞቅ ያለ መስተንግዶ ይደረግለታል።

ያ ሙዮቱ መጥፎ የማያልቀው የመንገደኛ ወሳት መግተልተል ሉን በመቅጠሉ እስካርሌት ልቡዋ ደንደነ። የሚበሉት፥ ወንቡዋ እስ

@OLDBOOKSPDF

ኪሰበር ጐብጣ የለቀመችውን አትክልት ፡ ሰንትና ስንት መንገድ ተጉላ የገዛችውን ምግብና ታራ ውስጥ ላሉት አፎች የተዘጋጀውን ነው ። ምግብ ማግኘት በጣም አዳጋች ነገር ነው ። የዚያ የያንክ. በርሳም የማይነጥፍ የዘለዓለም ገንዘብ አይደለም ። ጥቂት ጥሬ ገንዘብና ሁለት የወርቅ እንክብሎች ብቻ ናቸው አሁን የቀሩት ። ምነው በምን ዕዳዋ ነው ይሄን ሁሉ መንጋ ሠራዊት የምትቀልበው ? ጠርኑቱ አብቅቷል—ከእንግዲህ እንደነና በአዶጋና በእሷ ማሀል አይቆምም ። ስለዚህ ማንኛውም ወታደር ወዲህ ከመጣ ገበታውን ባዶ አድር ገው ብሳ ፖርክን አዘዘችው ። ያቺ "ባቡ"ን ከወለደች ወዲህ አቅመ-ቢስ ሙሉ ለሙሉ ያልተመለሰው ሚላኒ ፡ ፖርክን—ለኔ ትንሽ ብቻ ስጠኝና የቀረውን ፋንታዬን ለወታደሮች ሰጣቸው ብላ ስታደላ ፍረው ፤ እስካርሌት እስካየች ድረስ የበፊቱ ትእዛዝ አልተነሳም ።

"ይሄን ነገር ተይ ሚላኒ" አለች በቁጣ "በደምብ ካልተመገብሽ ያልጋ ቁራኛ ሆነሽ ትቀሪና አንቺን ማስታመም ይኖርብናል ። እንዚህ ሰዎች ይራቡ ምንቸገረሽ ። እነሱ ሊድኑመት ይችላሉ ። ለአራት ዓመታት ችለውት ኖረዋል ። አሁንም ለጥቂት ጊዜ ቢቆዩ ምንም አይሆኑም" ።

ሚላኒ ወደሷ ሀረች ። ፀይነዋ ውስጥ ከዚህ ቀደም እስካርሌት አይታው የማታውቀው ዓይነት የሰሚት ግንፍልታ ይታይባታል ።

"ባክሽ አትስደቢኝ እስካርሌት ። ይህንን ማድረግ ምን ያህል እንደሚረዳኝ አታውቂም ። አንድ እርዳታ ለአንዱ ደክማ በሰጠሁ ቁጥር ፡ ወደ ሰሜን አንድ ቦታ አንዲት ሴት ከራሱዋ ቀንሳ ለኔው አሽሌይ እንደዚሁ ታደርግለትና ወደቤት መምጫው ሰዓት ይታ ረባል እያልኩ እጨናነቃሁ !" ።

"የኔው አሽሌይ !"

"የኔ ፍቅር ወዳንቺ ጋ ፡ ወደቤት እየመጣሁ ነው ።"

እስካርሌት ቃል ሳትናገር ዞር አለች ። ከዚያ ወዲያ ገበታው ላይ ብዙ ምግብ መቀመጥ እንደጀመረ ሚላኒ ተገነዘበች ። እንግዶች ሲመጡ ምግብ ይቀርባል ።

በጣም የታመሙና መሄድ የማይችሉ ወታደሮችም ካሉ እስካርሌት እምብዛም ደስስ ብሎዋትም ባይሆን ታስተኛቸዋለች ። እያንዳንዱ የታመመ ወታደር አንድ ተጨማሪ አፍ ነው ። አስታማሚም ያስፈልገዋል ። ያ ማለት ደግሞ ከአጥር አጠራ ፡ ከቁፋሮ ፡ ከአረማና

@OLDBOOKSPDF

ከእርሻ አንድ ሰው መቅነስ ማለት ነው። አንድ ብጉር ፊቱ ላይ የወጣበት ልጅ አንድ ቀን በአንድ ወታደር ሽክም መጥቶ አበረንጻው ላይ አረፈ። ያመጣው ወታደር እመንገድ ላይ ነው እራሱን ስቶ ያገኘው። እኮርቻ ላይ አግድም አስተኝቶ አንጠልጥሎ ነው ቅርብ ወደ ሚገኘው ቤት ወደታራ ያመጣው። ሴቶቹ ከወታደር ትምህርት ቤት ተመልምለው ከነበሩት ጥቂት ካዴቶች አንዱ ይሆናል ብለው ነበር። ነገር ግን ልጁ እራሱን ሳያውቅ በዚያው ስለሞተና ኪሱንም በርብረው ምንም ስላጠ ቢያውቁት አልቻሉም።

ሽጋ ልጅ ነው- ከሩ ሰው። ይሄኔ ደቡብ ውስጥ አንዱጋ አንዲ ሴት ይህንን ቆንጆ ልጅ በመጠበቅ ፡የት ይሆን? መች ይመለስ ይሆን፣ እያልች መንገድ መንገዱን ታይ ይሆናል። አሷና ሚሳኒ ማናቸውም ጠም የወረሰው ወታደር ሲመጣ እንደሚያደርጉት ማለት ነው። ቦስቱ የአሃራ ትናንሽ ልጆች መቃብር አጠገብ ቁበሩት። ፖርክ አፈር ሲመልስበት ሚሳኒ አይታ ፤ምናልባት እኮ ሌሎች ባዕድ ሰዎችም አሽሌይ ረሻምም ሰውነት ላይ እንዲሁ ያደርጉ ይሆናል፤ ብላ ሆዱዋ ባባባትና ስትስቅ ብላ አሰቀሰች። አነባች።

ሌላው ማንነቱ ሳይታወቅ ኮርቻ ላይ አግድም ተንጠልጥሎ ራሱን እንደሳተ የመጣ ልጅ ሚል ቤንቺን ነው። ሚል የብርድ በሽታ ነው የያዘው። ሴቶቹ አልጋ ላይ እንዳስተኙት እንደፈተኛው ልጅ መቃብር ነው የሚጠብቀው ብለው ነበር።

የተከፋፍና ወባ ያንደደው የመሰለ የጀርሚያ እንጨት ፈላጭ መልከና ጠቆር ያለ ወይንጠጅማ ፀጉር አለው። እንዲህ ቅፍፍ ብሎት ሥቃይ ላይ እያለ እንኳ ትዝዝ ለዘብ ያሉ ዓይኖች አሉት። እንደኛው እግሩ ከጉልበቱ በታች ቆራጣ ነው። ከቆራጣው ጫፍ ላይ የተፋቀ እንጨት ተቀጥሎለታል። ከጥቂት ጊዜ በፊት የቀበሩት ልጅ የአትክልተኛ ልጅ እንደነበረ ሁሉ ይሄኛው ደግሞ እንጨት ፈላጭ ነው። ይሄን እንዴት አወቃችሁ ቢሏቸው ሴቶቹ እሚመልሱትን አያውቁም። እርግጥ ሚል አስቀድመው ታራ መጥተው ከነበሩት ሰዎች የባሰ ያደፈ፣ ፀጉሩ የተንጨበረረና የተበየ አይደለም። በሥቃይ እንዳለ የሚናገረው ቋንቋም ቢሆን የታርሌተን መንትዮችን ያህል ቀናነት አሳጣም። ነገር ግን የማይረባውን ፈረስ ከሚረባው ለመለየት እንደሚችሉ ሁሉ፣ ይሄም ልጅ የነሱ መደብ አባል እንዳልሆነ ቀልባቸው ነግሩዋቸዋል። ሆኖም ይህንን ማወቃቸው ልጁን ለማዳን ከመጣጣር አልገታቸውም።

በያንኪዎች እስር ቤት ውስጥ ዓመት ሙሉ ማቅቆ፣ በሚገባ ባል ተሰክው የአንጨት እግሩ ረኽቦም መንገድ ሲጉዋዝ ከርሞ ፣ የብርድ በሽ

@OLDBOOKSPDF
ታን ለመክላከል ያለው በጣም ትንሽ አቅም ብቻ ስለሆነ ለብዙ ቀናት አልጋ ላይ እያቃሰተ እየጮኸ ሁለተኛ ጠርነት ገጥሞ ከረመ። አንድም ቀን እናቴ፣ ሚስቴ፣ እህቴ ወይም ፍቅረኛዬ ብሶ አለማ ወቋ ካሪንን በጣም አስጨንቋታል።

"ሰው አንድ ዘመድ ሊኖረው ይገባል" አለች። "እሱ ግን በዓለም ላይ አንድ ነብስ እንኳ የሚያውቅ አይመስልም።"

ምንም ቀጭንና ረሽም ቢሆን ጥንክሬ እያፈራና መልክም እን ከብካቤ እያጣለበተው ሄደ። አንድ ቀን ካሪን መቅጠሪያዋን እየቆጠ ረሽ የፀሐይ ብርሃን በሽጋ ፀጉሮ ላይ ሲፈስ ወሣ ሲሚያሮ ዐ ዋቹ አካባቢውን መገንዘቢ ችለው እሱዋ ላይ አረፉ።

"ለካ ሀልም አይደለሽም" አለ ደረት ቃጥ ባለው ድምጼ። "ብዙ አስቸገርኩሽ ይሆን? አመቢት።"

የማገግሚያ ጊዜው ረሽም ሆነ። እዚያው እንዲቀንጋለል በመ ስኩ አሻግሮ የማግኛቢያ ዛርች እያየ ማንም ላያስቸገር ይውሰል። ካሪን በዝምተኝነትና በማያቋርጥ እርያታው ወደደችው። ወበቃ ማዎቹን ከሰዓት በኋላዎች በመሬ ቃል ሳትተናገስ እሳኑ ተቀምጣ ስታራግብለት ትውላለች።

ካሪን ሰሞኑን እንደጣረቻቸው አየተሳቸች ለስላሳ ለመናገር ስቃን ቀሳቅስ ስለውሰጠ - አቅሟና ስለምትሠራው ሥራ መናገር ትታለች። በጣም አጥብቃ ትፀልያለች። እንሳንዴ እስክርቤቶ በር ሳታ ንኳኳ እከፍሉዋ ስትገባ ተንበርክካ ስትፀልይ ታገኛታለች። እስክር ቤት የፀሎት ዘመን አልፎአል ብሎ ስለምታስብ ይሄ የካሪን ፀሎት ሳያናድዳት አልቀረም። እግዚሃር ሊቀጣቸው አስቦ ከሆነ ባይፀልዩም መቅጣቱ አይቀርም። እስክርቤት የሃይማኖት ነገር ዑልጊዜ የስምም ነት ጉዳይ ነው የሚሆንባት። እግዚሃር ስሚሠራላት ውለታ መልክም ፀባይ በማሳየት ልትከሰው ቃል ገብታለች። ሆኖም እግዚሃር በተ ደጋጋሚ ስምንታቸውን በማፍረሱ እሱዋም የገባችለትን ቃል ሙሉ ለሙሉ አፍርሳለች። እናም ካሪንን ተንበርክካ ስትፀልይ ባገ ኘቻት ቁጥር የራሷን ሽክም ለማቃለል የምትሞክር ስለሚመስላ ትና የቀን እንቅልፉዋንም ሆነ የስሬት ሥራዋን ዘነጋችው ብላ ስለ ምታስብ ይነዳታል።

አንድ ቀን ከሰዓት በኋላ ዊል ቤንቲን ተናብሎ መቀመጥ ሲችል አነጋግራው ነበር። እናም በቁጥታ እንዲህ ሲላት ገረማት።

@OLDBOOKSPDF

"እትዬ እስካርሌት ፤ ካሪን እዚሁ ትሁን ። በጣም ያጽናናታል እዚህ መሆኑ "።

"ያጽናናታል ?"

"አዎ ለአንቺ እናትና ለእሱ ነው የምትፀልየው" ።

"እሱ ማነው ?"

የደፈረሱ ውሃ ሰማያዊ ፀጉሮቹን ከአፈርማ ሽፋሽፍቶቹ ሥር ገለጥ አድርጎ ያለምንም መጣረም አስተዋላት ። ምንም ነገር ያስደነቀውም ሆነ ያደናገጠው አይመስልም ። ምናልባትም በርከት ያሉ ያልታሰቡ ነገሮች አጋጥመውት ሊሆን ስለሚችል ነው ። እስካርሌት በአህጉሯ ልብ ውስጥ ያለውን ነገር አሰማወቁዋ በሞራሽ አላስገረመውም ። ካሪን ከአንግዳ ጋር በማውራት ልትጽናና እንደምትችል የገመተው እንደማንኛውም የተለምዶ ድርጊት ነው ።

"ስለ ወዳጅዋ ነዋ፤ ጌትስበርግ ላይ ስለሞተው ስለ ብሬንት ። የሆነ ነገር ታስባልች ።"

"ወዳጄዋ ?" አለች እስካርሌት አጠር አድርጋ ። "እሱኮ ወዳጅዋ አይደለም፤ እሱና ወንድሙ የኔ ወዳጆች ነበሩ" ።

"አዎ አሱንም ነገረችኝ ። የመንደሩ ወጣቶች በሙሉ ያንቺ ወዳጆች የሆኑ ይመስላል ። ያውቅ ነው ግን ። አንቺ ስታርቂው እሱዋ ያዘችው ። ስለዚህም ነው ለእረፍት ከጦር ሜዳ በፊታድ ሊመጣ ቀለ በት ያሠሩት ። እሷ እንዳለችኝ ከሆነ ከሱ ወዲያ የምትጨነቅለት ወንድ የለም ። ስለዚህ ለሱ መፀለይዋ ያጽናናታል" ።

"አጨጨሞ!" አለች እስካርሌት መለስተኛ ቅናት አልቡዋ እየገባ ።

ትኩር ብላ ወደዚህ ሰውሳ ፤ አጥንቱ ትከሻው ላይ የገጠጠ ፣ ወይ ንጠጆግ ፀጉር ወዳለውና ቅዝዝ ያሉ አይኖቹ ረግተው መደቆሙ ልጅ አቅጣጫ ተመለከተች ። ይሄ ልጅ እንግዲህ እሷ ጉዳዬ ያላለ ችውን የቤተሰብ ጉዳይ ያውቃል ። ለካ ለዚህ ነው ካሪን እዛ ቤት ውስጥ ሳትፀልይ የማትውለው ። ብቻ ትረሳዋለች ትንሽ ቆይታ ። ብዙ ኮረዶች ፍቅረኞቻቸው ሞተውባቸዋል ። ብዙ ሴቶችም ባሎቻ ቸውን አጥተዋል ። እስካርሌት ራሷስ የቻርለስን ሞት ረስታ አልፋው የለም ። እንዲያውም አንዲት አትላንታ ውስጥ የምታውቃት ሴት እኮ ጦርነቱ ሶስት ባሎችዋን አሳጥቷት እስካሁን ወንዶችን ማማረጥ አል ተወችም ። ሰዊል ብዙ ነገር ነገረችው ፤ ግን እራሱን እየነቀነቀ፤—

@OLDBOOKSPDF

"ወይዘሪት ካሪን ፣ ገና አየሁህ አፍታም አለ በመጨረሻ ንግግሩን በመደምደም ።

ከዊል ጋር ማውራት በጣም ያስደስ ይሳል ። የሚያወራው ነገር ላይ በጣም ቁጥብ ነው ። ሲያዳምጥና ሲረዳ ግን በጣም ሳቢ ነው ። ስለዚህ ችግሩንም ሁሉ አረም የማረሙን ፡ የቁሩሮውን ፣ የኑግ ተክሳውን ፡ አሳማ የማስባቱንና ላም የማጠቡትን ችግር ሁሉ ነገረኸው ። አሁም ጀርሺያ ውስጥ ትንሽ እርሻና ሁለት ኔግሮዎች የነበሩት ስለነበር ጥሩ ምክሮች ለግሳት ። አሁን ባሪያዎቹ ነፃ እንደ ወጡና እርሻውንም መኸ እንደሰጠቻቸው ያውቃል ። እሁዱ ከባዕ ጋር ወደ ቂከሳስ በመሄዴ እሁን በዓለም ላይ ከራሱ በቀር ዘመድ የለውም ። ሆኖም ይህ ባለነው ፡ ጅዴ ዘመድ ማጣቱ ከቆራጣው እግሩ የበለጠ አይጨንቀውም ።

አም ፣ ዊል ለእስክርቤቶት ምኞ መጽናኛዋ ነው ። በተለይ ቀንን መሉ ኔግሮዎቹ ሲጨቀጭቁዋት ፡ ሱዚሰን በትውተውታቸውና ያ ጂራ ልድ እየደጋገመ ኤለን የት አለች ብሉ ሲለት ቆይታ በትመጣ፣ ምኞቱ መጽናኛዋ ዊል ነው ። ለሚለ ምንም ነገር ልታወራለት ትችላለች ። ሌላው ቀርቶ አንድ ያህኪ እንደገደለች እንኳ ነግራው "ደግ ልጅረግሽ" ሲላት በኩራት ፍም አልክትመስለ ነው የፈቅችው ።

ቀስ በቀስ ቤተሰቡ በሙሉ መጀዊል መኝታ ቤት ሄዶ ችግሩን ማዋየት ጀመረ ። ሌላው ቀርቶ ሙሮጢ ነው ፡ ሁለት ባሪያ ብቻ ነው ያለው እያለች ትርቀው የነበረችው ማዊ እንኳ ወደቡ ክፍል መግባት ጀምራለች ።

ቫል ብሉት ቤት ቤት ማለት ከጀመረ በኋላ ቨምቢል መሥራትና ያንኪዎች የሰባበሩትን ዕቃ መጠጋገን ዋና ሥራው አረገው ። የመጠገን ሥራውን የተካነው ይመስላል ። ትንሹ ዊድም ቢሆን እሻ ንጉሊት ለለሚሠራለት ክሞኑ አይጠፉም ። ዋድ ያሉት አሻንጉሊ ቶች እነዚሁ እሱ የሠራለት ናቸው ። ዊል እቤት በመኖሩ ቤተሰቡ በሙሉ ዋድንና ሁለቱን ሕፃናት ያለሐሳብ ትሎለት ይሄዳል ። ልክ እንደማሚ ነው ልጆቹን ሲንከባከባቸው ። ዋቁር ክነሙ አባበላና አሜ ውታ በመያገ የምትበልጠው ሚሊ ብቻ ናት ።

"እትዬ እስክርሌት ፡ በጣም ጥሩ ሰው ሆንሽልኛል" አለ ፡ "እኔ ካንቺ ጋር ምንም ዝምድና የሌለኝ ፣ ለሰጪ ባዳ ፡ ሳገሩ እንግዳ ሰው ነኝ ። የመከራና የችግር ዓይነት በኔ ምክንያት አየሽ ። እናም ምንም ለወጥ ካላመጣብሽ የሠራሽልኝን ውለታ በከፊል እንኳ እስክምከፍል ድረስ እዚሁ ሳገለግልሽ ለመቆየት አፈልጋለሁ ። እርግጥ ሁሉንም ውለታ

@OLDBOOKSPDF

ልክፍልሽ አልችልም ። ምክንያቱም ሰው የሕይወቱን ዋጋ ለመክፈል አይችልምና ነው ። ”

ስለዚህ እዚያው ሰንበት ። ቀስ በቀስ በተቃና ሁኔታ እስካርሌት ጫንቃ ላይ ተጭኖ የንበረው በርካታው የታራ ቮክም ወደ ዊል ቤን ዙን አጥንታማ ትከሻ ተሸጋገረ ።

❁ ❁ ❁

ወሩ መስከረም ነው ። የጥጥ ለቅማ ጊዜ ። ዊል ቤንቲን ከእስካርሌት እግር ሥር ተቀምጦ ብራውን የበለግ ወሐይ እየጠጣ ስለጥጥ መፈልቀቅ ዋጋና ፈይትቪል ስላለው የጥጥ መፈልቀቂያ መሣሪያ በረኽው ያወራሳታል ። ነገር ግን ፈይትቪል በነበረ ጊዜ እንዳየው ሁሉ ፣ ወዲያ የጥጥ ፍልቅታ ሥራ ዋጋ ፣ ለፋብሪካው ባለቤት ፈረስና ጋሪ ለጥቂት ሳምንታት በማከራየት በእራት እጅ ማስቀነስ እንደሚቻል ያውቃል ። ሆኖም ይህን የዋጋ ከርከር ከእስካርሌት ጋር እስኪወያይ በት ድረስ አዘግይቱታል ።

የበረንዳውን ምሰሶ ተደግፋ ወደዚህ አበባራሚ ፍጥረት ትመለከታለች ። ያልጥርጥር ማሚ እንዳለችው ይሄ ዊል የሚባል ሰው እግዚሃር የለማቸው ነው ። እስካርሌት ያለፉትን ጥቂት ወራት ያለሱ እንዴት እደርጋ ትዘልቃቸው እንደንበር አስባ ማርም አላት ። ብዙ አይናገርም ። በጭራሽ በማውራት ጉሉበቱን አያባክንም ። ስለራሱ በሚወራ ነገር ውስጥም በጭራሽ እጁን ማስገባትና ማውራት አይሻም ። ይህ ሁሉ ሆኖ ግን ታራ ውስጥ ስላለው ስለማናቸውም ሰው ታሪክ አውቋል ። ሥራ ግን ይሠራል ። ሲሰራ በዐጥታ ቢትእግሥትና ሁሉንም ጨርሶና ፈጽሞ ነው ። ምንም እንኳ ያለው አንድ እግር ቢሆን ሲሠራ ከፖርከ ይፈጥናል ። እንደውም የፖርከን ሥራ ሲሰራ እስካርሌትን ግራም ድንቅ ያሰኛታል ። ላሚ ስትታመምም ሆነ ፈረሱ ሊሞት ደርሶ ሲያቃስት ዊል ሌሊቱን ሙሉ ቁጭ ብሎ ነው ያዳናቸው ። እስካርሌት ሌላው የሚያስደስታት ነገር ጮሌ ነጋዴ መሆኑ ነው ። አንድ ወይም ሁለት ከረጢት ጥራጥሬ ስኳር ድንችና ሌሎችም ቅጠላ ቅጠሎች ይዞ ይሄድና የዘር እህል ፣ ብዙ ጨርቃ ጨርቅ ፣ ዱቄትና ሌሎች የጥጅታ ዕቃዎችን ይዞ ሲመለስ ስታይ ፣ ምንም እንኳን ራሷም ዋና ነጋዴ ብትሆን የሱን ያህል እንዳይደለች ይሰማትና በጣም ትደሰትበታለች ።

ቀስ በቀስ የቢተሰቡ አባል ወደመሆን ተሸጋግረና አልፎ ተርፎም ከጀራልድ መኣታ ቤት አጠገብ ካለችው የመልበሻ ክፍል ውስጥ አንድ ድንክ አልጋ ላይ ይተኛ ጀመር ። ታራን ለቅቆ ስለመሔድ ምንም ነገር አንስቶባት አያውቅም ። እስካርሌትም ብትሆን ይህን ጉዳይ ላለማንሳት በጣም ተጠንቅቃለች ። ምክንያቱም ካለታወሰችው ጥሰን ይሄዳል የሚል

@OLDBOOKSPDF

ሥጋት አላት። እንዳንዴ ትልቅ ሰው የነበረ ቢሆን ኖሮ ቤት እንኳ ባይኖረው የመሄድ ሐሞት ይኖረው ነበር ብላ ታስብ ነበር። ያም ሆኖ ግን እስከዘለዓለም ከቤቷ እንዳይሄድባት ከልቡዋ ትፀልያለች። ——እንዲህ ያለ ሰው ማግኘት እንዴት ያለ መታደል እኩ ነው።

እስካርሌት በሀሳቧ እቺ ካሪን የአይጥ ያህል እንኳ ጭንቅላት ቢኖራት ዊል እንደሚያስብላት ይገባት ነበር አለች። ዊል ካሪንን ላግባ ብሎ ቢጠይቅ እስካርሌት በየትኛውም መንገድ ቢሆን እንዲያገባት በማድረግ እስከዛሬ የሠራላትን ውለታ በመጠኑም ቢሆን ትከፍል ነበር። እርግጥ ከጦርነቱ በፊት ቢሆን እንኳ ዊል ለዚህ ጋብቻ ብቁ አይሆንም ነበር። ከነጭራሹ እሠሬ እርሻ አካባቢ ስሙ ያልተጠራ ወናጪ ደሀም ባይሆን ዝቅተኛ ግበሬ ነበር። ትምህርትም እስከዚህ አልገፋም። የሰዋስው ፅሁፉ አብዛኛውን ጊዜ ለስህተት የተጋለጠና በአሃዛ ቤተሰብ ዘር ሐረግ ውስጥ ጨው ወንድ ሊኖረው ይገባል የተባሉትን ወጎች ከነጭራሹም የማያውቅ ተራ ሰው ነበር። ለነገሩማ እስካርሌት ቀድሞ ነገር ጨዋ ሰው ልሁንለ ቢል እንዴት ይቻለዋል ብላ ተገርማለች። ሜላኒ ግን ለዊል ትሟገትለታለች። ማንም እንደዊል ያለ ደግ ልብና ለሰው አሳቢ አእምሮ ያለው ሰው የጨዋ ዘር ነው፤ እያለች ሽንጧን ገትራ ትቆምለታለች። እስካርሌት መቸም ፤ ሌለን ልጅሽ እንዲህ ያለ ወንድ አገባች ብለው ቢነግሯት እዚያው ድርቅ ብላ ትቀራለች። ደግነቱ ዛሬ ጊዜ እስካርሌት ውኔታው በጣም እየገፋት ከሌለን ትምህርት ያለልክ ርቃለች። ስለዚህም ማንንም አግብተው ፣ ለታራ አንድ ወንድ ማፍራት አለባቸው ባይ ሆኖለች። ካሪን ግን በዐሥት መጽሐፏ ውስጥ ተቀብራ በየዕለቱ ከተግባራዊው ዓለም በእጅድ አርምሽ እየራቀች በመሄዷ ዊልን እንደወንድሟ በቂር በተለየ ዐይን አይታው አታውቅም። እንዲያውም ለፖርክ ካላት ግምት የተሻለ ግምት አትሰጠውም።

"ካሪን እኔ ያደረኩላትን ውለታ ትንሽ ለማሰብ ብትችል ኖሮ፣ ለኔ ስትል እሱን አግብታ ከዚህ እንዳይሄድ ማድረግ ነበረባት።" ብላ አሰበች እስካርሌት ንድድ እያላት። "ግን ምን ያደርጋል እሷ ለራሷ ከቶውንም ቅንጣት ታህል ለማይጨነቅላትና ምናልባትም ዞር ብሎ እንኳ ለማያያት ወንድ ልቧን ታወልቃለች።"

በዚህ ዓይነት ዊል ታራ ውስጥ ቆየ። እስካርሌት የቆየበት ምክንያት አልገባትም። ያም ሆኖ ወንዳወንድነቱና ያለው የንግድ አዝማሚያ የሚያስደስታትም የሚደግፋትም ሆኖ አግኝታዋለች። የዊል ንብረ ሥራ ሁሉ ትጥ አንባሩ ለጠፋው ለጂራልድ ምንም የተለየ ሆኖ አይታየውም። ለእስካርሌት ግን ፅውንተኛው የቤቱ አባወራ ሆኖ ይሰማታል።

@OLDBOOKSPDF

እስካርሌት ምን እንደ ፈደሱ የቤተሰቡ መንቀሳቀሻ መሆኑን ብታውቅም ዊል ያመጣውን የማከራየት ሀሳብ ደገፈች ። በዚህ ጉዳይ ከሁሉ በላይ የሚከፋት ሱዌለን ናት ። የሷ ደስታ ፤ ዊል ለንግድ ወደ ጆንስቦሮ ወይም ፌት ቪል ሲሄድ አብራ መሆሩ ነበር ። ከቤተሰቡ አባላት ሁሉ ለየት ባለ ሁኔታ ለባብሳና የዱሮ ወዳጆችዋን እየዞረች በመጠየቅ የመንደሩን ወሬና ሐሜታ ቀራርማ ስትመጣ ፤ በአሃራ ቤተሰብ የታራ ዋና ቆንጆ ፣ ወይዘሪት አሃራ ፤ የሆነች ይመስላታል ። ሱዌለን የእርሻ ቦታውን ትታ የምትሄድበት አጋጣሚ ካገኘች በም ንም ዓይነት አያመልጣትም ። ወጣ ብሳ አረም ማረሚን ፣ አትክልት መትከሏንና አልጋ ማንጠፏን በማያውቁ ስዎች ፌት ልታይ ልታይ ማለትን ትወድዳለች ።

እቺ "ወይዘሮ አዲስ አየር" አኮ አንድ ሁለት ሳምንት ያለሽርሽር ሥራ እየሠራች መቀመጥ አለባት ፣ ብሳ ታስባለች እስካርሌት ። ጭቅ ጭንቋንና እጥል ጉራዋንም እንገላገላለን ።

ሚላኒ ልጅዋን እንዶትቀፈች ወደ በረንዳው መጥታ ከነሱ ተቀ ላቀለችና እንድ ያረጀ የብርድ ልብስ ወለሉ ላይ አንጥፋ ትንሹ ባቡ እየዳቩ እንዲጫወት ለቀቀችው ። ሚላኒ የአሽሌይ ደብዳቤ ከደረሳት ወዲህ ጊዜዋን የምታሳልፈው በመፈንደቅ ፣ በደስታ በመዘፈንና በጉ ጉት በመጠበቅ ነው ። ብቻ ቱደሰቱችም አልተደሰቱችም ሁልጊዜ ቀሙን ናት ። ሁልጊዜ ፊቷ ከሲታ ነው ። የተሰጣትን የሥራ ድርሻ ሁሉ ባታጉረመርም ትወጣለች ። ነገር ግን ሁልጊዜ ታማሚ ናት ። ዶክተር ፎንቴን መርምሯት ሲያበቃ ከሴትነቷ ጋር የተያያዘ ችግር መሆኑን ተናግሮ ልክ ዶክተር ሚድ እንዳሳት ሁሉ 'ባቡ'ን መውለድ አልነበረብሽም ብሏታል ። ከእንግዲህ ሌላ ልጅ መውለድ መሞቻሽ ነው ብሏታል ።

"ዛሬ ፌት ቪል ሄጂ ባለ" አለ ዊል "አንድ በጣም ግሩም ነገር አግኝቼ ለሴቶች ቆንጆ ነው ብዬ ወደቤት ይዤው መጣሁ" ። የሱ ሪውን የኋላ ኪስ ፈተሸ ፈተሸ አድርጎ ካሪን የሠራችለትን ከጥጥ ጨርቅ የተሠራና በዛፍ ቅርፊት የተጠናከረ ቦርሳ መሠ ፤ ከውስጡ የኮንፌዴሬሲውን ቼክ አወጣ ።

"ዊል ! የኮንፌዴሬሲው ገንዘብ የሚወደድ ነው ፤ ከሆነ የምት ለው ፤ በበኩሌ አልወደውም ። " አለች እስካርሌት ባጭሩ ። የኮንፌዴ ሬሲው ገንዘብ ገና ስታየው ደሟን ያፈላዋል ። "ካልከስ እኛም ባሁኗ ደቂቃ እንኳ አባባ ሻንጣ ውስጥ ሶስት ቪ ዶላር አለን ። እንደውም ማሚ ! ብርድ ስላስቸገረኝ የማድግዳውን ቀዳዳ በሱ ሸፍኜለኝ እያለች እየወተወተችኝ ነው ። እንዲያውም እሸፍንላታለሁ ። ቢያንስ ላንድ ነገር ያገለግል እንጂ ። "

@OLDBOOKSPDF

"እባክሽ 'ታላቁ ቂጣርም ሞቶ አፈር በልቶታል' አለች ሚላኒ የሐዘን ፈገግታ እያሳየች"። "በከንቱ አታበሳሽው እስካርሌት—ለዋድ አስቀምጪለት። አንድ ቀን ይኮራበት ይሆናል።"

"እኔ መቼም ስለታላቁ ቂጣር ምንም የማውቀው ነገር የለኝም።" አለ ዊል በትእግሥት። "እኔ እማስበው ግን አሁን ወ/ሮ ሚላኒ ስለዋድ የተናገርሺውን ነው። በዚህ ቼክ ጀርባ ላይ የተለጠፈ አንድ ግጥም አለ። ወ/ሮ እስካርሌት እንኳ ስለግጥም እስከዚህም ትመስለ ኖለች። ነገር ግን ይሄ ይጥማታል ብዬ ገምቻለሁ።"

ቼኩን ገለበጠው። በጀርባው ላይ ትንሽ ሻካራ ወረቀት ተለጥ ፋለች። አገር ውስጥ በተሠራ ቀለም ተጽፎባታል። ዊል ጉሮሮውን አጥርቶ በቀስታና በችግር አነበበው።

"አርእስቱ —'በኮንፌዴሬሲው ብር ጀርባ ላይ ያሉ ስንኞች' ይላል" አለ።

"ወድቋል ዋጋም የለው
ዛሬ ፋይዳ ቢስ ነው።

ከቶም በእግዚር ምድር
አይመነዛር።

ውቅያኖስ ቢጣባ
ጥቅም የለው አይረባ፤

አሳየው ላሳየ ካንተ ጋራ ይኑር
ዋስትና ነውና ለሞተችው አገር።

አሰማው ላልሰማ፤ ጀሮ ለሚያውስህ
ይቺን ትንሽ ታሪክ፤ ተረት ተረት ብለህ።
ተረቱ ይሄው ልህ—

ከጀግኖች ሀልም አብራክ ነባትት ቢፈጠር
በአውሎ ንፋስ ታዝሎ እረገፈች አገር!"

"ዉ . . . እንዴት ቆንጆ ነው! እንዴት ልብ የሚነካ ግጥም ነው! አለች ሚላኔ በጩኸት" እስካርሌት፤ ማሚ አሮጌ ግድግዳ ላይ ትለጥፈው ብለሽ በጭራሽ መስጠት የለብሽም። ይሄ እኮ እንዲያው ተራ ወረቀት እንዳይመስልሽ —ከወረቀት በላይ ነው። ልክ ግጥሙ እንዳለው፣—ለሞተች አገር ዋስትና ነው!!"

"ኤጭ ሜሊ! ይሄን ያህል ቡቡና ስሜት ስለ ለምን ትሆኛለሽ! ወረቀት ወረቀት ነው። እኛ ደግሞ ያለን ወረቀት በቂ ነው። ማሚ

@OLDBOOKSPDF

ስለማድማው ቀዳዳና ሽንቁር ጭቅጨቃዋ ድክም ብሎኛል። ዋድ ሲያድግ እንዲኖረው የምፈልገው እንዲህ ያለውን የኮንዶሬሲ ውዳቂ ብር ሳይሆን ከጀርባው በአረንጓዴ የተሣሪበትን የአሜሪካ እውነተኛ ዶላር ነው።"

ዊል ይሄ ሁሉ ክርክር ሲካሄድ ቹኩን በአጭ እንዳያዘ ትንሹን ጎበጎን ሲያጫውት ቆይቶ ድንገት ቀና ብሎ በእጁ ፀጉሩን ከፀሐይ ከልሎ ቁልቁል መደመኪና መንገዱ አየ።

"ሁጨማሪ ዓደኛ" አለ ፀጉሩን ወደ ፀሐይዋ እያጨናቆረ -"ሴላ ወታደር"። እስካርሌትም እሱ ወደ ሚያይበት አቅጣጫ ተመለከተች። የምታውቀው ዓይነት ወታደር ይታያታል። አንድ ጢማም ሰው፣ የአርዘ ሊባኖስ ሰልፈኛ ዘፎች ባጀቡት ወደ ግቢው በሚያመራው መንገድ፣ ቂስ እያለ ወደላይ ይመጣል። የሸማያዊና የጫጫ ድሪቶ ዩኒፎርም የለበሰ፣ እንግሩን ደፍጭ በድክም የሚንቀሳቀስ፣ እግሩን ተራ በተራ በቀስታ እያንጠተተ የሚራመድ ሰው ነው።

"እኔኮ እንዚህ ወታደሮች መጥቱው መጥተው አልቀው ተነ ላግለናል ብዬ ነበር።" አለች። "መቼም ይሄኛው የተራበ እንደማ ይሆን ተስፋ አደርጋለሁ።"

"መራቡማ የት ይታሬል" አለ ዊል ባጭሩ።

ሜላኒ ተንሰኘች።

"ዲልሲን ተጨማሪ ገበታ አዘጋጂ ብላት ይሻላል" አለች። "ማሚን ደሞ እንዶሎቹ የዚህንም ወታደር ልብስ ድንገት ምንጭቅ አድርገሽ እንዳታወልቂበት ልበላትና . . . ."

ድንገት ንጣጩንም እንቅበታቴዋንም ስታቆም እስካርሌት ምን ሆነች ብላ ዞራ አየቻት። ሜላኒ የጉሮሮዋ ቆዳ የሚበሳ አስኪመስል ድረስ እንፋቷን በአጅዋ ጭምቅ አድርጋ ያዘች። እስካርሌት ሜላኒ እጅ ላይ ያለው ደም ሥር ትር ትር ሲል ይታያታል። ፊቷ አመድ መሰለ። ዙጣ ዐይኗም ድፍርስርሱ ወጣ።

በቃ ራሷን ስታ ልትወድቅ ነው ብላ አሰበች እስካርሌት፤ ፍጥን ብላ ተነስታ ከንዲን እየያዘቻት።

ሜላኒ ግን ከመቅጽበት የእስካርሌትን እጅ ገፍትራ ከከንዲ አላታ፣ ቁልቁል ደረጃውን ተንደርድራ ወረደች። እንደወፍ ቅልል ብላ፣ ቀለሙ የለቀቀ ቀሚሷን ከኋላዋ እንደጅረት እያተራመሰች ከንዲን ወደፊት ዘርግታ፣ ቁልቁል በጠጠራማው መንገድ ላይ ከነፈች። እስ ካርሌት እውነቱ ግልጽ ብሎ ታወቃት። አንድ ጊዜ የጉንተላት ስሜት

@OLDBOOKSPDF

እቅጩን አሳወቃት ። ያ መንደኛ ሰው በቅሻሻ በናማ ጢም የተሸ
ፈነ ፊቱን ቀና ሲያደርግ እስክርሌት ወደኋላዋ ተሽከርክራ ከበረ
ንዳው ምሰሶ ጋር ተለተመች ። ያ መንገደኛ በድካም ብዛት የአንድ እር
ምሻ ጠፌ የያዘው ይመስል ባለበት ቆሞ ወደ ቤቱ አቅጣጫ ይመለ
ከታል ። ሚሰኒ ቅጥ የሌለው የተሰባበረ ጩኸት እየሙሸች በአዳ
ፋው ወታደር አቅፍ ላይ ስትወድቅና እሱም ከጭንቅላቱ ንንበስ ሲል
የእስክርሌት ልብ አንዴ ተሰፈንጥሮ ዘሎ ደም ቀጥ አለ ። ደም ወዲ
ያው ልክ የሌለው ግልቢያውን ፡ ልንም የሌለው የትርታ ግልቢያ
ወጎ ተያያዘው ። እስክርሌት ድንገት እመር ብላ የራሷ የሚያክለ
ሁለት ትላልቅ እርምጃዎችን ስትጀምር ገና ፡ ዊል ቃሚቷን አፈፍ
አድርጎ ይዞ ከመሄድ ተታትና ፡

"አታደፍርቨው" አላት በቀስታ ።

"ልቀቅኝ አንተ ጅል ፡ልቀቅኝ ! አሽሌይ እኮ ነው !"

እሱ ግን ጭብጡን አላላሳም ።

"የኔ ባፏ እኮ ነው ። አይደል እንዴ?" ሲል ዊል በጥሞና
ጠየቃት ። እስክርሌት በደስታ ሰክራ ፡ አቅም በሌለው የንዴት ወደን
ዊልን ቁልቁል ስታስተውለው ፡ ዝምታ በዋጣቸው ወይኖቹ ጥልቀት
ውስጥ ጉዳይዋን የተረዳለትና ያበሳለት መሆኑን አየች ።

@OLDBOOKSPDF

ጎንም ሰላ ቀን ነው (ጉን ቺካ ዘ ቺንደ)
... በ1936 ዕኤ 30 ቀን ለመጀመሪያ ጊዜ ታትሞ ፣
ዓመቱ ሳይገባንጅ ከአንድ ሚሊዮን በላይ የተሸጠና
ራሱን የሚያሸው ምዕተ ዓመት ዝነኛ ልብ ወለድ አሰኙት
ለወግ ማዕረግ የበቃ መጽሐፍ ነው ። እስከ 1965 ብቻ
ባአርባ አገሮች ውስጥ በሠላሳ የተለያዩ ቋንቋዎች ተተርጉሞ
ተሚል ።

ዶናልድ አዳምስ
ስፔሺያ አፍ ባክስ ኤንድ ላይፍ

በ1930 የ[illegible] ተሸጠ ። ተሸጭ ። ሸኘ ።
እስከ 1973 ሶረስ ብቻ ከሃያ አንድ ሚሊዮን በላይ
ተሸጧል ።

በሲኒማ ዓለም [illegible]
አዋርድ)። [illegible] ደረሻ
ከፋብ ፣ ሊስኮ [illegible]

ዋጋ ብር 11.50

ቦሌ ማተሚያ ቤት